
# ዶክተር አሸብር

## እና ሌሎችም



አሌክስ አብርሃም

2ኛ ዕትም

# ማውጫ


አስር የሽቶ ጠርሙዞች በግድግዳ ላይ ........ 4
ተሰቀለ ቢሉኝ ". ባርኔጣው" ነው ብየ ........ 11
የፍሪምባ ጦርነት ........ 16
ተ ሸ ከ መ ና ታ ል!! ........ 18
የአባየ ስልክ እና ባዮሎጂ ........ 19
ሁለት ብር ስንት ዶላር ነው? ........ 23
ንፋስ ወዴት ነህ ቢሉት ማርና ወተት ወዳለበት ........ 48
እብድ እና ዘመናይ ........ 51
በብረትና ቻፕስቲክ በተከበበ ከተማ እንሆ የመለአክ ድምፅ ተሰማ!! ........ 54
ዝግመተ ለውጥ ........ 57
"ሸረኛ" " እና " "ደህና" በአንድ ላይ ሲሄዱ በሸረኛው በኩል ተናደ መንገዱ ........ 64
አለሁላት !! ........ 72
ዶክተር አሸብር ........ 76
የቀድሞው ጠ /ሚ መለስ ዜናዊ በሰማይ ቤት ........ 116
በአልጋው ትክክል ........ 146
የነ ሜሮን ፍሪጅ ........ 229
ሄደች አሉ ጋራ ጋራውን ........ 235
የቤተ ዘመዱ ይታያል ጉዱ ........ 245
ዙሪያሽ ሳትፈልግ ፖለቲከኛ ሆነች ........ 254
ዘንዶ ቢጠመጠም በወገቤ ላይ ........ 255
ዘላለም የመኖር ጥበብ (የህዝብ ተረት) ........ 256
ዋጋህን ሳይሆን ሻጭህን አስብ ........ 258
ካካካካ ካካ !! ........ 260
ኪነት ........ 261
ከወየውልሽ ወደ ወየውልሽ ........ 262
ከነፈሰው ጋር ........ 272
ከሚቀበሉ ይልቅ የሚሰጡ ብፁአን ናቸው ........ 273
እዛው የለመድክበት !! ........ 275
አጥፍተው እንዳትጠፉ ይሉናል ........ 282
አስቴር አወቀ እና "ቲቸር" መልከአ ........ 286

ትንቢተ ቃሊቲ ........ 288
ባቢሎን ድብልቅልቅ ........ 289
ምርጫ በአንዲት አፈሪካዊት መንደር ........ 304
መቀስ ሸርጥ ቦለቲካ........ 305
አንዲት ቃል!........ 309
የቀን ጅቦች ነን!........ 314
የአደዋ ጦርነት ገና አላለቀም........315
የሚያስጠልሉ ብፁአን ናቸው .... ዝናቡ ይቆማልና! ........ 318
እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ ........ 320
ፍቅር አኬልዳማ........323
የሰርግ ቀን ስድቦች........325
የተንጨባረረ ሂወት በፍቅር ሚዶ ሲበጠር ........327
ሴትነት ድንበሩ የት ነው? ........ 328
የመዝጊያ ንግግር........331
የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት........333

# አስር የሽቶ ጠርሙዞች በግድግዳ ላይ

እሽክም እሽክም እሽክም (ያዝ እንግዲህ )

ደግሞ እስክስስስስስስ (አሳየው ላላየው)

እልልልልልልልልልልልልልልልልል ችቦ አይሞላም ወገቧ  (ያዝ እንግዲህ)

የጎረቤታችን ሰርግ ነው የኑአሚን ተፈራ ዘፋኝ ስለሆነች ይሆን ዘፈኑ የደመቀው ማንትስ ባንድ የሚባል እንደ አንበሳ አዳኝ "ያዝ እንግዲህ" ማለት ከሚያበዛ የባህል ዘፋኝ ጋር ሰርጉን እያደመቁት ነው መንደሩ አብዷል ቢራ አራት መኪና ሙሉ ተዘርግፎ "ጠጡ" ተባለ! ጠጅ ወይ ጠጅ አባይ ቢጫ ልብስ ለብሶ ሰርጉ ላይ የተገኘ እስኪመስል ስክርርር እስኪል አላፊ አግዳሚው

ከሰርጉ በፊት

"የልጃችን የወሪት ኑአሚን ተፈራ እና የታደለ ግርማ የጋብቻ ስነስረአት የሚፈፀመው እሁድ ከቀኑ 7፡00 ሰአት 19 ዓም ስለሆነ ከባለቤተዎ ጋር ተገኝተው የደስታችን ተካፋይ እንዲሆኑ ተጋብዘዋል "

ጥቅስን እንደመፎክር ፡- "እግዚያብሄር አንድ ያደረገውን ማንም አይለያየው ምእራፍ 7 ቁጥር 3 ሌላ መፎክር ፡- ከእንግዲህ አንድ ናቸው እንጅ ሁለት አይደሉም ምእራፍ ቁጥር የምር ምስጋና አድርገህልኛልና ለዘላለም አመሰግንሃለሁ (እንደገና ስጦታ ካርድ የሚከፋፈተው አብረቅራቂ የጥሪ ወረቀት ላይ በየገፁ ጥቅስ አለ የሙሽሪት የሂወት ገፅ ቢገላበጥ እንኳን የመፀሃፍ ቅዱስ ጥቅስ የዘወትሩ "አባታችን ሆይ " በወጉ አይገኝም "የእለት እንጀራችን.." ላይ ያልቃል እምነቷ !! )

አድራሻችን "ከፊታውራሪ አሰፋ ግዛው ቤት ጎን " ይሄ የጥሪ ካርድ የተሰጠው ለአባቴ "ፊታውሪ አሰፋ ግዛው ነው" !! ያውም በወርቃማ ቀለም ተሸሞንሙኖ እንደግቢ በር በትልቁ ግራና ቀኝ ተከፋች ተደርጎ የሙሽራውና የሙሽሪት ፎቶ አስማት በሚመስል ቀለም ተስሎበት ደግሞ ካርዱ በጨለማ ውስጥ ያበራል !! (እዮብ አንድ ቀን የሚያበራ ፅሁፍ ያለበት እስክርቢቶ ይዞ "እንዴት በጨለማ ያበራል" አልኩት " በፎስፎረስ ነው ፅሁፉ የተፃፈው" አለኝ!! ከዛች ቀን ጀምሮ ፀሃይ.. ጨረቃ አብሪ ትል የቤታችን አምፑል ከፎስፎረስ የተሰሩ መሰለኝ )

አባቴ ተቃጠለ !! ነደደ!! የጥሪ ካርዱን ሲያይ በከዘራው መሬቱን ቀጭ ቀጭ እያደረገ በእግሩም እየተመተመ አይኑን የሚያሳርፍበት ቦታ አጥቶ ተንከራተተ በሰንሰል ቅጠል በቆርቆሮ እና በጥሬ ካብ የተዋቀረውን ዘባተሎ የግቢያችንን አጥር ተገንጥሎ ቋሚው ጋር በሽቦ የታሰረውን የግቢውን የቆርቆሮ በር አየ መዛግ ጀምሯል በሩ ሲዝግ ይገነጠላል !! የበሰበሰውን የበረንዳ መደገፊያ ጣውላ ቃኘ " እንዲህ ምልክት አድርጉኝ እንጅ በወግ ማረግ ለመዳሩማ አልታደልኩም አዎ ከእኔ ቤት ጎን ሰርገኛው ይጉረፍ  " አለ ! ወይኔ አባባ ሊያለቅስ ነው እንዴ አልኩ እኔ  ከምር እንባው በአይኑ ሞልቷል!!

እህቴ እዮብን አፈቀረችው !! እዮብም አፈቀራት !! በጣም ተፋቀሩ!! (እዮብ ማነው ካላችሁ እዮብ የእህቴ ፍቅረኛ ነው! ሌላ መታወቂያም ማንነትም የለውም እህቴ የእዮብ ባንዲራ ናት ኢትዮጲያዊያን ሮጡም ተዋጉም ባንዲራው ነው አይደለም ቀድሞ የሚታየው እዮብ ይኑርም አይኑርም በእህቴ ነው የሚከብረው (እዮብ ማነው ? ይሄ የሳምሪ ጓደኛ?) አይነጣጠሉም "ጠይም ባንዲራው" ናት )

ሁሉም ሰው እዮብን "እድለኛ ነው" "አፈስ" ይለዋል ለእህቴ የሚሰጠው አስተያየት ግን ይቀላቀላል ፒያሳ ታክሲ እየጠበቀ "የምትገርም አፍቃሪ..የእግዜር ሰው ትሁት " ያለው አስተያየት ሰጭ ቁራ ሳይደርስ " ምን ነክቷት ነው እዚህ (ጣሙጋ ሬሳ ጣውላ ቀድረ ቀላል ጠኒያም "ሱሰኛ" ቦዘኔ የቆመ እባብ የመሰለ እህል አይቶ የማያወቅ የመሰለ ) ልጅ ላይ ሙጭጭ ያለችው እችን የመሰለች (ኬክ መልአክ ውብ መለሎ ሞናሊዛ ወለላ የማር ሰፈፍ ፀሃይ ፅጌሬዳ እንቡጥ ጠይም አሳ መሳይ "ሴክሲ") ይላል!! በእርግጥ እዮብም እንዳሉት ነው "ሱሰኛ" ከሚለው

ውጭ እህቴም እንዳሏት ናት "ሴክሲ" የምትለዋ ቃል ግን ተናጋሪወቹ ሲናገሯት ከስሪቷ ታፈነግጣለች ። አርፈው (አማላይ) ቢሉስ !!

ቆንጆ ሴት መውለድን ቤት ውስጥ የነዳጅ ጉድጓድ እንደማግኘት አድርጎ የሚወስደው "የአዲስ አበባ" ህዝብ እህቴን ሲያይ " የብረት መዝጊያ የሚሆን አማች አምጥታ እዚህ እድሜ ልኩን ከፍቱን የኖረ በሩ የዛገ ቤት ላይ ትገጠግጠዋለች" ብሎ በኩራት ይናገር ነበር!!

እህቴ ግን.. እዚህ ግባ የማይባለውን ለሰው አይን እንደፉየ ገላ የቀለለውን የሂወት ነፋስ ማሳረፊያ አሳጥቶ የሚያንሳፍፈውን እዮብን አፈቀረች!! ያውም በፍፁም ልቧ በፍፁም ነፍሷ እንደእግዜር !! እዮብ የእህቴ እግዜር ነው!! እግዜር በእህቴ አይቀየምም እግዜር እንደመንደራችን ጎረምሶች አይደለም የፍቅር አምላክ ስለፍቅር እስከጥግ መውረድን መዋረድን ያውቃታል !! እናም እዮብ የእኔ መለአክ የእህቴ እግዜር ነው !!

"ኸ ረ እጂ ላይ እንዳይሞት ይሄ ሞት የጀመረው ልጅ" ይላሉ እህቴን የሚቋምጡ ቁምጥና ልብና ህሊናቸውን ያጠቃው ባለጉንድሽ ልብ ጎረምሶች !! ጠዋት ሲወጡ ሰባት ልብስ ለከተው ስምንተኛውን መርጠው የሚለብሱ ሴት አውሎች !! እዮቤን ያሙታል (እዮቤ የኔ ሚስኪን በድሪቶ የተጠቀለለ ወርቅ ) እነዚህ የሴት ስም ሲያቆላምጡ የሚውሉ የዘነጡ ቆሻሾች እዮቤን ያሙታል !!

"እዩብየ ና እኛ ጋር ዋል ዛሬ " ትለዋለች እህቴ ደውላ

" አባባ አሉ እንዴ?" በፍርሃት ይጠይቃል

"ችግር የለውም እንደውም "ያ ልጅ የት ጠፋ" ሲል ነበር ማታ " ትላለች እህቴ ! አባባ ግን እንደዛ አላለም ማታ ! አባቴ እዮብን ለአይኑ ይፀየፈዋል ሲያየው ደሙ ይፈላል እዮብ ሲመጣ አባቴ ተነስቶ ከቤት ይወጣል እየፈራ " አባባ ደህና ዋሉ" ሲለው እንዳልሰማ ያልፈዋል !! እዮብ ዞር ብሎ ሰው ያያል ሃፍረቱን ማን እንደተጋራው ሊቃኝ ምንጊዜም እኔን ብቻ ነው ከስሩ የሚያየኝ !! እኔ የእዮቤ ጋራ ነኝ !! በሰለለ ሂወቱ ብቸኝነት በሚረጭ አይኑ "የኔ ጋራ የሚሆን ሲል" እኔኔኔኔ ብየ ላንቃየ እስኪሰነጠቅ የጮሁኩ!! እናም ከጎኑ የቆምኩ እህቴማ ጎኑ አይደለችም ውስጡ ናት

" ከምን ተሰራሽ" ብትባል "ከስጋ ፣ ከመንፈስና ከእዮብ "የምትል እህቴ!!

ታደለ የሚባል ሰው ወደሰፈራችን እህቴን ወደድኩ ብሎ መጣ። የት እንዳያት አላውቅም (በክፉ አይኑ) ቁመቱ የሚያምር ፈገግታው "ሳቁ እንሳቅ" አዋጅ!! የቀይ ዳማ አንዳች ግርማ ሞገስ ያጎናፀፈው ሳድግ እንደሱ ነው የምራመደው ብያለሁ ሳድግ እንደሱ ነው እጀን በመስኮት ላይ አስደግፌ መኪና የምነዳው ብያለሁ ሳድግ እንደሱ ነው በእርጋታ የውሃ መያዣ ጎማ" ቷ" አድርጌ የምገፍተው ብያለሁ ሳድግ አማርኛን በእንግሊዝኛ ላንቃ የምለፋደድባት እንደሱ ነው ብያለሁ ይሄ ሰው እህቴን ወዶ ወደእኛ ሰፈር መጣ ያውም በቆመችበት ሰው ሲነካት "ፒው ፒው" የምትል መኪና ይዞ !!

ሰፈሩ ሁሉ የታደለ መሪ ጠቋሚው ሆነ አማልዱኝ ሳይል ድፍን አገር አማላጁ ሆነ (እንግዳ ተቀባይ ሂሂሂ)

"አወስትራሊያ ዘጠኝ አመት አሜሪካ ሶስት ስዊዲን ሁለት አመት ኖሮ የመጣ ዶክተር ነው " አሏት

" ሁለት ሴቶች በፍቅሩ በረኪና ጠጥተዋል ፣ አንዷቷ መኪናው ጎማ ስር ተነጥፋ ካላገባሃኝ ጨፍልቀኝ ብላው ቆስላ ተርፋለች ፣ ሶስት ከህንፃ ዘለው ተፈጥፍጠዋል ፣ አስራ ሰባት የት እንደደረሱ አይታወቅም ልብሳቸውን ጥለው ብን ጥን ብለውለታል!! (አምስት ሙት አንድ ቁስለኛ አስራ ሰባቱ የት እንደደረሱ ያልታወቁ ሂሂሂ) " ለእህቴ ይሄን ዜና አንብበውላታል (አለሙን ሁሉ ንቆ ተከተለሽ ብለው ሴትነቷን ሊለኩሱት)!!

" መኪናው ሚሊየን ስልኩ አምሳ ሽ ፈሪ ነው ቤቱ ከውበቱና ከታላቅነቱ ብዛት አንድ ቀን ጠቅላይ ሚንስትሩ " ውይ ዛሬ ከምን ጊዜው ቤተ መንግስት ደረስኩ ብለው ዘው" ብለዋል እዚህ ፍልውሃ ጋ " አሏት

እዮቤ አጠገቧ ቁሞ እየሰማ ” የወንዶች አውራ ባል መጥቶልሻል አልጋ ሲሉሽ አመድ አትሁኝ “ አሏት

“ ኸረ የወንድ ጡር አለው “ እነሄለን እነሜሮንና ገሊላ (የመንደራችን ዘመነኛ ሴቶች! ባዶ ቦርሳቸውን አንጠልጥለው ቦሌ ለቦሌ ሲያቃጥኑ ያጡት “ዲያስፖራ” መንደራቸው ድረስ ሲከሰት “አሳዝኗቸው”)

“የወንድ ጡር አለው አታንገላችው “ አሏት በወንድ ጡር የተገዛ ቀሚሳቸውን እየነሰነሱ፣ በወንድ ጡር ግብሻ የገዘፈ ዳሊያቸውን እያውረገረጉ (እኔ ብሆን ኑሮ አይነት ቁጭት) የስጋ ክምሮች ! ሰው መሆን ሰውነታቸውን ለቆ የጠፋባቸው ባዶ የኪራይ ቤቶች !! (ባለትዳር አናከራይም ሂሂሂ)

“ወደዛ ቶሎ እንደሚሆን አድርጊውና ሰርጉን አብሊን” ያሉም አሉ (አፈር ጠጠር ይብሉ)

አንድ ቀን ሳምሪ ክፍል ውስጥ ቡና ተፈልቶ ክፍሏ በእጣን ታፍና ሳምሪ በቢጃማ ፍራሹ ላይ ተቀምጣ አስቴር እየዘፈነች (ቁጨ ብለህ አጫውተኝ አትለይ ከጎኔ እያለች ) እንዲህ አለ

“ ሳምሪ “

“ወይየ እዩ” በአፏ አቤት ማለቷ አልበቃት ብሏት በእጇ እጁን እየያዘችው እዮብ መናገር ይፈራል እጁን ይዛ አይን አይኑን እያየች ጠበቀችው

“አንድ ነገር ልነግርሽ ነበር እንዳትቆጭ” እየፈራ ፊቱ በሃዘን ተወሮ አስፈቀዳት

እጁን ቀስ ብላ ለቀቀችው ፊቷ ተቀያየረ ምን እንደሚል ቀድማ የሰማች ይመስል ሳግ በተናነቀው ድምፅ “ተወው አትንገረኝ እ..ን ዳ ት ና ግ ረ ው !” አለች!!

“ታ ዲያ እኔ ጋር እስከመቸ ሳምሪ ” እዮብ በምሬት ተነፈሰ

“ ካልፈለከኝ ሂድ አልፈለኩሽም ሰለቸሽኝ በል ሰበብ አታብዛ” እንበዋ ተዘረገፈ

ዝምምምምምምምምምምምምም !! የተጣደው ቡና ይንተከተካል !! እንበዋ ጠብጠብ ጠብ ጠ.ብ ጠ..ብ ጠ ብ ጠ ብ ጠ ብ! ጠ “ልሂድ “ አለና ተነሳ እዮብ እጀን ይዞኝ ከእጁ ጋር እየተጫወትኩ ነበር እጁ ላይ ባለችው የነሃስ ብራዝሌት (ማን ሰጥቶህ ነው እናቴ ብሎኛል አንድ ቀን) እህቴ ዝም! አለች እዮብ አፍንጫዋ ጠመም ያለች ቆዳ ጫማውን አጠለቀ ጫማውን ሊያጠልቅ ጎንበስ ሲል አየዋለሁ ከኋላው ጥቁር ጅንስ ሱሪው የኋላ ኪሶቹ ጠርዝ ላይ በረዶ መስሎ ጨርቷል ሳስቷል ሳውቀው ጀምሮ እችው ናት ሱሪው ወጥቶ ሄደ

እህቴና እኔ ተነስተን በሩ ላይ ቆምን ከኋላው እያየነው መንገዱን ቀጠለ ሲያፍተለትላት የነበረችውን የማስቲካ ልባስ እጁን አወናጭፎ ወረወራት ወደአበባው ውስጥ

ድንገት “እዩየ” ብላ ተጣራች እህቴ ዞረ እዮብ

“ጠብቀኝ “ ወደቤት ገባች ለቃው የሄደችውን እጀን በአየር ላይ እንዳንከረፈፍኩት አሰብኩ ወደእዮብ ልሂድ ወይስ እንደቆምኩ በፌስታል የተጠቀለለ ነገር ይዛ መጣች በአጠገቤ ስታልፍ ዱለት ሸተተኝ አሃ ዛሬ በግ ታርዶ ነበር ለካ!! አቀብላው የሆነ ነገር ተነጋግረው ተመለሰች ወደእኔ ስትቃረብ እዮብ እንዲህ አላት

“ሳምሪ የበቀደሙኝ ሰሀን ሳላየው ቁሜበት ተሰበረ “ በይቅርታ አይነት

“ደንባራ ማሚ እንዳትሰማ ከዚህ ጥፋ “ ተሳሳቁ

ወደቤት ስንመለስ “የትኛው ሰሃን ነው የተሰበረው “ አልኳት

“ዝም በል”

ዝም!!

ዲያስፖራው ከሰማይ ከምድር የከበዱ ሽማግሌዎች ወደቤታችን ላከ። አባቴ ፊታውራሪ አሰፋ ግዛው በደስታ አበደ እናቴ በፍርሃት ዝም ብላለች ጎረቤቱ አሰፍስፎ ሰርጉን ጠበቀ ለሰርጉ የሚለብሰውን መረጠ "ያው ዲያስፖራ ጠይቆ እንቢ አይባልም ያውም አንዲት ተራ ፀሃፊ የጡረተኛ ልጅ" እየተባባለ ይሁንና መልሱን ለመስማት አሰፈሰፈ የብሄራዊ ቡድን ወሳኝ ጨዋታ ውጤት ለመስማት እንጅ የእህቴን አገባለሁ አላገባም ምላሽ ለመስማት አይመስልም አሰፋሰፉ ሰፍሳፋ ሁሉ!!

እህቴ ሳምራዊት ላቧን ጠብ አድርጋ የምትኖር ጨዋ መሆኗን ማንም ያውቃል !! በወር 1600 ብር ደመወዝ እየተከፈላት ቴሌ በኦፕሬተርነት ትሰራለች !! ጥሩ ልብስ አትለብስ አትኳኳል ጓደኛ የላት 1600 ብር ትቀበልና 700 ብር ለእማማ 300 ብር ለአባባ ትሰጣለች 300 ብር ለይታ ታስቀምጠለች በቀጣዩ ቀን ስራ የምትገባ ከሆነ በሚስጥር "እዩብ ሲመጣ ይሄንን ስጠው እሽ እንዳትጥል" ብላ 300 ብሩን ትሰጠኛለች እዮብ ሲቀበለኝ ደስ አይለውም እኔ ብሆን እጨፍርለት ነበር ይሄን ሁሉ ብር ባገኝ አንዳንዴ የታክሲ ብር ስታጣ (ብዙ ጊዜ አታጣም) "ማሚ ትንሽ ከአስቤዛ የተረፈ ብር ይኖርሻል " ትላለች!!

ስራ ስትሄድ ከመሬት ተነስቶ እናፍቃታለሁ ከዛ እደውልላታለሁ "ጤና ይስጥልኝ የሰሜን ምስራቅ ሪጅን ቴሌ ኮሚዩኒኬሽን ፅ/ቤት እባክዎ ምን ልርዳወት ?" ትላለች ሳምሪ ! መንፈስ ትመስለኛለች ! የማላውቃት ደግሞ ፍጥነቷ ሳምሪ እኮ ስትናገር ቀስ ብላ ነው እንዴት ቻለችበት!! እንደትልቅ ሰው ስላናገረችኝ እህቴን እፈራታለሁ.. ቀስ ብየ ስልኩን እዘገዋለሁ..ድምጿን ስሰማ ደስታ በመላ አካላቴ ይፈሳል እወዳታለሁ ! አንድም ቀን ግን ደውየላት እንደነበረ ነግሪያት አላውቅም ) በዚች ደመወዝ ቤተሰባችንን ታስተዳድራለች የአባባም ጡረታ ተጨምሮበት ።

ሽማግሌወቹ ለሳምንት ተቀጥረው ከሄዱ በኋላ አባባ ምን አለ " እግዜር ቀኝ እግሩን እቤታችን አስገባ"።

ሳምሪ ሲነገራት ምንም ሳትደናገጥ "አይ አባባ የማይሆን ነገር ለምን ታስባለህ"

"ምን.? (ምናልሽ አንች ጨምላቃ በሚመስል የፊት ገፅታና ድምፅ)..ምኑ ነው የማይሆነው ነገር የተከበረ ጨዋ ምራቁን የዋጠ ባል ማግባቱ ነው የሚሆነውን ንገሪኛ" አለ በደም ፍላት አይኑን እያጉረጠረጠባት ! እየው አባቴ ፊታውራሪ አሰፋ ግዛው ባንዴ ፊታውራሪ መሸሻ ሲሆን ያውም መሃል አዲስ አበባ ላይ!!

"አባባ እኔ አሁን ማግባት አልፈልግም !! " ትንሽ የፈራች መሰለች

" ምን ዳር ዳር ትያለሽ ይሄ እንደተተኮሰባት ሚዳቆ ውቃቢው የተገፈፈ ዱርየ ጋር ስጃጃል ቁሜ ልቅር አትይም"( የእግዜርን ቀኝ እግር ገፍታ ከቤት ስታስወጣ ምን ያድርጋት)

ሳምሪ እንባዋ መጣ ጭንቅ አትወድም አማርኛው ሁሉ ያጥራታል ለፍቅር ብቻ ፈጥሯት ለንትርክ የሚሆን ቃል ከየትአባቷ ታምጣ።

አባቴ ቀጠለ " የማንንም ስልክ እየተቀበልሽ "ሃሎ" ስትይ ከመዋል በክብር ብትንፈላሰሽ አይሻልም (አንዳንዴ አዲስ ነገር ሲጭኑብን ሲፈልጉ ያለንን የሚያስጥሉብን ልምጭ ብዛቱ)

"ስራየን እወደዋለሁ አባባ አንተስ "በጀግንነት የተዋጋህለትን" የቆሰልክለትን ህዝብ አይደል "ሃሎ" እያልኩ ሳገለግል የምውለው " እንዴ ሳምሪ ናት የተናገረችው ገረመኝ

"በጀግንነት የተዋጋህለትን" የሚሉት ሁለት ቃላት አባባን ለሁለት ዲቃ ዝም አስብለውት ቆዩና ወደነበረ ቁጣው ተመለሰ "እሱን ተይው ድፍን የኢትዮጲያን ህዝብ ሃሎ ከማለት "ከአማሪካ የተደወለ አንድ ስልክ ማንሳት ይሻላል ደሃ ቢደውልም ቢያነሳም ትረፉ ብር ማስቆጠርና ጆሮ ማደንቆር ነው"

"አባባ አጭሩ ነገር እኔ አላገባም " ብላ ብዲግ ስትል

"ተቀመጭ!" ብሎ ጮኸባት ! በድንጋጤ ዘፍ ብላ ተቀመጠች የሆነ ሰው ከኋላዋ ፀጉሯን ጎትቶ ያስቀመጣት ነበር የምትመስለው.. እኔ ራሴ ተከትያት ልነሳ ነበር። ለሷ የተወረወረው "ተቀመጭ" አስቀመጠኝ እንደለማዳ ውሻ

ምንጣፉ ላይ ከእግሯስር ኩስስ ብየ ነው ይሄን ሁሉ የምሰማው ስታወራ በደመነፍስ ፀጉሬን በጣቶቿ ታበጥርልኛለች

ከዛን ቀን ጀምሮ በገባች በወጣች ቁጠር አባቴ ጋር ዱላ ቀረሽ አምባጓሮ ሆነ አባባ የሚናገረው ቃል ሁሉ ያበሳጫል "አንችን ከመውለድ ጦር ሜዳ በሞትኩ ለአሞራ እራት በሆንኩ" ይላል

ሽማግሌወቹ እንደነገ ወዲያ ሊመጡ እንደዛሬ ሳምሪ ድክም ብሏት ስትገባ ገና ከበረንዳው አባባ ተቀበላት እስከማታ ሰደባት "የሰው ትንሽ "አላት "እቤቴ ድረስ ወንድ እየጎተተሽ ስትዳሪ ዝም ማለቴ አስናቀኝ" አላት

ሳምሪ በአንድ ሳምንት የቀኝ አኘኗ ስር ማዲያት የሚመስል ነገር ወጣባት ፊቷ ጠቆረ አይኗ ስታለቅስ የምታድርበት ያስታውቃል

"ብዙ ነገር ያየን ሰወች ነን ማግኘትንም ማጣትንም ገና ለገና እያመጣሽ የምትወረውሪልንን ደመወዝ ጠባቂ አድርገሽን ናቅሽን ማን አለብኝ አልሽ "

"ኧረ ተው እንዲህ አይባልም" አለች ክፉ ደግ ተንፍሳ የማታውቀው እናቴ በቁጣ አይኗ እየተንቀለቀለ እንባዋ እየቀደማት እናቴ ከተናገረች ጉዳዩ መሯል ማለት ነው !!

"ዝም በይ! አንች ነሽ የልብ ልብ የሰጠሽት እንደሰወቹ እናቶች አትመክሪያትም ስትንዘላዘል ጭራሽ ለእርሷ ከማበር ለነገሩ አንችስ ማን ሆንሽና የእናቷ ልጅ!!" ብሎ እናቴን ኩም አደረጋት!! (እናቴን ከቡና ቤት አግኝቶ ነው ያገባት)

ወደእህቴ ዞሮ "አይንሽን እዚህ ቤት እንዳላየው መደሃኒያለም አይለመነኝ አንዱ ቦታ ሂጂ አንጥፊ እለምንለሁ እንጅ ያንች ገንዘብ ከእንግዲህ አልበላም !! "አላት እየተንዘፈዘፈ!

"አባባ እኔ ምን መሄጃ አለኝ ካለእናንተ !" አለች ሳምሪ (ሳግ ባነቀው ድምፅ)

"መሄጃሽንማ ገፋሽ ወርቅሽን ጭቃ ላይ ጣልሽው ሂጂ እዛ ከንቱ ጋር አብረሽው በየጎዳናው ዙሪ አባይ ማደሪያ ሳይኖረው አሉ "

እህቴ ዝም ብላ ፀጉሬን ታሻሻለች አያያዟን ግን እስኪያመኝ ድረስ አጥብቃው ነበር በጣቶቿ መቆፈር አይነት ለአባባ ያላትን ፍቅር አናቴ ላይ ገላ ልትቀብረው ያሰበች ነው የምትመስለው እንደውም በዚህ ሳምንት በጠና ታሞ ነበር። ተነስታ ወደክፍሏ ሄደች ተከትያት ሄድኩ ክፍሏ ውስጥ ገብታ እንደወትሮው "ጫማዋን አልቀየረችም" ሻንጣዋን አነሳች ከፊተችው አልጋዋ ትራስጌ የነበረውን የእዮብን ፎቶ ስታነሳ አለቀሰች በቲሸርት ጠቅልላ ሻንጣዋ ውስጥ አስቀመጠችው አንድ "የቆየ ባዶ የሽቶ እቃ" ወደቦርሳዋ ጨመረች።

"ሂድ ወደ ሳሎን " አለችኝ

"አልሄድም" ብየ እግሯ ላይ ተጠመጠምኩ !! ብር ብላ የምትሄድብኝ መሰለኝ !! እንቅ! እጇ እስከደረሰበት አቅፊያት!!

እቅፍ አደረገችኝ እቅፏ ላይ እንቅልፍ እንደወሰደኝ ትዝ ያለኝ ጠዋት ስነቃ ነበር የለችም የእዮብ ፎቶ የለም ሻንጣዋ የለም ጫማወቿ የሉም ፎጣዋ የለም የጥርስ ቡርሽ የጥፍር መቁረጫና መሞረጃወቿ የሉም የእህቴ ትዝታወች ቤቱ ውስጥ የሉም ልቤ ብቻ ቤቱ ቤት ብቻ ሁኗል አይ ቤቱ በረንዳ ሁኗል እኔ በረንዳ አዳሪ

ትራሱ ላይ "ይሄን ለእማማ ስጣት የሄን ለእዮቤ እንዳትጥል " ከሚል ማስታወሻ ጋር የመቶ እና የአምሳ ብር የብር ኖቶች (የት ሄደች?)

በጥድፊያ ሳሎኑን አልፌ ወደበረንዳው ሄድኩ አባቴ ውዳሴ ማሪያሙን በተመስፆ ይደግማል

"አባባ ሳምሪስ ?" አልኩት ሳልፈራው

“ሂድ ወዲያ !!” አለችና ወደውዳሴው ”አንች የማለዳ ብርሃን ነሽ አንች መጠጊያ ላጡ ”

ወደቤት ገባቸ

“እማማ ሳምሪስ ? “ ፀጥ ብላ አየችኝና በማይሰማ ደካማ ድምፅ “ሄደች” ብላኝ ወደጓዳ ገባች !!

ተንደርድሬ ወደስልኩ ሄድኩ አባባ ያየኛል ብየ ሳልፈራ ደወልኩ “ጤና ይስጥልኝ ቴሌ ነው ምን ልርዳወት “ አለ አንድ ጎርናና ድምፅ ያለው ኦፕሬተር

“ ሳምሪን ነው የምፈልገው ሳምሪ እህቴን አለች ? ነይ እኔንም ውሰጅኝ ብሎሻል በልልኝ እኔ እኮ እወድሻለሁ ለምን ትተሽኝ ሄድሽ በልልኝ ሳምሪ እህቴን “

“ማሙሽየ ይሄ እኮ ቴሌ ነው ሃሃሃሃ ”

****** ******** *******

ዲያስፖራው እዛው ጎረቤታችን ኑአሚን የምትባል የማታ ጭፈራ ቤት የምትሰራ ዘፋኝ አገባ አስተማሪ “ቦይ ፍሬንዷን አፍንጫህን ላስ “ ብላው ለእህቴ በተተኮሰው የሃብት ጥይት ፍቅሯን ገደለች !!

****** ****** *********

ቁራሌ የሚሰራ አንድ የሰፈራችን ልጅ አለ ከነስሙ “ጃምቦ ቁራሌው” አንድ ቀን የሰፈር ልጆች ጋር ኢላማ ኢላማ ስንጫወት ደረሰና ኬሻውን አስቀምጦ ተቀላቀለን የእኛን ኢላማ ሰብረን ኢላማ የሚሆን ነገር ስናፈላልግ ድንገት ከእቃ ማስቀመጫው ውስጥ አንድ ጠርሙዝ አወጣና አስቀምጦ ጠርሙዟን ለመስበር ድንጋይ አነሳን ጃምቦ ወረወረ ሳታት ተረኛ እኔ ነኝ አነጣጠርኩ ጠርሙዙን አየሁት ልቤ ደነገጠ ቀርቤ አየሁት የሳምሪ የሽቶ ጠርሙዝ !! ቢቆሽሽም እራሱ ነው

“አንተ የት አባህ አገኘኸው “ አልኩት ግራ ተጋብቸ እንባየ መጥቶብኝ ሳምሪየን ያገኟት ነው የመሰለኝ ሳምሪየን ኢላማ አድርገን በድንጋይ ያባረርናት ቤተሰቡ ሰፈሩ ህብረተሰቡ ዲያስፖራው ሳምሪን የወገርናት “ከእናንት ሀፂያት የሌለበት ይውገራት “ ሲባል ዘራፍ እኛ ሀፂያት የለብንም.. እኛ ቅዱሳን እኛ ንፁሃን ብለን ሳምሪ ላይ የወረወርን መሄጃ የሌላትን ወፍ በድንጋይ ከደሃ ጎጆዋ ያባረርናት

“ኧረ ማሪያምን ሰርቄው አይደለም እህትህ ሻንጣ ይዛ የሄደች ቀን እዛ ሱቁ አካባቢ አገኘችኝና “ይሄን ትገዛለህ “ ስትለኝ ብር ከስሙኒ ገዛኋት የሚፈለግ መስሎኝ ነበር ግን በቃ አይፈለግም ሲሉኝ ዝም ብየ አስቀምጨው ነበር ከፈለክ ውሰደው “ አለ ጃምቦ

ጠርሙዙን ወሰድኩት!! እቅፍ አድርጌ.. በቲሸርቴ ስር ሰውነቴ ላይ ለጥፌ ((((((ይሄ ጠርሙስ ባዶ የሆነው ምን ሁኖ ነው ሽቶው ሳምሪየ የምትባል ሚስኪን እዮብ የሚባል ፍቅሯ እግር ላይ ደፍታው ነው.. በቃ እንደዛ ነው ”ሽቶውን ስለምን እናባክነዋለን ሽጠን ለድሃ አንመፀውተውምን “ብለዋት ነበር ጎረቤቶች አባቴን ጨምሮ))))))) !! ከሳምሪ የቀረኝ ነገር አንድ ባዶ የሽቶ ጠርሙዝ ብቻ ከኋላ ጓደኞቸ ሌላ ጠርሙዝ ሲሰብሩ ሰማሁ ከሸሸሸሸ!!

አስር የሽቶ ጠርሙዞች በግድግዳ ላይ አንዱን ስንከሰክሰው ምንም ይቀራል

ምንም ይቀራል

ምንም ይቀራል

ምንም ይቀራል ( ተጠንቀቅ!! ባንዲራውን አውርድ ጠይሙን ባንዲራ ለሞላ ንፋስ እንዳይውለበለብ የከለከልከውን ቆንቋና ሁሉ!! ባወረድከው የክብር ባንዲራ ፋንታ ድሪቶህን ስቀል ! ቀለም አልባ ታሪክ አልባ ድሪቶህን !! ቡቱቷም )

ሂሳብ ምናባቱ ያገበዋል ስለ ስሜት ቁጥር አባቱ ይብላና!!

ሌላ ቀን ማታ አባባ አንድ ነገር ጠየቀኝ ሰርጉ ባለፈ በስንት ወሩ " ይሄ የሰርግ መጥሪያ ሌሊት ሌሊት እንደ አብሪ ትል የሚያበራው ለምንድን ነው ? "

ረጋ ብየ መለስኩለት እንደሳይንቲስት

"ፅሁፉ ከፎስፎረስ ስለተፃፈ ነው" አባባ ዝም ብሎ ቆየና ወደዛ ወስደህ ጣልልኝ!!" አለ !!

ምኝታ ቤቴ ወስጀ የሳምሪ ሽቱ ጠርሙስ ጎን አስቀመጥኩት። ማታ መብራቱን ሳጠፋ ካርዱ ላይ ያሉት ፅሁፎችና ጌጣጌጦች ተብረቀረቁ ግን "ፎስፎረስ" ምንድን ነው ካርዱ ያበራል የሳምሪ የሽቶ ጠርሙዝ ግን አያበራም ያልታደለ ዘመን ላይ ቅጥፊት ነው የሚያብረቀርቀው !!!!

ይነጋል ! የሳምሪ ጠርሙዝ ያበራል !

ይነጋል ! ቀጣፊው ካርድ ይጨልምበታል

ይነጋል! የበራው ሁሉ ብርሃን አለመሆኑ የሚገለጥበት ዘመን ይመጣል ! አንስቸ በጨለማው ውስጥ ወረወርኩት ጨለማው ላይ አፍጥጬ አሰብኩ እራሴ እስኪፈነዳ

እህት አለችኝ ጥቁር ዘንፋላ ፀጉር ያላት ሳቋ " እንደፎስፎረስ" በጨለማ የሚያበራ እህት አለችኝ እጆቿ ፀጉሬ ላይ ሲርመሰመሱ የሚያስፈነጥዙኝ እህት አለችኝ ሙዚቃ ድምፅ ያላት እህት አለችኝ ለተራበ ዱለት የምትሰጥ

ታድየ !! እህት አለችኝ አንድ ቦታ ስሟ በክፉ የማይነሳ ሴቶች ላይ ክፉ ሊናገር የጀመረ ሁሉ እሷን ሲያይ ዝም የሚልላት ጨዋ እህት አለችኝ

እህት አለችኝ ሳምሪ የምትባል ፍቅሯን ሽጣ በሊሞንዚን ከመሄድ የሽቱ ጠርሙዝ ለቁራሌ ሽጣ በታክሲ መሄድን የመረጠች ያላትን ለእማማ ሰጥታ የአለምን ችግር በብር ከስሙኒ ልትፋለመው የወጣች

ስሟ ሳምራዊት ነው !! የአባቷን ስም አላውቀውም አባት የላትም እኔም አባት የለኝም!!

ኃይለኛ ዝናብ ጣለ!!

# ተሰቀለ ቢሉኝ ”. ባርኔጣው” ነው ብየ

የአራተኛ አመት ተማሪወች እንደነበርን አስቻለው የሚባል ጓደኛችን ለስምንት የምንጋራው ዶርም ውስጥ እራሱን በቀበቶ ሰቅሎ ተገኘ!! አስደንጋጭ አሳዛኝ ጉዳይ!! አስቻለው የለየለት ሱሰኛ ነበር (የሞተ ሰው ወቀስክ አትበሉኝና) ያጨሳል ፣ይቅማል ፣ ይጠጣል (ያገኘውን ሁሉ ይጠጣል ) ውሃ ሲጠጣ ራሱ “ትፍ ትፍ “ ይላል በጠላ ገፊት ለምዶበት !! ሃሽሽ ምናምንም ከመውሰድ አልፎ ግቢ ውስጥ ያከፋፍል ነበር ኧረ አበዛሃው እንዳትሉኝ እንጅ ሴተኛ አዳሪ ይዞ ዶርም ይመጣ ሁሉ ነበር (አልፎ አልፎ እንግሊዝኛ ጣል የምታደርግ ሴተኛ አዳሪ ከገጠመቻችሁ ግቢ ጎራ ብላ ልታውቅ ትችላለች ብላችሁ ጠርጥሩ።)

ያው አንዳንዴ ደግሞ ታጥቦ የተሰጣ ልብስ ያነሳ ነበር እየተባለ ይታማል (እኔንኳ ቲሸርቴን ከወሰደብኝ በኋላ እንዲህ ሲል አስፈቅዶኛል ”አብርሽ ያንተ መሆኗን ሳላውቅ ያችን ሁልጊዜ የምትለብሳትን ሰሚያዊ ቲሸርት ወስጃታለሁ” )እና አስቻለው እራሱን ሰቅሎ ሞተ።

ታዲያ ብዙ ተማሪዎች እኛ ዶርም እየመጡ አስተዛዘኑን “አስቹ አሪፍ ልጅ ነበር አይዞን ወይ አስቺ ሆዱ ኮ ንፁህ ነው ላፉ ይናገራል እንጅ አንዴ ምን አደረገ መሰላችሁ ” እያሉ ስለደግነቱ ስለቸርነቱ እንደጉድ አወሩ። ሲቆይ ዶርማችን በር ላይ በቀይ ተፅፎ የተገኘው ሙሾ እንዲህ ይል ነበር

ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብየ (የድግሪው ቆብ)

ተሰቀለ ቢሉኝ ያ ሱሪው ነው ብየ (የነበረው አንድ ያረጀ ጅንስ ሱሪ ብቻ ነበር)

ተሰቀለ ቢሉኝ “ግሬዱ” ነው ብየ

ለካስ አስቻለው ነው ትልቁ ዱርየ !!

ቢከፋንም ነገሩን በቅሬታ ፈገግታ አለፍነው (ይቅርታ አላለፍነውም) ማታ ግማሹ ተኝቶ አንዳንዶቹም አልጋቸውን ጋርደው እያጠኑ አስናቀ የሚባለው የዶርማችን ልጅ “ግን ምን ለማለት ተፈልጎ ነው “ አለ ፊቱ ላይ ቁጣ እየተንተገተገ እኔን ነበር የጠየቀኝ።

ጫማየን እየፈታሁ ነበር ልተኛ።

“ምኑ አስኔ” አልኩት አይኔን ከጫማ ማሰሪያየ ላይ ሳልነቅል

“ በር ላይ የተፃፈው ግጥም ነዋ!! “

“ያው ሙድ ለመያዝ ምናምን ነው የሚሆነው የግቢ ነገር ታውቀው የለ ያንተ ሃዘን የሌላው ሃዘን ላይሆን ይችላል” አልኩ ቀለል አድርጌ

“ ኖ ኖ ሙድ እማ አይደለም ሆነ ብሎ የጎጃምን ህዝብ ታሪክ ለማጉደፍ የተሰራ ሴራ ነው” ብሎ ጠረንቤዛውን በቡጢ ደቃው

“ኧረ አስኔ ምን ያገናኛዋል ጎጃም እዛ ማዶ ዩኒቨርስቲ አዚህ “

“የኒቨርስቲ እንጅ ስንቱን ታሪክ ኩል የሚኩል ስንቱን ጥላሸት የሚቀባ የተንኮል ማጀት”

“ቆይ አስቻለው የሸሮ ሜዳ ልጅ የተፃፈው ስለሱ እና ጎጃም ” አልኩ ሳቅ እየተናነቀኝ

“ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብየ ለካስ በላይ ኑሯል ትልቁ ሰውየ “ የሚለውን ግጥም እኮ ነው ቀይረው ለማንም ዱርየ የሚጠቀሙበት ”

“አይ አስቻለውንማ “ማንም” አትለውም አይደብርህም ትላንት ተለይቶን ዛሬ ” አንዱን ጫማየን ፈትቼ አንዱን ሳልፈታ ከርከር

“አይ ዶንት ኬር የበላይ ክብር በማንም ደደብ አይጎድፍም ” አለ እንደዛሬው ሲበሳጭ አይቸው አላውቅም በጣም እየጮኸ ስለነበር የሚናገረው የዶርም ልጆች ከተኙበት እየበረገጉ ተነሱ የሚያጠኑት ግርዶሻቸውን ገለጥ እያደረጉ ብቅ አሉ

“ምን ድን ነው ሰላም አይደላችሁም “ አለ ገብረ መስቀል በአስናቀ ጩኸት ከእንቅልፉ በርግጎ ተነስቶ

“ማን ጠራህ አንተን ?!” አለ አስናቀ በበለጠ ቁጣ ለነገር ተጋብዞ

“እ”

“ደንቆሮ”

“ማነው ደንቆሮ “ አለ ገብረ መስቀል ህልም ይሁን እውነት ግራ ገብቶት፡፡ “አንተ ነሃ! ሴታሴት! በር ላይ እየተደበክ የሰው ታሪክ ከማጉደፍ እንደወንዶቹ ፊት ለፊት አትናገርም”

“ዋይ ምን ጉድፍ ታሪክ ነው እሱ አተ ግሬድ ተለጠፈ እንዴ ?” አለ ገብረ መስቀል፡፡ የታሪክ ተማሪ ነው ቀልድ መስሎት ነበር፡፡

“በላይ አገር አላስገነጠለም ! በላይ ወንዱ በዘር አልከፋፈለንም ! ለአንድ ኢትዮጲያ ሂወቱን የሰጠ ጀግና ነው “

“ዋ ይ ታዲያ በዚህ ሌሊት በላይ በላይ ምትሎው ሙን ሁነኖህ ነው ? “

“በላይን እንኳን በር ላይ የተፃፈ ዝባዝንኬ ባህር በር ላይ በመርከብ የተዘረገፈ ሰላቶ ክብሩን አልነጠቀውም”

“ባክህ አትጨሁብን እናጥናበት” አለ ቶሎሳ ከግርዶሹ ብቅ ብሎ

“ ዝም በል ባክህ ! አንተ ላይ ማን ደረሰ ”

“ጩኸትህ ረበሸኛ “(ቶሎሳም የታሪክ ተማሪ ነው)

“ ጩኸቱ ጩኸትህ ነበር ቢገባህ በላይ ላንተም ክብር ነበር የታገለው ኢትዮጲያዊነት ስሜት ቢኖርህ ይቆጭህ ነበር” አለው ሽቅብ ወደ ቶሎሳ አልጋ እየተመለከተ

“ ማነው ኢትዮጲያዊነት ስሜት የሌለው “

“አንተ ነሃ! ለስሙ የታሪክ ተማሪ ነህ! በርህ ላይ ታሪክ ታንክ እንደሄደባት የቤት መኪኛ ተጨራምቶ እየተፃፈ አንተ ጋርደህ የአውሮፓ ተረት ታነባለህ “ማንትስ በመርከብ ተኩዞ አሜሪካን አገኘ” በል የራስህ አገር ከእጅህ ላይ እየጠፋች”

“ አብርሃም ኸረ በክርስቶስ ይሄን ሰው ፀበል ውሰዱት” አለ ዲንሳሞ እየሳቀ ቀልድ ይቀናዋል ሁልጊዜ ሳቂታ ነው

“ስርአት! ፀበል መቀለጃ መሰልህ እንዴ” አልኩት በብስጭት ጴንጤ ስለሆነ ኦርቶዶክስ እምነቴ ላይ ምናባቱ ያላግጣል ብየ ቱግ አልኩ!!

“እንዴ ፀበል ያድናል ትሉ የለ እንዴ “

“ መቀለድ ሳይሆን ሞክረው አንተም ከዚህ እብደትህ ትፈወሳለህ”አልኩት አፍጥጬበት !በእምነትና በሚስትማ ቀልድ የለም(ሚስት እንኳን )

“እኔማ ቃሉ እንደሚል “መዳን በሌላ በማንም የለም ትድኑበት ዘንድ ”

“ዝጋ እዛ የምትሰብከውን ስበክ ይሄን ተረትህን “

“ጌታ ይገስፅህ “

“ ማንን ነው የሚገስፀው አንተ ? ” በብስጭት ከአልጋው ላይ ጎትቸ ላወርደው ስንደረደር የጫማ ማሰሪያየ አወላከፈኝና አልጋው ስር ጥቅልል አልኩ !! ዲንሳሞ ጭራሽ መዘመር ጀመረ “ ነብሱ በትእቢት ያበጠ ጠላቴ ተገለበጠ ሃሌ ሉ ያ ” ተነስቸ ላጋጨው ስል ሄኖክ ከዛ ተወርው መጥቶ ገላገለን!!

ዲንሳሞ ሊያቆም ነው “ እሽ ካልቻላችሁ ሪፈር ፃፉለት እንፀልይለት በኢየሱስ ስ ም! “ አለ እጁን ወዳስናቀ ዘርግቶ እየሳቀ

“ መናፍቅ! ዋና ታሪክ አጥፊወቹ እናንተ ናችሁ ምን ታሾፋለህ ዘረኞችን አትገስፅም “ አለ አስናቀ ወደገብረ መስቀል በአገጩ እየጠቆመ

“አተ አትጨሚለቅ ሞታገስ አታውቅም? ዙም ብለህ ሰው ጭቅላት ላይ ፉጥ ትላለህ ጨምላቃ.” ብሎ ዘሎ ከምኝታው ወረደ ዶርሙ ቀውጢ ሆነ !! አስናቀ ባለ በሌለ ሀይሉ ገብረ መስቀልን ሲደረግመው አልጋው ብረት ጋር ተጋጨ ወዲያው የገብረ መስቀል እርግጫ አስናቀን ክፉ ቦታ ላይ አገኘው እንደምንም አገላግለናቸውና ገበረ መስቀል ወጥቶ ሄዶ ሌላ ዶርም አደረ በቀጣዩ ቀን አስናቀ ከየት እንደተወረወረ ባልታወቀ ድንጋይ ተፈንክቶ ክሊኒክ ዋልን!! ነጭ ፋሻውን አናቱ ላይ ጠምጥሞ ሲፎክር ቅስናውን የገፈፉት ቄስ ይመስል ነበር !! ሰላም ጠፋ ግቢ ውስጥ በአንድ ሳምንት ብቻ አራት ተማሪ ተፈነከተ

የተፈነከቱ ተማሪወች ዝርዝር፡-

ሰኞ አስናቀ

ማክሰኞ ማታ ጎይቶም

እሮብ አረጋ

ሃሙስ ተክላይ

አርብ መላኩ

ቅዳሜ ትርሃስ (የሴቶች እኩልነት)

እሁድ አትጠገብ (ቤተ-ክርስቲያን ስትሄድ)

ሰኞ ማታ ሚስኪኑ አብርሃም !!ሰምታችሁኛል? አብርሃም እኮ እኔ ነኝ !!

ስለአፈነካከቴ አጭር ገለፃ ፡-

ሰአቱ ማታ 3፡00 ሰዓት አካባቢ ይሆናል በግ ተራ ሂሩት እና እኔ ጨለም ያለ ቦታ መርጠን በነፋሻው አየር እየተሳሳምን ነበር።

ሚ ሚጷጷጷ እስከዘላለሙ እወድሻለሁ ሂሩትዮ”

.......ጷጷጷሚ አ ብርሽየ ለምን ስልክ ስደውል ትዘጋብኛለህ?

ላይብረሪ ነበርኩ የኔ ማር ጷጷጷ

“አብርሽ እስከዘላለሙ አብሬህ መሆን እፈልጋለሁ ምንም ቢፈጠር”

ቀኝ እጆ በቲሸርቷ ስር አልፎ የጡት ማስያዣዋን ጠንካራ ከፈፍ መሰርሰር ጀመረ( ጡት የላትም ለምንድን ነው የጡጥ ማስያዣ የምታደርገው ?! አንዳንድ ሴቶች በሌለ ጡት የጡት ማስያዣ ሲያደርጉ ልባቸውን ለመያዝ የሚጠቀሙበት ነው የሚመስለኝ ታዲያ ጡት ከሌላት እጆ ምን እየፈለገ ነው? ምን አፈላሰፈኝ ዝም ብየ አልስምም ጲጲጲሚ)

አይኖቻችንን ጨፍነን በፍቅር አየር ላይ መንሳፈፍ ጀመርን ሚፅፅፅፅ ሚ ድንገት ጓ !!!. ከፍቅር ሰማይ የሚያምዘገዝግ የአየር መቃወሚያ!! ከነበርኩበት ከፍታ አምዘግዝጎ እውነተኛው አለም ላይ የፈጠፈጠኝ ድንጋይ ከኋላየ ራስ ቅሌን ነረተኝ!! "ሂሩት ባል አላት እንዴ " የሚል ሃሳብ በለጭ አለብኝና እራሴን ስቸ ወደኩ።

ክሊኒክ ውስጥ ስነቃ ግቢው ቀውጢ ሆኗል ፌዴራል ፖሊስ የአመፅ መበተኛ መኪና

የተማሪ አመፅ ጩኸት መዝሙር !!

""አስቻለው ለምን ለምን ሞተ?"

"አብርሃም ለምን ለምን ሞተ ?"

ምን ? አ ብ ር ሃ ም ? አይኔን ስገልጥ የዩኒቨርስቲያችን ነርስ (ያምሮት) እና ሶስት ፌዴራል ፖሊሶች ቁመዋል "ሲስተር አብርሃም ለምን ሞተ ሲሉ ሰማሁ? "

"አዎ ! እንዴት ነህ አሁን? " ጣረ ሞት የጠራት ይመስል ደንግጣ።

" አንችኑ ልጠይቅሽ እንጂ ተማሪወቹ እንደሚሉት ሙቻለሁ ወይስ ?????? " ከት ብላ ሳቀች እንደምንም ተነስቸ አልጋው ላይ ቁጭ ስል

"ስማ " አለኝ ፌዴራል ፖሊሱ

"አ ቤት" አልኩ በድንጋጤ የጨበጠውን ጥቁር ዱላ እያየሁ ዱላው አፍ አውጥቶ የጠራኝ ነበር የመሰለኝ

"ተሻለህ?"

"አዎ አሁንማ " ብየ ከአልጋየ ላይ ወርጀ ወደበሩ ሳመራ

"ወዴት ነው?" አለኝ በግርምት እያየኝ

"ወደውጭ" መለስኩ።

"ተመለስ!!" "ዘሩ ቀለጠ" አለ ያ ሰውየ !! ለካስ ሶስት ፖሊስ ለኔው ነበር!!

"አብርሽየ እስኪ ተረጋጋ ክርስቶስ እንኳን በሶስተኛ ቀኑ ነው ከሞት የተነሳው" አለች ነርሷ ሳቋን አፍና

"ሲስተር ምንድን ነው? "

" እስረኛ ነህ!! " አለች በሹክሹክታ !!

"እ"

"ሰ ም ተ ሃ ል"

" ዩኒቨርስቲው ውስጥ በዘር በተነሳ ግጭት አንተና አስቻለው ባልታወቁ ሰወች ተገላችኋል! አሁን ተማሪው ለምን እንደተገደላችሁ እንዲገለፅለት እየጠየቀ ነው እና ደግሞ ግጭቱን ያስነሳችሁት አንተ አስናቀ እና ዲንሳሞ ናችሁ የሃይማኖትም ጉዳይ አለበት አብርሃ አርፈህ ብትማር ምናለበት " አለችኝ የመጨረሻ ቃሏን ኮስተር ብላ ነበር የተናገረቻት ወዲያው ፌዴራል ፖሊሱ ቆፍጠን ባለ አነጋገር

" አልጋህ ላይ ተሰቀል" ብሎ አዘዘኝ።

“እሽ” ብየ ወደአልጋው ተጠጋሁ እንደቀራኒዮ እራቀብኝ በሁለት ጊዜ ሙከራ አልጋው ላይ ተሰቀልኩ።

በሃሳቤ....

ተሰቀለ ቢሉኝ ባርኔጣው ነው ብየ (የድግሪው)

ተሰቀለ ቢሉኝ አስቻለው ነው ብየ

አብርሽም ታዘዘ ኼረ እናንተ ሆየ

ብዬ ቀጥ ስል የነርሷ ትልልቅ ጡቶች መሃል መስቀሏ ተንጠልጥሏል መስቀሉ ላይ ጌታ ኢየሱስ ተሰቅሎ አየሁት።

“ሂሩትዬስ“ ብየ ነርሷን ጠየኳት ፍቅራችንን ታውቃለች ስንታመም ሁሉ ወደ ክሊኒክ የምንመጣው ከሂሩት ጋር አብረን ነበር።

“ሂሩትዬማ..አንተ ተፈንከተህ እንደወደቅከ ሂሩት ተያዘችና ሶስቱም ፖሊሶች በየተራ ታውቂዋለሽ?” እያሉ ሲጠይቋት ሶስት ጊዜ " አላውቀውም" ብላ ወደቤቷ ሄደች” አለችኝ !!

አሁን መሰቀል ሙሉ ሆነች ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ?

# የፍሪምባ ጦርነት

በንቃት ድንበር እየጠበኩ ነው !! ጠላት ፊት ለፊቴ አፍጥጧል በማንኛውም ሰአት ወደእኔ ሊንደረደር ይችላል። በመጠኑ ያደፈች ጅንስ ቁምጣየን ከጉርድ ቀይ ካኔተራ ጋር ለብሸ ነጠላ ጫማየኝ ከእግሬ ላይ ትበር ይመስል በእግሮቸ ጣቶች በመንከስ ከቤታችን በር ላይ ነው ያለሁት በእጀ ከአቅሜ በላይ የሆነ ብትር ይዣለሁ የአያቴ የተሰበረ መቋሚያ ነው መቋሚያውም የተሰበረው እዚሁ በአይነ ቁራኛ የምጠብቀው ጠላት ጀርባ ላይ ነበር !! አባቶቻችን ያወረሱንን ጠላት አያቶቻችን ባወረሱን ሰባራ መቋሚያ እየተከላከልሁ ነው።

ነገ በአል ነው ቤታችን ትንሽ ጠቦት ታርዶ ቤቱ ስጋ ስጋ ይሸታል እናቴ ቤቱን እና ስጋውን እንድጠብቅ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥታኝ ገባየ ሄዳለች በዋናነት የተሰጠኝ ተልእኮ

1. ዶሮወች የተሰጣውን የሽሮ ክክ እንዳይበትኑ
2. ሌባ ወደቤታችን እንዳይገባ

3ኛው እና ዋናው " ገንባው እዚች ግድም ድርሽ እንዳይል" ነው (እዚች ግድም ድርሽ እንዳይል ማን ? ገንባው !!)

ዶሮወች ስጡ አካባቢ መለቃቀም ይችላሉ ስጡን መብላትም ሆነ መበተን ግን የለባቸውም ሌባ በአጥራችን ጥግ መሄድ ይችላል "ደህና አደራችሁ" ብሎም ማለፍ አይከለከልም (ሰላምታ የግዜር ነው ትላለች እናቴ በእርግጥ ሲደጋግሙባት "ሶስት ጊዜ እንዴት አደራችሁ አንዱ ለነገር ነው" ትልና የእግዜር ሰላምታ ሲደጋገም ባለቤትነቱ የሰይጣን ሊሆን እንደሚችል በተዘዋዋሪ ትናገራለች ) እና ሌባው እስካልደጋገመ ድረስ ሰላም ብሎ ማለፍ ይችላል ገንባው ግን እዚች ግድም ድርሽ ማለት የለበትም!! ወላ ሰላም ማለት አይችልም ሰላምታውን ደገመም አልደገመም! በቃ የበላይ ትዛዝ ነው!!

ገንባው በመንደራችን የሚኖር ባለቤት የሌለው ትልቅ ድመት ነው!! የበግ ግልገል የሚያክል ዥጉርጉር ድመት ! እኔ ከተቀመጥኩበት አንድ አስራ አምስት ሜትር ራቅ ብሎ ከኋላው ሸብረክ በማለት ሁለት የፊት እግሮቹን ቀጥ አድርጎና ደረቱን ነፍቶ ጉርድ ፎቶ ሊነሳ ፎቶ አንሽ ፊት የተቀመጠ ጎረምሳ መስሎ ቁሟል !!

ተራ ድመት እንዳይመስላችሁ በሰፈራችን ውስጥ ያልገለበጠው ድስት ፣ ያልከፈተው ሞሰብ ፣የመንጠቅ ሙከራ ያላደረገበት የስጋ ዘር የለም መንደራችን ውስጥ ዶሮም ይሁን በግ ሲታረድ ገንባውን ጠባቂ ቃፊር ማቆም ቸል የማይባል ጉዳይ ነው "ገንባው ቢመቸው ቁሞ ከሚሄድ በግ ሳንባ ይመነትፋል " ይሉታል ሞኝ ሰፈርተኞች !! ታሪክ የሚተነፍሱበትን ፣ የተአማኝነት ሳንባቸውን በቁማቸው እንደመነተፉቸው ማን በነገራቸው።

ገንባው ግዙፍ ቢሆንም የተበሳቀለና በእድሜ የገፋ ድመት ነው ትንሽ ያነክሳል በዛ ላይ አንድ አይን የለውም ጅራቱም ቆራጣ ነው ሲጮኽ ድምፁ ያስፈራራል እማማ ብርዘገን ለፋሲካ የገነጣጠሏትን ዶሮ ላጥ አድርጎባቸው ሲሮጥ ጉሮሮውን በቢለዋ ወግተውት ነው ድምፁ ተበላሽቶ የቀረው የዛሬን አያርገውና "ሚያውውውው " ሲል የአይጥ ሰራዊትን የሚያርድ ሴት ድመቶችን የሚያማልል ድምፀ መረዋ ድመት ነበር!!

ድሮ የጋሽ ታምሩ ድመት ነበረ አንድ ቀን ታዲያ ፍርምባ የሚባል ነገር ሰረቀ ብለው አባ ታምሩ በአንካሴ ወጉት ከዛ በኋላ እሳቸው ቤት መኖር አቆመ ጨካኝ ናቸው ፍሪምባ ለምታክል ስጋ ብለው ተወልዶ ካደገበት ቤት አባረሩት ያውም በአንካሴ ወግተው እሳቸው ግን "ድመቱን ለፍርምባ ብየ አልወጋሁትም" ብለው ዋሹ ትልቅ ሰው ይዋሻል ? ደግሞ እኮ ያኔ የሆነውን ሁሉ በአይኔ በብረቱ አይቻለሁ ማሪያምን አይቻለሁ!

ድመቱ ፍርምባውን በአፉ አንጠልጥሎ መሬት ለመሬት እየጎተተ እኛ በት ፊት ለፊት ወዳለው የውሃ መውረጃ ቱቦ ሲሮጥ አባ ታምሩ ልክ እንደኦሎምፒክ ተወዳዳሪ ግራ እጃቸውን ወደፊት ቀስረውና ጦር የጨበጠ ቀኝ እጃቸውን እስከቻሉት ድረስ ወደኋላ ለጥጠው በሰፋፊ ርምጃወች ተንደረደሩ 1 2 3 ጦሩን ዥ ው አደረጉት ድመቱ

ሲሮጥ ጦሩ ሲከተለው ጦሩ ሂወት ያለው ይመስል ነበር ልክ ትቦው ጫፍ ላይ ሲደርስ የድመቱ የኋላ እግር ታፋ ላይ ተቀበቀበ አቤ ት ገንባው እንዴት አሰቃቂ ጩኸት እንደጮኸ እንዳንቡላንስ ነው የጮኸው ሲጮህ በአፉ የያዘው ፍርምባ ወደቀ አንድ ነጭ ያልቆሰለም ያልተወጋም ድመት ቀልቦት ወደትቦው ውስጥ ጥልቅ አለ !!

ጎረቤቱ ሁሉ "አቤት አጨካከን እናትየ የእግዜር ፍጡር ነው ምን በደለ?" እያለ ሲያጉረመርም አባ ታምሩ ታሪክ ፈጠሩ "የልጅ ልጇን አይኗን ሊያወጣት ነበር እኮ ግዴላችሁም ይሄ ድመት አውሬ ሁኗል " በማለት የፍርምባውን ፀብ "ትውልድ ለማዳን" የተደረገ ጦርነት አስመሰሉት ፡፡

የሚገርመኝ ታዲያ የመንደሩ ሰው ነው በወሬ ወሬ "ይሄ ድመት ምን ሁኖ ነው የሚያነክሰው ?" ሲባል "ይሄ "አውሬ" ነው የጋሽ ታምሩን የልጅ ልጅ አይኗን ሊያወጣት ሲል አያቷ ደርሰው ባአንካሴ ወጉት" ይላል !! ጭራሽ አይጦቻቸውን እያሳደደ እንዳልፈጀላቸው "አውሬ" የሚል ስም ሰጡት ለዚህ ሚስኪን ገንባው !!

ትልልቆቹ ሰወች ሁሉ ፀጉራቸው የሸበተ አስተማሪው ሰውየ (ትልቁ ግቢ ቤት ውስጥ የሚኖሩት ) ሳይቀሩ ይሄን የፈጠራ ታሪክ ያወራሉ ፡፡ ታዲያ ስለአገር ታሪክ እናውራ ሲሉ አላምናቸውም ትላንት አፍንጫቸው ስር ያውም በጠራራ ፀሃይ የተፈፀመ የድመት ታሪክ ወጊው በፈለገበት መንገድ የተረኩ ሁሉ ስለአገሬ ታሪክ እናውራህ ሲሉኝ እንዴት ልመናቸው ? በመንደራቸው የድመት ታሪክ ያልታመኑ ሁሉ ስለአገራቸው አንበሶች ጀብዱ ሲደሰኩሩ እንዴት ልቤ እሽ ብሎ ይቀበል ? ታሪክ ማውራት ታሪክ ከመስራት እኩል ጀግንነት እንደሚጠይቅ የገባኝ ያኔ ነው

ከዛን ቀን ጀምሮ ጦርነቶች ሁሉ የአደባባይ ምክንያታቸው ምንም ይሁን ምን ከኋላቸው ፍሪምባ የሚባል ስጋ ያለ ይመስለኛል ገንባው አውሬ አይደለም ገንባው የከለከሉትን የእለት እንጀራ ነጥቆ "ተመስገን" የሚል ሚስኪን ድመት ነው የእለት እንጀራውን ሲነጥቃቸው የዘላለም ስሙን ነጠቁት " ያኔ ባንካሴ ባንወጋው ኖሮ ትውልዱ ሁሉ እውር በሆነ " እያሉ ከድመት ጥፍር በባሰ የውሸት ጥፍራም ታሪክ ጭፍን ትውልድ ይፈጥራሉ፡፡

በኃላ ካቀረቀርኩበት ቀና ስል ገንባው የለም፡፡ "በስማም የት ሄደ ?" ሰባራ መቋሚያየን ወድሬ ወደጓዳ ሮጥኩ፡፡ መስኮቱ ገርበብ ብሏል፡፡ የጠቦቱ ታፋም ተሰቅሎ በነበረበት ቦታ የለም

ሮጨ ወደውጭ ስወጣ ገንባው ታፋውን እየጎተተ ወደትቦው ጥልቅ ሲል አየሁት፡፡

"ወይኔ አንካሴ ኑሮኝ በነበር ይሄን አውሬ አለቀውም ነበር" አልኩ ለራሴ ፡፡

# ተ ሸ ከ መ ና ታ ል!!

እናቴ ሁልጊዜ እንድናጠና ስትመክረን እንዲህ ትላለች

"እናተ ልጆች አጥኑ ተማሩ  እኔ ባለመማሬ ነው ጉዴን ተሸክሜ የዋልኩት " ማንበብም መፃፍም ስለማትችል በቁጭት አንድ ቀን ታዲያ ጠየኳት

"ማሚ የምን ጉድ ነው ተሸክመሽ የዋልሽው "

አወራችኝ

በደርግ ጊዜ መስከረም ሁለት ቀን ህዝቡ በግድም በውድም የድጋፍ ሰልፍ ይወጣ ነበር መስከረም ሁለት ደርግ ንጉሱን ገልብጦ ስልጣን የያዘበት ቀን ሳይሆን አይቀርም በአጭር አገላለፅ መስከረም ሁለት የደርግ ግንቦት ሃያ ነበር ።

ታዲያ እናቴ በወቅቱ የነበረውን የግዳጅ ውትድርና በመፍራት የመጀመሪያ ልጇን ወታደር ቤት እንዳይወስዱባት ደብቃ ሁለተኛ ልጇንም ገጠር እናቷ ጋር ደብቃ  ሶስተኛውን ልጇን አልጋ ስር አስቀምጣ አባቴንም "ታምሚያለሁ" በል ብላው እሷግን ነጭ ልብስ ለብሳ ሰልፍ ወጣች ግዴታ ነዋ!

የቀበሌው የሴቶች ሊግ ሃላፊ የነበረች ሴት በባለ እጀታ የጣውላ ሰሌዳ ላይ ተፅፈው የተዘጋጁ በሙቶ የሚቆጠሩ መፎክሮችን ለእናቴ እያሳየቻት

" ምረጭና አንዱን ውሰጅ " አለቻት

እናቴ ቀለል ያለችና በደማቅ ቀይ ቀለም የተሸሞነሞነች መፎክር መርጣ አነሳችና ወደሰልፉ ተቀላቀለች ከለበሰችው የሚያምር የአበሻ ቀሚስ እና ከራሷም ቁንጅና ጋር ተዳምሮ የኦሎምፒክ መክፈቻ ላይ "ኢትዮጲያ" የሚል ምልክት ይዛ ሰልፉን የምትመራ ቆንጆ አበሻ ትመስል ነበር !!

ታዲያ በዛ ሰሞን ማታ በቴሌቪዥን ደጋግመው እናቴን ከነመፎክሯ ያሳዩዋት ጀመረ ምን ይሄ ብቻ አመቱን ሙሉ ፎክረውም እናቴን ማሳየት ኢሃፓ ብለውም እናቴን መኢሶን ብለውም እናቴን ቀይ ሽብር ብለውም እናቴን ጓድ ሊቀመንበር ተናግረው ሲያበቁም እናቴን ማሳየት ጭራሽ ብሄራዊ ውትድርና ተብሎ ምድረ ወጣት ሲጓፈፍ የብሄራዊ ውትድርና አገር አቀፍ አርማ የእናቴ ፎቶ ሆኖ በየቦታው ተለጠፈ ከነመፎክሯ !! እንደውም አንድ ጋዜጣ ላይ የእናቴ ፎቶ ስር እንዲህ የሚል ፅሁፍ ሰፍሮ ነበር "አብዮታዊት ሶሻሊስት ኢትዮጲያ ነጭ ቀሚስ ለብሳ"

እናቴ ታዲያ መጀመሪያ አካባቢ በቴሌቪዥን በታየች ቁጥር በቁንጅናዋ የተመረጠች መስሏት አባቴ ላይ በኩራት ትነሰነስበት ነበር ሲደጋገምባት ግን ፈራች! በተለይም ጓድ መንግስቱ ሃይለማሪያም መስቀል አደባባይ በትልቁ የተሰቀለውን የእናቴን ፎቶ ለተሰበሰበው ህዝብ እያሳዩ በደም ፍላት " እንደነዚህ አይነት ጀግና እናቶች ያሉባት አገር በማንም ወመኔ ከሃዲ ስትወረር እንዴት ወንዶቿ አልጋ ስር ይደበቃሉ? እነዚህን በቅቧቃ ወንዳገረዶች በሳንጃ " እያሉ ንግግር ካደረጉ በኋላ እናቴ ስጋቷ ከፍ አለ እናም "ይሄ መፎክር ምንድን ነው የሚለው " ብላ ጠየቀች (ተሸክማው የነበረውን) ሲነበብላት አመዷ ቡን አለ !!

መፎክሩ እንዲህ ነበር የሚለው "የአብዮት ጠላቶችን ለማደባየት እኛ እናቶች ልጆቻችንን ካስፈለገም ባሎቻችንን በደስታ እናዘምታለን!!"

# የአባየ ስልክ እና ባዮሎጂ

እንዲህ እንደዛሬው በየሰው ኪሱ ሳይልከሰከስ በፊት ስልክ ተአምራዊ ንብረት ነበር !! አቤ.....ት ስልክ እንዴት እንደሚከበር እነደሚፈራ ...... ያኔ ኔትወርክ እንጅ ስልክ አልነበረም ዛሬ ግን ስልክ እንጅ ኔትወርክ የለም ሰው እራሱ ግንኙነቱ ከልብ ወዳጅነቱም ካንጀት ነበርና! ወይ ጊዜ !! እንግዲህ በሰፈራችን አንድ የቤት ስልክ ብቻ ነበረ ያለው ስሙ ደግሞ "የአባየ ስልክ " ብዙው የሰፈር ሰው የእኔን እናት ጨምሮ በዚህ ስልክ ነበር የሚጠቀመው ደግሞ ድምፁ የትና የት እንደሚሰማ ....ኪሊሊሊሊሊሊሊሊ ሲል የመንደሩ ሰው ሁሉ ስራ ያቆማል ወጣቶች ፍቅረኞቻቸው የደወሉ መስሏቸው የያዙትን ስራ እርግፍ አድርገው ጆሮና ልባቸውን ያቆማሉ እናቶች ሊጥም እያቦኩ ከሆነ ነጭ የቦክስ ጓንት ያጠለቁ መስለው ብቅ ይላሉ ... ግጥም ሁሉ አለ... ከሌላ የህዝብ ግጥም ተወስዶ ለአባየ ስልክ የተቀናበረ ...የመንደሩ ህፃናት ከዜማ ጋር የምንለው ...."የአባይይየ ስልክ ጩኸቱን ቢለቀው ከነሊጧ ወጣች ሳትለቃለቀው የሚል ስልኩ ሲጮኽ ልጆቻቸው አረብ አገር ያሉ እናቶች ልባቸው ይሰቀላል ... እናቴ እራሷ

"አቡቹ እስቲ እሱን ቆርቆሮ ቀንሰው " ትላለች ቴፑን ማለቷ ነው እንግዲህ ይሄ ሁሉ ሰው እንዳቆበቆበ የአባየ ልጅ ቡጡጡ በራቸው ላይ ትቆምና "እማማ ፋጤ ስ.....ልክ ከውጭ ነው ቶሎ በሉ" ብላ ትጮሃለች እማማ ፋጤ ወደአባየ ቤት ሲሮጡ ሌላው ጎረቤት ወደየስራው ይመለሳል ...... ስልኩ በተደጋጋሚ የሚጮኸው ለበአል አካባቢ ነው በተለይ ....ለአዲስ አመት ..... ቀላል ስልክ እንዳይመስላችሁ .....በዚህ ስልክ ስንቱ ከውዱ ጋር አውግቷል ...ስንቱ የውዱን መርዶ ተረድቶ በድንጋጤ ስልኩ የተቀመጠበት ጠረንጴዛ ስር ተጠቅልሏል ...ስንቱ ከጠፋ ዘመዱ ተገናኝቷል ...ስንቱስ ብር እንደተላከለት ሰምቶ ፈንጥዟል ...ኧረ ስንቱ ወደአባየ ቤት ሲንደረደር እንቅፋት አንግሎት ጥፍሩ ተነቅሏል ....ባፍጢሙም የተተከለ አለ ...... ይሄ ስልክ ስልክ ብቻ አይደለም ጩኸቱ የምስራች ነው ...ጩኸቱ መርዶ ነው ...... ከመንደራችን በላይያለው የጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ደውል ድምፅ የአባየን ስልክ ጩኸት ያህል ግርማ ሞገስ የለውም ለመንደርተኛው ........ወፍራም እንጀራ ...ደንዳና ናፍቆትና ፍቅር በቀጭን የስልክ ሽቦ ውስጥ ተጉዞ የሚያርፍበት ኬላ የት ነው ቢሏችሁ "የአባየ ቤት" በሉ!! ይህን ስልክ በጉጉት ከሚጠብቁ ቤተሰቦች መሃል የእኛ ቤተሰብ አንዱ ነበር አባቴ ለስራ ከእኛ እርቆ ይኖር ስለነበር እኛን ልጆቹን የሚመክረው ለሚስቱም የሆድ የሆዱን የሚናገረው በአባየ ስልክ ነበር ! እንደውም ግንባር ቀደሙ የአባየ ስልክ ተጠቃሚ ቤተሰብ የእኛ ቤተሰብ ነበር ታዲያ አባቴ ለበአል ሲመጣ ለአባየ የሆነ ነገር ይዞ ስለሚመጣ ስልክ ስንጠራ ቤተሰባዊ ቃና ባለው መንገድ ነው "ስልክ" ብቻ አንባልም

"እንዳይቆጥርበት ፍጠኑ ጋሽ ነው " የሚል ማስጠንቀቂያም ይጨመርበታል ለምሳሌ አባቴ ሲደውል እናቴ ከፊት እህቴ ከኋላ ወንድሜ ቀጥሎ እኔ ትንሸዋ እህቴ ተግተልትለን እንሄዳለን መጀመሪያ እናቴ ናት የምታናግረው ድምጿን ቀንሳ ፊቷ በሃፍረት በናፍቆትና በፍቅር ተጥለቅልቆ ብዙ አወ እና አይይ የበዛት ንግግር ታደርጋለች

አዎ

አዎ

አዎ

አይይይይይ

እሽ!

የአባየ ስልክ ደግሞ ለክፋቱ ይጮሃል በአሁኖቹ የእጅ ስልኮች ቋቋ "ላውድ ስፒከር " ላይ ያደረጉት ይመስላል

" እንደምነሽ ምነው ድምፅሽ ጎረነነ አመመሽ እነዴ እናት " አይይይይ ትለለች እናቴ አባቴ ደግሞ አንዳንድ የፍቅር ነገርም ስለሚናገር ቶሎ መሰናበት ትፈልጋለች ባሏ እወድሻለሁ ሲላት ታፍራለች !

ቀጣይ ትልቅ እህቴ ናት

“ምን ልላክልሽ “

“ስኒከር ጫማ እሽ ነጭ

“ እሽ የኔ ማር “ ድምፁ ውስጥ መናፈቅ አለ እንደባለፈው ሰፊ እንዳታመጣብኝ ባባ “ እሽ የኔ ቆንጆ ወንድሜ ይቀጥላል

“ታኬታ ጫማ ባለቡሎኑን “

“ ባለቡሎን ጫማ አለ እንዴ “ ይላል አባቴ

“እንከት “

“እሽ እፈልጋለሁ አንተ ብቻ እናትህን እንዳታስቸግር በደንብ ተማር “

እኔ አባትህን አናግር ስባል አላናግርም አብሬ ሩጨ አባየ ቤት ድረስ ሂጆ ሳበቃ ብሞት አላናግርም እናቴ ትበሳጫለች “እሽ ምን ላምጣልህ ይለሃል “ ትላለች በብስጭት

“ም ን ም “ እንባየ ይመጣብኛል አባቴን እወደዋለሁ ግን በስልክ አላናግረውም ለምን ቢባል መልስ የለኝም ! የተባለው ነገር ሁሉ ሲመጣ ግን እህቴ ያንን ሁሉ ማብራሪያ ሰጥታ ጫማዋ ይሰፋል ወንድሜ ባለቡለን ታኬታ አይመጣለትም እኔ ግን ምንም ሳልናገር ምርጥ ነገር ይመጣልኛል አባቴ እኔን

እራሴን እስኪመስለኝ ምርጫው ልክ ነው !

** *** ***

እኛ ሰፈር አንዷት ሴት ጎረመሰች የምትባለው በአባየ ስልክ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ያልሆነ ወንድ ከደወለላት ነበር ሁሉም ሴቶች ለፍቅረኞቻቸው የአባየን ስልክ ነው የሚሰጡት ወንዶችም አልፎ አልፎ ይሰጣሉ ! ታዲያ አባየ ቤት የተወራችው ነገር ስልኩ እንደሜጋፎን እየጮኸ ሚስጥሩን ስለሚዘራው

ጎረቤቱ ጋር ወዲያው ይደርሳል

“ሮማን የያዘችው ልጅ ሹፌር ነው መሰል ሁልጊዜ ከተለያየ

አገር ነው የሚደውለው “

“አትይኝም “

“ሙች ቢጣ ሲያወራ ሰምታ ነው የነገረችኝ “ (ቢጣ የአባየ ልጅ ናት) እንዲህ እየተባለ በቃ የተወራው የተደረገው ሁሉ ሰፈሩ ውስጥ ይናኛል አንዷት ሴት ወይም ወንድ በአባየ ስልክ ካልተደወለለት ጉርምስናው እውቅና አያገኝም ! እከሊት ጎረመሰች ከተባለ አባየ ቤት ጀመረች እንዴ የሚል ማረጋገጫ ይጠየቃል

“ውይ እሷ አንገቷን የደፋች አባየ ቤት አንድ ቀን ረግጣ አታውቅም “ ይባላል

ወይም “እች ልጅ የአባየን ቤት አዘወተረች መዘዟን እንዳትመዝ “ ይባላል የጨዋነት መስመር የጉርምስና መስፈሪያ ነበር የአባየ ስልክ ! ታዲያ የአባየን ቤት ከማይረግጡ “ጨዋ “ ጎረምሶች መሃል አንዱ እኔ ነበርኩ ስምንተኛ ክፍል ስደርስ ግን ጨዋነቴ ተገሰሰ ! የስምንተኛ ክፍል ባዮሎጅ አስተማሪያችን እትየ መከሊት በጣም አይናፋር ሴት ነበረች “ ምእራፍ ዘጠኝ የስነተዋልዶ አካላት “ የሚል ርእስ ላይ ስንደርስ የክፍሉ ልጅ በሙሉ እየተቁነጠነጠ ለመማር ተዘጋጀ እትየ ግን ፊቷ ቀልቶ እያፈረች ላለማስተማር የተቻላትን ሁሉ ታደርጋለች

“የስነታዋልዶ አካላት እንግዲህ ያው ወንድ እና ሴት

ያው ” ጭንቅ ይላታል እትየ መከሊት እኛ ደግሞ ጆሮ ብቻ እንሆናለን ስልሳ የምሆን የአንድ ክፍል ልጆች የስነተዋልዶ አካል ነገር ልባችንን ሰቅሎት ፍጥጥ መርፌ ቢወድቅ ይሰማል ፀጥ !!

“ውይ ምነው ሁልጊዜ እንዲህ በትኩረት ትምህርታችሁን በተከታተላችሁ እንደጢንቸል ጆሯችሁ ቆ አያችሁ መማር ለራስ ነው ትምህርት አገርን ይቀይራል ያደጉት አገሮች ዝም ብለው አላደጉም ትምህርት ” ኤጭጭ እኛ ስለስነተዋልዶ አካላት ለመስማት ጓጉተን እትየ ምክር ! መከራ መከራ

ምክሯ ሲያልቅባት “ ወንድ ልጅ ሲጎረምስ ፂም ማውጣት የተለያየ የሰውነት ክፍሉ ላይ ፀጉር ማብቀል እና ድምፅ መጎርነን ይጀምራል ገባችሁ “ ኢለኒ እጇን ታወጣለች “ ፀጉር የሚያወጣባቸው የተለያ አካላት የትኞቹ ናቸው ቲቸር “ “ ውይ አንች ደግሞ ፈተና ላይ የማይመጣ ነገር ምን አጠያየቀሽ “ ትልና ታፍራለች እትየ ሁላችንም እንስቃለን መስፍን እጁን ያወጣል የመስፍን እጅ ማውጣት ይገርመናል

በገመድ አስረውም ቢጎትቱት እጁ የማይዘረጋ ልጅ ዛሬ እጁን ሲያወጣ ይገርመናል ሽባ የተተረተረ ያህል በግርምት እንመለከተዋለን

“ ሴት ስትጎረምስስ ምን ምልከት ይታይባታል “ ብሎ ይጠይቃል ክፍሉ በሳቅና በጩኸት ይንቀጠቀጣል እትየ ታፍራለች

“ዝም በሉ ልክ ነው ጥያቄው የምን መገልፈጥ ነው እስቲ ከእናተ ይህን ጥያቄ የሚመልስ “ ትልና እኛኑ ታጋፍጠናለች ቶማስ እጁን ያወጣል “ ሴት ስትጎረምስ ያው አለ አይደል ”ብሎ ደረቱ ላይ እጆቹን ያሳርፍና እንደጡት ያጎብጣቸዋል ክላሱ በሳቅ ያውካካል እትየ በሃፍረት መግቢያው ይጠፉባታል ድንገት አንድኛችንን ትጣራለች “አብርሃም “ አቤት እላለሁ በድንጋጤ

“የሴት ልጅ ጉርምስና ምልክቶች ምን ምን ናቸው ” እንዴ እች ሴትዮ ሴቶቹን ራሳቸውን አትጠይቅም እንዴ በፍርሃት ላብ ላብ እያለኝ እየፈራሁ ሞከርኩ ” ስ ስልክ”

“ምን “

“ስልክ ማለት የአባየ ስልክ “ ክፍሉ በሳቅ ተንጫጫ

“ጥያቄው አልገባህም ” ብላ እንድቀመጥ ምልክት አሳየችኝ ምልሱ ስላልገባት ጥያቀው አልገባህም ትላለች እንዴ ብየ አኮረፍኩ ! አጎጥጎጤ የድምፅ መስረቅረቅ የዳሌ መስፋት እና

የወር አበባ ማየት የሴት ልጅ ጉርምስና ምልክቶች መሆናቸውን ባዮሎጂው ነገረን !

*** **** *****

ኢለኒ የምትባል የክላስ ልጅ የወደድኩት በዛው ሰሞን ነበር ኢለኒ ቆንጆ በነፃነት ያደገች የሃብታም ልጅ ናት አጎጠጎጤዋ በደንብ ያጎጠጎጠ ዳሌዋ የሰፋ ድምጿ የሚስረቀረቅ የወር አበባ እንዳየችም ነግራኛለች “ማንስትራሽን ላይ ነኝ “ ብላኛለች አንድ ቀን ! እቤታቸው ስልክ አላቸው ! ኢለኒ ብቸኛ ችግሯ ምላሳም ነበረች ስታወራ የምትጮህ በቃ ቀስ ብሎ ማውራት አትችልም ! ሁሉን ነገር ለመሞከር የቸኮለች ጓደኛ እንሁን ብየ በጠየኳት በሶስተኛው ቀን ከክፍላችን ኋላ ተቀምጠን ጉንጨን ስማ አስነዘረችኝ ከምር ነዘረኝ በቀጣዩ ሳምንት ከንፈሬን ስማ ንዝረቱን ከፍ አደረገችው በጣም ስለወደድኳት ከትምህርት ቤት ውጭ ላዋራት ፈለኩ እናም “የአባየን ስልክ “ ቁጥር ሰጠኋት ጉርምስነዋ ሙሉ ይሁን ብየ !! እስከዛሬ ሰፈር መንደሩ የመሰከረልኝ ጨዋ ልጅ ሰፈር መንደሩ በተሰበሰበት ጉድ ሆንኩ !! ቀኑ የኪዳነምህረት ቀን ነበር አባየ ቤት ዝክር ተደርጎ ፀበል ፃዲቅ ቀማሹ ከሩቅም ከቅርብም የተሰበሰበው ጎረቤትና ዘመድ አዝማድ ግጥም ብሎ ያውካካል ቢጣ ተጣራች

“አብርሽ ስልክ “

“ አቤት መጣሁ “ አለች እናቴ

“ጋሽ አይደለም አብርሽን የሚፈልግ ሌላ ሰው ነው “ አለች ሚጣ “ሌላ ሰው” የታወቀ ነው ትርጉሙ ! እናቴ ለስልኩም ባይሆን ለፀበሉ መንገድ ጀምራ ነበር ወደአባየ ቤት አባየ ቤት ስደርስ መራመጃ እንኳን አልነበረም

ግጥም ብሏል ቤቱ ደግሞ ለክፋቱ ስልኩ ስር ያለች ኩርሲ ላይ እማማ በላይነሽ የሚባሉት የሰፈራችን ነገረኛ ባልቴት ተቀምጠዋል ገና ከመግባቴ ለከፉኝ "አቡቹ አንተም መጣህ ና እለፍ በዚህ" አሉኝ ኢለኒ ነበረች ኢለኒ በባህሪዋ ጫሂ ናት እንኳን የሚጮህ ስልክ ጋር ተዳምራ

"አብርሽየ"

"አቤት " አልኩ ኮስተር ብየ ፀበል ቀማሹ ሁሉ ወሬ ቅመስ ተብሎ የተጠራ ይመስል ጭጭ ብሎ ጆሮውን ቀሰረ

"አብርሽ ምነው ጨዋ ሆንክ " አለችኝ ኢለኒ ልክ እንደሬዲዮ ድራማ ፀበልተኛው ይሰማል

"እ "

"አብርሽ ችግር አለ ትላንት ከንፈርህን ስለሳምኩህ ደበርኩህ " እግዚኦኦኦኦኦኦኦ ስልኩ አጠገብ የኪዳነ ምህረት ስእል ተቀምጧል

"ኪዳነምህረት የዚችን ልጅ አፍ ወይም የፀበልተኛውን ጆሮ ከዘጋሽልኝ የዛሬ ወር አንድ ፓኮ ሻማ " ብየ ተሳልኩ ኢለኒ ትቀባጥራለች " አብርሽ እኔኮ ሴክስ እናድርግ ስትለኝ እንቢ ያልኩህ ፈርቸ ነው በናትህ አብርሽ እሽ በቃ አርብ አክስቴ ቤት አድሬያለሁ ልበልና አንተም አመቻችተህ " እማማ በላይነሽ ወሬ እያዳመጡ ፉት ያሉት ጠላ ስርናቸው ውስጥ ገብቶ ትን አላቸው ከኩርሲያቸው ላይ እስኪፈነገሉ ተንፈራፈሩ "ውሃ ውሃ ስጧቸው ጀርባቸውን ምቷቸው ይል ጀመረ ፀበልተኛው እኔም የአባየን ስልክ ዘግቸ ቀስ ብየ ወጥቸ ተፈተለኩ ወደቤቴ ወዲያው ሰፈሩ ውስጥ ዝናየ በመወራቱ እናቴ አበደች

"እንዴት ታዋርደኛለህ እንዲህ ላገር መሳቂያ ታደርገኛለህ አብረሃም  አባቱ ባይኖር ሴት ቢያሳድገው ልታስብለኝ " እያለች እንባ እየተናነቃት ስትገስፀኝ ቢጣ ተጣራች " ሶስና ሶሲ ስልክ " እናቴ በድንጋጤ ውሃ ሆነች ሶስና ትንሿ እህቴ ናት የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ! ሶሲ ጎረመሰች ! ጉርምስና ጠቅልላ ቤታችን ገባች !

# ሁለት ብር ስንት ዶላር ነው?

## (አንዷን ወንዝ ሁለት ጊዜ ስንሻገራት)

ከአስራ አንድ አመታት በፊት ደሃ ነበርን ! ያጣን የነጣን ሙልጭ ያልን ነጭ ድሆች

ከድህነታችን ክብደት የተነሳ ስንት ሰአት ላይ እንደምንበላ ሳይሆን ስንት ሰአት ላይ እርሃባችን ጋብ እንደሚል ነበር ዘወትር የምናስበው እኔና እህቴ ትምህርት ቤት "አበበ በሶ ባላ" የሚል ምሳሌ "ቲቸር" ሲናገሩ በመጎምጀት ምራቃችንን እንውጥ ነበር ፡፡

እቤታችን ውስጥ አንድ የሸቦ አልጋ፣ ሁለት የሳር ፍራሾችና አራት የተወላገዱ ኩርሲ ወንበሮች ብቻ እንደነበሩን ዛሬም ድረስ እናቴ ሳጥን ውስጥ ያሉት ታሪካዊ ፎቶች ያሳብቃሉ!! ግድግዳ ላይ ገና እንደተረገዝኩ የሞተ አባቴ ፎቶ ግራፍ በላስቲክ ተለብዶ !! እንግዲህ ቤታችን ሁለት ክፍል ነበረች አሁን የነገርኳችሁ የሳሎናችንን (ወጉ እንዳይቀር) ይዞታ ነው ፡፡ ወደጓዳ ስትገቡ ውስጣቸው የእንጀራ ላስቲክ ብቻ ያለባቸው ሁለት ትልልቅ እና አሮጌ ሞሰቦች ታገኛላችሁ ጠርዛቸውን አይጥ የቸረቸፈው!! ሁለቱም ሁልጊዜ ባዶ ነበሩ (አይጦች ከልጆቻቸው ጋር በእነዚህ ሞሰቦች አጠገብ ሲያልፉ ለልጆቻቸው እንዲህ እያሉ ታሪክ የሚያወሩላቸው ይመስለኛል እንዲህ እያሉ "በድሮ ጊዜ በአያቶቻችን ዘመን እነዚህ ሞሰቦች ውስጥ ተበልቶ የማያልቅ እንጀራ ነበር የዛሬን አያድርገውና ለስንቱ የአይጥ ሰርግ ድግስ የበቃ ) እናቴ ታዲያ አማኝ ናት በየሶስት ቀኑ ሞሰቡ ውስጥ የሚቀመጡትን የእንጀራ ላስቲኮች እያጠበች አድርቃ ወደሞሰቡ ትመልሳቸዋለች " በረከት ሲመጣ አዋጅ አያስነግርም ድንገት ከተፍ ቢል ተዘጋጅተን መጠበቁ ደግ ነው " ትላለች ይሄ መራር ስብከቷን አልወደውም ግን ትንቢቷ ሰመረ!! እናቴ ነብይ ነበረች ደሃ ነብይ በቤቱ አይከበርም እናትም ብትሆን !! አከበርናትም አላከበርናትም ትንቢቷ ሰመረና በረከት እንደመብረቅ ወረደብን !!(ምናባቴ ልበል ታዲያ)

በስድስት ወር ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ጎረቤቶች ተርታ ተሰለፍን!! ጎረቤቱ ጉድ ብሎ ሳያባራ በአሙቱ ምን የመሰለ ቤት ሰራን ባለ አምስት ክፍል ዙሪያውን በግንብ የታጠረ አጥሩ ሰው እንዳይመጣብን ሳይሆን በለመደ እግራችን ልንቀላውጥ እንዳንሄድ!! በተለይ ገና ሃብታም እንደሆንን አካባቢ አኗኗሩን አንላመደው ብለን ነበር እንግዲህ የዚህ ድንገተኛ ለውጥ ምክንያቱ እህቴ ፈረንጅ ማግባቷ ነበር (ደግ ፈረንጅ) እንዴት እንዳገባችው(ይቅርታ እንዳገባት) ላውራችሁ

ከትምህርት ቤት እየመጣች ልክ ኡስማን ሱቅ አካባቢ ስትደርስ ፈረንጁ መኪናውን ፉጭጭጭጭ አድርጎ አቆመና " አ ማይ ጋድ" በማለት የእህቴን ውበት አደነቀ፡፡ በበኩሌ የእህቴ ውበት የፈረንጅ መኪና ማስቆም ቀርቶ የራሷን ሳንቲም "ሆጭ" አድርጋ ከፍላ የምትሳፈርበት ታክሲ እንኳን እጇን ብትዘረጋ የሚቆምላት አይመስለኝም ነበር ፡፡ ግን ምን ይደረግ ፈረንጆች ነገራቸው ሁሉ ግራ ነው መኪናውን እዛው ጥሎት እህቴን ተከትሎ እቤታችን ድረስ መጣ!! እናቴ ለእርዳታ የመጣ መስሏት ከአይኖቿ "ትራጀዲ" ብርሃን ለቀቀች ፡፡ የመንደራችን እንግሊዝኛ አዋቂ(የህቴም ወዳጅ ቢጤ) ሲራጅ ተጠርቶ መጣና ፈረንጁ ምን እንደሚል ተረጎመልን "እሷን ማግባት እፈልጋለሁ" ነው የሚለው አለ ቅር ብሎት ወደአህቴ እየጠቆመ፡፡ እናቴ ባለማመን "ማንን እጅጋየሁን" አለች..(እህቴ እጅጋየሁ ነው ስሟ)

"አወ ሌላ ማን አለ ታዲያ እማማ አረጋሽ " ሲራጅ ተነጫነጨ (እህቴ ጋር ማታ ማታ እዛ እንጆሪዋ ዛፍ ስር ይቆሙ ነበር !! ) እናቴ አንዴ ፈረንጁን አንዴ እህቴን ስታይ ቆየችና

"ሲራጅ ግን እንግሊዘኛ በደንብ ታውቃለህ" ስትል ባለማመን ጠየቀች ፈረንጁ ግን ወደእህቴ እየጠቆመ በተኮላተፈ አማረኛ "ኮንጆ ኮንጆ.." በማለቱ "ይሄ ሰው አምርሯል" አለች እናቴ ያው ጉዳዩ የፈጀውን ጊዜ ፈጅቶ በአንድ ወር ውስጥ ተጋቡ!! ይሄ ፈረንጅ(ይቅርታ የእህቴ ባለቤት) ታዋቂ የታሪክ ተመራማሪም ነበር ይሄን የሰማሁ

ቀን "እህቴ ከመከሳቷ የተነሳ ሉሲን መስላው ይሆን" ብየ አሰብኩ ወይስ እህቴ ይሄን ሚስኪን ፒተር ምናምን አስነካችው ከተማውን የሞሉት ቆነጃጅት ሁሉ ፒተርን ሲያዩ ተበድረው የሚስቁ መቀመጫቸውን እንደባንዲራ የሚያውለበልቡ እንደአቦ ሸማኔ ሽንጣቸውን እየመዘዙ አማላይ ሊሆኑ የሚደክሙ

ስለምን ለአይኑ አልሞሉም ? ግዴላችሁም ይሄ ፒተር ጤነኛ አይደለም ገዳይ ዘመን የሌለው አፅም ሲያገላብጥ ተዘግቶ የኖረ ዋሻ ሲበረብር አንዳች ነገር ተጣልቶታል አንዷት የ ከርዳዳ ፀጉሯ ቱማታ አዳማ ድረስ የሚሰማ በመረገጥ ብዛት ሶሉ ተረከዙ ላይ የተሸነቆረ ነጠላ ጫማ የምትጎትት ሴት በልእልት ሂሳብ የሚያሳይ ሰይጣነ መነፀር አይኑ ላይ የለጠፈበት ነገር አለ!! እንጅ እህቴ ላይ እንዲህ ሙጭጭ ባላለ

ሚስኪን ፒተር እቤት መጥቶ እዛች ጠማማ ዱካ ላይ ቁጭ ብሎ እህቴን አይን አይኗን ሲያይ በእውነት እንደስጋ ዘመዴ አንጀቴ ይንሰፈሰፋል እንግዲህ ይሄ ፈረንጅ እህቴን ጠቅልሎ ከመውሰዱ በፊት ትምህርቷን እንድትጨርስ ተብሎ ለሁለት አመት አዚሁ ተቀመጠች ፒተር ታዲያ በየስድስት ወሩ እየመጣ ቤታችንን ጥምቀት ከማድረጉም በላይ ይሄን ዶላር ልኬ ልሙት አለ ! ይልካል ይመነዘራል ይልካል ይመነዘራል ወላ በጥቁር ወላ በነጭ ገበያ እየተመነዘረ አለማችንን አየን ስልካችን ከጮኸ ጎረቤቱ "አሁን አብርሃም ወደባንክ ሊሮጥ ነው" ይላል ቤታችን እግር የጣለው ሰው ሁሉ በሞቴ አፈር ስሆን ተብሎ ተጋብዞ ነው የሚሄደው!! የእንግዳ ማረፊያ የአብርሃም ድንኳን !! በየቀኑ ብቅ እያሉ የሚመፀወቱ የኔ ቢጤወችም ብዙ ነበሩ አንዳንዶቹማ ደንበኛ ከመሆናቸው ብዛት "ስለሙብርሃን " አይሉም የግቢያችንን በር ያንኳኳሉ በቃ በልተው ጠጥተው ይሄዳሉ እንደውም አንዱ የኔ ብጤ መመፅወቱን መብት አድርጎት "ምነው ዛሬ ጨውን አሳነሳችሁት " ብሎ እስከመቆጣት ደረሰ.. ይሄው ሰውየ ሌላ ቀን የጎድን አጥንት ስለተሰጠው አኩርፎ ሳይመርቅ ሄደ እናቴ እንደገና ጠርታ ወዙ የሚፍለቀለቅ ቅልጥም ሰጠችው

ደስ ብሎት "በክፉ የሚያይሽ ቅልጥሙ ይሰበር " ብሎ መረቃት!!

"ደሃ ብር አያግኝ ሲቆጥር ይጥላል" እንደሚባለው የእህቴ ፀባይ ይቀያየር ጀመረ ልብሷን ለባብሳ ቦርሳዋን አንጠልጥላ ጧት የወጣች ማታ ትመለሳለች ። ድሮ ከሰው የማይቆጥሯት ጎረምሶች ሁሉ እንደጥላ ከስሯ አንጠፉ አሉ እሷን ብለው ሳይሆን የፈረንጅ ሚስት ጋር ዋልን ለማለት !! እጅግየ እጅግሻ ጅጅ ጃ ጆ.. ጅን ጅንአድ(ካፒታሷን ይሆን) በቃ ስሟ ፍዳውን አየ በዚህ ዘመቻ ፊታውራሪው "ሲራጅ" ነበር ( ተከተለኝ ወደእጅጋየሁ ልዘምት ነው )።

የእህቴ ድፍረት ገደቡን ጣሰና ጭራሽ አርግዛ ቁጭ!! ደግነቱ በዚያ አመት የእናቴ አምላክ የፒተርን እግር ያዘው !! እናቴ መጀመሪያ እርግዝናው ከፒተር መስሏት ነገር ልታበላሽ ነበር " ለፒተር ንገሩልኝ ደስ ይበለው "አይንህን ባይንህ ልታይ ነው " በሉልኝ ምናምን !" ልጅቱ ስትወለድ ከፆታዋ በስተቀር ቁርጥ "ሲራጅን"!! (የመንደራችን ነገረኛ ሴቶች ግር ብለው "ላንጉጅ" ትምህርት ቤት ተመዘገቡ ይሄን ጉድ ለፒተር ለመንገር!!) ጉዳዩ ተሸፋፍኖ ተደባብሶ "ሾላ በድፍን" የስድስት ወር ልጇን ለእኛ ጥላ እህቴ አሜሪካ ገባች !! ህፃኗን እልም ያለ ገጠር የምትኖር አክስታችን ጋር ላክናት ሲራጅ "የገጠሪቱ ኢትዮጲያ ህፃናት የትምህርትና የጤና እድል የማግኘት አድላቸው አናሳ ነው " አለ ሃሃሃሃ ( ሰውየው አሉ ከሚስቱ ውጭ ፋጤ ከምትባል ሴት በድብቅ ወልዶ ልጁ ሞተ ብለው አረዱት ሚስቱ ፊት አያለቅስ ነገር ቸገረው ዝም አይል ነገር ልጁ ሆኖበት እና ምን አለ "አጀብ አላህ የፋጤን ልጅ ትገልባት" ) ሲራጅም ልጀን ገጠር አትላኩብኝ አይል ነገር ቸግሮት ዝም አይል ነገር የአባት አንጀት ሆነና " አጀብ አላህ የገጠሪቱን ኢትዮጲያ ህፃናት " ብሎ አረፈው !!

"ሄሎ አብርሽየ ደርሻለሁ ለሲራጅ ደርሻለሁ በልልኝ" እያት እንግዲህ እህቴ ከንስንክሳሯ አሜሪካ ላይ

እንደነገ ልትበር እንደ ዛሬ ማታ በጓሮ በኩል እንጆሪው ዛፍ ስር ሲራጅ ጋር ቁጭ ብለው እያወሩ ሲራጅ እንባውን ሲጠርግ አየሁት አሳዘነኝ ለስንቱ ልዘን !! ሲራጅ ጋራጅ እየሰራ እናቱን ይረዳል እህቱን ያስተምራል በፊት ደስ የሚል ቀይ ልጅ ነበር መልከ መልካም ጥቁርቁር ብሏል አሁን በየበረሃው ተበላሽቶ የቆመ መኪና ተከትሎ ሲባዝን !! እዚህ እንጆሪ ዛፍ ስር ህፃን ሁነን እኔ እህቴና ሲራጅ እቃቃ አንጫወት ነበር ሲራጅ እና እህቴ ባል እና

ሚስት ሁነው ደግሞ ሲራጅ ከመብሰሉ ብዛት ወደጥቁርነት የሚያደላ ያሞከሞከ የእንጆሪ ፍሬ ለእህቴ ይሰጣት ነበር እህቴ በጋራጅ ስራ የፈረጠመው የሲራጅ ትከሻ ላይ ራሷን ጣል አድርገዋለች የሆነ ህልም ነገር ነበር የሚመስለው

በፊት በፊት እናቴ ሳንቲም ይቸግራትና የዘወትሩን ቡና እንኳን ሳታፈላ በር ላይ ቁጭ ብላ ትተክዛለች እህቴ ወጣ ትልና ቡና ዳቦ ምናምን ይዛ ትመጣለች ቤታችን ትንሽ ፋሲካ ይሆናል ሲራጅ ብር እየሰጣት እንደሆነ እኔ አውቃለሁ እናቴም ታውቃለች ግን አትጠይቃትም ድህነት ልጇን የመገሰፅ ድፍረቷን ሰልቦት !! ሲራጅ ለእኛ ቤተሰብ በትላንትና እና በዛሬ መካከል የነበረ ድልድያችን ነበር !!

(እየው እንግዲህ የንጨት ድልድዩን አፍርሰን የብረት ድልድይ ስንዘረጋ ተመልከት አንዱን ወንዝ ሁለት ጊዜ ስንሻገር )

ሳንደፈር የኖርን ማለት ምንድን ነው ምድራችንን ፎክረን ለተቀበልናቸው ሚስቶቻችንን አልቅሰን እናስረክባቸዋለን !! ኡፍፍፍ ይሄ የእነማን ጦርነት ነው የሲራጅና የፒተር የአበሻና የፈረንጅ የጥቅምና የፍቅር የብረት መዝጊያና የጭራሮ

******* ********* **********

ከአራት አመት በኋላ እህቴ መጣች አምሮባት (ፈረንጅ መስላ " ሰውን ማንን ይመስላል ቢሉ ኑሮውን") አገር ምድሩን ጉድ ያስባለ መኪና አንድ ቸኮሌት የመሰለ የሁለት አመት ህፃን ልጅ ይዛ መጣች !! ባለ ምናምን ኮከብ ሆቴል ፒተር እኔ እሷ እና የሁለት አመት ክልስ ልጇ ምሳ እየበላን ፒተር የራሱን ጨርሶ እጁን ሊታጠብ ሲሄድ ልጁ ድክ ድክ እያለ አባቱን ተከትሎ ከአይናችን እንደተሰወሩ እህቴ ወደኔ ሰገግ ብላ "አብርሽ ሲራጅ አሁንም ሰፈር ነው የሚኖረው " አለችኝ እፍረት በተቀላቀለበት ጉጉት !! እውነቱን ለመናገር እረስቸው ነበር !

"እኔጃ ካየሁት ቆየሁ የሆነ ሰአት ላይ ግን ጀዝቦ ነበር " አልኳት በግዴለሽነት ዩኒቨርስቲ ገብቸ ስለነበር በእርግጥም ካየሁት ሁለት አመት አልፎኝ ነበር ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ሰፈር ድንገት ከስራ ሲገባ ነበር ጅዝብ ብሎ በእጁ ባንጠለጠላት ፌስታል ሶስት ዳቦወች ይዞ " እሽ አብርሽ ስራ ጥሩ ነው " አለኝ ተማሪ መሆኔን ያውቃል ደግሞ አይኔን ማየት አልፈለገም እህቴ ያዘጋጀችውን ጉርሻ ወደሰሃኑ መልሳ ፍዝዝ ብላ ቀረች ፒተር ያመጣልኝን ስልክ እየጎረጎርኩ እህቴን ከትካዜዋ ጋር ረሳኋት ፓ እንዴት ቀውጢ ስልክ ነው !!

"እኔ የምልሽ ይሄ ስልክ ዋጋው ውድ ነው አይደል? " አልኳት በማዳነቅ እህቴ በትዝብት እያየችኝ " ሰባት መቶ ዶላር "

"ወደኛ ብር ሲመነዘር " ብየ ሳሰላ

" ወደኛ ብር ሲመነዘር ሲራጅ ለእማማ ቡና ብሎ ከሚሰጠኝ ሁለት ብር አይበልጥም ሲራጅ ለአብርሽ ብሎ ይሰጠኝ ከነበረው እስክርቢቶ አይበልጥም " ብላኝ ወደመታጠቢያ ቤቱ ሄደች ፒተርና ልጇ ታጥበው ሲወጡ እሷ ልትታጠብ ስትሄድ መንገድ ላይ ተላለፉ ፒተር ፈገግ አለላት እህቴ እንደማታውቃቸው ዝም ብላ አልፋቸው ሄደች ሲራጅ እስክርቢቶ ይልክልኝ እንደነበር ትዝ አለኝ ስልኩን ጠረንቤዛው ላይ አስቀምጬ ወደመታጠቢያ ቤቱ በትካዜ አመራሁ እህቴ እያለቀሰች ነበር ከአሜሪካ በመጣልኝ እስኒከር ጫማ ሲራጅ የሚባል አራት አመት ተቀብሮ የኖረ ፈንጅ እረገጥኩ ሲመቸን የምንረግጠውን አናውቅ! እረገጥኩት ቡምምምምምምምምምምምምምም ቁስለኛ እህቴ ሙት እህቴ

እማማ ጨምሪው

እማማ ጨምሪው ስም የሌለው ታዋቂ ምግብ ቤት ባለቤት ናቸው ! ምግብ ቤታቸው በሩ ላይ የተፃፈስም ምግብ ቤት መሆኑን የሚያሳይ ምልክት የለውም ! በስሙ ሳይሆን በስራው የታወቀ የተመሰገነ መሆኑን ማንም

ያውቃል ኧረ የሳቸውን ምግብ ቤት የማያውቅ ሰው የለም ! ድንገት ከሩቅ አገር የመጣ እንግዳ የምግብ ቤቱን ዝና ሰምቶ "የማማ ጨምሪው ምግብ ቤት የቱ ጋ ነው " ብሎ ይጠይቃል አይደል ?

" እንግዳ ነሽ ማለት ነው ወዳጀ ለማንኛውም ነዳጅ ማደያውን እልፍ እንዳልክ የፌዴራል ፖሊስ ካምፕ አለ ... ካምፑን አልፈህ ደግሞ ቀበሌ አለ በቀበሌውና በካምፑ መሃል ላይ ያለው በቃ ምግብ ቤቱ ነው ከጠፋህ እዛ ፖሊስ ጣቢያው በር ላይ ስትደርስ አይንህን ጨፍንና አፍንጫህን ከፊት ወላ ቀስር የምግቡ መአዛ እየጎተተ እዛው ያደርሰሃል " እንዲህ ነው የሚለው መንገድ ጠቋሚው

እማማ ጨምሪው አጠር ብለው ደልደል ያሉ ቀይ ሴት ናቸው ላዘቦቱ አበባ ጣል ጣል ያደረገበት አንገቱ እስከደረታቸው ከፊት ያለ ቀሚስ በተከፋች ሹራብ የሚለብሱ ወገባቸው ላይ ለወጉ እንደመቀነት ያለ ነጠላ ነገር ሸብ የሚያደርጉ ሞንዳላ እመቤት ! ከራሳቸው ላይ እንደኳስ ደበልበል ብሎ የሚታሰር ሻሻቸውን አስር ጊዜ ማስተካከል አመላቸው ነው በተለይ ነገር ሲሸታቸው እጃቸው ወደራሳቸው ቶሎ ቶሎ ይመላለሳል !

ድፍን የምግ ቤቱ ደንበኛ " እማማ ጨምሪውየ " ይላቸዋል ትክክለኛ ስማቸው ማን እንደሆነ አይታወቅም !

" ኤዲያ ስሜን የ እየጨመራችሁ አታንዘላዝሉብኝ " ይላሉ ሁልጊዜም ከእጃቸው በማይጠፋው ጭልፋ ተጣሪውን ለመማታት እየቃጡ የተቃጣበት ሰው ደስ እንዲላቸው እጆቹን ዘርግቶ ይከላከላል አልያም ሸሸት ይላል " ቆይ ትመጣታለህ አንት ጋንድያ " ይሉታል ...ቢመጣ ምንም አያደርጉትም በሞፈር የማይሰቀሰቅ እንጀራውን ባማረው ወጥ ጥርቅም አድርጎ በልቶ ይሄዳል እንጅ ! የማማ ጨምሪው ቤት ነዋ !!

በነገራችን ላይ እማማ ጨምሪው ጭልፋ ዘወትር ከእጃቸው አይጠፋም እንደውም ጠባቧ ምግብ ቤት ውስጥ በላተኛው ተደርድሮ ምግቡን ሲያጣድፈው ጭልፋቸውን ይዘው ከደንበኞቻቸው ፊት በመቆም በጭልፋው እየጠቆሙ ወጥ ላለቀበት " ማነሽ አንች ልጅ ነይ እዛ ወጥ ጨምሪለት .... ለእከሌ እንጀራ ጨምሩለት እንጅ ወጡ ብቻ ቀርቶ ትሪው ብረት ድስት መሰለ እኮ ኤዲያ ፍየል ይመስል ቅጠል ቅጠሉን ማጋበስ ምንድን ነው እቴ.... ወጡን ድፈረው እንጅ ነይማ አዛ ውሃ ስጭልኝ ደሞ በትንታ ሙቶ ዘብጥያ እንዳያወርደኝ የት ይሄድብኛል ብሎ ነው እንዲህ እህሉን እያሳደደ የሚወቃው ..." እያሉ እጃቸውን ከፍ ዝቅ ዚያደርጉ የበላተኛ ኦኬስትራ የሚመሩ የሙዚቃ "ኮንዳክተር " ይመስላሉ ለነገሩ አንዳንዱ ሰው አለማመጡ ጭብጨባ ስለሚመስል በእርግጥም ቤቱ ኦኬስትራ ይመስላል !

እማማ ጨምሪውን ባለምግብ ቤት ሳይሆን መንግስት ያላወቃቸው የእርዳታ ድርጅት ማለት ይቀላል ! ለወጉ በሚከፈል ትንሽ ብር በላተኛው ጥግብ እስኪል በልቶ የሚወጣበት የእናት ማጀት ነው ምግብ ቤታቸው ! ምግብ ቤቱንም የከፈቱት እንደው እንጀራ በወጥ ሸጠው ለማትረፍ አይደለም ... ኧረ እሳቸው ብር ምን ሊያደርግላቸው አራት ልጆቻቸው ከፍ ያለ ትምህርት ተምረው ውጭ አገር ነው የሚኖሩት ቀብረር አድርገው ያኖሯቸዋል ! እዚህ ሰንጋ ተራ ምን የመሰለ ለሱቅ የተከራየ ቤት አላቸው ! ግን " ምነው እንዳጋሰስ የተጣለልኝን እያመሰካሁ የምኖር " ብለው ምግብ ቤት ከፈቱ ከሰው ጋር ለማውራት ለመጫወት እንደው እቤት ላለማረፍ ብለው ! " መላወስ ደግ ነው ጅማት ያፍታታል " ይላሉ

እንግዲህ የእማማ ጨምሪውን ምግብ ቤት ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥ ስንመለከት በግራ በኩል በቅርብ የተሰራው የቀበሌ ህንፃ እንደጆቢራ ተገትሮ በግራ ደግሞ የፌዴራል ፖሊስ ካምፕ ያዋስኗቸዋል በሰሜን በኩል ዩኒቨረስቲ ሲኖር በምእራብ ቀለበት መንገዱን አለፍ ብሎ "ዳቦ ለድሆች " የተባለ የተቃዋሚ ፓርቲ ቢሮ አለ ! እንግዲህ የቀበሌው ሰራተኞች የፌዴራል ፖሊስ ካምፑ ውስጥ ያሉ ፖሊሶች እንዲሁም የዩኒቨርስቲው ተማሪወች ከወደላይ ሰፈርም ሰአሊወች ገጣሚያንና ደራሲወች እማማ ጨምሪው ቤት ለእህል ውሃ ጉዳይ ጎራ ማለታቸው አይቀርም ! ምን ይሄ ብቻ ከሰሞኑ እንደውም ለመንገድ ስራ የመጡ ቻይናዊያንም ቤቱን እያዘወተሩት ነው !

የዚች ምግብ ቤት ስርአት ለእንግዳ ሰው ሳየገርመው አይቀርም ለምሳሌ አንዱ ገብቶ "እማማ ጨምሪውየ አንድ ሽሮ " ብሎ ያዛል ከእርሱ በፊት ሌላ ሰው ሽሮ አዞ እየጠበቀ ነው

" ማነሽ አንች ልጅ ሁለት ሽሮ ባንድ ትሪ ቶሎ በይ " ይላሉ እማማ ጨምሪው

"እማማ ጨምሪው አንድ እኮ ነው ያዘዝኩት " ይላል አዲስ መጤው

" ኤዲያ ለእናተ ማን ሁለት ትሪ ይጎትታል አብራችሁ ብሉ .... ዞሮ ዞሮ ሳጠግቡ አትነሱ " ይሉና የማይተዋወቁትን ሰወች አንድ መአድ ላይ አገናኝተዋቸው ቁጭ ! ታዲያ ሁለቱም ሳይጠግቡ አይነሱም "ማነሽ ወጥ ጨምሪላቸው ...ውይ እንጀራው አለቀባቸው ጨምሪላቸው " በቃ እንዲህ እያሉ ሲያስጨምሩ ደንበኞቻቸው ጥግብ ብለው ይሄዳሉ ! ለዛም ነው እማማ ጨመሪው የተባሉት !

እንግዲህ በዚህ ትሪ የመጋራት የቤቱ ህግ መሰረት የዩኒቨርስቲ ተማሪው ከፌዴራል ፖሊስ ጋር አንድ ትሪ ላይ ሊቀርብ አልያም የቀበሌው ካድሬ ከተቀዋሚ ፓርቲ አባል ጋር ተሪ ሊጋራ ይችላል .... ይሄ የእማማ ጨምሪው ቤት ነው ያሻህ ልዩነት ይኑርህ መአዱ አንድ ነው !!

ከዛሬ ጀምሮ እማማ ጨምሪው ቤት ብቅ እያልን በእማማ ጨምሪው ወግ ዘና ብለን ከጣፋጭ ማእዳቸውም ቀማምሰን እንወጣለን ... ምንም እንኳን እማማ ጨምሪው ሙሉ በሙሉ የፈጠራ ገፀ ባህሪያችን ቢሆኑም ያው ያለው የነበረው ላይ ትንሽ ነገር ጣል ከማድረግ ውጭ የሁላችንም እናቶች ባህሪ ተዋጥቶ የሚታይባቸው አንዲት ኢትዮጲያዊት እናት ማሳያ ናሙናችን ናቸው ! እንግዲህ በእናት ለዛ የማያወሩልን ነገር የለም ደግሞ ምግብ ቤቱ አጋጣሚ አያጣውም ወደማማ ጨምሪው ምናባዊ ምግብ ቤት እንኳን ደህና መጣችሁ .....ማነሽ አንች ልጅ ለአሌክስ አብርሃም ጓደኞች ተከታዮችና አንባቢወች ሁሉ ባንድ ትሪ በያይነቱ አቅርቢላቸው ለነሱ ስንት ሽ ትሪ ማን ይጎትታል

ሊሆን ይችላል!!

ለሚስቴ ያለኝ ፍቅር ከእለት ወደእለት እየጨመረ ነው የሚሄደው.... ችግሩ ፍቅሩ የሚጨምረው ብቻውን አልነበረም እግር እጅ የሌለው ቅናት ጋር እንጅ! በእኔ ልብ ውስጥ ፍቅር እና ቅናት እንደመንትያ ልጆች እኩል ነበር የሚያድጉት! እየቆየ ግን የፍቅር አቅም እየኮሰመነ የቅናቴ ጡንቻ እየፈረጠመ ሄደና ቅናቴ እንደምርቃት ቆብ ከነመነሳንሱ አናቴ ላይ በኩራት ጉብ አለ! አያድርስ ነው! ርኩሳዊ ቅናት የሰይጣን አንዱ ስራ ነው ይባላል እንጅ እንደኔ እንደኔ ቅናት ራሱ ሰይጣን ሳይሆን አይቀርም ።

ሚስቴ መአዛ ጨዋነቷን አገር ይመሰክርላታል .... ግን ምን ዋጋ አለው የእኔ የባሏ ሆድ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ሻከሯል ። አገር የመሰከረላትን ሴት የእኔ የባለቤቷ ልብ ካልመሰከረላት በከፋትም ቢሆን "ሆድ ከአገር ይሰፋል" ማለት ይሄኔ ነው! "ምን ክፉ ስራ ስታደርግ አይተሃት ቀናህ? " ብባል መልስ የለኝም ... ግን እቀናለሁ!! ስቀና እበሳጭባታለሁ አንዳንዴ እንደውም ከመሬት ተነስቸ ሁለት ቀን ሶስት ቀን አኮርፋታለሁ ። ግራ ይገባታል የምትይዝ የምትጨብጠውን ታጣለች አብረን እየኖርን ስዘጋት የምታድገው ነገር ታጣለች .... ደስ ይለኛል ... ጭንቀቷ ነፍሴን ያረካታል አንዳች የመበቀል ስሜት ይሰማኛል! ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠና ቀይ ጉንጯ በርበሬ መስሎ ግራ ተጋብታ ስመለከታት በኩራት ኩፍስ ብየ በስቃዩዋ እዝናናለሁ! ...ብዙ ጊዜ በተለይ ወንዶች በፍቅረኝነት እያሉ ቅናት ያጠቃቸዋል ፤ ያፈቀሯትን ሲያገቡ ግን በቁጥጥራቸው ስር የዋለች መስሎ ስለሚሰማቸው አይቀኑም " ሲባል ነበር የሰማሁት ... የእኔ

ቅናት ግን የተገላቢጦሽ ነው ! በፍቅረኝነት እንደነበርንም ይሁን የተጋባን ሰሞን አልቀናም ነበር! ለዛም ሳይሆን አይቀርም መአዛን ብዙም ትኩረት ሰጥቸ የት ገባች የት ወጣች የማልለው! የኋላ ኋላ ግን ቅናት ከነልጅ ልጁ ሰፈረብኝ ። የቅናት ትልቁ ችግር የሚቀኑበት ሰው እንደሚያስቡት መሆን አለመሆኑ ላይ አይደለም .... የሚቀናውን ሰው ራሱን በበታችነት ስሜት አጥለቅልቆ ያልሆነውን ማድረጉ እንጅ! መአዛ ፊልም እየተመለከተች አንዱን የፊልም ተዋናይ ካደነቀች የጨጓራ ህመሜ ይነሳል ! በቃ ስለምቀና አገር ያወቀው ፀሃይ የሞቀውን ጎበዝ እና ጨዋ የፊልም ተዋናይ ማጣጣል እጀምራለሁ ...መአዛ ከተከራከረችኝማ ሰውነቴ ሁሉ በብስጭት ይንገበገባል... እቀናለሁ ! "ምናባቱ ይሄ ሴታሴት ካሜራ ፊት ጀግና ይመስላል ልክስክስ እዚህ ካሳንችስ መጠጥ ቤት ለመጠጥ ቤት ጫት

ቤት ለጫት ቤት ሲዞር አይደል የሚውለው እሱ ያልተኛቸው ሴተኛ አዳሪወች የሉም እንደውም በየቦታው ነው ልጅ የሚወልደው " እላለሁ "ኧረ አብርሽ በእግዚአብሄር ክፉ አትናገር የተከበረ ባለትዳር የሁለት ልጆች አባት ነው ..." ትላለች መአዚ "አንች ስለሱ ሂወት ስታጣሪ ነው የምትውይው..... ምን ታውቂያለሽ "

"እኔማ ምን አውቃለሁ ራሱ ነው በቲቪ ከነሚስቱ ቀርቦ ኢንተርቪው ሲሰጥ ያየሁት " ትላለች ጮኸቴ አስደንግጧት አንገቷን እየደፋች "እና በቴሌቪዥን ቀርቦ እጠጣለሁ እቅማለሁ ሴት አይተርፈኝም

ይበል ? " አፈጥባታለሁ ....መአዚ በግርምት እየተመለከተችኝ ዝም ትላለች ! አንዳንዴ አይምሮየ የታወከ እየመሰላት ትፈራለች ! ፊልም በተከፈተ ቁጥር የምታደንቀውን ሰው ስዘልፍና ሳጣጥል ፊልሙን በቅጡ ሳናየው ስለሚያልፍ መአዚ ማድነቋን አቆመች ! እኔ ግን መቅናቴን አላቆምኩም ...አንዱ ወንድ ተዋናይ በተናገረው ነገር ከሳቀች ወይም በመደነቅ እራሷን ከነቀነቀች ቅናቴ ያስለፈልፈኛል " እነዚህ የጠላ ቤትና የጫት ቤት ቀልድ እያመጡ ይቀባጥራሉ አይ የኢትዮጲያ .......ፊልም እንዲህ የዱርየ መነሃሪያ የማንም ቦዘኔ አፍ መካፈቻ ሁኖ ይቅር ...ምን የፊልም ኢንዳስትሪ ነው የዱርየ የስራ ፈት ኢንዳስተሪ

ቢሉት ይሻላል " ይሄ ባህሪየ ሲያስመርራት መአዚ እኔ ጋር ፊልም ማየት አቆመች ! በፊት ፊልም ሲከፈት ተንደርድራ መጥታ ጎኔ ትቀመጥና እራሷን ትከሻየ ላይ ዘንበል አድርጋ ነበር የምትመለከተው ...የሚያስቅ ነገር ስትመለከት አንገቴ ስር ገብታ ፍርፍር ብላ ትስቅ ነበር ...እድሜ ለቅናቴ ይሄው ፊልም እኔጋር

ማየት አቆመችና አረፈችው! ፊልም ሲከፈት ወይ ጓዳ ገብታ ታንጎዳጉዳለች ...አልያም ምኝታ ቤት ትገባና ትተኛለች ወይም ታነባለች ።

"ፊልም አታይም እንዴ ? " እላታለሁ

"አይቸዋለሁ "

"የት አየሽው"

"ባለፈው እማየ ጋ የሄድኩ ጊዜ "

" እማየ ቴሌቪዥናቸው ተበላሸ አላልሽም "

" ሌላ ገዛች"

"ማን ገዛላቸው "

"ኧረ አብርሽ በእግዚአብሄር አታጨናንቀኝ " ትልና በምሬት ታየኛለች ! በቃ እናቷ ቤት አይደለም ያየችው ...የሆነ ወንድ ጋር ትከሻው ላይ ራሷን ጣል አድርጋ (በየመሃሉ እየተሳሳሙም ሊሆን ይችላል ) በቃ እንደዛ ነው ያየችው ....ልክስክስ ውይ ሴቶች !! እብሰለሰላለሁ ....ትከሻውን የተደገፈችው ወንድ ማን ይሆን....

ምናልባት አብረውም ተኝተው ሊሆን ይችላል ..... አብራ ፊልም ለማየት ያልተመለሰች ......እሽ ለእናቷ ማን ቴሌቪዥን ገዛላቸው ? ....ይሄው ታሪኩ ሲገጣጠም .......መአዛ ሃብታም ወንድ ጋር ሄደች... እቤቱ ሂደው

ፊልም አብረው ሲመለከቱ ቆዩና (ሶፋ ላይ አብረው ተቀምጠው ጫማዋን አውልቃ የሚያማምሩ እግሮቿን ሶፋው ላይ ሰብስባ አስቀምጣ ልክ እንደቤቷ ዘና ብላ) ከዛ አብረው ምኝታ ቤት ገቡ ....ኧረ ሶፋውን ማን ይዞባቸው ...ከዛ ነፍሳቸው መለስ ሲል አወሩ

"ፊልም ትወጃለሽ የኔ ቆንጆ " ሊላት ይችላል ግን "የኔ ማር"ነው የሚላት (ለምን አይላት እንዲህ ተንከባክቤ የያዝኩትን ፀሃይ ነክቶት የማያውቅ ገላ ሲያቅፍ እንኳን ማር ሌላስ ቢላት )

"በ...ጣ...ም " ትለዋለች ደረቱ ላይ ተለጥፋ ይች መዥገር ! ሁለቱም መዥገር ናቸው እንጅ ! እሷም እሱ ላይ እሱም ትዳሬ ላይ የተጣበቁ መዥገሮች !

"እና በየቀኑ ትመለከቻለሻ "

"በፊት ነበር አሁን ባሌ እየተነዛነዘ በየት በኩል ሊያሳየኝ ብለህ"

"ኡ...... ባልሽ ግን ምናይነት ደደብ ቅል ራስ ነው ባክሽ ሙቪ እያያችሁ ይነዛነዛል ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አማይዚንግ ! "

"በ...ጣ...ም ...ምን ቅል ብቻ ድንጋይ ...ባልጩት ራስ ነገር ነው እንጅ ሲገባ ሲወጣ መነዛነዝ ነው እነዳልተሳካለት ተዋናይ ያየውን ተዋናይ ሁሉ መዘለፍ ነው ስራው "ትለዋለች እሷን ባፈቀርኩ ቤቴን ትዳሬን ባልኩ የማንም ዱርየ ጋር ስታማኝ አያበሳጭም ? ....ውስጤ ይብከነከናል ላብ ላብ ይለኛል !

በላብ የጨቀየ መዳፌን በእልህ ጨብጬ ሶፋውን በቡጢ እነርተዋለሁ ! መአዛ በድንጋጤ ከራማዋ ተገፎ እያማተበች ትቀርበኝና ጭንቀት በወረረው ፊቷ ላይ እንባ በኳተሩ አይኖቿ እየተመለከተችኝ

"ምነው ፍቅር ምን ሆንክ ? ሰው ጋር ተጣላህ እንዴ ? ላብ በላብ ሆንክ እኮ አመመህ እንዴ የኔ ፍቅር ....?" ጉንጬ ላይ እጇን ልታሳርፍ ስትልክ እጇን ወደዛ እሽቀንጥሬ ተነስቸ ወደምኝታ ቤቴ እገባና የቁም ቅዣቴን ተኝቸ እቀጥላለሁ ! እሷም ግራ በመጋባት ወገቧን ይዛ መኝታ ቤት በር ላይ ቁማ ትቆያለች !

"ምን አዳ ገባሁ" እያለች !! እቀናለሁ እቀናለሁ እቀናለሁ ! አንዳንዴማ በህልሜ ሁሉ ስለምቃዥ መአዛ ፀበል እንሂድ ትለኛለች ! ቢመቻት እብድ ነው ብላ አማኑኤል አሳስራኝ አለሟን ከሌላ ወንድ ጋር ልትቀጭ

እንዳሰበች እጠረጥራለሁ ....ተገኝቶ ነው ? አሁን ሌላ ወንድ ጋር ብትሄድ ሰው አያስቀምጣትም " አስኪ ምን አጣች ጥጋብ ልክስክስነት እንጅ ቱ ! ይሄን የመሰለ ሽበላ የጠገበ ደመወዝ የሚበላ አየር መንገድ የሚሰራ ባል ትታ ...ወይ ጥጋብ " ይላታል ....ካበድኩላት ግን እንዳሻት ትዘላለች ሰውም አይቃወማትም "ምን ታድርግ እብድ ጋር ትኑር እንዴ ታዲያ.....ወጣት ናት ቆንጆ ናት ስንት ነገር ያምራታል ምን በወጣት" ሊሉ ይችላሉ ! እኔ ደግሞ ለእልኳ አላብድ ! ሲያምራት ይቅር !! ሌላ ቀን ደማቅ ሰማያዊ ሹራብ በቢጫ ሱሪ ለብሸ ልወጣ ስል "ኧረ አብርሽ አብሮ አይሄድም ሱሪውን ቀይረው የኔ ቆንጆ ፊትህ ጥቁር ቢሆን እንኳን ያምርብህ ነበር አንተ ጋር ግን አይሄድም " ብላ በሳቅ ፍርስ አለች ! ቆይ እሷ ስለወንድ አለባበስ እንዴት አወቀች ? ...ይሄ ስለልብስ ቀለም ሳይሆን ስለእኔ ምርጫ አለማወቅ ለመናገር ሆነ ብላ የተናገረችው ነገር መሆን አለበት ...እንዳልሰማ ሰው ትቻት ወጣሁ ! እዛ ላስቀመጠችው ለእናቷ

ቴሌቪዥን ለሚገዛው ደደብ ውሽማዋ ትንገረው ምናልባት ጥቁር ሊሆን ይችላል ... !! ትቻት ወጣሁ ለምን እንደሆነ እንጃ እንደማላከብራት ማሳየት እፈልጋለሁ ! እንደምንቃትና የጥፍር ቆሻሻየን ያህል ቦታ እንደማልሰጣት ማሳየት ያምረኛል !! ከቤቴ እንደወጣሁ በር ላይ አንድ የማልወደው ጎረቤቴ ደረቱን ገልብጦ በጧቱ በፓከ አውትና በቁምጣ ኮንዶሚኒየሙ ደረጃ ላይ አገኘሁት ...እኔ ስወርድ እሱ ሲወጣ ነበር የተገናኘነው ...በእጁ የመዝለያ ገመድ ይዟል ከስፖርት እየተመለሰ ነው

"ሰላም አብርሽ" አለኝ በፈገግታ

"ሰላም ሰለሞን " ብየው ላልፍ ስል

"ምነው ይሄ አለባበስህ ትንሽ አልደመቀም " አለና ፈገግ አለ (ቀልዶ ሙቷል ለዛ ቢስ ለካፊ ሁሉ) እንዳልሰማሁ አለፍኩት ...ጣሳ ራስ እሱ ስለኔ አለባበስ ምን አገባው ! ይሄ ቦዘኔ ጎረቤቴ ስራው ምን እንደሆነ አይታወቅም (ስራ እንኳን ያለው አይመስለኝም) ሁልጊዜ የምንጋራው በረንዳ ላይ ወንበር ያወጣና ዝሆኔ የያዘው የሚመስል(ፈርጣማ ይሉታል አንዳንዶች) ጠብደል ግንዲላ እግሩን ዘርግቶ ጋዜጣ ያነባል ...ኑሮው ዘና ያለ ነው ...አንዳንዴ ውድ የሆነ ሙሉ ልብሱን ይለብስና ዲኤክስ መኪናውን

አስነስቶ ይሄዳል ... አፍታ ሳይቆይ ደግሞ ይመለሳል .......ቤቱ ውስጥ የቀበረው ነገር ሳይኖር አይቀርም ! ከቤቱ ርቆ አይሄድም ! ይዞት ይሂድና ! ቆይ ግን እቤት እየዋለ እንዲህ ተዝናንቶ የሚኖርበትን ገንዘብ ከየት አባቱ ነው የሚያመጣው ሌባ ይሆን ...ወይንስ ቅጥር ነብሰ ገዳይ ....? ይህን እያሰብኩ ታክሲ የምይዝበት ቦታ እንደደረስኩ ......ድንገት አንድ ሃሳብ አይምሮየ ውስጥ ፈነዳና ቀጥ ብየ ቆምኩ ፉጭጭጭጭጭጭጭጭጭ እንደመኪና ! አቋቋሜ ድንገተኛ ስለነበር ከኋላየ የነበረች ልጅ ልትጋጨኝ ለትንሽ ተረፈች ! (((((ቆይ ይሄ ጎረቤቴ እቤት ሲውል ምን እያደረገ ይውላል ? ))))))) መደዳውን አራት ቤቶች አሉ ....ጥግ ላይ የኔ ቤት መአዛ ስራ ስለሌላት ቤት ነው የምትውለው .... ቀጥሎ ሁልጊዜ ዝግ

የሆነው እንደኔ ከርታታው ጎረቤቴ (ፊልድ ነው ስራው) ቤቱ ሁልጊዜ ዝግ ነው የሸረሪት ድር ሁሉ በሩ ላይ ያደራል ! ቀጥሎ ይሄ ቦዘኔ አለ! ቦዘኔው መልኩ ጥቁር ነው ...ልክ እንደፊልም የሚስቴ ንግግር በምልሰት ታየኝ "ጥቁር እንኳን ብትሆን ....." ነው ያለችው አይደል ....ቢንን!!! ተበላሁ ...ውሻየን ጎረቤት አስሬ

የምን ስራ ...! ቦዘኔው እቤት ነው የሚውለው !ምን እቤት አኔ ቤት ልበል እንጅ !! መቸስ በአንድ ዝግ ቤት ዳርና ዳር ቦዘኔውና ሚስቴ ብቻቸውን ሲውሉ አይነጋገሩም ማለት ዘበት ነው ....እንዴ ...አብረውም ፊልም ሊመለከቱ ይችላሉ እንጅ ...በእኔው ቴሌቭዥን በእኔው ዲቪዲ እኔው ሶፋ ላይ እኔው የምወዳት የረዥሙ ሶፋ ጥግ ላይ !! .....ሊሆን ይችላል !! ተመልሸ ወደቤቴ ሮጥኩ ! ጉድና ጅራት ...አሉ ! ወይ ድፍረት

.....በቤቴ በራሴ ቤት... በራሴ አልጋ... በራሴ ብርድ ልብስ... በራሴ አንሶላ... በራሴ ፍራሽ...በራሴ ትራስ .... በራሴ ሚስት በራሴ .....! ባፍጢሜ እስከምደፋ ተጣደፍኩ ...ምን ዋጋ አለው እስካሁን ነገር የተበላሸውን ! ... አልጋውን እንደሆነ እኔ ሚስኪኑ እኔ ራሴ እንደመኪና አሙቄ ትቸለት ወጥቻለሁ .... መአዛንም ቢሆን ሌሊቱን ልታቅፈኝ ስትሞክር በኩርፊያ እጇን እየገፋሁ ጀርባየን ሰጥቻት በአምሮት አቃጥያት ነው ትቻት የወጣሁት .....በስስ ፒጃማ የሞቀ አልጋ ውስጥ እሳት ሁና ትጠብቀዋለች ..... በቃ ምን ቸገረው ቁምጣውን ወለቅ አድርጎ በጧቱ ገነት መግባት ነው !!!!!!!!! ጉድ ጉድ ጉድ አሟሙቄ ለሰው ! ወይ ነዶ !! ሮጥኩ .....ኮቴ እንደክንፍ እየተውለበለበ ........ ወደቤቴ ! (ምን ቤት አለኝ) ቤቴ ፈራርሶ ! ሱናሜ አውሎ ነፋስ ከስር

መሰረቱ ቤቴን ነቅሎ የሚጥል ጎርፍ ከጎረቤት አገር ! መንገዱ ረዘሙብኝ የመአዛ ደረት ...የተላጠ ሸንኩርት መስሎ ታየኝ ....ጡቶቿ ስስ ፒጃማዋን ወጥረው ጫፋቸው ባቄላ ባቄላ መስሎ ቀይ ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠ ከስር ተንጋላ ስትቃትት ታየችኝ ድምጿ ተሰማኝ "የኔ ጠረንገሎ እወድሃለሁ ከዛ ከነዝናዛ ከልፍስፍስ ባሌ ሽ እጥፍ ትበልጣለህ " ስትል በሃሳቤ ሰማኋት ልትል ትችላለች ! ...የሚያማምሩ እግሮቿ በጠንገሎው ዙሪያ

ተጠምጥመው.... እግሮቿማ ለምን አያምሩ እሾህ አይወጋቸው ጋሬጣ..... ሎሚ መስለው እንደተቀመጡ ሳይወጡ ሳይወርዱ እቤታቸው ...ምኝታ ቤታቸው ድረስ ካንድ አይሉ ሁለት ባል ሲመጣላቸው ... ለምን አያምሩ ! ያ የገደል ስባሪ የሚያህል ቦዘኔ ጎረቤቴ ከነላቡ ከነጠረኑ አልጋየ ላይ ታየኝ ...ምናለ ሻወር እንኳን ቢወስድ .... የሰው አልጋ መድፈሩ ካልቀረ ለወጉ ለስርአቱ ሰውነቱን ለቅለቅ ብሎ ቢዳፈር ምናለ...ስራ ውየ ደክሞኝ ነው የምገባው ለኔስ አያዝኑም ? አንሶላ መጋፈፉን ቢቀማኝ አንሶላ ለብሽ ኩርምት የምልባትን አልጋ ምናለ ቢተውልኝ ? ወይ ጭካኔ ! ታየኝ ላቡ እንደማስቲሽ መአዛ ውብ ሰውነት ላይ ተመርጎ አለቅም ሲል ...ማን ያውቃል የራሴ ሚስት በስሜት እየተስረቀረቀች "የኔ ጌታ ጠረንህ የናርዶስ ሽቶ ነው " እያለችው ይሆናል ... ፍቅር እንኳን አፍንጫን አይምሮን ይዘጋ የለ ! አዎ ልትለው ትችላለች

.....ሊሆን ይችላል !! ደግሞ እንደአባወራ ቤት አለኝ ብየ ሶፋ ላይ ተጎልቸ የማላውቀው አገር እሳተ ገሞራ ሲፈነዳ በሃዘን ከንፈሬን እየመጠጥኩ በቢቢሲ አያለሁ .... የዋህ አባወራ እሳቱን ጎረቤት አስቀምጦ አሳተገሞራ በዜና ያያል .....እኔን ራሴን ዜና አደረጉኝ! እድሜ ለሚስቴ እኔን ራሴን ዜና ...ያውም ሰበር ዜና... ሞራሌንም ቅስሜንም የሚሰባብር የሚያነካክት ሰበር ዜና ! ...እዚህ አገር ምን ጋዜጠኛ አለ ....ቢኖርማ ካሜራቸውን ይዘው ከኋላየ ተከትለውኝ በሮጡ ነበር !! ዝም ብለው ስለግድብ ያውሩ

እዚህ ስንት ሚሊየን ሜጋ ዋት እሳት ከምኝታ ቤቴ ሲመነጭ መቸ በቁም ነገር ተመለከቱት ....!! እቤቴ ስደርስ በሩ ብርግድ ብሏል ....እግዚኦ ድፍረት! ምናለ በሩን እንኳን መለስ ገርበብ ቢያደርጉት ... እግዜርን ባይፈሩ ሰው ባይፈሩ ነፋስ እንኳን አይፈሩም ?... አየ መቸ አጣሁት ይህን ጊዜ የምኝታ ቤቱን በር ቆልፈው.... ሊሆን ይችላል !! በተከፈተው በር ተወርውሬ ስገባ መአዛ በድንጋጤ “ እብርሽየ ድረስ “ ብላ በእጇ የያዘችውን የዱቄት ሳሙና በቁሟ ለቀቀችው (ባትለኝም ደርሸ ነበር እኔማ) ... ዱቄት መስሎ ሳሎኑ ምንጣፍ ላይ ተዘራ ...ራቅ ብሎ ሊታጠብ የተዘጋጀ የእኔ የቆሸሸ ልብስ ተከምሯል ! በዚህ ሌሊት ልብሴን ልታጥብ እየተዘጋጀች ነበር መአዛ ! የሃፍረቴን ወደምኝታ ቤት ገብቸ ኮሜዲኖውን ከፈትኩና የረሳሁትን እቃ የወሰድኩ መስየ ተመልሸ ወደስራየ ሮጥኩ ! መአዛ ግን በትዝብት እያየችኝ ነበረ !! ትንሽ ሃፍረት ቢሰማኝም አይምሮየ ውስጥ ግን አንድ ሃሳብ መጣብኝ .... መአዛ ልብስ አጥባ ካሰጣጣች በኋላ የተሰጣው ልብስ እስከሚደርቅ ምን ትሰራለች ? ....በተሰጣው ልብስ ውስጥ ጠረንገሎው ጎረቤቴ እየተሽሎከሎከ ወደቤቴ ሲገባ በሩ ሲዘጋ .....ታየኝ! ሊሆን ይችላል ! ከሰአት ከቢሮየ ሆኘ ለመአዛ ስልክ ደወልኩላት...... አንዴ ጠራ ...2...3...4...5 “የደወሉላቸው ደንበኛ ስልክ አይመልስም! እባክዎ ....” ወይ እባክዎ ምኑን ተከበርኩት ...ምኑን ለአንቱታ በቃሁት ...ኮት መልበስ ብቻውን አንቱ አያስብል ...ቢሮ ያማረ ወንበር መኖሉት አንቱ አያስብል ጓዳየ እየፈረሰ ቤቴ እየተገረሰሰ ሶስት ጉልቻ ያልኩት ትዳሬ ስድስት ጉልቻ እየሆነ ወይ አንቱታ .....! ስልኩ ያለ ሳሎን ሚስቴ እስካሁን ምኝታ ቤት ...ወይም ጠረንገሎው ጎረቤቴ ቤት ትሆናለች ማን ያንሳው ስልኩን.... ዘመድ እንደሌለው ሃዘንተኛ ብቻውን የትም ተጥሎ ያልቅስ እንጅ ! ብቻውን ስልኩ .... ስብሰከሰክ ስልኬ ጠራ... መአዛ ነበረች

“የት ሂደሽ ነው ስልኩ ይሄን ያህል ሲጠራ “

“ልብስ ሳጥብ ውየ አሁን ገና ጨረስኩና ሻወር ገብቸ እኮ ነው ...ከነሳሙናየ ራቁቴን ነው አሁን የቆምኩት ፍቅር ብታየኝ ሳስቅ”

“ ማን አለ ? “ “ማን አለ ? የት ? “ አለች በግርምትና ግራ መጋባት ...ያመለጠኝን ጥያቄ አልደገምኩትም ! መአዛም ከዛ በኋላ አላነሳችውም ! ቅናቴ ሲጨምር ልፍስፍስና በራሴ የማልተማመን ሰው ሆንኩ

በፊት በቀላሉ የምሰራውን ነገር ሁሉ ቀላሉን ስራ ሳይቀር መስራት አልቻልኩም ! ቅናት አቅም ያሳጣል ...አንድ የማይረባ ነገር ላይ ብቻ በማተኮር በዙሪያችን ያሉ መልካም ነገሮችን ሁሉ ይጋርድብናል! አንድ ቀን መአዚ ጋር ሻይ ቡና እንበል ብለን ወጣንና አምሽተን ስንመለስ እኔ ይዠው የነበረው የቤት ቁልፍ

ጠፋ ! ውጭ ጋር ቁመን አማራጭ መፈለግ ጀመርን ..... እኔ ሰብረን እንግባ ስል መአዚ ሳይመሽና ታክሲ ሳናጣ እናቷ ቤት ሂደን እንድናድር ሃሳብ አቀረበች ! ልሰማት አልፈለኩም ...ቁልፉን ለመስበር መታገል ጀመርኩ እታች አንደኛ ፎቅ ላይ ካሉ ጎረ - ታች ቤት (ለኮንዶሚኒየም የታች ጎረቤቶች የሰጠሁት ስም ነው

..ላይ ያሉትን ጎረ - ላይ ቤት ......ከጎን (ሰው የለም እንጅ ) “ጎረቤት” ይሆን ነበር እና ከጎረታችቤት ቢላዋ ፔንሳ መፍቻ ተውሸ መጣሁና መታገል ጀመርኩ ወይ ፍንክች በሩ ! መአዚ ረዥም ጫማ ስላደረገችና ዋክ እያደረግን ስለመጣን መቆም ደክሟት የለበሰችውም ቀሚስ አጭር ስለነበር ብርድ እያንሰፈሰፋት ከጎኔ ጡቶቿን በእጆቿ አቅፋ ትንቀጠቀጣለች ። አንድ ሰአት የሚሆን ታግየ ላብ በላብ ሁኘእና እጀ ደም አርግዞ

ያተረፍኩት ነገር ቢኖር በሩ ሊከፈት እንደማይችል ማረጋገጥ ነበር !

“በቃ አይከፈትም “ አልኳት

“ነግሬህ ነበር እኮ ፍቅር! በቃ እማማ ጋር እንሂድ “ አለችኝ እየተቻኮለች ! በዚች ቅፅበት የጠረንገሎው “ጎረቤት “ በር ተከፈተ ! በሩ ሲከፈት በበሩ ስፋት ልክ የብርሃ ምንጣፍ በሩ ፊት ለፊት ያለው በረንዳ ላይ ተነጠፈ ...ጠረንገሎው የደረቱን እና የእጆቹን ጡንቻ አጉልቶ የሚያሳይ ጉርድ ቲሸርት ከቁምጣ ጋር

ለብሶ ብቅ አለ ! የብርሃን ምንጣፉ ላይ ቁሞ ወደእኛ አየት አደረገና

"ደህና አመሻችሁ አብርሽ " አለ እሱን ሳይ እልሄ ኬየት መጣ ሳልለው ከንብል አለብኝ ለሰላምታው መልስ ሳልሰጥ ኮቴን አውልቄ "ያዠ " አልኳትና ቢላውን አንስቶ ቁልፉን መጎርጎር ጀመርኩ

"ሰላም አመሸህ አቶ ሰለሞን ቁልፍ ጠፍቶብን ለመክፈት እየታገልን ነው ይሄውልህ " አለች መአዛ ...ምን አስለፈለፋት ! እየተንጎራደደ መጥቶ አጠገባችን ሲቆም ጥላው ከበደኝ ... አያያዜን ትንሽ ተመለከተና "እስኪ መፍቻዋን ስጭኝ" ብሎ ከመአዛ ተቀበለ ..... እንዳቀረቀርኩ ገመትኩ .....መአዛ መፍቻውን ስትሰጠው እጆቻቸው ተነካክተዋል አይኗን አይኑ ላይ ተክላ ፈገግ ብላም ሊሆን ይችላል ...እጁ ሲነካት ብርድ ላይ ያመሸ ሰውነቷ በደስታ ተፍታቶ ሙቀት በሙቀት ሁኖም ሊሆን ይችላል "በዚህ ብርድ ይሄ ደፍዳፋ ባሌ ድራሹ ጠፍቶ አንተ ቤት ገብቸ እቅፍ ብታደርገኝ " የሚል መልእክት በአይኖቿ ልትነገረው

ትችላለች .....እሱም በጉርድ ቀሚስ ያልተሸፈኑትን ውብ እግሮቿን ተስገብግቦ እየተመለከተ ይሆናል እግሮቿን ሊስማቸው እያለመስ እንደሆነ ማን ያውቃል ....

"አብርሽ አንዴ ልሞክረው እስኪ " አለኝ ወደበሩ ጠጋ ብሎ

"አይ አይከፈትም ሞከርኩትኮ ...በቃ ነገ በባለሙያ እናስከፍተዋለን ቁልፉን ቢሮም ረስቸው ሊሆን ይችላል" ብየ ቀበጣጠርኩ ጠረንገሎው ግን እኔ ስናገር ወደበሩ ጠጋ ብሎ ጀርባውን ሰጠኝና በሴኮንዶች እድሜ በሩን ሲነካካው ....ምኑን እንደነካው እንጃ ቀጭ ብሎ በሩ ተበረገደ! ካለባለቤቱ አይነድም እሳቱ

ባለቤት ሁኖበት የለ ቤቱን ...ገና ሲነካው ተበረገደ ! ውስጤ በብስጭት በመበለጥ ስሜት በቅናት ተንገበገበ ! ደካማነት ተሰማኝ መአዛ ፊት ይሄ ቦዘኔ ተራራ አክሎ እኔ ጠጠር ያከልኩ መሰለኝ !

መአዛ በሳቅ እና ደስታ በታጀበ ስርቅርቅ ድምፅ "አ እግዚአብሄር ይስጥልን " አለችው ! ይሄ ድምፀዋ ከነፍሷ ስትደሰት ነው ከውስጧ የሚወጣው ! ለምሳሌ አግቢኝ ያልኳት ቀን ኦማይጋድ ብላለች ..... ከወሲብ በኋላም በጣም ስትደሰት ኦማይ ጋድ ትላለች አሁንም ይሄው ይሄ ጠረንገሎ "እኔ ያላላሁትን ስለከፈተ" ደገመችው ! ቦዘኔው በሩን ሳይሆን የመአዛን እግሮች በሃይ የከፈታቸው ያህል ጠላሁት !!

ጭራሽ መአዛ "እባክህ ግባና ሻይ ጠጥተህ ትሄዳለህ" እያለች ትለምነው ጀመረ ! ይሄ ጠረንገሎ በሩን ብቻ አይደለም የሚስቴንም ልብ ነው የበረገደው ! አመሰግናሁ እንኳን ማለት አልቻልኩም ገብቸ ወደምኝታ ቤቴ አመራሁ ...በዚህ አያያዛቸው ቀድመው መኝታ ቤቴን ሳይዙብኝ አረፍ ልበል ብየ ! "እሽ ደህና እደር " ስትለው ይሰማኛል! ምናልባት ዞር ብላ አለመኖሬን ስታውቅ ከንፈሩን ስማው ይሆናል ተንጠራርታ ቱቶቿ ደረቱ ላይ አልፈው ! እሱም ትንሽ ሸብረክ ብሎላት ! እሚ!! መአዛ ሰውየዋን ሸኝታ ወደምኝታ ቤት መጣችና ፊቷ ተቀያይሮ ፊቴ ቆመች ያላየኋት መስየ አይኖቸን ጨፈንኩ !

"ስማ አብርሽ ለምን ይሄን ያህል ባለጌ ትሆናለህ ...ሰው ጎረቤቱ ሲረዳው ማመስገኑ ቢቀር እንዲህ መገላመጥ አለበት ለምን እኔንስ ታሳፍረኛለህ ምንድነው ችግርህ የተማርክ አይደለህም እንዴ "

" ምንድነው የረዳን የሰው ቤት ቁልፍ ስለፈለቀቀ ....ወሮ በላ ይሄ እንደውም ልምድ ያለው ቤት ፈልቃቂ ሳይሆን አይቀርም "

"ኧረ በእግዚአብሔር አብርሽ ስርአት ይኑርህ "

" አፍሽን ዝጊ " ብየ ቤቱን በሚያናጋ ድምፅ ጮህኩባት ! ሽምቅቅ አለች " ስርአት አንች ነሽ የምታስተምሪኝ ? ...መጀመሪያ ራስሽ ስርአት ይኑርሽ ሌላውን በሌለሁበት የምታደርጊውን ሁሉ ያላወኩ መስየ ብችለው ጭራሽ የማንንም ቤት ሰርሳሪ እየጠራሽ ቤቴን ማሰበር ጀመርሽ " መአዛ ትክ ብላ

እየተመለከተችኝ በተረጋጋና በሚያስፈራ ድምፅ

" ምንድነው በሌለህበት ያደረኩት ?" አለችኝ

“አላውቅልሽም ልተኛበት “ ብየ ልብሴን ማወላለቅ ጀመርኩ

“ ምንድነው በሌለህበት ያደረኩት “ ብላ ከበፊቱ ጠንከር ባለ ድምፅ ጠየቀችኝ ....

“ ቁልፍ ሰባሪ ጓደኛሽን ሂጅና ጠይቂው “ አልኳት በእልህ !! መአዛ ነገሩን እሷ ያወራችው ይመስል አፏን በእጆቿ አፍና እንደመንቀጥቀጥ አደረጋት ! ....በዚች ቅፅበት በራችን ተንኳኳ የጎለጎለችብኝ አይኗን እንደተጎለጎለ በሩን ልትከፍት ሄደች !

“ ረስቸው መፍቻውን ይዣባችሁ ሄድኩ” ሲል ሰማሁት ጠረንገሎው ...ምን ትረሰዋለህ በየምክንያቱ አይንሽን ልይ አትልም ...እላለሁ በውስጤ

“ውይ መጥቸ እወስደው አልነበር ምን አመላለሰህ “ ስትል ሰማኋት ከበፊቱ ሻከር ባለ ድምፅ ...ይሄን የመአዚ ድምፅ ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ሰምቸዋለሁ ! ለሁለት አመት ትምህርት ሌላ አገር ልሄድ ስትሰናበተኝና እናቴ እንዳላገባት ፊቷ የነገረችኝ ቀን ...ይሄን ድምጿን እፈረዋለሁ ... መኝታ ቤቴን ከውስጥ መቀርቀር ከጀለኝ ....ማንን ደስ ይበለው ብየ ! መአዛን ጠበኳት ወደመኝታ ቤት አልመጣችም ቀስ ብየ ወደሳሎን ሄድኩ ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ ባዶው ላይ አፍጥጣለች ...ወዳፈጠጠችበት ተመለከትኩ የሰርጋችን ፎቶ አለ ....ምናልባት በእኔ ቦታ ጠረንገሎውን ተከታ እያሰበች ይሆናል ... ተመልሸ ተኛሁ ! ሌሊት ወደዘጠኝ ሰአት ከእንቅልፌ ስነቃ መአዛ አሁንም ጎኔ የለችም ቀስ ብየ ወደሳሎን ሄድኩ ...ማታ እንዳየኋት ከነልብሷ ከነጫማዋ ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ የሰርጋችን ፎቶ ላይ አፍጥጣለች ተመልሸ ተኛሁ! ጠዋት ተነስቸ ወደሳሎን ሄድኩ ...መአዛ የተተኮሰ ልብስ .... ቁርስ አላዘጋጀችልኝም እዛው ቦታ በዛው ሁኔታ ተቀምጣ እንቅልፍ ወስዷታል ! እንደተኛች ወጣሁ !

“ምን ቢያኮርፍ ያሙን ያድራል “ አሉ .... ጠረንገሎው መኪና ማቆሚያው አካባቢ ገመድ ይዘላል! ቁንጣን ያዘለለውና ! ማታ ወደቤት ስመለስ መአዛ ቤቱን ትታልኝ ሂዳለች ! አሁን ቅናት ሙሉ ሆነች ! ማሰብ ጀመርኩ ሻንጣዋን ይዛ ስትሄድ የሆነ ባለመኪና አገኛት ... “ቆንጆ ወዴት ነው ልሸኝሽ “ ይላታል ... ትገባለች ...እያለቀሰች ታሪኳን ትነግረዋለች ....አቅፎ ያባብላታል ....ምናልባትም አንገቷን ሊስማት ይችላል ...የመአዛ አንገት ምን እንዳለው አላውቅም ተኮራርፈን እምኳን አንገቷን ከሰምኳት እሳት እንደነካው ቅቤ ፍስስ ነው የምትለው ...አንገቷ ዙሪያ ሃብል ሳይሆን የስሜቷን ቁልፍ አንጠልጥላ ትዞር ይመስል ! መአዛ አልተመለሰችም .... ንፁህ አፍቃሪ መሆኗን ባውቅም ሁለት ሰው የሆንኩ እስኪመስለኝ አይምሮየ የቅናት ቅዠቱን ሊያቆምልኝ አልቻለም ...ልቤ ይገስፀኛል ልቤን ገደል ግባ ስለው ነው ድሮም ራሴ ገደል የገባሁት! ቁጭ ብለን ልባችን ጣራ ላይ የሰቀልነውን ልምድ ቁመን ልናወርደው አይቻለንም ! እናቷ ቤት የለችም ጓደኛም ከእኔ ውጭ አልነበራትምና ማን ጋር ሂጀ ልጠይቅ ....ሌላ ሰው አግብታ ይሆን እንዴ ምናልባት እኔ

ጋር እያለች ይገናኙ የነበረ ሃብታም ....ሊሆን ይችላል !! ከአራት አመት መለያየት በኋላ አየር መንገድ ስራ ላይ እያለሁ ከሳውዲ ታፍሰው ከተባረሩ ኢትዮጲያዊያን ስም ዝርዝር መካከል የመአዛን ስም ተመለከትኩት .... ሌላ ሴት ጋር ፍቅር ጀምሬ ነበርና ከዚህ በላይ ስለመአዛ ማሰብ አልፈለኩም ... ግን አዲሷ ፍቅረኛየ ዛሬ እንዴት ሳትደውል ቀረች ...ያ በፀሃፊነት የሚያሰራት አስቀያሚ ሃብታም ጋር .... አዎ የሆነ ነገር ያዛትና ቢሮው ስትገባ ያንን ፀይም ጉንጪን ሊደባብሰው ይችላል በጉርድ ቀሚሷ ውስጥ ታፋዋ ላይ እጁን እያመላለሰ ስለስራ እድገት ሊያወራላት ይችላል ... .......ሊሆን ይችላል !!

አንዷት መርፌ ስንቱን ቀዳዳ ትስፋው

ይህ ተከታታይ ወግ ሁለት ክፍሎች አሉት

(ክፍል 1)

ዙቤዳ ስልክ ደወለችና “አብርሽ “ አለችኝ ድምጿ ውስጥ ምቾት አለ አይጎረብጥም

“ወይየ የኔ ቆንጆ ...የኔ ማር የኔ ለስላሳ ... የኔ ሃር ....የኔ ፍቅር ....የኔ ደስታ ...የኔ ....ሳቅ ....የኔፌሽታ ....የኔ ሃሴት .....የኔ .....

ዙቤዳ ዝም ብላ ስታዳምጠኝ ቆየችና ( ዝምታዋ አስክርቢቶና ወረቀት ይዛ ያልኩትን ሁሉ የምትመዘግብ ነበር የሚያስመስላት) ረጋ ብላ “አባባ ሊናግሩህ ይፈልጋሉ “ አለችኝ

“ምን ...?” ብየ በድንጋጤ ዝም አልኩ የጨው አምድ !

“ምነው ድምፅህ ጠፋ ...አንበሳ እገላለሁ የሚለው ባልሽ ቅጠል ሲንኮሻኮሽ ገደል ገባልሽ ...ሂሂሂሂ” ብላ በሚያምር ሳቋ ተቅጨለጨለች

“አባባ እማ ቅጠል ብቻ አይደሉም ትቀልጃለሽ ..... ግንድ ነው የወደቀብኝ “ አልኳት ! አባባ የምትላቸው አባቷን ጋሽ ጀማልን ነው ... በጣም የሚገርመኝና የሚደንቀኝ ነገር የዙቤዳ እህትና ወንድሞች በሙሉ አባታቸውን “አንቱ” ነው የሚሏቸው ! አንድ ቀን ታዲያ ዙቤዳን ጠየኳት “ዜድየ እንዴት አባትሽን አንቱ ትያለሽ ? “

“ትልቅ እህቴ ዘሃራ አንቱ ስትል ሰማሁ በዛው ቀጠልኩ የእኔ ታናናሾችም አንቱ ነው የሚሏቸው “ አለችኝ !ትልቅ እህቷ ዘሃራ ጋር (የዛሬን አያርገውና ) እንግባባ ስለነበር ዘሃራንም ጠየኳት “ዘሃራ አባት አንቱ ይባላል እንዴ ? “

“ትልቅ ወንድማችን አንዋር አንቱ ይል ስለነበር በዛው ለመድኩ “ አለችኝ .....ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አንቱታ ! በጣም የሚያስቀው ታዲያ የመጀመሪያው የአንቱታው ጅማሬ ትልቁ ልጅ ኡስማን ሲሆን የጋሽ ጀማል ልጅ ሳይሆን ገና ትዳር እንደመሰረቱ ልጅ ሳይወልዱ በፊት አብሯቸው መኖር የጀመረ የጓደኛቸው ልጅ ነበር ....ከዛ በኋላ የተወለዱት ሁሉ አባታቸውን አንቱ እያሉ ቀጠሉ !

የዙቤዳ አባት ጋሽ ጀማል የተፈሩ የተከበሩ የአገር ሽማግሌ በዛ ላይ አዱኒያ ሞልቶ የተልከሰከሰላቸው ሃብታም ናቸው ! በአመቱ ለረመዳን ዝሆን የመያካክሉ በሬዎች እያረዱ ሰደቃ ያበላሉ፣ ሚስኪኖችን ያስፈጥራሉ ! ቤታቸው አስፈሪ ግርማ ሞገስ አለው ... ወደላይ የአጥሩ ግንብ ርዝመት እንኳን ተራማጅ ፍጥረት በራሪም አእዋፋት የሚዘሉት አይመስሉም ! በዛ ላይ አጥሩ ጫፍ ላይ የተጠማዘዘው ሽቦ ...... አንዳንዴ የነዙቤዳን አጥር ስመለከት በሰሩት ወንጀል የዘላለም እስራት የተፈረደባቸው አደገኛ እስኞች የታጎሩበት እስር ቤት ይመስለኛል !

ታዲያ ፍቅር የሚባል ጉድ የማያሻግረው ወንዝ የማያዘልለው ከፍታ የለምና መሰላል ሁኖ ይሄን አጥር አዘለለኝ! ምን ማዘለል ብቻ ግቢውን አልፌ የዋናውን ቤት በር በርግጀ እነዙቤዳ ሳሎን እዛ የሚያምር ምንጣፍ ላይ “ከነጫማየ” ስቆም ቤተሰቡ ተበጣበጠ! ዙቤዳ የምትባለውን ወርቅ የሆነች ልጃቸውን አፍቅሬ አገባታለሁ አልኩ ! ዙቤዳም ብትሆን የምትይዝ የምትጨብጠውን እስከታጣ አፍቅራኝ ነበር ! ግን ዙቤዳ እንደእኔ ማሬ ፍቅሬ ጅኒጃንካ አትልም ....ዝም ብላ አለምን በሚያስረሱ ውብ አይኖቿ የፍቅር ጅረት እያጎረፈች ነፍሴን በሃሴት ታረሰርሰዋለች ...

ዶሮ እንቁላሏን አቅፋ በሙቀቷ ጫጩቶችን እንደምታስፈለፍል ዙቤዳ በሩህሩህ እና ደግ ፀባይ እቅፍ አድርጋኝ ከዚህ አለም የሻገተ እና በክፋት በበሸቀጠ ቅርፊት የተጠቀለልኩ እኔን በፍቅር ትወልደኛለች ! በአይኗ እቅፍ አድርጋ ታሞቀቀኛለች “አይን የተፈጠረው ሁሉን ለማየት ነው” ሲሏችሁ አትስሙ የዙቤዳ አይን የተፈጠረው እኔን ብቻ ለማየት ነው ! አቤት ዙቤዳ ማየት ስትችልበት ! አስተያየቷ ቅኔ አለው አስተያየቷ ጀግና ያደርገኛል.... አስተያየቷ ሁሉ ነገሯን እንደሰጠችኝ የሚያረጋግጥ የብርሃን ፊርማ ነው! ዙቤዳን በሙሉ ልቤ አፈቅራታለሁ !

እናቷ ቢመክሯት አባቷ ቢዝቱ እና ቢቆጡ ወንድሞቿ በመሃበር ተደራጅተው ጧትና ማታ ፊቷ ቢፎክሩ..... ዙቤዳ የኔ የፍቅር ሰው ወይ ፍንክች!! “ አብርሽን እወደዋለሁ ወላሂ እወደዋለሁ !! “ ብላቸው ክችች !

ይሄ ንግግሯ እነዙቤዳ ቤት ታላቅ ታሪካዊ ድፍረት ተደርጎ ተመዘገበ የቅድም ቅድም ቅድም አያቶቿ ሁሉ ይሄን ድፍረት ቢሰሙ እንደማይክል ጃክሰን ትሪለር መቃብራቸውን እየፈነቃቀሉ ተነስተው ወላ ዱላ ወላ መፍለጫ

ይዘው እኔና ዙቤዳን መንገድ ላይ ይከቡን ነበር በዘፈን ሳይሆን በሙሾ ! "ይሄ አብርሃም የሚባል ልጅ ወይ አንድ ነገር አስነክቷታል ወይም እህታችንን ኢብሊስ ተጠግቷታል " አለ አሉ ወንድሟ... ራሷ ዙቤዳ ናት የነገረችኝ

"ኢብሊስ ምንድን ነው ዜድየ " አልኳት ዙቤዳን ስሟን ሳቀናጣው ዜድ አደርገዋለሁ አንዳንዴ

"ኢብሊስማ የሽይጧን አለቃ ነገር ነው " አለችና ከት ብላ ሳቀች !

" አሁንስ ወንድምሽ አበዛው ! ወይ አንች ትርጉሙን አሳስተሽዋል አሁን ለኔ አለቃነቱን ትቶ ምናለ ተራ ሰይጣን ቢያደርገኝ "

"ሂሂሂሂሂሂ " ዙቤዳ በሚያምር ሳቋ ትንከተከታለች ከዛም አይኖቿን ጣል ታደርግብኛለች !

ባየችኝ ቁጥር የሆነ መአረግ የተጨመረልኝ ይመስለኛል ! የኔ ማር እንዴት እንደማፈቅራት እኮ! ስትስቅ ብዙ ቀን ምኗን እንደምስማት ታውቃላችሁ..... ጥርሷን !! ያው ጥርሷን ስሜ ስመለስ አግረመንገዴን ከንፈሯንም መዘየሬ አይቀርም ታዲያ !

እውነቱን ለመናገር ለዙቤዳ ነፍስህን ስጥ ብባል አሰጣለሁ ...እሳሳላታለሁ ሰው ሲያያት የምታልቅብኝ ነው ነምትመስለኝ እንደጣፋጭ ከረሜላ ስሟ አፌ ውስጥ ሲሟሟ ይሰማኛል ! ፈሳሹ በጉሮሮየ አድርጎ ልቤን ሁሉ አረስርሶ እስከእግር ጥፍሬ ውስጤን ሲያጣፍጠው ይታወቀኛል ! እኔ ራሴ ትልቅ ጣፋጭ የሆንኩ ይመስለኛል ...ንግግሬ ሲጣፍጥ ለራሴ ይሰማኛል !!

ዙ ቤ ዳ ስሟ ከፊደላት አይደለም የተፃፈው "አግቹጰርስደፈሬተገፈዴየ" ከሚባል በገነት ከሚገኝ ፍሬ ጭማቂ ነው ተቀምሞ የተሰራው .... ይሄ ፍሬ መለአክቶች "ለአመት በአል" የሚመገቡት ጣፋጭ ፍሬ ነው.... ቅርፁ የብርቱካን አይነት ሁኖ ልጣጩ ከብርሃን የሚሰራ ! እሰይ ዙቤዳየን እንዲህ ሳደንቃት ሳሞግሳት ባይወጣልኝም ደስ ይለኛል! ይገባታል !

ዙቤዳ አገሬ ትመስለኛለች እትብቴ የተቀበረባት አገሬ፤ ፈገግታዋ ባንዲራየ ...አይኗ መከላከያ ሰራዊቴ ብቸኝነት የሚባል ጥላቴን አደባይቶ የደስታ ባንዲራየን በልቤ ግዛት ላይ ከፍ አድርጎ የሚያውለበልብ ...ፍቅሯ በምድር የተደበቀ ነዳጅ እና የከበረ ድንጋይ ታማኝነቷ የአገር ሚስጢር ..... ዙሪያዋ ድንበር ካለእኔ ካለልጇ ፈቃድ ማንም የማያልፈው እኔ ግን የምድህበት ዳዴ የምልበት የምቦርቅበት ለወግ ለመአረግ የምበቃበት ምድሬ........ ዙቤዳ አገሬ ናት !

የትኛውምንም የመኖሪያ ቤት አጥር ከውጭ ወደውስጥ መዝለል ይከብዳል ከውስጥ ፍቅር ገፍቶት ለሚወጣ ግን ቀላል ነው ! ዙቤዳ ከታላቁ ቤታቸው እየወጣች ለሁለት አመታት አለማችንን ቀጭተናል ! አለማችን መተያየት ነው ...አለማችን መነካካት ነው አለማችን እኔ እሷ አጠገብ እሷም እኔ አጠገብ መቀመጣችን ነው ! ያ ጊዜ ማንም ምንም የማይልብን ጊዜ ስለነበር ለእኛ ሰርግና ምላሽ ሁኖልን ነበር !

ፍቅራችን ሲጀመር ቤተሰቦቿ ያን ያህል አላሳሰባቸውም ....ሲደጋገምም ልጃቸውን አጫዋች ያገኙ መስሏቸው ወንድሞቿ እምብዛም ፊታቸውን አላጠቆሩብንም ... እንደውም ወንድሞቿ ወደሱቃቸው ብቅ ስል አብሽር እያሉ ያስተናግዱኝ ነበር! ሲቆይ እህቷ ዘሃራ አይነ ውሃየ እንዳላማራት ለዙቤዳ ነገረቻት (አይነ ውሃ ምንድነው ግን )

በጣም ሲቆይ ያበጠው ፈነዳ ቡምምምምምምምምምምምም ዙቤዳን ላያት ሱቃቸው ሄጀ እያወራን እየተሳሳቅን ቆየንና ልወጣ ስነሳ ያው ሁልጊዜ እንደምናደርገው ከንፈሯን ሳምኳት ! አቤት የዙቤዳን ከንፈር መሳም ....የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ መሳም በሉት...... ይነዝራል ያንዘረዝራል የሆነ በለጭ የሚል ነገር ሁሉ አይምሮ ውስጥ ይፈጥራል.... ይሄን ከንፈሯን ከምኑ እንደሰራው እንጃ ! ምናልባት ከትልቅ የኤሌክትሪክ ግድብ የግራ ጎን ከንፈሯን ለብቻው ፈጥሮት ይሆን ? (ዙቤዳን የሳምኳት እኔ ! እናተ ምኑ ይገባችኋል ዝም ብላችሁ ተጋነነ ትላላችሁ እንዴ ? )

እንግዲህ ዙቤዳን ስስማትና የዙቤዳ ታላቅ እህት ዘሃራ ወደሱቁ ስትገባ ልክ እንደሂሳብ ቀመር ልክ መጣ ! ጠገጣጠምን !! እህቷ በአይኗ በብረቱ ስንሳሳም ስታየን በብረት ዱላ አናቷን የነረቷት ይመስል ደርቃ ቀረች ! ዘሃራ የዙቤዳ እህት በቃ ደረቀች ! አደራረቋን ላየ ሰው እንደገና ነፍስ ዘርታ ትመለሳለች ለማለት ይከብደዋል ! ጦርነቱ ተጀመረ ! ከዛን ቀን ጀምሮ ቤተሰቡ ሙሉ ሃሳቡን ሙሉ ሃብቱን ሙሉ ዘመዱን (የሞቱትንም ሳይቀር ) እኔና ዙቤዳ ላይ አሰለፈ !

እኔና ዜድየ ደግሞ የማይታየው የእሳት ሰረገላ አገሩን ሁሉ ከቦ እኛን ሲጠብቅ እናየው ነበርና ማንንም አንፈራም ነበር ....ፍቅር !! “ድሮም አዚህ ሱቅ ሲልከሰከስ አላማረኝም” አለች ዘሃራ ... ዘር ቆጠራው ከረረ “በዘራችን እንዲህ አይነት ውርደት ቅሌት ....” እየተባለ ! የአያታቸው ጨዋነት የእናታቸው ትሁትነትና የተመሰገነ ባህሪ የአክስቶቻቸውና የአክስቶቻቸው ልጆች የልጅ ልጆች ስመ መልካምነት ተነሳ ተጣለ ! ይሄ ሁሉ የታሪክ ብራና የተዘረጋው በዘር ማንዘራችን ሃጊያት የፈፀመ የለምና ሃጊያተኛዋ ዙቤዳ ትወገር ትሰቀል ለማለት ነው !

የእኔና ዙቤዳን ግንኙነት በመጥፎ ከሚስሉት ሰወች መካከል አንዱ የዙቤዳ ወንድሞች ጋር ጓደኛ የሆነ ነቢል የሚባል ልጅ ነበረ ....ነቢል በጣም የሚያሳፍር ባህሪ ያለው ጨዋ ቦዘኔ ነበር ! ስራ አይሰራም መርካቶ ለመርካቶ እየዞረ ለሃብታም ይላላካል ። ለዙቤዳ አባትና ወንድሞችም በዚሁ መላላኩ ቤተሰብ ለመሆን በቅቷል ! ታዲያ ገና ሳያውቀኝ ስሜን በማጥፋት ስራ ተጠምዶ ነበር ምን እንደሚያተርፍ አላውቅም !

አንድ ቀን ቤተሰቡ በዙቤዳ ጉዳይ ሳሎኑን ሞልቶ ሲታመስ ይሄው ነቢል መርዙን እረጨ “ይሄ አብርሃም የሚባለው ልጅ ፀጉሩን አንጨብርሮ ጫት ቤት ለጫት ቤት የሚዞር ሱሰኛ ነው “እህታችን” አጠገብ ድርሽ እንዳይል አንድ ነገር ማድረግ አለብን “ አለ ! “ማን ቢወልድ ማን “ ትላለች ዙቤዳ በሆዷ....እኔና ዜድ ዙቤዳን እንደሚከጅላት ጠንቅቀን እናውቃለን ! እንደውም አንዴ አፍ አውጥቶ ጠይቋታል ! አሁን አፉን ሞልቶ “እህታችን” ሲል አያፍርም ! ዙቤዳ እንደውም እዛ ሱቅ ተኮርምቾ ስውል አንዳንዴ እጀን ይዛ ወስዳ ሻይ ቡና እንላለን እንኳን ጫት ቤት ልዞር ....እንደው አንዳንዱ ሰው እህ ብለው ከሰሙት የሚናገረውን አያውቀውም !

ዙቤዳን ያወኳት እዚህ ቄራ አካባቢ ከቡልጋሪያ ከፍ ብሎ የከባድ እቃ ማስመጫ ሱቅ ውስጥ በሻጭነት ተቀጥሬ ስሰራ ነበር! ሱቃቸው ከምሰራበት ሱቅ ጎን ሲሆን ሱቆቻችን የድንጋይ ቤቶች ስለነበሩ ይቀዘቅዛሉ ! ጧት ወንበር ውጭ ጋ እናወጣና ፀሃይ እንሞቃለን ....እነዙቤዳ ሱቅ በር ላይ የአንድ ትልቅ ህንፃ ጥላ ስለሚያርፍ ፀሃይ ፍለጋ እኔ ወደምሰራበት ሱቅ በር ጠጋ ብላ ነበር የምትቀመጠው ! እኔም ወንበር አወጣላትና ጎን ለጎን ተቀምጠን ፀሃያችንን እየኮመኮምን እናወራለን ....

አንዳንዴ እህቷም አብራን ትሆናለች ብዙ ጊዜ ግን ብቻችንን ነን ! እናም ይሄ ቅርርብ ስቦ ስቦ ስጋችን ፀሃይ ነፍሶቻችንም ፍቅር ይሞቁ ጀመረ ! አንድ ቀን ዙቤዳ ከመሬት ተነስታ “ ይሄ ፀሃይ ሱስ ሆነብኝ “ አለችኝ ....ያዝ እንግዲህ !! በኋላ ፍቅራችን ከለየለት በኋላ “አንተን ማየት ሱስ ሆነብኝ ማለቴ ነበር የማይገባህ ሆንክ እንጅ” ብላ አስቃኛለች ! እሷም ስለማይገባት እንጅ እኔም ሱስ ሁናብኝ ነበር! ዙቤዳ ከቤት ወጥታ የማታውቅ ውብ ልጅ ነበረች .... ፀሃይ ሲነካት ታብረቀርቃለች ቆዳዋ ወርቃማ ነው ! አላፊ አግዳሚው ባፍጢሙ እስኪደፋ አንገቱን ጠምዝዞ የሚመለከታት ልጅ ነበረች ! እንደው ስለወደድኳት ሳይሆን ዙቤዳ ከቤተሰቦቿ አንደኛ ቆንጆ ነበረች !

አባቷ ጋሽ ጀማል ታዲያ መከረውም ዘከረውም በዘመድ አዝማድ ልጃቸውን አስመስከረውም አልሆን ሲላቸው ረጋ ብለው ሲያስቡ ቆዩና

“ዙቤዳ “ አሏት ልጃቸውን

“ አቤት አባባ”

“ አስቲ ልጁን ጥሪውና እንየው “ አሉ ! ወንድምና እህቶቿ ተበሳጩ

“እንዴት አንድ ዱርየ ላናግር ይላሉ አባባ “ አሏቸው

" እንኳን ፊት ሰጥተውት ልጁ አይናውጣ ነገር ነው አባባ " አለች የዙቤዳ እህት ! ( ሚሊየን ጊዜ ስለአይናፋርነቴ ነግራኛለችኮ በፊት ፀሃይ ስንሞቅ ዛሬ ተጣላንና .....ግዴለም )

" ቢሆንስ እንየው ማለት ምን ጉዳት አለው እኔም እናታችሁም እናናግረውና የምንወስነውን እንወስናለን " ብለው ቆጣ አሉ ! ልጆቹም ደንገጥ ብለው ዝም አሉ

"ግን አባባ እስከዛሬ እንዴት አላወቁትም ቄራ ሱቃችን ጎን ተቀጥሮ የሚሰራው ልጅ እኮ ነው " አለች ዘምዘም የምትባለው ሁለተኛዋ ልጅ ... ጋሽ ጀማል አሰቡ አሰቡና " አሃ ይሄ ቀይ መኪና የሚይዘው ልጅ ነው " ብለው ጠየቁ (ቀይ መኪና የሚይዘው አሰሪየ ነው )

"ኧረ አባባ እሱ እንኳን መኪና ሊይዝ ለእግሩም ደህና ጫማ የለውም የሆነ አንጀት የራቀው ላንጤሳ ነገር ነው " አለች ዘሃራ

"አንች እንዲህ አይባልም ...አዱኒያ ተአላህ ዘንዳ ነው የምን ትቢት ነው " አሉ የዙቤዳ እናት በቁጣ ! ዘሃራ ደንግጣ ዝም አለች ! እች ጉረኛ ! የዘሃራ ጉራ ልክ የለውም ትእቢቷም በጓደኞቿ ሁሉ የታወቀ ነው ! ስለሁሉም ነገር ከእኔ በላይ አዋቂ የለም የምትል ልጅ ነበረች! እኔንማ ጥምድ አድርጋ ነው የያዘችኝ ! ሴት ልጅ ጉረኛ ስትሆን እንዴት ያስጠላል ! ባይሆን ኩሩ ስትሆን ይሻላል!

የሆነ ሁኖ የዙቤዳ አባት ሊያናገሩኝ ወስነው እንድጠራ አዘዙ!! ዙቤዳም ጠራችኝ አባቷ ሊያምኑ መንገድ መጀመራቸውን ገምታ ነበር ! ታዲያ ቀድማ መከረችኝ "አብርሽ እቤት ስትገባ ጫማህን አውልቅ"

"እሽ"

" ደግሞ ማስቲካ በአፍህ እንዳትይዝ አባባ ማስቲካ የሚያላምጥ ሰው አይወዱም"

"እሽ" ብየ በአፌ የያዝኩትን ማስቲካ ልተፋው ስል

"ማን አሁን አለህ እቤት ስደርስ ነው ያልኩህ " አለችና ሳቀች ....እኔ አልሳኩም ተጨናንቄ ነበር ! ማስቲካየን ወደአፌ መልሽ ምክሯን ማድመጥ ጀመርኩ !

" ደግሞ አብርሽየ ብዙ እንዳታወራ (በእኔ ለምደህ እንዳትቀባጥር የኔ ማር ፈገግ አለች ) እ .....ሌላው ነገር .......አዎ ነገር ለማለሳለስ ብለህ አንድም ነገር እንዳትዋሽ የሆነውን የተሰማህን ነገር ብቻ ተናገር ...በተረፈ በጣም ስለምኮራብህ እና ምንም ነገር ቢፈጠር እኔ ስለማፈቅርህ እንዳትፈራ የኔ ቆንጆ እሽ አብርሽየ "

"እሽ"

ጉንጩን ስማኝ "እሽ እሽ ስትል አሳዘንከኝየኔ ሚስኪን " አለችና ወደቤታቸው መንገድ ጀመርን በዙቤዳ ሙጥቅላ መኪና !

በቃ ልቤን ሞልታ ሳሎናቸው ውስጥ ወደቆመው ችሎት ላከችኝ ! ቤታቸው ስደርስ ተንሸራታቹ በር እንደባቡር እየተንተተ ተከፈተ ...የመቃብሬ ድንጋይ የተከፈተ ነበር የመሰለኝ ልቤ ይፈራገጣል ! ዙቤዳ ነበረች ይዛኝ የሄደችው ! ወደግቢው ስገባ ደነገጥሉ እንዲህ ያምራል ብየ አላሰብኩም ነበር ጀነት ! እንዴት ደስ ይላል ! እዚህ ግቢ አድጎ እንዴት ሰላማዊ አለመሆን ይቻላል ! ዘሃራ ሌላ ቦታ መሆን አለበት ያደገችው እች ነገረኛ ! አሁን ትኖር ይሆን ?

የሳሎኑ በር ሲከፈት አስፈሪው ምንጣፍ አዳራሽ ከሚያክል በር ጋር ጠበቀኝ ... እናትና አበቷ ምችት ብሏቸው ከዛም በፊት ከዛም በኋላ አይቸው የማላውቀው "አረቢያን መጅሊስ" ላይ ተቀምጠዋል ጫማየን በር ላይ ላወልቅ ሳጎነብስ በአፍጢሜ ልደፋ ነበር ሳላስነቃ ራሴን ተቆጣጥሬ አወለኩ ! ፈርቸ ነበር በጣም ፈርቸ ነበር !

በዙቤዳ መሪነት ኳስ ሜዳ በሚያክለው ምቹ ምንጣፍ ላይ እየተራመድኩ አባትና እናቷ ፊት ቆምኩ ! በፈገግታ ተቀበሉኝ በአክብሮት ጎንበስ ብየ በሁለት እጀ አባቷን ጨበጥኳቸው እሳቸው ግን የቀኝ እጀን መዳፍ ወደራሳቸው

ሳብ አድርገው አይበሉባየን ሳሙኝና እንደተጨባበጥን የሳቸውን መልሰው ወደኔ አስጠጉ እጃቸውን ሳምኩ መልሰው ሳሙኝ መልሸ ሳምኳቸው ...መልሰው ሳሙኝ (ኧረ ስንሳሳም መዋላችን ነው ) ተዘያየርን ! እናቷም ጋር በተመሳሳይ ተዘያየርን በእድሜ ቢገፉም በጣም ቆንጆ ሴትዮ ነበሩ ! እንዲሁ የእናቷ ቀልብ እንደወደደኝ ትከሻየ ነገረኝ !

"ተቀመጥ ልጄ " አሉኝ አባቷ ...ፊታቸው ላይ ምንም ነገር ማንበብ አልቻልኩም ክፉ የለ ደግ ዝም ያለ ፊት ! ዞር ብየ ዙሪያውን ተመለከትኩ የወንበር ዘር በቤቱ ውስጥ የለም ...."የት ነው የምቀመጠው ?" እያልኩ ሳስብ የእኔ መሪ ኮከብ ደረሰችልኝ ... እዚህ ጋር ብላ ከወላጆቿ ፊት ለፊት ጥግ ይዞ ወደተጋደመው አረቢያን መጅሊስ መራችኝ ! ተቀመጥኩ

....አባትና እናት በዛ በኩል አብርሃም ብቻውን በዚህ ተፋጠጥኩ ! ፊት ለፊት ....በግንባር ! ዙቤዳ አባቷ ጎን ተቀመጠችና ፈገግ አለችልኝ ....ልቤ በድፍረት ተሞላ ሚሊየን ታንከኛ ሚሊየን መድፈኛ ጦር በደጀንነት የቆመልኝ ሜጀር ጀኔራል አብርሃም ! ....ተዋጊ ጀቶቸ ጠላቴን ሊያደባዩ ከላየ የሚያንዣብቡልኝ ልበሙሉ ጦር የሆንኩ ያህል ተሰማኝ ....ዙቤዳ የኔ ፍቅር የኔ የድፍረት ክብሪት በጀግንነት ልቤን የምትለኩሳት እሳት ከፊቴ ናት አይኖቿ በለው እንዳትፈራ ይሉኛል ! ዘራፍ !

እንደው ዘራፌዋ ...

እንደው ዘራፌዋ

ሰላም እወዳለሁ

ዘራፍም አልጠላ

የርቀ ሰላም ፍሬ

የፍቅር መሃላ !

እያልኩ በልቤ ስሸልል " ስራ ደግ ነው " አሉኝ የዙቤዳ አባት ረጋ ብለው !

" እግዚአብሄር ይመስገን " አልኩ ! ጉድ ፈላ !! .................... ረስቸው ማስቲካውን አፌ ውስጥ ይዤው ነበር የገባሁት !

## ክፍል 2

"ስምህ ማነውሳ" አሉኝ የዙቤዳ አባት (ተጀመረ)

"አብርሃም " አልኩ እንደሳቸው ረጋ ለማለት እየሞከርኩ

" ያው በኛ ኢብራሂም ማለት ነው " አሉ የዙቤዳ እናት .....ነግሪያችሁ የለ ....እች ቆንጆ ሴትዮ ቀልባቸው ወዶኛል! ዙቤዳ ፈገግ አለች አሪፍ ነው ማለት ነው !

" ቤተሰቦችህ እዚሁ አገር ናቸው "

"አዎ "

" ምን ይሰራሉሳ " አባባ በየንግግራቸው መጨረሻ "ሳ" ይጨምራሉ ሳ ምን ይሆን

"አባቴ የሁለተኛ ክፍል ሂሳብ አስተማሪ ነው እናቴ ስራ የላትም ...የቤት እመቤት"

"አንተስ ምን እየሰራህ ነው "

" እኔ ያው ተቀጥሬ ሱቅ ውስጥ እሰራለሁ ...የማታ በዲፕሎማ አካውንቲንግ እየተማርኩ ነው " ዜድየን አየኋት ፈገግ አለችልኝ ! ደጀናችን በፈገግታ መድፍ ፍርሃታችንን እያደባየው ነው ቡምመምምምም ወደፊት ! የዙቤዳ ፈገግታ በሂወት ዘመን ውድ ነገር ብቻ በሚቀመጡበት የአይምሮ ካዝና ውስጥ በጥንቃቄ የሚቀመጥ ቅርስ ነው !!

"ዲፕሎማ " አሉ አባቷ የጥያቄም የመገረምም አልነበረም እንዲሁ ነገሩን የሆነ ቦታ የሚያውቁትና የሚያውቁበት የጠፋባቸው አይነት ነበር !

የዜድ እናት ቀደም ብለው "ዲፕሎማ ማለት እንደአብዱ ያለ ትምርት ነው ...ቀስ ብሎ ደሞ ድግሪ ይጭናል ... ከበረታም ሌላውን ነገር ሁሉ ይጭናል ገና ልጅ ነው..... አይደለም እንዴ አየዋ ? " አሉኝ ....ኸረ እንዴት አይነት መለአክ የሆኑ ምራት ገጠሙኝ እናተ ...ዜድ አፏን አፍና በሳቅ ትንፈራፈራለች ! ልስቅ ፈልጌ ነበር ግን በየት አባቴ "ግንባር ላይ ተሰልፎ መሳቅ ያስመታል " ይሉ ነበር የምሰራበት ሱቅ ዘበኛ መቶ አለቃ ለገሰ !

"ልክ ነው እማማ " አልኩ

"እናቴዋ....." እ ማ ማ " አባባሉ ልክ እንደአብዱ " አሉና ባለቤታቸውን ተመለከቷቸው ...በሴትዮዋ ጣልቃ ገብነት የተደሰቱ አይመስሉም ! ቢሆንም እራሳቸውን በአወንታ ነቀነቁላቸው ! በጣም ...እጅግ በጣም የገረመኝ ነገር ጋሽ ጀማል ለዙቤዳ እናት (ለባለቤታቸው) ያላቸው ክብር ! በፊት ዙቤዳ ስትነግረኝ አላምንም ነበር ! ግን በአይኔ ተመልክቶ አረጋገጥኩ የዙቤዳ እናት በባላቸው ፊት ትልቅ ግርማ ሞገስ ነበራቸው !

በዚች ቅፅበት አይኔ ዙቤዳ እግሮች ላይ አረፈ በቃ ተበላሁላችሁ !! ለምን እደብቃችኋለሁ እኔ ከሴት ልጅ ውበት ቀልቤን የሚያስተኝ ነገር ቢኖር የእግር ውበት ነው ! ልክፍት አለብኝ ቆንጆ የሴት እግር ካየሁ አብሾ ነገር ይነሳብኛል! አቤየየየየየየየየት የሴት እግር...ቆንጆ የሴት እግር ማየት ስወድ !

ብዙወቹ እንዲህ አይነቱን ወንድ "ልክስክስ" ይሉታል... !! ድፍን የአለም ህዝብ ከኋላየ እየተከተለ በአለም ቋንቋወች ሁሉ "...አብርሃም ልክስክስ ለከስካሳ ውሻ " እያለኝ ቢጮህ እንኳን እግር ከማየት ቆንጆ የሴት ልጅ እግር ከማድነቅ ወደኋላ አልልም ! እኔ ይሄን ስድብ በፀጋ ተቀብየ እግር ማየቴን መቸም አላቆምም!የሴት ልጅ እግር የውበት ጥጌ ነው ! ለሰርጌ ቀን አይበለውና እግሯ የሚያምር ግን አንገቷ የተቆረጠ ሴት ጎኔ አምጥተው ሚስትህ ናት ቢሉኝ "በደስታ ይሁን በሃዘን ....." ብየ ከመፈረም አልመለስም ! እንዲህ የምንሰፈሰፍለት የምማልልለት የምልከሰከስለት ልክስክስከስ የምልለት የሴት ልጅ እግር እንደኔ እንደኔ በሁለት ትላልቅ ክፍል ይከፈላል

1ኛ. የአለም ሴቶች እግር ሁሉ በአጠቃላይ ማለት ነው !

2ኛ. የዙቤዳ እግር ! በቃ እኔን የሚያልከሰክሰኝ በምኞት አፌን የሚያስከፍተኝ ሳመው ሳመው የሚለኝ ይሄ ሁለተኛው እግር ነው ! እናም ድንገት ከቀሚሷ ወጣ ብሎ ፍም የመሰለ ተረከዟ የእጅ ጣት የመሳሰሉ ጣቶቿ ውሃ የመሰሉ (መስተዋትም ይመስሉኛል) ጥፍሮቿ ምንም ቀለም ሳይቀቡ ደግሞ የቁርጭምጭሚት አጥንቶቿ ብይ ብይ መስለው ጠቆር ያለው አረቢያን መጅሊስ ላይ እንደእሳት ሲንቀለቀሉ ሳይ ቀልቤን ሳትኩ ...ውሻ ሆንኩ ተንደርድሬ ሂጀ እግሮቿን ብስማቸው ደስታየ የሆነ ነገር ሂድ ሂድ እያለ ይገፋኛል! ይሄ ይዞ ሚች ሊያስበላኝ !

"እ" አሉኝ የዜድ አባት

"እ" አልኳቸው እኔም ...የተናገሩትን ባለመስማቴ አፍሬም ደንግጬም ነበር (ታዲያ ምን ላድርግ እኔ የብቸኝነት ፣የከህደት፣ የውሸት፣ የማስመሰል ፣ የጥቅም ማሳደድ እና የዝሙት ቆፈን በሚያቆራምደው ከተማ የፍቅር እሳታቸውን ወልደው )

"እናቴዋ ...ቀልቡን ወሰድ ያደርገዋል አንዳንዴ እንደአብዱ " አሉ የዜድ እናት ( ጎበዝ ኸረ ይሄ አብዱ ማነው ? ) ዙቤዳ ቡፍ ብላ ሳቀች ! እናቷም ሰውነታቸው እስኪረግፍ ሳቁ አባቷ ግን ኮስተር እንዳሉ ፂማቸውን በመዳፋቸው እየዳሰሱ ዝም ብለው ቆዩ በዝምታው ውስጥ ድምፃቸው የሚያማምረ ህፃናት በስርቅርቅ ድምፃቸው ቁርአን ይቀራሉ ለምን እንደሆነ ባላውቅም የህፃናቱ ድምፅ የአባቷ ዝምታ የዙቤዳ አቀርቅራ በከሪሟ መጫወት

ተዳምሮ ዜድን ላጣት ዜድ ጋር ልንለያይ ሴኮንዶች የቀሩ መሰለኝ እንባየ ሁሉ ይታገለኝ ጀመረ እልህ ውስጤ ተንተገተገ !

ድንገት ዝምታውን ሰብረው “ ዘምዘም “ ብለው ተጣሩ የዜድ እናት

“አቤት እማማ “ ብላ የዙቤዳ እህት ከውስጠኛው ክፍል የግቢ በር የሚያከለውን በጌጥ የተሽቆጠቆጠ ባለሁለት ተከፋች የጣውላ በር ከፍታ ገባች ! ዘምዘም ቁመቷ የትየለሌ ነው .... በዛ ቁመት ላይ ሙልት ያለ ሰውነቷ ተጨምሮበት ትከብዳለች አይገልፀውም ! ሳሎኑ ውስጥ መጥታ ስትቆም የሆነ ረዥም ማማ ነገር የቆመ ነበር የሚመስለው አንጋጥጬ አየኋት ! ኮስተር አለችብኝ ...

አሁን የመረረው ባላጋራ መጣ አልኩ በሆዴ በተቻለኝ መጠን ዘምዘምን ላለማየት ወደዙቤዳ ዞርኩ ፈ ገ ግ አለችልኝ ዜድ ! ታምኑኛላችሁ ... ወደዘምዘም በድፍረት ዞርኩ ቡትሌ አክላ ታየችኝ አስማተኛው የዜድ ፈገግታ እንኳን አንዷት ሴት ኪሊማንጃሮን በፊቴ ጠጠር ያሳክለዋል ! ከፍቅር የሚገዝፍ ነገር የለማ !!

“ምሳ አልደረሰም እንዴ ...እንግዳ ጠርታችሁ በራብ ልትገሉት ነው እንዴ “ አሉ ዘምዘም ወደውስጥ ተመልሳ ገባች ! እኛም በዝምታችን እንደፀናን በሩ ተበረገደ እና የምግብ መፎክር ያነገቱ ሰላማዊ ሰልፈኞች ገቡ አራት እህትና አንዷት ሰራተኛ !! ዘሃራም ከሰልፈኞቹ አንዷ ነበረች...የያዘችውን ሰሃን በትኩረት ተመለከትኩት “እሷ ከያዘችው ሰሃን አልበላም” አልኩ ለራሴ ! ሰራተኛዋ ምንጣፉ መሃል ላይ አንድ ሰፊ ክብ ላስቲክ አነጠፈች ....ከዛ የምግብ አይነት በሚያማምር ሰፋፊ የሸክላ ሰሃኖች ላሰቲኩ ላይ ዙሪያውን የተደረደረሩትን ነጫጭ ሰሃኖች በክብ ተደርድረው ስመለከት በምህዋራቸው የሚሽከረከሩ ፕላኔቶች ስእል ትዝ አለኝ !

ከዛ ሰልፈኞቹ ወጡና ሁለት እህቶቿ ተመልሰው ሌላ ሰሃን ይዘው ተመለሱ ... ብስኩቱ ጣፋጩ ስሙን የማላውቀው ነገራ ነገር ሁሉ !ባይነት ተደረደረ አንድ ነገር ውስጤን በሃዘን ሞላው ! ዙቤዳ ሱቅ ፀሃይ ልንሞቅ ስንቀመጥ የምጋብዛትን ቦንቦሊኖ ለመብላት ቁርስ ሳትበላ ትመጣ እንደነበር አስታወስኩ....

ይታያችሁ ይሄን ማእድ ስለፍቅር ረግጣ “አብርሽ ኧረ ርቦኛል ቦንቦሊኖ ግዛልኝ “ ትላለች ፀሃያችን እየሞቅን ፊት ለፊታችን ካለች ሻይ ቤት ቦንቦሊኖ አዘን እየተጎራረስን በሻይ እንበላለን ! እንደውም አንድ ጊዜ አረፋ በአል ሁኖ የነዙቤዳ ሱቅ ዝግ ነበር እኔ ተቀጥሬ የምሰራበት ሱቅ ደግሞ አልተዘጋም ዙቤዳ ከቤቷ ሹልክ ብላ መጥታ በበአሉ ቀን እዛች ሻይ ቤት ሄድንና ቦንቦሊኖ በሻይ በላን ! ለረመዳን ሙሉ ቀን ዙቤዳ ስለማትበላ እኔም ሳልበላ የምውልባቸው ቀናት ይበዙ ነበር !!

የዙቤዳ እናት “በል ና ወዲህ ዙቤዳ ነቅነቅ በይ እንጅ መታጠቢያ ቤቱን አሳይው “ አሉ ዙቤዳ እየመራች በሚያምረው በር አልፋ ወደመታጠቢያው ወሰደችኝ ...አንዳንድ ነገሮች አሉ በአክብሮት ሲደረጉ ስድብ የሚሆኑ ...የነዙቤዳ መታጠሚያ ቤት ስፋት የአባቴን ምኝታ ቤት ያክላል የመታጠቢያ ሸክላወቹ ንጣት የቤቱ አስደሳች ጠረን አፍ አውጥቶ የሰደበኝ መሰለኝ “አንተ አመዳም ደሃ ልካችንን እየው” የሚለኝ መሰለኝ !

ዙቤዳ ፈዝዥ መቆሜን ስታይ “ ታጠብ አለችኝና ዞር ብላ ወደኋላዋ ተመለከታ ማንም አለመኖሩን ካረጋገጠች በኋላ ...ጉንጬን ሳም አደረገችኝ ! ከንፈሯ ይሞቃል ! የሆነ ርጥበቱ ጉንጬ ላይ የቀረ መሰለኝ ! ስትስመኝ ድንጋጤው ይሁን ንዝረቱ አስበረገገኝ ...”ብቻችንን ከሆንን አያስችለኝም ቶሎ ውጣ” አለችኝ እየሳቀች እና ራሷ እጇን መታጠብ ጀመረች ...በመስተዋቱ ውስጥ አይኖቿ አፍጥጠውብኝ ነበር የመታጠቢያ ቤቱ ውበት ውበቷን አጉልቶት ነው መሰል ዙቤዳ በጣም አማረችብኝ !! ለዜች ልጅ እማ “አንድ ሰውና አንድ ትይት እስኪቀር ....” ታጥበን ወጣን !

ወደሳሎን ስንመለስ የዙቤዳ እናት “ነወር “ አሉኝ አባቷ ግን አሁንም ፂማቸውን እያሻሹ ዝም ብለው ተቀምጠዋል ... እንደውም ከቅድሙ በላይ ፊታቸው ተቀያይሮ ቁጣ ነበር ከግንባራቸው የሚስፈነጠረው ! እንዴት ይጨንቃሉ ! ዘሃራ ጭልፋ ይዛ ስትገባ እኛ ታጥበን ስንገባ አንድ ሆነ በግርምት እግሬን ተመለከተችኝ አይኗን ተከትየ ወደእግሬ ስመለከት ወደመታጠቢያ ቤት ስገባ ያደረኩት የዙቤዳን ሰንደል ጫማ ነበር ! ያውም ብዙ ጊዜ

ሎዱ ስታደርግ የምትጫማውን ! እሾህ ! አይኗ የማያየው ነገር የለም ! እኔ ራሴ ጫማ ሳድርግ በእግሬ ልሁን ትዝ ያለኝ አሁን ነው !

አንዷት ትንሽ ትራስ ነገር ከተሰደረው ምግብ ፊት ዙቤዳ አመቻቸችልኝና ተቀመጥኩ ... አባቷ ከምግቡ ወዲያ እኔ ወዲህ ! ምግብን ድንበር አድርገን የተፋጠጥን ጠላቶች ! መብላት አልቻልኩም አባቷ አይኔን ላለማየት ሲሽሹ ምግቡ ዘጋኝ ! በቤታቸው ምግብ አቅርበው ፊታቸውን ሲያጠቁሩብኝ ለልመና የመጣሁ እስኪመስለኝ አፈርኩ ! ዙቤዳ ገብቷታል... ምንም ነገር ሳትፈራ ሰሃኔ ላይ እንጀራና ንጣቱ የሚገርም ነጭ ቂጣ አድርጋ ወጥ ጨለፈችልኝ ብዙ አይነት ቀለም ካላቸው ሩዞች ጨመረችልኝ ! "ብላ አብርሽ" አለችኝ የአባቷ ማኩረፍ አስከፍቷታል !

ከእኔ የበለጠ ማፈሯን የጉንጮቿ ቅላት ይመስክራል ! የዜድ እናት በጋሽ ጀማል ኩርፊያ ግራ ተጋብተው አንዴ እኔን አንዴ ባላቸውን እየተመለከቱ "ብላ አይዞህ " ይሉኛል ! ጭራሽ የዜድ አባት ሁለት ጊዜ ጎርሰው ሰሃናቸውን አስቀመጡና ሶፍት አንስተው እጃቸውን መጠራረግ ጀመሩ ! እኔም ከዛ በላይ መብላት አልቻልኩም ! እናቷም ብላ ብለው ማስቸገር አልፈለጉም ገብቷቸዋል ! ወጥ የነካ ጣታቸውን አንከርፍፈው ምንጣፍ ምንጣፉን እያዩ ተከዙ .....ጋሽ ጀማል ከተቀመጡበት ተነሱና ክፉም ደግም ሳይናገሩ ወደውጭ ወጡ ትንሽ ቆይተው ዙቤዳን ጠሯት ....በሂወቴ ከሰማኋቸው ሰቆቃወች ሁሉ የከፋው ሰቆቃ ከበረንዳው መጣ ....." አንች ባለጌ አሳዳጊ የበደለሽ ....እንዴት ወንድ እየጎተትሽ እቤቴ ድረስ ....."

"አባባ አንቱ አይደለሁ ጥሪው ያልኩኝ ኸረ አላህን ፍሩ "

"ሰው መስሎኝ ነበራ ...ደግሞ አብረሽ ማድ ላይ ታቀርቢኛለሽ የማንም ....." ዝምታ ! መኪናቸው ሲነሳ ሰማሁ በቃ ሔዱ !! "ያውልህ ቤቱ አንተን ከማይ " ያሉኝ መሰለኝ ! የዙቤዳ እናት እንዲህ አሉ ያፅናኑኝ መስሏቸው "ስራውም ግብሩም እያበሳጨው አንዳንዴ እንዲህ ይሆናል ላንተም ብቻ አይደለም አየዋ አይዞህ "

እማማን አመስግኘ ወጣሁ ...በረንዳ ላይ ዘሃራና እህቶቿ ተቀምጠዋል የታፈነ ሳቃቸው ፊታቸው ላይ ነበረ ! የሴት መአት ጅሪ ! ቁመት ብቻ መልክ ብቻ ቅላት ብቻ ባዶ ቆነጃጅቶች ፍቅር አይገባቸው ሂወት አይገባቸው ዘለው ትዳር ውስጥ ይዘፈቃሉ ለነሱ ይሄ ነው ክብር ! ዙቤዳ ሊፈነዳ የሚታገላት እንባዋን እየታገለች ፊቷ ላይ ሊገልፁት የማይችሉት ስቃይ እየታየባት እህቶቿን ላለማየት አንገቷን አቀርቅራ ወደመኪናዋ መራችኝ ! በእግሬ መሄድ እንደምፈልግ ነገርኳት አላንገራገረችም ! "እሽ አብርሽ" ብላኝ በር ድረስ ሸኘችኝ ! እንደወትሮው አንድ ላይ ሁነን ሃዘናችንን ከማሸነፍ ይልቅ ለየብቻችን ሽንፈታችንን ልንወጣው ፈልገናል ! አይዟችሁ ባይ በሌለበት ! ! ዜድ ቶሎ መኝታ ቤቷ መግባት አልቅሳ ሊወጣላት ስቃዩን መዋረዷን በእንባ ልትሸኘው ቸኩላለች !

ከትልቁ ግቢ እንደወጣሁ ከት ብየ ሳኩ ....እግዜር ይጠብቀኝ እንጅ እብደት ሳይጀምረኝ አልቀረም ! ካበድኩ አይቀር መንገድ ላይ ከምዋረድ እዛች መከረኛ እናቴ ጋር ሂጀ ልበድ ብየ እርምጃየን አፈጠንኩት አይምሮየ ግን በሚያስፈራ ድምፅ ቁጣውን እያስገመገመ ነበር !!

አንዳንዴ መገፋታችን ሳይሆን የተገፋንበት ሁኔታና ቦታ ያመናል ! እኒህ ሰውየ ህዝብ የመሰከረላቸው ደግ ጨዋ ሰው ነበሩ... ደሃውን ሁሉ በሬ ጥለው የሚያበሉ ! የተጣላን የሚያስታርቁ ! እኔ ...አንድ እኔ ግን ፍቅርን ተርቤ ቤታቸው ስሄድ ገፍተውኛል ! ...ፍቅርን ለመቀበል ደግነት ብቻውን በቂ አይደለም ! የተጣላን ማስታረቅ በፍቅር ከራስ ጋር እንደመታረቅ አይከብድም ! በሬ አርደው የከተማውን ሁሉ ደሃ የሚያበሉት እኒህ ሰው የልጃቸውን ፍቅር ለተራብ አንድ ደሃ ፍርዳቸው ተዛብቷል !እኔን ብቻ አይደለም ልጃቸውንም በፍቅር ርሃብ ገድለዋታል !

((((((እግዚያብሔርም አብረሃምን እንዲህ አለው ያንተን ዶሮ ያንተን በግ ያንተን "በሬ" አልፈልግልህም ካከበርከኝ ልጅህን ሰዋልኝ ... አብርሃምም ልጁን ሊሰዋ በእግዚአብሔር ፊት አጋደመው " ለፍቅር የሚሰዋው ለካ ፍቅር የሚሰማው ሰው ብቻ ነበር !! ስለፍቅር ልጁን የሚሰዋ ሲጠፋ የሰው ልጅ ልብ ይንኮታኮታል ....ትዳር ! ትዳር አብሮ መኖር ነው ያለው ማነው የግራ አጥንትን ነጥሎ ሌላ ጎን ላይ ሊገጥሙ ቢሞክሩ ወይ አጥንቱን መስበር አልያም እድሜ ልኩን እንደተዟዟረ ጫማ የተወናከረ በኩርፊያ ጉንጩን የነፋ ትዳር ተብየ የሁለት ሰው አሰልች

ስብሰባ መጥራት ነው ትርፉ ! የልጆቻቸውን ፍቅር ቀምተው እየገደሉ "የልጅልጅ አየን " የሚሉ ስግብግብ ራስ ወዳድ አያቶች ስንቱን ትዳር እንደሻገተ ቲማቲም አቦሽርቀውታል ! ያቻትላቸው ልጃቸው ስግብግብ ሁሉ !

ብርን ታች ላሉ ሰወች መስጠት ደግነት ብቻ በቂው ነው ... እራስን ዝቅ አድርጎ ከታችኞቹ ጋር መዋል ግን ከባዱን የፍቅር ቀንበር መሸከምን ይጠይቃል !! ማነው በፍቅር ለተጠሙ ደራሽ ...የማን ህንፃ የማን ቪላ ነው የጥላቻ ፀሃይ የመገፋት ሃሩር ላደረቀው ሚስኪን የፍቅር ጥላውን የሚጥል ! እኔ ለዙቤዳ ከፉ ነኝ ? ....ፈጣሪ ይመለከታል ዙቤዳን ከቤተሰቦቿ የበለጠ ካልተንከባከብኳት ! እንደወንድ ይዣት ለመጋደም አልተጣደፍኩም ...አዎ ዙቤዳ ከልክላኝ አልነበረም ተቃቅፈን ባዶ ቤት ማንም በሌለበት "አብርሽ የፈለከውን ጠይቀኝ " ስትለኝ ሰማይና ምድር ሰምተዋል ..... ነገዋን እንዳላበላሽ የናቁኝኝ ቤተሰቦቿን አክብሬ ጫፏን ሳልነካት ከስሜቴ ይልቅ የዙቤዳ ክብር የገዘፈብኝ አፍቃሪዋ ነበርኩ !

በዛች በተከራየኋት አንዲት ክፍል ቤት ተንበርክኬ እግሯን ሳጥባት ከሷ ምንም ፈልጌ አልነበረም ስለማከብራት ስለምወዳት ብቻ ! ኤጭ ሃብታም ለልጁ ሊያወርስ የሚችለው ነገር የለም ማለት ነው ? ! ቢያንስ በዚህ በዚህ ምክንያት ልጃችንን እንድታገባት አንፈልግም ቢሉኝ ምናለበት ? የልጃቸው ልብ እንዳይሰበር የእኔን ልብ እንዲህ ማንኮታኮት ነበር አላማቸው ? ቤታቸው ጠርተው ማዋረድ ? ባለጌ ! ከነሚያበሉት በሬ ገደል ይግቡ ! ደሞ ከሳቸው ብሎ አንቱ ! ሰው መስሎኝ ነበር ይላሉ ...ሱቃቸው ሂደን ስንገዛቸው ነው ሰው የምንመስላቸው

ዙቤዳን ላገባትና ቤተሰቦቿን ጉዳያችሁ ልንላቸው እንችል ነበር ! ዙቤዳም አሁን ነይ ብላት ያ ትልቅ አጥር ሳያግዳት ከድምፄ ቀድማ አጠገቤ ነበረች ...ግን ....ዜድ አደገኛ በሽታ ነበረባት ድንገት ደርሶ የሚጥላት ቤተሰቦቿ ብዙ ብር እየከፈሉ ከውጭ የሚገዙት መድሃኒት አለ በየጊዜው የምትወስደው ! የእኔ ቆንጆ ስትሞት ከማይ እኔ እድሜየን ሙሉ ፍቅሯ የተቀበረብኝ የሬሳ ሳጥን ሁኘ ብኖር እመርጣለሁ ! ዜድ አላለቀሰችም ትክብላ ሳታቋርጥ ፊቴን አየችኝ እፊቷ መቀመጤን በአይኖቿ ብቻ ማረጋገጥ ያቃታት ይመስል በእጆቿ ፊቴን ዳሰሰችኝ እንደሃውልት ዝም ብየ በለስላሳ እጆቿ ተዳሰስኩ !

ፊቷ እንደወረቀት ገርጥቶ ነበር ! ቀስ ብላ ስትነሳ መቆም አቅቷት ተንገዳገደች እጆቿን ይዠ ደገፍኳት ! እስከምትረጋጋ አይኖቿን ጨፍና ቆየች ! ዝም ተባብለን እቤቷ ድረስ ሸኘኋት በእግራችን ! እኔ ስቆም ዜድ አልቆመችም ! ዝም ብላ ዙራ ሳታየኝ ወደግቢው በር ተጓዘች .... የመቃብሩ በር ተከፈተ መጀመሪያ እግሯ ከዛ ሌላኛው እግሯ ገባ ቀሚሷ ቀስ እያለ ወደውስጥ ገባ ...ግቢው ተዘጋ!

*** *** ****

ስራ ለቅቄ ከፍለ ሃገር ሄድኩ ሃረር ! እዛም ኑሮ አልተመቸኝም ! ሰው ኑሮ የማይመቸው አካባቢው ስለማይመቸው አይደለም ውስጡ የማይመቸውነገር ሲቀመጥ እንጅ ! ግን በራሴ ላይ የፈረድኩትን አመክሮ የሌለው እስራት ....የዙቤዳንም ሂወት ያለመበጥበጥ መሃላ ላለማፍረስ ሶስት አመታት ቆየሁ ! ስልክ የለኝም ለእናቴ በመስመር ስልክ እደውላለሁ ! ለዙቤዳ ላለመደወል ሁሉንም አቅሜን ተጠቅሚያለሁ ! ድምፀዋን ከሰማሁ በቀጣዩ ቀን አዲስ አበባ ነኝና !!

ከሶስት አመት በኋላ አዲስ አበባ ስመለስ ዙቤዳ ማግባቷን እና አሁንም እዛው ሱቅ እንደምትሰራ መንታ ልጆች ወልዳ አንደኛው ልጅ እንደሞተባት ሰማሁ ! ባለቤቷ ሃብታም ነው አሉ ብዙውን ጊዜ ውጭ ስለሚኖር ዙቤዳ ቤተሰቦቿ ጋር ነው የምትኖረው ! እንደው ዝም ብየ ሳስብ ቤተሰቦቿ ደስ እንዲላቸው ያገባች ግን ደግሞ ባሏ ዘጠገቧ እንዳይኖር ሆነ ብላ ይህን ሰው ያገባቸው መሰለኝ !

አንድ ቀን ታዲያ አረፋ በአል ሁኖ ህዝበ ሙስሊሙ አምሮና ተውቦ ወደሶላት ሲተም አንድ ነገር ውስጤን ገፋፍቶት እግሬ ወደቁራ ተጓዘ ....እኔና ዜድ ውብ የፍቅር ጊዜያት ያሳለፍንበት ሰፈር ስደርስ የሁለታችንም ሱቆች እንደነበሩ ተቆልፈው አገኘኋቸው ገና ጠዋት ነበር ....ሻይ ቤቷ ክፍት ነበረች ....ቀጥ ብየ ገባሁና እንደፅጌሬዳ አበባ ሽታ የሻይ ቤቷን መአዛ በአፍንጫየ ስስበው ዜድን ያገኘኋት ያህል ውስጤ በአንዳች እርካታ ተሞላ !

“ምን ልታዘዝ” አለችኝ አስተናጋጇ

“ቦ ን ቦ ሊ ኖ በሻ ይ “ አልኳት ክፍሏን በአይኔ እየተመለከትኩ ቦንቦሊኖየ መጣልኝ ...በፍቅር ገመጥኩት ለምን እንደሆነ ባይገባኝም አቅለሸለሸኝ ....ምንም ሰላም አልሰማ አለኝ ! ተረበሽኩ ...አንዱ አስተናጋጅ ጮክ ብሎ እንዲህ አለ “ አንድ ቦንቦሊኖ በሻይ ዙቤዳ ሱቅ “

አስተናጋጇ በግርምት እንዲህ አለችው “ዛሬ አረፋ አይደል እነዴ ዙቤዳ እንዴት ገባች “

“እንጃ ምን የሷ ነገር ነካ ያደርጋታል “ አለ አስተናጋጁ ...ዙቤዳን እኮ ነው አይገርምም ? ....ነካ ያደርጋታል ?

ሂሳቤን ከፍየ ወጣሁ ... እንደምንም አይኔን ወደዙቤዳ ሱቅ ላኩት ...........ዙቤዳ ጀርባዋን ለመንገዱ ሰጥታ ፀሃይ የምንሞቅበት ቦታ ላይ ተቀምጣለች ፀሃይ የለም ! እንደውም ክረምት ስለሆነ ደመና አንዣቦ ነበር ! ሱቁ በደንብ አልተከፈተም ከሁለቱ ተከፋች በሮች አንዱ ብቻ ነበር ገርበብ ያለው ! ቀስ ብየ ሽቅብ ወደሜክሲኮ በእግሬ መንገዴን ተያያዝኩት !

ስክር እብድ የሚያደርግ ፍቅር ውስጥ የወደቅነው ድንገት ነበር ! ዛሬም የዙቤዳን ስም ሳነሳ ሰውነቴ በሆነ ሃይል ይሞላል ደስታ በመላው አካላቴ እንደዥረት ሲፈስ ይሰማኛል ....ታምኑኛላችሁ ? ከተለያየን ከሶስት አመት በኋላ እንኳን ጠረኗ አጠገቤ ያለች ያህል ይሸተኛል ! ድምፀዋ ይሰማኛል የልብሷ ቱማታ ሳይቀር ይሰማኛል ...

ነፍሰ ጡሮች አማረን እንደሚሉት ዙቤዳ ክፉኛ ታምረኛለች ድምጿ...አይኖቻ ያምሩኛል ! እኔስ የማይወለድ ፍቅር ያውም የጨነገፈ ግን ከውስጥ የማይወጣ ፅንስ ፀንሸ የለ ከነብሰ ጡር ምኑን ተሻልኩት ... ድፍን አገሩ በአንድም በሌላም ብሶት ያረገዘው ብዙ ብሶት ውል የሚልበትም እልፍ አምሮት አለው !!

ፍሬ ፍሬውን

“ሚስተር አብረሃም “

“አቤት “

“ ግባ ግባ ተቀመጥ “ አለኝ አለቃየ ፈገግ ብሎ ! “ይሄ ሰው ቀልቡ ወዶኛል “ ብየ እያሰብኩ ወደቢሮው ገባሁና ምቹው ሶፋ ላይ ተቀመጥኩ ! እዚህ ሶፋ ላይ በተቀመጥኩ ቁጥር የሳሙና አረፋ ላይ ወይም የሆነ ደመና ላይ የተቀመጥኩ ነው የሚመስለኝ ! ታዲያ ሁልጊዜ “እቤቴ የዚህ አይነት ሶፋ ቢኖረኝ በቃ ቁጭ ብየ 999999999999 ገፅ ያለው መፅሃፍ እፅፍ ነበር” እያልኩ አስባለሁ! ምቹ ወንበር እወዳለሁ .... ካፍቴሪያም ይሁን ሆቴል ከምግቡ ይልቅ ምቹ ወንበር ቢኖረው ምርጫየ ነው ! እናቴ ራሷ ልጅ እያለሁ “ አቡቹ ከመቀመጥህ በፊት ይሄን ይሄን ስራ አንተ እንደሆንክ አንዴ እንደአክሱም ሃውልት ከተተከልክ አትንቀሳቀስም “ትለኝ ነበር ! አንዳንዴ ከተተከልክ የሚለውን “ ከተጎለትክ” በሚል ቃል ትተካዋለች !

“እሽ ፈልገሽኝ እንደነበር ሃና ነገረችኝ እ...በሰላም ነው ? “አለኝ ...ሃና ፀሃፊው ናት ! በጣም ቆንጆ ከመሆኗ የተነሳ ፀሃፊ ሳይሆን አለቃ ነው የምትመስለኝ !እዚህ ቢሮ ከስራ አስኪያጁ ሶፋ ቀጥሎ የሃና መልክና ባህሪ ምቾት ይሰጠኛል .... መቸም እሷን የምትመስል ሚስት እቤቴ ብትኖረኝ 99999999999 ጊዜ እስማት ነበር በቀን ማለት ነው! እና ደግሞ ምንም ነገር አልሰራም ነበር ! በቃ ቁጭ ብየ አይናይኗን አይን አይኗን እየተመለከትኩ እስማረጅ እኖር ነበር ... (ላካብደው ብየ ነው )

“ አዎ በሰላም ነው ባለፈው ለስራ ማስኬጃ እንዲገዛልህ ምትፈልገው ነገር ካለ አሳውቀኝ ስላልከኝ ላሳውቅህ ነበር አመጣጤ “ አልኩት በትህትና ! ትህትና አያምርብኝም !

“ኦ.......ኬ አለና እስክርቢቶ አንስቶ መፅሃፍ ቅዱስ የሚመስል ጥቁር ማስታወሻ ደብተሩን ገለጠ ከዛም “እሽ ምን ምን አሰብክ “ አለኝ

“የመጀመሪያው ነገር አንድ የማይሽከረከር የማይንቀሳቀስ ወንበር ለቢሮየ ቢገዛልኝ “

“የማይንቀሳቀስ የማይሽከረከር ወንበር ለቢሮ ? አለና ቀና ብሎ በመነፅሩ አናት ተመለከተኝ

“አዎ” አልኩት

“እሽ” አለ (ከፈለክ ምንቸገረኝ በሚመስል ድምፅ)

“ሌላው የመኪና እጥረት አለ... ያሉት መኪናወች ሁሉ ለእኔ ስራ አይመቹም አንድ ለዚሁ ስራ ተብላ የምትመደብ መኪና ብትገዛ ስራውን ለማፋጠን ይረዳኛል “

“ መ...ኪ....ና “ ብሎ ፃፈና “ሌላስ “ አለኝ

“ ሌላ እንኳን ለጊዜው አያስፈልገኝም “ አርብ ለት ይህን ተነጋግረን ዛሬ የማኔጅመንት አባላቱን ሰበሰበና በተለይ በሚኪናው ግዥ ላይ ጥቅሙንና አስፈላጊነቱን እንዳስረዳ እኔንም ጠራኝ ፡፡ “ያው እንግዲህ መኪና ያስፈለገበትን ምክንያት” ብየ በመጀመር ስለመኪናው አስፈላጊነት አብራራሁ ፡፡ ብዙ ጊዜ የማኔጅመንት አባላት ለምን ደነዝ እንደሚሆኑ አይገባኝም ፡፡ በግል የምታውቁት አሪፍ ሰው ሁሉ ነገር የሚገባው ....የማኔጅመንት አባል ሲሆን ይደነዝዛል፡፡

በጣም የማልወደው የፋይናስ ምናምን ሃላፊ ተንደርድሮ እጁን አወጣ ...አቤት መናገር ሲወድ... መናገር ሱስ የሆነበት ሰው ነው ፡፡ እንደውም መናገር ብቻ ሳይሆን ዝም የሚል ሰው ጤነኛ አይመስለውም፡፡ በቃ ይሄ ነጃሳ ሰውየ ሊነጅሰኝ ነው ብየ ተስፋ ቆረጥኩ ! የዘህ ሰው ስራ የድርጅቱን ገቢና ወጭ ማስላት ክፍያ መፈፀም ምናምን ሳይሆን ግዥ እንዳይፈፀም መከላከል ይመስለኛል ፡፡ አሁንም እችን መኪና እንዳትገዛ ሊከራከር ነው ምናለ በሉኝ ...ቱ !

“ እ....አሁን ባለው ሁኔታ የመኪናው አስፈላጊነት አይታየኝም “ አላልኳችሁም!! “ ደግሞም መኪና ሲባል ምናይነት መኪና ነው ቲወታ አለ ...ኒሳን አለ እ..........ሌላም ብዙ አይነት አለ! ...እ...በመጠንም ቢሆን ደግሞ የቤት መኪና አለ ፣ሚኒባስ አለ ፣ዲኤክስ መኪኖች አሉ፣ ጭነት መኪና አለ፣ ተሳቢ አለ .......” በቃ አያባራም !

ይሄን ሰው ስታዩት እንዴት ያበሳጫል መሰላችሁ ....በሸሚዙ ደረት ኪስ የማይሰካው የእስክርቢቶ አይነት የለም ሰማያዊ ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ እርሳስ ወይነጠጅ እስክርቢቶ ሁሉ ይይዛል ! እስክርቢቶወቹ ከዳናቸው ከሸሚዙ ኪስ ብቅ ብቅ ብሎ ሹሎ በሰልፍ ተደርድረው ሲታዩ ደረቱ ላይ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ጥይቶች የተሰኩበት ዝናር ያጋደመ ይመስላል፡፡ ሰውየው ራሱ ሲፈጠር የተጣበቀ አንጀቱን በጠፈር ቀበቶ ጥብቅ አድርጎ ያሰረዋል ! ወገቡ ወደውስጥ ገብቶ ሱሪውና ሸሚዙ ቡፍ ሲል ጠቅልለው በሲባጎ ወገቡ ላይ ያሰሩት የስፖንጅ ፍራሽ ይመስላል ፡፡

“ እ ...በናፍጣ የሚሰራ መኪና አለ ...በቤንዚን የሚሰራ አለ ...ዝም ብሎ መኪና አይባልም “ አበሳጨኝ ! ሊያቆመ መሰላችሁ ውሃ ተጎነጨና ቀጠለ “የፊልድ መኪና አለ ... ባለ አንድ ጋቢና አለ ...ባለሁለት አለ ...ከኋላ ክፍት ሆኖ እቃ መጫኛ ያለው አለ ...ድፍን መኪናም አለ ....” ከቢሯችን በላይ ያለው ሚካኤል አፍህን ድፍን ያድርገው ማለት ይቃጣኛል ! ደግሞ እዛ አቀርቅራ ቃለ ጉባኤ የምትይዘው ሴትዮ ርግማኔን ፅፋ እያዞረች ብታስፈርምበት ብየ እፈራና በራሴ ቀልድ በውስጤ እስቃለሁ !

“ቢሆንም ግን አሁን ባለው ሁኔታ የመኪና አስፈላጊነት አይታየኝም ሞልቶናል መኪና እች ትንሿ ቀይ መኪና አለች ...ጥቁሩ ቲዮታ አለ ሁለቱ ሚኒባሶችም ቁመው ነው የሚውሉት አስፈላጊ ከሆነም የስራ አስኪያጁን መኪና መጠቀም ይቻላል “ ብሎ አሳረገ እስኪ ካላስፈለገ ይሄን ሁሉ ነገር ምን አስለፈለፈው ? እንደው አንዳንዱ ሰው ...እንቢ ለማለት ይሄን ሁሉ የቀባጠረ ቢፈቀድ ምን ያህል ሊያወራ ነበር ....ኤጭ!

ሌሎቹም የማኔጅመንት አባላት ይሄን ነጃሳ ሰውየ ተከትለው ጠመሙ ! ሃላፊው “የተጠየቀወ መኪና ይገዛ” ብሎ ኮስተር ቢል እንደውሻ ተከትለውት እንደሚጮሁ አውቃለሁ ....ግን እሱም እንዲገዛ ስላልፈለገ አይደል መጀመሪያውኑ ወደማኔጅመንት ነገሩን የገፋው .....በቃ መኪናው አልተፈቀደም ተባለ ፡፡ ተነስቸ ልወጣ ስል ሃላፊው

“አብርሃም ቆይ የወንበሩን አልጨረስንም አለ” ከዛም የወንበር ግዥውን ጥያቄ አቀረበ ! ይሄ ማኔጅመንት የሚሰራው አጥቷል ....ለአንድ ወንበር ደግሞ ሌላ ግማሽ ቀን ሊነታረክ ነው ?

አሁንም የፋይናሱ ነጃሳ እጁን አውጥቶ መናገር ጀመረ “ ወንበር ሲባል ብዙ አይነት ወንበር አለ ....”ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ

“አቶ ገረመው “ አልኩ አቋርጨው “ የማይሽከረከር የማይንቀሳቀስ ወንበር ብየ አቅርቢያለሁኮ “ አልኩት

“ ቢሆንም የማይሽከረከር የማይንቀሳቀስ ወንበር ወንበር ሲባል ብዙ አይነት አለው እኮ ......ባለ መደገፊያ ወንበር አለ ...ባለ ስፖንጅ አለ..ደረቅ ወንበር አለ ....” አድርቅ የሆነ ሰውየ መለፍለፍ አይታክተውም ግን ?

“.....በዛ ላይ አሁን አንተ ቢሮ ያለው ወንበር ከተገዛ ገና አመት አልሞላውም ....አለ ከተባለ የቢሮ እቃ አቅራቢ ነው የተገዛው ምናለ ፍሬ ያለው ነገር ብንጠይቅ “ አለ ! ማኔጅመንቱ ወንበር እንዳይገዛ ወሰነ! መሄጃ መኪና የለ መቀመጫ ወንበር የለ በቃ እርፍ! እድሜ ለነጃሳው!

ከቢሮ እንደወጣሁ እራሴን እንዲህ እያልኩ መከርኩት “አብርሽ በቃ በማንም ሽማግሌ አትበሳጭ እዛች እንኳ አንዳንዴ ቅዳሜ ቅዳሜ ብቅ የምትልባት ሬስቶራንት ሂድና እስቲ ራትህን ብላ እንደውም ዛሬ ሰኞ ነው ግርግር አይኖርም ቆንጆ ቆንጆ ፍቅረኛሞችን እየተመለከትክ ራትህን በልተህ ዘና ብለህ ትመለሳለህ” የራሴን ምክር ሰምቸ ወደሬስቶራንቱ ጎራ አልኩ (መካሪ አያሳጣኝ ሃሃ) ምናይነት ነገር ነው እንደው ይሄ ህዝብ ቅዳሜ አይል እሁድ ታክሲና ሬስቶራንት መሙላት ነው እንዴ ስራው ? ቤቱ ጢም ብሎ ሞልቷል ! ሴትና ወንድ ሴትና ወንድ ...ሴትና ወንድ ! እኔ ብቻ አንድ ነጠላየን !

አንድ ወንበር አግኝቸ ተቀመጥኩ አጠገቤ ደግሞ አንድ ባዶ ወንበር አለ ! ባዶውን ወንበር ስመለከተው ያልቀጠርኳትን ልጅ መጠበቅ ጀመርኩ። በጣም ርቦኝ ስለነበር ቋንጣ ፍርፍር አዘዝኩ። ሌላ ልዩነት ! ሁሉም የሚበላው ፒዛ በርገር ስፓጌቲ ምናምን ነው ! እኔ ቅላቱ እንደሳት ፍም የሚንቀለቀል ፍርፍር ....መሃሉ ላይ የሰጎን የሚያክል ትልቅ እንቁላል እንቁላል የጥያ ትክል ድንጋይን መስሎ ተተክሎበት ፊቴ ክምር አለ! አንዴ እንደጎረስኩ ገና ሳልውጠው “ይቅርታ የኔ ጌታ ይሄ ወንበር ሰው አለው ? “ አለችኝ አንዲት ድምጿ እንደማር በእርጋታ የሚፈስ ቆንጆ ሴት ! ልብሷ ቦርሳዋ አቋሟ በተለይ ቁመቷ የሚገርም ነበር ።

“የለውም” አልኳት ስናገር ትን ሊለኝ ነበር

ወንበሩን ስባ ተቀመጠችና “የለውም አይባልም ...እባክሽ ተቀመጭ የእኔ እመቤት ነው የሚባለው” ብላ ፈገግ አለች ሳልወድ በግዴ ፈገግ አልኩ አወራሯ ደስ ይላል። በራስ መተማመኗ እንደአንዳንድ በራስ መተማመንና ጉራ እንደተቀላቀለባቸው እንስቶች አይደለም በቃ ራሷን ናት ! አስተናጋጁን ጠርታ የሆነ ቸቸቸቸ የሚል ነገር የበዛበት ምግብ አዘዘችው እኔ ቸክን መስሎኝ ነበር... አስተናጋጁ ግን ሰሃን ላይ የተከመረ ሰላጣ ከሹካ ጋር አቀረበላት “በቃ ያ ሁሉ ቸቸቸ ለዚህ ነው “ብየ ገረመኝ !

እጇን ልትታጠብ ስትነሳ ከኋላዋ አየት አደረኳት ወይ ግሩም ! የእግሯ ርዝመት ጥራት በዛ ላይ የለበሰችው ጉርድ ቀሚስና ባለተረከዝ ጫማ እንዴት ነው ያማረባት ደርባባ እመቤት የምትባለው እንዲህ አይነቷ መሰለችኝ ! እድሜዋ አርባ አካባቢ ይሆናል ! በሰል ያለች ሴት ናት ! ስትመለስ እንዲህ አለችኝ “ ቆንጆ ቤት መታጠቢያው ንፁህ አስተናጋጆቹ ትሁት “ ብላ ወደሰላጣዋ አተኮረች

በሹካ እየወጋች አንዴ ትጎርስና በሶፍት የሚያማምሩ ከንፈሮቿን ትጠርጋለች ከዛም ሹካዋን ሰሃኑ ላይ አስቀምጣ ቤት ውስጥ ያለውን ሁኔታ ዘና ብላ ትመለከትና እንደገና ወደሹካዋ ለምን እንደሆነ ባይገባኝም ላዋራት በጣም ፈልጊያለሁ ። በቃ አይታችሁ የምትወዱት ሰው አለ አይደል እንደዛ ናት ።ከሴትነቷ በላይ የገዘፈ ነገር አላት ! ለማውራት ምንም ቅድመሁኔታ የላትም በቀጥታ ወደጉዳዩ ትገባለች

“እኔ የምልህ ራት ቋንጣ ፍርፍር እንዴት ነው ነገሩ” አለችኝ

" እ...ማለት"

"ምን ማለት አለው በርበሬው በዛ ላይ ብዛቱ እንቁላል አልቀረ ስጋ እና አይከብድህም" ሌላ ሰው ቢናገረው ያበሳጭ ነበር የዚች ሴት አነጋገር ግን የትዝብት ሳይሆን ልክ የእናት አይነት ግሳፄ ይመስላል።

"ይከብዳል "

"አዎ ...ሳይህ እኮ ለኔም ከበደኝ " አለች አነጋገሯ የመጨረሻ አሳቀኝ !

" ያው እንግዲህ ቋንጣ ፍርፍር ከእርሃብ አይከብድም ብየ ነው " አልኳት ....ትክ ብላ አየችኝና

"ደራሲ ነህ" ስትል ጥያቄ ወረወረች

"አይደለሁም"

"እራት ግን ቀለል ያለ ነገር ብትመገብ ጥሩ ነው ...ወጣት ነህ ጤነኛ ነህ እራስህን ለምን ታስጨንቃለህ... አትክልት ነገር አለ ...ፓስታ አለ...ጁስም አለ ....." ወይኔ ጉዱ ያ ነጃሳ አካውንታንት የሴት ስጋ ለብሶ ተከሰተ

" ራሱ ይሄ የአትክልት ፒዛ ጥሩ ነው ...."

ዝም አልኳት ....ዝም ተባባልን ምግባችን ላይ አተኮርን ፊት ለፊታችን አንዲት ፊቷ በሜካፕ የተለሰነ ወጣት ከአንድ ወጣት እጇቿን እያወናጨፈች ታወራለች በየመሃሉ በአፈድስት ብርጭቆ የተሞላውን ዋይን ትገለብጠዋለች ! ዋይን በነፃ የታደለ እስኪመስል ሁሉም ጠረንጴዛወች ላይ ይታያል !

ሁለታችንም መብላት ጀመርን ። አፍሬ ይሁን ፈርቸ እንጃ ትንሽ ትንሽ ስቆነጥር የቤቱ መብራት ድንገት ድርግም ብሎ ቤቱ በጨለማ ተዋጠ ! በጭላንጭል በቱን የሞሉት ጥንዶች ሲጠጋጉና ከንፈር ለከንፈር ሲሳሳሙ ይታያሉ .....ወይ የእኛ ነገር ሁሉን በጨለማ !! እኔም ነፃነት ካሳጣኝ የቆንጂ ሴት እይታታ በጨለማው ስለተከለልኩ በጨለማው ውስጥ አንድ ጠቀም ያለ ጉርሻ ጠቅልየ ጎረስኩና እንደው በቅጡ ሳላላምጥ ዋጥኩት ...ወዲያው ፍርፍሩ ውስጥ ጣቶቸን በዳበሳ እየላኩ ቋንጣወቹን እለቅማቸው ጀመረ ለቀም ለቀም አድርጌ ርሃቤ ሰከን እንዳለልኝ የጠፋው መብራት በቤቱ ጀኔኔተር አማካኝነት ቦግ አለ ።

ወዳጀ ፈገግ ብላ "እንኳን ለመተያየት አበቃን" አለች .... ሹካዋን አንስታ አንዲት የሰላጣ ቁራጭ አንስታ ወደአፏ ላከች ግን አልጎረሰቻም ወደሰሃኑ መልሳ አስቀመጠቻትና ወደእጀ በግርምት ተመለከተች እኔም አይኗን ተከትየ የራሴን እጅ ተመለከትኩት በጣም ያስቅ ነበር ቋንጣ ለቀማ በፍርፍሩ ውስጥ ሲዳክር የቆየ እጀ ከላይ እስከታች ወጥ በወጥ ሁኗል ሰሃኑ ላይ በስርአት ተከምሮ የነበረው ፍርፍር ብትንትኑ ወጥቷል እንደውም ጠረንጴዛው ልብስ ላይ ሁሉ ተዝረክርኳል

"ፖለቲከኛ ነህ " አለችኝ

"ኸረ አይደለሁም " አልኳት ጥያቄዋ ገርሞኝ

" አፍሪካዊ ፖለቲከኛ መሰልከኝ ...አፍሪካዊ ባለስልጣን "

"ምኔ ነው ባለስልጣን የሚመስለው " አልኳት እየሳኩ

" አፍሪካዊያን መሪወቻችን ባለስልጣኖቻችን እንዲህ እንዳንተ ፍርፍር ነው አጨዋወታቸው ....ህዝቡ ጨለማ ውስጥ ሲዳክር ሲሳሳም ሲዘሙት ሲጠጣና አሸሸ ሲል እነሱ በጨለማ ውስጥ እጃቸውን ልከው ፍሬ ፍሬዋን ለቀም ለቀም ያደርጓታል ...ህዝቡ ሲበራለት እነሱ በጥጋብ ሰማይ ጥግ ደርሰዋል .... ህዝቡ ከጨለማው ሲነቃ ተራ ፍርፋሪ ነው አገሩ ማእድ ላይ የሚጠብቀው ገኘውም ለስርቆት ተራውም ህዝብ ለተራ ስሜቱ ጨለማ እንዳሳደደ ነው .... ጨለማዋ አህጉር ፍሬ ቢስ የሆነችው ለምን መሰለህ ታዲያ " አለችና በሶፍት አፏን ጠራርጋ ሂሳቧን ከፈለች ከዛም

ቦርሳዋን አንስታ እያነገተች " ለማንኛውም ራት ቀለል ያለ ነገር ውሰድ " ብላኝ ለሰላምታ እጇን ዘረጋችልኝ ጨበጥኳት መዳፏ ሸካራና ጠንካራ ነበር ! ከሬስቶራንቱ ወጥታ እስክትርቅ ከኋላዋ እየተመለከትኳት ነበር

ፊት ለፊቴ ያለችው ፊቷ በሜካፕ የተለሰነው ወጣት ቶሎ ቶሎ ወይኗን እያጋባች እጇን እያወናጨፈች ታወራለች በየጠረንጴዛው የቤቱን ፈዛዛ ብርሃን ተገን ያደረገ ትውልድ ዋይኑን ይጨልጣል ...ፍሬ ፍሬውን እያስለቀመ በደጅ !

# ንፋስ ወዴት ነህ ቢሉት ማርና ወተት ወዳለበት

እማማ አረጋሽ ቤት ተሰብስበናል ሩጫ ልናይ ልጃቸው ከውጭ አገር ትልቅ ቴሌፊዥን ስላምጣችላቸው በሳቸው ቴሌቪዥን ማየት የሩጫ ጥም ቆርጣል መቸስ ቴሌቪዥኑ ግድግዳ በሉት የእማማ አረጋሽ ቤት ከሶስት ግድግዳና ከአንድ ቴሌቪዥን ነው የተዋቀረው ቢባል ማጋነን አይሆንም ባለቤታቸው አቶ ፈንታው ነብሳቸውን ይማራቸው ዜና ለማየት በየቀበሌው እንደዞሩ ይሄን አለም ሳያዩ ሞቱ ሲያልፍላቸው ሞቱ ቁጭ ብለው ቴሌቪዥን በማየታቸው ሞቱ (ይላል ጎረቤቱ) ጀመረ ሩጫው ገንዘቤ ዲባባ አበባ አረጋዊ ቴሌቪዥኑን እየሞሉ ደሞ ራቅ እያሉ

እኛም "ገንዘብ ገንዘብየ ገንዘባችን ሩጭ አሳያቸው አይዞሽ " እያልን ያው አበባ አረጋዊ ፈትለክ ብላ ወርቁን ወሰደችው ያውም የስዊዲን ማልያ ለብሳ በስዊዲን ባንዲራ ተውባ! ብዙወቻችን ቀዝቀዝ ስንል እማማ ወለላ "እልልልልልልልልልልልልል እሰይ እሰይ " አሉ (ጎረቤት ናቸው)

"እንዴ ለስዊዲን እኮ ነው የሮጠችው " ብንላቸው

"ይሁና ልጃችን ናት " አሉ

እማማ አረጋሽ ታዲያ " አይ ወለላየ አሁንስ እማማ ፅጌን መሰልሽኝ " አሉ ።

ስለእማማ ፅጌ ለመስማት ጆሯችን ቆመ።

"ማናቸው እማማ ፅጌ ?"

እማማ አረጋሽ ስላነሷቸው ሴት ታሪክ አወጉን

*** ******

በድሮ ጊዜ እኛ ሰፈር እች አሁን ጋሽ እቁባይ ገፋ አድርገው ያጠሯት ቦታ ላይ አንዲት የእማማ ፅጌ ድንጋይ የምትባል ጥቁር ድንጋይ ነበረች አጠገቧ ደግሞ የላስቲክ ቤት አሁንም አጥሩ ውስጥ ድንጋዩ አለ ታሪክን ቢያጥሩት ያው አጥሩ ውስጥም ሁኖ ቢሆን ይጮሃል

እማማ ፅጌ አንዲት ልጅ ነበረቻቸው መቸስ ቁንጅናዋ አይወራም መለአክ መለአክ በሏት አንዲት ልጃቸው ናት አባቷ አይታወቅም እችው ባልቴት እናቷ እዚች ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ድንችም ቲማቲምም እየቸረቸሩ አሳደጓት በኋላ ህመሙም እርጅናውም ሲጫጫናቸው ግማሽ ችርቻሮ ግማሽ ልመና በሆነ ሂወት ይውተረተሩ ጀመር።

መቸስ ልጅቱ መንገድ ዳር እየኖረች ልእልት መሰለች የመንደሩ ሴቶች ጠርሙስ ሙሉ ቅባት ጨርሰው ያማረ ለብሰው ትኩስ በልተው ጠብ ያላለላቸው መልክ እዚች መንገድ ዳር ላስቲክ ከልላ በምፅዋት የምትኖር ልጅ ላይ ፈሰሰ ፀጉሯ ተዘናፈለ ዳሌዋ ሞላ ወንዱ ሁሉ አይኑ ይቀላውጣት ጀመረ።

አንድ ምሽት እማማ ፅጌ ኡኡ አሉ መንደርተኛው ወደላስቲኳ ቤታቸው ተሰበሰበ ልጅቱ የለችም ጠፋች መንደርተኛው እማማ ፅጌ ጋር በመሆን ሳምንት ሙሉ ፈለገ የለችም ቆንጆዋ ባልቴት እናቷን ትታ ምጥ ትግባ ስምጥ እልም ድርግም አለች !! ጎረቤቱ ተስፋ ቆርጦ ወደየራሱ ጉዳይ ቢመለስም ሚስኪኗ ባልቴት ግን ከዛች ቀን ጀምሮ ለአስራ አንድ አመታት ታየች በተባለበት ተንከራተቱ ኢትዮጲያ ውስጥ የቀራቸው ከተማ የተረፋቸው መንደር የለም።

በየደረሱበት የእለት ጉርሳቸውን እየለመኑ ፅንፍ የለሽ በሆነ የእናት ፍቅር ልጃቸውን ፈለጉ።

በአስራ አንደኛው አመት ልጃቸው ውጭ አገር ኑራ እንደተመለሰችና እና አንድ ባለፀጋ ልታገባ ሰርጉ እየተደገሰ መሆኑን ከሁነኛ ሰው ሰሙ "አይ ልጀ ፈልጋ አጥታኝ ነው " አሉና ወደአዲሳባ አቀኑ አዲሳባ እንደገቡ አንድ ጥግ

ላይ ከያዟት ፌስታል ለክት ቀን ብለው ያስቀመጧትንና ላለፉት አስራ አንድ አመታት ለብሰዋት የማያውቋትን ቀሚስ አውጥተው ለበሱ እራሳቸውን አየት አደረጉና "እመቤት መሰልኩ አይደለም እንዴ ልጀን እማ አላዋርዳትም " አሉና ፈገግ አሉ፡፡

ልጃቸው " አለች" ወደተባለበት ቤት ሳያርፉ ጉዞ ጀመሩ ቤተ መንግስት የመሰለው ቤት በሁለት ዘበኞች ይጠበቃል "የልጀ ቤት" አሉ በኩራት ፊት ለፊት ቁመው ከዛም ጢጋ ሲሉ "እግዜር ይስጥሽ " አለ አንዱ ዘበኛ እማፅጌ ይሄን ቃል ሽ ጊዜ ሰምተውታል የዛሬው ግን ለየት አለባቸው፡፡

ሳቅ ሳቅ አላቸው ይሄ ጥበቃ ከደይቃወች በኋላ ጎንበስ ቀና ሲልላቸው ታያቸው

"ልጀዋ እኔ እንኳን የመጣሁት ቢጢየን ብየ ነው"

"ቢጢ ማናት"

"ልጀ ናታ እዚህ ቤት እንደምትኖር ነግረውኛል "

" እንደዛ የምትባል ሴት የለችም እዚህ እማማ"

ጢጋ አሉትና " ሙሽራይቱ ማነው ስሟ "

"እሜቴ ስማቸው ብሩክታዊት ነው "

ግራ ተጋብተው እንደቆሙ የግቢው በር ቢጢ ከሽበላ ባለቤቷ ጋር ውሃ በመሰለ መኪና ብቅ አለች እራሷናት እናትና ልጅ ፊት ለፊት ተፋጠጡ እናት ችል መቆም አልቻሉም ጉልበታቸው ተብረከረከ " ቢጢ የ ያይኔ አበባ "" ብለው ወደመኪናው በእንብርክክ ቀረቡ  ልጅ ኮስተር አለች የመኪናውን መስተዋት ዝቅ አደረገጭ ጥቁር መነፅረዋን ወደፀጉሯ ከፍ ራሷን መታ አድርጋ ውብ ፀጉሯን ወደጎን አለችና "

ምንድነው " አለች ፊቷን አጨፍግጋ፡፡

" ቢጢየ እናትሽ ስንከራተት ኑሬ ይሄው መጣሁልሽ ሄድኩ አይባልም ሜዳ ላይ ጣል አድርገሽኝ ማን ኣላት ብለሽ "

"ማነህ ወደዛ ውሰዳት የማንም ወፈፌ እየመጣ እንሂድ "ሃኒ" " አለች ቢጣ መኪናውን ወደሚያሽከረክረው ሰው ዞር ብላ ፡፡

"ሃሃሃሃሃ ሃኒየ አትበሳጭ አዲሳበባ በነዚህ አይነት ፈጣጣወች ነው የተሞላው " ነዳጁን ሰጠና ፈትለክ እማማ ፅጌ ተንበርክከው ቀሩ ራሳቸውን አይተው "ልጀ እስክትረሳኝ ተበሳቁያለሁ ማለት ነው " አሉ በልጃቸው አልፈረዱም፡፡

እስከሰርጉ ቀን ከግቢው ፊት ለፊት ካለች በረንዳ ላይ ዝናብኛ ፀሃይ እየተፈራረቀባቸው ልጃቸው መኪና እንደልብስ እየቀያየረች ስትገባና ስትወጣ እየተመለከቱ በልጃቸው ምቾትና ታላቅ ደረጃ መድረስ የራሳቸውን መከራ ረስተው ቆዩ አንድ ቀን እናቴ ብላ እጇን እንደምትዘረጋላቸው ተስፋ በማድረግ (((ልጅ ያላየቻቸው እየመሰለች ስታልፍ ቆየች ከአንድ ወር በላይ!!)))

የሰርጉ ቀን እናት ያችን ቀሚስ ከፌስታላቸው አወጡና ለበሱ የኖሩባት በረንዳ ጠራረጉ ፌስታላቸው ውስጥ ያስቀመጧትን ትንሽ ብልቃጥ አወጡና በረንዳው ላይ ባለ መስታወት አይናቸውን ተኳሉ፡፡

ከሰአት ሙሽራዋ በነጭ ቀሚስ ተውባ በክፍት መኪና ስትደርስ ጎረቤቱ ሰርገኛው ሲተረማመስ መሃል መንገድ ላይ ከሰርጉ መኪና ፊት ለፊት እማማ ፅጌ እስከታቸውን አወረዱት ሰው ሁሉ እብድ መስለውት ለአፍታ ትኩረቱን ወደባልቴቷ አዞረ ከጫጫታው ከሙዚቃው በላይ የገዘፈ ድምፅ ከባልቴቷ ወጣ፡፡

“ መጣችም ሄደችም ደሟ ከደሜ ስጋዋ ከስጋየ የተጨለፈ ልጀ ቢጢየ እቻት  እንኳን ደስ ያለሽ በሉኝ ሙሽራው ልጀን አደራ “ አሉና ፊታቸውን አዙረው ወደበረንዳቸው ሄዱ ከኋላቸው የእድምተኛው ሳቅና ፌዝ እየተከተላቸው፡፡

ሌሊቱን ሲጨፈር ሲደለቅ ታድሮ ጧት ያደረው ሰርገኛ ሲወጣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የአስክሬን ማንሻ መኪና ከሰርጉ ቤት ፊት ለፊት ካለ ሱቅ በረንዳ ላይ የአንዲት ባልቴት ሬሳ ሲያነሳ ታየ ሬሳው ከተነሳበት በረንዳ ንፋስ እየገፋ ወደሰርግ ቤቱ በር የወሰደው አንድ ጥቁርና ነጭ ፎቶ ዘበኛው እግር ስር ደረሰ እናትና ልጅ የተነሱት ፎቶ ነበር

“ ወይ የሰው መመሳሰል ልጅቱ እትየን አትመስልም ?.” አለ ዘበኛው ለጓደኛው

“ኤዲያ እሱን ወዲያ ጥለህ ይሄን ያዝ “ ብሎ ከሰርጉ የተረፈ ቢራ ሰጠው፡፡ ዘበኛው ፎቶውን ጥሎ ወደቢራው ዞረ ነፋስ ጥቁርና ነጩን ፎቶ ወዳልታወቀ ቦታ እየገፋ ወሰደው፡፡

“እኛ ያሳደግናት በማር በወተት  ” የሰርግ ዘፈን ከግቢው ይሰማል

# እብድ እና ዘመናይ

ጓደኞችን አመሃ አበደ!!

ድንገት ነው እንደትንታ እንደሳል እንደንጥሻ እብደቱ ያመለጠው እኔ አይምሯችን ግን "ጅኒየስ" ምናምን እንላታለን እንጅ የሆነ ጊዜ "ጅሊየስ" ትሆናለች ( መጃጃልን ሳቀላምጣት መሆኑ ነው ) አይምሯችንን ልንጠብቃት ይገባል አለች ስንላት ገደል ገብታ ገደል ታስገባናለች ወይኔ አምሽ ምነው ሴት ሆኖ ተፈጥሮ በነበር ይሻለው ነበር! ባንዴ ከማበድ በየቀኑ ትንሽ ትንሽ ማበድ !

የስነ አእምሮ ጠበብቶች "ሴቶች የማበድ እድላቸው ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ነው ምክንያቱም ሴቶች ብስጭታቸውን መከፋታቸውን በእንባ ይሸኙታል በጩኸት ይሸውዱታል ወንዶች ግን አፍነው ስለሚይዙት ውስጣቸው ይጠራቀምና ጉድ ያደርጋቸዋል " ይላሉ በነጋዴ ቋኛ ስንገልፀው ሴቶች የሚያብዱት በችርቻሮ ሲሆን ወንዶች ግን በግምላ ነው እንደማለት !!

ጓደኞችን አመሃ ማለት ኮሌጃችን ውስጥ ወላ ባለባበስ ወላ በትምህርት የሚደነቅ ሲበዛ ዝምተኛ ልጅ ነበር " ሃይ ባይ " ነው ቅፅል ስሙ በቃ ስንገኛኝ " ሃይ " ይላል አንዲት ቃል ሳይተነፍስ ስንለያይ "ባይ" !! አምሻ ልዩ ልጅ ነበር ምድረ ኩታራ ከየዶርማችን ሱክ ሱክ እያልን ወደ "ክላስ" ስንጣደፍ አምሃ ፅዳ ባለ ፓጃሮ ከተፍ ይላል ይሄ ይሄ ተደማምሮ እንኳን እብደት ድብርት በአመሃ አጠገብ ያልፋል ብሎ የሚገምትም አልነበረ ፀጉራም በግ አለ ሲባል ይሞታል እንዲሉ አበው!! በሃብት ፀጉር የደለበ የመሰለን አምሃ "አለ" ስንለው "ለቀቀ" !!

አምሃ እና እኔ ጓደኞች ነን። እንደውም አመሃ ሁለት ጓደኛ ብቻ ነው ያለው እኔና ናትናኤል የሚባል በፊት አብረው ሳንፎርድ የተማሩ ልጅ። በቃ ሌላ ጓደኛ የለውም። ያው ፍቅረኛው እንዳለች ሁና !! እቤቱ ሁሉ ወስዶ ሞልቃቃ እናቱ ጋር አስተዋውቆኛል።

እንደ አመሃ እናት በጣም አጭር ጅንስ ቁንጣ የለበሰች ወጣት እናት ከዛ በፊትም ከዛ በኋላም አይቶ አላውቅም !የእግሮቿ አረዛዘም ሰበር ሰካ አረማመዷ ወጣት ይፈትናል ከላይ ጣል ያደረገችው ስስ ቡዲ ነገር የጡት ማስያዣዋን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል አመሃ ሁለታችንን ትቶን ወደውስጥ ሲገባ "የዛሬ ልጆች ቆንጆወች ናችሁ" አለችኝ እናታዊ አድናቆት አልመስልህ አለኝ የለም የለም እቺ ሴት የእናት ቀለም የላትም።

አንድ እግሯን ሶፋው ላይ አውጥታ በአረገኸኸም የእጇ ጣቶች ጉልበቷን በስሱ እንደማከክ አደረገችው ቁንጣዋ በጣም ተሰብስቦ ሰውነቷን አጋለጠው ጥርት ያለ ያታፋዋ ቆዳ ላይ እና የሚያማምሩ የእግሯ ጣቶች ላይ አይኔን አለማሳረፍ አልቻልኩም በዛ ላይ ውስጥን ሰርስሮ የሚያይ የሚመስል አስተያየቷ "ምነው ባልመጣሁ " አስባለኝ።

በምድር ላይ ያሉ እናቶች ሁሉ ሽንሽን ቀሚስ "ዩኒፎርማቸው" ይመስለኝ ነበር ያደኩበት መንደር ሁሉም የሚለብሱት እንደዛ ስለነበረ ሲቀመጡ እንኳን ዘርፋፋ ቀሚሳቸውን እንዴት ሰብሰብ አድርገው እንደሚቀመጡ ሳስብ የዚች "እናት" ነገር ግራ ገባኝ

የአመሃ አባት ውጭ አገር በሚገኝ ዩኒቨርስቲ መምህር ናቸው እናቱ አብራቸው ሂዳ እዛ እንዲኖሩ ብትለመን ብትመከር በአንገቴ ገመድ ቢገባ አልሄድም በማለቷ ሁለቱ ብቻቸውን እዚህ በቅንጦት የተምነሸነሸ ቪላ ውስጥ ይኖራሉ። አባቱ በስድስት ወር አንዴ ብቅ እያሉ ይጎበኟቸዋል እራሱ አመሃ ነው የነገረኝ። "ህዳር ላይ የሚያብድ መስከረም ሱሪውን ከፍ ከፍ ያደርጋል" ይላሉ እማማ ሩቅያ አንድ ቀን አመሃ ለይቶለት ከማበዱ አንድ ወር በፊት ሱሪውን አስር ጊዜ ከፍ ያደርጋል "ሰፍቶሃል እንዴ ይሄ ሱሪ " አልኩት "አይ ቀበቶየን ረስቸ ሳልታጠቅ ነው የመጣሁት አለኝ " እንዲህ የምንባባለው ወደላይብረሪ እየሄድን ነበር ላይብረሪ ውስጥ ጎን ለጎን ለመቀመጥ ቦታ ስላልነበር በያገኘነው ወንበር ተራርቀን ተቀመጥን ድንገት አመሃ ቁጭ ሲል ሸሚዙ ከኋላው ሰብሰብ አለና ቀበቶ ማድረጉን አየሁ አላደረኩም ማለቱ ገርሞኝ ስንወጣ እጠይቀዋለሁ ብየ በዛው ረሳሁት.አላህ ሲቆጣ ብትር አይቆርጥም ያደርጋል እንጅ ነገር እንዳይጥም (ይሄንንም የሚሉት እማማ ሩቅያ ናቸው)

እኔና አመሃ አንድ ታዋቂ ሬስቶራንት ውስጥ ገባንና ምግብ አዘዝን "ፒዛ" አመሃ ቀመስ አደረገና አስተናጋጇን ጠርቶ "ምንድን ነው ይሄ ሁሉ ጨው እቤቱ ውስጥ ያለውን ጨው ሁሉ ነው የሞጀራችሁት " ብሎ ጮኸባት እንደእውነቱ ከሆነ አመሃ ሲጮኽም ሆነ በቁጣ ሲናገር ሰምቾ ስለማላውቅ ከምላሴ ይልቅ አመሃን አምኘው ነበር አስተናጋጇ ግን በትህትና " ይቅርታ እኛ ፒዛ ስናዘጋጅ ጨው አንጠቀምም ደንበኛው እራሱ በሚፈልገው መጠን እንዲጠቀም ለብቻ ነው የምናቀርበው " አለች ፊታችን የተቀመጠውን የጨው እቃ እያሳየችን "ሂጅ ወደዛ ይሄን ልመን አንችን " አላት ምላሱን በአስፈሪ ሁኔታ ጎልጉሎ በግራ እጁ ጫፉን በመያዝ ለአስተናጋጇ እያሳያት

ፒዛውን ትተነው ሌላ ቤት ገባንና ለስላሳ አዘዘ አንድ ጊዜ ተጎንጭቶ ፊቱን አጨፈገገና "ቱ " ብሎ ወለሉ ላይ ተፋው "እንዴት ሚሪንዳ ውስጥ ሎሚ ትጨምራችሁ" ብሎ እዛም ግብ ግብ ፈጠረ በቃ ይሄ ልጅ ነገር ሁሉ አልጥመው አለ (ሊያብድ አስር ቀናት ብቻ ነበሩ የቀሩት)

3.እብድ ሌላ ቀን መኪናውን እያሽከረከረ ወደማቆሚያው አመራና የዶክተር ታደሰን አሮጌ ዲኤክስ መኪና ከኋላዋ ገጫት (ድሮም ሆድ የባሳት ነበረች) ከዛም ሰው ተሰብስቦ ወሬ ሲያይ አመሃ ረጋ ብሎ ወረደና ልክ እንደትራፊክ ፖሊስ ኮስተር ብሎ ግጭቱን ከተለያየ አቅጣጫ አይኑን እያጨነቆረና አንገቱን እየሰበቀ ከተመለከተ በኋላ(ፎቶ የሚያነሳ ነበር የሚመስለው ) ወደዶክተር ታደሰ ቢሮ ሄደ ሳያንኳኳ በሩን በርግዶ ገባና ዶክተሩ ላይ አፍጥጦ " አንተም ብሎ ዶክተር መኪና እንኳን በስርአት ማቆም የማትችል " ብሎ ሙልጭ አድርጎ ሰድቧቸው ወጣ

"ይሄ ልጅ እብድ ነው እንዴ" አሉ ዶክተሩ

4. ዘመናይ

ሄለን የምትባል "ዘመናዊ" የዲፓርትመንታችን ልጅ አለች ምንም ነገር ስትናገር ለነገየ የማትል " ውይ እሷ ጣጣ የላትም "ፍሪ" እኮነች" እያለ ለእብደት የቀረበ ዘመናይነቷን ተማሪው ያባባሰባት አመሃ ጋር አንድ ሰፈር ናቸው እንደውም ቤተሰብ ናቸው ማለት ይቀላል። አንድ ቀን አመሃ እኔ እሷ ሁነን የኒቨርስቲው መናፈሻው ውስጥ እንደተቀመጥን አንዱ አስተማሪ በፊታችን ሲያልፍ "ይሄ ስድ የሆነ ሰውየ ባለፈው ቢሮው አስገብቶ ቀሚሴን ሊገልበው " አለች።

"ምን ይሄ ቆሻሻ " ብሎ አመሃ ወደሰውየው ሊንደረደር ሲነሳ እንቅ አድርጌ ያዝኩት መጠርጠር ጀምሬ ነበር አምሽ ለቀቅ እያደረገ እንደነበር

"ምን ነካህ ስትቀልድ እኮ ነው እሷ " አልኩት።

"እየቀለድሽ ነው " አላት አመሃ ወደሄለን ዙሮ አዎ እንድትል ጠቀስኳት

"አዎ" ከማለቷ አመሃ በጥፊ አጮላት አስደንጋጭ ነገር ነበር ስድድብ ጀመሩ

"ጀዝባ" አለችው ሰው ስትሳደብ አይቻት አላውቅም መናፈሻው ውስጥ ያለተማሪ ሁሉ ወደእኛ ዞረ

"ሽርሙጣ" አላት ከአመሃ ይሄ ቃል ይወጣል ብሎ ማንም አይገምትም።

"ቆሻሻ" አለችው

"ግማታም " አላት

"ስማ አባትህ የደሃ ገንዘብ ዘርፎ ሃብታም ስለሆነ ጥጋብ ፈነቀለህ ደደብ"

"እና እንዳንች እናት በመሸርሞጥ ሃብታም መሆን ይሻላል " ተማሪ በተሰበሰበበት እብድና ዘመናይ ልክ ልካቸውን ተነጋገሩ አመሃ ሊለይለት ሶስት ቀን ቀርቶት ነበር።

6. ልበቢስ

የመጀመሪያውን ሴሚስተር ጨርሰን ሁለተኛውን መጀመራችን ነበር አዲስ ኮርስ የሚሰጡን መምህር ወደ "ክላስ" ገቡ ፀጉራቸው ወደኋላ የተደለሰ ህንዳዊ ናቸው ስታስቲክስ የሚባል ኮርስ ነው የሚያስቴምሩት ይሄ መምህር ከአንድ የመንግስት የኒቨርስቲ በተማሪወቹ የ"አንፈልጋቸውም" ተቃውሞ የተባሩ ህንዳዊ ቢሆኑም አሁን የምንማርበት ኮሌጅ ግን "ከውጭ በመጡ ታዋቂ መምህራን " እያለ የቴሌቪዥን ማስታወቂያ የሚሰራባቸው የስንፍና ጥግ ናቸው!! ያው እንግዳ ተቀባይ ነንና አክብረን ተቀበልናቸው

በተኮላተፈ እንግሊዝኛቸው ማስተማር ጀመሩ

" ስታስቲክስ ከሌሎች የጥናት መስኮች የሚለየው አንዲት አገር "የልብ ምቷን" የምታዳምጥበት መሳሪያ በመሆኑ ነው" አሉ በኩራት።

አመሃ ድንገት ብዲግ ብሎ "ዝም በል"!" አላቸው።

ቲቸርን " ከራማቸውን ነው የገፈፈው እኛንም እንጅ!

"ሁሉም አስተማሪ እየመጣ የልብ ምት የልብ ምት ይልብናል። ኢኮኖሚክስ የአነዲት አገር የልብ ምት የሚለካበት የጥናት መስክ ነው ህግ የአነዲት አገር የልብ ምት የሚለካበት ፖለቲካል ሳይንስ ሁለንተናዊ የአገር የልብ ትርታን የሚያዳምጥ የጥናት ዘርፍ ነው " ቆይ የዚች አገር ልብ በስንቱ ነው የሚለካው ሲጀመር አገራችን ልብ ቢኖራት እንዳንተ አይነቱ ፊት ታስቀምጠን ነበር ?

አገራችን ልብ አላት ወይስ የላትም" የሚለውን ሃቅ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ያስፈልገናል የልብ ትርታ ከመለካታችን በፊት ልብ መለኪያውን ይዞ ከየዩንቨርስቲው በየአመቱ ወደህዝብ የሚጎርፈው ሁሉ "እዚህ ልብ የለም የምትሄድበት ሂደህ ፈልግ ካልሆነም ልብ ፍጠር " እየተባለ ስለየትኛው ልብ ስለየትኛው ልብ ስለየትኛው ትርታ ነው የምትቀባጥረው !! ሳልፈልግ ብዙ አታስወራኝ ሃሃሃሃሃሃ "

አመሃ ለየለት !! አፋፍሰን አማኑኤል ወሰድነው እዛው ቀረ!!

ከብዙ ጊዜ በኋላ ሄለን አምሃ በእናቱ ምክንያት አይምሮው እንደተናጋ አወጋችኝ " አንድ ቀን አምሃ ሶደሬ ሊሄድ ከሴት ጓደኛው ጋር ቀጠሮ ያዙ ለእናቱም ይሄንኑ ነግሯት መንገድ እንደጀመሩ የጓደኛው እናት የደም ግፊታቸው ከፍ ብሎ ጉዟቸው ተሰናከለ ሆስፒታል ቆይቶ ወደቤቱ ሲመለስ እናቱ ናትናኤል ከሚባለው ከራሱ ከአመሃ ጓደኛ ጋር ያውም አባቱ አልጋ ላይ

"ሄለን "ፍሪ" ስለሆነች በሚያሳብድ ቃል ነው የነገረችኝ

"አብርሽ " አለችኝ እየሳቀች።

"ምን ሆንሽ " አወራሯ አበሳጭቶኝ ነበር።

" ተረኛው አንተ ነህ ሂሂሂሂሂ"

ተራየ ለእብደቱ ይሁን ለ አልገባኝም ግን አልጠየኳትም። ምክኛቱም ሄለንም በጅምላ አብዳ ስይንሱን ጉድ ልታደርገው እየተዘጋጀች ስለመሰለኝ ነበር።

# በብረትና ቻፕስቲክ በተከበበ ከተማ እንሆ የመለአክ ድምፅ ተሰማ!!

ወደ አንድ የግል ሆስፒታል ሰሞኑን ጎራ ብየ ነበር ! ታዲያ ሆስፒታሉ ውስጥ ለቁጥር የሚያዳግቱ "ሴት" ነርሶችን ስመለከት" ይህ ነገር የግል ኮሌጅ ነው ወይስ የግል ሆስፒታል" ብየ አሰብኩ

ገና በሩ ላይ ስደርስ አንዲት በተናገረች ቁጥር ከንፈሯ ጆሮዋ ጥግ እና ጥግ እየደረሰ የሚመለስ እዚያው ከንፈሯ ላይ የደፈደፈችው ቻፕስቲክ አፏን ፀሃይ ላይ የተቀመጠ የቅቤ ቅል ያስመሰለው ነርስ ወደኔ መጣችና በቁሙ የሞተ ፈገግታ እያሳየችኝ "ምን ልርዳክ?" አለችኝ ስትናገር ቃላቶቹ ያዳልጣቸዋል ቻፕስቲኩ ይሆን!?! ጥርሷ በብረት ታስሯል እስኪ አሁን እስኪፈታላት ብትታገስ ምን ትሆናለች "ካልሳቅሽ ወዮልሽ " ያላት አለ ? እኔ የዚች ነርስ ጓደኛ ብሆን(አይበልብኝና) ከንፈሯን እንድታሳስረው ነበር የምመክራት !

" እኔ እንኳን የመጣሁት እናተን ለመርዳት ነው " አልኩ ስለከፍያቸው ውድነት ማሸሞሬ ነበር! እርሷ ግን ፊቷ በፈገግታ ተጥለቀለቀ አቁነጠነጣት "የተናገርኩት ይሄን ያህል ያስደስታል ወይንስ የእውነት የእርዳታ ድርጅት ምናምን ልኮኝ የመጣሁ መስሏት ነው " እያልኩ ስገረም " ኢ..ው ኬ አዲስ የተመደቡት ዶክተር እርስዎ ነዎት? " አለች። አቤት "ኢ..ኬ " ላይ ከንፈሯን እንዴት እንደምታደርገው የከተማው ሴቶች ሀሉ በእንግሊዝኛ የከንፈር ቀመር አማርኛ ካላወራን እያሉ ከንፈራቸውን ለጥጠውት ሊሞቱ ነው

ክርስቶስ ሊፈውስህ መጣ የተባለ የእድሜ ልክ በሽተኛ እንኳን እንደሷ አይፍነከነክም የቃል ኪዳን ቀለበቷን አውልቃ ሳትደብቀው በፊት(ማን ይሆን ያገባት) "እኔ እንኳን ልታከም የመጣሁ በሽተኛ ነኝ " አልኳት ወዲያው ፊቷላይ የተጥለቀለቀው የሳቅ መአበል ድራሹ ጠፍቶ "ተከተለኝ " አለችና ወደካርድ ክፍል መራችኝ እየተቆናጠረች የሆነ ሰበር ሰካ የማለት ሙከራ አይነት !! እች አረማመድ ለአዲሱ ዶክተር ተቀምራ የተቀመጠች ሳትሆን አትቀርም!

ካርድ ክፍል አንድ እግሯን አጥፋ ተሸከርካሪ ወንበር ላይ የተጎለተች ሌላ "ቻፕስቲካም" ሴት ስም እድሜ (ማስቲካዋን ቀጭ) 250 ብር ".አለችኝ ከፈልኩ ካርዱን አቀበለችኝ አየሁት ስሜን አሳስታ ነው የፃፈችው!! "ስሜን አሳስተሸዋል" አልኳት በመስተዋቱ ሽንቁር ጎንበስ ብየ " ሶሪ እስኪ አብርሃም አይደል ስምህ?" አለች ስህተቷ አልገባትም " አዎ አንች ግን "አርሃም" ብለሽ ነው የፃፍሽው" ቢን" ረስተሻታል" ኮስተር ብላ አዲስ ካርድ አወጣችና እያቀበለችኝ "ስምህን ሞልተህ ትሰጠኝ " አለችኝ የቅሬታ ፈገግታ እያሳየችኝ የዚችም ጥርስ በብረት ታስሯል ደሞዛቸውን ቻፕስቲክና የጥርስ ማሰሪያ ብረት የሚከፍሏቸው ነው የሚመስሉት !! ወይስ " ሆዴን ከመቻል ተርፎ ጥርሴን የሚያሳስር ባል ወላ ጓደኛ አለኝ " መልእክት ነው?!! መቸስ የአዲስ አበባ ወንድ ብሩ ተረግሟል !

ስሜን ሞልቸ "እድሜየንም ልሙላልሽ" አልኳት ሆነ ብየ ለማበሳጨት! የመንጠቅ ያህል ካርዱን ከእጀ ላይ ወሰደችና የምትሞላውን ነገር ሞልታ "ዶ/ር ሰናይት ጋር ነህ ከፊትህ አምስት ሰው ይቀድመሃል" አለችኝ በጣም ተበሳጭታለች "ይቅርታ ወንድ ዶክተር የላችሁም" አልኳት በረዥሙ ተንፍሳ ካርዴን ተቀበለችኝና ዶር አምሃ ብላ ፃፈችበት "አመሰግናለሁ" አልኳት በሚያበሳጭ ድምፅ ከዛም ካርዱን አየሁትና ተመልሸ "ይቅርታ የዶክተሩን ስም ማን ነበረ ያልሽኝ " አልኳት በግርምት አየችኝና "ዶ/ር አምሃ 3 ቁጥር ላይ" አለች ቃሉን ረገጥ አድርጋ! "አማ" ነው የሚለው ኤች የለችም አልኳት ካርዱን እያሳየኋት (የእውነትም የለችም ነበር) ስልችት ብያት አንገሽግሻት በመጨረሻ ትእግስቷ አስተካከለቻት !!

ወረፋ ስጠብቅ ከፊቴ የሚቀድሙኝ አራት የሚሆኑ ሴት ታካሚወች እየገቡ በጣም ከቆዩ በኋላ በጣም እየሳቁ ይወጣሉ አረማመዳቸው እራሱ ይቀየራል እየተንኳተቱ ገብተው እንደሞዴሊስት እየተውረገረጉ ይወጣሉ። ውስጥ የተቀመጠው ዶክተር ነው ወይስ ክበበው ገዳ እያልኩ ሳስብ ተራየ ደረሰና ለመሳቅ ተዘጋጅቸ ገባሁ !

ጎልማሳ መላጣ ዶክተር በእስክርቢቶው ወንበር ጠቆመኝ ኮስተር ብሎ ! እስታይሉ ነው መጨረሻ ላይ ያስቀኛል አይ ዶክተር ተቀመጥኩ " እሽ አብርሃም እንዴት ነው የሚያደርግህ " አለኝ ከበፊቱ በባሰ ኮስተር ብሎ ! የመጨረሻዋን ሴት እኔ ያባረርኳት ሳይመስለው አይቀርም መላጣ ምናባቱ ያኮሳትረዋል

በሩ ተንኳኳ "ይግቡ " አለ የመጨረሻዋ ታካሚ ነበረች ተመልሳ የገባችው ስልኳን እረስታ ልትወስድ ዶክተሩ ፈገገታው ፈነዳ "አኬ ብሎ ተነስቶ ሰጣት" ዳሌዋ ሰፋ ያለ መልከመልካም የሃብታም ሚስት ነገር ናት(ልክ ስልኳን ሲሰጣት የሆነ አይነት ለየት ያለ መተያየት ያየሁባቸው መሰለኝ) በተረከዘ ረጅም ጫማዋ ወለሉን እየደቃችው እየተውረገረገች ወጣች ሽቷዋ ግን ክፍሉን ሞላው ዶክተሩ ከተዘጋው በር ላይ አይኑን መለሰና ፈገግታውን አከሰመው ልክ "እፍ" እንዳሏት ሻማ! "ይቅረታ (ካርዴን አየት አድርጎ) አብርሃም እንዴት ነው የሚያደርግህ " ነገርኩት!!

ያስቀምጠሃል?

አያስቀምጠኝም ( ምን ታስቀምጣለህ ኮሶ ፊት)

ያስመልስሃል ?

አያስመልሰኝም (ስልክ ብረሳም አያስመልሰኝም) ብለው አሪፍ ነበር በሽተኛ ቅኔ አያምርበትም ብየ ተውኩት

ምግብ ይዘጋሃል?

አይዘጋኝም!

የመቆረጣጠም ስሜት አለው?

የለውም!! (ታይፎይድ ለማለት ቋምጦ ነበር !) ስላበሳጨኝ ባጭሩ ነበር የምመልስለት ! 250 ብሬን ከፍየ ይገለምጠኛል? ይሄን የህፃናት ምኞት የሆነ ስራውን ሊኮራበት ይፈልጋል ደግሞ ምን ያጣድፈዋል ከእኔ በፊት የገቡት ሴቶች በሌላ በር የወጡ እስኪመስለኝ ነው የቆዩት "እጅጌህን ሰብስብ" አለኝ ማዳመጫውን ጆሮው ላይ እየሰካ ! ኸረ ይሄን ሰው አንድ በሉት ጉርድ ሸሚዝ ለብሽ እጅጌህን ሰብስብ ይላል ለምን ከቀልቡ አይሆንም !!

ቀጥሎ ደረቴ ላይ ማዳመጫዋን ለጠፋትና ተንፍስ ትንሽ ወደዛ ዘወር አለ እንዳልተነፍስበት አንጀቴን አሳረረው አጥንታም ደረቴ ላይ ቀዝቃዛ ማዳመጫውን ለጥፎ ተንፍስ ከእኔ በፊት ያከማትን ሴት ደረት እያሰበ መሆን አለበት ! ታዲያ ምን አቆየው ወረቀት ላይ ምልክት አደረገና ወደመንግስተ ሰማየት ይቅርታ ወደላብራቶሪ ላከኝ

ላብራቶሪ ማለት የግል ሆስፒታሎች ቫይረስ ፣ባክቴሪያ፣ ጀርም እና የታካሚውን ብር ፈልገው የሚያገኙበት ቦታ ነው!! ወደላብራቶሪው ስገባ "መለአክ" ጠበቀኝ በቃ መለአክ ነጭጋውን ለብሶ !! ውብ የሆነች ልች ከመቀመጨዋ ተነስታ ተቀበለችኝ ያውም በፈገግታ!! አቤት ፈገግተዋ ሲያምር ልክ የህንድ ፊልም ላይ አክተሩ ያፈቀራትን ሴት ሲያይ እንደሚፈዘው ፈዘዝኩ አቤት ፈገግታ ምን የተባረከ በሽታ ነው ዛሬ እዚህ የጣለኝ በዛ ላይ ጥርሷ በብረት አልታሰረም (ከእስራቱ ነፃ ወጥቶ ይሆን) ቁመቷ ደግሞ ሲገርም እኔ እንኳን ረዥም የምባለው ትከሻዋ ላይ ቀረሁ!! በዛ ላይ የድምፅዋ መለስለስ ወላ መስረቅረቅ ቆዳዋ ጥርት ከማለቱ ብዛት አንገቷ ስር ያለው ደም ስር ጥቁር አረንጓዴ ሁኖ ይታያል ወረቀቴን አየችና "ምን ገጠመህ አብርሽ? " አለችኝ! አፌ ቁርጥ ይበል ! መኪና ሙሉ ብርቱካን ተሳቢ መኪና ሙሉ ሙዝ ቦቴ መኪና ሙሉ የማንጎ ጭማቂ ይዞ ሌላ ሰው ከሚጠይቀኝ እሷ በሳምንት አንዴ "ምነው አብርሽ?" ብትለኝ እመኑኝ እፈወሳለሁ!!

"ትንሽ አመመኝ" አልኳት። ካለወትሮው የራሴ ድምፅ ጨዋ ሁኖ ተሰማኝ !! " ቆየብህ? " ጥያቄዋን ቀጠለች መርፌና ስሪንጅ እያዘጋጀች " አይይ ትላንት ነው የጀመረኝ " አልኳት ወደዛ ወደዚህ ስትል አይኔ አብሯት ይንከራተታል አቤት አይኔ ሲያሳዝን "ኦ ጥንቁቅ ልጅ መሆን አለብህ በጊዜ ነው የመጠሃው እስቲ እጅህን እዚህ ጋር አድርገው ጨብጠው አ ዎ ደሜ ወደሰሪንጁ ሲገባ አየሁት ክንዴ ላይ ያረፉት ውብ ጣቶቿን ተመስጬ አያለሁ ጣቶቿ የኔ ደም ስሮች መሰሉኝ!! ጥፍር ቀለም አልተቀባችም ቀይ እና ረዣዥም ጣቶቿ ተወዳዳሪ የላቸውም !

ልንገራችሁ አይደል "አብርሽ እግረ መንገዴን ለቀይ መስቀል ደም ልውሰድ እንዴ ?" ብትለኝ እንስራ ሙሉ ደም በደስታ እለግስ ነበር !! አይ ቀይ መስቀል ቤት መኪና 8100 ምናምን ከሚል እችን መለአክ ቀመስ ልጅ

በቴሌቪዥን ብቅ አድርጎ “ደም ስጡ” ብላ አንዴ ፈገግ ብትል ለኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ከፈሰሰው ደም በላይ 17 አመት የእርስ በእርስ ጦርነታችን ከተለገሰው ደም በላይ አይተነውም ሳናየውም ከፈሰሰው ደም በላይ እንለግስ ነበር !! እንትና የምትባለውን ለዛ ቢስ ሴትዮ እያሳዩ ደማችንን ከሚያፈሉት !!

“ አሳመምኩህ እንዴ ?” አለችኝ ድንገት ፈገግ ብላ ለኔ ግን ፈገግግግግግግግግ ሆነ !የላብራቶሪው ቅራቅንቦወች ሁሉ የሳቁ መሰለኝ አጉሊ መነፅሩ እግሩን አንስቶ የሳቀ መሰለኝ ኢጋነንኩት? ደግ አደረኩ !! ”ኧረ አላመመኝም” አልኩ ፈገግታዋን በፈገግታ እየመለስኩ እሷን የሆንኩ መሰለኝ በቃ ሳቋ ግድግዳውም ላይ መደርደሪያውም ላይ እኔም ላይ ነጥሮ ይመለሳል “አለም የገደል ማሚቱይሁንልሽ “ ብሎ የመረቃት ሰው አለ !!

እችን የመሰለች ቆንጆ እዚች ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ መገኘቷ ገረመኝ ቁራጭ ቁንጅና ይዘው ከተማውን የሞሉት ምድረ ወልጋዳ ወልካፋ ጉረኛ ቻፕስቲካም ”ሂውማን ሄራም” ሁሉ ታይፈስ እየያዛቸው እዚህ በመጡና በቅናት ደም ግፊት ጨምረው በሄዱ ትንሽ የፕላስቲክ ብልቃጥ እየሰጠችኝ በዚች ትንሽ “““”ታመጣለህ አለችኝ ! ደበረኝ !ለምን እንደሆነ እኔጃ ! ቢሆንም “በዚች ትንሽ”“““ “ ታመጣለህ ስትለኝ “““““ እራሱ እሷ ስትጠራው ሲያምር! ይሄ ነገር ከዚህ በፊት ስሙ እንዲህ ያምር ነበር እንዴ አልኩ !!

ወጥቸ ወደመፀዳጃ ቤቱ ስሄድ አንዲት ጠረንገሎ ነርስ ቁማ በስልክ እያወራች ትገለፍጣለች ማስቲካ እያላመጠች ፀጉረዋን ስልክ ባልያዘው እጇ እያፍተለተለች አላየችም ፀጉር ”ይቅርታ ሽንት ቤቱ በየቱ ጋር ነው? “ አልኳት ሆን ብየ “መፀዳጃ ቤት” ሳልል ስልክ እንደያዘች ያላየሁ በመምሰል በምልክት ጠቆመችኝ ስልኩ ያጓጓት ትመስላለች አሁን ከዘጋው የደወለላት ሰው መቸም የማይደውልላት አይነት “ ይቅርታ ወደግራ ነው? “ ያልገባኝ መስየ ጠየኳት ስልኩን በእጇ መዳፍ አፈነችና “ወደቀኝ በዛጋ ስትታጠፍ “አለችኝ በትህትና

“.ታዲያ በምልክት ያሳየሽኝ እኮ ወደግራ ነው ግራና ቀኝሽን ሳትለይ ነው የሽንት ቤት አቅጣጫ ጠቋሚ አድርገው የቀጠሩሽ?! “ ብያት መንገዴን ቀጠልኩ። ስልኩን በመዳፏ እንዳፈነች በግርምትና በብስጭት አፈጠጠችብኝ “ ሳልሰማ የአይምሮ ህክምና ጀመርን እንዴ” ሳትል አትቀርም

መፀዳጃ ቤቱ እየተፀዳ ስለነበር የፅዳት ሰራተኛዋ “ ይቅርታ እዛ ተጠቀም ለጊዜው” አለች በትህትና የሴቶችን መፀዳጃ ቤት እያሳየችኝ “ አይይይ! ከተፀዳ ሲኦል ያልተፀዳ መፀዳጃ ቤት ይሻላል “ አልኳት አልገባትም! ምን ይገባታል ከመኖር ብዛት ሴትነት ገነት መስሏት!!

የላብራቶሪ ውጤቴ ጋር የወሰድኩት ነገር አስደሳች ነበር “የላብራቶሪ ቴክኒሻኗን ስልክ!!!!!!!!!!!!!!!!!!” ደግሞ ስሟ ሲገርም “መና” ጠበቅ አድርጋችሁ አንብቡት!! ይሄን ስም ሌሎች ሴቶች ላይ ከሰማችሁት ላላ አድርጋችሁ እንድታነቡት እመክራችኋለሁ! ግጥም ፃፍኩላት አይንሽን ለማየት ሁልጊዜ እንድመጣ ከሰኞ እስከሰኞ ምናል ጤና ባጣ !!

“ አብርሽ ተሻለህ? ” በቀጣዩ ቀን ደውላ የሰው መውደድ ይስጥህ ከተባላችሁ መላአክንም እንደሚያጠቃልል እንዳትረሱ!!

“ አብርሽ እንዳልጠይቅህ ቤትህን ደበክ ” ከ 3 ቀን በኋላ ደውላ ጉድ በል ጎጃም አለ !

“ ደም ስትወስጅ በስህተት ልቤን ወስደሽው ይሆን ” ከ15 ቀን በኋላ እኔ ደውየ ሳቀችልኝ በሳቅ ፍርስስስስ አለችልኝ ያወራሃው ይጣፍጥልህ ተብላችሁ ከተመረቃችሁ መለአከትም ይስቁላችኋል ሌላ ቀን የፅሁፍ መልእክት ላከችልኝ,, hi Arshe,, “ B” ተረስታለች ቢ ፊደልን ድሮም አልወዳት እንኳን እረሳቻት !!

# ዝግመተ ለውጥ

## ክፍል 1

እረኘም ነገር አልወድም!! እረኘም ቁመት እንደሰብለ፣እረኘም መንገድ በእኔና በእነሰብለ ቤት መካከል እንዳለው ፣እረኘም ወሬ ሰብለ እኔን አስቀምጣ በስልክ እንደምታወራው ፣እረኘም እድሜ እንደሰብለ አያት እና እረኘም ቀን እንደዛሬው ዛሬ እሁድ ነው !

እሁድ ከመርዘሙ የተነሳ የሚመሸው ከነገ ወዲያ ይመስለኛል! እሁድ ለእኔ መጀመሪያና መጨረሻ ያለው ዘላለም ነው! ለምን እንዳትሉኝ ታሪኩ እረኘም ነው እረኘም ታሪክ አልወድም እንደእኔና እነደሰብለ የፍቅር ታሪክ

ሰብለ ፍቅረኛየ ነበረች ሰብለ የሚለው ስም በዝግመተለውጥ የተገኘ ይመስለኛል ሰላቢ ሰለበ ሰብለ እያለ የተሸሻለ አይነት እሁድም ከ24 ሰአት ተነስቶ ዘላለም የሆነ

ዛሬ እሁድ ነው ! ይሄ ጋግርታም ህፃን እሁድ አርጅቶ መካነ ሰኞ ውስጥ እስኪከተት ምናባቴ እየሰራሁ የት አባቴ ሂጀ ላሳልፈው ይሆን እያልኩ አስባለሁ አንድ ሃሳብ መጣልኝ እቤቴ በር ላይ ተቀምጨ ፀሃይ እየሞኩ የሆነ ነገር ማንበብ በቃ!

ኩርሲ ነገር አወጣሁና ተመልሸ ከጠረጴዛየ ላይ የሚነበብ ነገር ስፈልግ አንድ ጋዜጣ አገኘሁ መልሸ አስቀመጥኩት ረኘም ጋዜጣ ነው ! የሰብለ አባት ይሄን ጋዜጣ ይወዱት ነበር ነብሳቸውን ይማረውና እሳቸው የሞቱ ቀን የቀብር ስነስርአቱ አረዛዘም መቸም አይረሳኝ ከሰው የተለየ ሃጢያት የተበተባቸው ይመስል ፍትሃቱ እረኘም ነበር ! ለነገሩ አራጣ አበዳሪ ነበሩ!

ሃሳቤን ቀየርኩና ጋዜጣውን ይዤ ወጣሁ ፀሃዩ ሲጠነክር አናቴ ላይ ጣል አደርገዋለሁ።

በር ላይ ቁጭ ብየ አላፊ አግዳሚውን መመልከት ጀመርኩ እማማ ትሁኔ የሽሮ እህል ያስጣጣሉ የሚገርሙ ሴትዮ ሁልጊዜ የሚያሰጡት ነገር አያጡም የሚሰጣ ነገር ቢጠፉ የማስጫውን ሰሚያዊ ፕላስቲክ ብቻውን ያሰጡታል። ታዲያ ያሰጡትን ቢያሰጡ ስጡ ላይ አንድ ሁለት ከሰል ጣል ማድረጋቸው አይቀርም። አንድ ቀን ጠየኳቸው

“እማማ ትሁኔ”

“ወይየ አብርሽ “

“ይሄ ከሰሉ ምንድን ነው “

“የቱ “ “ይሄ ስጡ ላይ ያለው “

“ኧረ ይሄን እስከዛሬ አታውቅም ሆሆ “ ካሉ በኋላ ባለማወቄ ተገርመው አጭር ማብራሪያ ሰጡኝ።

“ይሄ እንግዲህ ስጥ ስታሰጣ አንድ ሁለት ከሰል ጣል ካደረክበት ሰላቢ አጠገቡ አይደርስም መዳኒት ነው” አሉ ወደአልማዝ ቤት እያዩ ፀበኛ ናቸው

“ሰላቢ ምንድን ነው “

“የሚሰልብ ነዋ አንተ ይንበርስቲ በጥሰህ ሰላቢ ይጠፉሃል ሰላቢ ባይኑ የሚሰልብ ነው ያየውን ነገር ሁሉ ላጥ የሚያደርግ እህል አይል ዘይት አይል ሊጥ አይል የተጋገረ እንጀራ በቃ አየት ሲያደርጋት ሽው ነው ወደቤቱ ያጋባታል ” አሉ አልማዝ እንድትሰማ ጮክ ብለው

ከሰል ከሰላቢ ቢያድን እኔ ኩንታል ከሰል ተሸክሜ ሰብለን ስከተላት በዋልኩ ነበር አንድ ሰላቢ ባለጋራጅ ነው የሰለበኝ ለነገሩ ሰብለ እንኳን ከሰል ጣል ማድረግ ከሰል ጉድጓድ ውስጥ ቢያስሯትም መሰለቧ አይቀርም ሲፈጥራት ሰላቢ ነገር ነበረች።

አንድ ባለጋራጅ ከእጀ ነጥቆ ወሰዳት ምን ይወስዳታል ሄደች እንጅ አንዳንዴ ከስራ ስወጣ በምታምር መኪና ሲሸኛት እንገጣጠማለን ጋቢና ተቀምጣ በኩራት ታየኛለች "አየህ ያለሁበትን " አይነት መኮፈስ ሰው ከሰው ልብ ላይ ወርዶ ቆርቆሮ ውስጥ ስለተቀመጠ ይሄን ያህል መኮፈስ ነበረበት ?

በሬ ላይ ተቀምጨ አላፊ አግዳሚውን መመልከቴን ቀጠልኩ ኤጭጭ መምሬ ታምሩ ሳር ቅጠሉን ሰላም እያሉና እያሳለሙ መጡብኝ !! ምክራቸው እረዥም ስለሆነ ሳያቸው ገና ይደክመኛል እንግዲህ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም " ሊሉኝ ነው! ታዲያ ለሳቸው ስል ከማን አባቴ ጋር ልሁን የእናቴ ንስሃ አባት ነበሩ እሳቸው ግን እራሳቸውን የኔም ንስሃ አባት አድርገው ቁጭ አሉ ! ንስሃ አያቴ።

አጠገቤ ሲደርሱ "አብረሃም እንደምን አደርክ "

"ደህና አደሩ አባ"

"አይ የአንተ ነገር ሰው ሲያነብ መነጠሩን ነው የሚወለውለው አንተ ሁልጊዜም ስታነብ ጥርሰህን ትፍቃለህ በጥርስህ ታነብ ይመስል " አሉኝ ! አሁን ይሄ ከንሰሃ አባት የሚጠበቅ ንግግር ነው በርግጥ የወይራ መፋቂያ ይዤ ነበር  በአክብሮት ቆምኩና ሁለት እጆቸን እንስራ እንደተሸከመች ሴት ከኋላየ አነባብሬ ግንባሬን ወደሳቸው አሰገግኩ።

ወደሰማይ አይናቸውን ተክለው ጋቢ እና ካቦርታቸውን በቀኝ እጃቸው እየሰረሰሩ ከኮታቸው የውስጥ ኪስ መስቀላቸውን ሊያወጡ ሲታገሉ በትእግስት ጠበኳቸው። ሁልጊዜም እንዲህ ሲያደርጉ መስቀላቸውን ከኪሳቸው ሳይሆን ከልባቸው ውስጥ የሚያወጡ ነው የሚመስለኝ። አሳለሙኝ እዚህ ሁሉ ልብስ ውስጥ ተቀምጣ መስቀላቸው ግንባሬን ስትነካኝ ለምን እንደምትቀዘቅዘኝ ይገርመኛል!!

"አብረሃም " አሉኝ ድምፃቸውን አለስልሰው !! እንግዲህ ሊጀምሩ ነው

"አቤት አባ "

"እንደው ቢመክሩህ አልሰማ አልክ ኧረ ተው ተው አብረሃም ተው እኔ ወድጀ አይደለም የምነዘንዝህ የናትህ አደራ ከብዶኝ ነው ምናለ አንዷን ጥሩ ክርስቲያን አግብተህ ብታርፍ ለነገሩ የት ታገኛታለህ ቤተስኪያን መምጣቱንም ትተኸዋል !! እስቲ ምን ጎደለህ የጠገበ ደመወዝ ትበላለህ ምን የመሰለ ሰፊ አልጋ አለህ " አሉ በአገጫቸው ወደቤቴ ውስጥ እያመለከቱ እንዴ ይሄ ሰውየ አልጋና ትዳር ምን ያገናኘዋል ያላገባሁት አልጋ ይጠበኛል ብየ መሰላቸው እንዴ ወይስ በትዳር ወጥመድ ውስጥ እንድገባ አልጋየ ላይ ቁራጭ ስጋ እየጣሉልኝ ነው

" ሁልጊዜ ልጅነት የለም እየው " አሉና ሚስጥር እንደሚያወራ ሰው ጠጋ አሉኝና ድምፃቸውን ቀነስ አድርገው " እንደውም አንዲት ትሁት እግዜር የባረካት ልጅ አቃለሁ ከዚህ ማነው ይሄ ሴቶቹ ከሚሄዱበት አገር ማነው "

"አረብ አገር" አልኩ ቶሎ እንዲላቀቁኝ !

"እእእ ተባረክ አረብ አገር እና እዛ ሂዳ ትንሽ አመም አድርጓት ነው የመጣችው ጨ ዋ ኩሽ ስትል የማትሰማ ከቤቷ ቤተስኪያን ከቤተስኪያን እቤቷ ነው እርግት ያለች የጨዋ ልጅ  ላንተ የምትሆን ናት ግዴለህም እያት! ሳምንት እኔው እራሴ አስተዋውቀሃለሁ  አንተማ ዞሮብሃል እንኳን የትዳር አጋር ልትፈልግ እራስህም ጠፍቶሃል ምን ታረግ ቤትህ ጠበል አይረጭበት ዳዊት እንኳን አትደግም " ልቃወም አፌን ከፍቸ ተውኩት

"አይደለማ አይደለም " ብለው እንደገና ሌላ ረዥም ምክር እንዳይጀምሩ ፈርቸ ዝም አልኩ!!

ብቻቸውን በግእዝ እያነበነቡ ወደታች ወረዱ።

እንዲሁ ስለመምሬ እና ስላሏት ልጅ እያሰብኩ የያዝኩትን ጋዜጣ መቃኘት ጀመርኩ።

በደማቅ ጥቁር ቀለም " በመሃበር ተደራጅተው ጫት የሚያመርቱ አርሶ አደሮች ኑሯችን ተለውጧል አሉ " ይላል።

ወረድ ብሎ " አንዳንድ የመሃበሩ አባላት ጫት በመሸጥ አይሱዙ መኪና ገዝተናል ልጆቻችንንም ከተማ ልከን እያስተማርን ነው ሲሉ ገልፀዋል" ይላል ከስሩ አይሱዙ መኪና ተደግፈው ፎቶ የተነሱ አርሶ አደር ምስል ይታያል

ወረድ ብሎ ሌላ አርእስት

" አንድ አይሱዙ መኪና ገደል ገብቶ ከላይ ጭኗቸው የነበሩ ሰባት ሰወች ሞቱ ከሟቾቹ አራቱ ከገጠር ከተማ እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪወች ነበሩ ፖሊስ የአደጋው መንስኤ ሹፌሩ ጫት እየቃመ ማሽከርከሩ ነው ብሏል!!"

ጋዜጣውን አጥፌ ሰፈራችንን ማየት ጀመርኩ ቅድስት ቀይ የእራት ልብስ ለብሳ እቃ ታጥባለች እያንጎራጎረች "በሰባራ ፎሌ " አይ ቅድስት ! እንደኛ ሰፈር ሴት የባከነበት መንደር ያለ አይመስለኝም ቆንጆ ናት " ሞዴሊስት" የመሆን ፅኑ ፍላጎት ነበራት እንደውም የሰፈር ልጆቸህ ሲፎግሯት "ውበት ውጫዊና ውስጣዊ ነው" ሲሉ ሰምታ ውስጣዊ ውበቷን ለማየት አልትራሳውንድ ተነሳች " ይሷታል ስታንጎራጉር እየሰማኋት በድምጿ ማማር ተገረምኩ "ወይ እች አገር ዘፋኞቿ በየማጀቱ እቃ እያጠቡ እቃ አጣቢወቿ በየአደባባዩ እንዝፈን እያሉ ያደነቁሩናል " አልኩ ለራሴ

እስቲ አስቂኙን የመንደራችንን የአንድ ቀን ውሎ እንመልከት

## ክፍል 2

የመንደራችን የአንድ እሁድ ውሎ ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው ነው ከጧቱ 12፡00 ሰአት አልማዝ የምትባለው ጎረቤታችን በሯ ላይ ስለተጣለው ድግምት ታማርራለች ትራገማለች ጠበል ታርከፈክፋለች ድግምት በመጣል የሚጠረጠሩ ጎረቤቶችን ታሸሙራለች "እችኑ ኑሮ ብለዋት " እያለች ብዙ ጊዜ የሞተ አይጥ ነው በሯ ላይ ተጥሎ የሚገኘው

ከ 12፡30 እስከ ጧቱ 2፡00 ሰአት እማማ ዘብይደሩ ጭንቅሎ የተባለውን የልጅ ልጃቸውን ይረግማሉ ይሳደባሉ ይወግራሉ አንዳንዴ ወገራው ሲበዛ ገላጋዮች ይገባሉ ባጭር ቅር ይሉትና ሲታመም ሆስፒታል ለሆስፒታል አዝለውት ይዞራሉ

ከሁለት ሰአት እስከ አራት ሰአት የመንደሩ ልጆች እኔ ቤት ፊት ለፊት ያለች (ሰርቢስ ቤት እንኳን የማታቆም) ቢጢቃ ሜዳ ላይ ኳስ ይራገጣሉ የሚያስነሱት አቧራ ልጆቹን ስለሚሸፍናቸው እንደህልም ነው ብዥ ብለው የሚታዩት

ከሚጫወቱት ልጆች መሃል ጭንቅሎ (የእማማ ዘብ ይደሩ የልጅ ልጅ) ሃይለሚካኤል "አረቡ" (የእማማ የውብዳር የልጅ ልጅ) ሙስጦፋ (የእማማ ዘሃራ የልጅ ልጅ) ሲቲና "ወንዳወንድ ስለሆነች ከቤ ይሏታል (የእማማ ትርሃስ የልጅ ልጅ ናት)

ከላይ ከተዘረዘረው የዘር ሃረግ እንደሚታየው መንደራችን አንድ "እናት" የሚባል ትውልድ ገድፏል "አባት" የሚባል ሃረግ ዘሏል ህፃናቱ ከአያቶቻቸው ጋር ነው ያደጉት ያውም አቅም ከሌላቸው ደሃና አቅመ ደካማ ባልቴት አያቶቻቸው ጋር!

እናቶቻቸው የት ሄዱ ? አባቶቻቸውን ምን በላቸው ? ቢባል መልሱ ከሁለት ጉዳዮች አያልፍም አንድም ወልደው ለእናቶቻቸው እየሰጡ አረብ አገር ሂደዋል አልያም በኤችአይቪ አልቀዋል የመንደራችን እውነታ ነው

ይሄ!! ደግሞ ህፃናቱ የተመካከሩ ይመስል በየምክንያቱ ሲጣሉና ሲነታረኩ የሁሉም መሃላ አንድ አይነት "እናቴ ትሙት!!" የሚል ነው!!

ልክ ከአራት ሰአት እስከ አምስት ሰአት ሁለቱ የመንደራችን እንጀራ ሻጮች ሙሉና ዝናሽ ዱላ ቀረሽ ስድድብ ይጀምራሉ በደንበኛ መቀማማት ነው የሚጣሉት "ለማያውቅሽ ታጠኝ ደግሞ ሙያ እንዳለው ሰው ማየት የተሳነው እንጀራ እየጠፈጠፍሽ እኩል ታወሪያለሽ " "ኤጅ እባክሽ እኔ ሙሉ በወፍጮ ቤት ጥራጊ አይደለም ደንበኞችን የማስተናግደው ጥርት ባለ ጤፍ ጥር ት " "ሂሂሂሂሂ መጣፈጡ ቀርቶ እጀን በለቀቀኝ አሉ እትየ አሰለፍ ጥራቱ ቀርቶብሽ ቡሃቃሽን በወር አንዴ እንኳን ባጠብሽው ሰውን ሁሉ በሆድ ቁርጠት ጨረሽው" ትላለች ዝናሽ የሙሉ ደንበኛ ስለሆንኩ በዚህ አባባሏ ሆዴ ይጮሃል ኡ ወር ሙሉ የማይታጠብ ቡሃቃ እች ስድድብ ደንበኛን ለማስከዳት ወሳኝ የቃላት ጦርነታቸው ናት

ልክ አምስት ሰአት ሲሆን እማማ መጣፈጥና ስንቅነሽ ቡና ይጠራራሉ ወደስድስት ሰአት ጀሚላ የቅንድቧን ኩል ጆሮና ጆሯዋ ጥግ ድረስ ተኩላ በስልኳ እያወራች ወደላይ ትጣደፋለች "ሃቢቢ መጣሁ ወጥቻለሁ" እያለች አፍንጫ የሚሰነፍጥ ሽቶዋ መንደሩን ያውደዋል ጀሚላ ስታልፍ ጥርኝ ያለፈች ነው የሚመስለው የታከከችው ነገር ሁሉ ሽቶ ሽቶ መቸም "ሃቢቢዋ" የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ያደረገ ሰው መሆን አለበት

ይሄን ሁሉ ሳይ ይከፋኛል ብቸኝነት ይጫጫነኛል ከወንዙ ተገንጥሎ ኩሬ ውስጥ እንደተኳተረ ውሃ እዛው የምሻግት አልያም የተቀመጥኩበት በትነት የማልቅ ነገር መስሎ ነው የሚሰማኝ

ይሄ የተረገመ እሁድ ወደዛ አልቆ ስራየ በገባሁ! ለነገሩ ከእሁድ ይሻላል ብየ እንጅ ስራየም ሰልችቶኛል የባንክ ሰራተኛ ነኝ ብዙ ሰወች የባንክ ሰራተኛ መሆኔን እንደትልቅ እና አስደሳች ስራ አድርገው ሲያወሩ ይገርመኛል ለእኔ የባንክ ስራ በምድር ላይ ካሉ አስከፊ ስራወች ሁሉ አስከፊው ይመስለኛል እንደውም ለሰው ሳይሆን ለረቦቶች የሚስማማ ስራ ቢኖር የባንክ ስራ ነው እያልኩ አስባለሁ

አንድ አይነት ቅርፅ ያላቸው "ብር" የሚባሉ መርገምቶችን መቁጠር አራት አመት ሙሉ ቆጠርኳቸው ኤጭ ድፍን አገር የሚራኮትለት ብር ለእኔ አንዳች ቆሻሻ ነገር መስሎ ነው የሚታየኝ ብር ይሸታል ካላመናችሁ ወደአፍንጫችሁ አስጠጉና ሞክሩት እንደብር መጥፎ ሽታ ያለው ነገር ምን አለ? ለነገሩ የዘንድሮ ብር ላሽትተውም ብትሉ አፍንጫችሁ ላይ ሳይደርስ ያልቃል ሰላቢ ነገር ነው

ምስላቸው ብር ኖት ላይ ያሉት ሰወች ከመኖር ብዛት የቢሮ ባልደረባ መስለውኛል ደግሞ አልወዳቸውም! ለምሳሌ አንድ ብር ኖት ላይ ምስሉ ያለውን ሰው መንገድ ላይ ባገኘው ገለማምጨው የማልፍ ይመስለኛል አስር ብር ላይ ያለችው ሴትማ በስማም ስታበሳጨኝ የሆነች ነገረኛ ነገር በደንብ አይታችኋታል ? ስፌት የምትሰፋ ትመስላለች እንጅ ጆሯን አቁማ ነገር የምትሰማ እኮ ነው የምትመስለው ደግሞ ፊቷ ላይ የአሽሙር ፈገግታ አለ ከሁሉም ከሁሉም የሚያበሳጨኝ ነገር ደግሞ ከንፈሯ!! የከንፈሯ ማማር የሰብለን ከንፈር እኮ ነው የሚመስለው !! ከነስፌቷ እጎኗ ላለው አንበሳ ነበር መስጠት !!

ባንክ ቤት ስትሰሩ ስጋችሁ በሱፍ ተጀቡኖ ወሩ መጨረሻ ላይ የሱፍ ቆሎ መግዣ እንኳን የማይተርፋችሁ መናጢ ደሃ መሆናችሁን ብዙ ሰው አይረዳም ቁጥርና ስጋት ባንድ ላይ የሚኖሩት ባንክ ቤት ውስጥ ነው ብር ስትቆጥሩ በስጋት ነው አንዱን የብር ኖት ሌላ የተደረበበት እየመሰላችሁ በፍትጊያ ፍዳውን ታበሉታላችሁ በዛ ላይ ሰው ለብር ያለውን ሟችነት ስግብግብነት ደግነትም ጭምር ትታዘባላችሁ

ሃሃሃ የሆነ ነገር ትዝ አለኝ አንድ ቀን አንዷ እኔ ወዳለሁበት መስኮት ጠጋ አለችና ትልልቅና የተራቆቱ ጡቶቿን መስታወቱ ጋር ጨፍልቃቸው በሽንቁሩ ታናግረኝ ጀመረ ደረቷና ጡቷን የወረራት ብጉር መሰል ነጠብጣብ ያሰቅቃል ሙቶ ሽ ቁጫጮች የሚርመሰመሱበት ደረት ነው የሚመስለው እንደው አንዳንድ ሴቶች ምን ማሳየት እና ምን መደበቅ እንዳለባቸው አያውቁም

እኔ ደግሞ ከኋላዋ ተራ የሚጠብቁ ደንበኞች ወደሷ ሲያፈጡ “እች ሴት ታዋቂ ትሆን “ ብየ አሰብኩ ለካስ ወደኔ ስታጎነብስ በጣም አጭር ጉርድ ቀሚሷ ከኋላዋ ታፋዋ ድረስ በመራቆቱ ነበር ያ ሁሉ እይታ “ምን ልታዘዝ የኔ እመቤት” አልኳት በሚያበሳጭ መሞላቀቅ ቻፕስቲክ አውጥታ ደዘደዝ ከንፈሯን ቀባችና ቀጭ አድርጋ ዘግታ ወደቦርሳዋ መለሰች በትእግስት ጠበኳት “ ዶላር ተልኮልኝ ነበር “ “ከየት ነው “ “ከዲሲ አሜሪካ” “የላኪው ስም “ “ዳኒየ” አለች በፈገግታ “ ዳንኤል ነው “ “ያ” “ስንት ነው የላከልሽ” “ ስሪ ኦር ፎር ሃንድረድ ዶላ ር” ስታወራ አንገቷን ትሰብቀዋለች ዳንኤል የላከላት ግን አንድ መቶ ዶላር ለዛውም መላኪያው ከዛው ላይ የሚቆረጥ ነበር ይሄንኑ ስነግራት ደዘደዟ ሞልቃቃዋ እና ቁጫጫሚ ሞልቃቃ ፊቷ ተቀያየረ ስልኳን አውጥታ ደወለችና ጥርት ባለ አማርኛ “ አንች ያ ችጋራም መቶ ዶላር ብቻ ነው የላከልኝ ዳንኤል እርገጤ ነዋ “ ብላ እርፍ ወዲያው አንድ ቁሽሽ ያለ ቱታ የለበሰ ጎልማሳ ሰው መጣና “የቅርታ እችን ብር ትራንስፈር ታደርግልኝ “ አለኝ እየተጣደፈ በልጅቱ ትከሻ ላይ የባንክ ደብተሩን እያቀበለኝ ልጅቱ የቱታው መቆሽሽ ደብሯት ፊቷን አጨፈገገች “ ወደየት ነው “ አልኩት “ወደ ጅማ “ “ መጠኑ “ “አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን “ ሞልቃቃዋ ሰውየውን ቀጥ ብላ አየችውና ፈገግ ብላ በአክብሮት ቦታውን ለቀቀችለት ወዲያው የሚያደርጋትን አሳጣት “ወደዚህ ጠጋ ብለህ አናግረው ሶሪ ቦታ ያዝኩብህ” አለችው በፈገግታ ዞሮ እንኳን አላያትም(የውሸት አክብሮቷና ፈገግታዋ ከሰረ) ሰውየው እናትየ ስራ ልቡን ያወለቀው ላብ አደር ነገር ነው እሷን ለማየት ጊዜውም የለው !! ሚስኪን ዳኒየ አልኩ በሆዴ

በቃ ይሄ ነው ስራየ ብር መቁጠር መስጠት ብር ማስገባት ማስወጣት ኤጭጭ!! ቢሆንም ከእሁድ ይሻላል

እማማ መጣፈጥ ስንቅነሽን ቡና ሲጣሩ ሰማሁ ገና አምስት ሰአት ወይ እዳ!

ቅድስት አሁንም እያንጎራጎረች ነው ”የቤቴ ወለሉ ጣራ እና ግድግዳው ” የቤታቸውን ግድግዳና ጣራ ከውጭ በኩል በረዥም መጥረጊያ እያፀዳች ነበር ቆንጆ ናት ፀይም ቆዳዋ ጥርት ያለ በተለይ እንዲህ ከኋላዋ ሁኖ ስትንጠራራ ላያት የአቦሸማኔ ሽንጥ ቅድስት ቆንጆ ናት እንደው ተፈራርተን እንጅ እኔና ቅድስት ሳንከጃጀልም አልቀረን ባየኋት ቁጥር አቅፈህ ሳማት ሳማት ይለኛል እሷም በሰበብ አስባቡ እቤቴ ጎራ ማለት ታበዛለች ግን እንፈራራለን

ቅድስት፣ አርሴማ ፣ሃያት ፣ጀሚላ፣ ሜሮን ሂሩት እና ሄለን አረብ አገር ለስራ ሂደው የተመለሱ የመንደራችን ሴቶች ናቸው ያልተመለሱትን እማ አረብ አገር እዛው ይቁጠራቸው

መጀመሪያ አረብ አገር የሄደችው አርሴማ ነበረች እናዳሁኑ ባልተለመደበት ጊዜ ታዲያ አርሴማ ብዙ አልቆየችም ባልታወቀ ምክንያት በሶስት ወሯ ተመለሰች ዘጠኝ ወር ሲሞላት ግን ምክንያቱ ታወቀ ወንድ ልጅ ተገላገለች ! የመንደሩ ሰው እርጉዝ መሆኗን ካወቀበት ቀን ጀምሮ “የሚወለደው ልጅ አረብ ይመስላል አይመስልም “ እያለ ሲነታረክ፣ ሲወራረድና ብር ሲያሲዝ ከረመ አርሴማ የሚያምር ክልስ ልጅ ወለደች ገና ከአራስ ቤት ሳትወጣ ደግሞ መነሻው ያልታወቀ ወሬ ይናፈስ ጀመረ “አርሴማ የወለደችው ትሰራበት የነበረ ቤት ተቀጥሮ ከሚሰራ ፓኪስታናዊ ዘበኛ ነው “ ይሄ ወሬ ለጉድ ተናፈሰ “ቱ ለሞላ ወንድ “ተባለ “ አንገት ደፊ አገር አጥፊ “ ተባለ ይሄ ወሬ እድሜው ከሳምንት አላለፈም የመልስ ምት በሚመስል ሌላ ወሬ ተተካ

“አርሴማ ያረገዘችዉ ከኪዌቱ አሚር ሁለተኛ ልጅ አብደል ናስር ነሰረዲን ነው እነሱ ቤት ነበር የምትሰራው “ ይሄንኛው ወሬ ከመጀመሪያው የበለጠ ገነነ አንደውም በቅርቡ መጥቶ ሰፈራችንን በሊዝ ሊገዛውና ለአርሴማ በኢትዮጲያ አንደኛ የሆነ ህንፃ ሊገነባላት እንደሚችል ሁሉ ተወራ ” ሲወዳት መቸስ ለብቻው ነው እሷን ሲያይ ጥምጣሙ እስኪበር ነው በደስታ የሚምነሸነሸው “ እየተባለ ወሬው ደመቀ ጥምጣሙ እስኪበር የሚያፈቅር የአሚር ልጅ እዚህ ጭርንቁስ መንደራችን ውስጥ መጥቶ ለማየት እኔ ራሱ ጓጓሁ የፍቅርን ሃያልነት ለመታዘብ አሰፈሰፍኩ

ህፃኑን ልጅ አያቱ “ሃይለሚካኤል” አሉት! ሃይለሚካኤል አብደል ናስር ነሰረዲን በዚህ ሁኔታ የመንደራችን አባል ሆነ (አረቡ ይሉታል በቅፅል ስም በኢትዮጲያና ኪዌት መካከል ወደፊት ለሚኖረው ወዳጅነት ይህ “ታሪካዊ” እንበቀቅላ ታላቅ ሚና ሳይኖረው አይቀርም ሂሂሂ) አድጎ አስር አመት እስኪሆነው ግን አባቱ ነኝ ያለ የአሚር ልጅ አልታየም ። አንድ ቀን ታዲያ አያቱ “ አሚሩ ቀርቶበት ዘበኛውም በመጣና የአባትን ጣእም ባወቀው” አሉ በቁጭት

ከአርሴማ በኋላ ሜሮንና ጀሚላ አረብ አገር በመሄድ ሁለት አመት ቆይተው ተመለሱ እነጀሚላ ቤት አዲስ መንጣፍ ስለተነጠፈ ጫማ ሳያወልቁ መግባት ተከልክሎ ነበር በአንድ እግሩ ምንጣፉን የረገጠ እንግዳ በጀሚላ ጩኸት ሁለተኛ እግሩን በአየር ላይ እንዳንጠለጠለ ደርቆ ይቆማል እማማ ሃዋ (የጀሚላ እናት) ታዲያ " ይሄን ምንጣፍ ወዲያ አንሽልኝ ስታመም ጠያቂ ሲቸግረኝ ደራሽ ጎረቤቶቸን አሳቀቀብኝ" አሉ ሲቆይ ግን ምንጣፉም ቆሸሸ መአቀቡም ተነሳ መጀመሪያ ቤተሰቡ ከዛም ሁላችንም መንደርተኞች ከነጫማችን መግባት ጀመርን

ሜሮን እንደመጣች አካባቢ ደግሞ የተረፈ ምግብ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እየደፋች አስቸግራ ነበር "ኧረ ለልጆቹ መቅሰስ ይሆናል እህሉን አትድፊ ጡር ነው" ብትባል "ላላ ላላ" እያለች መገልበጥ ሆነ ከወራቶች በኋላ እንኳን ሊተርፍ ዋናውም እያነሰ ቤተሰቡ መነጫነጭ ስለጀመረ እህል መድፋቱ በዛው ቆመ

አረብ አገር የሄዱት ሁሉ ኩንትራታቸውን ጨርሰው ባንዴ ወደመንደራችን በመጡበት ወቅት የሚገርም የባህል የኢኮኖሚ የቋንቋ መቀየጥ ተከሰተ ፓስፖርት ፣ቪዛ ፣ኩንትራት፣ በርሚል ፣ ካርጎ ፣ ጉሙሩክ፣ ሃቢቢ ሃቢቢቲ የሚሉ ቃላት ተዘወተሩ በመንደራችን ሻይ አብዝቶ መጠጣትና ሩዝን ከእንጀራ እኩል ገበታ ላይ ማቅረብም ተለመደ በሳተላይት ዲሽ የአረብኛ ፊልሞችና ተከታታይ ድራማወችን ማየትም አንዱ ለውጥ ነበር

እርስ በእርስ መንደርተኞች ሲጣሉ አረብኛ ስድቦችን መቀላቀል ሁሉ ተጀመረ እንደውም አንድ አረብኛ ስድብ ለእኔም ደርሶኛል ቅድስት የአስቴርን ሲዲ ልትዋስ ቤቴ ስትመጣ በቃሌ የሸመደድኩትን ግጥም ብቻየን ሳነበንብ ደረሰችና "መጅኑን " አለችኝ በኋላ ሜሮን እንደተረጎመችልኝ ከሆነ "ወፈፌ " ማለት ነው አሉ

በዚህ ወቅት ሂሩት አረብ አገር እሄዳለሁ ብላ ተነሳች "እንዴ ደግሞ አንች ምን አጣሽ ኑሯችሁ ጥሩ ትምህርትሽን እየተማርሽ ነው " ብትባል " እንዴት ነው ምን አጣሽ ተውኝ ተውኝ እባካችሁ ሆድ አታስብሱኝ ያጣሁትን እኔ ነኝ የማውቀው የመንደሩ ሴት ሁሉ በአረብኛ ሲሰዳደብ እኔ እስከመቸ በአማርኛ ስሳደብ እኖራለሁ ማን ከማን ያንሳል" አለች እንባ እየተናነቃት ሄደችና ሁለት አመት ቆይታ ብዙ አረብኛ ስድቦችና አንድ በርሚል ልብስ ይዛ ተመለሰች

አስገራሚ በሆነ ሁኔታ በርሚሉ ውስጥ ሙሉ የቤሩት መቶ አለቃ ዩኒፎርም ተገኘ የሂሩት አባት ያንን ግጥም አድርገው ለብሰው አንዳንድ ቤሩት ኑረው የመጡ ሴት እህቶቻችንን በሰላም አገር ሲያስደነግጡ ከረሙ ሂሩትም ሃሜት አልቀረላትም "ፖሊስ ቤት ተቀጥራ ነበር የምትሰራው ልብሱን ሰርቃ አምጥታ ነው አሏት "

ሂሩት ግን አንድ ቀን ቁጭ ብለን ስናወራ "ስለዩኒፎርሙ" ይሄን ታሪክ ነገረችኝ አንድ መቶ አለቃ ሂሩትን ድንገት አያትና በፍቅሯ ተነደፈ መጀመሪያ በሃር የተጠለፈ መሃረሙን ላከላት (የፍቅር መግለጫ መሆኑ ነው) ዝም ስትለው አሃ አንሶብሽ ነው በማለት የፖሊስ ኮቱን ከነሙሉ መአረጉ ላከላት በመጨረሻ መልስ ሲያጣ ሱሪውን ላከላት በሱሪው ተጠቅልሎ ደግሞ ክላሽ እንኮፍ ጠመንጃው አብሮ ነበር እንግዲህ ወንድ ልጅ ሱሪና ጠመንጃውን ከሰጠ ምን ቀረው ይሄ ሚስኪን አፍቃሪ ፖሊስ እስካሁን በፓክአውትና በግልገል ሱሪ በቤሩት ጎዳናወች ላይ ግዳጁን እየተወጣ ይገኛል(አያድርስ ነው አይሳቅም! እኔስ አለሁ አይደል ለዛች ሰላቢ ሰብለ ነብሴን ሰጥቸ እርቃኔን የቀረሁ)

ሂሩት የኒፎርሙንም ክለሽንኮቭ ጠመንጃውንም ይዛ ወደኢትዮጲያ ስትገባ ኤርፖርት ፍተሻ ላይ ተያዘች

"መሳሪያው አያልፍም ይወረሳል ዩኒፎርሙን ችግር የለም ማስገባት ትችያለሽ "አሏት ፈታሾቹ

"ኧረ የሰው ስጦታ ነው በናታችሁ " ብትላቸው

"ህግ ነው" ብለው ግግም አሉባት ወደሃላፊው ቢሮ ገብታ ጉዳዩኝ ነገረችው ገና "ክላሽ" ስትለው " አያልፍም" አላት በቁጣ

"ምናለበት ባታካብዱ ባንድ ጠመንጃ መንግስት አይገለበጥ " አለችው ግልፍ ብሏት

“ዋይ ተይ ባክሽ እኛም ደርግን ስንገለብጠው ባንድ ክላሽንኮቭ ነው የጀመርነው ” ብሎ ሸኛት!!

ሂሩትና ጀሚላ “ዩኒፎርም ሰርቃለች” በሚው ሃሜት አቧራ ያስነሳ ፀብ ገጠሙ በአረብኛ እና በአማርኛ ነበረ ስድድቡ ቅድስት መሃል ገብታ እየገላገለች እግረ መንገዷን አረብኛ ስድቦችን ለእኛ ለመንደርተኞች ትተረጉምልን ነበር፡፡

“ከልብ “ አለች ሂሩት ጀሚላን ቅድስት “ኧረ እንዲህ አይባልም እግዜር አይወደውም ሂሩት “ በማለት ነገሩ እንበርድ እየሞከረች ወደእኛ ዞር ብላ

“ከልብ ማለት ውሻ ማለት ነው፡፡“ ትለንና ወደመገላገሏ ትመለሳለች

እልልልልልልልልልልልልለልልልልልልል እሁድ መሸ ! ድንገት ቅድስት ዝንጥ ብላ እቤቴ መጣች ከሰአት ሰርግ ነበራት ኡፍፍፍ የለበሰችው ረዥም ቀሚስ እንዴት እንዳማረባት

ስናወራ ቆየንና “ለምን ቡና አናፈላም” ብላ ሳታስፈቀደኝ ማቀራረብ ጀመረች ባንዴ ቤቱን ነፍስ ዘራችበት እጣኑ ተጫጭሶ ሙዚቃው ተከፍቶ ቅድስት ፊት ለፊቴ የሚያምር ጠይም እግሯ በቀሚሷ ቅድ እየታየ እንደተቀመጠች ደስታ መላ ሰውነቴን አጥለቀለቀኝ እውነቱን ልንገራችሁ አይደል ማግባት ሁሉ አማረኝ፡፡

በድፍረት “ዛሬ ለምን እዚህ አታድሪም አልኳት “

ባለጌ ስትለኝ ላለመስማት ጆሮየን ልይዝ ነበር

“እና ካሁን በኋላ ልሄድልህ ነው “ ስትለኝ ማመን አልቻልኩም ዞር ብየ አልጋየን አየሁት እስከዛሬ እዚህ ባህር ላይ ብቻየን የምንሳፈፍ ሚስኪን ጀልባ መሆኔ ተሰማኝ ዘልየ አቀፍኳትና ግጥም አድርጌ ከንፈሯን ሳምኳት ”ሂድ መጅኑን” አለችኝ እንደዚህ ቃል አሪፍ የፍቅር ቃል ሰምቸ አላውቅም ራሴ ስተረጉመው “ በፍቅር የወፈፈ” ማለት ሳይሆን አይቀርም !! “ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም “ እደግመዋለሁ አባ ልክ ናቸው

የእሁድ ሌሊት እንዴት አጭር ነው ለዚህ ጊዜማ ይጣደፋል !!

# "ሽረኛ" " እና " "ደህና" በአንድ ላይ ሲሄዱ በሽረኛው በኩል ተናደ መንገዱ

## ይህ ተከታታይ ወግ ሁለት ክፍሎች አሉት

## ክፍል 1

ሽረኛ

የዶ/ር ደበጫ እርገጤ መዝገበ ቃላት ሽረኛ የሚለውን ቃል ሲያብራራው እንዲህ ይላል ሽረኛ - ስም እንዳገባቡ "ተውላጠ ስም" እንዳወጣጡ "ግስ" ሳይገባም ሳይወጣም እራሱን ችሎ አረፍተ ነገር !!

ትርጉሙ (በተንኮል የሰው ማንነት ፣መልካም ስም ፣መልካም ስራ፣ መልካም ግንኙነት የሚሸረሽር የሚሰረስር የሚቦረቡር የሚደረምስ የሚያጠለሽ ) ይለዋል !! መዝገበ ቃላቱ ይሄን ሁሉ ነገር ከሚያንዛዛ በቀላሉ መግለፅ ይችል ነበር ልክ እንደዚህ

ሽረኛ - ሰው- አቶ እጅጉ!! በቃ!! አጭር ግልፅና ወቅታዊ ፍች !!

ምሳሌ አቶ እጅጉ ሽረኛ ነው ትክክል!! ይሄ ምሳሌ አይደለም እጅጉ (እጅ እግሩን አስሮ ሲኦል ይወርውረውና) "ሽረኛ" ነው !! ሽረኛ ብቻ አይደለም ምቀኛ ነው የሚቀናበት ነገር ቢያጣ እኩል በተሰጠን 24 ሰአት ይቀናል !! ("እንደው በየትኛው ጊዜ ብትማሩት ነው ይሄን ሁሉ ነገር ያወቃችሁት " ይላል የማያውቀውን ነገር አውቀን ካገኘን ! ለነገሩ እሱ ምንም አያውቅም ) ምን ይሄ ብቻ እግዜር በፈጠረው አየር ሳይቀር የቀናል የቢሯችን መስኮት ተከፍቶ እንደልብ አየር ሲገባ ብቅ ይልና " ይሄን አየር " በነፃ ትሉታላችሁ" ይላል (እንክፈል) ሽረኛም ምቀኛም ብቻ አይደለም መሰሪ ተንኮለኛ ነው (አሟልቶ አይሰጥም ይባላል እንጅ ይሄው የተሟላ ከፉ ሰው )

እንግዲህ ሽረኛ ምቀኛ..መሰሪ ሁኖ ደግሞ አለቃየ ነው !! ጥሎበት አይወደኝም እኔም ስለማልወደው "ተመስገን ቢወደኝ ምን ይውጠኝ ነበር" እላለሁ ሁልጊዜ! ለምወደው ሰው ነው የምጨነቀው። አሁን በዚች ቅፅበት በሆነ አጋጣሚ ነገር ሎተሪ ምናምን አይነት እድል ገጥሞኝ በድንገት የብዙ ብር ባለቤት ብሆን (ኧረ የትንሽም ቢሆን ) የመጀመሪያ ስራየ ሁለት እጆቸን ኪስና ኪሴ ከትቸ በቀዳዳ ኪሴ ውስጥ በሾለኩ ጣቶቸ ራቁት ታፋየን በማፏጨው ሙዚቃ ሪትም እየተመተምኩ ጀነን ብየ ወደአለቃየ ቢሮ እሄድና እንኳኳለሁ ኖ ኖ ! አላንኳኳም ! በሩን በእግሬ ገፋ አድርጌው እገባለሁ!!(ካፈቀሩ ከነፍስ ከጠሉም ከነፍስ ነው የምን ማስመሰል ፊት ለፊት ጉማሬ ፊቱ አለቃየ ሁልጊዜ በሚደፈርሱ አስቀያሚ ደመኛ አይኖቹ ያፈጥብኛል ቀጥሎ ኪሶች ውስጥ የወሸኳቸውን እጆቸን በቁጣ ያያል (ደንግጨ ከኪሴ እንዳወጣቸው እንድርበተበት) ፀጥ ብየ በትእቢት ሳየው የኢትዮጲያን ሲጋራ ሁሉ ብቻውን ያጨሰ ከሚያስመስሉት አስቀያሚና ገጣባ ከንፈሮቹ ቃላት ይፈለፈላሉ ሰው ሰው የማይሸቱ እብሪተኛ ቃላት ።

ምናልባትም "ብላችሁ ብላችሁ ማንኳኳቱንም ተዋችሁት " ይል ይሆናል (እግዜርና ሰይጣን ለዚች ቅፅበት እርቅ አውርደው ይሄን ድንጋይ ራስ አለቃየን በመዶሻ ያንኳኩትና ) ወይም "ኪስህ የወሸከውን እጅህን አውጣ " ሊልም ይችላል አላወጣም ! ( ኪሴ ቀዳዳ ቢሆንም ቀዳዳውን ተሻግሮ ያለውም ወንድነት የራሴ እርስት ነው ዘራፍ! በቀዳዳ እኛነታችን ውስጥ እያለፉ ወንድነታችንን ያኮላሹን ከፉወች ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ አድርጉ ያሉትን አናደርግም )

ኮራ ብየ "እእእእ አቶ እጅጉ " እለዋለሁ !!( "አቶ" በማሾፍ ሲጠራ እንዴት ያለ አሪፍ ስድብ ነው) ለምሳሌ እኔ "አቶ" ከሚለው ቅፅል ይልቅ ከስሜ በፊት ሰሃራን የሚያህል ባዶ ምድረ በዳ ቢዘረጋ ይሻለኛል !! በተለይ አለቃየ

“አቶ” ከሚለኝ !! አዎ !እሱ “አቶ” ሲለኝ በውስጡ “መቸም ለአቶነት አትበቃም በቾርነቴ አቶነት ልስጥህ እስቲ “ የሚል ይመስልበታል !! አቷም!!

እና “አቶ እጅጉ ከዛሬ ጀምሮ ስራ ለቅቂያለሁ” እለዋለሁ በኩራት !! “ እእእእ “ የምትለዋን ዘገምተኛ ቃል ማስቀደም አረሳም !! አራት አመት ሙሉ የሱን አስቀያሚ “እእእ” ቾየ ኑሬ የለ ስለዚህ የምለው እንደዚህ ነው “ እእእእ አቶ እጅጉ ከዛሬ ጀምሮ እእእእ ስራ ለቅቂያለሁ!! “

ይደነግጣል አያምንም!! እኔ ስፈጋ የዋልኩበትን ስራ ሁሉ ለአለቆቹ እንዲህ ሰርቻው እንዲህ አድርጌው እያለ በስልክ መወሸከቱ ሊቆም ስለሆነ ይደነግጣል እሰይ ! ወሽካቶች መደንገጥ አለባቸው !!

ወዲያው የበሰበሰ የማኔጅመንት “ሲስተሙን” እኔ ላይ ሊሞክራት ይፍገመገማል “አትደንግጥ የበታች ሰራተኛህ ፊት አዋቂ ልበ ሙሉ ምንትስ ሁነህ ቅረብ ባትሆንም ሁን ” የምትለዋን ያስብና ጉሮሮውን ጠራርጎ ”እእእ እዚህ መስሪያቤቱ ራስህን ለማሳደግም ሆነ ቤተሰብህን ለመርዳት አይሻልህም ?” ይላል ስራ ብለቅ ቤተሰቦቸ በረሃብ ዛሬውኑ የሚያልቁ በሚያስመስል ሁኔታ “ቤተሰብ” የምትለዋ ቃል ላይ ላይ አፅኖት ሰጥቶ !!

ክፉዎቾ መሳሪያ ልጅህ ላይ ባይደግኑም እናትና አባትህን አፍነው ባይወስዱም የነገን ጨለማነት እየነገሩ ያግቱሃል !! ስንቱ መሰለህ ቁራጭ ዳቦ እንዳይነሱት ፈርቶ ለማንም አጋሰስ ጉልበቱን የሚገፈግፈው ስንቱስ ነው “ከስራ መባረር” የሚባል የታንክ አፈ ሙዝ ልቡ ላይ ተደግኖበት ዘመናዊ ባሪያ የሆነው!! ስንቷን ሚስኪን በፀሃፊነት ስም የጭን ገረዱ ያደረጋት ጋንጩር አለ ቢሮ ይቁጠረው !!

ሃላፊ ሲባል አርቲስት ነው ወንበሩን መድረክ ያደረገ ተዋናይ ያውም ድብን ያለ ትራጀዲ የሚተውን እና እኔ ምን እለዋለሁ ” ሃሳቤ ደስ ብሎኝ ሳምሰለስል

ዙፋን ዘው ብላ ወደቢሮየ ገባቾ ጥሎባት ማንኳኳት አትወድም “አንኳኪ” ብሏት የሚያውቅም የለም

“አብርሽየ” ትለኛለቾ (ስሟን ከነአያቷ ቁስ ይጥራትና) ! ሁልጊዜ ስትጠራኝ እንዲሁ ነው ! ታዲያ አጠራረዋ ከማማሩ ብዛት እኔን ለጠራቾኝ ሌሎቹ “ወይየ” ሊሏት የዳዳቸዋል !!

“ እንዲህ በሃሳብ ጭልጥ ያልከው ወዴት ሂደህብኝ ነው ” ወዴትስ ብሄድ ምን አገባት ጭራሽ የምሄደውስ የምቀረውስ ለሷ ነው እንዴ (ሂደህብኝ !! ጥርግ ብል እንትናየ እያለቾ አንዱ ቢሮ ልትንኳተት )

“ እ ምነው ጠፋሽ “ አልኩ እንደመጣልኝ የምለው አጥቾ እንጅ ዙፋን ደግሞ መቸ ጠፍታ ታውቅና በአንድ ጊዜ ሰባት ቢሮ ውስጥ የምትገኘውን ዙፋንን ጠፋሽ ማለት መሬትን “ ምነው በዚህ ሳምንት መዞርሽን አቆምሽ “ ብሎ ከመጠየቅ አይተናነስም !!

“ ሆሆ ከየት ተገኘሽ አሁን እንኳን ስመጣ አራተኛየ ነው “ አለቾና ከጠረንጴዛየ ፊት ለፊት ወንበር ስባ ተቀመጠቾ ወንበሩ ተንጫጫ ጉርድ ቀሚሷ ቀይ ታፋዋን ወለል አድርጎ ያሳያል ኤጭጭጭጭጭጭጭ!!

“ቆንጆ ናት “ ይባላል ትሁት ናትም ይሏታል የሰለጠነች ሰው አክባሪ የሚሏትም ብዙ ናቸው  እንደው ባጠቃላይ እዚህ ቢሮ ዙፋንን ለማናገር ለማቅረብ ቢመቸው ወደአልጋው ጎትቶ አብሯት ለመጋደም የማይመኝ ያለ አይመስለኝም

ዙፋን እኛ ቢሮ ስራ ስትጀምር ከስራ ልምዷ ጋር ከእግዜር የተላከ “ከዛሬ ጀምሮ “ያየ አመነዘረ “ የሚለው ጥቅስ ተሰርዟል “ የሚል ደብዳቤ ይዛ የመጣቾ ይመስል እዛ ፋይናንስ ከሚሰራው ዲያቆን ወልዱ ጀምሮ ሰው ሰላም ሲል አገጩ መሬት እስኪነካ የሚጎነበሰው ጴንጤው ምክትል ሃላፊያቾን የዙፋንን እግርና መቀመጫ አይተን እንሙት አሉ!! ዙፋንም ታዲያ የእለት እንጀራዋ የሰው አይን ይመስል ነገረ ስራዋ ሁሉ የታይታ ነው !! አቤተ መታየት ስትወድ ሰው ከኋላዋ እንደሚያያት ከጠረጠረቾ ለክፉ ቀን ያስቀመጠቾውን መቆናጠር ሁሉ ትጠቀምበታለቾ !!

ጥሎብኝ አልወዳትም እሷም ታውቀዋለች ! ምንም ትልበስ እንዴትም ትራመድ እንደገለባ ትቀልብኛለች !! ብትሞት ቢሮየን ሳትረገጥ አትውልም ( ዛሬስ እንዴት ነኝ አይነት ) የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ፀሃፊ ናት ቅርብ ጊዜ ነው የተቀጠረችው (ሃሃሃ ወይ መቀጠር ቅጥረኛ ነብሰ ገዳይ)

የአለቃየ አለቃ ፀሃፊ ናት። የተመቻት የሃብታም ልጅ እቤት ከመዋል ብላ ፀሃፊ የሆነች ። እሷ "ፀሃፊ" ሲሏት አትወድም "ሴክሬታሪ" ነኝ ነው የምትለው ውድ ልብሶችን የምትለብስ በተረከዘ ረጅም ጫማ ከቢሮ ቢሮ "ስታውደለድል" የምትውል ቆንጆ እንዴት ፀሃፊ ትባላለች የሚያማልሉ ቀያይ እግሮች ያሏት የከረመ እና የታጀለ የወረቀት ጠረን የሞላውን ቢሮ በሽቷ የምትፈውስ ዙፋን እንዴት ፀሃፊ ትባላለች ሳያት ገና እንደረኸምና እንደማያልቅ መንገድ ትደከመኛለች እንደለዛ ቢስ ረኸም ወሬ ትሰለቸኛለች ከልቤ ትሰለቸኛለች ባትመጣብኝ ደስታየ ነው ይሄንን ነገር ማመን አልቻለችም በሂወት ዘመኗ እንደኔ ፊት ነስቷት የሚያውቅ ወንድ ያለም አይመስለኝም

ትለዋለች በተዘዋዋሪ " እከሌ እኮ ጨዋ ነው የኔ ጌታ እሱን ያገባች የታደለች ቢሮው ስሄድ ከወንበሩ ብዲግ ብሎ ስራውን እርግፍ አድርጎ ትቶ እኮ ነው የሚያዋራኝ " እንኳን ተነሳላት ! ለምን ከመነሳት አልፎ ዘሎ ኮርንሱ ጋር አይጋጭም እንኳን ለደይቃ ስራ ማቆም ለምን የስራ መልቀቂያ አያስገባላትም አዝግ ታዝገኛለች ኮተታም ክብር አሳዳጅ

የጠላሁባት ምክንያት እንደአንዳንድ ወንዶች ከራሳቸው ጋር ፈተና ሲገቡ መሻታቸውን ሊሸሹ ሴት እንደሚየንቋሽሽት አይነት አይደለም ቁልጭ ያለ አገር ያወቀው ፀሃይ ያገረረው በአምባ ገነን እግሯ ምንም በሆነ ሴትነቷ ፍትህ ተረግጣለች ! ያማረችው በሚስኪኖች እንባ ታጥባ ነው ንፅህናዋ ንፁህ ነብሳትን ትቢያ አድርጋ ነው ያውም ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ሚስኪኖችን ሽረኛ ናት ዙፋን ሽረኛ ናት አለቃየ ሽረኛ ነው እዚህ የተሰበሰቡ ወተፈናም ሃላፊ ተብየወች ሁሉ ሽረኞች ናቸው

እና መዝገበ ቃላቱ እና የምትለዋን ቃል አያየኸ ብቻዋን የማትቆም ቁንፅል ይላታል

በአጭር ምሳሌ እና እኔ ነኝ በሽረኞቹ እና በደህነኞቹ መሃል ያለሁ ወይ አልሸርር ወይ አልደህንን "እና" እኔ ነኝ ምንም ታሪከ ምንም ትርጉም የለኝም ስራየም ባህሪየም በሆኑ ነገሮች መሃል መደበቅ ይበዛበታል እና ነኝ !! እና ምን ይጠበስ

ደህና እማማ መለኮት መዝገበ ቃላቱ ሳይሆን መዝገበ እግዚሃር "ደህና" ብሎ የሚላቸው አይነት እማማ መለኮት እድሚያቸው አምሳ ሁለት ወይም አምሳ ሰባት (እራሳቸው እንደሚት) ትሁት በዚህ እድሚያቸው ለሁሉም ሰው ታዛኸ እና የሁላችንም መካሪ እማማ መለኮትን የማይወድ ማንም የለም መስፈሪያው ቢለያይም በምንም ይሰፈር በምን እንደኔ የሚወዳቸው ግን የለም!!

የዛሬ አመት አካባቢ እማማ መለኮት ቢሮየ መጥተው ከጠረንጲዛየ አንድ ሁለት እርምጃ ራቅ ብለው ቆሙና ከወገባቸው ጎንበስ በማለት ሰላምታ አቀረቡ (ለእኔ እማማ መለኮት ጎንበስ አሉ) ያረጁ ይመስላሉ ፊታቸው በሃዘን አኮፍኩፎ በእድሜ እናቴን ይበልጣሉ ከወንቤ ተነስቸ ለሰላምታ እጄን ዘረጋሁላቸው በሁለት እጃቻቸው አሁንም ጎንበስ ብለው ሰላም አሉኝ !እጃቸው ይሻክራል ልክ እንደእናቴ እጅ እነዚህ ሞረድ እጆች የስንቶቻችንን ባለ ለስላሳ እጆች ሂወት እንደሞረዱ ፈጣሪ ይወቅ !

እንዲቀመጡ ወዳመለከትኳቸው ወንበር ቀስ ብለው ተቀመጡና የመጡበትን ጉዳይ ቀስ ብለው አስረዱኝ

" አቶ አብረሃም (አቤት አቶ በሳቸው አንደበት እንዴት ክብር እንዳለው) ያው እንደምታውቀው..እዚህ ቤት ነገረ ስራቸው ሁሉ ውስጥ ለውስጥ ነው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል በሰራሁ ለትንሽ ትልቁ እሽ ብየ ባደርኩ ድንገት ከስራየ ነቀሉኝ " አሉና እንባቸው ተዘረገፈ እድሜ በሸነተረው የቆዳቸው እጥፋት ሽብሽብ ውስጥ እንባቸው ጎረፈ በነጠላቸው ጫፍ አይናቸውን ጠረጉ (አዚች ባልቴት ውስጥ ይሄ ሁሉ እንባ እንዴት ሊኖር ቻለ እድሜ ልካቸውን ያጠራቀሙት ይሆን) እማማ መለኮት ከፅዳት የስራ መደብ ተነስተው በሃያ አመት የቢሮክራሲ ባቡር ጉዘው ፀሃፊ

ለመሆን የበቁ ፅኑ ሴት ናቸው ! ከልምድ እንዳየሁት ብዙ ታላላቅ ድርጅቶች ሱፍ ለብሰው በሚኮፈሱት አለቆቻቸው ሳይሆን በሚስኪኖች ትከሻ ላይ ተጨነው ነው የቆሙት እማማ መለኮት የድርጅታችን ዋልታ ይሄው ተባረሩ

ከዛ በፊት ከመባረራቸው በፊት አሽሙር የሚመስል ስብሰባ ተደረገ አንዲት እረዳት የሌላቸው ሚስኪን ባልቴት ለማባረር ቱባ ቱባ ባለስልጣን ከቱባው የተተረተሩ ክር አቃጣሪወች እና "እናወች" ውሃ ቡና ቀርቦ ስብሰባ ተደረገ የስብሰባው መሪ ሽረኛው እጅጉ ፀሃፊው ሽረኛው አለሙ ተላላኪው ወሬ አቀባዩ (እንደ ሰው አልባ አውሮፕላን እያንዣበበ ለላኩት አለቆቹ ወሬ ይቃርማል "መታዘዝ ፅድቅ ነው" ሲባል የመታዘዝ ፅድቅነትን የማያመዛዝን አይምሮ ተሸክሞ የሌሎች ባሪያ መሆን ማለት አይደለም ሰበአዊ ትዛዝ ሰው መሆን "ይቅርብህ" ተብለህ ሳይሆን ለኔ ማለት ይቆየኝ ቅድሚያ ለሌሎች ከሚል በጎነት መነሳት ነው በጎነት በትዛዝ አይመጣም )

ስብሰባው ተጀመረ ለአንዲት ባልቴት ተሰበሰቡ እንዳይባል የማይረባ አርሲ ኩርሲ አጀንዳ ጋር ተደምሮ የእማማ መለኮት መባረር "መቀነስ" የሚል የዳቦ ስም ተሰጥቶት አጀንዳ ሆነ

ባንድ ላይ ሲሄዱ መዝገበ ቃላቱ በአንድ ላይ መሄድን በአንድ ላይ ከመታየት ነጥሎ አለማየቱ ትልቅ ጉድለት ነው

" ሽረኛ " "እና" "ደህና" ስብሰባው ላይ በአንድ ላይ ተገኛንን በማገኛችን በኩል መንገዱ እንደሚናድ ልናይ ቀድሞ የተናደውን

ተናደ

# (ክፍል 2)

ስብሰባውን የጀመረው አለቃችን አቶ እጅጉ ነበር ኩፍስ ብሎ የኮቱ እጥፋት ሸብዳዳ ትከሻው ላይ ተከምሮ ( ከኮቱ ውስጥ ትንሽ የሶፋ ትራስ ያስቀመጠ ይመስለኛል) ጨዋ ለመምሰል በሚዳዳው ድምፅ ስብሰባው መጀመሩን አረዳ (አበሰረ የሚሉም አሉ "ከሽረኞች ወገን ናቸው" )

"እ ያው እንደምታውቁት " አለ (ምንም በማናውቀው ነገር) " መስሪያ ቤታችን ያለውን መልካም ስምና ዝና ለማስቀጠል (ሂሂሂሂ ጉድ ፈላ በቀን የሚመጣው ባለጉዳይ ሁሉ እየየየ እያለ ተራግሞ የሚሄድበት መስሪያ ቤት "መልካም ስምና ዝና ይሁና ) ዘመናዊ የአሰራር ሲስተምና ዘመን አፈራሽ መሳሪያወች እንደሚያስፈልጉ በማመን የተለያዩ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ወስደን እየተንቀሳቀስን "ያለበት ሁኔታ ነው ያለው"

እነዚህ ዘመናዊ መሳሪያወች ደግሞ ብቻቸውን "ጠብ" የሚል ለውጥ እንደማያመጡ "እሙን" ነው ። ስለዚህ ቢሯችንን "በአመለካከት" "በእውቀት" "እና" "በተግባር" መሳሪያወቹ ጋር አብሮ በሚሄድ "ወጣት" የሰው ሃይል" ማደራጀቱ ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ተግባር ነው !! "

በእማማ መለኮት በኩል መንገዱ ተናደ ጨዋነትን የጫነው መኪና ገደል ገባ ትህትና ተሽቀነጠረ መንገድ ስለሌለ ወደኋላ ተመለስን መንገድ አፍራሽ ሽረኞች ራእይ እንደህልም ያያል እንጅ ከመድረስ ተጣልቷል ! መንገድ የለማ !! ከአባይ ወዲያ ማዶ ያለ ዘመድ ሆነ የእማማ መለኮት ስራ እንባቸው በአይናቸው የሞላ እለት ዋይ ብለው ቀሩ!!

አንዲት በእድሜ የገፉ ሚስኪን አባሮ በየቢሮው እየዞረች ምስጋና የምትቀላውጥ ገልቱ ለመቅጠር ምድረ ጉማሬ ሚስኪኑን ላብ አደር ሰብስቦ አላዘነ ደግሞ ስለዘመናዊነት ያወራሉ እግዚኦ አለቆቻችን ስለዘመናዊነት አወሩ ስልካቸው ባትሪ ሲጨርስ ተበላሸ ብለው ስሪ ቤት የሚሮጡ አለቆቻችን ዘመናዊነትን ሰበኩ ከፕሪንተር የሚወጣ ወረቀት ደመና ሰንጥቆ እንደሚወጣ መለአክት በግርምት የሚመለከቱ( አይ ፈረንጅ ነብስ መፍጠር እኮ ነው የቀረው እየተባባሉ) አለቆቻችን ዘመናዊ እንሁን አሉ

እማማ መለኮት በጡረታ ስም ተባረሩ (ተቀነሱ በል አቶ አብረሃም ተብያለሁ) ዙፋን ተቀጠረች ”(((አሁን ድርጅቱ ዘመናዊ ሆነ “))) እንደምን ዋላችሁ “ሃይ ጋይስ “ በሚል ሰላምታ በመተካቱ እልልል ቢሯችን ዘመናዊ ሆነ

ዙፋን የዘመናዊነት ፋና ወጊ አንድ ገፅ ደብዳቤ ስትፅፍ አንድ ከግማሽ ገፅ ስህተት የምትዘራ ጉድ ወሬ ብቻ መሽኮርመም ብቻ በየስሙ ላይ “የ” መጨመር ብቻ (አብርሽየ ቶማስየ ጋሽ ሰይድየ ተፈራየ ሃጎስየ ገኒየ እግዚያብሄርየ ጀሰስየ ) እንደየ ፊደል ትልቅ አፍ ብቻ ያላት መርገምት ደህና ነገር ሲናገር ከንፈሩ እንደደረቀ ሰው በየደይቃው ቻፕስቲክ እየተለቀለቀች በየቢሮው ማውራት !! (ውይ ጥርስ አታስከድንም ተጨዋች ምናምን ይላታል የሽረኛው መንጋ )

ቆንጆ ብቻ መሆን እንዴት ይቀፋል ሴት ብቻ በመሆን ከወንድ የሚቸር ወሲባዊ ክብር ምንኛ ውድቀት ነው እድሜ ከፍ ባለ ቁጥር የሚናድ የእንቧይ ካብ እንዴት ሰውን ያህል ፍጥረት ያውም እናትነትን ያህል አደራ ትቀበል ዘንድ ተፈጥሮ የወከለቻት “ሴት” ስለጥፍር አንድ ሰአት ሙሉ ታወራለች ስለፀጉር ሁለት ሰአት ስለጥፍር ቀለም ሙሉ ቀኝ ስለልብስ

የመታየት ልክፍት (ኤግዝቪዥኒዚም ይላዋል በሬቻ) በፋሽን ስም ነጋቸው ላይ ውበት ሊዘሩበት የሚችሉትን ዛሬ አርሲ ኩርሲ የውበት ኮተት እያወሩ ይፈጁታል ይሄ የሴት ውበት ነው የሴት ብክነት ስለውበት የሚደሰኩር ሚዲያ ላይ አፍጥጣ የምትውል ዙፋን ቆዳዋን በምናምን አደንድና ፍቅር እንዳይሰርፅ እራሷን ስታዋድድ ትኖራለች ሴት ከመልክ የተሸለ መወዳደሪያ ከሌላት ውድድሩ ውስጥም የምትኖረው ቢበዛ ጥቂት አመታት ነው ባካና! ዙፋን ባካና ናት ስሟ ራሱ እሷ ላይ ሲደርስ ዙፋን የሆነ የመወዘፍ አይነት ደውል ነው (ውዝፍ ከሚለው ስርወ ቃል የመጣ )

አለቃየ ጋር በአይኗ ስትዳራ ስንት ጊዜ ታዘብኩ እማማ መለኮትን ነቅላ ላትፀድቅ ነገር እራሷን የተከለችበትን ቆሻሻ መንገዷን አይቻለሁ!! ለፀሃፊነት ስራ ውድድር መሰለፍ የማይችል ባልጩት ጨንቅላቷ ላይ ሰው ሰራሽ ፀጉር ጎዝጉዛ ክቡር ሴትነቷን በየቢሮው ስትጎዘጉዝ ሳናይ አላወራንም “ጭስ ካለ እሳት አለ” ብለንም አይደለም ቆይቶ የተደረገ ግምገማ ላይ የተገደደች አስመስላ ቀባጠረችው እንጅ (የሽረኞች መንገድ የተናደች እለት)

ባለቤት የለሽ ስጥ ማንም አላፊ አግዳሚ የሚዘግናት ወንዶች በምናምናቸው እየተመሩ የሚደርሱባት ጥግ የሴትነት ባንዲራ ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባት ፀያፍ ምሰሶ ለወረደ የሴትነት ባንዲራ ሴሰኛ ወንዶች ሲዘምሩ ምሰሶው እንዴት “ቴንኪው” እያለ ይሽኮረመማል “

የእድሜ ጉዳይ ነው ያች የሴትነት ባንዲራ ትወርዳለች ያኔ ዘማሪ ሲጠፋ ሴትነት የተነጠለው “ሰው መሆን ብቻውን” ሲቆም ይሄ ከተማውን የሞላው አላፊ አግዳሚውን በቅናት ግልምጫ የሚጎነትል ምክሩ ላይ ስቆ የመከራ ዱላ መድረሻ ያሳጣው ፍቅር አልባ የሴት ፊት ሁሉ ዙፋን የተባለች መሃበርተኛ ይመረቅለታል

አቀባበል ይደረግላት ተባለ ዙፋን ሰው እንዴት ምንም ይቀበላል

በግ ታርዶ ቢራ ቀርቦ “አንዲት ፀሃፊ ለመቀበል ይሄ ሁሉ ድግስ” እንዳይባል ለአቀባበሉ ህዝባዊ ስም ወጣለት “የሩብ አመቱ የግምገማ ማጠቃለያ “ ሲበላ ሲጠጣ ሽረኞች የሽረኛ ልእልታቸውን ከበው እያውካኩ ጥሬ ከብስል ሲሰለቅጡ እማማ መለኮት ናፈቁኝ እንዲህ ዝግጅት ሲኖር እሳቸው ሌሊት ሁሉ እያደሩ ወጥ ይሰሩ ነበር አምስት ሳይከፈላቸው ነጭ ልብሳቸውን ለብሰው ምድረ ሆዳም ሲያስተናግዱ ይውሉ ነበር

መንገዱ

ከግብዣው ሹልክ ብየ ወጣሁና አጠያይቄ እማማ መለኮት ቤት ሄድኩ በራቸው ላይ ቁጭ ብለው የምስር ክክ እየለቀሙ ነበር ሲያዩኝ በድንጋጤና በግርምት ተርበተበቱ የምስር ክክ የያዘውን ትሪ ወደቀኛቸው ካለች መደብ ነገር ላይ ሲያስቀምጡ (((( የተለቀመው ካልተለቀመው ተቀላቀለ ))) እንደእኛ ቢሮ እንደእኛ ሃሳብ እንደእኛ

ፖለቲካ እንደእኛ እኛነት ተመልሶ መልቀም አዲስ እንግዳ ሃሳብ እንግዳ አሰራር እንግዳ ርዕዮተ አለም ሲመጣ ያከበርን መስሎን የሰራነውን ማፍረስ

ከመቀበጫቸው ብዲግ ብለው በአክብሮት ቆሙ “ ውይ በሞትኩት እዚህ ድረስ ምን አለፋህ አቶ አብረሃም እጀ ቆሻሻ ነው ቆይ “ ብለው ቀሚሳቸው ጋር ጠራረጉና በተስፋ እያዩኝ ጨበጥኳቸው (ምናልባት ወደስራ ልመልሳቸው የሄድኩ ይመስላቸው ይሆን) ግባ አሉኝ ገባሁ ንፁህና ጠባብ ናት ክፍላቸው ወደጓዳ መግቢያ ላይ ባለጥልፍ ነጭ መጋረጃ ባለመደገፊያ የቀርቀሃ ሶፋ ግድግዳ ላይ አንድ ጥቁርና ነጭ የትልቅ ሰው ፎቶ አለ(ባላቸው ይሆኑ) ከጎኑ ባለድግሪ ወጣት ባለቀለም ፎቶ እማማ መለኮት መጋረጃዋን ገለጥ አድርገው ወደ ጓዳ ገቡ

***** ********

ቡና እንደምወድ ያውቃሉ ላፍላልህ ሳይሉ ቡናውን አቀራረቡ አወሩኝ ስለነበረው

“ግራ ገብቶኛል እንቅልፍም አልወስድሽ ብሎኝ ነው ያደርኩት እንግዲህ በዚህ እድሜ ሰው ቤት ልብስ ላጥብ ነው ? እንጀራ ልጋግር ? እኔኮ ሌላው አይደለም ያሳዘነኝ ይሄን ያህል አመት ያገለገልኩበት ቤት ነው ምናለ ለወጉ ጠርተው እንግዲህ በቃሽ ቢሉኝ አቶ እጅጉ መጥቶ ስሜን እንኳን አልጠራኝም ይሄን ኮምፒተር አፀዳጅው እንግዲህ ጡረታ መውጫሽም እየደረሰ ነው “ በቃ እንዲህ ነው ያለኝ የዛሬን ቀን አያምሽልኝ እንዲሁ አለኝ ይባላል ? አቶ አብርሃም እስቲ ፍረድ ፍርድ ለራስ ነው መቸም ”

አለቀሱ እማማ መለኮት። የማደርገው ነገር ጠፋብኝ። “ብዙ ያየሁ ሰው ነኝ ይከፋኛል ማግኘትም ማጣትም ማጀቴን የጎበኘው ሰው ነኝ ባሌ የሞተብኝ ሴት ነኝ አርጅቻለሁ ልጀ ምጥ ይግባ ስምጥ የጠፋብኝ ብሶተኛ ነኝ ለትንሽ ትልቁ ደፋ ቀና የምለው ቀባሪ የለኝም የአገሬ ሰው ነው ቀባሪየ ብየ ነው እንዴት እንዲህ ያመንኩት ህዝብ ይተፉኛል እንዴት ባእድ እሆናለሁ አይዞሽ ማንን ገደለ ፀሃፊነቱን ይተውት እናትነት ይወረወራል ? አንድ ሰው በሬ ዝር አይልም ? በሃዘን በደስታው ከስራየ አልፎ ተርፎ ለድግሳቸው ጉልበቴን ገብሬ ቤታቸውን አላቀናሁም ? ፍረድ አቶ አብረሃም ፍርድ እንደራስ ነው ” ስኳር ወደስኒወቹ ጨመሩ መዝምታችን ውስጥ ቡናው ሲቀዳ ደስ የሚል ድምፁ ጠባቧን ቤት ሞላት አንዲት ክስት ያለች ጥቁር ድመት ገብታ ረከቦቱ አጠገብ ቆመች ለቡና ቁርስ ከተቆራረሰው ዳቦ ቆንጥረው ሰጧት

“እማማ መለኮት” አልኩ ቀስ ብየ

“ወይየ” አሉ ቡናውን እያቀበሉኝ

“ልጀ ጠፋ ነው ያሉኝ ?” ወይ ወሬ መውደድ አሁን የሰው ብሶት ከመቀስቀስ ውጭ ምንም ላልፈይድ ምን አጠያየቀኝ

“አዎ ይሄ ፎቶ የሱ ነው” አሉ ወደባለድግሪው ወጣት እየጠቆሙኝ ጭራሽ ተነስተው ፎቶውን ከተሰቀለበት አወረዱና ሰጡኝ መልከመልካም ወጣት ነው ሳቂታ

“ልጀ ነው አንድ ልጀ ስድስት ኪሎ በድግሪ ተመርቆ ወር ሳይቆይ ወደውጭ አገር ልሂድ ብሎ ተነሳ ኬኒያ የሚባል አገር ደረስኩ ብሎ ደወለልኝ ይሄውልህ ከዛ በኋላ ይኑርም ይሙትም ወሬው የለ “ ብለው እንባቸውን ዘረገፉት

“ከሄደ ቆየ ? ” በሃሳቤ ኬኒያ ያሉ ጓደኞቸን ይሄን ልጅ ካላገኛችሁ ወዮላችሁ ልል ተዘጋጀቸ

“እንግዲህ ወደአስራ አምስት አመት አይሆነውም ብለህ ነው ?” ፎቶው ላይ አፍጥጨ ቀረሁ

“ቡናው ቀዘቀዘብህ የኔ ነገር “ብለው ፎቶውን ከእጀ ተቀበሉና ቦታው መለሱት

ስናወራ ቆይተን እንደምጠይቃቸው ነግሪያቸው ስወጣ

“አቶ አብረሃም ካላስቸገርኩህ በቀደም ተጣድፌ እኔ መሳቢያ ውስጥ መሃረሜን ረስቸው መጣሁ እንደው ላቶ ሽበሩ ብትሰጥልኝ በዚሁ ሲያልፍ ያቀብለኛል” አሉ አቶ ሽብሩ የመስሪያ ቤታችን ሹፌር ነው !

ያችን ተአምረኛ መሃረም የቢሮው ሰው ያውቃታል እማማ መለኮት ፀበል ቤት ይሄዱና ወይም ቤታቸው ዝክር ቢጠየ ትኖራቸውና ለምንቀርባቸው ባልደረቦቻቸው የፀበል ቤት ዳቦ በመሃረማቸው ጠቅልለው ያመጡልናል በቀይ ክር የሃረግ ጥልፍ ዙሪያውን የተጠለፈበት መሃረም

***** ******* ******

በቀጣዩ ቀን ቢሮ ስገባ አቶ እጅጉ ደረጃው ላይአገኘኝና “አቶ አብረሃም ምነው ድግስ ረግጠህ ወጣህ “ አለኝ

“ኢጋሰስ” አላልኩትም።

የእማማ መለኮትን መሃረም ለማምጣት ወደዙፋን ቢሮ ሄድኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር እማማ መለኮት ከለቀቁ በኋላ ወደዚህ ቢሮ የመጣሁት ዙፋን አፏን ከፈተችው ” አ ንተ በመጨረሻ መጣህ ዝም ብለህ ትንቀባረራለህ መምጣትህ ላይቀር ” አለች ፊቷ አንበሳ ገዳይ አይነት ፉከራ ሰፍሮበት ደነዝ!! አጎንብሳ እግሯን የሆነ ነገር እያደረገች ነበር የምታወራኝ ጠረንቤዛው እግረዋን ጋርዶኛል

“ምን እዚህ ይሄ መንገዳችሁ አቧራ ብቻ ነው ኤጭ ተሸከርካሪ ወንበሯን ወደእኔ ስታዞረው የተራቆተ ቀኝ ታፋዋ ስለተቀመጠች በጣም ገዝፎታየኝ አይኔን ወደታች ስልክ ባለተረከዝ ጫማዋን እየወለመለች እንደነበር ገባኝ በእጇ በቀይ ክር ሃረግ የተጠለፈበት የእማማ መለኮት መሃረብ በከፊል አቧራ ለብሶ

ስራየ በዛው ግድም ነበር (ሀና)

ስራየ በዛው ግድም ነበርና ደጋግሜ ሳያት ከቀን ወደቀን እየባሰ የሚሄድ ይሄ ጎደለው የማይባል ፍፁም የሆነ አስቀያሚነት እንዳሸከማት እየተገረምኩ ታዘብኩ

ግና የገረመኝ “አቤት ስታስጠላ “ እያልኩ ላያት መፈለጌ ደንበኛ ሆንኩ ምን ልታዘዝ ቡና ምን ላምጣ ቡና ሰላም ምን ላምጣልህ ቡና ቡና ነው ዛሬም (ፈገግ ላለማለት እየሞከረች ) አዎ (በፈገግታ) ከዛ ሳላዛት ቡና አመጣችልኝ ቡና ቡና ቡና ሰላምታ ሃና ነው ስሟ አንድ ቀን ጠየኳት ነገረችኝ ስራ ከሌላት አጠገቤ ትመጣለች እናወራለን እንዴት ደስ እንደምትል ትልልቅ ጡቶቿን አልፎ ልቧ ይታያል ንፁህ ነው !!

አንድ ቀን ከጎኔ የተቀመጡ ተስተናጋጆች “ የሰው ጅብ “ ሲሏት ጆሮየ ጥልቅ አለ ያዘዝነው ዘገየብን ብለው !! በመሰደቧ ሳይሆን እኔ ፊት በመሰደቧ የቅስሟ መስተዋት ክፍት አፍ በወረወረው የዘለፋ ጠጠር ሲንኮታኮት ፊቷ ላይ እንዴት አንጀት የሚበላ መሳቀቅ አየሁ ተሳዳቢወቹ ጋር የነበረች አንዷት ሴትም ላንቃዋ እስኪላቀቅ ሳቀች አዘንኩ ለምን አዘንኩ እኔጃ!!

የውበት ጥርሳቸውን ስለው ወንዱን ሊከረትፉት ከተማውን በቀን የወረሩት ሴቶች ያውም የጉም ጅቦች ላይ አፋቸውን ለአድናቆት ሲበረግዱ የሚውሉ ዘመናዊ ተብየ ቅርፊት የከተማ ወንዶች አንዷት ደሃ ሚስኪን “የሰው ጅብ “ ብለው ተሳሳቁ!! ሰርታ በኖረች በጅብ አፋቸው ጅብ አሏት

በቀጣዩ ቀን አንገቷን ደፍታ “ምን ልታዘዝ” አለችኝ በመከራ አንገቷን ብቅ ካደረገችበት ግንኙነታችን በዘለፋ ኩርኩም ወደትንሽነቷ መልሰዋት ከ ሀ አስጀመሯት “ስልክ አለሽ” አልኳት “ቡና “የምል መስሏት ልትመለስ ካለች በኋላ ያልኩትን ባለማመን “እ” አለችኝ “ስልክ ቁጥርሽን ስጭኝ” “የድርጅቱን ነው” ስትል ጠየቀችኝ “ኖ ! ያንችን የራስሽን “ ዝም አለች ቆይታ ቆይታ “09 ” አለች “09 ” አልኳት ስልኬ ላይ እየፃፍኩ “እ 09 ” ፈራች ማመን ከበዳት የኔ ሚስኪን ጀግናው ወገኗ ዘላፊ ወገኗ ሃይማኖተኛ ህዝቧ የገደላት ሙት መቃብሯን ለመፈንቀል ሁሉም በየአፉ የወረወረባትን ደንጋይ በአሸሙር አካፋው በለበጣ መጋፊያው የመለሰባትን የቀብር አፈር መፈንቀል ከበዳት “በዚህ ምልክት አድርጊልኝ እጠብቅሻለሁ “ ብየ ቁጥሬን ያመጣችው ደረሰኝ ላይ ፅፌ ሰጠኋት ”

የሴት ክብር መሳም ነው ? መታቀፍ ነው ? ተስመው የተወረወሩ ታቅፈው የተሸቀነጠሩ ይናገሩ ወንድ ያመነችውን ሴት ጣላት ተዋት ከሚል አሽሙር ሲታደጋት ያኔ ነው ክብር ቦታዋ ላይ የምትቀመጠው ሴት ልጅ ስታፈቅር እድሜዋን ነው ሽርፉ የምትሰጠው ሽራርፈው ሽራርፈው ሴቶቹን ከእደሜያቸውም ከውበታቸውም አጣልተው ገሸሽ ያሉ ወንዶች ይስሙ እኔ ሽቅርቅሩ ሃናን ወደድኳት ወረተኛ አይደለሁም ምንም ቢመጣ አልተዋትም አዝኘ አይደለም ስማኋት አይኔን ሳልወድ በግድ አስጨፈነችኝ

መንገድ ላይ ሃኒየን በኩራት ሳቅፋት "የሚታቀፍ ጠፍቶ " ይላሉ ሊታቀፉ ከየቤታቸው የወጡ እቅፍ ናፋቂወች ሁሉ ስስማት የሚያቅለሸልሻቸው አይናቸውን አዞሩ ሃኒየን አበድኩላት !! ሃና ሴት ናት!! እግዜር "ሴትነትን " መደበቂያ ቢያጣ ባረባ ስጋ ጠቅልሎ ያኖረባት የክብር መዝገብ ወንዶች እግር ላይ ሴትነትን ሲፈልጉ ያማረ አፍንጫና ጥርስ ላይ ሴትነትን ሊያጠምዱ መንጠቆ ሲወረውሩ እግዜር እንቁውን የት እንዳስቀመጠው ተመልከቱ

አገባታለሁ ሃናን አገባታለሁ ያልኩ ቀን ሙሾ ባይነት ባይነት ወረደ ሃና ራሷ ደነገጠች ከዛ በፊት እንዲሁ ከምቀር ፍቅር የሚባለውን ነገር ልሞክረው ቢያንስ ትዝታው ጋር እኖራለሁ ብላ እንጂ ያገባኛል ብላ በምን ጠርጥራ(በኋላ እንደነገረችኝ) ተወራ በመንደሩ አብርሃም ቡጡቃ ሻይ ቤት ያለችውን "ሆረር " ሊያገባ ነው አትቀልድ ባክህ ማሪያምን ክርቶስ ምስክሬ ወላሂ አበደ እንዴ መካሪ የለውም ተቀባበ ሉት ወሬውን

ለክብሩ ለወጉ ለማረጉ "ሃኒን ላገባት ነው ዳሩኝ " አልኩ ቤተሰቦቸን "አያገባንም!! " አሉ

የራሳችሁ ጉዳይ ብያቸው ሃኒ ጋር አብረን መኖር ጀመርን !! ወላ ቤተሰብ ወላ ጓደኛ ድራሹ ጠፋ ሃኒየን ወደድኳት ከዚህ ሁሉ አሰቃቂ መልከጥፉነት መሃል የተረፉ ጡቶቿ ወስውሰውኝ በስሜት እንዳይሆን የወደድኳት ብየ ጀመአው ሲንጫጫ ፈራሁ ኧረ ሃቂቃው ፍቅር ነው !!

አራት አመት እሳት በሆነ ፍቅር ኖርን ባሰብኝ ወደድኳት ይሄው እርጉዝ ናት ያውም የስመንት ወር ሃኒ እኔ ጋር ትስቃለች እኔ ጋር እግሯን አትደብቅም በነበረው ግዝፈት ላይ እርግዝና ያሳበጠው አስቀያሚ እግሯን ጉልበቴ ላይ አስቀምጨ ሳሽላት አንዴት ደስ እንደሚለኝ

" አብርሽየ " ያ " እላታለሁ "እንትን ፈልጌ ነበር " " ምን " በቦታህ አብርሽ ተዘጋጅ "ሥ " ሂድ ዲዲዲዲዲዲዲ ሥጋ ሥእል (ከሰአሊ ጓደኛየ) ሥስ ፒጃማ ስንግ ሥራስር ነገር (ድንች ቀይ ስር ካሮት) ሥእለት (ለማሪያም ሃኒ በሰላም ትላገል ብየ) እያለከለኩ ስመለስ "ወይ አብርሽየ "ስልኬን አቀብለኝ " ለማለት ነበርኮ ሮጥክብኝ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ እኔ ፊት ስትስቅ አትሳቀቅም ሃኒየ!!

# አለሁላት !!

እናቴ ሁልጊዜ ሁለት እጆቿን ወደሰማይ ዘርግታ እግዜርን እንዲህ ትለዋለች

" አብርሽየ የሚያገባትን ሴት ሳታሳየኝ እንዳትገለኝ "

አገባሁ !!

እናቴ ሁለት እጆቿን ወደሰማይ ዘርግታ እግዜርነ እንዲህ አለችው

" ምነው ይሄንንስ ከሚያሳየኝ በገደለኝ "

ሃና ምን ተስኖት ትባላለች የምኮራባት ሚስቴ እወዳታለሁ አፈቅራታለሁ ከፉ ነገር በሰፈሯ እንዲያልፍ አልፈልግም ሃኒየ የእኔ ጥሩ ሱስ "ካላያኋት ያዛጋኛል" ስል ሰወች አያምኑኝም ሃኒ የእኔ ልብ የጠላችው ጠላቴ ነው "ይሄ ኦባማ የሚባል ሰውየ በቴሌቪዥን ያደረገው ንግግር አስጠላኝ " ብትለኝ ሲአይኤን ሳልፍራ ኤፍ ቢአይን ከቁብ ሳልቆጥረው ኦባማ ላይ የግድያ ሙከራ ባደርግ ደስታየ ነው እንቅ አድርጌ አይኑን አፍጥጦ " ኧረ አብርሽ በእናትህ የዛሬን ማረኝ ሁለተኛ በየትኛውም ሚዲያ ከመቅረቤ በፊት ንግግሬን ለ ሃና ምን ተስኖት አሳውቃታለሁ ካልፈቀደችልኝ አላደርገውም" ቢለኝ አልምረውም እማምላክን አ ል ም ረ ው ም !!

ሃናየ የነብሴ ፍራሽ ሳያት ድሎቴ ናት ሃና ካዘዘችኝ አቤት ፍጥነቴ! ገና ልትናገር ስትጀምር እኔ ሩጫለሁ ። አልጋ ላይ ጋደም ብላ ቴሊቪዥን እያየች እኔ ቆንጆ ቡና እያፈላሁላት የሆነ ነገር ብትፈልግ ልትናገር ስትጀምረው ነገሩን አምጥቸዋለሁ!! ለምን ትጨርሰዋለች ቃሏ ፍቅር ነው ፊደሎቿ እንደረሃብ ቀን እህል ያሳሱኛል።

"አብርሽ "ስትለኝ በቦታህ እንዳሉት እሯጭ እዘጋጃለሁ ወደመሻቷ ተፈትልኬ በምድር ላይ ያሉ ወንዶች ሁሉ የሚስቶቻቸውን ፍላጎት ካሟሉበት ሰአት የተሻለውን ለማስመዝገብ። "ድ" ብላ ስትጀምር ፈትለክ ብየ ድስት ድራፍት ድንች ድልህ ድፍድፍ (ከእማማ ፈጠኑ ቤት)..ድመት ድንጋይ ድራማ(በሲዲ) ይዠላት እያለከለኩ ከተፍ ስል "ውይ አብርሽየ በቲቪ "ድብ" አይቸ "ድቡን እየው ልልህ ነበር እኮ " ትለኛለች በፍቅር አይን እያየችኝ !! አይከፋኝም ለምን እከፋለሁ እንደገና ድብ ባየችና "ድ" ብላ ስትጀምር አሁን ባመጠኋቸው ነገሮች ላይ ድብ ጨምሬ ባመጣሁላት የእኔ ሃኒ መከሊት ብያታለሁ እሷ ናት ቀኝም ግራም ጎኔ

ሃኒየን እናቴ አትወዳትም "አንዳች አስነክታው ነው ልጀን እች የሰው ጉድ " ትላታለች አባቴ እማ ገና ሲያያት የእናቱ የአባቱ የሁለት እህቶቹና የአንድ እህቱ ገዳይ ነው የምትመስለው አቤት ሲጠላት በወሬ ወሬ " መንገድ ላይ አብረሃም እና " ሲሉት "በቃ!" ብሎ ይጮሃል " አብርሃም ካላችሁ አይበቃም እናን ምን አመጣው " ይላል ያውቃል ማንም ጋር እንደማልታይ ሃኒ ጋር ነኝ ቤት ውስጥ የምትበላውን እየሰራሁላት ሃኒ ጋር ነኝ በመንገድ ቦርሳዋን ይዠላት ዣንጥላዋን ይዠላት እቃ ከገዛን አስቤዛም ቢሆን እኔ ይዠላት ሃኒ ጋር ነኝ የትም!!

ሃኒን እህቴ አትወዳትም ዘመናዊ ጓደኞቿ ጋር ሁና ከሩቅ ካየችኝ በሬ እንዳሯሯጠው ሰው መንገድ አሳብራ የጓደኞቿን እጅ እየጎተተች ትሸሻለች "ወንድሜ በሬ አገባ" እያለች ነው የምታወራው አሉ !

ወንድሜ ሃናን አይወዳትም "እዚች አዚፋ ጋር ትወዘፋለህ ለስንት ስንጠብቅህ" ይለኛል አዚፋ ምን እንደሆነ አላውቅም ግዴለም ሃኒየ "አዚፋ" ከሆነች አዚፋ ይባረክ!! ስድብ ሰውን ካረከሰው ሰው ስድቡን ስለምን አያከብረውም ሃኒየ አዚፋን አከበረችው እወዳታለሁ

ሃኒ ቆንጆ አይደለችም የኔ ቆንጆ ቆንጆ አይደለችም

"ኪሚኪ ፀጉሯ ጧት ስትነሳ ያስፈራል "ይላሉ አዎ እውነት ነው

አፍንጫዋ በአይኗና በላይኛው ከንፈሯ መካከል ያለ ሁለት የሽንቁር ነጥብ ነው እያሉ ያሚታል እውነት ነው !!

ከንፈሯ ወጣወጣ ባሉ ጥርሶቿ (በገጣጣ ነው እነሱ የሚሉት) ከእርስቱ ተገፍቷል በዛ ላይ ብትስቅ ዙሮ ማጅራቷ ላይ ይዘያየራል ይላሉ አዎ እውነት ነው !!

የጣቶቿ መዶልዶም ከዘጠኝ አመቷ እስከ አስራዘጠኝ አመቷ 100000000000000000000 ኩንታል ገብስ ሳታቋርጥ የወቀጠች ያስመስሏታል ቢሉም (ተጋነነ እንጅ) እውነት ነው !!

እግሯ ከየትኛውም ጫማ ጋር እንዲጣላ ተደርጎ ነው የተፈጠረው ያሉትም አልዋሹም

በዚህ ሁሉ መናቅ በዚህ ሁሉ መገፋት ተገፍታ እኔ የምባል ጥግ ላይ ደረሰች የሃኒየ አለም መጨረሻ የት ትሂድላቸው አለሁላት ወንድሟ ነኝ ፍቀረኛዋ ነኝ ባሏም ነኝ !!አላፍርባትም እኮራባታለሁ !! ሃኒየ የኔ ናት ማነው እኔን አልፎ የሚዘልፋት ወንድ !! የኤሌክትሪክ አጥሯ ጠባቂ ውሻዋ ነኝ ከእግሯ ስር የማልጠፋ ባለቤቱ ያላከበረው አሞሌ ወላ መልኩ ወላ ዘመናዊነቱ አያስከብረውም አንዱ የወረወራቸው አይደሉ ሌላኛው መኪና ላይ የሚኮፈሱት የተናቁ አሞሌወች !! ሃኒየን አከብራታለሁ !! እግዜር ያውቃል ልቤን !!

ጥርስሽ አያምርም ቢሏት ከሳቅ ተጣላችላቸው ሰው ፊት አትስቅም ሃኒ የመፃፍ መብታችን የመሰለፍ መብታችን  ተነካ የሚሉ የአገሬ ልጆች የሃኒየን የመሳቅ መብት በአደባባይ ነጠቁ እስካሁን ሻይ ቡና ለማለት ካፍቴሪያ መግባት ያስፈራታል አራሷ ቤት ውስጥ ስትቀመጥ እንኳን እግሮቿን ሶፋ ስር ልትደብቅ ይከጅላታል በመንገድ ዳር ዘለፋ መሳቀቅን ሸልመዋት

ሰው ለሰላምታ ስትጨብጥ ትሳቀቃለች የመዳፏን ሸካራነት በየጭብብጡ የሚጮኸ አዋጅ አድርገው ልቧ ውስጥ ተክለውባት

ሃኒን ቆንጆ ካልሆንሽ ሰው ከመሆን መንበር ተንኮታኩተሽል ብለዋታልና ቆንጆወች አምላክ ይመስሏታል

የሴት ልጅ የክብር ጥጉ በየሆቴሉ ወንበር ተጎትቶላት መቀመጧ ነውን ? በአደባባይ መታቀፍስ የፍቅር አሜጋ ሁኖ የታወጀው መቸ ነው? አየተውረገረጉ የወንድ ጭብጨባ ያደነቆራቸው ሃኒን ቃል ሳያወጡ በድርጊት ቀበሯት

እንሆ ለአንዲት ደሃ ለአንዲት መልከጥፉ ደሃ ተልኬ የምታስተናግድኬት ተራ ሻይ ቤት ተከሰትኩ ያውም አዩኝ ብሎ የሚቆሸሽ ነጭ ሸሚዝ ባማረ ጅንስ ሱሪ ለብሸ ጥቁር መነፀሬን ሰክቸ እየተቆነንኩ በረንዳው ላይ ካሉት ወንበሮች በአንዱ ላይ ሰፈርኩ

“ምን ልታዘዝ” አለች ሃኒየ እየተሽቆጠቆጠች ሳያት ላማትብ ቃጥቶኝ ነበር እግዜር ሰውን የት ድረስ ውብ እንደሚያደርግ አውቃለሁ የት ድረስ መልከ ጥፉ አድርጎ እንደሚፈጥር እነሆ የእጁን ውጤት ፊቴ አቁሞ አሳየኝ “አቤት ችሎታው ምን ይሳነዋል” አልኩ!!

ስራየ በዛው ግድም ነበርና ደጋግሜ ሳያት ከቀን ወደቀን እየባሰ የሚሄድ ይሄ ጎደለው የማይባል ፍፁም የሆነ አስቀያሚነት እንዳሸከማት እየተገረምኩ ታዘብኩ

ግና የገረመኝ “አቤት ስታስጠላ “ እያልኩ ላያት መፈለጌ ደንበኛ ሆንኩ

ምን ልታዘዝ

ቡና

ምን ላምጣ

ቡና

ሰላም ምን ላምጣልህ

ቡና

ቡና ነው ዛሬም (ፈገግ ላለማለት እየሞከረች )

አዎ (በፈገግታ)

ከዛ ሳላዛት ቡና አመጣችልኝ ቡና ቡና ቡና ሰላምታ ሃና ነው ስሟ አንድ ቀን ጠየኳት ነገረችኝ

ስራ ከሌላት አጠገቤ ትመጣለች እናወራለን እንዴት ደስ እንደምትል ትልልቅ ጡቶቿን አልፎ ልቧ ይታያል ንፁህ ነው !!

አንድ ቀን ከጎኔ የተቀመጡ ተስተናጋጆች “ የሰው ጅብ “ ሲሏት ጆሮየ ጥልቅ አለ ያዘዝነው ዘገየብን ብለው !! በመሰደቧ ሳይሆን እኔ ፊት በመሰደቧ የቅስሟ መስተዋት ክፍት አፍ በወረወረው የዘለፋ ጠጠር ሲንኮታኮት ፊቷ ላይ እንዴት አንጀት የሚበላ መሳቀቅ አየሁ ተሳዳቢወቹ ጋር የነበረች አንዷት ሴትም ላንቃዋ እስኪላቀቅ ሳቀች አዘንኩ ለምን አዘንኩ እኔጃ!!

የውበት ጥርሳቸውን ስለው ወንዱን ሊከረትፉት ከተማውን በቀን የወረሩት ሴቶች ያውም የጉም ጅቦች ላይ አፋቸውን ለአድናቆት ሲበረግዱ የሚውሉ ዘመናዊ ተብየ ቅርፊት የከተማ ወንዶች አንዷት ደሃ ሚስኪን “የሰው ጅብ “ ብለው ተሳሳቁ!! ሰርታ በኖረች በጅብ አፋቸው ጅብ አሏት

በቀጣዩ ቀን አንገቷን ደፍታ “ምን ልታዘዝ” አለችኝ በመከራ አንገቷን ብቅ ካደረገችበት ግንኙነታችን በዘለፋ ኩርኩም ወደትንሽነቷ መልሰዋት ከ ሀ አስጀመሯት

“ስልክ አለሽ” አልኳት

“ቡና “የምል መስሏት ልትመለስ ካለች በኋላ ያልኩትን ባለማመን

“እ” አለችኝ

“ስልክ ቁጥርሽን ስጭኝ”

“የድርጅቱን ነው” ስትል ጠየቀችኝ

“ኖ ! ያንችን የራስሽን “ ዝም አለች ቆይታ ቆይታ

“09 ” አለች

“09 ” አልኳት ስልኬ ላይ እየፃፍኩ

“እ 09 ” ፈራች ማመን ከበዳት የኔ ሚስኪን ጀግናው ወገኗ ዘላፊ ወገኗ ሃይማኖተኛ ህዝቧ የገደላት ሙት መቃብሯን ለመፈንቀል ሁሉም በየአፉ የወረወረባትን ደንጋይ በአሽሙር አካፋው በለበጣ መጋፊያው የመለሰባትን የቀብር አፈር መፈንቀል ከበዳት

“በዚህ ምልክት አድርጊልኝ እጠብቅሻለሁ “ ብየ ቁጥሬን ያመጣችው ደረሰኝ ላይ ፅፌ ሰጠኋት ”

የሴት ክብር መሳም ነው ? መታቀፍ ነው ? ተስመው የተወረወሩ ታቅፈው የተሽቀነጠሩ ይናገሩ ወንድ ያመነችውን ሴት ጣላት ተዋት ከሚል አሽሙር ሲታደጋት ያኔ ነው ክብር ቦታዋ ላይ የምትቀመጠው ሴት ልጅ ስታፈቅር እድሜዋን ነው ሽርፋ የምትሰጠው ሽራርፈው ሽራርፈው ሴቶቹን ከእደሜያቸውም ከውበታቸውም አጣልተው ገሸሽ ያሉ ወንዶች ይስሙ እኔ ሽቅርቅሩ ሃናን ወደድኳት ወረተኛ አይደለሁም ምንም ቢመጣ አልተዋትም አዝኘ አይደለም ስማኋት አይኔን ሳልወድ በግድ አስጨፈነችኝ

መንገድ ላይ ሃኒየን በኩራት ሳቅፋት “የሚታቀፍ ጠፍቶ ” ይላሉ ሊታቀፉ ከየቤታቸው የወጡ እቅፍ ናፋቂወች ሁሉ

ስስማት የሚያቅለሸልሻቸው አይናቸውን አዞሩ ሃኒየን አበድኩላት !! ሃና ሴት ናት!! እግዜር "ሴትነትን " መደበቂያ ቢያጣ ባረባ ስጋ ጠቅልሎ ያኖረባት የክብር መዝገብ ወንዶች እግር ላይ ሴትነትን ሲፈልጉ ያማረ አፍንጫና ጥርስ ላይ ሴትነትን ሊያጠምዱ መንጠቆ ሲወረውሩ እግዜር እንቁውን የት እንዳስቀመጠው ተመልከቱ

አገባታለሁ ሃናን አገባታለሁ ያልኩ ቀን ሙሾ ባይነት ባይነት ወረደ ሃና ራሷ ደነገጠች ከዛ በፊት እንዲሁ ከምቀር ፍቅር የሚባለውን ነገር ልሞክረው ቢያንስ ትዝታው ጋር እኖራለሁ ብላ እንጂ ያገባኛል ብላ በምን ጠርጥራ(በኋላ እንደነገረችኝ) ተወራ በመንደሩ

አብርሃም ቡጡቃ ሻይ ቤት ያለችውን "ሆረር " ሊያገባ ነው

አትቀልድ ባክህ

ማሪያምን

ክርቶስ ምስክሬ

ወላሂ

አበደ እንዴ መካሪ የለውም ተቀባበሉት ወሬውን

ለክብሩ ለወጉ ለማረጉ "ሃኒን ላገባት ነው ዳሩኝ " አልኩ ቤተሰቦቸን

"አያገባንም!! " አሉ

የራሳችሁ ጉዳይ ብያቸው ሃኒ ጋር አብረን መኖር ጀመርን !! ወላ ቤተሰብ ወላ ጓደኛ ድራሹ ጠፋ ሃኒየን ወደድኳት ከዚህ ሁሉ አሰቃቂ መልከጥፉነት መሃል የተረፉ ጡቶቿ ወስውሰውኝ በስሜት እንዳይሆን የወደድኳት ብየ ጀመአው ሲንጫጫ ፈራሁ ኸረ ሃቂቃው ፍቅር ነው !!

አራት አመት እሳት በሆነ ፍቅር ኖርን ባሰብኝ ወደድኳት ይሄው እርጉዝ ናት ያውም የስመንት ወር ሃኒ እኔ ጋር ትስቃለች እኔ ጋር እግሯን አትደብቅም በነበረው ግዝፈት ላይ እርግዝና ያሳበጠው አስቀያሚ እግሯን ጉልበቴ ላይ አስቀምጬ ሳሸላት አንዴት ደስ እንደሚለኝ

" አብርሽየ

" ያ " እላታለሁ

"እንትን ፈልጌ ነበር "

" ምን " በቦታህ አብርሽ ተዘጋጅ

"ሥ " ሂድ ዲዲዲዲዲዲዲ ሥጋ ሥእል (ከሰአሊ ጓደኛየ) ሥስ ፒጃማ ስንግ ሥራስር ነገር (ድንች ቀይ ስር ካሮት) ሥእለት (ለማሪያም ሃኒ በሰላም ትላገል ብየ) እያለከለኩ ስመለስ "ወይ አብርሽየ "ስልኬን አቀብለኝ " ለማለት ነበርኮ ሮጥክብኝ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ እኔ ፊት ስትስቅ አትሳቀቅም ሃኒየ!!

# ዶክተር አሽብር

## ክፍል 1

ኒውክሌር ቦምብ እንዲኖረኝ እፈልግ ነበር !! ልክ እንደ እጅ ስልኬ በፈለኩበት ሰአት ቁልፎቹን የምጫነው የራሴ የግሌ ሲፈነዳ ንዝረቱ የሩሲያን የበረዶ ግግር የሚሰነጣጥቅ ካናዳ ሊታጨድ የደረሰውን የስንዴ አዝመራ የሚያረግፍ ኒውክሌር ቦምብ እንዲኖረኝ እፈልግ ነበር ቢኖረኝ ለመጥፎ ነገር አልጠቀምበትም በቀጥታ ወስጀ አቶ ቀለመወርቅ ግቢ ላይ እጥለውና እንዲፈነዳ ቁልፌን እጫነዋለሁ

ቡምምምምምምምምም ከእኛ ሰፈር ጀምሮ አፈር ነሽ ዲንጋይ ዛፍ ነሽ ተራራ ነሽ እ የ ጠ ራ ረ ገ ወደታች ወደ ሜክሲኮ ህንፃውን ሁሉ አመድ እያደረገ ከዛ ወደጦር ሃይሎች (አቶ ቀለመወርቅ እዛ ወንድም አላቸው) ከዛ ወደ አየር ጤና አለም ባንክ ( አዲስ ቤት እያስገነቡ ነው ተብሏል አለም ባንክ )

በዚህ በኩል ደግሞ በመስቀል አደባባይ አድርጎ ካሳንችስ ነሽ ሃያ ሁለት መገናኛ መሪ ሲ ኤም ሲ እየጠራረገ በኮተቤ በኩል ስቪልሰርቪስ (እዛ ትልቁ ልጃቸው ይማራል ይሄ ደነዝ ተምሮ ላይገባው የመንግስት እህል ይፈጃል) ፍንዳታው ወደቦሌ ኢምፔሪያል ገርጅም መሄድ አለበት በቃ !! ማነው የሚከለክለኝ የፈለኩትን ማሰብ መብቴ ነው! ማንም ሰው በሃሳቡ በአንድ ጀምበር አለምን ማጥፋት ይችላል እንኳን እችን ቢጢቃ ካላቅሚ የምትንጠራራ በውራጅ የምትንደላቀቅ አዲስአበባ!!

አዲስ አበባ አቅፋ ደብቃ ጠጅ እያጠጣች ጮማ እያስቆረጠች "አንቱ" ብላ ባኖረችው "ቀለመወርቅ" በሚባል ቦርጫም ጭራቅ ሽማግሌ ምክንያት አዲስ አበባነቷን ሳትወድ ተነጥቃ አዲስ ፍራሽ ትሆናታለች የታባቷ መብቴ ነው በሃሳቤ ህንፃወቿን የፍርስራሽ ክምር ማድረግ ታሪክ ማድረግ "እዚህ ላይ እኮ ቀለበት መንገድ ነበር" እያለ ድሮ የሚያውቃት እስኪያዝንላት አመድ ማድረግ እችን አመዳም!!

እንዲህ እያልኩ ሳስብ ነፍሴ ትረካለች ውስጤ ይረጋጋል አዲስአበባን የተበቀልኳት ይመስለኛል ደስ ይለኛል የጋለ ሰውነቴ ይቀዘቅዛል አይምሮየም ተረጋግቶ ወደማሰቡ ይመለሳል አበቦች አበባ ሊመስሉኝ ይጀምራሉ አይኔም በጎበጎውን ማየት ይጀምራል ውር ውር የሚለውን ሰው ቆንጆወቹን ሴቶች ባጠቃላይ ህዝቡን ማየት እጀምራለሁ ግን ሁሉንም እጠላቸዋለሁ አልወዳቸውም!! ምነው "በደፈናው ጥላቻ " የሚል ዳፍንታም ቢንጋጋም አዲስአበባን ከነህዝቧ አ ል ወ ዳ ት ም!! ደግሞ "አዲስ አዱ ገነት " እያሉ ይመፃደቁላታል ኡኡቴ አዱ ሲአል!! የአፍሪካ ዋና ጀሃነም የሰይጣን ህብረት መሰብሰቢያቸውን !!

## ክፍል 2

አሽብር ነው ስሜ ዶክተር አሽብር በአምላክ! " በአምላክ" አባቴ አይደለም አያቴም አይደለም ማን እንደሆነ አላውቅም እናቴም አታውቅም!! ልክ ለኔ አሽብር የሚል ስም እንደወጣልኝ "አባት" ለሚለውም ቃል በአምላክ የሚል ስም ወጣለት የእኔን ስም ያወጣችው ብዙ ላሞች ያሏት አቃጣሪ እና ጠንጋራ ባልቴት ስትሆን የአባቴን ስም ያወጣችልኝ ""እናቴ"" ናት!! እናቴ አፀደ! አቲየ ነው የምላት (በዚች ምድር ላይ ስሟ ላይ የ ጨምሬ የማቀናጣት ብቸኛ ሰው እኔ ልጇ ብቻ ነበርኩ)

አንደኛ ክፍል እስከመዘገብ የአባት ስም አልነበረኝም ልክ ትምህርት ቤት አቲየ ወስዳኝ ስመዘገብ ጉጉት የመሰለው መዝጋቢ እናቴን ጠየቃት ድሪቶ ቀሚሷ ለአይኑ ቀፎት እያመናጨቃት አይቸዋለሁ በዚያው ድሪቶ ቀሚስ ስር በፍርሃት ተከልየ ተመዝግቤ ስንመለስ እናቴ ከፊቱ ዞር ስትል ፊቱን አጨፍግጎ መጥፎ ጠረን እንደሚያባርር ሰው በግራ እጁ አየሩን እያራገበ ሲያባርር አይቸዋለሁ በእርግጥ እናቴ እማማ የብር ኳል ቤት እንኩሮ እያነኮረች ነበር "ምዝገባው ዛሬ ነው የሚያልቀው" ሲሏት ብድግ ብላ የመጣችው ቢሆንስ ልክ ቆሻሻ እንደሸተተው ሰው ሰው

እንዲያየው አድርጎ እጁን ያራግባል የእማማ የብርጓል ቁጥር አንድ የጠላ ደንበኛ እንዳልሆነ ሁሉ ነብር አየው ያንን የውሻ ልጅ አስተማሪ እንደጠመድኩት ጡረታ ወጣ!! ደግሞኮ አያፍርም “የኔ ተማሪ ነው “ እያለ በኩራት ያወራል፡፡

“ስም? “ አላት አቲየን

“የእኔን ነው? “ አለች እየፈራች ፈሪ ነበረች እናቴ፡፡ ፈሪው የአዲስ አበባ ህዝብ እንደያቅሙ ደሃ ማስፈራራትን ተከኖበታል

“አንች ነሽ አንደኛ ክፍል የምትመዘገቢው? “ አላት፡፡ አጠገባችን ያሉት ሁሉ ሳቁለት አቲየ ተሳቀቀች ሰውነቷ ሽምቅቅ ሲል ቀሚሷን አንቄ ተሰምቶኛል መሸማቀቋ፡፡ “የልጅሽን ስም ንገሪኝ ሴትዮ “ አላት እያከላፈታት “ የእሱ አ ሽብር አሸብር ነው ስሙ “ አለች እራሴን እያሻሸች፡፡

“የአባት ስም? “

“አባ ት “ ብላ ዝም አለች “የአባቱ ስም ማነው ” “ቀ “ መጨረስ አልቻለችም  ቀለመወርቅ ልትል ፈልጋ እንደነበር የገባኝ ካደኩ በኋላ ነው “የዛሬዋ ደግሞ የጉድ ናት የልጇም አባት የሚጠፋት ” ብሎ እንደገና እንዲስቁለት ሰወቹን አየ ያልደመቀ ሳቅ ተሳቀለት “በይ ወደዛ ሁኚ ስታስታውሽ ትመለሻለሽ ተረኛ ቀጥል “ አለ እስክርቢቶውን እያወናጨፈ እናቴ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው “በአምላለክ በአምላክ ነው የአባቱ ስም “ አለች መዝጋቢው እራሱን ግራና ቀኝ በብስጨት እያወዛወዘ መዘገበኝ

ወደቤት ስንመለስ አቲየን ጠየኳት “አባቴ ማነው “ ደንግጣ አየችኝና አጥብቃ በያዘችው እጀ ወደመንገዱ ዳር ሳብ አደረገችኝ ከሩቅ የሚመጣ እኛ ያለንበት ነገም የሚደርስ የማይመስል ጭነት መኪና እንዳይገጨኝ አቲየ መኪና ድምፁ ሁሉ የሚገጨኝ ነው የሚመስላት ትሳሳልኛለች!! “አባትህማ በአምላክ ነው በአምላክ “ አለች “የት ነው ያለው “ “ሁሉም ቦታ “ “የታለ “ ብየ ዞርዞር አልኩ “ አይታይም እሱ ግን እኔና አንተን ያየናል የሆነ ችግር ካጋጠመን ከየት መጣ ሳይባል ከተፍ ይላል “ “አቲየ “ “ወይየ” “ልክ እንደእግዚያቤር ነው “ “አዎ ቁርጥ እንደግዚያብሄር “ በአባቴ ዝና ትንሽ ልቤ ይሞላል  “ አቲየ” “ወይ “ ትንሽ ያሰለቸኋት ትመስላለች “ከእግዚያብሔርና ከአባቴ ማን ይበልጣል “ “እኩል ናቸው እኩል” ትለኛለች

# ክፍል 3

አሸብር ብላ ስም ያወጣችልኝ ከቤታችን በላይ ብዙ ላም የምታረባ ቅሌታም አቃጣሪ ባልቴት ናት  ስሙ እኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም እኔ ልወለድ አቲየ ምጥ የተያዘች ቀን የዚች አቃጣሪ ባልቴት የአሜሪካ ላም ያልታወቀ ነገር በልታ ሆዷ ተቆዝሮና አረፋ ደፍቃ እየጓጎረች ነበር አሉ

የመንደሩ ሰው ከአቲየ ምጥ ይልቅ የዚች የመንደር ሃብታም ላም ነብስ አስጨንቆት አዋላጇ አልማዝ ሳትቀር ወደዛው ሂደው ነበርና አቲየ ብቻዋን እኔን ተገላገለች!! ብቻዋን!! የቀን ስራ ያጠነከራት ብርቱ ሴት ባትሆን ኑሮ ሚች ነበረች ብቻዋን ወለደችኝ!! አንድ የእንስሳት ሃኪም ተጠርቶ የአቃጣሪዋን ዘርፌ ላም ሆድ እስክርቢቶ በሚመስል ነገር ወግቶ ሲያስተነፍስላትና ላሟ መጓጎሯን ስታቆም መንደርተኛው እልልታውን አቀለጠው በዚህ መሃል አዋላጇ “በሞትኩት ያች ሚስኪን ምን ደርሳ ይሆን “ ብላ ወደቤታችን ተጣደፈች አቲየ እኔን አቅፋ አገኘቻት!! ዘርፌ የሚሏት ሃብታም ውሻ ወደማታ አስር እንጀራና ክክ ወጥ ይዛ እቤታችን መጣችና “ መንደርተኛው በእኔ ላም በተሸበረበት ቀን ተወልዷልና አሸብር ብየዋለሁ “ አለች አሸብር ሁኘ ቀረሁ!! ነገ አድጌ ብረብሽ “ስምን መለአክ ያወጣዋል በሚል ሂሳብ “መለአክ ነኝ” ልትል እች ስድብ የማይገልፃት!! ትልቅ ለ “አንቱታ” የደረሰች ሴትዮ ናት “አንች” የምላት ባትሰማኝም ስንቃት ደስ ስለሚለኝ ነው ፡፡

እንግዲህ አሸብር የተባልኩት አንዲት ተራ  አጋሰስ የአሜሪካ ላም ባገበሰችው ፌስታል ታማ መንደርተኛውን ባሸበረቸረበተረ ቀን በመወለዴ ነው በቃ !! ደግሞ ምኔም የማያሸብር እንደውም ቅጠል ሲንኮሻ አቲየ አሮጌ ቀሚሰ ስር የምደበቅ ፈሪ ነበርኩ ስሜን ያወጣው መለአክ አይደለም ዘርፌ የምትባል ቀንዳም ሰይጣን ናት !!

እኔኮ የሚያበሳጩኝ የዛን ጊዜ ዘመኑ ስላልሰለጠ ነው ብየ ውስጤ ከተመረዘበት ጥላቻ እንዳይሽር ዛሬም ድረስ ጎረቤቶቻችን ስለዛ ጊዜ ሲያወሩ እፊታቸው የተቀመጠችውን አቲየን ብቻዋን መውለዷን ከቁም ነገር ሳይቆጥሩት ማለፋቸውና ከሞተች የቆየችውን የአሜሪካ ላም ደግነት ባልዲ ሙሉ መታለብ ፌስታል በልታ ስታቃስት አንጀታቸው መንሰፍሰፉን እየተቀባበሉ ማውራታቸው ነው ደግሞ የሚንሰፈሰፍ አንጀት እንዳለው ሰው ጎማ አንጀት ሁሉ !! አቤት ስጠላቸው ልቤ ተሸንቁሮ የቋጠረው ፍቅር ፈሶ ያለቀበት ይመስል የተረፈኝ አፅናፍ የለሽ ጥላቻ ብቻ ነው ! ማንንም አልወድም ሁሉንም እጠላለሁ !!

# ክፍል 4

አቲየ ከገጠር ወደአዲስአበባ ስትገባ ገና 14 አመት እንኳን አሳምሮ አልሞላትም ነበር. ገጠርም ቤተሰቦቿ ደሃ ስለነበሩ ገና በልጅነቷ ነው ልፋት እጣፋንታዋ የሆነው ስልችት አላት ገጠር የልጅነት እግሮቿ ወደ አዲስ አበባ መሯት እዚሁ ሰፈር ዘርፌ የምትባል አቃጣሪ በደሃ መንደር ሃብታም ከኔ ወዲያ ላሳር የምትል ክብረ ቢስ ባልቴት ብዙ የአሜሪካ ላሞች ያሏት በሰራተኝነት ቀጠረቻት

ገጠር ትታው የመጣችው አዛባ መዛቅና ላም ማለብ እዚህም መሃል አዲሳበባ ጠበቃት እጣ ፋንታህን በመሸሽ አታመልጠውም. ከአበሻ ላም ወደአሜሪካ ላም አዲሳባ ራሷ የአሜሪካ ላም ናት ብዙ ላበላት ብዙ የምትታለብ. አላቢም ታላቢም በግፍ የሞላባት  !!

አንዳንድ የአሜሪካ ላሞች ከሰው ልጆች የበለጠ ክብር ይሰጣቸዋል የአሜሪካ ላም ስለሆኑ ወይም ላም ብቻ ስለሆኑ አይደለም ወተት ስለሚታለቡ !! ስጋቸው ስለሚበላ እና ሌላ የሚታለብ ላም የሚታረድ በሬ ስለሚወልዱ !! ይሄ የአለማችን የደነዘ ኢኮኖሚክስ ቀመር ነው "የበለጠ የሚታለበውን የበለጠ ተንከባከበው !!" አገር ይሁን ሰው ምንም ከሌለው ምናምቴ ነው! ይገፋል ይረገጣል ለጠብታ ነዳጅ አንድ አገር ሰው ሲፈጅ አለም ጭጭ የሚለው ለፅድቅ ነበር ወትሮስ !! ሰበአዊነት ገደል ይግባ ብለው ሰው መሆንህን ሊክዱ የሚዳዳቸው ሁሉ በእድልም ይሁን በችሎታህ አምልጠህ ሰው ስትሆንባቸው ገደል ያስገቧትን ሰበአዊነት ጎትተው የሚያወጡባትን ገመድ እነድትሰጣቸው ፊትህ ቁመው ጅራታቸውን ይቆላሉ !!

# (ክፍል 5)

እናም እንደሰው ባልቆጠሯት እናቴ ጉልበት ሰው የሆኑ ብዙዎች "ሰው ብቻ" እንዳልሆኑ ይልቅ "በጣም ሰው" እንደሆኑ ሲሰማቸው(ከጣት ጣት ይበላለጣል የሚል ተረት ሁሉ አላቸው ) የአቲየ ወጣት ሰውነት ላይ አይናቸን ያቁለጨልጩ ጀመረ ቀለመወርቅ የሚባል ካፖርትና ክብ ኮፍያ የማይለየው ባለትልቅ ቤት ባለ መኪና ሰው "ነበር" እሱስ አሁንም አለ እኔ ውስጥ ከሞተ ቆየ እንጅ !

ሁሉም ሰው "ጋሽ ቀለሙ" ነው የሚለው እና ይሄ ካፖርታም ቤታም እና መኪናም አጋሰስ በእናቴ ቁንጅና ወጣትነት ቋመጠ ትልልቅ ልጆች አሉት ሚስቱ ጋር ተፋቷል ይሄ የአምሳ ምናምን አመት ሰው አንዲት ፍሬ ልጅ ሊያጠምድ ዘርፌ የምትባል አቃጣሪ ያረጀች አሮጌ መረብ ሰፈሩ ላይ ወረወረ አቲየ የምትባል ሚስኪን አሳ የሂወትን ዋና ልትለማመድ ስተፍገመገም መረቡ ውስጥ ገባች ዘርፌ የምትባል ቁራጭ የአሳማ ስጋ የክፋት መንጠቆ ላይ ተሰክታ አቲየን አታለለቻት።

" አፀደ "

“እመት እትየ”

“ ኤዲያ እንደባላገር እመት አትበይ አቤት ነው የሚባል። ነይ እስቲ ለጋሽ ቀለሙ ወተት አድርሽለት “ አለች አቃጣሪዋ

“እሽ” ብላ የወተት ጠርሙሱን አንስታ ልትሄድ ስትል ባልቴቷ ተቆጣች

“ ነይ ወዲህ የምን መንኳተት ነው እቴ ማንም መደዴ ቤት የምትሄድ መሰላት እንዴ እንዲህ ተንቧተሽ ትልቅ ሰው ቤት ምኗ ገልቱ ነሽ አንችየ በይ ፊትሽን ታጠቢ እግርሽንም አዛ ድንጋው ላይ ፈግፍገሽ ታጠቢው “ አቲየ ሰውነቷ ነክቶት የማያውቀውን ልብስ እግሯ ተጫምቶት የማያውቀውን ጫማ ከእመቤቷ ተቸራት አበባ መሰለች ድሮም አበባ ነበርች!! እንኳን ያኔ አሁንም ውብ ናት የእኔ አቲየ !!

በዚህ አይነት ቀለሙ ለሚባለው ውሻ ወተት አደረሰች። ደጋገመችው። ስትመላለስ ቆየች።

የቀለመወርቅ ቤት ቤተመቅደስ መሰላት ካልታጠቡ የማይረግጡት። አንድ ቀን አቃጣሪዋ ዘርፌ ተጣራች።

“አፀደ “

እመ አቤት እትየ (እመት አትበይ የባላገር ነው ተብላለቻ )

“ጋሽ ቀለሙ አመም አርጎታል እቤት ሰውም የለ ሂጅ እስቲ እህል ውሃ ስሪለት እኛ እያለን በረሃብ አይሞት መቸስ ጡር ነው።“

“ምን አገኛቸው “ አለች አቲየ የኔ የዋህ በእባቦች ጨዋታ መሃል ንፁህ ልቧን በአደራ እያስቀመጠች።

ያኔ አቶ ቀለሙ ቤት ዋለች አደረች። አቲየ ከዛን ቀን ጀምሮ ቅስሟ ተሰበረ ፈገግታዋ ጠፋ አንገቷን ደፋች ወጣትነቷን የመጠጠው ይመስል ቀለመወርቅ ይሉት መዥገር አማረበት አረማመዱ ሁሉ እንደወጣት ሆነ። ወይኔ ሽጉጥ ቢኖረኝ አሱን ሰውየ ወይም ለአንድ ቀን እግዜርን ብሆን በመብረቅ

“አፀደ” አለች እባቧ አቃጣሪዋ ዘርፌ አቲየ “አቤት” አላለችም ዝም ብላ አቃጣሪዋ ፊት ሂዳ ቆመች እመትን በስልጣኔ ስም አቤትን ከክብሯ ጋር ቀምተዋት ምኑን አቤት ትበል “ጋሽ ቀለሙ ቤት ሂጅና ” “አልሄድም !!” አለች እንባ ተናንቋት “ምናልሽ አንች እከከከከከ ጭቅቅትሽን ሳላቅቅልሽ እንዲህ አፍሽን ሞልተሽ ስደቢኝ ” አቲየን በያዘችው የንኬል ሰሃን ፊቷ ላይ ደረገመቻትና “እች ደነዝ እጀን አሳመመችኝ “ አለች ሰሃኑ የስሚንቶው ወለል ላይ ወድቆ ተቅጨለጨለ

አቲየ በቀኝ እጇ ሰሃኑ ያረፈበትን ፊቷን ሸፍና እግሯ እንደመራት ወደመኪና መንገዱ በረረች ትንሽ እንደሄደች እዚህ አሁን ትልቁ ዳቦ ቤት የተሰራበት ቦታ ላይ አንዲት ኪወስክ ነበረች አንዳንዴ አቲየ እየተላከች እቃ የምትገዛባት ባለቤቷ የአቲን ወጣትነት ስታይ ሁሌ ምራቋን የምትውጥ (ለሰራተኝነት) ጠራቻት “አፀደ አንችን እኮ ነው “ ዝም “ምን ሁነሻል “ ዝም እርምጃዋን ቀንሳ እየቆመች “አንችን እኮ ነው” ዝም “እንዴ ደግሞ ፊትሽ ምን ጉድ ነው ኧረ ጉዴ ምንድነው ይሄ ሁሉ ደም “ አቲየ ደነገጠች እጇን ከፊቷ ላይ አንስታ ተመለከተችው በደም ተሸፍኖ ነበር አሁን ያፈነችው እንባ ፈነዳ ከልጅነቷ ጀምሮ ውስጧ የተጠራቀመው ጩኸት እና እየየ መንደሩን የሚያሸብር ዋይታ ሆነ መንደርተኛው ተሰበሰበ።

ምንድን ነው

እንዴ የእትየ ዘርፌ ሰራተኛ አይደለችም እንዴ ምን አገኛት።

ማናባቱ ነው የዘርፍየን ልጅ እንዲህ ያደረጋት ዘርፌ ዘርፍየ ወሮ ዘርፌ እሜቴ ዘርፌ።

የዚች ሁሉ ዘርፌ ሰራተኛ ሰው በመሆኗ ሳይሆን በዘርፌ ንብረትነቷ መንደሩ ዘራፍ አለ።

እኮ ማናባቱ ነው የነካት

ተናገሪ ማነው የመታሽ

ዘ ር ፌ ራሷ !!

ዝም ሰፈሩ!!

ዝምምምምምምምምምምምምምምም ምምምምምምምምምም!!

"ምን አጥፍተሽ ነው " አሏት አቲየን እሷም ዝም !!

"ታስታውቃለች ተንኮለኛ ዝም ያለችው ጥፋቷ ቢሆን ነው "

"እንዲች ዘርፌ የሴት ወንድ መች መጨማለቅ ትወድና አንድ ነገር ስታደርጊ አግኝታሽ ነው።"

መንደርተኛው ዘባረቀ ይሄ ዘባራቂ ሁሉ ይሄ ጉዳይ ከሆነ ስንት እና ስንት አመቱ ሰፈሩ ግን አሁንም ዘባራቂ ነው !! ባለኪወስኳ ብቻ ለአቲየ አገዘች "የሚመታ ይምታት ምንስ ብታደርግ እንዲህ ደም በደም እስክትሆን ትመታታለች እች ጥጋበኛ ባልቴት

" ባለኪወስኳ እና ዘርፌ ፀበኞች ነበሩ ሁለቱም በመንደሩ ውስጥ የተሰሚነት የክብር ጉዳይ ያጋጫቸው አቲየ ባለኪወስኳ ጋር ሰራተኛ ሁና ቀረች !! እጣፋንታን በመሸሽ አያመልጡትም።

የምትደገፈው ሁሉ እሾህ የምትረግጠው ሁሉ አረንቋ ይሆንባት ዘንድ ድፍን አዲስ አበባን ማነው በአሜኬላ የሞላባት እችን ሴት የእኔ ከርታታ ኩንታል ሙሉ የምስር ክክ ሱቅ ሙሉ ባልትና ማዘጋጀት የሚሸጥ እንጀራ መጠፍጠፍ ነበር የጠበቃት ልብሷ ሰውነቷ ላይ ተበጣጥቆ ፀጉሯ እላይዋ ላይ ጀልቶ በብልጣብልጧ ባለኪወስክ ጉልበቷን እንደምስጥ መጠጠቻት።

ደም መጣጭ የደሃ ክብር መጣጭ መንደር ሙሉ መዥገር እች ሚሊየን አዲስ አበቤ አምራ በየመንገዱ ሰበር ሰካ የምትል ወይዛዝርት የሚንጎማለል ሸበላ "የሰው ላብ ገንዘቤ ውስጥ የለም ብለህ ማል " ቢባል እግሬ አውጭን በሚል እሯጭ መንገዱ በተሞላ !!

## ክፍል 6

ስድስት ወር እንደፈጋች ክረምት ገባ ባለኪወስኳ የአቲየን ድሪቶ ልብሶች በፌስታል ቋጥራ ከድፍን አምሳ ብር ጋር ሰጠቻትና "በይ እግዜር ይከተልሽ " ብላ ከቤቷ አስወጥታ ወረወረቻት። የአቲየ ሆድ ገፍቶ ነበር የቀለመወርቅ ፅንስ ከውስጥ የመንደሩ ሰው ከውጭ እየገፉ ሰው በሞላው አገር እናቴን ምድረ በዳ ላይ አቆማት

ስትፈጭ የዋለችው የምስር ክክ ብናኝ ፊቷና ፀጉሯ ላይ ተነስንሶ ነበር ከስድስት ወር በፊት የነበረችው ልጅ እግር ቆንጆ ልጃገረድ ናት ቢባል ቀለሙ ራሱ አያምንም !! መንገድ ዳር ቆመች የክረምት ዝናብ ያካፋል አንድ የመኪና እቃ መለዋወጫ ሱቅ በር ላይ ቆመች ምንም እያየች ምንም ሰው ምንም መኪና ምንም ቤት ሂወት ዝም የምትልበት አይምሮ ዝም የሚልበት ሰው ለሆነች ቅፅበት በቁሙ የሚሞትበት ቅፅበት አለ አይደል አቲ በቁሟ ሞተች።

አላዛርን ከሞት ያስነሳ ራሱም ከሞት የተነሳ ክርስቶስ "አቲየ" ብሎ ልክ እንደኔ ጠራትና ዞር አለች ክርስቶስ ሳይሆን አንዲት ምቾት መድረሻ ያሳጣት ቆንጆ ወጣት ነበረች ሮማን የምትባል "ወደ ውስጥ ግቢ ዝናብ መታሽ እኮ " አለቻት አቲየን።

ወጣቷ ከፍ ያለ ወንበር ላይ ተቀምጣ እንፋሎቱ ወደላይ የሚመዘዝ ትኩስ ሻይ እየጠጣች ነበር።

ገባች አቲየ ኩርምት ብላ አንዱ ጥግ ቆመች እንደቆመች ዝናቡ አባራ ሰው በያቅጣጫው ሩጫውን ጀመረ አቲየ ግን አልወጣችም የእርሷ ዝናብ አላባራም መጠጊያ ላጣ ሰው የሂወት ዶፍ አባርቶ አያውቅም ሰው የፍቅር

ዣንጥላ የዝምድና ዣንጥላ የጓደኝነት ዣንጥላ የትዳር ዣንጥላ የእውቀት ዣንጥላ የስራ ዣንጥላ የተስፋ ዣንጥላ የእምነት ዣንጥላ ይዞ ስለሚኖር እንጅ ከሂወት ሰማይ ላይ ነብስን የሚያበሰብስ መንፈስን እንደወረቀት የሚያላሽቅ የብቸኝነት እና የተስፋ መቁረጥ ዝናብ አባርቶ አያውቅም

.የአቲየ ዝናብ አላባራም። ይሄን ሁሉ የነብስ ዣንጥላ ጨካኝ ንፋስ ከእጇ ነጥቋታል ንፋሱ ቀሚሷን በግድ ገልቦ ውስጧ ቅዝቃዜ አስቀምጧል። ንፋሱ የሂወት አቧራ አንስቶ ፊቷና ፀጉሯን አልብሷል ንፋሱ የተስፋ ጎጆዋን አፈራርሶ እዚህ አቁሟታል አቲየ የእኔ እናት መሄጃ የላትም!!

ቁልፎች ተንኳኩ ቆንጆዋ ልጅ ጃኬቷን ለባበሰች ውጭ የተደረደሩ እቃወችን አስገባች እናም ቁልፏን በሚያማምሩ ጣቶቿ እንዳንጠለጠለች አቲየን ግራ በመጋባት አየቻት

አቲየ ዝናብ እስኪያባራ ከተጠለለችበት ሱቅ በቀስታ እርምጃ ወጣችና በረንዳው ላይ ቆመች ባለሱቋ ቆንጆ ሴት ሱቋን ቆላለፈች የአቲየ ነገር ሳያሳዝናት አልቀረም “እ ምን ሁነሽ ነው እናትየ ” አለቻት አቲ ዝም አይኗ እንባ አቅርሮ ዝም ወደሞቀ ቤቷ አልያም ወደቀጠራት ፍቅረኛዋ ልትሄት ያኩበኮበች ወጣት የአቲየን የ አርባ ቀን እጣ ከ የት ጀምሮ ቢነገራት ይገባታል አቲ ዝም አለች አለመደባትም “እንዲህ ሆንኩ “ ብሎ ማውራት አለመደባትም ምሬት

ወጣቷ ጥቂት ብሮች ከቦርሳዋ አውጥታ ለአቲ ዘረጋችላትና “አይዞሽ ይሄን ያዥ በቃ “ አለቻት አቲ ግን አማትባ ከተዘረጋው የወጣቷ እጅ በድንጋጤ አፈገፈገች ልክ ጩቤ እንደተሰነዘረበት ሰው “ለማኝ ልሆን “ ብላ ብላ በውስጧ አሰበች እንባዋን እያዘራች ሽቅብ እግሯን ተከትላ ትጓዝ ጀመረ

የትም የማያደርሱ የሚመስሉ እርምጃወች አንዳንዴ አይምሮ አስቦ ከሚደርስበት የተሻለ መፍትሄ ላይ ያደርሳሉ አቲየ ዝም ብላ ብዙ ርቀት ተጓዘች መታጠፊያ ስታገኝ እየታጠፈች መንገድ ስታገኝ እየተሻገረች ዝም ብላ ወደፊት ከእጣ ፋንታዋ ትሸሽ ይመስል።

እናም ቀጥ ብላ ተመለከተች ፀጥ ያለ የቤተክርስቲያን ከነታላቅ ጉልላቱ ፊትለፊቷ መንገዱን ተሸግሮ ይታያል የልብስ ፌስታሏን አንጠልጥላ አሮጌ አምሳ ብሯን በእጇ እንደጨበጠች ፊትለፊት አለምን በመዳፉ የጨበጠ እግዚአብሔር ጋር የተፋጠጠች መሰላት !

የዚህ ሁሉ በደል የዚህ ሁሉ ግፍና ስቃይ ጠንሳሽ “እግዚአብሔርን” ፊት ለፊት ያገኘችው መሰላት አቲየ አይቷት ሳያፈገፍግ የበደላት ሁሉ አሳፍሮት ሳይሸሽ በፊት ልትደርስበት መንገዱን አቋርጣ ወደቤተክርስቲያኑ ገሰገሰች።

እግዜር ፈርቷት እግሬ አውጭኝ የሚል መሰላት አቲየ መኪናወች አምባረቁ ሹፌሮች በመኪናቸው መስኮት ብቅ ብለው ፀያፍ ስድብ ወረወሩባት አንበሳ ጋር ልትፋለም ታላቁን ፈጣሪ “በለሃ ልበልሃ “ ልትለው በድፍረት የምትገሰግስ ጀግና በእንቁራሪቶች ጩኸት የምትበረግግ መስሏቸው

እግዜር ያኔ ለየት ያለ ድምፅ ሰማ ከሰማየ ሰማያት “ቅዱስ ቅዱስ ” እያሉ በታላቅ ድምፅ የሚሰግዱና የሚያሸበሽቡ እልፍ አእላፍ መላእክትን “ዝም በሉ አንድ ለየት ያለ ድምፅ ከምድር ሰምቻለሁ” አለ

“ጌታ ሆይ ሞልቃቆች በስሱ እያማታቡ መኪናቸው ውስጥ ሁነው ሽው የሚሉት አይነት ድምፅ “ ይሆናል አሉት መላእክቱ።

“አይደለም “ አለ እግዚአብሄር።

“የኮተታሞች የኮተት ጥያቄ ይሆናል “ አሉት በምድራዊ ትርኪምርኪ የሰጋ ጥያቄ የተማረሩት መላእክት።

“አይደለም አልኩ እኮ “ አለ እግዚአብሔር በታላቅ ድምፅ

“ጌታ ሆይ ምናልባት የሃብታሞች “ከስኳር ከደም ግፊት ከፈወስከኝ መጋረጃ ዣንጥላ የሚሉት አይነት የተለመደው ስእለት ይሆን “ ጠየቁ መላእክቱ።

ዝም አለ እግዚአብሔር!! ዝምታው አንዳች አስፈሪ ነገር አለው በዝምታው ውስጥ ፅንፍ የለሽ ሃዘንና ፍቅር ነበር።

ከልጅ ስጠኝ ንዝንዝ ከስራ ስጠኝ ንትርክም የተለየ ድምፅ ነበር ድምፄ ካማረልኝ ብላ የምትዘምር ሴትም አልነበረችም " በታላቅ ግርማ ሞገስህ በእሳት ሰረገላ ደርሰህ ጠላቴን አፈር ድቤ የምታስበላ የነገስታት ንጉስ ከፀሃይ አስራዘጠኝ እጅ የምታበራ " እያለች በተጠና መንፈሳዊ ፉከራ መንፈሳዊ ዘራፍ የምታደነቁር ሴትም አልነበረችም። ከተሰበረ ልቧ በወጣ ማቃተት ዙፋኑን የነቀነቀችው እዚህ ግቢ የማትባል ሴት ናት አንዲት ሴት በሩ ላይ ስትቆ "ማነው የልብሴን ጫፍ በእምነት የነካው " ብሏል እግዚአብሄር !!

አቲየ የእኔ ጀግና ማንንም ደጅ አልጠናችም በልብሷ መቆሸሽ ይናቋት እንጅ የእኔ እናት ከአዲስ አበባ የህዝብ ጎርፍ ቁራሽ አለመነችም ለማን ስሞታ እንደምትናገር አውቃለች አጥሩን በድንጋይ ቢያጥር ባማረ መኪና ቢንፈላሰስ ሴቱ በወርቅ ቢሽቆጠቆጥ የአዲስ አበባ ሰው እና አቲየ ተነቃቅተዋል

አይተዋለች ህዝቡን የሂሊናውን አይን ጨፍኖ ጎዳና የፈሰሱትን የራሱን ጉዶች እንቁልልጭ እያለ በየስጋ ቤቱ በረንዳ ላይ ጥሬ ስጋውን ሲያጋብስ ቢራና ውስኪውን ሲገለብጥ አይተዋለች።

በእርሃብ የተቆራመቱ ልብሳቸው እላያቸው ላይ ያለቀ ሚስኪን ህፃናት በምቾት ብዛት ገና በህፃንነታቸው የስጋ ክምር ከተሸከሙ ቢጤወቻቸው የሚሆኑ ህፃናት የተረፋቸውን እንዲሰጧቸው እጃቸውን በልመና ሲዘረጉ አይታለች የደሃ ልጆች የሃብታም ልጆችን መኪና እየተከተሉ ሲለምኑ አይታለች የተረፈውን ሳንቲም በምፅዋት ስም ሲወረውር ደግ ይመስላል ህዝቡ ስግብግቡ የደግነት ከበሮ እየደለቀ ደግነት ባህሌ ነው የሚለው !!

የልብስ ፌስታሏን ከጎኗ አስቀምጣ በግንባሯ ተደፍታ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ቃል አልተነፈሰችም ከበሩ ተነስታ ቀጥ ብላ ወደምፅዋት ማስቀመጫ ሳጥኑ ሄደችና በእጇ የጨበጠጭውን ድፍን አምሳ ብር አጣጥፋ በጠባቧ ቀዳዳ አስገብታት ፊቷን አዙራ እርምጃዋን ቀጠለች ባዶዋን !!

እግዚአብሔር በምድር ላይ ከባዱን ብድር ጥላበት የሄደችውን ሴት እንዲህ አላት።

"በልጅሽ እልፍ እጥፍ ብድርሽን እከፍልሻለሁ " አቲ መሃፀን ውስጥ በፅንስነቴ ከተገላበጥኩ በቃ በዚህ ቀን መሆን አለበት !! እስከዛሬ ድረስ ትልልቅ እና ውብ ቤተ ክርስቲያኖችን ሳይ በአቲየ አምሳ ብር የተገነቡ ነው የሚመስለኝ !!

ቀና ስትል ፊት ለፊቷ ማንን አገኘች አባ እስቲፋኖስን !! በተአምር ማመን የዳዳኝ አቲየ ይሄንን ስትነግረኝ ነው አባ እስቲፋኖስ አቲየን እያዩ " አንች ዘርፌ ቤት የነበሽው ልጅ አይደለሽም እንዴ ? " አሉና ጠየቋት መነፅራቸውን እያስተካከሉ !! አባ እንኳን በዚህ ድንግዝግዝ ደመናማ አመሻሽ በጠራራ ፀሃይ የቤተ ክርስቲያኑን ዋና በር የሚስቱ ፅኑ የእይታ ችግር ያለባቸው አባት ነበሩ አቲን ግን ተመለከቷት በመነፅራቸው ሳይሆን በእግዜር አይኖች !!

ያን ቀን አባ እስቲፋኖስ ቤተክርስቲያን ውስጥ አንዲት እናት መነኩሲት የሚኖሩባት የመቃብር ቤት አቲየን ወስደው አኖሯት !! ሆዷ ውስጥ ወደዚች ምድር ሊቀላቀል የተዘጋጀ ፅንስ ከረገጠችው የቤቱ ወለል ስር እችን አለም ጥግብ እስኪል ኑሮባት የተሰናበታት ሃብታም ሽማግሌ አቲየ መሃል ላይ

# ክፍል 7

አቲየ ያረፈችባቸው መነኩሲት "የኔ ልጅ አይዞሽ የበላነውን እየበላሽ ልብሽ እስከፈቀደው ጊዜ መቆየት ትችያለሽ የእግዜር ቤት ነው ቤትሽ ነው " አሉና ድርብ የሰሌን ምንጣፍ ብዙ ቦታ ላይ በብዙ አይነት ክር እና መጣፊያ ከተጠቀመ ብርድ ልብስ ጋር ሰጧት !! አንዷ ጥግ ላይ እራሳቸው አነጣጠፉላት አለም ላይ ጭካኔ ሲፈነጭ ማን አለብኝነት በሃሴት ዋንጫ ልቅለቃውን ሲያስነካው ሰበአዊነት መቃብር ቤት ውስጥ በፍፁም ፀጥታ አትየ ጋር ተገናኘ !!

አቲየ ከደጓ መነኩሲት ጋር በመቃብር ቤቱ ውስጥ ተቀመጠች “ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል “ ቢባልም ቅሉ ኑሮው አልሞቃትም አጥንቷ ድረስ ዘልቆ የሚያንዘፈዝፍ የፍርሃት ብርድ ሰላም ነሳት !! መሄጃ የለኝም ከሚል ስጋት ለጊዜውም ቢሆን አርፋለች  ግን መቃብር ቤቱ ውሰጥ የነበራት ቆይታ የስቃይና የፍርሃት ነበር

ሰው የተቀበረበት ቤት ውስጥ መተኛቷ ፍርሃት ለቀቀባት ከተኛችበት ሰሌን ስር በስብሶ አፅሙ የቀረ ሬሳ ተኝቷል  በአፈ ታሪክ እንደሰማችው ( አሁንም ድረስ እንደምታምነው) ደግሞ ሙታን አካላቸው ቢጋደምም መንፈሳቸው አርፎ አይቀመጥም መነኩሲቷ ወጣ ካሉ ተከትላ ደጅ ትቆማለች እየፈራች  እንቅልፍ ሸለብ ሲያደርጋት አንድ ስጋው ሁሉ ረግፎ ጭራሮ የመሰሉ ጣቶቹ ብቻ የቀሩ አጥንታም እጅ የተኛችበትን መሬት ፈነቃቅሎ አንገቷን ሲያንቃት ይታያትና ኡኡታዋን ታቀልጠዋለች ቅዠት !! መነኩሲቷ አቲየን ማረጋጋት ለአቲየ መፀለይ ብቻ ሆነ ስራቸው

አቲየ በፍርሃት ሁለት ቀን እና ሌሊት እንቅልፍ ስላልወሰዳት በሶስተኛው ቀን ምሽት እንቅልፍ አሰከራት እና ሰሌኗ ላይ ኩርምት ብላ ተኛች አለም ገፍቶ ገፍቶ የመገነግ ሰሌኗ ላይ የጣላትን ሚስኪን ሴት መነኩሲቷ በሃዘን ግንባሯን እንደትንሽ ልጅ እያሻሹና አተነፋፈሷ የተስተካከለ መሆኑን እያዳመጡ እንደመልካም ወላጅ ቀስ ብለው ድራቡን አልብሰዋት ወደፆለታቸው ተመለሱ

ብዙ ሳይቆይ ትንሽዋ የመቃብር ቤት በአስደንጋጭ ጩኸት ተሞላች አቲ “ልጆን ልጆን “ እያለች እንደእብድ ከምኝታዋ በርግጋ በመነሳት እራሷን ይዛ መጮህ ጀመረች አቅመ ደካማዋ መነኩሲት አቲን ሊያቆሟት አልቻሉም የሷ ባልሆነ ጉልበት ገፈታትራቸው በሚገርም ፍጥነት ሰሌኑን ጠቅልላ የቤቱን ወለል በጥፍሯ ትቧጥጥ ጀመረች “ልጆ ን ልጆን ወሰዱብኝ እያለች በመረገጥ ብዛት የደደረውን አፈር ትመነጭር ጀመረ።

እንባዋ በጉንጮቿ ላይ ለጉድ እየፈሰሰ በላብ ተነክራ እየቃተተች ከትንንሾቹ መቃብር ቤቶች ጩኸቷን ሰምተው የወጡ መነኮሳት ወደማሆይ ቤት መጥተው ተረባርበው እስኪያስቆሟት ድረስ አቲየ በአስሩም ጥፍሯ መሬቱን እየቧጠጠችና እየቆፈረች ኡኡታዋን አላቆመችም ነበር።

ቅዠት ነበር የዘወትር ቅዠቷ የሆነው ጭራሮ እጅ ዛሬ ከፈነቀለው መቃብር ውስጥ እጇን ብቻ ሳይሆን ከትከሻው በላይ ነበር ተመዞ የወጣው አፈር እንደለበሰ !! ከዛም በአስፈሪ አይኖቹ አቲየ ላይ አፈጠጠባት አየችው ቀለመወርቅ ያውም አፈር ከነለበሰ ባርኔጣና ካፖርታው !! ”ልጆን አምጭ ብሎ “ አጥንታም እጇን ወደሆዷ ላከና በቅፅበት አንድ ቀይ የሚያምር ህፃን ይዞ ተመለሰ ሆዷ ባዶ ሲሆን ታያት ቀለላት ከዛም ልጇን በደስታ ተመለከተውና ወደውስጥ ወደመሬት ይዞት ሰረገ ልክ ጫጩት ነጥቆ ወደጉድጓዱ እንደሚገባ ሽለመጥማጥ !!

በቀጣዩ ቀን አባ ስቲፋኖስ ሁኔታው ሲነገራቸው ድሮም ለአቲ ቋሚ መኖረያ ሲያፈላልጉ ነበርና ፍለጋውን አፋጥነው ከሁለት ቀን በኋላ በፊት ትኖርበት ወደነበረው መንደር ወስደው አንዲት ከዋናው የቀበሌ አጥር ጋር ተያይዛ የተሰራች የቆርቆሮ ቤት ውስጥ አስገቧት የመንደሩ እድር እቃ ማስቀመጫ ነበረች ጣራና ግድግዳዋ በደንብ ስላልገጠመ ሌሊት ብርዱ ቀን ፀሃዩ ይገባ ነበር አባ ከንስሃ ልጆቻቸው ለምነውም ተለማምጠውም ያገኟቸው አሮጌ ፍራሽ ብርድ ልብስና የውሃ መያዣ ጎማ ለአቲ እያሳዩ

“ልጆ እንግዲህ እኔ እንደምታውቂው ቤሳቤስቲን የሌለኝ የእግዜር አገልጋይ ነኝ ከዚህ የተሻለ ነገር አላገኘሁልሽም ባይሆን ጎንሽን ማሳረፊያ ካገኘሽ ሌላው ሌላው በፈጣሪ ፈቃድ ቀስ እያለ ይሟላል እኔም እየመጣሁ አይሻለሁ ይሄ የኔ ልጅ ትንሹ ራትሽን ያመጣልሻል አይዞሽ “ ብለዋት ሄዱ

## ክፍል 8

አቲየ ለብዙ ሌሊቶች ጣራውን ነፋስ ባንኳኳው ቁጥር ስትበረግግ በፍርሃት ስትርድ ቆይታለች። የእድሩ ድንኳን እንጨቶች ወንበሮች ስጋጃ ምንጣፎች በአንድ በኩል ተሰድረው ገባ ብሎ ወደውስጥ ባለችው ትርፍ ቦታ

ላይ የአቲየ ፍራሽ ተዘርግታለች ብዙ ጊዜ ሞት ወይም መርዶ ስለሚኖር የእድሩ እቃ አይኖርም ስለዚህ ሰፋ ትላለች ቤቷ አንዳንዴ ደግሞ እድርተኛው እቃውን ሲመልስ በግዴለሽነት ወንበሩን እንጨቱን ከባባዶቹን ምንጣፎች አቲየ ምኝታ ላይ በቸልተኝነት ጥለውት ይሄዳሉ ያንን ጎትቶ ቦታ ማስያዙ ለአንዲት ነብሰ ጡር ሴት ፈተና ነበር።

አቲየ ግን ታደርገዋለች "እንዲህ አታድርጉ" አትል ነገር ሆሆ ወደዛ ውጭ ቢሏትስ

አባ ብዙ ቤት ሊያስቀጥሯት ደከመው ነበር ያው ነብሰ ጡር መሆኗን ሲሰሙ ሁሉም እቤታቸው ማስገባት አልፈለጉም አባ ቢጨንቃቸው አቃጣሪዋ ዘርፌ ቤት ሳይቀር ሄዱና "እችን ደሃ ይቅር በያት ባክሽ" ብለው ተማፀኑ

"አይይይይ አባ ምነው እያወቁት እንደልጆቾ አንከብክቤ በያዘኩ አይደለም እንዴ ጥጋብ ፈንቅሏት ለመንደሩ ሁሉ ስሜን አጥፍታው የሄደች " አለች አቃጣሪዋ አባን በአፍ መሸንገል እግዜርን መሸንገል ይመስል የአቲን በደለኝነት ስትዘረዝር ደስ እያላት

"ልጅ አይደለችም እንዴ ወለተ ማሪያም ደግሞስ አንች ቤት ከመቸ ወዲህ ነው ይቅርታ የነጠፈው ተይ እንጂ " አሉ አባ !!

"በዛብኛ አባ በዛብኝ ምን በደልኩ እናት በሆንኳት የበላሁትን ባበላሁ የለበስኩትን ባለበስኩ ሰው ሁኝ ሰልጥኝ ባልኩ ይሄ ይገባኝ ነበር " እንባ እየተናነቃት አንዳች ሰይጣን ይነቃትና እች አስመሳይ !!

" ይሄው የትም ስትንዘላዘል ዲቃላዋን ይዛ አረፈችው " አለች ዘርፌ "ከእኔ የተጣላ እጣ ፋንታው ውድቀት ነው" ልትል እየዳዳት

አባ እንደሆኑ የአቲየን ነብስ መታደግ ይቅደም ብለው እንጂ የቀለመወርቅንና የዘርፌን ሴራ ውስጣቸው ያውቀዋል አንዳንዴ የእግዜር አገልጋይ ከመሆን ሽፍታ በሆንኩ ነብሰ ገዳይ በሆንኩ የሚያስብሉ እንደዘርፌ አይነት ገርፈው የሚጮኹ ጅራፎች ሲያጋጥሙ የንስሃ አባቶች ልብ ምን ያህል ይሰበር ይሆን !! ቢቻል ጥምጣምና መስቀልን ላንዴ አስቀምጡ ምንሽር መታጠቅና እንዲህ አይነቶቹን እድሜ ጠገብ እባቦች ግንባር ግንባራቸውን ማለት ነበር

ዘርፌ ከዚህ ሁሉ ፉከራና ማስመሰል በኋላ አቲየን ቤቷ እንደማትመልሳትና ከፈለገች በተመላላሽ ላሞቹን የመንከባከብ ልብስ የማጠብ ስራ እንድትሰራ በወር 10 ብር ልትከፍላት ለአባ ቃል ገባች!!

"ያው ለነብሴ ብየ እንጅ የደረሰች እርጉዝ ምኗ " አለቻቸው ለአባ

"ግዴለም ወለተ ማሪያም መቸስ ሰው እንዳረገዘ አይኖር ሁሉ ነገር ሊወለድ ጊዜ አለው ደግም ይሁን ክፉ ተረግዞ አይቀርም ነገን ነው ማየት " አሉ አባ !! የቄስ ምንሽሩ ቅኔ ነው ተኮሱባት አባ !!

የቅኔ ጥይት ከተኳሹ እስከኢላማው ለመድረስ ጊዜ ይወስዳል ለዛ ነው ዘርፌ አባ እግር ስር ድፍት ያላለችው ይድፋትና !!

አቲየ በዙሪያ ገጠም እጣ ፋንታዋ ዙራ ዘርፌ ቤት ገባች (ዙሮ ዙሮ መዝጊያው ጭራሮ እያለ መንደሩ እውር ቢሸፍት ኋሮ ድረስ ነው እያለ አሽሟጣጩ ) እንደገና ወተት ማለብ ፤እንደገና አዛባ መዛቅ እንደገና ጉልበቷን መገፍገፍ ያውም ቀጥ ብላ እመቤቷን በማታይበት የሞራል መዳሸቅ ተተብትባ የበደሏትን ይቅርታ ጠይቃ! የዘርፌ ደግነት ግን በመንደሩ ተወራ "መልሳ ተቀበለቻት እኮ ዘርፍየ ሆዷ ቂም አይቋጥር " እየተባለ

አቲ አባ ባገኙላት የቆርቆሮ ቤት ውስጥ እየኖረች ለመንደሩ ሰው ሁሉ የቀን ስራ እየሰራች ኑሮዋን ጀመረች ዘርፌን በድላ በመመለሷ እንደተማረከ ባሪያ ጉልበቷን ትገፈገፍ ጀመረ የመንደሩ ሰው ሁሉ ዳኛ ወንጀለኛው ሁሉ ፈራጅ ሆነ እናቴ ላይ !! የማያሰሯት ነገር አልነበረም

እነዚህ ባሎቻቸው ከየመሸታ ቤቱ እያነሱ ከየመንገዱ እየለቃቀሙ ከየገጠሩ እያመጡ ሰው ያደረጓቸው ጊዜ ያነሳቸው ቅሎች ለፍቶ በመኖር አምላክን በማመን በእጇቿ ንፁህ ፍሬ የምትኖር እናቴን ብረት መንፈስ ሰበሩ !!

ጊዜ ያነሳው ቅል እንኳን ድንጋይ ብረት ይሰብራል!!

እጠላቸዋለሁ!!

በባሎቻቸው ገንዘብ እድሚያቸውን የሚገፉ ሰማኒያ በሚባል ህጋዊ ፈቃድ የባሎቻቸውን ዳረጎት እየተቀበሉ የሚዘባነኑ የሰማኒያ ለማኞች ሰማኒያ የሚሉት ፍቅር ሲያልፍ ያልነካው የልመና ንግድ ፈቃዳቸው ቢቀደድ ከአቲየ የባሰ አዘቅት ውስጥ የሚወድቁ ሁሉ እናቴ ላይ ተዘባነኑባት !

"ምነው ይሄ ምንጣፍ እንዳረባ ነገር እዚህ ተጣለ ?" ይላል አንዱ ጎረቤት ወደአንዱ ጥግ የዘመን ቆሻሻውን ተሸክሞ ወደተጣለ አሮጌ ምንጣፍ እያሳየ "አየ አፈር ተሸክሞ በስብሶ ማን እሱን ይታገላል" ትላለች ባለቤት ተብየዋ ትላንት የከሰል ጆንያ ሳይቀር የምታጥብ የነበረች ከሰራተኝነት ወደሚስትነት በአንድ ሌሊት ወለምታ የተሸጋገረች መሆኗን አገር እያወቀ !!

" ግዴለሽም "አፀደ ግማሽ ቀን ብትውልበት" አበባ ይመስላል " ይላል መካሪው

አቲን ይጠሩና ያዟታል ግማሽ ቀን ጭቃ ታጥባለች አበባ ይመስላል ምንጣፉ "አቤት ቤት አያያዝ ! የምንጣፏ ንጣት ብቻ ለመርገጥ ያሳዝናል እኮ እከሊት የእሷ ባል ሚስት አገባሁ ይበል " ይባልላታል ተወዝፋ አቲየን ቁራሽ በማይገዛ ብር መንደር የሚያለብስ ምንጣፍ ያሳጠበች እከሊትን "አፀደ በይ እንች ያዥ " ትልና ሶስት ብር ትሰጣታለች አቲየ ተቀብላ ወደማደሪያዋ ትመለሳለች አትከራከርም !!

ቀናቸው የተዳረሰ እርጉዞች ሰላሳ ትራስ ደልድለው በረንዳቸው ላይ ይቀመጡና ቀኗ የደረሰ እናቴን "በደንብ እሽው እንጂ" እያሉ ልብስ ያሳጥቧታል ለዘመናት በስንፍናቸው ቤታቸው የከመሩትን ቆሻሻ ሲያስፀዷት ይውላሉ ማሪያም ማረችሽ የሚል ጠያቂ ቤታቸውን እንዳይታዘብ  የበከተ ቤታቸውን ከቅዱስ ይኳንስ እስከ ቅዱስ ይኳንስ ውሃ ነክቶት የማያውቅ መጋረጃቸውን ያሳጥቧታል !! ወይስ ከእርጉዝ እርጉዝ ይለያል የድሃ እርግዝና ቢጨነግፍም እዳው ገብስ ነው አይነት ፍዳዋን ያበሏት ነበር እናቴን

ለምን ለፋች አይደለም የለፋችበትን ከልክለዋታል አፈር ያብላቸውና የደም ገንዘብ የበሉ ናቸው፡፡ ዳሌያቸውን እያገማሸሩ ወንድ የሚያሳድዱ ሴት ልጆቻቸው አቲየ ከእርግዝና ህመም ጋር እየታገለች ያጠበችውን ልብስ የለበሱ እርኩሳን ናቸው ህፃናት ልጆቻቸው በየሜዳው ሲንከባለሉ እናቶቹ በሳምንቱ መጨረሻ ስለሚደክመው የአቲየ ጉልበት ሳይሆን ስለሳሙናቸው ነበር የሚጨነቁት "አንተ ልጅ ኸረ የሳሙና ጡር አለው " እያሉ አቲየ ቃል ሳትተነፍስ ማንንም ሳታማርር አስከወለደችበት ቀን ድረስ ስትሰራ ነበር፡፡

# ክፍል 9

እኔ የተወለድኩ ቀን ከጧት " አቃጣሪዋ ዘርፌ" ቤት ወተት ስታልብ ነበር ረፋዱ ላይ የአንዲት ጎረቤት በርበሬ ስትቀነጥስ ዋለች ውጋት ሲጀምራትና ምጡ ሲጫናት ወደ መንደር አዋላጇ አልማዝ ቤት ሂዳ እየፈራች "እትየ አልማዝ እያመመኝ ነው ምጥ ነው መሰለኝ " አለቻት

"ውይ በሞትኩት መጣሁ እቤትሽ አረፍ በይ " አለቻት አልማዝ ግን አልመጣችላትም

እኔ ልወለድ አቲየ ምጥ የተያዘች ቀን ዘርፌ የምትባለዋ አቃጣሪ ባልቴት የአሜሪካ ላሟ ያልታወቀ ነገር በልታ ሆዷ ተቆዝሮና አረፋ ደፍቃ እየጓጎረች ነበር አሉ  የመንደሩ ሰው ከአቲየ ምጥ ይልቅ የዚች የአሜሪካ ላም ነብስ አስጨንቆት አዋላጇ አልማዝ ሳትቀር ወደዛው ሂደው ነበርና አቲየ ብቻዋን እኔን ተገላገለች!! ብቻዋን !! የቀን ስራ ያጠነከራት ብርቱ ሴት ባትሆን ኑሮ ሟች ነበረች ብቻዋን ወለደችኝ!! አንድ የእንስሳት ሃኪም ተጠርቶ የአቃጣሪዋን ዘርፌ ላም ሆድ እስክርቢቶ በሚመስል ነገር ወግቶ ሲያስተነፍስላትና ላሟ መጓጎሯን ስታቆም መንደርተኛው እልልታውን አቀለጠው እኔ ስወለድ ግን ማንም እልል አላለም !!

በዚህ መሃል አዋላጇ አልማዝ “በሞትኩት ያች ሚስኪን ምን ደርሳ ይሆን “ ብላ ወደቤታችን ተጣደፈች አቲየ እኔን አቅፋ አገኘቻት “የወርቅ ፍልቃቂ የመሰልኩ እኔ” በእሳት የተፈተንኩና የጥላቻ እሳት የምተፋ እኔ አላፊ አግዳሚውን የምራገም እኔ በእናቴ እቅፍ ላይ!!

ታሪክ ይወቀኝም አይወቀኝም እናት የተባለች ታላቅ አገር ከስግብግብ ከአስመሳይ ከራስ ወዳድ ከአሽቃባጭ ደሃ ከማይወድ እምነት ከሌለው ሆድ አምላኩ ከሆነ አመንዝራ እና ጨካኝ ጎረቤት ቅኝ ግዛት ያወጣሁ ጀግና እኔ ተወለድኩ !! አገሬ እናቴ አፀደ ናት ! ባንዲራየም የእናቴ ቀለም አልባ አሮጌ ቀሚስ ድምጿ መዝሙሬ ነው ትዛዟ ህገመንግስቴ !! እናቴ አፀደ ወይንም ሞት!! አቲየ ትቅደም!! አቲየ ለዘላለም ትኑር።

መዝሙሬ።

ተንቀሽ የኖርሽው ድሮ ከዚህ ቀደም

እናትየ አፀደ የደፈረሽ ይውደም !!

በሰሜን ስግብግብ የደሃ ደም መጣጭ ጎረቤቶች በደቡብ ራስ ወዳድ በደሃ እምባ የሚዋኙ አጋሰሶች በምስራቅ የእናቴን ፀሃይ እንዳትወጣ የሚጋርዱ አስመሳይና ሆዳሞች በምእራብ ደፋሪወች እና ትውልድ የሚከዱ ካፖርታሞች ከታች በባዶ እግሯ የምትረግጠው ምድር ከላይ እግዚአብሔር (የባህር በሯ) የሚያዋስናት አገር አፀደ ትባላለች የእኔ አገር እሷ ናት !!

አፀደ ከሰማይ ዱብ እንዳለ ጉድ ዘመድ የላትም እናት አባት አክስት አጎት የላትም አልተማረችም ገንዘብም የላትም ግን ሁሉ በእጇ ሁሉ በደጇ ለሆነ ባለፀጋ እግዚያብሔር እንባና ድፍን የኢትዮጲያ አምሳ ብር ያበደረች ልበ ሙሉ ሴት ናት እግዚያብሔርም የማንም ብድር በእጁ ይቆይ ዘንድ አይወድምና ብድሩን ይከፍል ዘንድ እኔን መንገድ አደረገ ለድፍን ሃያ አምስት አመታትም አነፀኝ ደለደለኝ

እግዚአብሔር ፈጠነም ዘገየም ወደእያንዳንዱ ሰው ሒወት ውስጥ ይመጣል ሲመጣ የእግዜርን እርምጃ የእግሩንም ዳና የሚቋቋም መንገድ የሚሰራው “መከራ” በሚባል ኮንክሪት ነው!! ዙሪያህን የከበበህን ችግርና እልህ አስጨራሽ የሂወት ፈተና ስታልፍ የእግዜር የመጀመሪያ እርምጃ ትጀመራለች ያኔ ታዲያ እርሃብን ብቻ ሳይሆን ጥጋብንም የምትችል አድርጎ እንዳነፀህ ይገበሃል

አሰራሩ እንደዛ ነው አንተን ከድህነት ማውጣት ብቻ ሳይሆን መጭውን የጥጋብ ዘመንም የሚሸከም ትከሻ እንዲኖርህ አድርጎ ይሰረሃል ካላመንክ እንደየእምነትህ መፅሃፍህን ግለጥ አዱኒያን እንደምናምንቱ ንቀው ፈጣሪን ያመኑ የተከተሉ ሁሉ ሰፈርህ ህንፃ አቁሞ እንደሚሸልለው እብሪተኛ ሃብታም ባንዴ ሰማይ ጥግ አልደረሱም

ፈጣሪ ሲሰራህ ቀስ ብሎ ነው ግን መቸም እንዳትፈርስ አድርጎ!! ያኔ ደስ ይልሃል ወደህ ነው ጎንበስ ብለህ ታመሰግናለህ በግድህ !! አንተ ላለማመስገን ብትጥር እንኳን ስጋህ ያማረ ፍራሽ ላይ ለሽ ሲል በእርሃብ የተንሰፈሰፈ አንጀትህ ውስጥ የጣመ ምግብ ሲጎዘጎዝ በላዩ ላይ ጥሩ ቡና ስትጨምርበት ከምንም በላይ ደግሞ ራስህን ስትገዛና ልብህ በሰላም ሲሞላ “እግዚያብሔር “ ይመስገን ወላ “አልሃምዱሊላሂ” ይልብሃል አፍህ ከአንተ ትዛዝ ውጭ !! ሰባኪ ከመሰልኩህ ገደል ግባ !! ከገደል ሲያወጣህ ተመስገን ትላለህ !! ቆይ ! ገደል ከመግባትህ በፊት ግን የጀመርኩትን ልጨርስልህ።

## ክፍል 10

አቲየ እኔን ከወለደች በኋላ ትንሽ ተስፋ ልቧ ውስጥ አደረ “አባቱ በልጁ አይጨክንም መቸም “ ብላ ግን አባት በልጁ ጨከነ “ቀለመወርቅ “ አባት የመሆን ሞራሉም ብቃቱም የሌለው ሴሰኛ ሽማግሌ መሆኑን የአቲ ልብ ያወቀው ብዙ ቆይቶ ነበር በሰባት ቀኗ ከአራስ ቤቷ ተነስታ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ስራዋን ጀመረች “ኧረ ወገብሽ ይጥና “ ያላት አልነበረም የበሰበሰ ድሪቷቸውን ከምረው ጠበቋት እንጅ !! “የምትገርሚ ጠንካራ ልጅ “ እያሉ አርባ ቀን

ሙሉ ተዘፍዝፈው ሊጣቸውን ሲያሻምዱ ኑረው ሲወጡ እኳን አራስነት ምን ያህል ከባድ መሆኑን እንደማያውቁ ሁሉ

ልጅ ይዛ ስራ መስራት ከባድ ነበር ለአቲ በየቤቱ በረንዳ ላይ እያስተኛች ሳለቅስባት እያጠባችኝ (ምናባቴ እንደሚያስለቅሰኝ እንጃ) አቲየ ብርቱ እናት ከሂት ጋር ትግሏን ቀጠለች አንድ ሁለት ሶስት አራት ወር ለአቃጣሪዋ ዘርፌ አቲ እየፈራች እንዲህ አለቻት

"አትየ እኔ እንግዲህ እስካሁን ለልጁ አንድ ነገር ያደርጋሉ ብየ ጠበኳቸው እሳቸው ግን " "ማናቸው ልጀ " አለች ዘርፌ አካሄዱ አላምር ብሏት ፊቷን አጨፍግጋ "ጋሽ ቀለመወርቅ" አለች አቲ " እህ ደሞ እሱ ምን ቤት ነው ባንች ልጅ " "እትየ ፈርቸ አልነገርኮትም እንጅ ተሳቸው ነው " "ወዲያ ዝም በይ ምን ትላለች እች የተከበረ ሰው አናት ዘሎ ፊጥ ማለት ምን ይሉት ብልግና ነው ሁለተኛ እንዲህ ያለ ነውር ስትተነፍሽ ብሰማ ውርድ ከራሴ ሂጂ አሁን ወዲያ ያው ደመወዝሽ " ብላ አስር ብር ወረወረችላት ስራዋ አስደንግጧት እንጅ ሳምንት ነው ገና ደመወዝ ለአቲ ከከፈለቻት

ቀለመ ወርቅ ይህችን ጭምጭምታ ሲሰማ ተንኮሉን ጀመረው አቲየን ከመንደሩ ሊነቅል እንቅልፍ አጣ ! አቲየ ለአባ ስቲፋኖስ ሽምግልና ላከችበት ሽምጥጥ አድርጎ ካደ "ምን ማለተዎ ነው አባ እኔን በእንዲህ ያለው ቅሌት እንዴት ይገምቱኛል " ብሎ በአባ ክፉኛ ተቆጣ ። ይባስ ብሎ ከዘርፌ ጀምሮ መንደርተኛው ሁሉ አቲየን ስራ ማሰራቱን አቆመ አንድ መንደር ህዝብ አንዲት ደሃ ላይ አምፀ

ቀለመወርቅ እና ዘርፌ ነበሩ የተንኮል ድሩ ፊታዮች " ነገ ባልሽን ስሙን ብታጠፋውስ ሰው እንደሆነ አንች ቤት ልብስ ማጠቧን ገባ ወጣ ማለቷን ነው የሚያየው " ይሏታል ለአንዷ አሰሪ "እውነተዎትን ነው እትየ ዘርፌ ለአቶ ቀለመ ወርቅ ያልተመለሰች እች " ትላለች በቃ አቲየን በስበብ አስባብ ታባርራታለች "ውይትላንት ልጆቹ አጠቡት ልብሱን " በቃ !!

አቲየ ግራ ገባት እኔን አዝላ ስትንከራተተት ትውልና የሚሰራ ስራ አጥታ ማታ እቤት ትመለሳለች እቤት ውስጥ የነበረችው እርጋፊ በሶ ብቻ ነበረች ወደማታውቀው መንደር እየሄደች "የሚታጠብ ልብስ አላችሁ " ትላለች "የለንም" ወፍጮ የሚሄድ እህል በርበሬ ካለ "የለም የለም " ይላሉ ያዘለችውን ልጅ እያዩ

አቲየ ተንከራተተች በመጨረሻም ያላት አማራጭ ልጇ በርሃብ ከሚሞት ቀለመወርቅ እግር ላይ ወድቃ "ይማሩኝ " ማለት ነው ቀለመ ወርቅ ቀጣፊው ነብይ አሱ በመንደሩ "ይታሰር" ያለውን ስራ ሰይጣን በድፍን አዲስ አበባ ያስረዋል!! አቲየ "ይቅረ ይበሉኝ ልጁ የእርሰዎ አይደለም ቢቸግረኝ ነው ክፉ የተናገርኩት" ልትል ወደቀለመወርቅ ቤት ገሰገሰች

ለክፋቱ ደግሞ አይን የለ አፍንጫ ፀጉር የለ ጆሮ እኔ ቁርጥ ቀለመ ወርቅን ነበር የምመስለው ብቻውን የወለደኝ ይመስል አቲየን የሚመስል አንዲት ነገር የለኝም የቀለመወርቅ የልጅነት ፎቶ ቁጭ!! ቢሆኑም " ይቅር በለኝ ልጅህ አይደለሁም" ልል በእናቴ ጀርባ ላይ ወደአባቴ እየሄድኩ ነው አባት ያሳጣውና ይሄ የውሻልጅ !!

ቀለመ ወርቅ የእድር ዳኛው ጋር ተነጋግሮ አቲየን ከማደሪያዋ ሊያፈናቅላት ሲዶልት እንዳመሸ የዘርፌ ላም ጠባቂ ለአቲየ ትላንት ሹክ ብሏት ነበር ለይቅርታ የባሰ ያሮጣት አንዱ ጉዳይም ይሄ ነው ደግነት ጥግ እንደሌለው ሁሉ ክፋትም መጨረሻ የለውም ይሄ ክፉ አቲየን ማሳደዱን በትጋት ተያይዞት ነበር እናም አቲየ ይቅረታ ልትጠይቅ " ማረኝ ጌታየ " ልትለው ሄደች

ወዳጀ እግዜር ይቅርታ ይወዳል ማለት " ማንም ጥጋበኛ እግር ስር " እየሄድክ እንድትደፋ ይሻል ማለት አይደለም አቲየ የእኔን የልጇን ነብስ ለማትረፍ እራሱን በፈጣሪ ቦታ አስቀምጦ ይቅርታ ሊጠየቅ የተዘጋጀው ካፖርታሙ ቀለመወርቅ ቤት ልክ በሩ ላይ ስትደርስ በቃ የግቢውን በር ልታንኳኳ እጇን ስታነሳ እግዜር "ተመለሽ " አላት ያው እንግዲህ እግዜር ሲናገር በሰው አይደል

የእድር ለፋፊው እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ አቲየን ከኋላዋ በቁጣ ጠራት በስሟ አይደለም “አንች አንችን እኮ ነው ምን ያለችው ናት ጃል “ እያለ  አቲ እየተጣደፈ ወደእርሷ የሚመጣውን ለፋፊ ቁማ ጠበቀችው አጠገቧ ሲደርስ “ ምን መሆንሽ ነው አንች ሴትዮ የአዙሪት ቅጠል ረግጠሻል “ አለ “ምነው “ አለች ግራ ገብቷት “ምነው ትለኛለች እንዴ በይ ነይ አሁን እቃ ማስቀመጫ ቤቱን ከፈችላቸው ሰው ሙቶ ድንኳን ልናወጣ ብንል ቁልፍ ይዘሽ ጠፋሽ አገር ተረፈ እነዴ ያልኳተንኩበት የለም አንችን ፍለጋ “ አለ በማማረር አቲየ ቁልፍ ልትሰጠው አስባ አንድ እቃ ቢጠፋስ ብላ ስለፈራች የሰውየውን የማያቋርጥ ድንፋታ እየሰማች ተመለሱ “አገር ተረፈኝ እንዴ ዘርፌ ቤት ከዘርፌ ቤት ጀሚላ ቤት ጀሚላ “ወደላይ ሄደች” ብትለኝ ዝናሽ ቤት  ዝናሽ ” አንዳንዱ ሰው አያባራም ከሱ ያነሰ ሰው ያገኘ ሲመስለው ሌሎች ያልሰሙትን ሁሉ ይዘረግፋል ሌሎች ያሉትንም ይላል

እቃ ቤቱ ሲደርሱ ብዙ ሰወች ተሰብስበው ነበር አንዲት ነጭ የእቃመጫኛ መኪናም ቁማለች  መኪናዋ ጎን ነጠላዋን ያዘቀዘቀች ሴት ጀርባዋ ላይ ፎጣ ጣል ያደረገች ፀጉሯን በሻሽ አስራ ከቀሚሷ ስር ቱታ ሱሪ የቱታውን ጫፍ ካልሲዋ ውስት ጠቅጥቃ ነጭ ሸራ ጫማ የተጫማች ደልደል ያለች ወይዘሮ ቁማለች (የአዲስ አበባ ሴቶች ሃዘን ማካበድ ይችሉበታል ትጥቃቸው ሲታይ ዘመቻ የሚሄዱ እኮ ነው የሚመስሉት)

እች ከራስ ሻሸዋ እስከ እግር ካልሲዋ የነገርኳችሁ ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ትባላለች ዋናው መንገድ ላይ ወደግራ ታጥፎ ከሹልቃ ክትፎ ቤት አጠገብ ያለው ባለሁለት ሆቴል ቤት የእርሷ ነው!! እዚህ ነዳጅ ማደያው ኋላ ያለው መኖሪያ ቤቷ እራሱ የሚያስፈራ ትልቅ ግቢ ነው እና እች ሃብታም ሴትዮ አቲየ ተጠርታ ከመድረሷ በፊት በወሬ ወሬ “ዘበኛው ነው የጠፋው ? “ ትላለች “አይ እዚህ የምትኖረው ልጅ ናት “ አላት የእድሩ ሊቀመንበር “እዚህ መጋዘን ውስጥ ሰው ይኖራል ያውም ሴት ልጅ ? “ አለች ከልቧ ደንግጣ በቆርቆሮ ቤቱ ዙሪያ የሸንት መሸኝያ ቆሻሻ መድፊያ ቦታ ሲሆን እዛ አካባቢ ለደይቃ መቆም እንኳን ክርፋቱ አይጣል ነበር በቤቱ ጥግ ጥግ ሳርና ቅጠላ ቅጠል አብቅሎበት መቃብር ቤት አስመስሎታል ጣራውም ላይ ሃረግ ተንዝንዟል

አቲየ ስትደርስ የሴትየዋ ድንጋጤ እና ሃዘን ጨመረ ከጎኗ ለቆመው ሰው “ጭራሽ ህፃን ልጅም ይዛ ነው እዚህ የምትኖረው “ አለችው “እዚሁ ነው እኮ የወለደችው “ አላት አንጀቷ ተንሰፈሰፈ ቤቱ ሲከፈት እች ሴት ጉዱን ልየው ብላ ወደውስጥ ተራመደች “እትየ እጥፍወርቅ ኸረ አቧራ ነው ጉንፋን ያስይዝሻል “ እያሉ ተንጫጩ የእድሩ ሰወች ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ግን ወደውስጥ ገብታ የአቲየንና የኔን ምኝታ አየች የተበሳሳውን የቤቱን ግድግዳና ጣሪያ ተመለከተች በራሷ አይን ሳይሆን በእግዜር አይን እናም ሁለት ጊዜ አስነጠሰችና አቲየን እንዲህ አለቻት

“አሁኑ የምትፈልጊውን እቃሽን መኪና ላይ ጫኝ እኔ ቤት ትኖሪያለሽ ማነህ ና አግዛት “ አለችው የእድሩን ለፋፊ እቃችን የቆመችው መኪና ላይ ተጫነ (ወጉ አይቀር እቃ ልበል እንጅ ) የእድር ለፋፊው ማውራቱን አላቋረጠም “ያንች እጣ ፋንታ እንደመብራት ሊበራ እኔ ካላምስት ሳንቲም እንዲህ መኳተን ነገ ሰው ብትሆኝ አንድ ዋንጫ ጠላ አትይኝም አውቀዋለሁ እጀ አመድ አፋሽ ነው አገር ቀረኝ እንዴ ዘርፌ ቤት የለችም ሲሉኝ ” እንደአዲስ ጀመረ

## ክፍል ፲፩

አቲየ ለመርገጥ የሚያስፈራው የወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ግቢ ውስጥ አንዲት ቆንጆ ሠርቪስ ቤት ተሰጣት። ያውም ከነሙሉ እቃው።

“ማነው ስምሽ እናቴ “ አለቻት አቲየን ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ

“አጠደ”

“ውይ የኔ ድንቡሽቡሽ ስንት ወሩ ነው “ አለች እኔን እያየች

“አሁን የፊታችን ገብሬል መንፈቅ ይሞለዋል “ እጇን ወደኔ ዘረጋች ፈገግ ብየ እጇን ለቀም ህፃናትን መለይካው ይመራቸዋል የሚባለው እውነት ሳይሆን አይቀርም ወይም ሴትየዋ እጅ ላይ የተገጠገጠው የወርቅ ቀለበትና ጌጣጌጥ መጫወቻ መስሎኝ ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ አቲየን እንዲህ አለቻት

“ ላንችና ለልጅሽ ሆድ አታስቢ እዚህ ተርፎ ለሚደፋ እህል የበላነውን ትበያለሽ ብትወጅ እኛ ጋር እየሰራሽ ከፈለግሽም ያሻብሽ እየዋልሽ እዚሁ ኑሪ ቤትሽ ነው

“ ኑሪ ኑሪ ኑሪ ኑሪ ኑሪ በሂወት ኑሪ ሌሊት ኮሽ ባለ ቁጥር ሳትሰጊ ኑሪ ልጅሽን እንደፈለግሽ የምታጥቢበት የሽንት ጨርቅ የምታጥቢበት ውሃ ሳያሳስብሽ ኑሪ ልጅሽ የሚበላው ነገር ሳይቸግረው ኑሪ ኑሪ እግዜርም ሲናገር ልክ እንዲህ ነበር ”ያውላችሁ ምድር ኑሩበት ውሃው ያው ምግቡ ያው መኖሪያው ያው ” ይሄው ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ግቢ ዘፍጥረት እራሱን ሲደግም

“በመጀመሪያ ምድር ባዶ ነበረ ባዶው ላይ አንዲት የጨለመባት ሚስኪን ሴት ልጅ አዝላ ቁማ ነበረ እግዜር ብርሃን ይሁን አለ ቦግ !! “ ከእግዜር ብርሃን ጋር ሲወዳደር ቀለመወርቅ አብሪ ትል ማለት ነው ዘርፌ ሃይሏን የጨረሰች የእጅ ባትሪ ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ጨረቃ የእግዜርን ብርሃን የምታንፀባርቅ እግዜር ግን ፀሃይ ከአድማስ እስከአድማስ በብርሃን የሚያጥለቀልቅ እናም የሚሞቅ !!

አቲየ በተሰጣት ምርጫ መሰረት አዛው ቤት ልትሰራ ወሰነች በእርግጥም የተሸለ ምርጫ ነበረ !! የማንንም ፊት ከማየት በእጅጉ የተሸለ ለእኔ በተለይ ግቢው መቦረቂያ የወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ፈገግታ ምቾሆት ሆነልኝ በዛ ሰፊ ግቢ ውስጥ ወይዘ እጥፍ ወርቅ ወጣት ተማሪ ልጃቸውና እኛ ብቻ ነበርን የምንኖረው የወይዘሮ እጥፍ ወርቅ አምስት ልጆች ኑሯቸው በውጭ አገር ነበር !!

ወሮ እጥፍ ወረቅ አስገራሚ ሴት ነበረች እንኳን አቲየ የድሮ እመቤቷ ዘርፌ እንኳን የማታልመውን ከውጭ አገር የመጣ አንድ ሻንጣ ልብስ ሰጠቻት ለኔም ቆንጆቆንጆ ልብስ ገዛችልኝ ዘነጥን !! እኔና አቲየ ቂቅ ብለን ዘነጥን ደግሞ ስናምር !!

አቲየ ከወይዘሮ እጥፍ ወርቅ የተሰጣትን ልብስ ለብሳ አበባ መስላ ብቅ ስትል ዘርፌ አይኗ ደም ለበሰ ቀለመወርቅ ደም ግፊቱ ከፍ አለ ክፉ አሳቢወች ምን ሃብት ቢተርፋቸው የሚጠሉት ሰው ጥቃቅን ለውጥ ያንገበግባቸው የለ ዘርፌና ቀለመወርቅ የምቀኛ ግንባር ፈጥረው ተንገበገቡ የግንባሩ ፀሃፊ ሰይጣን!!

እናም ሰይጣን ከቀለምወርቅ እና ዘርፌ ኋላ እግዜርም ከአቲየ ፊት ቁመው ጦርነቱ ተጀመረ !! አሁን በኑሮ ማስፈራራት በክብር መንጠባረር የለም ማንም ሆዱ ከሞላ ጀግና ነው ማንም ቢመታ የሚወድቅበት ቢቆስል የሚታከምበት ካለው ጀግና ነው ማንም የሚያከብረው ሰው ከጎኑ ካለ በሌሎች ንቀት ሞራሉ እንደደረቅ እንጨት አይሰበርም ዋናው ስንቅና ትጥቅ ግን ማንም እግዚያብሄር ከኋላው እንዳለ ካመነ ልበ ሙሉነው!! አቲየ ይሄን ሁሉ ሁና ነውወደጦርነቱ የገባችው !! እናም ጦርነቱ በታሪክ “ወርቃማው ጦርነት” በመባል ይታወቃል በእኔ በነብሴ ዘገባ !! ወደፊት ልጆቾ “ለምን ወርቃማው ጦርነት ተባለ “ ብለው ቢጠይቁኝ መልሴ አንድ እና አንድ ነው በቀለመወርቅና በእጥፍ ወርቅ መካከል በተደረገ ሰበአዊ ጦርነት በእሳት የተፈተኑ ወርቆች ወደምቾት አገር ስለተሰደዱ !!

## ክፍል 12

የባርነት አስከፊ ገፅታ ያለው በባርነት መገዛቱ ላይ ሳይሆን በባርነት የተገዙበት መንገድ ላይ ነው በፍላጎት ለሌሎች ባሪያ መሆን ለራስ ሂሊና የጌትነት ማእረግ ስለሚያጎናፅፍ ለነፃነት ትግል ሳይሆን ለምስጋና ራስህን እንድታዘጋጅ ነው የሚያደርግህ (እሰይ እንኳንም ባሪያ ሆንኩ የሚባልለት ባርነት አለኮ ) ሰወች በፍቅር ለአገራቸው ባሪያ ይሆናሉ ለፈጣሪያቸው ይገዛሉ ለሚወዷቸው ያገለግላሉ ግን ደስተኞች ናቸው ለምን መንገዱ ፍቅር ነዋ !!

አቲየ ዙሪያውን በእረኸም የግንብ አጥር ወደተከበበው ግቢ ገብታ ብትከትምም እጣ ፋንታዋን አላመለጠችውም እጣ ፋንታ እኮ ጥላ ነው በዙሪያህ ያለውን ችግራና መከራ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ብርሃን ሲጠፋ አብሮ የጠፋ ይመስለሃል እንጅ ቀን የሚሉት ፀሃይ ወጋገኑን ሲቀድ እጣ ፋንታህ ከትላንቱ በላይ ደምቆ ካንተ በላይ ገዝፎና ወፍሮ ከፊትህ ይመረሃል ከኋላህ ይከተለሃል አቲየም እጣ ፋንታዋን ስንዝር አላመለጠችውም ከባርነት ወደፍቅር ባርነት ተቀይሮ በትልቁ ግቢ ውስጥ ጠበቃት እንጅ ሰው አጥቶ ውርማ ውጦት የነበረውን የወይዘሮ እጥፍወርቅ ግቢ ነፍስ ዘራችበት ሰፊውን ግቢ ከጧት እስከማታ አፅድታ ትልቁን ቤት ውበት ትደፋበታለች የወይዘሮ እጥፍ ወርቅንም ሆቴል ቀጥ አድርጋ የያዘችው አቲየ እራሷ ነበረች

የሆቴሉን እንጀራ ሙሉ በሙሉ ትጋግራለች የአልቤረጎወቹን አንሶላዎች ታጥባለች እንደዛም ሁኖ በጣም ደስተኛ ነበረች ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ደግ ሴት ነበረችና ምንም ቢደረግላት ይገባታል የአቲየ ባርነት ጣፋጭ ነበር መሃተመ ጋንዲ" ወደወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ግቢ ጎራ ቢሉ ኖሮ "ነመስቲ እኛም የታገልነው ለዚች አይነቷ ባርነት ነበር በርቱ " ብለው የሚሄዱ ይመስለኛል !!

ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ አቲየን እንጀራ "ጋግሪ" አላለቻትም እራሷ አቲየ ለሆቴሉ እንጀራ ግዥ በቀን የሚወጣውን ብር ስትመለከት "ምጣድ ግዙልኝ እራሴ እጋግራለሁ " አለች የሆቴሉን አንሶላ" እጠቢ" ያላት ማንም አልነበረም አጣቢዋ ስትጨማለቅ ስታያት አቲየ የእኔ የልብ ሰው"ምነው እቴ ሰው የሚተኛበት አይደለም እንዴ " አለችና እጇን ሰቅስቃ ገባችበት "አቦ የእጥፍ ወርቅ ቤርጎ አንሶላው ብትል ፎጣው እንዴት ይጸዳል " እስኪባል የወይዘሮ እጥፈ ወርቅ ልብ አሴን በልጅነት መንበር ላይ ወስዶ አስቀመጣት እኔንም በልጅ ልጅነት!!

ግቢው የእኔ ነበር እንዳሻኝ የምሆንበት ግዛቴ የሳሎኑ እቃ የእኔ ነበር ጆሮ ጭው የሚያደርግ ዋጋ የተከሰከሰበት ሶፋ ላይ ሸንቸበታለሁ ወተት ደፍቸበታለሁ አቀርሸቸበታለሁ ለአይን የሚያሳሳውን የቡፌ እቃ አንኮታኩቸዋለሁ የወይዘሮ እጥፍ ወርቅን ባለ አልማዝ ፈርጥ የአንገት ሃብል ከአንገቷ ላይ በጣጥሸዋለሁ (የዚህ አገር ወርቅ አንጥረኛ አይሰራውም ተብሎ ተቀምጦ ቀረ ) የፋናየን (እህቴ ማለት ናት የወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ልጅ) ቀይና ውብ ፊት ቦጫጭሬዋለሁ ፋኒ እንደህፃን ልጅ ነበር የማስለቅሳት አቲየ ስትነግረኝ ፋናየ ከትምህርት ቤት ስትመጣ ቦርሰዋን እንዳዘለች እኔ ላይ ትጠመጠምና ድብድብ ነው አሻንጉሊት ካየች የህፃን ልብስና መጫወቻ አይኗ ውስጥ ከገባ ለእኔ ለመግዛት እናቷ ጋር "ብር ስጭኝ አልሰጥም " ጦርነት ነው

የእናቴ ንፁህ ልብ እንደስፖንጅ ፍራሽ በሂወቴ መንገድ ላይ ተነጥፎ በዛች ቅፅበት የነበረ ልጅነቴን እንከን አልባ አድርጎልኛል ጥፋቴን የሳቅ ምንጭ ለቅሶየ ለማባበል ለሚራወጡ ቤተሰቦቸ የ "ማባበል ስራ ጀምሩ " ደወል ነበር የፍቅር እና የቤተሰብ ቅንጦት ቶምቦላ በጧቱ የወጣልኝ ጨቅላ !!

ሶስተኛ አመቴን ልይዝ ሁለት ወራት ብቻ ሲቀሩ በእኔና በአቲየ ሂወት ላይ ድንገት ፀሃይ ጠለቀች ብርሃን ይሁን ያለ አምላክ በቁጣ "ጨለማ ይሁን" ብሎ ያዘዘ ይመስል የዚህን ሁሉ ጊዜ ውብ ብርሃናችንን በአንዲት ቅፅበት ድርግም አለ !! እንደማብሪያ ማጥፊያ ቀጭ አድርጎ ድርግም!! ድቅድቅ ጨለማ ከቀኑ ሰባት ሰአት ላይ በጠራራ ፀሃይ አይከሰትም ያለው ማን ነው የፀሃይ ግርዶሽ ማለትም ሳይንሱ ያሻውን ይበል እንጅ እውነታው በምንወዳቸው ሰወችና በእኛ መካከል ሞት የሚባል ግርዶሽ መጋረጥ ነው !!

ወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ለኋደኛዋ ልጅ ምርቃን ተጠርታ ወደአዳማ ስትሄድ መንገድ ላይ አንድ ከባድ መኪና ትንሽ ዲኤክስ መኪናዋ ላይ ወጣባት ደግ አይበረከትም !! ተረት አውሪወች ደፋሮች ናቸው "ሲኖሩ ሲኖሩ ሞቱ" ይላሉ ቀለል አድርገው ! ሞት ከተረትም ከታሪክም ከዛሬና ነገም በላይ የገዘፈ ሰቆቃ መሆኑን ማን በነገራቸው "ወይዘሮ እጥፍወርቅ ደግ ሰው ነበረች ስትኖር ስትኖር በተወለደች በምናምን አመቷ በድንገተኛ አደጋ ከዚህ አለም በሞት ተለየች " ተባለ በቃ!!

ስለወይዘሮ እጥፍወርቅ ሞት አቲየ ለማንም ምንም ስታወራ ሰምቻት አላውቅም እግዜር ስትደገፈው የሚወድቅ ምርኩዝ ለአቲየ በማዋሱ ብዙ አመታት ቤተክስቲያን እየሄደች ወቅሰዋለች !! " ስለምን ደግ ኑሮን እንቁልልጭሽ

ትለኛለህ ለተራበ ውሻ ቁራጭ ስጋ ይዞ ሲያጓጓ እንደቆየ ሰው ከጠላቶቸ አይን በላይ ሰቅለህ አኖርከኝ እንዲቦጫጭቁኝ ወደነሱ ጣልከኝ “ እያለች

እኔም ነብስ ካወኩ በኋላ እግዜርን ወቅሸዋለሁ “ ዘርፌ ለመኪና ሞት ምን ይጎድላታል አዳማ መንገድ ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ተጨፍልቆ ለመሞት ቀለመወርቅ ምን ያንሰው ነበር “ ዘፋኞቹ እየተቀባበሉ

“መንገድ አይኑ ይፍሰስ አይባልም ደርሶ

የወሰደውን ሰው ያመጣል መልሶ “ ይላሉ የታለ የአዳማ መንገድ ወይዘሮ እጥፍወርቅን የመለሰው ቢሆንም እግዜር የለም አላልኩም አቲየ እግዜር አለ ካለች ማንም ፈላስፋ ሃሳቤን ስንዝር አያናውጣትም እግዜርን በድፍረት ልናገረው ልነተርከው ልነዘንዘው እና ልነጫነጭበት እችላለሁ በምድር ላይ ሰው ሁሉ ከነእናቴ የተፋኝ እኔ እግዜር የለም ብየ ማን ላይ ልነጫነጭ ማን ላይ ልመናቸክ ማንንስ ልነዝንዝ

በእርግጥ አይኑ ይፍሰስ የተባለው መንገድ ዘርፌንና ቀለመወርቅን ወስዶ ባይመልስም ባልከፋ እግዜርስ ምኑ ሞኝ እነዚህን ጥራጊ ፍጥረቶች ወደሰማይ ቤት የሚጠራ እዚሁ ይጨማለቁ እንጅ ደሃ ላይ አፋቸውን ይክፈቱ አስመሳይ መንደርተኛ ግፋቸውን ባናቱ ስማቸውን በምላሱ ተሸክሞ ሲኖር አግዜር ለሲኦላቸው የሚሆን ማገዶ ይሰበስቡ ዘንድ እድሜ ይጨምርላቸው በየአመቱ ልደታቸውን በፌሽታ ያክብሩ !!

ደስ የሚለው ነገር አዳማ መንገድ ላይም ባይሆን በመኪና አደጋም ባይሆን ዘርፌና ቀለመ ወርቅ ይሞታሉ!!!!( ሃሌ ሉያ ) ያች አቃጣሪ ባልቴት ሽንሽን ቀሚሷን ጥላ እርቃኗን ትገነዛታለች የአሜሪካ ላሞቿ አማላጅ ሆነው ገነት ያስገቧት እንደሆነ እናያለን !! ይሄ ባለጌ ሽማግሌ ቀለመወርቅ ካፖርትና ኮፍያውን መለአከቶች በር ላይ በክብር ይቀበሉትና ማጅራቱን ይዘው ወደእሳት ጉድጓድ ውስጥ ይወረውሩታል !! ያኔ “አሸብር ልጀ ነው “ እያለ ቢቀባጥር እሳቱ ይበርድ እንደሆነ እናያለን !! እንዴ ፈላስፋወች ምን ነካቸው “ሲኦል” የለም የሚሉት ስለቱ ካለ አፎቱን እንዴት የለም ይላሉ ሲኦል መኖር አለበት !!

# ክፍል 13

ከሃዘኑ በኋላ ነገሮች ህልም በሚመስል ሁኔታ ተቀያየሩ ሃዘኑ ባበቃ በጥቂት ጊዜ ፋናየን ወንድሞቿ ስዊዲን ወደሚባል አገር ወሰዷት ፋኒ የእኔ እህት አቲየን ስማ በተሰበረ ልብ ግቢውን ለቀቀች አቲ በምድር ላይ ያሏትን ሁለት ዘመዶች አጣች ዛሬም ይሔን ስታወራኝ አይኗ ውስጥ ህመም ይንቀለቀላል ነብሷ ይቃትታል ዝም ብላ ትቆይና

“አሹዋ “ ትለኛለች

“አቤት አቲየ “

“ስዊዲን የሚሉት አገር ወዴት ነው. ስዊዲን አገር ቤትና ህዝብ ተቆጥሮ የህዝቡ ቁጥር ምናምን ሚሊየን ደረሰ ቢባል አቲየ አታምንም የስዊዲን ህዝብ ቁጥር “አንድ ብቻ” ነው ፋናየ ብቻ !!

አንዲት እድሜዋ አርባ የሚሆን ሽቅርቅር ሲበዛ ቆንጆ የሆነች ሴትዮ (የወይዘሮ እጥፍ ወርቅ እህት ናት ይላሉ) ከሁለት ጨምላቃ ሴት ልጆቿ ጋር ግቢውን ወርሳ ይሁን ጠብቂ ተብላ ትኖርበት ጀመረ ሆቴሉ ተሸጠ እች ሴት አስቴር ትባላለች ምኗም የማይጨበጥ ተልካሻ ሴት ! ከእድሜዋ ጋር ጦርነት የገጠመች ማቶ ! አንዳንዴ በተረት የሚታወቀው አስማተኛ መስተዋት ምኝታ ቤቷ ውስጥ ያለ ይመስል ገብታ በወጣች ቁጥር ልብስ የምትቀይር የሆነ ቦታ በመልክ የምትበልጥሽ ውብ ሴት አለች “ እያላት መስተዋቱ ፊቷ ላይ የትራስ ሰንበር ለደይቃ ከሚወጣ ኢትዮጲያ ላይ ከሰሜን እስከደቡብ ጫፍ አዲስ ስምጥ ሸለቆ ቢፈጠር የምትመርጥ የውበት ስይታም !! የእለት እንጀራዋ የሰው አይን የሆነ ከንቱ

አቲየን እንደሰራተኛ ስለምታስባት ማመናጨቅ የጀመረቻት ገና የሃዘንተኛው እግር ጨርሶ ሳይወጣ ነበር እኔንማ ግልገል ሰይጣን አድርጋ ነው የምታየኝ በወይዘሮ እጥፍ ወርቁ የለመድኩትን መዘባነን ታጥቄ ወደሳሎን ዘው ስል በቲሸርቴ አንጠልጥላ መሬት ለመሬት እየጎተተች በረንዳው ላይ የመወርወር ያህል ትጎልትተኝና "ማነሽ አንች ልጅ ነይ ወደዛ ውሰጅ ይሄን ልጅ እንዴዴ የምን መጨማለቅ ነው እሱ ሁለተኛ እዚህ ምንጣፍ ላይ ሲወጣ እንዳላይ " ብላ እጇን ታራግፋለች አቲየ ነፍስና ስጋዋ እየተሟገተ መወልወያ ይዛ ትገባና ያበላሸሁት ነገር ካለ ትፈልጋለች ብዙ ጊዜ ግን የዚች ከንቱ ጩኸት ምክንያት አልነበረውም ! ምክንያቷ ሰው አለመፈለግ ነው !! ሰውን በማራቅ ሰላም ይገኝ ይመስል ! ሁካታ ነፍሷን ሃቅ አጉርሳ ዝም እንደማስባል የቀረባትን ሁሉ ታፍናለች !!

በዚያ ከወራት በፊት ምግብ ይልከሰከስበት በነበረ ግቢ ውስጥ ጣረሞት ረሃብ ያንዣብብ ጀመረ በፊት ወተት የምትገዛልኝ እጥፍ ወርቅ ነበረች ሞሰቧ ሞሰባችን ድስቷም ድስታችን ነበረ እንዲህ ባጭር ጊዜ ከጓዳችን ቁራሽ ዳቦ ንጣይ እንጀራ ይነጥፋል ብሎ ማን አስቦ አንዳንዴ ምቾት ያዘናጋል ምቾት ስትኖርበት ዘላለማዊ ይመስላል ሜዳ ላይ ጥሎህ እንደጉም ሲተን ነው ፊቱ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንደሞጀሩበት ሰው የምትበረግገው ስንቱ ቤተሰብ ድንገት ከምቾቱ በችግር ተኮርኩሞ ነቅቷል ስንቱ ባለስራ ስራውን ተደግፎ ድጋፉ ሲከዳው ወድቆ ቀርቷል ስንቷ ባለትዳር የባሏ እጅ ሲነጥፍ አብራ ቅስሟ ተሰብሯል አግኝቶ ማጣት ብሎ ህዝቡ የሚጠራው ይሄንን አይደል ተገኝቶ መጥፋት ቢሉት ይሻል ነበር !!

አስቴር አቲየን ታዛታለች ታመናጭቃታለች ትልካታለች ግን ብርም ሆነ ምግብ አትሰጣትም የሚገርመው ደግሞ እቤቱ ውስጥ እንጀራ አይጋገርም ወጥም አይሰራም እናትና ቦዘኔ ልጆቿ የታሸገ ነገር ይገዙና መኪናውም ውስጥ መንገድም ላይ ይበላሉ ማሸጊያውን ወዳገኙበት ይወረውሩታል እነዛን ደማቅ ፅሁፍ ያላቸው የቸኮሌት ላስቲኮች በእርሃብ እየተንሰፈሰፍኩ ቀድጀ የላስኩባቸው ጊዜያት ብዙ ነበሩ ዛሬ ቸኮሌት እንደመርዝ እጠላለሁ !! እነዛ ባዶ የፍራፍሬ ጭማቂ እቃወች ስይት ነበሩ ለኔ ዘመናዊነት ያደነዘዛቸው እናትና ልጆች ምቾት ውስጥ የመነኑ የስንፍናና የክፋት ቆብ የጫኑ ርኩሶች ነበሩ

እንኳን ግቢያቸው ውስጥ ለተጠጉ ሚስኪኖች እርስ በእርሳቸውም የተለያዩ የሰው ከብቶች ምኝታ ቤታቸውን በየፊናቸው ዘግተው ማንም አራት እግሩን ቢበላ አልሰማንም አላየንም ብሎ የሚጮህ ጋግርታም የግለኝነት ባህር ውስጥ የተጠመቁ የምእራብያኑን ቆሻሻ ግለኝነት የስልጣኔ አልፋ የእውቀት ኦሜጋ ያደረጉ ፋዞወች በእንግሊዝኛ እየተለፋደዱ በአማርኛ የአይምሮ መቃወስ ውስጥ የተዘፈቁ "ቤተ እቃወች "

የሞራልም ይሁን የሃይማኖት አልያም ከነፍስ ስልጣኔ የሚመነጭ ጠንካራ ሰብእና የሌለው ኢትዮጲያዊ ውጭ አገር ደርሶ ሲመለስ ምናይነት አሰቃቂ ማቶነት ውስጥ እንደሚነከር የታዘብኩት በነዚህ ከንቱወች ነበር እናታቸው ሃያ አመት ልጆቹ እየሄዱ እየመጡ ከአስር አመት በላይ አሜሪካ ኑረዋል አስቴር ታዲያ ለአመታት ከኖረችበት አሜሪካ ምን ይዛ መጣች ስትደሰኩር ሰምቻታለሁ ለመጣ ለሄደው

"አበሻ ስራ አይወድም ነጮቹ እኮ ለሰአት ያላቸው ክብር ለስራ ያላቸው "

"አበሻ የተመጣጠነ ምግብ አያውቅም ማድፋት ጥሬ ከብስል ማጋበስ "

"አበሻ መቸ ንፅህና ይወዳል ነጮቹ እኮ "

"ኤዲያ የአበሻ ወንድ መቸ ሴት ያከብራል ነጮቹኮ "

"የአበሻ ልጅ አስተዳደግ "

"የአበሻ ህክምና ደግሞ እራሱ በሽታ ነው ነጮቹ እኮ "

"አበሻ ገንዘብ ከመሬት የሚታፈስ ነው የሚመስለው አይኑን በጨው አጥቦ "ዶላር ላኩ ነው" ነጮቹ እኮ አስራ ስምንት አመት ከሞላቸው " ነጭ የባርነት ቀንበር ጫንቃዋ ላይ ተሸክማ የምትደሰኩር ቱልቱላ ከየትም

የፈለፈለቻቸው ልጆቿ በአስተዳደግ ይሁን በግል ባህሪ ምናይነት እናት እንደሆነች ጨኸው እያወጁ አይናችሁን ጨፍኑ ላሙኛችሁ ትለናለች

የነጮቹ ፅንፍ የለሽ ውክቢያ እድሜዋን ሙሉ ያጨቀባት የታላቅነት አባዜ "አበሻን" በበጎ እንዳታይ እንደጋሪ ፈረስ ቀይዷት ለእግዜር ሰላምታ የቀረባት ሁሉ የፈጋችበትን ዶላር የሚነጥቃት እየመሰላት ስጋዋ ያልቃል ልጆቿም በየአጥሩ ጥግ ከሚያናንቋት የአበሻ ወንድ ጋር ሲሳሳሙ እና በየመሸታ ቤቱ ሲዳሩ ከማመሸት ውጭ የፈየዱት ተአምር የለም  በነፃይቱ አገር ኑረው ለመጡ የስልጣኔ ጥጎች የከንፈር ዋጋው የዶላሩን ያህል ውድ አይደለም እነዛ ወንበር ሰበው በክብር ሴትን ልጅ የሚያስቀምጡ "ነጫጭ ወንዶች" የሴትነትን ክብር እየሰበኩ ሰበአዊነታቸውን ከእግራቸው ስር እንደጨፈላለቁት ለመረዳት የጋረዳቸው ነጭ ደመና አይፈቅድላቸውም !!

ለእነዚህ የስልጣኔ ርዝራዦች የሰው ልጅ ስለክብሩ መኖር ስለማተቡ አለማዊነትን በልክ ይሁን ማለቱ "ተራ መኮፈስ ነው" ቦርሳቸውን ከመክፈት ለማንም አላፊ አግዳሚ እግራቸውን መክፈት ይቀላቸዋል ምክንያቱም "ዶላር" "የተከበሩት የነጮች ውድ ቅርስ " ሲሆን ሰውነታቸው የእርካሾቹ የሰነፎቹ ያልተማሩት ስራ የማይወዱት ብር ከመሬት የሚታፈስ የሚመስላቸው አበሾች ርካሽ ንብረት ነው !! በዚህ ፍልስፍና አገሩን አጥመቀውት አገሬው ፈረንጅ ባል ፍለጋ ሲራኮት ቢታይ ምን ይገርማል !!

አቲየ አንድ ቀን እየፈራች ሴትዮዋን አናገረቻት "እትየ ወጥቸ አንዳንድ ስራ ልሰራ ነበረ ምናልባት ከፈለጉኝ ብየ ነው "

"ስራሽ ምንድን ነው " አለች ሴትዮዋ አቲየን ከታች እስከላይ እያየቻት

"እኔ እትየ እጥፍ ወርቅ ጋር እንጀራም እጋግራለሁ ያው ለሁቴሉ እዚሁ ነው ስራየ ሌላ ምን ስራ አለኝ "

"እኔ የማሰራሽ ነገር የለም ውጭ ነው የምንበላው ልትሄጅ ትችያለሽ " አቲየ ደነገጠች

" ቀን ቀን ስራ ሌላ ስፍራ እየሰራሁ ለማደሪያየ እዚሁ ቢፈቅዱልኝ መሄጃም የለኝም ከነልጀ ለነብሴ ብለው እትየ እጥፍ ወርቅ አስጠግተውኝ ነው "

"ኤጭ አበሻ ሲባል "የነፃ ራት " ካልበላ እንቅልፍ አይወስደውም ጤነኛ ነሽ እግር እጅ አለሽ ሰርተሽ ሳትሳቀቂ ቤት ተከራይተሽ መኖር ስትችይ አስጠግተውኝ ቅብርጥሶ ማለት ምን አመጣው ነጮቹ ቢሆኑ " ደሰኮረች አቲየ አዛ መቆየቷ ብዙ ደስ አላላትም ቢሆንም አንዳንድ ስራ ማሰራቱ እንዳለ ልቧ አውቆታል "የነፃ ጉልበት " የማይፈልግ የነጭ አድናቂ ማን አለ እናም አቲየን እነዲህ አለቻት "እንግዲህ ያው ፀባይሽን አሳምረሽ ኑሪ እኔ ጫጫታ ምናምን አልወድም ቤቱን ከፈለኩት በማንኛውም ጊዜ ትለቂያለሽ "

አቲየ እኔን አዝላ ወደረሳችው መንከራተት ተመለሰች  አዲሳባ ውስጥ የምታውቀው መንደር አንድ ነው እዛም ቀለመወርቅና ዘርፌ አሉ ! አሳ ነባሪወቹ ሶስት አመት ፀሃይ ሳይነካት ብርቱካን መስላ የወጣችውን አቲየን ሲያዩ ጥርሳቸውን አፏጩ ቀለመወርቅ ደፋሩ ምራቁን እየዋጠ እንደገና ተመኛት ስላማረባት መንደርተኛው በሙሉ ጠላት ዘርፌ የከፋት ልምጪን አዘጋጅታ ነበር የጠበቀቻት

ከከፍታ እንደመውረድ ውርደት ረግጠው ወዳለፉት ነገር እንደመመለስ ታላቅ ሰቆቃ የለም የራስህ ወገኖች መብረር ስትጀምር "እሰይ" ከማለት ይልቅ ከንፍህ ተሰባብሮ እግራቸው ስር ወድቀህ ስትፈጠፈጥ ለማየት ይጓጓሉ እናም ስትወድቅ ይረካሉ "ብየ ነበር አያችሁ እየተባባሉ" የምቀኝነት ትንቢታቸው የሰመረ ምቀኛ ነብያት ይንጫጫሉ ብሄራዊ ምቀኝነት የተጠናወተው ህዝብ እንደኛ ይኖር ይሆን "ለምን በደፈናው እንሰደባለን" ይለሃል "ምቀኛ" ስትለው የተዳፈነበት አመክንዮ እየደረደረ "ሁሉም አንድ አይደለም" ይለሃል ግን ሁሉም አንድ ነው ጠጥቶታል እንደውሃ በልቶታል እንደእንጀራና ጥሬ ስጋው !! ቢማርም ቢያገኝም ምቀኝነቱን ያዘምናታል እንጅ ቢሞት አይጥላትም ! ማተቡ ናት !!

ከዚህ በኋላ የሆነውን ዝርዝር ነገር ስናገር ማንንም ሳይሆን እራሴን እጠላለሁ ስለዚህ አልናገርም !! አቲየ በስጋም በነፍስም የቀለመወርቅ መጫወቻ የዘርፌ ገረድ ሁና ኖረች ለስንት አመት ዘርፌ ቤት የመደሃኒያለም ዝክር እከሊት ቤት የኪዳነ ምህረት ዝክር አሻሮ የጠላ ቂጣ ድፎ ዳቦ የእከሊት ልጅ ልታገባ ነው ወጥ ሰሪ ጠላ ጠማቂ ሲወልዱ ልደት ክርስትና እሳት በላት እናቴን ውበቷን ጤናዋን ወጣትነቷን እሳት በላው አቲየ እንደብረት ምጣድ እሳት ላይ ተጥዳ እኔ የምባል ጣፋጭ ኬክ በላይዋ ላይ በሰልኩ ይሄ ሁሉ ስራ በዚች ሚስኪን ሴት ላይ ተጭኖ ማታ ወደማደሪያዋ ስትመለስ የአስቴር ጨምላቃ ሴት ልጆች የውስጥ ልብስ ሳይቀር በየቦታው ተወርውሮ ይጠብቃታል

ቀን እናትና ልጆች ሲወጡ ወንድ የሚራኮትላቸው ዘናጮች ሽቷቸው ከሩቅ የሚጣራ ሽቅርቅሮች የቤታቸውን ጉድ ወላድ አይየው እነዚህ በየአደባባዩ ሽቅርቅር የሚሉ ሰወች ቤታቸው የዝርክርክነት ጥግ የሚሆነው ለምንድን ነው ግን ብዙ ሰው አየሁ ሴት ልጅ ቢያንስ የውስጥ ልብሷን የራሷን ገመና እንዴት ሌላ ሰው እንዲያጥብላት ትፈልጋለች ለዛውም በየካፍቴሪያው ተጎልተው ሲገለፍጡ የሚውሉ ስራ ፈት ሴቶች

አይቻለሁ በአስቴር ልጆች እናታቸውም ያው ናት የዘር ነው መቆሸሸ ከማን ይማራሉ ! ያኔ ነው ረጅም ጫማ አድርጎ ከመቆነን በፊት ፀጉር እየነሰነሱ አገር ይየን ከማለት በፊት “ሴት” ሲባል ፊቴ የሚደቀነው ይሄው ፅንፍ አልባ ስንፍና የሆነው የሴት ልጅ ስንፍና እንዴት ይቀፋል መንገድ ላይ ሰበር ሰካ የሚሉ ሴቶች ሁሉ ከውበታቸው በፊት ሻወር ቤታቸው ነው አይኔ ላይ የሚደቀነው

ድንገተኛ ፍተሻ ይደረግ ቢባል ከዝርክርኩ ወንደላጤ ካልሲ በየቦታው ከሚጥለው ወንድ የባሰ ስንት ጉድ ሴቶች አሉ ስንትና ስንት ወር ሙሉ ሰው ሰራሽ ፀጉር አናታቸው ላይ ጀልቶ መሬት አይንካን የሚሉ በዛ የልጅነት እድሜ ተላላኪነትን በተማርኩባት ለመኖር ስል የመሽቆጥቆጥን እርምጃ ዳዴ ባልኩባት በሂወት ውጣ ውረዴ ነበር ሴትነት ደራሽ ንፋስ የሚከምረው ደራሽ ንፋስ የሚበትነው የምድረበዳ የአሸዋ ክምር ነው ብየ በሴት ተስፋ የቆረጥኩት የአስቴር ልጆች “ሴት” መስለውኝ !!

# ክፍል 14

መማርን ጌታ ይባርከው !! መማር መቃጠል ነው ይላሉ ተምሮ ማቃጠል ለእኔ አለሜ ሆነች !!

አንደኛ ክፍል እስከመዘገብ የአባት ስም አልነበረኝም አሸብር ብቻ ነበርኩ ልክ ትምህርት ቤት አቲየ ወስዳኝ ስመዘገብ ጉጉት የመሰለው መዝጋቢ እናቴን ጠየቃት ድሪቶ ቀሚሷ ለአይኑ ቀፎት እያመናጨቃት አይቸዋለሁ ተመዝግቤ ስንመለስ አቲየ ከፊቱ ዞር ስትል ፊቱን አጨፍግጎ መጥፎ ጠረን እንደሚያባርር ሰው በግራ እጁ አየሩን እያራገበ ሲያባርር አይቸዋለሁ

በእርግጥ አቲየ እማማ የብር ጓል ቤት እንኩሮ እያነኮረች ነበር “ምዝገባው ዛሬ ነው የሚያልቀው” ሲሏት ብድግ ብላ ነው የመጣችው ቢሆንስ ልክ ቆሻሻ እንደሸተተው ሰው ሰው እንዲያየው አድርጎ እጁን ያራግባል እንዴ የእማማ የብርጓል ቁጥር አንድ የጠላ ደንበኛ እንዳልሆነ ሁሉ ሊያስተምረን ክፍል ውስጥ ሲገባ እንደባቡር ሃዲድ የረዘመ የጠላ ትንፋግ ተከትሎት እንደማይገባ ሁሉ ነብር አየው ያንን የውሻ ልጅ አስተማሪው እንደጠመድኩት ጡረታ ወጣ !! ደግሞኮ አያፍርም መንገድ ላይ ላገኘው ሁሉ “እኔ ነኝ ያስተማርኩት “ እያለ በኩራት ያወራል በእርሱ የትምህርት አይነት ብቻ ዶክተር የሆንኩ ይመስል !!

“ስም ?” አላት አቲየን

“የእኔን ነው ?” አለች እየፈራች ፈሪ ነበረች እናቴ ፈሪው የአዲስ አበባ ህዝብ እንደያቅሙ ደሃ ማስፈራራትን ተክኖበታል

“አንች ነሽ አንደኛ ክፍል የምትመዘገቢው ?” አላት አጠገባችን ያሉት ሁሉ ሳቁለት አቲየ ተሳቀቀች ሰውነቷ ሽምቅቅ ሲል ቀሚሷን አንቄ ተሰምቶኛል መሸማቀቋ

“የልጅሽን ስም ንገሪኝ ሴትዮ “ አላት እያከላፈታት

“ የእሱ ኢ..ሸብር አሸብር ነው ስሙ “ አለች እራሴን እያሻሸች

“የአባት ስም ?”

“አባ ት “ ብላ ዝም አለች

“የአባቱ ስም ማነው ”

“ቀ “ መጨረስ አልቻለችም ቀለመወርቅ ልትል ፈልጋ እንደነበር የገባኝ ካደኩ በኋላ ነው

“የዛሬዋ ደግሞ የጉድ ናት የልጇም አባት የሚጠፋት ” ብሎ እንደገና እንዲስቁለት ሰወቹን አየ ያልደመቀ ሳቅ ተሳቀለት

“በይ ወደዛ ሁኚ ስታስታውሽ ትመለሻለሽ ተረኛ ቀጥል ” አለ እስክርቢቶውን እያወናጨፈ (አረሳትም ግማሽ ድረስ ቀለሟ ያለቀ ሰሚያዊ ቢክ እስክርቢቶ )

እናቴ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው “በአምላለክ በአምላክ ነው የአባቱ ስም “ አለች መዝጋቢው እራሱን ግራና ቀኝ በብስጨት እያወዛወዘ መዘገበኝ

የአባቱ ስም በአምላክ (በአምላክ አባቴ አይደለም አቲየ ለአምላክ ሰጠችኝ የአምሳ ብሩ ሲገርመው ለእግዜር ሰው አበደረችው አቲየ የእኔ እናት በሂወት ባንክ ውስጥ ብድር ለሚመልስ ብድር በመስጠት የተካነች ባለሙያ ነበረች ነገን የምታይ !! እግዜር የተበደረው ትውልድ ወለዱ የተባረከ ዘር ማንዘር ነው “እስከ ሽ ትውልድ ዘርህን እባርካለሁ “ ብሏል እራሱ እግዜር !!

ትምህርት ቤት ገባሁ !! የክፍላችን ልጆች የኑሮ ደረጃ በዳግማዊትና በእኔ መካከል የተወሰነ ነበር ዳግማዊት የሚታዘል ባለ ዚፕ ቦርሳ ያላት ቆንጆ አንደኛ የሃብታም ልጅ ስትሆን እኔ ከሹራብ የተሰራች ኮሮጆ የነበረኝ አንደኛ የደሃ ልጅ ይሁን እንጅ በንፅህና አልታማም ልብሶቸ ሁልጊዜም ንፁሆች ነበሩ ሰኞ ሰኞ ሰልፍ ሜዳ ላይ የእጅ ጥፍሮቻችን ሲታዩ ንፁህ ነበርኩ የዳግማዊትን ያህል “በፈገግታ “ “ጎበዝ” ባልባልም ከቆሻሻና ከስንፍና የተጣላች ቆራጥ ደሃ እናት አለችኝና ስንፍናና ቆሻሻ አጠገቤ ዝር አይሉም !!

አንድ ቀን ግን በሂወቴ ስሳቀቅበት የኖርኩበት ነገር ተፈጠረ

እንግዲህ አስቴር ከዋናው ቤት አሮጌ ፍራሽ (የሆቴሉ አልቤርጎ ውስጥ የነበሩ ) እና ሌሎችም እቃወችን ከእቃ ቤቷ አስወጥታ እኔና አቲየ የምኖርበት ክፍል ውስጥ አስቀመጠች እንደእቃ ቤት እናም ቤታችን ውስጥ በታጨቀው እቃ ምክንያት ቤቱን እንደልብ ማፅዳት ባለመቻሉ ቁንጫ እንደጉድ ይፈነጭ ጀመረ

አቶ መሃሪ አካባቢ ሳይንስ መምህራችን ነበር ሲያስተምር ስወደው የእረሱን ትምህረት አስር ካስር ነው ሁልጊዜም የምደፍነው አንድ ቀን ግን ዘላለማዊ ጠላቴ ያደረገውን የማይረባ ነገር አደረገ ስለጓሮ አትክልት ጥቅም እያስተማረ እያለ “ዋይ” ብላ ጮኸች ዳግማዊት ቦርሳዋ ላይ ሁለት እሳት የመሳሰሉ ቁንጫወች ዘለውባት ነበር

መምህሩ ሁኔታውን አየ እኔ ከዳግማዊት ጎን ነበር የምቀመጠው ባልገባኝ ምክንያት ተቆጣ “አስቲ ቦርሳህ” አለኝ በቃ እንዲህ ነው ያለኝ ከወንበሩ ስር ከተሰራው የደብተር ማስቀመጫ የሹራብ ኮሮጆየን አወጣሁ አስደንጋጭ ነገር ነበር በርካታ ቁንጮች ከእኔ ኮሮጆ ላይ ተፈናጠሩ መምህር መሃሪ ፊቱን አጨፍግጎ ኮሮጆየን አነሳና ወደፊት ወደጥቁር ሰሌዳው ወረወረው ደብተሮቸ በአየር ላይ ወረቀታቸውን እያርገበገቡ ተበታተኑ (እስከዛሬም ደብተሮቸ በአየር ላይ እየተንሳፈፉ ይታዩኛል አላረፉም ) “ውጣ ጀሮህን ያዝ “ ብሎ በኩርኩም አፈለሰኝ ወጥቸ ጀሮየን ያዝኩ

ከኩርኩሙ በላይ ሃፍረቱ ጠዝጥዞኝ ነበር የታፈነ የጓደኞቸ ሳቅ በትምህርት አልችለኝ ሲሉ እችን እንደውድቀት እችን ከእነሱ እንዳነስኩባት አጋጣሚ ሊጠቀሙባት የእፋኝት ልጆች ስንቱን ትምህርት ስደፍን ለጭብጨባ በመከራ የሚነሳ እጃቸው ዛሬ ሳቃቸውን ሊያፍን ወደአፋቸው ተወነጨፈ ቡፍ ቡፍ ሂሂሂ

መምህሩ መሃሪ (ስሙን ቄስ ይጥራውና ) ስለኋሮ አትክልት የፃፈውን አጥፍቶ ጥቁር ሰሌዳው ላይ "ተ ስ ቦ " ብሎ በትልቁ ፃፈና ከስሩ በድርቡ አሰመረበት !! ያውም አረንጓዴ ቀለም ባለው እና እንደብርቅ በምናየው ጠመኔ !!

ከዛም ስለተስቦ ሙሉ ክፍለጊዜውን ሲለፈልፍ ዋለ " አያችሁ ልክ እናተ ወደትምህርት ቤት ወይም ዘመድ ለመጠየቅ በታክሲ በአውቶብስ ተሳፍራችሁ እንደምትሄዱት ቁኒጫዎችም በአይጦች ተሳፍረው ንፅህናው ወዳልተጠበቀ ቤት ይሄዳሉ  አሁን እሱ ደብተር መያዣ ላይ እንዳያችሁት (እኔን እየጠቆመ) በልብስ ሻንጣ በደብተር መያዣ በሌላም ቁሳቁሶች አማካይነት እየተንጠላጠሉ ከቦታ ወደቦታ በመንቀሳቀስ እንደዳግማዊት አይነት ንፁህ ልጆች በተስቦ ይያዛሉ " በማለት አስተማረ ምን ያስተምራል አስተማሪ የሚባለው ነገር የጥላት ስም እንዲመስለኝ አደረገ እንጅ!! ለረዥም ጊዜ "ተ ስ ቦ" እያሉ ገዋደኞቸ ያበሽቁኝ ነበር ከአርባው ስንፈተን ግን ስለተስቦ ተጠይቀን የደፈንኩት እኔ ብቻ ነበርኩ ሰው ስድቡን አይረሳማ!!

በተለይ እኔ ስድቤን አረሳም!! መገፋቴን አረሳም !! ስድብና መገፋት እንደአረግራጊ ሳንቃ ሽቅብ ተኩሰው በቀል የሚባል ጨረቃ ላይ የሚያሳርፉኝ ሮኬቶቸ ነበሩ እንዲያ ካልሆነ በቀል መቸ አምሮ !! የሰደበኝን ሁሉ አለቀውም!! ለምን ዘላለም አይኖርም አረሳም ! የአዲስ አበባ ህዝብ ሂትለሩን አቅፎ እያሳደገ መሆኑን መች ጠርጥሮ ለፋሽስቱ እድገት ኩርኩምና እርግማን እያዋጣ እንደሆነ መቸ ቀልቡ ነግሮት ሬዲዮና ቴሌቪዥኑ አደንቁሮት ፊልምና ድራማው አሳውሮት ሽቅርቅሮቹ ልቡን አጥፍተውት ህዝቡ ምን እያሳደገ እንደሆነ አያስተውልም !! እያንዳንዱ መንደር አለ የተገፉ ህፃን ሂትለር በቀጥታ ሳይሆን ሳያውቁ ለልጆቻቸው በሚያለብሱት ልብስ በሚያገምጡት ኬክ እንቁልልጭ እያሉ አርፎ የተኛ ረሃቡን ቀስቅሰው ያስነከሱት

ህዝቤ ያሳረፈብኝን የጥላቻ ኩርኩም ነገ በጅምላ እልቂት እከፍለዋለሁ ብቻ ልደግ ደግሞ ብቻየን አይደለሁም ይሄ ሁሉ ተገፍቶ ጎዳና የሚንከራተት ሕፃን ነገ ተንደላቀው የሚማሩትን ቆንጆ የለበሱትን ልጆችህን ሂወት ያመሳቅለዋል የዘረሃትን የጥላቻ ፍሬ ታፍሳታለህ ነገ የበደልከው ያከላፈትከው የረገምከው ህፃን እጅ ላይ ትወድቃታለህ ያኔ በቀሉን በሁለት እጅህ ትቀበላለህ ድፍን አገር ይስማ ተቀምጣችሁ የሰቀላችሁትን ቁማችሁ ማውረድ የሚያቅትባችሁ ቀን ይመጣል  ቱ!! አሸብር አይደለሁማ !!

እኔ ዶክተር አሸብር የሚስኪን እናቴን በደል የምከፍልበትን የመጨረሻውን ክፉ በቀል እያሰብኩ ነው ያደኩት ኒውክሌር ቦንብ ቢኖረኝ እያልኩ ወሰጀ ቀለመወርቅ ግቢ እጥለውና ቁልፉን እጫነዋለሁ የቀለመ ወርቅ ባርኔጣ ከነ እራስ ቅሉ በሮ ኬኒያ ጠረፍ ቢገኝ ግድ አለኝ እነዛን የአሜሪካ ላሞች እንደኢላማ ፊት ለፊት አቁሜ በመድፍ ነገር ሁዳቸውን ብደረማምሰው ወተታቸው ወደሰማይ ጉኖ አዲስ አበባ ላይ እንደነጭ ዝናብ ቢዘንብ  እችን ያህል ሊሰማኝ ነው በአውቶሞቢል በታክሲ በአውቶብስ የሚጓዘውን ህዝብ አንዳች ሃይል ኑሮኝ አፋፍሸ ቀበና ብከተው አይወጣልኝም የእሳት ዲን እንዲያወርድና እግዚአብሄርን ብዙ ቀን ለምኘዋለሁ ዝም ሲል "እግዚአብሄር ለአዲስ አበባ ህዝብ አዝኖ ሳይሆን ህዝቡን ተፀይፎ "ለእነዚህ ማን እሳት ያባክናል " ብሎ ትቷቸው ነው" እያልኩ አስባለሁ

ቢሆንም አንድ ቀራፎ አስተማሪ አፉን ከፈተብኝ ብየ አልተዘናጋሁም ብዙ ሰወች ጎበዝ ተማሪ ነህ ሲሉኝ ይገርመኛል እኔ ምንም የተለየ ነገር አላደርግም አስተማሪው ሲናገር የፃፍኩትንም ሳነብ ከዚህ በፊት የማውቀውን ታሪክ የምሰማ ነበር የሚመስለኝ ፈተናወችን ሁሉ እኔ እራሴ ያወጣኋቸው እስኪመስለኝ ነበር መልሶቻቸውን ጠንቅቄ የማውቀው በትምህርት ቤታችን ማንም ጎበዝ ነኝ የሚል ተማሪ ሲያድግ ከእኔ ጋር እኩል ለመሆን ይመኝ ነበር ብል ማጋነን አይሆንም እነሱ እስከሚያድጉ ቁሜ እጠብቃቸው ይመስል !! "የዛሬ ምናምን አመት አሸብር የደረሰበት እንደርሳለን " የዛሬ ምናሚን አመት አሸብር የኒውክሌር ቦምብ ባለቤት ይሆናል ቡምምምምምምምምምምምምምምም ጥርግርግ

እነዚህ ጉረኛ ሴቶች ሁሉ ሰው ሰራሽ ፀጉራቸው እንደችቦ አናታቸው ላይ እየነደደ ሰቀላ ጫማቸውን ወርውረው በባዶ እግራቸው ለመዳን ሲሮጡ ሆዴን ይዡ እስቃለሁ "ሽማግሌወች መሸሸ አቅቷቸው ሲንቀጠቀጡ እነዛ ልጆቻቸውን በትልቅነት ያልገሰፁ ሁሉ አላዝንላቸውም የቀለመወርቅን በደል አይተው እንዳላዩ ያለፉ አይኔ አፍንጫየ ቁርጥ ቀለመወርቅን መምሰሉን እያዩ "በየት ቤት ብሎ ኧረ ቀለመወርቅ ቀጭን ጌታ ነው እዚህ ቋቁቻም ጋር ምኑም አይመሳሰል" እያሉ ያሽቃበጡ ሁሉ አባቴ ጣረሞት ነው ብየ እልቂት ይዡ ፊታቸው ስቆም " ቁርጥ ጣረሞትን " ይሏታል አልምራቸውም !!

## ክፍል 15

የአስቴር ትልቋ ልጅ "ዛፒ" ትባላለች ትርጉሙ ምን እንደሆነ አላውቅም ምናልባትም "ሰይጣናዊ መዝገበ ቃላት" የሚባል ነገር ካለ ትክክለኛ ትርጉሙ እዛ ላይ ሳይገኝ አይቀርም  እስከዛው ግን በግምት "ዋጋቢስ " ብየ ተርጉሜዋለሁ !! ዘር ከልጓም ይስባል እንዲሉ ቁርጥ እናቷን (ለነገሩ አባቷን የት አውቄው ) እኔ ከስምንተኛ ክፍል ወደዘጠነኛ ክፍል ሳልፍ እሷ የሃያ አምስት ወይም የሃያ ስድስት አመት ወጣት ነበረች ተስፋ የቆረጠች ወጣት እናቷ እና ትንሽ እህቷ ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደውጭ አገር ሲመለሱ እሷ እዚሁ እኛ የነበርንበት ግቢ ውስጥ አንድ ደስ የሚል የተረጋጋ ወጣት ጋር መኖር ጀመረች

መጀመሪያ መኪናውን ውጭ ጋር ያቆምና ተያይዘው ይሄዱ ነበር  ከመሄዳቸው በፊት ዋጋ ቢሷ ትጠራኝና "አሸብር ና እችን መኪና ወልውል " ትላለች "ዛፒየ አሁን እኮ ነው ያሳጠብኳት " ይላታል እርሱ የዋጋ ቢሷ መልእክት ተንቀጥቅጦ የሚታዘዛት ሚስኪን መኖሩን ማሳየት መሆኑን መቸ አውቆ

ቆይቶ እቤት እየገባ መቆየት ጀመረ "አሸብር ና ለስላሳ ግዛ ና ቢራ ግዛ " ብታምኑም ባታምኑም ኮንዶም ሁሉ ታስገዛኝ ነበር መላላኩ ሳይሆን በዛ እድሜ ፋርማሲ ሂዶ ኮንዶም መግዛት ያሳቅቀኝ ነበር ፋርማሲስቶቹ በትዝብት ያዩኛል "የተቀደደ ሱሪውን ሳይቀይር " በሚል ግርምት ሱሪው የተቀደደ ሰው እንትን አያደርግም የተባለ ይመስል

ከዛ ማደር ጀመሩ  በጨለማ በዛ በኮረኮንች መንገድ ቢራ ተሸክሜ እጀን እጀታ እየከረከረኝ የተላላኩበት ጊዜ መቸም አይረሳኝ አቲየ ግቢው በር ላይ ብርድ እያቆራመታት ቁማ ትጠብቀኛለች ገብቸ ቢራውን ስሰጥ ዛፒ ልክ ከፍሪጅ ያወጣችው ያህል ከእጀ ላይ ትወስድና "እንካ ሁለት ፓኬት ሮዝማን ግዛና ና " ትላለች

በመጨረሻ ጠቅልሎ ገባና አብረው መኖር ጀመሩ መኪና ማጠብ ቋሚ ስራየ ሆነ

እውነቱን ለመናገር ጥሩ ባል ነበር ዋሲሁን ይባላል ቤቱ የባለትዳር ቤት እንዲመስል የተቻለውን ሁሉ ይጥር ነበረ ዛፒ ግን የሚቋቋማት አይነት "ሚስት" አልነበረችም ጉራዋ ፀጉር ያስነጫል በውበቷ ስትመካ ልክ የላትም የእናቷ ጫማ ውስጥ ዘላ የገባች ጉረኛ አቤት ጉረኛ ሴት እንዴት እንደምትቀፍ ከምትናገራቸው አስር አረፍተ ነገሮች አስራ አንዱ ስለራሷ ውበት ስለቆዳዋ ጥራት ስለጣቶቿ አለንጋነት ስለልብስና ሽቶወቿ " ብራንድ " በቀጥታ አልያም በተዘዋዋሪ ይተርካሉ !!

ዘላ የተዘፈቀችበት ትዳር ከጭፈራ ቤት መዳራት በምን እንደሚለይ ገና ያልገባት አካሏ ብቻ ሀሊናዋን ጥሎ ያደገባት ከንቱ ነበረች ዋሲሁን ውጭ መመገብ አይወድም የታሸጉ መግቦችን ገና ሲመለከታቸው ያንገሸግሸዋል እንጀራ በሽሮ ወጥ ነፍሱ ነው !! ዛፒ ታዲያ እቤት ውስጥ ለባለቤቷ ምግብ አብስሎ ማቅረብን በሴት ልጅ ላይ የሚፈፀም ታላቅ በደል አድርጋ ነበር የምታየው

"የአበሻ ወንድ ጓዳ ለጓዳ ካልተንደፋደፈች ሚስቱ ሚስት አትመስለውም ሴት አደባባይ መውጣቷ ያማቸዋል " የምትለው ከእናቷ የወረሰችው ዘይቤ አላት በጓዳም በአደባባይም ምንም የማትፈይድ የወሬ ቋት ኩኪስ አልያም ጭማቂ ነገር ከፍሪጅ ታወጣና ሶፏዋ ላይ እግሯን አጣጥፋ ቴሌቪዥን እያየች ትበላለች ትጠጣለች ስለአለም

ፖለቲካ ትደሰኩራለች ስለፋሽን ሳታቋርጥ ትቀባጥራለች  በአለም ላይ ስላሉ የቅንጦት ሆቴሎችና ጌጣጌጦች “ዋ ው “ እያለች ትቋምጣለች እቤቷም የምትመኘውም ቦታ የለችም የትም የሌለች የውሃ ላይ ኩበት ነገር !!

ዘሪሁን ያደገበትን የቤተሰብ ስነስርአት የኢትዮጲያዊነት ወግ ምሳ ተዘጋጅቶ ቡና ተፈልቶ ቤቱ ሞቅ ብሎ እንደሚጠብቀው በማመን እንደአባወራ ምሳ ሰአት ላይ ሲመጣ ዛፒ ጠረንጴዛው ላይ እግሯን ሰቅላ ዙሪያዋን የጥፍር ቀለሞ ጠርሙዞች ከበዋት ቤቱ በአልኮል ሽታ ታፍኖ ስትቀነጃጅ ያገኛታል ማታ ሲመጣ ዛፒ ለባብሳ እንዲወጡ ስትጠብቀው ይደርሳል “ሃኒ ዋክ እናድርግ” ትለዋለች ባል ጋር መታየት እንጅ የባልን መሻት ማየት አልተፈጠረባትም ክንዱን ይዛ መንገድ ላይ ስትውረገረግ ቢጤዎቿ “ዋው ምናይነት ጥምረት ነው “ማች” ያደርጋሉ “ እያሉ ያወሩላታል ዋሲሁን ሳይወድ በግድ ሲዞር አምሽቶ እኩለ ሌሊት ላይ ስልችት ብሎት ይመለሳሉ የተሰቀለችበት ባለተረከዝ ጫማ ለመራመድ ስለማይመቻት ክንዱ ላይ ተዘፍዝፋ ትወናገራለች “ሃኒ ዲጀው “ሸቶሸ ብራንዱ ምን ድን ነው “ሲለኝ ሰምተኸዋል “

“አልሰማሁትም” ይላል ትክት ብሎት

“ሃሃሃሃሃሃ ጠጥተህ ነበር ብ ዙ ሰካራም ሃሃሃሃ “ ትላለች እየተለፋደደች አብሯት አይስቅም

“ በናትህ ቀሚሴ ላይ ዋይን ደፋብኝ ያ ወልካፋ አስተናጋጅ “ ትላለች ረዥም የእራት ቀሚሷን እያሳየችው

“ይታጠባል ደግሞ አንች ስታልፊ እኮ ነው የገጨሽው “ ይላታል ስልችት ብሎት

“ እዚህ አገር ምን ላውንደሪ አለ  ሰባት መቶ ዶላር የወጣበት ቀሚስ እንደቀልድ ምናይነት አገር ነው “ ብላ ቀሚሷ በአደባባይ ባለመከበሩ አስራ አምስት ቀን ታወራለች ስለተራ ቀሚስ ሳይሆን ስለባንዲራ መደፈር የምታወራ ነው የምትመስለው !!

ጧት ተነስቶ በተሰላቸ መንፈስ ወደስራ ሲሄድ ዛፒ አትሰማም አትለማም ተኝታለች ምሳ ሰአት እንደገና ጓደኞቿ ጋር እንደሄደች ትደውልለትና “ ምሳህን ውጭ ብላ ሃኒ “ ትለዋለች በዛውም አያችሁ ባሌን ሳዘው “ እያለች ለከንቱ ጓደኞቿ  ምሳ እራት ቁርስ በአበሻ ባህል ከምግብ የዘለለ ፋይዳው ለዛፒ አልታያትም ነበር የቤተሰብ እትብት ከእናት ማእድ ጋር እንደሚያያዝ ማን ይመግራታል ዋሲሁን ለአንድ አመት አብሯት ቆየና ክፉ ደግ ሳይናገር “አንች ጋር እንግዲህ በቃኝ” ብሏት ሄደ !! መሄድ ብቻ አይደለም አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ድል ባለ ሰርግ ሌላ ሴት አገባ !! ዛፒ መጀመሪያ “ጥርግ ይበል ለሞላ ወንድ” አለች  ቆይታ ይሄ ችጋራም ፒዛ እንኳን መብላት ያለማመድኩት እኔ ነበርኩ ጥጋበኛ የድሃ ልጅ “ ማለት ጀመረች

ዛፒ ሲበዛ ቆንጆ ናት ልብሶቿ ጌጣጌጦቿ የሴቶች ቅዠት  ግን ዋሲሁን ከሄደ በኋላ ወንድ የሚባል አልቀርብ አላት ይፈሯታል የተጋነነ ቁንጅናዋና ውድ ጌጣጌጦቿ የማትደፈር ግዛት ስለሚያስመስላት የሚመኛት እንጅ ድፍሮ የሚቀርባት ጠፋ “የአበሻ ወነድ” ተመካከሮ ሸሸ  ስልሰካራም ሆነች ማታ ማታ ሰክራ ትመጣና

“ ስቱፒድ ቅቢያም ሴቶቻችሁ ጋር እየሄዳችሁ ተጋደሙ ቦርጫም ሴቶቻችሁን አንዘፋዝፉ በምን አባታችሁ እድላችሁ ነው እኔን የምትስሙት እዛ የጉራጌ ጫማ ደንቅረው የቻይና ሱሪ ውስጥ የተቆጠሩ ኋላ ቀር ሰራተኛ ሴቶቻችሁ ጋር ኑሩ ”ን ቱ ሄል “ ቆሻሾች ቦርጫሞች “በጅም” አጠገብ አልፋችሁ የማታውቁ ” እያለች ድፍን የአበሻን ወንድ ትሳደባለች በረንዳዋ ላይ ቁማ

በጣም ስክር ብላ ጨርቅ ሁና ያመጣት ባለታክሲ ግቢ ውስጥ ደግፎ አስገብቷት ሲመለስ ትጠራኛለች

“አሸብር ና ጫማየን አውልቅ ” ጫማዋን አወልቅላታለሁ እች የውሻ ልጅ የእግሮቿ ጣቶች የመላእክትን ጣቶች ይመስላሉ አረዛዘማቸው ጥራታቸው

“ቀስ በል አንተ ! ሶሉን ልትገነጥለው ነው የእናትህን ኮንጎ ጫ ማ አደረከው ይሄ ኮ አራት መቶ ዶላር በዚች ችጋራም አገር ወረቀት ሲመነዘር ስንት ይሆናል አንደኛ አይደል ከክላስ የወጣሃው (እደነግጣለሁ ማን ነገራት

ስለመፈጠሬም የማታስታውስ ሴት ደረጃየን እውነቱን ለመናገር ትንሽ ኩራት ይሰማኛል ) እስኪ አስበዋ እኔ የቻይና ሸራ ጫማ የምደነቅር መሰለህ እየለፈለፈች ምኝታ ክፍሏ አስገባታለሁ አቤት ሽቶዋ ቆም ብላ አልጋውን በጥላቻ ታየውና ወደሳሎን ትገፋኛለች እያንዘፋዘፍኩ ሳሎን ሶፋው ላይ አስተኛታለሁ እየለፈለፈች እንቅልፍ ይወስዳታል ጧት ምንም እነዳልተፈጠረ አታናግረኝም መኖሬም ትዝ አይላትም !!

ዛፒን እጠላታለሁ ጉረኛ ናት ሰው ትንቃለች ግን የማይደበቀው ሃቅ ከእናቷ ትሻላለች ድንገት አቲየን ትጠራትና ያውልሽ ይሄን ውሰጅ ብላ ገና ያልተከፈተ ውድ ሽቶ ትሰጣታለች አቲየ ግን እጇን የሆነ ነገር ሲቆርጣት ብቻ ቁስሉ ላይ ስትረጨው ነው የማያት

ሌላ ቀን አቲየን ትጠራትና “እስቲ ቡና” አፍሊ ትላታለች አቲየ ሽር ጉድ ብላ አጫጭሳ ቤቱን ነፍስ ትዘራበታለች ዛፒ ግን ቡና አትጠጣም አቲም ስለምትፈራ አትጠጣም አነሳስታ ወደቤት ትመለሳለች ዛፒ አይምሮዋ ጤነኛ አለመሆኑን መጠራጠር ጀምሬ ነበር

አንድ ቀን ሰላማዊት የምትባል የሰፈራችን ልጅ አገባችና ሰፈሩ በጭፈራ ቀውጢ ሲሆን ዛፒ ጠራችኝ

“ማናት ያገባችው “ አለችኝ ነገርኳት

“ቆንጆ ልጅ ናት እንዴ “

“አንድ ቀን ጋሽ ዋሲሁን ጋር ሁናችሁ አሚት በመኪና ሆስፒታል የወሰዳችኋት ልጅ ናት እኮ “

“እና እሷ ልጅ ቆንጆ ናት እንዴ ” ምን ልበል ጨነቀኝ

“እኔጃ “ አልኩ ዝም ስትል የጨረሰች መስሎኝ ልሄድ ስል

“መልኳ ከእኔ ይበልጣል “ አለችኝ

“ኧረ ” ብየ ሳኩ

“ምን ያስቃሃል ዝም ብለህ የጠየኩህን አትመልስም “ አለች በቁጣ

ፈገግታየ ፊቴ ላይ ከስሞ “አንች ላይ ጫፍሽ ላይ አትደርስም አንች እኮ በጣም ቆንጆ ነሽ “ አልኳት ከልቤ ነበረ የተናገርኩት ትኩር ብላ አየችኝና ወደምኝታ ክፍሏ ገባች የክፍል ደረጃየን የማታውቀው እንዳስገረመኝ ቁንጅናዋን አይቸው የማላውቅ መስሏት ነበር መሰል “ምን አስለፈለፈኝ “ እያልኩ ወደቤቴ ገባሁ

እየው እንግዲህ “የነገር አመጣጥ እንደውሃ አፈሳሰስ ነው “ ነው የሚለው መጣፉ ይሄን ነው ጠብ ጠብጠብ ፈሰስ ኮለል ጎረፍ ዠቅዠቅዠቅ ከዛ ግንድ የለ ድንጋይ ይጠራርገዋል ጠብታው ምኝታ ቤቱ ነው ግንዱ ሰርቪስ

አስቴር አወቀ ዛፒ መኝታ ቤት ድፅዋን ከፍ አድርጋ ትዘፍናለች ምን እያለች እኔጃ!! ምናልባት እንዴት እንደምትጎርፍ እየመከረቻት ይሆናል !! አስቴር እኮ ዘፋኝ አይደለችም መካሪ ናት ስንቱ መኝታ ቤት እየገባች በጆሯቸው የሚሆንም የማይሆንም ነገር ሹክ ስትል ከርማለች የዛፒ አይን እንደአንቴና መዞ ወዲያው አሳድጎኛል ሳድግ ፈሪ ሆንኩ የባሰ !

## ክፍል 16

ጥቁር አምበሳ ኮከበ ፅባህ ሚኒሊክ መነን አዲስ ከተማ ድል በር ቦሌ ከሚማሩ የ አስረኛ ክፍል ተማሪወች ሁሉ “ አንደኛ ጎበዝ አንተ ነህ” አሉና የምስክር ወረቀት ሸለሙኝ እኔ ግን ጥቁር አምበሳ ኮከበ ፅባህ ሚኒሊክ መነን አዲስ ከተማ ድል በር ቦሌ ከሚማሩ ሴት ተማሪወች ሁሉ አንደኛ ቆንጆ የሆነችው ዮርዳኖስ የት ተቀምጣ ይሆን እያልኩ በአይኔ ከተሰበሰቡት ሰወች መሃል እየፈለኳት ነበር ዮርዳኖስ ማለት ማንም አይደለችም ለመጀመሪያ ጊዜ

ከመሬት ተነስታ ጉንጨን የሳመስኝ ልጅ ነች ጉንጨን ሳይሆን በቀኝ በኩል ከከንፈሬ ጥግ ሁለት ኧረ አንድ ተኩል ሴንቲሜትር ርቀት ላይ ነው የሳመችኝ ( ለሞላ ጉንጭ )

ዮርዳኖስ ቀይ ልጅ ናት ለነገሩ ቀይ ሳትሆን ጠየም ያለች ግን ቀይ ዳማ እንደሚሉት ሳትሆን አትቀርም አቦ የራሷ ጉዳይ ገደል ትግባ ብትፈልግ !! ኤጭጭ ይሄው ስንት ጊዜየ ሌትም ቀንም ዮርዳኖስ ቀይናት ቀይ ዳማ እያልኩ ስዛብር ማደር ከጀመርኩ እንኳን ሴት ልጅ ቆንጆ ወጣት ሴት ልጅ ነብስ ካወኩ ጀምሮ ሰው ሲስመኝ የመጀመሪያየ ስለነበር ዮርዳኖስ ጉንጨን ሳይሆን ልቤ ላይ እንደሳመችኝ እርግጠኛ ነበርኩ ማስረጃ ብባል ከዛን ጊዜ ጀምሮ አተነፋፈሴ ልክ አይደለም !! ሳያት የሆነ ነገር ያፍነኛል ሳላያት እንደነብር አዳኝ ትንፋሸን ውጨ በጉጉት በአይኔ እፈልጋታለሁ ሳላያት ታፍኘ ሳያትም ታፍኘ ልሞት ሆነ !!

“አንች ዮርዳኖስ የምትባይ ምን ቆርጦሽ ነው ኧረ ከከንፈሬ አንድ ተኩል ሴንቲሜትር እርቀት ላይ በሚሞቅና በሚለሰልስ እርጥብ ከንፈርሽ የሳምሽኝ “ ብላት ደስታየ ግን ታፍኛለሁ !!

አርብ ቀን ከትምህርት ቤት ወጥቸ ወደቤቴ እሄዳለሁ ምንም እያሰብኩ አልነበረም ዝም ብየ እየተራመድኩ እና በግዴለሽነት ሁሉንም ከፊቴ ያለውን ነገር እየተመለከትኩ እራመዳለሁ ”አሸብር” አለችኝ ከኋላየ ስሜ ሲጠራ የምደነግጠውን ያህል የሰይጣን ስም ቢጠራ እንኳን አልደነግጥም ሰዎች ስሜን ሲጠሩኝ ከዝምታየ ባህር በምላሳቸው መንጠቆ ጠልፈው ያወጡኝ ይመስለኛል

ጭራሽ ጠሪዋ ዮርዳኖስ ስትሆን ደግሞ በመንጠቆው ላይ መረብ ተተበተብኩ !! እኔ ጋር ብዙ ሰወች ወደኋላ አብረው ዞሩ ሰው ሁሉ ሳይጠራ ሲዞር ጠሪዋን ተመልክቶ ደስ ካለችው ስሙን አሸብር ሊያስብል ያሰበ ይመስል እኔ ለተጠራሁት መአት ሰው ዞረ

ዮርዳኖስን ዞሬ አየኋት ጉርድ ቀሚሷ በደንብ አላራምዳት ስላለ በእጇ ሰብሰብ አድርጋ ወደእኔ ትጣደፋለች እግሯ ቀይ ነው ባቷ ፍርጥም ያለ ከእድሜዋ በላይ ትልቅ ትመስለኛለች ጡቶቿ ደግሞ እዛና እዚህ ይላጋሉ ስትጣደፍ በሁለት እጆቿ ከንዶች ገፋ አድርጋ ታረጋጋቸዋለች ፀጉረዋ አጭር ነው ግንባሯ ትንሽ ወጣ ያለ ቀረበችኝና ፈገግ አለች አይኖቿ እንዴት ያምራሉ ኡፍፍፍፍፍፍፍፍፍ አሁን ስትጠራኝ መኪና እየነዳሁ ቢሆን ኖሮ ከአይኖቿ ለማምለጥ ስል ፊት ለፊት የሚያላዝነው ቦት መኪና ጋር እላተም ነበር የያዘው ነዳጅ ይዘረገፍና ከዮርዳኖስ ፈገግታ እሳት ለኩሶ ጭሱ ፀሃይን ጥቁር ጉልቻ እስክትመስል የሚያጥን ሰማይ የሚነካ እሳት ይነሳ ነበር

“እንዴት ነው የምትሮጠው ወተት ጥደሃል እቤትህ ?” ቀለደች አልሳኩላትም ስላልሳኩላት ግን እራሷ ከመሳቅ አልታቀበችም እየሳቀች ወሬዋን ቀጠለች

“ቤትህ በዚህ በኩል ነው እንዴ ?”

“አዎ”

“እኔ ግን አይቸህ አላውቅም “ ዝም አልኩ እና ካላየችኝ ምን ይሁን ወሬዋን ቀጠለች

፤ ,.

አዎ

አዎ

አዎ

“አዎ ብቻ ነው እንዴ የምታውቀው ?”

“አይ” እላታለሁ አነጋገሬ ሴት የመፍራት ሳይሆን ሰው የመሰልቸት ነበር ! አንዳንዴ የሰወች ንግግር ይረዝምብኛል “ሰላም” ሲሉኝ ይረዝምብኛል ሰ ላ ም እጃቸውን አንስተው ግንባራቸውን ነቅንቀው ፈገግ ብለው አንዳንዴም እጃቸውን ለሰላምታ ዘርግተው ይሄን ሁሉ ነገር አድርገው “ሰላም” ብቻ !!

ዝም አለች አብረን ሄድን ሄድንና የሆነ መገንጠያ ላይ ስንደርስ ክንዴን ይዛ አቆመችኝና ተንጠራርታ ሳመችኝ ምንም አላማ የሌለው ምክንያት የሌለው ወይም “ደፋር ነኝ አየህ “ የሚል ምናልባትም “ዘመናዊ ነኝ መንገድ ላይ የወንድ ጉንጭ መሳም አልፈራም “ አሳሳሟ የሆነ ድምፅ አለው የሚያፏጭ አይነት ድምፅ  የመምጠጥ አይነት ድምፅ የበዛ ግለኝነቴን ምጥጥ አድርጋ የሃሳብ ሃይቄን አደረቀችው የሰው አለማያ ሆንኩ !! ባደረቀችው የብቸኝነት ኩሬ ራሷን ሞላችው አዚህ ዮርዳኖስ የምትባል ውሃ የሞላችው ባህር ውስጥ ልቤ አምልጦኝ ገባ ይሄውአስባታለሁ የተረገመች ዮርዳኖስ !!

እየጠበቀችኝ ይሁን እየተገጣጠምን ብቻ ከዛን ጊዜ በኋላ በየቀኑ እንገኛኝ ጀመረ ሲቆይ ግን ጉዳዩ የነፍስ ቀጠሮ ሆነ ጠበኩሽ ላለማለት በቀስታ እየተራመድኩ እጓዛለሁ ከየትኛውም እርቀት ላይ አውቃታለሁ ፊት ለፊት ሳላያት መንፈሷ እዛ አካባቢ ካረበበ ትካሻየ ሹክ ይለኛል ትከብደኛለች “አንተ “ የሚል ድምጽ እጠብቃለሁ “አንተ” ትለኛለች ውስጣችን ያውቃል እንደምንጠባበቅ ከዛም ታወራኛለች

ዛሬ ይበርዳል

አዎ

“ሆም ዎርክ” ሰራህ

አዎ

.

.

አዎ ብቻ ነው የምታውቀው

“አይይ” አሁን ግን ምን ማውራት እንዳለብኝ እያሰብኩ ነው ! ችግሩ አስቤ ሳልጨርስ እንደርሳለን

ስንመለስም እንገናኛለን ስንመለስ መለያያችን ላይ ትስመኛለች “ቻው “ ከሚል ስርቅርቅ ያለ መለያየቱ ያስከፋው ድምፅ ጋር ከንፈሯ ጆሮየ ላይ ያፏጫል አንዴ መሃል ጉንጨ ላይ አንዴ ዝቅ አንዴ ከፍ እያለች ትስመኛለች በየቀኑ ትስመኛለች ዝም ብየ እሳማለሁ ከንፈሯ ክብ ነው በሃሳቤ ስትስመኝ ክብ ቅርፅ ጉንጨ ላይ የታተመ ይመስለኛል የሳምንቱ ክቦች ተቆላልፈው ቅዳሜ የኦሎምፒክ አርማ ጉንጨ ላይ ታትሞ በጉልህ ይታየኛል አንዱ ክብ እንደ ደቡብ ኦሞ ሴቶች ከንፈሬን ተልትሎ ከንፈሬ ላይ ተንጠልጥሎ አየሁት በህልሜ !

አንድ ቀን ግጥም ፃፍኩ በሂወት ዘመኔ የፃፍኩት ብቸኛ ግጥም ወደፊትም ግጥም አልፅፍም ግጥም ያስጠላኛል ሰው ዝም ማለት እያለለት ለማውራት ቃል መጠምዘዝ መድከም ምን ያደርግለታል ቢፅፍ ላይጠቀም ባይፅፍ ላይዳ ባይ ነኝ! ደግሞ አዲስ ግጥም ሰምቸ አላውቅም ግጥሞች ሁሉ አንድ ናቸው ደራሲያቸው ይለያይ እንጅ ባይ ነኝ !!

እኔን የገረመኝ (ርእሱ)

እኔን የገረመኝ

እኔ የጠላሁትን

እኔነት ሳትጠላ

ልጅቱ ስትስመኝ !!

በቃ !! ይሄው ነው ግጥሙ ግጥም ማለት ቤት የሚመታ ቀለሙ ስንኙ የሚሉ ሰወችን ተዋቸውና ግጥም ማለት እስከርቶ ሳትጨብጥ ወረቀት ፊትህ ሳይነጠፍ እንደአፍ ወለምታ ከከንፈርህም ከነፍስህም ከአይምሮህም የሚያመልጥ ነገር ነው ለምሳሌ በዚች አለም ላይ ከሰማኋቸው ግጥሞች አሳዛኙ የአቲየ ግጥም ነው እርእሱ "እሽ" ግጥሙም "እሽ " አበቃ ማንም ለጀመረው የትእዛዝ ስንኝ አቲየ እሽ የሚል ግጣም እየሰራችለት የማንም ቤት እንዲቆም አድርጋለች የእኔ እናት ገጣሚ ናት

ቤት ጥረጊ

እሽ

ልብስ እጠቢ

እሽ

ሂጂና ሳሙና ግዥ

እሽ

እንጀራ ጋግሪ

እሽ

ደመወዝሽን ሌላ ቀን ውሰጅ

እሽ

ግጥም ይሄ ነው ከትእዙ እኩል ይሁንታው ዜማ ሲፈጥር እናም ያሉትን ሲሆኑ ቤት መምታት ይሄ ነው መጥፎ ቃል የደሃ ስጋ ለብሶ አዛዥ ቤት ሲያድር በአሙቱ አይኑ በምኞት የሚዛብር "ገጣሚ" ውዴ ዘላለም ልፈጥፈጥልሽ ልቆራመትልሽ ቢል አይገባኝም ግጥም ከቃል ሲጭበረበር ሳይሆን ከነፍስ ሲመዘዝ ከሂወት ሲቀመም ነው ቤት የሚመታው

ቢሆንም ግጥም ገጠምኩ አላሰብኩም አልደለዝኩም አልሰረዝኩም አንድ ደብተሬ ጀርባ ላይ በቀጥታ ፃፍኩት ያውም ኬሚስትሪ የሚባል ትምህርት እየተማርን ልክ ስልክ ቁጥር እንደሚፅፍ ሰው ሳላስብ ግጥም ፃፍኩ ከብዙ አመት በኋላ ይሄን ግጥም ያሳየሁት ገጣሚ "ጭብጡ የላላ ወደታች የተፃፈ ስድ ፅሁፍ ነው የሚመስለው " አለኝ !! ጉዳየ አልነበረም !!ድሮስ መቸ ግጥም መፃፌ ገረመኝ በልጅቱ ጉንጨን ያውም አንድ ተኩል ሳንቲሜትር ለከንፈሬ የቀረበ ቦታ ላይ መሳሜ እንጅ !!

ዮርዳኖስ አንድ ቀን ጠራችኝ

"አሹ " ብላ !! "አሹ " ማለት ለካ አሸብር ማለት አይደለም በጭራሽ "አሹ " ማለት ከአሸብር ጋር የሚገናኘው ሁቱም አጠራር ስለሚያስደነግጡኝ ብቻ ነው እንጅ አሸብር አሹ አይደለም !! ከየት አመጣችው ግን እች ዮርዳኖስ !! ደግሞ አሹ ከአሸብር ይረዝማል አሹ ሙሉ ቀን ጆሮ ላይ ያቃጭላል አይገርምም ?

ከተማሪወች ሁሉ አንደኛ የወጣና የተሸለምኩ ቀን ሌሊት ከእንቅልፌ ነቃሁ.. ምን እንዳነቃኝ እኔጃ ፀጥታው የነቃ ያስተኛል እንኳን የተኛ ሊቀሰቅስ ግን ነቃሁ ነቃሁና ልክ አይኔን ስከፍት ዮርዳኖስ ያንኳኳችውን በር የከፈትኩ ይመስል ምስሏ ፊት ለፊቴ ተደቀነ ልትስመኝ ስታሞጠሙጥ ስትስቅ እና "አሹ" ስትለኝ "ፍቅር ይዞኛል " የሚል የማልፈልገው አረፍተ ነገር ከምኔ እንዳመለጠ ሳላውቅ ፈነዳ ቡምምምምምምምምምምምምምምም ፍቅር እርፍ !!

ልክ እንደግጥሙ ያልፈለኩት እንባ ጉንጨ ላይ ተንኳለለ በምድር ላይ አለኝ ከምለው አንድ የሆነ እምነት የተካካድኩ መሰለኝ ለነብስ ጉዳይ የተበደርኩት ብር ከኪሴ የጠፋ ያህል ተሰማኝ እንባየን ጠረኩና መብራቱን አበራሁት ፊት ለፊት ያለው ግድግዳ ላይ በፌስታል የተሰቀለ የአቲየ ልቃቂት ራቅ ብሎ ትንሽ መጋረጃ እንደ እቃ

ቤት የምንጠቀምባትን ቦታ የከለለች ከመጋረጀዋ ፊት ለፊት አቲየ ፍራሽ ላይ አሮጌ ብርድ ልብስ ለብሳ ኩርምት ብላ ተኝታ ቤታችን አስጠላኝ እራሴ አስጠላኝ አስረኛ ክፍል አስጠላኝ ከአሁን በኋላ ስንት አመት ተምሬ ነው ስራ የምይዘው

አቲየ ድንገት ባነነችና "አሸብር ምነው አመመህ እንዴ " አለችኝ ከወገቧ ቀና ብላ ዝም ብየ አየኋት አቲየ እያረጀች ነው ደረቷ ክስት ብሏል ፊቷ ላይ ማዲያት ነገር አለ ግንባሯ ላይ ብዙ መስመሮች ተጋድመዋል አንገቷ ስር ያለው ቆዳም ተሸብሽቧል እስከዛሬ አላየኋትም ወይስ "እውር ያደርጋል " የሚሉት ፍቅር የእኔን አይን ገለጠው ? ገመናየን አሳይቶ "ልክህን እወቅ" ሊለኝ አቲየን ስራ እስከምይዝ በምን ላፅናናት

"አቲ ደስ ብሎኝ ነው " አልኳት ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ

"እሰይ ኧረ ደስ ይበልልኝ " አለች ከእኔ የበለጠ ፈገግ ብላ ምኑንም ሳትሰማ ምን ተገኘ እንኳን አላለችኝም በቃ ደስ ካለኝ ደስ ይላታል

"ከአዲስ አበባ ተማሪወች ሁሉ አንደኛ ወጥቸ ሰልፍ ሜዳ ተማሪወች ፊት ተሸለምኩ " አልኳት "አዲስ አበባ " ያልኩት ሆን ብየ ነበረ "የገፋሽ ህዝብ ሰነፍ ነው ያንከራተተሽ ህዝብ ልጆች በአንች በተንከራታቿ በአንች ልጅ አፈር ድቤ ግጧል ተበልጠዋል በእጅ አዙር በልጠሻቸዋል " ለማለት ሌላም ለማለት

አቲየ ፊቷ በፍርሃት ተወረረ "ልጀን የሰው አይን ውስጥ ሊያስገቡብኝ " አለች

"አቲየ ደግሞ ሁልጊዜ እንተያይ የለ " አልኳት አይን ውስጥ ግን ገብቻለሁ ልክ ነው ዮርዳኖስ የምትባል ቡዳ በልታኛለች በከንፈሯ!!

"በል ጧት ሂድና ማለፍህን ንገራት " አለችኝ በአገጯ ወደ ዛፒ ቤት እየጠቆመች አቲየ ከሚገርመኝ ባህሪዋ ማንንም በስም አትጠራም !! ተመልከቱ ምን ያህል እንደተበደለች እች ሴት የሰውን ስም መጥራት በራሱ መናቅ እንዳይመስልባት ትፈራለች ትፈራለች !! እናም ለዛፒ ምን ብየ እንደምነግራት አሰብኩ

ዛፒ አንደኛ ወጣሁ ዛፒ አለፍኩ ዛፒ ሰካራም ዛፒ ጠብራራ ዮርዳኖስን አፈቀርኳት ኡፍፍፍፍፍፍ ላብድ መሰለኝ መብራቱን አጠፋሁት ጨለማው ውስጥ ዮርዳኖስ ገጭ አለች እች ግንባራም ! እግሯ ቀይ ነው ጡቶቿ ትልልቅ ናቸው ስትራመድ ይነቃነቃሉ ግን ጡት ሴቶችን ይከብዳቸዋል አይከብዳቸውም ታዲያ ዮርዲ ለምንድን ነው ስትራመድ ጎበጥ የምትለው "ዮርዲ " ነው ያልኩት ? ሃሃሃሃሃሃሃሃ ከአቲየ ቀጥሎ በዚች ምድር ያቆላመጥኩት ስም እነሆ

## ክፍል 17

ጠዋት "ዩኒፎርሜን" ለብሸ ደብተሮቸን አዘጋጀሁና እየቀፈፈኝ ወደትልቁ ቤት ሄጀ አንኳኳሁ

"ማነው " ደነገጥኩ

"እ ኔ ነኝ " አልኩ እየፈራሁ

"ግባ ክፍት ነው " ገፋ ሳደርገው የሚያብረቀርቀው የጣውላ በር ድምፅ ሳያሰማ ተከፈተ (ክፍቱን ነው ያደረው ማለት ነው) ዝርክርክርክርክርክርክ ያለው ሳሎን ጋር ተፋጠጥኩ ዛፒ ሶፋው ላይ የአልጋ ልብስ ጣል አድርጋ ተኝታለች ፊቷ ያለው ጠረንጴዛ ላይ የሻይ ብርጭቆ የውሃ ጠርሙስ እሩቡ ብቻ የተበላ ሰላጣ ምንም ያልተነካ ዳቦ ዝርክርክ ብሏል ብዙ ምግብ ማቅረብና ምንም አለመብላት ለማደ ነው ይገርመኛል !

"ምንድነው በጧቱ " አለች እየተነጫነጨች

"እ ትምህርት ቤት ከሁሉም ትምህርት ቤቶች አንደኛ ወጣሁ ልንገርሽ ብየ ነው " ድምጼ ተንቀጠቀጠብኝ ቀጥ ብላ ግራ በገባው ፊት አየችኝ የሌሊት ልብሷን ትከሻዋና ትከሻዋ አካባቢ ይዛ አስተካከለች አቤት ደረቷ አቀላሉ "እኔ ምናገባኝ ታዲያ" የምትል መስሎኝ ነበር ድንገት የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሰው ፈገግ ብላ " እና እንደዚህ ነው የሚነገረው " አለችኝ እና ሁለት እጆቿን እንደክንፍ ዘረጋቻቸው ፈገግግግግ ብላ ሁለት ጡቶቿ አፈጠጡብኝ

ግራ ገብቶኝ እንደቆምኩ "ና እንጅ ሳመኝ " አለችኝ በደመነፍስ እየተደነቃቀፍኩ ሂጀ ሂጀ ሂጀ ሂጀ ሂጀ ሂጀ እጆቿ ሲጠመጠሙብኝ ሁሉ እርምጃየን ያቆምኮ አልመሰለኝም ጥብቅ አድርጋ አቅፋኝ "ጎበዝ የኔ ወንድም እኮራበሃለሁ " አለችኝ በ ለ ው !!!! ከሽ አለ የሻዩ ብርጭቆ ከጠረንጴዛው ላይ ወድቆ "ይሰበር ተወው " አለችኝ እና ጉንጨን ስማ ለቀቀችኝ ይሄ ቤት ለካ የወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ቤት ነው !!

ከዛፒ ጋር እንደወጣሁ በደስታ ሰክሬ መንገዱን ሁሉ ሰውን ሁሉ አየሁት መቸ ነው ይሄ ትልቅ የመኪና ኪራይ ማስታወቂያ ነዳጅ ማደያው ፊት ለፊት የተሰቀለው መቸ ነው ይሄንኛው ህንፃ ተሰርቶ ያለቀው ወቸ ጉድ አዲስአበባ እንዴት ተለውጣለች ከሆነ አገር የመጣሁ መሰለኝ ደግሞ ደስ የሚል ነገር ይሸተኛል አፍንጫየም ዛሬ ገና የተከፈተ ይመስል

ዮርዳኖስ ጋር ስንገናኝ "ምነው" አለችኝ

"እ " አልኳት

"አይ ቁመህ ሳገኝህ ነዋ " አለችኝ ለካስ ዮርዳኖስን ቁሜ አልነበረም የምጠብቃት ያልጠበኳት መስየ ነበር መጠበቅ የነበረብኝ ሳመችኝ ጉንጨን ዛፒና ዮርዳኖስ እኔ በምባል ኳስ በከንፈራቸው እየተቀባበሉ "ቮሊቦል " የሚጫወቱ መሰለኝ "ተስመህ ትወጣለህ ስመው ይቀበሉሃል " የሚል ትንቢት ከሰማይ የታወጀም መሰለኝ ድፍን አዲስ አበባ እንደዳቦ እንደዘይት እንደታክሲ እኔን ለመሳም የተሰለፈ መስሎ ተሰማኝ

ዮርዳኖስ ፈገግ ብላ አፍንጫዋን በመቀሰር ጠጋ አለችኝና "ደግሞ አሪፍ ሽቶ እፉፉፉፉፉፉ ያደረገብህ ማነው " አለች አፈርኩ ለካ የዛፒ ሽቶ ነው ሲከተለኝ የነበረው የዛፒ ሽቶ የዋዛ አልነበረም ከዚች ቀን ጀምሮ እድሜ ልኬን ሲከተለኝ ነው የኖረው ሲያሳድደኝ ሳይሆን ሲከተለኝ

ሰው ወደውስጥ የሚስበው አየር " ኦክስጅን " ወደውጭ የሚያስወጣው " ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ " እያሉ ያስተማሩን ቅኔ ነበር ሳይንሳዊ ቅኔ!! አሁን አሸብር ወደውስጥ የሚስበው ፍቅር መፈቀር መከበር መፈለግን ነው ወደውጭ የሚተነፍሰው እርካታ!! የአየር ብክለት ማለት ሌላ ትርጉም የለውም እኮ የተገፉ የተገለሉ የተናቁ ህዝቦች ጥላቻን ወደውስጣቸው ስበው መልሰው ጥላቻን ወደመላው አለም መተንፈሳቸው ነው መፍትሄው የፍቅር ችግኝ በልባቸው መትከል ነው እንሆ ዮርዳኖስ የተከለችውን ዝግባ ዛፒ የምትባል ዝናብ ስታረሰርሰው እኔማ ዛፒ ጥቁር ደመና አዝላ እያጉረመረመች ሰማይ ላይ ተንጠልጥላ ሳያት መሽቆጥቆጥና ጥላቻየን እንደዣንጥላ ስዘረጋ ነበር የኖርኩት !

## ክፍል 18

" አንተ ሴት ነህ እንዴ " ብላ ዛፒ ሳቀችብኝ አፈርኩ ልብስ ልትገዛልኝ ወሰደችኝና "ምረጥ " ስትለኝ መጀመሪያ እጀ አንድ ቀሚስ ላይ አረፈ ለአቲየ ልኳ የሚሆን ቀሚስ ነበረ ለዛ ነበር የሳቀችው !! ልብስና ጫማ ገዛችልኝ የሱሪየን ቁጥር ስጠየቅ አላውቅም ነበር ሱሪ ገዝቸ አላውቅማ የጫማ ቁጥር አላውቅም የሃብታም ልጆች ልብስና ጫማቸው ከሱቅ የተገዛ ሳይሆን አብሯቸው የሚወለድ ይመስለኝ ነበረ

ሃሃሃ ግን ይሄው ሁሉ ነገር ሱቅ ውስጥ አለ ሸቀጥ ነው ያው እዛ ጋ ቶማስ የሚባለው ሁልጊዜ በሴት የሚከበበው የክፍላችን ልጅ ጫማ ይሄው የራሄል ቦርሳ ኧረ ጉድ የቲቸር ተስፋየ ጥቁር ባለብዙ ኪስ ጃኬትም ያውና ትንሽ ብቆይ እነዛ "ውድ ነን" የሚሉ ልጆች እዚህ ተደርድረው ሲሸጡ አገኛቸው ይሆናል ሲገርም ሁለት

ሱሪ አንድ ጫማ ሁለት ሸሚዝ አንድ ሹራብ ነብስ ካወኩ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ ልብስ ከሱቅ ገዛሁ ለካሁት መስተዋቱ ፊት ስቆም ደነገጥኩ "ልብስ ማለት ተራ ድሪቶ ነው ምናምን" የሚሉ ሰወች እንዴት ጅሎች ናቸው እባካችሁ እራሴን በመስተዋት ሳየው ታላቅ ፍንዳታ አይምሮየ ውስጥ ተፈጠረ !

እወራረዳለሁ ጥቁር አምበሳ ኮከበ ፅባህ ሚኒሊክ መነን አዲስ ከተማ ድል በር ቦሌ ከሚማሩ ተማሪወች ሁሉ አንደኛ ቆንጆና ወንዳወንድ አቋም ያለኝ ልጅ እኔ ነኝ እግዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዚዘዚአ ከቤተ ክርስቲያን ሃቢያቱን ተናዞ እንደወጣ ሰው ሸክሜ ቀለለኝ አደኩ ደግሞ !! የክፍሌን ልጆች በየቤታቸው እየሄድኩ እጀን ኪስና ኪሴ አስገብቶ "ሃይ " ማለት አማረኝ

ዛፒ የለበስኩት አዲስ ሹራቡ ላይ የነበረውን ወረቀት ከኋላየ ክሩን በጥሳ አላቀቀችልኝና " አንተ ልጅ ቆንጆ እኮ ነህ " አለችኝ በሙቅ ውሃ በተሞላ ገንዳ ውስጥ የመግባት ያህል ቃሏ ይሞቅ ነበር

ዝም ብላችሁ የሂወት መንገዳችሁን ዞሩና ተመልከቱ አለቀ ያላችሁበት ቦታ ላይ የነበረውንና የሚመጣውን የሚያያይዝ አጋጣሚ የሚባል ድልድይ ይኖራል ይሄን ድልድይ የሚያምኑ ፈጣሪ ነው ይሉታል የማያምኑ የስነ ሂወት መርህ ነው ይሉታል ለእምነቱም ለሳይንሱም ግድ የማይሰጣቸው እድል ይሉታል እኔ ግን ይሄ አንዴ በዛ አንዴ በዚህ የሂወቴን ተራዳ እየደገፈ የሚያቆመው ከአቲየ ድፍን አምሳ ብር የተበደረው እግዚያብሄር ነው እላለሁ !! እንዲያ ነው የመቀጠላችን ስንክሳር ባማረ የሂወት አትራኖስ ላይ ተቀምጦ የሚገለጠው

ዛፒ ልብስ ከገዛችለኝ ከሳምንት በኋላ ትምህርት ቤት ቁጭ ብየ መቁረጫ የሌለው ሃሳብ ውስጥ ተዘፈኩ ልብሴ የብዙወች ፊት እንዲበራ አደርጓል መንገድ ላይ ሴቶች ያዩኛል አንዳንዴ ማፍጠጣቸው ሲበዛ " እነዚህ ሴቶች ግን ያለበሰ ሰው ያላብረቀረቀ ነገር "አብስትራክት" ይሆንባቸዋል ቶሎ አይታያቸውም " እያልኩ አስባለሁ ዮርዳኖስ ከንዴን ጨምድዳ መሄድ ከጀመረች ቆየች ጓደኞቿ "ኤክስ ሬይ ነገር ነሽ ይሄ ልጅ ለካ ገና በፊት ውበቱ ታይቶሻል " እንዳሏት ነገረችኝ እግረመንገዷን " ዛሬ ስለለበስክ ሳይሆን በፊት ከነድሪቶህ ሰው ሳያይህ በፊት ነው የቀረብኩህ " መልእክት !!

እውነቱን ለመናገር ሰው ራስ ወዳድ ነው በዚህ ሁሉ ሃሳቤ ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳን ስለአቲየ አላሰብኩም እኔነት ሲያደክመው የኖረ ሰው ሸክሙን ጣጥሎ ብቻውን የሚቆምበት ቀን አለ አይደለ ጥፋታችንን ብቻችንን የምንጋፈጥበት እራሳችንን የምንወቅስበት ደስታ እና ስኬታችንን "በራሳችን ልፋት ያመጣነው ነው" የምንልበት በቃ ራሳችንን ብቻ የምንሆንበት የዛን ቀን እንደዛ ሆኘ ነበር  ታዲያ ውጤት ነበረው በውስጤ የተተረማመሱ ሃሳቦች በስረአት ተሰደሩ "ሙተዋል" ያልኳቸው ጉዳዮች አፈራቸውን እያራገፉ በሂሊናየ አደባባይ በትንሳኤ ቆሙ ፍቅር የሴት ይሁን የሰው ይሁን የእናት አገር ይሁን የፈጣሪ  ያለየለት ባለብዙ ዘርፍ ፍቅር ባዶውን የኖረ የልቤ መስቀል ላይ እንደገና የተሰቀለ መሰለኝ

እንደሰው ስንቆጠርና ቤተሰብ ጓደኛ ጎረቤት መንደርተኛ አገሬው ቦታ ሲሰጠን ወይም የሰጠን ሲመስለን ከመሃበረሰብ ያፈነገጠ ውስጣዊም ውጫዊም ሰብእናችንን ሰልፉን እንዲያሳምር ውስጣችን እራሱን ይመክራል እንደዛ ነው የሆንኩት እንደሰው ከመቆጠር ስናልፍና አንፋሽ አከንፋሻችን ሲበዛ የሰልፉ መሪ የሆንን እየመሰለን እንደገና ያገኘንበት እንረግጣለን መልካም መካሪ ካገኘን ወደሰልፋችን የመመለሳችን ነገር ያውም በጭብጨባ ታጅቦ ይደገማል ካልሆነም ማንነት ስም አላማ ሰብእና እብድ የበላው በሶ ሆኖ ይቀራል  የታዋቂ እውቅና መንኮታኮቱ የአገር ፖለቲካ ኢኮኖሚ በልክ እንዳልተሰፋ ቀሚስ መንዘላዘሉ የትውልድ ሸሸት ከመጥበሻው ወደእሳቱ የመሆኑም ነገር ሁሉ የማንነትን ሰልፍ መሳት ነው አጉል ወደድኩ ብሎ ሰልፍ ስትጥስ የሚያጨበጭብልህ ጠላሁ ብሎ ጎትቶ ከሰልፍህ የሚያስወጣህ በሞላባት ምድር ጥላቻና ፍቅር እኩል የጥፋት መንገድ መሆናቸው የሚገባህ እንዲህ እራስህ ጋር ሃቅ ሃቁን ስትነጋገር ነው

እናም ባነንኩ !!

እኔ አሸብር ነኝ ! እናቴ አፀደ ትባላለች በዚች ምድር ላይ የስጋ ዘመድ የምንለው የለንም እናቴ በየሰው ቤት እንጀራ ትጋግራለች ልብስ ታጥባለች እንደሰው ተከብራ አታውቅም ተስፋ የምታደርገው እኔን ብቻ ነው ብቸኛ አላማየ አገር ህዝብ ወገን አይደለም እናቴ ናት !!

ማንም በፖለቲካ አመለካከት ቢራኮት ማንም ማንንም ቢከተል ስሜት አይሰጠኝም የትኛውም እምነት ወየውልህ ቢል በዚያ በዚህ ቢፈልግ በአምላኩ ቢያሻው በፖለቲካው ተከልሎ ቢባደን "እችን ታህል" አይገርመኝም እናቴን ነፃ ለማውጣት የሂወት ጦርነት ውስጥ ያለሁ ታጋይ ነኝ

ሆችሚኒ ነኝ ግዙፉን "አምባገነን ህዝብ " ከትንሽ የእናትነት ግዛቴ የማባርር ቸኩቨራ ነኝ በስግብግብና እራስ ወዳዶች ክንድ ስር በፅናት አልፌ የሚስኪን እናቴን ከፍታ በሚያረጋግጥ አብዮት ምድርን የምንጥ አንጀላ ደቪስ ነኝ ፋራንትዝ ፋኖን ነኝ

የእናቴ ጠላት ድህነት አይደለም "ስለነፃነት የሚቀባጥረው ህዝብ እንጅ " የህዝብ ልጅ የሚባል ቀልድ አይገባኝም የእናቴ ብቻ ልጅ ነኝ ፅንፈኛ ነኝ ዘረኛ ነኝ አክራሪ ነኝ ከእናቴ ጋር በጭፍን የተሰለፍኩ ሌላው የተረገመ ነው ብየ የማምን ዘረኛ ነኝ ከእናቴ ወዲያ ታጋሽ ጨዋ ለሰው ልጆች አሳቢ አዋቂ ጀግና ዘር የለም የምል አክራሪ ነኝ ከእኔ እናት ሌላ ሌላ እናት እናት የማይመስለኝ እናም ጠላቴ ህዝብ ነው ህዝብን መበቀል ቀላል ነው ምክንያቱም ጠላትህ የትም የሚገኝ እንደትቢያ እያፈስክ የትም የምትበትነው ገለባ ነው

አስተማሪ ብትሆን ከጠመኔህ ስር ጠላትህ አለ ጥላቻ አይምሮው ውስጥ እየዘራህ ሰይጣን ታፈራለህ ሹፌር ብትሆን የጠላትህ ነብስ በእጅህ ነው ይዘኸው ገደል ልትገባ ትችላለህ ግንበኛ ወላ አናፂ ብትሆን የምትሰራለት ቤት በላዩ ላይ ፈርሶ እንዲቀብረው የማድረግ ስልጣን በእጅህ ነው ባለስልጣን ከሆንክማ "እባቡም ከእግርህ ዱላውም ከእጅህ" ብትፈልግ ቀይ ሽብር ወንጀለኛ ምናምን ቅብርጥስ ብለህ በየመንገዱ ትደፋዋለህ ካሻህ እድሜ ልኩን በድህነት እንዲሟቅቅ ታደርገዋለህ

ደግሞ ለበቀልህ ማን ይተባበረኛል ብለህ አትሰጋም ህዝቡ እራሱ ለመባረክ ስትቆም ነጠላውን አጣፍቶ ከጎንህ ነው ለማረድ ስትቆምም ቢለዋውን ስሎ ከጎንህ ነው ከሌላ አለም ረዳት መጥራት ሳያሻህ ወንደሙ ላይ የሚጨክን "ፈሪሃ እግዚአብሄር " ያለው ህዝብ ጠላትህ ከሆ ለበቀልህ ታዛዥ ነው ደነዝ ህዝብ ደነዝ መሪ እንደሚወልድ እስኪገባው ትጫወትበታለህ ጭራቅ ህዝብ ጭራቅ መሪወች እንደሚፈለፍል እስኪያውቅ ታሽዋለህ አዎ ጠላትህ ህዝብ ከሆነ በቀልህ ቦታ እና ጊዜ ሳይመርጥ የትም ሊፈፀም ይችላል !! ደግሞ ታዝበህ ከሆነ ከልብህ የህዝብ ጠላት ከሆንክ ህዝብ ይወደሃል !! ስላንተ ይዘምራል !!

ወዳጁን እየካደና እየቀረጠፈ ውለታውን ትቢያ የሚያለብስ ህዝብ የእናቴን ጉልበት እንደምስጥ መጦ እንጨቷን አስቀረ ብየ አላዝንም ሰው እሆናለሁ በእኔ ሰው መሆን ትላንት ፍሬ የምትሰጥ ለምለም ዛፍ የነበረች ህዝብ ያደረቃት እናት የምትባል "እንጨት" ከማገዶነት አፋፍ ተመልሳ እንደ ኢሴይ ብትር ትለመልማለች ያኔ በልጅ ልጆቿ ልብ ውስጥ ከቅዱስ ቅዱሳኑ ለዘላለም በክብር ትቀመጣለች ቱ ! አሸብር አይደለሁማ !

ታጋይ በሴት አይፈተንም ሴቷ ቀይ እግር ቢኖራትም አይኗ ቢያምርም ተንጠራርታ ብትስምም ስሟ ዮርዳኖስ ቢሆንም ማታ ማታ ትዝ ብትልም ከነድሪቶየ ብትቀርበኝም የጠላት ልጅ ያው ጠላት ነው !! ዮርዳኖስን ርግፍ አድርጌ ተውኳት ከባድ አልነበረም እንደውም አይኔን ስገልጥ ዮርዳኖስ ለእኔ ሸክም ነበረች !! በብልጣብልጥ ሴትነት ነገን አሻግራ ያየች መረቧን ተሸክማ ግራ በገባው አሳ ዙሪያ የምትሽከረከር የአዲሳባ ሴት እሾሁን አራግፋ ልትቀረጥፈው !! ተውኳት "ልብሱን ሲቀይር ተወኝ " አለች ተባለ እሷ የድሮ ልብሴን የሆነች ይመስል ብዙ ሴቶች አለመፈለግን ክህደት ያደርጉታል

# ክፍል 19

አስራ ሁለተኛ ክፍል ከፍተኛ ውጤት አምጥተው ዩኒቨርስቲ ሊገቡ ከተዘጋጁ ትቂትተማሪወች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ አራት ነጥብ ! አራት ነጥብ የሚባል አንድ ጠመንጃ ይዠ ለትጥቅ ትግል ዩኒቨርስቲ ወደሚባል ጫካ ልዘምት ተዘጋጀሁ ዛፒ አንድ የናጠጠ የሃብታም ልጅ ሊኖረው ከሚችለው በላይ ልብስና ጫማ ሌሎችም ቁሳቁሶችን ከአገር ወስጥ ብቻ ሳይሆን ከቤተሰቦቿም ጭምር አስመጥታልኝ ነበረ ምርር ያለ ቤተሰባዊ ፍቅር ውስጥ ገብተን ነበር አይናፂ ይወደኝ ነበረ ያስታውቃል በተለይ አስራ ሁለተኛ ክፍል ተፈትኘ ውጤት ስጠብቅ ዛፒ ጋር ያሳለፍነው ጊዜ የሚገርም ነበረ ያልዞርንበት መዝናኛ አልነበረም የትም ስትሄድ ከጎኗ አለሁ እኔን "ወንድሜ" ብላ ማስተዋወቅ እንዴት እንደሚያኮራት የእውነትም ደግሞ ወንድሟ እመስል ነበረ

ዛፒ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለአቲም ደግነቷ ተንሰራፍቶ ነበር ማታ ማታ ቡና ተፈልቶ በረንዳ ላይ ወይም ሳሎን ደስ የሚል ጊዜ ሶስታችንም እናሳልፋለን ዛፒን ከምቾት ጋር ያገለለ አለም እኔና አቲየንም ከብስቁልና ጋር የተፋ ሂወት በምን ሂሳብ እንዳቀላቀለን ባይገባኝም ቅልቅሉ ግን ከልብ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስርን ፈጥሮ ነበረ

አንድ ቀን "አቲየ" አልኳት

"አቤት "

"ምን ብሆን ደስ ይልሻል "

" ኧረ እኔ ምን አውቄ እኔ ትምርት የለኝ አላቀው " ብላ ሳቀች

"ግዴለሽም ተምሬ እኔ ልጅሽ ምን ብሆንልሽ ደስ ይልሻል "

" እሷን አማክራት እስቲ " አለችኝ ዛፒን ማለቷ ነበር

"አቲ ዘሬ ካልነገርሽኝ አለቅሽም ራስሽ ንገሪኝ "

ትንሽ አሰበችና " ዶፍተር " አለችኝ በሳቅ ሁለታችንም ፍርስስስ አልን አነጋገሯ በእርግጥም ያስቅ ነበር

ህክምና የመማሬ ብቸኛ ምክንያት ይሄው ነው !! ህዝቤንና ወገኔን ከበሽታ ለመታደግ ምናምን ብየ አይደለም !! እናቴ የምወዳት እናቴ የአይምሮዋ ጥግ የታላቅነት መጨረሻ የመሰላትን ነገር ለመሆን !!

የዩኒቨርስቲ ቆይታየ የደስታና የቅንጦንት ነበረ ዛፒ ውብ ሁና ግቢ ስትመጣ አይኑ የማይፈጥ ተማሪ አልነበረም ብዙ ሰው እናቴ ያደርጋት ነበረ ሴቶቹ የዛፒ ጫማና ልብስ ላይ አይናቸው ይንለነካል ከዚህ የቆንጆ ዘር በረከቱን ሊካፈሉ የቋመጡ በስልምልም አይን በጨዋ መሳይ ፈገግታ ሊቀርቡኝ ሲዞሩኝ ነበር "ፀዳ ያለ ልጅ" ይሉኛል ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አላልኳችሁም በድፍን ግምት ወደድን ብለው ከሰልፍ ሊያስወጡ መሞከር ይሄ ነው እኮ

በቁም ነገር ባለመቁጠር በቀሌን አንድ ብየ ጀመርኩ ኮተታሞቹ የግቢ ልጆች ራሳቸውን ችለው መቆም ይፈራሉ ሴቶቹ ወንድ ታዛ ስር ካልተጠለሉ ሰው የሆኑ አይመስላቸውም ወንዶቹ የተፈጥሮን ፆታዊ መፈላለግ ሳይንስ ሊያደርጉት ጅራት ሲቆሉ ግራ የገባቸው የከተማ ልጆች ጭልጥ ወዳለው ማህበራዊ እንስሳነት ሲወርዱ በግቢያችን ውስጥ እንደሰው መኖርን ያጣጣምከዋት እኔ ከፍ ባለ ክብር እየተማርኩ ሁሉንም ተማሪ ፅንፍ በሌለው ጥላቻና ንቀት እመለከት ነበረ የናቀውን የሚወድ ህዝብ ግን ከጎኔ ነበር ! አሹየ አሹነት ሹ ሸቢ ሹሹ ከቤተሰቦቻቸው የወረሱት እባብነት የስም ግንድ ላይ ሲጠመጠም ላለመነደፍ ልቤን ቆዳ አልብሸው ነበረ ማቆላመጥ የሚወድ ሰው ጤነኛ አይመስለኝም አጭበርባሪ ነጋዴ ነው የሚመስለኝ በየስሙ ላይ የ መለደፍ የፍቅር ሃዋሪያ መሆን ይመስላቸዋል

የቤተሰቦቻቸው መርዝ አልሰራ ሲል ( የተመረተበት ጊዜ አልፎ እንዳይሆን ሰግተው) ከፊልምም ከመፅሄትም አዳዲስ መርዝ እየተሸከሙ ብቅ ይላሉ በአነጋገር በአለባበስ በአስተያየት በእግር በዳሌ በጣት በፀጉር እናም

በመጨረሻ በሃሜት "ይሄ ልጅ ሴት አይመቸውም እንዴ ማን ያውቃል ዘመኑ ከፉ ነው እናትየ እንትን እንዳይሆን " እነሱ ጋር ያልሆነ እነሱን ያልፈለገ ጭራ አለው ደብቆት ነው እንጅ ቀንድ አለው ጥፍር አለው በዚች ምድር ላይ እንደመናቅ የሚያም ነገር የለም አመማቸው

ቡም ምምምምምምምም "ይሄ ቀብራራ እዚህ ይኮፈሳል እናቱ እንጀራ ጋጋሪ ልብስ አጣቢ ነች አሉ " ጮማ ወሬ ተገኘ ዳሊያቸውን እየናጡ ፀጉራቸውን እየነሰነሱ ጅራታቸውን ከሚቆሉላቸው ወንዶቻቸው ጋር አወሩ ተሳለቁ ሊያሸማቅቁኝ ሞከሩ ራሳቸውን ችለው መቆም ሲፈሩ የእፉኝት ልጆች በልብስ አጣቢ ልጅ ሳቁ የቤታቸውን አጠራቅመው ለዘመን መለወጫ ቤታቸውን የሚያፀዱ ሁሉ ሰው ሰራሽ ጠጉራቸው ራሳቸው ላይ ጀልቶ በፆም በፆለት የሚፈታ ሁሉ ተብረቅርቀው ሰው ነን ሊሉ ልክ ለልክ ከተዋወቅን ቆየንና ይሄም ጥይታቸው ከሸፈ

ቢሆንም እኔ አሸብር "ላይፍ "በሚሉት ጋጋታ ወስጥ ከሙታን ጋር መሃበር አለመጠጣቴ እንዳበገናቸው ወደ "ዱፍትርናው" ተንደረደርኩ !!

ልማዴ ነው ስለኔ የሚንሜጩትን ትንሽ እያደረኩ ማለፍ እንከን ፈላጊወች ሚዛናቸው ከአሉባልታ ሌላ ምን ሊሰፍር ቡፉፉፉፉ ለማሸነፍ የተጠራሁ መሆኔ ሲገባኝ ተሸናፊ አቆላምጦም ይሁን ሳያቆላምጥ ሲጠራኝ አቤት አልልም አልኩ !! አቤት ብትላቸው ቃላቸው አንድ ነው " ኑና አብረን እንውደቅ "

# ክፍል 20

የህክምና ትምህርቴን ከጀመርኩ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የአንዲት ሴት አስከሬን አየሁ እድሜዋ አምሳ የነበረ አሁን ግን ዘላለም የሆነ ጠይም ሴት አስከሬኑ ለተማሪወች የተግባር ልምምድ ትምህርት የሚውል ነበር ሁላችንም ለአስከሬን አዲስ ስለነበርን አንዳንዶቹ ደነገጡ አንዳንዶቹ ተንቀጠቀጡ አንዳንዶቹ ሊያስመልሳቸው ሞከረ (አንዲት ልጅ አስመልሷታል) እኔ ግን እንባየ መጣ !!

ሰው ሙቶ ሲያዩት እንዴት ያሳዝናል ኢትዮጲያዊ ሙቶ ሲያዩት እንዴት ያሳዝናል የአንድ ሚስኪን ኢትዮጲያዊ አስከሬን ማየት ከሞቱ ከራሱ የበለጠ ያሳዝናል ያስደነግጣል ከዛ በኋላ በርካታ የፈረንጅ አስከሬን አይቻለሁ ግን የፈረንጅ አስከሬን እንደኢትዮጲያዊ አስከሬን አያስደነግጥም ባእድ ምድር ላይ የኢትዮጲያን ባንዲራ ስትመለከቱ የሚሰማችሁ የደመነብስ ድንጋጤ አይነት ግኡዝ ኢትዮጲያዊ አስከሬን ስታዩ ሂወት ያለው ኢትዮጲያዊነት ረቦበት ይታያችኋል

ኢትዮጲያዊት እናት ሙታ ስትታይ እንዴት አንጀት ትበላለች መሰላችሁ ዝም ይላል የሞተ ሰው እጅና እግሩን አሳርፎ ዝም !! ሰው እየጮኸ እየተንጫጫ ወደዝምታው ነው የሚሮጠው !! እና እች ሴትዮ ዝምታዋ ላይ ደርሳ ነበረ !! ምነው ዘርፌ በሆነች አላልኩም ዘርፌንም ከዚህ ይሰውራት አልኩ እንጅ !!

አንዳንድ ሰው በቁጣ "ዝም በል" ሲል "አፍህን ዝጋ" ማለቱ ብቻ አይደም ከዛ ያለፈ እርግማን ነገር አለው መምራት የምንፈልገው ሬሳ ነው ካላሉ በስተቀር ለምንድን ነው መሪወች ህዝባቸውን "ዝም በል " የሚሉት ዝምታ ሰላም አይደለም አሁን እች ሴት "ሰላማዊ" ናት ? ዝምታ ኩርፊያ አይደለም አሁን እች ሴት አኩርፋለች ? ዝምታ ትእግስስት አይደለም እች ሴት ታጋሽ ናት ?

በምድርም የተመቻት አይነት ሴት ስላለነበረች ነው መሰል በጣም የተበሳቆለ ሰውነት ነበረ ያላት (በነገራችን ላይ አስከሬን አንቱ አይባልም የተባለ ይመስል አንች ነበር ሁላችንም የምንላት) እንግዲህ መፅሃፉ "የብልሆች እግር ወደሃዘን ቤት ነው " የሚለው ለምን እንደሆን የገባኝ አሁን ነው ህክምና የምማረውም ለምን እንደሆነ የገባኝ አሁን ነው

"ፍጠን አሸብር ሰወች ዝምታቸው ላይ ሳይደርሱ " የሚል መልእክት በውስጤ ፈነዳ

ሰወች ከፉም ይሁኑ ደግ የሚጠቅምም ነገር ይናገሩ የማይጠቅም ዝባዝንኬ ብቻ ዝምታቸው ላይ እንዳይወድቁ መሮጥ አለብኝ ልቤ ታዲያ ደረቴን ፈጥርቆ የወጣ እስኪመስለኝ ይመታል ታፍኖ የኖረ ሚስኪን ሳያልፍለት እንዳይሞት በደሉን ሳይተነፍስ ዝም እንዳይል የብዙ ብዙ በደል መቃብር እንደሆነ ወደመቃብር እንዳይወርድ እኔ አሸብር ዶክተር እሆናለሁ ሰው ከቀኑ አያልፍም ቢባልም ቅሉ ቀኑን እስካላወቅነው ድረስ እንሮጣለን !!

ለእኔ ሰው በሁለት ይከፈላል እናቴ አቲየ እና ሌላው !! አቲየ ትኑርልኝ በቃ መኖር ያለባት ሰው ናት እኔ ልጇ ባልሆንም አቲየ መኖር አለባት ሌሎችም ይኑሩ አቲየ መኖረዋን ኑራም ያንን አዘቅት መሻገሯን እንዲመሰክሩ !! እንግዲህ አንድ አስከሬን ነው ይሄን ሁሉ የሚያሳሰበኝ።

እኔኮ አስከሬን ሲባል የሚያብረቀርቅ ልብስ የሚለብስና ለአራት የሚሸከሙት አልጋ ነበር የሚመስለኝ ሞት እንዳለ አወኩ ሰማሁ ሳይሆን አየሁት ሞት ያፈረሰውን የሂወት ከተማ አየሁት ያውም እናት የምትባል ዋና ከተማ። መምህራችን ዶክተር ዘሩ ፊታችን ለተጋደመው አስከሬን የሚሰጡትን ትልቅ ክብር እና እንክብካቤ ሳይ ገረመኝ አንዳንድ ዶክተሮች በሂወት ላለ በሽተኛ ከሚያደርጉት እንክብካቤ በጣም የተሻለ ነበር !! ይህ አስከሬን ከዛ በኋላ ያለ ሂወቴን ቀይሯል አስተሳሰቤን ቀይሯል ሞት ማለት እርግማን መሆኑን አምኛለሁ (ሳይንሱ ባይልም ) ዝምታ ጤናማ አይደለም !! ከጭቆና ሁሉ ጭቆና “ዝም በሉ “ ማለት መሆኑን አስከሬኑ እየጮኸ ይመሰክራል

ለሰወች ማዘን በተለይ ዝም ለሚሉ ሰወች የጀመርኩትም ያኔ ሳይሆን አይቀርም ቢሆንም እስከምመረቅ ሲበዛ ዝምተኛ ነበርኩ ውስጤ የሞተ ነገር ነበረ ትንሳኤ የሚያሻው ትንሳኤው በር ድረስ ታደርሰኝ ዘነድ የተሰጠችኝ ደግሞ ዛፒ ነበረች የኔ ሚስኪን ዛፒ ግራ የገባት ሙሴ የድህነትን ባህር እየከፈለች እኔና እናቴን ያሻገረች መሪ ነበረች

ዛፒ ምንም እንኳን በግል ሂወቷ ደስተኛ ባትሆንም ሙሉ የዩኒቨርስቲ ወጭየን ልክ በፍርድ ቤት እንደተወሰነበት ሰው ሳታስተጓጉል ትሸፍንልኝ ነበር አደረገችልኝ ብየ አይደለም የማመሰግናት ደግነቷ አያሸማቅቅም ከእርሷ ብር መውሰድ ሙብቴ እንዲመስለኝ አድርጋ ነው የምትረዳኝ “አሹ እስኪ ዛሬ ጥናት ከሌለህ ራት ጋብዘኝ “ ትልና እራት ትጋብዘኛለች

በአኔና በዛፒ መካከል ለቁጥር የሚያዳግት የእድሜ ልዩነት አለ ግን ግን ጓደኛዋ የሆንኩ መስሎ እንዲሰማኝ አድርጋኛለች የመጨረሻዋ ውብ ሴት ብትሆን እንኳን ከልእልትነት ዙፋን ተምዘግዝጋ ታች የምትገኝበት የዝቅታ ዘመን አለ ለሴት ልጅ ይሄ ከባድ ነው ቢሆንም ሴቶች ከወንዶች በላይ ውድቀትን ዘንጠው እየሳቁ መቀበል ይችሉበታል በእርግጥ ዛፒ አንዳንዴ በተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ ባለሁበት ሰአት ከግቢ ትጠራኛለች እንቢ ማለት አልችልም።

እቤት እሄዳለሁ። ራሷን ጣል አድርጋ ደብሯት አገኛታለሁ ከዚህ ድብርቷ ላወጣት እሞክራለሁ። በየቀኑ እደውልላታለሁ ሲመቸኝ ወጣ ብለን እንዝናናለን።

የአዲስ አበባ ወንድ እንደፈራ ዛፒም እንደደበራት አምስት አመታት ነጎዱ በዚህ ብቸኝነትና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሁናም ግን ደግነቷ ልክ አልነበረውም።

ተመርቄ እስከምወጣ ሁለት ጊዜ ቤተሰቦቿ ጋር ውጭ ሂዳ ወደአንድ አመት ስትቆይ እንኳን ጠቀም ያለ ገንዘብ ለእኔም ለአቲየም መላኳን አቋርጣ አታውቅም ነበር

አቲየ ቀስ በቀስ የሰው ቤት ስራዋን እያቆመች የተወሰኑ ቤቶች ብቻ ለዛውም ሰርግ ሲኖር በኩንትራት ወጥ መስራት የመሳሰለ ስራ ላይ ብቻ ተወሰነች ሰውነቷ ግን በጣም ተበሳቁሎ ነበር ድህነት የማይፋቅ አሻራውን ቆዳዋ ላይ አትሞ ቀርቷል እጆቿ መሻከር የሚለው ቃል በማይገልፀው መልኩ ተፍረከርከዋል አይኗ ለዘመናት በተጋፈጠችው የአሻሮና የማገዶ ጭስ እንዳያገግም ሁኖ ተጎድቷል ከዚህ ሁሉ በላ ግን አቲየ ልክ በሌለው ፍርሃት ውስጥ ተዘፍቃ ነበር

አንዳንዴ በዚህ ባህሪዋ እበሳጭና እጮህባታለሁ “ምን ላድርግ ብለህ ነው አሹየ” ስትለኝ እንባየ ይመጣል የመንደሩ ትንሽ ልጆች ጋር መንገድ ላይ ስትገናኝ ቁማ ልታሳልፋቸው ትሞክራለች ኳሳቸው ወደግቢ ቢገባባቸው በሁለት እጇ አንስታ ትሰጣቸዋለች የሆነ ቦታ ሂዳ እንደትልቅ ሰው ወንበር ላይ ከመቀመጥ ይልቅ እየፈራች ምንጣፍ ላይ ወይም ቁጢጥ ብላ አንድ ጥግ ትቀመጣለች ማንም ሲመጣ ወንበር ትለቃለች ታክሲ ውስጥ ሁሉ አንድ ቀን ላንዲት ልጅ ቦታ ልትለቅ ስትሞክር እጇን ይዤ በብስጭት አስቀምጫታለሁ በቃ አይምሮዋ ውስጥ “ትንሽ ነሽ” የሚል ክፉ መሃተም አኑረውባታል !

ድህነት ገንዘብ የሚገዛውን ነገር ብቻ አይደለም የሚያሳጣው በነገሮች ሁሉ ሰልፍህን ከኋላ ያደርገዋል አንዳንዴ ከአቲየ በአስተሳሰብም በገንዘብም የሚያንሱ መንደርተኞች አቲየን ሲያዩ እራሳቸውን ሊቆልሉ ሲሞክሩ እያየሁ ይገርመኛል በቃ እች አዲስ አበባ ዝቅ ሲሉላት እሰው አናት ላይ ቁማ ልትጨፍር ይዳዳታል እራሷ አናት ላይ ማንም ሲፈነጭባት አትነቃም እንጅ!!

# ክፍል 21

ግቢ ውስጥ የነበረኝ ሂወት የአንድ መልካም ተረት ፍፃሜ ይመስል ነበር ልክ “ ከዛም በሰላምና በደስታ ይኖሩ ጀመር” ተብሎ እንዳለቀ ተረት ብር አልቸገርም ባለኝ ጊዜ ሁሉ አቲየን አያታለሁ በየቀኑም እደውላለሁ አቲየን ማውራት ከባድ ነው በቃ ጥያቄወቿ አንድ አይነት ናቸው ”እንጀራው ጥሩ ነው ልብስህ አልቆሸሸም ንባብ አታብዛ በጊዜ ተኛ ራስህን ያመሃል ማታ ማታ ጋቢ ልበስ አሹ ደሞ እጅህን ወጣ ወጣ አታድርግ የሰው አይን ጥሩ አይደለም ” ሁሉንም በጥሞና አዳምጣታለሁ

ስለራሷ ስጠይቃት “እኔ ምን አለብኝ ብለህ” ብቻ ነው መልሷ አቲየ የሚያሰቃይ የወገብ ህመም እንዳለባት ያወኩት እንኳን ከተመረኩ ከሁለት አመት በኋላ ነው እንዳልጨነቅ ደብቃኝ። ፍፁም በተረጋጋ ሂወት ውስጥ ትምህርቴ ላይ ብቻ ሙሉ ሃሳቤን ሰብስቤ የሰው አፈጣጠሩ እየገረመኝ የበሽታ መከሰቻው ምክንያት ብዛት እና መንገድ እያስደነቀኝ በዛውም የሰው ልጅ ምህረቱ ባይበዛለት በቀናት እድሜ ከምድር ተጠራርጎ የሚጠፋ ትቢያ መሆኑ እያስደመመኝ ሰው የምጠላ እኔ የሰው ጥላት የሆነ በሽታ ጋር ድብብቆሽ ስጨዋት ወደመመረቂያየ ተቃረብኩ።

“ሴት አይቀርብም” ይሉኛል። ይሄም እንደጨዋነት ተቆጥሮልኝ ነበር እኔ ባጠቃላይ ሰው ነው የማልቀርበው። ለምን ለይተው “ሴት አይቀርብም” እንደሚሉኝ ይገርመኛል። ሲጀመር ማንም ጋር በሚያገናኘኝ የትምህርትና መሰል ጉዳዮች ከሴትም ይሁን ከወንድ እርቄ አላውቅም።

ሲጀመር ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለዛውም የህክምና ትምህርት ላይ ብቸኛ መሆን ቀላል ነገር አይደለም ቢሆንም ከማይረባ መጠላለፍና በሂወቴ አንድ እርምጃ እልፍ በማያደርገኝ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ የመዳከር ፍላጎቱ አልነበረኝም። ለምሳሌ ፆታዊ ፍቅር ወንድ እና ሴት ቁመው ወይም አንድ ጥግ ተቀምጠው ያንን ሁሉ ሰአት ሲቆዩ ምን ጉድ እንደሚያወሩ ይገርመኛል። ፍቅር ለምን አይዘኝም ብየ ያሰብኩት አንዲት ልጅ እንዳፈቀረችኝ የነገረችኝ ጊዜ ነው ማህሌት ነው ስሟ መጀመሪያ ስታፈጥብኝ አጋጣሚ መስሎኝ ነበር ሲደጋገም የሆነ ነገር ፈልጋ ይሆናል ብየ ችላ አልኩት ከዛ ከበበችኝ አየር ሆነች ላይብረሪ ካለሁ አለች የሆነ ቦታ ከተቀመጥኩ ከሆነቦታው ፊትለፊት ከኋላ ወይም ከጎን አለች ባለፍኩበት ታጋጥመኛለች ሰላሳ መንታ እህቶቿ ጋር ወደዩኒቨርስቲው አብራ የገባች እስኪመስለኝ በዛችብኝ በመጨረሻ ወደድኩህ አለችኝ።

እንደው አጋጣሚውን አልለፈው ምንስ አባቴ ቢከደኝ ባባቴ ወንድ አይደለሁ አልኩና ልሞክር ወሰንኩ ግን ልጅቱ በቀጣዩ ቀኝ ሰለቸችኝ !!

በቃ እግዚአብሄርን ባፈቅር ይሻላል የሴት ፍቅር አያዋጣም አልኩ። ሳይቆይ ግን አለም እግዜርን የሚያፈቅርበት አካሄድ እኔ ከማፈቅርበት ጋር አልገጥም አለኝ።

አንድ ቀን ከግቢ ወጥቸ የተማሪው ኪስ ሞላ ሲል የሚያዘወትራት ሬስቶራንት ሄድኩ አዝዣ ስጠብቅ የዲፓርትመንቴ ልጆች መጡና ፊት ለፊት ተቀመጡ ሶስት ሴቶች ብዙ ሴቶች ሲሰበሰቡ ህብረተሰቡ የጫነባቸውን የዖታ ተፅእኖ ቀንበር የሰበሩት ይመስላቸዋል መሰል ድፍረት ይጨምራሉ ጮክ ብለው ማውራት መሳቅ ምናምን

ያዘዝኩት ምግብ ጭሱን እያግተለተለ መጣ ርቦኝ ስለነበረ የምግቡ ሽታ የተለየ ሆነብኝ አንገቴን ዝቅ አድርጌ አይኖቸኝ ጨፈንኩ ፆሎት ይመስላል ግን አልነበረም በጭራሽ !! መቸ እንደጀመርኩት ባላስታውስም በተለይ እርቦኝ የሚበላ ነገር ሳገኝና ደስ የሚል ምግብ ሲቀርብልኝ ሁልጊዜም እንዲህ አደርጋለሁ ጥልቅ የሆነ ስሜት ውስጤን የሚያስገርም የአፍታ ዝምታ ውስጥ እገባለሁ ለሞተው የእረሃብ ዘመኔ አጭር የሂሊና ፆሎት !

ቀጥ ስል ሴቶቹ በግርምት አፋቸውን ከፍተው ያዩኛል ልክ እንደማላውቃቸው ሰወች ችላ ብያቸው መብላት ጀመርኩ በልቸ እንደጨረስኩ ቡና አዘዝኩ አንዷ ወደኔ መጣች ኤጭጭጭጭ !

“ሰላም ላንተ ይሁን አሸብር”

“ሃይ” አልኳት ባጭሩ ስናገር ሊያገሳኝ ነበር

“መቀመጥ ይቻላል ?” አለች ለመቀመጥ መንገድ ጀምራ ከዛም እንደእኔ ቡና አዘዘች እና ወሬ ጀመረች

“ስታመሰግን አየንህ ክርስቲያን እንደሆንክ አናውቅም ነበር “ አለች ፈገግተዋ ፊቷ ላይ እየተንተተገተገ አልመለስኩላትም

“ፌሎሽፕ አለን ብንጋብዝህ ደስ ይለኛል በቃ አብረን ጌታን ማምለክ ነው ሮብና ቅዳሜ ከሰአት ነው ፕሮግራሙ “ የሆነች ወረቀት ሰጠችኝ እና አመስናኝ ቡናዋን ሳታጋምሰው ሄደች ጓደኞቿጋር ተያይዘው ወጡ ተመራርጠው ጓደኛ የሆኑ ይመስል ሶስቱም ቆንጆወች ነበሩ ድሎት ያሰቃያቸው የሚመስሉ

እንግዲህ ይሄ ምግብ ሲቀርብ ማቀርቀሬ ነው የ “የአብረን እናምልክ “ ግብዣ ያመጠብኝ ወላ ያመጣልኝ ዝም ብየ ሳስብ እነዚህ ልጆች ጋር እንዴት ነው በጋራ የምናመልከው ብየ ገረመኝ እኔ ለየትኛውም እምነት ለየትኛም አምልኮ ግድ ያለኝ ሰው አይደለሁም በሂወቴ ሙሉ የፀለይኩበት ቀን ኑሮ አያውቅም እግዚአብሄር የእኔ ብቻ ስለሚመስለኝ ሌሎች ጋር በጋራ ማምለኩም መዘመሩም ምኑም ትዝ ብሎኝ አያውቅም

እግዚአብሄር እኔ ጋር በመተባበር አዲስ አበባን ድራሽዋን ለማጥፋት እስከመረቅ እየጠበቀኝ አልያም እንደ ኖህና ቤተሰቡ እኔና አቲየ ወደመርከቡ እንድንገባ ፈልጎ የጥፋት ውሃውን ያዘገየው ስለሚመስለኝ ማንም ጋር ማምለክ ፈልጌ አላውቅም ስለዚህ በተጋበዝኩበት ቀን ቀረሁ ንዝንዛቸው ግን መቆሚያ መቀመጫ አሳጣኝ አንድ ቀን “ይቅረታ የምትሉበት ቦታ መሄድ ስለማልፈልግ ካሁን በኋላ በዚሁ ብናቆም “ አልኳት አንዷን በቁጣ

አዎ ተቆጥቸ ነበር!! እግዚአብሄርን በምኞት የሚያውቁት ሞልቃቆች የቻፕስቲክ መግዣ ቢያጡ “እግዚአብሄር ማነው “ የሚሉ እግዚአብሄርን እንዲያስተዋውቁኝ አልፈልግም አይቻቸዋለሁ በዩኒቨርስቲ ቆይታየ ዶሮ ሶስት ጊዜ ሳይጮህ ጴጥሮስን ጌታን ሶስት ጊዜ እንደካደው የሚያተት መዝሙር እያንጎራጎሩ እነሱ ራሳቸው የሃብታም መኪና ጡሩንባ በባረቀ ቁጥር ከራሳቸው ሰላሳ ጊዜ ሲካካዱ

አይቻቸዋለሁ የጌታ የማዳን ድንበር አቃቂና ኮተቤ ድረስ ብቻ ይመስል የአዲስ አበባ ልጆች ብቻ ተጠራርተው “በጌታ ፍቅር “ ምሳ ሲገባበዙ ቸርች ሲሄዱ በፅንፍ የለሽ ከተሚያዊ ዘረኝነት የሚነበብ ነገር ሲዋዋሱ አይቻቸዋለሁ በየእምነቱ ተቧድነው ሲናቆሩ ሲጠዛጠዙ እኔ ከነናቴ እግዚአብሄርን ገደል ጫፍ ላይ እንደተንጠለጠለ ገመድ የሙጥኝ ብለን ህዝብ ከዛ ከዚህ ሲገፋን ድህነት እጃችንን እየቀጠቀጠ የመዳኛ ገመዳችንን ሊያስለቅቀን ሲታገል “አንለቅም “ ብለን የተረፍን ሚስኪኖች ነን ”ሰው አትመልከት እግዜርን እንጅ “ ይሉኛል አብረን እናምልክ ብሎ ጠርቶ ሰው አትመልከት ማለት ምንድን ነው

እግዚአብሄርን የማረፊያ ምቹ ሳሎን ሳይሆነን በፊት የውሽንፍርና የመአበል መሻገሪያ ድልድያችን ሁኖ እናውቀዋለን መዝሙር በአፋችን የለም እንጠቅሰው ምእራፍ እንመዘው ቁጥር የለንም ግን አንድ ነገር እናውቃለን እግዚአብሄር እራሱን ያስተዋወቀን "አደርጋለሁ እሰራለሁ" እያለ በመፎከር ብቻ ሳይሆን እየሰራና እያደረገ ነው ፅኑ ክንዱን እያሳየ ያስጨነቀንን ነገር ሁሉ እንደትቢያ ሲበታትነው እኔና እናቴ የአይን ምስክሮች ነን ሽባ ተተረተረ ቢሉን እውር በራ ቢሉን ሰማይ ቢከፈት ምድር ቢናወጥ ተአምር ቢነግሩን መልሳችን አንድ ነው " አልሰሜን ግባ በለው እግዚአብሄር ለእኛ ያደረገውን ነው ለሌሎች ያደረገው " ከራሱ ከፈጣሪ የተሰበከን ነን በስራው!!

ምግብ ፊቴ ሲቀርብ ስለምን መደነቅ ይሞላኛል እነዚህ በመከራ ጩኸት እና በነብስ ዋይታ ሳይሆን በመዝሙር የተጠሩ ቆንጆወች ይህን ብነግራቸው ያምናሉ ? አቲየ ጋር ህፃን ሁኘ ልብስ የምታጥብበት ቤት እንሄዳለን አቲ የተቀለለ ቆሻሻ ልብሳቸውን ስታጥብ ባለቤቶቹ አጥንቱ ብቅ ጥልቅ እያለ የሚንተከተክ ቀይወጥ በረንዳቸው ላይ በትልቅ ብረት ድስት ጥደው አያለሁ የሚንተከተክ ሽሮ አያለሁ የሚጋገር ትኩስ እንጀራ አያለሁ ደግሞ ሽታው አፌን በምራቅ ይሞላዋል ያቅለሸልሸኛል !!

እኔና አቲየ ቁርስ ሳንበላ ነው የምንወጣው አቤቤቤቤት ምሳ ሰአት አራራቁ ልጆቻቸውን ከሚጫወቱበት ለምሳ ይጠሯቸዋል አቧራ የነካ የልጆቻቸውን ልብስ ወደአቲየ የልብስ ቁልል ይጥሉና ይዘዋቸው ይገባሉ በመቀነሻ ሰሃን ወጡኝ አጥነቱን ጭምር ቀንሰው ይገባሉ ይርበኛል ሲንተከተክ ድምፁ እስከዛሬ ጆሮየ ላይ አለ ድምፃቸው ይሰማኛል " ብሉ እንጅ አጥንቱን ምነው ፈራችሁት " እየተባባሉ "አልጫውን አልጣፈጣችሁም " እየተባባሉ ትሪ ጭልፋ ሲንኳኳ

አባወራው "እስቲ የአጥንት መቀጥቀጫ አምጭ "ይላል ስጋውን የተገፈፈ ነጭ እንቢልታ የሚያህል ቅልጥም ወድሮ ወደበረንዳ እየወጣ ከሽ ያደርገውና አንጋጦ መቅኒውን ይስባል ጉሮሮው ወደላይ ወደታች ይነቀሳቀሳል የኔም ይንቀሳቀሳል በማያገባው ጉዳይ

የቅልጥሙ መርዘም እና ሰውየው ወደሰማይ ወድሮ ጫፉን አፉ ውስጥ አስገብቶ ሲመጠው ሰማይ ላይ ያለውን ደመና በቀስም የሚመጠው ይመስላል "አይ ወደቀ "ይላል ወደመሬት እያየ ሚስቱ ጉርሻ ጠቅልላ ወደበረንዳ ትወጣለች "እችን ብቻ አፈር ስሆን " እያለች በወጥ የረሰረሰ ጉርሻ (.ውስጡ የተከተፈ ስጋ ወይም እንቁላል ሊኖረው ይችላል እላለሁ በሆዴ)

"አሸብር " ትለኛለች አቲየ ድንገት ማፍጠጤ ሲበዛ "እንካ ብስኩት ግዛና ና " ብላ አሮጌ መሃረቧን ፈታ አንድ ብር ትሰጠኛለች አንድ ብሩን ስታወጣ መሃረሙ ባዶ ይሆናል ብስኩት ገዝቸ እመለሳለሁ ዛሬ ላይ ሳስበው የሚቆጨኝ ለአቲየ ብስኩት አልሰጣተም ነበር ብቻየን እበላለሁ በሩ ይከፈትና "አፀደ እችን ለቅለቅ አድርጊያት ልጆቹ ሲንቀዠቀዡ ወጥ ደፉበት " አንዳች የሚያክል የሰውየውን ኮት ትጨምራለች ባለቤቷ !! ሁልጊዜም በሩ ሲከፈት ሰሃን ይዛ የምትወጣና "ምሳችሁን ብሉ" የምትል ይመስለኝ ነበር ግን ብላን አታውቅም !!

አንዳንዱ ቤት ደግሞ ቁራሽ እንጀራ (ወጥ የነካካ) በሰሃን ይዘው ይወጡና "እናትየ እሷን ለቅለቅ አድርገሽ ስትጨርሽ እችን ብይ " ትላለች አሰሪዋ "እሷን ለቅለቅ" ያለቻት ቢደረደር ሱቅ የሚሞላ ድርቶ እኮ ነው በነገራችን ላይ በራሴ ገጠመኝ እንዳየሁት ብዙ ሚስቶች ከፉወች ስስታሞችና ታላቅነታቸውን ለማሳየት ሰራተኛ የሚበድሉ ናቸው ባሎቻቸው ይሻላሉ አቲየ ታዲያ "አሹ እችን ብላ " ትልና ፈገግ ብላ ሰሃኑን ለኔ ሰጥታ ስራዋን ትቀጥላለች አቲየ ስትበላ አይቻት አላውቅም ይገርመኛል

ርሃብ እንደብርድ እንደሙቀት እንደደስታ እንደሃዘን ሰውነታችን ውስጥ የሚፈጠር ስሜት ብቻ የሚመስላቸው ሞኞች አሉ ርሃብ በሽታ ነው ቆሻሻ የሆነ በሽታ ነው !! ዘመን ተሻግረው ስለሰባሰባት ድርቅ ሲያወሩ ስለስልሳስድስት ርሃብ ሲደሰኩሩ እዚሁ በረንዳቸው ስር ከነእናቴ የተቀራመድንበት ስንት አሰቃቂ ቀን አልፏን ስንት ክፉ ቀናት ወደውስጥ አስለቅሰውናል መሃል አዲስ አበባ በእረሃብ የሚሞት የለም ሲሉኝ "ጥጋበኞች" የምላቸው ስንቶች ናቸው ዛሬ !!

ይሄ ልመናን ስራው ያደረገ ለማኝ ይመስለናል የሚራበው እሱ ክብሩንም ይሉኝታውንም ጥሎ ሆዱን ሞልቶ “የአዲሳባ ህዝብ ውሎ ይግባ” እያለ ያድራል መቀመጫዋን እያየህ በአይንህ የምትከተላት ዘናጭ ቆንጆ ሆዷ ቢፈተሸ ግን ማን ያውቃል ሱፉን ለብሶ ላፕቶፑን አንጠልጥሎ ከስራ የሚወጣውን ጎልማሳ ብትመረምረው ግን ሙሉ ቀን እህል በአፉ አልዞረም ይሆናል ራበኝ ለማለት ይሉኝታ ያነቀው ባለድገሪ ነው

ረሃብተኛው እርሃቡ እስኪጥለው የሚንጠራወት በየበረንዳው ጃንቦውን ወዝቶ የምታየው ህዝብ የበላውን እንዲያንሸራሽርለት የፈለገ ብቻ እንዳይመስልህ ይሄ ፌርማታው ላይ ያልደረሰ ጅምር ቢራ እራቱ ሊሆን ይችላል ወዳጅ ፀጉራሙ በግ ነው አለ ሲባል የሚሞተው !!

እናም እነዛ የእረሃብ ዘመኖች አልፈው ጭሱ የሚመዘዝ ሽፍንፍን ያለ ቋንጣ ፍርፍር ፊቴ ሲቀርብ ሳልወድ በግድ አንገቴን ደፍቶ አንዳንዴም እንባየ እየመጣ እግዚአብሄርን እንዲህ እለዋለሁ “ አቤት ማጥገብ ስትችል “ በቃ !! ምግብ ሲቀርብ ምንግዜም የምለው ይሄንን ነው እንደውም ለእግዚአብሄር አይደለም ለራሴ ነው “ይሄ እግዚአብሄር ማጥገብ ሲችል “ የምለው ልቤ ታዲያ ያውቃል “ቀላል ይችላል “ ይለኛል !! ይሄንን የነብስ ወግ ያዩት ሞልቃቆች ታዲያ

“ጌ ታ ሆ ይ ይሄን ምግብ ባርክልን “ የምል መስሏቸው “አብረን እናምልክ “ ይሉኛል !! እግዚአብሄርን በእውነትና በመንፈስ ለማምለክ መንፈስህን በደቆሰ የሂወት ክንድ ስር እያለህ የእውነት መዳን የእውነት ትንሳኤ መኖሩን በመጀመሪያ እመን በተመረጠ ቃል በጣፈጠ ዜማ መራር እውነትህን ለእግዚአብሄር አብረን እንንገረው ብትለኝ እዛው የለመድክበት ነው የምልህ !! እዛው የለመድክበት ያውም ተረት ጋር “እንቧይና ቅል አበቃቀሉ የየቅል “

# ክፍል 22

አንዳንዱ ሰው ዘመንን ተሸግሮ ታሪክን ተረማምዶ ከአላማችሁ ሊያደናቅፋችሁ ፊታችሁ ይጋረጣል ቶሎ ተምሬ ይሄንን ህዝብ የምጫወትበት መቸ ነው እያልኩ ሳስብ የምበቀለው እንዴት ነው እያልኩ ሳምሰለስል መመረቂያ ቀኔ ደረሰ ያስተማሩን የተከበሩ መምህራኖቻችን መድረኩ ላይ በየመአረግ ልብሳቸው ተቀምጠዋል ወደበኋላ ዶክተር የእኔ አምላክ ይነሱና “ ተመርቃችኋል ወደምድር ሁሉ ሂዱ ይሄንን ህዝብ ፍዳውን አብሉት “ ማለታቸው አይቀርም ባይሉም ለእኔ ትርጉሙ ያ ነው !! ይሄን ሁሉ አመት ስማር የህክምና ስነምግባር ከህዝብ ክፋት በልጦ ልቤን ሊያራራው አልቻለም።

እኔ ግራ የገባኝ “ ህዝቡ ማነው ? “ የሚለው ጥያቄ ነው

ህዝቡ የገፉቸው ብዙ አቲየወች አሉ ገፊውን ከተገፊው ያለየ በቀል ያን ያህል አያረካም ህዝቡ ማነው ? አንዳንዴ ደሃው ከፍ ሲል ሌላ ደሃ እየገፋ የተገፋው ነፃ ሲወጣ የባሰ ገፊ ሲሆን እያየሁ ሁሉንም በጅምላ ጠራርጌ አገር እንደሳር አዲስ ትውልድ ቢያቆጠቁጥባት ይሻላል እላለሁ።

የዚህ ህዝብ ዘርፌ የምትባል አመልካች ጣቱ ቀለመወርቅ የሚባል አውራ ጣቱ ብቻ ጋንግሪን እንደለከፈው እግር ተቆርጦ የሚጣል አይደለም አገር በሙሉ ሙሉ አካሉ ተበላሽቷል በክፋት ደዌ ነፍረቋል

ምፅአት “እቃቃው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ “ አይነት የምድር እቃቃ ፍፃሜ አለመሆኑ የገባኝ ያኔ ነው የኖህ ውሃ የሎጥ እሳት እንደምርቃኔ ቀን ይናፍቀኛል በየሆቴሉ ህዝቡ ሲበላ ሲጠጣ ሆዱን የሞላበትን ሰሃን ጓዳ ውስጥ የምትፈትግ የእሱን ወጥ የምትቀቅል የራባት ወጥ ቤት ከኋላው በግፍ እንደምትገረድ እየታየኝ እበሳጫለሁ

ሲፋቀር ሲጋባና ሲወልድ ያበሳጨኛል አንዱ ሞቶ ሌሎች ሊቀብሩ ሲሄዱ መሞት አልነበረበትም አይነት ጩኸታቸውና የአዞ እንባቸው ያስጠላኛል ሰወች ታመው ደፋ ቀና ተብሎላቸው መሞታቸው ይቆጨኛል የሎጥ እሳት እሳት እሳት እሳት !! በየመንገዱ ይሄ ጨብራራ ፀጉራቸው በእሳት ተያይዞ ሲጮኹ ማየት እፈልጋለሁ ጅምላ

ጨራሽ መሳሪያ ስሙ ራሱ ይማርከኛል ይሄን በጅምላ ክፋት ባህሉ ያደረገ ክፉ ህዝብ በጅምላ ቡምምምምምምምምም!! ጭ ጭ!!

ሽክ ብየ የበቀል ደወል በሚደወልበት ቀን ወደመመረቂያ አዳራሹ ገባሁ ሁሉም ያየኛል አውቃለሁ ምክንያቱም ጎበዝ ነበርኩ ጎበዝ ነኝ !! እዛ ጋ የተቀመጠው ዋንጫ የእኔ ነው ይሄን ህዝብ ኮሶ የማጠጣበት ምድረ ኩታራ ስራ ፈላጊ "የክብር እና የሙያ ስም አሳዳጅ " ሁሉ አይናቸው እያየ በፊታቸው እንደምነግስ በመአረግ ዘሬ እንደምቀባ ያውቃሉ ! ለበቀል እንደምቀባ አያውቁም ዩኒቨርስቲ ሰይፏን ስላ ወደህዝብ አንገት በመአረግ ልታውዘገዝግ ነው መጣሁልሽ አዲስ አበባ ሃሃሃሃ እያቃሰትሽ ከፊቴ ልትሰለፊ ምጥ እያጣደፈሽ አድነኝ ልትይ ደምሽ እየተንዠቀዠቀ አትርፈኝ ልትይ ሃሃሃ !!

እንኳን ደስ አላችሁ

እንኳን ደስ አላችሁ

እንኳን ደስ አላችሁ እልልልልልልልል የበቀል ቀን እንዴት ፈጣን ነው ይሄው ደረሰ !!

ተመልከቱ ከኳላ ወንበር ማን እንደተቀመጠ ነጭ ፀጉር ጣል ጣል ያደረገባት ያበሻ ቀሚስ የለበሰች ከዘመናት ብስቁልናዋ አዲስ ልብስና ሹርባዋ ያልታደጋት ሚስኪን እናቴ አቲየ እናቴ!! አቤት ሳያት ሰውነቴኝ እንዴት እልህ እንደሚሞላው !! አዳራሹ እንደዛሬ ሙሉ ሁኖ አያውቅም እዚህ አዳራሽ ውስጥ ታላላቅ ሙህራን በተገኙበት አራት አምስት ጊዜ ተገኝቸ አውቃለሁ ዛሬ ግን ሙሉ ነው አቲየ አለቻ !!

የህዝቡ ብዛት ግርግሩ ግራ እንዳጋባት ከዛፒ ጎን ተቀምጣለች አልመጣም ብላ አስቸግራ ነበር ፈርታ አቲየኮ ይሄን ሁሉ ዘመን "ሰው" የዋለበት ውላ አታውቅም  እንግዳ እንኳ እነዛፒ ቤት ከመጣ ምግብ አቀራርባ ወደጓዳ ነው ሩጫዋ ሰውን ፊት ለፊት ቀጥ ብላ አታይም ቀምተዋታል ሰበአዊነቷን "ሰው ፊት እንዲህ አይቆምም" እያሉ "እቃ እንዲህ አይያዝም " እያሉ "ምን ትንከረፈፊያለሽ " እያሉ የእኔን እናት ካላሳነሱ ትልቅ መሆን የማይችሉ ይመስል ምድረ ገለባ እስኪበቃው እናቴ ላይ ተጨማልቋል

ዛፒ እጇን አውለበለበችልኝ ! ደግሞ ፈገግተዋ እንዴት ነው ደስ ያላት  ሳላስበው አፍጥጨባቸው ነበር ለካ አቲየ በስስት እንደምታየኝ ከዚህ ርቀት አውቂያለሁ የእርሷ መሲህ ጥቁር መጎናፀፊያ ለብሸ ሰላሳ ስምንት አመት የተኛችበትን የድህነት አልጋ የመገፋት አልጋ የመከላፈትና የመናቅ አልጋ "አንች ሴት ልጅሽ ደርሶልሻል ተሸከሚሽ ሂጅ" ልላት እፊቷ ቁሜያለሁ ሃሌ ሉያያያያያያያ እኔ ዶክተር አሸብር ነኝ ዶክተር አሸብር በአምላክ !! የተገፋችው የተናቀችው የአፀደ ልጅ !!

እንኳን ደስ አላችሁ

እንኳን ደስ አላችሁ

እንኳን ደስ አላችሁ

አንዳንዱ ሰው ዘመንን ተሻግሮ ታሪክን ተረማምዶ ከአላማችሁ ሊያደናቅፋችሁ ፊታችሁ ይጋረጣል ለምሳሌ ሂፖቅራጥስ ይሄ ሰው የዘርፌ የበኸር ልጅ እስኪመስለኝ የቀለመወርቅ የነብስ ወዳጅ ነው ብየ እስከጠረጥር ዛሬ ቅጥልልል ነው ያደረገኝ !! በጓጓሁለት የምርቃን ቀኔ ፊቴ ተጋርጦ ማንም ሳያዘው ሽማግሌ ይሆናል ? (ወይስ የአዲስ አበባ ህዝብ ፈርቶ "አሸብር ጋር አስታርቀኝ" ብሎ ልኮት ነው ?)

የህክምና ዶክተር ሲመረቅ ቃለ መሃላ እንደሚፈፅም ባውቅም ረስቸው ነበር  በዚች ቀን ግን የሂፖቅራጥስ መሃላ (Hippocratic Oath) የሚባለውን አስመራቂው ዶክተር ቃል በቃል እያነበቡ ደግመን እንድንናገር ሲያደርጉን ሆነ ተብሎ አሻጥር የተፈፀመብኝ እስኪመስለኝ ከፍቶኝ ነበር

እንዴት ነው “ ህዝብን ሙያየን ተገን አድርጌ አልጎዳም” ብየ የምመለው? በምንስ ሂሳብ ነው በጨዋነት የህመምተኛውን ክብር እና ሰብእና በሚጎዳ መልኩ ምንም መጥፎ ነገር ላላደርግ ብየ የምምል የምገዘተው ? ይሄ ህዝብ እናቴ ላይ በነብሰ ስጋዋ ሲጫወትባት ሂፖክራተስ ከነመሃለው የት ነበረ

ኸረ ቀልድ ህዝቡ “ ልጇ አይደለህም “ ብሎ የወረወረኝ እኔ  ህዝቡ ከአሜሪካ ላሙ እኩል ሊያየኝ ያልፈለገ እኔ “ህዝቡን እንደቤተሰቤ የህዝቡን ልጅ እንደራሴ ልጅ ላይ “ ብየ እንድምል ሂፖራጥስ ሽምግልና ፊቴ ቆመ ይሄ “ዶክተር” ለመባል የቸኮለ ሁሉ የተባለውን ተመስጦ ይደግማል

“በህክምና ወቅት የምሰማውን የህመምተኛውን ሚስጥርም ሆነ የግል ጉዳይ በታማኝነት ልጠብቅ ” ወቻ ጉድ !

“ህዝቤን ከልብ በመነጨ ፍቅር ፣ሰበአዊነት እና ሙያዊ ስነምግባር ላገለግል ” ካለፍኩበት የትምህርት ውጣውረድ ይልቅ ይህን ታላቅ መሃላ ማለፍ ከባድ ነበረ ያውም እኮ በእግዚአብሄር ስም በእኔና በአቲየ እግዚአብሄር ስም ግን አንድ እውነት ልንገራችሁ መሃላው ልብን ያርዳል ከውስጤ የፎከርኩበት በቀል ሲተን እግዚአብሄር የበቀል ብተሬን ከእጀ ላይ ፈልቅቆ ሲወስድ ይሰማኛል ስምል እንባየ በጉንጨ ላይ እየፈሰሰ ነበር

ግን ምን አደረገ የአዲስ አበባ ህዝብ ??? ሂወት ሰለሜ ሰለሜ እያጫወተው ከከፉው ኋላ ከፉ ተሰልፎ ማለቂያ በሌለው የከፋት ሰልፍ አንድ አልንጋ ከኋላው እያራወጠው የሚኖር ሚስኪን ምን አደረገ ?? ልጆቻችን ተመረቁልን ብሎ አልጋው ላይ እያቃሰተ እየጠበቀን ይሆናል ውጋቱኝ ችሎ ቁርጠቱን ችሎ ኤዲያ በቃ አፉ ብየዋለሁ !! ኡፍፍፍፍፍፍፍፍፍ ራሴን ቀለለኝ ስሜ ከመድረክ ሲጠራ አዳረሹ በጭብጨባ ሲናወጥ መድረክ ላይ ቁሜ ተመለከትኩ የማታጨበጭብ ብቸኛ ታዳሚ አቲየ ነበረች ”የሰው አይን ልጀን ” እያለች እኮ ነው መች አጣሁት

እናም አልኩ “ እህቴ ዛፒ እወድሻለሁ “ ሁሉም ወደሷ ዞሮ አጨበጨበ እንዴ ዛፒ አለቀሰች !!

አቲየን አየኋት ዛሬ ድረስ ቪዲዮውን ሳየው አልቅስ አልቅስ ይለኛል አቲየን ስሟን ብቻ እንደጠራሁ እንባየ ተዘረገፈ በቃ!! ሌሊቱን ሙሉ ምን ብየ እንደማመሰግናት አጥንቻ ነበር እኮ !!

*** **** ****

ብዙዙዙዙዘ አመታት አለፉ በርካታ የውጭ አገራትን ለትምህርት እረግጫለሁ “እጁ መድሃኒት ነው “ የምባል ስመ ገናና ዶክተር ነኝ አስተማሪም ነኝ ዛፒ ግቢውን ቀስ በቀስ ተከፍሎ በሚያልቅ ክፍያ በስሜ አዞረችልኝና ጠቅልላ አሜሪካ ገባች ! ያንንም ለወይዘሮ እጥፍ ወርቅ ልጆች ነበር የምልከው

ዛሬ ይሄ ግቢ ብዙወች የሚፈወሱበት የእኔ የእራሴ የግል ከፍተኛ ክሊኒክ ነው የረገጥከውን ትወርሳለህ ይልሃል መፅሃፉ ”አፀደ ከፍተኛ የግል ክልኒክ ሲባል ከሰማችሁ “ በኩራት እነግራችኋለሁ ባለቤቱ እኔ ነኝ !!

አቲየን “ ለስምሽ ግብር ልክፈል እንዴ “ ብየ ጠይቂያት ነበር እንደቀልድ

“አዎ እስቲ ልጅ ውለድና በአይነት ክፈለኝ “ አለችና ቀጠል አድርጋ እንዲህ “አሹየ በቀደም በተስኪያን ስታደርሰኝ አብራን የተሳፈረችው ልጅ አሚት ነው የመጣች ? “ አለችኝ ሁለታችንም በሳቅ ሞትን ሃሌታ የምትባል ቆንጆ ልጅ ጋር ጉድ ጉድ ማለት ጀምሬ ነበረ ኸረ እንደውም ሲለይለት ለአቲየ ለሳውቃት ብየ እንጅ ነገሩስ ብዙ ሂዷል አቲየ ደግሞ ለመዳር እንኳን እኔን

ውስጤ ፍፁም ሰላም ይሻል ለአለም ህዝብ ሁሉ ሰላም  ኒውክሌር ቦምብ በአጋጣሚ ቢኖረኝ ወስጀ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያውላችሁ !! ለሰላማዊ ጉዳይ ለሃይል ማመንጫ ምናምን ማለት የለም በህግ አምላክ ውሰዱልኝ ይልቅ በጅምላ ህዝብ የሚፈጁትን ወባና ኤች አይቪ እንዋጋቸው ዘንድ መከላከያውን በግፍ ላኩልንማ !!

ተፈፀመ!!

# የቀድሞው ጠ /ሚ መለስ ዜናዊ በሰማይ ቤት

## (ምናባዊ ወግ)

## ይህ ተከታታይ ወግ አስራሁለት ክፍሎች አሉት

ይህ ፅሁፍ ፌስ ቡክ ስጀምር በመጀመሪያው ቀን የለጠፍኩት ነበር … በወቅቱ ዋርካ ፎረም ይህን ፅሁፍ ለጥፎት በርካታ አስተያየቶች በስሙ ሲሰጡት (ብዙው ሰው ፅሁፉ የራሱ የመክብብ መስሏቸው ነበር) መክብብ በጨዋ ደንብ ይህን አስተያየት ሰጥቶ ነበር

“ይሄን ድንቅ ስራ ጓደኛዬ ልኮልኝ አንበብኩት እና ምናልባት ያላነበቡት አንብበው እንድኔ እንዲደሰቱ ብዬ ወደ ዋርካ አመጣሁት። ስለዚህ ጽሁፉ የኔ አየደለም ። አሌክስ አብርሀም ነው ይላል ። አሌክስ አብርሀም ማን እንደሆነ አላቅም ። ልክ እንደናንተ እኔም አንብቤው ከምቀምቅጫዬ ተንስቼ አጨበጨብኩለት ። ጽሁፉንም ለናንተ አካፈልኩት ። ሰለዚህ የጻፋችሁት ምስጋና ለዚህ ድንቅ ደራሲ ይድረሰው”

## ክፍል 1

## መግቢያ

“ ለምን መግበያ አስፈለገ “ካላችሁ መልሴ “ጥያቄ አታብዙ” ብቻ ነው ! እንደውም በቀጥታ ወደታሪኩ ልግባ

ሰማይ ቤት ነው ፀሃይ በደቡብ በኩል የሚያምር “ፒንክ” ብርሃኗን ረጭታለች ( አላያችሁትም አላየሁትም የፈለኩትን ብናገር እንዳትነተርኩኝ !!) እዚህ ሞቱ ብለን አይናችን እስኪጠፋ ያለቀስንላቸው ሁሉ ዘና ብለው በቀን አስራ ሶስት ጊዜ እየበሉ እንደየምርጫቸው እየለበሱ በቅንጦት ይኖራሉ !! ድሮ የሞተ ዘንድሮ የሞተ የለም ! ማንም ሲሞት በቃ ይቀላቀላል እዛ ጥግ ላይ ቅደስት አርሴማን የመሰለች ቆኝጆ ብርሃን የመሳሰሉ ወንድና ሴት አሳላፊወች አጅበዋት በፍቅር ለቁርስ የተሰለፉትን ሙታን ትመለከታለች ቁርስ የሚታደለው ስም እየተጠራ ነው ቆንጆዋ ሴት ፈገግ ብላ ተናገረች “ አዲስ የመጣችሁ እንኳን ደህና መጣችሁ ይሄ የእግዚአብሄር መንግስት ነው።

አሁን በዚህኛው አለም አቆጣጠር ከዘላለሙ አስር ቢሊየን ሶስት መቶ ሚሊየን ዘጠና ሁለት ሽ አራት መቶ ሰባኛው ሰአት ነው። የዛሬው ቁርስ ክሮቶ ፐረሰኪ ነው “ ስትል ሁሉም አጨበጨቡ። በሰማይ ቤት እጅግ ተወዳጅ የሆነና ፓስታ የሚመስል ምግብ ነው !! ብዙ ጊዜ ይሄ ምግብ የሚዘጋጀው እንግዳ (አዲስ ሟች) ሲመጣ መሆኑን ሁሉም ስለሚያውቁ ማን መጥቶ ይሆን በማለት ዞር ዞር እያሉ ተመለከቱ።

በእርግጥም አንድ አዲስ እንግዳ መሃላቸው ነበር “የምድራዊት ኢዮጲያን ለ 21 አመት የመሩ አቶ መለስ ዜናዊ “አለ አንድ ግዙፍ ሰውነት ያለው መልአክ። ሁሉም “እንኳዋን ደህና መጣህ “ እያሉ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉ ለእንግዳው ለአቶ መለስ !! በዚህ ሁኔታ ቅድሚያ እንግዳው ቁርስ አንስቶ በግዙፉ መለአክ እየተመራ ኢትዮጲያዊያን ወዳሉበት ታላቅ መናፈሻ የሚመስል ቦታ ሄደ  ንጉስ ሃይለስላሴን ገና እንዳያቸው ነበር ያወቃቸው ምንም አልተቀየሩም ያኔ ዊንጌት በትምህርት ጥሩ ውጤት አምጥቶ የሸለሙት ጊዜ እንዳያቸው !!

ከጎናቸው ታላቁ ሚኒሊክ ለጣይቱ “ አፈር ስሆን እችን “ እያሉ ጉርሻ ዘርግተው በፍቅር ይስቃሉ። ትንሽ ራቅ ብሎ ኮስተር ያለ ሰው ሹርባው ትከሻው ላይ ዘንፈል ብሎ በዝምታ ቁርሱን ይበላል ! ዝምታው ያስፍራል። መለስ በግርምት ይህን ሰው አየው ለራሱ “ቴውድሮስ “ብሎ አንሾካሾከ። ሌላ ባለሹርባ ሰው ደግሞ ከቴድሮስ ጎን ተቀምጧል ይኋንስ ነበር መለስ ራመድ ብሎ ይኋንስ አጠገብ የነበረ ክፍት ቦታ ላይ ተቀመጠና ወደዩሃንስ እያየ

“ከመይ” አለ !! ድንገት ሁሉም በሳቅ ፈነዱ !! ቴውድሮስ ሳይቀሩ እግራቸውን አንስተው ሳቁ !! ሚኒሊክ ሳህናቸውን በግራ እጃቸው ይዘው በቀኛቸው አይበሉባ እንባቸውን እየጠራረጉ “ እመብርሃንን ቀስ ብሎ ወደ ይኄንስ ሲጠጋ ያገሩ ሰው እንደሆነ ገምቸ ነበር” ሲሉ ሳቁ የበለጠ ሞቀ !! “ወዳጄ” አሉ ሚኒሊክ “ እዚህ ምድራዊ ቋንቋ የለም ትንሽ ስትቆይ ውስጥህ በአንድ ቋንቋ ይሞላል እሱም የፍቅር ቋንቋ እንለዋለን !! “

መለስ ወደ ይኄንስ ተመለከተ እራሱን በመነቅነቅ የሚኒሊክን ቃል እውነት መሆኑን አረጋገጠለት፡፡

ሲፈራ ሲቸር “ እዚህ አለም ላይ የብሄሮች እኩልነት የለም ማለት ነው፡፡ ....እንዴት አንድ ቋንቋ ብቻ ሌሎች ላይ ይጫናል”ሲል ኮስተር ብሎ ጠየቀ ” ቴውድሮስ በአትኩሮት ሲመለከተው ከቆየ በኋላ “ፍቅር የማንም አይደለም፡፡ ፍቅር ደግሞ የሁሉም ነው፡፡ ....ስለዚህ ፊደል ሳትቀርፅ ቃል ሳትቀላቅል ድንበርም ሳታበጅለት የምትግባባበት ቋንቋ ካለህ ስለምን ሌላ ቋንቋ ትፈልጋለህ” አለና ሰሃኑን ለአሳላፊው አቀበለው፡፡ ምግቡ እምብዛም አልተበላለትም !!

መለስ ቴውድሮስን በግርምት እያየው “ ቋዋንቋ እኮ መግባቢያ ብቻ ሳይሆን ማንነትም ጭምር ነው ” አለ፡፡ “ ማን እንደሆንክ ለሚያውቅህ አለም ማንነትህን ማሳወቂያ እንቶ ፈንቶ ምን ያደርጋል” ቴውድሮስ መለስ !! መለስ “እነዚህ ሰወች የደርግ ርዝራዥ መሰሉኝ” አለና ከአፉ ላይ መለሰው !! እልህ ቢጤ ግን ሸው አለበት፡፡

ድንገት አንድ ወጣት እያፏጨ መጣና ተቀላቀላቸው”ሀይ ጋይስ ደግሞ እች መላጣ ማናት “ አለ ወደ መለስ እየጠቆመ፡፡ ሃይለስላሴ ባይናቸው ሲገለምጡት ዝም አለ ወጣቱ !! “ ልጅ እያሱ ይባላል” ብለው ለመለስ አስተዋወቁት ! ልጅ እያሱ ሳቅ ብሎ ወደ መለስ እያየ “ እንዴት መጣህ ; እንደሱ እራስህን አጥፍተህ ” ወደ ቴውድሮስ እያሳየ ” ወይስ እንደሼባው በወታደር ጫማ በካልቾ ብለው አባረሩሽ ሂሂሂሂ” ሃይለስላሴ ተበሳጩ !! የልጅ ኢያሱ አነጋገር ቀለል ያለ አላጋጭ ነገር ነው ...ለምንም አይነት ጉዳይ ግድ ያለው አይመስልም! ሚኒሊክ መለስ ነገሩ እንዳልተዋጠለት ገብቷቸው ወደጀመሩት ወሬ ተመለሱና “ ሰማህ መስቀል በፈረንጅ አፍ ጥራው በአበሻ ልሳን ሰይመው ቅድስናውን አትቀንሰውም !! ያው መስቀል ነው ፣ መስቀሉ ላይ ስለሁሉ የሞተው በቋንቋ መከፋፈልን ሽሮ ፍቅር ይሉት ቋንቋ አብስሯልና መስቀሉ በምንም ቋንቋ ቢጠራ ሁሉ ይግባባበታል ሁሉ ያከብረዋል !! አገርም እንዲሁ ነው !! ባንዲራው ቋንቋው “ብሄር” ያልከው ሁሉ ቅዱስ መስቀል ነው መስቀሉ ላይ የአገር ፍቅር ይሉት እውነት ከሌለ ከንቱ ነው !! ፍቅር ነው ማንነት ! መለስ ቁርሱን መብላት ጀመረ በውስጡ “ እነዚህ ሰወች የሚለቁኝ አይነት አይደሉም ...እንደገና ያችን ትግል ከ ሃ ሊያስጀምሩኝ ነው “ እያለ ማሰብ ጀምሮ ነበር !!

“ ያ ባለጌ የት ሂዶ ነው አንተ የነገስከው” ሲሉ ሃይለስላሴ ድንገት ጠየቁ

“ማን” አለ መለስ

“ እኛን የደፈረን ያ መንግስቱ የሚባል ወሮ በላ” አሉ ቆጣ ብለው !!

“ እሱ የተከበረውን የኢትዮጲያ ህዝብ 17 አመት ሙሉ ሲያሰቃይ ሲያስርና ሲገድል ይሄ ግፍ እንዲቆም በሰላም ብንጠይቀው እንቢ ስላለ ለህዝብ መብት መከበር ስንል ጫካ ገብተን ድራሹን አጠፋነው፡፡ እኛ ኢትዮጲያን ስንቆጣጠር ግፍና ጭፍጨፋው ቆመ” ከማለቱ ከአጠገባቸው የተቀመጡ በርከት ያሉ ወጣቶች በሳቅ አውካኩ፡፡ መለስ ዞር ብሎ አይቷቸው ሲያበቃ እነማን ናቸው ብሎ ይኄንስን ጠየቀው..... ይኄንስ በረጅሙ ተነፈሰና “ በምድር አቆጣጠር 1997 በአንድ ላይ የመጡ ናቸው “ አለው ባጭሩ!! “ እዚህም ጩኸት አለቻ” ሲል አሰበ መለስ !! ከዛ በኋላ ዝምታ ነገሰ፡፡ የልጅ እያሱ ፉጨት ብቻ ነበር የሚሰማው ፉጨቱ ምድር ላይ ታዋቂ የነበረች አንዲት ዘፈን ነበረች ... “በቁም ካፈቀርሽኝ ስሞት እንዳትረሽኝ”

## ክፍል 2

አቶ መለስ በመጀመሪያ ቀን የመንግስተ ሰማይ ቆይታቸው የተሰጣቸው ክፍል እጅግ ሰፊና የኢትዮጲያ ቀደምት ነገስታት ጋር በጋራ የሚጠቀሙበት በመሆኑ ነገሩ እንግዳ ሆኖባቸው እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ብዙ አምሽተው ነበር። እንቅልፍ እምቢ ብሏቸው ሲገላበጡ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ አቶ መለስን

" እንግዳው አልተኛህም እንዴ ?" ሲሉ ጠየቋቸው

" አለሁ" አሉ ...ድንገት ከንጉሱ በተሰነዘረው ጥያቄ ደንገጥ ብለው !!

" ማን አልከኝ ስምህን "

" መለስ መለስ ዜናዊ "

" መለስ ከፊቱም ከኋላውም ቅጥያ የለውም ስምህ ?"

"ያው ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ነበር የሚሉኝ"

" ሚንስትር ነሃ ?!."

" አይ ጠቅላይ ሚንስትር ነኝ " አቶ መለስ ጠበቅ አድርገው ተናገሩ "

"ታዲያ ንጉሱ ማነው "

"ንጉስ የለም"

"ፕሬዝዳንቱ ማነው"

"ፕሬዝዳንትም የለም ይቅርታ ፕረዝደንት አለ ክቡር ፕሬዝዳንት ግርማ "ይባላሉ !!

"እንቅልፍ እምቢ አለህ እንዴ ?"

" አይ በጊዜ መተኛት ስላለመድኩ ትንሽ "

" ፈርተኸን እንዳይሆን ሃሃሃሃ " አሉ ንጉሱ ነገር ፍለጋ በሚመስል ድምፅ

" ለምን እፈራችሀዋለሁ ? ሁላችንስ የሰራነው ላንዲት አገር አልነበር "

" እሱን እንኳን ተወው ! ያ ዲቃላ ባለመምጣቱ እግዜርን

አመስግን እሱ ቢኖር በትራስ አፍኖ ነበር በተኛህበት የሚያስቀርህ"

"ማነው እሱ ?" አሉ አቶ መለስ ደንገጥ ብለው

"እኛን የካደን ይሁዳ "

"እ መንግስቱ ? "

"ስሙን ቄስ ይጥራው ""

አቶ መለስ ከት ብለው ሳቁና " እሱስ ቢኖር ለእርሰወም ስጋት ነበር " አሉ !! ሁለቱም ሲስቁ ቆዩና

አቶ መለስ ድንገት ሳቃቸው ጠፍቶ

" እኔ እምለው ድንገት መንግስቱ ቢሞት እዚህ ክፍል ይመደብ ይሆን እንዴ ?" አሉ ለመልሱ ጓጉተው ከምኝታቸው ቀና እያሉ

" ሌላ ቦታ የት ይሄድ ብለህ ... እዚሁ መጥቶ ጉዱን ማየት ነው እንጅ

" አቶ መለስ ሳያስቡት አማተቡ !

ለአፍታ ዝም ተባብለው እንደቆዩ ሃይለስላሴ

" የሆነስ ሆነና አሁን በቦታህ ማን ተተካ ?." ሲሉ በጉጉት ጠየቁ

."ሃይለማሪያም የሚባል ምክትሌ የነበረ ሰው "

"እሱ ነው የገደለህ ?"

"ኸረ እኔ የእግዜር ሞት ነው የሞትኩት""

" ታዲያ ይሄ ንግስና ያወረስከው ሰው ጋር ዝምድናችሁ እንዴት ነው የሚቆጠረው ?"

"የምን ዝምድና ?"

" እችን ይወዳል ተፈሪ" ብለው ከወገባቸው ቀና አሉና " የትም ለማታቀውቀው ሰው ነው አገርን ያህል ነገር ሰጥተህ የመጣሃው ?" አሉ ቆጣ ብለው። የንጉሱ ድምፅ የቀሰቀሰው ልጅ እያሱ " ይሄ ሼባ ሲለፈልፍብኝ ሊያድር ነው እንዴ "አለ በምሬት። ቀጥሎም እንቅልፍ ባጭነጭነው አይኑ መለስን እያየ " አንተ አይደከምህም እንዴ ወደዛ አትተኛም ...ሽማግሌው እንደሆነ ሲያወራ ቢያድርም አይታክተው ..." አለ እያመናጨቀ።

ንጉሱ እየሳቁ "ና ጉድህን ስማ ኢትዮጲያን ሃይለማሪያም ለሚባል የትም ለማላውቀው ሰው ሰጥቻት መጣሁ ይላል እንግዳው"

"ይስጣታ ! እንተስ ለማንም ወታደር ሰጥተሃት መጥተህ የለ እንዴ" ብሎ ንጉሱን በነገር ወጋ ካደረገ በኋላ የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሁሉ ወደመለስ በግርምት ዞሮ

" ከምር ግን ለማታውቀው ሰው ነው የሰጠኻት አገራችንን " ሲል ጠየቀ

" ዝምድና የለንም አልኩ እንጅ ላላውቀውም አላልኩም ምክትሌ ነበር በዛ ላይ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ነበር በዛ ላይ የተማረ ነው ስለውሃ ጉደይ ምህንድስና ተምሯል " እያሉ ሲዘረዝሩ

ንጉሱ " ውሃ አስበላኋት በለን እንጅ" አሉ !!

እያሱ " አሁን የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ማነው" አላቸው አቶ መለስን

" ቴድሮስ አድሃኖም የሚባል የጤና ሚንስትር የነበረ ይሁን ብየ ነው የመጣሁት"

" እሱንስ ታውቀዋለህ"

" እ ማለት ያው አንድ ብሄር ነን "

" ታዲያ እሱ እስኪመቻች ሃይለማሪያምን አስቀመጥነው አትልም" ካለ በኋላ ወደ መለስ እያየ " ይልቅ ቁም ነገሩን ሚስቶችህን ለማን ጥለሃቸው መጣህ ? እንዴት ነበሩ። ሳይህ አደገኛ ምላስ ነው ያለህ አሪፍ አሪፍ ሴቶች ሳትጠብስ አትቀርም" አለ።

አቶ መለስ የዚህን ልጅ ጋጠወጥነት አልወደዱለትም "እኔ የነበረችኝ አንዲት ህጋዊ ሚስት ነበረችኝ " ሲሉ ሃይለስላሴም እያሱም በሳቅ አውካኩ እያሱ እየሳቀ

" ወዳጀ ይሄ እኮ ሰማይ ቤት ነው የሚወቅስህ የለ የሚያመሰግንህ አንመርጥህም የሚል ህዝብ የለ ምን የለ እውነቱን አውራ ባክህ  ሆሆ አንድ ሚስት ይላል እንዴ ሃሃሃሃ ሼባውም አተራምሶታል እንኳን አንተ !" ወደ ኃይለስላሴ በአሽሙር እያየ " የት አየኸን ሴት ስናተራምስ አንተ ? እኛ አንተን መሰልንህ ? " አሉ የውሸት ቁጣ እየተቆጡ !! በሰማይ ቤት ሁሉም ነገር ቀሪ መሆኑ ስለታየ የምር ቁጣ የለም ! ልጅ እያሱ ወደ መለስ ቀረብ ብሎ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለና " ሚስትህ ቆን ጆ ነበረች ?" ሲል ጠየቀ መለስ እንደመተከዝ አለና

"ጀግና ነበረች  ሲያስፈልግ እሳት የሚተፋ ብረት ይዛ "

" ኧረ ባክህ ባጭሩ መልስ ! አሁን ስለብረት ማን ጠየቀ ፡ ቆንጆ ነበረች አልነበረችም መልኳ አቋሟ ፍቅር ስትለዋወጡ " ልጅ እያሱ መልሱን ለመስማት በጉጉት መለስ ላይ አፈጠጠ አቶ መለስ ኮስተር ብለው " ደርግ ጋር በተደረጉ የተኩስ ልውውጦች ባንድ እጅዋ እየተኮሰች በሌላኛው እጇ የፍቅር ደብዳቤ ትፅፍ ልኝ ነበር "

" አንተ ሰውየ ለምን በቀጥታ አትመልስም " ሲል ጮኸ እያሱ

" ቆራጥ ነበረች " ሁሉም ባንድ ላይ ረጅም ሳቅ ከሳቁ በኃላ " ለምን ያንን ጓደኛህን አትጠራውምና አይነግረንም " አሉ ንጉሱ ፡ እያሱን እያዩ "አሪፍ ሃሳብ " ብሎ የሆነ ሰው ሊጠራ ወጣ እያሱ

" ማነው " አሉ አቶ መለስ እያሱ ሊጠራ የሄደው ሰው ማንነት አሳስቧቸው !

"በቅርቡ ወደዚህ የመጣ ኢትዮጲያዊ ነው እያሱ ጋር ሽርክ ናቸው በተለይ ስለሴትና ስለውድ ጉዳይ ሁለቱ ወግ ከጀመሩ ድፍን ሰማይ ቤትን በሳቅ ነው የሚሞሉት ..... !! "

"ባለስልጣን ነው " ሲሉ ጠየቁ አቶ መለስ

"ጠሃፊ ነው " እያሱ በሚገርም ፍጥነት ሰውየውን ይዞት ተመለሰ። ተጠርቶ የመጣው ሰው ደራሲ ስብሃት ገ /እግዚአብሄር ነበር ! " እንደምን አመሻችሁ ወዳጆቸ " ካለ በሀኋላ ፂሙን እየላገ እንዴ መለስ እንዳትሆን ብቻ " አለ ስብሃት ተገርሞ !

አቶ መለስ ፈገግ አሉ " ስብሃት እንዴት ነህ ስራ በዝቶብኝ ምድር ላይ ሳንገናኝ "

"እንኳንም ...ያልተገናኘን ! እዛ ብታገኘኝ ወይ ደምህ ይፈላና እስር ቤት ትወረውረኛለህ ወይ በአንዱ ጠባቂህ በዱላ እንደጌሾ ታስወቅጠኛለህ ...ግ ን አማልክቱ ለኔ ያደላሉ አንተንም እኔንም ደፉንና እዚህ አገናኙን" ሁሉም በስብሃት ንግግር ከት ብለው ሳቁ "እሱማ ድርጅቴ ካመነበት" ብለው ዝም አሉ አቶ መለስ "እንኳን ከነዛ ብሽቅ ካድሬወችህ ገላገለህ ወዳጀ" አለ ስብሃት የመለስን እጅ እየጨበጠ እያሱ ተቻኩሎ መናገር ጀመረ " ስብሃት ለምስክርነት ነው የተጠራሃው የዚህ ሰው ሚስት ቆንጆ ናት አይደለችም እስቲ ከነማብራሪያው ንገረን ስንነዛነዝ ነበር"

" ሚስቱ ሚስቱ.... እስቲ መጀመሪያ ያችን ነገር አምጣ" አለ ስብሃት። አጠገቡ ያገኘው እያሱ አልጋ ላይ እግሩን አጣጥፎ እየተቀመጠ ! እያሱ ከወደትራስጌው በትንሽ ጠርሙዝ አረቄ ለስብሃት ቀዳለት ለራሱም ያዘ ለንጉሱም አቀበላቸው ችርስ ተባባሉ ስብሃት በረዥሙ ከአረቂው ሳብ አድርጎ በጎርናና ድምፁ

"እነ አብረሃም እነማቱሳላ ጠጡ ካቲካላ " ብሎ የሚያምር ሳቁን ሳቀ ሓሓሓሓሓሓሓሓሓሓ !!

" እሽ ንገረና " አሉ ንጉሱ " ከመጣህ አይቀር ንገረን። ስለሚስቱ ስለርስቱ ስለ መለስ አጠቃላይ ነገር ንገረን በል ጠሃፊ አይደለህም ስላገራችን ኢትዮጲያ ንገረን ያየኸውን የሰማሀውን ሁሉ አብራራው " ስብሃት ግን ያቆማትን ግጥም ቀጠለ "አባባ ጃንሆይ እርስዎ ተማሪው ሲያበሳጭዎት አንዱንም በጡጫ አንዱንም በርግጫ ሲሉት እኔ ዝም በማለቴ ተረፍኩ። ...ደርግ መጣና ቀይ ሽብር ብሎ ትውልዱን ጓደኞቻችንን ሁሉ ሲጠራርግ እኔ ዝም በማለቴ ተረፍኩ። መለስ መጣና አንዱን በሽብር አንዱን በሽብር ፈጣሪ ፀሃፊነት እያነቀ እስር ቤት ሲወረውር ዝም በማለቴ ተረፍኩ " "እና ይሄ ሁሉ ትረካ ምንድነው ስብሃት አሁን የጠየቅንህን መልስልን" አለ ልጅ ኢያሱ እየተጣደፈ

" እነአብርሃም እነማቱሳላ ጠጡ ካቲካላ

እድሜ የሚያረዝም ጠጥተውም ዝም ዝምምምም !! ""

እነአዜብ እነ አባ ዱላ ጠጡ ካቲካላ ለማንም ምንም አላሉም

ጠጥተውም ዝም ዝምምምም !! ዝምምምም !

እነ አርከበ.... እነ ኩማ እነ ስዩም እነ ገደብረ ፂወን እነ አቦይ ስብሃት

እነ ካሱ ኢላላ ጠጡ ካጢካላ

ጠጥተውም ዝምምምም

እነ ስባት እነሪድዋን እነአባዱላ ጠጡ ካቲካላ

በ አማራ በኦሮሞ ቤኒሻንጉል ደግሞ በጋምቤላ

ጠጡ ካቲካላ

ለማንም ምንም አላሉም

ጠጥተውም ዝም ዝምምምም !!

ኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃኃ ዝምምምምምምም !!!! ሊቀጥል ነው ብለው ሲጠብቁት ስብሃት ከተቀመጠበት ተነስቶ ....ትቷቸው መንገዱን ቀጠለ...

## ክፍል 3

ጧት በተፈጠረው ነገር አቶ መለስ ተበሳጭተው እና አዝነው ነገስታቱም ሁሉ አቶ መለስን አኩርፈው እርስ በእርሳቸውም እንደወትሮው ከመጫወትና ከመሳሳቅ ይልቅ አልፎ አልፎ ብቻ ቃል እየተለዋወጡ ነበር የዋሉት! ልጅ እያሱም ሁኔታው አላምርህ ሲለው ገና በጧቱ ነበር ሹልክ ብሎ ወደስብሃት ገ/እግዚያብሄር የሄደው፡፡ በጧት የተፈጠረው ሁኔታ እንደቀልድ ተጀምሮ ነበር ለያዥ ለገናዥ ያስቸገረ የከረረ ፀብ ሁኖ ቁጭ ያለው.

******** **************** *************** ********

አቶ መለስ ምሽቱን ልጅ እያሱና ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ጋር ሲጫወቱ ስላመሹ ድክም ብለዋቸው ነበር፡፡ ጧት ታዲያ አርፍደው ሲነሱ ክፍሉ ውስጥ ማንም ሰው አልነበረም፡፡ ከምኝታቸው ተነስተው በመስኮት ወደውጭ ሲመለከቱ የኢትዮጲያ ነገስታት በሙሉ አንድ ጉብታ ላይ ቆመው ወደሆነ ቦታ በጉጉት ሲያዩ ተመለከቱ፡፡ ነገሩ ገርሟቸው እየተቻኮሉ ወደነገስታቱ ሄዱ፡፡ ነገስታቱ በሁኔታው ከመመሰጣቸው የተነሳ አቶ መለስ አጠገባቸው ሂደው ሲቆሙ እንኳን አላየዋቸውም ነበር፡፡ የሁሉም ወደ አንድ አቅጣጫ መመልከት የገረማቸው መለስ ወደዛው አቅጣጫ አይናቸውን ላኩ አድማስ ላይ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀስተ ደመና ተዘርግቷል የሰማይ ቤት አድማስ የኢትዮጲያ ብቻ አድማስ መስሏል.

ባንዲራው በዛ ሁኔታ፣ ያውም ከሞቱ በኋላ ሲታይ አይንን በእንባ ይሞላል ውስጥን በልዩ ስሜት ያናውጣል አፄ ሚኒሊክ በሲቃ መናገር ጀመሩ “ አገራችን እግርዋ ምድር ላይ ቢሆንም እራሷ ሰማያዊ ነው የፈጣሪ ግዛት ናት ይሄው ምልክቱ ይሄው የጦጲያችን ባንዲራ ተዚህ በላይ ምን እማኝ አለ “ ነገስታቱ ሁሉ በወኔ ተናገሩ “ እውነት ነው! ውሸትም የለበት መጠርጠሩስ”

“ ኮከቡ የታለ?” የሚል ጥያቄ ድንገት ሁሉንም አስደነገጣቸው ፡፡ አቶ መለስ ነበሩ የጠየቁት

“የምን ኮከብ” ሚኒሊክ ጠየቁ

“ የኢትዮጲያን ህዝብ አንድነትና ተስፋ የሚያመለክተው ኮከብ” አቶ መለስ በተገረሙት ነገስታት ተገርመው ጠየቁ!! ሁሉም የአቶ መለስ ጥያቄ ስላልገባቸው እርስ በእርስ ሲተያዩ ልጅ እያሱ ወደ መለስ ጠጋ ብሎ “ ስማ እንቅልፍህን አልጨረስክም እንዴ” አለ ፈገግ ብሎ ሁሉም በሳቅ አውካኩና ወደቀስተደመናው ሲዞሩ አቶ መለስ ከመጀመሪያው የበለጠ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው “ ይሄ የምታዩት አረንገዋዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ብቻውን የኢትዮጲያ ባንዲራ አይደለም” አሉና የነገስታቱን ቆሌ ገፈፉት “ ታዲያ ለማን ልትሰጠው ነው ወዳጆ” አሉ ሚኒሊክ የመለስን ጤነኝነት በጥርጣሬ እየተመለከቱ

" የማን እንደሆነ አላውቅም !!

የኢትዮጲያ ባንዲራ ህገ መንግስቱ ላይ እንደተቀመጠው መሃሉ ላይ በሰማያዊ መደብ የህዝቦችን አንድነት የሚያመለክት ኮከብ እና "

"ዝም በል!!" አፄ ቴውድሮስ አንባረቁ ሁሉም በድንጋጤ ሽምቅቅ አሉ!!

" ለምን ዝም እላለሁ ኮከቡኮ "

"መይሳው !! አፍህን ዝጋ አልኩኮ አንተ ሁርጋጥ!! ይሄ ሞት የሚሉት የሚያመጣው ያጣ ይመስል የማንንም ሁርጋጥ ይሰበስባል እዚህ ሲሞቱ ከሰው እኩል የሆኑ ይመስላቸዋል" አሉና በእልህ ተንጎራደዱ " ሞት የማንኛውም ሰው ዲሞክራሲያዊ መብት ነው ትንሽ ትልቅ ሃብታም ደሃ የለም" አሉ አቶ መለስ ሁርጋጥ መባላቸው አበሳጭቷቸው. " ኧረ በማምላክ ዝም በል አንተ ሰው ምን ነካህ" አሉ ሚኒሊክ መለስን እያዩ.

" አልልም!

ዝም አልልም እኔ መለስ እንኳን እናንተ ፊት ይቅርና የአፍሪካ ህብረት የጂ ኤት ስብሰባ ላይ ማንም አላስቆመኝ እናገራለሁ ያመንኩበትን ከመናገር ማንም ዝም በል ሊለኝ አይችልም" "የአፍሪካ ህብረት ሃሃሃሃሃ ባቀናነው ስካር ተወላገዱበት አሉ !

የአፍሪካ ህብረትን የተከልነው እኛ አለም በፋሽስት ፍቅር ሰከራ ጥቁርን እንደደዌ ተጠይፋ ባለችበት ወቅት ነጮች እየተሳለቁብንና እየሰደቡን እራሳቸው መድረክ ላይ ቁመን ልክ ልካቸውን የተናገርንም እኛ ምኑ ነው ብርቅና ድንቁ ምኑስ ነው ዘራፍ የሚያስብለው" አሉ ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ መለስን በቁጣ እያዩ

" ስማ ደማችንን አፍሰሰን አጥንታችንን ከስክሰን በዘመናት የገነባናትን አገር እንደድፎ ቆርሰህ እነደፀበል የምናመነውን ውሃ እንካችሁ ብለህ ለጅብ አስረክበህ መምጣትህን ያልሰማን መሰለህ. ጅብ የማያውቁት አገር ሂዶ አጎዛ አንጥፉልኝ እንዳለው መሆኑ ነው. እንዳሻህ የምትቀባጥርበት ሂድና ቀባጥር እንግዳ ነህ ቀድመን ሙተናል ብለን አንኮራም ብለን ብናስጠጋህ ምድር ላይ የለመድከውን አርቲ ቡርቲ ድስኩር በለመደ አፍህ እኛ ላይ " አሉ ሚኒሊክ

" እንነጋገራ" አሉ አቶ መለስ እንደቀላል ያዩት ጉዳይ ተራዝሞ እዚህ መድረሱ አስደንግጧቸው

" ሂድ ወዲያ የሚያነጋግርና የማያነጋግር ጉዳይ ለይ መጀመሪያ" አሉ ቴውድሮስ

" አንተ ሰውየ ከኔ ጋር ችግር አለብህ ከመጣሁ ጀምሮ በክፉ አይንህ ነው የምታየኝ ላንተ ስል በሂወት ልኑርልህ "

አሉ አቶ መለስ ቴውድሮስ ፊት ላይ የሚነበበው ንቀትና ጥላቻ አንገሽግሿቸው" " ለቴድሮስ ብለህ ለምን ዘላለም ቁመህ አትቀርም ደግሞ ካንተ ብሶ። ንጉስ ሰላቢ ! ዘር ማንዘርህ ከሃዲ" አሉ ቴውድሮስ አጼ ይኋንስ እያዩ አቶ መለስ በብስጭት ቴውድሮስን እያዩ እንደተፋጠጡ ድንገት ኃ/ስላሴ ተናገሩ" ባንዲራ የአንደኛ ክፍል የስእል ደብተር መሰለህ ከመሬት ተነስተህ ኮከብ የምትስልበት " እያሱ ወደ ንጉሱ እያየ " ሽባው ተው እንጅ አንተስ ባንዲራው ላይ ወልጋዳ አንበሳ እየለጠፍክ የእንስሳት ማቆያ ባንዲራ አስመስለኸው አልነበር " አለ። በቀልዱ የሳቀ አልነበረም!! አቶ መለስ በነገስታቱ ግትርነት ተበሳጭተው ወደ ክፍላቸው ገቡ ነገስታቱ መለስን እንዴት እንደሚያባርሩት መመካከር ጀመሩ ድንገት ኃ/ስላሴ የሆነ ሃሳብ በለጭ አለባቸው

## ክፍል 4

አቶ መለስ የነገስታቱ ግልምጫና ኩርፊያ የነገሰበት ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ከመፋጠጥ ይሻላል በማለት ሰማይ ቤትን ዞር ዞር ብለው ለመጎብኘት አሰቡና ከክፍላቸው ወጥተው እጅግ በተዋበው መንገድ መጓዋዝ ጀመሩ ሰማይ

ቤት ዛፎቹ አበቦቹና ኮረበታወቹ በደስታ ያስክራሉ ሁሉም ሰው ጤነኛ ነው ሁሉም ሰው አይራብም ማንም ሰው በጥላቻ አይተያይም. ሁሉም በሚያየው ነገር እየተደሰተ በተመሳሳይ ቋንቋ እያወራ ያለምንም አላማና ምኞት በሰላም ይኖራል።

አቶ መለስ አረፍ ማለት ስለፈለጉ ቅርንጫፎቹ ዘርፈፍ ካሉ ዝግባ የሚመስል ዛፍ ስር ቁጭ አሉ ግንዱ በጣም ወፍራም ከመሆኑ የተነሳ አስር ሰው እጅ ለእጅ ቢያያዝ እንከዋን ሊከበው አይችልም። ከተቀመጡበት ራቅ ብሎ ቁልቁል የሚወርድ ፏፏቴ ይታያል፤ ውሃው ንፁህ ከመሆኑ ብዛት የወተት ጎርፍ ይመስላል ። ወዲያው አባይ ትዝ አላቸው ግድቡ !! እስካሁን እንዴት እንደረሱት ለራሳቸውም ገርመዋቸው እያለ አንድ ሰው "ጭስ አባይን አይመስልም " አለ !! በድንጋጤ ዞር ዞር ቢሉ ማንም ባከባቢው የለም ! ሊያማትቡ እጃቸውን ሲያነሱ ሌላ ድምፅ

" አባይ ብትል ትዝ አለኝ ቦንድ ገዝተህ ነው የሞትከው ወይስ " ሲል ሰሙ

" ቦንድ ገዝቸ ወለዱን ስጠብቅ አይደል አንድ ከልፍልፍ ሹፌር ገጭቶ የገደለኝ ወይኔ የአንድ ወር ደመወዜ" አለ ሌላኛው በቁጭት አቶ መለስ በሰወቹ ወሬ ተገርመው ማዳመጣቸውን ቀጠሉ ሰወቹም ወረያቸውን ቀጠሉ

" ባክህ ለትውልድ ይሆናል ልጆቻችን በደስታ ይኖራሉ"

"ተው እንጅ የእነማን ልጆች ከመሞትህ በፊት ወያኔ ነበርክ መሰል" አለ ሌላኛው

በሳቅ አውካኩ

" ማነው አባይን የወያኔ ያደረገው " ሲል ሳቁ ጋር እየታገለ ጠየቀ ሌላኛው

" ያ ሰላቢ መላጣ ነዋ!! እንደወያኔ ባለስልጣኖች ሆድ የማይሞላ አቅማዳ አስቀምጦ ሞተ ይሄው ቦንድ ብናስገባ ደመወዝ ብንሰጥ ቅምም አላለው ወይ ግድብ እንደው ይሄ ቢሊየን የሚባል ብር 666 ይሆን እነዴ አካውንት ቁጥሩ ሰይጣን!! በቃ ተዋጥቶ ተዋጥቶ አሁን ሞላ ሲባል 3 ቢሊየን ደርሰናል ይሉናል ያውም አላሙዲን ሳይቀር ሰጥቶ!! ይብላኝለት ለኗሪው እኛስ ቦንድ የለብን ደሞዝ የለን የገደለን አምላክ ይክበር ይመስገን!! " አለ ሌላኛው በምሬት!! አቶ መለስ ተበሳጩ !! ቢሆንም የሰወቹን ወሬ ላለማቋረጥ ዝም ብለው መስማታቸውን ቀጠሉ!!

" እኔ እምልህ አንተ ስትሞት ግድቡ ምን ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር " አለ አንድኛው ፤ አቶ መለስ የሰውየው ጥያቄ ደስ አላቸው መልሱን ለመስማት ገዋጉተው ተመቻቹ እንደሩቅ ሰው ስላስጀመሩት ግድብ ተደብቀው ሪፖርት መስማታቸው ለራሳቸውም እየገረማቸው" ግድቡ አሁንም ይቆፈራል ስመኘው በቀለ የሚባል ኢኝጅነር በቴሌፊዥን ብቅ እያለ እየቆፈርነው ነው ይሄን ያህል ሜትር ኪዩብ አፈር ቆፈርን ይላል ሌላ ቀን ደግሞ ብቅ ብሎ ጓጉተን "ለሰማኒያ ሚሊዮን ህዝብ ብርሃን ፈጠርን" ሊል ነው ብለን ስንጠብቀው "ለ ስድስት ሽ ኢትዮጲያዊን የስራ እድል ፈጠርን " ብሎ ይሄ ስመኘው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሃላፊነቱን ትቶ የሰራተኛና ማሃበራዊ ጉደይ ስራ አስኪያጅ ሆነ እነዴ እስከንል ግራ ያጋባናል!!

" እና አሁንም እየተቆፈረ ነው "

" አወ! እኔ ልሞት አካባቢ ቁፋሮው 2 አመት ሊሞላው ነው እያሉ በአል ሊያከብሩ ሽር ጉድ ሲሉ ነበር" አቶ መለስ ተገረሙ " እንዴት ነው ሁለት አመት የሞላው ጊዜው እንዴት ይሮጣል" ሲሉ አሰቡ! ሰወቹ ወጋቸውን ቀጠሉ " ሰውየው ከሞተ በኋላ አገሪቱን የሞላት የእርሱ ፎቶና መፎክር ብቻ ነው ! ወደየትም ብትዞር" አቶ መለስ ደነገጡ ይሄን ወሬ ማመን አልቻሉም ከተቀመጡበት ብዲግ አሉና ወደሰወቹ ሂደው " የኔ ፎቶ ነው አገሩን የሞላው " አሉ በቁጣ!! ሰወቹ በድንጋጠ በርግገው ተነሱና እያማተቡ አቶ መለስ ላይ ባለማመን አፈጠጡ አፋቸው ተያያዘ " መለ ከክክክክ ቡር ጠቅላይ ሚንስትር እንዴ እዚህ ምን ይሰራሉ " ሰወቹ በድንጋጠየ የሚናገሩት አጡ "ተረጋጉ ድንገት እዚህ አረፍ አልኩና የምታወሩትን ስሰማ ገርሞኝ ነው" አሉ አቶ መለስ ሰወቹን ለማረጋጋት እየሞከሩ።

ሰወቹን ለማረጋጋት እረዥም ጊዜ ወሰደባቸው !! እየቆየም አሁን ያሉት ሰማይ ቤት መሆኑ ትዝ ሲላቸውና የአቶ መለስ ስልጣን ምድር ላይ እንደቀረ ሲታወሳቸው ተረጋግተውና ተግባብተው አቶ መለስ ጋር ሞቅ ያለ ጨዋታ ጀመሩ

“ እና እርሰወ ከሞቱ ጀምሮ ”

“አንተ በለኝ ባክህ”

“ እሽ ያው አንተ ሞትክ ተብሎ ህዝቡ አውርቶ በሃሳቡ አርባህን ሊበላ ሲዘጋጅ እንደገና ሞትክ ተባለ”

“ እንዴት እንዴት ” አሉ አቶ መለስ ግራ ገብቷቸው

“ አንተ ለህክምና ከሄድክ በኋላ የበላህ ጅብ አልጮህ አለ!! ስላንተ ህዝቡ ያወራል ሚስትህን ጨምሮ ባለስልጣኖችህ ዝም ጭጭ አሉ ኧረ የት ሄደ መለስ ሲባል “በመልካም ጤንነት ላይ ነው” እያሉ ህዝቡ በቃ የማያተርፈው ይዞት ነው እያለ የማይወደውን ኢቲቪ ጧትና ማታ እየከፈተ ስላንተ ሞትህንም ሽረትህንም ሲጠብቅ እግረ መንገዱን እንደሞትክ ሲያወራ ”

“ ገፊ ሁሉ “ አሉ አቶ መለስ በብስጭት

“ ከዛ አቶ በረከት መስከረም ላይ ተሽሎህ ስራ እንደምትጀምር ለህዝቡ ሲናገር ህዝቡ በቃ ትንሽ ተረጋጋ ”

“ በረከት እሱ ምናለበት !! እኔ እምለው ህዝቡ የኔ መኖር የኔስ ደህንነት ከመቸ ወዲህ ነው ያስጨነቀው” አሉ አቶ መለስ ግርም ብሏቸው “ኧረ ህዝቡስ በጣም ነው የሚገርመው የኢትዮጲያ ህዝብ የትዳር አጋሩን ብቻ አይደለም እወድሻለሁ አፈቅርሻለሁ ብሎ በአንደበቱ የማይናገረው ጠ/ሚንስትሩንም በግልፅ እወደሃለሁ አይልም ! ግን ይወድህ ነበር !! ”

“ እሽ ቀጥል ”

“ መስከረም ላይ ፓርላማ ውስጥ ሊያይህ ቀጠሮ ለያዘው ህዝብ ነሃሴ አጋማሹ ላይ በኢቲቪ ያ ሰላምታ ሲያቀርብ ግንባሩ ጠረንቤዛውን ሊነካ የሚደርሰው ጋዜጠኛ ሞተወን ለኢትዮጲያ ህዝብ በጧቱ አረዳው”

“ እንደው ምን ብሎ ተናገረ. አፈር ስሆን ንገረኝ” አሉ አቶ መለስ

“ ለሃያ አመታት ኢትዮጲያን በቆራጥነት ሲመሩ የነበሩት ቆራጡ መሪ አቶ መለስ ከዘህ አለም በሞት ተለዩ!!” በቃ ልክ እንደዚህ ነው ያለው!! አቶ መለስ ትክዝ አሉ ። ዜናው ጠላቶቻቸውን ምን ያህል እንደሚያስፈነድቅ አሰቡ ዒሳያስ አፈወርቂ ውስኪ አስወርዶ በድፍን ኤርትራ ያሉ ከበሮወችንና ክራሮችን አሰብስቦ ኤርትራን የሚያክል ክበብ በሰራ ጨፋሪ ተከቦ እስክስ ሲል ታያቸው ሳዋ ሃያ ሽ ጊዜ መድፍ ስትተኩስ ምድር ቃጤ ስትሆን ታያቸው ብርሃኑ ነጋ ወገቡን ታጥቆ ጉራጌኛውን ሲያስነካው ለድፍን የግንቦት ሰባት አባላት ዛሬ የክትፎ ቀን ነው ብሎ ሲያውጅ ታያቸው መራራ ጉዲና” ሰው ቢሄድ ሰው ይተካል ችግሩ ኢትዮጲያን አጥፍቶ መጥፋቱ ነው” እንደሚሉ ገመቱ አቶ ቡልቻ “ጠላታችን ሰው አይደለም መለስ ለልጆቹ ቢኖር ለሚስቱ ቢኖር” እያሉ አባታዊ አስተያየት ሲሰጡ አሰባቸው ልደቱ አያሌው “ እኛም በማኒፌስቷችን ያልነው ይሄንን ነው ሰው ሰው ሟች ነው ” እያለ ሲፈላሰፍ ብለጭ አለባቸው ስየ አብርሃ “ እስካሁን የሞትኩት እኔ ብሆን ድፍን ትግራይ ማቅ ለብሶ አመድ ነስንሶ ነበር የሚቀመጠው” እያለ ጉራውን ሲነሰንስ ታያቸው ታማኝ በየነ ሞታቸውን ለአለም ለማወጅ ከአሜሪካ ቻይና በእግሩ ሲሄድ ታያቸው ብቻ ውስጣቸው በዜናው አዘነ

“ እሽ ከዛስ በኋላ ምን ተፈጠረ ህዘቡ ምን አለ አለም ምን አለ” አሉ አቶ መለስ ሰውየው ግን አቶ መለስ የጠየቁትን ከመመለስ ይልቅ ፈርፍር ብሎ መሳቅ ጀመረ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ ሃሃሃሃ

## ክፍል 5

በቅርቡ በመኪና አደጋ የሞተው ኢትዮጲያዊ ለአቶ መለስ ስለቀብር ስነስረአታቸው በዝርዝር እንዲህ ሲል አወጋቸው “ ኢትዮጲያ ጭጭ አለች !!ብዙ ሰው ቀድሞ ሙተሃል እያለ ሲያሚርት የነበረው ሳይቀር መሞትህን ማመን አልቻለም “ኢቲቪ እንከዋን ዘንቦበት እንደውም ጤዛ ነው “ ሙሉ ቀን ስላንተ ሞት ሲያውራ ሲደጋግም ዋለ ዋሽንቱ ሆድ ይበላ ነበር አስከሬንህ ማታ 3 ሰአት ይገባል ተብሎ ሲነገር ህዝቡ ወድዛው ጎረፈ”

“ ሚርተኛ ሁሉ ምን ሊሰራ ነው የሚጎርፈው መሞቴን ለማረጋገጥ” አሉ አቶ መለስ

“ ኧረ አይደለም አቶ መለስ ህዝቡ በቃ ጎረፈ ቦሌ መንገዱ በሰው ተሞላ ሴቶቹ ከምን ጊዜ ጥቁር ልብስ እንደለበሱ ቢያዩ ይገረማሉ አስከሬንህ ቦሌ እስኪደርስ ህዝቡ እየተላቀሰ ደረቱን እየደቃ መልየ እያለ”

“ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ የኢትዮጲያ ህዝብ ነው መልየ የሚለው አጭበርባሪ የዝናብ ፀሃይ አትከኖ አትከኖ ከደፋኝ በኋላ መልየ ወይኔ መለስ ኑሬ በነበር ታንክ ነበር የማዘምትበት“

“ ኧረ በስማም በል ያከበረህ ህዝብ አልቅሶ አስለቅሶ ቤተሰብህን አስተዛዝኖ በቀበረህ ህዝብ ላይ ታንክ”

“ዝም በል !! ቀጣፊ!! የኢትዮጲያን ህዝብ መች አጣሁት በተለይ ያዲስ አበባ ሰው እስስት ነው ! በውስጡ እየሳቀ ነው ድራማ የሚሰራው አስመሳይ!! ደሞ መልየ አሉ ይለኛል መለመላቸውን ያስቀራቸው ሌባ ሁሉ!! “

“ኧረ ከልቡ ነው ህዝቡ ያዘነው እንደውም እሳቸው የጀመሩትን እንጨርሰዋለን እያለ እኔ እስከሞት ድረስ ሲፎክር ነበር ህዘቡ” አለ የአቶ መለስን ቁጣ የፈራው ተናጋሪ “ እሳቸው የጀመሩትን ጥገኛ ሁሉ እኔ የጀመርኩት ላይ እንደዝንብ ከሚሰፍር የራሱን አይጀምርም የተጀመረ መጨረስ ምኑ ነው የሚያስፎክረው ወሬኛ አስመሳይ ሁሉ!! በንጉሱ እንደፎከረ በደርግ እንደፎከረ ደሞ በእኔ ሊፎክር አፉን ይከፍታል ክፍታፍ ሁሉ! ይሄ ሳቀ ሲሉት የሚያለቅስ አለቀሰ ሲሉት የሚስቅ የተቀዣበረበት ህዝብ እሱን ልመራ ያቃጠልኩት እድሜ ጉልበት የአዲስ አበባ ህዝብ በየበረንዳው ተኮልኩሎ ድራፍቱን ሲግፍ እኔ በመኪና ታሽጌ ስብሰባ ኮንፈረንስ ስሯሯጥ ካንዱ አገር አንዱ አገር ስራወጥ ኖርኩ ደግሞ አለማፈሩ መለስ ሞተ ብሎ ሲያለቅስ ሆዳም ሁሉ”

“አቶ መለስ ምነው የአዲስ አበባ ህዝብ ላይ ወረዱበት ትግሬ ብቻ ነው ለእርሰወ የአገር ፍቅር ያለው” አለ ተናጋሪው ተበሳጭቶ ተወልዶ ያደገባት የተማረባት በመኪና ተገጭቶ የሞተባት አዲስ አበባ ስትወቀስ ቆርቁሮት” አቶ መለስ በፌዝ ፈገግ ብለው “ትግሬ አልክ እነሱ እንጂ እንደመዥገር ተጣብቀው በስሜ ሲነግዱ በተሰጣቸው ስልጣን ሲጨማለቁ ለዚህ ያበቁኝ ወይ አይማሩ ወይ አያነቡ የትግል ተረት እየተረኩ ተወዝፈው አገራችንን የወዘፏት የትግራይን ሚስኪን ህዝብ በጦርነት በተጠበሰ በእርሃብ በተሰቃየ ባልዋለበት ስሙን ያስነሱ ከወንድሙ የኢትዮጲያ ህዝብ የለዩ ሆዳሞች መሃይሞች ስግብግቦች”

“ ታዱያ መሪያቸው አንተ አልነበርክ ስታደርግ ያላዩትን አያደርጉ” አለ ዝም ብሎ የቆየው መዋች ኢትዮጲያዊ

“ ልክ ነህ ይህን ስም ያሰጡንም እነሱ ናቸው!! አልሙ ብለን ኢፈርትን ብንመሰርት ቦጥቡጠው ቦጥቡጠው ቀፎውን አስቀሩት

ስሩ ብለን ፊት ብንሰጣቸው ኮንትሮባንድ የለ ስርቆት የለ የታገሉለትን ህዝብ በጠራራ ፀሃይ ዘረፉት “

“ እኮ እነማን “ አለ አቶ መለስን እያየ ጠያቂው ከትግረይ ህዝብ አብራክ የወጡት አምነናቸው የነበሩት” ብለው ትክዝ አሉና “ለመሆኑ አባ ዱላ ገመዳ ደህና ነው “ ሲሉ ድንገት ጠየቁ

“ አወ እሳቸው አምሮባቸዋል” ቀብርህ ላይ ሲያለቅሱ የሁሉንም ኢትዮጲያዊ ሆድ ነው የበሉት

“ ማን አባዱላ አለቀሰ “ ሲሉ ጠየቁ አቶ መለስ “ ማን ያላለቀሰ አለ በታሪክ እንዲህ ተለቅሶ አያውቅም

ቁመህ ካስለቀስከው ይልቅ ሙተህ ያስለቀስከው ነበር የበዛው “ አለ ተናጋሪው አቶ መለስ አሽሙሩን ያልሰሙ መስለው አለፉት እና “ አቶ ግረማ ወልደ ጊወርጊስ ደህና ናቸው “ ሲሉ ጠየቁ

" ደህና ናቸው እሳቸው ምን አለባአቸው አልባሌ ቦታ ከመዋልብለው አላፊ አግዳሚውን ሰላም እያሉ ቁጭ ብለዋል"

"መሞቴን ሲሰሙ ምን አሉ" አሉ አቶ መለስ ፈገግ ብለው

" ልጅ ይሮጣል እንጅ አባቱን አይቀድምም " አሉ እየተባለ ሲወራ ነበር!! አቶ መለስ ሁኔታውን ሲያስቡት ገረማቸው መሞታቸውን ማመን አልቻሉም ኢትዮጲያ በጣም ናፈቀቻቸው ! ወደከፍላቸው ከመመለስ ብለው ወደደራሲወች መንደር ጉዟቸውን ቀጠሉ ሲያወራቸው ከነበሩት አንዱ አቶ መለስ " ምናይነት መኪና ገጭቶ እንደገደለኝ ታውቃለህ " ሲል ጠየቃቸደው እራሳቸውን በአሉታ ወዘወዙ

" የመከላከያ መኪና ነው ጭፍልቅ አድርጎ የገደለኝ"

"ዳር ዳሩን መሄድ ነበረብህ " አሉ አቶ መለስ

" መንገዱን ስቶ በእግረኛ መንገድ ላይ ገብቶ እኮ ነው የገደለኝ" አለ በስጨት ብሎ

"ለመሆሙ ስራህ ምን ነበር " ሲሉ ጠየቁ አቶ መለስ

" ተቀዋሚ ነበርኩ"

" እናንተማ የእገረኛ መንገድ መጠቀም አትወዱም "

"ምናልከኝ አቶ መለስ"

ጠላትህን መንገድ ላይ ካላገኘኸው በመንገዱ ሂድና ፈልገው የሚል የትግራ ገበሬወች ተረት ትዝ አለኝ ሃሃሃሃ ስላም ዋሉ" አቶ መለስ ሲሄዱ ሁለቱ ሰወች ከኋላቸው ቁመው ሲያዩአቸው ቆዩና "ይሄ መላጣ ያንድ ወር ደመወዜን አስበላኝ" አለ አንዱ።

# ክፍል 6

አቶ መለስ ሰማይ ቤት በማንም አንገታቸው እየታነቀ እየተወቀሱና እየተከሰሱ መኖር ዲሞክራሲያዊ አይደለም ሲሉ አሰቡ!! በዛ ላይ እስካሁን ድረስ የኢትዮጲያ ነገስታትና በርካታ ኢትዮጲያዊያን ሙታኖች ጋር በምንም ነገር ሊስማሙ አልቻሉም። ያገኛቸው ኢትዮጲያዊ ሁሉ ከንፈሩን እየነከሰና እየዛተ አልፎ ተርፎም ፀያፍ ስድብ እየሰነዘረባቸው ተቸገሩ።

በአንድ በሆነ መንገድ ከዚህ ሰማይ ቤት ከሚሉት ቦታ መውጣት አለብኝ እያሉ ሲያስቡ ሰነበቱና ይህን ሃሳባቸውን የሚያካፍሉት ሚስጥር ጠባቂ ጓደኛ ማፈላለግ ለመጀመር ወሰኑ "ስንት የማይደፈር ነገር የደፈርኩ ነኝ " አሉ ለራሳቸው ይህን ከሰማይ ቤት የማምለጥ ዘመቻ ሊደግፍ የሚችል ኢትዮጲያዊ ሟች ለመፈለግ የመጀመሪያ ምርጫቸው የቀድሞ ታጋዮች መንደር ነበር ለራሳቸውም በማያውቁት ምክንያት የቀድሞ ታጋዮችን ማግኘት ያስፈራቸዋል በእርግጥ ብዙ ወዳጆቻቸው እንዳሉ ቢያውቁም በምድር የነበረው አንዳነድ የፖለቲካ ሽኩቻና መጠላለፉፉ ቅሬታ ያሳደረባቸው ታጋዮች ሊኖሩም ይችላሉ ።

ሰማይ ቤት ነገሮችን በመነጋገር መፍታት ከባድ ነው ኢትዮጲያ ውስጥ እያሉ "መነጋገር" ቀላል ነበር : ካመነ ያምናል ካላመነ አቶ መለስ ሁልጊዜም ልክ ይሆናሉ ! እዚህ ሰማይ ቤት ግን ማሳመን ካልቻልክ ማመን አለብህ !! ለማሳመን ደግሞ የመናገር ጥበብ ሳይሆን እውነት ብቻ ነው መንገዱ ቢሆንም ታጋዮችን ማሳመንና በእርሳቸው መስመር ማሰለፍ አማራጭ የሌለው ምርጫ ሆነባቸው ለአቶ መለስ።

*******************************************

የታጋዮች መንደር ሲደርሱ ያጋጠማቸው ነገር ግራ አጋባቸው ፡፡ “እንኳን ሲታገል የሞተው ታጋይ ድፍን የትግራይ ህዝብ ቢቆጠር ይህን ያህል ቁጥር ይኖረዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል” አሉ አቶ መለስ የሚርመሰመሰው ህዝብ ብዛት ተገርመው፡፡ ”የኔን መምጣት የሰሙ ታጋዮች ሰማይ ቤቷን በደስታና በጭፈራ ቀውጢ ያደርጓታል” ብለው ያሰቡት አቶ መለስ ረጋ ባለና ግርማ ሞገስ ባለው እርምጃ ወደአንድ ትልቅ አዳራሽ ገቡ ፊት ለፊት ትልቁን የካራንቡላ ጠረንጴዛ ከበው የሞቀ ጨዋታ የሚመለከቱ በርካታ ታጋዮች አቶ መለስን ከመጤፍም አልቆጠሯቸው አላዩኝም ማለት ነው ብለው ያሰቡት መለስ ጉሮሯቸውን ጠራረጉ እህ አህህህህ ማንም ዞሮ አላያቸውም !! ተበሳጩና “ ምድረ ቁማርተኛ” አሉ በውስጣቸው!!

በሰወቹ መሃል በውልብታ ሲመለከቱ ሃየሎም የካራሙቡላውን ድንጋይ ሊወረውር ሲያነጣጥር አዩ ሊጮሁ ምንም አልቀራቸው “ ትጋዳላይ ሰላም ናችሁ” አቶ መለስ ውስጣቸው እየፈራ ጮህ ብለው ተናገሩ!! ማንም ስላምታቸውን የመለሰ የለም! ፍርሃታቸው ወደ ስጋት ተቀየረ “ ታጋይ ሲሰዋ ደንቆሮ የሆናል እንዴ” ሲሉ አሰቡ!!

“ ሃየሎም” ቤቱን በሚያናጋ ድምፅ ተጣሩ ፡፡ መልስ የለም !!

“ ሙሴ” ዝም!! ወደፊት ተራመዱና የተሰበሰቡትን ታጋዮች ገፈታትረው ሃየሎም ፊተ በቁጣ ቆሙና

“ስማ ምን ይዘጋሃል? “ ሲሉ በብስጭት ጠየቁት ሃየሎም በሚያስፈራ እርጋታ እና ቅዝቅዝ ባለ ድምፅ

“እንጫወትበት ዘወር በልልን” አላቸው

“ ዞር በልልን? ሃየሎም መለስ እኮ ነኝ! እንዴት ነው እንደዚህ የምትናገረው ባክህ?”

ሃየሎም አቶ መለስን ከመናገር ይልቅ ከጎኑ ወደቆመው ተጋጣሚው ዞሮ “ ያንተ ተራ ነው ተጫዋት”አለው ፡፡ አቶ መለስ ሃየሎም ጋር ካራንቡላ የሚጫወተውን ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከቱት ”.የሃየሎም ገዳይ” ተብሎ በምድር ሞት የተፈረደበት ሰው ነበር! የሰማይ ቤት ነገር ግራ አጋባቸው !! “ በሬ ካራጁ” ብለው ተረቱ!! በመቀጠልም ታጋዮቹን ሁሉ ተራ በተራ ካዩ በኋላ “እስቲ እንነጋገር ምንድን ነው በውስጣችን ያለው ቅሬታ ምንድነው ያሳዘነን ነገር በትግል ባህላችን በግልፅ እንወያይ የእናንተን የነፃነት ችቦ ተቀብሎ 21 አመት ሙሉ ሲለፋ ሲደክም ለኖረ ጓዳችሁ ይሄ ነበር የሚገባው አቀባበል?.” እያሉ በተለሳለሰ አነጋገር ግኡዝ የሆኑት ታጋዮች ላይ እስትንፋስ ሊዘሩባቸው ጣሩ! ወይ ፍንክች!! ዝምታ ብቻ!! ቀጠሉ መለስ “ የሞታችሁለት ህዝብ የታገላችሁለት ህዝብ ኑሮው ተቀይሮ በየቀኑ ያመሰግናችኋል ንፁህ ውሃ ሲጠጣ ያመሰግናችኋል፣ በቀን ሶስት ጊዜ ሲበላ፣ በነፃነት ሲናገር፣ በነፃነት የፈለገውን የፖለቲካ ፓርቲ ሲመርጥ፣ያስታውሳችኋል የሞታችሁለት የኢትዮጲያ ህዝብ!!”

ዝም!! ሃየሎም ዝም ! ሙሴ ዝም! ስበሃት ገ/እግዚአብሄር ትዝ አላቸው መለስ እነአብርሃም እነማቱሳላ ጠጡ ካቲካላ ለማንም ምንም አላሉም ጠጥተውም ዝም ዝምምምምም!! እነሙሴ እነማርታ እነሃየሎም ሲጫወቱ ካራምቡላ እየጠጡ ካቲካላ ዝምምምም!! አቶ መለስ ቀጠሉ “ የአፈናና የዝምታን ቀንበር በደማችሁ የሰበራችሁ እናንተ እንዴት በባርነት እንደተያዘ ህዝብ ዝም ትላላችሁ?” ዝም ! ቄሱም ዝም መፀሃፉም ዝም !!

አቶ መለስ የሚያደርጉት አጡ ዝም ብለው ሃየሎምን አዩት፡፡ የሃየሎም ፊት የሞናሊዛን ፊት የሚያስንቅ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት እየተነበበት ፊታቸው ቁሟል “ስላም ዋሉ” ብለው ውልቅ አሉ አቶ መለስ ፡፡ ማመን ግን አልቻሉም ”እንዴ የህወሃት ጉባኤ ላይ ለመናገር እድል ይሰጠን ብለው እጃቸውን እንደጭራሮ የሚያንጨፈርሩ ታጋዮች ምን ነካን ብለው ነው ወይ ጉድ “ ከታጋዮች ሰፈር ወጥተው ወደነገስታት ሰፈር የሚየስኬደውን ረዥም ጎዳና እያዩ ወገባቸውን ይዘው ቆሙ ትእይንቱ አሳዛኝ ነበር ፡፡ አራት ኪሎ ናፈቃቸው ፣ፓርላማው ናፈቃቸው ፣ አዲስ አበባ ናፈቀቻቸው ሁሉም ቦታ ሁሉም አለም ናፈቃቸው ከሰማይ ቤት ውጭ!! ከዚህ እስራት ለመውጣት ሰው ማፈላለግ አለባቸው ” እንደውም ሰማይ ቤትን ሰብሮ ለመውጣት የሰማይ ቤትን መነሻና መድረሻ የሚተነትን መፀሃፍ ማግኘት አለብኝ” አሉና ጉዟቸውን ወደደራሲያን መንደር አደረጉ!! የስብሃት ግጥም በአይምሯቸው እየተብላላች

እነአብርሃም እነማቱሳላ ጠጡ ካቲካላ

ለማንም ምንም አላሉም

ዝም ዝምምምምምም!!

ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባም

.ዝምታ ወርቅ ነው

ዝም አይነቅዝም

" ነቀዝ ሁሉ" አሉ አቶ መለስ ምድርና ሰማይን የሚያናጋ በሚመስል ድምፅ

## ክፍል 7

አቶ መለስ ስብሃት ጋር ሲገኛኙ ከረባታቸው ተጣሞ አይናቸው ላይ ድካም በግልፅ እየታየና ከወትሮው ትንሽ እርጅና የተጫናቸው መስለው ነበር። ወደቤት ጎራ ሲሉ ስብሃት ብቻውን ተቀምጦ መፀሃፍ እያነበበ ነበር ያገኙት ቀና ብሎ አያቸውና

" ውዳጀ ምነው ጠፋህ ግባ ና እስቲ እዚህ ጋር አረፍ በል" አሉ የተቀመጡበትን ምቹ ፍራሽ በእጃቸው መታ መታ እደረጉ

" ሰው ሁሉ የት ሂዶ ነው ብቻህን " አሉ ከስብሃት ጎን እየተቀመጡ

" ያው በየፊናው ዘምቷል ይመጣሉ እሽ እንዴት ይዞሃልሳ ይሄ አለም ለመድከው "

አቶ መለስ በረዥሙ ተነፈሱና ዝም አሉ

" ምነው ችግር አለ እንዴ"

" ስብሃት አንድ ጉዳይ ላማክርህ ነው የመጣሁት ለጊዜው በእኔና አንተ መሃል የሚቀር ጉዳይ ነው"

"እንስማዋ " ስብሃት የመለስን መጨናነቅ ሲያዩ የያዙትን መፅሃፍ ወደጎን ወርወር አደረጉና ለመስማት ተዘጋጁ። መለስ ቀጠሉ " ሰማይ ቤት አልተመቸኝም፣ ነገስታቱ በክፉ አይን ነው የሚያዩኝ መነገድ ላይ የሚያየኝ ሁሉ በክፉ አይን ነው የሚያየኝ በዛ ላይ ይሄ አለም እጅግ በጣም ይሰለቻል " እየሰመዋቸው መሆኑን ወሬያቸውን ቆም አደረጉ "ቀጥል እየሰማሁ ነው " አሉ ስብሃት ፂማቸውን እየላጉ። መለስ ደስ አላቸው ። ተረጋግቶ የሚሰማቸው ሰው ከሞቱ ጀምሮ አላገኙም ነበር። ቀጠሉ ታጋዮቹ ጋር ያጋጠማቸውንም ካጫወታቸው በኋላ ".. እና እንደነገርኩህ ይሰለቻል ስለዚህ በሆነ መንገድ ከዚህ ልጠፋ አስቤያለሁ የሚያስከፍለኝን መሰዋትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ ነኝ" ስብሃት በግርምት መለስን እያዩ

"አምልጠህ የት ልትሄድ " ሲሉ ጠየቁ

" የትስ ቢሆን ብቻ ከሰማይ ቤት ልወጣ"!! አሉ በምሬት!! ስብሃት በዝምታ ሲያስቡ ቆዩና

"ይሄን ጉዳይ ከሰአት በአሉ ግርማ ይምጣና አብረን እናውራበት እሱ አብዮት ነክ ነገር ላይ ከኔ የተሸለ ሳይሆን አይቀርም"

" እንዴ ምን ነካህ ሚስጥር ነው እያልኩህ ለበአሉ" በድንጋጠየ ጮሁ መለስ

"ተው እንጅ መለስ! እኔን ለምን አመንከኝ"

" አንት ያው"

" ያው ትግሬ ስለሆንኩ ያው የአድዋ ሰው ስለሆንኩ.ትንሽ የማልወድልህ እች ሳብ የምታደርግህን የጎጥ ስሜት ነው "

" ኖ ኖ ! እንደዛ አስቤ አልነበረም ግን ብዙ ሰው በሰማ ቁጥር ሚስጥርነቱ"

" እሽ ! አሁን የምልህን ስማኝ ሃሳብህን ወድጄታለሁ እኔም ሰማይ ቤት ሰልችቶኛል አሁኑ አራት ኪሎ ቢጥሉኝ ደስታውን አልችለውም ሞት እንከዋን የሌለበት አገር ፣አምሮት የሌለበት አገር ፣ህመም የሌለበት አገር ባክህ ሃሳብህ የማትገኝ ናት እሳት እኮ ነሽ! ምድር ላይ እዛ አዚማም ግቢ ተቀብረሽ እድሜሽን ፈጀሽ እንጅ ለማንኛውም በአሉን በኔ ይሁንብህ እመነው " አሉ ስብሃት በደስታ አይናቸው እያበራ በመጨረሻም " ሽርክ" ብለው ትንሿን ጣታቸውን ለመለስ ላኩለት አቶ መለስ ሳቁ ! ጣታቸውን ልከው አቆላለፉና የየራሳቸውን ጣቶች ሳሙ!!

" ሚስጥር ልንገርህ እዚህ ቆ ንጆ ጫት አለች። ልጅ እያሱ ነው አፈላልጎ ያገኛት አንዲት የሃረር ቆንጆ ወዳጁ ናት የምታመጣለት ለኛም ይተርፋል ከሰአት እሷን እየነከስን አቢዮታችንን እንቀምራታለን" አሉ በሹክሹክታ።

" ከምርህ ነው ሰማይ ቤት ጫት"

"ታዲያስ " አሉ ስብሃት በኩራት!!

" የምልህ ጠ/ሚንስትር ሲመረቅን እንዴት ነው ደራሲ ሲመረቅን ወደ ብሩ ነው አንተ መቸስ ወደጠመንጃ ሊሆን አይችልም ሃሃሃሃሃ"

" ባክህ እኔ ብዙ አልቅምም ነበር ያው አንዳንዴ ስራ ሲብዛ እንዲሁ " አሉ አቶ መለስ እየሳቁ..

"እመቤታችንን አልከተብካትም "

"ማንን"

" የተከበሩ ወ/ሮ አዜብን ነዋ.." ሁለቱም ሳቅ በሳቅ ሆኑ "

" ባክህ እሷ እንዲህ አይነት ነገር አይመቻትም እንደውም ትቆጣለች አንዴ እንዲሁ ነከስ አድርጌ እያነበብኩ መጣች አ በል አለችኝ እሳት ለብሳ እሳት ጎርሳ " እነዴ አዜ እያነበብኩ እኮ ነው አትረብሽኝ እንጅ " ብየ ላጭበረብር ብሞክር ወይ ፍንክች ከዛ በፊት ላልቅም ቃል ገብቸላት ነበር "

"እሽ" አሉ ስብሃት ፊታቸው ሁሉ ሳቅ ሁኖ

" ከዛ ምን እንዳልከዋት ረሳሁት ብቻ እንደምንም አሳምኛት አንድ ሁለት ቅጠል አጎረስከዋት ቆይቶ ጨመርኩላት "

"አንድ ያጣላል ብለህ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ" አሉ ስብሃት

" ከዛ ማን ይቻላት አስማት የሆኑ ሃሳቦች ታጎርፍ ጀመር እንደውም" ኢፈርትን ለምን እኔ አልመራውም መሌ " ብላኝ አረፈች ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ"

"እሽ " ስብሃት እንባቸውን እየጠረጉ ወሬውን እንዲጨርስላቸው ለመኑት

" ኧረ አዜ ተረጋጊ ኢፈርት እኮ በጣም የተመሰቃቀለ በሙስናና በአቦይ ስበሃት ቤተሰቦች የተጨማለቀ ቤት ነው አልኳት እሽ ወርቅነህ ገበየሁን አባር እና እኔን የፌዴራል ፖሊስ አዛዥ አድርገኝ" ስትል በቃ እንደመረቀነች ገባኝ አዜ እራት ልጋብዝሽ ብየ ይዣት ወጣሁ ሲነፍስባት ተረጋጋች ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አይ አዜ ሚስኪን እኮ ነች" አሉ አቶ መለስ አይናቸው ላይ ናፍቆት እየታየ ስብሃት የመለስን ትከሻ መታ መታ እያደረጉ " አይዞን አብዮታችንን አሳክተን ኢትዮጲያ እንገባለን ኢንሻ አላህ!! "

# ክፍል 8

ከሰአት በኋላ ልጅ እያሱ ጫት ከምታመጣለት የሃረር ልጅ ጋር ሊያስተዋውቃቸው መለስንና ስብሃትን ይዟቸው ሔደ!! ልጅቱ ቤት ሲደርሱ ቀድመዋቸው የደረሱ አንድ ሁለት ሰወች ነበሩ ! አንዱ አቶ መለስን ሲያይ “ አጅሬው በመጨረሻ ተገናኘን “አለ ነገር ፍለጋ በሚመስል አነጋገር ። ይሄ አረብ የሚመስል ሰው አቶ መለስን ጠጋ ብሎ “ ስማ አባይን መገደብ የማይታሰብ ነገር ነው እኛ ግብፃዊያን በአባይ የመጣብንን ችላ ብለን አናልፈውም ታሪክ አንብብ” አላቸው ልጅ እያሱ “ አቦ አትወግመና አባይ ምናምን እኛ የመጣነው ጫት ልንገዛ ነው “ አለው! ሰውየው ነዝናዛ ቢጤ ነው አቶ መለስን “ የግብፅ ህዝብ በህልውናው አይደራደርም እንኳን የውጭ ጠላት ደፍሮን አይተሃል ሙባረክን 18 ቀን ሙሉ ታህሪር አደባባይ ላይ ሳንበላ ሳንጠጣ እንደገለበጥነው “እያለ ይደነፋ ጀመረ.

አቶ መለስ “ 18 ቀን ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ እኛ የኢትዮጲያ ህዝቦች 5 አመት ሳናቋርጥ የኢጣሊያን ፋሽስት ድራሹን አጥፍተነዋል እኛ የኢትዮጲያ ህዝቦች ሳንበላ ሳንጠጣ 17 አመት ተዋግተን ደርግን አስወግደነዋል 18 ቀን ይላል እንዴ. ሃሃሃሃሃሃ” ግብፃዊው ተሸማቀቀ። አገሩ ላይ ለስራ የሚሄዱ ኢትዮጲያዊያንን እንዳሻው የሚናገር የግብፅ አርሶ አደር “ ከአገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ “ እያሉ ዝም ይሉት ስለነበር እንዲህ አይነት ኢትዮጲያዊ ይገጥመኛል ብሎ አላሰበም ነበር

“ እና አባይን ልትገድቡት ነው” አለ እንባ እየተናነቀው

“ግጥም አድርገን “ አለ ልጅ እያሱ ስብሃትና መለስ በሳቅ አውካኩ በመጨረሻም ለግብፃዊው የጫቱን ሂሳብ ከፍለውለት እየተሳሳቁ ወደሰፈራቸው ተመለሱ!!

*************** ****************************** ********

መለስ ፣ስብሃት፣ በአሉ ግርማ እና ልጅ እያሱ በአቶ መለስ አጀንዳ ላይ ለመነጋገር አንዲት ጨለምለም ያለች ጥግ ላይ ተቀምጠዋል ይሄ ሁኔታ አቶ መለስን የመጀመሪያውን የህወሃት ጉባኤ አስታወሳቸው ውስጣቸው በትግል እና በአቢዮት ስሜት ተሞላ። በዛ ላይ የገዘዋትን ጫት ሲጀምሩ በቃ ነገሩ ሁሉ ተገላለጠላቸው።. ሰማይ ቤት በአቢዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ መመራት አለበት ሲሉ አሰቡ! ከሰማይ ቤት ማምለጥ ብቻ ሳይሆን መላውን ጭቁኑን የሰማይ ቤት ህዝብ ከዚህ የአፈና ስርአት ነፃ ማውጣት አማራቸው እናም የእለቱን አጀንዳ ደራሲ ስብሃት ከፈቱት

“ በአሉ እንዲሁም እያሱ ወንድማችን መለስ አንዲት ሃሳብ ተከስታለታለች እናንተ ጋር እንመካከርባት ብለን ነው ”አሉ

“ ምን ችግር አለው እንነጋገርበታ“ አለ በአሉ በእርጋታ ስብሃት ከገነት ስለማምለጥ መለስ ያወረዋቸውን በዝርዝር ከተናገሩ በኋላ “ የሚጨመር ካለ መለስ ተናገር”

“ ሁሉንም ነገር በሚገባ ገልፀኸዋል

አሁን ደግሞ ምን አሰብኩ ብቻችንን ከምናመልጥ ለምን እዚህ ያለውን ስርአት አንቀይረውም “ በአሉ ከትከት ብሎ ሳቀና “ወይ መመሳሰል !” አለ

“ ማን ጋር ?” አሉ አቶ መለስ ይሄን ሃሳብ ቀድሞኝ ያሰበ ይኖር ይሆን ብለው

“ሳጥናኤል ጋር ነዋ!!

እሱም ወደምድር ከመወርወሩ በፊት ልክ እንዳንተ ነበር ያሰበው ሃሃሃሃሃሃሃ”በአሉ ሳቁን ማቆም አልቻለም!!

“ ሳጥናኤል ሰይጣኑ? “ አቶ መለስ በግርምት ጠየቁ

“ ታዲያስ እሱ ነበር የእግዜር መንግስት ላይ አብዮት ያስነሳው ከዛ በኋላ ደግሞ ይሄው አንተ ተነሳህ ሃሃሃሃ “

“መቼ “ አቶ መለስ ጠየቁ በጉጉት

“ የዛሬ ብዙ ሚሊየን አመት አካባቢ” ካለ በኋላ የሳጥናኤልን አመፅ ይተርክላቸው ጀመረ

********************** ******************** *******************

ሳጥናኤል ለድፍን ሰማያዊ ግዛት የእግዜር ወኪል የግዜር ጋራጅና አራጅ ሁኖ ተመርጦ ነበር ! ውበቱ ወንዳወንድነቱ ግረማ ሞገሱ ባጠቃላይ ሙሉ ሁኖ የተፈጠረ ማንም “የማይሳፈጠው” ታላቅ መለአክ ነበር !! እግዜርን ፊት ለፊት ማየት የተፈቀደለት ብቸኛ መለአክ !! እንግዲህ እግዚአብሔር ከፀሃይ 7 ሽ እጅ የደመቀ ስለነበር እሱን ቀጥ ብሎ ማየት የማይታሰብ ነው ወላ መለአከት ወላ ሌላው ፍጥረት ፈጣሪን ፊት ለፊት አየሁት የሚል አልነበረም ፡፡ ሳጥናኤል ግን አይቶታል ፡፡ የእግዜር ኪሩብ ነበር

እግዜር በችሎቱ ሲቀመጥ ሚሊን ቢሊየን ትሪሊየን ከዋትሪሊየን መለአከት በግንባሩ መሬት ላይ ተደፍቶ ቅዱስ ቅዱስ እያለ ይሰግዳል ሳጥናኤል ፊቱን ወደሰጋጁ መለአከት ጀርባውን ለእግዚአብሔር አድርጎ ከምድር ጥግ እስከጥግ የሚደርስ ክንፉን ዘርገቶ ይቆማል፡፡ የፈጣሪ ሃያል ብርሃን እንደጥቁር መነፀር ከፊቱ በቆመው ሳጥናኤል ክንፍ ውስጥ ያልፍና ሃይሉ ተቀንሶ ብርሃኑም ተለሳልሶ ለሌሎቹ ይታያል እንዲህ እየሆነ ብዙ ሚሊየን አመት እንደተቆጠረ አንድ ቀን ሳጥናኤል ክፉ ሃሳብ ሽው አለበት መለአከቱ ለኔ ነው ወይስ ከሀዋላየ ለቆመው ፈጣሪ የሚሰግዱት ሲል አሰበ!!

“ አይ ለኔ ነው ባይሆንም ለኔ መሆን አለበት “አለና በልቡ ያሰበውን ጩሆ ተናገረው

“ አዋጅ አዋጅ ከዛሬ ጀምሮ የምትሰግዱት ለኔ ለታላቁ ሳጥናኤል መሆኑን አውቃችሁ ስግደታችሁን አጠናክራችሁ ቀጥሉ” ሲል በታላቅ ድምፅ አንባረቀ፡፡ እግዚአብሄርም እስቲ ጉዱን ልየው ብሎ ዝም!! ግማሹ መለአክ ለሳጥኛኤል በግንባሩ ተደፋ ሚካኤል ግን “ ምናልክ አንተ “ ሲል በቁጣ ጮኸ!!

“ምንስ ብል ምን ያገባሃል ዝም ብለህ ስገድ “ ሲል ሳጥናኤል በትእቢት ተናገረ “እኮ ላማን ነው የምስግደው” አለ ሚካኤል ደሙ ፈልቶ “ ለኔ ለታላቁ ሳጥናኤል ነዋ”አለ ሳጥናኤል ከዛ በፊት ባልታየ ወደፊትም በማይታይ ትእቢት “አላደርገውም ለታለቁ ፈጣሪ ብቻ ነው የምሰግደው “

“ ከእኔ በላይ ታላቅ የለም”

“ እንዲህ ነኝና ሚካኤል “ ብሎ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ የእሳት ሰይፉን መዥረጥ ሲያደርገው ሳጥናኤልም አስፈሪ ሰይፉን መዘዘ እልፍ አእላፍ መላእክት ለሁለት ተከፈሉ ግማሹ ከሚካኤል ግማሹ ከሳጥናኤል ያሁሉ የእሳት ሰይፉን እያንቦገቦገ ተፋጠጠ እግዜር ጉዱን አያለሁ ብሎ ዝም!!!!!!

እነአብርሃ እነማቱሳላ ጠጡ ካቲካላ

እነሰይጦ እነሚኪ ተማዘዙ ሻሙላ

ለማንም ምንም አላሉም ጉዱ እስኪለይ ዝም ዝምምም!!

በዛ በኩል እነገብረኤል እነፋኑኤል የግዜር ጦር በዚህ በኩል እነኩሽካኩ እነማናኩ የሳጥናኤል ጦር ተጀጀመረ !! የሚካኤልና የሳጥናኤል ሰይፍ ሲጋጭ ፀኃይ ተፈነካከተች ፣ኮከቦች ረገፉ፣ ዘጠኝ ትናንሽ አለማት ተፈጠሩ ፣ ሰማይ ቤት ተደረማመሰ ፣ ምድረ መለአክ ተጠዛጠዘ.ድሉ ወደሳጥናኤል አደላ ከእልፉ እሩብ እልፍ በሰይፍ አለቀ ሳጥናኤል አሁን ሜርኩሪ የምንላትን ፕላኔት አንስቶ ሚካኤል ላይ ወረወረበት ለትንሽ ሳተው ሚካኤል በተራው ማርስን አንስቶ እንደአለሎ ወደሳጥናኤል ወረወረበት የቀራቸው ፕላኔት የለም ተወራወሩ!! የሚካኤል ጦር ተዳከመ ከዛ ሁሉ መለአክ ጥቂት ቀሩ የሳጥናኤል ጦር ግን የመፋለም ወኔው እየጨመረ ጭራሽ እነሚካኤልን መክበብ ጀመረ በመጨረሻ ሚካኤል ጦሩን ሊያይ ዞር ባለበት ቅፅበት የሳጥናኤል ክንድ አረፈበትና ወደቀ!! ሳጥናኤል

በፍፁም ትእቢት ሚካኤልን ቁልቁል እያየ ሰይፉን ከፍፍፍፍፍ አደረገና በሚካኤል ልብ ትክክል ቁልቁል ሊሰካበት ሲያነጣጥር ሚካኤል የቀኝ ክንፉን ለመነሳት ዘረጋ

በዚች ቅፅበት ሚካኤል ክንፉ ላይ በደማቅ ቀይ ቀለም የተፃፈው የፈጣሪ ስም የሳጥናኤልን ሰይፍ እጁ ላይ አሟሟው። አይኑ ጨለማ ጉልበቱ ቄጤማ ሆነበት ነገር ተገለባበጠ በቃ!! ሳጥናኤል የፊጥኝ ተጠፍሮ ቁልቁል ወደጨለማ ተጣለ ግብረአበሮቹ በምድር እንደትቢያ ተበተኑ እነጅኒ እነ መተት እነቡዳ." አለና በአሉ ግርማ ትረካውን ጨረሰ !!

አቶ መለስ በጥሞና ሲያዳምጡ ቆዩና " በጣም ጥሩ ሳጥናኤል የተሸነፈበትን ምክንያት ስንገመግም

1. ሳጥናኤል ህዝባዊ አልነበረም ሰራዊቱም የተሳሳተ መነሻ ይዞ ነበር የተዋጋው
2. ሳጥናኤል በቂ እና አሳማኝ ቅስቀሳ አላደረገም! ቅስቀሳው ቢደረግ ኖሮ በቀላሉ የቀሩትን መላእክት ከጎኑ ማሰለፍ ይችል ነበር
3. ባጠቃላይ የዚህ ጦርነት ጥሩ ጎን ቢሸነፍም ወደምድር ተወርውሯል ። እኛም የምንፈልገው ተወርውረንም ይሁን በክብር ተሸኝተን ወደምድር መመለስ ነው ስለዚህ በዚህ ጦርነት ተሸናፊ የለም"

" አለቻ ወኔ " አሉ ስብሃት!!

# ክፍል 9

ልጅ እያሱ በበአሉ ግርማ ትረካ በታም ተበሳጨ " ስለሳጥናኤል ይሄ ሁሉ ተረት እና ዝብዘባ ለምን አስፈለገ ወይ በአሉ " አለ። ስብሃት እያሱን እያየ " እንኳንም አብዮትን ከስር መሰረቷ አየናት በአሉ! የሆነስ ሆነና እች ሰማይ ቤት ተመችታሃለች "ሲሉ ጠየቁት በአሉ እግሩን ለማፍታታት ቆመና" በበኩሌ ተመቸኝም አልተመቸኝም ተመልሸ ወደኢትዮጲያ መሄድ አልፈልግም"

"ደርግ እኮ የለም ብትፈልግ እነደገና ኦሮማይን ብትፅፍ ዝንብህን እሽ የሚል የለም " አሉ አቶ መለስ በአሉን በአቢዮቱ ለማሳተፍ እየገፋፉት

" ሃሃሃ እሱን እንኳን ተወው መለስ የመፃፍ ነፃነት ሃሃሃሃሃሃ " አሉ ስብሃት

" ተው እንጅ ስብሃት ደግሞ አንተ ምንህ ተነካ ያሻህን ስትፅፍ ኑረህ በክብር አይደለም የሞትከው አሁን ማን ይሙት ኢትዮጲያ ውስጥ የመፃፍ ነፃነት የለም የምትልበት አፍ አለህ " አሉ አቶ መለስ በትዝብት ስብሃትን እያዩ። ስብሃት መለስን በግርምት እያዩ " እየውልህ መለስ !ደራሲ አንተ የምትሰጠውን የመፃፍ ነፃነት እንደምፅዋት አይጠብቅም ያሻውን ይፅፋል የድርሰት ቆሌው እንጅ ወላ የደርግ ወላ ያንተ በጎፍቃድ አይደለም ፃፍና አትፃፍ የሚለው" አሉ ለወትሮው ታይቶባቸው የማይታወቅ ቁጣ አይናቸው ላይ እየነደደ ቀጠል አረጉና " ቢበዛ ማሰርና መግደል ነው የሚችለው ባለስልጣን!!

ለዛውም ደራሲውን ብቻ ደራሲው የፈጠራቸው ገፀ ባህሪያት ግን ዘላለማዊ ናቸው ። አንተ የፈጠርካቸው ወታደሮች ይሞታሉ ይቆስላሉ አንተ የፈጠርካቸው ነጋዴወች ይከስራሉ ይነስራሉ አንተ የፈጠርካቸው ሞዴል አርሶ አደሮች ዝናብ ቢጠፋ ወንዝ ቢደርቅ ይደርቃሉ ኮፊዳቸውን ይዘው ከተማ ይገቡልሃል አንተ የፈጠርካቸው ዲያስፖራወች ፊትህ ቢጠቁርባቸው ጣጥለውህ ይሄዳሉ ወደመጡበት

የደራሲው ፍጡራን ግን ዘላለማዊ ናቸው ጉዱ ካሳን ጃንሆይ ምን አደረጉት ፀጋየ ፊያሜታ ምን ሆኑ ሰብለ በዛብህ ምን ሆኑ አየህ የገዥን ግፍ እየተናገሩ ጉድህን እየዘከዘኩ ያውም አገራቸው ላይ በክብር የሚኖሩ ፍጥረታትን ስለሚፈጥር ነው ደራሲን የምትፈራው " ስብሃት ተንተገተጉ መለስ የአቢዮቱ ነገር እንዳይበላሽ ነገሩን ለማለዘብ ፈለገ " በርግጥ ልክ ነህ ስብሃት ግን በአሉ በኢሃዴግ አገዛዝ ቢፈጠር እስካሁን የት ይደርስ ነበር "

" ቃሊቲ ነበራ የሚደርሰው ዘብጥያ "

"ትንሽ አጋነንከው ስብሃት "

" መለስ ትሰማኛለህ እያንዳንዱ አገዛዝ ጥሎበት ፊዳ የሚያደርገው ዜጋ አያጣም በተለይ ደራሲ እና ጋዜጠኛ ከመንግስት ጋር እሳትና ጭድ ናቸው። ሁነውም አይራራቁም በከፉም በደጉም! አንተም አስርሃል፣ ገርፈሃል፣ ገለህም ከሆነ ቀስ በቀስ እዚሁ እናገኛቸዋለን " አሉ ስብሃት ትክዝ ብለው !!

መለስ ስብሃትን በአትኩሮት እያየ "ይሄ ሰው ግን በእርግጥ የተወለደው አደዋ ነው እንዴ" ሲሉ አሰቡና

" እንደደርግ ግን በግፍ አንገድልም በዚህ እንተማመን " አሉ በአሉ አንድ ሁለት ጊዜ አሳለና

" ይቅርታ ስለደርግ ባናነሳ" አለ

"ለምን በግፍ ስለገደለህ አረመኔ ለምን አናነሳም ለምን አንወቅሰውም " አሉ አቶ መለስ ለበአሉ የተቆረቀሩ ይመስላሉ

" ምክንያቱም መንግስቱ እዚህ የለም በሌለበት ደግሞ ርእሳችን ሊሆን አይገባም " አለ በአሉ

" አንተ ሳጥናኤል በሌለበት ታሪኩን ስታወራልን አልነበር " መለስ ጠየቁ

" ሳጥናኤል እማ አለ ሃሃሃሃሃሃሃሃ"

"የታለ " አሉ መለስ ደንገጥ ብለው በአሉ ጥቂት የጫት ቅጠል ጠቀለለና

"ይህን የማጎርሰው እሱ ሳጥናኤል ነው" ብሎ ወደመለስ የጫት ጉርሻውን ዘረጋላቸው ቤቱ ባሳቅ ተሞላ መለስ የቅሬታ ፈገግታ ፊታቸው ላይ እየታየ ! ከቀልዱ ባሻገር በአሉ በአቢወቱ ሃሳብ መስማማቱ ቁልጭ ብሎ ታያቸው!! ጫቱን ተቀበሉት !!

" ለአቢዮቱ ስም ማውጣት አለብን " አለ ልጅ እያሱ መለስ ቀደም ብለው" እንግዲህ እዚህ ሁለት ሰው ከአድዋ አለ እኔና ስብሃት ! አድዋ ታሪካዊ የጥቁሮች ተምሳሌት ነው፣ አደዋ ባርነት ድል የተመታበት ቦታ ነው፣ አድዋ የማይቻል የሚመስል ገድል የተፈፀመበት ቦታ ነው "

" ባክህ ነገር አታንዛዛ ! ባጭሩ የአብዮቱ ስም ምን ይሁን "

አለ በአሉ መለስን እያየ

"ዘመቻ ሰማያዊት አድዋ" አቶ መለስ ባጭሩ መለሱ

"እስቲ ከተለመደው ነገር እንውጣ " አሉ ስብሃት " አድዋ ማይጨው ለምን ከጦርነት የራቀ ስም አንሰጠውም ለምሳሌ እእእ " ድንገት በር ተንኳኳ የገባውን ሰው መለስ አላወቁትም እነስብሃት ሞቅ ባለ ሰላምታ ተቀበሉት ስብሃት እንግዳውንና መለስን አስተዋወቋቸው " ዳኛቸው ወርቁ" አለ ድምፁ የታፈነ ይመስላል። በአሉ ድንገት ጮኸ " ለዘመቻው ስም ተገኘ በቃ ተገኘ "ዘመቻ አደፍርስ" ዳኛቸው አደፍርስን ተከራይተንሃል !! " አቶ መለስ ተበሳጩ እነዚህ ደራሲወች አፋቸው ሚስጥር አይቋጥርም ለመጣው ሁሉ ይሄን የሚያክል ከባድ ሚስጥር ይዘረግፉሉ ሲሉ በውስጣቸው ተማረሩ!! ዳኛቸው "ለመሆኑ የምን ዘመቻ ነው " አለ ስብሃት በአሉና ልጅ እያሱ እየተፈራረቁ አንዱ ካንዱ አፍ እየነጠቀ ለዳኛቸው ስለዘመቻው እየተሻሙ ሲነግሩት መለስ በግርምት ይመለከቱ ጀመር።

# ክፍል 10

ከቀኑ 67:30 ሰአት ላይ በሰማይ ቤት አቆጣጠር አቶ መለስ ከዋሉበት የደራሲወች መንደር እጆቻቸውን ኪስና ኪሳቸው አስገብተው " የማያልፉት የለም" የተባለውን ምድራዊ የትግል ዘፈን እያፈዋጩ ወደነገስታት መንደር እየተመለሱ ነው የነገስታት መንደር ደብሯቸዋል በትንሽ በትልቁ ንዝንዝና ጭቅጭቅ ይበዛል፣ ባንዲራ ላይ ለምን ኮከብ ተቀመጠ ብለው አጼ ቴውድሮስ መለስን ካኮረፉ አንድ ወር አለፋቸው ሚኒሊክም ቢሆኑ የሆዳቸውን በሆዳቸው መያዝ የሚችሉ ስለሆኑ እንጅ በባንዲራው ጉዳይ አቶ መለስ ላይ ሆዳቸው ሻክሯል ።

ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ " ካልጠፋ አንበሳ የኮከብ ያውም ወልጣ ቀኝ የሆነ ኮከብ ማስቀመጡን ምን አመጣው " ብለው ከአንገት በላይ ነው መለስን ሰላም የሚሉት። ልጅ እያሱ ብቻ የቤተሰቦቹ ችግር እንዳልገባው ህፃን እንዳሻው ይናገራል!! አጼ ይኋንስ በበኩላቸው ከመለስ እንዳይሆኑ ነገስታቱን በተለይ ቴውደሮስን ፈርተው ከነገስታቱ እንዳይሆኑ የመለስ ነገር እያሳዘናቸው መሃል ሰፋሪ ሁነው በዝምታ ከረሙ!! አቶ መለስ ወደነገስታት መንደር ሲሄዱ ወደሲኦል የሚወርዱ ነው የሚመስላቸው ቴውድሮስ ፊት ላይ የሚነደው እሳት፣ ሚኒሊክ ፊት ላይ የሚታየው ጥልቅ አስፈሪ ዝምታ፣ የሃይለ ስላሴ እንደ ዝናብ ፀሃይ ያለየለት ስሜት፣ የይኋንስ መጨናነቅ".ኤጭ ሰማይ ቤት ብሎ ነገር " አሉ መለስ ድንገት አጠገባቸው ሰው እንደነበረ ያዩት ከተናገሩ በኋላ ነበር።

አንድ ጎልማሳ ፀጉሩ ላይ ሽበት ጣል ያደረገበት አረማመዱ ግርማ ሞገስ ያለው የገጠር ሃብታም የሚመስል ሰው ከመለስ ኋላ እየተከተላቸው ነበር ። አቶ መለስ ብቻቸውን ሲያወሩ ስለሰማቸው እፍረት ቢጤ ተሰምቷቸው "ስላም ዋልክ " አሉት

"እግዚሃር ይመስገን እንደምን ዋሉ ጌታየ" አለ ሰውየው በፍፁም አክብሮት

" ትንሽ ሃሳብ ቢጤ ገብታኝ እኮ እንደ እብድ ብቻየን እያወራሁ "

" አይ ጌታው  ሃሳብ ምን ይፈይዳል ሁሉንስ ጣጥለነው መጥተን የለ ከእንግዲህ ማረፍ ነው እንጅ" አለ ሰውየው ጨዋታ አዋቂ ቢጤና ቀለል ያለ ሰው ነው።

"ሰማይ ቤት እንዴት ነው" አሉ መለስ ጨዋታ ለመክፈት ያህል " ምን ጥያቄ አለው መልካም ነው"

"አንዳንድ ሰወች ነፃነት የለም ዘላለማዊ እስራት ነው ይላሉ "

" እነማናቸውሳ እንዲያ የሚሉት ጌታው " መለስ ለመናገር እያቅማሙ " አንዳንድ ኢትዮጲያዊያን "

" ኸረ ወዴት ሂጀ ልሳቀው እናንተ ሆየ ሆሆ ድልዳል ሲሏት አመድ አሉ " አለና በሳቅ ፈረሰ ሰውየው

" ምን አሳቀህ "

" ነፃነት አጣን ያሉት ኢትዮጲያዊያን ናቸዋ የሚያስቁኝ ጌታው ሆሆ! አሁን ማን ይሙት "

"ቆይ አንተ ተመችቶሃል? ሌላው ቢቀር ሞት እንኳን የሌለበት አለም ዝም ብሎ መኖር ስልጣን የለ ትምርት የለ በዛ ላይ ንዝንዝ ከዚህ እሳት የሚንቀለቀልበት ትል የሚርመሰመስበት ሲኦል ይሻላል !"አሉ አቶ መለስ እሳቸው አብዮት እያሰቡ እንዲህ ስለሰማይ ቤት ምቾት የሚሰብክ ሰው በማግኘታቸው ተበሳጭተው " ሃሃሃሃሃ ለካስ እርሰዎም ኢትዮጲያዊ ነወት ሃሃሃሃሃሃሃ" ሰውየው ጭራሽ ሳቁ ባሰበት " ሳቅህ አልገባኝም ምንድነው የ የ የሚያስቅህ " አሉ ፡ ሊሉ የፈለጉት እንኳን "የሚያስገለፍጥህ" ነበር !!

" ሲኦል ሲሉ ጊዜ ነዋ ጌታው"

" ሲኦል ምኑ ያስቃል "

" ጌታየ ሲኦል እሳት ያለበት ትል የሚርመሰመስበት ማለት ምድር ላይ ቀረ ሲኦልንም ገነትንም ተሸክመናት ነው የምንኖረው እርሰወን የሚከተለወት የምድር ስራወት ነው እኔንም እንደዛው "

" ለመሆኑ አንተ የመጣሃው ከየት ነው " ሲሉ መለስ ሰውየውን ጠየቁት

"ከጎዣም"

" ጭራሽ ከጎጃም መጥተህ ነው ሲኦል የለም የምትለው "

" ሃዲያስ ጎዣሜ እውነት ቢናገር ምን ነውር አለው "

"ኧረ አንተ ሰው ነገር አጠምዝዝ ሃይማኖቱን ከሚያጠብቅ አገር ማለቴ ነው ፡፡ከሆነስ ሆነና ስራህ ምን ነበር ምድር ላይ ሰውየው ሳቅ እያለ

" ተቀዋሚ!!" ሲል መለሰ

" የምን ተቀዋሚ?" መለስ ደንገጥ ብለው ጠየቁ ጎጃሜ ተቀዋሚ በአይምሯቸው እያሰላሰሉ "ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ ልደቱ አያሌው፣ መራራም አሮሞ ነው ማን አለ ጎጃም "እያሉ ሲያወጡና ሲያወርዱ

"እኔ የምቃወመው ግፍና ጭቆናን ነው አንዱ የበታች አንዱ የበላይ አንዱ ታላቅ ዘር ሌላው ወራዳ ዘር ነው የሚሉትን "

" እኮ የየትኛው ፓርቲ አባል ነህ"

" ፓርቲ ደሞ ምንድን ነው ጌታው "

" ፓርቲ ማለት መሃበር ነው ፡፡የፖለቲካ መሃበር!! አንድ አይነት የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ሰወች ተሰብስበው የሚመሰርቱት"

" ሃዲያ ተመስርቶ ምን ይሰራል ይሄ ያሉት መሃበር እንደሰንበቴ ጠበል ጣዲቅ ያለ ነው"

" ገዥውን መንግስት ወይም የነገሰውን ንጉስ ሲሳሳት ይቃወማል ትክክል ሲስራ ይደግፋል ዋና አላማው በስልጣን ላይ ያለውን ገልብጦ ስልጣን መያዝና የተሻለ ነገር ለህዝብ መስራት ነው"

" አሀ ሃዲያ መንግስት ልገልብጥ ታለ ሽፍታ ነዋ ! የሽፍታ መሃበር አይሉኝም"

" እንደፈለክ በለው ዋናው ነገር አንተ ተደራጅተህ ነበር ወይስ እንዴት ነው"

"ጌታው እኔ የማንም አባል አይደለሁም የማይዋጥልኝን ለመቃወም ስብሰባ አልጠራም እዛው ፊት ለፊት ልኩን እነግረዋለሁ! ለዛ አይደለም ህዝቡ እብድ ጉድ ብሎ ያገለለኝ "

"ቆይ አንተ ማነህ"

" እኔማ ካሳ ዳምጤ ነኝ "ጉዱ ካሳ" አሉኝ ጉዳቸውን የዘከዘኩባቸው

" እችን ይወዳል መለስ! ሰው ጋር መስሎኝ የማወራው አንተ ልብ ወለድ ላይ ያለህ ገፀ ባህሪ አይደለህም እነዴ? እንዴት እዚህ መጣህ አሉ መለስ መንገዳቸውን አቁመው ጉዱ ካሳን እያዩት ?"

"ምድር ላይ በመጣፍም በሊቅ አፍም የተፈጠርን ገፀ ባህሪያት ለፍርድ ቀን መምከራችንን መዝከራችንነ ልንመሰክር እዚህ ህያው ሁነን እንኖራለን የደራሲወች መንደር ያሁሉ ሰው ደራሲ ብቻ ይመስለወታል ጌታው የለም የለም ደራሲ ከነፈጠረው ህዝብ ነው የሚመጣው፡፡ በሰማይ ቤት ደራሲ ምድር ላይ በፈጠራቸው ታጅቦ ሲኖር ነብሰ ገዳይ ምድር ላይ በገደላቸው ተከቦ በሰቆቃ ይኖራል ሲኦልም ገነትም ስራችን ነው ያልኩዎት ያንን ነው "

"አሁን የት እየሄድክ ነው ታዲያ;" አሉት መለስን

" እዚህ ላይ አንድ ወዳጅ አለኝ እሱ ጋር አምሽቸ ልመለስ ነው እንዴት ያለ ሰው መሰለወት ጌታው እንዲህ እንደርስዎ የተማረ ሊቅ ነው!! አነጋገሩ መቸስ ፍሬ ፍሬዋን ፍሬ ፍሬዋን ነው! ደፈረኝ አይበሉኝና ባስተዋውቀወ እንዴት መልካም መሰለውት" አለ እንግዳው አቶ መለስን ባክብሮት እየተመለከተ አቶ መለስ የማያውቁት ለዛውም

የልብ ወለድ ሰው ጋር ተከትለው መሄድ ባይፈልጉም በጊዜ ነገስታት ስፈር ሂደው ተፋጠው ከማምሸት ይሻለኛል በሚል ጉዱ ካሳ ጋር ወደተባለው ሰው ሰፈር አቀኑ በዛውም ለአብዮቱ የሚጠቅም ሰው አገኝ ይሆናል ሲሉም አሰቡ! እግዜሩም ተንኮል መሳይ ግጥጥሞሽ አቀናብሮ ጉዱን ማየት ሳያዝናናው አይቀርም እንዴት ማለት ጥሩ ነው ጉዱ ካሳ ከፊት እየመራ ያማረ መናፈሻ መሰል ግቢ ውስጥ ወደተሰሩ ቤቶች አቶ መለስን ወሰዳቸው ከቤቶቹ ወደ አንዱ ከደረሱ በኋላ ጉዱ ካሳ አንኳኳ አቤት አለ አንድ ለስለስ ያለ ድምፅ ተያይዘው እንደገቡ መለስ ፊታቸው የቆመውን ሰው ሲያዩ በድንጋጤ ደነዘዙ ! በምን ሂሳብ በየት በኩል በተቆጠረ ጉርብትና እንደተወዳጁ ባይገባቸውም እነሆ የጉዱ ካሳ ጓደኛ ፐ/ር አስራት ወልደየስ ሁነው መለስ ፊት ቁመዋል!! ይሄ ጉዱ ካሳ ጉድ ይስራውና ጉድ ውስጥ ከተተኝ ሲሉ አሰቡ በልባቸው። ፐ/ር አስራት እረጋ ባለ ድምፅ “ ግቡ አረፍ በሉ “ አሉ ፈገግ ብለው።

አቶ መለስ ግራ ገባቸው ይሄ ሰው አውቆኛል ወይስ እረስቶኝ ነው እያሉ በሩ አካባቢ ያለ ወንበር ላይ አረፍ ሊሉ ሲሉ “ ተዋወቅ እኒህ አስራተ ይባላሉ እኝህ መንገድ ላይ ተገናኝተን ነው እኔም ስማቸውን አላውቀውም ሃሃሃሃ” አለ ጉዱ ካሳ የአቶ መለስን ስም ያን ሁሉ መንገድ ሲመጡ አለመጠየቁ ገርሞት ፐ/ር ለትውውቅ እጃቸውን ከፈገግታ ጋር ሲዘረጉ መለስ እረስቶኛል ብለው እፎይ አሉና እጃቸውን ዘረጉ ፐ/ሩ ግን የዋዛ አልነበሩም ፈገግታ ከፊታቸው ሳይደበዝዝ “ አቶ መለስ እንኳን ደህና መጣህ “ አሉ ።

****************** ************************* ********************************

ፐ/ር አስራት አቶ መለስን በትዝብት እያዩ “ ኢትዮጲያ ደህናናት “ አሉ

“አዎ እንደድሮው እንዳትመስለወት መንገዱ መብራቱ ውሃው ኢንዳስትሪወች ብቻ በጣም ተለውጣለች”

“ ህዝቡን ምነው እረሳሃው ህዝቡ ደህና ነው” ፈገግ አሉ

“ ያው ለህዝቡ አይደል ሁሉስ ያው መንግስት ጋር ተባብሮ ድህነት ጋር ጦርነት ገጥሟል ጦርነቱ ሲፋፋም ነው ድንገት የመጣሁት”

“ ሃሃሃሃ አንተ ጦርነት ብዙ አትወድም ሲፋፋም ዞር ትላለህ ይሉ ነበር ድሮም”

“ያው የተፈፈጥሮ ጉዳይ ነው ! ሞት” አሉ አቶ መለስ የፐ/ር አሽሙር ገብቷቸዋል

“ እና አገር እየለማ ነው በለኛ”

“ አዎ ሆስፒታል ትላላቅ እርሻወች፣ የአየር ማረፊያ፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆቴሎች”

“ አቶ መለስ ይሄኮ መሪ ስትሆን ልትሰራው ሚገባህ ግዴታህ ነው እንደጀብዱ መንገድ ሰራሁ ውሃ ተከልኩ እያልክ ልታወራው አይገባም ታደያ ይሄን ካልሰራህ ምን ልትሰራ ኑረዋለ” አሉ አቶ አስራት አሁንም ፈገግ እያሉ “ትልልቅ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫወች፣ ባቡር፣ ኮንዶሚኒየም ቤቶች”

“ ኧረ በህግ አቶ መለስ ”

“.በብሄራዊ ስሜት ህዝቡ ተነቃንቆ በልማት ስራ ላይ በሰሰሰሰሰሰፊው”

“እንዴ አቶ መለስ እዚህ ግምገማ እያካሄድን አይደለም ዳግም ስለማንመለስባት እናት አገራችን በንስሃ ስሜት እያወራን ነው ህዝብን በብሄራዊ ስሜት ማነቃነቁ አይደለም ዋናው ቁም ነገር መሰረታዊ ብሄራዊ ጥቅምን ለእያንዳንዱ ብሄር ለእያንዳንዱ ግለሰብ እኩል ማዳረሱ ላይ ነው”

“ ይሄ እኮ ነው ችግርዎ ፐ/ር! አሁን ይሄ ዳር ዳር ገብቶኛል

“አማራው ተጎዳ ትግሬው ተጠቀመ “ የሚል የሰነበተ አጀንዳ ላይ ክርክር ሊከፍቱ ነው”

“ ሃሃሃሃ” የአቦየን ቅጠል የበላች ፍየል ያስለፈልፋታል አሉ” እኔ ስለዘር ስለጎሳ አይደለም ጥያቄየ ስለብሄራዊ ጥቅም ነው“

" አገራችን ደሃ ናት ከየት አምጥተን ነው እኩል የምናካፍለው "

" ያለውን በፍትሃዊነት ማካፈል ካልቻልክ ቢኖርህም አታካፍልም"

" ማን ተበደለ የትኛው ብሄር አድሎ ተፈፀመበት ሁሉም ቦታ መንገድ እየተሰራ ነው ልማት ሁሉም ክልሎች ላይ እየተስፋፋ ነው ርሃብ ድራሹ ጠፍቷል ቢበዛ ድርቅ ነው ያለው ስኳር ቀምሰው የማያውቁ ዛሬ ስኳር መቅመስ ጀምረዋል"

" ኤዲያ ላንች ብርቅሽ የዘንጋዳ ሙቅሽ" አሉ ስኳር ትላለህ እንዴ የኢትዮጲያ አርሶ አደር ከጓሮው ማር እየቆረጠ አላፊ አግዳሚውን ብሉልኝ ሲል የኖረ ነው ስከዋር አቀመስኩት እያልክ አዋጅ አትለፍፍ"

" ሁሉም ማር ሲበላ አልኖረም ፐ/ር ይሄ ጭፍን አድናቆት ድህነታችንን አይደብቅልንም"

" እኔስ ምናልኩህ ሁሉም ማር ስለማይበላ ማር አይተው የማያውቁትን ወደላይ ከማሳደግ ይልቅ ባለ ማሮቹን ወደታች ጎትቶ ስኳር እንዲቀምሱ ማስገደድን ልማት አትበለው ነውኮ የምልህ"

" ብሄሮች እንደሚሉት እንዳያድጉ የተደረገበት አጋጣሚ የለም ይሄ ተራ ወሬ ነው"

" ጥሩ ሲጀመር አንተ ለብሄሮች ማን ተከራካሪ አደረገህ ብሄሮች በሉ ጠጡ ብለህ አስተርገዋሚ አትሁን

ብሄር ያልካቸው እራሳቸው በላን ጠጣን ይበሉ ካድሬወችህ ጋዜጠኞችህ ህዝቡ እንዲያወራ ፋታ ይስጡት !! መንገድ ያልከው ነገር ተራ ጉዳይ ነው ማንም ኢትዮጲያዊ መንገድ በመሰራቱ አይከፋም ጥያቀው መንገዶቹ ወዴት ያመራሉ ማንስ ነው ባማረ መኪና ሽር ጉድ የሚልባቸው ነው "

" ህዝቡ ነዋ ማንም በተሰራው መንገድ እንዳትሄድ ያለው የለም " አሉ አቶ መለስ የፐ/ር አስራት አካሄድ አላምር ብለዋቸው

" ጥሩ የብሄሮች እኩልነት ማለት አንዱ ብሄር ጠግቦ ከበሮ ሲደልቅ ሌላው እንዲመለከተው ቴሌቪዥን ጣቢያወችን ማስፋፋት ነው ላንተ የአንዱ ጎተራ በእህል ሲሞላ የሌላው ያዛጋ የሁሉም ብሄር አባቶች እና አያቶች ደማቸውን ያፈሰሱባትን አገር አፊሴላዊ ጀግና ይሄንኛው ብሄር ብቻ ነው ብሎ በመአረግና በስልጣን ማንበሽበሽ ነው ለዛውም በችሎታ ሳይሆን አይን ባወጣ ዘረኝነት "

" አሃ! ፐ/ር አስራት! ደደቦች ናችሁ ካለችሎታችሁ ነው ስልጣኑን የያዛችት እያሉ መሰለኝ"

" በመሰረቱ አንድን ብሄር ደደብ ወይም ሙህር ነው ማለት አይቻልም። ይሁንና በርካታ ደደቦች ከአንድ ብሄር ሊወጡ ይችላሉ ምሁራንም እንደዛው ።

" የስልጣን ማማ ጫፍ ላይ የተቀመጠው የኔ ወገን ነው" በሚል ፅንፍ የለሽ ትምክት ከጠላ

ቤት እስከአለም አቀፍ መድረኮች የሚደነፉ የፍቅርና የአንድነት ፅዋ የሚደፉ መኖሩ እንደማይካድ ሁሉ ፤ ተጨቁኛለሁ ተገፍቻለሁ ብሎ ሳር ቅጠሉን የሚረግም ገፍቶኛል ያለውን ብሔር አልያም አገዛዝ ለማጥቃት አገርንም ደርቦ የሚያንቋሽሽ በምንም ነገር ላለመስማማት ከራሱ የተማማለ የሚመስልም ይኖራል። እነዚህ ሁለት አመለካከቶች ከዳርና ዳር አገራችንን እንደበሬ ቆዳ ገድግደው ከማስጨነቃቸውም በላይ ከኛ ያልሆነ ከሰይጣን ነው አዋጅ እያስነገሩ ስንቱን ሚስኪን ፍዳውን አብልተውታል!!"

" የሚሉት ነገር የድርጅትንና የአንድ ብሄር ስም ማጠልሸት ካልሆነ ሌላ ትርጉም አለው ማለት አልችልም"

"ሃሃሃሃ ኢትዮጲያ ውስጥ አንድ ብሄር እየመረጠ የሚወጣ ሎተሪ አለ እንዴ በግልፅ የሃብትና የስራ እድል እነማን እጅ እንዳለ አታውቅም መለስ ተው እንጂ ! አንተው እራስህ ልትቆጣጠራቸው ያልቻልካቸው ስንቶች ነበሩ "

" ስልጣን እና ሃብት ምን አገናኘው ለህዝብ ስላገለገልን ስማችን ይብጠለጠላል " አሉ አቶ መለስ ድምጻቸው ግን የወትሮው አልነበረም!!

" አየህ አቶ መለስ ስልጣን መጥፎ ነው !! ደሃ ስትሆን ድህነት ያሯሩጥሃል ባለስልጣን ስትሆን ግን ሃብት ያሳድደሃል፣ ብር ይከተለሃል ፣አዱኒያ እግርህ ስር ይልከሰከሳል!! ፈተናው ብዙ ነው ፈተናውን ከወደክ ብቻህን አትወድቅም ህዝብ ይዘህ ትወድቃለህ ያውም ያመነህን ባያምንህም የሚከተልህን።

ማንም ሳያየኝ ቆንጠር ላድርግ ብትል እንኳን ለመቆንጠር የላከው እጅህ ብር ብቻ ሳይሆን ስምና ክብርህን የህዝብ እምነትና ፍቅር የሚያቆሽሽ አቧራ ዘግኖ ይመለሳል! ወዲያው ህዝብ በየጓዳው ሲያስነጥስ ይሰማሃል እችን ጉንፋን በየትኛውም ማስተባበያ አታድበሰብሳትም የመነተፍከው የህዝብ ሃብት ባንክ አስቀምጠኸው ከሚያስገኝልህ ወለድ በላይ በህዝብ ሃሜት ከዋናው በላይ ይወልዳል እከሌ እዚህ ባንክ ይሄን ያህል ቢሊየን ብር ደብቋል ይለሃል አውርቶ ብቻ ዝም አይልም ደሃ ነህና ህዝብህን ለሆነ ጉዳይ " አዋጣ " ማለትህ አይቀርም ያኔ ይከፋዋል ህዝብህ ከምር ይከፋል!! ያዋጣው ገንዘብ የአንተ የብር ክምር ላይ ጠብ ሲል ይታይዋል ከዩኒቨርስቲ ሲመረቅ በገዛት ሱፍ ለዛውም ሱሪው የወየበ እየለበሰ ፋይል ጋር የሚኖረው ህዝብህ ይከፋዋል ግርጌው ቀበኛ እንደበላው ጨርቅ የተተፈተፈ ጅንስ ሱሪ

ለብሶ፣ በስንት መከራ ስራ ቢጤ ያገኘ ወጣት ይከፋዋል ማርና ወተት ምድርህ ላይ ይልከሰከሳል ያልከው ህዝብህ አንጀቱ በአምሮት አሲድ ሲያጎርፍ ይከፋዋል ልጆችህ መንገድ ላይ የተኳተረ ውሃ በሚያማምሩ መኪኖቻቸው ረጭተውበት የሚያልፉት ታክሲ ጠባቂ ህዝብህ ይከፋዋል የምትሄድበት መኪና ከውጭ ወደውስጥ ባያሳይም ህዝብህ ያይሃል ያውቀሃል!! አንተ ግን ከውስጥ ወደውጭ ህዝብህን እያየኸውም አታውቀውም አመፁን ተወው ትግሉን ተወው ዝም ብሎ የሰራሃውን ብትስራ እንደባእድ ዳር ቁሞ የሚያይህ ህዝብ እኮ ስታልፍ ስታገድም ርግማኑን ያልጎመጉማል!! "እየውልህ የእግዚአብሄር እጣ ፋንታ ህዝቡ ነው" ይላል የክርስቲያኖች መፅሃፍ ቅዱስ በየትኛውም እምነት ህዝብ የባለስልጣን ሳይሆን የፈጣሪ ሃብት ነው! ህዝብ ብረት አንስቶ ባይፋለምህ ከተማ ወጥቶ ባለስልጣን ባይሳደብ ይህ ህዝብ የቲም አይደለም ባለቤት አለው! ባለቤቱ የተነሳ ቀን ባለስልጣኖችህን እንዳሳማ አመድ ያስልሳቸዋል በህዝብ ገንዘብና ሃብት የሚሞላቀቁትን ሁሉ " ፕሮፌሰር ሳግ ተናነቃቸው እንባቸው በአይናቸው ሞላ

## ክፍል 11

ፕሮፌሰር አስራት ጥልቅ በሆነ ዝምታ ውስጥ ቆዩእና በትህትና " ይቅርታ እንግዲህ ወንድሜ ከወግና ከባህላችን አፈንግጬ እንግዳየን በመነትረኬ " አሉ አቶ መለስን ቅሬታ ባዘለ ፈገግታ እየተመለከቱ " ግድ የለም ፕ/ር ሃሳብዎትን በግልፅ በመናገረወ ተደስቻለሁ ፤በቀጣይ ለምናካሂደው የልማት ስራ ግብአት ይሆነናል" አሉ አቶ መለስ " ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ እንዴ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃ ይቅርታ በቀጣይ ነው ያልከው ? ሃሃሃሃ አንተ ሰው መሞትህን እስካሁን አላመንክም ማለት ነው? ሃሃሃ ለዘላለም ከዚህ ውልፍት ማለት የለም አቶ መለስ! አለቀ! ተከተተ! ቀጣይ የሚባል ታሪክ የለም " ፕ/ር ሳቃቸውን ማቆም አልቻሉም!! አቶ መለስ ወደ ፕ/ር አስራት ጠጋ አሉና " ፕ/ር! እኔና እርሰዎ የተለያየ አመለካከት፣ የተለያየ እሳቤና ባህሪ እንዳለን ግልፅ ፤ነው ግን በአንድ ነገር የምንስማማ ይመስለኛል እሱም ላመንበት ነገር ወደኋላ አንልም!! ምድርም ላይ እያለን ሁለታችንም እግራችንን ከተከልንበት የአመለካከት ድንበር ላይ መነቃነቅ አቅቶን ነው የሆነው ሁሉ የሆነው!! ገላጋይ አጥተን ሁሉም ድንጋይ የሚያቀብል "

" እስቲ ወደነጥብህ አቶ መለስ "

" ልነግረወት እኮ ነው ከዛ በፊት ግን ልጠይቀወት፣ አንድ እድል ተሰጥቶዎት ወደኢትዮጲያ ቢሄዱ ምን ያደርጋሉ ?"

" አሁን ኢትዮጲያ ላይ ገዡ ማነው? "

"ኢህዴግ "

"እንግዲያውስ መሄድ አልፈልግም !!"

"እሽ ሌላ መንግስት ነው እንበል" አሉ አቶ መለስ ሊያማትቡ

እየቃጣቸው

" ጥሩ አንተም ወደምድር ትመለሳለህ ወይስ ብቻየን ነው የምንሄደው? "

" ማለት በቃ እኔም እርሰዎም ምድር ላይ ብንመለስ "

" ጥሩ ሁለታችንም ብንመለስና ኢትዮጲያ "ፍትሃዊ በሆነ መንግስት" እየተዳደረች ብትጠብቀን ማለት ነው?"

"ትክክል!! " አሉ አቶ መለስ ለመልሱ ጓጉተው

" እንደዛ ቢሆንማ " አሉ ፐ/ር.. ፊታቸው በደስታ በርቶ አይኖቻቸውን ጨፍነው ሁለት እጆቻቸውን ወደሰማይ ዘርግተው

"እንደዛ ቢሆን የመጀመሪያ ስራየ እርሰወን ፍርድ ቤት መገተር ነበር!! ያው ፍርድ ቤቱ ለሰሩት ግፍና በደል ሞት ስለሚፈርድብዎ እርሰወ እኔን ሸኝተው ይመለሳሉ!! እኔ አገሬ ላይ ቀሪ እድሜን የናፈቅኹን ነፃነት እያጣጣምኩ ሁሉም በስራው ልክ የሚጠቀምባት አገሬን እንደጧት ፀሃይ እየሞኳት ወጣቶቿ ጥለዋት የማይፈረጥጡባትን አገሬን ጥጋበኛና ጉቦኛ አስመሳይና ዘረኛ ባለስልጣናት የማይፈነጩባትን አገሬን እያየሁ እውር ፍርድ ቤት አካለጎደሎ ዲሞክራሲ እጁ የሰለለ ህገ-መንግስት "ኮማ" ውስጥ የገባ የምርጫ ቦርድ ሳይሆን የፍትህ ክንዱ ግፈኞችን የሚደቁስ፣ እውነት ሳትወጣ መዶሻው ጠረንጴዛ የማይደቃ ፍርድ ቤት ያለባት አገሬን "ህዝብ ብሏል" የተባለለት ሳይሆን ህዝብ በትክክል ይሁን ያለው ህገ መንግስት ያለባት አገሬን በአንድ አይኑ የባለስልጣን ቁጣ በሌላኛው አይኑ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ እያየ የማይፈርድ ዳኛ ያለባት አገሬን እያየሁ በቃህ እስካለኝ እኖር ነበር!!" አሉና ግን ምን ያደርጋል ብለው ዝም አሉ አቶ መለስ ስለአቢዮታቸው እያሰቡ " በቃ ይሄው ነው ምኞትዎ ? "አሉ

" ሌላ ሌላ አዎ!! ሁልጊዜ እሁድ እሁድ የእርሰወን ባለስልጣናት ቃሊቲ እስር ቤት እየሄድኩ እጠይቃቸው ነበር። ሁሉም መታጎራቸው ስለማይቀር "

" ፐ/ር ሰማይ ቤት አስደስቶዎታል"

" በሚገባ! ማንም ሲገፋ አላይም ማንም ሲራብ አላይም ማንም ሲታሰር አላይም "

" ፐ/ር ሁላችንም እኮ እስረኛ ነን እንደውም የዘላለም ይሄ እንዴት አይታይዎትም"

"ሃሃሃሃሃሃሃ"

"ምን አሳቀዎት"

" እስር ያስጠላል አይደል "

" በጣም"

" ይሄንን ስታስፈፅም ነው የኖርከው !! በቂ ባልሆነ ምክንያት ስታስር ከኖርክ አንተንም ያሰረህ በቂ ምክንያት ያለው አይመስልህም"

" እኔ ማንንም ካለበቂ ምክንያት አላሰርኩም የማሰርም ስልጣን አልነበረኝም የአገርን ሰላም የአገርን ደህንነት የማስጠበቅ ህዝባዊ ሃላፊነት ነበረብኝ ። ህገ መንግስቱን የጣሰ ማንም ሰው ከየትም ይምጣ የትኛውም የትምህርት ደረጃ ይኑረው በሃገሪቱ ህግ ይዳኛል"

" የትኛውም ስልጣን ቢኖረውስ"

"እባክዎ ፐ/ር አያላግጡ እያወራን ያለነው ስለሃገር መሰለኝ"

"አአአአ ስለሃገር ሳይሆን ስለኢትዮጲያ ነው"

"ኢትዮጲያ አገር አይደለችም እንዴ"

" አገር ማለት ምድሯ ላይ የተወለዱ ሁሉ ንብረት ናት ካልን ኢትዮጲያ አገር ለመሆን ህዝብ ይቀራታል"

"ህዝቡ የት ሄደ ያውም በቋንቋ በባህል በታሪክ ሃብታም የሆነ ህዝብ ያላት አገር መሆኗን ማንም ይመሰክራል"

" ልክነህ ማንም ይመሰክራል ህዝቡ ራሱ ግን አይመሰክርም..ህዝቡ የለም እኮ ሸፍቷል አረብ አገር የሚሉት ጫካ ሴቱ ዘምቷል፣ ወንዱ "

" የሰው ልጅ የፈለገበት አገር ሂዶ የመስራትም ሆነ የመኖር ሰበአዊ መብቱ ሊከበር ይገባል "

"መብትን ተጠቅሞ በምርጫ መሄድ ሌላ በድህነት ካልቾ ተጠልዞ አገርን ጥሎ መሄድ ሌላ"

"ፐ/ር ለምን ሁሉን ነገር ያጨላልሙታል ለምን እኛ ላይ ሲደርስ ሌላ አገር ሂዶ መስራት ብርቅና ድንቅ ይሆናል ስንትና ስንት ህዝብ ካንዱ አገር ወደሌላው እየሄደ ይኖር የለም እንዴ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ቻይናውያን በመላው አለም አገራችንን ጨምሮ ተሰራጭተው እየሰሩ አይደለም እንዴ "

"አቶ መለስ ! ስለመሄድ አይደለም የማወራህ ሳይፈልጉ ስለመሄድ ነው !! ደግሞስ ከሌላው አለም ወደአገራቹንም ሆነ ወደ ሌላ ገር የሚሄዱ ዜጎች እንደኛ ተዋርደውና ሰበአዊ ክብራቸው ተረግጦ ነው እንዴ የሚኖሩት በታሪክ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጲያ ሂዶ የተዋረደ ሰው ያውቃሉ የነብዩን መልእክተኞች ተቀብላ አርዳና ጋርዳ ያኖረች አገር ልጆችዋ ከፎቅ እየተወረወሩ እንደሌባና ቀማኛ እየተሳደዱ ነው ዛሬ

የአገሬ ቄስ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት በእግሩ ሲንከራተት ስለእሙብርሃን እያለ በቁራሽ ርሃቡን እያስታገሰ ያገኘውን ቅስና እየናቅን አገሩ ላይ መክለፍት ሲያሳድድ የኖረ እዚህ ግባ

የማይባል የፈረንጅ ዲያቆን አገራችን ላይ በክብር የነገስታት አማካሪ ሁኖ ሲንደላቀቅ ነው የኖረው ! ወርቅ ቢያነጥፉላቸው ዞረው የማያዩ ሴት ልጆቻችን "ሰይጣንም ቢሆን አግብቶ ከዚች አገር ያውጣን " እያሉ አይደለም እንዴ "

" ይሄ ከግል ስነምግባር ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው "

"የቱ ነው ከግል ስነምግባር ጋር የተያያዘ ጉዳይ "

"የሴት እህቶቻችን"

" ምኑ ላይ ነው የስነምግባር ችግርነቱ "

" ሴትነትን የችግር መፍቻ ቁልፍ አድርጎ የመጠቀሙ አመለካከት ነዋ !! በየትኛውም አገዛዝ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለሴቶች መብት ታግለናል!! ሴቶች ላይ ተጭኖ የኖረው የባርነት ቀንበር ከባድ ከመሆኑ ብዛት ምንግስትና ህዝብ ተባብረው እንኳን ባንዴ ሊያወርዱት አልቻሉም። ሴቶችን ከወንዶች ጭቆና ቀርቶ ከራሳቸው "የአንችልም" እሳቤ ማላቀቅ ራሱን የቻለ ከባድ ስራ ነው!! ከጓዳ ወደትምህርት ቤት ወደ ስራ ብሎም ወደስልጣን እና ወደ ታላላቅ ሃላፊነቶች ሴቶችን ማምጣት ፈተና ነበር ለእኛ ። ቢሆንም ወደዚህ እስከመጣሁበት ጊዜ አበረታች የሆኑ ለውጦች አይተናል "

"አቶ መለስ"

"አቤት ፐ/ር "

“ ሰለቸኸኝ !! ”

“እንግዲያውስ ልሂድ” ብለው ከተቀመጡበት ተነሱ አቶ መለስ

“ ሰለቸኸኝ እንጅ ሂድ አላልኩም”

“ አይ እኔም እርስዎ ስለሰለቹኝ ብሄድ ይሻላል ብየ ነው” አሉ እልህ በሚመስል አነጋገር።

“ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ ኖ! ርእስ እንቀይር ማለት ነበር የእኔ ሃሳብ ሶሪ ስላስቀየምኩህ “

“ አሁን መሄድ አለብኝ !!! ባይሆን ሌላ ቀን እንገናኛለን “

“ ጥሩ ከመሄድህ በፊት ግን አንድ ነገር ልጠይቅህ ይሄ ሰማይ ቤት ነው እውነትን ደበቅን አልደበቅን ዋጋ የለውም እንዴው ከኢሃዴግ ባለስልጣናት በጣም የምትጠላው እና በጣም የምትወደዳቸውን ንገረኝ እስቲ” አቶ መለስ ጥያቄው አሳቃቸው ሳቁን እንደቀልድ ጀመሩትና የሆነ የሆነ ነገር ትዝ እያላቸው ሰማይ ቤት ከመጡ ጀምሮ ስቀው የማያውቁትን ሳቅ ሳቁ “ ሃሃሃሃሃሃሃ ሂሂሂሂሂ ”

## ክፍል 12

ባጭሩ ባለፈው ወጋችን ጠ/ሚንስትር መለስ ፐ/ር አስራት ጋር የሞቀ ክርክር አድርገው እንደነበር አውስተናል።

ቀጣዩ እነሆ በሰማይ ቤት ነገስታት የሚያርፉበት ቦታ ሌላው ተራ ህዝብ ከሚያርፍበት ቦታ ይለያል።

በሩ ላይ ክንፉ ከኮተቤ አቃቂ የሚደርስ መለአክ ጎርደድ ጎርደድ እያለ ይጠብቃል !! አቶ መለስ በዚህ ግቢ ለሁለት ወራት ሲኖሩ እንደፈለጉ ሲገቡና ሲወጡ አይተውት ስለማያውቁ ዛሬ እንደ ጀቢራ ፊታቸው ተገትሮ መንገድ ሲከለክላቸው ግራ ተጋቡ! ቀጥ ብለው አዩት ደራሲወች መንደር ውለው መሸት እስከሚል ድረስ ደግሞ ፐ/ር አስራት ጋር ቆይተው ገና መመለሳቸው ነበር!

“የምድራዊው ሙታን ጭቅጭቅ ሲገርመኝ መለአኩ ደግሞ ምን ፍጠር ይለኛል” አሉና ሲፈሩ ሲቸሩ “ጌታየ ችግር አለ” አሉት አይናገር አይጋገር ዝም!!

“እዚህ ውስጥ ነው የምኖረው መለስ እባላላሁ” ዝም!!

“ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ እኮ ነኝ” ዝም ! አልፈውት ሊሄዱ ሲሉ ክንፉን ዘረጋው እየተዘረጋ እየተዘረጋ አይናቸው ማየት እስኪችለው ድረስ ተዘርግቶ ጫፉ አድማስ ውስጥ ገባ አቶ መለስ

“የባቡር ሃዲድ በዚህ ፍጥነት ቢዘረጋ ” ብለው አሰቡና

“ ይቅርታ ይሄን ሁሉ ክንፍ የሚያዘረጋ ምን ችግር ችግር ተፈጠረ “ ሲሉ ጠየቁ ዝም!!

ስብሃት ገ/እግዚያብሔር ትዝ አሏቸው እነአብርሃም እነማቱሳላ ጠጡ ካቲካላ

ጠጥተውም ዝም ! ዝምምምምም እንደመለአኩ ክንፍ የረዘመ ዝምታ!!

“ ለምን አታሳልፈኝም ” ዝም!!

“የምድራዊት ኢትዮጲያ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ አስረስ እኮ ነኝ”

“ብትሆንስ?” አስገምጋሚው የመለአክ ድምፅ መለስን ወደኋላ አስፈነጠራቸው

“ እሱማ ብሆንም ዋጋ የለውም አልፏል” አሉ ነገሩን ለማረጋጋት

“ ባያልፍስ?” መለአኩ በበለጠ ድምፅ አስገመገመ

“ማለቴ ያው ቆይ ግን ለምንድነው እንዳልገባ የተከለከልኩት? “

“ጠ/ሚንስትር እዚህ አይገባም” አለ መለአኩ ባጭሩ

"እና ምኖች ናቸው የሚገቡት?”

“ነገስታት ብቻ”

“ እኛ አገር የምንተዳደረው በንጉስ ሳይሆን እንደ እንግሊዝ እንደ በቃ ንጉስ ልትለኝ ትችላለህ!! !የንጉሳዊ አገዛዝ በአገራችን ስለሌለ እንጅ ንጉስ ማለት ነኝ ያው”

“ አይመለከተኝም ንጉስ ብቻ ነው እዚህ የሚገባው “

“ እና አገር መሪ አይገባም ?”

“ይገባል! ሚንስትር ሚንስትሮች ጋር ነው “

“እኔኮ ሚንስትር አይደለሁም ለምን አትረዳኝም ጠቅላይ ነኝ ”

“ ጠቅላይ ምን”

“ሚንስትር”

“ሚንስትሮች ጋር ሂድ”

“ንጉስና አገር መሪ ምን አለያየው 21 አመት አገር መርቻለሁ”

“እኔም 21 አመት አገር መርቻለሁ” አለ መለአኩ 21 አመት አገር መምራት ብርቅ ነው እንዴ በሚል ድምፅ መለስ በጣም ተገርመው “የት ነው አንተ አገር የመረሃው ደግሞ እኔ በታሪክም በአካልም ሰምቸም አይቸም አላውቅም እንዳንተ አይነት ማለት ” አሉ ክንፉን እያዩ

“ ክንፌ ገርሞህ ነው ሃሃሃሃ! ምድር ላይ አገር መሪ የነበራችሁ ሁሉ በአይን ስለማይታይ እንጅ አንዳንዶቻችሁ ጭራ አንዳንዶቻችሁ ቀንድ አላችሁ በጣም አልፎ አልፎ ክንፍ ቢጤ ያላቸውም ነበሩ” አለ ቀልድ በሚመስል አነጋገር

“ ቆይ አንተ 21 አመት የመረሃው የትኛውን አገር ነው “ አሉ መለስ

“ኢትዮጲያን”

“ አ ኢትዮጲያ ኢትጲያ ምድር ላይ ያለችውን ኢትዮጲያ ”

“ አዎ”

“ ትቀልዳለህ”

“አልቀለድኩም” የተቆጣ መሰለ መለአኩ

“እና ኢትዮጲያን ከመቸ እስከመቸ መራሃት ”

“ ከ 1983 እስከ 2004”

“ይሄ ጊዜ እኮ እኔ ኢትዮጲያን የመራሁበት ነው”

“ አይግረምህ! ድፍን አፍሪካ እንደመሪወቿ ግፍና በደል ቢሆን ኖሮ እስካሁን አትኖርም ነበር፤ አንድ ገዥ ስልጣን ሲይዝ አንድ ሃያል መለአክ ህዝቡን ለመጠበቅ ይመደባል ምክንያቱም ህዝቡ ንብረትነቱ የታላቁ ፈጣሪ እንጅ የመሪው አይደለም ፡፡” አቶ መለስ በመለአኩ ንግግር ተበሳጩ

“ ተው እንጅ እና ነገስታቱ ህዝቡ፣ ሳር ቅጠሉ ፣የምትተነፍሱት አየር ሳይቀር የኛ ነው ሲሉ የት ነበራችሁ ህዝቡ የሚያመልከውን አምላክ ሳይቀር ነገስታቱ ሲመርጡለት የት ነበራችሁ ደርግ ያንን ሁሉ ህዝብ ሲያርደው የት ነበራችሁ ” አሉና አፈጠጡበት

“ ምነው አቆምከ ” አለ መለአኩ በትዝብት ፈገግ ብሎ

“ ሂትለር ያንን ሁሉ አይሁድ ”

“ቆይ ቆይ ከደርግ ቀጥሎ ሂትለር ነበር ኢትዮጲያ ላይ ገዥ የነበረው? ስለራስህ ተናገር”

“ እኔ ምን አደረኩ ? “

“ቅድም ያልካቸው ነገስታትም እኛ ምን አደረግን ነው የሚሉት ሂትለር እራሱ እንደዛ ነው የሚለው ”

“ያው 21 አመት ገዛሁ ካልክ በእኔ የስልጣን ዘመን ያየኸውን ስህተት ተናገር በእኔ ጊዜ ነው የሃይማኖት ነፃነት የተከበረው በእኔ ጊዜ ነው ሃይማኖትና መንግስት ተለያይቶ የየራሱን ጉዳይ ካለማንም ጣልቃ ገብነት ሲያከናውን የነበረው ለምን እንዳላየ ትሆናለህ ”

መለአኩ ፈገግ አለና

“ ባአንተ ጊዜ ነው ሞራል እና ስነ ምግባር የሂወት መንገድ መሆኑ ቀርቶ አንድ የትምህርት አይነት

ብቻ የሆነው ባንተ ጊዜ ነው ፖለቲካ የሚተነፍስ እየታነቀ ድራሹ ሲጠፋ መገናኛ ብዙሃኑ ሁሉ ስለዘሙት እናስተምር ብለው ዝሙት ህዝብ ውስጥ የዘሩት ባንተ ጊዜ ነው የወሲብ አብዮት ፈንድቶ ሴት ወንዱ በአሰቃቂ ጥልፍልፎሽ ውስጥ የወደቀው ትውልድ በዝሙት የተጥለቀለቀው ባንተ ጊዜ ነው

ግብረሰዶም ያቆጠቆጠው “

አቶ መለስ በውስጣቸው

“ ይሄ መለአክ የግንቦት 7 አባል ነው እንዴ “ ብለው አሰቡ

“ እና አሁን በሩን ትለቅልኛለህ ወይስ ልመለስ “

“ተመለስ”

“ እስካሁን እዚህ ስኖር ለምን አልተከለከልኩም”

“ ነገስታቱ አልከለከሉህም ነበር “

“እና አሁን ከለከሉ “

“ አዎ እንዳይመጣብን አሉ”

መለስ ቱግ አሉ እልሃቸው ውስጣቸው ተንተገተገ “ ስማ! ገደል ግቡ በላቸው ይሄ ተንኮልና ክፋታችሁ ነው አገራችንን ወደኋላ ያስቀራት ብሏችኋል በላቸው ፈሪ ቦቅቧቃ ናችሁ በላቸው ወላ አድዋ ወላ መቅደላ ትላላችሁ እንጅ እውነት ፊት ለሴከንድ መቆም የማትችሉ የተንኮል አባቶች ናችሁ በላቸው..”

አሉ በብስጭት እየተወራጩ

“እኔ ነገር አመላላሽ አይደለሁም”

“ እሽ አንዴ ፍቀድልኝና እራሴ ነግሪያቸው ልመለስ”

“ ጥፋ ከዚህ” መለአኩ ድፍን ሰማይ ቤትን የሚያናጋ በሚመስል ድምፅ አንባረቀ።

አቶ መለስ ቁጣቸው እንደዝንብ መንጋ ግርርር ብሎ ከላያቸው ላይ ሲሄድ ታወቃቸው ፡፡ “እንዳልክ” አሉ በማይሰማ ድምፅ ዙረው መንገዳቸውን ቀጠሉ!! ለረዥም ሰአት መናገርም ማሰብም ተስኗቸው እግሮቻቸውን ተከትለው ከተጓዙ በኋላ ድምፃቸውን ቀንሰው

“ ምን ያስደነፋዋል ታዲያ ፈጣሪ የሰጠውን ስልጣን በስርአት አይጠቀምም አምባ ገነን..” አሉና ወደኋላቸው ዞር ብለው ተገላመጡ ወዲያው ቀጥ ብለው ሲያዩ ዙሪያውን በንፁህ ውሃ የተከበበ ደሴት ከሩቁ ተመለከቱ ዳሩ ላይ አረፍ አሉና በትካዜ ደሴቱን እያዩ ውሃ በሆነ ሙታን ህዝብ ውሃ በሆነ አለም ውሃ

በሆነ መለአክ ውሃ በሆነ ፕሮፌሰር የተከበብኩ ደሴት ነኝ” አሉ!! የማያውቅት ስሜት ወደደሴቷ እንዲሄዱ ገፋፋቸው፡፡ ግን መንገድ የለውም ዙሪያውን ውሃ ነበር!! ከተቀመጡበት ተነስተው ሲንጎራደዱ ሁለት ሰወች ከኃላቸው መጥተው በቀጥታ ወደውሃው ሄዱ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ እየሳቁ ወደ ውሃው

ገቡ ! ውሃውን ያዩት አይመስልም አቶ መለስ ሊጮሁ ብለው ተውትና የሚገርመውን ተአምር ማየት ጀመሩ ሰወቹ በውሃው ላይ እየተራመዱ ወደደሴቱ ይገሰግሱ ጀመረ  አቶ መለስ ነገሩን ማመን አልቻሉም መሞከር እንዳለባቸው ወስነው ወደውሃው ተጠጉና ቀኝ እግራቸውን አስቀድመው ውሃውን ረገጥ አደረጉት እንደመሬት ጠንካራ ነው ደጋግመው ሞከሩና አንድ እግራቸውን አስከተሉ ቀስ በቀስ በድፍረት

በውሃው ላይ መራመድ ጀመሩ ከዛ ሶምሶማ በመጨረሻም እንደ እብድ እየሳቁ እሩጫ ጀመሩ፡፡

በውሃ ላይ መሮጥ እጅግ በጣም የሚያዝናና ነበር ሃሳባቸውን ሃዘናቸውን አስረሳቸው፡፡ “የኢትዮጳያ ህዝብ ይህንን ቢያይ ምን ይላል “ ሲሉ አሰቡ መጀመሪያ የኢሃዴግ ባለስልጣናት ሃሳቡ አዝናናቸው አባዱላ ገመዳ “ እሳቸው የጀመሩትን ” ብሎ ቢሸፍቱ ሃይቅ ውስጥ ሲዘፈዘፍ ታያቸው ሳሞራ ታንክ ይዠ

ካልተሸገርኩ ማለቱ አይቀርም ስዩም መስፍን ረጋ ብሎ ፊቱን በውሃ ውስጥ እያየ ሲያዘግም አዲሱ ለገሰ ጣናን እንዴት የእግር መንገድ ማድረግ ይቻላል ብሎ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በረከት ስምኦን ለቪኦኤ እንግሊዝኛው ክፍል “ለህዝብ ጥቅም እንኳን በውሃ ላይ በእሳት ውስጥ አልፈን ነው የመጣነው ምኑ

ነው የሚያስደንቀው “ ሲልም ታያቸው

.”.አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ምን ይል ይሆን “ “አሉና ሩጫቸውን አቁመው ማሰብ ጀመሩ

ምናልባት” የኢትዮጲያ ህዝብ ሆይ የተከበራችሁ ሴቶች ፣የተከበራችሁ ወንዶች የተከበራችሁ ተማሪወች ፣ የተከበራችሁ የንዳና ተዳዳሪወች የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ እኔና ፓርቲየ ግራ

ገብቶናል ክርስቶስም በውሃ ላይ ተራምደዋል መለስም ተራምደዋል ክርስቶስም ተከተሉኝ ብለዋል መለስም ተከተሉኝ ብለዋል ያም ስለኛ ተሰውቷል ይሄም ስለኛ ”

ተቀዋሚወችም ዝም አይሉም! ብርሃኑ ነጋ

“በውሃ ላይ መራመድ ስለቻልን ብቻ ትርፍ በሌለው ጉዞ እግራችን እስኪቀጥን መዳከር የለብንም”

ማለቱ አይቀርም ፡፡ አቶ ቡልቻ

“ይሄ ክርስቶስን መጋፋት ነው እንኳን አምላክን ተጋፍተን እንደውም የተገፋን ነን”

እያሉ አባታዊ ምክራቸውን ይሰጣሉ በየነ ጴጥሮስ

“ ጥያቀው እንዴት ወደደሴቱ ሄድን ሳይሆን ደሴቱ ላይ ምን አለ የሚለው ይመስለኛል ተረጋግተን ብናየው መልካም ነው”

ልደቱ አያሌው “ኢዴፓ የሚያምነው መራመድ ጥሩ ቢሆንም ይሄ የሚራመዱበት ውሃ እርስዎ እንዲራመዱበት ተብሎ ጠጣር ሲሆን በውስጡ ይኖሩ የነበሩ በርካታ አሶች ማለቃቸው ተገቢ

አይደለም ብሎ ነው ” ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር ደመቀ መኮነን “ታላቁ ጠቅላይ ሚንስትራችን በአፍሪካ የመጀመሪያ በአለም ሁለተኛ የሆነውንየውሃ ላይ ጉዞ በማድረጋቸው መላው የአማራ ህዝብ የተሰማውን ኩራት እየገለፀ ይህ ጉዟቸው እንዳይቋረጥ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጣና ሃይቅን ለክቡር ጠ/ሚንስትር መለስ በስጦታነት አበርክቷል!!” አርቲስት ሰራዊት ፍቅሬ

“ ውሃን እንደምንጣፍ ረግጦ ከልማት ወደልማት አገርን ያሻገረ በግርማ ሞገሱ ባህር ያሸበረ

በየብስ በባህር ያሰበበት የሚደርስ መለስ!!!”

እያለ በኢቲቪሞቅ ሲያደርገው ታያቸው ይሄን ይሄን እያሰቡ ደሴቱ መግቢያ ላይ ሲደርሱ የአረብ አገራት ነገስታት ሲሞቱ የሚገቡበት ደሴት መሆኑን በሩ ላይ በተለጠፈው ፅሁፍ አወቁ ወደውስጥ ሲገቡ ታላላቅ ቤተመንግስት የሚመሳስሉ ቤቶች ደሴቱን ሞልተውታል ወደ አንዱ ጠጋ ብለው ሲመለከቱ በሩ ላይ ማን እንደሚኖርበት የሚገልፅ ፅሁፍ ተለጥፎበታል። አንድ አምስት ቤቶችን እንዳለፉ ያዩት ፅሁፍ አስቆማቸው “ ኮሮኔል መአመር ጋዳፊ የምድራዊት ሊቢያ ንጉስ የነበሩ” ይላል ። መለስ በሩ ላይ ቁመው አሰቡ “ይሄ ነውጠኛ ሰውየ ስለአብዮቱ ባማከረው በደስታ ነው የሚፈነድቀው ስለዚህ ”

ብለው ወደውስጥ መግባት ጀመሩ!!

(ይቀጥላል።

# በአልጋው ትክክል

## ይህ ተከታታይ ወግ ሀያ ሁለት ክፍሎች አሉት

### ክፍል 1

በዛ ....ከምር በዛ ...!! እንዴ እግዜር በሚያውቀው እኔ ክፉ ነገር አስቤ ወይ የሱን ትዳር ለመበተን አስቤ ያደረኩት ነገር አይደለም ....በቃ በበጎነት በፍፁም ቅንነት ያደረኩት ነገር ነው ! እውነቴን ነው ...የሱ ትዳር ስለተበተነ እኔ ምን አገኛለሁ ?... ትዳሩስ ስለሞቀና ስለደመቀ ምን አጣለሁ ?... እንደው አንዳንዱ ሰው የሱ ተራ ጉዳይ ሳይቀር ማምሻውን በቢቢሲ የተዘገበ በአልጀዚራ ተሰራጭቶ አየሩን ሁሉ የሸፈነው ይመስል "አሁን አንተ ይሄን ነገር ሳትሰማ ቀርተህ ነው ????" ብሎ መቆነን ያምረዋል! ቁንን !! የሱን የጓዳ እንቶ ፈንቶ የምሰማው ምን ስለሆነ ነው አይ እዚህ ሰፈር አጉል ተናንቀናል እስቲ አሁን ማን ይሙት ጥፋቴ ምንድነው ምን አጠፋሁ? ....ባለፈው እሁድ ጧት እንቁላልና ዳቦ ገዝቸ (ለቁርስ) ከሱቅ ስመለስ ልክ ኮንዶሚኒየሙ ደረጃ ላይ አንዲት ቆንጆ ልጅ የወገቧ ቅጥነት የማይታይ መዳፍ ግራና ቀኝ ጨምቆ የያዛት የሚመስል.... በዛ ላይ ደግሞ ባየር ላይ የቆሙ የሚመሳሰሉ ትላልቅ ጡቶች ያላት እንደነገሩ በሻሽ ሸብ ያደረገችው ፀጉሯ ግማሹ ከሻሹ አምልጦ ትከሻዋ ላይ ጥቁር ሰርዶ መስሎ የሚዘናፈል...ትልቅ ሻንጣ እያንዘፋዘፈች ከብዷት ደረጃውን ስትወርድ ተገጣጠምን ...ደግሞ የአይኖቿ መተላለቅና ጥራት ..."ይችን የመሰለች ቆንጆ ከበላየ አድራ" ሲያቃዠኝ አለማደሩ ብል ማጋነን ይመስላል !

እውነቱን ለመናገር ከዚህ በፊት አይቻት እንኳን አላውቅም ! ሴት ልጅ ስትቸገር መርዳት ደንብ ነው ብየ .....እንቁላልና ዳቦየን የደረጃው ከፈፍ ግንብ ላይ አስቀመጥኩና (እንደውም አንዱ እንቁላል ተሰብሯል) ሻንጣዋን ይዠ ደረጃውን አወረድኩላት ...ፊት ለፊት ወደቆመው ታክሲም ሸኘኋት..... በዛ የንጋትት ኮከብ በሚመስሉ ውብ አይኖቿ አንዴ አይታኝ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ" ብላኝ ቁሞ በሚጠብቃት ላዳ ታክሲ ተሳፍራ ሄደች ...በቃ ይሄው ነው ! እኔ በህልሜም በውኔም እንዲህ ያለ ጉድ ይመጣብኛል ብየ በምን አባቴ አስቤ።

...ይች በጎነት መዘዟን መዘዘቻ ! ለካስ የሸኘኋት ቆንጆ አራተኛ ፎቅ ላይ የምትኖር ባለትዳር ነበረች! ወንድየ የሚባል ባል ያላት ! ማታ ባሏ ጋር ትጣላና ሻንጣዋን ይዛ ትወጣለች። ...ባል የሆነ ቡጥጥ ኩራተኛ ቢጤ ነው እሱን እንኳን በአይኔ አውቀዋለሁ የአገር ቁልፍ የተሰካበት የቁልፍ መያዣ እንደፅናፅል እያንሿሿ የሚወጣና የሚወርድ ጎልማሳ ነው ...እንደውም እኔ በፊት በፊት የብሎኩን ቤቶች ሁሉ ቁልፍ የሚይዝ ነበር የሚመስለኝ !

እና ይች ቆንጆ ሚስቱ በብስጭት ሻንጣዋን ይዛ እሄዳለሁ ስትል ..."ጥርግ በይ" ብሏት ጭራሽ ከነሻንጣዋ ወደውጭ ገፈታትሯት በሩን ከኋላዋ ጠረቀመባት።

....እኔማ ማታ አራት ሰዓት አካባቢ በር በሃይል ሲጋጭና ብሎኩ ሲንቀጠቀጥ ሰምቸ ነበር ... እስቲ አሁን ማን ይሙት እንኳን በር አይን እንኳን ተጨክኖ የማይከደንባት የምታሳሳ ቆንጆ ልጅ ላይ እንዲህ ይደረጋል? ወይስ የፈለገ ቆንጆ ብትሆን ሴት ልጅ ሚስት ስትሆን የሆነ የሚሰለች ነገር አላት ?? የራሳቸው ጉዳይ ሚስቱ ናት እንደፈለገ ! በዛ በጨለማ ሻንጣዋን ይዛ መሄጃ ስታጣ እዛው ጎረቤት ያለች ገና ከወለደች አንድ ሳምንት የሆናት ጓደኛዋ ቤት ትገባና ... እስከሚነጋ ጓደኛዋ እዚሁ እደሪ ብላት ታድራለች ....ጧት ታዲያ ከጓደኛዋ ቤት ስትወጣና ደረጃውን ስትወርድ ነበር እኔ ጋር የተገጣጠምነው።

...(መቸም የሳትራት ነኝ እድሌ የሚጥለኝ እሳት ላይ ነው) እንግዲህ ባል ሚስቱ የት ትደር የት አያውቅም ጧት በመስኮቱ ብቅ ሲል ሻንጣዋን እያንዘፋዘፍኩ ታክሲ ውስጥ ሳስገባት አየኛ ! በሱ ቤት ሚስቱ እኔ ቤት አድራ እጅ ከፍንጅ ይዞን ልቡ ውልቅ ብሏል ! "ሲያጋልጥ የየዋህ አምላክ ልበ ንፁህነቴን አይቶ ....." ብሎ ፉከራውን ጀመረዋ!

"እዚሁ አፍንጫየ ስር ምናለ ራቅ ብትል

... ምናለ ብሎክ አስራዘጠኝ

ሃያ

ሃያ አንድ

ሃያ ሁለት ብትሄድ

....ብሎክ ሃያ ሶስትም ቢሆን በዚህ በግሮሰሪው በኩል ቅርብ ነው .... እዚሁ በአልጋየ ትክክል ከስሬ ...አለ ወደታች ወደኔ ቤት እየጠቆመና በእግሩ የእኔን ቤት ከሱ ቤት የሚለየውን ወለል በእልህ እየረገጠ ..." በዚህ ሊያበቃ መሰላችሁ ...ቀጠለ " ይሄ ማለት ሌላ ቤት መሄድ አይደለም እኮ ወገኖቸ ሌላ ወንድ ይዛ አልጋየ ስር እንደተኛች ነው የምቆጥረው ...ያውም እኔ አልጋው ላይ ተኝቸ ...ታዲያ ይሄ ሞት አይደለም ወገኖቸ ...? ሰው ወዶ ነው ሚስቱን በገጀራ የሚገድለው ...? ሰው ወዶ ነው አንድ ጠርሙዝ አረቄ ብቻውን አንጠፍጥፎ የሚጠጣው ...? እ...ፍረዱኝ እንጅ" ....ይላል።

...ያች ነገረኛ ጎረቤታችን ደግሞ እንደትልቅ ሰው እንደማረጋጋትና እንደመምከር ነገሩን ያባብሳሉ... " ይሄማ ንቀት ነው ምን ጥያቄ አለው ...... ምን አንተን ብቻ እኛንም ጎረቤቱን አገሩን የ<ኢቶቢያን> ህዝብ ሁሉ መናቅ ነው ...ዘነዘና አለ፣ መፍለጫ አለ ቢጠፋ ቢጠፋ ድንጋይ አለ ...ሞቅ ብሎህ የሞት ታናሽ የሆነ እንቅልፍ ወስዶህ እግዜር ጋረደላቸው እንጅ ... ድንገት በለጭ ብሎብህ በተኙበት ጨፍጭፈህ እጅህን ለመንግስት ብትሰጥ የማን ያለህ ይባላል ....አንተ እንደሆንክ እንኳን ሰይጣንህ ተነስቶ ብቻህንም አንድ ጦር አይመልስህ ...ጎረቤቱም ቢሆን ደግ አረገ ነው የሚልህ " ይሉታል ! ይታያችሁ አሁን ይች ሴትዮ ባልቴት ናቸው?! እኔንማ እዚህ ቤት ከተከራየሁ ጀምሮ ጥምድ አድርገው ይዘውኛል ....ምክንያታቸው ደግሞ

"ሲገባ ሲወጣ ሰላም አይለኝም" የሚል ነው !

"እኔማ አሁን ሂጀ ነው ተሸክሜ አራተኛ ፎቅ ካመጣሁት በኋላ ቁልቁል የምፈጠፍጠው አለቀውም እዛ ብሎኬቱጋ ነው የምፈጠፍጠው ..." አለ ጎረቤቱ አንገቱን ቁልቁል አስግጎ የምፈጠፈጥበትን ቦታ እያየ ያማትባል ...ፎካሪው "እኔን ከቤቴ ተሸክሞ ለመውሰድ መንገድ ሲጀምር "ተው ተው ጦስ ይሆንብሃል ". ብለው ከፊት ከኋላ ከግራ ከቀኝ ይዘው ያቆሙታል ..."ወይኔ ወንድየ አንበሳው" ብሎ በመዳፉ ግንባሩን ይገጭና በብስጭት ይብከነከናል ጎረቤቶቹ ከንፈራቸውን ይመጡለታል !

" ማን እንደሆንኩ አሳየዋለሁ" ይላል

"አንተ ማን እንደሆንክ ድፍን ጎተራ እስከሳሪስ

...ድፍን ቄራ እስከሳር ቤት እና ሜክሲኮ ያውቃል ....ሳያውቅህ ቀርቶ መሰለህ መታወቅ ቢያስከብር ከሚስትህ በላይ ማን ያውቅህ ነበር " ይላሉ ነገረኛዋ ባልቴት ...."ወንድየ አንበሳው" ሚስቱ እንዳስደፈረችው ትዝ ይለዋል " ልቀቁኝ የገባችበት ገብቸ አነጠለልጥየ አምጥቸ ከዚህ ፎቅ ላይ ወርውሬ የምፈጠፍጣት " ብሎ ጎረቤት ለምኖ ያስቆመዋል።

...እንግዲህ እንደሰማሁት የሚስቱ ሰፈር ኮተቤ ነው አሉ ....ከኮተቤ እዚህ ድረስ ተሸክሞ አምጥቶ ያችን ቆንጆ ስንቱ በፍቅሯ ከንፎ ልፈጥፈጥልሽ የሚላትን ልጅ ሲፈጠፍጣት ታየኝ ... ከኮተቤ እዚህ እንኳን የሱን ሚስት መፈጥፈጫ በዣንጥላ የሚያዘልሉ ስንት ፎቆች አሉለት አይደል ...ወሬኛ !!

ይሄን ሁሉ ፉከራ የምሰማው በኋላ ነው ...እኔ እንቁላል ፍርፍር እየሰራሁ ትልቅ የሳይንስ ጥናት እንደሚሰራ ኬሚስት በቅመማ ተመስጫለሁ ! ለካስ ወንዴ አንበሳው እንደእንቁላል ፈጥርቆ የወኔ አስኳሌን ሊያፈሰው ከበላየ በሰላሳ ገላጋይ ተይዞ እየተጋበዘ ነው።

ባልቴቷ ወንዴ አንበሳው ቀዝቀዝ ያለ ሲመስላቸው እንዲህ ሲሉ ለአንዷ ገላጋይ የሚያወሩ መስለው በሾርኔ እኔን መጨፍጨፊያ መሳሪያ ያለበትን ቦታ ይጠቁሙታል... " አልጋነሽ ሙች ! እውነቴን እኮ ነው ...አሁን ይሄ ልጅ ድንገት ማታ እጅ ከፍንጅ ቢይዛቸው (((እኔ በር ሃያ አራት ሰዓት የሚቀመጥ))) ገብስ መፈተጊያው የእንጨቱ ሙቀጫ ዘነዘና አለ ..... ድንገት ፊቱ ሲያገኘው ላጥ አድርጎ እንካ ቅመስ ቢለው ...."

አልጋነሽ ታዲያ እንዲህ አለቻቸው " በቀደም ለማሪያም ዝክር መውቀጫ አውሱኝ ብልዎት የለም ጠፋ አላሉም እንዴ ?" ... ማን ያውቃል ጠቡን ሲሰሙ ለወንዴ አንበሳው ሊያስታጥቁ አውጥተው አስቀምጠውት ይሆናል! መቸም ሴትዮይቱ ወደኔ የሚዘምት አጥተው እንጅ ስንቅና ትጥቅ ከማቀበል አይመለሱም !!

ወንዴ አንበሳው አሁንም ይጋበዛል "ልቀቁኝ...... በእማማ ቁንጥሬ ገብስ መፈተጊያ ዘነዘና ነው እናቱን የማፈራርስለት" እያለ ! ...እውነትም እማማ ቁንጥሬ !! ከዚህ ቀን በኋላ ወንዴ አንበሳው ብስጭቱ ቢበርድለትም በአይነቁራኛ እያየኝና እየገለመጠኝ ያልፋል ! በነገራችን ላይ ወንዴ አንበሳው ፈሪ ነው! ይሄን ነገር ከሰማሁ በኋላ እውነቱን ላስረዳው ፈለኩ ድንገት ደረጃው ላይ ስንገናኝና ደረቱን ነፍቶ ገልምጦኝ ሊያልፍ ሲል "ወንድየ" አልኩት እኔ ደግሞ "ምናባህ ፈለክ " ይለኛል ይሄ ባይሆን እንኳን "ስምህን ቄስ ይጥራው " ይለኛል ብየ ነበር።

እሱ እቴ ...ልክ ድምጼን ሲሰማ እንደተተኮሰባት ሚዳቋ በድንጋጤ ዘሎ አማተበ አማትቦ እስከሚጨርስ ጠበኩና የሆነውን ሁሉ ረጋ ብየ አስረዳሁት ... "አውቃለሁ አብርሃም ...አውቃለሁ እሷ አለሌ ነገር ናት እንዳታሳስትህ ብየ እንጅ አንተማ በምን እዳህ " ብሎኝ እርፍ ! ስሜን ማን ነገረው ...ኧረ ጉድ !! ቆይ ይሄ ሰውየ ምንድነው ሲያወራኝ አይኑ እዛና እዚህ እየተወናጨፈ አይኔን ማየት የሚፈራው ....ደግሞ እጁ ይንቀጠቀጣል ...ከምር ሚስቴን የቀማኝ እንጅ በሚስቱ የጠረረገኝ አልመስልህ አለኝ !! እና ወንዴ አንበሳው ጋር ከዚች ቀን ጀምሮ ሰላም ወረደ ! ያች ነገረኛ ባልቴትም እኔና ወንዴ ሞቅ ያለ ሰላምታ ስንለዋወጥ በብስጭት ያሽሙራሉ ....

"ወይ ስምንተኛው ሽ ሚስትን አስረክቦ መገልፈጥ

... አይ አንተ መድሃኒያለም ይሄን ጉድ ከምታሳየኝ ምነው ብትወስደኝ

....እንደው አሁን ሞልቶ ለተትረፈረፈ ቸርነትህ በሰማይ ቤት ለኔ ኮስማና ነብስ ቦታ አጥተህ ነው ?

... ወይስ እንደው እዚሁ የማንንም የወንድ አልጫ እያየች ድብን ትክን ትበል ብለህ "ይላሉ

... ወንዴ አንበሳው ጋር ከሰላምታም አልፎ ጥሩ ወዳጆች ሆንን እንደውም ባለማወቅ ሻንጣዋን ይዠ የሸኘኋት ሚስቱን መልሶ የማስታረቅ አደራው እኔ ላይ ወደቀና አረፈው። ... ወይ ጣጣ ያችን ውብ ልጅ ወደዚህ አንዴ አንበሳ አንዴ በግ ወደሚያደርገው ባሏ ለመመለስ ሳይሉኝ ሽማግሌ ሆኘ የልጅቱን ስልክ ተቀበልኩ !... ይሄን ነገር የሰሙት ነገረኛ ባልቴት ታዲያ

"አሄሄ የልብን ሰርቶ በሽምግልና ስም ትራፊውን ለባል መመለስ ቱ እኔይቱ ልጅት የፊተኛውም የኋለኛውም ሶስተኛም ባሌ እንዲህ አይነት አልጫነት አያቃቸውም ...እንኳን መንካት ቀጥ ብሎ በሙሉ ዓይኑ ያየኝን ወንድ በወይራ ብትር ግንባሩን እየሰነጠቁ ጉሽርጥ ነበር የሚያስመስሉት ኤዲያ ...ወንድ ድሮ ቀረ " ወቸ ጉድ! ሰው ካልተጣላ ብለው እንዲህ እንደ እብድ ብቻቸውን የሚያስለፈልፋቸው ሴትዮ ምን ይባላሉ ....የሆነ ሁኖ ያችን አንዴ ብቻ ያየኋትን ቆንጆ ልጅ በሽምግልና ስም እንደገና የማየት እድሉ ሊገጥመኝ ሆነ....

## ክፍል 2

የተጣሉ ባልና ሚስትን ለማስታረቅ ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች መካከል አንዱ የተጣሉበትን ምክንያት ጠንቅቆ ማወቅና ...የፀቡን ምክንያት ወይ ((ማካበድ)) ወይ ((ማቃለል)) ነው

....ለምሳሌ የፀቡ ምክንያት ባል ሚስቱን " ከጎረቤቷ የሚገኝ ጎረምሳ ጋር አጓጉል ነገር ጀምራለች " በሚል "ተልካሻ ምክንያት" ጠርጥሯት ቢሆንና በዚሁ ሰበብ ቢለያዩ (ምሳሌ ነው) ለሽምግልና የተመረጠው ሰው ይህን ጉዳይ "በማካበድ" ወይም "በማቃለል" በጥርጣሬ የተበጠበጠውን ትዳር ወደ እርቅ ለመመለስ ይችላል።

....እንዴት ማለት ጥሩ

.... እንግዲህ ሽማግሌው ወደተጠረጠረችው ሚስት ይዞርና "የቱ ነው ለመሆኑ የተጠረጠረሽበት ጎረምሳ...?" ብሎ ጎረምሳውን ቢያውቁትም ልክ እንዳላወቁት መጠየቅ...!!

የፈለገ ብታውቀው የተጠረጠረችው ሚስት መልሷ ሊሆን የሚችለው "ምን አውቅለታለሁ... እሱን ጠይቁት እንጅ በህልሙ ይሁን በውኑ የሚያወራው " ብላ እንደዳቦ ሊጥ ኩፍ ባለ የኩርፊያ ፊት ወደባሏ በአገጯ መጠቆም ነው .... የሆነ ሁኖ ልክ የተጠረጠረውን ጎረምሳ ሽማግሌው በምልክትም ይሁን በስም ሲነገረው .... ጎረምሳውን እስከሰማይ ጥግ ማጋነን ይጠበቅበታል ...."

አበስኩ ገበርኩ....

እሱን ነው እንዴ ?????

...... እሱማ ሰው ቀና ብሎ የማያይ አለባበሱ ብቻ ሚኒስቴር የመሰለ ....በዛ ላይ ጨዋነቱስ ቢሆን .... እንዲህ ቀላል ቦታ የሚውል ሰው አልነበረም እኮ ... ሁኔታውን ወዘናውን ሳየው (በአመት የማያልቅ የወር ደመዎዝ) ያለው ነው የሚመስለኝ ....አይይይ እሱጋ እንኳን እንጃ አጉል ጥርጣሬ ነው የሚመስለኝ ... ምን አጥቶ የመንደሩ ሴት ሁሉ በየመጋረጃዋ ተከልላ የምታየው ሽበላ ምን አጣሁ ብሎ ከሰው ሚስት ጋር ይማግጣል" እያሉ ሰማይ ጥግ ድረስ መቆለል (አለ አይደል እሱጋርማ እንኳን ሄድሽ በሚመስል ድምፅ )

.... ሚስት ከአድናቆቱ ብዛት ..."እንዴ ይሄ የሰረኩት ልጅ እንዲህ ከባድ ሰው ነው እንዴ ... እኔ ግን ይህን ጅንን በፍቅሬ አንበርክኬ ያውም እግሬን ስሞ ....ሁለት ወር ከግማሽ ቀን ለምኖኝ ነው እሽ ያልኩት" ....ብላ ልታምን እስኪዳዳት ...እላይ መስቀል !!

(ምናልባት ሰኞ ቀን ከሰዓት ባሏ ስራ ሲሄድ ይሆናል ጎረቤቷ ቤት የገባችው ግማሹ ቀን እሱ ነው)

ይህ ሰቀላና ማጋነን ሚስት "የተሳሳትኩት የማይረባ ሰው ጋር አይደለም" ብላ ለስህተቷ እና ላሳሳታት ወይ ላሳሳተችው ጎረምሳ ክብር ለሰጠው ሽማግሌ .....በምላሹ ክብር እንድትሰጥና ...ቀጥሎ የሚያቀርበውን ሃሳብ እንድትቀበል የሚያዘጋጃት አቻ የሌለው መላ ነው !! (እውነትም ከባሏ ውጭ ከሄደች ማለት ነው ካልኬደች ምን ይቀባጥራል ልትል ወይም ግነቱ አማሏት ለመሄድ ውስዋስ ሊሆንባትም ይችላል)

መቸስ በዛሬ ጊዜ ድርጊቱ ቆሻሻ ቢሆንም እንኳን "ምን አደረገች" ወይ "አደረገ" ሳይሆን "ማን ጋር አደረገች" የሚለው ነጥብ ነው በሰዎች ልቦና ውስጥ ሃፂያትን የሚያቀለውም የሚያከብደውም ....."እሷ ፀዳ ፀዳ ያሉ ወንዶች ጋር ነው የምትወጣው " ብሎ የሚቀና ስንት ድንዙዝ አለ።

....."ፓ እንትና አንዲት የሃብታም ሚስት ጠበሰኮ" ተብሎ የሚደነቅበት ዘመን ነው ...

ሚስቱን ትቶ ሰራተኛው ጋ ጉድ ጉድ ያለ ወንድ ሲታማ እንኳን "ቱ እመብርሃንን የመሰለች ሚስት አስቀምጦ "ገረድ" ጋር ዳዳ ለዳዳ ያልከስክስ አባቱ እቴ " እኮ ነው የሚባለው ....እንዲሁ ነው የሚባለው ! እሽ ሚስቱ እመብርሃንን ባትመስልስ ሌላ ሴት ጋር ይሂድ ግዴለም ነው ....? ይሄ ነው የብዙሃኑ ስነልቦና መቀጨጭ ምልክቱ! ሞራል አልባ ግሳንግስ እንደኳሻኮር ፍቅር ያጠረው አካላችንን ወጥሮት ስንታይ ድሎት ይመስለናል እንጅ ቀጭጭጨናል ! ስለዚህ ሽምግልና ይችን የሰዎች ድክመት ለበጎ መጠቀምን ቢዋሳት ለተሳካ ሽምግልና ፍቱን እንደሆነች አምኛለሁ ! ይህን የተጠረጠረ የጎረቤት ጎረምሳ ማሳቀሉ ...."በሚስቴ ተካድኩ" ለሚለውም ባል ቢሆን "አልታረቅም ምናምን ብለህ እንቧ ከረዩ ትልና ሚስትህ ያረፈችበት ጎረምሳ ቀላል ሰው እንዳይመስልህ ....ካፍህ

ላይ ልፎ ነው የሚጠቀልላት" የሚል ማስፈራሪያ በመስጠት ቶሎ ሽምግልናውን ተቀብሎ ሚስቱን ወደቤት እንዲመልስ የሚያደርግ ጥበብ ነው።!!

ምን ጥርጥር አለው ...የብዙሃኑ የአበሻ ወንዶች ፍቅራችን አንድ እግሩ "አግብቻታለሁና የትም አትሄድም" በሚል አንካሳ የትእቢት ድጋፍ ....ሌላኛው "ቅናት ላይ" ሶስተኛው እግርም "ሰው ምን ይለኛል" ላይ የቆመ ነው ...ምናልባትም ሶስት ጉልቻ የምንለው ይሄን ይሆናል! እዚህ ጉልቻ ላይ ተጥደን ስንገበገብ ማለቴ ነው ! ... አስተዳደጋችን ያመጣብን ጠንቅ ሳይሆን አይቀርም ! ፍቅር እኮ ዋና ምሰሶ የሆነበት ትዳር ትንሽ ነው።

አሮጌ ሰፈር ውስጥ ያለ አሮጌ ቤት ...አይታችሁ ታውቁ የለ ?? ጣራው ላይ ቆርቆሮው በነፋስ እንዳይነሳ ድንጋይ...ዝናብ እንዳያስገባ ላስቲክ የተደረተበት ጥግንግን ....ልክ እንደዛ ነው አንዳንዱ ትዳር ... የጥንዶቹ የአብሮነት ጣራ በፍቅር ሚስማር ሳይሆን፣ የጎረቤት ይሉኝታ፣ ልጅ ወልዶ የመለያየት ይሉኝታ፣ የዘመድ አዝማድ ድጋፍ ማስፈራሪያ ምናምን ብንፋታ ንብረታችን ይበታተናል የሚሉ ከድንጋይ የከበደ ምክያት ተሸክሞ የቆመ ነገር ነው። ላንቦጫቦጭነው አብሮነት እንደቅመም ነው በተን የምናደረገው ፍቅርን። !

እንግዲህ ይሄን የሽምግልና "የማናናቅና የማሳቀል" መላ ድፍን ሌሊት "ተመራምሬ" ያገኘሁት ራሴ ነኝ !! መቸም የኛ ሰው አንዱን ነጭ ፈጠረው ካልተባለ በስተቀር የስነልቦና ይሁን የፍልስፍና ጉዳይ አይዋጥለትም ! ተዋጠም አልተዋጠም ግን ((እጅግ ውብ)) የሆነችውን ጎረቤቴን ((እጅግ አሰልች)) ከሆነ ባሏ ጋር ለማስታረቅ ከተመረጥኩባት ደቂቃ ጀምሮ ይህን ጉዳይ ስመረምር ቆይቸ የደረስኩበት መደምደሚያ ይሄው ነው !! የተጠረጠረችበትን ወንድ ማጋነን! ከእግዜር ዝቅ አድርጎ ሰማይ ላይ በደመና ማቀፊያ እሽሩሩ ማለት፣ ማንሳፈፍ ! ባል ከዚህ ክፉ ባላጋራ ሲሸሽ ሽማግሌው ሃሳብ ላይ ያርፋል!

አዎ ሽምግልና ቀላል ነገር አይደለም እየተፈላለጉ የተራራቁ ሰዎችን በየፊናቸው ጨምድዶ የያዛቸውን እልህ እና ትእቢት አስጥሎ (ሁለቱም አሸናፊነት እንዲሰማቸው በማድረግ) ወደእርቅ የማምጣት ጥበብ ነው በትዳር መካከል የሚደረግ ሽምግልና ቀላል ነገር አይደለም በተጣሉ ባልና ሚስት መካከል አርጅቶ ሙቶ የተቀበረ ፍቅርን በጥበብና በብልሀነት መቆፈሪያ የለበሰውን አፈር በመቆፈር የደረቀውን የፍቅር ውሃ እንደገና በየልባቸው ውስጥ እንዲመነጭ የማድረግ ጥበብ ነው። እውነተኛ ሽምግልናን የሞራል፣ የሃይማኖት እና የሰበዓዊነት ዋጋ ብቻ ሊገዛው የሚችል ውድ ነገር ነው !! ሲጀመር ሽማግሌ መሆን የሚችል ሰው ራሱን የገዛ የሌሎች ህመም የሚያመው የሌሎች መዋደድ የሚያስደስተው ሰው መሆን ይኖርበታል ....አዎ! ምቀኛ ሽማግሌ መሆን አይችልም፣ ተንኮለኛ ሰው ሽማግሌ ሊሆን አይችልም፣ ተጠራጣሪ ሰው ሽማግሌ ሊሆን አይችልም ማንም ከመሬት ተነስቶ ሽማግሌ ሊሆን አይችልም ሽምግልና ንፁህ ልቦናን ይፈልጋል አሁን ዋናው ጥያቄ ይሄ ነው ...(((የዚች ውብ ጎረቤቴና የዚህ ጅል ባሏ መታረቅ ለሽምግልና የተመረጥኩ እኔን ያስደስተኛል ወይ ???))))....

በሚገባ !!

ለምን ትዳራቸው መፍረሱ አሳዝኖኝ ነው ?

በጭራሽ ! እናስ ምንድነው?

በእርቅም ይሁን በፍርድ ቤት ትዛዝ ብቻ ያችን ውብ ልጅ እዚህ ሰፈሬ ያውም እዚህ ብሎኬ ላይ እንደገና የማየት ከፍ ያለ ጉጉት ስላደረብኝ ነዋ!! (ለምን ይዋሻል ውሸት በልብ ይዞ ሽምግልናማ ነውር ነው) ላያት እፈልጋለሁ ... "እንዴዴዴዴዴ ....የሰው ሚስት ለምን ታያለህ " ...የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል... ጥሩ ጥያቄ ነው! ....ግን ለምን የሰው ሚስት ለማየት እንደጓጓሁ እንጃልኝ !! (መሞቻየም ሁና እንደሁ እንጃ)።

እንግዲህ ሁለተኛው የሽምግልና መንገድ ማናናቅ ነው። ማናናቅ ለሽምግልና እንዴት ጠቃሚ ነገር መሰላችሁ አሁን ከላይ ባነሳነው የእነዚህ ሁለት ጎረቤቶቸ ጉዳይ ላይ እንኳን ብናየው ማናናቅ ወደእርቅ እንደሚመልሳቸው አትጠራጠሩ ....! ባሏ ሚስቲቱን (ያችን ቆንጆ ሚስት ...ያችን የማለዳ ኮከብ የመሰሉ አይኖች ያሏት ሚስት) "አለሌ ናት" ብሎ ዘልፏታል ....እና የት አለለች? ለምን አለለች ከማንስ ጋር ? ተብሎ ቢጠየቅ አንዱን የጠረጠረውን ወንድ

ስም ማንሳቱ አይቀርም ... አሁን እንግዲህ ማናናቅን ተግባራዊ ማድረግ ነው " ፐስስስ ....ስጋ ቁጠር ቢሉት አሉ ጣፊያ አንድ አለ ....አሁን ማን ይሙት አንተን የመሰለ እናት የሆነ ባል ትታ እዚህ በኤሌክትሪክ ምድጃ ሲቀቀል መብራት እንደጠፋበት ፓስታ የተሸማቀቀ ሳይበስልም ሳይጠርርም(ጥሬ ሳይሆን) የቆመ "መሃል ሰፋሪ" ጋር ትሄዳለች ብለህ ታስባለህ... ? ተው ተው ! ተጣላን ብለህማ እንዲህ ያረባ ቦታ አትጣላት ...ምንስ ቢሆን አንተን የመሰልክ ሸበላ ክንድ አቅፋ ያደረች ሴት እኮ ናት !! ነውር ነው አይባልም! ...በል ለሌላ ሰው ይሄን ወሬ ብለህ እንዳታወራ ኧረ በመድሃኒያለ........ም" ብሎ ባልየውን ሰማይ ጥግ ....ተጠርጣሪውን አምዘግዝጎ ካፈር መደባለቅ ! በቃ ባል ልቡ ሙልት ይላል !! ድሮም ቀናተኛ ባል ስለሚስቱ ሌላ ወንድ ጋር መሄድ ሲያወራ ....እንዲያስተባብሉለት እንጅ "አዎ ልክነው ሚስትህ አንተን ትታ ሌላ ወንድ ጋር አልላለች "ብለው ቁስሉን እንዲያባብሱበት አይደለምና.... ለመታረቅ ልቡ ቧ ብሎ ነው የሚከፈተው ! ሚስቱ ሌላ ወንድ ጋር መሄዷን ባይኑ በብረቱ ቢያይም እኮ ነው ...መሸነፍን አይወድማ ! ቆፍጣናው አበሻ፡፡!

እና ይሄን ይሄን በቁም ነገር አሰላስየ ሽምግልናየን ለመጀመር ወደልጅቱ ልደውልና ልቀጥራት መሸት እስኪል መጠበቅ ጀመርኩ ( የምትገኘው በእህቷ ስልክ ስለሆነና እህቷ ወደቤት የምትገባው ወደምሽቱ ሁለት ሰዓት ስለሆነ.... በዛ ሰዓት ደውልላት ብሎኝ ነበር ባሏ "ወንድየ አንበሳው" !! ሁለት ሰዓት ሲሆን ስልኬን አነሳሁና የተሰጠኝን ቁጥር ከወረቀት ላይ አይቸ ልደውል ካልኩ በኋላ አንድ ነገር ትዝ አለኝ ...ስሟን አላውቀውም !! ወይ ጉድ.... ስሟን እንኳን ሳላውቅ ነው ይሄ ሁሉ ከመንገድ የረዘመ ሃሳብና ሃተታ ....ኤዲያ ! ለነገሩ ሁሉም ቆንጆ ሴቶች ስማቸው "ቆንጆ" ስለሆነ ነው መሰል ስለስማቸው የምናስበው ቆይተን ነው !

ለነገሩ በህይዎት ቅኔ ውስጥ ስም ወርቅም ይሁን ቆርቆሮ ማንነትን መሸፈኛ ሰም ነው! ስም እንደውም ሰምና ወርቅ ከሚለው ነገር የመጣ ሳይሆን አይቀርም !

..... ወቸ ጉድ! ምንድነው ግን እንዲህ የባጥ የቆጡን የሚያስለፈልፈኝ ...አንድ ችግርማ አለ ! ሽቶኛል ግዴላችሁም የሆነ ጣፋጭ ችግርማ ሽቅብ የቤቴን ደረጃ ሲወጣ እየተሰማኝ ነው !! (እዚህ ብሎክ ላይ አብርሃም የሚባለው ልጅ የተከራው ቤት የትኛው ነው እያለ) (እኔ ነኝ ችግርየ ና ግባ ...የምል አይነት እየተሰማኝ ነው ...ሆሆ "ተው ልቤ ተው ልቤ ገደል ትገባለህ " አለ ዘፋኙ)

"ለወንድየ አንበሳው" ደወልኩ ....

"ሄሎ" አለኝ ...ድምፁ የተቆጣ ይመስላል ...ከኋላው የጠርሙዝ ካካታና የሰዎች ጫጫታ ይሰማል ...አጅሬው መጠጥ ቤት ነው ማለት ነው ...

"ሄሎ ወንድየ አብርሃም ነኝ ...ሰላም አመሸህ"

"ደህና" ባጭሩ ቆጣ ብሎ መለሰልኝ ! ሆሆ

" ለባለቤትህ ልደውልላት ብየኮ ስሟን ለካ አላውቀውም "

" ወንዴ አንበሳው ውሃ በላሽ...." ብሎ ፎከረና

...."ስማ ጭራሽ ደውለህ የሚስትህን ስም ንገረኝ ትላለህ ....ጎረቤት አክብሬ ነፍስህን ባተርፋት ጭራሽ ለኔው ደውለህ የሚስቴን ስም .... ወይኔ ወንዴ አ....." ከሸ ! በብስጭት የመጠጥ ጠርሙዙን ሳይሰብረው አልቀረም ..... ግዴላችሁም ይሄ ልጅ ጨረቃ ሲወጣ የሚነሳበት አጋንንት አለ ... ጧት ሰላም አልነበር እንዴ ??....ግራ ገባኝ! ደውልና አስታርቀኝ ብሎ ስልኳን ሰጥቶ ምናባቱ ነው እንዲህ የሚያስፎገራው ... እኔም ቱግ አልኩ ....በውስጤ ግን " እስቲ ብስጭቱም ናፍቆቱም ይሆናል" ብየ ታገስኩ ! ( እንደራስ ነው መፍረድ ....እኔስ ብሆን ...ያችን የመሰለች ልጅ ትታኝ ብትሄድ እንኳን ጠርሙዝ ጨረቃን አውርጀ አላንኮታኩታትም?? ...የሚሰበር ነገር ሁሉ አልሰብርም እንዴ ...ከቤቴ ኮተቤ ሰፈሯ ድረስ ሩጨ ሪከርድ ጭምር አልሰብርም እንዴ ??.....ቢቆጣ እውነት አለው ! )

እና ላረጋጋው ሞከርኩ!

“ወንዴ ኧረ ተረጋጋ ....እኔ የደወልኩት የባለቤትህን ስም ሳላውቀው ብደውልላት ....” አቋረጠኝ

“ተው እንጅ ....እና ስሟን ሳታውቅ ነው ሚስቴን የበ ....” እግዚኦኦኦኦ!! አፈረጠው ብልግናውን!! ስድ!! ምናለ አማርኛውን ለስለስ ቢያደርገው ...ምናለ

“ስሟን እንኳን ሳታውቅ ነው ሚስቴ ጋር አንሶላ የተጋፈፋችሁት” ቢል ...እሽ ይሄን ባይችል እንኳን ...ምናለበት

“ስሟን እንኳን ሳታውቅ ነው ....ሚስቴ ጋር አለምህን የቀጨኸው “ ቢለኝ ....ምናለ ? ስልኩን በብስጭት ጆሮው ላይ ዘግቸ በግርምትና ግራ በመጋባት ቁጭ አልኩ ....

“ሆሆ ሚስቴን....” ወይ ብልግና እናተ ! እኔስ እሽ ይሁን ...ይሄን ብልግናውን ብትሰማ ያች ቆንጆ ሚስቱ ምን ትላለች .....ሽምግልና ውሃ በላት !

**** ****** ******

ልክ ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ በግርምት ከተቀመጥኩበት ንቅንቅ ሳልል የቤቴ በር በሃይል ተንኳኳና በድንጋጤ አስደነበረኝ ....ምን ተንኳኳ ብየ አለሰልሰዋለሁ ተንዃዃ እንጅ ! ዃ ዃ ዃ

“ማነው “ አልኩ ድምፄን ጎርነን አድርጌ ( ድምፅ በማጎርነን ጠላት ቢመለስ ኑሮ ጥሊያን ያንን ሁሉ ፉከራና ሽለላ ንቆ ድንበራችን ላይ ድርሽ ባላለ ነበር ወንድነት በድምፅ አይደለም ከድምፁ በኋላ ባለው ክንድም እንጅ)

“ወንድየ ነኝ “ አለ ከኔም በጎረነነ ድምፅ .....አሁን ነው የወንድልኩ እንግዲህ !! “ ዘራፍ “ ለማለትም “እውይ እድሌ” ለማለትም ግራ እንደገባኝ በሩ ከበፊቱ ጠንከር ባለ ጉሸማ ተንዃዃ.... (አሜሪካ መኖር ጥቅሙ ለዚህ ጊዜ ነበር 911 ደወል ይደረጋል... እዚህ ...ወይ ደውየ “ብሎክ አስራ ስምንት ሰዎች ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተዋል” ካላልኩ በስተቀር ነጋሪት ቢጎሰምም ፖሊስ ከነገ ወዲያ ነው የሚደርሰው) ለነገሩ እንጅ እኔ አብርሃም ይሄን ሰካራም ፈርቸ ነው ለፖሊስ ምደውለው ? ወንድ አያውቅም !

ዃዃዃዃዃዃዃዃ .....አሁንስ በእግሩ ነው መሰል ያንኳኳው !! እንግዲህ የመጣው ይምጣ ብየ ወደበሩ ሄድኩና “ማነው “ አልኩ ....ሃሃሃ ....ቅድም ማን እንደሆነ ነግሮኝ ነበር እኮ ....አይ ፈርቸ እንኳን አይደለም.... ((በስህተት ሰላማዊ ሰው ላይ ጥቃት እንዳልፈፅም ብየ ነው)) እነአሜሪካ በኢራቅ በአፍጋኒስታን ....የአየር ድብደባቸው የሚተቸው ለምንድነው? ....እነኢስራኤል የሚወቀሱት ለምንድነው? ...በቅርቡ እንኳን ራሽያ የአየር ጥቃቷ ሲወገዝ የነበረው ለምንድነው ? ....."ሰላማዊ ሰው ላይ ጥቃት እያደረሳችሁ ነው” በሚል አይደል?!! ....ከነሱ መማር አለብኝ ...ዜና መስማትማ ሁሉም ይሰማል ዋናው ነገር ከዜና መማሩ ነው !! ተምረን ለአለም ሰላም የራሳችንን አስተዋፅኦ ማበርከት ይኖርብናል !! ጠላቴን አፈር ከድሜ ከማስበላቴ በፊት ...ከዚህ ፎቅ ላይ አምዘግዝጌ እዛ ታች ያለ ብሎኬት ላይ ከመፈጥፈጤ በፊት ...በጥቃቴ የማይጎዳ ሰላማዊ ሰው በሬ ላይ አለመኖሩን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለብኝ !! አዋ.... “ወንዴ አንበሳው”ን ቁልቁል ስወረውረው ባሏ አምሽቶባት ውጭ ቁማ የምትጠብቅ ሚስኪን ሰላማዊ ሴት ላይ ቢያርፍስ ... !! ሰውስ ባትሆን ....የምሽት ጉርሱን የሚለቃቅም ውሻስ ቢሆን ካለአዳው ለምን ይሙት ????..... ደግሞ በሬን ያንኳኳው ሌላ ጎረቤት ቢሆንስ ... ሰው ለስንት ነገር ጎረቤቱ ጋር ይሄዳል ...ሰዓት ሊጠይቅ የመጣ ጎረቤት ሊሆን ይችላል ...የዛሬ ሁለት ወር አሞኝ ነበር ምናልባት ያኔ ያልተመቸው ጎረቤት ሲመቸው መሻሌን ለመጠየቅ ብርቱካን ቢጤ ጠልጠል አድርጎ መጥቶም ሊሆን ይችላል ...እና ለማረጋገጥ እንጅ ፈርቸ አይደለም !! ለምን እፈራለሁ “ወንዴ አንበሳው “ እንዳይገድለኝ ? ቲሽ ! ...ልሙታ ! እንኳን ((ያችን ለመሰለች ውብ ልጅ)) ሰው ላረባ ነገርስ ተፋልሞ ይሞት የለ እንዴ ....ኧረ ለልማት ተቆፍሮ ክፍቱን በተተወ ጉድጓድ ውስጥም ገብቶ መሞትም አለ

...አንድ ፈላስፋ “የምትሞትለት ነገር ከሌለህ የምትኖርለት ምክንያት የለህም “ አለ ነው የተባለው ? ይበል ምናለበት እሱ... እንደኔ በሩ በጨለማ አልተንኳኳ ..... እከፍተዋለሁ በሩን ችግር የለም ! ይብላኝለት “ለወንዴ

አንበሳው" መለዓክ የመሰለች ሚስቱን ትቶ በመለዓከ ሞት ጥቁር አክናፍ ታንቆ ወደሲኦል ለሚምዘገዘገው ....እኔማ ከዚህ ምድር ምን ሊቀርብኝ ....ማቄ ነው ጨርቄ ......ዘራፍ !! እከፍተዋለሁ!!

# ክፍል 3

"ተመስገን.... ዋናው መትረፉ ነው ! ወደልቡ ከፍ ቢል ኖሮ ወይ ቆሽቱን ቢያገኘው የማን ያለህ ይባላል " የሚል ድምፅ ስሰማ ልክ እንደብርቱ ክንድ ትከሻና ትከሻየን ይዞ እያርገፈገፈ ከከባድ እንቅልፍ የቀሰቀሰኝ መሰለኝ ! አ?? አላመንኩም .... መትረፌ ብቻ አይደለም የገረመኝ .... የመትረፌን የምስራች በመትረፌ የተቆጨ በሚመስል ድምፅ ቀድሞ በመንገር ያነቃኝ የዛች የነገረኛ "እማማ ቁንጥሬ " ድምፅ መሆኑ እንጅ ! ከዛም ሁሉም ነገር ዝምምም አለ...ወዲያው ግን ጉንጨ ላይ ግራና ቀኝ ሁለት ሸካራ መዳፎች ሲያርፉ ተሰማኝ ...እንኳን ሰመመን ውስጥ ሁኘ ሙቸም ቢነኩኝ እነዚህ እጆች የማን እንደሆኑ የምለያቸው ይመስለኛል ...የእናቴ እጆች ናቸው!! ...

"አቡቹ" ስትል ሰማኋት ስጋት በተሞላና ቀስ ባለ ድምፅ ......ይሄው ድምፅዋ ተከተለ ራሷ ናት !! ጥፋቴ ባይሆንም በአጉል ጀብደኝነት በሩን በመክፈቴ አዘንኩ "ፈሪ ለናቱ " ይሉት ሃቅ የገባኝ በዚች ቅፅበት ነው ! ....አቤት አለሁ ...ተርፌያለሁ ...በዚች አለም ለመኖር ሌላ እድል ተሰጥቶኛል ብየ ለመጮህ አስቤ ነበር ...አንችም አይኖች ላይ ሊዘንብ እንደተዘጋጀ ደመና የተንቸረፈፈ እንባሽ ይትነንና ከንፈርሽ በሳቅ ይሞላ ......ልላት ነበር እናቴን ....ግን ለምን እንደሆነ እንጃ ወደዚህ አለም ሙሉ ለሙሉ ከመመለሴ በፊት በሞትና ህይዎት መሃል ባለችው ሰመመን ትንሽ ጊዜ መቆየት ፈለኩ

..."አቡቹ አለህልኝ ...አለሁ በለኝ "

ቀጠለ የእናቴ ጥሪ ...ሰው በጥሪ ከሞት ይመለስ ይመስል ! ምን እዚህ አገር መሰመሚያ(በሰመመን መቆያ) የለ፣ መተኛ የለ፣ መሞቻ ራሱ የለም ! አይኔን ቦግ አድርጌ ገለጥኩት ....ብዥ ካለ የብዙ ሰዎች ምስል ጋር የእናቴ እልልታ ከግድግዳ ግድግዳ፣ ከዛም ግቢውን ፣ከዛም ሰፈሩን ድፍን አዲስ አበባን እንደእፊያ ሲከድነው ተሰማኝ ... እማማ ቁንጥሬም እልል ሲሉ ሰማሁ ...አሄሄ ይች የእማማ ቁንጥሬ እልልታ ጥሪ መሆን አለባት " ወንዴ አንበሳው ይሄ ነጃሳ አጉል ነካክተህ ተርፎልሃል ና ጨርሰው " የምትል ጥሪ ! እንጅ ማን ይሙት አሁን በእኔ መትረፍ እማማ ቁንጥሬ ደስ ብሏቸው እልል ሊሉ ??!!

"ይቅርታ ማዘር እንዲህ አይጮህም ሌሎች በሽተኞች ይረበሻሉ..." የሚል የተቆጣች ሴት ድምፅ ተከተለ ...ሌሎች በሽተኞች ? እንዴ ያ መናጢ "ወንዴ አንበሳው " ማታ ጉድ የሰራው ድፍን የብሎኩን ሰው ነው እንዴ ...እና ሌሎች በሽተኞች ከየት መጡ ? ...ተገለጠልኝ !! ...ያለሁት ሆስፒታል ነበር ......ክንዴ ላይ የተመሰገው የግልኮስ መርፌ ሲጠዘጥዘኝ የመድሃኒት ሽታ ሲሰነፍጠኝ የተኛሁበት አልጋም ካለዎትሮው ከወደትካሻየ ቀና ሲልብኝ ሆስፒታል መሆኔን ወዲያው አወኩ ! ጆሮየ፣ አፍንጫየ እና አይኔ በየተራ ስራቸውን ሲጀምሩ ሁሉም ነገር ተገከለጠልኝ ....የቀኝ ጎኔ ላይ አንዳች ሃይለኛ ህመም እና መጠዝጠዝ ሲሰማኝ ደግሞ ማታ የሆነው ሁሉ ግልጥ ብሎ ታወሰኝ ....ይሄ ብሽቅ ሰካራም ቆይ ልነሳ ብቻ !!

ማታ በሬን ሲያንኳኳ ....ያው መቸም አንዳንዴ አጉል ጀግና መሆን ይዞ ሚች ነገር ነው ...በሬን ከፈትኩ ....ልክ ስከፍት "ወንዴ አንበሳው" እንደጅብራ በሬ ላይ ተገትሯል .... "ሰላም አመሸህ ወንዴ" አልኩት እኔማ ሰው ነው ብየ ነበር .... እሱ ግን ለድፍን መንደሩ በሚሰማ ጋጋኖ ድምፁ "አንተ ሰውየ ግን ከሚስቴ ራስ ላይ አትወርድም እንዴ ኧረ ስለግዚሃር ተወኝ ....ተወኝ ብያለሁ ተወኝ ...እኔ አልደረስኩብህም ተወኝ ....በህግ አምላክ ተወኝ ..... " ብሎ ሲጮህ በሃፍረት ሽምቅቅ አልኩ። ....ትንፋሹ ጋኒቱን ራሷን ! በዛ ላይ እጁ ኪሱ ውስጥ ነው ....የሆነ ነገር እንደያዘ አለመጠርጠሬ አሁን ሳስበው ይገርመኛል ....ለነገሩ ብዙ ጊዜ ሰካራሞች እጃቸውን ኪሳቸው ውስጥ አስገብተው መጀነን ባህሪያቸው ነው ብየ ችላ ብየውም ይሆናል !

"ምን ሁነሃል?" አልኩት እንዲህ የተበደለ መስሎ ኡኡ ሲል ግራ ተጋብቸ !

“ምን ሁነሃል ?” ብሎ ከበፊቱ በጎላ ድምፅ መልሶ ጥያቄን ደገመውና

“ምን ሁነሃል ትለኛለህ እንዴ ....ከዚህ በላይ ምን ልሁንልህ ....በቁሜ ሚስቴን ቀማሃኝ

የሞቀ ትዳሬ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ በባልዲ ገለበጥክበት

.....አይኔ እያየ ያውም በአልጋየ ትክክል ....አብረሃት አድረህ ...ሂጅ ወንዴን ሜዳ ላይ ጥለሽው ጥፊ ብለህ ሚስቴን የግራ ጎኔን አካሌን ....በኩንትራት ታክሲ ሸኘሃት፣ ትዳሬን በተንኮ ፈጣሪ ይፍረደኝ ብየ እንባየን ወደላይ ረጭቸ ጉልበቴን አቅፌ ብቻየን ኩርምት ብየ በተኛሁበት ....ጭራሽ ለእኔው ለራሴ ደውለህ ....”

“አንተ አፍህን አትክፈት ...ማን ጋር እንደምታወራ እወቅ መጀመሪያ!! “ አልኩ ከምር ተበሳጭቸ...ደግሞ እንዴት እንዴት ነው ወሬውን የሚያሳምረው በእግዚአብሔር .....

“ ...ማን ጋር እንደምታወራ እወቅ ?????? ይችን ይወዳል ወንዴ አንበሳ.......ው ....” ብሎ ፎከረና “ አንተም ማን ጋር እንደምታወራ አሳውቀሃለሁ “ ብሎ አንድ እርምጃ ወደኔ ተራመደ ...በዛው ቅፅበት ከኪሱ ተፈትልኮ የወጣ እጁ ወደ ሆዴ ሲወነጨፍ የሆነ የሚያብረቀርቅ ነገር በለጭ ሲል አየሁ ... ቢላ ነበር ...እንዳጋጣሚ ዞር ማለቴ ጠቀመኝ እንጅ እንዳሰነዛዘሩ ቢሆን አልተርፍም ነበር ....ይሄ ሁሉ የሆነበት ፍጥነት ከጥቂት ሴኮንዶች አይበልጥም ....ለካስ ይች ጤዛ ህይዎት እንዲህ በሰከንድ ነው እርግፍ ብላ የምታርፈው ! ከዛ በኋላ መንደርተኛው ሲንጫጫ ...... እሪታው ሲቀልጥ ነው በደብዛዛው የተሰማኝ (የሪታው ጀማሪ እማማ ቁንጥሬ ነበሩ እንግዲህ እስኪወጋኝ ተደብቀው በጉጉት እየጠበቁ ይሆናል ) ...

በሬ ላይ በአንድ ሰካራም እንዲህ መሆኔ ...መደፈሬ ቢቆጨኝም መትረፌ ተአምር ነበር .... የግቢው ዘበኞች “ወንዴ አንበሳውን” እንደአህያ እየወገሩ ለፖሊስ ሲያስረክቡ እኔንም አፋፍሰው እዚህ ያለሁበት ሆስፒታል አመጡኝ .....መንገድ ላይ የፈሰሰኝ ደም ይሁን ወይም ቁስሉ እንጃ ብቻ ሁሉም ነገር ጨላለመብኝ ይሄው እዚህ ነቃሁ !! የተኛሁባት ክፍል በሰው ተሞልታለች ... እናቴ ከትራስጌየ ተቀምጣ አይን አይኔን ታያለች ...ሁለት እህቶቸ አልጋውን ከበው ቆመዋል .......ደግሞ ጥግ ላይ የቆሙት ጎረምሶች እነማን ናቸው ? አሃ .........የሁለቱ እህቶቸ ፍቅርኞች ....አይይ እነሱም መጡ? (ይችን ይችንማ እናውቃታለን ....የኔን አደጋ ሰበብ አድርገው በእናቴ ፊት “የብረት በር የሆንን አማቾች አለን” የምትል ግንባር ማስመታት ናት ሂሂ ....በሰው ችግር መሞዳሞድማ ተገቢ አይደለም !) በኋላ ስሰማ አንዱ የእህቴ ጓደኛ “ወንዴ አንበሳውን “ በሽጉጥ ግንባሩን እንደሸንኮራ ካልሰነጣጠኩት ብሎ በስንት ገላጋይ ነው አሉ የተመለሰው ...እህቴን ጠርቸ

“እኔ የምልሽ ....በሽጉጥ ነው የተባለው?” አልኳት

“ አዋ “ አለች...የሆነች ኩራት ቢጤ ፊቷ ላይ በስሱ እየተንሳፈፈችባት! (ሌላው ቢቀር ላንተ ለወንድሜ ደምህን የማይመልስ ፍቅረኛማ አላጣም አይነት፡)

“አሃ ....ጓደኛሽ ቀድሞ ታጋይ ነበር እንዴ” አልኳት ...

“ከግንድ ያታግልህ !....እስቲ ታመሃል አሁን እንኳን ዝም ብለህ ተኛ “ ብላኝ እየተቆናጠረች ወጣች ... ምን መተኛ አለ ....ዛሬ “ወንዴ አንበሳው ላይ” ሽጉጥ የመዘዘ የእህቴ ፍቅረኛ ነገ እህቴን ለትዳር ብንከለክለው ይች አፈሙዝ ወደኛው መዞሯ አይደል ? ኧረ እኔ እዳ አያጣኝም ! የአርባ ቀን አድሌ አነፍንፎ ችግር ይጠራል! ይሄን እያሰብኩ ስማረር ....ድንገት ያለንበት ክፍል በቀስታ ተንኳኳ....በር አካባቢ ያሉት ለመክፈት ሲራኮቱ በውስጤ እንዲህ እላለሁ (((ተው የተንኳ በር ዘላችሁ አትክፈቱ...በኔ ይብቃ ትውልድ ይዳን )))

....እህቴ ከፈተችው ..... አንዲት ቆንጆ ሴት በነጭ ፌስታል ሙሉ... የሆነ ነገር የያዘች በቀስታ (እየፈራች) ገባች ... ከላይ ትንሽ እንደበረዶ የነጣች ነጠላ ፀጉሯና ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋለች .....ብዛቱ የጤፍ ክምር የመሰለ ጥቁር ፀጉሯ ነጠላውን የተወጠረ ድንኳን አስመስሎታል ! እርፍ !! የ”ወንዴ አንበሳው” ሚስት መጣችላችሁ!!!! (ድሮ እቃ ጠፍቶ በፍለጋ ስንማስን “ተውት ሰይጣኑ ሲበርድ አፍንጫችሁ ስር ታገኙታላችሁ” ይል ነበር አያቴ ....) ይች ውብ

ልጅ ግን ሰይጣኑ ሲሞቅ ያለሁበት ድረስ ከች አለችና አረፈችው ! እግዚዮ ደግሞ እንዴት አምሮባታል .... ምንም እንኳን ካለስራየ ቢሆንም ለዚህ የበቃሁት ...ለዚች ቆንጆ የከፈልኩት መስዋእትነት ግን አንሶ ታየኝ ... ምን አላት ያ ናዚላ ባሏ በሸንኩርት ቢለዋኮ ነው ጫር ያደረገኝ ....ለነገሩ ጥቃቱ ከ"ጫርም" ያለፈ ነበር ከኩላሊቴ ከፍ ከጎድን አጥንቴ ዝቅ ብሎ በቀኝ በኩል ነው ያገኘኝ በግራ ቢሆን ልብህን ያገኘው ነበር ይሉኛል ...ልብ ቢኖረኝ መቸ በሬን ስከፍት! ግን ይችን መልዓክ የመሰለች ልጅ ሳያት በስለት መወጋቴ "ጫር" ሁና ታየችኝ !!ታየኘ በቃ !

ልጅቱ ቀስ ብላ ወደኔ መጣችና "እንኳን እግዚአብሔር አተረፈህ" ብላ እንባዋ እንደሃር በለሰለሱ ጉንጮቿ ላይ ድንገት ተዘረገፈ .... ማታ ከፈሰሰው የእኔ ደም ይልቅ የዚች ልጅ እንባ አሳዘነኝ ! ፊቷ ክረምት የጠባበት ውብ ምድር ይመስላል ... አይኖቿ በሃምሌ ሰማይ ላይ የሚያብለጨልጩ ኮከቦች ....በተፈጠረው ነገር ክፉኛ ደንግጣለች ...እራሷን እንደጥፋተኛ ስለቆጠረች በፊታችን ተሳቃ ነበር ...ልክ እሷ ስታለቅስ እስካሁን ጥጋቸውን ይዘው እናቴ ጋር ሲያወሩ የነበሩት እማማ ቁንጥሬ በረዥሙ ተንፍሰው (የነገር ናት ትንፋሻቸው) "በ.........ሉ ደህና ዋሉ " ብለው በሩን ከፈቱ ....ልክ የበሯን እጀታ እንደያዙ ይችን ቆንጆ ከእግር እስከራሷ ገርምመዋት ወጡ ! አስተያየታቸው የሆነ መኪና በጨለማ ውስጥ ረዥም መብራቱን ያበራው አይነት ነበር የሚመስለው።

...እንኳን ሄዱ !አንድ አዛ ቀለለ ...አሁን እንዲህ የተጣደፉት ...ሰፈር ሂደው ከምድር እስከአራተኛ ፎቅ የቡና ሙቀጫ ነጋሪታቸውን ጎስመው .... "ጭራሽ የመንደሩ አልበቃ ብሏት ሆስፒታል ድረስ ሄደች ወይ ዘጠነኛው ሽ" ብለው ለማውራት ነው ....ይሄ ጮማ የሆነ ወሬማ "በስምንተኛው ሽ" ብቻ አይደምቅም !! እስቲ ምን ታድርጋቸው ለራሷ ሆድ ብሷታል ! ከእህቶቸ ፍቅረኛ አንዱ እማማ ቆንጥሬ የለቀቁትን ወንበር ለዚች ቆንጆ ጠጋ አደረገላት " ጎበዝ ! ይሄ የተባረከ ልጅ ነው ...እህቴን ለትዳር ቢጠይቅ አሁኑኑ ነበር ከነትምህርት ማስረጃዋ አፋፍሽ የምሰጠው:) ኧረ ይውሰድ ...ሽጉጥ ከመምዘዝ ወንበር መስጠት ታላቅነት ነው ! ይቸኛይቱ እህቴ ምርጫዋ ልክ ነው ... ድሮም አስተዋይ ነበረች ! የዛችኛይቱ እህቴ ጓደኛ ግን ሰፌድ የሚያክል ስልኩን እየጎረጎረ ጥግ ላይ ግድግዳ ተደግፎ ቁሟል

...ይሄን ጊዜ የፌስ ቡክ ግድግዳው ላይ

"ሃኒየ ወንድምሽ ላይ በተፈጠረው ነገር ከልቤ አዝኛለሁ እግዚአብሔር ምህረቱን ይላክለት ገፈኞችን የገቡበት ገብተን ለፍርድ እናቀርባቸዋልን " የሚል ፅሁፍ እየለጠፈ ይሆናል !

አንዱ ችኩል ጓደኛው ታዲያ "RIP" ብሎ አስተያየት ሰጥቶም ይሆናል ! ገፊ ሁሉ !

ልጅቱ አልጋየ ጎን ተቀመጠችና አሁንም እንባ በሞሉ ትልልቅ አይኖቿ እያየችኝ ..."ይቅርታ አብርሽ ይሄ ሁሉ የኔ ጦስ ነው !" ብላ እንባዋን በሶፍት ጠረገች ....አብር((ሽ )) ? እስቲ ዶክተሩን ጥሩልኝ ...ጆሮየ ላይ አደጋው ያሳደረው ተፅእኖ አለ ወይስ ይች ((ሽ)) በትክክል ከልጅቱ አፍ ወጥታለች ??((ሽሽሽሽ))

እንደሬዲዮ እሽታው ጆሮየ ላይ ጮኸብኝ ....ማጥራት ሳይኖርብኝ አይቀርም ...

"ኧረ ምንም አይደል ያው ትንሽ ተበሳጭቶ ነው " አልኩ

....አለ አይደል

"ቢበድሉንም ይቅር ባይ ነን" አይነት ጨዋነት በቆንጆዋ ልብ ውስጥ በሊዝ ለማስቀመጥ ! አሁንኮ "ባሌ ልክ ነው" ብትል ዘራፍ ነበር የምለው ...የጨዋነት ካባ የለበሰች ስንት ትእቢት አለች! " ምን ይበሳጫል ድሮም ውሻ ነው ... እኔን ያሰቃየው ቁም ስቅሌን ያበላኝ አነሰውና ምንም የማያውቅ ትሁት ሰው ቀና ብሎ የማያይ ልጅ ጋር እንዲህ ያለ ጉድ .... " አለች.... ይህኛውን ስትናገር ለእኔ ይሁን ለእናቴ አልያም ለራሷ እግዜር ይወቅ ....እንደገና አለቀሰች .... ኤዲያ እንዲህ አልቅሳ የምትቀብር ቆንጆ ባለችበት አገር እንኳን ቆስሎ መትረፍ ቢሞትስ ...ብየ ሳስብ እናቴ የልጅቱን ለቅሶ ተቀብላ የራሷን ስትመርቅበትና በነጠላዋ ጫፍ እንባዋን ስትጠርግ " ኧረ ለናቴ ልኑር" ብየ ሃሳቤን ቀየርኩ ....ለካስ ለቅሶ እና ለቅሶ ይለያያል !! ቆንጆዋ ብዙ ሰዓት ስታወራን ቆየች የበዛውን ሰዓት ከእናቴ ጋር ነበር ያወሩት ....አልፎ አልፎ አይኗን ጣል ታደርግብኛለች (ይሻለኛል) አይኗ እንደተሳለ የፋሲካ ቢለዋ ልቤን ሸርክት ያደረገው

ይመስለኛል ... ባልና ሚስት ባለቢለዋ ( ባል የጀመረውን የስለት ጥቃት ሚስት ዳር ለማድረስ በውብ አይኖች ስለት እንደማስቀጠል ተልእኮ ዓይነት ...እንኳንም ተላከች) ባል ባለቢላዋ ሚስት ባለጎራዴ እዚች ሆስፒታል ውስጥ መከረምህ ነው ጓዴ (እያልኩ እገጥማለሁ...የግጥም ተሰጥኦ እንዳለኝ የጠረጠርኩት አሁን ነው)

ድንገት እጅን ላንቀሳቅስ ስሞክር ብርድ ልብስ ያረፈበት የ "ግልኮስ ቲዩብ" ያዝ ስላደረገኝ እናቴ "ቆይ ላስለቅቅልህ" ብላ ከወንበሯ እንደመነሳት ስትል ....ልጅቱ ቅርብ ስለነበረች ከእናቴ ቀድማ ተነሳችና በእኔ ላይ ተንጠራርታ ብርድ ልብሱን አስለቀቀችው ....ተኝቸ ስላየኋት ነው መሰል አቤት መለሎነት ....በዚች ቅፅበት ሶስት ነገሮች ተከሰቱ

አንደኛ...ጡቶቿ ከበላየ ሁነው እንደደመና ተንሳፈፉ ....ደግሞም በትንሹ የግራ ትከሻየን እና ደረቴን ነካ አደረጉኝ ... ሲነኩኝ ጫፋቸው ሁሉ ሲወጋኝ ተሰምቶኛል !!

ሁለት ጠረኗ አውሎ ንፋስ እንዳስነሳው አቧራ አፍንጫየ ላይ ተሞጀረብኝ ...ሃኪም ካዘዘልኝና ሲያገሳኝ አስቀያሚ ጠረኑ በአፍንጫ ከሚመጣው መድሃኒት ይልቅ ይሄ ጠረን አገግም ዘንድ በቀን አንድ ቢታዘዝልኝ ባንድ ጀምበር ሳልድን አልቀርም ብየ አጋነንኩት !!

ሶስት በሉማ.... ብርድ ልብሱን አንስታ እጀን በለስላሳ መዳፎቿ ያዘችና ወደግራ በኩል አስተካከለችው (ይችን እንኳን እንደምርቃት የጨመረቻት መሆን አለባት) ይሄን ያህል በጎራዴ አንገቴ አልተቆረጠ ....የምን በሽተኛን ማቅበጥ ነው እንኳን ፊት ሰጥታኝ ...) እነዚህ ሶስት ነገሮች ከልጅቱ ቁንጅናና ካለሁበት ሁኔታ ጋር ተዳምረው ....አለ አይደል "በዚች ልጅ የታማሁት እውነት ይሆን እንዴ" ብየ እራሴን እንድጠረጥር አደረገኝ !!

በመሃል ....ስንትና ስንት ብርቱካን እየተላጠ ተበልቶ ...ለእኔም ቅቤው እንደጀልባ የሚንሳፈፍበት ሾርባ (ልጅቱ ያመጣችው) አንኮላ በሚያክል ቀንዳም ኩባያ ተሰጥቶኝ ..."አቤት ሙያ " እያልኩ ግማሽ አድርሸው....ደግሞም "መልኩን ይስጠኝ እንጅ ሙያ ከጎረቤት " የሚባለው ተረት ትዝ ብሎኝ "አሁንይችን ልጅ መልኩን ብቻ ሰጥቶ ቢተዋት ኑሮ ከየትኛው ጎረቤት ሙያ ትማር ነበር ....መቸስ ከእማማ ቁንጥሬ አይሞከርም " እያልኩ ....ሳስብ .....እናቴ ድንገት ልጅቱን ...ምን ልትጠይቃት ፈልጋ እንደሆነ እንጃ እንዲህ አለቻት "ማን አልሽኝ ስምሽን እናትየ " ....ፓ! የኔ እናትኮ.... በአለም ላይ ያሉ ጋዜጠኞችን ሁሉ የምታስከነዳ ምርጧ ጠያቂ ናት ... ይሄን ጥያቄ ማሰብ ከጀመርኩ ስንት ቀኔ? ...ለዚህ አደጋ የዳረገኝስ ምን ሆነና ይሄው ማዙካ አፈረጠችዋ ...የህዝብ አይንና ጆሮ ሆነቻ! .... ልጅቱ በትህትና እንዲህ ስትል መለሰች

"ልእልት" !!

ይሄው ...ተረቱ ልክ ሲመጣ

...ስምን ማን ያወጣዋል ??????? መለዓክ !!

ይሄን ስም አሁን ማን ይሙት ገንፎ የበላ አራስ ጠያቂ ጎረቤት ሊያወጣ ይቻለዋል ???? በፍፁም !! ....በቃ መለዓኩ ራሱ ነው በክንፉ ለክቶ በሌላኛው ክንፉ ቆርጦና አስተካክሎ በልኳ አምጥቶ እዚህ ውብ ስጋና ደም ላይ ልክክ ያደረገው ...ልእልት ......."ልእልት ሆይ ! ለሽ አመት ብርቱካን ለሌላ ሽ አመት ሾርባ ይዘው ይጠይቁኝ !!"ሃሃሃ ! ል እ ል ት አፍ ላይ እንዴት ደስ የሚል ስም ነው ....የሆነ እንደፈንድሻ አፍ ሙልት አድርጎ ኮርሸም ሲያደርጉት ጥፍት የሚል አይነት ስም ....የማይጠገብ ስም ! ልእልት

....ታዲያ ይችን ልእልት በሽንኩርት ቢለዋ የሚፋለም ሙትቻ ንጉስ ላይ ማነው የጣላት ...? ደሃና ገበያ ሳይገናኝ ይሞታል ማለትኮ ይሄ ነው ! ልእልት ተመልሳ እንደምትጠይቀኝ ....ነግራኝና እንደገና ለባሏ የብልግና ድርጊት ይቅርታ ጠይቃኝ ...ወጣች.... ስትወጣ አይኔ ተከተላት ... አንዳንዱን ሲፈጥረው ከኋላም ከፊትም ከግራም ከቀኝም ውብ ያደርገዋል እንደልእልት ! ፈዘዝኩ ...የዘጋችው በር ላይ አይኔን ተክየ ቆይቸ መለስ ሳደርገው ማን ጋር ተገጣጠምኩ ? እናቴ ጋር !

"አቡቹ እንዴት ነው አሁን ቀለል አለህ?" አለችኝ !! አስተያየቷም ሆነ አነጋገሯ " እውነትም ልጅቱ ጋር እንደሚባለው ተነካክተሃል እንዴ አንተ ልጅ" የሚል ትዝብት ቢጤ ነበረበት ! ማ......እኔ ያንች ልጅ እዚች ልጅ ጋር ? ያውም እዚች ባለትዳር ልጅ ጋር ልነካካ ??????? በምን እድሌ !!

## ክፍል 4

አንዷት መልከመልካም ነርስ ነበረች እየተመላለሰች የምትንከባከበኝ ... ከስራዋ በተጨማሪ በመጣች ቁጥር የምታገኛቸው ወጣት ጓደኞቾ ጋር አንድ ሁለት ቃላት (አለ አይደል እንደማሸኮርመም የሚያደርጉ) ስለምትወራወር የእኔን ክፍል ከስራ ቦታነት በተጨማሪ እንደመዝናኛ ቦታ ሳታያት አልቀረችም

... ታዲያ ይች ነርስ እናቴም ጋር ከመግባባቷ ብዛት በቬርሙዝ የመጣ ቡና ሁሉ ካልጠጣሽ ብላ ስትለምናት ነበር ....አንድ ቀልቡ ያረፈባት የስራ ባልደረባየ ታዲያ ከእናቴ አፍ ላፍ አድርጎ እንዲህ አለ "ማዙ ተያት ስንወጣ እኔ እጋብዛታለሁ" የኔ የዋህ እናት በአንድ እጇ ቬርሙዝ በአንድ እጇ የቡና ስኒ እንደያዘች "ይሻላል ?...እሽ እንዳትረሳ ባይሆን ....ጥሩ ልጅ ናት አደራህን ጋብዝልኝ " ትልልኛለቻ ... ነርስየ ከሳቅ ጋር እሽኩርምም ....በለው ! በኔ ውድቀት ግማሹ ጀግንነቱን ሲያሳይ ....ግማሹ ነርስ ሲያሽኮረምም ...ተኝቸ አያለሁ !

እናቴ ... ጠያቂውን እያስተናገደች ... ሰው ጋፐ ሲል ትመክረኛለች "አቡቹ ጀግና ማለት ደረቱን ነፍቶ ችግር ላይ የሚጣድ አይደለም .... አዎ ጀግና ማለት የሚፈራበትን ጊዜ የሚየውቅ ነው "

በነገራችን ላይ ነርሷን የሚያሽኮረምመው ታዲዮስ ነው ...

ታዲዮስን ታውቁት የለ ? ...የሆነች ትንሽ መኪና ያለችው የስራ ባልደረባየ ብየ የነገርኳችሁ ...እንደውም የሆነ ጊዜ አንድ መኪና መንገድ ይዘጋበትና በብስጭት እጁን በመስኮት አውጥቶ አጉል የብልግና ምልክት መንገዱን ለዘጋበት መኪና ሹፌር ያሳያል ....ወዲያው ስልኩ ውስጥ "ቴክስት" ሲገባ ሰማ... ከፍቶ ሲመለከት "ጣትህን ይቁረጠው ስድ ዘልዛላ አሳዳጊ የበደለህ" የሚል እርግማን ... መኪናው ፈጠን ብሎ ከጎኑ ሲቆም በመስኮቱ ቀና ብሎ ያያል አዲስ የጠበሳት ልጅ አባት ናቸው ... ደግሞ ለከፋቱ እሷም ከጎናቸው ቁጭ ብላለች....ቀይ ፊቷ እሳት ለብሶ ..."

እና ምን አደረክ" ስንለው ...እንዲህ አለን

"ነዳጁን ሰጠ......ሁት"

በቃ!! ይባስ ብሎ ይሄን እየነገረኝ የእኔ ስልክም ውስጥ ቴክስት ገባ እንዲህ ይላል "አንድ አይነት ክንፍ ያላቸው ወፎች በአንድ ላይ ይበራሉ" የታዲዮስ ፍቅረኛ ናት ! ያሰድበን ምናለ ... ከዛ በኋላ ልጅት ጋር አይንና ናጫ ሆኑ !! እንግዲህ ለዛች ወፍ እግር ጓደኛው አሰደበኝ.... አሁን ደግሞ በስርዓት እንዳታስታምመኝ ይሄው ይችን ነርስ ልቧን ያጠፋልኛል ! እሷም ቀልቧ ሳይከጅለው አልቀረም ... እግዜር ይጠብቀኝ እንግዲህ ለሌላ የታዘዘ መርፌ

... ወንድየ አንበሳው በቢለዋ ከወጋኝ ዛሬ ሰባት ቀን ሞላኝ .... ጥሩ ጤንነት ቢሰማኝም ዶክተሩ መራመድና መንቀሳቀስ የለብህብም ብሎ ሆስፒታል አልጋ ላይ እንዳጣበቀኝ አለሁ ! ላይጠግን አይሰብርም እንዲሉ ሰባትኑም ቀን ል እ ል ት ሰባተኛው ሰማይ ድረስ መዓዛው የሚያውድ ሾርባ እያመጣች(የጠላቴን ገንዘብ ከወዳጀ እጅ ፉት እያልኩት እንደማለት) እንዲሁም እኔን ራሴን በደስታ ሰባተኛው ሰማይ የሚያደርስ ፈገግታዋን ይዛ እየመጣች አስታመመችኝ ... እንግዲህ እግዜሩ ባልን ወጊ ሚስትን አስታማሚ አድርጎ ሲሰጥ ቁስሉም የውሻ ቁስል ይሆናል መሰል ቶሎ ደረቀ !! (በነገራችን ላይ ያች እማማ ቁንጥሬ መቸለታ ነው መጡና አፋቸውን ሸርመም አድርገው "የውሻ ቁስል ቶሎ ይድናል" ብለው ሄዱ ....እናቴ ምርቃት መስሏት "አሚን" አለች እኔ ግን ቅኔዋ ገብታኛላች ...የሰው ሚስት ጋር የምትልከሰከስ **ውሻ !** ማለታቸው ነው ...ከምር ነቅቻለሁ ...እና "የውሻ ቁስል ያድርግልህ" እንጅ

"የውሻ ቁስል ቶሎ ይድናል " ይባላል ? ደግነቱ እንደገና ትላንት መጥተው ማዘርን ቀልቧን ገፈፏት ... ከምር ጠላቻቸው ...!!

"ማነህ አቡቹ ተሻለኝ ብለህ እንዳትንቀለቀል... ይሄ የቻይና ቢላ ለሌላ ነገር ሲሉት አይነቃም እንጅ ሰው ላይ ሲያርፍ መርዝ ነው ..." አሉ

"እንዴት ማለት እማማ " አለች እናቴ ተጨንቃ" አፋቸውን ጠራርገው ለወሬ ተዘጋጁና "እንዴት ማለት መልካም ....የዛሬ አመት እዚህ ቢሸፍቱ የሚኖር አንድ የአጎቴ ልጅ እንዲህ እንዳንተ በቢላ ተወግቶ ....እሱ እንኳን በሴት ተጣልቶ አይደለም ...ዘራፊዎች ናቸው (እዩልኝ ይችን እሾህ የሆኑ ሴት) ..... እና ዳንኩ ብሎ ፈንጠር ፈንጠር ሲል .... ምን የመሰለ ሸበላ በዲብሎማ ከተመረቀ ገና መንፈቅ ያልሆነው ልጅ አጣጥሞ እንኳን ደሞዙን ሳይበላ ... ቁስሉ አመርቅዞ ገደለው" አላሉም?! ....እናቴ ፊቷ ተቀያየረ ወጣ ሲሉ ገና በብስጭት እየተብከነከነች ብቻዋን ማውራት ጀመረች "ምን ያሉት ክፉ ናቸው ...የታመመ ሰው ፊት እንዲህ ይባላል?" ብላ ሙሉ ቀን ሸክኳት "ወቸ ጉድ ስንት አይነት ሰው አለ" ስትል ዋለች ...

ጭራሽ እንደውም እኔ ላይ ወረደችብኝ "ስንት ደህና ጎረቤት ባለበት አገር እንዲች ያሉት አባርሰኛ ሴት ጎን ሂደህ መከራየት ....ተሸሎህ ውጣ እንጅ እዛች ግድም አትሄዳትም" ብላ ተቆላጨች ! ወደማታ እኔ ረሳችው ብየ ነርሷ ስትመጣ "ቁስሉ ያመረቅዝ ይሆን እንዴ ሲስተርየ " ብላ በስጋት ጠየቀቻት ....ይች ሽብርተኛ ሴትዮ እናቴን አሸበሯት !

*** **** ****

"ወንዴ አንበሳው" ዛሬ ለሁለተኛ ጊዜ ፍርድ ቤት ቀረበ አሉ ... ጓደኛየ ታዲዮስ እንዳወራልኝ ከሆነ(መቸም የሱ ነገር እውነት ይሁን ቀልድ እግዜር ነው የሚያውቀው ) የወንድየ የምርመራ ፋይል እንደሚያሳየው ከሆነ.... በዛ ቀን ከቀኑ አስር ሰዓት ጀምሮ ብቻውን ግጨው ግሮሰሪ የሚባል ነበር ያመሸው (ግጨው ግሮሰሪ እዛው ኮንዶሚኒየማችን ግቢ ውስጥ ነው ያለው.... ግሮሰሪው እንኳን "ብስራት" የሚል ስም ነው የተለጠፈበት ....ግን ባለቤቱ በቮልስ መኪናው ብዙ ሰው ስለገጨ ግጨው ይሉታል ....በተለይ ወደኋላ ሲሄድ የሆነ ነገር ካልገጨ አይቆምም እያሉ ያሙታል )

እንግዲህ ወንድየ አንበሳው ብዙ ድራማዎችና ፊልሞች ላይ እንደሚታየው ወንድ ልጅ "ሚስቴ ከዳችኝ ብሎ" ሲያስብ እንደሚያደርገው ግሮሰሪው ውስጥ ጅን የሚባል መጠጥ እየጠጣ ሲጋራ ሲያጨስ እግረ ጭሰቱንና እግረ መጠጡን ሚስቱን እና እኔን እያሰበ ሲበሳጭ ድንገት "ሰይጣን" በሙዚቃ አስመስሎ ምን ማድረግ እንዳለበት ሹክ አለው (የሰይጣንን ስራ ተመልከቱ) ግሮሰሪው ውስጥ ከተከፈተው የባህል ሙዚቃ አንዷ ግጥም ከዛ ሁሉ የሰካራም ጫጫታና የዘፈን ግጥም ተለይታ ወንድየ ጆሮ ውስጥ ጥልቅ አለች !

ሚስቴን ነካ ብለህ ሚስቱን አትንካበት

በ "ቻይና" ቢለዋ አንጀቱን ግባበት

.... (አሁን በነፍሬው ሃይሉ ....በነጥላሁን .... በነሜሪ አርሜዲ ....በነአስቴር ...በነጅጅ... በነባህሩ ቀኘ ...በነማሪቱ ለገሰ ... በነቴዲ አፍሮ... በነግራጫው መሰንቆ በነስንቱ ዘፋኝ አገር እንዲህ ያለ ዘፈን ይዘፈናል?? ....ይሄ ግልፅ የጦርነት አዋጅ እንጅ ዘፈን ነው ...?) አሁን ይሄን ዘፈን የሰማ ሰው ማን ይሙት ፍቅረኛውን ወላ ሚስቱን ይዞ ወደክለብ ይሄዳል? ...በባለሁለት ክፋይ አገልግል በግማሹ ቋንጣውን በግማሹ ሰነፍ ቆሎውን ሰንቆ ወደጠላቱ እንጅ ... ወንዴ ተገለጠለት ...ወደቴፑ ዞሮ "ልክነህ ባትለውስ ምን ሚስት አለው ይሄ ነጠላ ጥላቢስ ወንደላጤ" ...እያለ ጮኸ ልክ በዚች ቅፅበት ደግሞ ሲያገጣጥም እኔ ደውየ የሚስቱን ስም ጠየኩታ !!

ሰኔና ሰኞ ገጠመ !

ወንዴ ተነስቶ ሲገሰግስ ወደቤቱ ሄደ ....ደረጃውን ባንዴ ሁለት ሁለቱን እየዘለለ በሩን ከፍቶ ሊገባ ሲል ሌላ ብሎክ ላይ በስህተት እንደወጣ አወቀ ተመልሶ ቁልቁልና ሽቅብ ተምዘግዝጎና ተተኩሶ የራሱን ቤት አገኘው ከፈተ .... ኪችን ገባ ...ጭራሽ ኪችኑን ሲመለከት የሚስቱ ናፍቆት ተቀሰቀሰበት ...ጠረኗ ጠረነው አጭር ቀሚስ ለብሳ ጉድ ጉድ ስትል ሶፋው ላይ ተጎልቶ የሚያያቸው ...እነዛ እንደሰም አእማድ የተዋቡ እግሮቿ ታወሱት ....እንደማር ሰፈፍ በኪችኑ ስትንሳፈፍበት ....ጠረኗ ከምትሰራው ምግብ ጠረን ጋር ተዳምሮ ሲጠርነው ...ፍርፍሯ፣ ጨጨብሰዋ፣ ገንፎዋ፣ ሽሮዋ፣ ክትፎዋ ታወሰው ...በተለይ"አፈር ስሆን ወንዴ " እያለች ባፍ ባፉ አጉርሳው ... እራት ከበሉ በኋላ እንደአንበውሃ ጥጋቡን ብትንትኑን የሚያወጣው እቅፏ ትዝ አለው ... ባንዴ ሆዱም ልቡም ጮኸበት ...ይሄን ሁሉ እህል ታችኛው ፎቅ ላይ የሚኖረው "አብርሃም" የሚባል ጠላቱ ሲያግበሰብሰውና ቆንጆ ሚስቱን ያውም በሱ አልጋ ትክክል የተዘረጋ አልጋ ላይ ሲያቅፋት ታየው እና አቅፎ አድሮ አይደል ጧት ሻንጣዋን ይዞ የሸኛት ሲል አሰበ

....ቢለዋውን መዥረጥ አድርጎ ተመልሶ ወደኔ ቤት ተንደረደረ !

"ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው አስቀድሞ መውጋት ሚስት አስኮብላዩን ነው " ከሚል ፉከራ እና ሽለላ ጋር .... የአብራሃምን በር አንኳኳ ...አብርሃም የዋሁ... የብሎኬት ድንኳኑን መግቢያ ከፈተለታ ....አገኘኛ ....!! እንካ ቅመስ!! ወንዴ በዚች ቅፅበት ከንዴቱ ነቃ! ከግሮሰሪ ጃስ ብሎ ያስሮጠው ዘፋኙ የማይኩን ገመድ ጠቅልሎ ከአካባቢው ድምፄ አውጭኝ ብሏል ! ወንዴን ውሃ በላት አለ ! ጥበቃወቹ እንደበርበሬ እየደለዙ ወደህግ ወፍጮ ሲወስዱት "እጀን በጀ" ሳይል አልቀረም .... ምን ዋጋ አለው መጠጥ ...ጎርፍ ነው ማደሪያ ሳይኖረው ግንድ ይዞ የሚዞር ደግሞኮ ግንዱን እያሳሳቀ ነው የሚወስደው "አፈር ስሆን እኔ ቤት እደር ቤተ መንግስት የመሰለ ቤት አለኝ" እያለ ....ከዛ አምነው ሲጨልጡትና ራስን ሲጥሉበት አውላላ ሜዳ ላይ እንደግሳንግስ ዘርግፎ እብስ !!

ወንዴ አንበሳው ራሱን አውላላው ላይ አገኘው ...ሽቤ !! ይሄን የምርመራ ፋይል እያስታወስኩ እንደተቀመጥኩ በሩ ተከፈተ ... ል እ ል ት!! ... ደግሞ አጋጣሚው እናተ ....ክፍሉ ውስጥ ማንም አልነበረም እናቴም እቤት ደርሽ ልምጣ ብላ ወጥታለች... እህቶቸም የሉም ( በሽጉጥ ታጅበው ማኪያቶ ለመጠጣት ወጣ ብለው ይሆናል) ማንም የለም ...ልእልት ገብታ ፈገግ አለች ... ነጭ ቱታ ሱሪ ወገቡ ላይ በራሱ ማሰሪያ ሽብ የተደረገ ለብሳለች አቤት እንዴት እንዳሽነቀጣት ....ይች ልጅ ግን ጡቶቿ እና ዳሌዋ የተያያዙት በአስማት ነው እንዴ

ከምር ቦርጭ ይቅርና ሆድ ራሱ የላትም ...በአየር ላይ የቆሙ ጡቶቿን አይቶ በቃ ወደታች ካለምንም ማያያዣ ረዘም ካለ ክፍተት በኋላ ሰፋ ያለ ዳሌ በቃ !! ደገፍ ብየ ወደተቀመጥኩበት መጥታ ሰሞኑን እንደጀመርነው ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳምን ...ያ ነብስ የሚያስት ጠረን ውጭ ባለው ፀሃይ ምክንያት መጠኑ ከፍ ብሎ ...እንደዳመና ሲከበኝ ልእልት የሚባል ብራንድ ሽቶ እላለሁ ለራሴ !! (ዘ ፐርፊውም የተባለው ፊልም ላይ ሽቶ ቀማሚው የቆንጆ ሴት ጠረን ለሽቶ መስሪያ ይሆነው ዘንድ ስንቷን ቆንጆ የጨፈጨፈው ወዶ ነው እንዴ) ፌስታሏን መደርደሪያው ላይ አስቀመጠች ...ደረጃው አድክሟት ነው መሰል ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ...ከምር አሁን ያ ጦረኛ ባሏ በዚች ቅፅበት ቢደርስ "ምናባታችሁ አድርጋችሁ ነው እንዲህ ትንፋሽሽ ቁርጥ ቁርጥ የሚለው " ብሎ ገጀራ መምዘዙ አይቀርም ነበር ....

"አብርሽ ....እንዴት ነህ አሁን " አለችኝ በፈገግታ አይን አይኔን እያየችኝ

እንዴት ነህ አትበሉኝ መልሴ ሊሆን ደህና

ህይወት ተጠያቂ ጠያቂም ናትና

....እንዲል ባለቅኔው ዝም ብየ አየ አየኋት ....ምናልባት ፈገግ ብየ ይሆናል ! ስታምር...... የሰው ሚስት የሰው ሚስት ይሉኛል.... ምንድነው የሰው ሚስት? ......ያ ሁሉንም ነገር "አለ" የሚባለው የእንግሊዙ ደራሲ ሼክስፒር እንዴት ስለሰው ሚስት ምንም ሳይል ቀረ ? ለምሳሌ " አንዲት ሴት የሰው ሚስት ከመሆኗ በፊት ሰው ነበረች" ለማለት አፉን ምን ሰይጣን ያዘው?? ል እ ል ት ወንበር ሳበችና ወደአልጋው ጠ......ጋ ብላ ተቀመጠች ...ወንበሩ እሷ ስትቀመጥበት ዙፋን መሰለኝ !!

“የዛሬውን አቀማመጧን ከትላንትናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሳነፃፅረው “... አስራ አንድ ነጥብ ዘጠኝ በሙቶ ከንፈሯ ቀርቦኛል !!

# ክፍል 5

እኔማ ችግር አለብኝ ...ከምር ችግር አለብኝ !! አሁን ሰው ሲሉኝ አሁን አፈር ...አሁን ደህና ነገር እያወራሁ በቃ ሰው አፉን ከፍቶ እየሰማኝ በመሃል ዘብረቅ አድርጌ ሰው ማስቀየም ! ኤጭ ይሄ ልክፍት ነው እንጅ ሌላ ምን ይባላል ... ለኔማ እንኳን ቢላ ጎራዴም ሲያንስ ነው የማረባ ...!! እግዜርም በኔ ነገር ተቸገረ ...አንድ ነገር ስፈልግ በልመና መቆሚያ መቀመጫ አሳጣውና “እስቲ ያውልህ” ብሎ ሲሰጠኝ ብልሽትሽት ! ለነገሩ ይሄን እንኳን እድል ያመቻቸልኝ እግዚአብሔር አይመስለኝም ....ሰይጣን ራሱ ነው .... ነዋ ....እና እግዚአብሔር የሰው ሚስት “ንፁህ” ካለው አልጋዋ “፣ቅዱስ” ካለው ትዳሯ አንስቶ እንዳረካት አድርጋት ያቻትልህ አይልም ....እሱ እንዲህ ያለው የተዝረከረከ ጉዳይ ውስጥ እንዲች ብሎ እጁን አይልክም ! .... ነቅቸበታለሁ ልእልትና እኔን እንዲህ ብቻችንን ያውም በመስኮት በኩል ፅዱ በነፋስ በሚንሻሻ ...አየሩ በተከፈተው መስኮት ለስለስ ብሎ የሚገባ ክፍል ውስጥ እንደሂሳብ ውጤት ቀንሶ ደምሮ ቁጭ ያደረገን ሰይጣን ነው

.....እንኳን እግሯን አይኗን እንኳ ከታመምኩ ጀምሮ ከእኔ ላይ ያልነቀለች እናቴን ዛሬ እቤቷ የላካት ሰይጣን ነው .... ንግስት ወንበሯን እንዲህ አፍንጫየ ስር አቅርባ በጠረኗ ተከብቤ እንድትቀመጥ ያደረገው ሰይጣን ነው .... ግን ሰይጣን ይሄን ሁሉ ውለታ የሚሰራልኝ ምናባቱ ሊያስከፍለኝ ይሆን ? እሱ እንደሆነ ሂሳቡ ጥልቅ ናት ... ሲጀምር ግብዣውን በነፃ ያውም “አፈር ስሆን” እያለ ያቀርብና ....መጨረሻ ላይ ቢሉን ሲያቀርበው ዋጋው ካለነፍስ አይመነዘርም ! ቢሆንም ዛሬ ሰይጣን የሰራት ስራ ከመሰይጠኑ በፊት ከነበረችው የዋህ ልብ የቀረች እንጥፍጣፊ ቸርነቱን ተጠቅሞ መሆን አለበት

.....ምን ዋጋ አለው ... እኔ ሁሉንም ነገር አበላሽሁት ! ልእልት አጠገቤ ከተቀመጠች በኋላ ትኩሳቴን ለመለካት ይሁን ወይም ሌላ እንጃ ግራ እጇን አንስታ ግንባሬ ላይ አሳረፈችና “ዛሬ ትኩሳቱም ቀንሶልሃል” ብላ ፈገግ አለች ...እጇን ግን ቶሎ አላነሳችውም ....((ትኩሳቴን ነው ወይስ የማስበውን የምትለካው )) የእጇ ልስላሴ ከደመና የተሰራ ጓንት ያጠለቀች ነው የሚመስለው ....እጇ ላይ ሰመመን የሚመስል ልስላሴ አለ ያውም ለብ ያለ ሙቀት ጋር ....ድንገት ግን በዚህ ልስላሴ መሃል እንደብርጭቆ ወረቀት የሻከረ፣ በዚህ ለብታ መሃል እንደበረዶ ግግር ግንባር የሚፈነክት፣ በዚህ ሰመመን መሃል እንደመድፍ ጩኸት አናት የሚያናጋ፣ በዚህ ስስ አነካኳ ውስጥ እንደ ብርቱ ኩርኩም ራስ የሚቆፍር ነገር ተከስቶ አስበረገገኝ .....ቀለበቷ ! የጋብቻ ቀለበቷ ....ሲነካኝ እንደሌላ የቢላ ጥቃት ነው ሰቀጠጠኝ .... እውነቱን ለመናገር የሰውን ሚስት ክፉኛ ለተመኘ ሰው የመሻት ኢጋንቱን የሚያባርር ፀበል በባለትዳሮች ግራ እጅ ጣት ላይ ይፈልቃል ....ቢባል ግነት አይሆንም ! ትዳር አንዳች ሃይል አለው ....ባለቤቱ ድንበሩን ካልከፈተው በስተቀር ....ቀለበት የትዳር ቅጥር ትልቅ ሰረገላ ቁልፍ ነው ....!! ድፍን የከተማው ወንድና ሴት ጣቱ ላይ ሰክቶት ወዲያ ወዲህ ሲል ቀላል ነገር ይመስላል እንጅ ቀለበት ከወርቅ የተሰራ መንፈስ ነው ....መሻቴ ለቅፅበትም ቢሆን እብድ የበላው በሶ ሲሆን ተሰማኝ ....ብትን !!

“ምነው ....”አለችኝ ልእልት በድንጋጤ እጇን ሰብስባ .... (ስትደነግጥ ስታሳዝን) ሳላስበው በርግጌ ይሆናል ያስደነገጥኳት ....አንግዲህ በዚች ቅፅበት ምናለበት “ትንሽ ቁስሉ አሞኝ ነው” ብየ ባረጋጋት ...ወይም “ኸረ ምንም አልሆንኩ “ ብል ....እኔ ግን የማይገናኝ ጥያቄ ልእልት ፊት አፈረጥኩና ፊቷን እንደበርበሬ አቀላሁት ... “ወንዴን እስር ቤት ሂደሽ ጠየቅሽው ? “ ግርምት ይሁን ትዝብት ባልገባኝ አስተያየት አየት አደረገችኝና ....አንገቷን ደፍታ ዝም አለች ከንፈሯ የተንቀጠቀጠ መሰለኝ ....ዝምምምምምም.... ድንገት በዝምታ ጋን የጠነሰሰችው የሚመስል እንባ ጉንጯ ላይ ተዘረገፈ .....ኸረ ጉዴ .... ይች ልጅ መፍሰሻ ያጣ ብዙ እንባ ውስጧ አለ ልበል ....ዛሬ ጋር ስታለቅስ ሳያት ሶስተኛዋ ! ባልሽን እስር ቤት ሂደሽ ጠየቅሽው እንዴ ማለት ምኑ ያስከፋል ....አዎ ወይም አልጠየኩትም አበቃ ....

"ይቅርታ ለማለት የፈለኩት " አልኩ

...በነጠላዋ ጫፍ አይኗንና አፍንጫዋን ጠራረገችና ...ከወንበሯ ተነስታ "ልሂድ" አለች .... "ልእልት ...ይቅርታ እኔ ላስቀይምሽ ፈልጌ አልነበረም ..." ተንተባተብኩ እኔ ስንተባተብ ልእልት ልትሄድ አንድ እግሯን ስታነሳ በሩ ተከፈተ ....እህቴ ! "ወይ ልእልትየ መጥተሽል እንዴ?" አለች ወደሷ በፈገግታ እየቀረበች ...ወቸ ጉድ እስቲ አሁን ከምኔው አውቃት ሰው ሚስት ስም ላይ "የ" ጨመረችበት ... ?? ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ እሟ እሟ እሟ ....አቤት አሳሳም .... እህቴ ከዘመቻ የመጣች ልእልትም የናፈቀቻት (ላለፉት ሰባት አመታት ያልተያዩ) እናትና ልጅ ነውኮ የሚመስሉት ! ደግሞ የልእልት ፊት ከምኔው ያንን ሁሉ በቦንድ እንኳን የሚገደብ የማይመስል እንባ ዋጥ አድርጎት እንዲህ ፈገግታ በፈገግታ ሆነ .....ውይ ሴቶች ! በዚህ አይነት እህቴስ ፍቅረኛዋ ጋር ሙሾ ስታወርድ እንባ ስትራጭ ቆይታ ላለመምጣቷ ምን ማረጋገጫ አለ ??

እህቴ ፈገግታዋ ፊቷ ላይ ሳይከስም ጠየቀች "ምነው ቆምሽ ልትሄጅ ነው እንዴ " ኧረ የኔም ጥያቄ ነው ...ልእልት "አዎ ከመጣሁ ቆየሁኮ ልሄድ ነው" ትላለች ብየ ስጠብቅ ... " አይ ሾርባ ልቀዳለት ስነሳ ነው የመጣሽው " ብላ እርፍ! ....አአአአአአአአአአአአአአ..... ሴቶች ምንም በማያስዋሽ ቦታ ወሪያቸው ዘነፍ ካለች ችግር አለ ማለት ነው (አንድ ጥናት አይደለም ያመለከተው እራሴ ከልምድ አውቃታለሁ)

.....አለ አይደል

"የእኔና አንተን ኩርፊያም ይሁን ቅይይም የግላችን ነው ....ሌላ ሶስተኛ ሰው በመሃላችን አያገባውም " አይነት መልእክት....ኧረ ቆይይይይ....ደግሞ ልእልት ካለወትሮዋ ዛሬ እንዴት ሾርባውን ረስታው ቆየች "ሳይቀዘቅዝ ቶሎ ልቅዳልህ" አልነበር የምትለው ....... ያዝ እንግዲህ ....የልእልታችን ነፍስ በትንሹ ሞቅ እንዳለው ሰው (በልክ እንደሰከረ) ገድገድ ያለች መሰለኝ .... ተመልሳ ቬርሙዝ ወደተቀመጠበት የብረት መደርደሪያ ሂዳ ሾርባ ስትቀዳ ....ውብ አቋሟን ከኋላዋ እየቃኘሁ (በአንድ አይኔ እህቴን በሌላኛው ልእልትን አየ እንዳልባል አድርጌ እያየሁ ሂሂ) ልእልት ስለተመለሰች ደስ ብሎኝ ....."ማነሽ ልእልት "የ" ..... ከበር መልስ በኔ ሂሳብ ሾርባ ቅጅላቸው " ማለት ዳድቶኝ ነበር ሂሂ

.....እህቴ እየተፍለቀለቀች ...."ልእልቴ ትንሽ ከቆየሽ ጓደኞቸን ሸኝቻቸው ልምጣ አቡቹ ጋር ተጫወቱ " አለቻት "ኧረ ችግር የለም ....የምቸኩልበት ጉዳይ የለም ደርሰሽ ነይ " አለቻ ልእልት ....እውነቷን ነው ምን ያስቸኩላል ....ባሏም ታስሯል ! "አንበሳው ፍርግርግ ውስጥ ነው " እህቴ ሹልክ ብላ ወጣች ....ልእልት በዝምታ የሾርባውን ኩባያ አቀበለችኝ....እና ወንበሯን ትንሽ ወደኋላ ሳብ አድርጋ እግሯን አነባብራ ተቀመጠች ...አቀርቅራ አንድ እግሯ ላይ ተንጠልጥሎ የሚወዛወዝ እግሯን እየተመለከተች ....ዝም ብየ ሾርባየን መምጠጥ ጀመርኩ .... ድንገት ቀና ብላ "ቅቤ አነሰው እንዴ " አለችኝ ...ሃሳብ ውስጥ ሰምጨ ዝም ብየ እጠጣለሁ እንጅ ይጣፍጥም ይምረርም አላጣጣምኩትም ነበር

"ኧረ አሪፍ ነው " አልኳት .....

እንደገና ረዥም ዝምታ በመካከላችን ሰፍኖ ቆየና ልእልት ያለምንም መንደርደሪያ እንዲህ አለች (ስታወራ ለእኔ አይመስልም)

"ወንዴ ባለጌ ነው " ...ደነገጥኩ ! ምን ልበል ....እሷም አምልጧት ውስጧ ስታስበው ቆይታ የነገር እርሾ ያቦካው ብሶቷ ገንፍሎ ይመስለኛል ቃል ሁኖ ያመለጣት ....እና ምን ልበል

"ልክ ነው ባልሽ ባለጌ ነው " ልበል ... ወይስ ምናባቴ ልበል ....ነገ ዙረው ቢታረቁ (አይበለውና) ለምን "አለ" መባል ይትረፈኝ ብየ ላፅናናት አሰብኩ

"አይ ....ማንም ሰው በብስጭት ያልሆነ ነገር ሊሰራ ይችላል በዛ ላይ ሞቅ ብሎት ነበር ...ስለዚህ እኔን በቢለዋ መውጋቱ ባለጌ አያስብልምኮ ልእልት ...."

"አንተ ላይ ስላደረገው ነገር አይደለም ያወራሁት አብርሽ " አለችና ኩም አደረገችኝ .....ኩም ብየ ሳላባራ .....በቁጣ የሚንተገተጉ አይኖቿን ወደኔ አዙራ "ታውቃለህ እኔ ተጣላሁ ብየ እንኳን ባሌን ማንንም የማማ ሴት አይደለሁም ....ላለፉት ሰባት አመታት አንዲት ቃል ለአንድም ሰው ስለወንዴ ተንፍሸ አላውቅም ...ለእናቴም ቢሆን ....." አለችና ስለወንዴ ....ትዘረግፈው ጀመረ ...እግዚዮ ይሄ ኮንዶሚኒየም ስንቱን ጉድ ነው እንዳነባበሮ ደራርቦ የያዘው ... ልእልት በእልህ የሚንተገተጉ አይኖቿን ተከላብኝ በጓዳ ታፍኖ የኖረ ገመናዋን ትዘከዝከው ጀመረ ...ከምር ተሳቀኩ ....አሁን ወንዴ አንበሳውን ይሄ ብሽቅ ብለው አንባቢ "ሚስቱን ስለከጀልካት ወደሷ ማድላትህ ነው " ይለኛል ...ግን አይደለም ... ማንኛዋም ሴት ብትሆን ይሄን ያህል ግፍ ከምትሸከም እንደኔ ቢለዋዋን ቀምሳ እርፍ ብትለው በስንት ጠዓሙ ....!! እኔ የምለው ግን እሽ ነገሩስ መቸም አንዴ ሆነ ...ሲሆን ኖረ ልእልት እንዴት ለእኔ ነገረችኝ ....ከቢለዋ የባሰ ግፍ ተሸክሜ ኑሪያለሁ ብላ ባሏ ላደረሰብኝ ጥቃት በሷ በኩል የሚደርሰኝን ይቅርታ እና ማፅናናት እየሰጠችኝ ይሆን ?

ልእልት ያንን አስገራሚ ህይቷን እያወራችኝ ....ቆይታ እህቴ ስትመጣ ተሰናብታን ሄደች .....ልቤ አብሯት ሄደ .....ልክ ልእልትን ሸኝታ በሩን እንደዘጋች ....እህቴ አንድ አይኗን ጨፍና ወገቧን ልክ እንደነገረኛ ባልቴት ይዛና ፊቴ ልክ እንደሞዴሊስት አንድ ሁለቴ ሰበር ሰካ ብላ

"አጅሬው የሚባለው እውነት ነው እንዴ ....??" አለችኝ

"ምኑ? "

"ባክህ ገብቶሃል! ....ልጅቱ ጋር ጉዳይ ሳይኖራችሁማ አይቀርም!! ..."

"ዝም ብለሽ የመጣልሽን አታውሪ ባክሽ... ይልቅ የምጠጣው ውሃ ስጭኝ" አልኩ ቆጣ ለማለት እየሞከርኩ

"ባክህ አልጠማህም " ብላ የልእልት ወንበር ላይ ተቀመጠች ...ከምር እውነቷን ነው አልጠማኝም ነበር (ቡዳ የሆነች ልጅ) አንገቷን ሰገግ አድርጋ ....

"ስማ ቅድም ስመጣ በሆነ ነገር እንደተቋቆራችሁ ባንኘባችኋለሁ .... አረጋጉት ብየ ነው የወጣሁት እሽ? ማንንም አልሸኘሁም "

"አንች ስራ ፈት ነሽ አቦ "

"ተው እንጅ ....እና በየት አገር ነው በሽተኛ ጠያቂው ጋር ተጣልቶ እንደዛ ተወርውራ ልትሄድ ያለች ሴት እኔን ስታይ የተረጋጋችው ?....ደግሞ አልቅሳ ነበር "

"እንዴዴዴዴደዴ አንች ልጅ ዛሬ ምን ሁነሻል " አልኩ ከምር ተበሳጭቸ .....ሰው የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩት የህል መሳቅ ብቻ ሳይሆን የጠረቀሙት ያህልም ይቆጣል ....ተቆጣሁ ....

"አብርሽ ....እኔ ሚስጥርህን ላስፈለፍልህ አይደለም ....ግን ይሄ ነገር ሸክኮኛል ....ከባለትዳር ሴት ጋር መሳፈጥ ከቢላም የባሳ መዘዝ ነው የሚመዘው ... እንደውም ይሄን ያህል መመላለስም አያስፈልጋትምኮ ....ባሏ በቢላ የወጋህ ሳይሆን ራሷ በመኪና ገጭታህ ምታስታምምህኮነው ምትመስለው ....እግዜር ይስጥልኝ ብለህ በጊዜ ሸኛት ልጅቱም እንዳንት ጅል ቢጤ ነች ተያይዛችሁ እንዳታልቁ ....በኋላ የለሁበትም ....አሁንም ምን ከመሳሳለ ፕሮግራም ቀርቸ ነው እዚህ አንተን የማስታምመው....

" ተንቀለቀለችብኝ እህቴ ... ይች ልጅ ግን እኔ የት ሂጀ ነው እንዲህ ጣጥላኝ ያደገችው ....ከምር ታላቄ መሰለችኝ! ያለችው ሁሉ ልክ ነው ይገባኛልኮ ግን ምን ላድርግ ልእልትን ከፉኛ ነው የምናፍቃት ...

"ለማንኛውም ሁለተኛ በዚህ ጉዳይ እንዲህ ስትይ እንዳልሰማሽ ....ምንም አይነት ግንኙነት የለንም ...እግዚአብሔርን "እስካሁን" ምንም ርሌሽን የለንም ...." አልኩ ...አመነችኝ እህቴ ካላመረርኩ እንደማልምል ታውቃለች !

“ይሄን በመስማቴ ደስ ብሎኛል …ውዱ ወንድሜ …..ግን

“እስካሁን “ የሚለው ቃል “ካሁን ኋላስ” የሚል ጥያቄ አነሳ ዘንድ ያስገድደኛል ብላ ….ከት ከት ብላ ሳቀች …እኔም ሳኩኝ አሁንስ …ምናባቴ ልበል ታዲያ …..

“እሽ ውሃ ስጭኝ …. “

“አሁን የእውነት ጠምቶሻል ታስታውቂያለሽ ….ውሃ ውሃ አሰኘችህ …አይደል ….ግንኮ ልጅቱ እንዴት አባቷ እንደምታምር …” ብላ ውሃውን አቀበለችኝ …..ስጠጣ ትክ ብላ እያየችኝ ነበር ጥናት የሚመስል አስተያየት …. በቀልዷ ውስጥ ስጋቷ ቁልጭ ብሎ ይታየኝ ነበር …. ቢሆንም ወዲያው ልእልት የነገረችኝ ጉዳይ አእምሮየን ሞላውና እህቴን በቆመችበት ረሳኋት !!

# ክፍል 6

ዛሬ በጧቱ አንድ ጅንስ ሱሪና ነጭ አዲዳስ ሲኒከር ጫማ ያደረገ (እድሜው አምሳ የሚሆን እንቢ አላረጅም ነገር) ማስቲካ የሚያላምጥ ….ደግሞ በሽቶ ተጠምቆ የወጣ የሚመስል …. (ልክ ሲገባ ክፍሉ በሽቶ ተሞላ) ወደተኛሁባት ክፍል ገባና መነፅሩን አውልቆ አንዴ ክፍሏን በትእቢተኛ አይኑ ገርምሟት ሲያበቃ …ወደእኔ በመነፅሩ እጀታ እየጠቆመ እህቴን እንዲህ ሲል ጠየቃት

“ አብርሃም ማለት እሱ ነው? “ እንግዲህ እኔ አልተኛሁ …አፍጥጨ እያየሁት ነው… ልክ እዛ እንደሌለሁ አክብራው ለቆመችው እህቴ ሰላምታ እንኳን ሳያቀርብ በንቀት ጥያቄውን ፊቷ ላይ ወረወረላት ……

“አወ …ልክነዎት ይቀመጡ አለችው “ በአክብሮት እየተሽቆጠቆጠች …..ተመልሶ ክፍቱን ትቶት በገባው በር አንገቱን ብቻ ብቅ አደረገና “ ና” የምትል ቀጭን ትዛዝ ውጭ ለቆመ ሰው ተናገረ …. በፌስታል ሙሉ የታሸገ ጭማቂና ፍራፍሬ ያንጠለጠለ ወጣት እየተሽቆጠቆጠ ገባ ….. ሰውየው አለቃው ነው የሚመስለው …እንደውሻ ጅራቱን እየቆላ ከሰውየው ስር ቆመ …..ይሄ ትእቢተኛ ሰውየ እህቴ ያስጠጋችለት ወንበር ላይ አረፍ አለና ገና ከመቀመጡ የጫማውን ሶል ለእኔ ሊያሳይ የመጣ ይመስል አንድ እግሩን ሌላኛው ላይ ጭኖ “እንኳን ተረፍክ ወንድሜ” አለኝ ….አንቱም አንተም ለማለት የሚቸግር ሰውየ ስለሆነ እኔ ራሱ ተደበላለቀብኝ … አነጋገሩ መትረፌ የገረመው አይነት ቅላፄ አለው (አለ አይደል ወንድየ በቢላ የወጋቸው ሰዎች የመትረፍ እድላቸው ከሙቶ አንድ ነው የሚል አይነት) ቀጠል አድርጎም “ ነገ ዛሬ እመጣለሁ ስል ስራውም ምኑም ሲያዋክበኝ ሳላይህ ቀረሁ ….አሁን እንዴት ነህ ….ለነገሩ ብዙም እንዳልተጎዳህ ሰምቸ ነበር “ አለኝ …ኧረ ይሄ ሰውየ ማነው ?…..መነፅሩ መስተዋት ላይ ትንፋሹን እፉ እፉ አለና መሃረሙን አውጥቶ እየወለወለ … “በዚህ ዘመን ሞልቶ ለተልከሰከሰ ሴት እንዴት በሴት ትጋጫላችሁ …? አትረቡም!! ካፍቴሪያ ብትገባ ሴት ነው … መንገዱን ሴትና ሴት የጫነ መኪና ነው ያጣበበው….የትም ብትሄድ ሴት ነው ….. የዛሬ ልጆች “ደሃ ልጅ አፈር አበድሩኝ ብሎ ይጣላል “ እንደሚባለው ናችሁ ጎንበስ ብሎ መዝገን ሲችል ….ሃሃሃሃ” አለ …ፌስታል ተሸካሚው ልጅ አለቃው ስለሳቀ ለማጀብ ነው መሰል ሂሂሂሂ እያለ አጀበው ….የልጁ ድምፅ የዛገ የብረት በር ሲከፈት የሚያሰማው አይነት ሲጥሲጥታ ይመስላል …ሰውየው ልጁን በፈገግታ ዞሮ አየው …ልክ ሲያየው “ሳቅ ጨምር” ያለው ይመስል በዛ ድምፁ ፍርፍር ብሎ ሳቀ ! መሳቅ ብቻ መሰላችሁ የሰውየውን ንግግር አብራራው “ጋሽ ያለው ነገር ልክ ነው …ዛሬኮ አዲስ አበባ ላይ ዘጠና ፐርሰንቱ ነዋሪ ሴት ነው ….በዚህ ሰዓት በሴት መጣላት ያስቃል ሂሂሂ” እኔም እህቴም ተገርመን እናያቸዋለን …..

“እ ….አብርሃም ….ይቅርታ አላወከኝም መሰል…. የወንድየ አባት ነኝ …. ያው የመጣሁት ሁለታችሁም ያደረጋችሁት ነገር ልክ አለመሆኑን እንደአባት ለመገሰፅና ነገሮችን በቀላሉ ለመፍታት ነው ….ይችኮ ይሄን ያህልም የምትጋነን ነገር አልነበረችም ….እኔ አባትህ ስንቱን ነገር ፈትቸዋለሁ …. እንኳን በጩቤ መጫጫር በሽጉጥ ስንፈሳፈስ በብረት ቦክስ ስንቱን ጥርስ ስናረግፈው ….ነው የኖርነው …ምናላት ይች …?!.” አለ

ሰውየው .....ታዲያ ከመጀመሪያው አይናገርም?..... ልጅየው ከዚህ ሰው ወጥቶ እንኳን ቢላ መድፍ እየጎተተ ቢመጣ ምን ይገርማል ...ዘረ እብሪተኛ !! ልጁ ትልቅ ነገር እንደሰራ ሲጀነን ደግሞ አለማፈሩ !

"ጋሽ አሁን ያለው ነገር ልክ ነው ... ምናላት ይች በ"ፒስ" የምታልቅ ነገር ነች .... ጋሽ እንኳን ያኔ አሁንም ስንቱን ነው ካፈር የሚደባልቀው ...." አለ ፌስታል ተሸካሚው .... "እንደውም ቀደም ብየ ብደርስ ደህና ሆስፒታል ታክመህ እስካሁን ስራ ላይ ነበርክ ...እዚህ ስርቻ ውስጥ ይሄን ያህል ቀን ..." ብሎ በአይኑ ክፍሏን ገረመማት የወንድየ አንበሳው አባት ሌላው "አንበሳ".... የሚገርመው እስካሁን እኔም እህቴም አንድ ነገር አልተናገርንም ሰውየውም ግድ ያለው አይመስልም ... " ጋሽ አሁን ያለው ነገር ልክ ነው ...ስንት ስፔሻሊስት ሃኪሞች በእጁ ነበሩ ...እንዳዘዛቸው የሚሆኑ የሰው ጭንቅላት ነቅላችሁ ግጠሙ ቢላቸው የሚገጥሙ ..... " ኧረ ይሄንን ልጅ ዛሬ አንድ በሉልኝ ... እጎኔ በጠቀመጠው ልእልት ባመጣችው የሾርባ ብርጭቆ አናቱን ልለው ትንሽ ነው የቀረኝ ከምር ! የምን አስተርጓሚ መሆን ነው ....ደግሞኮ ልጁ ስለሰውየው እያጋነነ ሲናገር ሰውየው በፈገግታ እየተመለከተው "ጥሩ ብለሃል" አይነት ራሱን በመስማማት ይነቀንቅለታል .... ሰውን ምን ነካው ገድሉን አጅቦ የሚጮህ በቀቀን ይዞ ይዞራል እንዴ ? "እ....እህቱ ነሽ ....?" አላት እህቴን

"አዎ"

"ኦ የቆንጆ ልጅ ወንድም ደብድቦ ይሄ ባለጌ ልጅ ....እንዲህ ከሚያንከራትተኝ እንዳንች አይነት ቆንጆ ጋር ተዛምዶ ቢያኮራኝ ምን ነበረበት ሃሃሃሃ " እህቴን በጎረምሳና እና አስቀያሚ አይን ከእግር እስከፀጉሯ ተመለከታት ...እግሯን ሰብሰብ ስታደርግ አያታለሁ ! "ያው መቸም ጉዳየን ትረጅዋለሽ በእናተ የመጣ ፀብ አይበርድም ወጣትነት አለ በዛ ላይ ወንድየ አስተዳደጉም ባህሪውም ፍርሃት የሚባል ነገር አያውቀውም ....ሰው ላይ አይደርስም ከደረሱበት ደግሞ አይመለስም ይገርምሻል ... ያች ሚስት ተብየዋን ከአመድ ላይ አንስተን እዚህ ያደረስናት እኛ ነን ....እንዲህ አፍንጫው ስር ሌላ ወንድ ጋር ....." "አሁን ጋሽ ያለው ነገር ልክ ነው ....ልእልት ወንዴ ጋር ስትተዋወቅ ፀጉሯ ራሱ እንደጃርት የቆመ ነበር ...ምን ፀጉሯ ብቻ...."

"ይቅርታ የኔ ወንድም እሳቸው እየተናገሩ ነው አይደል እንዴ ....የአንተ ማብራሪያ ምንድነው ....." አልኩት ደሜ ፈልቶ .... "አይ ጋሽ ባሉት ላይ ለመጨመር ያህል ነው ....ልእልት ያደረገችው ነገር በጣም ሽም ነው ...ወይ ሰው ግን ....ማን ይታመናል በዚህ ዘመን " ብሎ ምራቁን ወደመሬት ትፍ አለ ... ሲያወራ ልክ እንደ ነገረኛ ሴት ነው ...አንገቱን እየሰበቀ ....ቀፈፈኝ ! ሰውየው ቀጠሉ ..."እየውልህ አብርሃም በቃ የሆነው ሆነ ....ስህተቱ ያንተም የወንድየም አይደለም ...የዛች የውሻ ነው ... አሁን መሆን ያለበት ..."ከምር ልእልትን ውሻ ሲሏት ሰውነቴ ሰማ እንደነካኝ ሲለበልበኝ ተሰማኝ .... "ይቅርታ .....ስህተቱ የእርሰዎ ልጅ ነው ...ባልተፈጠረ ነገር በራሱ ቅዠት ያውም እንደሚሉት ጀግና ስለሆነ ምናምን ሳይሆን በመጠጥ ጥንቢራው ዙሮና ባላሰብኩት ሰአት የፈሪ ብትር ያሳረፈብኝ ...ይሄ የሚያዳንቁት ባለጌ ልጅዎት ነው ... ለመሆኑ እንደአባት ትንሽ እንኳን በልጅዎት ድርጊት እንደመፀፀት ጭራሽ እዚህ ድረስ መጥተው የማይረባ እንቶ ፈንቶ ሲያወሩ አያፍሩም" ብየ ልቀጥል ስል

"አብርሽ " አለችኝ እህቴ

...ሲተረጎም ዝም በል ማለት ነው ! ቁጣየ ሲንቀለቀል ሰውየው ያነባበሩትን እግራቸውን አወረዱ ፌስታል ያገቱም እግሩን አወረደ ...እኔም ስላልወጣልኝ ቀጠልኩ...

"ልጅዎት በመታሰሩ እግዚአብሔርን ያመስግኑ ... ከዚህ በኋላ እፊቴ ባገኘው በሂዎት አያገኙትም !! ሁለተኛ ደግሞ እዚህ መጥተው ደህና ልጅ እንዳሳደገ ሰው እንዳይኮፈሱብኝ !!"

"ኖኖ አብርሃም ....ልል የፈለኩት ምን መሰለህ ...ድርጊቱ ተገቢ ነው እያልኩ አይደለም ....ግን ወንዴ አንድ ፍሬ ....ልጅ ነው ..."

"ምን ልጅ ነው .....እኔን ዘጠኝ አመት በእድሜ የሚበልጥ ሰውየ ልጅ ነው ይላሉ እንዴ " አፈጠጥኩባቸው ....ሰውየው በልጃቸው ነው የወጡት ቆጣ ሲሉባቸው ይደነግጣሉ ...ማታ ቢላ ይዘው ካልተመለሱ !!

"አይ ጋሽ ሊል የፈለገው ..." አለ ፌስታል ያዡ

" አንተ ዝም በል በናትህ ...ወንድ ልጅ ቆፍጠን ሲል ነው ደስ የሚለው ምን ጋሽ ጋሽ ትላለህ " አለችው እህቴ ሽምቅቅ አለ ! ሰውየው ረጋ ብሎ ወደእኔ አጎበደደና "አብርሃም ...እባክህ ብስጭትህንም ቁጣህንም ተቆጣጠረውና የሚሻለውን እንነጋገር"

"የሚሻለውንማ ህግ ይዞታል ...መጥተው ስላዩኝ እግዜር ይስጥልኝ ...ካሁን በኋላ እዛው ፍርድ ቤት እንገናኝ "

"አይ እንዲህማ አይደረግም አብርሃም .....ማንም ሰው ይሳሳታል ...እየውልህ ...እኔ ለህክምና ያወጣሃውን ወጭ እሸፍናለሁ ....ልጆ ስንት ቀን ሙሉ ከማንም ወሮበላ ጋር ቁንጫ እየበላው መታሰሩ በራሱ ትልቅ ቅጣት ነው ....እኔም ይቀጣ ብየ ነው "ይሄን ሁሉ ቀን" ዝም ያልኩት ...እንጅ ባለስልጣኑም ፖሊሱም ዳኛውም በእጀ ነው ...."

"ጋሽ አሁን ያለው ልክ ነው .... ጓዳ ጎድጓዳውን እንደእጁ መዳፍ ነው የሚያውቀው ....ለጋሽ ይች ምናላት ..." እህቴ ዞር ብላ አየችን እኔም በግርምት አየኋት (ምን በሽታ ነው ይሄን ልጅ የለከፈው )

" ጥሩ እንግዲያውስ እርሰዎ ልጅዎትን ከዛች እስር ቤት በብርም ይሁን በዘመድ ያስፈቱት ቀን እኔ ደግሞ

ወደማይመለስበት እልክለዎታለሁ ....እኔ ብምረው እንኳን ዘመድና ጓደኞቹ አይለቁትም " ስል ከብዙ ጉራ ከትንሽ ውሸት እንዲሁም ከመካከለኛ እልህ የተቀመመ ፉከራ ፎከርኩ ! አባትየው ግን ካሰብኩት በላይ በድንጋጤ ሙሽሽ ብለው አንዴ እህቴን አንዴ እኔን እያዩ ....ቆዩና ..."ቆንጆ ወንድምሽን ምከሪው እንጅ" አሏት .....አሁንም ትእቢታቸው በደንብ አልተነፈሰችም !

" ኧረ እመክረዋለሁ .... " አለችና ወደኔ ዙራ ኮስተር ባለ ንግግር " ወንድሜ አንተ አትነካካ ...ያንን ጫት የጨረሰው ልጅ ገና ከእስር ቤት እግሩ ሲወጣ እኔ ራሴ አንዱን ጎረምሳ ልኬ ነው የማስደፋው " ብላ በእልህ ወደሰውየው ዞረች እና እጇን አነባብራ አፈጠጠችባቸው! ሰውየው ቀልቡ ተገፈፈ ... ከምር አንዴ እኔን አንዴ እህቴን ተራ በተራ እየተመለከተ ግራ ተጋባ ... የሆነ የአእምሮ ችግር ያለብን ሳይመስለው አልቀረም ...." ይቅርታ ጠየኩኮ ... በቃ የለት ግጭት ነው ...ተሳሳተ ልጅ ነው .... አብርሃም እባክህ እሽ በለኝ ጉዳዩን በሽምግልና እንጨርሰው.... እኔ ላንተ የፈለከውን ያህል ካሳ ልክፈል ...እኔ ግርማቸው እንኳን ላንተ ለስንቱ እተርፋለሁ ሰው ነው የማደርግህ" ብሎኝ እርፍ ...

"ኧረ ሰው የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው አንቱ ሰውየ

....በገንዘበዎት ከሚመኩ ቢያንስ ከልብዎ ይቅርታ እንኳን ቢጠይቁ ምናለ " አለች እህቴ.... አሁን ከምር እንደተበሳጨች ታስታውቃለች ....የወንዴ አንበሳው አባት ልባችን ዝቅ እስከሚል ብዙ ብዙ ትእቢት የቀላቀለ ውሽንፍር ወሬ ሲያዘንብብን ቆይቶ እንደሚመለስ ነግሮን ወጣ .... ሲወጣ " ይችን እስቲ ያዝ ባዶ እጀን ከምመጣ ብየ ነው" ብሎ ፌስታሉን ወደአልጋየ ጠጋ አድርጎ አስቀመጠ እና እየተጀነነ ያንን ቶስቷሳ ልጅ አስከትሎ ወጣ .....! ልጆ ሲወጣ ዞር ብሎ ልክ እንደቅብጥብጥ ሴት እጆን እየወዘወዘ "ባ....ይ " አለን !

ሰውየው እንደወጡ ...ሁለታችንም ከት ብለን ሳቅን .....እህቴ በእጁ አየሩን ወደአፍንጫዋ እያርገበገበች " አንተ ሽባው ግን ሽቷቸው እንዴት ይጥማል ...ይሄንን ሳምንት ሙሉ የሾርባና መድሃኒት ሽታ ያፈነው ቤት ሙዱን ቀያየሩትኮ ...በአፍንጫየ ነበር ትእቢታቸውን ስሰማው የነበረው ሂሂ ...ምን ዋጋ አለው ትእቢታቸው ከሽቶው በላይ ገኖ ይቀረናል " ብላ ያመጡትን ፌስታል ወደመደርደሪያው ልትወስድ ስታነሳው ቡትርፍ ብሎ ፍራፍሬ መሬቱን ሞላው ... የታሸገ ሶስት ኪሎ የሚሆን አፕል ...የታሸገ የሆነ ነገር ጭማቂ ...በስሎ የጠቆረ የወይን ዘለላ ... እና ስሙን የማላውቀው የታሸጉ ባቄላ ባቄላ በሚያካክሉ ፍሬዎች ....ፌስታሉ ሞልቶ ነበር ....እህቴ የተበተነውን እየሰበሰበች "የሚስታችሁ አባት ይሄን ሁሉ ፍራፍሬ ኬት አመጡት ባክህ ...በትእቢት ከገነት ተባረው ነው መሰል የመጡት

ሂሂሂ” ልእልትን “ሚስታችሁ “ እያለች ማውራት ጀምራለች ...ፍራፍሬውን አስቀምጣ አንዱን አፕል አወጣችና ...አጠበች ....ከዛም ወደወንበሯ ላይ ተቀምጣ ኮርሽም አድርጋ አንዴ ገመጠችለትና

“እኔ የምልህ አብርሽ .....ወንዴ አንበሳው በዘጠኝ አመት እንደሚበልጥህ በምን አወክ .... ?” አለችኝና የነገረኛ ፈገግታዋን ፈገግ አለችው ...እንግዲህ ጀመራት ...አንዲት ነገር አታመልጣትምኮ ....(አምልጦኝ በዘጠኝ አመት እንደሚበልጠኝ የተናገርኩት ልእልት ነግራኝ ነበር )እንደው ብቻየን አፍኘ ከምይዘው ብየ ለእህቴ የልእልትን ታሪክ ልነግራት ወሰንኩ እና እንዲህ ብየ ጀመርኩት

“ ወንዴ አንበሳው ባለጌ ነበር ...ያውም ምንም ሽም የሌለው ባለጌ ...”

“ባለጌም ቢሆን ሚስቱን መመኘት የለብህም ....” ብላ ከነጀሰችኝ በኋላ ታሪኩን ለመስማት ተመቻቸች .....ልክ ልእልትን ሁኘ የሰማሁትን ነገርኳት ...

“ይሄ ብሽቅ እኔ ብሆን የተኛበት ነበር ጋዝ አርከፍክፌ እሳት የምለቅበት “ ብላ እጇ ላይ የተረፋትን አፕል በብስጭት ወደቆሻሻው ቅርጫት ወረወረችው ... ትራፊው አፕል ልክ ጎበዝ የባስኬት ቦል ተጫዋች እንደወረወረው ኳስ ቅርጫቱ ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ !

## ክፍል 7

“ከደነዘዘ ሃብታም ከመወለድ ነቃ ካለ ድሃ ቤተሰብ መውጣት በስንት ጠዓሙ “ አለች ልእልት ታሪኳን ስትጀምርልኝ .... እኔ እንኳን “ገንዘብ የደነዘዘውን ሁሉ ነቃ የሚያደርግ አስማት ነገር” እንደሆነ እየሰማሁ ስላደኩ አባባሏ ብሶት የወለደው የተሳሳተ ጥቅስ መስሎኝ ነበር .... እውነቴን ነው “እከሊት ብር ካገኘች በኋላ ቆንዳ ቆንዳ አለች ....ወይ ገንዘብ መድሃኒቱ.....እከሌ እንዴት ነው ንብ የሆነው ጃል ...ድሮኮ ፀሃይ እንደቀጠቀጠው መጋዣ አንድ ቦታ ቁሞ ራሱን ከመወዝወዝ በስተቀር የማይላወስ ፈንዜ ነበረ” ይባላል .... እንደውም አንድ የድሮ የህዝብ እንጉርጉሮ ላይ “ባጥፈው ደነዘዝኝ ምላሴን እንደ,ግር ጤናና ገንዘብ ነው የልብ የሚያናግር “ የሚል ግጥም ሰምቸ አውቃለሁ

....እንግዲህ ሆድ የባሳት ልእልት ግን “ሲያጥፉት ከሚደነዝዝ ምላስ በላይ ሲያቅፉት የሚደነዝዘው ያጣ ሳይሆን ድንዙዝ ሃብታም የወለደው ባል ነው ትለኛለች .... እሰማለሁ “እንዴት ማለት ልእል((ቴ)) እያልኩ ....

“...ወንዴ ጋር የተዋወቅነው የአስራአንደኛ ክፍል ተማሪ እንደነበርኩ ነው .... ያኔ ትምህርት ቤታችን ጎን የአባቱ ጣውላና ሲሚንቶ መሸጫ ትልቅ መጋዘን ስለነበር(አሁንም አለ) “እዛ ስመላለስ አየሁሽ “ ነው የሚለው እሱ .... አንድ ቀን መኪናውን አቁሞ(ጥቁር ቢኤም ደብሊው) አራት እንሁን አምስት ሁነን ከቆምን ጓደኞች መሃል በመስኮቱ አጎንብሶ ... ወደመኪናው እንድሄድ በምልክት ይጣራል ....ሁሉም ጓደኞቸ ኮስተር ቆጣ ብለው (ልክ መጠራታቸውን እንዳልፈለጉት ሁሉ) “እኔን ነው ?” አይነት ጥያቄ በምልክት ሲጠይቁ እራሱን እየነቀነቀ ሁሉንም እንዳልሆነ ሲያሳይ ..... እንግዲህ ሁሉም ተዳርሰው ተራው እኔ ላይ ደረሰ እኔን እንደሆነ ቢገባኝም እንዳላየ ፊቴን አዞርኩ (ወጉ ነዋ ኩራት..... በውስጤ ግን ትንሽ እንዲለማመጠኝ ፈልጌ ነበር .....ድንገት አስነስቶ ፈትለክ እንዳይል እየፀለይኩ “ ፈገግ አለች ልእልት ..... ፈገግታዋ ያሳዝናል ....ልክ አንድ ትልቅ ህንፃ እያየ “ይሄ ህንፃኮ የኔ ነበር ባንክ በሃራጅ ሸጠብኝ እንጅ” እንደሚል ጊዜ የጣለው ባለሃብት ፊቷ ላይ የሚያንገበግብ ቁጭት ነበር ! ፍዝዝ ባለ ቀለም ግድግዳው ላይ ትዝታዋ የተፃፈ ይመስል ውብ አይኖቿን ግድግዳው ላይ ተክላ ነበር የምታወራኝ ....በዚህ አመለካከቷ ለቀጣይ አስር ደይቃ ከቀጠለች የምታይበት ቦታ ላይ ግድግዳው የሚሸነቆር እስኪመስለኝ እንኳን እኔን እያየች ያላወራች ... ምንበወጣኝ ሌላ ቢላ ያውም ሁለት ....ያውም ልቤ ላይ(ትንሽ ከፍ ቢል ልቡን ነበር አሉ እማማ ቁንጥሬ...ትንሽ ዘወር ብትል ልቤን ነበር .....) የታችኛው ከንፈሯን ወደአፏ ውስጥ ሳብ አደረገችና ምጥጥ አድርጋ ለቀቀችው ርጥብ አለ ....ከንፈሯ ሊጠበስ የተዘጋጀ ቀይ ጥሬ ስጋ መሰለ ! ግሎ የሚጠብቀው መጥበሻ ላይ ጣል ሲደረግ ቻሰስስስ የሚል ዓይነት ! (ጥሬ ስጋ ስለማልወድ በልቸ አላውቅም ...ምን ምን ይል ይሆን ብየ አሰብኩ

...ይሄ ሁሉ ወፈ ሰማይ የአበሻ ህዝብ በየስጋ ቤቱ ጥሬ ስጋውን እየቆረጠ ያለነገር አልተኮለኮለ ) ...በእነዚህ እርጥብ ከናፍርት ምናለ የሆነ ስርቅርቅ የሚል ዘፈን ነገር ቢዘፈንባቸው...ምናለ የሆነ የፍቅር ነገር ቢወራባቸው .... ብየ ሳስብ ልእልት ቀጠለች

" እና እኔን ነው ? እና እኔን ነው ? ሲሉ ቆይተው ...ጓደኞቾ የራሳቸውን ጨርሰው እጃቸውን እኔ ላይ ቀስረው አመለከቱትና

"እሷን ነው " ሲሉት .... "አዎ" አለ ....

"ይጠራሻል" አሉኝ በጉጉት ......ሁሉም በአንድ ላይ (እስቲ አንድኛቸው ቢነግሩኝ አይበቃም?) ልክ ለሽልማት ወደመድረክ የተጠራሁ ይመስል ግማሽ ቅናት ግማሽ ቅሬታ (ጥሪው ለእነሱ ስላልሆነ) ፊታቸው ላይ ተኮፍሶባቸው ....ከእነዚያ ሁሉ ቆንጆዎች ተመርጬ ያውም መኪና ....ከመኪናም ቢኤም ደብሊው በያዘ ወንድ መጠራቴ ፊታቸውን በቅፅበት ለዋውጦታል "ከማን በልጣ ነው " አይነት ....

(ያኔ የመኪና ስም ማጥናት የጀማመርንበት እድሜ ነበረቻ ... አለኮ ባይስክል ባይኖረንም የሚናቅና የሚከበር መኪና ብለን የምንፈርጀው ነገር ....ከማየት ብዛት የእራሳችንን ህያው ቁንጅና አባይ ሚዛን ላይ አስቀምጠን "ልኬ ይሄ ወንድ ነው " ሳይሆን "ልኬ ይሄን መኪና የያዘ ወንድ ነው" የምንልበት" ..... እና በጊዜው ያንን አማላይ መኪና በሚነዳ ወንድ በመጠራቴ ኩራት ተሰማኝ .....ግን ኮስተር ብየ እንዳላየ ዘጋሁት ...ጓደኞቸን "እረፉ" ከሚል ግሳፄ ጋር ! ሁሉም ተቁነጠነጡ ....ልጆች ነበርን ያኔ መኪና የያዘ ወንድ አለምን የገዛ ነበር የሚመስለን ....በእኔ ትእቢት የእነሱን አለመመረጥ የተበቀልኩት ይመስል "ደግ አደረግሽው ይሄ ፈጣጣ ልክስክስ" እያሉ አሞካሹኝ ! አይ ልክስክስ እቴ መጀመሪያኮ ጺጽ ሲል አዟዟራችን ... ሹፌሩ ሳይሆን መኪናው የጠራን ነበር የሚመስለን " ዝም ብላ አፍታ ቆየች.....

" መኪናውን አስነስቶ ሄደ ... ወዲያው ጓደኞቸ ጋር ሌላ ወሬ ጀመርን ...አለ አይደል "ሄደ መጣ ግድ አይሰጠንም" ለማለት ያህል ...ግን የሁላችንንም ልብ ጭኖት ነበር የሄደው .... በተለይ እኔ ውስጥ ትንሽ መቆላጨት ነበረች ... ፍቅረኛ እንዲኖረኝ አይኔ ግራ ቀኝ የሚቃብዝበት እድሜ ነበር ...ከጓደኞቸ የተሻለ ፍቅረኛ እንዲኖረኝ የምመኝበት ጊዜ ነበር ... ፍቅረኛ የተለየ ፍጥረት እንጅ ከፒያሳ ከቦሌ ከአቃቂ ከሜክስኮ ወይ ከሆነ ክፍለ ሃገር የሚመጣ ሰው አይመስለኝም ነበር ....ፍቅረኛ የሆነ ህልም ነገር ነበር ለኔ ! አንዳንዴ ገና በማላውቀው ፍቅረኛየ ሁሉ ሌላ ሴት ጋር ቢሆንስ ብየ የምቀናበት አስገራሚ እድሜ ...... ሁሉም ሰው ቆንጆ ነሽ ይለኛል ... በየቀኑ የፍቅር ደብዳቤ ከተማሪ እስከአስተማሪ ይጎርፋል.... ያ አድናቆት እራሴን እንደተራ ልጃገረድ ትምህርት ቤት ሳር ላይ ተቀምጬ ተማሪ ጋር የምሟዘዝበት እንዳልሆነ እንዳስብ አድርጎኝ ነበር ...በዚች ሁሉ ነገር በገንዘብ በሚሸቀጥባት ርካሽ አለም ....ቁንጅናየን ራቅ ባለ መደርደሪያ ላይ ወስደው ሰቅለውት ....ለማውረድ ዘለግ ያለ የሃብት ወይ የእውቅና ቁመት ያለው ሰው ፍለጋ አፍላ ነፍሴ ስትቃትት ነበር .... እንደልጅ እዛና እዚህ ቦርቄ ከማለፍ ይልቅ አግብታ እንደፈታች ሴት ስቆነንና ሁሉን ነገር አይቸዋለሁ አይነት ባዶ ኩፈሳ እድሜየን በላው

የሆነ ለየት ያለ ሰው ሳፈላልግ ነበር ....ከመለአክ ዝቅ ያለ ምስሉ ሁሉ አእምሮየ ውስጥ ነበር .....ምናልባት ከአንዱ ፊልም ላይ አንጎሌ ውስጥ የተሻጠ የቅዠት ስእል ይሆናል.....ግን "ኮራሽ... አንች ገንዘብ ያለው ወንድ ነው የምትፈልጊው " ለሚሉኝ ጎረምሳ ተሜዎች ሁሉ "ዋናው ፍቅር ነው" ነበር መልሴ(ወግ አይቀር ንቄቱን ከነማስተባባያው ታጥቀነው ነበር ......የሴትነት ግርዶሽ እንግዲህ መመፃደቅም በለው ) ይሄውልህ እንግዲህ ሳልጀምረው ነበር የአድናቆት ዛፍ ላይ በተቋጠረ የውብት ገመድ ፍቅርን ያንጠለጠልኩት ! የሚቆጨኝ .....አንድ ልጅ (እስከአድማስ የሚባል ... እውነትም እስካድማስ ) የለመነኝ ልመና ....አለባበሱ አሁንም አይኔ ላይ አለ .... ቅጥነቱ ... የአፍንጫው ስልክክ ማለት አይኖቹ ((((ልክ እንዳንተ ))) (በለው አሁኑኑ ከሆስፒታል ብወጣ አንድ ቁስል አይገኝብኝም በስማም እንዳንተ ብላ አፈረጠችውኮ እንዲህ ሲያምልጥ ደስ ይላል ) ..... ሰው አራት አመት ሙሉ ይለምናል አብርሽ ? ... ግን ልመናው በየቀኑ የሚያወራልኝ ወሬና አድናቆት ሁሉ እንደተበጠበጠ ስሚንቶ በጆሮየ እየገባ ልቤን በትእቢት ኮንክሪት አሳበጣት እንጅ ምንም ...ርህራሄ የሚባል እንዲች ብሎ አልፈጠረብኝም

... አውርቶኝ አውርቶኝ ... ቀና ብየ ስመለከተው ያወራኝ ሁሉ ብን ብሎ ይጠፋል ከውስጤ ....አራት አመት ለመነኝ .... ውሸት ነው ሴት ልጅ በጆሮዋ ታምናለች ምናምን የሚባለው ...ቢታመን ያ ሚስኪን ልጅ ጆሮየ ተቆርጦ እስኪበር ያወራልኝ ያህል በህይዎት ዘመኔ ሁሉ ማንም እንደማይደግመው ያኔውኑ አውቄ ነበር ... ሚስኪን እስከአድማስ ...እኔን ውሃ ይብላኝ ወደሊቢያ ነው ወደየት አገር በባህር ሲያቋርጡ ጀልባ ተሰብሮ ሞተ ብለው ባለፈው ሲነግሩኝ ተደብቄ አለቀስኩ ... በቃ ያኔእኔን ለፍቅር ማሰብ ደመና መጨበጥ ነበር ... እንኳን ለሌላው ልገኝ ከራሴም ጠፍቸ ነበራ !

ወንዴ ጋር እንደተጋባን አካባቢ "ያ ትእቢቴ የማንም መጨዋቻ ከመሆን አድኖ በክብር እንድዳር እንድኳል አደረገኝ " እያልኩ ሃሴት አድርጌ ነበር....ግን መጣልሃ የኋላ ኋላ ...በሚሊየን ተባዝቶ !! ትእቢቴ እንደረመጥ የጊዜ አመድ ውስጥ ተቀብሮ ኑሮ ባዶ እግሬን በቆምኩበት ሰዓት ተገልጦ አንገበገበኝ !! ሌላ ቀን ከትምህርት ቤት ወጥተን ከጓደኞቸ ጋር በኤሊ እርምጃ ወደቤታችን እናዘግማለን ....ከትምህርት ቤት እቤቴ ድረስ ፈጠን ባለ እርምጃ እንኳን ብሄድ አስር ደይቃ አይሞላም ነበር ....ግን ጓደኞቸ ጋር ወሬው መንገድ ላይ በአይን መጎነታተሉ እንዲሁ የእለቱን አድናቆት ከማናውቀውም ከምናውቀውም ጎረምሳ መስማቱ (የደፈረ ቃል አውጥቶ ያልደፈረም በእይታው የሚለን ነገር ነበር ...የልባችንን መዝገብ በርግደን በደማቅ ቀለም ድምፁንም ድምፅ አልባውንም አድናቆት የምንመዘግብባት መድረክ ነበርች ያች ሰዓትና ያች መንገድ ... ድንገት ወንዴ ሌላ መኪና ይዞ (ምናይነትም እንደሆነች እንጃ ነጭ መሆኗ ብቻ ነው ትዝ የሚለኝ) ከኋላችን ክላክስ አደረገ....ሁላችንም ዞርን ....ጓደኞቸ ያ የባለፈው ጥቁር መኪና የያዘው ልጅ ምናምን እያሉ አንሾካሾኩ ....ጭራሽ ከጎናችን መኪናዋን ከእኛም እርምጃ ባነሰ ፍጥነት እየነዳ (የውሃ ቱቦ ውስጥ እንዳይገባ ይሄ ሰው እያልን እየተሳሳቅን)

"ልእልት ሌላው ቢቀር ሰላም በይኝ " አይለኝ መሰለህ ....ልቤ ስንጥቅ ነው ያለው ....ዞር ብየ አየሁት ያው እንዳየኸው መልኩ ቆንጆ ነው ....በዛ ላይ የለበሰው ጨለማ የመሰለ ድፍን ሹራብ ቅላቱን አድምቆታል .....መቸስ ሰው ነኝ ....በዛ ላይ መኪናው አለ ...ከሁሉም በላይ ጓደኞቸ ፊት ያውም ከነመኪናው ተንበርክኮ ከፍ ያደረገኝ ወንድ ባወጣ ባወርድ የምገፋበት ምክንያት አጣሁ ...ደግሞ ስሜን ማወቁ እኔንም ጓደኞቼንም አስደነቀን (ከባድ ነገር ይመስል) አንዳንዴኮ ልባችን እንዴት ትንሽ ንፋስ የሚያርገበግባት ፌስታል ነገር እንደሆነች ...ስሜን አወቀው የሚለው ሳይሆን እኔም በሌለሁበት ስሜን ለማወቅ መጣሩ "ቁም ነገረኛ ...እኔ ህልሙ የሆንኩ ከርታታ " መስሎ እንዲታየኝ አደረገ ...አራት አመት ስሜን ከነምንጅላቴ ሲደግም የኖረው እስካድማስ ምን ይባል .....ውሃ ይብላኝ የኔ ጌታ ውሃ በላው !

እንባዋ ተዘረገፈ ...ወዲያው ጠራረገችው ! ያው እንደነገርኩህ ነው .... ብዙ ጊዜ ንግግሩ ሳይሆን ተናጋሪው ያለበት ሁኔታ ነው የሚሰማን !!((( ሃብት፣ እውቅና ፣ስልጣንና ቁንጅና እንደድምፅ ማጉሊያ ነገር ናቸው ..... ከእነዚህ አንዱ ካለህ የተናገርከው ነገር ምን ተልካሻ ቢሆንም እንኳን ....አንተ ስትናገረው ግን ጮክ ብሎ ሁሉም ጆሮ ላይ ሁሉም ልብ ላይ ይደርሳል ! ሰዎች ቢጥማቸውም ባይጥማቸውም በመስማማት ራሳቸውን ሲነቀንቁ ታያለህ ....."አይ ተሳስተሃል" የማለት ድፍረቱ ያላቸው በጣም ትንሽ ናቸው)) እንዳለመታደል ሁኖ ያኔ እነዚሁም ጥቂቶች አጠገቤ አልነበሩም ...ቢኖሩም እሰማቸው ነበር? ....እንጃ !

.....እና ....ያን ቀን ላለመግፋትም ላለመሳብም ዞር ብየ ወንዴን አየሁት ...በተለሳለሰች አዟዟር ብዙም በማትቆረቁር አይን ....እንደውም ድምሩ ወደፈገግታ በሚያደላ ፊት ! እንጃ ከአይኔ ምን እንዳደመጠ ፍጥነቱን ጨምሮ ተፈተለከ..... "ውይ አንች ልጅ ግፍሽ " አሉኝ ጓደኞቸ ... አራት አመት ለለመነኝ ሚስኪን ያላሉትን ... ልእልት ... ስታወራኝ በወሬዋ መሃል ሁለት ሶስት ጊዜ ጣቶቿን ቀጥ አድርጋ ዘርግታ የጋብቻ ቀለበቷን በቁጭት ትመለከታለች ... የወርቅ ቀለበቷ ....ጣቷ ከጊዜ በኋላ የመጣ ውፍረት ተጨምሮበት ሳይሆን አይቀርም በስጋዋ ተውጧል .... ጣቶቿ ቀለበት ከሚያርፍበት ቦታ ጀምሮ እስከአንጓው ወፈር ብለው ይወርዱና ከአንጓው በኋላ እየቀጠኑ ሂደው እንደጦር የሾለ ጫፋቸው ላይ ይፈፀማሉ .... ቆንጆ ጣቶች ቆንጆ መዳፍ .....የመዳፏና የመዳፏ

ጀርባ ወደቅላት የሚወስደው ጥይምና አንድ አይነት ነው .... ፊቷና እጆቿም አንድ አይነት ናቸው ....ምናልባትኮ ሙሉ ሰውነቷ አንድ አይነት ይሆናል እያልኩ አስባለሁ (ያው ሃሳብ ነው)

የልእልትን ታሪክ አጠር ላድርገው ....እንግዲህ ከብዙ ምልልሶችና ብዙ ፊት ምንሳቶች በኋላ አንድ ቀን ብቻዋን ወደቤቷ ስትጣደፍ (ጓደኞቿ የት እንደሄዱ እሷም ራሷ ትዝ አይላት) ወንዴ ከኋላ ከች አለ ! ክላክስ አላደረገም ...ጠጋ ብሎ ጠራት "ልእልት" ዞራ አየችው ከዛ ዙራ ጓደኞቿ አለመኖራቸውን ተመለከተች ....እናም ወደመኪናው ሄደች .... እጁን ለሰላምታ ዘረጋላት ጨበጠችው .... መኪና ውስጥ "ግቢ" ..." አልገባም" ለደይቃዎች ከተነታረኩ በኋላ ከመኪናው ውስጥ የሚወጣው መልካም የሽቶ ጠረን ...የወንዴ ጨዋ ልመና እንዲሁም የውስጥ መሻቷ እንደበሽተኛ ደጋግፊው ወንዴ መኪና ውስጥ አስገቧት ....ከዛን ቀን ጀምሮ ...እዳው ገብስ ሆነ ... ምን ችግር ወንዴ ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ .... የትምህርት ቤት ሰርቪሷ እስኪመስል ከትምህርት ቤት ስትወጣ በር ላይ ወንዴ አለ ....ቤቷ ቅርብ ስለሆነ የዙሪያ ጥምጥም እያወራት ....ይወስዳታል አንዳንዴም ሻይ ቡና ይላሉ ....ወንዴን "ልክስክስ" ያሉት ጓደኞቹ በመደዳው ግብዣውን አኾንድጉዶ ቀናቸውን ፋሲካ ሲያደርገው "ፅድት ያለ ልጅ " አሉና ማእቀባቸውን አነሱ

...."በፋሲካ የተገዛች ባሪያ ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስላታል"

" ወደድኩት" አለች ልእልት ስትነግረኝ " ወሬው አይደለም .... እንደውም ወንዴ ከተዋወቅን ጀምሮ እስካሁን ምን ፍሬ ያለው ነገር አወራሽ ብትለኝ ይሄ ነው ብየ የማነሳው ነገር የለም ....እውቀቱ አይደለም ወንዴ ትምህርት ከንቱ ድካም ነው ይላል ....የሆነ ጊዜ አምኘው ነበር .....ቁንጅናውም አይደለም ....ውይ እንደውም ከቀረብኩት በኋላ ቆንጆ መሆኑ ትዝ የሚለኝ ሌሎች ሲነግሩኝ ነው ....መልከ ጥፉ ሰውም ቢሆን ከቀረብነው መልከጥፉነቱ ለሌሎች እንደሚታየው ለእኛ እንደማይታየን የገባኝ ያኔ ነበር ....ግን በቃ ምቾቱ አሰነፈኝ ....ስሄድ ስመጣ በመኪና ...አይደክመኝም ....ትምህርት ከደበረኝ እደውልለታለሁ ወንዴ አፍታ ሳይቆይ ከች ይላል.. በቃ ምቹ መኪናው ውስጥ ወንበሬን ወደኋላ ለጥጬ በምቾት እንፈላሰስና ወደፈለገበት እንዲወስደኝ መንገር ነው .... አይኖቸን ስገልጥ የሆነ መናፈሻ ውስጥ ወይም ምርጥ ሬስቶራንት በር ላይ ነን ....ምቾቱ አሰነፈኝ ...ስንፍና የወለደው ፍቅር ወንዴ ጋር አጣበቀኝ ...."

ልእልት አይኖቿ ከበፊቱ የበለጠ ቦዘዙ ...እንደውም እንባ የኳተሩ መሰለኝ ...ፊት ለፊት ማየት ስለምፈራ እንዲሁ በጨለፍታ የማየው ነገር ላይ እርግጠኛ ስለማልሆን ነው መሰለኝ የምለው ..... ለስላሳ እጆቹ ምን ጊዜም ፀጉሬን እየነካኩ ናቸው ደስ ይለኛል.... መላ ሰውነቴ ላይ እጆቹ አሉ ....ወንዴ ብዙ እጅ ያለው እስኪመስለኝ እጆቸ ከእጆቹ ውስጥ አይወጡም ....ደስ ይለኛል ....በቃ ለእኔ ይሄ ህይዎት የምቾት ምናኔ ነበር .... ወንዴም ከዛ አቧራ ፀሃይና የሰው አይን ...የሚጠብቅ ቅጥር ... አዲስ አበባ ዝቅ አለችብኝ ....ጓደኞቸ ከትምህርት ቤት ወጥተው በእግራቸው ሲኳትኑ ሳይ ለትምህርት ሳይሆን ለሆነ ግዞት ስንቃቸውን በቦርሳቸው ቋጥረው የሚያዘግሙ ይመስሉኛል ....ቀስ በቀስ ከጓደኞቸ ጋር ተራራቅን ወንዴ ብቻ አለሜ ሆነ ....በሆነ የምቾት ባሉን ተንሳፈፍኩ ያ ምቾትም ዘላለማዊ መሰለኝ ...በህግ የተደነገገ የማይሰረዝ የማይበረዝ ሰማያዊ ትዛዝ ....እናም ወንዴ ወደአልጋ ሲጎትተኝ አንዳች ፍርሃትም ስጋትም አልተሰማኝም ....የመጀመሪያየ ነበር ... ግን ደስ አለኝ ! በዚህ ምቾት ላይ ወሲብ ሲጨመርበት እንኳን ሌላውን ጉዳይ ራሴን ረሳሁ !! መሳሳም ነፍሴ ነው (ቀና ብየ አየኋት ...ይሄን ከንፈር ይዛ መሳሳም ነፍሷ ባይሆን ነበር የሚገርመው የልእልት) ቀጠለች ልእልት ...(ኧረ ትቀጥል እንዲህ አይነት ጣፋጭ ገመና እንደመስማት የሚጥም ምን ነገር አለ ....) ወንዴ በሁሉም ነገር የእኔ የራሴ ግልባጭ እስከሚመስለኝ ....በቃ ራሴ ጋር የምኖር እስከሚመስለኝ ሁሉ ነገሩ ይመቸኝ ነበር .... ሁሉ ነገሩ ....አይኖቹ ይናፍቁኛል ከንፈሩ በቁሜም ህልሜ ነበር ...አንገቱ ስር በቅበጥ እንዴት እወድ እንደነበር ....ደረቱ ...ወይኔ ደረቱ ሁልጊዜ ደረቱ ላይ እንደተለጠፍኩ .....እንደዛሬው እንዳይመስልህ ሆዱ ዛሬ ትንሽ ቦርጭ አውጥቷል ያኔ ምንም አልነበረውም .......(አሃ አይን ከንፈር አንገት ደረት ሆድ...... ተው ይች ልጅ አ ሽ ቆ ለ ቆ ለ ች ) .....ለምን እደብቅሃለሁ .....ወንዴ ጋር "ሴክስ" ስናደርግም ልብሴን ጥየ ነበር የማብደው !!!!!! (መጀመሪያ ልብሳቸውን ሳይጥሉ ነው እንዴ ወደገደለው

የሚገቡት የሚል "ነገር ስንጠቃ" አእምሮየ ሲያምረው "ዝም በል" ብየ እገስፀውና ወደልእልት ወሬ ጆሮየን አቆማለሁ አሁን እየተወራ ያለው ጉዳይ እጅጅጅጅጅጅጅጅግ መሳጭ ጉዳይ ነው ....ውጋቴ ወላ የቁስሉ ጥዝጠዛ ሁሉ ድራሹ ጠፋኮ እናተ ግን ልእልት ያመጣችልኝና የጠጣሁት ሾርባ እንደመዓበል ሆዴ ውስጥ እየተነሳ ሲፈርጥ ተሰማኝ )

ልእልት ድንገት ወደኔ ዞራ "አብርሽ" አለችኝ

"አቤት!! " አልኩ

ከወሬዋ ምሳጤ ነቃ ብየ!! "አቤት" አባባሌን ለተመለከተው ጦር ሜዳ መሪው የጠራው ወታደር እንጅ ከጠያቂው ጋር የሚያወራ በሽተኛ አልመስልም ነበር ! ....የራሷን ጡቶች በሁለት እጆቿ ጭንቅ እስኪላቸው ....እቅፍ አድርጋ "ወንዴንኮ ስወደው ...." ብላኝ እርፍ !! (ብስጭት ብስጭትጭት ! እግዜር በቸርነቱ አፋታልኝ ....የዛን ወፈፌ ባሏን ጉዳይ እንደሰንኮፍ ከልቧ ነቀለልኝ ብየ ከስንት ጠያቂ መሃል የሷን ኮቴ ጆሮየን አቁሜ ስጠብቅ ....ከስንት ጉድ ቬርሙዝ ለይቸ እስቲ ከዛ አረንጓዴ ቬርሙዝ ሾርባ ቅዱልኝ እያልኩ ....ከስንት ጉድ ፍራፍሬ ከስንት ነገር ......ኤዲያ ...ደግሞ አለች ወንዴን እወደዋለሁ .....

አንዱ እንደኔ አንጀቱ የበገነ ሰውየ ነው አሉ ድሮ .... እንዲህ እንደኔ አንዷን አይናይናን በአጉል ከጃሎት ሲመከለከት ያምሽና ወደማታ ባሏ ከች ብሎ ተያይዘው ወደምኝታቸው ይሄዳሉ ....ሰውየው ታዲያ እንደኔ አልጋ ላይ ተጋድሞ ሲብከነከን አላመሽም ቢያንስ ተናግሮ ወጣለት

"ተቀብል " አለው አዝማሪውን

"ያማሪካን ስንዴ የሚያልቀው በንኩቶ

ይዛው ጋደም አለች ባል ተገኝቶ ሙቶ !!

ሃቅ !

አሁን እኔ እዛ ቦታ ብኖር ድፍን መቶ ብር እዚህ ሰውየ ግንባር ላይ ብለጥፍ ይፈረድብኛል ?? እንዲህ ስርቅርቅ ብላ "ወንዴንኮ ስወደው" ትላለች እንዴ ... በሽተኛ ነኝ ....በሷ ጠንቅ የደረሰብኝን ((መካከለኛ የመቁሰል አደጋ)) እያስታመምኩ ያለሁ ሰው ነኝ .... እንደውም ብርቱ ልጅ ሁኘ እንጅ በዚህ ንግግሯ የተሰፋው ቁስል ትርትር ባለና እማማ ቁንጥሬ እንዳሉት ቁስሉ አመርቅዞ ከነገወዲያ ሳልስቱ በወጣ ነበር !! መዘዘኛ !!....ያንን የሚያክል ሻንጣ እያንዘፋዘፍሽ ለኔም ጦስ ከመሆን አርፈሽ አትቀመጭም አዋ ያኔ ደረጃው ላይ ባላገኞት አርፌ እንቁላል ፍርፍሬን በበላሁና "በቀኝ አውለኝ" ብየ ወደጉዳየ በሄድኩ ነበር ... አሁን ግን እንኳን የፈሰሰው ደሜ ያኔ እሷን ለማገዝ ብየ እንቁላል የያዝኩበትን ፌስታል ግንቡ ላይ ሳስቀምጠው የተሰበረችው አንዷት እንቁላል ቆጨችኝ !! ....ድሮ ሰፈራችን ትልቅ ሰው ሲወድቅ የወደቀበት ቦታ ላይ እንቁላል የሰበርለት ነበር (ሴጣን እንዳይጣላው መሆኑ ነው) ዛሬ ነበር ለእኔ እንቁላል መስበር ከምር ....ከተስፋየ ላይ እኮ ነው አውርዳ ዘጭ ያደረገችኝ ! ለራሴም እስኪገርመኝ ወንዴ ስለሚባለው "አጋሰስ " በጎ በጎውን ስታወራ ቅናት እንደቢላ ቆዳየን ሲሰነጥቀው ተሰማኝ ... ደግሞ እንጅ አወራሯ ምናለ ለስለስ አድርጋ ብታወራ ! ከምር ማንም ወንድ አንዷት ውብ ሴት ስለሌላ ወንድ እንዲህ በፍቅር ስታወራ ቢሰማና ቢያይ መቅናቱ አይቀርም !! ተበሳጨሁ እራሴ የገነባሁት ቀቢፀ ተስፋ እንደባቢሎን ግንብ ተንዶ ሲጫነኝ የቁስሌም ጥዝጠዛ አብሮ ሲነሳ ተሰማኝ ....

" እኔ የምልሽ ልእልት እንዲህ አካብደሽ ምታወሪለት ወንዴ የትኛው ነው ? ይሄ ሰካራሙ ...ይሄ ባላደረግሽው ነገር በእኔ ጠርጥሮሽ በቢላ የወጋኝ ....ይሄ በደረቅ ሌሊት እንደ ጥራጊ ከነልብስሽ ገፍትሮ አስወጥቶ በር የዘጋብሽ " ብየ ከጣፋጭ ትዝታዋ ቀስቅሸ የወንዴን መጥፎ መጥፎ ነገር እንድትነግረኝ ወደዛሬ ላመጣት ከጅየ ነበር ! እንዴዴዴ አወራሯኮ አሁኑኑ ብር ብላ ወንዴ ጋር መሄድ የናፈቃት አይነት ሴት ነው የምትመስለው !!(ይሄማ ያፈሰስኩላትን ደም የከሰከስኩላትን አጥንት በአጠቃላይ የከፈልኩላትን መስዋእት መዘንጋት ነው )

"ወንዴንኮ እወደዋለሁሁሁሁሁ??" አሁን በዚች ምድር "እንደወንድየ አንበሳው" የታደለ ሰው አለ?

ምንም ሳይሰራ ገድሉን በፍቅር የምትተርክ ውብ ሚስት አለችው.... ያውም በትዝታውና በፍቅሩ ስርቅርቅ እያለች ...በዛ ላይ ከተራ ፖሊስ እስከባለስልጣናት በትውውቅም በእጅ መንሻም ልጃቸውን ነፃ ለማውጣት የሚራወጡ አባት አሉት .....ከሃብታም አባቱ እና ዘመዶቹ የሚላክለትን ምግብና ያሰኘውን አይነት ልብስ እየቀያየረ .....ጥርስ ከማያስከድኑ እስረኞች ጋር ዘና ብሎ እየተጫወተ ይሆናል ....ምናልባትም ልክ እንደሬንቦ ፊልም እኔን እንዴት እንደዘረረኝ እየተረከ እያስደመማቸው ይሆናል ....

" ሚስቱን ስለነካሁበት ብቻ ከአራተኛው ፎቅ ላይ በገመድ ተንጠላጥሎ ከወረደ በኋላ እኔ ቤት ሲደርስ እንደኮማንዶ በእግሩ የመስኮቴን መስተዋት ሰባብሮ ተንከረባብቶ ምኝታ ቤቴ ገባ ...እኔ ተኝቸ እያንኮራፋሁ ነበር ....ድንገት የመስተዋቱ መሰባበር ከእንቅልፌ አንቅቶኝ ፊቴ በግርማ ሞገስ የተገተረውን ወንዴ አንበሳውን ሳይ ከመደንገጤ ብዛት ከእንቅልፌ ነቅቸም ማንኮራፋቴን ቀጥየ ነበር ....ሊምረኝ አስቦ ነበር ግን ቆንጆ ሚስቱን እንዲህ አይነት አንኮራፊ ወንድ መድፈሩ ትዝ ሲለው "ሰይጣኑ" ተነሳ .....እናም በግራና ቀኝ ታፋው ላይ የያዛቸውን ጩቤዎች አልሞ በመወርወር እንዴት በአንዴ አንገቴ ላይ እና ደረቴ አካባቢ እንደሰካቸው " ለእስረኞቹ እየተረከላቸው ይሆናል

... እስረኞቹም እየሰሙት ይሆናል ...ልእልት እንዳለችው ሃብታም ቆንጆ እና ባለስልጣን ምንም ቢል ይሰማል !! ልእልትን ቀና ብየ አየኋት አሁንም ትልልቅ ጡቶቿን እንዳቀፈች ግድግዳው ላይ አይኖቿን ተክላ በራሷ ትዝታ ጠፍታለች .....( የሚያቅፍ ይቀፍሽ እቴ) እንግዲህ ምን እላለሁ ቀሪውን ገድል እየሰማሁ ልቃጠል እንጅ .....ልእልት ቀጠለች .....

## ክፍል 8

የኔ ነገር ...ምንድናት ቀበሮ ትሁን ጥንቸል(ለካ ጢንቸል ስጋ አትበላም) ብቻ የሆነች "ጅል" እንስሳ ናት አሉ.... ከዝሆን ኋላ ኋላ እየተከተለች ሙሉ ቀን ዋለች እንደሚባለው ሆነ ....ምንትሱ ሲወዛወዝ ይወድቃል ብላኮ ነው ....እኔም እንደዛች እንስሳ ነው የሆንኩት ....የልእልትን ትረካ ልቤ ተንጠልጥሎ እየሰማሁ ካሁን ካሁን ለዛ ወፈፌ ባሏ ያላት ፍቅር በትረካዋ ሲወዛወዝ ከልቧ ተነቅሎ ይወድቅና እኔም እፎይ እላለሁ ብየ....

እሷ እናትየ.... አውርታ አውርታ በየመሃሉ "ወንዴን ግን ስወደውኮ" ትለኛለች .....ይች ልጅ ባሏ በቢለዋ የጀመረውን ራእይ በቅናት ለማስቀጠል የተላከች እስኪመስለኝ ....ቆዳየን በሚሰነጥቅ ጥልቅ ስሜት ባሏን እንደምትወደው ትነግረኛለች ...... አንዴት ሚስት የተጣላቸውን ባሏን ለምን ወደደች አይደለም የእኔ ቅሬታ ግን ቢያንስ በነብስ የምንፈላለግ ሰዎች መሃል ስለአንድ ሰው መለዓከነት ማውራት ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው ...?? ምንስ ልእልትን ቀልቤ ቢወዳት ምንስ ቁንጅናዋ አፍ ቢያስከፍት ስለት መዞ በጭካኔ ሊገድለኝ የሞከረን ሰው ሩህሩህ ነው ብሎ ሃሳቤን ያስቀይረኝ ዘንድ የሷ ቃል ምን ተአምር አለው ....??.በእርግጥ ሴቶች ስላለፈ ሂወታቸው ማውራት እንደሚወዱ በትንሹም ቢሆን ካሳለፍኩት ተረድቻለሁ ....አንዳንዴማ ሴትን ከወንድ የጎን አጥንት ሳይሆን ከታሪክ ጎድን የፈጠራት እስኪመስለኝ ስለትላንት ማውራት በፍቅር የሚወዱ ሴቶች አጋጥመውኛል ....ልእልትም ትላንትን እንዲህ ቦርቀቅ አድርጋ ትሰልቀው ይዛለች .....ችግሩ ገፀ ባህሪዋ ቀድሞ እኔ ውስጥ ስለጠቆረ ታሪኩም ታሪክ ሳይሆን የጥላሸት ብናኝ ሁኖብኝ ልቤን እያጨፈገገው ተቸገርኩ ! ድንገት ግን ልእልት ..... እንደሃምሌ ሰማይ ፊቷ ጠቋቆረ ....አይኖቿ ከትዝታ ሰገባቸው ተመዘው ወጡ ....እናም መራር ታሪኳን በምሬት ትዘረግፈው ገባች ... "ወንዴ ውሻ ነው" አለች (እንዲህ ደግ ደጉን ማውራት ነዋ ልእልቴ) ግን እያመረረች ስትሄድ "ጉዳዩ ምንም ይሁን ስለፍቅር ማውራት ይሻላል አልኩ ...ያንን ያህል ጥላቻዋን ስናፍቀው እንዳልቆየሁ ! ልእልት ግን በሚንተገተግ ቁጣዋ ትረካዋን ቀጠለች (እንደው እነዚህ ቆንጆ ሴቶች ላይ የሚያስጠላው ነገር ምን ይሆን ...? ቁጣ ራሱ እሷ ፊት ላይ ዘንጦ ነው የሚቆጣው)

"...የእኔና የወንዴ ፍቅር እንዲህ የሚያሳብድ ነበር..... በኋላ ሳስበው ግን (መቸም በኋላ ነው ሁሉን ነገር የምናስበው) የወንዴ ፍቅር በለስላሳ ስፖንጅ የተጠቀለለ የብረት ዱላ ነገር ነበር ....ወንዴ በዚያ ብትር ሲመታኝ ህመሙ አይሰማኝም ነበር ....በደሉ አይቆረቆረኝም ነበር ....ግን እድሜ ስፖንጁን እየበላው አብሮ መቆየት ድልዳሉን እያሳሳው ...ትክክለኛው ዱላ ፈጦ መውጣት ጀመረ ... የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ እስከአጥንቴ ዘልቀው ይሰሙኝ ጀመር..... አብጀለት ነበር ስልህ አብርሽ ....እይውልህ ልክ 12ኛ ክፍል ስገባ ትምህርት ቤት በትርፍ ጊዜየ የምሄድበት ቦታ ሆነ ....ጭራሽ ተማሪዎቹም መምህራኑም አስጠሉኝ .... ልቤ ወንዴ ጋር ነው ....ስንት መዝናኛዎችን ባየሁበት አይኔ ....እዛ የጠመኔና ጥቁር ሰሌዳ ትግል የፈጠረው አቧራ የሞላው ክፍል ውስጥ ተጎልቶ መዋል መወፈፍ መሰለኝ ..... ተማሪ ነሽ አስተማሪ አነሰብኝ ....ተምረን ስራ ይዘን ደመዎዝ ምናምን ሲባል ....እኔ ምኞቱን ቀድሜ ደርሸበት ወደትምህርት ቤት የተመለስኩ መሰለኝ ....(መቸስ አገራችን ላይ ተምሮ ሮኬት ለማምጠቅ ከሚያስብው ተማሪ ይልቅ ያችኑ የወር ደመወዙን ተቀብሎ ዶኬውን ግፋ ቢልም የፈረደበትን ጥሬ ስጋ የሚያልመው ይበዛል) እና ለየትኛው ተአምር ነው የምማረው እየው የትምህርት ጡንቻ ሲልፈሰፈስ መማር ኑሮን መቀየሪያ መሳሪያ ሳይሆን በራሱ ኑሮ ይሆናል፣ እንደመነገድ፣ እንደመዝፈን፣ እንደመደለል መማር ገንዘብ ማግኛ አንድ የስራ ዘርፍ ይሆናል .....ያኔ ነው ራእይ ገንዘብ የሚሆነው ....በቃ ተምረህም አምጣው፣ ሰርቀህ፣ አመንዝረህም አግኘው፣ ሎተሪ ደርሶህ ብር ማግኘት ከቻልክ መማር እድሜ መፍጀት መስሎ ይሰማሃል ! ምን ይሰራልሃል ... የውስኪ ብርጭቆ አያያዝ ለማሳመር ሀ ሁ ምን ቤት ነው ጥሬ ስጋ ለመቁረጥ ኤቢሲዲ ሚጥሚጣ ነው ዳጣ እንዲህ ነው ትምህርት ግርማ መጎሱ የሚገፈፈው

እናቴና እህቴ ጋር ወንዴን አስተዋወኩት ወደዱት (ባይወዱት ነበር የሚገርመኝ) ...አባቴ ከሞተ ቆይቷል በእርግጠኝነት የምነግርህ አባቴ ቢኖር ወንዴን አይወደውም ነበር እንግዲህ በምድር ላይ ያሉኝ ዘመዶች እነዚሁ ሁለቱ ናቸው ወንዴን ወደዱት ወንዴ እቤት መጥቶ እንደእቃ አንጠልጥሎኝ ሲሄድ እናቴ የምትናገረው አንድ ቃል ብቻ ነው "አታምሹ"...(አይ አለማምሸት እቴ ) ወደቤት አልመለስም በዛው እናድራለን ማታ ደውየ ለእህቴ እነግራታለሁ (ለእናቴ ደፍሬ ወንድ ጋር ላድር ነው ማለት መቸስ ይከብዳል ....የኛ ነገር ማድረጉ አይከብደንም እንጅ መናገሩ ላይ አጉል ጨዋ ካልሆንን የምንለው ነገር አለ ) የሴት ልጅ ትልቁ ድክመት መልኳንም መፈቀሯንም ዘላለማዊ አድርጋ ማየቷ ነው ያ ደስታችን ዘላለማዊ መስሎኝ ያችኑ የፊደል ቆጣሪ ሁሉ ተስፋ (ደመዎዝ) ተቋድሽ ይችን ጤዛ ህይዎቴን እንኳን በራሴ እንዳቅሜ እንዳልመራት እንደቅንጡ አይነስውር ያለችኝን አንዲት ብትር አሽቀንጥሬ ጣልኳት ትምህርቴን ! ምናለ ትምህርቴን በወጉ ባቋርጠው ምንስ ቢሆን አስራ አንድ አመት ተንገታግቸበታለሁ ውድቀትንም ታሪካዊ ማድረግ አንድ ነገር ነው ሰበብም ጥሩኮ ነው ውድቀትን ሰበብ ማስደገፍም ቢያንስ ወሬ ለማሳመር እንኳን ይረዳል አብርሽ ሙት እስቲ አሁን ምንም ሳትሆን መጥተህ የሆስፒታል አልጋ ላይ ብትተኛ ለጠያቂስ ምን ይባላል በቃ ትምህርቴን ያለምክንያት ከመሬት ተነስቸ ተውኩት መተዌ አይደለም የሚገርመኝ የተውኩበት መንገድ ከሞቱ አሟሟቱ ነው ምናምን የሚባል ተረት አለ

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት እንደወጣሁ ወንዴ ጋር እራት በልተን በዛው አብረን አደርን ያው ትክ ብሎ ካየኝም ተከትየው መንጎድ ነው መቸስ በፍቅር ስም እንደለማዳ ውሻ መከተል ጧት (አብረን ስናድር ቀጣዩ ቀን ቅዳሜ ከሆነ ጧታችን አራት ሰዓት ወይ አምስት ሰዓት ነበር ) ያን ቀን ግን ትምህርት ስለነበር በጧት "ወንዴ ውይ ረፈደብኝ " ብየ ልነሳ ስል አይኑን እንኳን አልገለጠም በጎረነነ የጧት ድምፅ " አቦ አርፈሽ ተኚ "" ብሎ አቀፈኝ አይገርምህም አብርሽ እቅፉ ውስጥ ገብቸ ለሸ ...ምን ለሸ.... መሟሟት በለው በኋላ የሚሆነው ሁሉ ሁኖ የውሻሽት ልክ እሱ ብቻውን አስገድዶ በር ላይ ወታደር አቁሞ እጅና እግሬን አስሮ ያስቀረኝ ይመስል ከትምህርት ቤት አስቀረኸኝ ብየ ተነጫነጭኩ አለ አይደል " መቅረቴን በሆነ መንገድ እንዲባርከውና ለራሴም ከትምህርት ቤት መቅረቴ ልክ ነበር ለካ እንድል "

"ልእልትየ ....ይሄን ትምህርት ምናምን ተይው በቃ!! ተጋብተን አሪፍ ቤት ተከራይተን እንኑር አለኝ " ልቤ ለሁለት ስንጥቅ ያለች ነው የመሰለኝ ...ወንዴን አየሁት ከምሩ ነው ....

"እውነትህን ነው ? "

"አባቴ ይሙት "

በአባቱ ከማለ አይዋሽም .....አባቱም በወንዴ ከማሉ አይዋሹም ....(አንድ አይነቶች) በቃ ትምህርቴን !! የሚገርምህ ዩኒፎርሜን እንኳን ያደርንበት ሆቴል እንደተውኩት ያስታወስኩት በቅርቡ ነው (ማሰብ ስጀምር) ተውኩት በቃ ! ከዛን ቀን ጀምሮ ትምህርት ቤቱን ዞሬ አላየሁትም ! ታዲያ የማቋረጥ ሳይሆን የሆነ የመመረቅ ስሜት ነበር የሚሰማኝ ይሄ በሜዳሊያ ምናምን መመረቅ እንደሚሉት እውነቴን ነው አብርሽ አንዳንዴ ከስንት እንዳቋረጥኩ ሁሉ ትዝ የሚለኝ አስቤ ነው

ወንዴ ጋር ቤት ተከራየን (ለነገሩ ከዛም በፊት ነበረው መሰል ተከራየሁ ብሎ በውድ እቃ የተሞላ ኮንዶሚኒየም ውስጥ ሲያስገባኝ ግራ ቀኙን አላየሁም እንደእቃ ገብቸ ተጎለትኩ) ከመሬት ተነስቸ የተከበረች የቤት እመቤት የመሆን መንፈስ ከበበኝ ! ጧት ተነስቸ ፒጃማየን እንደለበስኩ ቁርስ ለመስራት ጉድ ጉድ ስል "አስር አመት በትዳር የኖረች ሚስት አስንቃለሁ" በገዛ ህይዎት ላይ ድራማ መስራት! ልክ ፊልም ላይ እንዳየሁት ነበር ትዳርን ያገኘሁት ! ወንዴ ከውጭ ሲመጣ ከንፈሩን ስሜ መቀበል ዘንጠን ወጥተን እራት መገባበዝ እና ሰዎች የሚፋቱት ደደብ ስለሆኑ ነው ብየ ያሰብኩት ስንት ቀን መሰለህ እናቴን ስፈራ ስቸር ወንዴ ጋር ልንጋባ ማሰባችንን ነገርኳት

"በሞትኩት እኔስ እንደዘመኑ ልጆች መስሎኝ ነበር ለካስ ቁም ነገረኛ ኑሯል" አለችኝ እህቴ ገና ድሮ ስለቬሎ ማውራት ጀምራ ነበር በቃ! ወንዴ ለአባቱ ሲነግራቸው አጠገቡ ነበርኩ ትዝ ይለኛል እዛ ሲሚንቶ መሸጫ ሱቃቸው ውስጥ አብረን ሂደን (ከዛም በፊት አስተዋውቆ ወደውኝ ነበር እንደውም አንዳንዴ ወንዴ ጋር ስንሄድ እኔን ወደኋላ ያስቀሩና "የሻይ" ብለው የሻይ ንግድ ብጀምር ወረት የሚሆን ብር ይሰጡኛል ወንዴ ጋር አመድ እናደርገዋለን !) ታዲያ ልንጋባ እንዳሰብን ሲነግራቸው ብዙ ብር እየቆጠሩ ነበር መቁጠራቸውን ቆም አድርገው ሁለታችንንም በግርምት ተመለከቱንና" ልእልት ይሄ ልጅ የሚያወራው እውነቱን ነው ?? " ብለው ጠየቁኝ ወንዴ ክንድ ላይ እንደተጣበኩ እራሴን ከፍ ዝቅ አድርጌ አረጋገጥኩላቸው

"ሂዱ እስቲ ሻይ ቡና በሉና ተመለሱ " ብለው እጃቸው ላይ የገባውን ብር አፍሰው ሰጡን " ትንሽ ተረባብሸው ነበር .....ከሱቅ ስንወጣ አባቱ ሲያፏጩ ነበር ..... ቆይቸ ይሄን የሚያፏጩትን ዜማ የት ነው የማውቀው ስል ....የሆነ ዘፋኝ ስለትዳር የዘፈነው ነው

"ማየት መልካም ሁሉን እይው ግን በትዳር ቀልዱን ተይው ..... ይችን ራሷን ነው ሲያፏጩ የነበሩት የሆነ ሁኖ ተጋባን ሰርጉ ለእኔ ድካም ነበር ወደዛ ቬሎየን ወርውሬ ወንዴ ጋር ብቻችንን የሆነ ቦታ መሆን ነበር ያማረኝ እስካሁን እንደህልም የሰርጉ ጭፈራ ይታየኛል ጓደኞቹ ሲያብዱ (ምን አሳበዳቸው) ጭፈራቸው ራሱ ዛር ነበር የሚመስለው ከዛም በኋላ ስንትና ስንት ወር ሙሉ የወንዴ ዘመዶች ስጦታ እየያዙ እቤታችን እየመጡ ከረሙ ብቻችንን መሆን እስኪናፍቀን.!! ከተጋባን በኋላ አባቱ እራሳቸው ግቢ ውስጥ እንድንኖር ፈልገው ነበር እኔም ወንዴም ግን ወጣ ማለት ፈለግን ወደሲኤም ሲ ቤት አሰራላችኋሁ አሉን ያሰሩ አያሰሩ እንጃ ሰውየው ባህሪያቸው ምንም የሚያዝ የሚጨበጥ አይደለም ! ለነገሩ እኛም አብረን እንሁን እንጅ ቤት ይሁን በረት ግድ አይሰጠንም ያኔ እዚህ ኮንዶሚኒየም መጥተን መኖር ጀመርን እኔ ሰፈሩን ወድጀው ነበር ወንዴም ተመችቶታል እንደቀልድ ሶስት አመት አለፈን የወንዴ ጓደኞች ከሰዓት ውሏቸው እኛ ቤት ነበር ሁልጊዜ በሰው እንደተከበብን ነን ቀን ጓደኞቹ ጫት ይዘው ይመጣሉ እኔም "ምናለበት" ሲሉኝ " አታስደብሪና እናተን ብለን መጥተን" ሲሉኝ እንዳልለይ አንድ ሁለት ስል የለየልኝ ቃሚ ሁኘ ቁጭ አልኩ አብረን ምሳ እንበላለን በየሄድንበት አስተናጋጆች ያውቁናል ጫት ይገዛል እንቅማለን ፊልም እናያለን ወደማታ ወጥተን አብረን ራት መብላት መጠጣት ሁሉ ጀመርን ሲደጋገም ህይዎታችን ይሄው ሆነ ተመሳሳይ ፕሮግም ነበር በየቀኑ

ሁሉም የወንዴ ጓደኞች የሃብታም ልጆች ናቸው በየቀኑ አዲስ ሰው ይዘው ይመጣሉ ሴቶችም ወንዶችም እኔ ራሱ ይናፍቁኛል ወሬው ሳቁ ምን ልበልህ ሰው መልመድ ክፉ ነው ከቤት ባልወጣም በእነሱ በኩል ከተማው

ውስጥ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ልክ በቦታው ያለሁ ያህል ሁኘ አውቀዋለሁ ደግሞ እቤት ስለምውል ነው መሰል አማረብኝ ፊቴ ጥርት አለ በቃ ተስማማኝ በምድር ላይ እንደኔ ደስተኛ ሴት ያለች አይመስለኝም ነበር አንዳንዴ እንዲሁ በረንዳ ላይ ቁሜ ከስራ የሚመጡ ሴቶችን ስመለከት በዛ ጠራራ ፀሃይ ከልተው ከልተው የሚሉ ሴቶችን ሳይ "እንዴት እድለኛ ልጅ ነኝ" እያልኩ እታበያለሁ በወንዴ ጓደኞች ታጅቤ ወጣ ባልኩ ቁጥር እውነትም የልእልትነት ስሜት ነበር የሚሰማኝ በእኛ ነገረ ስራ የማይቀና አልነበረም አንዴ እቤታችን የመጣ ወይም የመጣች ሴት በቃ በግሩፑ ፍቅር ከመውደቅ አትድንም አስደሳች ጊዜ ነበር የምናሳልፈው

ጉዱ የመጣው አንድ ቀን ነው ታዲያ ይሄ አእምሯችን አብርሽ" አለች በውብ አመልካች ጣቷ ከጆሮዋ ከፍ ብሎ ያለ ጭንቅላቷን እየነካችና ጣቷን እንደቡለን መፍቻ ግራ ቀኝ እያሽከረከረች" ....ይሄ አእምሯችን እንደተቀበረ ፈንጅ እኮ ነው የፈለገ ምቾት ውስጥ ብትቀብረው ብር ውስጥ ብትቀብረው ግርግር እና አጀብ ውስጥ ብተሸጉጠው አንድ ቀን የእውነት እግር የረገጠው ቀን መፈንዳቱ አይቀርም በቃ ምን እየሰራህ ነው ይለሃል ይሄውልህ ወንዴ ጋር ያሻንን በልተን ጠጥተን የፈለግንበት ቦታ ሂደን እየኖርንን ነው ምንም ነገር ቸግሮን አያውቅም ልብስ ብትል አገር ያስለቀቀ ነው ያ ባለፈው ያየኸው መዘዘኛ ሻንጣ ካለኝ ልብስ እንደው ለጊዜው የምለብሰው ብየ እንዲሁ ቆንጠር ያደረኩት ነው (የሻንጣውን ክብደት አስታውሽ አባባሏ ገረመኝ ያንን የሚያህል ሻንጣ ሙሉ ልብስ "ቆንጠር" ) እና አንዲት ቀን አኮ ናት የነወንዴ ጓደኛ የመኪና አደጋ ደረሰበት ተብሎ ወንዴ ከነጓደኞቹ እዚህ ደብረ ዘይት ሂደው ብቻየን ነበርኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻየን እቤት የዋልኩበት ቀን ነው በቃ ብቻየን ቁጭ ብየ የማደርገው ነገር ጠፍቶኝ አንዴ ፊልም እከፍታለሁ አንዴ በረንዳ ላይ ወጥቸ እቆማለሁ በቃ ቤቱ ሊበላኝ አልቅሽ አልቅሽ አላኝ እና ግራ ቢገባኝ ቤት ገብቸ ሶፋ ላይ ኩርምት ብየ ተቀመጥኩ ደግሞ ደጋግሞ ያዛጋኛል ያን ሁሉ ጊዜ ያላሰብኩት የጥያቄ ናዳ ወረደብኝ አእምሮየ ብቻየን ሲያገኘኝ ቤተክርስቲያን እንደገባች ውሻ ከዛ ከዚህ ያዋክበኝ ጀመረ ደግሞ ሁሉም ጥያቄ መልስ የሌለው!! እሽ ከዚህ በኋላ ኑሮየ ምንድን ነው ብየ አሰብኩ .... መልስ የለም!! ....እሽ ዛሬ አደጋ የደረሰበት ወንዴ ቢሆን ኑሮ ቀጥሎ የማደርገው ነገር ምንድን ነበር አልኩ መልስ የለም !!.....ሌላው ይቅር እጀ ላይ እንኳን ያለው ብር ስንት ነው ? አልኩ እዛ ጠረንጴዛው ላይ ከተቀመጠ ትንሽ ብር ውጭ ምንም አልነበረኝም (አንድ ሽ ብር እንኳን መሙላቷን እንጃ) ከሆነስ ሆነና ወንዴ ስራው ምንድነው? ብየ አሰብኩ አይገርምህም ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ የባሌ ስራ ምን እንደሆነ አላውቅም ከምር አላውቅም (ማን ያምናል ይሄንን) ...በቃ ይሄዳል ይመጣል ብር ሁልጊዜ እጁ ላይ አለ አባቱ ናቸው የሚሰጡት ! ወንዴ እንዲች ብሎ አንዲት ስራ አይሰራም ሰርቶም አያውቅም ግራ ገባኝ ልክ ከእንቅልፍ እንደመባነን ባነንኩ አንዳንዴ መቸስ ከራሳችን ጋር መፋጠጥ ጥሩ ነው ይሄ ግርግር ስንቱን ጉድ እውነት አድበስብሶ ቀብሮታል መሰለህ ይሄው ያንተ ቁስል እንኳን የሚጠዘጥዝህ ብቻህን ስትሆን አይደል (እውነት ነው በተለይ ልእልት ሳትኖር) ልእልት አሁንም በሆነው ነገር ሁሉ ተደምማ ታወራኛለች ተደምሜ እሰማለሁ

" አሰብኩ በቃ አእምሮየ ሊፈነዳ" እንደው ሌላው ሁሉ ይቅር ወንዴ ሌላ ሴት ወዶ በቃኝ ቢለኝ ምንድነው የኔ መጨረሻ ትምህርቴን አቋርጫለሁ ቤተሰቦቸ ያው ለራሳቸው አይነሱ እንጅ እንደገና ወደነሱ መሄድ ሞት ነው ምቾት ብየ የተደገፍኩት ነገር ሁሉ የንቧይ ካብ ሁኖ ታየኝ ነብሴ ውስጥ የስጋት ሻማ ለመጀመሪያ ጊዜ ተለኮሰ ሻማው ሲለኮስ ግር ግር ጨለማ ውጧቸው የሌሉ የመሰሉ ግን በነብሴ ውስጥ የታጨቁ በርካታ ጉዳዮች አቧራቸውን እያራገፉ እፊቴ መጋረጣቸውን አየሁ! የማልሸሻቸው ሃቆች !! ወንዴ ሲመጣ በስርዓት ስለወደፊት ህይወታችን መነጋገር እንዳለብን ወሰንኩ እናም ማዛጋቱ ሲበዛብኝ እየፈራሁ እዛው ሰፈራችን ያለች ጫት ቤት ሂጀ ጫት ገዝቸ ተመለስኩ እንግዲህ ይታይህ ስንት አመት ሳመነዝከው የኖርኩትን ጫት ዋጋ እንኳን ገና ዛሬ መስማቴ ነው

የገባኝ አንድ ነገር ብቻየን ሁኘ ጫቱን ስመለከተው ሳቄ መጣ ይሄንን ነው ስበላ የኖርኩት ብየ አገላብጬ አየሁት አዲስ እንደተወለደ ህፃን ሁሉ ነገር እንግዳ ሆነብኝ በፍቅርም ይሁን በቤተሰብ ወይም በዝምድና አለኝታ የሚመስሉን ሰዎች እንደመቃብር አፈር ተጭነው ከአለም አለያይተውን እንደኖሩ የሚገባን ልክ እነሱ ሲነጠሉን በራሳችን አንድ እርምጃ እንኳን ለመራመድ ሁሉ ነገር ጨለማ ሲሆንብን ነው ደግሞ አንዳንዴ የምንደገፋቸው

ሰዎች እንኳን እኛን አስደግፈው ሊቆዩ ራሳቸውም ምን ተደግፈው እንደቆሙ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው እስቲ አሁን ወንዴ አባቱ ባይኖሩ በዚች ምድር ምን ሰርቶ ምን ሁኖ ነበር የሚኖረው እኔስ ወንዴ ባይኖር ምን ሁኘ ምን ሰርቸ ነበር የምኖረው ማን ማንን ነው የተደገፈው ይሄስ ድግፍግፍ ጥግንግን ህይዎት እንዴት ነው ራስን ችሎ ወደመቆም የሚቀየረው

ወንዴ ይምጣልኝ ጓደኛ አልፈልግም፣ ሰው አልፈልግም፣ ፊልም አልፈልግም፣ ብር አልፈልግም፣ ጫት አልፈልግም፣ መዝናናት አልፈልግም፣ መሳሳም መተሸሸት አብሮ መተኛትም አልፈልግም ሆዴ ማሬ እያሉ መንቆለጳጰስ አልፈልግም !! ምፈልገው ነገየን ነው ቢያሻው ጠንቋይ ቤት ሂዶ ይጠይቅ ከፈለገ እንደመንግስት መስሪያ ቤት ራእይ ምናምን ብሎ በሩ ላይ ፅፎ ይለጥፍ አያገባኝም ብቻ ወንዴ አንዲነግረኝ እፈልጋለሁ የነገ እጣ ፋንታችን ምን እንደሚሆን እንዲነግረኝ እፈልጋለሁ "መቸም አባባ እስከሚሞት ጠብቀን ሃብቱን መውረስና የሱን ንግድ መቀጠል ካለኝ ገርሞኝ አላባራም !"

ብቻ ወንዴ ይምጣ ደግሞ ልቤ ተጨንቀ ሲመለሱ መንገድ ላይ የሆነ ነገር ቢገጥማቸውስ ብየ "እግዚአብሔርየ " ብየ አይኔን ወደላይ ወደኮርኒሱ አነሳሁ "ውይ ልእልት ዛሬስ ከምን አስታወሽኝ በስንት ዘመንሽ" ያለኝ ነው የመሰለኝ እግዚአብሔር

# ክፍል 9

ትላንት 10 :00 ሰዓት አካባቢ ከሆስፒታል ወጣሁ ልክ በጓደኞቸ በእናቴና በእህቶቸ መሃል ሁኘ ከሆስፒታል ሳይሆን የሆነ ትልቅ ጀብዱ ሰርቸ ከዘመቻ የምመለስ ነበር የምመስለው ልክ ሆስፒታሉ ኮሪደር ላይ ስደርስ ሁለት ነርሶች ነጭ ጨርቅ ጣል የተደረገበት አስከሬን በተሸከርካሪ አልጋ እየገፉ በአጠገባችን አለፉ የሆነ ነገር ሸከከኝ ከኋላ የሟቹ ዘመዶች ሆስፒታሉ እስኪንቀጠቀጥ እየጮሁና በተለይ አንዷ ፊቷን እየነጨች አለፉ

እህቴ (መቸም ወሬኛ ናት) አስከሬኑን ተከትለው ከሚሄዱት አንዱን ቁመቱ ከመርዘሙ የተነሳ ሱሪው ብቻ ሳይሆን ቆዳው ራሱ ያጠረው የሚመስል ልጅ ክንዱን ያዝ አድርጋ አስቆመችውና ....

"ይቅርታ ወንደሜ ምን ሁኖ ነው " አለችው ወደአስከሬኑ በአገጯ እየጠቆመች

" ሙቶ ነዋ ሌላ ምን ይሆናል " ብሏት በዛ ቁመቱ ለሶስት ሰው የሚሆን የእርምጃ በጀት ባንዴ እያፈሰና እየሩን እየቀዘፈ ትቷት ሄደ የሰውየውን መጣደፍ ለተመለከተ አስከሬኑን ሳይሆን የሟቹን ነፍስ ርቃ ሳትሄድ ለማስመለስ የሚሮጥ ይመስል ነበር ! እንደው እዛ እየተለቀሰ አንስቅም ብለን እንጅ እኔም ጓደኞቸም በሰውየው መልስ ሳቃችን እስከነገ ባላለቀ ነበር እናቴ እጀን ያዝ አድርጋ ፈጠን ፈጠን እያለች ወደውጭ መንገዳችንን ቀጠልን እህቴ እናቴን እያየች ፈገግ አለችና ወደጆሮየ ጠጋ ብላ

" ማሚ ፈርታለች " አለችኝ !

"አንችስ" አልኳት የኛ ጀግና በሚል የማሾፍ ድምፅ

"እኔማ ሞት ጋር አንገት ላንገት በመተናነቅ ይሄው አትርፌ ወደቤትህ እየወሰድኩህ ነው "ብላ ቀለደች ድምፅዋ እንደወትሮው አልነበረም ጎርነን አለብኝ (ህቴን ድምፅ መች አጣሁት) ዞር ብየ አየኋት አቀርቅራ ነው ምትራመደው አገጭን በሁለት ጣቶቸ ደግፌ ቀና አደረኳት አይኖቿ እንባ ሞልተው ነበር በቃ እንዲህ ናት የሞተ ሰው ስትመለከት ከሞት አፋፍ መመለሴ ዛሬ ገና ትዝ ሳይላት አልቀረም  አቀፍኳት እቅፌ ውስጥ ልጥፍ አለች ! "አብርሽ ትንሽ ለእኛ እንኳን አትጠነቀቅም ለምን የማይረባ ድፍረት ትዳፈራለህ ምናለበት እኛ ጋር ብትሆን ለምን ብቻህን ትሆናለህ አንድ እዚህ ግባ የማይባል ተራ ዱርየ ዘመድ እንደሌለው ሰው እንዲህ ሲጨማለቅብህ" ብላ እየየ

"አንቸ በሰላም አገር የምን ለቅሶ ነው" ብሎ ጓደኛየ ሊያሾፍ ሲሞክር

"ዝም በል እዛ አያገባህም " ብላ ቀልቡን በጩኸት ገፈፈችው ሰው ሁሉ ዞር ብሎ እስኪያየን (አራስ ነብር)

"እናንተ ጓደኛ ከሆናችሁ አትመከሩትም. የናት ያባቱ ቤት እያለ የትም ብቻውን ሲንከራተት እንደጓደኛ አትመከሩትም በስርአት ምግብ እንኳን አይበላ ሁልጊዜ ብቻውን አትመከሩትም ጓደኞቹ ከሆናችሁ" ብላ ጠንካራ የምላት እህቴ እንባ በእንባ እንደህፃን እቅፌን ጠበቅ አድርጌ አባበልኳት

"ልቀቀኝ እዛ ህፃንህን ፈልግ" ብላ ቆንጠር ቆንጠር እያለች በእናቴ በኩል ዞራ ቆመች እናቴ አንድ ነገር አልተናገረችም ይሄ ዝምታ እህቴን መደገፍ መሆኑን አውቃለሁ! ሁልጊዜ የተከራየሁትን ቤት ለቅቄ ቤተሰቦቸ ጋር እንድኖር እንደነዘነዘችኝ ነው እንኳን ይች ሰበብ ተገኝታ !

እንደውም ፈጠን ፈጠን ብለን እንድንሄድ እየመራችን ነበር የእናቴን ፍርሃትና ፍጥነት ለተመለከተ ሰው ሃኪሞቹ ከኋላ ጠርተው "አብርሃም በስህተት ነው ከነህይዎትህ የወጣሃው ና ተመልሰህ ሙት " የሚሉኝ ነበር ያስመሰለችው በዚሁ ስሜት በዝምታ ተውጠን ስንወጣ ልክ በር ላይ እማማ ቁንጥሬ ሲገቡ አገኘናቸው (ተመስገን በሚዶክክ ስሜት ውስጥ እማማ ቁንጥሬንም ቢሆን ልኮ ከዝምታ ያወጣን አምላክ) በእጃቸው ቬርሙዝ ይዘዋል

"ውይ ወጣህ እንዴ ምን አስቸኮለህ ልጀ " አሉ ...እናቴ በስጨት ብላ አየቻቸው ! ቀጠል አድርገው "እሰይ ከተሸለህማ እንኳን ወጣህ ወደቤት ነው የምትመጣው አይደለም? " ሲሉ ጠየቁኝ (ይች ሴትዮ ነገር ያበላሽ ርእስ አንስተው አረፉ እዚች ሴትዮ ውስጥማ ሰይጣን አለ)

"አይ ትንሽ እኔጋ ይሁን እማማ " አለች ማዘር" አዎ ትንሽ እናትህ ቤት አረፍ በል ቤት አከራይህም በጧት መጥተው በርህን ሲወግሩ ነው ያረፈዱት እኔም ማታ እንቅልፍ ወስዶኝ ያላየሁት ድራማ እያየሁ እንዳላቋርጥ ብየ "የለም " አላልኳቸውም" አሉና ሳንወድ በግዳችን አሳቁን ተንኮለኛ እኮ ናቸው እስቲ አከራየ እጃቸው እስላይ ቤቴን ሲያንኳኩ ብቅ ብለው የለም ለማለት ምን ጊዜ ይወስዳል አይ እማማ ቁንጥሬ !

"ይሄን ያዥ እናቴ. እንግዲህ እንደወጣቶቹ ሾርባ ጣፍጦህ ባትጠጣውም ምንም አይልህ ሌላው ቢቀር የቬርሙዙን ቀለም እያየህ ጨክነህ ጠጣው " አሉና እማማ ቁንጥሬ ቬርሙዙን ለእህቴ እያቀበሏት (ይች አሽሙር እንግዲህ የልእልትን ሾርባ ለመንካት ነው ልክ ሲናገሩ ነው የቬርሙዙ ቀለም አረንጓዴ መሆኑን ያስተዋልኩት ልክ እንደልእልት ቬርሙዝ አሁንማ እንኳን እኔ እናቴም ባናባቸዋለች ነገረኛ የሆኑ ሴትዩ ) እህቴ ፊቷ በታፈነ ሳቅ ተሞልቶ በአክብሮት ተቀበለቻቸው እማማ ቁንጥሬ እንደሄዱ እህቴ "ይች ሴትዮ ግን የመጨረሻ ነው የተመቹኝ በደንብ ከቀረብካቸው አሪፍ ዘመድ የሚሆኑ ነገር ናቸው ሂሂሂሂ" አለችኝ የቅድሙ ኩርፊያና ለቅሶዋ ድራሹ ጠፍቷል !

" አንች ራስሽ ቁንጥሬ ነገር አይደለሽ ሌላ ነገረኛ ዘመድ ምን ያደርግልኛል "

"እስቲ አትነዝንዥው አንችየ " አለች እናቴ (አይ ቅድም እንደዚህ አትልም ነበር) ሆስፒታሉን ዞር ብየ አየሁት ለምን እንደሆነ እንጃ ከሆስፒታል ሳይሆን ተወልጀ ያደኩበትን አገር ጥየ የምሰደድ መስሎ ተሰማኝ እህቴ በነገረኛ አይኗ አይታኝ ወደጆሮየ ጠጋ አለችና በሹክሹክታ

" ለልእልት ደውየ ከሆስፒታል መውጣትህን ነግሪያታለሁ " አለችኝ

" ማን አዘዘሽ ከምር አንች ልጅ ግን አንዳንዴ ታበዥዋለሽ" አልኩ ቆጣ ብየ እሷ እንኳን ቁጣየ ሊያስደነግጣት ጭራሽ ፈገግ ብላ እንዲህ አለችኝ

" አቡቹ ከሆስፒታል እንደወጣ እኛ ቤት ነው የሚቆየው ያንን በምድራችን ላይ ካሉ ምግቦች ሁሉ ወንድሜ የሚወደውን ሾርባሽን ይዘሽ ሆስፒታል ድረስ እንዳትደክሚ ብየ የቤታችንን አድራሻም ነግሪያታለሁ" በግርምት አየኋት

" በተያያዘ ዜና ልእልት "እንኳን ለዚህ አበቃህ ነገ ጧት እመጣለሁ" ብላለች " ብላኝ ጠቀሰችኝ (እህቴን እንደዛሬ ወድጃት አላውቅም የኔ ምርጥ እህት !!) ቢሆንም ኮስተር ብየ እንዲህ አልኳት "ማድረግ አልነበረብሽም ሌላ ነገር አስመሰልሽው !" (ለታናሽ እህት ፊት አይሰጥም እንጅ አቅፌ ብስማትም ሲያንሳት ነው)

"ሌላ ነገር ሳይመስል እንዲሆን ነበር የምትፈልጉት ሂሂሂ " እንዲሁ ከጎኔ ተሸጉጣ እየጠዘጠዘችኝ በአጀብ ወደእናቴ ቤት ሄድኩ ! እህቴ ቅድም አስደንግጣው ዝም ላለው ሚስኪን ጓደኛየም አልተመለሰች" ነርሷን ቻው አልካት ?" አለችው ቅድም ለጮኸችው ጨኸት ይቅርታ መጠየቅ በሚመስል ድምፅ የትንሸዋን መኪና መሪ በጥንቃቄ ይዞ

"ልንዳበት ....እንግዲህ አትነጅሽኝ አንች ልጅ " አላት ...እና ምንም በሌለበት ጺፕ አደረገው ክላክሱን

"ባዶው መንገድ ላይ መንፈሷ ጋውን ለብሶ ገባብህ እንዴ " አለች እህቴ

"ይች ልጅ ግን ያንች ልጅ ነች ማዙ የእማማ ቁንጥሬ ልጅ እየመሰለችኝ ነው" አለ ጓደኛየ ታረቁ ማለት ነው በቃ ... !!

**** ****** ******

በቀጣዩ ቀን ጧት ወደአራት ሰዓት አካባቢ እህቴ መኝታ ቤቴን በርግዳው ገባችና "ሚስታችሁ መጣችልህ " ብላ በመጣችበት ፍጥነት ተመልሳ ወጣች ስልኳ እጇ ላይ እየጮኸ ነበር ልእልትን ልትቀበል እየሄደች ነው ከአልጋየ መነሳት ሸክም ሁኖብኝ ስገላበጥ ያረፈድኩ ሰውየ እንደጥይት ተስፈንጥሬ ተነሳሁና ከላይ የለበስኩትን ፒጃማየን አሽቀንጥሬ ጥየ ቲሸርት ለበስኩ

ፊቴን ታጠብኩ መቸም ልእልትን የምትቀጥራት ሹሉቃ ሻይ ቤት ነው ማንም ሰው ቤታችን ሲመጣ እዛ ነው ምልክቱ ጅራታም ኮከብን በሚያስንቅ ፍጥነት ሳሎኑን አቋርጬ ምኝታ ቤቴ ተመለስኩና የተዝረከረከውን ልብስ የት የት እንደሸጎጥኩት እንጃ ምኝታ ቤቴ ፀዳ አለች ከዛ የአልጋ ልብሴን ለብሸ ምንም እንዳልተፈጠረ ለጥ አልኩ (አለ አይደል ሁልጊዜም ቢሆን የተዝረከረከ ነገር አይመቸኝም የሚል መልእክት መሆኑ ነው) እህቴና ልእልት እንደአስር አመት ጓደኛሞች እተሳሳቁ መጡ

ልእልት እናቴ ጋር ሰላምታ ስትለዋወጥ ከምኝታ ቤቴ ሁኘ ድምፅዋን እንደሰመመን እየሰማሁ ደስ አለኝ እናቴ ቤት ድረስ ተወልጀ ያደኩበት ቤት ድረስ ስትመጣ እንዲሁ የበለጠ የመቀራረብ ስሜት ተሰማኝ (((አብረን ውሃ እየተራጨን አፈር እየፈጨን ያደግን መሰለኝ ))) እህቴ እየመራች መኝታ ቤቴ ድረስ አመጣቻት (ይች ልጅ በዚህ ኢያያዟ አቅፋ አልጋየ ላይ ሳታስቀምጣት አትቀርም) ልእልት ዛሬ ደግሞ ለየት ብላለች ስታየኝ ፊቷ በፈገግታ ተጥለቀለቀ (እኔ ከልእልት የሚገርመኝ አንድ ነገር ቢኖር (እሱማ ብዙ ነገር ነው የሚገርመኝ) ፈገግታዋ የህፃን ልጅ ፊት የለበሰች ያስመስላታል የሆነ አንጀት የሚበላ እናቱን የናፈቀ ድንቡሽ ህፃን አይነት)) ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳምንና " አብርሽ ...እንኳን ለቤትህ አበቃህ " አለችኝ ....ያ አረንጓዴ ፔርሙዝ አብሯት ነበር እህቴ ተቀበለቻትና ወደኔ ዞር ብላ ጠቀሰችኝ " ተጫዎቱ " ብላን በሩን ዘግታው ሄደች ልእልት የምኝታ ቤቴን ከዳር እስከዳር ቃኘቻት

" እዚህ ድረስ ደከምሽ " አልኳት

"ኧረ ችግር የለውም " ብላ ትክ ብላ አየችኝና ትንሸ ፈገግ ብላ

"አሁን ምንም አይሰማህም አይደል " አለችኝ ((አሁንማ ምንም አይሰማኝ መስሚያየ ጥጥ ነው አንች እያለሽ ልእልትየ )))) ማለት እያማረኝ " አሁንማ ዳንኩ በቃ" አልኩ !

" ፊትህ ራሱ ተመለሰ እንደድሮህ ሆንክ " አለችኝ ... ( አአአአአአ?? ድሮ መቸ ነው?? ከዚህ በፊት ታውቀኝ ነበር ማለት ነው ?) ((ይሄማ በገለልተኛ ወገን ሌላ ጊዜ መጣራት ይኖርበታል !)) ልእልት እና እኔ የምናወራው የጠፋብን ይመስል ዝም ብለን ተቀመጥን እኔ ግን በሃሳቤ የነገረችኝን ታሪኳን ተመልሸ ማሰብ ጀመርኩ አንዳንዱ

ታሪክ ከባለ ታሪኩ ፊት ጋር አይሄድም ለምሳሌ የሂትለርን ፎቶ እያዩ ታሪኩን ቢያነቡ እውነተም ይሄ ግንባሩ የጨካኝ ይመስላል ምናምን ይባላል የእማሆይ ቴሬሳን ፊት እያዩ ደግ ሰውነታቸውን ቢሰሙ ፊታቸው ከስራቸው ጋር ይሄዳል የአንስታይንን ፎቶ ያየ ማንም "ይሄ ፎቶው የሚታየው ሰውየ ሳይንቲስት ነው በሳይንስ ጢባጢቦ የተጫወተ ሰው ነው " ቢባል ያምናል ማንም ሰው ግን የልእልትን ፊት እያየ ከፉ ትሁን ደግ ማሰብ አይችልም እውነቴን ነው በቃ ዝም ያለ ፊት ነው እዛ ፊት ፊት ማሰብ አይቻልም ዋጥ ነው የሚያደርገው ፒርሙዳ ትሪያንግል ልእልት ፊት ላይ ይዞታ ሳይኖረው አይቀርም ! ሁሉም ሃሳቤ ልእልት ፊት ላይ ሲደርስ የደረሰበት ይጠፋኛል !! በዛ ላይ አእምሮየ ማንንም ይጠረጥራል እያንዳንዷን ቃል ይሰነጥቃል ልእልት ላይ ግን ዝም !!

ልእልት ደግ ፊት ናት ሰላም ፊት ናት ረፍት ፊት ናት ወደቅላት የሚወስደው ይይምናዋ ሰፊ የሰላም መስክ አይኖቿ መስኩ ላይ በንፁህ ውሃ ተሞልተው የተቀመጡ ጉድጓዶች

ልእልት ውብ ናት !! ሰው ይሄን ገላ አቅፎ ተኝቶ እነዚህን ጡቶች ተንተርሶ ኑሮ በእነዚህ ከንፈሮች እንደሚፈቀር ተመስክሮለት እንዴት ቢላ ይዞ ጎረቤቱ ላይ ይዘምታል በግዚአብሔር ?? ለነገሩ መልክ አሳሳች ነው ስንቱ የውብ ፊት ባለቤት ነው ደግ ሩህሩህ መስሎን ልባችንን እንደፈሪ ጅብ ዘንጥሎት የሮጠው የደበቀውን ክፋት እድሜ ልክ የማናጸዳው ፀፀትና ቁጭት ገልብጦብን የሄደው ስንቶችስ ናቸው አረመኔ መሳይ ቆዳቸው አስፈርቶን የሸሸናቸው ሰዎች ስንቀርባቸው ግን መለአክ ሁነው ያገኘናቸው ምን እሩቅ አስኬደን የዚች የውበት ስንክሳር የተከተበባት ልእልት ባል" ወንዴ አንበሳው" አለ አይደል ቆንጆ ሴት ሊመስል ግማሽ መንገድ የጀመረ ቆንጆ ፊቱን አይቶ ገራገር የመሰለኝ ሰው ቢላውን ይዞ ከተፍ ያለው! (((በዚች ምድር እንደሰው ፊት የተወሳሰበ ስሜት የተፃፈበት ምን መፅሃፍ አለ ?))) ቢሆንም ጠንክረው ሊቆሙ የሚፍገመገሙት የልቤ እግሮች የልእልት አይኖች ባረፉብኝ ቁጥር እያዳለጣቸው ይንገዳገዳሉ ምናልባት በፍቅር ይሁን በሌላ መሻት ይች ልእልት መንገዱን እያጨቀየችባቸው ይሆናል? መንሸራተቱስ ይሁን እየወደቁም እየተነሱም ይወጡታል ብቻ ይሄ የልእልት ውበት አሮንቃ ሁኖ እስከአንገታቸው ሰጥመው እንዳያርፉ ጎታች እንኳን በሌለበት ማንስ ቢሆን ማን የሰው ትዳር አሮንቃ ውስጥ ግቡ አላቸው ነው የሚለው እንጅ እንዲች ብሎ እወጣ ዘንድ እጁን የሚልክ የለም ምን ውዳሴው ቢበዛ ምንም ባየኋት እና ባሰብኳት ቁጥር ውስጤ የሚሰማው አድናቆት ለልእልት ቢያንስ ምንም የልእልት ውበት የምድር ውበትና የምቾት ፍፃሜ ቢመስልም ቅሉ (((በዚች ምድር እንደሰው ፊት የተወሳሰበ ስሜት የተፃፈበት ምን መፅሃፍ አለ ?))) ይሄን ገራገርና ሳቂታ ውበቱ ልብን ፀሃይ ላይ እንደተቀመጠ ቅቤ የሚያቀልጥ የልእልትን ፊት ስንገልፀውም እንደሚመስለው ሳይሆን በተቃራኒው ይህ ሰቆቃና የህይዎት ውጣ ውረድ ተፅፎበት እናገኘዋለን ....

## ክፍል 10

"እንክብካቤ ሁሉ አክብሮት አይደለም " አለች ልእልት

"ይሄውልህ እንግዲህ አማርኛ ፊልም ላይ ድራማ ምናምን ወይ ጸጉር ቤት ስቀመጥ የታጠበ ፀጉሬ እስኪደርቅ በአተት ኮተት ታሪካቸው የሚያደርቁኝ የፋሽን መፅሄቶች (በኋላ ነው አድርቅ መሆናቸው የገባኝ በፊትማ እንደውዳሴ ማሪያም ነበር የምደግማቸው ) እነዚህ የፋሽን መፅሄቶች ለሴት ያደላ በሚመስል የስጋ ወግ ስለስንት አይነት እንክብካቤ ነግረውኛል "ባሌን የምወደው ስለሚንከባከበኝ ነው " የምትል ዘፋኝ ሞዴል ምናምን በየመፅሄቱ አትጠፋም እኔም እነዚህ ሴቶች የሴቶች ቁንጮ መስለውኝ (ያው መቸስ ሰው ባዶውን መፅሄት ሽፋን ላይ ኩፍስ ብሎ የሚወጣ አይመስለኝም ነበርና) በቃ ወንዴ ስለሚንከባከበኝ ምርጥ ባል ነው ብየ ቁጭ ብየ ነበር ! አንዳንዶቹ መፅሄት ላይ የወጡ ሴቶች እዛው እኔ ፀጉሬን የምሰራበት ፀጉር ቤት እኔው ጎን ተቀምጠው የራሳቸውን "ኢንተርቪው" ላስረኛ ጊዜ ሲያነቡ አያቸዋለሁ ! እነሱ ጎን መቀመጤ ከዚች አገር ተመርጠን ለድሎትና ለምቾት የታደልን ወይዛዝርት አድርጌ እራሴን እንዳስብ ያደርገኝ ነበር ! "ኦ እከሊት የምትሰራበት ፀጉር ቤትኮ ነው የምሰራው" ይሉት ተልካሻ ኩራት ! እና እነዚህ ሴቶች በነበረ ድድብና እንቅልፌ ላይ በጥሬ ፍልስፍናቸው እንቅልፍ ጨምረውልኝ ኑረዋል እንክብካቤ ምንድነው ባል ለሚስቱ ቀሚስ ገዛ ተብሎ እንክብካቤ ሲባል አስበኸዋል አንዲት

ሴት "ባሌ ስለማይደበድበኝ በጊዜ እቤቱ ስለሚገባ ይንከባከበኛል "የምትልበት አገር ይታይህ አለመደብደብ እንክብካቤ ሲሆን እንግዲህ ሚስትን መደብደብ ወንጀል ሳይሆን "የእንክብካቤ ጉድለት " ሊሆን አይደል እድገታችን ራሱ ወንድ ለሴት ልጅ ሊያደርግ የሚገባውን እንክብካቤ ከስጦታና ከሰማነው አስከፊ ትዳር የተለየ ትዳር ስላለን ብቻ ይሄንኑ ሚዛን እንድናደርገው አድርጎናል እውነቱ ግን የወንድ ጨዋነት ልኩ የሚታየው ሚስቱ ምንም ይሁን ምን እሱን ተከትላ መንኳተቷን አቁማ "ለምን" ማለት የጀመረች ቀን የሚያሳየው ጨዋነት ነው የሚሰጠው ትክክለኛ ምላሽ ነው !! እንክብካቤ ልኩ ሚስትን አቋሟን የሚያሳምር ቀሚስ አልብሶ መንተት ሳይሆን በራሷ እንድትቆም በሞራልም ሚችለውን ሁሉ መርዳት መቻል ላይ ነው፡፡

ለሴት ልጅ የማያቋርጥ ስጦታ እየሰጡ ስጦታ ጠባቂ ተስፈኛ ማድረግ እንክብካቤ አይደለም እንደውም ከጡረታ እኩል ነው ወጣት ጡረተኛ ማድረግ ቆንጆ ጡረተኛ ! የፍቅር ጡረተኛ !! ሲቆይ በብሬ ነው የማኖራት የሚል የንብረት ባለቤትነት መንፈስ ያነግሳል ! ምርጥ ወንድ በእኔ ተማመኝ የሚል አይደለም እኔ ባልኖርም ግራ መጋባት ባጠገብሽ እንዳያልፍ ብሎ መንገድ የሚመራ ነው ስንቶቹ ናቸው አባወራ ሲሞት ሜዳ ላይ ልጆቻቸውን ይዘው የወደቁ !! ወንድ ባል ወላ ፍቅረኛ እድሜ ልክ የሚኖር ብረት ምሰሶ አይደል ሰው ነው ወይስ ይሄም ቢሄድ ራስን ለሌላ ወንድ ጉዲፈቻ ለመስጠት ተስፋ ማድረግ ነው ትዳር አይደለም ይሄ ጉዲፈቻ ነው የሚስት የፍቅረኛ ጉዲፈቻ ! ልክ ወንዴ ደብረዘይት የመኪና አደጋ የደረሰበት ጓደኛውን ለማየት የሄደ ቀን ዝን እንደቆመ ማሽን (መኪና ምናምን) በምቾት እና ሆሆታ ታስሮ የቆመ አእምሮየ ድንገት እያቃሰተ ተነስቶ ለራሴም ልቆጣጠረው በማልችለው ፍጥነት በሃሳብ ተፈተለከ

ልክ እንደጣውላ መሰንጠቂያ ማሽን ነበር ሁሉም ነገር የሚጮህብኝ ለምን እንዴት የጥያቄ እና ወቀሳ መዓት እያመጣ ይቆልልብኝ ነበር .... ምንም ይሁን ማሰብ መጀመር ፈውስ ነው ....አብርሽ ሙት !! እንደውም የሴቶች ቀን የባንዲራ ቀን የፍቅር ቀን ምናምን እንደሚባለው ይች አገር ይሄ ህዝብ "የሃሳብ ቀን" የሚል አንድ ቀን ሊሰይምለት ይገባል ሁሉም ብቻውን ቁጭ ብሎ ፋታ ወስዶ አነሰም በዛም የሚያስብበት !! የሰው ልጅ ከእንስሳ የሚለየው ማሰብ በመቻሉ ነው ይላሉ ምናይነት ሃሳብ ማሰብ በመቻሉ ??? የሄንኛው ቀሚስ ከዚህኛው ጫማ ጋር ማች ያደርጋል የሚል ሃሳብ ነው ከእንስሳ የሚለየን? ይሄንኛው ቅባት ከዛንኛው የተሸለ ቆዳየን ያለሰልሳዋል ማለት ነው ከእንስሳ የሚለየን ሃሳብ? ለራሳችን ብዙ ሳቅና የጨረባ ተስካር የሚሉት አይነት ጫጫታ በመፍጠር አለምን መርሳቱ ነው ትልቁ የአእምሯችን ፈጠራ ? ልእልት ትክ ብላ አየችኝ አይኖቿ ጥርት ያሉ ምን ማለት እንደፈለገች በትክክል የገባት በትክክልም ዓይኖቿ ነገዋን የሚመለከቱ ይመስላሉ ኖርኩበት የምትለው ህይዎት እና አነጋገሯ አልገጥምልህ ብሎኝ አያታለሁ ማሰብ ከመማር እንደሚበልጥም በልእልት ገባኝ ሳይማሩ ማሰብ ይቻላል ተምሮም አለማሰብ ይቻላል ትክክለኛው ትምህርት ምን ማሰብ እንዳለብን የሚያስለጥነን ሳይሆን እንዴት ማሰብ እንዳለብን የሚመራ ብርሃን በፊታችን የሚያበራ ነው

"እንዴት" ማለት ስንጀምር "ለምን ማለት ስንጀምር" ቢያንስ ችግራችንን ፊት ለፊት ማየት እንጀምራለን እንደውም መማር ባንማርም ለምናውቀው ችግር መፍትሄ ይዞ ሲመጣ ነው የእድገትም እንበለው የውድቀት መሳሪያ የሚሆነው እና ልእልት ያንን ምቾት ያንን ድሎትና ፍቅር የመሰላትን አብሮነት በአንድ ቀን እሷ እንደምትለው

"የተረገመ ይሁን የተመረቀ ቀን" ብቻ "ለምን " ብላ ጠየቀች

"እና አብርሽ የዛን ቀን እዛች ሶፋ ላይ ተኮርምቸ የነገ እጣ ፋንታየ ምንድነው ብየ አሰብኩ ሚሊየኖች ላባቸውን ጠብ አድርገው እንደልፋታቸው ሳይደሰቱ በሚኖሩባት አገር ሚሊየኖች እንደኔው ከደሃ ቤተሰብ ተፈጥረው ግን ከእኔ በላይ በስራ ፈግተው ቁራሽ ዳቦ እያጡ በርሃብ በሚጠራሞቱባት አገር

የፈሰሰ ውሃ የማላቀና እኔ በህይዎት ዘመኔ አንዲት ነገር ሰርቸ የማላውቅ እኔ እንዲህ የተቀማጠለ ህይዎት ለመኖር የታደልኩት በምን ምክንያት ነው አልኩ ቆንጆ ሴት ስለሆንኩ ብቻ ? በቃ ? አእምሮየ የመጣልሽን እድል አትግፊ አርፈሽ በድሎት ኑሪ ይለኛል ለማንም አስቤ አይደለም አገር ህዝብ ለሚባለው ነገር የምቆረቆር ሁኘም

አይደለም ግን ዛሬ ለዚህ ምቾት የዳረገኘን እድልም በለው አጋጣሚ ነገ ከተሰቀልኩበት ማማ አውርዶ ችግር ላይ እንዳይፈጠፍጠኝ አስተማማኝ ነገር ለመፍጠር እየቃተትኩ ነበር"

በቀጣዩ ቀን ወንዴ ከደብረ ዘይት መጣ ጓደኞቹ ሁሉ ከነሳቃቸው ከነጫዋታቸው ከነጫታቸው ከነቆንጆ ሴት ጓደኞቻቸው ቤታችንን ሞሉት ነብሴ ትላንት ሙሉ ቀን በብቸኝነት ስትላቅጥበት የነበው ሃሳብ ያ ሁሉ ፍልስፍና ላስታውስህ ብለው ከየት ይምጣ በቃ ወንዴን እጠይቀዋለሁ ያልኩት ሃሳብ ሁሉ ድራሹ ጠፋብኝ ምሳ ይበላ ሲባል እና ካ ከዚህጉርሻ ታጠቁ እጆች ወደኔ ሲወነጨፉ (ሁልጊዜም ወንዶችም ይሁን ሴቶች መሃል ስገኝ እንክብካቤው ወደኔ ያደላል መሃል እሆናለው በቃ ትኩረቱ እኔ ላይ ይሆናል ትንሽ ኩራት ሳይጭርብኝ አልቀረም ይሄ ነገር ) ቡና ይፈላ ሲባል፣ ጫት ሲቀራርብ፣ ቤቱ በእጣን ጭስ ተሞልቶ ጨዋታና ሳቃቸው የማይጠገብ ጓደኞቻችን ግራ ቀኝ ጥርስ የማያስከድን ጨዋታቸውን ሲያዘንቡት ደግሞም በዛ ህልም በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ወንዴ አስር ጊዜ በፈገግታ ሲመለከተኝ በስሱ አይኖቹ እየተመለከተኝ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው የጫት ቅጠሎቹን እየቀነጣጠሰ ሲሰጠኝ ጫቱ ራሱም ውስጤ ስራውን ሲሰራ እንኳን ለነገ ለቀጣይ ሽ አመታት በምድር ብኖር ችግር እንዲች ብሎ የማይነካኝ ዘላለም ልእልት ሁኘ በፍቅር ነግሽ የምኖር መስሎ ተሰማኝ !!

"አብርሽ "አለችኝ ድንገት

"ወይየ ልእልት" አልኩ (በለውውውው "ወይየ" ያች ነገረኛ እህቴ በአካባቢው አለመኖሯ እንጅ ይች ቃል ታሪካዊ ሁና በተመዘገበች ነበር በህይወቴ ማንንም "ወይየ" ብየ አላውቅም እንኳን ወይየ ወይ እራሱ የሆነ ማግኔት መንፈስ ያለው ቃል እኮ ነው አቤት አለሁልሽ ምን ልታዘዝ ስለጠራሽኝ ደስ ብሎኛል የፈለግሽውን ጠይቂኝ ወዘተ የሚል "እንስፍስፍ" ቃል ነውኮ ወይየ !! መንገድ ላይ ድንገት መንገድ ጠፍቶብን ልንጠይቃት አንዷን ልጅ ይቅርታ የኔ እህት ስንላት "ወይየ " ብትለን የሆነ የሚነዝር ስሜት አለውኮ ኧረ ስለወይየ እናውራ ካልን ስንት ጉድ አለ አስማተኛ ቃል ነው እና ልእልት "አብርሽ" ስትለኝ "ወይየ" አልኳት )

"መቸም ጫት ቅመህ ታውቃለህ !!" አለችኝ ጥያቄ ሳይሆን

"እና ጫት መቃምን እንደምታውቀው " ብላ ወሬዋን ለመቀጠል እንደመንደርደሪያ ነበር ጣል ያደረገችው

"አይ አላውቅም " ስላት ቀጥ ብላ በግርምት ተመለከተችኝ አልገረመኝም ብዙ ጓደኞቸ ጫት ቅሜ አላውቅም ስል ልክ "ከተወለድኩ ጀምሮ ውሃ ጠጥቸ አላውቅም ወይም ምግብ በልቸ አላውቅም " ያልኩ ያህል በግርምት ይመለከቱኛል ግርምቱ ውስጥ ብዙ አለማመንና ግማሽ አታካብድ ባክህ የምን ማካበድ ነው " የሚል ወቀሳ ቢጤም አለበት ...እና የልእልት ግርምት አልገረመኝም

"ማለት ...?" አለችኝ

"ምን ማለት ....?" አልኳት ግራ ገብቶኝ

"ጫት ምንም ቅመህ አታውቅም ወይስ አቁመህ ነው ?"

"አይ ጫት ቀምሸ አላውቅም " አልኳት ...(እሷ በመቃሟ ወቀሳ እንዳይመስልብኝ መቃምም አለመቃምም ያን ያህል የሚካበድ ጉዳይ እንዳልሆነ ለመግለፅ ቀለል ለማድረግ በሚሞክር ድምፅ

" ልእልት የግንባሯን ቆዳ ወደላይ ሰብሰብ አድርጋ መገረሟን ገለጸችና

"እንግዲያውስ የምልህ ሁሉ አይገባህም " አለችኝ

"ለምን አይገባኝም በደንብ ይገባኛል እንጅ " አልኳት በዚች ስበብ ታሪኳን እንዳታቋርጠው ፈርቸ ዝም ብላ ወደኮርኒሱ ስትመለከት ቆየችና " ጫት ስትቅም የጫት ስም ሲነሳ ጫቱ አይደለም ትዝ የሚልህ ስሜቱ ነው የሆነ የሚያንሰፈስፍ ስሜት አለው ለምሳሌ ሁልጊዜ የወንዴ ጓደኞች ሲመጡ ምሳ ስንበላ ቀጥሎ ጫት እንደምንቅም ቡና እንደሚፈላ ሳስብ የሚሰማኝ ጉጉት የሆነ አፌ ምራቅ ሁሉ ይሞላል የሆነ የሚያጣድፍ ነገር ውስጥህን

ይሞለዋል እንዴት ልበልህ በጣም የምታፈቅራት ልጅ ቀጥርሃት ልትመጣ ቤትህን ስታዘገጃጅ ነገር እንደዛ አይነት ስሜት አለው በቃ

ምሳ በልተን ቦታ ቦታችንን ይዘን ጫቱ የተጠቀለለበት ጋዜጣ ሲከፋፈት የሚያሰማው ድምፅ ጆሮየ ላይ እንደውብ ሙዚቃ ነበር የሚናፍቀኝ የመጀመሪያዋ የጫት ጉርሻ አፌ ውስጥ ስትጨመቅ መራር ግን አእምሮ ላይ የሆነ ንዝረት የሚፈጥር ጭማቂው በጉሮሮየ ሲወርድ ዝናብ እንደናፈቀው መሬት የሚረሰርስ አንዳች ነገር አለ ያኔ ሁሉንም ነገር በፍቅር ነው የማየው በዛች ቅፅበት ቀጥሎ ላለችው የጫት ጉርሻ አገር ሽጭልን ቢሉኝም ጆሮዋን ነበር የምላት " አባባሏ አሳቀኝ ከልቤ አሳቀኝ በዛ ላይ ቆንጆ ፊቷ ላይ እንደወሬው ስሜት የሚፍለቀለቀውና እዝን የሚለው ስሜቷ የሆነ የማይጠገብ ናፍቆት ይጭራል (እኔማ እንኳን ዘንቦብሽ አሉ እንደልእልት አባባል ጫት እንደተባለው አይነት ስሜት ካለው ለእኔ በዚህ ሰአት ልእልት ጫት ነው የሆነችብኝ ቀጣይ የወሬ ጉርሻዋን ለመስማት አገር ሽጥልን ቢሉኝ ከመረብ መልስ ጆሮዋን ነበር ይችን ጦቢያን!! ለብር ተሸራርፋ ከምታልቅ ለፍቅር ብትሸጥ ለሷም ሳያዋጣት ይቀራል ? ቢበዛ ለሴት ብሎ አገሩን ሸጠ ተብ ብወቀስ ነው እራሷ ጦቢያስ "አንች በሉኝ" ያለችው ሴትነትን መርጣ አይደል!!)

" እንግዲህ እንደዛ እንስፍስፍ ብየ የምጀምረው ጫት ጨዋታው እየሞቀ ምርቃናው(ቃሉ ያጠላኛል) ከፍ እያለ ይሄድና መልሶ ስሜቱ ወደመቀዛቀዝ ሲወርድ አንዱ የወንዴ ጓደኛ የሆነች ጉዳይ እንዳለችው ገልፆ ሲወጣ ሌላው ሲቀጥል ያ ሁሉ ጫት ወድሞ የጫት ገረባ ፊታችን ሲከመር የቅድሙ ፍክት ያለ ንጣታቸው ጠፍቶ የአተላ ቅሪት የተደፈደፈባቸው የቡና ሲኒዎች ፊታችን ተደርድረው አንዳንዶቹም ምንጣፉ ላይ ተከንብለው ሳይ ማጨሻው እሳቱ ከስሞ ከነአመዱ ሲያንቀላፋ ሆድ ይብሰኛል የሆነ (((እቃቃው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ))) አይነት ስሜት ነው የሚሰማኝ እና ያንን ደስታ ያንን ስሜት ለማምጣት የነገውን የመቃሚያ ጊዜ በናፍቆት እጠብቃለሁ ነገም ያው ነው ከነገወዲያም እንደዛው ያጫት ህይዎት በቃ ያች ከመጀመሪያ ጉርሻ እስከመጨረሻዋ ግረባ ያለችው ጊዜ ናት " ከዛ ግን የሚተርፍህ የተወዛገበ አእምሮ ብዙ ጊዜም የሌሊቱን ግማሽ በሚያስጠላ የሙቀት ስሜትና እንቅልፍ ማጣት እዚህና እዛ በሚዛብር ያልተጨበጠ ሃሳብ መባዘን ነው

" የዛን ቀንም ልክ ቂማው ሲያበቃ የወንዴ ጓደኞች አንድ ሁለት እያሉ ሲሰናበቱን እኔና ወንዴ ብቻችንን ስንቀር ባለፈው ቀን ሲያስጨንቀኝ የነበረው ሃሳብ ሁሉ ኬት መጣ ሳልለው ተንጋግቶ መጣልሃ ወንዴን ዝም ብየ አየሁት ሌላ ነገር የፈለኩ መስሎት በእጁ ያዘውን የጫት እንጨት ወርውሩ እጆቹ ጡቶቹ ላይ አረፉ ሌላ ሰው የነካ ይመስል ምንም አልተሰማኝ ዝም ብየ ሳየው እሱም ግራ ገባው መሰል " ሊ " አለ ሲጠራኝ "ሊ" እያለ ነው እንግዲህ ልእልት ሲቀናጣ መሆኑ ነው እኔም ሊ ሲለኝ ደስ ይለኛል በዚች ፊደል ስንት ቀን ዘራፍ ብሎ የተነሳ ልቤን ውሃ እየቸለሰ አቀዝቅዞታል

"ሰላም ነሽ የኔ ማር " አለኝ

"ወንዴ ትላንት ሳስብ ነበር"

"ምን የሚያሳስብ ነገር መጣ ልጆቹ ናቸው ስራው ነው ወይስ እግሬ ወጣ ሲል ጠብቀው በሌለሁበት መጥተው አገሪቱን ምሪልን ካላንች ተስፋ የላትም አሉሽ.. " ብሎ እየሳቀ አቀፈኝ ቀስ ብየ ከእቅፉ ወጣሁና ነገሬን ከምን እንደምጀምር ግራ ገብቶኝ አየሁት ወይኔ ባልቃምኩ ኑሮ አልኩ.!! አንዱን አስቤ አንዱን ቅዥብርብር አለብኝ እስቲ አሁን ከየት ልጀምረው ብየ ግራ ገባኝ ባወጣ ያውጣው ብየ አፌ ላይ ከመጣልኝ ዘነኮርኩት ደግነቱ የሴት ምላስ በራሱ አእምሮ ነገር ነው ነገሮችን ያደራጃቸዋል አሁንም በአባባሏ ሳኩ ደግሞ እውነት አላት ሴቶች ተበሳጭተው እንኳን እንደእኛ እንደወንዶች አይዘነኩሩም የፈለገ ቢያወሩ ቢጮሁ ምላሳቸው አእምሮ ነገር ነው ውሉን አይስትም !ደግሞ የተናገሯትም አይረሱም ነጥብ አይረሱም !! ልእልት ለወንዴ ኬት ጀምራ ምን ብላ እንደነገረችው ማየቱ በራሱ ይሄን ነገር ያረጋግጣል

"ትላንት ጓደኛህ የመኪና አደጋ ሲደርስበት ደነገጥኩ በጣም ፈራሁ ይሄ ነገር አንተ ላይ ቢሆን ኑሮስ ብየ ፈራሁ ወንዴ."አለችው ወንዴ የመፈቀር ሃሳብ ልቡን አስከፈተውና ቀጥሎ የምትነግረውን ሁሉ ለመስማት ሰፍ አለ ልእልት እንዲህ ብላ ወጓን ቀጠለችልኝ "ይሄን እየነገርኩት ሳላስበው እንባየ ተዘረገፈ ወንዴ ድንገት በተዘረገፈ እንባየ ደንግጦ ጥብቅ አድርጎ አቀፈኝና ምንም ያለሰብኩትን ዝባዝንኬ ያወራ ጀመር" ሊ የጓደኛየን አደጋ እኔ ጋ ምን ያገናኘዋል ጓደኛችንኮ ያው ሲነዳ ተሸውዶ ነው ፍሬን ያዝኩ ብሎ ነዳጅ ሰጠውና ፊት ለፊት የሚመጣ ሌላ መኪና ጋር ተላተመ አየሽ እንዲህ አይነት አደጋ ሲያጋጥም መሪ ላይ መጫዎት አለብሽ መኪናሽ ድንገት ወደፊት ሊወረወር ይችላል በተለይ ማኑዋል ከሆነ መኪናው" በቃ ወንዴ ማለት ይሄ ነው እስቲ አሁን ጓደኛህ እንዴት አደጋ ደረሰበት አልኩ? ወጣኝ ? ነዳጅ ይርገጥ ፍሬን ይርገጥ እኔ ምን ቤት ነኝ ? ዋናው ጥያቄ "አንተን ባጣ ምን እሆናለሁ? ነው ሰው የሚሞተው ፍሬን ረግጣለሁ ብሎ ነዳጅ ስለሰጠ ብቻ አይደለም መቸስ ትንታም በተቀመጥክበት ሊያስቀርህ ይችላል ከሞት በኋላስ ነው የኔ ጭንቀት ሚችማ ያው ወይ ገነት ወይ ሲኦል ይገባል እንደሚባለው ቀሪው ነው እንጅ በተለይ እንደኔ ሚች ላይ ተለጥፋ ቅንጡ ህይዎት የለመደች ከንቱ ነገር ነው እንጅ አሳሳቢው ! ጫቱ ነው መሰል ከዛ በኋላ ያሰብኩትን ልክ ባሰብኩበት መንገድ አንበለበልኩለት ለወንዴ ምንደነው የነገ እጣ ፋንታየ አልኩት አንተም ስራ የለህ እኔም አልሰራም እስከመቸ በቤተሰብ ሃብት ተማምነን በወጣትነታችን እየተጦርን እንኖራልን አልኩት

አንተ አንድ ነገር ብትሆን የእኔ እጣ ፋንታ ምንድነው አልኩት (ለራሷነው ለካ የተጨነቀችው ብሎ ይታዘበኛል ሳልል ይታዘባ!! ያወራሁት እውነት ነው አዎ ለራሴ እያሰብኩ ነው እና ከሆነ በኋላ ማነው ለኔ የሚያስብ) በቃ ከዚች ቀን ጀምሮ የራሳችን ነገር የምንተማመንብት የማንም ጥገኛ ሳንሆን እንደባልና ሚስት በራሳችን የምናዝበት ስራም ይሁን ሃብት ሊኖረን ይገባል አልኩት

እፎይይ !!

ወንዴ በግርምት አየኝ ፊቱ ሳቅም ግርምትም የተቀላቀለበት ግራ የገባው ፊት ነበር እና ሳይስቅም ሳይኮሳተርም እንዲህ አለኝ "ሊ ...ዛሬ ከምር መርቅነሻል እስቲ ወጣ ብለን እንመለስ እንደውም ዛሬ አሪፍ ራት እለቅብሻለሁ"

አየህ አብርሽ እንደዛ ሙሉ ቀን ከበረንዳ ሶፋ እየዘለልኩ የተጨነኩበት ጉዳይ ባጭሩ "ምርቃና " የሚል ስም ተለጠፈበት እና አረፈው እዛው ላይ ነገ ጫት እንደማልቅም ወሰንኩ አዎ ሳልቅም እነግረዋለሁ እውነትን ማስደግፊያ ሰበብ ሲያጣለት ያኔ ምን እንደሚለኝ አያለሁ ለማንኛውም ነገሮችን ከጅምሩ ላለማክረር ብየ የራት ግብዣውን ተቀበልኩ ሆዴ በአሩስቶ እና ዋይን ቢሞላም አእምሮየ አንዴ ከጨመደደው ሃቅ ዘወር አላለም ማሰብ ጀምሪያለኋ በቃ ጥያቄየ "ነጋችንስ" ነው

ወንዴ እንደልማዱ የዛን ቀን ደጋግሞ ጠጣ ሞቅ አለው በቃህ ብለውም አልሰማኝም ሰከረ ሰክሮ ደግሞ ወደመኪናው አእምሮየ ታዲያ ይችን ሰበብ ለቀም አደረገና ንትርኩን ቀጠለ " አየሽ እንግዲህ ይሄ ባልሽ በዚች ምሽት ፍሬን የረገጠ መስሎት ነዳጅ መስጫውን ቢረግጥ ቀጥሎ ህይወታችሁ ምን ሊሆን ይችላል??" እያለ ሁለታችንም ካለቅን ትርፉ ለሳጅን ማንትስ የጧት ዜና መሆን ነው ችግር የለውም ወንዴ አንድ ነገር ቢሆንና እኔ ብተርፍስ ? ለዜናም ለወሬም የማይመች ነገር ነው እንግዲህ ፈጣሪ ይጠብቀን ብየ ወደመኪናው ገባሁ ወንዴ እየነዳ ያወራኛል "የኔ ልእልት ሬስቶራንቱ ውስጥ ያለው ወንድ ሁሉ እንደውሻ በውብትሽ ልጋጉ እተዝረበረበኮ ነው የሚያይሽ አንች ግን የኔ ሚስት ነሽ የሰማኒያ ሚስቴ እኔ እያለሁልሽ ስለኑሮ ጭንቀት አሰብሽ? ወይኔ ወንዴ አንበሳው ብፈልግ የኮንዶሚኒየሙን ብሎክ ሙሉውን በስምሽ እገዛልሻለሁ ነዋሪውን ሁሉ እያስወጣሁ እያባረርኩ እቃቸውን ምን እቃ ነው ኮተታቸውን ቅራቅንቧቸውን ሙቀጫ ነሽ ብረት ምጣድ ማቡኪያ ነሽ መክተፊ ቲቪ ነሽ ላፕቶብ አሽቀንጥሬ ሳበቃ የኔን ልእልት ድፍን ብሎኩ ላይ ማኖር እችላለሁ የአባቴ ንብረት ማለት የኔ የራሴ ነው በአንድ የስልክ ጥሪ እንደፈለኩ የማዝበት ! ልእልትየ የኔ ውብ ዶክተር መሆን አቅቶኝ ነው? እንኳን እኔ ያ ሃብታሙ ዶክተር ሁኗል (ሃብታሙ የአባቱ ተላላኪ የነበረ ልጅ ነበር ተምሮ ዶክተር የሆነ ይቆጨዋል ዶክተር የሆነው ስለተማረ ሳይሆን ለአባቱ ስለተላላከ ይመስለዋል መሰል ምሳሌው ሁሌ እሱ ነው ) ኢንጅነር መሆንስ ያቅተኛል ? ልእልቴ

የኔ የውበት ጥግ አይደለም ልእልትየ ግን በቃ ምን አደከመኝ ሁሉም ድካም ለብር ነው ብር ደግሞ አለ አለና. ከመኪናው ኪስ ውስጥ አንድ እስር ብር አውጥቶ ታፋየ ላይ አስቀመጠው. ወደመኪናው ኪስ መለስኩት ! “ልእልትየ የኔ ውብ ምንድነው የምትፈልጊው መኪና፣ ቤት፣ቤትኮ ቤት ቆይ እንደውም አባባ ቤት ጀምሮልን አልነበር ምን ደረሰ ልደውልለት ቆይ ” ብሎ ስልኩን ለማውጣት ይታገላል እየነዳኮ ነው “ወንዴ ስርዓት ከመሸ ደውለህ ልታስደነግጣቸው ነው እኩለ ሌሊትኮ ነው “ ብየ ስልኩን ከእጁ ላይ ቀማሁት“ ለካ እኩለ ለሊት ነው የኔ ፀሃይ አንቺን የመሰልሽ የምታበሪ ልጅ ጎኔ ተቀምጠሽ እኩለ ቀን መሰለኝኮ ሃሃሃ ታበሪያለሽኮ የኔ ልእልት አሁን እኔ የመኪናውን የፊት መብራት ባጠፋው መብራት ሃይልም የመንገዱን መብራት ሁሉ ቢያጠፉፋው ከአንቺ አይኖች በሚወጣው ብርሃን ብቻ እስከሱዳን ድንበር መንዳት እችላለሁ ይሄው ካላመንሽ ” ብሎ መሃል መንገድ ላይ ያውም እንደዛ እየፈጠነ የመኪናውን የፊት መብራት ድርግም አደረገው እንኳን እስከሱዳን አምስት ሜትርም ከፊታችን ያለው መንገድ አይታይም ነበር የመንገድ ዳር መብራቱም ሲጀመር አልነበረም ጨለማ ድቅድቅ ያለ ጨለማ

አእምሮየ ታዲያ ይችን አጋጣሚ ተጠቅሞ ” አየሽ ነገሽ እንደዚህ ነው ጨለማ ምንም የማይታይበት ልክ እንደዚህ እንደመኪና ዝም ብለሽ ነው የምትጓዥው ትጋጫለሽ የመኪናው ቆርቆሮ እንደሚጨራመተው ይሄ ምቾት ያሳበደው ውበትና ኑሮሽ ይጨራመታል እንደመኪናው መስተዋት ተሰፋሽ ይንኮታኮታል አትጠገኝም !! “ ይለኛል ማሰብ ጀምሪያለኋ “ወንዴ መብራቱን አብራው ፕሊስ አብራው “ እያልኩ ስጮህ ፊት ለፊት አንድ ከባድ መኪና ጡሩንባውን እያንባረቀ አጭርና እረዥም መብራቱን እያበራብን ወደእኛ ሲምዘገዘግ ወንዴ ወደኔ ዞሮ አላየውም ”ቁርጡ ቀን መጣልሽ “ ብሎኝ አእምሮየ ትቶኝ ጠፋ

መደንዘዝ በለው

## ክፍል 11

ከመኪና አደጋው ለትንሽ ተረፍን ! ከባድ መኪናው ፊት ለፊታችን ተምዘግዝጎ ሲመጣና እኔ ጨኸቴን ስለቀው ወንዴ ባለ በሌለ ሃይሉ ፍሬኑን ረገጠው ወደፊት ተወርውሬ ስመለስ ከመኪናው ውጥቸ የተመለስኩ ነበር መሰለኝ ! መኪናችን እየተንሸራተተች ሂዳ ቀድሞን ፍሬን የያዘው ከባድ መኪና አፍንጫ ስር ቆመች ልክ ትልቅ ድመት አፍንጫ ስር የቆመች አይጥ በላት ! በየትኛውም አደጋ ውስጥ ትንሽ ደስታ አለ ምናልባት በህይዎት እንድንኖር አንድ እድል ስለተሰጠን ይሆናል ደስ አለኝ በመትረፌ ሞት እፈራለሁ አብርሽ እንደሞት የምፈራው ነገር የለም የከባድ መኪናውን ሹፌር አደነኩት እግዚአብሔር ይስጠው ከሞት አፋፍ መለሰን ትንሽ ቢዘናጋ ኑሮ በቃ አለቀልን ፊት ለፊቴ የሚታየኝ የመኪናው አፍንጫ ነበር እስሩ ገብተናል በቃ ሹፌሩ እንኳን አይታየንም ወርጀ ባመሰግነው ደስታየ ግን ምን ዋጋ አለው ሃሳቤን ሳልጨርሰው የከባድ መኪናው ሹፌር መኪናውን ወደኋላ ስቦ በወንዴ በኩል አለፈና በመስኮት ብቅ ብሎ “ አንተ የውሻ ልጅ አንዲት ሸርሙጣ ጋር እየተዳራህ ጣጣ ውስጥ ልትከተኝ ነው “ ብሎ መኪናውን አስጓርቶ ተፈተለከ እንደው በደፈናው ወንዱን ሁሉ አትውቀሽ አትበለኝ እንጅ እንኳን እንደጎን አጥንት ማክበር የሴትን አጥንት በአፉ የሚሰብር እንደኛ ወንድ ማን አለ !! እቤት ስንደርስ አፍንጫየ እየደማ እንደነበር አወኩ የራት ልብሴ ከፊት በደም ተበክሏል ደም አልወድም ቢሰከርም ወንዴ አይዞሽ እንዲለኝ ፈልጊያለሁ “እንዴ” ብየ ጮህኩ ወንዴ ዝም አለ !! አፍንጫየን በእጀ ጠርጌ ደም የነካ መዳፌን እንዲያየው እየዘረጋሁ እንደገና “እንዴ” አልኩ ወንዴ አየት አድርጎኝ ዝም አለ “ምን እንዴ እንዴ ትላለች ደም ብርቅ ነው እንዴ “ የሚል ነበር ሚመስለው ግራ ገባኝ ወንዴኮ በየወሩ “ማንስትሬሽን” ላይ ስሆን እንኳን የሚደነግጥ ልጅ ነበር ከደሙ በላይ የሱ ቸልተኝነት አስደነገጠኝ ድንጋጤው ድራሹን አጥፍቶ አፉን አዘግቶት የነበረ ስካሩ እቤት ስንገባ አገርሽቶበት የባጥ የቆጡን ሲቀባጥር የከባድ መኪናውን ሹፌር እገለዋለሁ እያለ ሲፎክር ቆይቶ ልብሱን እንኳን በቅጡ ሳያወላልቅ አልጋው ላይ በቁሙ ወድቆ እንቅልፍ ወሰደው

እንግዲህ የመጀመሪያ ቀን ያውም በተለሳለሰ ቃል ወንዴን ስለወደፊት ህይዎታችን መጠየቁ ይሄን ሁሉ መዓት ካመጣ አፈሩን ፈነቃቅሎ የተነሳን እውነት በራት ግብዣም በመጠጥም መልሶ ለመቅበር መሞከር እውነትን ማስቆጣት ነው የተቆጣ እውነት ደግሞ እንኳን በትዳር መሃል የሚፈጠር ብጥብጥ ቀርቶ በአገራት መካከል ጦርነት ከመቀስቀስም አይመለስ ! ነገስ ምን ይዞ ይመጣ ይሆን እንጃ ድክም አለኝ እኔም የራት ልብሴን ከኋላ ዚፑን ከፈትኩት ሰውነቴ ላይ እየተንሻለለ ወርዶ እግሬ ስር እንደውሃ ተኀዘኀዘ የከበበኝን ቀሚሴን ተራምጄ ወንዴ ጎን ተጋደምኩ

በቀጣዩ ቀን አርፍደን ተነሳን ማታ ስለሆነው ነገር ሁሉ ሁለታችንም አንዲት ነገር ትንፍሽ አላልንም እዛው ሰፈር ወዳለ ሬስቶራንት ሂደን ቁርስ በላን እንደው ቁርስ አልኩ እንጅ ሰዓቱ ወደምሳ ሰዓት እየተቃረበ ነበር የወንዴ ጓደኞች ተንጋግተው ወደሬስቶራንቱ መጡ የተለመደው ወከባ ሳቅና ጨዋታ ተጀመረ. እነሱ ጫት እስከሚገዙ እኔና አንዲት የወንዴ ጓደኛ "ሚስት" ወደቤት ሂደን ቤት አዘገጃጀን ለምን እንደሆነ እንጃ ብቻ ውስጤን ቅፍፍ ብሎታል ማታ የሳተኝ ሞት አመዱን አራግፎብኝ ሂዶ ነው መሰል እንደገና ቤታችን ሞቅ ሞቅ ሲል ጭሱ ወደላይ እየተነሳ የሳሎኑን አየር በመልካም መዓዛ ሲያውደው የወንዴ ጓደኞች አብረዋቸውም የመጡ ቆነጃጅት ሳቅና መሽኮርመም ለቤቱ ሙቀት አንዳች እሳት ሲጨምር ይች የምናፍቃት ሰዓት እንደወትሮው አልሆን አለችኝ ሁሉም የእኔን እንደወትሮው አለመሆን አልታዘቡም ነበር ወንዴን ጨምሮ ! ወንዴማ በተዓምር እንደተፈወሰ በሽተኛ ተሳስሮ የነበረ ምላሱ ተፈቶ የወሬው ፊታውራሪ ሁኖ ነበር እና በወሬ ውስጥ እየቀነጣጠሰ ፊቴ የሚያስቀምጥልኝ የጫት ቅጠል አለመንካቴን ያወቀው ቆይቶ ነበር ድንገት ዞር ሲል ጫቱ ፊቴ ተቆልሏል ቀና ብሎ ፊቴን አየ ከዛም ጫቱን አየ." አትቅሚም እንዴ " አለኝ" አልቅምም " አልኩ ከአፌ የወጣው ቃል አስደሰተኝ ዝም ብሎ የሆነ መጥፎ ነገር "አላደርግም" ስትል የሚሰማህ ኩራት አለ አይደል እንደዛ ተሰማኝ እናም ደገምኩት "አልቅምም " ይሄ ቃል ወንዴን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም እንደተለየ አዋጅ አስገርሟቸው "ምነው በሰላም ነው ሊ.....ችግር አለ እንዴ " እያሉ በጥያቄ አዋከቡኝ እንደውም እያሱ የሚባለው የወንዴ ጓደኛ (ነገር ማካበድ የሚወድ ሽቅርቅር እባብ ባህሪ ያለው ) በሪሞቱ ከትልቁ ሲዲ ቴፕ የሚንቆረቆረውን ሙዚቃ እየቀነሰ (የፈረደበት ቦብማርሊ ፀበኛ ፖለቲከኞች አስታረቀ ቅብርጥስ ቦብ ይሉልኛል ደግሞ ሲሉ አየሰሙ መጀመሪያ ቦብ ስላስታረቃቸው ፖለቲከኞች ከመደስኮር ከራሳቸው በታረቁ ) እና ይሄ እያሱ ሙዚቃውን ቀነሰና በዛ ጋጋኖ ድምፁ (ሲያወራ ጆሮው አፉ ስር ቢሆንም ይጮሃል) "አመመሽ እንዴ ወይስ ይሄ ሰውየሽ በሆነ ነገር አበሳጨሽ " ብሎ ወደወንዴ በአገጩ ጠቆመና አረንጓዴ ቅጠል የተጨቀጨቀበት ሙቀጫ የሚመስል አፉን ከፍቶ ሃሃሃሃሃ እያለ ሳቀ ምንም አያስቅም ሁልጊዜ ችግሮችን ወደወንዴ መግፋት ወንዴ የሚናገራቸውን ነገሮች በእኔ ፊት በማጣጣል በእኔ አይን ግርማ ሞገስ እንዲኖረው እንደሚጥር ገና ድሮ አውቃለሁ ! ተንኮለኛ እንደሆነ አውቃለሁ ደግሞ አስተያየቱን አልወደውም ሁልጊዜም እሱ ፊት ለፊት መቀመጥ አልፈልግም ልክ ወዳጅ መስሎ "ለ ልእልት ጫት ስጣት እንጅ ብሎ ወንዴን ይገስፀዋል " አባባሉ ውስጥ ከወንዴ የበለጠ አስብልሻለሁ የሚል መርዘኛ መልእክት አለ ... አውቃለሁ!! ምንስ ከ12ኛ ክፍል ባቋርጥ የሴት ደመነፍሴ እንዲች አይነቷን መብለጥለጥ ከህይዎት ዩኒቨርስቲ በመዓረግ ተመርቃባታለች! ማን እንደቋመጠብኝ ማን ምራቁን እንደሚውጥብኝ ጠንቅቄ አውቅ ዘንድ የመጣሁበት መንገድ ይሄንኑ ነው ሲሞላኝ የኖረው አእምሮየ ውስጥ ሂሳብ የለ ፊዚክስ ማን አየኝ ማን አሽኮረመመኝ በሚል ከንቱነት ነው እድሜየን የፈጀሁት ! ባይጠቅምም ይሄም እውቀት ነው ! ይሄንንም ልጅ አይኑ የጤና እንዳልሆነ አውቃለሁ እጠነቀቀዋለሁ ! ይሄን እያሱን ! ለምን እንደሆነ እንጃ ሁሉም እሱ ሲያወራ በአክብሮት ይሰሙታል እውቀቱ ግን አዲስ የመጡ ስልኮችን ጎርጉሮ ፈረንጅ የፈጠረውን "አፕ" እራሱ የሰራው ያህል ጥቅሙን አጠቃቀሙን አጋኖ ከማውራት አታልፍም ይሄም ታላቅ ጥበበኛ ሁኖ ይታይ ዘንድ ሰው በሌለበት የጫት ጉባኤ ትልቅ ሰው ተደርጎ እንደታሰበ አደረገው ነፍሴ ግን ትንቀዋለች አንድ ቀን ቃል አውጥቶ ተናግሮኝ አያውቅም ግን ይሸከከኛል እውቀት የለኝ ጥላቻየን ተንትኘ በዚህ ምክንያት ጠላሁት አልል ግን የእውቀት ማነስ ቀልብህን እንድታምን ያደርገሃል !! ቀልቤ አልወደደውም !! እና ((ጫት አልቅምም)) ማለቴ የቤቱን ሰው ሁሉ ሲያስደነግጠው እያሱ በዚች ንፋስ እንኳን በማታሳልፍ ቀዳዳ በትንሹ በተከፈተች የመኪና መስተዋት በኩል እንደምትነፍስ ስለታም ንፋስ እየነፈሰ ወደልቤ ለመግባት ጥራዝ ነጠቅ

እውቀቱን መሰላል ሊያደርጋት ሞከረ “ ሴቶችኮ ስስ ፍጥረቶች ናቸው ትንሽ ነገር ካሳዘናቸው ስሜታቸው እንደመስተዋት እንከሽ ነው በቃ ለምሳሌ ልእልት “ በቃ እንደመንገድ የረዘመ ወሩን ይተረትረው ጀመረ ደግሞ ለከፋቱ ሁሉም እራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰሙታል በኋላ ስሰማ ድግሪ አለው አሉ እውር ቤት አንድ አይና ብርቅ ነው ! እና ይሄ ድግሪ ቅጥ አጣ እንዴ ሰው እንዴት ድግሪውን እንደማርገብገቢያ የነገር እሳት ለማቀጣጠያነት ይጠቀምበታል ነገር ሸቶታል ኢያሱ በእኔና በወንዴ መሃል ሽብልቅ ሁኖ ሊሰነጥቀን እግሩን እያስገባ ነው! የኔም የደመነፍስ አፍንጫ ውሻ ያስንንል ከየትና የት ነው ከክፋት የምትሸተኝ ! ልእልት እያወራችኝ ከንፈሯን ነከሰች ይሄ እያሱ ያረጋት ነገር ይኖር ይሆን እንዴ ብየ አሰብኩ. ምን አስቸኮለኝ ልሰማው “ ከዛን ቀን ጀምሮ ጫት የሚባል ነገር በአፌ ሳይዞር ሳምንት ሞላኝ የወንዴ ጓደኞች እኔ ላይ የተፈጠረው ስሜት አልተመቻቸውም አንድ በአንድ እያሉ ከቤት መቅረት ጀመሩ ቤታችን እየቀዘቀዘ መጣ ወንዴ እኔና ይሄ እባብ እያሱ ብቻ ቀረን የወንዴ ጓደኞች ሌላ ቤት መቃም እንደጀመሩ ወንዴ አንድ ምሽት አዝኖ ነገረኝ “ሊ ጓደኞቸን እያስቀየምሻቸው ነው እቤታችን ሲመጡ ፊት መንሳት የለብንም “ አለኝ

“ምንድነው ፊት የነሳኋቸው “

“አይ አልቅምም ስትይ ደበራቸው” ይታይህ አብርሽ አንግዲህ እንግዳ ተቀባይነታችን የሚጨበጨብለት ራሳችንን ገድለን ከመጣ ከሄደው ጋር ስንመሳሰል ነው (እንደውም “ተመሳሰይና እኛን ምሰያ” የሚሉት ፈሊጥ ሁሉ አላቸው) ይሄው እንግዲህ ያ በሰው ተሞልቶ የሚውል ቤት በመጨረሻ ኦና ሆነ ሳቁ ከሰመ ወንዴ አንድ ሁለት ቀን ብቻውን ጫት ይዞ መጥቶ ሊቅም ሞከረ ምኑም ምኑም አልጣመውም ደግሞ ሊያስቀይመኝም አልፈለገም የሚገርምህ እንደዛ ቁጭ ብየ ሶስት አራት ጊዜ አፈላ የነበረው ቡና ለአንዴውም ሰለቸኝ ወንዴ ጋር ማውራት ነበር የምፈልገው ስለነገ ማውራት ምን እንስራ ምን እናድርግ ወንዴ ደግሞ ይሄ ወሬየ አንገሸገሸው እንደውም አንድ ቀን ጫት ልግዛ ብሎ እንደወጣ ደወለልኝና ጓደኞቹ ጋር እንደሚቆይ ነገረኝ ባሌን ጨምሮ ያ የጫት ጉባኤ ብቻየን ጎልቶኝ ሄደ ከዛች ቀን በኋላ ከሰዓት ብቻየን መዋል ጀመርኩ ወንዴን ለምን ትተኸኝ ትሄዳለህ ማለት አልፈለኩም የሆነ መለመን መስሎ ተሰማኝ ምለማመጥ መስሎ ተሰማኝ ሄደ መጣ ማለቴ አልነበረም ግን በሴት ልብ ውስጥ ብቻ ያለ ማንም ሊረዳው የማይችል የክብር መለኪያ አለ ማንንም ብንወድ እንኳን ልብሱን ጎትተን አትሂድብን ማለት አንችልም የክብር መስመር አለ ልብሱን ሳይሆን ነብሱን ጨምድደን ለመያዝ ነው ጥረታችን ችግሩ ያው የብዙሃኑ ወንድ ነብስ ደግሞ መያዝ አትወድም !! ወንዴን ዝም አልኩት በአይኔ ብቸኝነቴን ነገርኩት እንዳላየ ወደጓደኞቹ ሮጠ ጧት በሞፈር ተሰቅስቆ የማይነሳው ልጅ እንደወፍ ጧት መነሳት ጀመረ አብርሽ ወንዴ ቷት ሲነሳ በእሱ ቦታ የሚገባው ነፋስ እንዴት አጥንቴን እንደሚሰነጣጥረው ጧት ሲያቅፍ ደስ ይለኝ ነበር ጧት አልጋችን ውስጥ ሁነን የሚረባም የማይረባም ነገር በጎርናና የጧት ድምፅ ሲነግረኝ ደስታየ ልክ አልነበረውም እንዲህ እንደድንች ልጣጭ ብርድልብሱን ከላያችን ላይ ገሽልጦ ጥሎ መሮጥ ከየት እንዳመጣው እያሰብኩ እስካሁንም እገረማለሁ

አንድ ቀን ጠየኩት “ወንዴ ለምንድነው ጧት የምትነሳው”

“አባባን ማገዝ አለብኝ “ አለኝ “ስራ ጀምሪያለሁ “ የእኔ ጥያቄ ከትክክለኛ ስሜቴ ይልቅ መናቅን እንዳሳደረበት ገባኝ ስራ ለመለወጥ እንጅ ለእልህ አይሰራ ! አንድ ቀን ታዲያ እኔም አብሬህ እሄዳለሁ አልኩት ! “ከፈለግሽ” አለኝ ተያይዘን ወደአባቱ ሱቅ ሄድን. ወከባ ስሚንቶ ይጫናል ይወርዳል ብረት ይጫናል ይወርዳል ጣውላው ብቻ ሁሉም ነገር ሩጫ ነው ወንዴ ሰራተኞቹ መሃል ቁሞ “እንዲህ አድርጉት እንጅ እንደዛ አድርግ አንተ ምን ቁመህ ታየኛለህ “ እያለ ያመናጭቃቸዋል ያው ለእኔ ስራ እንደሚችል በአባቱ ንብረት ማዘዝ እንደሚችል ማሳየቱ ነው ሚስኪን ወንዴ አባቱ እኳን እንደሱ አይዋከቡም ሽክ ብለው በረንዳቸው ላይ ተቀምጠው ቡናቸውን እየጠጡ ያፏጫሉ እኔን ሲያዩኝ ከመቀመጫቸው ተነስተው ደረታቸው ላይ ልጥፍ አድርገው አቀፉኝና አብሯቸው ለነበረ አንድ ሰውየ አስተዋወቁኝ ” የወንድየ ሚስት ናት” አሉት ሰውየው በአድናቆት እያየኝ” እንደአወስትራሊያ ሞራሌ ቀጥ ያለች

ውብ ከየት አገኛት ባክህ “ ሁለቱም ሃሃሃሃሃ ብለው ሳቁ አወስትራሊያስ መቸም አወስትራሊያ ነው “ሞራሌ” ምንድነው እያልኩ ዝም አልኩ

የወንዴ አባት ጎረምሳ ነገረ ናቸው እንደእድሚያቸው አይደሉም የባጥ ቆጡን ሲያወሩኝ ቆይተው ምሳ ጋብዘውን ወንዴ እቤት አድርሶኝ ወደጓደኞቹ ተፈተለከ !! በቃ ብቻየን መዋልን ለመድኩት!! የማልዋሽህ እንኳን ወንዴ ጓደኞቹ ሁሉ እንደልእልት የሚያቀማጥሉብኝ ጊዜ ይናፍቀኛል አንዳንዴ የመስኮቴን መጋረጃ ከፍቸ ታች መንገዱ ላይ ወጣቶች ተያይዘው ሲሄዱ እያየሁ እንባየ ይመጣል ሰው እወዳለሁ ብቻየን የሆንኩባቸው ጊዚያት ትንሽ ናቸው ሰው ብቻውን ሲሆን ምን እንደሚያደርግ አላውቅም (ይሄ ይሆን ሰው ብቻውን መሆኑ ጥሩ አይደለም ነው ምናምን የሚባለው) እተኛለሁ እነሳለሁ ይበለኝ በሰላም አገር አጉል ቅብጠቴ ነው እንደሰባራ ቅል ያስወረወረኝ እላለሁ መገፋት ይመስለኛል የአገሩን ህግ ጥሶ ደጁ እንዳትደርሱ እንደተባለ ወንጀለኛ የተገለልኩ ይመስለኛል በቃ እንዲቹ ቁጭ ብድግ ስል እውላለሁ ወንዴ ጓደኞቹ ጋር ውሎ ይመጣል ”ሃይ ብለውሻል” ይለኝ ነበር መጀመሪያ አካባቢ ሲቆይ እሱም ራሱ ሲገባ ሃይ ማለቱን ተወው !! ቢጨንቀኝ እህቴን ቀን ቀን እንድታዋውለኝ እጠራት ጀመር ከዩኒቨርስቲ ታማ አቋርጣ መጥታ እቤት ነበረች (መቸስ ዞረን ባናያቸውም ለችግራችን ያው ቤተሰብ ነው) ወንዴን ፈራሁት ፊቱን እያቀጨመ ያችን ርእስ እንደገና እንዳላነሳት አደረገኝ መሸሸ ነበር መፍትሄው አብርሽ እንደውም አንድ ቀን ማታ ወንዴ ጋር ራት እየበላን (ምንም ፀባዩ ቢቀየርም ቢሞት ራት ውጭ አይበላም ) አለ አይደል ለወንድ መንበርከክ ልክ ባይሆንም ይሄንኛውኮ ባሌ ነው ብየ እስቲ ነገር ላብርድ አልኩና “ወንዴ እኔ ላስቀይምህ ፈልጌ አይደለም ስለወደፊት ኑሯችን ያነሳሁት” አልኩት ዝም ብሎ ይበላል አበላሉ የእልህ ነበር የሚመስለው ቀን እህቴ መጥታ የሰራችው ወጥ ዝም ሲለኝ ቀጠልኩ “አንተም እኔን ከመሸሸ ቢያንስ የተሰማህን ነገር በግልፅ ብትነግረኝ” ብየ ሳልጨርሰው እጁ ላይ የያዘውን ጉርሻ ሰሃኑ ላይ አስቀምጦት ተነሳ እጁን አወናጭፎ በሰለቸ ድምፅ “ ንዝንዝሽ ሰለቸኝ ምን ጎደለብሽ ልብስ ነው መዝናናት ነው ከማንም ሴት በላይ ድልቅቅ ብለሽ ትኖሪያለሽ ላንች ስል ከጓደኞቸ ልለያይ ምንድነው....ቀን ንዝንዝሽን ሽሽት ቤት እንደሌለው ሰው ማንም ቤት እውላለሁ ማታ ደግሞ የት ልሂድልሽ “ ብሎኝ እጁን ታጥቦ ወደምኝታ ቤት ሄደ! እጁን ሲያወናጭፍ ፊቴ ላይ አንዷት የወጥ ቅንጣት አረፈችብኝ ረዥም ሰዓት የተቀመጥኩበት ሳልነቃነቅ ቆየሁ ! በታሪክ ወንዴ ደፍሮ እንዲህ ገልምጦኝም ተናግሮኝም አያውቅም !! እጀ ላይ የያዝኳትን ጉርሻ ወደሰሃኑ መለስኩ የወንዴ ተዘጋጅታ የተቀመጠች ጉርሻ በዛ የኔ በዚህ ቁመው እየሞተ ላለው መከባበራችን መታሰቢያ የቆሙ ሃውልቶች መሰሉ እንደጥያ ትክል ድንጋዮች ጉርሻወቻችን በየፊታችን ሰሃኖቻችን ላይ ቆሙ አላዘንኩም እንደውም ከየት መጣ ሳልለው እልህ አይሉት ቁጣ ከተቀመጥኩበት አስፈንጥሮ አስነሳኝ እንዳበደ ውሻ ባሌ ፈርቶ የሚሸሸኝ ልእልት ሁኛለሁ ለካ የተለጎመ አፌን በግድ ከፍቶ ካልተናገርሽ የሚለኝ ባሌ ቃሌን አፉን ከፍቶ ከነጓደኞቹ በጉጉት ለሚሰማኝ ወንዴ “ንዝንዜ የሚሰለች መንቻካ ሚስት” ሁኘበታለሁ ለካ ከእግር እስከራሴ የሆነ ስሜት ወረረኝ ወደመኝታ ቤት ሂጀ በሩን በርግጀው ገባሁ ወንዴ ተከናንቦ የተኛውን የአልጋ ልብስ ከነብርድልብስ እና አንሶላው ገፍፌ መሬት ላይ ጣልኩት ወንዴ (((በሌሊት ልብስ))) ሁኖ በግርምት አፈጠጠብኝ ((((( ደግሞ ከመቸ ወዲህ ነው የሌሊት ልብስ ለብሶ መተኛት የጀመረው))))) ደሜ ፈላ ይሄ ቀላል ነገር ይመስላል አይደል .....አይደለም .....!! መጀመሪያ ቀን አብረን ካደርንባት ቀን ጀምሮ እኔ ጋር ሲያድር ወንዴ ራቁቱን ነበር የሚተኛው ከተጋባንም በኋላ ቢሆን ከቀለበቱ ውጭ መለመላውን ነው የማውቀው እኔም እንደዛው እንግዲህ ይሄ ምንድነው ሰውነቴ እንዳይነካው የልብስ ቅጥር ዙሪያውን ማቆሙ አይደል በፍቅረኞች መሃል ቃል የማይገልፃቸው ግን ከመንፈስ የሳሱ ስንት ድርጊቶች ስንት ልማዶች አሉ ከቃል በላይ ከድብደባ በላይ እነዛን ነገሮች በሚወዱት ላይ ሲቀየሩ ማየት ያበግናል ያቃጥላል !! ተቃጠልኩ መነጋገር ሳይሆን ወንዴን በጥርሴ መዘልዘል በጥፍሬ ሰውነቱን ማረስ አማረኝ እኔም ከዛ በፊት እንደዛ አይነት ልጅ መሆኔን አላውቅም ነበር ለካስ በውስጣችን ለክፉ ቀን የተቀመጠ ክፉ እኔነት አለ አሁን ልእልት አይደለሁም አሁን እንባ የሚቀድመኝ ልእልት አይደለሁም፣ አሁን በወንዴ አይኖች በወንዴ ቃሎች በወንዴ እጆች ዳሰሳ እንደቅቤ እጁ ላይ የምቀልጥ ልእልት አይደለሁም፣ አሁን ልውደቅልሽ ልነጠፍልሽ የሚለኝ ባሌ በዓይኑም በአንደበቱም ያቀለለኝ ያልተማርኩ ሃብት የሌለኝ ተስፋ የሌለኝ ልእልት የምባል ምንም ነኝ፣ አሁን በሃያል ጥላቻ ከንድ ከሳሎን ወደዚህ

ወደናቀኝ ወንድ የተወረወርኩ ድንጋይ ነኝ እንኳን ትላንት ጉልበቴ ስር ተንበርክኮ ሲያለቅስ የነበረ ወንድ ሰይጣንም በምትወደው ወንድ የተናቀች ሴት ፊት እግር ጥሎት ቢቆም ጅራቱን ሸጉጦ ነው እግሬ አውጭኝ የሚለው ወደፊት ተራመድኩ ወደአልጋው

# ክፍል 12

እንደዛ በብስጭት ተከኝ ወደአልጋው ስንደረደር ወንዴ ከመገረሙ በስተቀር ትንሽ እንኳን አልደነገጠም እንደውም ኮራ ብሎ "ልእልት እባክሽ ልተኛበት ብርድ ልብሱን አቀብይኝ "አለኝ

(ይታይህ ...ሊ የለ ምን የለ ....ልእልት....ፍቅር ሲራቆት መጀመሪያ አውልቆ የሚጥለው በፍቅር የተቆላመጠ የስምህን ካባ ነው ልእልት አለኝ እንደጎረቤት)

ፊቱ ላይ የነበረው መሰላቸው ቅዝቃዜ መቸም አይረሳኝም እንደው ለራሴ የአገልግሎት ዘመኔ ያበቃ የሆነ እቃ የሆንኩ መሰለኝ እቃ! "ምንድነው የሆንከው ምንድነው እንዲህ የሚያመናጭቅህ በስርአት አታናግረኝም " ብየ በእልህ እየተንቀጠቀጥኩ ፊቱ ቆምኩ !እኔማ ያ ግርማ መጎሴ አለ ብየ ያ እንኳን ተቆጥቶ በሰላሙም ቀን አይኔ ሲያርፍበት የሚሽቆተቆጠው ወንዴ አለ ብየ ነበር ታምነኛለህ አብርሽ ልክ ዝንብ እንደሚያባርር እጁን አንዴ አወናጭፎ ምን ልበልህ ንቀቱ ጥላቻው ፊቱ ላይ በቃ ልእልት እንባ ተናንቋት በእልህ ተንቀጠቀጠች" ንዝንዝሽ ሰለቸኝ " አለኝ! ንግግሩ አይደለም ያሳዘነኝ አነጋገሩ ድምፁ ፊቱ ላይ የነበረው ነገር እሱ ነው የሆነ ነገር ልቤ ላይ እንዲጫነኝ ትንፋሽ እጥር እንዲለኝ ያደረገኝ

ከአልጋው ላይ ተነስቶ በቆምኩበት ገፋ አድርጎኝ አለፈና የጣልኩትን ብርድ ልብስ እየጎተተ ወደአልጋው ተመለሰና ጥቅልል ብሎ ተኛ እንደዛ የተበሳጨሁት እንደዛ ተንደርድሬ የመጣሁት ልጅ ያ ሁሉ አነርነት ድራሹ ጠፍቶ እንደሃውልት ተገትሬ በብርድ ልብስ ተጀቡኖ ጀርባውን የሰጠኝን ወንዴን ማየት ብቻ ሆነ አቅሜ ! በቃ !! እንባየ ተዘረገፈ ወንዴ ምናለ ቢጮህብኝ ምናለ ቢሰድበኝ ምናለ ቢቸካቸከኝ

አፈርኩ አብርሽ ሴትን ልጅ አታሳፍር በህይዎት ዘመንህ ሴትን ልጅ አታሳፍር እስካሁን በህይዎቴ የዘገነኝ ነገር ያ የወንዴ ጀርባ ነው የሴት ልጅ እፍረት ከይቅርታም በኋላ ቢሆን ከአእምሮዋ አይወጣም መናቅን ሴት የመሳቢያ መንገድ አድርገው የሚያስቡ ወንዶች አሉ የለየለት ድድብና ነው ! የተናቀች ሴት ምናልባት ወንድን ከተከተለች ክብር ፍለጋ እንጅ ፍቅር ፍለጋ እንደማይሆን በራሴ አይቸዋለሁ ! ወንድ ልጅ ኮራ ሲል ነው እንጅ እየተባለ ስንቱ ወንድ ስንቷን ቅስም በሃፍረት ሰብሮ ጥሎታል !! ለዚሁም ይፎከራል ! አንዳንዴ ጀግንነታችን በሽተኛ ነው !! ልእለት በትካዜ ግድግዳውን እያየች ከሩቅ የሚሰማ በሚመስል ድምፅ ቀጠለች

"እግሬን እየጎተትኩ ወደሳሎን ሄድኩና ሶፋ ላይ ተኛሁ እንቅልፍ ግን እንዲች ብሎ በአይኔ አልዞረም ሌሊት የሆነ ነገር ኮሽ ባለ ቁጥር ወንዴ ይቅርታ ሊጠይቀኝ የመጣ እየመሰለኝ "እንዳትነካኝ " ብየ መርጫህ ምናምን እያሰብኩ (ያው መቸም ባንዴ አልታረቀውም አይነት የመለመን ፍላጎት ተስፋ አይሞትም አይደል) ተዘጋጅቸ ስጠብቀው ወንዴወደ ሳሎን ዝር ሳይል ነጋ !

በህፃንነቴ አባቴ የፈለገ ቢሆን ለምሳ እቤት ሳይመጣ አይቀርም ነበር ታዲያ ሁልጊዜ በር ላይ ቁሜ ነበር የምጠብቀው አንድ ቀን ግን ምን እንደሆነ እንጃ ቀረ የሚገርምህ ወንዴ ሳሎን ሳይመጣ ሲነጋ ከስንት አመት በኋላ ያች ቅፅበት ናት ትዝ ያለችኝ. በሞተ በስንት አመቱ ደግሞ አባቴ ናፈቀኝ !! ከምር አብርሽ አባቴ ከሞተ ስንት አመቱ እስቲ" ብላ አይኗን ወደላይ ወደጣራው ልካ አባቷ የሞተበትን አመት አሰላችና" አስራ ምናምን አመት" አለች ! አፏንና አፍንጫዋን በመዳፏ አፍና የሚታገላት እንባ እንዳይወርድ ስትታገል ቆየችና ቀጠለች.

"ወንዴ ተነሳ ታምነኛለህ አብርሽ የወንዴ ፊት እሩቅ አገር ሂዶ እንደተመለሰ ሰው ናፈቀኝ የሆነ ፊቱ ወደሌላ ሰው ፊት የተቀየረ መሰለኝ ሌላ ሰው መሰለኝ ወንዴ ! አንዴ ወደመታጠቢያ ቤት አንዴ ወደመኝታ ቤት ሲገባና

ሲወጣ ሶፋ ላይ ተኝቼ አየዋለሁ ልክ ብቻውን እንደሚኖር ሰው እቤት ውስጥ ሌላ ሰው እንደሌለ አንድ ጊዜ እንኳን ወደኔ አልዞረም እንደውም ለባብሶ ሊወጣ ወደሳሎኑ በር ሄደ አላስቻለኝም ተስፈንጥሬ ከሶፋው ላይ ተነሳሁና ፊቱ መንገዱን ዘግቼ ቁሜ ክንድና ክንዱን ያዝኩት በዚች ምድር ላይ ያሉትን ስድቦች ሁሉ ላራግፍበት ነበር አካሄዴ ግን ከአፌ የወጣው ቃል

"ይቅርታ ወንዴ" የሚል ነበር !

እስከዚች ደይቃ ያ ይቅርታ ለምን እንደሆነ አይገባኝም ! ቁንጅና በለው ሃብት በለው እውቀት በለው ብቻ የትኛውም ትእቢት ያሳደረብን ጉዳይ ስብር የሚልበት የሆነች ቅፅበት አለች ያች ቅፅበት እንደዛ ነበረች ለኔ ለአመታት ወንድን ያንበረክካል የምለው ቁንጅናየ ማንም አልፎኝ አይሄድም ማንም ይለምነኛል ይለማመጠኛል እንጅ ማንንም አልለማመጥም የሚለው ማንነቴ ስብር አለ !! ደግሞ ለካ ትእቢት ጥሩ ነበር ስሙ ትእቢት ይሁን አይሁን እኔጃ እንጅ የሆነ እንደጀርባ አጥንት ማንነታችንን ቀጥ አድርጎ የሚያቆም ስሜት አለ እሱ ነው ስብር ያለው ተልፈሰፈስኩ ወንዴን እግሩ ስር ወድቄ መለመን ሁሉ አሰኝቶኝ ነበር ምነው ይሄን ሰይጣን ሃሳብ ባልተናገርኩ ብየ ተፀፀትኩ !

ወንዴ ገፋ አድርጎኝ ትቶኝ ወጣ ብቻየን ቁጭ ብየ ማልቀስ ጀመርኩ እስኪወጣልኝ ተነፋርቄ ቀለል አለኝ !! እስቲ አሁን ለማን ይነገራል በምን ተጣላን ይባላል ድንገት አንድ ሰው ታወሰኝ የወንዴ አባት!! በቃ የሆነውን ሁሉ ለሳቸው መንገር መቸስ የልጃቸው ሚስት ነኝ ተቆጥተውም ገስፀውም ያስታርቁናል ብየ አሰብኩ እስቲ ይታይህ አብርሽ በሰላም የተቀመጠ ልጅ ያላሉኝን ተናግሬ እንዲህ ሰዶ ማሳደድ አንዳንዴ ምቾታችን ጠንካራ እየመሰለን ፍቅራችን ወዳጅነታችን ከላይ ውበቱን አይተን መንሰፍሰፉን አይተን ጠንካራ ሸክም ስንጭንበት እንክትክቱ ይወጣል ለካ የወንዴ ነገር እንደዛ ሆነ ! ለባብሸ ወደወንዴ አባት ለመሄድ ተነሳሁ እስከዚች ቅፅበት በምን እንደምሄድ እንኳን አላሰብኩም ነበር ! ምቾት እንዴት ነው የሚያደነዝዘው ወንዴ የለም መኪና የለም ኩንትራት ታክሲ ለመያዝ ወስኘ ብር መፈለግ ጀመርኩ በቤቱ ውስጥ የብር ዘር የለም !! አምስት ሳንቲም የለም ! አሁን ይሄ ይታመናል ?" ልእልት አይና እንባ እንደኳተረ ፈገግ አለች ፈገግታዋ ልብ ስንጥቅ ያደርጋል በሃዘን በዳመነ ፊቷ ውብ ፈገግታዋ ድንገት ፍንትው ሲል በደመና መሃል የወጣች ፀሃይ ትመስላለች ምን እንዳስፈገጋት እንጃ !

"ቁም ሳጥኑን ከፍቸ የወንዴን ሱሪዎች መፈተሽ ጀመርኩ" አለችና አንገቷን ወደመሬት አቀረቀረች ብር የለም !! ወንዴ ምናልባት ቁጣው በርዶለት ከሆነ ብየ ደወልኩለት ስልኩን ዘጋብኝ ! ልብሴን ቀያይሬ አርፌ ተቀመጥኩ !! በትዝታ ጭልጥ ብየ ወንዴ ድንገት ውጭ ሁኖ የሆነ ቦታ ለመሄድ አስቤ ከደወልኩለት "ወንዴ ቀስ ብለህ ንዳ ብዙ አያስቸኩልም " ከሚል ማስጠንቀቂያ ጋር ነበር ስጠራው እንደእብድ እየበረረ እንደሚደርስ አውቅ ነበር ፍቅርን ተከትለው የሚመጡ ነገሮች ሁሉ እንደጥላ ናቸው የፍቅር ፀሃይ ሲጠፋ ሁሉም ነገር ከስርህ ይጠፋል መከባበር፣ መደናነቅ ለስሜትህ መጠንቀቅ ሁሉም ነገር ከስርህ ይጠፋል !! የታደሉ እንደገና የፍቅር ፀሃይ ወጥቶላቸው ጥላቸውም ከነግርማ ሞገሱ ይመለስላቸዋል ካልታደልክ ጥላህ እንደናፈቀህ ጥላ ቢስ እንደሆንክ ይችን ምድር ተሰናብተህ ወደመቃብርህ ትወርዳለህ!! ጥላ ቢስ ሆንኩ አብርሽ !!

***** ***** ******

እህቴ የልእልትን ታሪክ ስነግራት እኔም ራሴ ያላሰብኩትን ጥያቄ ወረወረች (መቸም ነገረኛ አይደለች)

"እኔ የምልህ ወንድም አለም (ነገር ስትፈልግ ወንድማለም ነው የምትለኝ) ልእልት ይሄን ሁሉ ታሪክ ዝርግፍ አድርጋ የምትነግርህ አንተ ንስሃ አባት ነህ ወይስ ምን የሚያስወራ ነገር አስነካሃት ..."

"አይይይ ..."ስል

"ቆይ ሌላም ጥያቄ አለኝ

ልእልት በዚህ ሁሉ ጊዜ እንዴት ሳታረግዝ ቆየች“ ልነግርሽ አይደል ብየ ቀጠልኩ ልእልት የነገረችኝን እያስታወስኩ ....መቸስ ከነገረችኝ ውጭ ለምን እንዴት እንዳልል የሸበበኝ ነገር አለ .....

ልእልት የዛን ቀን ውሎዋን እንዲህ ስትል ቀጠለች አወራሯ ከንፈሮቿ ከምንም በላይ ደግሞ የምትናገረው ነገር ፍፁም እውነት መሆኑን የሚመሰክሩት ንፁህ አይኖቿና ገራገር አነጋገሯ ሙሉ ለሙሉ ቃል በቃል ነጥብ በነጥብ ትረካዋን በጉጉት እንድከታተለው አድርጎኛል .... ምንም ታውራ ደግሞ ልእልት ናት

በሃዘኗም በደስታዋም እኩል ልቤን የሚያሞቅ አንዳች ነገር ከመላ ሰውነቷ ላይ የሚነሳ ልጅ ልእልትን ወድጃታለሁ በዚያች ቅፅበት ከሷ ውጭ ማንንም አልፈልግም የልእልት ድምፅ በውስጤ የሆነ ተአምር የሚፈጥር ይመስለኛል አንዳንዴ ደግሞ ታሪኳ መልኳንም ልእልትነቷንም ያስረሳኝና ጆሮ ብቻ ሁኘ ፊቴ የተቀመጠች ሴት እውነትኛ ታሪክ ሳይሆን በሬዲዮ የሚተላለፍ ትረካ የምሰማ እስኪመስለኝ እመሰጣለሁ

“ ወንዴ ጋር ተጣልተን ያደርን ቀን ጧት ስነፋረቅ ብቻየን ሳለቅስ ዋልኩ ጠብታ እንባ እንኳን ውስጤ አልቀረም ማልቀስ እንዴት ፈውስ መሰለህ እንደውም እኛ ሴቶች ሲከፋን የምናለቅሰውና ከለቅሷችን በኋላ ለመወሰንም የሆነ ነገር ለማድረግም ቀለል የሚለን ከማልቀሳችን በፊት እንባችን ባህር ላይ ሃሳባችን እየዋለለ ስለሚያስቸግረን ሳይሆን አይቀርም !! አባባሏ አስፈገገኝ

“ከምር አብርሽ ልክ አልቅሽ ሲወጣልኝ ወዲያው ማሰብ ጀመርኩ ያውም ጥርት ያለ ሃሳብ አሰብኩ በቃ በዚች ምድር ማንም የለኝም አልኩ ቁጭ ብየ መነፋረቅ ጥቅም የለውም አልኩ እራሴን ደግሞ መውቀስ የለብኝም ምን አጠፋሁ ዞሮ ዞሮ ይሄ ቀን በእኔ ንግግር ሰበብ ቀድሞ ተገለጠ እንጅ ዘግይቶም ቢሆን መሰለቻቸቱ አይቀር እንኳንም ዛሬ ላይ ቀድሞ መጣ እንደውም የእኔና የወንዴ ፍቅር ትዳር የዛፍ ላይ እንቅልፍ ነበር እንኳን ዛፉ ሳያድግና ከዛ ርቀት ወድቄ ሳልፈጠፈጥ ዛሬ ላይ ከእንቅልፌ ነቃሁ አልኩ ዛሬም ልእልት ነኝ ዛሬም ቆንጆ ነኝ እንደውም ወንዴ ጋር ስንገናኝ ከነበርኩት በላይ አምሮብኛል ቆንጆ ሁኛለሁ (መቸስ ያለኝ ብቸኛ ነገር ቁንጅና ነው ሌላ ምን አለኝ ) ነገ በብስጭት ማዲያት ወርሶኝ ወይ ወልጀ ልጅ አቅፌ አፍንጫሽን ላሽ ቢለኝ ምን ይውጠኝ ነበር ብየ አሰብኩ .... ራሴን አፅናናሁት ተንጠፍጥፎ ባዶ ሁኖ የነበረ ውስጤን በራሴ ሞላሁት እንደውም ተነስቶ እዛው ሰፈር ወደምሰራበት ፀጉር ቤት ሄድኩ ችግር የለም ልጅቱ ወደማታ መጥታ ብር እንድትወስድ ልነግራት እችላለሁ እኔ የወንዴ ፊት ሲጠቁር አለም ሁሉ ፊቱ የጠቆረ መስሎኝ ወጣ ስል ሙቶ እርምጃ በማትሞላ ርቀት ሁለት ሶስት ወንድ “ቆንጆ “ እንሸኝሽ ሲሉኝ ፊቴን ኮስተር አድርጌ “ስላፅናናችሁኝ እግዜር ይስጣችሁ” እላለሁ በውስጤ “ ሁለታችንም ከልባችን ሳቅን ! “እውነቴን ነው አብርሽ የወንድ ለከፋ እንደዛች ሰአት ጣፍጦኝ አያውቅም አይዞሽ ልእልታችን ዛሬም ቆንጆ ነሽ ዛሬም እንወድሻለን ዛሬም ተስፋ አለሽ ያሉኝ ነበር የመሰለኝ የመጨረሻው ፀያፍ ነገር ሳይቀር አንዳንዴ መፅናኛህ ይሆናል በፊትማ እንደለከፉ ደሜን የሚያፈላው ነገር አልነበረም “ አለችኝና ሳቃችን ቀጠለ

ኦ ልእልት እንዴት እንደምታሳዝን እንዴት ደስ እንደምትል ! እኔ ራሱ የሴት ወሬ እንደዛን ቀን ጣፍጦኝ አያውቅም !!

“ ከፀጉር ቤት ስወጣ እምር እንዴት እንዳማርኩ ብታየኝ “ አለችና አንገቷን መዘዝ አድርጋ ያኔ እንዴት እንዳማረች ለማሳየት ጡቶቿን ወደፊት ገፋ አድርጋ ተውረገረገች “ከዚህ በላይ አምረሽ “ አልኩ ! አመለጠኝ አመለጠኝ አ.....መ......ለ......ጠ......ኝ ! ልእልት አይኗን በሃፍረት ጣል አድርጋብኝ ወደገድግዳው ዞር አለችና ልክ እንዳልሰማችኝ ወሬዋን ቀጠለች ግን ወሬዋን ያቆመችበት ጠፍቷት ትንሽ እንደማሰብ ብላ ነው የቀጠለችው (ወይ ጉድ እስቲ ምን አንቀለቀለኝ ) “ ከፀጉር ቤት ስመለስ እቤቴ ገብቸ አሪፍ ምሳ ሰራሁ ቆንጆ ቡና አፈላሁና “ልእልትየ የኔ ቆንጆ ብይልኝ ጠጭልኝ” እያልኩ ራሴን ግብዝ !!ቤቴን ፅድትድት አድርጌ ሙሉ ሌሊት ቁጭ ብየ አድሬ እንቅልፌ በቁሜ ሊጥለኝ ደርሶ የለ .....ምኝታ ቤቴ ገብቸ ለጥ የዛን ቀን የወሰደኝ እንቅልፍ መቸም ወስዶኝ አያውቅም ስነቃ ስለሚጠብቀኝ ነገር ሳላስብ እንደበፊቱ በፍፁም ሰላም ለጥ እውነቱን ልንገርህ አይደል በዛው እስከዘላለም ተኝቸ ብቀር ደስታየ ነበር ይሄ ሃሳብ አንድ ገራሚ ሃሳብ ጫረብኝ እዚች ምድር ላይ ይሄን ያህል ውጣ

ውረድ ለምኑ ነው ህይዎት እንደሆነች እስካሁን አቀማጥላኛለች አሁን ፊቷን እያጠቆረችብኝ ነው የባሰውን ሳታመጣው ራሴን ባጠፋስ ግልግል ነዋ ! “ አወራሯ ፊቷ ላይ ያለው ፈገግታ የፊቷ እንቅስቃሴ ሁሉ እንዴት ደስ እንደሚል ነበር የመጨረሻው ንግግር ግን ዘገነነኝ ልክ እንደባሏ አዘናግታ በሃሳብ ቢለዋ የመውጋት ያህል ነበር የሚያመው

# ክፍል 13

ሙሉ ለሙሉ ድኘ ስራ ከጀመርኩ ሁለት ሳምንት አለፈኝ ከመትረፌ የተረዳሁት ሞት የትም እንዳለ ሲሆን የትም ከሚገኝ ሞት የተረዳሁት እንዴትም ሊስተን እንደሚችል ነው እንዴትም መሳት ደግሞ እንዴትም ከመኖር ይልቅ ለሆነ ነገር መኖር እንዳለብን ያነቃናል ከሞት መትረፍ ልክ ሩጫ ላይ የመጨረሻው ዙር ሲደርስ እንደሚደወለው ደውል የህይዎትን አዙሪት ፈጠን ብልን እንድንዞር የሚያነቃ ነገር አለው አለበለዚያ ሞት ይቀድምሃል የሚል ዓይነት !! ከዛን ቀን ጀምሮ ሞት የሆነ ግዙፍ ጥንባሳ አሞራ ነገር መስሎ በሰዎች ሁሉ አናት ላይ ሲያንዣብብ ይታየኛል እኛም እንደጫጩት አቀርቅረን ከድካማችን አፈር ውስጥ ጠብ የሚል ጥሬ ስንለቅም ....የስም ጥሬ፣ ...የገንዘብ ጥሬ .... ታዲያ አንድ ቀን ጥንባሳው ተምዘግዝጎ ይወርዳል ከእኛ ከጫጩቶቹ አንዱን በተንጨፈረሩ ጥፍሮቹ አንቆ ሽቅብ ሊመጥቅ ከተሳካለት ይዞን እብስ ቀሪዎቹ ጫጩቶች ቀና ብለው ትንሽ ይንጫጩና ወደጥሪያቸው ይመለሳሉ ! ጥንባሳው እንደገና እስኪወርድና አንዱን እስኪያነሳው ! አንዳንዴ ታዲያ ...ከጥንባሳው ጥፍሮች አምልጠን መሬት ላይ ምንደፋደፍበትና እንደገና እንኖር ዘንድ አንድ እድል የምናገኝበት ጊዜ ይኖራል ....እንደኔ!!

ይሄው አለሁ ....ቢላ ተመስሎ ከመጣው ጥንብ አንሳ ሞት አምልጬ ሳመልጥ ታዲያ እኖር ዘንድ የተሰጠኝ አንድ እድል ለልእልት መኖር እየመሰለኝ ከጥቃቱ በፊት ምን እሰራ ምን አስብ እንደነበር ሁሉ ጠፍቶብኝ እሷን ብቻ እያሰብኩ ግራ ተጋብቻለሁ ! ልእልት ጋር በየቀኑ እንደዋወላለን ብዙ ጊዜ የምትደውለው እሷ ናት ንግግራችን “እንዴት ነህና እንዴት ነሽ “ ይበዛዋል! ለምን እንደሆነ እንጃ ውጭ ልቀጥራት አስብና እፈራለሁ በጣም እፈራለሁ ትናፍቀኛለች በጣም ትናፍቀኛለች ....ግን እፈራታለሁ ፍርሃቴ ደግሞ ብስጭትና ጭንቀት የተቀላቀለበት ነው ! ስለሷ ሙሉ ቀን አስባለሁ ሳቋ ትዝ እያለኝ አንዳንዴ ካለምክንያት ብቻየን ፈገግ እልና ዞር ዞር በማለት ....” ሰው አይቶኝ ይሆን” ብየ መታየት አለመታየቴን አረጋግጣለሁ! ትካዜዋ ሁሉም ነገሯ ፊቴ ተቀምጣ የማየት ያህል ይታወሰኛል ...

ከምንም በላይ ያንን ሁሉ ታሪክ አውርታልኝ ከንፈር ከመምጠጥ ውጭ ምንም ልረዳት አለመቻሌ ግራ ይገባኛል የሰው ታሪክ ያውም ለብቻችን ሲነገረን “ይገርማል” ብለን የምናልፈው ዜና አይደለም ወይም ከህዝብ ጋር በሬዲዮ እንደምንሰማው “እርስዎ ቢሆኑ ምን ያደርጋሉ “ አይነት የህዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ በጅምላ ደውለን ምክር የምናዋጣበት መድረክ አይደለም በተነገረን ልክ የተነገረንን ችግር ከነጋሪው ጋር አብረን እንጋፈጥ ዘንድ ሰበዓዊነቱ ቢቀር ያለን ቅርበት ያለን ቅርበት ቢቀር ለዛ ሰው በውስጣችን ያደረብን ስሜት ግድ ይለናል

እህቴ እውነቷን ነው “ምንም ካላደረክላት ለምን ያንን ሁሉ ታሪኳን ሰማህ” አለችኝ እንጃ!! መጀመሪያ ምንም ታውራ የልእልት ድምፅ የልእልት ከንፈሮች ሲንቀሳቀሱ ማየት ለእኔ ሃሴት ነበር ሲቆይ ግን የታሪኳ ጥቀርሻ መልኳን ሸፍኖ ልእልት ከጥቁር ግድግዳ ኋላ የቆመች ልጅ ሆነች ለኔ ! ከእርሷ ምንም ልፈልግ ምን መጀመሪያ ይህን የጋረዳትን ጥቁር ግድግዳ ማፍረስ ይጠበቅብኛል የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ ሰምቶ ዝምማ ሳይሰሙ ከመጮህ እኩል ኪሳራ ነው !!

“ወንዴ አንበሳው” እውነቱን ሳይሰማ ጮኸ ምን ተረፈው ዘብጥያ !! እኔ እውነቱን ሰምቸ ዝም አልኩ ምን ተረፈኝ የህሊና ዘብጥያ ! ልዩነቱ የእኔ እስር እኔው እፈታው ዘንድ ቁልፉ በእጀ ነው የወንዴ ግን እጣ ፋንታው በህግና በዳኛው እጅ ነው ! የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ ምን ነገር ....እኔንጃ!! ልእልት ግን “ላንተ ብሶቴን በመናገሬ

ቢያንስ ዝም ብለህ ስለሰመሃኝ ሃዘኔ ቀለል ብሎልኛል ደግሞ ባላደረጉት ነገር መወንጀል የጋራ ህመማችን ነው አብርሽ " አለችኝ "እኔም የማይታይ ስለት እድሜ ልኬን ማይድን ጠባሳ ጥሎብኛል ያውም ባስታወስኩት ቁጥር የሚጠዘጥዝ " አለችኝ ምንድነው "ቀለል ማለት" ችግሩን አሁንም ተሸክመዋለች አይደል እንዴ ልእልት በስስ ነፍሷ ያንን ችግር እንደመርግ ተሸክመዋለች

....የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ ቆንጆ ስለሆነች አይደለም ስለወደድኳት አይደለም (በነገራችን ላይ እንደወደድኳት ማሰብ አልፈልግም) ግን ልእልት እርዳታ ያስፈልጋታል የማንም ሳይሆን የእኔ እርዳታ ያስፈልጋታል ሰው ከገንዘብም ከሌላ ነገርም በፊት በትክክል ሊረዳ የሚችለው ሃሳቡን በተረዳለት ሰው ነው እኔ ልእልትን በሚገባ ተረድቻታለሁ ! ማንም ሰው ቢሆን ልእልትን ሊረዳት የሚችለው በጥርጣሬ ነው በተለይም ከእኔና ከዛ ድንዙዝ ባሏ ፀብ በኋላ ማንም ልእልትን የሚረዳት ባሏ በነዛው ቆሻሻ የፈጠራ ታሪክ አጅቦ ነው!" ጥጋብ ፍንቅል አድርጓት በትዳሯ ላይ የማገጠች "በሚል ተቀፅላ !!

የጎረቤቱን ነገርማ ዝም ነው ሲጀመርም ከድፍን የብሎኩ ሰው አንድ እንኳን ልእልትን የሚወዳት ሰው አለመኖሩ ምናይነት ስነልቦና ቀውስ ውስጥ መሆናችንን ያየሁበት ነው ! ከአደጋው በኋላ ከቤተሰቦቸ ቤት ወደቤቴ ከተመለስኩ በኋላ ድፍን የብሎኩ ሰው ወደማታ ላይ ከላይ እስከታች እቤቴ መጡ

"እንኳን ተረፍክ " ሲሉኝ (እስቲ ያችን የመሰለች ልጅ የሞላው የተረፈው ባሏን ትታ እቤቱ ድረስ የሄደችለት ቤቱ ምን ቢኖረው ነው ብለው ለመሰለልም ይሆናል) እና የግዜር ወንበር እንኳን የሌለበት ቤቴ መጥተው በቁማቸው እኔን "እንኳን አተረፈህ " እያሉ እግረ መንገዳቸውን ግን የልእልትን ስም እያነሱ እንዳትሸጥ እንዳትለወጥ አድርገው አብጠለጠሏት "ኧረ ተው እንዲህ አይደለችም " አልል ነገር "የተወራችው እውነት ናታ" ይሉኛል ብየ እፊቴ ካለሃፂያቷ ልእልትን ሲዘለዝሏት እንደኮሶ እየመረረኝ ዋጥ አድርጌ ዝም አልኩ !!(ያአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም አሉ)

የጎረቤቶቹ አሰላለፍ ልክ የኳስ ጨዋታ አይነት ነገር ይመስል ነበር (ለካስ ሃሜትም ጥበብ አለው ) እማማ ቁንጥሬ ናቸው የሃሜቱን ኳስ የሚያከፋፍሉት በጎረቤቶቻቸው አቅም እና ስሜት ልክ እየመጠኑ" እሱማ ምን ያድርግ " አሉ ወደኔ በአገጫቸው እየጠቆሙ " እሱማ ምን ያድርግ ካለሃሳብ እቤት ተወዝፋ እየበላች ያበጠ ዳሌዋን እያገማሸረች እቤቱ ድረስ ያውም በጨለማ ስትመጣበት " ይላሉ ልክ እቤቴ በምሽት ልእልት ስትገባ ባይናቸው በብረቱ ያዩ ይመስል" እሷ አታደርግም አትባልም ያንን ጫቷን አቅፋ ከጅሪወቿ ጋር ስትወጣና ስትወርድ ከጥፍሯ ቁራጭ አትቆጥረንምኮ እየተገላፈጠች ስትገባ ስትወጣ ሰው ሰላም አትል " ትላለች ሌላኛዋ ተቀብላ (የዚች ሴትዮ ዳሌ ከልእልት ይገዝፋል

ደግሞ ሰላም አለማለትና ከትዳር ውጭ መማገጥ ምን አገናኘው ወይስ በግላጭ ጫት አቅፋ ለመግባት ያልፈራች ሴት ከትዳሯ ውጭም ለመሄድ አትፈራም ነው ?? ) "ምን ታድርግ አቀማጥሎ ይዟት ቢነኳት የምትፈርጥ የተወለወለ መስተዋትኮ ነው የምትመስለው ጠገበቻ" አለ አንዱ ጥቁር መላጣው የሚያብረቀርቅ ሰውየ (ደግሞ ይሄ ማነው ቆይ ግን ይሄን ሁሉ ጎረቤት እንዴት እስከዛሬ በመልክ እንኳን አላውቅም) ወንድ እንዲህ አይነት ጉዳይ ላይ ገብቶ ሲፈተፍት ይደብራል ከምር ! ደግሞ አወራሩ በልእልት መጎምጀቱን ያሳብቅበታል" ቢነኳት የምትፈርጥ ነው የምትመስለው" ሲል ሳያፈርጣት መሄዱ ያበሳጨው አይነት ! እማማ ቁንጥሬ ነገሩ በረድ ሲል ጋዝ ያርከፈክፉበታል

" ይች ቢመቻት የሰው ባልም ከመቀማት አትመለስም ሙች" አሉ ወደአንዷ ደልደል ያለች ሴት ዙረው ይች ሴት እንኳን በመልክ አውቃታለሁ ሁልጊዜ ጧት ወደስራ ስሄድ ስተውጣ አያት ነበር እማማ ቁንጥሬ ታዲያ ወደሷ እየተመለከቱ እሳቱን ጫሩት ቀጠሉ "አሁን አንች አዜብየ የምትውይው ስራ ነው ባልሽ ያ የተረገመ መስሪያ ቤት ቀንሶት እቤት ከዋለ መንፈቅ ሆነው ያን የመሰለ ጎምላላ ከረባቱ ብቻ የሚበቃ እንግዲህ ጎረቤት ናችሁ ይች ባለጌ እግርሽን ጠብቃ ወጣ ስትይ ቤትሽ ዘው ብትል ምን ታውቂያለሽ መቸስ ወንድ አይቶ ልቡ አይጨክንባት ለቁም ነገር አታጋድድም እንጅ ዛላውንማ ሰጥቷል " አሉ

አዜብ የተባለችው አቀርቅራ ዝም አለች" ይሆን እንዴ" የምትል ነው የምትመስለው ! ልክ እባብ ለሀይዋን ፍሬዋን እንዳስታወሳት እማማ ቁንጥሬም ለአዜብ ባሏ ሌላ ቆንጆ የጎረቤት ሴት ጎን ስራ ፈቶ እየዋለ ተሳስቶ ቢሆንስ ....የሚል ጥርጣሬ አስታወሷት (ይች እማማ ቁንጥሬ የሚባሉ ሴትዮ መቸም እንኳን በሁለት ሰዎች መሃል በአገሮች መካከል ጦርነት መቀስቀስ የሚችል ቀንዳም ጋኔኔ ውስጣቸው ሳይኖር አይቀርም ፖለቲከኛ ማለትኮ ይች ሴትዮ ያላቸው ፀባይ ላይ ድግሪ ተጨምሮበት ማለት ነው ) " ታዲያ ... ሲጀምር ይሄን የመሰለ መልአክ ባል ትታ ወንድ የምታሳድድ ሴት እንኳን ጎረቤት አግኝታው መንገድስ ሂዳ ጎትታ ከማምጣት ትመለሳለች ይድፋት እቴ"

ትቀጥላለች ሌላዋ (ሁኔታቸውን ሳየው እንደምሳሌ ያነሱትን እቤት የሚውል ባል በልእልት ሳያሙት አልቀሩም እንግዲህ ጥግጥጉን ለሚስቲቱ ለመንገር ይሆናል ክፉዎች) " ሚስኪንኮነው ወንዴ የኔ ጌታ ! እሷ እንዲች ብላ ፀሃይ አይነካት በገባ ቁጥር ሊ..... ሊ እያለ አንዴ ከሰል አሸክሞ አንዴ እጁ እስኪገነጠል አስቤዛ አንጠልጥሎ አሁን እስቲ በማማ ሞት እንዲህ አይነት ባል በስለትስ ይገኛል ቱ እኛ ሴቶች መቸም ገና ለገና ቆንጆ ነን ብለን ጡራችን" ትላለች አንዷት ድሮ ቆንጆ እንደነበረች የምታስታውቅ ነገረኛ ነገር !

"ኤዲያ መልክ ታጥቦ አይጠጣ ትዳራችን ቤታችን ብለን ጓዳ ለጓዳ ቀበርነው እንጅ ለባብሰን እንሞላፈጥ ብንል መልኩ መች አነሰን መልካችን እንደሆነ ረጋፊ ነው" አለች ሌላኛዋ ልእልትን ስሟን አጥበው አለቅልቀው ሲጨልጡ አየዋሉ መልክ ታጥቦ አይጠጣ እና መልኳ ነው አንዲህ ያበሳጫቸው ! መልከ ጥፉ ሁሉ መንግስት የዚህን ብሎክ እጣ ሆነ ብሎ ለመልከ ጥፉዎች ያወጣው እኮ ነው የሚመስለው ወይስ ባለቤቶቹ ለመልከጥፉ አከራዩት ....እንጃለታቸው አበሳጭተውኛል !!

ዞር ብየ ተናጋሪዋን አየኋት...ከበሩ ኋላ ደማቅ ቀይ የእራት ቀሚስ ለብሳ ቁማለች (የራት ልብስ ለብሳ ለሃሜት መምጣት) አስሩም ጣቶቿ ላይ ረግዥም ሰው ሰራሽ ጥፍር ሰክታ ቦግ ያለ ቀለም ተቀብታቸዋለች!! የተነኮረ የጤፍ ቂጣ የመሰለች መልከ ጥፉ ናት ደግሞ አለች "መልኩ መች አነሰን" እውነት ይወራ ከተባለማ ቀላል አንሷታል ! እንደውም እንዲህ ነብሷን እስከትስት ዘንጣ መጥታ እንኳን አንሷታል

አሁን የዚች ሴት መልክ ምኑ ነው የሚረግፈው እንደተሰጣ ልብስ መልክ የሚባለውን ሁሉ ከላይዋ ላይ አራግፎ ወደህይዎት ያስገባት ነገር ወይኔ ልእልትየ የማንም ያፈር ገንፎ ስሟን ይፈትፍተው ! ) ተፀፀትኩ ! ሁሉም እኔንና ወንዴ አንበሳውን ጨዋ ልእልትን ባለጌ ስድ የማትታመን "ወንድ አውል" አድርገው እፊቴ ሲያበሻቅጧት (ልክ እቤቴ መጥታ አልፈልግም ብየ የመለስኳት ይመስል) ሲያሞካሹኝ (ሜዳሊያ አንገቴ ላይ ማጥለቅ ነው የቀራቸው) ዝም በማለቴ ተፀፀትኩ "ልእልት እንደምትሏት አይደለችም " ማለት ቢያቅተኝ እንኳ "ልእልት የዛን ቀን እዚህ አልመጣችም እኔ እዚህ እንደምትኖርም ያወኩት .... " ማለት እንዴት አቃተኝ ብየ ተፀፀትኩ ሌላው ቢቀር ወደኪችን ገብቶ ቢላ መዝዤ እነዚህን ጎረቤቶቸን ማሳደድ ሁሉ ተመኘቸ ነበር (እንኳን እኔ የማንም ቦዘኔ ለመዘዘው ቢላ ደግሞ) አንዳንዴ ግን ለምን ውሸት ሲወራ አፋችን እንደሚያያዝ ይገርመኛል እውነት ተናግሬ ከስራየ ብባረርስ ብታሰርስ እያልን ለምዶብን ምንም በማይፈጠርበት ሁኔታም አፋችንን በእውነት ላይ መሸበብ ብሔራዊ ዓመል ሁኖብን ቀረ !! ልእልት ምንም እንዳላደረገች አውቃለሁ አይደል እንዴ ??

እነዚህ ቱልቱላ ጎረቤቶች የቤት ኪራይ አይከፍሉልኝ ደመዎዝ አይከፍሉኝ እንዳሻቸው ሲቀደዱ ምን አፌን ለጎመው ውሸት ሲወራ ሰው ካለነገሩ ሲወነጀል ዝም ከማለት በላይ ውሸታምነት ህሊና ቢስነት የለም ! አሁን ነገ መስሪያ ቤት ጓደኞቸ ጋር አጉል ሃቀኛ ልሁን እያልኩ ስደሰኩር እገኛለሁ የሞትኩ !! ትልቁ ውሸታም ውሸት መሆኑን እያወቀ ውሸትን እራሱን እየነቀነቀ የሚያዳምጠው ሰው ነው !! ውሸታሙማ ያው ከውሸቱ የሚያገኘውን እርካታ እያጣጠመ ነው !! በእርግጥ ግማሻቸው ድፎ ግማሻቸው ብርቱካን ይዘው ቤቴ መጥተዋል ግን እውነት በድፎ ይቀየራል? (ይድፋቸውና) እውነት በብርቱካን ይቀየራል? ጉርብትናስ ከሃቅ የበለጠ ዋጋ አለው ?...አንዷት መድረሻ ያጣች ልጅ ላይ ይሄ ሁሉ ጎረቤት ያውም ካለስረዋ ሲረባረብ ዝምታ ነበር ከእኔ የሚጠበቀው ? ....እቤት ፊታቸው ላይ የነበረው ጥላቻ ....ዋና ችግራቸው ቅናት መሆኑን በሽ ማስረጃ አስደግፌ መናገር እችላለሁ

ልእልትን ስለወደድኳት ለሷ ለማገዝ ነው? ....አይደለም !! የሚገርመኝ ልእልት ይሄን ሁሉ ጊዜ ከቻለችው ችግርና መከራ ይልቅ ((((የመባለዳ ወሬ)))) እግር አውጥቶ አገሩን አዳርሶታል ለምን እንደሆነ እንጃ ህዝቡ ቆንጆ ሴትን እንደጥላት የመመልከት አባዜ ተጠናውቶታል ((ቆንጆዋ የእኔ ካልሆነች በቃ ባለጌ ናት አይነት እውር ድምዳሜ)) ስራ ብትይዝ በቁንጅናዋ ባልጋ በትምህርት የተሸለ ውጤት ብታመጣ አስተማሪዋ አልጋ ላይ እንጅ ትምህርት ቤት ወንበርና ጠረጴዛ ላይ ተፈትና ነው አይባል መኪና ብትይዝ በቁንጅናዋ አንዱ ሃብታም መፅውቷት ቢሞት ቆንጆ ሴትን የማያምን ማህበረሰብ የት አለ ቢባል እዚህ አዲስ አበባ!! የሴቶች መብት እኩልነት ምናምን እያለ በአደባባይ የሚጮኸው ሁሉ ቆንጆ ሴት መኪና ይዛ ባጠገቡ ካለፈች አይኑ ደም ይለብሳል !! እንኳን መኪና ደህና ጫማ አድርጋ ስታልፍም ሳይቸግረው የሚበሳጭ ህዝብ ! የቆንጆ ሴት ትዳር ሳይቀር በፍቅር የተመሰረተ ነው ማለት የሚተናነቀው ህዝብ እንደኛ የት አለ የቆንጆ ሴት ትዳር ከፈረሰ ሆዱ ቢያውቅ እንኳን ባል "ሚስቴ ወስልታ ነው" ካለ ይሄንኑ ወሬ ይዞ የሚሮጠው ይበዛል ቁንጅና በራሱ ብልግና እስኪመስል የሁሉም ፀያፍ ባህሪ ባለቤቶች ቆንጆ ሴቶች ተደርገው የመታየት አባዜ እንደወረርሽኝ ከቦናል ለነገሩ ድራማው ፊልሙ ሁሉም ቆንጆ ሴትን ብልግና በመተረክ በየቀኑ ይሞላናል የተሞላነው ፀባይ ሁኖ ወደውጭ ይረጫል !! ይሄም ሁኖ እያማን እያናናቅን እየሰደብን እና እየረገምን ቆንጆ ሴቶችን ስናሳድድ ውለን ስናሳድድ የምናድረው የትየለሌ ነን !

በውበቷ አሳሳተችኝ ለማለትኮ ነው ! ስራችንና ድርጊታችን የየቅል !! ታዲያ ሃሜት አስመስለን ጥላቻ አስመስለን ግሳፄ አስመስለን በሾርኔ (ርግማናችን ራሱ ሰምና ወርቅ አለው) "ቁንጅና የማያመጣው ሃብት የማየከፍተው በር የለም" የሚል መልእክት እንዘራለን የዛሬ ህፃን ሴቶች እያጠጣናቸው ባሳደግናቸው የርግማን ዝናብ እርግማን ለበስ አድናቆቷን አይስቷትም ( አበሻ አይደሉ እንዴ ቅኔ ለመፍታት ማን ብሏቸው !!)

እና ከሁሉም ቆንጆ ሴቶች ከሚወገዙበት ቃል ጀርባ ቁንጅና የሚያስገኘው ጥቅም የመርገምት "ሰሙን" ተጀቡኖ የስኬት "ወርቅ" ሁኖ ተቀምጧል ! በእጃቸው ሰርተው በአእምሯቸው አስበው ከማደር ይልቅ ተጎልተው ጥፍራቸውን እየሞረዱ በተመልካች አይን እና በወንድ አድናቆት ሚዛን ልክ ሰውነታቸውን እየመዘኑ የምናገኛቸው ቆነጃጅት ይችን መሃበረሰቡ የሚዘርፍላቸውን ቅኔ በሴትነት ቁልፍ የፈቱ ናቸው ለዚህ ነው በየመስሪያ ቤቱ በየመዝናኛው በየመንገዱ አንጥፈው ቁንጅናቸውን እንደለማኝ ድሪቶ አንጥፈው የስኬት ሳንቲም እስኪጣልላቸው አይናቸውን የሚያቁለጨልጩ ቆነጃጅት እንደአሸን የፈሉት !

እዚህ የኑሮ ህበረ ቃል ውስጥ እዚህ ለቅሶው ሳቅ ሳቁም ለቅሶ የሆነበት አዙሪት ውስጥ ስንቀለቀል ተዘፍቄ ፍዳየን አያለሁ !! አንዲት ቆንጆ (እጅግ በጣም ቆንጆ) ባለትዳር ሴት ያውም እኔ ጋር ግንኙነት እንዳላት በመጠርጠር ባሏ በቢለዋ ወግቶኝ እስር ቤት የሚገኝ ጎረቤቱም ግንኙነት ይኑረን አይኑረን ግራ ገብቶት በብዥታ ላይ ባለበት ሰዓት እንዴት ነው የምረዳት ?? መርዳቱ ይቅር እንዴት ነው የናፈቀኝ አይኗን የምመለከተው አውቃለሁ ልእልት ባለትዳር ናት .... ትዳር ክቡር ነገር ነው ... ፈጣሪም በማያወላውል ቋንቋ አስቀምጦታል ባለትዳር ሴት የቱንም ያህል ውብ ቆንጆ ትሁን የቱንም ያህል ትቅረብህ የቱንም ያህል ትዳሯ ጥሩ አይሁን ስታምርህ ትቅር ነው ትዛዙ !!

እኔ ግን አልቻልኩም !!. ከእናቴ ቤት ተመልሼ እቤቴ ከገባሁ በኋላ ደረጃዎቹ ላይ የልእልት ዳና ይታየኛል አልጋየ ላይ በጀርባየ ተንጋልየ ከበላየ ከተዘረጋው ጣራ በላይ ልእልት ስንት ሌሊቶች ተደፍታ ስታለቅስበት የነበረው አልጋ መኖሩን እያሰብኩ እተክዛለሁ አንሶላው ላይ አሸዋ የተዘራበት ይመስል ምኝታው ይኮሰኩሰኛል የቢሮ ወንበሬ ላይ ጠጠር በገልባጭ መኪና አምጥተው የደፉበት ይመስል መቀመጥ ስቃይ ሁኖብኛል ኡኡኡኡ ከምር ልእልት ናፍቃኛለች !!

*** **** *****

ትላንት እህቴ ደወለችና "ስማ በቃ አንተ እንደዚህ ቋጣሪ ሁነህ ቀረህ ትላንት የደሞዝ ቀንህ ነበር አይደል እስቲ ዛሬ ሞቅ ያለ ግብዣ ጋብዘን " አለችኝ" ምንን ምክንያት በማድረግ" አልኩ እህቴ ጋብዘን ካለችኝ የሆነ ወሬ አላት ማለት ነው

" ምክንያት ትላለህ እንዴ ብትሞት ኖሮ ዛሬ ሁለት ሰባትህ ነበርኮ ስለዚህ ለምን የቁም ተስካርህን ምክንያት በማድረግ አትጋብዘንም ?"

"እንዴ ስንት ናችሁ ?"

"አራት ነና ጓደኞቹ ጋር ሆስፒታል ሁነህ አብረውኝ ሲጨነቁ ነበር ዛሬ ላንተ በጭንቀት ያወጡትን ላብ ተካላቸው ሂሂሂ" እህቴና ሶስት ጓደኞቿ የማይለያዩ ናቸው ሁልጊዜም አራት ከሃይስኩል ጀምሮ አሉ አሉ እኔን እያከሰሩ ! "ተይ እንጅ "እህት አለም" አራት ሴት በምን አቅሜ አንድ ሰው ጣል ብታደርጉበት እኮ አምስት ሁናችሁ የትጥቅ ትግል መጀመር ትችላላችሁ " "አያስቅም!! በቃ ፓሮት ሬስቶራንት ፎቁ ላይ 9፡00 ሰዓት " ብላ ስልኳን ዘጋች እኔኮ ነገረ ስራዋ ያስቀኛል ....!!

*** **** *****

በጭራሽ አልጠበኩትም ነበር በጭራሽ በቀጠሯችን ሰዓት ሬስቶራንቱ ፎቅ አንድ ጥግ እህቴ ከልእልት ጋር ተቀምጣ አገኘኋት ልቤ ስንጥቅ ነው ያለው እህቴ አንድ ከጥይት የፈጠነ ጥቅሻ ጠቅሳኝ ምንም እንዳልተፈጠረ ዝም አለች ልእልት ፈገግ ብላ ከወንበሯ ተነሳች ፀጉሯ አሁንታጥባ የለቀቀችው አይነት ፍርፍር ብሏል ከላይ የለበሰችው ቢጫ ቦዲ ሰውነቷ ላይ ጥብቅ ብሎ ጡቶቿን አሳምሯቸዋል የዚች ልጅ ሆድ ግን ዝም ብየ ሳየው ወደውስጥ አየር ስባ የያዘችው ነው የሚመስለው እሷን ሳይ ስለሚጨንቀኝ እኔ ወደውጭ እተነፍሳለሁ !

ፈገግ ብላ "አብርሽ" አለችኝ ልክ አፋችን በትልቅ በሚጣፍጥና ወጥ በረሰረሰ የሚያስጨንቅ ጉርሻ እንደሚሞላው የልእልትን የፈገግታ ጉርሻ ጎርሶ አይኔ በእይታ ብቻ ጥግብ ሲል ይታወቀኛል ጉንጪ ጉንጩን ሲነካኝ ለስላሳ ቆዳዋ ሰመመን ሆነብኝ !(እግዜር ያሳድግሽ አንቺ ቀልቃላ እህቴ ) ቀድመውኝ አዘው ስለነበር ያዘዙት ፒዛ ሲቀርብ ልእልት ልትታጠብ ተነሳች ይችን አጋጣሚ ተጠቅሜ (ያልፈለኩ ለመምሰል) እህቴን አፈጠጥኩባትና

"ስሚ" ...አልኳት ኮስተር ብላ

"እ " ብላ እሷም ኮስተር ብላ ስታፈጥብኝ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ሳቁ አመለጠኝ ሁለታችንም ተሳሳቅን

"አራት ጓደኛ ምናምን አላልሽም"

"እሱን ተወው ....እኔማ በቁንጅናቸው አገር ያወቃቸው ጓደኞቹ ጋር ባስተዋውቅህ አንተ የሰው ሚስት ጋር ሙጭጭ አልክ"

" እነማናቸው ደግሞ አገር ያወቃቸው ቆንጆዎች"

"ባክህ ታውቃቸዋለህ ሄርሚ አሁን ፎቶዋ መፅሄት ላይ ቢወጣ አንድ ሚሊየን ኮፒ ነገውኑ አይሸጥም?" ብላ ጀመረች እውነቷን ነው ሄረሜላ በጣም ቆንጆ ትሁት የእህቴ ጓደኛ ነች ለምን እንደሆነ እንጃ የእህቴ ጓደኞች እህቴን ራሷን ነው የሚመስሉኝ እንኳን በሌላ ነገር ማሰብ እና ስለጓደኞቿ ካነሳች መቀለድ ነው የሚቀናኝ አሁንም ስለእህቴ ጓደኞች ከእህቴ አፍ ነጥቄ ቀጠልኩ

"እሱንኳን ተይው የሄርሜላን ኮስታራ ፊት መንግስት ራሱ መፅሄት ላይ ቢያየው የትጥቅ ትግል የጀመረች ታጋይ መስላው መፅሄቱን ወዲያው ነው የሚዘጋው ቬሽን ትንሽ አገጯ ረዘም ቢልም ውብ ነች ትእግስት ቁመቷ ከማጠሩ ውጭ ምን ይወጣላታል ያም ቢሆን ለማቀፍ ትመቻለች ሳምሪ በቀን አንድ ጊዜ ማልቀስ ሆቢዋ ከመሆኑና ውጭ የጠየም እንቁኮነች ከእነዚህ ሁሉ በላይ ግን የእኔ ምርጥ እህት አርባ ክንድ ምላሷ ጋር ሽጉጥ የታጠቀ የብረት አማች የምታመጣ ምርጥ

" ሂድ እዛ ቀልደህ ሙተሃል ሞዛዛ .....እየው ደግሞ ....የሰው ሚስት እንዲች ብለህ ትነካና ባሏ እንደሽንኮራ ለአራት ነው የሚሰነጣጥቅህ እንደውም ጀምሮሃል ..."

"ታዲያ ለምን አገናኘሽን ...."

“ የጀመረችልህን ታሪክ እንድትቀጥልልህ ነዋ ...አየህ በዛው እኔም ከልእልት ትዳር በመማር ትዳሬ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ችግር ከወዲሁ ...”

“እንዴ ....እኔ ሳልሰማ ባለሽጉጡ ሽማገሌ ላከ እንዴ ...”

“ሂድ ወደዛ.....” ብላ በእፍረት ተነስታ ልትታጠብ ሄደች እህቴና ልእልት መንገድ ላይ ተላለፉ ልእልት መጥታ እህቴ ወንበር ላይ ተቀመጠች (በለው የተነሳንበትን እስክንረሳ ከተምታታብንማ ጥሩ ጅማሬ ነው፡) እህቴ ስትመለስ በወንበሮቹ ለውጥ ትንሽ የተንኮል ፈገግታ ፊቷ ላይ በለጭ ብሎ ጠፋና ፒዛውን ጀመርነው ....ፒዛውን ስቆርጥ እህቴ በነገረኛ አይኗ አየት አደረገችኝና

“ ወንድም አለም እሱን ቢላ እንዳይቆርጥህ ተጠንቀቅ “ አለችኝ ልእልት ቡፍ ብላ ሳቀች ወይ ሴቶች ! እኔ የእህቴ አሽሙር ዘግይቶ ነበር የገባኝ !! የተረገመች !! ቀና ስል ልእልት ጋር አይን ለአይን ተጋጨን አይኖቿን ወደፒዛው መለሰቻቸው “እሰይ ልእልትየ እስቲ እንዲህ የማይናገረውን አርፈሽ ብይ “

## ክፍል 14

አምሽተን ከሬስቶራንቱ ልንወጣ አስተናጋጁን ጠርቸ ልከፍል ስል እህቴ “ተከፍሏል ዛሬ እኔ ነኝ ጋባዣችሁ “ አለችኝ (ኧረ ሲስቱካ ....ምን ታያት ዛሬ ) ከሬስቶራንቱ በቀኝ እህቴ ...በግራ ልእልት አጅበውኝ ስወጣ ምድረ ወንድ አይኑን እህቴና ልእልት ላይ እየተከለ ይነቅላል በነገራችን ላይ የልእልት ቃል የማይገልፀው ቁንጅና ዋጥ ስልቅጥ አድርጎት እንጅ እህቴም ብትሆን በቁንጅናው አትታማም እንግዲህ በዚህ ነፋሻ አየር በቆነጃጅት ታጅቦ በሚንጎማለል ጎረምሳ ያልተቀና በማን ይቀናል ያውም በቀኝ ባለሽጉጥ በግራ ባለ ቢለዋ አጋር ያላቸው ቆነጃጅት መሃል ....ሃሃሃ ደስ ብሎኛል ....ቢያንስ ናፍቆቱ ቀለል አለልኝ ልእልት ጋር አብረን አምሽን እላለሁ ለራሴ

ልእልትን የኮንትራት ታክሲአስይዘን ሸኘናት ቆሜ ታክሲዋ ስትርቅ ስመለከት “ አቡቹ አብረሽ በሃሳብ ሄድሽኮ እንሂዳ “ ብላ አባነነችኝ እህቴ ! በሃፍረት ፈገግ አልኩ ደስ ብሎኝ ነበር ልእልት እዚህ ድረስ ለአይኔ እንደናፈቀችኝ በምናባቴ አውቄ ! የናፍቆት ልኩ ለካ የተናፈቀው ሰው ሲገኝ ነው የሚታወቀው “ነገ ረፍት ነህ እስቲ እኛ ጋር እቤት እደር ዛሬ ባዶ ቤት ምን ትሰራለህ “ አለችኝ እህቴ እንደፍቅረኛ ክንዴን ይዛ ውለታዋ ከብዶኝ (ባልናገረውም) እሽ ብየ አብረን ወደቤት መንገድ ጀመርን

“ታክሲ እንያዛ “ አልኳት

“ወንድ ልጅ አይደለህ እንዴ ከዚች እዚች ታክሲ እስቲ አንዳንዴ ዎክ ማድረግ ልመድ የሚስትህ ባል እንደሆነ እስር ቤት ነው ሂሂሂ”

“ ኣኣ ...ቢያመልጥስ ....”

“መፋለም ነዋ ሁለት ወዶ አይሆን ወይ ሚስቱን ለቀቅ ወይ”

“አንች ልጅ ግን እንዴት ነው የምታስቢው ልእልት ጋር የሆነ ግንኙነት እንዳለን ታስቢያለሽ እንዴ ከምር ግራ እየገባሽኝ ነው እንደዛ ካሰብሽ ተሳስተሽል ባለትዳርኮ ነች ....”

“ ምንድነው ግንኙነት ማለት አስር ጊዜ እየተያያችሁ ስትሽኮረመሙብኝ አመሻችሁ ምንስ ታናሽ እህት ብሆን ትንሽ ብታፍሩኝ ብታከብሩኝ ምን አለበት መተፋፈር ወጉ ባህሉ ነበር እኔን በመስኮት ወርውራችሁ መሳሳምኮ ነው የቀራችሁ እና ከዚህ ወዲያ በሰው ሰማኒያ ላይ ሰማኒያ አታስር” አለችና በራሷ ቀልድ ከትከት ብላ ሳቀች ! ላለመሳቅ እየታገልኩ ...

“ችግር አለብሽ “ አልኳት ...

"ትክክል ! ችግርማ አለብኝ ...ችግሬ አንተ ነህ አብርሽ " አለችኝ ክንዴን ለቀቅ አድርጋ እጆቿን ኪስና ኪሷ እየከተተች "አቡቹ " ነው በሰላሙ ቀን የምትለኝ "አብርሽ" ካለች መረር ያለ ነገር ሊከተል ነው ማለት ነው" ስማ አብርሽ " አለች እንደፈራሁት

" እኔ እዚህ ድረስ ያለችኝን እረፍት አቃጥየ ልእልት ጋር ያገናኘኋችሁ የሰው ሚስት የማቃጥር ባለጌ ሁኘ አይደለም አንተ እንዳልከው ችግር ስለሆንክብኝ ነው ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለማሚም ለቤተሰቡም ለራስህም ችግር ስለሆንክ ነው ዝም ብለህ እንደ ፊልም ትሟዘዛለህ እግዚአብሔርም በግንትህን አይቶ እንደፊልም ከቢላ አተረፈህ ሁሌ መትረፍ ግን የለም አብርሽ ! ቢያንስ በእድሜ ትበልጠኛለህ እያደረክ ያለኸው ነገር ሁሉ ግን የህፃን ነው አንተ አታፍርም ነገ እዛው ኮንዶሚኒየምህ ግቢ ቀጥርሃት አንዱ በረንዳ ላይ ተጎልታችሁ አይናይኗን ስታይ ትገኛለህ እሷም ቀለበቷን አንተ ያደረክላት ሳይመስላት አልቀረም ተዋዳችኋል የጅል ፍቅር "

" ምንድነው የምታወሪው አብደሻል እንዴ ከተዋወቅን አንድ ወር እንኳን አልሞላንም ዝምብሎ መዋደድ አለ? ታበዥዋለሽ" አልኳት ውስጤ ግን "ተዋዳችኋል " ስትል ቢያንስ ለሶስተኛ ሰው እስከሚያስታውቅ ልእልት እኔን መውደዷን የሚያረጋግጥ ነገር ፊቷ ላይ መታየቱ ውስጤን አንዳች የንዝረት ስሜት ለቀቀበት ! እኔማ እንደወደድኳት ጥንቅቅ አድርጌ አውቃለሁ ! ሰው መቸስ ካለነገር በቢለዋ ተወግቶ የተኛበት ሆስፒታል ገነት መስሎ አይታየው ! እግዚአብሔር ይሁነኝ እንጅ የሰው ሚስትማ ወድጃለሁ ! ልእልትን ወድጃታለሁ ! አእምሮየ እንደድሮ ካሴት የራሱን ደስታ የራሱን ትዝታ ሁሉ እየደመሰሰ ልእልት የምትባል ዜማ እቀረፀበት ነው !!

"እንኳን አንድ ወር አንድ ሰዓት ይሁናችሁ ሴቶችን አታውቀንም መጠናናት ቅብርጥስ ስንል እውነት እንዳይመስልህ ማንኛዋም ሴት ውስጥ ገና በአንድ እይታ ገና በአንድ ቃል ወንድን መዝኖ ማንነቱን ቁጭ የሚያደርግ ደመነፍስ ነው ያለን ስሜታችን ደመነፍሳችን የሚነግረንን አውነት ገፍትሮ ስለሚጥለው ነው እኛም በእናንተ ተገፍትረን የትም የምንወድቀው "

"ጉረኛ ....እና የወንድን ልብ ብታውቁ በየቀኑ በሬዲዮ አይቀራችሁ በጋዜጣ አታለለኝ የሚፈልገውን ሲያገኝ እሱን አምኘ ቢቢቢቢ ...((በሽጉጥ አስፈራርቶኝ ))) የሚል ለቅሷችሁ ያደነቁረን ነበር ?"ብየ ከት ከት ብየ ሳኩ እህቴም የሽጉጧ ነገር አሳቀቻት !

"ብዙ "ፋክተር" አለ ... እኛ ሴቶች ውስጥ ተራራ የሚያክል በተፈጥሮ የተሰጠን "ራሽናል " የሆነ እውነት አለ ብትፈልግ ደመነፍስ በለው ማንኛዋም ሴት ውስጥ አለ የገጠር በላት የከተማ ይሄን እውነት ማንም ወንድ ሃቀኛ ፍቅር ይዞ ካልመጣ በስተቀር ሊገፋውም ሊያሳምነንም አይችልም !

" እናተ ውስጥ ደግሞ በተፈጥሮ ይሁን በአስተዳደግ የተሰጣችሁ ማህበረሰቡ ያስታጠቃችሁ "ኢሞሽናል ፈንጅ " አለ ....የሀብት ማቀጣጠያ ...የስልጣን ማቀጣጠያ የእውቅና ማቀጣጠያ ገመድ የተቀጠለበት (አጥፊና ጠፊ አድርጎን) ይሄንንም እናውቃለን በቃ የሆነች ቦታችን ላይ የሆነች ስሜታችን ላይ ተራራ እምነታችንን ትቦረቡሩና ያንን ፈንጃችሁን ትቀብሩብናላችሁ ራቅ ብላችሁ መለኮስ ነው አየህ ሲቀጣጠል ብናየውም የእሳቱን ከለር ሙቀቱን እያደነቅን ከመሸሽ ይልቅ ተገትረን እሳታችሁን ስንሞቅ እንደውም ዙሪያውን እንደሳትራት እየዞርን እንደካምፋየር ስንጨፍር .....ቡምምምምምም ! እምነት የለ ምክንያት የለ ቤተሰብ የለ ሞራል የለ ክብር የለ ሁሉን ነገር ትተን በፍንዳታው የፈራረሰ ማንነታችንን እግራችሁ ስር እንቆልልላችኋለን ! እናተም ፍርስራሻችን ላይ ከነአፍራሽ ማንነታችሁ ቁማችሁ እንደጀግና መፎከር ማህበረሰቡ የፈቀደላችሁ ወንዳዊ ጀብዱ ነው !! ወንዴ ልእልት ላይ ያደረገው ያንን ነው አልታወቀህም እንጅ ልእልት ድሮ ማንነቷን ስታወራህና ስታዳምጣት ለሁለት መልሳችሁ "ልእልት የምትባላዋን ልጅ እየገነባችኋት ነው" ያውም የማትፈርስ ልእልት በዚህ ግንባታ መሰረት አጣጣልህን ብቻ ለማየት አንድ ወር ብዙ ነው ልእልት ደግሞ ስሜትህን አንብበዋለች በግን ማን ይጠላል ስትፈልግ ታረበሃለች ስትፈልግ ታርድሃለች !!

"እና ልእልት በአንድ ወር መዝናህ ወድሃለች በፍቅርህ ልብሷን ጥላልሃለች ካላየችህ እህል አይበላላትም ገና እንዳየችህ ልቧ ትርክክ ብሎባታል እያልሽኝ ነው እህት አለም" አልኩ አገላለፅዋን ባደንቅም ትንሽ ነገሩን በቀልድ ላዋዛው ብየ "አላልኩም ልእልት ከምታስባት በላይ ብልህ ናት እያልኩ ነው እስቲ አስበው ከ አስራ አንድ ነው ከአስራሁለተኛ ክፍል ትምህርቷን ያቋረጠች ልጅ ያውም ከአንድ ወንድ በላይ ነክቷት የማያውቅ ሴት እንዴት ህይዎትን እንዲህ አብጠርጥራ ልታውቅ ቻለች? እሽ ይሄ አጋጣሚ ይሁን ባሏ ያን ያህል በደል ሲያደርስባት ለምን ትዳሯን መነቃቅራው ሌላ ወንድ ጋር አልሄደችም እግሯን ስሞ የሚጠቀልላት ወንድ በሽ ነው እልት ውብ ናት እኔ ጋር እንኳን ቅድም ስንሄድ ብቻዋን ያለች ይመስል ወንዱ ሁሉ እሷ ላይ አይኑን ሲያጉረጠርጥና እኔን እህትህን እንደተበላ ዕቁብ ርስት አድርጎ ሞራሌን ሲነካው አይተሃል ሂሂሂሂ …"

"አይዞሽ እህታለም የምንታይበት ጊዜ ይመጣል " ብየ በቀልድ አፅናናኋት

"አመሰግናለሁ ወንድማለም ሴት በወንድ አይን ብቻ አትኖርም በራሷም አይነ ህሊናም ጭምር እንጅ " አለችና በማሾፍ እንባዋን በጣቷ ጠርጋ ወደሰማይ ረጨችው (ከምር ይች ልጅኮ ፊልም ምናምን ብትሰራ ያዋጣት ነበር ) እና አቡቹ ነገሬን ሳሳርገው ተፈጥሮ አንዳንዴ ከምታስበው በላይ ጠንካራ ስብእናን በለስላሳና ቆንጆ መልክ ጠቅልላ መንገድህ ላይ ታስቀምጥልሃለች ልክ በህፃንነታችን ድንጋይ በካልሲ ጠቅልለው ጥፍራችን እስኪነቀል እንደሚያስጠልዙን ተንኮለኛ ልጆች ማለት ነው ከመጠለዝህ በፊት አስተውል አብርሽ እውነቴን ነው አስተውል እወድሃለሁ ላጣህ አልፈልግም" አለች ኮስተር ብላ አቀፍኳት ገድገድ ብላ ወደኔ ተጠጋችኝ" በስርአት ሴትን ልጅ ማቀፍ እንኳን ሳትችል ነው ከሰው እቅፍ ሰው ሚስጥ ለመንጠቅ የምትሮተው " አለች… ሃሃ ….እንዳቀፍኳት የሆኑ ወረቀቶች አስጨበጠችኝ" ምንድነው "

"ቅድም ካፌ ውስጥ ላንተና ለሚስታችሁ የከፈልኩት ቢል ነዋ "

"እና ምን ላድርገው "

"እቤት ስንደርስ እንተሳሰባለን " ከምር አሳቀችኝ …ከምር !!

"ታውቃለህ አቡቹ የልእልትን ታሪክ ስትነግረኝ በእያንዳንዷ ቃልህ ውስጥ ለሷ ያለህን ፍቅር በሁኔታህ ስትናገረው ነበርኮ…." አለችኝ

"መስሎሽ ነው ባክሽ "

"የገረመኝ ደግሞ እሷም ስላንተ ስታወራኝ ልክ እንዳንተ ፊቷ በፈገግታ ቦግ ብሎ ነው " አለችኝ …ድንገት መንገዱ ላይ ቀጥ ብየ ቆምኩና

" ከምር ልእልት ስለኔ አወራችሽ ምን አለችሽ " አልኩ በጉጉት

" ሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ " ብላ የሚያልፉት ሰዎች እየዞሩ እስከሚያዩን ሳቋን ለቀቀችውና " አየሽ አቡቹ እንዲህ ድንገት መንገድ ላይ ትንፋሽ አሳጥረውና ቀጥ አድርገው የሚያስቆሙ ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው አንዱ የፌዴራል ፖሊስ ሲሆን ሌላው ፍቅር ነው ሂሂሂሂሂ ….ለማንኛውም ሚስታችሁ የአንተ እህት በመሆኔ መታደሌን ነገረችኝ … " ብላ እስከቤት እየሳቀች መንገዳችንን ቀጠልን …..

# ክፍል 15

ዝም ያለ ነበር ህይዎቴ ዝምታ ሰላም እንዳልሆነ ያወኩት አሁን ነው አንዳንዴ ዝም ያለና ፀብም ፍቅርም የለሌበት ህይዎት ስጋትም ተስፋም የሌለበት ኑሮ እንደኩሬ ውሃ መሆኑም የተገለጠልኝ ሰሞኑን በልእልት ምክንያት በተፈጠረው ትርምስ ነው ! ላለፉት አምስት አመታት ተመልሽ የኖርኩትን ህይዎቴን ሳስበው ማንም ጋር ተጣልቸ አላውቅም በምንም ነገር ሰግቸም አላውቅም እሰራለሁ ደመዎዝ እቀበላለሁ እኖራለሁ ! ሰዎች ሁሉ "ጥሩ ልጅ"

ይሉኛል አበቃ ! ልእልት ግን መጣችና ልክ ወደውሃ እንደተወረወረ ጠጠር ዝም ባለ በረጋ አኗኗሬ ላይ ሞገድ አስነሳችበት (ጌታ ይባርካት) አንዳንዴ ፍቅር ራሱ "ካልደፈረስ አይጠራም" በሚባለው የአበሻ ብሂል ሳያምን አይቀርም መሰል እንደፍቅር ደስ የሚል ረብሻ አለ እንዴ ? ምንም ህግ የማያውቅ ለምንም አይነት ህግ የማይገዛ ጋጠወጥ ስሜት እኮ ነው ደግሞ ማንቀዥቀዡ ተንቀዠቀዥኩ! ቢሮየ ውስጥ ወንበሬ ላይ ደገፍ ብየ እያንዳንዷን የልእልትን ቃል እከልሳታለሁ ደግሞ የእህቴ "ከዚች ልጅ ተጠንቀቅ " ምክር ያብሰለስለኛል ግን ለምን እንደሆነ እንጃ አልፈራም ልእልትን ከወደድኳት ጀምሮ ፍርሃት የሚባል ነገር ከስሜቴ መዝገበቃላት ተሰርዟል የልእልት ታሪክ ያሳለፈችው ውጣ ውረድ ነው እንደጅረት አይምሮየን ሞልቶ የሚፈሰው ከነአተራረኳ ከነውብ ፈገግታና ሃዘኗ ልእልት ልእልት የወንዴ አንበሳው ሚስት ልእልት የእኔ ልእልት የእኔና የወንዴ አንበሳው ልእልት እንዲህ አለችኝ እንደኩሬ ውሃ ጥርት ባሉ አይኖቿ ግድግዳውን እየተመለከተች

**** **** *****

" በቃ ወንዴ ካኮረፈኝ ጀምሮ ፊልም አስጠላኝ መውጣት ከበፊቱም አልወድም ቁጭ ብየ እቆይና እተኛለሁ እነሳለሁ አንዳንዴ የተዘጋጀውን ቤት እንደገና እመነቃቅረውና ማዘጋጀት እጀምራለሁ (ምንድነው የሚባለው ስራ ያጣ መነኩሴ ምኑን ቀዳዶ ይሰፋል እንደሚባለው) የቁም ሳጥኑን ልብስ ተጣጥፎ ከተቀመጠበት እየጎለጎልኩ አወጣና እንደገና እያጣጠፍኩ መደርደር መሰቃቀል እጀምራለሁ እያንዳንዱ ልብሴ ላይ ትዝታ አለኝ እያንዳንዱን ቀሚስ ባነሳሁ ቁጥር ለብሸ የሄድኩበት ሬስቶራንት የሄድኩበት ኮንሰርት ተግተልትሎ ወደአእምሮየ ይመጣል ቁም ሳጥኑ ልብስ ሳይሆን ትዝታ የታጨቀበት ይመስለኛል አየህ አብርሽ (((ልብስ ሰውነታችንን መሸፈኛ ግርዶሽ ብቻ አይደለም እያንዳንዱ ውሏችን፣ ባህሪያችን፣ የኑሮ ደረጃችን፣ ፍላጎትና ምኞታችን ጭምር የሚፃፍበት የሚለበስ ብራና ነው !! "))) ልእልት በለበሰችው እጅጌ ረዥም ሹራብ ወደመዳፏ እጅጌውን ሳብ አድርጋ እንባዋን እንደህፃን ልጅ በልብሷ ጠራረገች

"በፊት በፊት ገደል መስሎ የሚታየኝ የቤት ስራ አሁን ሳልጀምረው ያልቅብኛል ቀኑ አይሄድም (ቀኑ እንዴት እንደሚንቀረፈፍ አብርሽ ) በረንዳ ላይ ወጥቼ እቆማለሁ ዝም ብየ ከላየ ወደታች አላፊ አግዳሚውን አያለሁ በደህናው ጊዜ ስራ ሲሄዱና ሲመጡ ወደትምህርት ቤት ዩኒፎርማቸውን ለብሰው የሚሄዱ ተማሪዎች ያሳዝኑኝ ነበር እንዲህ የሚደክሙት እንደኔ ለማረፍ ነበር የሚመስለኝ አሁን ግን ቀናሁባቸው ቢያንስ የሚሄዱበት ቦታ አላቸው ! ብዙም በረንዳ ላይ አልቆይም የጎረቤቱ አይን ሊበላኝ ይደርሳል ኑሮየ መበጥበጡን የሰሙና የሚስቁብኝ ይመስለኛል ለምን እንደሆነ እንጃ ሁሉም ጎረቤቶቻችን አይወዱኝም በኋላ ነው የተረዳሁት ይሄንን

አብርሽ."ጫት መሃበራዊ ኑሮን ያበረታታል ሰው ጋር ያቀራርባል ምናምን ሲባል ሰምተህ ይሆናል ውሸት ነው !! ውሸት !! ጫት የመጨረሻ ግዴለሽ ነው ሚያደርግህ ጫት እየቃምክ የምትቅምበት ቤት ተቃጠለ ቢሉህ እንኳን መነሳት ሸክም ነው የሚሆንብህ ከቃሚ ጓደኞችህ ውጭ ለዘመድ ግድ የለህ ጎረቤቶችህ ሰው ይሁኑ አውሬ ቀና ብለህ አታያቸው ቢታመሙ ቢቸገሩ አታስታውሳቸው መሃበራዊ ኑሮህን ግድል ነው የሚያደርገው ግድል! በቃ እያለህ የለህም !! አይገርምህም እንኳን ሌላ ቦታ መሄድ ኮካ ምናምን ምንጣፍ ላይ ሲደፋ እንኳን ከፍራሽህ ተነስተህ መወልወያ ማምጣት እዳ ነው ሚሆንብህ ስንት የሚቆጨኝ አጋጣሚ አለ መሰለህ እየቃምኩ እናቴ ደውላ እንደምትፈልገኝ እየፈራች ስትነግረኝ እቤት ላለመሄድ ሰበብ ደርድሬ የቀረሁበት ጊዜ አለ." ልእልት ሳግ እየተናነቃት አለቀሰች ውስጧን በቁጭት ያቃጠላት ነገር አለ በተለይ "እናቴ" ስትል ጉሮሮዋ ላይ አንዳች ነገር የተሰነቀረባት ነበር የምትመስለው ዝም ብየ አያታለሁ ከቃላት በላይ ፊቷ ላይ ያለው ሃዘን ብዙ ነገር ይናገር ነበር !

"አንድ ቀን ያች እማማ ቁንጥሬ የሚባሉት ሴትዮ ቤት ቡና ተፈልቶ ጎረቤቶቹ ሁሉ ሲሳሳቁና ሲጫዎቱ በረንዳ ላይ ቁሜ አያቸዋለሁ እንዴት እንደቀናሁ አብርሽ ቢጠሩኝ "እሽ" ብየ ነበር የምገባው እንደውም አትታዘበኝና የሆነ እንዲያዩኝና ነይ ምናምን እንዲሉኝ በረንዳው ላይ ወደደረጃው በኩል ጠጋ ብየ ቆምኩ ቡና ፈልጌ አይደለምኮ ሰው ናፈቀኝ በቃ እኩያቶቸ አይደሉም ግን ምንም ይሁኑ ራሴ ከመፈንዳቱ በፊትና ልብሴን ጥየ ከማብድ የሆነ ሰዎች መሃል መሆን ፈለኩ ልክ እንደሱስ ለካ የሰውም ሱስ ይዞኝ ነበር ከህፃንነቴ ጀምሮ ወንዴ ጋር እስክንጣላ በሰው

አጀብ መሃል ነበርኩ ዛሬ ራቁቴን አስቀሯት ነብሴን ሳቃቸው ጨዋታቸው ናፈቀኝ እስቲ አሁን ሌላው ሁሉ ቢቀር ያ እባብ ኢያሱ ይናፍቃል? አብርሽ ሙት የወንዴ ጓደኛ ኢያሱ ናፈቀኝ ቆይ እኔ የዚህ አገር ልጅ አይደለሁም እንዴ ብየ አሰብኩ የሆነ አረብ አገር ምናምን ብቻቸውን ጓዳ ውስጥ ይዘጋባቸዋል እንደሚባሉት ሴቶች አረብ አገር ያለሁ መሰለኝ አዲስ አበባ ያለሁ አልመስል አለኝ ዝም ብየ የእማማ ቁንጥሬን በር በራቸውን እያየሁ ቁሚያለሁ እማማ ቁንጥሬ ድንገት ወጥተው በር ላይ የከሰል ፍም ትርክክ ብሎ የተያያዘበትን ምድጃ አንስተው ሊገቡ ቀና ሲሉ አይን ለአይን ተገጣጠምን ሰላም ልላቸው ፈለኩ ያኔ ስማቸውን አላውቀው ምን ብየ ሰላም እንደምላቸውም ግራ ገባኝ መቸም ትልቅ ሰው ናቸው ሰላም ይሉኛል ብየ አይን አይናቸውን ሳይ “የምን እንደ ቁሪስት ሰው ላይ ማፍጠጥ ነው ተኮርቶ ተሙቷል “ ብለው ወደቤታቸው ገቡና በራቸውን ፊቴ ላይ ደረገሙት አዘጋጋቸውን ብታይ ተናካሽ ውሻ የሚያሯሩጣቸው ነበር የሚመስሉት ! ምንምኮ አላደረኳቸው አለም ሁሉ ፊቱን ያዞረብኝ ነው የመሰለኝ ሽክክ ብየ እቤት ገባሁና አርፌ ቁጭ አልኩ እስከማታ ከተቀመጥኩበት አልተንቀሳቀስኩም! “ በቃ ባዶ ቤት እንዲቹ ስንቆራጠጥ ይመሻል ወንዴ ይመጣል ደግሞ ማታ ሲመጣ አያመሽም በጣም ቆየ ከተባለ እስከአንድ ሰአት ነው አይገርምህም አብርሽ ባያናግረኝም መምጣቱ ውስጤን ያስፈነድቀዋል ወንዴ ብርቅ ይሆንብኛል ቤት ውስጥ የማይናገር የማይጋገር መንፈስ የገባ እንጅ ሰው የገባ አይመስለኝም አናወራም ባናወራም ካሁን አሁን የሆነ ቃል ከአፉ ወጥቶ ይፈውሰኛል እያልሁ እንደፈጣሪ ቃል የወንዴን ድምፅ በጉጉት እጠብቃለሁ ! ይገዝፍብኛል ወንድ ቤት እግርና እጁን ብቻ ይዛ የገባች ሴት ታላቅነቷ ፍቅር እስካለ ብቻ ነው ፍቅር ያከተመለት ቀን በስፒል እንደወጉት ፊኛ መንፈሷም ታላቅነቷም እየሞሸሸ ከባሏ እግር ስር ነው ኩርምት የምትለው!! ወንዴ ገብቶ ይተኛል ሰላምታ የለ ምን የለ ወደኔ ሁሉ አያይም መአም ማን ይመጣል ብሎ እንጅ ሶፋ ላይ በእኔ ምትክ የሆነ ሰውየ ተቀምጦ ቢጠብቀው እንኳን የሚለየን አይመስለኝም ወደምኝታ ቤት ሲገባ የእርምጃው ፍጥነት ላይ የሆነ መልክት አለ “እዚሁ ሳሎን ተኝ እንዳትመጭብኝ የሚል” የሆነ መግፋት አለ ! ፀብም እኮ አይነት አይነት አለው እንዲህ ጋግርታም ፀብ እንዴት ይቀፋል መሰለህ በባልና በሚስት መሃል ሳይሆን በሟችና በገዳይ መካከል ግድያው ከመፈፀሙ አንድ ሰዓት በፊት የሚኖር አይነት የመረረ ኩርፊያ ነበር !

ሰው እንዴት እንዲህ ባንዴ ይቀየራል እያልኩ አስባለሁ ቀን እንዲሁ ሰውነቴ ስለማይደክም ነው መሰል ሌሊት እንቅልፍ ያስቸግረኛል እንቅልፍ የወሰደው ሰው አጠገብ እንቅልፍ እንደማጣት የሚያሳቅቅ ነገር የለም መገላበጥ ራሱ ያስፈራሃል የምረብሸው እየመሰለኝ እጨነቃለሁ ወንዴ ድብን ያለ እንቅልፍ ይወስደዋል ሌሊቱ ከቀኑ የበለጠ ረዥም ነው አንድ ነገር ታዲያ ይከነክነኝ ጀመረ ሌላው ሁ......ሉ ነገር ይቅር እሽ ግን ወንዴ የወሲብ ፍላጎቱ የት ሄደ ?” ልእልት ይችን ቃል ስትናገር እንደማፈር አለች እፍረቷ በምሬት የተቀየጠ ነበር !

“ቢያንስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተጋጨን በኋላ (ከተጋጨን ልበል እንጅ ) ከሃያ ቀን በላይ እንዲች ብሎ አልነካኝም....ያ እንኳን አንድ አልጋ ላይ አጠገቡ ተኝቸ በጓደኞቹ መሃል እንኳን አይኑ ሲያርፍብኝ አይኑ በእኔ ፍላጎት የሚንቀለቀል ልጅ እጀ ሲነካው በደስታ የሚቃትት ልጅ ...ያ በሰው መሃል ሳይቀር አጉል ቦታ እየነካ የሚያሳቅቀኝ የሚያቅበጠብጠው ልጅ እንደሃረግ እኔ ላይ ካልተጠመጠመ የማይቆም ልጅ እንዲህ ነገር አለሙን ትቶት ለሽ የሚልበት መረጋጋት ከየት አመጣ እንዲሁ ይከነክነኝ ጀመረ እንዴ እንዲሁ መቅበጥ አምሮኝ እንኳን ጀርባየን የሰጠሁት ቀን(አለ አይደል ነገ የተም አትሂድ ብየው የሆነች ጉዳይ አለችኝ ደረስ ብየ ልመለስ ምናምን ብሎኝ ነገር ) ጆሮ ግንዴ ስር ከንፈሩን ደቅኖ የሚያንቆረቁርልኝ የማለማመጥና የቁልምጫ መዓት ፊቴን ወደሱ ካላዞርኩ በስተቀር አይቆምም ነበር እኔም አልጨክንበትም ነበር ያው መቆላመጡን መለመኑን ፈልጌ እንጅ

እና ዛሬ ምን ተፈጠረ ...

ከምር ምን ተፈጠረ ....አለችና አምስቱንም የግራ ጣቶቿን ውጥር አድርጋ ዘርግታ ቀለበት ያለበትን ጣቷን በትኩረት ስትመለከት ቆየች (ቆንጆ ጣቶቿን የምታደንቅ ነበር የምትመስለው ) ግን ልንገረው አልንገረው የሚል ማንገራገር ፊቷ ላይ ያየሁ መሰለኝ ደግነቱ ራሷ ቀጠለች

"አንድ ቀን ሌሊት ወንዴ እንቅልፍ ሳይወስደው ልክ እንቅልፍ እንደወሰደው ሰው ሲተነፍስ ታወቀኝ (ይችንማ ስንት ቀኔ እኔ ሳደርጋት ትጥፋኝ እንዴ እስቲ አሁን ምን ድራማ ያስፈልጋል...) እናም ማረጋገጥ ፈለኩ አየህ በዛች ቅፅበት ወሲብ ፈልጌ አልነበረም በጭራሽ ግን ቁርጤን ልወቀው ብየ ነው ለወንድ ልጅ የወስቢ ፍላጎቱን የሚያስገፋ ስሜት በልቡ ካደረ ነገሩ ቁርጥ ነው ፍቅር ሙቶ መተሳሰብ አፈር በልቶ እንኳን ወንድን ልጅ እንደቀጭን ክር ከሴት ጋር አያይዞ የሚያቆየው ወሲብ ስሜቱ ነው እሱን ከገፋ እናም ወንዴን ጠጋ ብየ ከኋላው አቀፍኩት እንዳልሰማ ሰው ዝም አለ ... (ትንፋሹን ዋጥ ሲያደርጋት ግን ገብቶኛል እንዳልተኛ) ጡቶቸ ጀርባው ላይ እስኪጨፈለቁ ተለጠፍኩበት በረዥሙ ተንፍሶ ወደኋላ በትከሻው ገፋ አደረገኝና ተነስቶ መብራቱን አበራ የአልጋ ልብሱን ጓፎ ከአልጋው ላይ አነሳና እየጎተተ ወደሳሎን ሄደ በቃ ሳሎን ሂዶ ተኛ !!" ብላኝ "አትገረምም እንዴ " በሚመስል አስተያየት ትክ ብላ አየችኝ ".ከምሽቶችም በጣም የጨለሙች ምሽት አለች ከጥላቻም አጥንትህን ሳይቀር ሰነጣጥሮ የሚጥል ጥላቻ አለ ከንቀትም እንደበረዶ የሚያገግርህ ንቀት አለ ...ፍቅርህ ሲናቅ ስጋህም ይናቃል ወንድን ልጅ ሁልጊዜ እንደውሻ ስጋ እየጣልክ ወዳንተ አታመጣውም አንዳንዴ ከውሻም የባሰ አውሬ ሁኖ ጫካ ውስጥ ያጠመደውን ስጋ እንክት አድርጎ መጥቶ ይሆናል ! የወንዴ ነገር እስካሁን "ነጋችንን እናስተካክል " በሚል ተራ የነገ ህልም ነበር ሲያመናቅረኝ የነበረው አሁን ግን ነገ አብረን ስለመሆናችንም ተጠራጠርኩ ስለዚህ ወንዴ ገደል ይግባ ለሱ ብየ እስረኛ ሁኛለሁ ትምህርቴን ትቻለሁና ካሳ ይገባኛል የሚል ሃሳብ ልቤ ውስጥ ተጫረ አብሮ ለመሻገር ሳይሆን ድርሻየን ይዠ ለማምለጥ ብቻ ማሰብ ጀመርኩ" እኔ " ብቻ ሆነ አጀንዳየ ! ደግሞ አፈርኩ ወንዴ አሳፈረኝ አያናግረኝ ግን እንደቆሻሻ ሲፀየፈኝ አሳፈረኝ በዛች ቅፅበት ብችል እኔም ወንዴ ከሸሸው ሰውነቴ ወጥቸ ወደሆነ ጥግ ብደበቅ ደስታየ ቆዳየን እንደልብስ አውልቄ እዛው አልጋው ላይ ጥየው ወደልጅነቴ ማንም ወዳልነካው ወንዴም ወደሚንሰፈሰፍለት ልጅነቴ ብሸሽ ደስታየ እንዲቹ ስንገበገብና ስገላበጥ ሊነጋ አካባቢ እንቅልፍ ወሰደኝ!

ስነቃ ረፍዶ ነበር እንደውም የምሳ ሰዓት እየተቃረበ ነበር ወንዴ የለም ተነስቸ በፒጃማ ሳሎኑ መሃል ቆምኩ ወንዴ ለብሶት ያደረው ብርድ ልብስ ግማሹ መሬት ግማሹ ሶፋው ላይ ተዝረክርኮ ተቀምጧል የሌሊት ልብሱ የሶፋው ጠረጴዛ ላይ በግዴለሽነት ተጥሏል ታውቃለህ ወንዴ ተጣላን ብየ አይዋሽም መዝረክረክ የማይወድ ልጅ ነበር ቢሞት የተኛንበትን አልጋ እንኳን ሳያነጥፍ አይወጣም ልብሱንማ ሲያጥፍ ትኩረቱ ራሱ የሆነ ተአምር የሚሰራ ነው የሚመስለው እንግዲህ ይሄ መዝረክረክ "ይህን እንኳን ሰርተሽ ብይ " የሚል ንቀት መሆኑ ነው ዝም ብየ ቤቴን አፀዳዳሁ ፍሪጅ ውስጥ ያገኘሁትን ወተት ጠጥቸ መልሸ ወደምኝታ ቤት ገብቸ ተኛሁ በሽተኛ የሆንኩ ነው የመሰለኝ ሻወር እንኳን ለመውሰድ አቅም አነሰኝ ከውስጤ የሆነ ነገር ተንጠፍጥፎ ሲያልቅ ይሰማኛል ! ብርሃን ማየት አስጠላኝ ሽፍንፍን ብየ ተኛሁ መደበቅ በለው ከማን እንደምደበቅ እንጃ እናቴ ጋር መሄድ ፈልጌ ነበር ግን እንደዚህ በተሰበረ ልብ መሄድና የእሷን አይኖች ፍተሸ በማስመሰል አልፌ ልሸውዳት አልችልም የእኔ ፊት ለእናቴ መፅሃፍ ነው ታነበዋለች "ምን ሆንሽ ብትለኝ ምን እላለሁ" ይሄን እያሰብኩ እንደተኛሁ በሬ ሲንኳኳ የሰማሁ መሰለኝ ምን እንዳስበረገገኝ እንጃ ዘልየ ተነሳሁ (ሰው መናፈቅኮ ነው አብርሽ ) እንደገና ተንኳኳ ማንም ይሁን ሌባ ነብሰ ገዳይ ምንም ይሁን ብቻ ሰው ቤቴን አንኳኳ እንኳን እኔ በሩም መንኳኳት የሰው እጅ የናፈቀ ይመስለኛል ድምፁ ሙዚቃ ነው የሆነብኝ ማነው እንኳን አላልኩም በሩን ከፈትኩ ኢያሱ !! ማመን አልቻልኩም በጉያው በጋዜጣ የተጠቀለለ ጫት ይዟል ፈገግ አለ ታምናለህ አብርሽ ያ መጥፎ ልጅ አልመስልሽ አለኝ ዘልየ ብጠመጠምበትና ብስመው ደስታየ ዝም ብየ አየሁት" ምነው መግባት ተከለከለ እንዴ " አለኝ ተሳሳቅን እቤት ገብቶ ጫማውን ሲያወልቅ ጫቱን ሶፋው ላይ ወርወር አድርጎ ፍራሹ ላይ ሲቀመጥ ዝም ብየ እንደ እንግዳ ፍጥረት አየዋለሁ በሩን እንኳን አልዘጋሁትም እንደውም እንባየ መጣ" ዛሬ ልእልትን ሳላያት አልውልም ብየ ሳልነግራቸው ሹልክ ብየ መጣሁ አላስችል አለኝ ጀመዓውማ ከቤቷ አባረረችን ብሎ አድሟል ሃሃሀሀ " አለ ሊያየኝ ስለመጣ ደስ አለኝ አሁን ገና ነው በአጭር የሌሊት ልብስ መሆኔ ትዝ ያለኝ ከውስጥ እንኳን ምንም ነገር አለበስኩም በሩን ዘግቸ ወደመኝታ ቤት ገብቸ ያገኘሁትን ፒጃማ አጥልቄ ፀጉሬንም እንደነገሩ አስተካክየ ወጣሁ የሆነ አመትባል ነው የመሰለኝ የኢያሱ ማንነት ያ የምፈራው ነገሩ ሁሉ ከአእምሮየ ድራሹ ጠፍቶ እንዲሁ ውስጤ ሲቀርበው ተሰማኝ ምሳ ልሰራ ቡናም

ላፈላለት ጉድ ጉድ ማለት ጀመርኩ እንደውም እንደገና እርም ብየ የተውኩት ጫት አምሮኝ እርፍ !! ምናለበት አንድ ሁለት ቅጠል ብነክስ ?

ካላበድኩ በስተቀር እንዲህ አስታውሶኝ የመጣ ልጅ እንደገና አላስቀይም መቸስ

“ተጫወት “አልኩት

“ ምኑን ተጫዎትኩት ትተሽኝ ጠፋሽኮ “ አለኝ በፈገግታ

”መጣሁ እኔም አልበላሁም ምሳ እየሰራሁ ነው .....”

“አምሮብሻል ደግሞ ...” አለኝ ከእግር እስከራሴ እያየኝ

“ምን ያምርብኛል ድብር ብሎኝ ነበር ባክህ” አልኩትና ወደኪችኔ ተመለስኩ ግን ከበረዶ ግግር ውስጥ ወጥቶ ፀሃይ እንደነካው አይነት አድናቆቱ ሰውነቴን ፈታ ሲያደርገው ተሰማኝ

## ክፍል 16

“ ኢያሱ እቤት እንደተቀመጠ ወጣሁና እንጀራ ገዝቸ ተመለስኩ በቅቤ እብድ ያለ ፍርፍር ሰራሁና (ኢያሱ ፍርፍር እንደሚወድ የሆነ ጊዜ ሲናገር ሰምቸ ነበር) አቀራረብኩ ቡና አፈላሁ(አላሳዝንህም አብርሽ ኢያሱ እንዳይሄድብኝ መንከባከቤኮ ነው በቃ ሽር ጉድ አልኩ ) በየመሃሉ ኢያሱ ያወራኛል” ልእልትየ ባክሽ አትቸገሪ እኔ ናፍቀሽኝ አንችን ላወራሽ ነው የመጣሁት ድምፅሽ የዋህነትሽ ሳቅሽ ሁሉ ነገር ነው የናፈቀኝ “ ይለኛል እንዳልሆነ ባውቅም ውስጤ ግን ደስ አለው አየህ የብቸኝነት ገደል ውስጥ ተንኮታኩተህ ከወደክ የሚላክልህ እጅ የማንም ይሁን ትጨብጣለህ ከገባህበት ገደል መውጣት ብቻ ነው ህልምህ ኢያሱ ሲያወራኝ ደስ እያለኝ እሰመዋለሁ እሱም ካለወትሮየ የሰጠሁት ፊት አደፋፍሮት ዝም ብሎ ያወራልኛል” ሌሊት ድንገት ትዝ አልሽኝ በቃ ይች ልጅ ማን ጋር ትውላለች ማን አላት እያልኩ አስባለሁ ስንት ነገር የለመደች ልጅ ሰው ከቧት ያደገች ልጅ ብቻዋን ባዶ ቤት ዛሬማ ሳላያት አልውልም ብየ “በቃ እናንተ ቃሙ እኔ ዛሬ ልእልትየ ጋር ነኝ” ብያቸው መጣሁ ወንዴን ና እንሂድ ስለው አልሄድም አለኝ የራስህ ጉዳይ ብየው መጣኋ እንኳን መጣሁ ሳይሽ እንዴት ደስ እንዳለኝ ልክ ነኝ አይደል እንዴ በዚህ ሁኔታ ሰው የሚያስፈልግሽ አንች ነሽ ልእልትየ ብቸኝነትን አውቀዋለሁ” እያወራ ያለው ኢያሱ ነው ይታይህ ኢያሱ ተንኮለኛ በሌላ ነገር የሚፈልገኝ ነገረ ስራው ሁሉ እንደሂሳብ ስሌት የተሰላ መሆኑን አውቃለሁ በኢያሱ ህይዎት ውስጥ ኢጋጣሚ ብሎ ነገር የለም !! ምናልባት ዛሬ እኔ ጋር እንደሚመጣ ከነሰአቷ ከአስራ አምስት ቀን በፊት ይሆናል ያሰበው ቢሆንም አመንኩት ! አብርሽ እውቀት ሁልጊዜ ጉልበት አይሆንም ማጨስ ይጎዳል ሁሉም ሰው ይሄንን ያውቃል መጠጣት ይጎዳል ህፃን ልጅም ያውቃል ግን እውቀትህን ተጠቅመህ ከሚመጣው ችግር ለመዳን ጉልበት ያስፈልግሃል ሰው ደግሞ ያንን ጉልበቱን በተለያየ ምክንያት ይቀማል ይነጠቃል. እኔም ተቀምቻለሁ ወንዴ ከነጓደኞቹ ባዶ ቤት እንደምናምንቴ ጥለውኝ ሂደው በራስ መተማመኔን ሁሉ ነገሬን ሰልበውኛል ትንሽ ንፋስ ቢነካኝ የትም የምወድቅ አቅመቢስ አድርገውኛል

ልእልት ስታወራኝ ተመስጬ እሰማታለሁ አንዴ ምን ታድርግ እያልኩ ደግሞ መልሽ የፈለገ ቢሆን ኢያሱ ጋር ምንም ነገር መፈጠርማ የለበትም እያልኩ (ኧረ እንደውም ኢያሱ ጋር የሆነ ነገር ቢከሰትስ ብየ እንደቅናት ሁሉ ጀመረኝ እስቲ ምን ባይ ነኝ ባሏ እያለ ) ልእልት በየወሬው መሃል የሚዘረገፍ እንባዋን እየጠራረገች ቀጠለች

“ .....ቤቱ የበፊት ድምቀቱ ተመለሰ የቡናውና የእጣኑ ጭስ ተቀላቅሎ ሙዚቃው ለሰስ ብሎ ተከፍቶ በዛ ላይ የኢያሱ የማፅናኛ ወሬ ሲዘንብ(መቸም ወሬ ይችላል) በብቸኝነት የደረቀ ልቤ እያንዳንዱን የቃሉን ጠብታ እንደደረቀ መሬት ዝናብ እንደናፈቀው ይመጠዋል ኢያሱ ምን መናገር እንዳለበት ያውቃል ምሳ ስንበላ አጎረሰኝ እያጎረሰኝ ያወራኛል እያወራኝ ያጎርሰኛል የንግግሩን የእጁን ፍጥነት መቋቋም ሁሉ አልቻልኩም ኢያሱ ፈጣን ነው ! ምሳ በልተን ስንጨርስ ጫት አቀበለኝ ተቀበልኩ !! ልክ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደቃመ ሰው ጫቱን አላምጨ

ጭማቂውን ስውጠው ምሬቱ አንገሸገሸኝ የተጨቀጨቀ ግራዋ በጉሮሮየ የተደፋ ነበር የመሰለኝ ቢሆንም የረሳሁት ምሬት የረሳሁትን ጣፋጭ የፍቅር ጊዜ ጎትቶ ውስጤን ሞላው ድባቡ ውስጤን አገለባበጠው ከምንም በላይ ደግሞ ኢያሱ ሲሄድ ወደዛ አሰቃቂ ብቸኝነቴ አንደገና እንደምመለስ ሳስብ ሳላስበው እንባየ ተዘረገፈ ! ኢያሱ ተጠጋኝና እጁን ትከሻየ ላይ አስቀመጠ ሲነካኝ ስቅቅ አለኝ እሱም በሰውነቴ መንቀጥቀጥ ሳይደነግጥ አይቀርም አብርሽ እኔኮ ከወንዴ ውጭ ሰውነቴን ነክቶት የሚያውቅ ወንድ አልነበረም" ምን ሆንሽ ልእልቴ ችግር አለ ንገሪኝ እኔ ወንድምሽ ማለት ነኝ " እያለ ነዘነዘኝ ኢያሱ በቃ አልቻልኩም በእኔና በወንዴ መሃል የተፈጠረውን ነገር ሁሉ ዝርግፍ አድርጌ ነገርኩት ዝም ብሎ ሲሰማኝ ቆየና

"አውቄ ነበር የሆነ ነገር መፈጠሩን አውቄ ነበር ልጠይቅሽ አስብና ግን በእናተ ትዳር ጣልቃ መግባት እንዳይመስልብ እያልኩ ዝምታን መረጥኩ ይገባኛል ልእልቴ እንደበፊቱ እንዳልሆንሽ በደንብ አውቂያለሁ ያ ውብ ፈገግታሽ የት አለ...ያ ደስታሽ የት አለ አንድ ቀን ግን አላስችለኝ ብሎ ወንዴን "ለምን ልጅቱን በብቸኝነት ትቀጣታለህ ...ዋ በኋላ ወጣ በትል እነዛን ውብ እግሮቿን ስሞ የሚቀበላት ወንድ የምታጣ እንዳይመስልህ አንተን ብላ ነው እቤት ታሽጋ የምትውለው አንተን ብላ ነው እኩዮቿ ሲዝናኑ ሲደሰቱ ልእልትየ ቤተሰቦቿ ጋር እንኳን የማትሄደው አንተን ብላ ነው አልኩት ጫቱን እያመነዠገ" ትሂዳ" አለኝ " አለና ኢያሱ ፍራሹን በቡጢ ጠልዞ" በቃ በዚች ቃሉ ወንዴ ጋር ተጣላን ጫታቸውን ወርውሬላቸው ከዛ ቤት ቀረሁ በስንት ልመና ጓደኞቻችንን ሁሉ ልከው ሲነዘንዙኝ ነው የታረቅነው "

"ትሂዳ አለ ወንዴ " ብየ ኢያሱን ጠየኩት የሆነ ነገር ውስጤ ድቅቅ ሲል ተሰምቶኝ ነበር

"ልእልትየ አንች እንደማታደርጊው አውቃለሁ ግን ወንዴ ያው አስተሳሰቡ ትንሽ አስቸጋሪ ነው ለብር ብለሽ እንደቀረብሽውና ለቤተሰቦችሽ በድብቅ ብር ስትልኪ እንደማያውቅ ዝም እንደሚልሽ ጭራሽ አሁን ደግሞ ቤት መኪና ምናምን በስምሽ እንድገዛላት ምናምን እንደፈለግሽ ነው የነገረን " ዝም ብየ በእልህ ጫቴን መቃም ጀመርኩ ኢያሱም ከዛ በኋላ ብዙም አላወራኝም ድንገት ቡናው ገንፍሎ ምንጣፉን ሲያጥለቀልቀው ነው የባነንኩት ተነስቸ በሩን ከፈትኩና መወልወያ አምጥቸ ምንጣፉን ወለወልኩ መወልወያውን መልሽ ከምድጃው ላይ የተነሳው ጭስ እንዲወጣ በሩን ገርበብ አድርጌ ተውኩት ነገሩ ግን አንገበገበኝ ወንዴ እኔን "ትሂዳ " አለ ማለቱንስ ይበል ምናልባት ዛሬ "ትሂዳ " ካለ ነገ "ሂጅልኝ " ካለኝ የት አባቴ ነው የምሄደው መቸም እናቴ ጋር አልሄድም እንደገና ውርደት እንደዛ ምድር መሬት ጠቦኝ በኩራት የወጣሁ ልጅ እዚሁ አዲስ አበባ ተቀምጣ "አንዳንዴ እንኳን ብቅ ብለሽ እይኝ እንጅ መኪና አላችሁ " እያለች ስትለምነኝ እንኳን ደጇን መርገጥ የከበደኝ እኔ ዛሬ እንደተባረረች የቤት ሰራተኛ ልብሴን አንጠልጥየ ወደ እናቴ ቤት ስሄድ ኤጭ! ሰው ዝም ብሎ ቆንጆ ሴት መሄጃ አታጣም ይላል እዚች አገር እንደቆንጆ ሴት መሄጃ የሌላት ፍጥረት የለችም የት ትሄዳለች የሄደችበት ሁሉ ማንም ሰውነቷን እንጅ ሴትነቷንም ሰው መሆኗንም አስታውሶ የሚቀበላት የለም የት ትሄዳለች ያልተማረች ብር የሌላት ቆንጆ የት ትሄዳለች ወንድ አባረረኝ ብላ ሌላ ወንድ ጋር ? ወይስ ቡና ቤት? እንደቆንጆና ደሃ ሴት ዋስትና የሌላት ፍጥረት የትም የለችም በውድ መኪና ጋቢና ተቀምጨ ስቀማጠል ተሰልፈው ታክሲ የሚጠብቁ ሴቶች ቀንተውብኝ ይሆናል ለዚች አገር ብዙ የሰሩ ላባቸውን ጠብ ያደረጉ ሰዎች በውስጣቸው እነሱ ጠብ በማይል ከወር እስከ ወር ደመዎዝ ተራራ ችግሯን ሲገፉ ምንም ሳንሰራላት እኔና መሰሎቸን በማቀማጠሏ በአገራቸው አዝነው ይሆናል ግን አገራቸውና አገሬ ዛሬ አየር ረግጨ ከወጣሁበት ከፍታ ስምዘገዘግ መውደቂያ ሜዳዋን ከማዘጋጀት ውጭ ምንም ልታደርግልኝ እንዳልቻለች ባዩልኝ !!

ከፍቅር የተሰናበተች ሴት ምን ሊዘጋጅላት ነበር ድሮስ ጡረታ አይዘጋጅ ነገር ! ወንዴን እወደዋለሁ ሁሉም ነገር ይቅር ብሩም ምኑም ይቅር እኔም ዛሬውኑ ሂጀ ጎዳና ልውደቅ ግን በዚች አለም አለኝ የምለው አንድ ነገር እሱም ለወንዴ ያለኝ ፍቅር እንዲህ በቀላል አለመግባባት እንደእቃቃ ቤት ፍርስርስ ብሎ ሲወድቅ የውጭ ሰው ባይገባው እንኳን ፍቅሬን እንዴት ወንዴ እውቅና ይንሳው ??? ወንዴን ነፍሴ እስኪወጣ እወደዋለሁ ይሄን ሁሉ ጊዜ መንሰፍሰፌ ለብሩ እንደሆነ ነበር ማለት ነው የሚያስበው ይሄን ሁሉ አመት እጆቸ የማንን እጅ ጨበጡ ይሄን

ሁሉ ዘመን ወጣ ብሎ እስኪመለስ አይኖቹ ማንን ተርበው ጠበቁ ይሄን ሁሉ ዘመን ማንንም ያለመደ ሰውነቴ ለማን ተንተተ የማንን እቅፍ ናፈቀ ከውስጤ ተፈንቅሎ የሚወጣ ሳቄና ደስታየስ በማን ነበር ወንዴኮ አገባኝ ሳይሆን አሳደገኝ ነው የምለው አብርሽ"

ልእልት ስርቅርቅ አለች በቁጭት በፀፀት ያንን ሁሉ ውድ ሬስቶራንት ይሄን ሁሉ ውድ ልብስና ጌጣጌጥ ማን ገዛልኝ ማን አሳየኝ ወንዴ ነው እኔማ ተራ ካፌስ የት አባቴ አውቅ ነበር እንኳን ግዛልኝ ልለው ከነመኖሩም ሰምቸው የማላውቀውን ልብስ ጫማ ሁሉ ወንዴ ነው እያመጣ የቀለለው ወንዴ ነው ካለበሽ ብሎ እንደህፃን ልጅ ከተቀመጥኩበት አንስቶ እያለበሰ የራሴን ሰውነት እንደሌላ ሰው ሰውነት በግርምት እንዳየው ያደረገኝ ውጭ ቆይቶ ሲመጣ ልጇን እንዳገኘች እናት ይዞልኝ የመጣውን ነገር ሳይሆን ወንዴን በናፍቆት ተንሰፍስፌ ስጠመጠምበት ያች ቤታችን አፍ አውጥታ ብትመሰክር ስንት ነገር ትል ነበር ገዝቶ ያመጣልኝ ልብስ ከነፌስታሉ አስቀምጨ ሳምንት ዙሬ ባለማየቴ ወንዴ ስንት ቀን ተበሳጭቶብኛል ! አንድ ቀን ቻፕስቲክ እንኳን ግዛልኝ ብየው ካወኩ እግዚአብሔር ምስክር ነው በገዛልኝ ስልክ እንኳን ከወንዴና ከቤተሰቦቸ ስልክ ቁጥር ውጭ የአንድ ሰው ስልክ "ሴቭ" አድርጌ አላውቅምኮ ማንንስ አውቃለሁ ከወንዴ ሌላ የሃይስኩል ጓደኞቸን ገና በፊት ነው እርግፍ አድርጌ የተውኳቸው ወንዴ አለሜ ነበርኮ አብርሽ !!

በእርግጥ ለወንዴ ምንም አድርጌለት አላውቅም (ምን አለኝና ምን አደርግለታለሁ) ግን ማፍቀሬስ እንዲህ ከቁም ነገር የማይፃፍ ተራ ነገር ነው ማለት ነው? ውለታው ይከብደኛል አብርሽ እኔና ወንዴ ከተጋባን ጀምሮ ለቤተሰቦቸ ሰባራ ሳንቲም ሰጥቻቸው አላውቅም ሰባራ ሳንቲም !! ብር ስለነበራቸው ነው ? የእኔን እርዳታ ስለማይፈልጉ ነበር? አይደለም ግቢያችን ውስጥ አባባ ሳይሞት ያሰራቸው ሁለት ሰርቪስ ቤቶች አሉ እህቴና እናቴ እነዛ ሰርቪሶች ውስጥ እየኖሩ ዋናውን ቤት አከራይተው በዛች ኪራይ ነው እማማና እህቴ የሚኖሩት በቃ !ሌላ ቤሳቤስቲን የሚረዳቸው ዘመድ የለም ! ታናሽ እህቴ <ዩንቨርስቲ> ውጤት ሲመጣላት ወንዴን ነግሬው ያኔም የነገርኩት እንዲሁ ዩኒቨርስቲ መግባቷ በደስታ አሳብዶኝ እንጅ ምንም አስቤ አልነበረም ምን አስባለሁ እኔ ሰው ዩኒቨርስቲ ሲገባ ምን ይያዝ ምን ይተው ምናውቃለሁ አብርሽ... እና ያኔ ብዙ ልብስ ገዝቶላታል ብርም ሰጥቷታል ስልክ የገዛላትም እሱ ነው ወንዴ ለእኔም እኔ ለምወዳቸውም ሁሉ አድርጎ አይጠግብም ነበር በእህቴም ውጤት አንደእኔ እንደውም ከእኔ በላይ ነበር የተደሰተው ይሄው ነው ከዛ በኋላም ቢሆን ወንዴ በየጊዜው ብር እየሰጠኝ ላኪላት ይለኛል እልክላታለሁ ከወንዴ ተደብቄ የሆነ ነገር ማድረግ ቀርቶ የብር ጥቅም ሁሉ ሳይጠፉኝ አይቀርም በወንዴ ፍቅር አብጀ ነበር በዚች ምድር የእኔ ብቸኛ ሃብት የወንዴ ፍቅር ነበር !! በቃ እንባየ ተዘረገፈ አብርሽ እንደዛን ቀን አልቅሽ አላውቅም

ኢያሱ እንደህፃን አቅፎ አባባለኝ. የኢያሱን ኢያሱነትም ወንድነትም ረስቸ ደረቱ ላይ ልጥፍ ብየ እስኪበቃኝ አስነካሁት እራሴ ሊፈነዳ ደረሰ እኔኮ ለወንዴ ህፃን ነበርኩ የወንዴ እንክብካቤኮ ዝም ብየ ሳስበው ከአባት እንኳን ይበልጥ ነበር ታውቃለህ አብርሽ" ማንስትሬሽን " ላይ ስሆን እንደትልቅ ህመም ቤቱ በጁስና በፍራፍሬ ይሞላል ወንዴ ከአጠገቤ ቢሞት አይርቅም ቁጭ ብሎ አይን አይኔን ሲያየኝ ይውላል እንደውም ኩርምት ሲል አንጀቴ ይንሰፈሰፍለት ነበር በአንድ ሰዓት አራት ጊዜ "አሁንስ አንዴት ነሽ ያምሻል " ይለኛል በቃ ጭንቀት ነው !"

ልእልት በሚያሳዝን ፊት ትክ....ዝ ብላ ለረዥም ደይቃዎች ቆየችና በረዥሙ ተንፍሳ እነዛን አሳዛኝ ውብ እና ገራገር አየኖቿን አይኖቸ ላይ ተክላብኝ ለራሷ በሚመስል እና በታከተው ሰው ድምፅ" ወንዶች ቢያንስ ስትንከባከቡት የቆያችሁትን ፍቅር አንስታችሁ ስታፈርጡት ምን ላይ ያርፋል ብላችሁ እንኳን አትጨነቁም ምናይነት ልብ እንዳደላችሁ ግን!!" አለችና እንባዋ እንዳይፈስ ወደላይ ወደኮርኒሱ ቀና አለች ጥርት ያለ አንገቷ ላይ በጣም ቀጭን የወርቅ ሃብል አስራለች አንገቷ ከአገጪ ወደታች በስርአት ተቀርፆ ይወርድና ቀኝና ግራ የተሰመሩ የሚመስሉ አጥንቶቿ አጥረውት እንደውሃ ጉድጓድ ስምጥ ያለ የትከሻዋ ጉድጓድ ላይ ተተክሎ ሲታይ ውብ የእብነበረድ አምድ ይመስላል ልእልት ውብ ናት አንዳንዴ የእግዚአብሔር ጥበብ ይገርመኛል ሁሉም ቁንጅና የራሱ መስእብ ቢኖረውም እንዲህ አይነቱ የልእልት ቁንጅና ላይ አንዳች አስደማሚ መንፈስ የጨመረበት ነው

የሚመስለኝ ይህን ውበት የሚረብሸው ታሪክ ጦርነት መሰለኝ የተሰናከለ ፍቅር ው-ብ የጥበብ ከተማን ከሚያጠፉ ጦርነት እኩል ነው ! ጦርነትም የተሰናከለ ፍቅርም የበለጠ ለሴቶች ሰቆቃ ነው !

አይኖቿን ከጣራው ስትመልስ በጣም በወረደ ፀፀት እና ሃዘን በተሞላበት ድምፅ እንዲህ አለችኝ" ያኔ ... አልቅሽ ወጥቶልኝም ከኢያሱ ደረት ላይ ቀና አላልኩም ዝም ብየ በሃሳብ ነጎድኩ. አንጀቴ ውስጥ ገብቶ የሚያንሰፈስፈኝ ነገር ነበር ብዙ ነገር ነበር ግንብ ልደገፍ እያሱን ልደገፍ ጉዳየ አልነበረም ብቻ መንቀሳቀስም ማሰብም መተንፈስም ጭምር አስጠልቶኝ ዝም ብየ ነበር በዚች ቅፅበት ቡናው ሲገነፍል ቤቱን የሞላው ጭስ እንዲወጣ ብየ ከፍቱን በተውኩት በር ከሰማይ ይውረድ ከመሬት ይውጣ እንጃ ወንዴ ሰተት ብሎ ገብቶ ፊታችን ተደነቀረ !! ኢያሱ ደረት ላይ እንደተለጠፍኩ አይኔን ብቻ ቀና አድርጌ እንደሰመመን አየሁት ወንዴን ህልም ነው የመሰለኝ እግዜር ይፍታው ይሄን ህልም ...

# ክፍል 17

አንዳንዴ "የሁሉ ነገር ፈራጅ" እየተባለ የሚንቆለጳጰሰው ((ጊዜ )) የሚሉት ጉድ ራሱ እልም ያለ ውሸት አሳባቂ ይሆናል" !! ....አዎ ቀን አቃጣሪ ይሆናል ቀን አሳብቆ እና አሳቅሎ እዚህ ግባ የሚባል ስራ ያልሰሩ ሰዎችን በህዝብ ፊት እንደተራራ ሲያገዝፋቸው አይቻለሁና ይሄን አልኩ ሃቀኛ ፈራጅ ነው የሚባልለት ((ጊዜ)) የሚሉት የማያልቅ ሰንሰለት ከተከበሩበት ታላቅነት ካለስራቸው ካለበደላቸው አምዘግዝጎ ካመድ በመደባለቅ መሳቂያ መሳለቂያ ያደረጋቸው ንፁሃን ሰዎችን አይቻለሁና ይሄን አልኩ እኔኮ "ጊዜ ጣለው " ሲባል እንዲሁ ተረት ይመስለኝ ነበር ልክ ነው ጊዜ ሲፈልግ ሰርቆ ከህንፃ ላይ የዘለለን ሰው ልክ አጋጣሚ አስመስሎ ፍራሽ የጫነ መኪና ከስር እንዲጠብቀው ያደርጋል (እሰይ እንኳን ሰረክ ና እዚህ ላይ እረፍ እንደማለት) ይሄንን የጊዜ "አሽቃብጦት" "አጋጣሚ" እንለዋለን ....!!

እኔ ግን የልእልትን ክፉ ግጥጥሞሽ ስሰማ "እንደጊዜ የወደቀ ግንድ ላይ ምሳሩን ይዞ የሚዘምት እንደጊዜ ለበዳዮች ጅራቱን የሚቆላ ምን ነገር አለ " ብየ በጊዜ ከፋት ተደነኩ (መቸስ የዚች ልጅ ጦስ ደግሞ ብሎ ብሎ ጊዜ ጋር ሊያጋጨኝ ጀምሮ የለ) ደግሞ "የጊዜ እንጅ የሰው ጀግና የለውም " ይባልልኛላ እንደጊዜ ፈሪ ከሳቁት ጋር ስምንት ሽ ጥርሱን እያገጠጠ የሚያላግጥ አስቀያሚ ነገር ምን አለ ! ይሄው ይችን ሚስኪን ይችን ልእልት እራሱ ጊዜ ከትምህርት ቤት ጎትቶ አውጥቶ እራሱ ኩሎ ድሮ ሲያበቃ የኳለው አይኗን በጨካኝ የግጥጥሞሽ ጥፊው አጥፍቶ በምንም ማስረጃ በምንም ቃል ማስተባበል የማይቻል አስመሳይ እውነት ላይ ጣላት ! ማንም ሰው የሰማኒያ ሚስቱ ያውም በራሱ ቤት ያውም በስስ የቤት ቀሚስ ያውም የጡት ማስያዣ እንኳን ሳታደርግ የራሱ ጓደኛ ደረት ላይ ልጥፍ ብላ የጓደኛውም እጅ ሰፊ የቀሚሱ የአንገት ቅድ ያጋለጠው ራቁት ጀርባዋ ላይ አረፍ ብሎ ቢያገኛት " ሚስቴ ንፁህ ናት" ሊል አይችልም !! በጣም ሩህሩህና ደግ የሃይማኖት አባት እንኳን በዚህ ሁኔታ ቢያገኟት" ከእናንተ ሃፂያት የሌለበት ይውገራት" የሚል ቃሉን ይጠቅሱ እንደሆነ እንጅ "የለም ይች ልጅ የመከፋት መአበል እየገፋ እዚህ ኢያሱ የሚባል ጨካኝ አለት ላይ የጣላት ሚስኪን ናት" ሊሉ አይችሉም ምናልባት የተለየ መገለጥ ከሰማየ ሰማይ ካልተላከላቸው በስተቀር ! ውስጤ በብስጭት ጨሰ በዛች ቅፅበት በልእልትና ፊት ለፊቷ ባፈጠጠበት "ባሏ" መካከል ቁሜ "በል እንግዲህ እኔን ግደልና በእኔ ሬሳ ላይ ተረማምደህ ትነካታለህ" ማለት አማረኝ ያች ቅፅበት እኮ (አያድርስ እንጅ) አይናችን ራሱ የሚዋሽበት ቅፅበት ናት !! በቃ ማንም ምንም ቢለን "ከአይኔ ወዲያ" ብለን ግግም የምንልበት ቅፅበት አለኮ (አይንም ምስክር ሁኖ ሞቶ ስንት ጉድ ሰቆቃ አልፎ የፈጠረው አጋጣሚ ላይ መጉረጥረጥ ጀግንነት ይመስል የሞተ ! ዓይን ራሱ አበሳጨኝ) ደግሞ አንድ ነገር ተመኘሁ አንዲት ነገር ብቻ ከምር ተመኘሁ ምን ተመኘሁ ?? እግዜር ከሰማየ ሰማያት ወላ በመብረቅ ወላ በብርሃን ሰይፉ ጣራውን ሰነጣጥቆ ግድግዳውን ደረማምሶ በልእልትና በወንዴ አንበሳው መሃል ከቾ እንዲልና "ልጀን ለቀቅ አድርጋት ንፁህ ናት " እንዲለው ! ወይም እግዜር የጊዜን ሰዓት ዞር አድርጎ አልያም በሆነ ተአምር ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የሆነው ሁሉ የተቀረፀበትን ካሴት ነገር ከእግዜር ቤተመዛግብት አውጥቶ ወንዴ ፊት "ተመልከት"

ብሎ እንዲከፍተው“ እ...........ሽ “ አልኩ ቀጥሎ የተፈጠረውን ጉድ ለመስማት ልቤ በጉጉት ዘላ ጉሮሮየ ውስጥ መወተፍ እየቃጣት የልእልት ውብ ፊት ላይ አይኔን ተክየ ....እንደዛሬ በሙሉ አይኔ ፍጥጥ ብየ አይቻት አላውቅም ደግሞ እንዲህ አልኩ “አሁን ይች ልጅ እንኳን ጓደኛየ ደረት ላይ ተለጥፋ እንዲሁ የትም ሳትሄድ ምንም ሳታደርግ አታስቀናም ? በሰው መፍረድ ከባድ ነው አንዳንዱ ሰው ከመሬት ተነስቶ በቅናት የሚትከነከነው በአፍቃሪው የሆነ ነገር ስለተፈጠረ ብቻ አይደለም ቁንጅናው በማንኛውም ሰዓት የሆነ ነገር የመፍጠር አቅም እንዳለው እየገባው ነው ለብዙሃኑ ወንድ የተጋነነ የሴት ልጅ ቁንጅና ፈንጅ ነው አንዴ የፍቅር መንገድ ላይ ከተጠመደ በኋላ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ማንም ሊረግጠውና ሊፈነዳ ይችላል ! ያኔ ራሱን ጨምሮ በአካባቢው ያለውን ነገር ሁሉ እንዳልነበር ከማድረግ ምንም አያግደው ! የልእልት ቁንጅና ደግሞ ኒውክሌር!!

“አልፈራሁም አልደነገጥኩም አልተጨነኩም” አለች ልእልት ቀጠል አድርጋ የዛን ቀኑን አጋጣሚ ስትነግረኝ “ግን በሁሉም ነገር ተስፋ ቆረጥኩ!! በፍቅር፣ በንፅህና፣ በእምነት በህይዎት በሁሉም ነገር ተስፋ ቆረጥኩ በእግዚአብሔር ደግሞ አዘንኩ እሽ እኔ ጥንቃቄ ይጉደለኝ እኔ ዝርክርክ ልሁን እኔ በቃ የማረባ ከንቱ ሴት ልሁን እምነት የሌለኝ ሴትም ልሁን ግን ሰይጣን እንዲህ አይነት ቆሻሻ ድራማውን በፍጡሩ ላይ ሲሰራ እግዚአብሔር ዝም ይላል ?? ደግሞ የሰዓቱ መገጣጠም ሰይጣን ግን ከምርም ሰይጣን ነው “ አለች አባባሏ በሌላ የሰላም ቀን ቢሰሙት ሳያስቅ አይቀርም በዚህ ሰዓት ግን እንኳን ሊያስቅ ፊቷ የሚረጨውን ህመም እንኳን አብሮ አለመታመም አይቻልም ነበር እውነቷን ነው ሰይጣን ከምርም ሰይጣን ነው !! “ ወንዴ በዛች ቅፅበት እኔና ኢያሱ ፊት በቆመበት ሰዓት ምን ሆነ መሰለህ ታምነኛለህ ምንም አልሆነም አብርሽ!! ስትለኝ እንደባሉን በጭንቀት የተወጣጠረ ስሜቴ ሙሽሽ ሲል ተሰማኝ ግን እንዴት ነው ምንም አለመሆን ባል ሚስቱን ጓደኛው ደረት ላይ ተለጥፋ አግኝቷት እንዴት ነው ምንም አለመሆን ልእልት ጥያቄ የወረረው ፊቴን አየት አድርጋ ቀጠለች”....ኢያሱ እንደዛን ቀን ገርሞኝ አያውቅም ሊደነግጥ መሰለህ ሊደነብር መሰለህ ዘና ብሎ ወንዴን እንዲህ አለው “ታሳዝናለህ ሴትን እንደዚህ ማስለቀስ ትልቅ ነገር መሰለህ? ደግሞ ታፈጣለህ ከምር አዝኘብሃለሁ” የኢያሱ ድምፅ ጉልበት የሆነኝ ይመስል ከደረቱ ላይ ቀጥ ብየ እንባየን ዘረገፍኩት (ተዘረገፈኝ እንጅ) እመነኝ አብርሽ የዛን ጊዜ አላለቀስኩም ምንም የሃዘንም የመከፋትም ስሜት አልተሰማኝም ዝም ብሎ እንባየ ሲከነበል ፀጉሬን ታጥቤ ከፀጉሬ ላይ ረግፎ ፊቴን እንደሚሸፍን ውሃ እንባየ ከአይኔ ሳይሆን ከላይ ጉንጨ ላይ የፈሰሰ ነው የመሰለኝ ወንዴ በዛ ሰዓት የፈለገውን ቢል የፈለገውን ቢያደርግ ውስጤ ባለቤቱ በድካም ሳይዘጋው እንደተኛ በር ተከፍቶ ክፍቱን ቀርቶ ነበር ምንም አላደረኩም ብሎ ለመከራከርም አንዳንዴ ይሰለችሃል ! ስንት አመት ታመንኩ ለወንዴ ስንት አመት በሬን ዘጋሁ አመቱን ተወው ከተጣላን ጀምሮ ራሴ ላይ በሬንም አእምሮየንም ዘግቸ ከወንዴ ውጭ ሌላ ወንድ እንደብልጭታ እድሜ እንኳን በአእምሮየ አልተከሰተም በዚህ ሁሉ ብቸኝነትና ሰቆቃየ ወንዴ ቀን ላይ ተሳስቶት እንኳን እቤት ብቅ ብሎም ደውሎም አያውቅም ዛሬ ይሄው ! ይሄው ወንዴ ሌላ ወንድ ደረት ላይ ተኝቸ እያየኝ በቃ ከዚህ በኋላ ያ ሁሉ የፍቅር ምስሌን ሰርዞ በዚህ ስእሌ ብቻ ሊያስታውሰኝ ወንዴ ፊቴ ቁሞ በጥሞና ያየኛል !! ኢያሱ “ተቀመጣ” አለው ዘና ብሎ ልክ ምንም እንዳልተፈጠረ (ለነገሩ ምን ተፈጠረ የፈጠረኝ አምላክ እኔን እንዲህ አይነቱ ምድጃ ላይ ስጣድ እያየ ዝም አለ እንጅ ማን እንደሚያወጣሽ ጉድሽን አያለሁ ብሎ ) ወንዴ የግንባሩን ቆዳ ወደላይ ለቅፅበት ሰብሰብ አድርጎ መለሰና ግንባሩን በመዳፉ እየፈተገ ዝም ብሎ አንዴ እኔን አንዴ ኢያሱን ተመልክቶ “ ጭራሽ በኔ ሆነ የሚታዘነው “ ብሎ ዞሮ ወጣና ሄደ ምን ከተቀመጥኩበት እንዳስፈነጠረኝ አላውቅም ከፍራሹ ላይ ተነስቸ ሮጥኩ ወንዴን ገና ደረጃውን ሳይወርድ ደረስኩበት ! ፊቱ ቁሜ በቃ የምለው ነገር ሁሉ ጠፍቶብኝ ከንፈሬ ሰውነቴም እየተንቀጠቀጠብኝ ዝም ብየ አየሁት ወንዴ ካለወትሮው አላኮረፈ አልተቆጣ ዝም ያሉ አይኖቹን አይኖቸ ላይ ተክሎ የምለውን ለመስማት ይጠብቀኛል ምነው በሆነ ስድብ ንግግር በጀመረ ምነው ከፊቱ ገፍትሮ ከዛ ፎቅ ላይ አምዘግዝጎ በገላገለኝ ዝም ! በቃ የደረጃውን ብረት ደገፍ ብሎ (መቆም የደከመው ነበር የሚመስለው) አየኝ ”ወንዴ” አልኩ በቃ ሌላ ምን ልበል ከየት ነው ይሄ ሁሉ ስንክሳር የሚጀመረው ወንዴ በረዥሙ ተነፈሰና “ልእልት አሳልፊኝ “ አለኝ አልነካኝም አልገፋኝም አልጮኸብኝም በቃ ይችን ቃል ሲናገር ፊቱ ላይ የነበረው ቅዝቃዜ ከመንገዱ ዞር አደረገኝ ”ልእልት አሳልፊኝ” ድምፁ እስከዛሬ ጆሮየ ላይ ያቃጭላል .... ዝም ብየ አየዋለሁ ....

ከደረጃው ወርዶ ወደመኪናው ሄደ ወንዴ ካለወትሮው አካሄዱ ድክም አለብኝ እግሩን እያነሳ እንዳገኘ ነበር የሚጥለው ደግሞ ትንሽ ጎበጥ ያለ መሰለኝ (ከላይ ሁኘ ስላየሁትም እንደሆነ እንጃ ) መኪናው የቆመችው ከኢያሱ ውድ መኪና ጎን ነው የመኪናውን በር ሊከፍት ሞከረና መቆለፉ ትዝ ሲለው ቁልፉን የትኛው ኪሱ ውስጥ እንዳስቀመጠው ጠፍቶበት ኪሶቹን በርብሮ አንዱ ኪሱ ውስጥ አገኘው መኪናው ውስጥ ገብቶ ረዥም ደይቃ ሳያስነሳ ቁጭ አለ ልክ መኪናውን ሲያስነሳ እንደሆነ ፍንዳታ ደንብሬ ከፈዘዝኩበት ነቃሁ ወንዴ እየሄደ ነው አይበልበትና አሁን መንገድ ላይ የሆነ አደጋ ደርሶበት አንድ ነገር ቢሆን እስከዘላለሙ “እንደካድኩት” አስቦ ሊቀር ነው አይደል ቁልቁል ወደታች ተንደረደርኩ ታች ስደርስ መኪናዋ ከግቢ ወጥታለች ወንዴ ሂዷል !! ወደቤት ስመለስ ተራራ መውጣት በለው ደረጃው ራቀኝ አይኔ ጭልምልም አለብኝ የመጨረሻውን ደረጃ ስወጣ እማማ ቁንጥሬ “ምነው ወንዴ ሰላም አይደለም እንዴ” አሉኝ

ይታይህ አናግረውኝ አያውቁምኮ ዘግቻቸው አለፍኩ ከኋላየ “ተቃጥለህ ሙት ያለው ልጅ” ሲሉ ጆሮየ ውስጥ ጥልቅ አለ ተንደርድሬ ወደሳቸው ተመለስኩ ከዛ በፊትም ከዛ በኋላም እስከአሁን ሰው እንደዛ ተናግሬ አላውቅም አብርሽ “ አንቱ ሴትዮ ምንድነው ችግርዎ በሰው ትዳር በሰው ጉዳይ ምን ያገባዎታል የራስዎትን ኑሮ አይኖሩም ስራ የለዎትም “ ብየ ብሎኩን በሚያንቀጠቅጥ ድምፅ አንባረኩባቸው እነዛ ነገረኛ ጎረቤቶች ልክ ስማቸው ከነአያታቸው የተጠራ ይመስል በራቸውን እየከፈቱ አሰፈሰፉ ወደቤቴ ገብቸ ባለ በሌለ ሃይሌ በሩን ፊታቸው ላይ ጠረቀምኩት በሩን ወርውሬ ስዘጋው የሆነ መስተዋት ነገር ከኋላየ ሲሰባበር ድምፁ አሰቅቆኝ ደንግጬ ዞርኩ ግድግዳ ላይ ስንት አመት ተሰቅሎ የኖረ የእኔና የወንዴ ባለመስተዋት ፍሬም የሰርግ ፎቶ ነበር የቲቪ ማስቀመጫው ጠርዝ ላይ ወድቆ የተንኮታኮተው !! የወንዴ አባት ከዱባይ አሰርተው ያመጡልን እጅግ ውድ ስጦታችን ነበር ወንዴ ይሄን ፎቶ ይወደዋል አይገልፀውም ከተጣላን በኋላ እንኳን በቅርቡ ድንገት ከመኝታ ቤት ብቅ ስል በጥንቃቄ በሶፍት ሲወለውለው አይቸዋለሁ !! (ወንዴ ፍቅሩ ጨርሶ አልሞተም ብየ ልቤ ውስጥ ቁራጭ ተስፋ ያኖርኩበት ቀንም ነበር) ኢያሱ ተረጋግቶ ከተቀመጠበት ፍራሽ ላይ ድንገት ተስፈንጥሮ ተነስቶ “ ልእልትየ እዛው ሁኝ የኔ ቆንጆ እንዳይቆርጥሽ ! እንዳንች አይነት ውብ እጆች ከሚቆረጡ የእኛ አይነቱ ከነትከሻው ተቆርጦ ይውደቅ “ እያለ የመስተዋት ስብርባሪ ይለቅማል በሩን በጀርባየ ተደግፌ ዝም ብየ ሳየው ቅንጥብጣቢ የሚለቅም ውሻ መሰለኝ በዛች ቅፅበት ምን እንዳማረኝ ታውቃለህ አብርሽ?? ተለቅ ያለውን የመስተዋት ስባሪ አንስቸ እዚህ ምቾት ያደነደነው ማጅራቱ ላይ መሰካት !! እሱም ላይ ብቻ ሳይሆን እራሴም ላይ !!

“ኢያሱ “ አልኩት

“ወይየ ልእልትየ “ (አሁን ይሄን ሁሉ “የ” ምን አመጣው )

“ ውጣ!! “

“እ??????” አለ በግርምት በርከክ ብሎ የመስተዋት ስብርባሪውን እንዳንከረፈፈ .....

“ከዚህ ቤት ውጣ ....ሁለተኛ እዚህ ቤት እንዳትመጣ ....!!”

“ል...እ...ል...ት..የ ...እኔኮ “

“ውጣልኝ በቃ !!” ብየ አምባረኩና በር ላይ የተቀመጠ ጫማውን አንስቸ አፍንጫው ስር ደነቀርኩለት ....ቀስ ብሎ ተነሳና

“እሽ ስብርባሪው እንዳይቆርጥሽ ላንሳው ....??” አለ

“ ው.....ጣ !” ጫማውን በቀስታ አጥልቆ የመኪና ቁልፉንና አውልቆ ያስቀመጠውን ጃኬት ከፍራሹ ላይ አንስቶ

“ስሜትሽን ረደዋለሁ ልእልትየ ወንዴ እያደረገ ያለው ስራ እንደሚከብድ አውቃለሁ ....”

"ስሙን አትጥራ ...." ብየ አፈጠጥኩበት ወጥቶ ሄደለኝ !! በሩን ቆልፌ ቁጭ አልኩና ስቅስቅ ብየ አለቀስኩ ሳሎኑ ውስጥ እንደተበታተኑት ስለታቸው የሚያስፈራ የመስተዋት ስብርባሪዎች ስለቱ የሚያስፈራ ቀን ከፊቴ እየመጣ መሆኑ በእንባየ ግርዶሽ ታየኝ ተስፋ የሚባል ነገር የለም ምንም !! መስተዋት ምንድነው ጊዜኮነው ኑሮኮ ነው ትላንት ያማረ መልክህን እያሳየ ጉድለትህን እንድታስተካክል እየመከረ አደባባይ ከመውጣትህ በፊት ሲያስውብህ ነበር ዛሬ ሰበብ ፈልጎ ከአብራኩ በወጡ ስለታም ስብርባሪዎቹ ደምህን ሊያፈሰው መንገድህ ላይ ስቃይ ሁኖ ተዘርቷል ትላንት ከፊቴ ቁመው ከእኔው ውስጥ የሚወጣውን ተስፋ ሲያሳዩኝ የነበሩት ውብ የቀን መስተዋቶች ሁሉ ተሰባብረው ፊቴ ወድቀዋል ምን አማራጭ አለኝ እንባ ማጭዴን ይዤ ጥቁር እርሻየ ላይ መጭውን ሰቆቃ ከማጨድ ውጭ

....ጊዜ ግን.....

# ክፍል 18

ቁጣ ነው ! ከዚህ በኋላ ያለው የልእልት ታሪክ ቁጣ ነው !! ውብና ገራገር ፊቷ እንኳን ለራሷ አብሯት ለተቀመጠው ሰው ሁሉ ሰላም የሚሰጥ ልእልት ኢያሱን ከቤቷ አባራ ለብቻዋ ከተቀመጠች በኋላ ያለው ታሪኳ በሙሉ ቁጣ ነው ግፏን አፍኖ የኖረው የውበቷ ቀላይ ተከፍቶ ያመጣባት ፍቅር ላይ ክፉ የሚሰብ የአርባ ቀን እጣ ፋንታዋ ላይ የቁጣ ዲኑን አወረደው እርህራሄ ፣ ፍቅር ፣ ትህትና፣ ፈገግታ ፣ የዋህነት እንደደረቀ ሳር በምድር ላይ እንደበቀለ አራሙቻ በቁጣዋ ሰደድ ተበሉ ቁንጅናዋ ከደምና ስጋ ሳይሆን ከአስፈሪ የብረት ቅርፅ የተሰራ ያህል ድርቅ ያለና የማይናወጥ ሁኖ በፊቴ ቆመ ታሪኩንም ዝንፍ በማይሉና እንደብረት ኳስ በጠጠሩ ቃላት እንደብረት ዘንግም ቀጥ ባለና በጠጠረ ድምፅ ያፈሰው ጀመር ብረት የመሸከም ያህል ልቤን እየከበደው ሰማሁ.

"ኢያሱን ያባረርኩበት ቀን ማታ ወንዴ ካለወትሮው አመሸ አምሽቶ የማያውቀው ልጅ አመሸ እስከምሽቱ ሁለት ሰአት አልመጣም ሶስት ሰዓት ሆነ አልመጣም ስልኩ ላይ ሞከርኩ ተዘግቷል ጭንቀት ለቀቀብኝ እወጣለሁ እገባለሁ ስልኩን እሞክራለሁ አራት ሰዓት ሆነ የመኪና ድምፅ በሰማሁ ቁጥር እወጣለሁ ወንዴ የለም አምስት ሰዓት ሆነ ከምሽቱ!! ከተጋባን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው እንግዲህ ተጨነኩ በቃ የማደርገው ነገር ግራ ገባኝ አንድ ነገር ሁኖ ቢሆንስ ኢያሱ ጋር ተጋጭተው ቢሆንስ የማላስበው ነገር የለም ድሮ በልጅነቴ አባባ ድንገት ሲያመሽ እናቴ በጭንቀት እየተንቆራጠጠች የምትጠብቀው ነገር ይሄው ስንት አመታት ተሻግሮ ትውልድንም ተራምዶ ዘመናዊ ነን የምንል እኛም ላይ ሴት ጠባቂ ወንድ ተጠባቂ ሁኖ ዳግም ነፍስ ዘርቶ አንሰራራ !! (ወልደሽ ቅመሽው ይሉት እርግማን ውስጥ አግበተሽ ቅመሽው የሚል ምርቃት መርገምት ሳይኖር አይቀርም) የወደዱትን ሲያጡ ያጡትን ይቀላውጡ እንደሚሉት

ኢያሱ ጋር ደወልኩ እና "ወንዴ አመሸብኝ ምናልባት አይተኸው ይሆን ከመሸ " አልኩት አላየውም ሁሉም ጓደኞቹ ጋር እየደወለ እንዲጠይቅልኝ ለመንኩት "ችግር የለውም ልእልትየ አንች አትጨነቂ መልሽ እደውላለሁ" አለኝ አየህ የኢያሱ ክፋት መገለጫው በምንም ነገር የማይናወጥ ደግነት ነው ቀን እንደውሻ አከላፍቶ አባርሬው ምንም እንዳልተፈጠረ አብሮኝ መጨነቁን እየነገረ ያፅናናኛል እንዲህ አይነት ሰዎች አሉ በቃ ደግነት የክፋታቸው አንድ አካል የሆነ እንዲቹ እየተጨነኩ ጠበኩ ኢያሱ አንድ ሰላሳ ደይቃ ቆይቶ ደወለና ማንኛቸውም ወንዴን ከመሸ እንዳላዩት ነገረኝ እሽ የት ሄደ ይባላል? በመጨረሻ የማደርገው ቢቸግረኝ ለወንዴ አባት ደወልኩ "ልእልት ሰላም አመሸሽ ምነው ወንዴ ሰላም አይደለም እንዴ? " አሉ ድምፃቸው በድንጋጤ ይንቀጠቀጣል

"አይ ሰላም ነን አባባ ወንዴ እስካሁን እቤት አልመጣም ምናልባት እርስዎ ጋር መጥቶ ከሆነ ብየ ነው"

"ስልኩ ላይ ደወልሽ ጓደኞቹ ጋርስ አልደወልሽም" አባቱ እንስፍስፍ አሉ (መቸም የሱ ነገር አይሆንላቸውም)

" ስልኩ ዝግ ነው ...አባባ "

"ልጀን ምናገኝብኝ የት ገባብኝ" እያሉ ስልኩን ሳይዘጉት ሲያወሩ ይሰማኛል ቻው እንኳን አላሉኝም ወዲያው ኢያሱ ደወለ

"ሄሎ ኢያሱ "

"ልእልትየ ...ምን አዲስ ነገር አለ ...?"

"ምንም የለም ጨንቆኛል እባክህ !" አልኩ ተጨንቄ ....

"ልእልት መጣሁ በቃ ወጣ ብለን እንፈልገዋለን አትጨናነቂ አለኝ " ይሻለኛል ! እቤት እየተጨነኩ ከመጎለት ቢያንስ ወንዴ ሊሄድ የሚችልባቸውን ቦታዎች ሂጀ ብፈልገው ይሻለኛል ሰዓቱ እኩለ ሌሊት ሁኗል የወንዴ አባት ደወሉ ....

"እኔ የምልሽ ልእልት ...ቀን ተጋጭታችሁ ነበር እንዴ ....."

"እ....ይ ...ዝም ብሎ ተራ .....ትንሽ የሆነ አለመስማማት ነበር እንጅ ይሄን ያህል እንኳን"

" ምነው ልእልት ....ምነው ....ያለእናት ያሳደኩት አንድ ልጀ ... አንችን እንደእህትም እንደእናትም አምኘ አደራ ብየ ብሰጥሽ ምነው ....." ብለው እንባ ቀረሽ የሆነ ብሶታቸውን ወቀሳቸውን አዘነቡብኝ ! (ልቤ እየተፈረፈረ የወደቀ እስኪመስለኝ) ምናባቴ ልበል .... ስልኩን ጆሮየ ላይ ዘጉብኝ .... ኢያሱ አፍታ ሳይቆይ ደረሰ ....ከላይ ሹራብ ደርቤ ፀጉሬን ባገኘሁት ሻሽ አሰርኩና ወጣን አየህ አብርሽ አሁን ላይ ነው የገባኝ ኢያሱ ወንዴ ይኖርበታል ብሎ የወሰደኝ ቦታዎች በሙሉ እንዴት ያሰቅቃሉ መሰለህ በህይዎቴ እንዲህ አይነት ቦታዎች ይኖራሉ ብየ አስቤ አላውቅም ብዙ ጊዜ ወንዴ ጋር ተያይዘን ከለብ ወጥተናል ተዝናንተናል ግን እንዲህ የሴተኛ አዳሪ እና የሰካራም መዓት የበዛባቸው ሽታቸው ብቻ ከበር የሚገፈትር ሲኦል የሆኑ ቦታዎች አጋጥመውኝ አያውቁም ኢትዮጲያ ውስጥ አልመስልሽ አለኝ

" ወንዴ እዚህ ይመጣ ነበር ?" ከአንዱ ቤት በወጣን ቁጥር እለዋለሁ በግርምት ኢያሱን "አዎ ልእልትየ! እና የሁልጊዜ ንትርካችን ምን ሆነና ተው ስርዓት ያለው ቦታ ዋል አንተ ባለትዳር ነህ አንተስ የራስህ ጉዳይ ልጅቱ ላይ የማይሆን እዳ እንዳታመጣባት ስለው በቃ እኔን እንደጥላት ሆነ የሚያየኝ" እያለ ከመጀመሪያው የባሰ ቦታ ይወስደኛል (በኋላ ቆይቶ ሲገባኝ ግን ኢያሱ ያንን ያደረገው ሆነ ብሎ ለወንዴ ያለኝ አመለካከት ዝቅ እንዲል ለማድረግ ነው ደግሞም በሰዓቱ ብቸኛ ሃሳቤ ወንዴን ማግኘት ይሁን እንጅ የእውነትም ወንዴ ይሄድባቸዋል የተባለባቸውን ቦታዎች ካየሁ በኋላ ውስጤ የሆነ ነገር ደፍርሶ ነበር " እንዲቹ ጉራንጉር ለጉራንጉር ኢያሱ ጋር ስዞር አምሽቸ ድንገት ስልኬ ጠራ ወንዴ ነው ማመን አልቻልኩም "ወንዴ....የት ነህ ምን አድርጌህ ነው ወንዴ " "የት ነህ ...? የ....ት ነህ .....? ሃሃሃሃ አንች ራስሽ ቤቱን ቆልፈሽው የት ነሽ? የቀኑ አልበቃ ብሎሽ ተከትለሽው ሄድሽ?? " አየህ አብርሽ ከተናገረው ነገር ይልቅ ያስደነገጠኝ ይሆናል ብየ በውኔም በህልሜም አስቤው የማላውቀው ነገር ወንዴ ስክር ብሎ እግዚአቤርየ ! ድራማ ላይ ፊክሽን ላይ እንደሚታየው ፊልም ላይ እንደምናየው ምናምን ወንዴ በእኔ ተናዶ ሰክሮ !! ውይ ጉዴ ! ለካስ ነጋችንን ነው ፊልም እያልን ስናይ የኖርነው ኢያሱን ኩንትራት ታክሲ አስይዞ እንዲልከኝ ነገርኩት

ደግሞ ወንዴ እሱ ጋር አይቶኝ ልብሱን እንዳይጥል ብየ ...

"ኖኖ ቆይ ...ጓደኛየ አለ ያደርስሻል " ብሎ የሆነ ልጅ ጋር ደወለ ልጁ ያለበት ወስዶኝ በዛንኛው መኪና ወደቤት ሄድኩኝ ልክ ከመኪና ስወርድ እና ወደላይ ስመለከት በራችን ላይ ሰው ተሰብስቧል በዚህ በሌሊት ነጫጭ ጋቢያቸውን ለብሰው ሃዘን ቤት ነው ያስመሰሉት አብርሽ ራሴን እንዳልስት እየፀለየኩ ያንን ደረጃ በምን ፍጥነት እንደወጣሁት አላውቅም ወንዴ ደረጃው ላይ ተቀምጦ አፉ ሁሉ እየተያያዘ ይለፈልፋል አባቱ በሩ እጎኑ ተቀምጠው እንደታመመ ሰው አቅፈው ያባብሉታል እማማ ቁንጥሬ ምን የቀረ ጎረቤት አለ ደረጃውን ወሮ ቁሟል " ወንዴ " አልኩ የከበቡትን ሰዎች አልፌ ፊቱ ቁጢጥ እያልኩ አብርሽ መዳፉን ፊቴ ላይ እንደዚህ አሳርፎ ወደኋላየ ቢገፋኝ ከዛ ከፎቅ ልምዘገዘግ እግዚአብሄር ነው ያወጣኝ ከኋላየ ማን እንደሆነ እንጃ ደግፎ አዳነኝ

" የሴት ልጅ ሴት ያሳደገሽ " አለኝ ወንዴ በቁሜ በረዶ ነው የሆንኩት ጎረቤቱ የወንዴን ፀያፍ ስድብ እየሰማ ተው ሊለው መሰለህ "በቃ አይዞህ አሁን ግባ " እያሉ ያባብሉታል አባትየው ዞረው እንኳን አላዩኝም በሌሊት ልብስ ላይ ካፖርት ደርበው ነው የመጡት እንግዲህ ወንዴ ሲመጣ ያግኙት ወይ ከሆነ ቦታ ያግኙት እግዜር ይወቅ "ሃሃ አያችኋት አይደል ቀን ሌላ ወንድ ጋር አሁን ደግሞ ሌላ ወንድ " አለ ያመጣኝ መኪና ቁሞ ወደነበረበት እያሳያቸው "ጧት አንድ ማታ አንድ አለ ሃኪም ሃሃሃሃ " ብሎ ሳቀ ወንዴ ጥንብዝ ብሎ ሰክሯል እንዳለ አካባቢው መጠጥ መጠጥ (ምኑን ቢጠጣው ነው በእግዚአብሔር) በተቀመጠበት እየተወዛወዘ እና መዳፉን ጨብጦ ልቡን እንደከበሮ እየደቃ ....

" አንቺ ....እኔን ...እኔን ወንዴን ንቀሽ ሌላ ወንድ ጋር ያውም በራሴ ቤት አባቴ የኔ አባት (አባቱን በሁለት እጆቾ ራሳቸውን ይዞ ወደራሱ ሳበና ግንባራቸውን ሳማቸው) አባቴ እንደላቀ ባኖረሽ የራሴ ጓደኛ ጋር ድሮም መንገድ ላይ የተገኘች ሴት መንገደኛ ናት እናትሽ ትበ የአባት ክብር የት ይገባሻል "ወንዴዋ ተው የኔ ጌታ ግባና አረፍ በል እዚህ በብስጭት ልብህ ጦሽ ቢል ሁሉም ደስታው ነው የናቴ ልጅ ተኳኩሎ አዳሜ እግሩን እያነሳ ነው የሚሄደው አባትህ ናቸው በሃዘን የሚሞቱብህ "እያሉ ያባብሉታል ይች ሴት እንዴት እንዳስጠሉኝ እንዴት እንደቀፈፉኝ !

"ትክክል!! ትክክል ነዎት እማማ (አገሳው ) ቁንጥርየ ልክ ነዎት !! ምድረ ሸርሙ.. የሸርሙ.. ልጅ ... እኔ ድፍት ብል ደስተዋ ነው እኔ ምን አሳጣኋት እማማ ቁንጥሬ እርሰዎ ጥሩ ሴትዮ ነዎት እናቴ ነዎት መካሪየ ነዎት ሁሉንም ያውቃሉ እኔ ለዚች ውሻ (ተነስቶ ወደኔ ሊመጣ ሲል ከግራ ከቀኝ ያዙት) አይታ የማታውቀውን ልብስ አላለበስኳትም እንዴ ? አላለበስኳትም ወይ እዚህ ቤት ስትመጣ አያውቋትም ርስዎ እማማ ቁንጥሬ?"

"ወንዴዋ ሁሉንም እናውቃለን ግባና አረፍ በል አባትህንኮ ብርድ ላይ አስቀምጠህ አሰቃየሃቸው " ያባብሉታል አባትየው እንገቱን አቅፈው ዝም ብለው ተከዘዋል ልክ ልጃቸው ተሰምቶ የማያውቅ በደል የተበደለ ዓይነት ፊታቸው ላይ የነበረው ሃዘንና ቁጣ ብታየው አብርሽ ያሳቅቃል !

"እ...ኮ ...እዚህ ሰፈር ....እዚህ...እዚህ ፎቅ .... እዚህ ቤት ስትመጣ ይች ውሻ ...(በእጁ ወደእኔ እየጠቆመ) ያንን እንደደረቀ ቅጠል የሚንኮሻኮሽ የትምርት ቤት ካሽ መሪ ዩኒፎርም ለብሳ ስትመጣ በተራመደች ቁጥር ሲንኮሻኮሽ እ.....ዛ ብሎክ አስር ድረስ እየተሰማ ስትመጣ እማማ ቁንጥሬ አይተዋት የለ? ዘበኞቹ አይተዋት የለ ? እኮ እኔ አባቴ ላቡን ጠብ አድር.....ጎ ስሚንቶ አቡንኖ ጣውላ ሽጦ አባቴ (ድንገት እየተንገዳገደ ተነስቶ አባቱ እግር ላይ ተደፋና እግራቸውን ሊስም ሲል ጎትተው አነስተው አስቀመጡት ) "ይቅር በለኝ አባቴ ሰው ይሆናል ብለህ ለእኔ ስትደክም እኔ ብርህን ለአንዲት ሸርሙ. በተንኩት ይሄው የእኔ አባት ሲሚንቶ ሻጭ ስለሆነ ጣውላ ሻጭ ስለሆነ ሚስማር ሻጭ ስለሆነ ስድስት ቁጥር ሚስማር ሸጦ ሰባት ቁጥር ቢስማር ሸጦ አስር ቁጥር ቢስማር ሸጦ ኩርንችት ሚስባር ሸጦ ሰው ስላደረጋት እኔን ልጁን ንቃ ኢያሱ ጋር የሪል ስቴት ባለቤት ልጅ ጋር ወይኔ ወንዴ አንበሳው (ግንባሩን በመዳፉ ገቸው) የኢያሱ አባትኮ ሌባ ነው እንደኔ አባት ሰርቶ ላቡን ጠብ አድርጎ አይደለም ሃብቱን ያገኘው እኔን በሌባ ልጅ ቀየረችኝ !! እማማ ቁንጥሬ የሌባ ልጅ ሰው ሁኖ ትዳር ተትቶ ይኬድለታል ? ራሴ ቤት እራሴ ፍራሽ ላይ ተቃቅፈው

"ኧረ ወንዴ በእግዚአብሔር " አልኩ መለፋደዱን መቋቋም ቢያቅተኝ ...

"አንቺ ውሻ ልጅ ....ዝም በይ ...." ብሎ ያንን አንዳች የሚያክል ውድ ስልኩን ወርውሮ ታፋየ ላይ መታኝ ስልኩ እኔ ላይ አርፎ ደረጃው ላይ ወደቀና ብትንትኑ ወጣ ...ግማሹ ከፎቁ ላይ ወደታች ወደቀ

"ምነካሽ አንቺ ዝም በይ እንጅ ደግሞ አማረብኝ ብለሽ ትናገሪያለሽ ... " ብለውኝ እርፍ አባትየው ...

" በግዚአቤር በግዚአቤር ሃሃሃሃሃሃሃ ባይኔ በብረቱ በዚህ (ሁለት አይኑን በእጆቹ በልጥጦ ለጎረቤቶቹ እያሳየ ) በዚህ ነው ያየኋት አንችንንም እሱንም ልክ ማስገባት አቅቶኝ ነው ? አይደለም !! ...ጨዋ አባት ስላሳደገኝ (አሁንም የአባቱን ግንባር እንደህፃን ልጅ ጎትቶ ሳመና) ጨዋ አባት ስላሳደገኝ ትቻችሁ ወጣሁ ለምን ሴት ሞልቷላ እንኳን

እንዳንች አይነት ችጋራም መሃይም የሴት ልጅ ቀርቶ ከተማውን የተማሩ ቆንጆ የሃብታም ልጆች ፈሰውብታል ሴት ሞልቷል አይደል እንዴ እማማ ቁንጥርየ ....? “ሞልቷል የኔ ጌታ ኧረ ሞልቷል ሴት እንጅ ከተማውን ያስለቀቀ አሁን ተነስና ግባ ”አሉት ያች ነገረኛ ባልቴት “እኮ ....በቃ አሁን ወደቤት !!... ነገ እንደሰራተኛ ልብስሽን በፌስታል ይዘሽ ከዚህ ቤት ውልቅ እዛ ሂደሽ ብትፈልጊ ለዛ ሪል ስቴታም ሌባ የሌባ ልጅ በባሬላ አሸዋና ስሚንቶ አግዥ. “ እየተንገዳገደ ተነስቶ ቆመና እጁን በዛቻ ለረዥም ደይቃ አወዛወዘብኝ “ውሻ” ብሎ መረቀበት ! አባትየው በቁጣና በንቀት አስተያየት ገልመጥ አድርገውኝ ”በሩን ከፈችው እንጅ ምን ቁመሽ ታይኛለሽ “ አሉኝ በወንዴ አጠገብ ወደበሩ ሳልፍ ስካር ባዝለፈለፈው እጁ በቃሪያ ጥፊ ሰንዝሮ ፀጉሬ ላይ ያሰርኩትን ሻሽ በተነው (መናቅ ፅዋዋ ሞላ) በሩን ከፍቸ ልክ እንደዘበኛ እነወንዴ እንዲገቡ ጥጌን ይዤ ቆምኩ.”አልገባም አባባ አንተ ጋር ነው የማድረው አባቴ ናፍቆሽኛል አንተ ጋር እያወራሁ ማደር ነው የምፈልገው ጋብቻ አልጋው ንፁህ ነው ይላል ቃሉ የኔ አልጋ ቆሽሽ ውሾች አቆሽሹት አባቴ ጋር ነው የማድረው ” አለ ወንዴ አባባ እሽ ብለው ደግፈውት ደረጃውን መውረድ ጀመሩ ጎረቤቱ አስከሬን እንደሚሸኝ ሰው ከኋላ እየተንኳተተ ተከተለ ወንዴ ቆም ብሎ በዛቻ እጁን ነቀነቀብኝና “ ደውይና ያንን የሌባ ልጅ ጥሪው ድግሪውን ደሞ የሰርጉን ፎቶ አውጥተሽ ጣይና ፍሬሙ ውስጥ ስቀይለት ለመሃይም ድግሪ ተአምር ነው ውሻ” ብሎኝ እየተወላገደ የአባቱን ትከሻ አቅፎ ቁልቁል ወረደ እታች ወንዴ ወደአባቱ መኪና ሲገባ ጎረቤቱ እንደአስከሬን መኪና ጥቁሩን ቢኤም ደብሊው አጅቦ እንደቆመ ልክ እንደህልም ይታየኛል መኪናዋ ተነስታ በቀስታ ከግቢ ወጣች ጎረቤቱም በቆመበት ሰብሰብ ብሎ የሚያወራውን እንጃ አፉን በጋቢው ከልሎ ይንሾካሾካል እያዘገሙም ደረጃውን ወጥተው “በሉ ሰላም እደሩ “ እየተባባሉ ተራ በተራ በራቸውን ሲዘጉ ይሰማኛል ከበር አዘጋግ እና ከአነጋገር ፍጥነታቸው እኔን ማናገር እንዳልፈለጉ ይገባኛል ተፀይፈውኛል!! የውጭ መብራቶች ተራ በተራ ጠፉ

ከነፍሳት ሲርሲርታና አልፎ አልፎ ከሩቅ ከሚሰሙ የውሻ ጩኸቶች በስተቀር ሁሉም ነገር ፀጥ አለ ረጭ !! ከቆምኩበት በረንዳ ቀና ብየ ፊት ለፊት የተዘረጋውን ሰፊ ጥቁር ሰማይ ተመለከትኩ ሙሉ ጨረቃ ሰማዩ ላይ ፏ ብላ ወጥታለች ስታምር እና የምታፅናናኝ መሰለኝ የምታዋራኝ ሁልጊዜ ሙሉ መሆን የለም ነገ ከነገ ወዲያ ተሸርፋ ግማሽ ትሆናለች ሙሉነቷ በጥቁር ደመና ይሸፈናል ንፅህናዋ በደመና ግርዶሽ ይቆሽሻል በጨለማም ይዋጣል ግን ከየትኛውም ከባድ ግርዶሽ ኋላ ጨረቃ ያው ሙሉ ናት ! አይናችን ጠንካራውን ግርዶሽ አልፎ የጨረቃን ሙሉነት ማየት ሲያቅተው “ ግማሽ ጨረቃ” የሚል ግማሽ እውነት እየነገረ ሊያሳምነን ይሞክራል እውነታው ግን በዚች ምድር ከየትኛውም ግርዶሽ ወዲያ አልፎ ማየት የሚችል ሙሉ አይን ያለው ፍቅር ብቻ መሆኑ ነው !! አይን የራሱን ድክመት ሲሸፍን “ፍቅር እውር ነው “ የሚል ተረት ፈጠረ !

ስልኬን አየሁት ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አልፏል ህይዎቴም እንደዛው ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት የሆነ ህይዎት በዛች ቅፅበት ከጨረቃው በላይ ከጥቁሩ ሰማዩ በላይ ከአስራ ምናምን አመት በፊት የሞተ አባቴ ጠንካራ እና ሞቃት ክንዶቹን ዘርግቶ ታየኝ ጠረኑም ሸተተኝ በጎርናና ድምፁም “የእኔ ልእልት ምነው ብርድ ላይ ግቢና ተኝ “ ሲለኝ ተሰማኝ እንባየ ጉንጬ ላይ እየፈሰሰ ነበር ጨለማ እፈራለሁ ያኔ ግን ወደድኩት ከሰው አይን እቅፍ አድርጎ የደበቀኝ መሰለኝ ባይነጋ ብየ ተመኘሁ የኔ የምለው ሰው ከሚፈፅሙብን በደል በላይ አስፈሪ ጨለማ በምድር ላይ የለም አሁንም እንባየ ጉንጬ ላይ ዝም ብሎ ይፈሳል ጨረቃ ድንቡሽቡሽ ያለች ህፃን ልጅ መሰለችኝ እንባየን በፈገግታ የምትጠባ

# ክፍል 19

ልእልትን አፍቅሪያታለሁ!! ግልግል!! ይህንን ቃል ለመናገር ይህንን ምርኮኝነቴን አምኘ እጀን ለማንሳት ከራሴ ጋር ስታገል ስንትና ስንት ቀኔ አውቃለሁ ባለትዳር ነች ትዳሯ ቅጥአምባሩ ቢወጣም ልእልት ባለትዳር ናት ! ትዳሯ እንዳለቀለት ባውቅም ያው ባለትዳር ናት ! ባለትዳር!!! በሰውም በፈጣሪም ፊት አንድ ወንዴ ለሚባል ወንድ ሚስት መሆኗን ቃል የገባች ሴት መሆኗን ጣቷ ላይ ያለው ቀለበት እጇ በተንቀሳቀሰ ቁጥር እየጮኸ ቢነግረኝም

ልእልትን ግን አፍቅሪያታለሁ !! (((ፍቅር በሞተበት ትዳር ውስጥ ቀለበት የቃልኪዳን ምልክት ሳይሆን ከወርቅ የታነፀ የሰቆቃ ህይዎት ሃውልት ነው !! የግፍ መታሰቢያ !!))) አሁን እንደባሏ ክፋት ቢሆን የልእልት ውብ ጣት ላይ ያለው የቃልኪዳን ቀለበት (ልጅቱ ልእልት ሁና እንጅ) ገና ድሮ ተወልቆ የቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ መጣል አልነበረበትም ? ! ግን የቃል ኪዳን ቀለበት የሰው ብቻ ሳይሆን የፈጣሪም እማኝነት ያለበት ህያው ቃል ነውና በልእልት ዙሪያ የሸቦ አጥር ሁኖ መግቢያ ቀዳዳ እንዳጣ ሌባ ዙሪያዋን ያዞረኛል!! የትኛውም የሞራል ህግ በፊቴ አቅመቢስ የሆነብኝ የልእልትን አይኖች ሙሉ ቀንና ሌሊት ማየት እንደአንዳች ሱስ የሚናፍቀኝ ስላፈቀርኳት ነው !! የልእልት አይኖች ሲያርፉብኝ አንዳች የማልገልፀው ናፍቆት የሚጨመርብኝ ስላፈቀርኳት ነው አይኗን ማየት ፈራሁ እየፈራሁ አይኗን ማየት ናፈኩ እየናፈኳት ደግሞ አልደውልላትም ለራሴ የገረመኝ ባለፈው ቢሮየ ቁጭ ብየ ስልኬን አነሳሁ ለልእልት ልደውል እና እጀ ተንቀጠቀጠ ማመን አልቻልኩም ሳያቋርጥ ነበር የሚንቀጠቀጠው ! መደወሌን ተውኩት እጀም መንቀጥቀጡን አቆመ ! አሁን ይሄን ነገር ፊልም ላይ ባየው ምን ያካብዳሉ አልልም ነበር ? እላለሁ እንጅ !!! ዘንድሮ ምን ጉድ ነው ከሰላም ኑሮየ እያንቀለቀለ እንዲህ አይነት ችግር ውስጥ ያስገባኝ በእግዚአብሔር ! የሆነ ጭንቀቴ ወሰን አጣ ፍቅር የነፍስ ጉዳይ ነው አይደል ነፍሴ ዝሆን የሚያክል ፍቅር ካለአቅሟ ውጣ ስትወጣጠርና ስጋየ ሲጠባት ይሰማኛል የሆነ በጭንቀት የምፈነዳ መስሎ ይሰማኛል ያ የተረገመ ወንዴ ስጋየን በቢላ ቀዶ ፍቅር የሚባል አየር ሞልቶ መልሶ የሰፋኝ እስኪመስለኝ ውስጤ እንደባሉን ውጥርጥር ሲል እና የተንሳፈፍኩ ሲመስለኝ ይሰማኛል ደግሞ የማያቋርጥ የራስ ምታት ያጣድፈኛል ቤተሰቦቸን ማየት አስጠላኝ ጓደኞቸን ማየት አስጠላኝ ስራየ ሁሉ አሰልች እየሆነብኝ መጣ (ይሄኔ ነው ፍቅር ጉሮሮየ ላይ ሊቆም ሽቅብ እየተናነቀኝ መሆኑ የገባኝ ) ቢገባኝ ምን ዋጋ አለው ምንም መፍትሄ የለኝማ የማነው ደፋር ለመሆኑ ፍቅርን ((የሚጣፍጥ ስቃይ)) ብሎ የተፈላሰፈው በምን ምላሱ ቀምሶት ነው የጣፈጠው? ወይስ ወሬ አሳምርኩ ብሎ ነው ወሬኛ !! እንዴት እንደሚመር እንደሚያንገሸግሽ የኔን የራሴን ፍቅር ግለፅ ብባል የሆነ እጅግ መራር የሆነ ነገር ምላስ ላይ አስቀምጦ መዋጥም መትፋትም አለመቻል አይነት ስሜት መሆኑን በተናገርኩ ነበር በቃ ልእልት ልእልት ልእልት ብቻ ልእልትኮ አስተያየቷ አነጋገሯ እያንዳንዷ እንቅስቃሴዋ አሳሳቋ ሃዘኗ ሁሉ ነገሯ ለስላሳ ሚሳኤል ነው የትኛውንም ጠንካራ ልብ በርግዶ አፈራርሶ የሚገባ ! አሁን ምናባቴ ነው የማደርገው እንዲህ ስጨነቅ ይች እንደመለአክ ከተፍ የምትል እህቴ ደወለችልኝ የእህቴን ድምፅ ስሰማ የተሰማኝን ሁሉ ዝርግፍ አድርጌ ነግሪያት እንደሴት ስቅስቅ ብየ ባለቅስ ብየ ሁሉ ተመኘሁ ! ግን ወዲያው ምን መንፈስ እንዳረፈብኝ እንጃ ኮስተር ብየ ማናገር ጀመርኩ (ምንም እንዳልተፈጠረ ሃሃ ከተፈጠረልኝ ነገር አንድም አልቀረምኮ ሁሉንም ልእልት ወስደዋለች)

“ጎረምሳው ጠፋህ” አለችኝ ! አነጋገሯ የሶስት ጊዜ ታላቂ እንጅ በሁለት አመት የምበልጣት ታናሽ እህቴ አትመስልም ”አለሁ ባክሽ .... “

“ባክሽን ምን አመጣው ታዲያ ?”

“ ድካም ነዋ”

“ ፓ! “ስታርስ ነው ስትጎለጉል” አለች ማሚ ቁጭ ብሎ የሰው ሚስት ማሰብ ምን ያደክማል??”

“እሽ ለምን ደወልሽ ...?”

“ባክህ አትኮሳተር እዛ የምትችለውን ምታ ቢሉት አሉ ወደ” ተረቱ ጠፋት ነገር ለማሳጠር ብየ

“ወደሚስቱ ሮጠ “ ብየ የጀመረችውን ተረት ጨረስኩላትና “እ ምን ልታወሪኝ ነው ?” አልኳት

“ ሂሂሂሂሂ ሚስት ነክ ተረቶች ላይ ብቃትክ ጨምሯል ወደሰው ሚስት ሮጠ ትላለህ ብየ ነበር ሂሂሂ “ ዝም አልኩ...

“ነገ ምን ፕሮግራም አለህ ?”

“ያው ስራ ነዋ “

“ቅዳሜኮ ነው “

“አ ረስቸው በቃ እቤት ነው የምውለው “

“ሃሃ ቀኑ እስኪጠፋህ ጢምቢራህ ዙሯል ቀጥሎ ስምህ ይጠፊሃል ከዛ እየደወልኩ አስታውስሃለሁ ! ሂሂሂ እእእ .....ነገ ሳምሪ ምሳ ጠርታናለች እና ያ ጅል ወንድምሽ እንዳይቀር ንገሪው ብላኛለች ”(ሳምሪ ጓደኛዋ ናት እኔም ጋር እንቀራረባለን)

“አይ አይመቸኝም ” አልኩ ስልችት ብሎኝ እንደውም ነገ አርብ መስሎኝ ነበር ቅዳሜ ከሆነማ እቤቴ ለጥ ብየ ማሳለፍ ነው እያልኩ በማሰብ ላይ ነበርኩኝ ይሄ ሳምንት እንደመርግ ነው ተጭኖኝ የነበረው ደግሞ ዝም ብሎ ራሴን ያመኛል “ አብርሽ ሰው አክብሮ ሲጠራህማ አትባልግ “ ድምፅዋ

ውስጥ ማለማመጥ አለ በዚች ምድር ላይ “አትባልግ”

የሚለውን ቃል በጨዋ ድምፅ ተናግራ ምርቃት የምታስመስል ብቸኛ ሴት እህቴ ትመስለኛለች !

“እግዜር ያክብርልኝ ግን አይመቸኝም ” አልኩ ቆጣ ብየ (እስቲ አሁን ምን አስቆጣኝ) እናም “ቻው “ ብያት ስልኩን ዘጋሁባት “ምሳ” ትላለች እንዴ ከሳምንት እስከሳምንት ልፋት በዛ ላይ የልእልት ነገር አዛ አድርጎኛል ለምን እንደሆነ ደግሞ እንጃ በእነዚህ ሁለት ቀናት አልደወለችም ስልኬን አንስቸ ደወልኩላት !(እንዴ ደወልኩላት ለልእልት ) አንዳንዴ እጅ ከአእምሮም ይፈጥናል ዛሬ ምን አጀገነው መንቀጥቀጥ የለ ምን የለ ደግሞ ቁጥሩን ሲጠቀጥቀው ፍጥነቱ (የሚገርመኝኮ ስልክ በቃሌ አልይዝም የቢሮየን ስልክ እንኳን “ኦፊስ” ብየ ሴቭ አድርጌ ነው የያዝኩት ቁጥሩን አላውቀውም የልእልትን ስልክ ደግሞ ሴቭ አላደረኩትም ግን ልክ እንደራሴ ስልክ ነው በቃሌ የማውቀው) እንጅማ ለልእልት መደወል ሳስብ አእምሮየ የማያግተለትለው ሃሳብ አልነበረም !!

“አ ብ ር ሽ የ “ አለችኝ ! ድምፅዋ ውስጥ ስርቅርቅ የሚል ደስታ አለ የዚችን ልጅ ድምፅ ስሰማ ውስጤ የሚሰርግ ሰላም አለ የሆነ ልቤ የድምፅዋ ባህር ውስጥ ተነክሮ የወጣ ስፖንጅ ይመስል ሙሉውን ቅላፄዋን ምጥጥ ነው የሚያደርገው ! ብቸኝነት ድሮም ድርቀት አይደል ! የደረቀ ልቤ አንዳች ለብ ያለ ውሃ የተሞላ ገንዳ ውስጥ የገባ ነው የሚመስለኝ .....

“ልእልት “ አልኳት ስሟ ላይ “የ” ልጨምርበት ነበር እንደምንም ነው ከከንፈሬ ላይ የመለስኳት “የ”ን !

“ አ....ሁን እያሰብኩህ ነበር የደወልከው አይገርምም ” አለች ከልቧ በሆነ ስሜት መታሰብ እንዴት ደስ ይላል ከምር “ሳስብህ ደወልክ” እንደመባል ለወደደ ሰው የሚያስፈነድቅ የመግቢያ ሰላምታ የለም! ከሆነስ ሆነና ልእልት ስታስበኝ ምኔን ታስበው ይሆን እኔ እንኳን ከአስር የእጅ ጣቶቿ (ያውም ስለትንሿ ጣቷ ብቻ ) አንድ ሙሉ ቀን ማሰብ እችላለሁ ! ከምር እችላለሁ ! ልእልት ማለትኮ ሙሉ አካሏ ቱባ ነው ማንም ቁጭ ብሎ ሲመነዝር መዋል ይችላል ይችን ልጅ ጎበዝ ገጣሚ በታክሲ ሲያልፍ እንኳን በውልብታ ቢያያት በሳምንቱ መፅሃፍ ይዞ ማተሚያ ቤት የሚገኝ ነው የሚመስለኝ !! ኧረ ደግሞ ስለልእልት ላስብ ከተባለ አእምሮየ ራሱ ደስ ብሎት ሌላ ስራውን ሁሉ እርግፍ አድርጎ ትቶ ነው የሷን ነገር ሲያመነዥግ የሚውለው !! ግን ልእልት ስለኔ ምን ልታስብ ትችላለች ? በደንብ አስተውላ ያየችኝ እንኳን ሆስፒታል ነው የግልኮስ ቲዩብ የተሰካበት ክንዴን ይሆን ቀድማ የምታስታውሰው ? ባሏ እንደጎመን በቢላ የቀረደደው ቆዳየን ይሆን ዝግንን ብሏት የምታስበው ? ዝም ብየ እየተቁለጨለጨኩ እሷን ማዳመጤን ይሆን ? ምኔን ነው የምታስታውሰው ? ምኔ ነው የሚታወሰው ....ለነገሩ እንኳን ልእልት እኔ ራሴ ስለራሴ ሳስብ ምንም ትዝ አይለኝም ከመሬት ተነስቶ ባዶነት ይሰማኛል ምንጊዜም በትንሹ እንኳን የተደሰትኩባቸውንና የረካሁባቸውን አጋጣሚዎች ለማደፍረስ “ከዛስ” የሚል ጥያቄ ከአእምሮየ ውስጥ አባርቶ አያውቅም ! ዛሬም ይሄ የተረገመ ጥያቄ አእምሮየ ውስጥ ፈነዳ “ልእልት ቀለበቷን አውልቃ ወርውራ አብርሽየ በቃ ካንተ አልለይም እንደፈለክ አድርገኝ ይዘኸኝ ከዚህ አገር ጥፋ ወይ አጥፍተኸኝ ጥፋ ወዘተርፈ ....ብትልህ ምንድነው የምታደርጋት “ ይለኛል አእምሮየ

እውነትኮነው ምንድነው የማደርጋት መቸም ህይወት ተረት ተረት አይደል "ከዛ በኋላ አብረው በፍቅርና በሰላም ይኖሩ ጀመር " ተብሎ አይዘጋ ነገር !! አገሩ አዲስ አበባ ልጅቱ ልእልት ሰውየው እኔ ኑሮየ ወር ደመወዝ ጠባቂ ልእልትን ባገባት እንደህንድ ፊልም ጫካ ሂደን ስንዘፍንና ውሃ ስንራጭ ውለን ስንመለስ ቤተመንግስት የመሰለ ቤት ተዘጋጅቶ አይጠብቀን የቤት አከራይ ነው የሚጠብቀን ሰው ሞኝ ነው "ብር ንቃ ፍቅር ተርባ ነው የመጣችው" ይል ይሆናል (ማለት ቀላል ነው መኖር ነው ከባድ) ሰው የሌለው ነገር ነው የሚናፍቀው ብርም ፍቅርም ነበራትኮ ልእልት እንደፀረ ሙስና ኮሚሽን የባሏ የሃብት ምንጭ ይጣራ ነጋችን በላባችን ፍሬ ላይ ይቁም ማለቷ ነው ህይወቷን ያተራመሰው ምን ለውጥ አለው ባገባት ስራ የላት ምን የላት ያው በእኔ ደመወዝ መኖሯ አይደል እንዴ እና የወንዴ የቅንጦት ጥገኛ ከመሆን ወጥታ የእኔ የድህነት ጥገኛ መሆን ለውጡ የቁጥር እንጅ ሌላ ምንድነው

በነገራችን ላይ ጭንቀቴ እንዳለ ሁኖ ትዳር የሚባለውን ነገር እንደቀትር ጋኔል የምፈራው ሰውየ "ልእልትን ባገባት" ብየ ሳስብ ገና አፌ ላይ ቃሉ ጣፈጠኝ ያንን መራራ ጎምዛዛ ግራ የገባው ፍቅር ጣፋጭ ነገር ሞላው ሰውን ውለድ ክበድ ብሎ ከመመረቅ እና ከመምከር "ከባድ ፍቅር እንደናዳ ይጫንህ " ብሎ መምከር ሳይሻል አይቀርም ፍቅር ልክ ያስገባው ወንድ ተንቀልቅሎ ነው ትዳር ውስጥ ባናቱ የሚገባው እንደው የቀን ህልም አይሁንብኝና ስከፍተው ቅዝቃዜው የምድር ዋልታን የሚያስንቅ ቤቴ ውስጥ ከውስጥ የልእልት ፈገግታ ሲጠብቀኝ ማሰብ ምን ያህል ደስ እንደሚል ማን ሊገምተው ይችላል በዛ ላይ እሷን የመሳሰሉ ስምንት ልጆች መውለድም አለ ትጎዳብኛለች ብየ እንጅ እኔማ አስራአንድ ልጅ ነው የምፈልገው ቀልድ አይደለም በዚች ምድር ላይ በጣም በብዛት እንዲኖረኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር ልጆች ናቸው እግዚአብሔር ብዙ ብር እንዲሰጠኝ የምመኘው ብዙ ልጅ ወልጀ ማሳደግ እንድችል ነው ለሰው ተናግሬው አላውቅም እንጅ

ሰዎች ሁለት ልጅ ወልደን ምናምን ማሳደግ ሲሉ(የደሃ ምኞት እላለሁ) አስራ አንድ ልጅ ልእልት ጋር ደርዘን !! ይሄ ነው ቤተሰብ ማለት !! ወላ ቤተ ስብሰባ ይባል !! የልእልት ድምፅ ከቁም ህልሜ አባነነኝ !

"እንዴት ነህ ጠፋሁኝ አይደል "አለችኝ ድምፅዋ ውስጥ እኔን የመጠየቅ ሃላፊነት ያለባት ይመስል እራሷን መውቀስ ነበረበት

" ልደውል እያሰብኩ ስራ በዛብኝ " ብየ ወቀሳውን ወደራሴ አዞርኩት

" አሁንኮ ሲስ ደውላልኝ (ሲስ የምትለው እህቴን ነው) ነገ ጓደኛዋ ቤት ምሳ መጋበዜን ነግራኝ በቃ እዛው እንገናኛለን እያልኩ ሳስብ ነበር "

"ተይ እንጅ ደወለችልሽ ትመጫለሽ ? " አልኳት ሰፍ ብየ....

"አዎ ....አንተም እንደምትመጣ ነግራኛለችኮ " አለችኝ (የተረገመችና የተመረቀች እህት እንደው ማዘር የኔ አይነቱን እንከፍ ትታ የሷ አይነት የተረገሙ አንድ ሶስት ልጆች ብትጨምር)

"አ.....ዎ ...አዎ እሄዳለሁ በቃ እዛው እንገናኝ " የልእልትን ስልክ እንደዘጋሁ በደስታ ሳስብ ቆየሁና ለእህቴ ደወልኩላት ስልኳ ተይዟል ...ቆይቸ ደወልኩ

" እ " አለችኝ ድምፀዋ ውስጥ ማሾፍ አለ

" ለሳምሪ አይመጣም ብለሽ እንዳታስቀይሚያት እንሄዳለን በቃ.... "

" ተ..........ው እንጅ ወንድማለ.......ም !! ሳምሪ እንዳትቀየም ነው እንዲህ በብርሃን ፍጥነት ሃሳብህን የቀየርከው ?....ሂሂሂሂ"

"እና?...ከፈለግሽ እቀራለሁ እሺ "

"እሽ !! ግን ለልእልት አሁን ደውለህ እንደምትመጣ ነግረሃታልኮ....ወንድ ልጅ ደግሞ ደሙን ላፈሰሰላት አጥንቱን ለከሰከሰላት ልጅ ቃሉን አያጥፍም .... ሂሂሂሂ" ብላ ሳቀች .... ጆሮዋ ላይ ዘግቸባት በረዥሙ ተነፈስኩ ፈገግታ ፊቴ ላይ እንደፅጌሬዳ አበባ ሲፈነዳ ይሰማኛል !! ያንን የአዲስ አመት ርችት እዚህ መስሪያ ቤት አምጥቸ ባፈነዳውም ሲያንስ ነው እንኳን ፈገግታ !

*** **** ****

በስማም !! ይች ልእልት የምትባል ልጅ ችግሯ ምንድነው በግዚአብሔር እንዴት ነው ዛሬ ደግሞ ያማረባት ቆይ ልብስ በቀየረች ቁጥር እኔ ልቤ ተሰነጣጥቆ ማለቅ አለበት እንዴ ደግሞ በዚህ ላይ ስታየኝ ፈገግታ ትጨምርበታለች (ግዴለም ሌላም ጠላት የለኝም እኔ ገዳየ እህቴ ነች )

"አ ብ ር ሽ የ ..."ብላ ጥምጥም አለችብኝ ልእልት ልክ የሚሰበር እቃ እንደሚይዝ ሰው በቀስታ እጇን ጀርባዋ ላይ አሳርፌ አቀፍኳት ፀጉሯ አዲስ ስለተሰራ አዲስ የተተኮሰ አይነት ሽታ አለው አፍንጫየ እስከቻለው ጠረኗን ከፀጉሯ ከሽቶዋ ጋር ሳብኩት ፍስሃ !! የሆነ የሚያሰክር ጠረን !! በዛ ላይ ጡቶቿ ደረቴ ላይ እንደትራስ በስሱ ተጨፍልቀው ሲመለሱ ልቤን ይዘውት የተመለሱ እስኪመስለኝ ውስጤ ባዶ የሆነ መሰለኝ እቅፍ እንዳደረኳት ብኖር ደስታየ የእህቴ ጓደኛ ሳምሪ ጥሩ ልጅ ነች አንድ መስሪያ ቤት ነው የሚሰሩት ቆንጆ ቤት አላት የቤተሰቦቿ ነው ሰጥተዋት አሜሪካ ይሁን ምናምን ሄዱ(የፈለጉበት ይሂዱ ምናገባኝ ) ታዲ እኔና ልእልትን እህቴና ሳምሪ አስተናገዱን አሪፍ ምሳ ጋበዙን (ልእልት ስትበላ አያታለሁ አቤት ጉርሻወቿ አተናነሻቸው ፈርታ መስሎኝ ነበር ግን የሁሉም ጉርሻወቿ መጠን እኩል መሆናቸውን ሳይ እንዲህማ ሳይፎርሹ ማስመሰል አይቻልም ብየ በቃ የልእልት ጉርሻወች እንደዚሁ መሆናቸውን ታዘብኩ ድንገት ሳያት ቀና ብላ አየችኝ ተገጣጠምን ደንገጥ ብላ መልሳ ፈገግ አለች አፍሬ "ብይ" አልኳት በዚያው ፍጥነት እህቴ ቀና ብላ ስታየኝ በአይኔ ግራ በኩል ይታየኛል ሳላያት ፊቷ ላይ የሆነ የማሽሟጠጥ ፈገግታዋ ይታየኛል (እንግዲህ አመለጠኝ ምን ይሁን )

ቡና ተፈልቶ እንደጠጣን እህቴና ጓደኛዋ ሳምሪ ለመሄድ ተነሱ (ኧረ ጉድ እንዲህ እሳት ላይ ጥለውኝማ አይሄዱም) ተገርሜ እህቴን አየኋት እንደውም ልእልት ይደብራታል ብየ ቀና ብየ አየኋት ፈገግ ብላ (ጥርግ በሉ በሚል አይነት ፊት) ታያቸዋለች የእህቴ ጓደኛ "በሉ ተጫዎቱ ጉዳይ አለን

ስትሄዱ ከደወላችሁልን ወደፒያሳ አንጠፉም " ብላን ወጣች እህቴ ወደኋላ ቀረት ብላ ቦርሳዋን ፈተሸችና ቁልፍ አውጥታ " ልእልትየ በቃ መሄዴ ነው የኔ ቆንጆ እንደነገርኩሽ " ብላ ቁልፉን አቀበለቻት (እንደነገርኩሽ ?? ምንድነው እዚህ ቤት የሚሰራው ነገር.??) እኔና ልእልት ብቻችንን ቀረን ቤቱ ከልእልት ላይ በሚነሳው ለስላሳ ሽቶና ቡና ሲቀዳ በተጨሰው እጣን ቅሪት ጠረን ተሞልቷል ህልም በሚመስል ሁኔታ እኔና ልእልት ጉልበታችን ሊነካካ ትንሽ ቀርቶት ፊት ለፊት ተፋጠን ተቀምጠናል

(ከጉልበቷ እስከጫማዋ ያለው እግሯ እርዝመት ይገርመኛል ) ሶፋ ላይ !እነዛ የተረገሙ እህቴና ጓደኛዋ መሃላችን ለቡና ብለው ሳብ አድርገውት ጠረጴዛው እንኳን የለም (ሜዳውንም ፈረሱንም ሳሎን ጥለውት ጠፉ)

" እሽ አብርሽ እንዴት ነበር ሳምንትህ " አለችኝ ልእልት ዝምታውን ለመስበር ሳይሆን ከልቧ እንደሆነ በሚያስታውቅ ድምፅ እኔ ጋር ማውራት ደስ እንደሚላት ከገባኝ ቆይቷል ግራ የገባኝ ይሄ ፍለጎቷ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ነው "ፍቅር" እንዳልል እህቴን የምታወራበትና እኔን የምታወራብት ፊትም ድምፅም አንድ አይነት ነው (ልእልት በግዚአብሔር ዘለሽ እቀፊኝና በፍቅሬ ማበድሽን ንገሪኝ እላሁ በውስጤ እንደወንድ ፈሪ ፍጥረት በዚች ምድር አለ ግን ዝም ብለን እኮ ነው ያዙኝ ልቀቁኝ የምንለው እስቲ ይችን የመሰለች ውብ ልጅ ፊት ለፊቴ አስቀምጨ በሃሳብ መዛበር ምን ይባላል አፈቅርሻለሁ ማለት ምን ቁም ነገር ሁኖ ነው እንዲህ ውስጤ የሚናወጠው)

" ደባሪ ሳምንት ነበር " አልኩ ....( በለው ! ለምን እንዴት ካለችኝ ከንፈሬ ላይ ያለው ምላሽ አንድና አንድ ነው መቸም ድምፅሽን ስላልሰማሁ ስለናፈቅሽኝ ልእልት ካላንች ሁሉም ነገር ስቃይ ነው ማለት ነው ያማረኝ በቃ !! ) ልእልት ግን ዝም ብላ ምንጣፉን ስታይ ቆየችና "እኔም አጉል ለምጃችሁ እቤት ቁጭ ስል እየናፈቃችሁኝ " አለች

እኛ እነማነን እኔና እህቴ መሆናችን ነው ልእልት እባክሽ ለይተሽ ተናገሪ የምን እናተ ነው አሁንስ እንደጃንሆይ “እኛ” ማለት እኔ ብቻ በሆነ ብየ ተመኘሁ ትክ ብየ አየኋት ልእልት ቆንጆ ናት እግዚአብሔርን ምንም ቃል የማይገልፃት ቆምጆ ናት ከነቃል ኪዳን ቀለበቷ ቆንጆ ናት ቀና አለች አይኖቻችን ተገጣጠሙ ከኋላየ የሆነ ሰው ቁሞ በሁለት እጆቹ ግራና ቀኝ የያዘኝ ይመስል ወደግራም ወደቀኝም መዞር አልቻልኩም ልእልት ላይ እንዳፈጠጥኩ ቀረሁ ልእልትም ዝም ብላ አየችኝ አይኖቿ እናባ የኳተሩ ይመስላሉ ልእልትን አፍቅሪያታለሁ ያፈቀርኳት ልእልት ይቻትና ፊት ለፊቴ ግንኮ ከምር ልእልት በትክክል የእኔ ሚስት ለመሆን የተሰራች ሴት ነች !! በሆነ ስህተት ነው እዛ ወንዴ ጋር ሂዳ የነበረችው በምን አወክ ላንተ መፈጠሯን ሊባል ይችላል የሆነ ጎኔ አካባቢ ያሉ አጥንቶች አፍ አውጥተው ”ጓደኛችን ተገኘች “ እያሉ ሲፈነደቁ ይሰማኛል ግነት አይደለም ሰው ጎኑ ላይ ብቻ ሳይሆን ልቡም ላይ ትልቅ ክፍተት ይዞ የሚኖር ፍጥረት ነው ያ ክፍተት በእይታ ብቻ ልኩን ሲያገኝ የሚሰማው ሙሉነት አለ

ልእልት ሙሉ ስታደርገኝ ይሰማኛል አይኖቿን ወደምንጣፉ መለሰቻቸውና አቀርቅራ ዝም አለች ትንሽ ወደግራ ዘንበል ብላ በግራ ክንዷ የሶፋውን ጠርዝ ደገፍ አለች ዳሌዋ ወደቀኝ ሰፋ ያለ ቦታ ይዞ ደረቷ ወደውጭ ወጣ አለና እነዛ ውብ ጡቶቿ የፍቅር ቤተመንግስት እንደሚጠብቁ የበር ዘቦች ቀጥ ብለው በተጠንቀቅ ቆሙ ከምኔው የተለየ ውብ አቀማመጥ ፈጠረች? ትንሽ በተንቀሳቀሰች ቁጥር ትልቅ ውበት የምትጨምር ጉድ!! ዝም ብየ አያታለሁ(ጅል ካመረረ አሉ) የግራ እጅ ጣቷ ላይ የቃል ኪዳን ቀለበቷ ያብረቀርቃል ቀለበቶቹ የተደራረቡ አንድ ባለፈርጥና አንድ “ኖርማል” የጋብቻ ቀለበቶች ናቸው እንደበፊቱ አላስፈሩኝም አዎ ፍቅር በሞተበት ትዳር ውስጥ ቀለበት የቃልኪዳን ምልክት ሳይሆን የሰቆቃ ህይዎት ወርቃማ ሃውልት ነው !! የግፍ መታሰቢያ !! የፍቅር ጡሩር የታጠኩ እኔ ይህን ጥላቻ የተቀረፀበት ሃውልት በፍቅር ብራና ላይ የፀፀት ታሪኩን በጥቁር ቀለም ተሽከሞ “ልእልት” የተባለች ውብ ከተማ ጣት ላይ የቆመ የጥላቻና የግፍ ሃውልት አፈርስ ዘንድ ፍቅር ልኮኛል !! ያኔ ፈገግታዋ ነፃ ይወጣል መጭው ትውልድም ልእልትን በጠቆረ ታሪኳ አያውቃትም ... ፍቅር የመከነ ነፍሷ እንደሃና ወደፈጣሪው ጩኋልና ከእኔ የብቸኝነት ጩኸት ተዳምሮ የሚፈጠር ተአምር በዚህ አለ ......

## ክፍል 20

እኔና ልእልት ባዶ ቤት ብቻችንን እንደተቀመጥን አንዳች ነገር “ንገረን” እያሉ የሚለምኑኝ የሚመስሉ አይኖቿን እየተመለከትኩ ”ልእልት አፈቅርሻለሁ ባለትዳር መሆንሽን አውቃለሁ ግን ከዚህ በኋላ ከአንች መለየት ለኔ ከባድ ነው ብሞት ይሻለኛል “ ብየ እውነቱን ማፍረጥ ተራራ ሆነብኝ ልእልትን ፈራኋት አንዲት ሴት ፊት ሳይሆን ትልቅ አዳራሽ ውስጥ የተሰበሰበ ህዝብ ፊት ቁሜ ንግግር እንዳደርግ የታዘዝኩ ያህል አፌ ተያያዘ ! ልእልት ታስፈራለች ረጋ ያለ ሰፊና ጥልቅ ውሃ ነው የምትመስለው

የማረባ ልጅኮ ነኝ !! ሰው ላይ የትም የማያውቃትን ቆንጆ መንገድ አስቁሞ ያዋራ የለ ሰው ያውም በግልምጫ የምታቀምሰውን ሴት ግልምጫውን ቻል አድርጎ እየተከተለ ያሰበውን ይናገር የለ እና እኔ አሁን ምን የሚሉኝ ሰው ነኝ እንዲህ በአክብሮት የምትመለከተኝን ሴት እንደምወዳት እንደማፈቅራት መናገር ምኑ ነው ገደል የሆነብኝ በቃ እንዲህ አፌን እንደለጎምኩ ይመሻል ትሄዳለች እዛ ወረቀት ወረቀት የሚሸት ቢሮና ባዶ ቤቴ እየተንቆራጠጥኩ ስጨነቅ እከርማለሁ በቃ ንገራት ይለኛል ውስጤ ! አይ ውስጤ በመጨረሻ ምን አልኩ ? “እህቴ እግዜር ይይልሽ !!” እንዲህ ምድጃ ላይ ጥላኝ ትሂድ

ልእልት ዝምታየ ጨንቋት ነው መሰል ስለስራ ጠየቀችኝ መለስኩ “ደባሪ ነው ትንሽ ይበዛል” ብየ ! ስለእህቴ ደግነት ጥሩ ልጅነት ነገረችኝ ”እ” ብየ ዝም !! ከምር የሆነ የሚያስጠላ ጋግርታም ባህሪኮ ነው ያለኝ ኧረ በእግዚአብሔር አንድ ነገር ተናገር እለዋለሁ እራሴን ወይ ፍንክች ድንጋይ !! ዝም ብየ ማየት (አይንህ ይጥፋ እቴ ሙትቻ) ቢጨንቀኝ (በሰው ቤት )”ልእልት ፊልም ልክፈትልሽ “ አልኳት

"እሽ ...ፊልም በጣ....ም ነው የምወደው አንተን እንዳላስደብረህ እንጅ ብላ ከማትሰስተው ፈገግታዋ ልቤ መሸከም የሚያቅተውን ያህል ፈገግ አለችልኝ (ፍልቅልቅ ቢባል ይሻላል) ተነስቶ ቲቪ ከፈትኩና የሆነ ፊልም አንድ ቻናል ላይ መርጬ ማየት ጀመርን ልእልት ተመስጣ ፊልሙን ስትመለከት እኔ ስላለፈ ታሪኳ እያሰብኩ የነገረችኝን ወደኋላ ተመልሽ እያስታወስኩ የለሁም ፈሪ ምን መሸሻ አለው ያው ወደትዝታው ነው የሚፈረጥጠው !!

*** **** *****

አንድ ሰው ስንት ነው ? በተለይ አንዲት ሴት ስንት ነች ? ኧረ ሁላችንም እንኳን ለሌሎች ለራሳችን ስንት ነን ? የልእልት ታሪክ በየቀኑ ሳስታውስ አንድ ሰው አልመስልህ እያለችኝ ግራ እጋባለሁ ሰው ማለት ከአካባቢው ባህልና ወግ ካደገበት ስነልቦና መደበኛም ይሁን መደበኛ ካልሆነው ትምህርት እንዲሁም ካለፈበት ውጣ ውረድና ከሚጠብቀው ተስፋ ተቀነጫጭቦ በአንድ ላይ በነፍሱ ልጥ የታሰረ ህያው ችቦ ነው ! እድሜ በሚሉት እሳት ተለኩሶ እየተቀጣጠለ ካለለት ለሌሎች እያበራ እና በህይዎት ጨለማ የተቀመጡ ደስታ ፍቅር ፀብ ወዘተ ሰዋዊ ስሜቶችን በራሱ ብርሃን እየተመለከተ ካላለትም በራሱ እሳት እራሱ እየተበላ ወደመቃብሩ የሚወርድ ፍጥረት ነው !! እንደዛ ሳይሆን አይቀርም እንጅ እንዴት አንዲት ሴት አንዲት ወጣት ሴት ይሄን ሁሉ ነገር ትሆናለች ??

ወንዴ ማታ ሰክሮ በጎረቤቶቿ ፊት አሞልጮ አሞልጮ ከለቀቃት በኋላ የልእልት ህይዎት ሌላ ቅርፅ ሌላ ዓለም ሁኖ "ሀ" ብሎ ጀመረ እንዲህ ስትል ነበር የተረከችልኝ " ወንዴ የዛን ቀን ሌሊት ባዶ ቤት ትቶኝ ከአባቱ ጋር ከሄደ በኋላ በቀጣዩም ቀን ሳይመጣ ቀረ እውነቱን ለመናገር አለመምጣቱ አስደስቶኛል "እንኳንም ቀረ" ነው ያልኩት !! እሱ ለተናገረው ፀያፍ ነገር ሁሉ እኔ አፍሬ ነበር እንዴት አይን ለአይን እንደምንተያይ ጨንቆኝ ነበር ወንዴ ይጥላኝ ግዴለም ከፈለገም አይንሽን እንዳላየው ሂጅልኝ ይበለኝ ግን በሰው ፊት ልቡ የሚያውቀውን እምነቴን እንደምናምንቴ ቆሻሻ ጥሎ ረጋገጠው ልክ እንደቁራጭ ስጋ የሃሜት ጥርሳቸውን አግጥጠው ለሚጠብቁ ጎረቤቶቸ ሻሞ ብሎ ወረወረኝ !!

ከዚህ በኋላ ምን እንደምጠብቅ ለራሴም አልገባሽ አለኝ በቃኝ !! እናቴ ቤት ለመሄድ ወሰንኩ እንኳን እኔ እሱስ ዋጋ ቢስ አድርገው ያሳደጉት አባቱ ቤት ሂዶ የለ ደግሞ ያበሳጨኝ የአባቱ ሾካካነት ማንም ሰው ልጁን ይወዳል አውቃለሁ ማንም ሰው ለልጁ ያደላል አውቃለሁ ግን እንደትልቅ ሰው ቢያንስ እኔን አከበሩኝም ናቁኝም ትዳር ብለን ስንጋባ ጉልበታቸውን ስመን መርቀውን የሸኙን አባት ናቸው የእኔም እናት እኮ አምና ልጇን ለልጃቸው ስትሰጥ ባለአደራ ናቸው "ምን ሆናችሁ " ማለት ማንን ገደለ ደግሞ ያውቁኛል ምንም ነገር ጠይቀውኝ እንደማልዋሽ ያውቃሉ (አብርሽ እኔ ለቀልድ እንኳን መዋሸት አላውቅበትም) ልጃቸው የዋሻቸው ሲመስላቸው እንኳን "ልእልቴ አትዋሽም እሷ ትንገረኝ " የሚሉ ሰው ነበሩኮ !

"ልጅን ሰው አደረግሽው ቤቴ ቤቴ እንዲል አደረግሽው የኔ ቆንጆ አንበሳ" ይሉኝ ነበረኮ ደግሞ ወንዴ እኔጋር ከመተዋወቁ በፊት በወር ሁለት ሶስት ጊዜ የሚታሰር በየመሸታ ቤቱ ማንም ጋር የሚደባደብ ልጅ እንደነበር ያውቃሉ በየጣቢያው እና በየመጠጥ ቤቱ ሲንተቱ ነበር ኑሯቸው ያን ሁሉ እፎይታ ያን ሁሉ ልጃቸው ላይ የተፈጠረ መረጋጋት አይከዱትም በእርግጥ እኔ ምንም አድርጌ አይደለም ወንዴን ተው ብየ መክሬውም አልነበረም ስለሚወደኝ ነበር እንጅ የዛን ጊዜ ግን አካሄዳቸውን ብታይኮ ልክ ልጃቸውን ከአውሬ የሚያሸሹ ነበር የሚመስሉት ! አለችና በምሬት ራሷን ነቀነቀች !! ልእልት ስታወራኝ ዝም ብየ አያታለሁ በዚህ ሁሉ መከራ የተደቆሰች ሴት አትመስልም ከድምፅዋ ጀምሮ ፊቷ ላይ የሚታየው ስሜት ሁሉ አንዳች ግርማ ሞገስ አለው ውብ!!

አየህ አብርሽ ለእነዛ አስቀያሚ ጎረቤቶቹ ቁልፉን ወርውሬለት እናቴ ቤት ልብሴን ይዤ መሄድ ነበር ያሰብኩት ግን የሱን ድሪቶ ይዤ ብሄድ ለቀባጠረው ቆሻሻ ወሬ አጉል ማረጋገጫ መስጠት ይሆንብኛል ብየ የለበስኳትን ልብስ እንደለበስኩ እጇላይ የነበረችውን ሁለት ሽ ምናምን ብር አንስቶ በታክሲ ወደእናቴ ቤት ሄድኩ ! በመንገዴ ሁሉ አእምሮየ ይዝት ነበር እንደ እብድ ከንፈሮቸ እየተንቀሳቀሱ ብቻየን አወራ ነበር "ምቾቱ ይቅር እንጅ ለማንም አሳልፋ የማትሰጥ እናት አለችኝ እንኳን ንፅህናየን ከዳ ልታቆሽሸኝ ምንም ባደርግ ገመናየን ሸፋኝ እናት አለችኝ ! ማሚየ እድሜዋ ይርዘምልኝ አዎ እናት አለችኝ ሁሉም ነገር ቀርቶብኝ እየተናኩ የሚወረወርልኝ ሃብትና ምቾት

ቀርቶብኝ ሩህሩህ አይኗን እያየሁ እግሯ ስር ዘላለም እኖራለሁ !! ያደኩበት ቤት ያደኩበት ሰፈር እሄዳለሁ ያሳደጉኝ ጎረቤቶች አሉኝ ሰፈር አለኝ ቤት አለኝ ውስጣቸው ምንም ያስብ ምን እንደነዚህ ውሻዎች ስጋየን በጨካኝ ጥፍራም ብልግናቸው የማይቧጥጡ በፍቅራቸው ያሳደጉኝ ጎረቤቶች አሉኝ ! ከእነዚህ የሰው ጅቦች እሸሻለሁ እኔ ልጃቸው ብሆን ነው ምን አደረኳቸው ? እሄዳለሁ እናቴ ጋር !! ማሚየ ጋ ድሮም የኔ የምንላቸውን ሰዎች ስንገፋ ነው ማንም እንደ ሆቴል በር ነፍስና ስጋችንን እየገፋ እንዳሻው ሲገባብንና ሲወጣብን የሚኖረው ሰው ብርም እውቀትም ቢቀር እንኳን አጉል አፈቀርኩ ብሎ የእኔ የሚለውን ዘመድ የእኔ የሚለውን ቤተሰብ የእኔ የሚለውን ታማኝ ጓደኛ መግፋት የለበትም ልክ ያስፈልጋል ፍቅር ሌላ ሌላው ህይዎት ሌላ ነው ሰው ራሱን ከወንዙ ነጥሎ ኩሬ ከሆነ ወይ መሻገት ወይ መትነን ነው እድሉ ማንም ሰው ደሴት ላይ መኖር አንድ ቀን ይሰለቸዋል አንድ ገፅ ብቻውን ህይወት አይሆንም እናቴ ጋር እሄዳለሁ ቤተሰቦቸ ጋር እሄዳለሁ እዛው እኖራለሁ እግዚአብሔር እንደገና በይቅርታ እጆቹ እስኪያነሳኝ ...ቤተሰቦቸ ላይ እወድቃለሁ!!

*** **** ******

እቤት ስደርስ እናቴና ሁለት ጎረቤቶቻችን ቡና እየጠጡ ደረስኩ እንደትልቅ ሰው ከወንበራቸው ተነስተው አገላብጠው ሳሙኝ "ሳቢየ ከየት ብቅ አልሽ በጠራራው " አሉኝ እማማ አስረበብ የሚባሉ ጎረቤታችን (ንግስት ሳባ ነው የሚሉኝ ከህፃንነቴ ጀምሮ ልእልት አይያዝላቸውም) እናቴ ልክ ትልቅ እንግዳ እንደመጣበት ሰው ጭንቅንቅ ብላ የሶፋውን ልብስ እያስተካከለች "ነይ ተቀመጭ ልእልቴ ምነው በጠራራው እናቴ" እያለች እንደልጅ ፊቴን በሸካራ እጇ ስትደባብሰኝ ሰው ፊት አላለቅስም ብየ እንጅ እንባየ ተናነቀኝ እናቴ እኔን አስቀምጣ ወደውጭ ብቅ እያለች "ወንዴስ ሳይገባ እንዳይሄድ የሱ ነገር " አለች ሁልጊዜ አድርሶኝ ስለሚመለስ ዛሬም እሱ ያመጣኝ መስሏት ነበር " እሱ አልመጣም ማሚየ ስራ በዝቶበት ሌላ ሰው ነው ያመጣኝ " አልኩ (ይሄ ውሻ እናቴ እንዲህ ስታከብረው የአባቱ ንቀት የባሰ ውስጤን እንደስለት ሲያቆስለው ተሰማኝ ) ስለደህንነቴ ስለወንዴ እየተቀባበሉ ከጠየቁኝ በኋላ ከመምጣጤ በፊት የጀመሩትን ወግ ቀጠሉ

እየው እንግዲህ አብርሽ ህይዎት በየቦታው ምድጃዋን ጥዳ የምረገጠውን ሁሉ እሳት እያደረገች ስትጠብቀኝ አለችና በግርምት አፏን እንደመያዝ አድርጋ እንዲህ አለችኝ " እነማሚየ ቤታቸው ከሶስት ወር በኋላ ለመንገድ ሊፈርስ ደብዳቤ ተሰጥቷቸው ሲጨናነቁ ነበር ለካ የደረስኩት በጭንቀት ጎረቤቱ ሁሉ የሚያወሩትም ይሄንን ነበር ጎረቤታችን እማማ አስረበብ ታዲያ በፍፁም የዋህነት ለማሚየ እንዲህ አሏት " አንችስ በደጉ ቀን ልጅሽ ደህና ሰው ጋር ተጠግታለች ህንጣውን ነው የምታቆመው የኔ ንግስተ ሳባ " እናቴ ዝም አለች እኔ ግን ጦር ነገር ልቤ ላይ የተሰካ ያህል ህመሙ እስካሁን ይሰማኛል !

እማማ አስረበብ ቀጠሉ "ሄሉም ብትሆን (ሄለን የልእልት ታናሽ እህት ነች ) ምን ቀራት እንግዲህ ...አሙቱ እንደሆነ ይሄዳል እግሯ ዩንበርስቲ ተረገጠ ጤናዋን ይስጣት እንጅ መመረቅ ነው " አብርሽ ዝም ብየ ጎረቤቶቻችን የሚሉትን ሰማሁ እናቴ ፊት ላይ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ተስፋ ነበር (በእኔ በልጇ መተማመን) ይታይህ እናቴ እና ዩኒፈርስቲ የገባች እህቴ የሚተዳደሩት ከዚቹ ቤት በሚገኝ ኪራይ ነው እሽ አሁን ፈረሰ ምንድን ነው ተስፋቸው? ሁሉም እኔን ነው ተስፋ ያደረጉት በዛ ላይ እህቴ ታማ ከዩኒቨርስቲ መጥታ ነበር አሁን ተሽሏት ልትመለስ እየተዘጋጀች ነው መቀሌ ዩኒቨርስቲ ኢኮኖሚክስ ነበር የምትማረው እህቴ ጎበዝ ተማሪ ናት በህይዎቴ ብቸኛ ተስፋ የማደርጋት እሷን ነው እሷን ማስተማር የመጨረሻ ምኞቴ ነው ደግሞ እንዴት እንደምታሳዝንህ ብታያት አብርሽ. ምግብ አትበላ ከቤት አትወጣ ሰው ጋር ፈታ ብላ አታወራ በቃ አቀርቅራ ማንበብ የመጨረሻ ከቤት ወጣች ከተባለ ቤተክርስቲያን መሄድ ነው እንኳን እኔ እህቷ ወንዴ ሲወዳት ልክ አልነበረውም (ዋሌቷን አውጥታ የእህቷን ፎቶ አሳየችኝ ጠይም ቆንጆ ልጅ ነች ከልእልት ቀጠን የምትል ) የእህቷን ፎቶ ስታሳየኝ እንባዋ ተዘረገፈ ልእልት ስታለቅስ ልቤ እየተነሳች ስትፈርጥ ይሰማኛል ! ምን ማለት እንዳለብኝም አላውቅም ! ፎቶውን ከመለስኩላት በኋላ ትክ ብላ ስትመለከተው ቆየችና በረዥሙ ተነፈሰችና ሄሉ ብቸኛ መመኪያ ነበረች አየህ ለወንዴ ጓደኞች እንኳን ስለሷ አውርቸ አልጠግብም ነበር እናተ ጋር ተቀምጩ ጫት ሳመነዝክ ብውልም ዩኒቨርስቲ የምትማር እህት አለችኝ

የምልላት እነሱ በቤታቸው ሃብት ሲኩራሩና ስለመኪናዎቻቸው ስለቤታቸው ሲያወሩ ብቸኛ በኩራት የምናገርበት ምክንያቴ ነበረች ሂሉ ማንንም ሰው ከጥፍር ቁራጩ የማይቆጥረው ኢያሱ እንኳን ሄሉን ሲጠራት በአክብሮት ነበር ! ምንጊዜም እኔን ሲያገኘኝ የወሬ መክፈቻው ሄለን ነበረች "ሄሉ ቆንጆ ደህና ነች " ይለኛል እንዲህ ሲለኝ ደስ ነው የሚለኝ !!

እንግዲህ "ትዳር ምናባቱ " ብየ በኩራት ቀና ብየ ኮብልየ የመጣሁት ልጅ ይሄን ሁሉ የቤተሰብ አደራ ተሸክሜ እና ጎብጬ ሾከክ ብየ ሲመሻሽ ቆልፌው ወደመጣሁት ቤቴ ተመለስኩ "ምናይነት እድል ነው " እያልኩ ! ማሚየ ፊት ኡኡ ብየ አልቅሸ ላፈሰው ያዘጋጀሁት እንባ በውስጤ ነዳጅ ሁኖ የተለኮሰ ይመስል በእልህ ጡፌ እና ተቀጣጥየ ነበር በዚች ምድር ላይ ይሄን ቤተሰብ መታደግ የእኔ ሃላፊነት ነው በቃ ይህን ለማድረግ ደግሞ ራሴን መታደግ ያውም አሁኑ ግድ ነው አልኩ !

ተመልሸ ወደቤቴ ገባሁ የሆነ ከገደል አፋፍ የተመለስኩ ይመስል እፎይታ ተሰማኝ ቤቴን እወዳታለሁ አብርሽ ለአንት ሴት ቤቷ ገዳሟ ነው እንዳይመስልህ ኬክ ቤት መዝናኛ ቦታዎች ሞልተን ስንገኝ ቤታችንን የምንጠላ ለሴት ልጅ ቤቷ ሉአላዊ ግዛቷ ነው ከቤቷ መገፋት ከአገሯ እንደመገፋት ነው እራሴ ወንዴ ጋር በወጣሁ ቁጥር እየመረጥኩ የምንገዛቸው ማንኪያ፣ ሹካ፣ ሰሃን፣ ብርጭቆ ትራስ፣ አንሶላ ሁሉም አፍ አውጥተው እንደልጅ በመመለሴ በደስታ የተንጫጩ መሰለኝ ይሄ የኔ ቤት ነው አልኩ ማንም እንደጥራጊ ገፍቶ የሚጥለኝ ልእልት አይደለሁም ምቹ ሶፋየ ላይ ቁጭ ብየ የሖነውን ሁሉ ረስቸ ነገሮችን ከየት እንደአዲስ እንደምጀምራቸው ማሰብ ጀመርኩ ከዛን ቀን በኋላ ወንዴ በማንኛውም ሰዓት ይመለሳል ብየ ብጠብቅም በተከታታይ ሳይመጣ አንድ ሳምንት አለፈው አልደወለም እንኳን ! ግን አሞት ቢሆንስ ብየ አሰብኩ እና አላስችል ብሎኝ ደወልኩ ስልኩ ዝግ ነው ለአባቱ ደወልኩ ስልኩን ዘጉብኝ ደግሜ ደወልኩ ዘጉብኝ ! እንግዲህ ስራ ላይ ሁነው ከሆነ ይደውላሉ ብየ ተውኩት በሰላሙ ጊዜ እንዲህ ደውየ ስልካቸው ድንገት ተይዞ ቢሆን እንኳን ዘግተው ነው ወዲያው የሚደውሉልኝ የነበረው እንዲቹ ስገረም ወንዴም እንደጠፋ እንደቀልድ አስር ቀን ሞላው ለጓደኞቹ በየተራ ደወልኩ አያነሱም አንዱ እንደውም ዘጋብኝ እኔ በህይወቴ የሚያቅለሸልሸኝ ነገር ቢኖር አብሮ በልቶ ጠጥቶ ችግር ሲፈጠር እንደውሻ ጅራቱን ሸጉጦ የሚጠፋ ጓደኛ የወንዴ ጓደኞች ጨርሰው ውሾች እንኳን ደውየላቸው አይኔ ሲያርፍባቸው የሚሽቆጠቆጡ ጓደኞቹ ገና ለገና ወንዴ ጋር ተጋጭተዋል ብለው ጀርባቸውን ሰጡኝ እኔኮ የሚገርመኝ የሃብታም ልጆች ናቸው አንዳንዶቹ "ደረስ ብየ ልምጣ" ብለው እዚህ ፒያሳ ደርሶ እንደመምጣት ኤሮፕ ደርሰው የሚመጡ ምንድነው እንዲህ ወኔያቸውን ሰልቦ ልክስክስ ጥገኛ ያደረጋቸው በእውነት የድሃ ልጅኮ ቆራጥ ነው

አብርሽ ! እነዚህ አንበሳ ገዳይ መስለው መኪናና ልብስ እያሳመሩ ውስኪና ጫት ቤት የሚያጣብቡ የሃብታም ልጆች እንዴት አይነት የጨቀየ መንፈስ መሰለህ ያላቸው ስልባቦቶች መሰሉህ "ኮንፊደንስ" የላቸው በመሃበር ተደጋግፈው ካልቆሙ ራሳቸውን ችለው ስልክ እንኳን መደወል የማይችሉ ድንዙዞች ስላበሳጩኝ ብቻ አይደለም አብርሽ ከሴት አቅም እንኳን በተፈጥሮ የተሰጣቸውን ማፍቀርና መፈቀር ጫት ላይ በመሃበር ካልተመከሩ ልባቸው አይከፈትም አውቃቸዋለሁ ይታይህ ቤቴ መፈንጠዣቸው ነበር በችግራቸው እህታቸው ነበርኩ ሰክረው ሲያስታውኩብኝ ሳልፀየፍ ያስታመምኳቸው ልእልት ነበርኩ ሲጣሉ ተቆጥቸ የማስታርቃቸው ነበርኩ ዛሬ ትዳሬ ችግር ላይ ሲወድቅ ሁሉም ሰምተዋል (በኋላ አውቂያለሁ እንደሰሙ) ግን ቢያንስ ስላሳለፍነው ጓደኝነት ሲሉ "ምን ሆንሽ ምን ላይ ወደቅሽ ልእልት " ማለቱ ይቅርና ስልኬን እንኳን ማንሳት ፈርተው በጫት ጉድጓዳቸው ተደብቀው ገፉኝ !!

## ክፍል 21

ወንዴ እቤት ሳይመጣ አስራ አምስት ቀን ሆነው እጄ ላይ ያለው ብር እያለቀ ነው ፍሪጅ ውስጥ ምንም የለም ባዶ ሆኗል ይሄም ሁሉ ብዙ አላስጨነቀኝም አንድ ቀን በጧት በሬ ተንኳኳ ምን እንደሆንኩ እንጃ በድንጋጤ ራሴን ልስት ነበር ወንዴ እንደሚሆን እርግጠኛ ነበርኩ ልቤ ተፈትልኮ የሚወጣ እስኪመስለኝ እየመታብኝ በሩን ከፈትኩ

ፊፅሞ አይቸው የማላውቀው እድሜው አምሳ የሚሆን አንዳች ሚያክል ጥቁር ሰውየ ነው ኮስተር ብሎ “ደህና አደርሽ” አለኝ

በሩን ልክ እንደራሱ ቤት ገፋ አድርጎ ወደውስጥ ሲገባ ከመደንገጤ ብዛት አፍጥጨ ከማየት ውጭ ምንም ማለት አልቻልኩም ሊፈራ መሰለህ እልፍ ብሎ ሶፋው ላይ ተቀመጠና ቀና ብሎ ተመለከተኝ ሰውየው ፊቱ ላይ በግራ በኩል ከጆሮው ጀምሮ እስከአገጩ የተጋደመው ጠባሳ ይዘገንናል ደግሞ የተቆጣ ይመስላል በክፉ አይኑ ነው የሚመለከተኝ በዚህ ድረሱልኝ ብየ እንኳን ብጮህ “ይበልሽ” የሚሉ ጎረቤቶች ባሉበት ፎቅ ምን ጉድ መጣብኝ ብየ አፍጥጨ አየሁት እሱም ቀና ብሎ አፈጠጠብኝ ጠባሳው ራሱ ሶስተኛ አይን ይመስላል ”ምንድነው እንዲህ ያለ አጓጉል ነገር እኔ ሰውላንተ እንደሆንኩ የሰው ብር የማልፈልግ የራሴንም ካለነገሩ የማልሰጥ ጨዋ ሰው ነኝ “ ብሎ አንገቱ ላይ ያሰረውን ማተብ አሳየኝ “ይቅርታ አላወኮዎትም” አልኩ እንደመንቀጥቀጥ እያልኩ ግን ትንሽ ተረጋግቸ ነበር መቸም ቀድሞ ማተቡን እያሳየ የሚደፍር የሚገድል ሰው የለም ብየ ...! “እሰይ እንዲህ አላውቅህም ብለሽ አሳርፊኝ “ ብሎ የግርምት ሳቅ ሳቀ ጥርሱ ስክክ ያለና ነጭ ነው የሌላ የቆንጆ ሰው ጥርስ ተውሶ የመጣ ነው የሚመስለው ጥርሱን ሳይ ደግሞ ለምን እንደሆን እንጃ ደግ ሰው መሰለኝ ” የምትኖሪበትን ቤት ባለቤት አታውቂም ...ሆሆ ...በይ አሁን ባለቤትሽ ካለበት ጥሪው ታልሆነም አንችው ኪራየን ስጭን ሳምንት ሙሉ እንዴት ኪራይ ዝም ይባላል ስልክ ስደውል እንዴት ይዘጋብኛል “ ብሎ አይኑን በቁጣ አጉረጠረጠ ”ይቅርታ አባባ ወንዴ ከባድ የቤተሰብ ጉዳይ ገጥሞት ሂዶ ነው ....እ...ነገ ይመለሳል ...ስልኩም የተዘጋው ለዛ ነው...እኔም አሁን እጀ ላይ ብር ባጋጣሚ የለም እባክዎትን ይቅርታ ያድርጉልን ነገ እኔ ራሴ ያሉበት አመጣለሁ እባክዎት ስልክዎትን ይስጡኝ “ አልኩ እንደመጣልኝ !ሰውየው አንዴ ወደላይ አንዴ ወደምንጣፉ ተመለከቱና በረኸርሙ ተንፍሰው የስልክ ቁጥራቸውን ነግረውኝ ደህና ዋይም ምንም ሳይሉኝ ተነስተው ወጡ ! ታምነኛለህ አብርሽ ቤቱ የኪራይ መሆኑንም በየወሩ እንደሚከፈልም እረስቸዋለሁ ሰዎች የቤት ኪራይ ተቸገርን ሲሉ የማውቀውም በፊልም ድራማ ምናምን ነበር አሁን ህዝብ እየሆንኩ ነው !! ወንዴ ስለኪራይ አንድ ቀን አውርቶኝ አያውቅም በውጭ ለሰውየው ይከፍላቸዋል መሰል እኔንጃ !

ሰውየው ከሄደ በኋላ ግራ ገባኝ የቤት ኪራይ ነገ እከፍለዎታለሁ ያልኩት ከየት አባቴ አምጥቸ ልከፍል ነው ስልኬን አንስቸ ለወንዴ ደወልኩ ስልኩ ዝግ ነው !! ለአባቱ ደወልኩ ዘጉብኝ !! እንዴ ወንዴ ጋር ተፋታን ማለት ነው ? መፋታት ከምር እንደዚህ ነው ? እንዲህ የምንሰፈሰፍለት ነፍሴን ስጋየን ማንነቴን ሁሉ ነገሬን ሰጠሁት አብሮነት መንገድ ላይ ድንገት እንዳገኙት ሰው እንኳን “ቻው “ ሳይባባሉ በመለያት ሊያከትም ማለት ነው ? እንዲህ ድግፍ ያሉት ሰው ባዶ ቤት በጀርባ አንጋሎ ትቶ መሄድ ነው መፋታት ? ለወንዴ አባት ደወልኩ ገና በአንድ ጥሪ ስልኩን ሲያነሱት ነፍሴ መለስ አለ

“አባባ “ አልኩ በስስት ልክ አባቴ ከሞት የተመለሰ ነው የመሰለኝ እያለቀስኩ ወንዴ ያደረገኝን ሁሉ ልዘረግፈው ከየት እንደምጀምረው ሳስብ አባቱ ቀድመው መናገር ጀመሩ ”አንች ልጅ ምነው ምነው ስርአት ቢኖርሽ ለምን በህይዎት ተረፈ ነው ? ለምን አንድ ልጅህ በብልግናየ ተበሳጭቶ ራሱን ካላጠፋ ነው ? ተይ እንጅ የሴት ወጉ ይኑርሽ ለሰሚውስ ምናይነት አይናውጣነት ነው ? ቤቱን ትቶልሽ ወጣ አይደለም በቃ ምን ትፈልጊያለሽ ?? ብትፈልጊ የምታግዣቸው ወንዶች ጋር እንዳሻሽ ማግጭበት ቢያሻሽ እቃውን ሻሽጠሽ ወደምትሄጅበት ሂጅ ሁለተኛ እንዳትደውይ ነግሪያለሁ ውርድ ከራሴ ልጀ አንድ ነገር ቢሆን ከነቤተሰብሽ አንላቀቅም ! ደም ነው የምንቃባው!! “ ብለው ጆሮየ ላይ ስልኩን ጠረቀሙት !!

ልእልት በመሃል ወጓን አቋረጠችና ቀና ብላ እያየችኝ “ደም መቃባት ምንድነው አብርሽ” አለችኝ አሳዘነችኝ ”ያው እገድልሻለሁ እንጋደላለን ምናምን ማለት መሰለኝ “ አልኳት ! ልእልት ዝም ብላ ቆየችና የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ሰው ብንን ብላ “ ወርቅ ጥሩ ነገር ነው “ አለችኝ አወራሯ ልክ ህፃን መሰለኝ ! ወርቅ ጥሩ መሆኑ ማን ይጠፊዋል...” አየህ በሰላሙ ቀን ወንዴ ወርቅ ልግዛልሽ ሲለኝ ሳቄ ነበር የሚመጣው በቃ ወርቅ የትልልቅ ሰዎች ነበር የሚመስለኝ ምኑም አያምረኝም ይሄ ቀለበቴ እንኳን ቀለበትነቱ እንጅ ወርቅነቱ ትዝ ብሎኝ አያውቅም ወንዴ

ያኔ ቆርቆሮም ጣቴ ላይ ቢያጠልቅልኝ ለውጥ አልነበረውም ማንኛውንም ነገር ውድም ርካሽም የሚያደርገው ነገሩ የተገኘበት ቦታና ጊዜ ነው ! እንደው ግራ እንደገባኝ ቁጭ ብየ መሸ ማታ ወደሁለት ሰዓት ቢጨንቀኝ ስልኬን አንስቸ ለእያሱ ደወልኩ አብርሽ ወንድ ልጅ ቢፈልግ ዱርየ ቢፈልግ ልክስክስ ወላ አስመሳይ ይሁን ግን በማንኛውም ባህሪው ውስጥ በትክክል ያለህበትን ሁኔታ ከተረዳ ያ ሱርየ ያ ልክስክስ ያ አስመሳይ ሰው ይሆነልሃል!! ምንድነው ሰው ማለት ሰው የሚሆን ነው ሰው የጠፋለት እንደሚባለው ኢያሱ ስልኬን አንስቶ "ወይየ ልእልት መቸም አታናግሪኝም ችግር ላይ ጥየሽ ጠፋሁ" ሲለኝ ኢያሱን በዚች ቃሉ በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ በላይ ወደድኩት ! ተወው ባህሪውን ወደድኩት በዛች ቅፅበት ኢያሱ አጠገቤ ቢሆን ብየ ተመኘሁ ዝም ብየ ሰማሁት ንግግሩን ባያቋርጥ ደስታየ "ልእልት አለሽ" አለኝ ....

አለቀስኩ በቃ አለቀስኩ ስቅስቅ ብየ ስልኩን ሳልዘጋው አለቀስኩ ኢያሱ በቃ ተጨናነቀ "ምን ሁነሽ ነው ልእልት እባክሽ ስሚኝ ይለኛል ስልኩን ዘግቸው በቃ ስቅስቅ ብየ አለቀስኩ ፀጉሬን ብነጭ ደስታየ ፊቴን ብተለትለው ደስታየ ብነግርህ የማይገባህ ብስጭት ደግሞ እዚህ ላይ (ከጡቷ ዝቅ ብሎ ያለውን ሰውነቷን ክፍል በመዳፏ ይዛ እያሳየቸኝ) ሃይለኛ ህመም ለሁለት እጥፍ የሚያደርግ የሚያቃጥል ነገር አመመኝ በቃ ሞቴን ተመኘሁ ለኢያሱ ደወልኩት "ለልመና" ነው በቃ የቤት ኪራ ገንዘብ እንዲመፀውተኝ ነው

ትላንት ኢያሱ እግሬ ስር ወርቅ ቢያነጥፍ ዞሬ የማላየው ልጅ ነበር አየህ የምትወደው ሰው ሲገፋህ ነው የትም ማንም እግር ስር በግንባርህ የምትደፋው ለምን እገፋለሁ ለምን ለማኝ እሆናለሁ ባፈቀርኩ እንደሰው አላማ ይኑረን እንደሰው ከጥገኝነት እንላቀቅ ባልኩ ለምን አብርሽ "

እንባዋን ጠረገች ልእልት ከማልቀሷ ብዛት የምትሟሟ እስኪመስለኝ እዚች አገር ላይ በወንዶች ክህደትም ሆነ በየቤቱ በሚፈጠር ቁርሾ የሚፈሰው የሴቶች እንባ ቢጠራቀም ሌላ አባይ ሳይፈጠር አይቀርም እስቲ የቤቷን የጓዳዋን የአመታት እንባ ትተነው እኔ ጋር ከተዋወቅን እንኳ ልእልት ያለቀሰችባቸውን ጊዚያት ብንደማምራቸው

አየህ ስልኩን ከዘጋሁት በኋላ አንድ ሰአት እንኳን የቆየሁ አይመስለኝም በሬ ተንኳኳ ቀጥ ብየ ሂጀ ከፈትኩት አየህ ብዙ ሰዎች የተገፋች ሴት ጨካኝ ናት ደፋር ናት ይላሉ አይደለችም የሴት ልጅ ህይዎት ውስጥ ፍርሃት ውብቷ አንድ አካል ነው አንዲት ሴት ፍርሃት የሚባል ነገሯን ሁሉ ጣጥላ ላንኳኳ ሁሉ በሯን ያውም በጨለማ ከከፈተች የሚመጣው ሞት ቀድሞ ውስጧ ከተቀመጠው ተስፋ መቁረጥ በታች ሁኗል ማለት ነው ! ከፈትኩት በሩን ኢያሱ ነው ምን ኢያሱ ነው ይሄ መለአክ ነው እንጅ እንባየ አስጨንቆት ሲከንፍ የሚደርስ ሰው ምኑ ላይ ነው አስመሳይነቱ ለምኑ ነው ስፈራ የኖርኩት ለሴትነቴ ? ምንድነው ሴትነት የማንም ደደብ እንጀራና ጫት ደመዎዝ እየከፈለ እንደከፈን ድሪቶ እያለበሰ እንዳሻው ሲያደርገው የኖረ ሴትነት ምኑ ብርቅ ሁኖ ነው ይሄን ያህል ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ? አንዱ ተንሰፍስፎ ያገኘው እስኪሰለቸው የተጫወተበት ስጋየ ሲሰለቸው ባዶ ቤት እንደተቀደደ ምንጣፍ ረግጦ ትቶት የወጣው ስጋ ሌላ ምን አለኝ ? እንኳን ስጋየ ነፍሴም እግዚአብሔር ወሰዳት ሰይጣን ዋጋ ምታወጣ አልነበረችም ለኔ ማንም ሰው የሆነ ቀን ቁሞ የሚሄድ ምንም የሚሆንበት ጊዜ አለ

በዛች ቅፅበት ኢያሱ በቆምኩበት ፒጃማየን ቢያወልቀው ተው አልለውም ነበር ብዙ የዋህ ወንዶች አንዲትን ቆንጆ ሴት በዚህ ሰዓት ሲያገኟት ለእነሱ ትልቅ እድል ትልቅ የማሳመን ችሎታ ትልቅ አማላይነት ተፈላጊነት ምናምን ይመስላቸዋል ግን ሁሉም አይደለም ማንኛዋም ሴት የሆነ ጊዜ በሆነ ምክንያት ከፊቷ የቆመው ሰው ይሁን ግድ ግድ የማይሰጥባት ጊዜ አለ !! ልክ አጋጣሚ የገደላትን ሴት ሬሳ እንደመንተት በለው ! ዝም ብየ አየሁት ኢያሱን በር ላይ ፊት ለፊት ስገተርበት ግራ ገብቶት ነው መሰል አንገቱን አስግጎ ወደውስጥ ተመለከተ ሰው አለ እንዴ ብሎ በሩ እንደተከፈተ ትቸው ወደቤት ገባሁና በቁሜ ሶፋው ላይ ተወዘፍኩበት ኢያሱ ቀስ እያለ ተከትሎኝ ገብቶ በእጅና እጁ ትከሻየን ይዞ በጭንቀት አየኝ አብርሽ ኢያሱን የዛን ቀን ብታየው እንዴት እንደሚያሳዝንህ ያ ረዥም ቁመቱ እጥፍጥፍ ብሎ ምንጣፍ ላይ ከፊቴ ተንበርክኮ ሲያባብለኝ ኢያሱ ድሮ ማን እንደነበር ለምን እንደጠላሁት ሁሉ ጠፋኝ ራስህን ከጠላህ የጠላሃቸውን ሁሉ ትረሳቸዋለህ...!!

“ ወንዴ ትቶኝ ሄደ ምንም አላደረኩትም ወንዴን እወደዋለሁ አባቱ ሰደቡኝ “ አልኩት ”ተያቸው እነሱን ልእልት አሁን አንች ተረጋጊ ” አለኝ ድምፁ ውስጥ እንዴት ደስ የሚል ወንድነት አለ የሆነ ማንም ቢሄድ ቢመጣም እኔ አለሁልሽ የሚል ድምፅ ! ቀጥ ብየ አየሁት ኢያሱ አዲስ ሰው ሆነብኝ ታምነኛለህ አብርሽ አይኖቹ እንባ ቋጥረው ነበር !!

“ማን ኢያሱ ?” አልኳት ተገርሜ

“ገረመህ አይደለ እኔም ልክ እንዳሁኑ እንዳንተ ነው የገረመኝ.” አለችና ፈገግ እንደማለት ብላ ”ግን ከምር ኢያሱ ሊያለቅስ ምንም አልቀረውም የሆነውን ሁሉ ነገርኩት ቤት አከራዩ ሰውየ መምጣቱንም ነገርኩት “

“ በቃ አታልቅሽ ... እኔ በጧት እመጣና አብረን ሰውየው ቤት እንሄዳለን ከዚህ በኋላ አትጨናነቂም የስድስት ወር ኪራዩን ወርውረንለት እንመጣለን እሽ ልእልትየ “ ይሄን ሁሉ ሲለኝ ፊቴ ተንበርክኮ አይን አይኔን እየኝ ነው ” አሁን ተነሽና ወተት ጠጭ በቃ ነቃ ብለሽ አሪፍ እንቅልፍ” ብሎኝ ተነስቶ ወደፍሪጁ ሂዶ ከፈተው ወተት እንደምወድ ያውቃል ፍሪጁ ባዶ ነው ኢያሱ ደነገጠ የፍሪጁን በር እንደያዘ በግርምት ወደኔ ዞሮ ተመለከተኝ “ ምንም ሳይናገር ፈሪጁን ዘግቶ ወጥቶ ሄደ ፊቱ ላይ የነበረውን ሃዘን ብታይ አብርሽ ኢያሱ አይመስልህም ቆይቶ ሲመለስ ፌስታል ሙሉ የታሸገ ወተት ዳቦ ....”ቴክ አዌ” ፒዛ “ ተሽከሞ መጣ ዝም ብየ አየዋለሁ ኪችን ገብቶ ብርጭቆ አወጣ ወተት ቀዳ ፒዛውን የሆነ ሰሃን ላይ አወጣና ፊቴ መጥቶ ተቀመጠ ብርጭቆውን አቀበለኝ ወተቱን እና ፒዛውን ሳይ ርሃቤ ክፉኛ ተቀሰቀሰ ሙሉ ቀን ምንም እንዳልቀመስኩ ትዝ አለኝ ! ዝም ብየ መብላት ጀመርኩ ኢያሱ አምሽቶ ሌላ ሌላ ወሬ አውርቶኝ እንደውም ያኔ ምን እንዳለኝ እንጃ እንጅ አስቆኛል ሁሉ !

ሊሄድ ሲል ስንት እንደሆነ ያላወኩት የተጠቀለለ ብር “ለማንኛውም” ብሎ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦልኝ ወጣ !! ሲሄድ አልሳመኝም ለምን እንደሆነ እንጃ ቶሎ መውጣት ፈልጎ ነበር አሳዘነኝው ይሆናል እኔጃ !! ኢያሱ በቀጣዩ ቀን መጣና ማታ እንዳለው ሰውየው ጋር ደውለን ሰፈራቸው ሄድን የስድስት ወር ኪራይ ስንሰጣቸው ማመን አልቻሉም ያ ማታ ያስፈሩኝ ሰውየ ከነዘር ማንዘሬ መርቀው ሸኙን !! ስንመለስ ምሳ ሰአት እስከሚደርስ ኢያሱ እንዲሁ ሲያዞረኝ ዋለ ደስ አለኝ ከተማው አዲስ እስኪሆንብኝ ምሳ ሰአት ሲደርስ የሆነ አይቸው የማላውቀው ቤት ወስዶ ምሳ ጋበዘኝ ታምነኛለህ አብርሽ ሃዘኔን ሁሉ ረሳሁት ! ምሳ በልተን እንደወጣን ኢያሱ ዝም ብሎ ወደሆነ ሰፈር ይዞኝ ሄደ የት ነው የለ ምን የለ ዝም ብየ የሚወስድብኝን ማየት ብቻ አንድ ትልቅ ግቢ ያለው ቤት ስንደርስ ገባንና የሚገርም ቪላ ውስጥ እየመራ አስገባኝ ሰራተኛ ብቻ ነች ያለችው አስተዋወቀን “ወ/ሮ ልእልት ትባላለች የጓደኛየ ባለቤት ነች ቡናሽ አሪፍ እንደሆነ ሰምታ ነው የመጣቸው” አላት አነጋገሩ ሁኔታው የሆነ ዝም ብሎ ቤተሰብ የሚያደርግህ አይነት ነው ልጅቱ መምጣቴ ደስ ብሏታል ከምኔው እንዳቀራረበችው እንጃ ቤቱን በእጣን ጭስ ሞላችው ቡናው ፈላ ”ይሄን ይመስላል ቤታችን ልእልት” አለኝ እያሱ ፊት ለፊቴ ተቀምጦ የሶፋውን ትራስ እንደአሻንጉሊት አቅፎ እያየኝ ”ያምራል “ አልኩት ከልቤ ነበር

“ አባትና እናቴ ተያይዘው ኤሮፕ ሂደዋል ታላቅ እህታችን ወልዳ ምንድን ነው የሚባለውን ሊያደርጉ” አለ ...ሰራተኛዋ ፈጠን ብለው “ሊያርሱ” አለች ተሳሳቅን ! ኢያሱ ረጋ ያለ ልጅ ሆነብኝ ያ የማውቀው ኢያሱ የት ሄደ እስከምል በዚች ቅፅበት ስልኬ ጮኸ ከቦርሳየ አውጥቸ ሳየው ማመን አልቻልኩም ማ መ ን አልቻልኩም አብርሽ ማን ቢሆን ጥሩ ነው ....ወንዴ !!

## ክፍል 22

ውሃ በተሞላ ብርጭቆ ውስጥ ማንም ውሃ መጨመር አይችልም ፍቅር የተሞላ ልብም ማንንም ማፍቀር አይችልም ሁለት ሰዎች ከተፋቀሩ ብቸኛው ምክንያት ሁለቱም ልብ ውስጥ ያለው ክፍተት ነው ሊሆን የሚችለው ! ልእልት እኔ እንዳፈቀርኳት ካፈቀረችኝ ሲጀመር የፍቅር ፅዋዋ ጎደሎ ነበር ማለት ነው ! አይ ባለትዳር ስለሆንሽ የፍቅር ኮታሽን ጨርሰሻል የሚለው ማነው ማንም ሰው ፍቅር ከያዘው ማንም ጋር ይጋባ ማንም ጋር ይሁን አብሮ

ነበር እንጅ አንድ ላይ አልነበረም !! አብሮ በመሆን ውስጥ ስንት አይነት መለያየት አለ አንዳንዴ ያፈቀርነውን ሰው ጉድለት ልንሞላ ያለንን ሃይል ሁሉ አንጠፍጥፈን ተፈቃሪውም ሳይሞላ እኛም ባዶ ሁነን የምንቀርበት ስንት ሰቆቃ አብሮነት አለ እና ምንድነው የሚያስጨንቀኝ ልእልት ጋር ማውራት አልደከመኝም አይደክመኝም ስታወራኝ አፏ ጥግ ከናፍርቶቿ ግርጌ ተደቅኘ በጉጉት ነው የምሰማት ሁልጊዜ እንደአዲስ የሚጀመር ታሪኳ በትረካ እግሩ የትም ረግጦ ማረፊያው እኔ እሆን ይሆናል የሚል ተስፋ ታሪኳ ጋር ሲያናውዘኝ ከከናፍርቷ የሚወጡት ቃላት በአንዳች ክር ከእኔ ፍርቱና ጋር ይቋጠሩ ይሆን ብየ ነው ስሰማት የኖርኩት ያውም ለልብ ድካም የሚዳርግ ተስፋ ውስጤን እየናጠኝ አንዳንዴ እንደፈልም እንደሙዚቃ "በሪሞት ኮንትሮል" የልእልትን ታሪክ ማሳለፍ ቢቻል ባንዴ አሳልፌው ዛሬ ምን ላይ ነሽ ነገስ የእኔና የአንች እጣ ፋንታ ምን ይሆን ማረፊያው የሚለውን ማየት እመኛለሁ ጭንቀት አልፈልግም፣ ሃሳብ አልፈልግም፣ ሞራል አልፈልግም፣ ህግ አልፈልግም፣ ሃይማኖት አልፈልግም፣ የምፈልገው ልእልትን ዝም ብየ ማፍቀር ነው !! ካለምንምና ካለማንም ገደብ!! አይኖቿን ማየት ምንም ታውራኝ ስታወራኝ ማየት !! ባለትዳር ነች አውቃለሁ ባለትዳርን ማግባት እንጅ ማፍቀር አይቻልም የሚል ህግ የት አገር ነው ያለው ? ቢኖርም የራሱ ጉዳይ ስሜቴን አፍኘ ባለትዳር ስለሆንሽ ካንች ጋር አልነከካም የሰው አፍ ቢስተኝ የግዜር ቁጣ በመብረቅ ያደባየኛል "ጎመን በጤና" ብየ በየደይቃው የሚያስበረግገኝን ስጋት ነግሪያት የተጨበጨበለት ጨዋ መሆን እችላለሁ ! "ዋው እሱ የህሊና ሰው" መባል እችላለሁ ! እሱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው መባል እችላለሁ ግን ፍቅር የነፍስ ሃቅ ነውና እድሜ ልኬን የሆነች ልጅ ስናፍቅ መኖር አልፈልግም እንኳን ካሁን በኋላ ለናፍቆት ራሴን ላስማርከ ቀርቶ ሳላውቃት ስናፍቃት የኖርኳት ልጅ እሷ እየመሰለችኝ ሳስበው ያለፈው ትላንትም ይደክመኛል !! ደግሞ ልቤ ላይ ያለው ፍቅር የሚነግረኝ ይሄንኑ ነው

ልእልትን "ቻው" ብየ እስከአለም ጥግ መሄድ እችላለሁ የሆነ ስርቻ ውስጥ መደበቅ እችላለሁ የሆነች ሴት እቅፍ ውስጥ ተሸጉጨ "ተውኩሽ" ማለት እችላለሁ ግን ልእልትን ከልቤ ከህሊናየ ከአንደበቴና ከትዝታየ ስንዝር ማራቅ አልችልም አፍቅሪያታለሁ !! ልቤ ተወጣጥራ ከተወሰኑ ደይቃዎች በኋላ ልትፈነዳ የተዘጋጀች የሰአት ቦምብ ትመስለኝ ከጀመረች ቆየች !! እያንዳንዱ የልብ ምቴ ፍንዳታውን ለማብሰር ቁልቁል የሚምዘገዘግ ቁጥር መሰለኝ ...10...9...8...7.... 6...... እንደዜሮ ሩቅ ቁጥር የለም ወደዛ ፈንድቶ በበታተነኝና ባረፍኩት እንደዚህ ሁኘ አላውቅም አፍቅሬ አውቃለሁ ግን እንደዚህ ሁኘ አላውቅም! እንደውም ይሄም ፍቅር ያም ፍቅር ከሆነ ያለፈው ፍቅሬ እቃቃ ጨዋታ ነበር !!

ትንፋሽ ያጥረኛል ሃሳብ ያጥረኛል በዚች አለም አጠረኝ ተብሎ የማይቆም ነገር ቢኖር ሃሳብ ነውና ልእልትን አስባታለሁ ሳላቋርጥ በቀን ሁሉንም ጊዜ አስባታለሁ ! በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ ፍርሃት ውስጥ አርጅቶ እንደቆመ ታንከ አፈሙዙን ዘቅዝቆ የኖረ የዛገ እኔነቴ ልእልትን ሳስብ ያንሰራራል አፈሙዙ ተቃንቶ ፊት ለፊቴ ወዳለው የብቸኝነት ተራራ የመገለል ግርዶሽ የልእልትን ፍቅር እንደጥይት ጎርሶ ሲተፋውና ሲያፈራርሰው ይታየኛል ለምን ቆንጆ ስለሆነች ነው ? አይደለም!! ከምር አይደለም! ያፈቀርኳት ስላወራችኝ ነው ልእልት ስታወራኝ የምታደምጠኝ ነው የሚመስለኝ ህይዎትን ስንዝር በስንዝር የምታይበት ጥልቀት አይኖቿ እኔ ላይ እንዲያርፉ ያስመኘኛል ያሳለፈችውን ስቃይ የማትረሳ ሴት የሚመጣውን ፍቅርም ለመቀበል ብዙ ቦታ በልቧ እንዳለ ነፍሴ ሹክ ይለኛል !! ደግሞ ባለፈችበት የሰቆቃ ህይዎት ሁሉ እኔ አብሪያት ስላልነበርኩ እራሴን እወቅሳለሁ አይገርምም ? ከዚህ በፊት የማላውቃት ሳይሆን እያወኳት እኔን አምና አድነኝ እያለች ልብሴን ስትጎትት ጀርባየን የሰጠኋትና በእኔ ቸልተኝነት ይሄ ሁሉ ቆሻሻ ችግር የደረሰባት እየመሰለኝ እራሴን እወቅሳለሁ ከዚህ በኋላ በዚች አለም ከእኔ ውጭ ጠባቂ የሌላት ትመስለኛለች !! ቢሆንም ልእልት ስታወራኝ እሰማታለሁ ቃል በቃል ነጥብ በነጥብ ትንፋሽ በትንፋሽ ! እሰማታለሁ ሳይሆን አጠናታለሁ ! ጣቷ ላይ ካለው የቃል ኪዳን ቀለበት የጠነከረ አንዳች ሰንሰለት ነገር ልባችንን ያስታሳሰረው እየመሰለኝ በዚች ምድር ላይ ሁሉንም ነገር እንቃለሁ ከእርሷ በስተቀር! በማፍቀሪያ እድሜዋ ይሄን ሁሉ የተንዠላዘለ መራር ታሪክ የሞላት ማነው እሰይ እንኳን አፈቀርኳት ባለትዳር አፈቀረ ብለው እርኩስ ይበሉኝ ሰዎች ከፈለጉ ሰልፍ ይውጡ !! ፎቶየን በየመንገዱ እያቃጠሉ ይቃወሙኝ ! አለም እኔን አስመስየ ከሚቀድሰኝ እውነቱን ለራሷ ነግሪያት ሲያረክሰኝ ይኑር

ሲጀመር ልእልት ያገባችው ባሏን ስለወደደችው እንጅ አብርሃም ከሚባል ልጅ ለመሸሽ ብላ ነበር እንዴ ?? ታዲያ ምንአባቱ ሁኖ ነው ህሊናየ የሚነተርከኝ ?? የልእልትን ትዳር ፈርቶ ? የህዝቡን አፍ ፈርቶ ? ነገ የሚሆነውን ፈርቶ ? ወይስ ፍርሃቱ በልእልት በኩል ይሆን በዛ ብሽቅ ባሏ የደረሰባት ግፍ ነገ ፍቅር ቀዝቅዞ በእኔም እንዳይደርስባት ልእልት ፈርታ ? ፈርቶ ፈርቶ ኤጭ ይሄ ህዝብ የሚኖረው ፈርቶ የሚሄደው ፈርቶ ! ደግሞ የእኛ አገር ትዳር እንደባህር አልጌ የተዝለገለገ እልፍ ጅራት እልፍ እግር የከበበው እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ማን ማንን ለምን እንዳገባው እርግጠኛ ሁኖ የሚናገር ማነው ? የዚች ልጅ ነገር ሊያሳብደኝ ነው ባለትዳር አፈቀርኩ እሷ ራሷ ባለትዳር ነኝና ካጠገቤ ጥፋ የማትለኝ ለምንድን ነው?? እኔስ ይሄን በውስጤ የሚደነፋውን የጓዳ ጀግንነቴን አውጥቸ የማላፈርጠው ለምንድን ነው እሽ ሌላው ሁሉ ይቅር መናገሩም ይቅር ልእልትን መራቁም ይቅር ግን እንዴት ማበድ ያቅተኛል ? ከምር አሁን ያማረኝ ማበድ ነው!! እሱም ቁም ነገር ሁኖ ጠፋብኝ !! ማንኛውም እብድ ድንጋይ ወርውሮ መስተዋት ከመስበሩ በፊት እራሱን ከማንኛውም ሰዋዊ ክብር ወርውሮ ያለፈ ህይወቱን የሚያሳየውን መስተዋት ያንኮታኩተዋል !! ትላንትን ዛሬን ነገንም ልረሳ እብደት እንድመኝ ያደረገኝ ምንድነው? የልእልት ፍቅር ነዋ !! ደግሞ የታሪኳ መከፋት .... እንዲህ ስትል ቀጠለች ....

*** **** ***

ኢያሱ ጋር ነፍሳችን የተቀራረበ ይመስለኛል ባለጌም ጨዋም ይመስለኛል ደሃም ሃብታምም ይመስለኛል ቆንጆም መልከ ጥፉም ይመስለኛል ኢያሱም ወንዴም ሲመስለኝ ነበር ለራሴ የደነገጥኩት ! አንድ ወንድ ጫማው ሳይሆን መነፅሩ ሳይሆን ከረቫትና ሱፉ ሳይሆን መኪናና ሃብቱ ሳይሆን ነፍሱ ባሌን ሲመስለኝ ነገር ተበላሸ !! ደመራ የሆንኩ መሰለኝ ግራ በመጋባት እሳት ተለኩሸ ህዝብ ከቦ ወደ ኢያሱ ከወደቀች ሲሳይ ነው ወደወንዴ ከወደቀች ዘመኑ ጦርነት ነው እያለ የሚተነብይብኝ ወዴትም ሳልወድቅ ወይ እንደጭስ ወደላይ ብን ብየ ብጠፋ ወይ እንደውሃ ወደመሬት ሰርጌ እልም ብል ደስታየ ነው !! እና እንዲህ ሳስብ እነኢያሱ ቤት ተቀምጨ የጠፋ ባሌ ወንዴ የሚባል ደወለ ስልኩ አላስደነገጠኝም እንደውም ከአንድ ደይቃ በፊት ደውሎልኝ ስናወራ የቆየን እንጅ ያንን ሁሉ ቀን ባዶ ቤት ጣጥሎኝ የጠፋ ባሌ አልመስልሽ አለኝ ስልኩን አነሳሁት

..."ልእልት " አለኝ

"አቤት "አልኩት በቃ ልክ እንደዚህ ነበር የጠራኝ እንደዚህ ነበር አቤት ያልኩት ደንግጦ ነው መሰል ትንሽ ዝም አለ አዎ ደንግጦ ነው ሲደውል ትንፋሽ ነበራ የሚያጥረኝ እንኳን ርቆኝ የሆነ ነገር ሊገዛ ወጣ ብሎ እንዲገዛ የነገርኩት ነገር ጠፍቶበት ሲደውል ተንሰፍስፌ ነበራ የማናግረው ሲጠራኝ አቤት ብየው አላውቅም እኔ ወንዴን "አቤት" አልኩት ማለት ስድብ ነበር በምድር ላይ ለቁልምጫ ሁሉ የማይበቃኝ ነበርኩ ለወንዴ !! ለዛ ነው ዝም ያለው እና ትንፋሹን ሰብስቦ እንዲህ አለኝ

"ማነው የቤት ኪራይ የከፈለልሽ ወንድ ?" አብርሽ ታምነኛለህ በዚች ቅፅበት ማስመሰል መደባበቅ ምናምን ከውስጤ ጥርግርግ ብለው ጠፍተው ነበር እና መለስኩለት

"ኢያሱ "

"ኢያሱ ?!"

"አዎ ኢያሱ "(ድምፁ ጥያቄም ምንም አልነበረም ኢያሱ የሚባለውን ስም የት ነው ሰማሁት የሚል ነበር የሚመስለው)

"አሁን የት ነሽ "

" ኢያሱ ቤት ቡና እየጠጣን " ስልኩን ጆሮየ ላይ ጠረቀመው ምንም አልመሰለኝም ገና ስልኬን ወደቦርሳየ ስመልስ መልሶ ደወለ አነሳሁ

..." አሁኑኑ እቤት ላገኝሽ እፈልጋለሁ "

"እሽ" ምንም አልተሰማኝም ተረጋግቸ ኢያሱ እንዲሸኝኝ ነገርኩት ገብቶታል አላንገራገረም

ኢያሱ ግቢ አድርሶኝ "ልእልት እራስሽን ጠብቂ" ብሎኝ ተመለሰ ለምን እንደሆነ እንጃ ሲሄድ ቅር አለኝ የፍቅር አይደለም ወንዴን የመጥላትና ወደ ኢያሱ የመቅረብ አይደለም ኢያሱ ልቤ ውስጥ ጭው ባለ ምድረበዳ ከሩቅ እንደሚታይ ብቻውን እንደቆመ ግራር አይነት ገዝፎብኝ ነው ! ከጥላው ስትርቅና ወደፀሃይ ስትገባ የሚሰማህን ቃጠሎ በመፍራት ጥላውን የመፈለግ አይነት ስሜት ደረጃውን ስወጣ ኬት እንደመጣ ያላወኩት የፍርሃት ስሜት ድንገት ወረረኝ ወንዴ እቤት ውስጥ እንዳለ ሳስብ ጉልበቴ ተንቀጠቀጠብኝ በር ላይ ደርሸ ቁልፉን በሩ ላይ ልሰካ ስሞክር ሁለት ጊዜ የቁልፉን ቀዳዳ ሳትኩት በሶስተኛው ስሞክር በሩ ተከፈተና ወንዴ ፊቴ ተጋረጠ አይኖቹ ፍም መስለው ቀልተዋል ፀጉሩ ተቆርጦ ካለወትሮው ሸክ ብሎ ዘንጧል ከሰውነቱ ላይ የሚተነው ሽቶ ድፍን ሰፈሩን የሚያውድ ነው የሚመስለው (ወንዴን ሳውቀው ለሽቶ ያለው ፍቅር ብዙም አልነበረም ) ሳላስበው ጎትቶ ወደውስጥ አስገባኝ በሩን በፍጥነት ቆልፎ ተመለሰ እራሴን አቅፌ መሃል ሳሎን ላይ እንደእንግዳ ቁሚያለሁ ቦርሳየን መንጥቆ ወረወረው የለበስኩትን ሸሚዝ ከላይ ይዞ ግራና ቀኝ ሲመነጭቀው ቁልፎቹ ተነቃቅለው እየተፈናጠሩ ምንጣፉ ላይ ወደቁ የጡት ማስያዣየን ከምኑ ላይ እንደበጣጠሰው እኔጃ በሴኮንዶች ውስጥ እራቁቴን ፊቱ ተገተርኩ ለምርመራ ልብሴን አወላልቄ ሃኪም ፊት አልያም ለወንጀል ምርመራ ርቃኔን ገራፊ ፊት የቆምኩ መሰለኝ!! ወንዴ ጎትቶ ምንጣፉ ላይ አስተኛኝ (ጣለኝ ብል ይሻላል) ከዛ በሆነው ነገር ሁሉ እንደታዛቢ ከስሩ ተኝቸ እገረማለሁ ወንዴ ጭራቅ ሆነ አንዳችም ስሜት አልተሰማኝም እንደውም ለምን እንደሆነ እስከዛሬም ባልገባኝ ምክንያት በዚህ አጉል ሰአት ኢያሱን እያሰብኩ ነበር !! ኢያሱ ሶፋው ላይ ተቀምጦ በእጣኑ ጭስ ውስጥ ፈገግ ሲል ታየኝ ኢያሱ ቡኒ ጫማ በነጭ ካልሲ አድርጎ ነበር ኢያሱ የቀኝ እጁ አንጓ ላይ ከብር የተሰራ ቀጭን ብራዝሌት አድርጎ ነበር ኢያሱ የሸሚዙ ቁልፍ ተከፍቶ ቀይ ደረቱ ላይ ያለው ፀጉሩ ይታይ ነበር ቡና ሲጠጣ ገና ቡናውን ፉት ሲል ፊቱ ግራዋ እንደጠጣ ሰው ሲኮማተር አይቸዋለሁ እንዴ. ኢያሱኮ ቡና አይወድም ነበር ታዲያ የዛን ጊዜ እቤት ሲመጣ አሁንም እቤታቸው ስሄድ እንዴት ቡና ጠጣ?? እኔ ጋር ስለሆነ እኔ እንድደሰት ?? ወንዴ እንደመርግ እላየ ላይ ተከምሮ አንገቴ ስር ተሸጉጦ እያለቃቀሰ "አፈቅርሻለሁ ልእልትየ " ሲል ሰማሁት (ሰው እየፎከረ ሂዶ እያለቀሰ ሲመለስ እንዴት ያበሳጫል ማንኛዋም ሴት ውስጥ እንዲህ አይነቱ ወንድ ልጅ ሽንፈት የሚፈጥረው ኩራት አለ እኔ ውስጥ ግን የመረረ ጥላቻ ነው የተፈጠረብኝ የማፈቅረውን ልጅ አፈራርሶ አመጣው ይሄ የማይረባ ) ኤጭ ጠረኑ ደግሞ ምንምንድነው የሚለው ፍየል !! ያ ሁሉ የተነከረበት ሽቶ እንኳን አላገደውም ! ፍቅር እውር ብቻ አይደለም አፍንጫንም ነው የሚደፍነው ባይሆን ኑሮ እዚህ ጠረን ጋር አንድ ቀን ማደሬም ተአምር ነው !! (ስለጠላሁት አይደለም ያኔ የተከፈተ አፍንጫየ ከዛ ቤት እስከወጣሁበት ቀን ድረስ ያረጋገጠልኝ ነገር ይሄንኑ ነው ) ከምር አንገሸገሸኝ አቅሙ ቢኖረኝ ወደላይ ወርውሬው ኮርኒሱ ጋር ባጋጨው ደስታየ ወንዴ ከውስጤ ታጥቦ እንደወጣ የተሰማኝ ያኔ ነው ሙሉ ሰውነቴ እሱን ተርቦ ሲያዛጋ እንዳላየ አርፎ ቆሻሻ ቅናቱ ገፍትሮት እንደጥንብ አንሳ በሃዘን የሞተ ስጋየ ላይ ሲከመር ዘገነነኝ ታዲያ እላየ ላይ ተከምሮ እንዳሻው እንዲሆን የምፈቅደው ለምንድን ነው አየህ አብርሽ በዚች ምድር ላይ አንደኛ አስደሳቹ ነገር ወሲብ ሲሆን አንደኛ ዘግናኙና አስቀያሚው ነገር ደግሞ ራሱ ወሲብ ነው !!

እንደሰው የራሱን ሲኦል መፍጠር የሚችል ፍጥረት በዚች ምድር የለም የትኛውንም ሰላም የትኛውንም ፍቅር ወደጦርነት መቀየርን ደግሞ እንደኛ ወንዶች የተካነ ፍጥረት የለም !! ጭር ሲል ያማችኋል ፍቅር የቅናትና የእሰጣ ገባ ምርኩዝ ላይ ካልቆመ ጤነኛ አልመሰል እያለው ጤናውን የሚያጣ ወንድ ጋር ስጋባ ቀለበቱን ያሰርነው ገነት ነበር የጫጉላ ሽርሽራችንን ሲኦል ያደረገው በእሳት የተፈተነ ፍቅር ፈልጎ ሳይሆን አፍቃሪው ጀርባ ላይ እሳት አለንጋ እያሰረፈ የበታችነቱን የልቤ ጀርባ ላይ ለመፃፍ ነው ተሳሳተ!! እንደውም ልቤ ላይ ተፅፎ የኖረ በጎነቱን በሙሉ ሰረዘው !! አሁን የእውነት የወንዴ አፍቃሪ ሳይሆን የወንዴ ሚስት ሆንኩ መብትና ግዴታየን በልቤ ሳይሆን በሰማኒያ ብራናየ ላይ ፅፌ የምኖር ሚስት ማታ ባሌን ሳይሆን ባሌ የሚመጣበትን ሰአት የምጠብቅ ሚስት !! ለወንዴ ሳይሆን ለትዳሬ የምታመን ሚስት ! እንግዲህ ሶስቱ ጉልቻ እኔ ወንዴ እና ትዳር ሆንን ራቅ ራቅ ብለን አንድ ቤት ውስጥ የተቀመጥን ጉልቻዎች !! የተጣደብንን የፍቅር ብረት ድስት ሳይበስል ወዲያ ጥለን የሚነድብንን

እሳት አጠፋፍተን በተዳፈነ ምድጃ ዳር ህግ ለማክበር የቆምን ሶስት ጉልቾች ! ፓ ትዳር ይለናል የሚመለከተን !! ፓ ! አድንቀው ሙተዋል !! ያ ሁሉ ነገር እንደጤዛ ረግፎ ባዶ እንደመቆም እንደው የከንቱ ከንቱ ንፋስ እንደመከተል የሚባለው ነገር ነው የሆነብኝ ህይዎት ንፋስ መከተልም አንድ ነገር ነው ኧረ አብርሽ ንፋስ የለ ፀሃይ የለ ደመና የለ ጭር ያለ ጉድ የሰው ልጅ በየትኛውም ችግር ውስጥ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ይሁን ከማንም ከምንም ጋር ይሁን ቢቻል ልብስ የሚያስጥል እብደትን የሚያስንቅ ካልቻለም የጥፍር ቁራጭ የምታክል ፍቅር ታስፈልገዋለች ! አህ አብርሽ ፍቅር እኮ እንዴት ደስ የሚል ነገር መሰለህ ” ብላ ልእልት ትክ ብላ አየችኝ ”እኮ እና እኔስ ምናልኩ ልእልት !” አልኳት በወሬዋ ተመስጬ ስለነበር ሳላስበው ....

“እ ?” አለችኝ

አልጋ !

አልጋ ተራ የቤት እቃ የሚመስላቸው ብዙ ሰወች አጋጥመውኛል ! “ማህበረሰቡ ስለአልጋ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ “ በዚህ ጉዳይ ላይ የበኩሌን አስተዋፅኦ ለማበርከት እነሆ ስለአልጋ ይህን አጠር ብሎ ረዘም ያለ መልእክት ፅፊያለሁ ፡፡

ውድ የፌስ ቡክ ተርቲበኞች ! እስቲ ወደዋናው ሃሳባችን ከመግባታችን በፊት ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄወች እንደመነሻ ለመመለስ ሞክሩ

1. አልጋ ስንት እግር አለው ?
2. አልጋ ስር ከሚቀመጡ እቃወች መካከል ሶስቱን ጥቀሱ?
3. አልጋ ላይ ከሚከናወኑ ድርጊቶች ሰላሳ ሰባቱን “ባጭሩ” አብራሩ .....?

ጥያቄወቹን በበቂ ሁኔታ እንደመለሳችኋቸው ተስፋ አደርጋለሁ ! ያው እንደምታውቁት አልጋ ብዙ አይነት ነው ! በቅርቡ ላሳትመው በማስበውና “ያልተቀላቀሉ ቃላት “ በሚለው መዝገበ ቃላት ላይ “አልጋ” ለሚለው ቃል የሰጠሁት ፍች እንደሚከተለው ነው :-

“አልጋ ...ከእንጨት ፣ከብረት ፣ ከጠፈረ ፣ ከቦንዳ የሚሰራ አንዳንዴም ከብረትና እንጨት ተዳቅሎ የሚዘጋጅ ... አራት እግር ስድስት እግር አንዳንዴም ምንም እግር የሌለው የ ((ቤት እና የዱር እቃ)) ! አልጋው ምንም አይነት ይሁን የአልጋው ባለቤት ማንም ይሁን አልጋ በየትኛውም አለም የተከበረ እና ከቤት እቃወች ሁሉ ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው ...እንዳጠቃቀሙ ቅዱስም እርኩስም ሊሆን የሚችል .....እንዳጠቃቀሙ ጦር ሜዳም የእረፍት መስክም ሊሆን የሚችል ራሱን የቻለ አለም ነው ! አንዳንዴም ሰወች ስሙን ለመጠሪያነት ይጠቀሙበታል “አልጋነሽ ፣ አልጋየ “ የሚለውን ዝርዝር ይመልከቱ .... (ሂሂ)

አልጋና ዘ ፍጥረት

አልጋ የሰው ልጆች ብቻ የሚገለገሉበት እቃ ነው ! በአለማችን ላይ ካለው ሰባት ቢሊየን የሚጠጋ ህዝብ መካከል ግማሽ የሚሆነው የሂወቱ ንድፍ የተቀመረው ወላጆች በሚባሉ ቡርሾች... አልጋ የሚባል ሸራ ላይ ነው ! እያንዳንዱ ሰው “ሀ” ብሎ ፅንሰቱ የጀመረው የት ነው ብሎ ራሱን ቢጠይቅ መልሱ አልጋ ላይ ነው የሚነጥረው ፡፡ እናም አልጋ ላይ ከአዳም ወዲህ ያለው ፍጥረት ሁሉ እየተፋፈረ ከአፈር የተፈጠረው ከአጥንቱ ከተፈጠረችው ጋር እሳት ትንፋሹን እፍ እየተባባለ ቁጥሩን ሲያባዛው ኑሯል አሁንም እያባዛው ነው ! ለዛም ነው አልጋና ዘ ፍጥረት ዝምድናቸው የጠበቀው !

አልጋ እና ፖለቲካ

ያው በአገራችንም ይሁን በአለም ላይ በተለይ ንጉሳዊ አገዛዞች ላይ ሲወራ ከሰማህ ንጉሱ ለልጁ ቆቡን አወረሰው ፣ብሩን አወረሰው ፣ ቤቱን አወረሰው፣ ጠመንጃውን አወረሰው ወይም ፈረሱን አወረሰው ሲባል ሰምትሃል .... ሲባል አጋጥሞሃል ? እየውልሃ ...ሁሉም የሚለው እንዲህ ነው “ አልጋ ወራሽ “ በአልጋው ውስጥ

ስንት ጉድ ነገር ይወረሳል መሰለህ ! አየህ አልጋን የውርስ ማረጋጋጫ ቅኔ ያደረጉት ንጉሱ ተኝቶ ስለኖረ አይደለም እንደውም ንጉስ ከአልጋው ይልቅ ዙፋኑ ላይ ነው ብዙ ጊዜ የሚያሳልፈው ....ዙፋን ግን ተገረሰሰ እንጅ ተወረሰ አይባልም .....ልብ በል አልጋ ከዙፋን ይበልጣል !

አልጋና ሃይማኖት

ክርስቶስ ኢየሱስ በመፅሃፍ ቅዱሱ ሽባወች ይተርተሩ ምርኩዛቸውን ይጣሉ ሲል ቆይቶ አንድን በህመም አልጋ ላይ የኖረ ሰው ምን አለው መሰላችሁ "አልሃህን ተሸከመህ ሂድ " እመኑኝ ያ ሰው አልጋውን ከዛ በኋላ በህመም መተኛ ሳይሆን ከፍ ብሎ እንደጠቀስነው አለሙን ሳይቀጭበት አይቀርም ! ታሪክ ሲቀየር እንዲህ ነዋ !

አልጋና ገመና

በብዙወቻችን ኢትዮጲያዊን ቤት የአልጋ ስር ገመና መከተቻ ተደርጎ ይታያል ! እንደውም በድሮው አራት እግር ባለው አልጋ ስር ተደብቀን ከመገረፍ የዳንን ከፍርሃታችን የተጠለልንም ስንቶቻችን ነን ...ከፍ ስንልም በተለይ ወንደላጤወች ያልታጠቡ ካልሲ ምናምን እንግዳ ሲመጣ ወደአልጋ ስር ገፋ ማድረግ እንዴት ነው ትረሳለች እንዴ ?

እንደውም ሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅረኛችሁ ቤቱ ሲወስዳችሁ የወንዱን ልብ ለማወቅ የአልጋውን ስር ቃኙት ማድረግ ነው ! (ወንዶች አማተባችሁ አይደል ?...ይቅርታ አንዳንዴ ሚስጥር አልችልም ...ታዲያ አልጋ ስር ጎንበስ ስትይ ደከም ካለ ጉንፋን በርታ ካለም አስምና ትዝብት ይዘሽ ትመለሻለሽ ...በእርግጥ አንዳንድ የቤታቸው ንፅህና የሴቶችን ቤት የሚያስንቅ ወንዶችም አሉ እንደኔ ! (እማማ ተዋቡ ያመጧት ተመላላሽ ሰራተኛ ውላ ትግባ እንጅ ገና እጎራለሁ ሂሂሂ )

አልጋና ጋብቻ

እየውላችሁ ሰው ትዳር ሲይዝ መቸም ሶስት ጉልቻ አንድ ቁም ሳጥን ሁለት ሰሃን አራት ስኒ ቢኖረውም ዋናው.......ጉዳይ ግን .....አልጋው ነው ! የሰርግ ዘፈን ግጥሞች ለምን ይመስላችኋል እንደወባ ትንኝ በአልጋ ዙሪያ የሚዞሩት "ወልዳችሁ ከብዳችሁ ..." ሲባል እኮ .....ዝም ብሎ አይወለድ ! "የኛ ሙሽራ ኩሪባቸው በእንግሊዝ አናግራቸው " ሲባልም ቅኔው ወዲህ ነው " እንደብዙዎቹ የአበሻ ሴቶች አይናፋር መሆን ቀርቶ "በንግሊዝ " ሂሂ ! ... ድሮ የሌለው እንግሊዝኛ መቸስ ለሰርግ ቀን አይገለጥ ....ያው አይነጥላ ስለሚገፈፍ ቋንቋው ሌላ ይሆናል ለማለት ነው ... ያገባ ያውቀዋል ..." የሰርግ ቀን ወደአልጋ ጎራ ሲባል ጉዳዩ ላይ አንዳንዴ ዝምተኛዋ ሴት እንኳን "በእንግሊዝ " መናገር ትጀምራለች የሚባል ሃሜት አለ ...ሃሜት ነው !

ዋናው ነጥብ ደግሞ አለላችሁ መፅሃፉ "ጋብቻ ቅዱስ ..... " ይልና ቀጥሎ ምን ይላል ?

ሀ. ቁም ሳጥኑም ንፁህ ...

ለ. ሶፋውም ንፁህ

ሐ. ቀለበቱም ንፁህ ...

መ..ጉልቻውም ንፁህ

ጨ መልስ የለም ! ሃሃሃሃ አየኸው አይደል መልሱ ስላልተፃፈ ሲቆርጥህ ! እግዜሩም ልካችንን ያውቃታል ወዳጀ ! ሲልህ ......እዛጋ ሚስትህ ያውም ህጋዊ አለም ሁሉ መርቆ የሰጠህ ሰፊው አልጋ ላይ ተቀምጣ ስትስለመለም በዛ ላይ ድሮ "ያየ አመነዘረ ፣ አታመንዝር ፣ ያንተ ያልሆነች ሴት ትነካና ትረክሳታለህ እዛ ሲኦል ውስጥ ነው የምወረውርህ ..." እያለ ሲያስፈራራህ የኖረ እግዚአብሔር " ጋብቻ ቅዱስ አልጋውም ንፁህ ነው .....ጃስ " ሲልህ በቃ ነብስህን አታውቅም

..... ኮትህን ሳታወልቅ ሸሚዝህን ትታገላለህ ካልሲህ አልወልቅም ብሎህ ስትነጫነጭ ሚስትህ "የኔ ፍቅር መጀመሪያ ጫማህን አውልቅ " ትልሃለች እየሳቀች ....ስትስቅ አልጋውም የሳቀ ይመስልሃል ...መኝታ ቤቱ የሳቀ ይመስልካል እግዜር ራሱ የሳቀ ይመስልሃል ! ደግሞ እኮ መፅሃፈ መክብብ ላይ አብረው ቢተኙ ይሞቃቸዋል ካንድ ሁለት ይሻላል ይላል ....መቸስ በአየር ላይ አይተኛ ! በእርግጥ አንዳንድ ሰው አለ ".....አልጋውም ንፁህ" ሲባል አንሶላው የታጠበ ብርድ ልብሱ አሁን ገና ከላውንደሪ የወጣ ማለት የሚመስለው !

አልጋ እና ፍች

ተጋባሁ ብለህ እያንኮራፋህ ለሽ የለም ! አለበለዚያ ሚስትህ " ዛሬም አልወለድሽም ? " ስትባል "ምን ወንድ አለና " ልትል ትችላለች ! አንተም ሚስትህም ((ጉዳዩ)) ላይ በስሜት እና በፍቅር የተሞላችሁ መሆን ይኖርባችኋል ... ስንቱ የትዳር ችግችክና ፀብ በሰለህ ሶፋ ላይ አልፈታ ብሎ በጠረጴዛ ዙሪያ መፍትሄ ጠፍቶለት አልጋ ላይ ድራሹ የጠፋው ! ለዛም ነው አልጋ ላይ ያልተፈታ ችግር የትም የማይፈታው ! ጉዳዩ ቀላል እንዳመስልህ በአሁኑ ሰአት ትልቁ የፍች ርእስ በአልጋ ዙሪያ ባልና ሚስት አለመነጋገራቸው ነው ! እናም አለመተማመን በትዳር ላይ ለከስከስ ማለት ...ከላይ ስጀምር አልጋ የቤትና የዱር እቃ ነው ያልኩ ለዛ ነው ከትዳርህ ውጭ /ከትዳርሽ ውጭ ከተልከሰከሽ አልጋሽ የዱር አልጋ ህግ የሌለበት ሞራል የሌለበት ሰበአዊነትም የጎደለበት መረን የዱር አልጋ የትም ሜዳና ጫካ የሚዘረጋ ሁኗል ማለት ነው ! እናም ሽማግሌወች ውይ እንትናና እንትና እኮ አልጋ ለዩ ሲባል ጉድ የሚባለው እንዲያ ስለሆነ ነው ትርጉሙ !

አልጋና ሃዘን

ስታዝን ፍራሽ አንጥፈህ መሬት ላይ የምትተኛው ለምን ይመስልሃል ? አልጋ የድሎት ምልክት ስለሆነ እኮ ነው ....እና አልጋ ከሌለህ ማዘንህም በዚህ መንገድ ለመግለፅ ከፍራሽህ ላይ አንሶላ አውርደህ መሬት ላይ አትተኛ ነገር !

አልጋና እድሜ

የሰው ልጅ የሚበዛ እድሜውን የት እንደሚያሳልፈው ታውቃለህ ....አልጋ ላይ ! ብትፈልግ በቀን ቢያንስ ስምንት ሰአት ብለህ በዛው አባዛው ! በአንድ ወር 240 ሰዓታትን ለሸሸሸሽ ! ያውም ሌላው ሌላው አይነት የአልጋ ላይ ቆይታ ሳይደመር ! አንዳንዱ አልጋ ላይ የሚበቅልም አለ !

አልጋና የሂወት ውጣ ውረድ

የሂወትን አባጣ ጎርባጣ ፣ የሰው ልጅን ውጣ ውረድ በአጭር ቃል ተናገር ብትባል "ሂወት አልጋ ባልጋ አይደለም" ትላለህ አይደል ? .... ሰው ይህን ሁሉ መስመር አልፎ በእርጅና አልያም በህመም ቤት ሲውል ደግሞ ....."አልጋ ላይ ዋለ" ይባላል !

አልጋና አይቀሬው ነገር

ያው በስተመጨረሻ ህዝብህ ውሎ ይባ እድርህ እድሜው ይርዘም .... በስከሬን አልጋ ወደመቃብርህ ደረስ አድርገውህ ይመለሳሉ ! አየህ ሂወትህ በአልጋ ይጀምራል በአልጋ ይጠናቀቃል ....በአልጋ ትመጣለህ አልጋ ላይ ዘርህን ትተካለህ በአልጋ ትሄዳለህ ! እውነቴን ነው በአልጋ ትመጣለህ በአልጋ ትሄዳለህ ! አልጋ የእድሜ ልክ ንብረትህ ነው !

አልጋና ዋናናናናናና ው ጉዳይ !!!!

የሰው ልጅ ድካሙ ልፋቱ ችግሩ የቀን ውሎና ፍዳው ሁሉ ተጭኖት በዛለ ሰውነት በደከመ አይምሮ ወደምኝታ ቤቱ ሲገባ ሰፊ አልጋ ተንጣሎ ገነትን መስሎ ሲጠብቀው ምን እንደሚል ታውቃለህ ?

እንደሰፊ እና ምቹ አልጋ !! ሰኞ ጋራዥ ቤት ማክሰኞ የሆነ ወፍጮ ቤት ፣እሮብ ማድ ቤት ፣ሃሙስ መታጠቢያ ቤት አርብ ሳሎን .......ቅ ዳ ሜ ...........የነፍሳችን ምኝታ ቤት ! የነፃ ህልማችን ግዛት ! ሃሃሃሃ

# የነ ሜሮን ፍሪጅ

አዲሳባ ውስጥ ከሚኖሩ አምሳ ዱርየ ሴቶች መካከል የሰላሳ ዘጠኙ ስም ሜሮን ይመስለኝ ነበር አምስቱ ሄለን አምስቱ ሃያት አንዷ ግን አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስም እየቀያየረች የምታጭበረብር ስሟ የማይታወቅ ቦሌ ቢባል ካሳንቸስ ፒያሳ ቢባል አራት ኪሎ ነርስ ብትሆን ሱቅ ጠባቂ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ብትሆን ሴተኛ አዳሪ እች ስሟን የምትቀያይር ሴት ነበረች የምትመስለኝ አዎ ስሟን እየቀያየረች በአንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስም የምትዶርር (ዱርየ የምትሆን) ትእግስት ፣ሳባ፣ ገነት፣ ማርታ፣ መቅደስ፣ ትርሃስ ፣ ሃረገወይን ፣ ወላንሳ፣ ዙሪያሽ፣ ፍሬ ፣ ቃልኪዳን ፣ቲቲ፣ መአዛ፣ ራሄል ፣ሚሚ፣ ሙና፣ አስናቁ፣ ዘሪቱ፣ መንበረ፣ አለምነሽ፣ ያኔት ፣ ሊና ፣ ሳራ፣ ሃና አንድ ነጥብ አምስተኛው ላይ ሜሮን ትሆናለች እች እስስት!!

እስስት ብያለሁ አዎ!! ስም እኮ ቀለም ነው ሰው ስሙን ሲቀያይር ቀለሙን ለመቀየር መሞከሩ ነው እና ጡሩወርቅ ጎጃምኛ ቀለሟን ቀይራ “ ሊያ “ ነኝ ስትል ጥቁር ፀጉሯን ቀይራ ቀይ ስትደፈደፈው ምን እየሆነች ነው ? አካባቢዋን እየመሰለች አዲሳበባን እየመሰለች እስስትስ ከዚህ የተለየ ምን አደረገች ? ያው አካባቢዋን ለመመሰል ቀለሟን ነው የቀየረችው እንደውም እስስት አነጋገሯንና ስሟን አልቀየተችም

ስምንተኛ ክፍል እንደነበርኩ ፍቅር ያዘኝ !! ሜሮን ከምትባል ሁልጊዜ በብዙ ሴት ጓደኞቿ በመትከበብ ልጅ ደግሞ ስትስቅ ታምራለች ስትኮሳተር ግን ታምራለች አነጋገሬ ተምታታ አይደል እንዲህ ነበር የተምታታብኝ!! ቀይ ናት ከቢጫነት ጋር የሚዋሰን ቅላት አፏ ሰፋ ያለ ከንፈሯ ቀይና ወደታች ወረድ ብሎ የሆነ “ከምታፈጥ መጥተህ አትስመኝም “ ብሎ የሚጣራ ነገረኛ ከንፈር ህፃን ሁነን አባ ገመቹ አጥር ላይ ተንጠልጥሎ የሚያስጎመዠንን ፕሪም የመሰለ የላይ እና የታች ከናናፍርቶቿ በአንድ ላይ ሲታዩ የሆነ ልብ የሚሰውሩ የልብ ቅርፅ ሄለንን በአይኔ ሳይሆን በልቤ ነበር የማያት ሳያት “የልቤ ሽፋሽፍት ይርገበገባል” በስንት መከራ ያውም ወደዘጠነኛ ክፍል ስናልፍ “ሳይሽ የልቤ ሽፋሽፍት ይርገበገባል ” ብየ ደብዳቤ ፃፍኩላት “ሄለን” እና “ሃያት” የሚባሉት ጋጠወጥ ጓደኞቿ ጋር በመሆን በዚች አረፍተ ነገር ምክንያት አመቱን ሙሉ መሳቂያ መሳለቂያ አደረጉኝ መሪያቸው አንዲት ስሟን የማላውቃት አይጠመንጎ ነበረች ልክ እኔ ሳልፍ ደረታቸውን በእጆቻቸው እያራገቡ በሳቅ ያውካካሉ አይጠ መጎጧ በአካፋ አይኗ አሸዋ ወንድ ስትግፍ የምትውል ከንቱ ስሟን አላውቀውም ስሟን አስር ጊዜ ትቀያይራለች ስሟ ብዙ ነው ሁሉንም ስሟን የኢትዮጲያ ቄሶች ሁሉ እየተጋገዙ ይጥሩትና እች እስስት የእርሷ ሳቅ ሳቁን ገድሎታል የእርሷ ጣረሞት እይታ ሩቅ እንዳላይ አንገቴን አስደፍቶኛል ”የልብ ሽፋሽፍት” የሚል ግጥም ፅፋ ለፀረ ምናምን ከበብ አመታዊ ዝግጅት ሰልፍ ሜዳ ላይ አንብባ 843 ተማሪ ወደእኔ ዞሮ ገልፍጧል የግጥሙ ርእስ “አብረሃምን እዩት” የሚል ነበር የሚመስለው 843 ተማሪ × 32ጥርስ = 26976 ጥርሳቸው ይርገፍና !! ውይ የአስተማሪወቹን ረስቸው + 23 × 32 = 736 -32 (ቲቸር ሙሴ አንድም ጊዜ አልሳቁም)

የፍቅር አፒታይቴን ምድረ ጥርሳም በሳቃቸው ቆልፈውት አስራሁለተኛ ክፍል ጨርሸ ዩኒቨርስቲ እስከምገባ ሴት የምትባል አጠገብ ድርሽ ብየ አላውቅም እንኳንም ያልቀረብኩ !! ምናቸው ይቀራል !! ያች አይጠመንጎ ፣ አስቀያሚ፣ጥርሳም፣ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ስማም ዛሬ የራሷ አንድ ስም እንኳን ጠፍቶ ማንም “አንች” የሚላት የካፍቴሪያ አስተናጋጅ ሁናለች ሻይ አዞ ስሙኒ ጉርሻ ለተወላት ሃና ቡና ጠጥቶ ለገለፈጠላት ናኒ እየሆነች እስስቷ የስሟን ቀለም እየቀያየረች አለች ብር ዛፍ ቁርስ ቤት !!

ዩኒቨርስቲ እንደገባሁ እዚሁ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ደስ አላለኝም ምክንያቱም ከአዲስ አበባ ውጭ ከወላጅ ራቅ ብየ የመኖር የቆየ ፍላጎቴ ተሰናከሏልና ! አስከፊው ነገር ደግሞ ዩኒቨርስቲው “የአዲስአበባ ልጆች እየተመላለሳችሁ ተማሩ በቂ ምኝታ የለኝም” አለ!! ይሄ ደግሞ ዩኒቨርስቲና “ሃይ ስኩል” የሚለያዩበትን አንድ ድንበር አፈራረሰው ዩኒቨርስቲ ውስጥ የገባሁ አልመስልህ አለኝ ወደ አስራዶስተኛ ክፍል ያለፍኩና እዛው የነበርኩበት ትምህርት ቤት የቀጠልኩ አይነት ስሜት ነበር የተሰማኝ ያ ሁሉ የተወራለት በፊልም በመፅሃፍ ብዙየተባለለት የዩኒቨርስቲ ሂወት ውሃ በላው !! ወይ ነዶ! አንድ አራት ወር እየተመላለስኩ እንደተማርኩ እዛው

ዩኒቨርስቲው አካባቢ ቤት ተከራይቸ ለመማር ወሰንኩ ምንም አስቤ ሳይሆን የአዲስ አበባ ታክሲ ጊዜየን እየበላብኝ ስለተቸገርኩ ነበር ማንም አልተከራከረኝም ዩኒቨርስቲው ከሚወረውርልኝ ሳንቲም ላይ ቤተሰብ በየወሩ ድጎማ እየመረቀበት ቤት ተከራየሁ ድክም ያለች ቤት አንድ ሰፈር ውስጥ

እንግዲህ የእኔ ቤትና ከጎኔ ያሉት ጭርንቁስ ቤቶች በመደዳ የተሰለፉ ናቸው ፊት ለፊት ደግሞ ፊታቸውን ወደእኛ ቤቶች ያዞሩ በስሪትም በመጠንም ከእኛ መደደዳ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌላ መደዳ ቤቶች አሉ መስኮቴን ስከፈት ፊት ለፊት ያለው ቤት መስኮት ጋር እፋጠጣለሁ በሬን ስከፍት ከበር ጋር !! ቡሁለቱ መደዳ ቤቶች መካከል ቀጭን የእግር መንገድ አለች የእኔ ቤትና ፊትለፊቴ ያለው ቤት ጣራቸው ሊገጣጠም ምንም ያህል ስለማይቀረው በመካከላችን በቀጭኗ የእግር መነገድ የሚያልፍ ሰው በሆነ ረዥም ኮሪደር ውስጥ የሚያልፍ ሊመስለው ይችላል ከበሬ ላይ አንድ ጠቀም ያለ ርምጃ ወደፊት ብራመድ ፊት ለፊት ያለው ቤት በር ላይ.አርፋለሁ ይሄ ነው የተከራየሁት ቤት

ሜሮንን ተሻግሮ ሜሮን አለች ወይ

በአንድ እርምጃ ርቀት ጣራየ ከጣራው የሚነካካው ቤት ውስጥ ፊት ለፊቴ "ሜሮን" የምትባል ልጅ!! አለች በጊዜና ቦታ ርቀት ትቸው የመጣሁት "ሜሮን " የሚባል እንደጥላ የሚከተል ስም እዚህም መጣ ሜሮን ሜሪ ሜሪቾ ሜሪየ ይላታል የመንደሩ ሰው ጥቁር ትሁን ቀይ አይቻት አላውቅም ነበር

ለሰባት ወራት ያህል ጧት እየወጣሁ ማታ እየገባሁ በሰላም ኖርኩ በአንድ ጠራራ የግንቦት ቀን " ከክላስ " ወደቤቴ እየገባሁ ነበር የፀሃዩ ቃጠሎ ከንፈሬን ሁሉ አድርቆታል ሰውነቴ ሁሉ የተነነ ነው የመሰለኝ ድርቅ!! ቀዝቃዛ ውሃ ለመግዛት ጫፍ ላይ ወዳለች ኪወስክ ሄድኩና "ቀዝቃዛ ውሃ ስጭኝ እስቲ" ብየ አስር ብር ባለሰሃኑ ሚዛን ላይ ጣል አደረኩላት አስር ብሩ ሚዛኑ ላይ ሲያርፍ ሚዛኑን ዝቅ አላደረገው ከፍ "ቀዝቀዛ የለም " አለች አስር ብሩን በእጇ ይዛ "እሽ ቀዝቃዛ ኮካ " "ቀዝቃዛ ኮካም የለም ከውጭ ለስጥህ " አለች "ቀዝቃዛ ነገር ምንድን ነው ያለሽ " "ፍሪጅ የለኝም ከውጭ ነው ሁሉም " "ተይው በቃ " ብየ ብሬን ልቀበል እጀን ዘረጋሁ ቅር እያላት ብሬን መለሰችልኝ ፊቴን ኮሶኮስኩ በጣም ነበር የተበሳጨሁት ኤጭ እቤቴ ገብቸ ቱታ ቀየርኩና ፍራሹ ላይ በጀርባየ ተንጋልየ በእፎይታ ተነፈስኩ ወዲያው በር ሲንኳኳ በግርምት ወደበሩ ተመለከትኩ ጆሮየን አቁሜ ብጠብቅም ምንም ድመፅ አልነበረም መልሽ ጋደም ልል ስል በድጋሜ ተንኳኳ በቀስታ ! ላለፉት ሰባት ወራት አንድም ጊዜ በሬ ተንኳኩቶ ስለማያውቅ ተገረምኩ ማነው አላልኩም በቀጥታ ሂጀ ከፈትኩት

አንዲት ቆንጆ ጠይም ሴት በሬ ላይ በትልቅ የጠርሙስ ጆግ ውሃ ይዛ ቁማለች ጆጉ ላይ የገገረው በረዶ ስለሚታይ ቅዝቃዜው ያስጎመዣል ምራቄን ዋጥኩ እና ልጅቱን አየኋት እሷም ታስጎመዣለች እሷን እንደመድሃኒት ውጦ በያዘችው ውሃ ማወራረድ ነበር !

እየፈራች "ሉቅ ውሃ ጠይቀህ ስላጣህ ከቤት አምጥቸልህ ነው " አለችኝና ውሃውን ዘረጋችልኝ ሳላንገራግር ተቀበልኳት "ቴንኪው" የለ ምን የለ ቆንጆ ነች በጣም ቆንጆ ነች በተለይ አይኗ በተለይ ጥቁር የሚያብረቀርቅ ፀጉሯ ከቁጥርጥሩ ገና የተፈታ እንደሆነ ያስታውቃል በተለይ ደግሞ ጡቷ የለበሰችውን ስስ ቡዲ በሽካክቶ ሊተኮስ የተሰናዳ የሆነ ተተኳሽ ነገር የተጋለጠ ደረቷ በተለይ ደግሞ እኔጃ ቆንጆ ነበረች ግን ልጅ ነበረች ቢበዛ አስራስድስት ቢሆናት ነው ዞር ስትል መቀመጫዋንም አይቻለሁ (ለምን ይደበቃል) ለአስራ ስድስት አመት ልጅ ይበዛል ግን ቆንጆ ቆንጆ እና ልጅ ቆንጆ ልጅ !! ትፍ ትፍ ትፍ እደጊ መቸም አዲሳባ ቆንጆ እያጣመመ ነው የሚያሳድገው !!

ከእኔ በር ወደራሷ ቤት ስትሄድ እኔም ውብ ሰውነቷን ቁሜ ስገመግም አንድ መንገደኛ "ታዲያስ ሜሪ" አላት እርፍ!! በፍቅር ውሃ ጥም ለአመታት ያደረቀችኝን ሜሮን የምትባል ደረቅ ወንዝ ተሸግሬ በቀዝቃዛ ውሃ ጥሜን የምታስታግስ ሜሮን የምትባል ጅረት ላይ ደረስኩ ሜሮንን ተሻግሮ ሜሮን አለች ወይ ሞትና ውሃ ጥም አንድ አይደለም ወይ እየጠጣህ አብርሽ ቀዝቃዛውን ላንደቀድቀው ነበር ግን ገና አንዴ ስጎነጭለት ጥርሶቸ ሁሉ ጠፉኝ

ቦታቸው ላይ ደነዘዙ ምን እዳ ነው ልብም ጥርስም ደንዝዞ የት ይደረሳል ጥርስ የሌለው ልበ ቢስ አንበሳ ቢሆንም አንድ የተለኮሰ ነገር ነበር

ፍሪጅ እና ቦኖ ውሃ በምን ይለያያል

ሜሮን ትላንት ያመጣችልኝኝ ጀግ ልትወስድ ስትመጣ ፈገግ ብየ ተቀበልኳት ባዶዋን አልነበረችም ሌላ ጀግ ሙሉ ቀዝቃዛ ውሃ ሰጥታኝ ባዶ ጀግ ወሰደች ጀግ ውሃ ጀግ ውሃ "የት ነው የምትማሪው " "ሚኒሊክ " ጀግ ውሃ ጀግ ውሃ " አሳይሜንት ተሰጥቶኝ ነበር ጊዜ ካለህ ትሰራልኛለህ? " "አምጭው ኧረ" ብጥርጥር አድርጌ ሰራሁላት አስረዳኋት እንዴዴዴዴ እንዲህ አይነት አደገኛ አስተማሪ ነበርኩ እንዴ ለካ ጀግ ውሃ ጀግ ወሃ ለስላሳ !! " የምን ለስላሳ ነው ሜሮን " "ታዘብኩህ ዛሬ ልደቴ ነበር 16 አመቴ "ሃፒ በርዝ ደይ" ሳትለኝ " ፈገግ ብላ "በቃ ቅዳሜ እራሴ አከብርልሻለሁ " "ፕሮሚስ" ብላ የሚያምር መዳፏን ዘረጋች "ፕሮሚስ " ብየ መዳፌን መዳፏ ላይ አስቀመጥኩ ለመጀመሪያ ጊዜ መነካካታችን ነበር !! እጁን አልሰበሰበችም እኔም እጅን አላነሳሁም እግዜር "መሃላውን እስካፀድቀው እጃችሁን እንዳለ ሳይለያይ አቆዩት " ያለን ነበር የምንመስለው አይኗ ውስጥ ፀሃይ አየሁ ሁለት ፀሃይ አማረችኝ ቅዳሜ መሰለችኝ ውስጧ እረፍት የተዘራ ሲደክም ለኖረ አንድ እኔ ሰፊ አልጋና እረፍት ያለባት አገር

ጀግ ውሃ ጀግ ውሃ ቅዳሜ ሆነ!!

ከማክሰኞ እሰከአርብ ያላሰብኩትን ቅዳሜ ጧት ተጨነኩ የአስራ ስድስት አመት ልጅ ይዤ የት አባቴ ነው የምጋብዛት ቤተሰቦቿስ ምን ይላሉ (ለነገሩ ሴትአያቷ እና እሷ ብቻ ናቸው የሚኖሩት) ጎረቤቱስ ወይ ጉድ

ሜሮን በጧት መጣች " አንተ እስካሁን ተኝተሃል " አለችኝና ፍራሹ ጫፍ ላይ ተቀመጠች ( እቤቴ መግባት ፍራሽም ላይ መቀመጥ ጀምራለች) ጧትስትመጣ ደስ አይለኝም ስስ ፒጃማ ቁምጣና ባለማንገቻ ጎርድ ቦዲ ስለምትለብስ እፈተናለሁ በዛ ላይ በጣም ተጠጋግተን ስለምንቀመጥ ጠረኗ አፍንጫየን ይዞ ወደጡቶቿ መሃል ይጎትተኛል ፈተና ነው በቃ እርሷ ደግሞ በፍፁም "ንጹህ" ልብ እንደፈለገች ትሆናለች

በቃሌ መሰረት ልደቷን ላስከብራት ተቀጣጠርን!! ከሰፈር አብረን መውጣቱ "ስለሚደብር" የሆነ እሷ የመረጠችው ሬስቶራንት ስምንት ሰአት ላይ እንገናኝ ተባባልን እኔ የዚህ አይነት ቤት አይቶ አላውቅም ቀድሚያት ነበር የደረስኩት ቀይ የለበሱት ጠረንጴዛወች የአገር ሹካና ማንኪያ ቢላዋና የጨው የምናምን እቃ ዙሪያቸውን ተደርድሮባቸው ፈዘዝ ያለ ብርሃን ያለበት አዳራሽ ውስጥ በሰፊው ተንጣለዋል ምቾት አይመቸኝም ቅንጦት አያቀናጣኝም ጨነቀኝ

ሜሮን ስትደርስ ልቤ በድንጋጤ ልትቆም ምንም አልቀራትም የሚያምር አጭር (ጉልበቷ ላይ የቆመ ) ቡና አይነት ቀሚስ ለብሳለች ውብ እግሮቿን ለማሳየት ሆነ ተብሎ የተሰራ የሚመስል ረዥም ተረከዝ ያለው ጫማ ጥልፍልፉ ፍርጥም ያለ ባቷ ላይ እንደሃረግ እየተጠመጠመ ወጥቶ ጉልበቷ ላይ የደረሰ ጡቶቿ ደረቱ ላይ ክፍት በሆነው ቀሚሷ ታቅፈውና ተሳስመው የሲኦል ሸለቆ እንደሰሩ ፀጉሯ ወደአንድ በኩል ተሰብስቦ በማስያዣ ተይዟል አይኗ በኩል ተከቧል ኦሀሀሀሀሀ ስታምር ! የአዲስ አበባ እናቶች እድሜ አቆጣር አይችሉም ይሆናል እንጅ እች ልች አስራ ስድስት አመቷ ብቻ አይመስለኝም በዚህ እድሜ ቀጠሮን የመከሸን ሳይንስ እንዴት ነው መካን የሚቻለው ቁሜ ተቀበልኳት ጉንጫችንን አነካካነው መሳሳም መሆኑ ነው አቤት ሽቶዋ ፊቴ ዝም ብላ ቆመች ቆምኩ አሃ ለካ ወንበር ይሳባል ሳብኩላት "ቴንኪው" ብላ ተቀመጠች "በጣም ቆንጆ ሁነሻል" "አመሰግናለሁ" የተጠና ምልልስ መሰለብኝ እንጅ ከልቤ ነበር የተናገርኩት በዚህ ቀን ሜሮን ጋር ከዘፍጥረት እስከራእይ አወራን ሜሮን ካለእድሜዋ የበሰለች ጉድ ነበረች እናም እንዲህ አልኩ " "አዲስ አበባ ውስጥ ከሚኖሩ አምሳ ዱርየ ሴቶች ውስጥ ሰላሳ ዘጠኙ ስማቸው ሜሮን ይመስለኛል " ግን ማናባቱ ነው ይሄን ቆጠራ ያካሄደው ደደብ " ሜሮን ጋር ተዋደን ነበር በቃ እኔ ጋር በመሆኗ ነፍሷን እስክትስት ተደስታ ነበር እኔማ ነፍሴን ከሳትኩ ሰንበቻለሁ

ደግሞ ወሬው ሁሉ ከየት መጣልኝ የሰው ሰው በሳቅ ልገድል !! እግዜር ሲያስወድድህ ብዙ ሳቅ የወደደህ ሰው ልብ ውስጥ ያስቀምጣል ከዛም የውድህ ሳቅ መውጫ በር መተንፈሻ መስኮት ያደርገሃል አንተ በፈለከው መንገድ አፍህን ከፈት ቃላትን አውጣ ሜሪየ የኔ ውብ አቤት ሳቋ ሲያምር እዛ ዩኒቨርስቲ “ ሄይይ ምን አዲስ ነገር አለ “ እያሉ ሳቅ ፍለጋ እንደሚባዝኑ ደነዝ ሂወታቸውን በጊዜ ያሚጠጡ ሴቶች አይደለችም ቻፕስቲካም ከንፈራቸውን እስከጆሮ ግንዳቸው ለቀው በ “ዊቲኒ ሆስተንኛ” ለመሳቅ ቆረቆሮ ድምፃቸውን እንደሚያኳኩ ኳኳታሞች አይደለችም !! ሜሪ ራሷ ሳቅ ነበረች !! ፍንትው ስትል ከእግር ጥፍሯ እስከአራስ ፀጉሯ በሳቅ የምትጥለቀለቅ አሁን እንደእኔ አይነቱ ሰው “ተሳቀልኝ “ ቢል ያምርበታል ተስቆለታላ !!

ልብ ነበራት የፍቅር የሰላም ያልተነካካ “ውይ ወንዶች “ እያሉ ያለፈ እንኩሮ ሂወታቸውን አዲስ የፍቅረኛ ምጣድ ላይ በትዝታ ስም እንደሚጠፈጥፉ ሴቶች አይደለችም እሷ ብታውቀውም ባታውቀውም ነገ ይናፍቃታል ማንንም አልጎዳች ማንም አልጎዳትም ተረት የላትም !! ተረት አይደለችም “እነእከሌ ተፋቀሩ” ስትባል አትቀናም “ተለያዩ” ሲባል አትፈርድም !! ከተማውን የሞላው ፈራጅኮ ግማሽ ፍርዱ በቀል ነው የደረሰበትን ሊበቀል ያደረሰውን ሊያስተባብል ሜሪ ግን ብቻዋን ናት ብቻዋን ወደሂወቴ መጣች አልከበደችኝም

ከዛን ቀን ጀምሮ ሁልጊዜ ማታ ማታ በር ላይ እንቆምና ስናወራ እናመሻለን ውሃ ልትደፋ ወጥታ ሊሆን ይችላል “ቻው በቃ መሸ “ ትለኝና ቆም ትላለች ከቻው በኋላ አንድ የሆነ ነገር የማድረግ ፍላጎት ሁለታችንም ልብ ውስጥ አለ ግን ማን ይድፈር ከቻው በኋላ አንድ ሰአት እናወራለን “ምን አወራችሁ ቢባል “ እንጃ!! ብዙ ጊዜ እቤቴ እንዳትገባ ሆነ ብየ አከላክላለሁ ይከብደኛል ፈተናው !! ስለዚህ በር ላይ ቁመን እናወራለን ወሬኛ ነኝ የማላወራላት ነገር የለም!! ላወራሁበት የምከፈለው ደሞዝ ሳቋ ነው የጠገበ ደመወዝ እግዜርየ የፍቅር ዩኒቨርስቲ አስመርቆ የሰጠኝ ምርጥ ስራ (ሃሌ ሉያ አስመርቆ ስራ ፍጠር ቢለኝ ምን ይውጠኝ ነበር ) ሳቋ ደመወዜ ነው አስቃታለሁ የማወራላት ምንም የማይጠቅም ነገር ቢሆንም የሳቅ ደመወዜን አስቀርታብኝ አታውቅም ታዲያ አንዳንዴ ማታ ቁመን ስናወራ ከሩቅ የጅብ ድምፅ ይሰማል አውውውው ወደእኔ ጠጋ ትላለች ሜሪየ የመጨረሻ ፈሪ ናት ጠረኗ ይጠርነኛል ከምሽቱ አየር ጋር ወደሳንባየ ተስገብግቤ አስበዋለሁ ጠረኗን !! እሷን እራሷን እንደአየር ስቤ ውስጤ ያስገባኋት እስኪመስለኝ ጅቡን እድሜውን ያርዝምልኝና በጣም ትጠጋኛለች

እስካሁን ስሚያት አላውቅም “ሳማት ሳማት ከንፈሯን ጉረሰው ጉረሰው “ ይለኛል ጨለማ የሆነ ሰይጣን ነገር ሳይኖረው አይቀርም ! ቀን እዚሁ ቦታ ላይ ቁመን በጭራሽ የማይሰማኝ ስሜት ማታ የሚገፋፋ አንዳች ነገር አለው ወደደረቴ ስትጠጋኝ የጡቱቿ ጫፎች ደረቴን ሸንቁረው በጀርባየ በኩል ብቅ ያሉ ይመስለኛል ፈተና ነው

ጅብ ሲጮህ ስለጅብ አወራታለሁ ድመት ከጮኸ ስለድመት አበባ ካለች ስለአበባ ስናወራ ስናወራ ሰካራሙ ጎረቤታች ጉግሳ እየተወላገደ እየዘፈነ ይመጣል “አንተ ጉግሳ መጣ አራት ሰአት ” ትላለች ሜሪ ጉግሳ አራት ሰአት ላይ እንደሚመጣ የታወቀ ነው !! የመንደሩ ሰአት ነው ጉግሳ ወሬ ሲወራ ሁሉ “ልክ ጉግሳ ሲመጣ” ይባላል ልክ አራት ሰአት እንደማለት እየዘፈነ እየገጠመ (እያዛናና እና እያስተማረ ይሉታል ሲፎግሩ) ከተፍ ይላል ለእግሩ ጫማ የለው ለራሱ ባርኔጣ የቅጣቸው አባት አሁን ገና መጣ ይላል ጉግሳ(ቅጣቸው ልጁ ነው) ወተር ወተር እያለ በጨለማው ውስጥ ሲራመድ የእማማ ትሩፋት ቡችላ ትጮህበታለች ው ው ው ው ው ው ው ው

ጉግሳ ቆም ብሎ ቡችላዋ ወዳለችበት ግቢበንቀት እያየ “ ቡችላ አስመሳይ የእመቤትሽ ውሽሞች አጥር ሲዘሉ አትጮሂም ወንድ ከሆንሽ በአገልግል ዶሮው ተቋጥሮ በጓሮ በር ለውሽሞች ሲላክ አትጮሂም ቡችላ የውሻ ልጅ!! ይቅርታ እናትሽን አሰደብሽኝ ነብሷን ይማርና እናትሽ ጥሩሩሩሩሩሩሩ ውሻ ነበረች ቤቱ ድረስ ሸኝታ ነበር ቤቷ የምትገባው የልጅ ዘመድ የለውም አንች ” አይጨርሰውም

ጉግሳ እኔና ሜሪን ያየናል ከእርሱ በፊት ቀድሞ አጠገባችን የሚደርሰው የአረቂና ጠጅ ሽታ ነው ቆም ብሎ ንፋስ እንደገፋው ዛፍ እየተወዛወዘ ኮፍያውን ያወልቅና በአክብሮት ጎንበስ ብሎ (በግንባሩ እንዳይደፋ እሰጋለሁ)

"ወጣቶች ልጆቻችን የነገ አገር ተረካቢ እንደምን አመሻችሁ ሃሃሃሃሃ እኛንም እንዲህ ነበር የሚሉን የአገር ርክክቡ ሲዘገይ እየጠጣን እንጠብቀው ብለን ሰካራም ሆንን " ይላል በስካር ድምፅ "ደህና አመሹ ጋሽ ጉግሳ " እንለዋለን ትክ ብሎ ያየንና " መፋቀር ጥሩ ነው እጅግ በጣም በጣም ጥሩ ነው !! ይሄ ቡዳ ሰፈር ቡዳ እንዳይበላችሁ እቤት ግቡ " ይለናል ሜሪ ሳቋን አፍና ዝም ትላለች "መፅሃፉ ጋብቻ ቅዱስ ነው ይላል ደሞ ፍቅር ከሌለ ቆርቆሮ ቁራሌ ቆረቆንዳ ነህ ይላል !! መፀሃፉ ተፋቀሩ ይላል ! ጎበዞች! አይዟችሁ ደህና እደሩ " ይልና እየተወላገደ ያልፋል ሜሪ ደረቴ ላይ ድፍት ብላ በሳቅ ፍርስስስስ ስትተነፍስብኝ እቃጠላለሁ

ጉግሳ ትንሽ አለፍ እንዳለ " እያንዳንድሽ ወየውልሽ በየጥጋጥጉ እየቆምሽ የምትባልጊ ሁሉ ወየውልሽ" ይላል እጁን ወደሰማይ ዘርግቶ አመልካች ጣቱን እየነቀነቀ " መፀሃፉ በጨለማ የሰራሽውን ሁሉ በፀሃይ እገልፀዋለሁ ስራሽን እንበርበሬ ዛላ እንደታጠበ ልብስ ለወፍጮ እንደተዘጋጀ የሸሮ ክክ ፀሃይ ላይ አሰጠዋለሁ ይላል መፀሃፉ ወዮልሽ አርፈሽ አትማሪና ኮከብ ስትቆጥሪ አምሽ " ካለ በኋላ በዜማ ይቀጥላል

እንኳን ቤትና የለኝም አጥር አደጅ አድራለሁ ኮከብ ስቆጥር ኮከብ ቆጣሪ አስማተኛ ሁሉ ሌላ ርእስ ውስጥ ይገባል

ሜሪ ጋር አንዳንዴ " ወክ " እናደርጋለን ንፁህና ፀጥ ያለ ኤምባሲ አለ በሱ በኩል ማታ ክንዴን ደገፍ ብላኝ በጣም ተነካክተን ብርዱ ለስላሳ ቆዳችን ላይ የፈጠራቸው መንደብደቦች የእኔ እንድብድቦችና የሜሪ እንድብድቦች እየተነካኩ ሽቶዋ እየተቀላቀለብኝ ደስ ብሎን እንዝናናለን ስንሄድም ሆነ ስንመለስ አገር ቢያየን ግድ አልነበረንም አሁን አውርተናል ውስጤ ውስጥ ነሽ ብያታለሁ ምንም አላለችኝም ግን እንባዋ መጥቶ ነበር

አንድ ቀን ከ "ወክ" ስንመለስ እኔ ቤት ገባን ፍራሽ ላይ እግሯን አነባብራ ዘርግታ ተቀመጠች ቀሚሷ ስላጠራት ትንሽ ተጨናንቃ ነበር አጠገቧ ተቀመጥኩ ሁለታችንም የሆነ ነገር በጣም በጣም ፈልገናል ግን አየኋት ቀሚሷ ላይ ባለች ቁልፍ ትጫወታለች ፈራሁ አይምሮየ በሃሳብ ተራወጠ

1. የኢትዮጲያ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንዲት ሴት አስራ ስምንት አመት ሳይሞላት ወዳና ፈቅዳም ሆና ሳትወድና ሳትፈቅድ ወሲብ ብትፈፅም ወሲብ የፈፀመባትን ሰው ዘብጥያ ከርቸሌ ወላ ጀሜ አስገባው ይላል!!
2. ህገ እግዚሃር ወዳ ፈቅዳ ሴት ወንድ ምናምን አይልም አታመንዝር በቃ!! ከፈለክ የከጀልካትን ሴት አግብተህ እንዳሻህ ሁን አለበለዚያ አምሮትህን ሲያምርህ ይቅር ብለህ ገስፀው አለበለዛ ሲኦል ወላ ጀሃነም ትወረወራታለህ ይላል
3. የእኔ ይዞ ሟች ልብ የሜሪን የሚያምር ባት የፈረጠመ ዳሌና ጫፋቸው የሚጣራ ጠይም ጡቶች እያየ ከምድራዊውም ከሰማያዊውም ህግ ሊያጋጨኝ በደም ፍላት ደም ይረጫል ልቤ ሲደልቅ ግግም ግግም ግግም ሲል አንድ ታዋቂ ትግረኛ ዘፋኝ ከነከበሮ ደላቂው ልቤ ውስጥ የሙዚቃ ስራውን የሚያቀርብ ይመስለኛል

የልቤ ምክር "አብርሽ ሜሪ ትወዳሃለች ያደረጋችሁትን ለማንም አትናገርም ደግሞ እያት ከንፈሯ እንዴት እንደሚንቀጠቀጥ ስትንከረፈፍ አንዱ እንዳይልፍህ እጆችህን ጡቶቿ ላይ አሳርፋቸው አይዞህ ጠጋ በላት ኤጭጭጭ የምን መጨናነቅ ነው የወንጀል ህጉ አንጀባ ነው ባክህ እግዜር ደግሞ እንኳን አንተን ስንቱን ይቅር ብሎ የለ ኧረ ሳይመሽ ፍጠን ነገ በዚህ ስሜት አተገኛትም እንደውም ያልፈለካት መስሏት በዛው ነው የምትቀረው ቱ " ብሎ ደም ይተፋል ልቤ

እነሆ በ ህገ እግዜር በወኝጀለኛ መቅጫ ህግና በግልፍተኛ ልብ መሃል ሚስኪኑ አብረሃም

ሜሪ አንድ እግሯን ሰብሰብ ስታደርገው ከጠይምነቷ የቀላ ለስላሳ ታፋዋ ተጋለጠ ቀሚሷን ሳብ አደረገችው ግን አልሸፈናትም ቀጥ ብላ አየችኝ አይኗ ቡዝዝ ብሎ ነበር ትከሻየ ላይ ራሷን ደገፍ አደረገችው ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ ጠረኗ አመንዝር ይለኛል ውበቷ አመንዝር ይለኛል ልቤ አመንዝር ይለኛ ቤቱ አመንዝር ይለኛል ሁኔታው አመንዝር ይለኛል ፍራሹ "ኑ እንጅ እየጠበኳችሁ አይደለም እንዴ ይለኛል " እርግጠኛ ነኝ ሰይጣንም እንደአምፌ ቲያትር ከነጅሪው ተሰብስቦ እያየን ነው

ሜሪ በቀኝ እጇ ጣቶች እየተጫወተች ነበር አቤት እጇ አለሳለሱ ደግሞ ይሞቃል ቆይ ምናባቴ ነው የማደርገው ህግ ይሄን ያያል ? አያይም ! ህግ የሜሪ ጡቶች ማማራቸውን እንደቅጣት ማቃለያ ያያል ?አያይም እናቴ አበባ ይዛ ምርቃቱ ላይ ለመገኘት ካሁኑ ስታወራ ምን ያህል በደስታ እንደምትምነሸነሽ እያወኩ ምርቃት በቴሌቪዥን ባየች ቁጥር "አሁን የኔ ልጅ " እያለች በደስታ እና በተስፋ ፊቷ ላይ የምትለኩሰውን ብርሃን እፍ ብየ ላጥፋው ? "ልጅሽስ?" ስትባል (ኧረ ሳትባልም ) በኩራት "ዩኒበርስቲ ገባኮ " እያለች በሳቅ የምትምነሸነሽ እናቴን በሃዘን አንገቷን ደፍታ እስር ቤት ሰሃን ይዛ እድሜ ልኳን እንድትመላለስ ልፍረድ? ከሁሉም በላይ እግዚያብሄር ይቅር ባይ ነው ልክ ነው ! የንስሃ ቀብድ ግን አይቀበልም < ላጥፋ እንዴ ይቅር ትለኝ እንደሆን?> እንደማለት !!

የሜሪን እጅ ከእጀ ላይ አነሳሁ ከፍራሹ ላይ ተነስቸ ቆምኩ ከዛም "መሸ" አልኳት"ውጭ" ነበር የሚመስለው አነጋገሬ ገብቷታል ተነስታ ልብሷን አስተካከለችና " አንተ ፍሪጅ አያስፈልግህም እራስህ ማቀዝቀዣ ነገር ነህ " አለችኝና ደህና እደር ሳትለኝ ወጣች  አልተመለሰችም !! የፍሪጅ ውሃውም በዛው ቆመ !!

እግዚያብሔር ታዲያ እነዲህ ሲል በታላቅ ድምፅ ያወጀ መሰለኝ " ልጀ አብረሃም ሆይ ህግጋቴን ላከበሩ በፈተና ሰአትም የቃሌን ጭላንጭል ሊመለከቱ ለተፍገመገሙ ሁሉ አንድ ጆግ ቀዝቃዛ ውሃ ቢከለከሉ እንኳን ስለነሱ አለምን በቀዝቃዛ ውሃ አረሰርሳታለሁ !!!"

ክረምት ገባ ዝናብ ውሽንፍሩ ደመናው  አዲስ አበባ ቀዝቀዝ አለች !! ክረምቱ የእኔ ክረምት መሰለኝ !!

አዲሳበባ ውስጥ ፍሪጅ ካላቸው አምሳ ሴቶች መካከል አምሳውም ስማቸው ሜሮን ይመስለኛል የፍሪጆቹ አይነትና ስም ቢለያይም ባህሪያቸው አንድ ነው "አመድ በዱቄት መለወጥ" በሰጣት ጠብታ ውሃ ጎርፍ ማንነትን በውለታ መልክ መቀበል ያምረዋል ፍሪጁ !! ፍሪጁን ከነስጦታው የሚሹ ይሄ ታላቅ ክረምት የእነርሱ አይደለም !!

(አዲስአበባ ኢትዮጵያ) (ጳጉሜ/1/2005)

# ሄደች አሉ ጋራ ጋራውን

## ይህ ተከታታይ ወግ አራት ክፍሎች አሉት

## ክፍል 1

(ውስጡ ውስጥ ያለው ነው ውስጡን የሚያስጠላው )

ሽማግሌው አንድ ማለዳ ተነሳና ባዶ ሜዳ ላይ “የሆነ ነገር “ መስራት ጀመረ !! መንደርተኛው ሁሉ ሽማግሌው የሚጎትተውን ትልልቅ ግንድ በግርምት እያየ ጠየቀው

“ምን እየሰራህ ነው?” “መርከብ!!” አለ ቆፍጠን ባለ ድምፅ

ዙሪያውን ያሉት ሰወች እንደወትሮው እየተሳሳቁና እየተጫወቱ ነበር የሚያዋሩት ሽማግሌው ግን እንጨቶቹን እየጠረበ ያለዎትሮው ሳቂታና ተጨዋች የነበረ ፊቱ በሃዘን ተኮማትሯል ፍርሃትም አርብቦበታል

“መርከብ ምንድን ነው ? “ አለ መንደርተኛው ከዚያ በፊት መርከብ የሚባል ነገር አይቶም ሰምቶም አያውቅም !

“መርከብ ? መርከብ ማለት እማ ያው መርከብ ነው” አለ ሽማግው መንደርተኛው የባሰ ግራ ተጋባ “ይሄ መርከብ ያልከው ነገር ለምን ይጠቅማል ?” ሽማግሌውን ከበው በጥያቄ አጣደፉት “መርከብ መርከብ እንግዲህ ለምን እንደሚያገለግል የሚያውቀው እግዚአብሄር ነው “ ጎረቤቶቹ ለዚህ የአምስት መቶ አመት ሽማግሌ አዘኑ “በቃ ወፈፍ አድርጎት ነው” አሉና ወደየጉዳያቸው ተበታተኑ “ካረጁ አይበጁ “ እያሉ ይሄ ሽማግሌ ሰው ግን ከምድር ሁሉ ህዝብ ተመርጦ ሊጠፉ በተደገሰለት አለምና እንደገና ሊፈጠር በታቀደለት አዲስ አለም መሃል ትውልድ መቀጠያ ክር ተደርጎ የተመረጠው ፃዲቁ ኖህ ነበረ።

ጠፊውን ከለሚው የሚያገናኝ ድልድይ አዳሜ ድልድዩን “ወዴት ትሄዳለህ” ይለዋል በድልድዩ እንደመሻገር

“““ “““ ““““

የኖህ መርከብ የጎረቤቱ አይን እያየት ግንባታዋ ተፋጠነ ሽማግሌው አንዲት ሰአት ዝንፍ ሳይል እንጨቶችን በመገጣጠም በመጥረብና በማሰር በጣም ብዙ አመታት ሰራ አንድ ቀን ታዲያ ከወደሰማይ “አባታችን ኖህ እንደምን ዋልክ “ የሚል ድምፅ ሰማ “እግዚሃር ይመስገን እንደምን ዋልክ “ ብሎ ፀሃይ ለመከላከል እጁን ግንባሩ ላይ ጣል አድርጎ ቀጥ ቢል አንዱ የመርከብ ምሰሶ ላይ ያረፈ ቁራ ሁኖ አገኘው “እረግ ቁራ አንተ ነህ እንዴ ምን እግር ጣለህ? “ አለ ኖህ ወደስራው እየተመለሰ “እረ እኔስ በዚሁ ሳልፍ አች ያረፍኩባት ምሰሶ ተጣማ ባያት ጊዜ እንድታስተካክላት ልንገርህ ብየ ነው “ አለ ቁራ “አሃ ምኗ ተጣመመ ? “ አለ ኖህ ምሰሶዋን እየቃኘ “ አይ ከላይ ሁነህ ካላየሃት አታስታውቅም ወደሰሜን አዝምማለች “ አለ ቁራ ቁልቁል ኖህን እየተመለከተ ኖህ በደንብ ሲያስተውል እውነትም ምሰሶው የተተከለበት ጎድገዋድ ውስጥ ተስተካክሎ ስላልገባ ማዝመሙን ተመለከተ ጉድጓዱ ውስጥም ጨለም ያለ ሰፊ ክፍተት ነበር “ እውነትክን ነው ጃል “ አለና ምሶሶውን አስሮ የሚጎትትበት ገመድ ሊያመጣ ዘወር አለ በዚሁ ቅፅበት ከጨለማዋ ጉድጓድ ውስጥ እባብ ፈትለክ ብሎ ወጣና በአንድ እንጨት ስር ተደበቀ እባብ በስህተት የተፈጠረችው ጉድጓድ ምቹና የምትሞቅ መቀመጫ ሁናለት ነበር በቁራ ጥቆማ ቤቱን ሊያጣ በመሆኑ እጅግ በጣም ተበሳጨ “ይሄ አቃጣሪ ቁራ “ አለ ደሙ ፈልቶ ኖህ ምሰሶውን አስተካክሎ ጉድጓዱ ውስጥ እንዳስገባ ቁራ ባናቱ ላይ እየበረረ “አሁን ግሩም አድርግህ አስተካከልከው በል ሰላም ዋል “ አለ “እግዜር ይባርክህ ቁራ ሰላም ዋል” አለ ኖህ

እባብ ተብሰከሰከ “እሽ የት አባቴ ልሂድ ሰወች ሲሳሳቱ ብቻ ነው ለእኔ ቦታ የሚፈጠረው” አለ ቀበቁራ ከፉኛ ቂም እንደቋጠረ ወደቀዝቃዛው የድንጋይ ካብ በቁጣ ተምዘገዘገ አካሄዱን ላየ እግር ያለው ይመስል ነበር ጎረቤቱ ግራ ገባው ኖህን “እብድ ነው “ ብለው እንዳይተውት እች መርከብ የተባለችው ጉድ በራቸው ላይ እያደገች መጣች “ እች ነገር ቤትም ትመስላለች መስኮት አላት “ ይላሉ “ኧረ የከብት በረትም ልትሆን ይዳዳታል “ ይባባላሉ መንደርተኛው በግምትና በትንታኔ ልቡን ሲያደርቅ ሞቱ ላይ ቁሞ ሲፈላሰፍ ኖህ ላይ ሲዘባበትና ሲቀልድ ይህ ብርቱ ሽማግሌ ግን ደይቃ ሳያዛንፍ ከንድፉ ስንዝር ሳይገድፍ መርከቧን ሠርቶ ጨረሰ ፡፡

መንደርተኛው ከጅማሬው ይልቅ በመርከቧ ፍፃሜ የባሰውን ግራ ተጋባ “ አንድ ስራ የፈታ ሽማግሌ ቀዶ የሰፋት ቆብ” እያለ ያሽሟጠጣት መርከብ ሶስት መቶ ክንድ ርዝማኔ አምሳ ክንድ ወርድና ሰላሳ ክንድ ከፍታ ያላት ግዙፍ ጉድ ሁና መንደሩ መሃል እንደተራራ ተገተረች አሁን ከመንደሩ አልፎ የከተማው ህዝብ ይጎበኛት ጀመረ “እች ነገር ወይ እንደቤት መሰረቷን ከመሬት አልቀበረች እንደው ምን ይሆን ፍጥረቷ “ ይባባል ጀመረ “ ይሄ ሽማግሌ እንጨት ሲቀጠቅጥ በድካም መሞቱ ነው” አለ ሞቱን ተሸከሞ የሰው ሞት ተንታኝ ሁሉ “ኖህ እች ነገር ምን ትሆናለች እንደው መጨረሻዋ ምንድን ነው እዚሁ በስብሳ ካፈር ልትቀበር ነው ? “

“ ካፈር በታች በስባሹንም ካፈር በላይ ነዋሪውንም እግዜር ነው የሚያውቀው ልጆች “

አለ ኖህ እያዘነ

ኖህ ስድስት መቶ አመት ሞላው ጎረቤቱ የልደት ድፎ ሊበላ በልደት ድግስ ሊጨፍርና ሊዳራ እንዳሰፈሰፈ ኖህ ብቻ ማንነቱን የሚያውቀው አስፈሪ ድምፅ ከሰማይ ተሰማ የቁርጥ ቀን ከተፍ አለች “ኖህ” አለ አስገምጋሚው ድምፅ “እንሆት ጌታየ ባሪያህ በፊትህ ነው “ ብሎ መሬት ላይ በግንባሩ ተደፋ “ወደመርከቡ ልጆችህን የልጆችህምንም ሚስቶች ይዘህ ግባ አንተ ጋር በሂወት ይኖሩ ዘንድ ስጋ ካለው እንስሳት ሁሉ ሁለት ሁለት ተባትና እንስት ይግቡ “ ኖህ እግዜር በሰጠው ስልጣን አዘዘ የዱር አራዊት የሰማይ ወፎች ወደመርከቧ ተንጋጉ እነ አንበሳ እንደጥጃ መሰሰስ ብለው ገቡ ማግሳት የለ መጎድራት እነ ነብር እነዝሆን ሁሉም ገብቶ እንዳለቀ ኖህ በሩ ላይ ቁሞ ቃኘት ቃኘት አደረገና “ቁራ የት ሄደ ? “ ሲል ጠየቀ “ቁራ እኮ የአንተን የአባታችንን ትዛዝ የማይሰማ ትእቢተኛ ነው ጌታየ “ አለ እባብ ፈጠን ብሎ

ኖህ ወደውጭ ሲመለከት ቁራ ሰውነቱ በጭቃ ተጨመላልቆና ተዳክሞ ሲበር ከሩቅ ተመለከተው በጥፍሮቹ አንዳች ከባድ ነገር አንጠልጥሏል እየበረረ መርከቧ በር ላይ ሲደርስ ከነሸክሙ ወደቀ ተሸክሞ እያንዘፋዘፈ ያመጣት ኤሊ ነበረች ከዛም በድካም እያለከለከ “አባታችን እች ኤሊ ጥሪውን ሰምታ ቶሎ ለመምጣት ስላልቻለች ይዣት ለመምጣት ስሞክር ነው የዘገየሁት “ አለ ቁራ በፍፁም ትህትና “መልካም አደረክ” አለ ኖህ ኤሊን አንስቶ ወደውስጥ እያስገባት ሁሉም ወደውስጥ ገብተው ቦታቸውን እንደያዙ ጎረቤቱ እንደአስገራሚ ድራማ ቁሞ ጥርሱን እየፋቀ ትርኢቱን ሲመለከት ማን እንደዘጋው መንደርተኛው ሳያውቅ የመርከቧ ትልቅ በር ከውጭ በኩል ተጠረቀመ በቅፅበት ደመና አንዣበበ ካለማስጠንቀቂያ የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ ዝናብ ሳይሆን ወንዝ ዘነበ

ቅድም ደረቅ መሬት የነበረው ሜዳ ወደባህር ለመቀየር አፍታ አልፈጀበትም መንደርተኛው ተራወጠ ቤቱ ጣራ ላይ ወጣ ቤቱ ሰጠመ ዛፍ ላይ ተንጠላጠለ ዛፎች ሰጠሙ ተራራ ጫፍ ላይ የወጣው ህዝብ አመለጥነው ብሎ ሳይጨርስ ተራራወች በባህሩ መዋጥ ጀመሩ ወሃው በዚህ ሁሉ ጥፋት ውስጥ የኖህን መርከብ ጨቅላ ልጁን እንደሚያቅፍ የእናት ክንድ ተንከባከቦ ከፍ አደረጋት ከፍ ከፍ ከፍ

መርከቧ ውስጥ ንቅናቄው ያንገዳገዳቸው ፍጥረታት በየወለሉ ላይ ተለሸለሹ ቁራ ከሚስቱ ጋር ወለሉ ላይ ተንደፋደፈ እባብ አንድ ምሰሶ ላይ ተጠምጥሞ ከወደቁት ስፍር ቁጥር የሌላቸው እንስሳት መካከል መርጦ ቁራን እንዲህ አለው “ልፍስፍስ አቃጣሪ ለነገር ሲሉህ አንደኛ ነህ ለችግር ግን እች ጠቋራ ሚስትህን ይዘህ ትገነደሳለህ ውዳቂ “ ቁራ የእባብ ዘለፋና የስድብ ውርጅብኝ ግራ አጋብቶት “እኔን ነው ? “ አለው

# ክፍል 2

ውሃው እስኪሞላና መርከቧም ከፍ እስክትል እንስሳት ሰው እና እቃ በየሸርኩቻውና በየ ወለሉ ሲወድቅ ሲነሳ አንዱ በአንዱ ላይ ሲወድቅና አቅም የሌለው በባለ ጉልበቱ ሲጨፈላለቅ ቆይቶ መርከቧ መናወጧን አቁማ በከፍታ ስትንሳፈፍ በውስጧ የነበሩት ሰወችና እንስሳት ሁሉ ከየወደቁበት ተነስተው ቦታ ቦታቸውን ያዙና በነውጡ ወቅት የሰሩትን ጀብዱ ይተርኩ ጀመረ

“መርከቧ ወደግራ ስታዘም በቀኝ በኩል ሁኘ ወጥሬ ባሊዝ እስካሁን አዳሜ አልቆልሽ ነበር” አለ “አንበሳ” በመርከቧ ቀኝ በኩል ተዘርሮ በፍርሃት ሲናጥ እንዳልታየ “ ጣራዋ ተደርምሶ ሊጫነን ሲል በኩንቢየ የያዝኩት እኔ ነበርኩ “ እያለ ዝሆን ፉከራ ቃጣው “ ምሰሶው ላይ ተጠምጥሜ ባልይዘው ኑሮ እች መርከብ እስካሁን እንጦሮጦስ ነበረች “ አለ እባብ ኖህ ሁሉንም በዝምታ ሲያዳምጥ ቆይቶ “የሁላችሁንም ፉከራና ጀብዱ ሰማሁ ግን ከእናተ መሃል ከመርከቧ ውጭ ቢሆን ኖሮ በብርታቱና በጉልበቱ የሚተርፍ ማን ነበር አስቲ ይሄን መአበል አስቁሞ መርከቧን አንዴ ወደግራ አንዴ ወደቀኝ ከመባዘን የሚያድን ጀግና ማነው ? “ አለና ጠየቃቸው ምድረ ፎካሪና አሽቀራሪ አንበሳ ነሽ አቦ ሽማኔ ዝም ጭጭ!! ስለመርከቧ ተፈለጥኩ ተቆረጥኩ ባይ ሁሉ የምር ጥያቄ የተሰነዘረች ቀን አፉ ተለጎመ !! የትላንትን መፈለጥ መቆረጥ እያወሩ ዛሬ ግራ በገባው ማረፊያውን ባላወቀ ሚስኪን ተሳፋሪ ፊት ራሳቸውን የሚቆልሉ ሁሉ ጭጭ!!

ኖህ ቀጠለ “አያችሁ መርከቧን ያቆመ ፈጣሪ ነው መርከቧ ውስጥ ያሉትን ጠባቂም ራሱ ፈጣሪ ነው ሁላችንም የምንራወጠው በሂወት መአበል እየተናጥን እንጅ በጀግንነታችንና በብርታታችን አይደለም መአበሉ አንዱን ከላይ አንዱን ከታች ያደርገዋል አንዱን ይጥላል አንዱን ያነሳል የቆምክ ዘላለም የምትቆም መስሎህ አትጀነን “ማንም የቆመ ቢመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ “ እንደተባለው ውሃ የበላቸው ወገኖቻችንም እንደእናተ በትእቢት ሲወጠሩ ነው ዝማ የወረዱት እንዴት የቆመው ከሞተው አይማርም ? ያተረፈን ፈጣሪ ብቻ ነው “ አለና ትቷቸው ወደምኝታው ሄደ  ዝምታ ሰፈነ መርከቧ በቀስታ ምድርን ባጥለቀለቀው ውሃ ላይ ትንሳፈፍ ጀመር እንደቁራጭ ቅጠል  ማረፊያዋ ናፍቋት

*** ***

ጧት ቁርስ ሰአት ላይ ኖህ እና ልጆቹ እንስሳቱ የሚበሉትን እንደየድርሻቸው ሲያድሉ ቆይተው ቀጥ ቢሉ ለወትሮው የሚስገበገቡት እንስሳት በኩርፊያ ፊታቸውን ኮሶ አስመስለው የቀረበላቸውን መኖ ንክች ሳያደርጉ ቁመዋል ከድፍን የመርከቧ ፍጥረት ቁራና ሚስቱ ብቻ ነበሩ የተበተነላቸውን ስንዴ በፍቅር እየተጎራረሱ በደስታ ሲበሉ የነበሩት በኋላ ግን የሙሉ መርከቧ ዝምታ እና ኩርፊያ አስፈርቷቸው የማንቁርታቸውን ጥሬ ጥለው ግራ በመጋባት ቆሙ “ምን ሁናችኋል አትበሉም እንዴ? “ አለ ኖህ ግራ ተጋብቶ “አንበላም “ የሚል የቁጣ ድምፅ መርከቧን አናወጣት “ አሃ ለምን ቢባል ?” የበለጠ ተገርሞ

“ አባታችን ኖህ በእውነት ታላቁ እና መሃሪው እሩህሩሁና አዛኙ አምላካችን እግዚአብሄር ተሰድቦ እንዴት እህል ልንበላ ይቻለናል “ አለ አንበሳ በአስፈሪ ቁጣ ኖህ በሰማው ነገር ደነገጠ “ማነው እግዚያብሄርን የሰደበ ከመካከላችሁ? “ አለ ኖህ በቁጣ አይኑ እየተንተገተገ አንበሳ ወደእባብ እያየ “ እባብ ያየኸውን ለአባታችን ኖህ ሳትቀናንስ ንገረው” አለው በትእዛዝ አይነት ድምፅ

እባብ በደረቱ አንድ ሁለቴ ሳብ ሳብ ብሎ ወደፊት ወጣና “እድሉ ስለተሰጠኝ እግዜር ይስጥልኝ እንግዲህ ጌታየ መቸም ሁላችንም ለዚህ የበቃነው በአምላካችን፣ በታላቁ፣ በሁሉን ቻዩ፣ በአዳኙ እና በጥበበኛው አምላካችን እግዚያብሄር ነው አይደለም እንዴ ጓዶች “ አለ ወደእንስሳቱ ዞሮ “እውነት ነው “ “መልካም ብለሃል” “አይ መማር ደጌ” “እሰይ የኔ ንግግር አዋቂ “ “ አንደበተ ጣፋጭ “ እያሉ እባብን በታላቅ ጫጫታና ሁካታ ደገፉት አደነቁት አበረታቱት በዚህም የልብ ልብ የተሰማው እባብ ንግግሩን ቀጠለ

“ እናም አባታችን ኖህ ትላንት በጉልበታችንና በአቅማችን የተረፍን መስሎን ስንፎክር አንተ የታበረክ እና በግዜር የተመረጥክ አባታችን ” ታላቁ እግዚአብሄር ነው ያዳናችሁ የተናገራችሁት ሃጢያት ነው” ስትለን ስሀተታችን ገብቶን ሌሊቱን በታላቅ ሃዘንና የንሰሃ ፆለት “ይቅር በለን” እያልን ስናለቅስ ነው ስቅስቅ ስቅ ብለን ስናለቅስ ጌታየ አዎ እንዲያ ነው ያደርነው አዎ ተንበርክከን ስንፀልይ “ አለ እባብ እንባውን እየጠረገ

“ሌሊት ፆለት ነበር እንዴ “ አለች የቁራ ሚስት ወደባሏ ጆሮ ጠጋ ብላ “ኧረ እኔ አልሰማሁም ተኝተን አልፎን መሆን አለበት “ አለ ቁራ ተገርሞ

እባብ ቀጠለ “ ይሁንና ጌታየ በዚህ መሃል ፈጣሪያችን ሲሰደብ ሰማሁ” አለና ስቅስቅ ብሎ ሲያለቅስ ሁሉም ይላቀሱ ጀመረ

“ቆይ እስቲ አንዴ ማነው ተሳዳቢው ምንስ ብሎ ተሳደበ “ አለ ኖህ በቁጣ

“ ይሄ ቁራ ነዋ ” አለ እባብ ወደቁራ በመርዙ እየጠቆመ ቁራ በድንጋጤ ከሰፈረበት ቆጥ ላይ ሊወድቅ ክንፉን አርገብግቦ ተረፈ “ ማን እኔ “ አለ ቁራ “ዝም በል አፍ አለኝ ብለህ ልታወራ ነው “ እንስሳቱ ሁሉ ወደቁራ ተንደርድረው ለፃብ ተጋበዙ ቁራና ሚስቱ በፍርሃት ተቃቅፈው ኖህን እንዲያድናቸው በአይናቸው ተማፀኑት “በቃ” አለ ኖህ ቡጩኸት ሁሉም በርግገው ወደቦታቸው ተመለሱ “ምን ብሎ እንደተሳደበ ተናገር “ አለው እባብን “ጌታየ እኔ በግዜር ላይ የስድብ ቃል ከአፌ ላወጣ እንደሱ ድፍረት የለኝም “ አለ ወደቁራ እየጠቆመ “ይሁንና ተናገር ካልከኝ ቁራ ሌሊት አጠገቡ ሰው የሌለ መስሎት ለሚስቱ እንዲህ ሲል ነበር “ይሄ ኖህ የሚባል ስራ ፈት ሽማግሌ “እግዜር ነው ያተረፋችሁ” ይላል እንዴ እግዚያብሄር ምን ያተርፈናል አጎቶቻችንን ፣አክስቶቻችንን ፣አብሮአደግ ጓደኞቻችንን እና ጎረቤቶቻችን ሁሉ በውሃ አስበልቶ እኛንም እዚህ ሳጥን ውስጥ አሽጎ አስቀመጠን እንጅ አላየንም ማዳን “ ሲል ቃል በቃል ሰምቸዋለሁ አለ እባብ

“ወይ ነዶ “ አለ አህያ በእግዜር መሰደብ ተቆጨሁ ሊል ከወደ ጥግ ሌሎቸሁም ተንጫጩ

ኖህ በጥሞና ሲያምሰለስል ቆየና ቁራን “ ና እስቲ ወድስጥ “ ብሎት ለሰወች ወደተዘጋጀው ክፍል ወሰደው ገባ ቁራ ከነሚስቱ ኖህን ተከተለው “ምንድነው የምሰማው እውነት ነው ይሄ ፀያፍ ቃል ከአንተ ወጥቷል “ አለ ኖህ በጥርጣሬ ቁራን እየተመለከተው “ኧረ ጌታየ እኔም ያለዛሬ እንህ ያለ ነገር አልሰማሁ እንኳዋን ከአፌ ሊወጣ “ “እና ከየት አምጥተው አወሩት “ “ኧረረረረ ምን አውቄ ጌታየ “ “የለም! ካለነገሩ ነገር አይወራም ሃቁን ተናገር “ አለ ኖህ ተቆጥቶ “ይሄው ከምወዳት ሚስቴ ከቁሪት ይለየኝ ቀብሬን ባህር ላይ ያርገው ቃል አልተነፈስኩም “ አለ ቁራ እንባ በአይኑ ሞልቶ ያሳምንበት ቃል ጠፍቶበት ኖህ መንፈሱ የቁራን ሃቀኝነት ሹክ አለው ቁራ ነፃ ወጣ

ይሁንና ቁራና ሚስቱ ቁሪት ከመላው እንስሳ ተገለሉ አብሯቸው የሚያወራ አጠገባቸው የሚደርስ አንድ እንኳን ፍጥረት ሳይኖር ወራትን ገፉ ፍቅራቸው ብቻ አፅናኝ ሁኗቸው እባብ በዚህም ተንገበገበ ቀና ተብሰከሰከ ቁራና ቁሪት እርስ በእርስ በፍቅር ሲተካከኩ “ቁንቁናችሁን አታራግፉብን ወዲያ” እያለ ያሾሙራል የራሱ የቅናት እና ተንኮል ቅንቅን ማከኪያ ጥፍር ጠፍቶለት ማራገፊያ መላ አጥቶለት ቁንቁናም ይላቸዋል ሲያልፍ ሲያገድም

መከራ አንድም ፍቅርን ይስላል አንድም ፍቅርን ያዶለዱማል የነቁራ ፍቅር በመከራ ውስጥ ስለቱ አብለጨለጨ ከመርከቡ ታዳሚ እንዲያስራቸው የተወረወረባቸውን የመገለልና የብቸኝነት ገመድ የፍቅራቸው ስለት እየበጣጠሰ ተንኮል በነገሰበት መርከብ ማግለል በተንሰራፋበት የመዳን ዋሻ የእነቁራ ፍቅር ፈካ

በዚች ምድር የትኛውንም አይነት የሚታይም ይሁን የማይታይ ጦር እና ፍላፃ የሚከላከል ወደር የለሽ ጋሻ ፍቅር ነው !! ቁራና ቁሪት በዚህ ጋሻ ከአንበሳ ፉከራ ከእባብ ተንኮል ከተከታይ እርግማንና ጫጫታ ተከልለው በርካታ ወራቶች ኖሩ እንስሳቱ እባብን ከበው ይቆሙና ዞር ብለው እነቁራን አየተው በሳቅ ያውካካሉ በእርግጥ ቅስም የሚሰብር ውስጥንም የሚነካ ነገር ነበር

አንዳንዴ ደግሞ ቁራ እንዲሰማ አድርገው “ እች ጠቋራ ሚስቱ እኮ የለየላት አለሌ ነበረች ትዝ አይላችሁም እንትና ጫካ እንትን ወንዝ ከጅግራ ጋር ስትዳራ ከእርግብ ጋር ስትሳሳም ከጥንባሳ ጋር በየሜዳው ክንፏ እስኪቀጥን ስትበር ዱርየ የጠየቀ የማያጣት የወፍ ዘር ሁሉ የድርሻውን የዘገነላት ወፍ አውል “ እያሉ ያወራሉ ቁራ እየሰማ ችሎ ዝም ይላል

ሌላ ቀን ቁሪትን ቅዱስ ያደርጉና ቁራን ይቦጭቁታል “ይሄ ልክስክስ ሴት ወፍ ተከትሎ አለም መጨረሻ ድረስ ይሄዳል እንደው እችን የመሰለች ቁሪተ ምን ነክቷት ነው እዚህ አቃጣሪ ወልጋዳ ጠቋራ አመዳም ቁራ ጋር የተለጠፈችው በናታችሁ “ ይባባላሉ

ቁሪትና ቁራ ግን የሰሙትን እንደእሳት የሚለበልብ አሽሙር በፍቅር መወድስ ያጠፉታል እንዲህ ይላታል ቁራ ቁሪትን “ የእኔ እመቤት የእኔ ጥቁር አልማዝ አውቅሻለሁ ፀሃይን በእጆቹ የነካ ማነው ሁሉም ግን ይመኛል የ አንችንም የክንፍሽን ጫፍ የነካ የወፍ ዘር የለም !! እንኳን ሰውነትሽ የበረርሽበት ሰማይ ያረፍሽበት ዛፍ ቅዱስ ነው የኔ ንፁህ የልቤ ፅላት ነሽ የፍቅር ቤተ መቅደሴ “ ይላታል ከልቡ የዛን ሁሉ ሃሜተኛ ፣ከፉ፣ሽራኛ ፣ነጃሳ፣ ተሳቢ ተራማጅ ተንፉቃቂ ሃሜኛ ሁሉ አሽሙር ከልቧ ድረሹን ያጠፉዋል ድምፅ ብቻ ሳይሆን ነብሱ ቃል ሁኖ ወደነብሷ ሲፈስ ልቧን ደቅና ትቀደዋለች እንዳሉባት መርከብ በመወድሱ ትንሳፈፋለች በፍቅሩ መአበል ልቧ ይናወጣል

“ አውቅሻለሁ ከሃዲ እንዳልሆንሽ ያኔ አነር ነክሶኝ ታምሜ የተኛሁ ጊዜ ቁራጭ ስጋ በአፍሽ አንጠልጥለሽ እልፍ አእላፍ ርቀት ተጉዘሽ የምትመግቢኝ ፍቅሬ ነሽ አውቅሻለሁ አየር ቀዛፊ ክንፋቸው ልብ የሚያርድ የወፍ ዘሮች እንደመለአክ ዙሪያሽን ሲያረቡ ደመናውን ሰነጣጥቀሽ ወደእኔ ስትበሪ እንዳንች ታማኝ ለፍቅር ሟች በምድር የለም የኔ ወላንሳ” ይላታል አይኖቿን ጨፍና ደረቱ ላይ ፍስስ ትላለች ምድረ እንስሳ በቅናት ድብን ! እባብ በብስጭት ዙሮ ጅራቱን እስኪነድፍ

አንድ ቀን ሌሊት እንስሳው ሁሉ እንደተኛ እርግብ ቀስ ብላ ወደቁራ ሄደች እንስሳቱ “ ከእድራችን ተለይታ ያወገዝነው ጋር ታየች “ እንዳይሏት ፈርታ ቀን ባታናግረውም ሌሎቸሁ ወፎች ተካፍለው የሚበሉትን ነገር ሁሉ በዚህ አይነት ሌሊት ላይ ለቁራ ታቀብለዋለች ቁራና ቁሪት ያሳዝኗት ነበር ቀስ ብላ ቁራን ቀሰቀሰችውና ወደአንድ ጥግ ወስዳ የአሳ ቁራጭ ሰጠችው “አይዟችሁ” ብላው ሄደች እባብ በዚች ቀን እንደአጋጣሚ ሲቀባበሉ ተመለከታቸው (ሰይጣን ቀስቅሶት መሆን አለበት )

## ክፍል 3

እባብ እንቅልፍ በአይኑ ሳይዞር አደረ እርግብና ቁራ የተቀባበሏትን ቁራጭ አሳ በቅናት ውሃ በተሞላ ባህር አይምሮው ውስጥ አሳድጎ አሳ ነባሪ አሳከላት እችን ቅብብል እንዴት አድርጎ መርከቧን የምታናውጥ ወሬ እንደሚያደርጋት አወጣ አወረደ “ለምን እግዚያብሔር እንዳትበሉ እርኩስ ነው ያለውን ስጋ ሲቀባበሉ አየሁ አለልም “ ሲል ሃሳቧን አምሰለሰላት “አዎ ቁራጭ አሳ ሃይማኖታዊ ጭራ ከተቀጠለላት ባህሩን የምትንጥ መርከቧን የምትገለብጥ አሳ ነባሪ መሆን ትችላለች “ አለና ለራሱ አረጋገጠ ግን ሃሳቡ አልዋጥ አለው ምክንያቱም “ እነአንበሳ እነዝሆንና እነነብር እምነታቸው ጉልበት ነው ለሃይማኖት ግድ የላቸውም ብነግራቸውም ችላ ሊሉት ይችላሉ ሌላ ስስ ብልት መፈለግ አለብኝ የሚያጋጭ የሚያናጭ ” አለና መልሶ በሃሳብ ተዘፈቀ

“ ለምን ፖለቲካ አላደርገውም ይሄ በትክክል ፖለቲካ መሆን የሚችል ጉዳይ ነው !! ቁራጭ አሳን ፖለቲካ የማድረግ ጥበብ ቀላል ነው እች መርከብ በውስጧ ያለው ትንሽ ምግብ በመሆኑ እንስሳው ሁሉ እስኪጠግብ እንደማይበላ የታወቀ ነው ታዲያ ሌሊት ሌሊት “የአሳ ስጋ ሲቆርጡ እና ውስኪ ሲጠጡ “ የሚያመሹ ለፍቶና ደክሞ የሚኖረው ሚስኪን ጭቁን የመርከቧ ነዋሪ ሆዱ እየጮኸ ሲተኛ “ጨለማን ተገን በማድረግ “ ጮማ የሚገባበዙ ሆዳሞች “ በመሃላችን አሉ “ ይሄ ብቻ አይደለም ጮማ እየቆረጡ እችን የሰላም መርከብ ከጉዟ

ሊያሰናክሉ በሌሊት ይመካከራሉ ብል ሁሉም ሆድ ይብሰዋል “ አለና እባብ ባቀናበረው ሃሳብ ተደሰተ ቆይቶ ግን ይሄንኛውንም ሃሳብ ውድቅ አደረገው” እዚች መርከብ ውስጥ ፖለቲካ ማለት የነፈሰበት ጨዋታ ነው ማን ግድ ይሰጠዋል ” አለና ተከዘ

እባብ ሲያሰላስል ቆይቶ ቁራጯን አሳ “ከዘር” ጋር ሊያያይዛት ወሰነ እንዴት እስካሁን እንዳልመጣለት ገረመው ከዛም ነገ ለመርከቡ ነዋሪ እንዴት ጉዳዩን አካብዶ እንደሚነግራቸው ማሰላሰል ጀመረ “ ጀግናው የአንበሳ ዘር የዝሆን ዘር የነብር ዘር የጎሽና የጉማሬ ዘር ሁሉ ስማኝ ተደፍረሃል አንተ ባቀናሃው ጫካ ደምህን ባፈሰስክበት ምድር ሲበር የኖረ መድረሻቢስ የወፍ ዘር ሁሉ አንተን አስተኝቶህ አሳ ይገባበዛል አሳወችም ስሙ አንድ ባንድ ከውሃ እያወጣ እየለቀመ ሊጨርሳችሁ ዘረኛው የወፎች ቡድን ሌሊት ሌሊት እየተመሳጠረ ነው “ እባብ አሳክቶ ባዘጋጀው ንግግር ረካ እች መርከብ ነገ የጦር ቀጠና ስትሆን የት ላይ እንደሚቀመጥ ገለልተኛ ቦታ መረጠ ከዛም በእርካታ ለጥ ብሎ ተኛ

**** **** *****

ኖህ የዘወትር ፆለቱን እያደረሰ ባለበት ማለዳ መርከቧን የሚያናውጥ ታላቅ ድምፅ ተፈጠረ በድንጋጤ ፆለቱን አቋርጦ ወደእንስሳቶቹ አዳራሽ ቢገባ “ምድር ቃጤ” ሁናለች ፎካሪው አሸቀራሪው ባለመፎከሩ ታሪክ ነጋሪው ሁሉ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል ገላጋዩ ሲረብሽ ረባሹ ይገላግላል ወዲው ደግሞ ገላጋዩ ረባሽ ረባሹ ገላጋይ ይሆናል ግርግሙ ሁሉ ተሰባብሮ ጎርፍ የዘለለበት ከተማ መስሏል መርከቡ !!

“ምንድን ነው? “ አለ ኖህ ከእግዜር የተቸረው ግርማ ሞገስ አስፈሪ ነውና ሁሉም የኖህን ድምፅ ሲሰሙ ዝም አሉ “ጌታየ ተከባብረንና ተፋቅረን የምንኖርባትን መርከብ ዘረኞች በጠበጧት “ አለ ነብር “እንዴት ማለት” አለ ኖህ እንስሳው ሁሉ እየተቀባበለ እየተሽቀዳደመ ስለቁራና ርግብ “የሌሊት ግብሣ” ለኖህ ነገረው ኖህም እባብን ተርቶ ስለጉዳዩ እንዲያስረዳ አዘዘው

“ጌታየ የሆነው ነገር ሁሉ ህልም እንጅ እውነት አይመስልም ቁራ ከምኝታው ተነስቶ ወደ እርግብ ምኝታ ሄደና ባለቤቷ መተኛቱን ካረጋገጠ በኋላ ቀስ ብሎ ቀሰቀሳት እሷም ተከትላው ወደዛ ወደውሃ ማስቀመጫው ሄዱ እኔ ደግሞ ““እንደሁልጊዜው ሊሳሳሙና ሊዳሩ ነው ብየ““ ችላ አልኳቸው “ አለና በቆረጣ የቁራን ሚስት አየት አደረጋት ተሳክቶለት ነበር ፊቷ ተቀያይሮ ቁራን በቁጣ ስታየው ተመለከተ “ ከዛ ከየት እንዳወጡት ያላየሁትን አሳ አወጡና እየተጎራረሱ እየተገባበዙ ዋጥ ስልቅጥ አደረጉት እና በቁጠባና በፈረቃ እየተመገብን እነሱ ተረፏቸው ሁሉ ሲጫወቱበት ነበር በቃ በዚች መርከብ ውስጥ የወፍ ዘር ካልተሆነ መኖር አልተቻለም ጌታየ “ አለና በውሸት ምሬት ተንገፈገፈ

“ ለመሆኑ ይህን ነገር ያየ ሌላ ሰው አለ ;” ሲል ጠየቀ ኖህ ሁሉም ዝም አሉ “እስቲ የሌሊት ወፍ ወዲህ ነይ ሌሊት የት ነበርሽ “ “እዚሁ አካባቢ ስዞር ነበር ጌታየ “ አለች የሌሊተ ወፍ “የተባለው እውነት ነው ?” “ኧረ ጌታየ አላየሁም እኔ ያየሁት እንደሁልጊዜው ርግብ ለቁራ የተራረፈ ቁራጭ አሳ ስትሰጠው ነው ይህ ደግሞ ከማዘን የመጣ እንጅ ሌላም ተንኮል ያለበት አይመስለኝም “ አለች እባብ አይኑን አጉረጠረጠባት

ኖህ በታላቅ ቁጣ “አንድ ጩኸትና ግርግር እነዳልሰማ “ብሎ ወደእባብ እና ወደሌሎቹም አንባረቀባቸውና ወደውስጥ ገባ ነገሩም በዚሁ በረደ በእርግጥም ኖህ እባብ እንደዋሸ በሚገባ አውቆ ነበር

ምንም እንኳን ግጭቱ ባጭር ቢቀጭም ቁሪት ልብ ውስጥ ግን ከፉኛ ቅሬታ አድሮ ነበር ባሏ እሷን አስተኝቶ እርግብ ጋር መዳራቱን አምናለች እባብን ባታምን እንኳን የሌሊት ወፍም ሁልጊዜ እንደሚገናኙ መስክራለች ህዝብ ይቅር አለህ ማለት ሚስትህ ይቅር አለችህ ማለት አይደለም ሚስትህ ይቅር አለችህ ማለት ሂሊናህ ይቅር አለህ ማለት አይደለም እናም እችን ክፍተት አስፍቶ ቁራና ቁሪትን ሊለያይ እባብ ቆርጦ ተነሳ !!

እባብ ወደ ቁሪት ሄደና እንዲህ አላት “እንደማትወድኝ አውቃለሁ በእርግጥ እኔ ማንም ወደደኝ ጠላኝ ግድ የለኝም ግን እዚህ ሁላችንም ወገኖቻችንን ጥለን ነው የመጣነው እርስ በእርሳችን ካልተረዳዳን ማንም

አይመጣልንም ለዛ ነው አንጀቴ አልችል ስላለ አንድ ነገር ልመክርሽ የመጣሁት ወንዶች ሲባሉ በፍቅር ሲወድቁላቸው ሲታመኑላቸው ሴትን እንደጅል የማየት ክፉ አባዜ አለባቸው "አንች ውብ ነሽ" እዚህ ያለ የወፍ ዘር ሁሉ የሚመኝሽ የሚሰግድልሽ ገና ለገና ጠቆር አልሽ ብሎ አፍንጫሽ ስር ከእርግብ ጋር ሲዳራ ማየት ያማል ሁላችንም እህት አለን ለምን እንዲህ ይሰራል " ሲል ሰበካት

" ስማ እባብ የፈለገውን ቢያደርግ ቁራን አምነዋለሁ" አለች እርግብ ድምጧ ግን እንደወትሮው በፍቅርና በራስ መተማመን የተሞላ አልነበረም ገብቶታል እባብ ሲጀመር ለክፉ አፍ መክፈት ትረፉ ሌላ ክፋት እንዲወልድ መርዳት ነው

እባብ ቀጠለ " የገረመኝ ደግሞ እርግብን ሲያደንቃት ለነገየ አለማለቱ "የኔ ማር የላባሽ ንጣት እኮ በረዶ ነው የሚመስለው ሚስቴ ቁሪት ጋር ስውል ቀኑ ጨለማ ይመስለኛል አንችን ሳይሽ ግን ሌሊቱ ቀን ይሆንልኛል አላት እርሷ ደግሞ ደረቱ ላይ እየታከከች አይኖቿን ጨፍና በደስታ ስክር "

ቁሪት ዝም አለች

" በእርግጥ እርግብ "ኸረ ቁሪት እንዳትሰማ " ብላው ነበር ባልሽን ወዳንች እያሳየች እሱ ግን በንቀት ወዳንች እያየ ባክሽ አንዴ ከተጋደመች አትነቃም ገና በጊዜ ትሰፍራለች ስታንኮራፉ ታድራለች ብሏት ተሳሳቁ "

" ደደብ በላቸው ሳቁ አልሳቁ " አለች ቁሪት በእልህ "እኔ እንድትበሳጭ አይደለም የነገርኩሽ ያው ማንም ሲጠቃ ስለማልወድ ነው ይቅርታ አሳዘንኩሽ በቀረብኝ ባልነገርኩሽ " አለ እባብ ያዘነ ለመምሰል ፊቱን ከስክሶ

"ኸረ አንተ ምን አደረክ እባብ"የ" ለእኔ ብለህ ነው " አለች ቁሪት "እኔ የምልሽ ቆንጆ "አለ ቁራ በተበረገደው የዋህ የቁሪት ልብ ሙሉ ክፋቱን ሊያንጋጋው እተዘጋጀ "ወይየ " አለች ቁሪት በጉጉት "ለምን ለዚህ ከሃዲ ልክሽን አታሳይውም "በሚያደፋፍር ድምፅ "እእ እኔማ ከትላን ጀምሮ ዘግቸዋለሁኮ " አለች "ኤዲያ መዝጋት ምን አላት እሱ እንኳን አንች ሁላችንም ዘግተነው መች ተሰማው ይልቅ የናቀሽን ያህል ከሱ የተሸለ ወንድ "ጠብሰሽ" አሳይው በቅናት ይብገን እግርሽ ላይ ወድቆ ይቅር በይኝ ይበል " አላት "አይ እንደዛ እንኳን " አለች ቁሪት ፈፅሞ ያላሰበችው ነገር ሁኖባት "ባክሽ አታካብጅው እስቲ አሁን ማን ይሙት ከንስር የበለጠ ጀግና ልበ ሙሉ ወንድ ወፍ አለ ንገሪኝ አለ? ታዲያ በፍቅርሽ ማበዱን አታውቂም ?" "ማን ንስር በእኔ ፍቅር " አለች ቁሪት ልቧ መምታቱን ሊያቆም ነበር በድንጋጤ "አዎና ሁሉም ያውቃል ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው አሉ አልሰማሽም ?" "ኸረ እኔ " "በቃ በኋላ እናወራለን " ብሎ መንገድ ሲጀምር "እንዴ አውራኝ እንጅ እንዲህ ልቤን ሰቅለህማ " "በኋላ እናወራለን " ብሏት ሄደ

ቁሪት ሃሳቧ ሁሉ ስለ ንስር ሆነ አይኗን ከእርሱ ላይ መንቀል አልችል አለች እንደውም በአጋጣሚ አይናቸው ደጋግሞ መጋጨት ጀመረ "ውይ አይኖቹ ሲያምሩ" አለች በውስጧ ስለንስር ጀብዱ ሲወራ ብዙ ሰምታለች እናትና አባቷ ሳይቀሩ ከዘመነ ጫጩትነቷ ጀምሮ ንስርን ሲፈሩና በስሙ ሲርበደበዱ ታውቃለች የወፎች ንጉስ መሆኑን ከደመና በላይ በግርማ ሞገስ እየተንሳፈፈ ጠላቶቹን ድባቅ እንደሚመታ እንደውም ሰወች ሳቀሩ ሲደናነቁ "እንደንስር ብርቱ" እንደሚባባሉ ብዙ ነገር ሰምታለች እና ይሄ ታላቅ ፍጥረት በፍቅሯ መውደቁን ስትሰማ ተሸበረች

በቀጣዩ ቀን እባብ ወደንስር ጠጋ አለና "ግን አንተ ያዩህ ሴቶች ሁሉ እንዲህ በፍቅር ውድቅ የሚሉልህ ለምንድን ነው ? " ሲል ጠየቀው "ለማን ለኔ " አለ ንስር ተገርሞ "ታዲያ ! ቁሪት ባንተ ፍቅር አብዳ የባሏ አይን ሁሉ አስጠልቷታል አላወኩም ልትል ነው " "እኔ አላውቅም " አለ በጉጉት ወደእባብ ጠጋ ብሎ ሌላ ወግ ለመስማት " እችን ይወዳል በቃ አንተን ካላየች ምግብ ሁሉ አትበላም " " አሃ ለካ ሰሞኑን የምታፈጥብኝ " አለ ንስር በሃሳቡ ንስር ቀጥ ባለ ቁጥር ቁሪት ጋር መፋጠጥ ሆነ አይናቸውን እያስለመለሙና ሆን ብለው ሊተያዩ የሚችሉበት ቦታ መርጠው በመቀመጥ ፍቅር የመሰላቸውን የተንኮል መረብ በጋራለበሱት ሲተላለፉና ባገጣሚ ሲቀራረቡ ሁነ ብለው መነካካት ጀመሩ በተለይ ቁሪት ሰውነታቸው በተነካካ ቁጥር የሚነዝራትን አንዳች ስሜት መቋቋ ፈተና ሆነባት

አንድ ሌሊት ቁራ ከእንቀልፉ ሲነቃ ቁሪት ከጎኑ አልነበረችም ቀጥ ብሎ ግራ ቀኝ ሲቃኝ ልክ ርግብ ጋር ቁራጭ አሳ የተቀባበለበት ቦታ ላይ "ታላቁ ንስር" ደረት ላይ የእርሱ ቁሪት በሰመመን ደገፍ ብላ አለሟን ስትቀጭ እንደህልም ብዥዥዥዠ ብላ ታየችው ቁራጭ አሳ እየተቀበለች አልነበረም ሙሉ እሷነቷን እያስረከበች እንጂ

# ክፍል 4

ቁራ በዚች ምድር ላይ አለችኝ የሚላትን ሚስቱን አጣ የንስርና የቁሪት ወዳጅነት በድፍን የመርከቡ ታዳሚ ተደነቀ "እንዲህ ነው ነው እንጅ ሲያገጣጥም" ተባለለት ቁሪትና ንስርም በወረት ፍቅር ክንፋቸውን ጥለው አበዱ ሲበሉ አብረው ሲጠጡ አብረው ሌላው ቢቀር "ንስር " ተብሎ ሲጠራ ቁሪት "አቤት" እስከማለት ደረሰች የተዘፈቀችበት እግር እጅ የሌለው እልህ ከተከበበቸበት ጋር ተዳምሮ የቁራን የነብስ ጩኸት እንዳትሰማ አደነቆራት!!

ፍቅር ተራቁቶ መለመላውን ሲቀር ማንነት ስለሚበርደው ድሪቶ ይሰበስባል  የአድናቆት ድሪቶ የስም ድሪቶ የአጃቢ ድሪቶ የቁሳቁስ ድሪቶ ፍቅር ውስጥ የምትፈጠር ቀዳዳ በፍቅር ካልተደፈነች በምንም አትደፈንምና ስለድሪቶ ፍቅራቸውን መስዋዕት ያደረጉ መደራረብ ሙቀት የሚሆን መስሏቸው እድሜ ልካቸውን እንደተንኳተቱ ይኖራሉ ስጋ ላይ የተደረበ ድሪቶ የነብስን ገመና ይሸፍን ይመስል !! ቁሪት ዝነኛ ሁና ነበር ግን ዝናዋ ባዶነቷን ያማይደፍን ሆኖ ነብሷ ለማዛጋት አፍታ አልፈጀበትም ወደአቅሏ ልትመለስ ከቅዠቷ ስትባንን እባብ እና ቢጤዎቹ በተስፋ ጭብጨባ ከነፍስ ጥያቄዋ ያጣሏታል "አቤት ንስርና ቁሪት የሚወልዱት ልጅ " እያሉ ዘር መርጠው ማንነት አነፍንፈው ድሪቶ ትውልድ ስለፈጠሩ ምድር ላይ ቅድስና ያሰፍኑ ይመስል ድሪቷም ተስፋ ይደርታሉ

ቁራ በአንድ ወር ውስጥ ጀርባው ጎበጠ አይኖቹ ቦዘዙ ሁለት ሶስት ቀን አንድ ቃል ሳይናገር የሚቆይበት ጊዜ ነበር ከባድ ዝምታ ውስጥ ተዘፍቆ የማያዩ አይኖቹን አፍጥጦ ቆጡ ላይ በትካዜ ይውላል ቁሪትን ለማነገር አፍታ ጊዜ እንኳን ማግኘት አልቻለችም ሁልጊዜ አጀብ ውስጥ ናት ሁልጊዜ እባብ አጠገቧ አለ ሁልጊዜ ንስር ደረት ላይ ናት "አንድ እድል " ይላታል እናባ በኳተሩ አይኖቹ እያየት አታየውም !!

ቁራ ከፉ ደግ አልወጣውም ቀስ በቀስ የምግብ ፍላጎቱ ቀንሶና ቅስሙ ተሰብሮ አንዳንዴ ብቻውን ማውራት ሁሉ ጀመረ እርግብ ሁኔታው አንጀቷን ቢበላውም እርሷም በባለቤቷ ዘንድ ታላቅ ወቀሳ ደርሶባት ነበርና ልትረዳው አልቻለችም አንዴ ቁራ በጣም ስለተራብ ከሚታደለው ምግብ አንዲት አንስቶ ወደቆጡ ሊበር ሲሞክር አቅም ከድቶት መሃል መንገድ ላይ ወደቀ ጥቁር ክንፉን በረዥሙ ዘርግቶ ሊነሳ ሲንደፋደፍ የወለሉ አቧራ ዙሪያውን ተነሳ ድፍን የእንስሳ ዘር በሳቅ አውካካ ቁራ ካለቁራ ወጉ ሙብረሩን ትቶ በቀስታ እርምጃ ወደቆጡ አዘገመ ቀጥ ብሎ ቆጡን አየ ራቀበት ከስር ቆሞ ያመጣትን ምግብ በቀስታ ሙብላት ጀመረ  እባብ በሳቁ መሃል ቁሪትን አያት ፊቷ ላይ ቅሬታ ነበር አልሳቀችም "እች አስቀያሚ ፍቅሯ አሁንም አለ " ብሎ አሰበና ልቧ የሚቆርጥበትን አንድ ሌላ ተንኮል ወጠነ "አባቶቻችን ሰውን ከእግዚአብሔር ለያይተዋል እኔ ልጃቸው ቁራን ከቁራ መለየት እንዴት ያቅትኛል ይሄ ጠቋራ መቀመጫየኝ እንደነሳኝ መቀመጫውን ነው የምነሳው " አለና ፎከረ

መርከቧ በውሃ ላይ ስትንሳፈፍ ሰባት ወር አለፋት የመርከቡ ውስጥ ኑሮ አሰልች ቢሆንም እርስ በእርስ እንስሳቱ በፈጠሩት የእርስ በርስ ትስስር ሂወትን ሊያጣፍጧት ይጥራሉ  ኖህና ቤተሰቦቹም እንስሳቱ ጋር መልካም ወደጅነት መስርተው ነበር አንዳንዴ እንደውም ኖህ እንስሳቱ መሃል ተቀምጦ ዙሪያውን ከበውት በፍቅር ያወጋቸው ነበር እንስሳቱም ሰለሜካ ውሏቸው ይተርኩለታል ኖህ የተረዳው ነገር ምድራዊዊው የሰው ልጆች አኗኗር እምብዛም ከእንስሳቱ አለም ሽኩቻ እንደማይሻል ነበር በዚህ የህብረት ሳቅና ጨዋታ ውስጥ ቁራን ያስተዋለው አልነበረም ኖህን ጨምሮ አንድ ቀን ጧት ኖህ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ወደቁራ መጣ "ስማ አንተ እንዴት ብትንቀኝ ነው እንዲህ አይነት ፀያፍ ነገር መናገርህ " አለና ቁራ ላይ አፈጠጠበት ቁራ ለመናገር እንኳን አቅም አጥቶ ስለነበር አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ "አንተን እኮ ነው ምን አንገትህን ትደፋለህ "ደግሞ አሁን ምን አጠፋሁ አባታችን " አለ ቁራ እንደመንም ተጣጥሮ "ለሚስትህ ምንድን ነው ስለኔ ያልካት " "ሚስቴ ሚስቴ እኮ ከሄደች ከተወችኝ ብቻየን

ከተወቾኝ ሰነበተች " አለ ቁራ ፊቱ ላይ ስቃይ ነበረ " እሱ የራስህ ጉዳይ ነው ድሮስ በዚህ አመልህ አንተ ጋር ልትቆይ ኑሯል "

መከረኛው ቁራ ተናገረ ተብሎ የተወራበት ይህ ክስ በእርግጥም ኖህን የሚሳምን ነበር ቅሉ እባብ ቢሆንም የወሬው መነሻ ጉዳዩ ግን አሳማኝ ነበር ትላንት ማታ እባብ ወደኖህ ሄደና " ጌታየ እች መርከብ ባህር ላይ ተበታትና ነው የምትቀረው እየተባለ ይታማል " አለ "ማነው እንዲያ የሚለው " " አይ ቁራ አባታችን ኖህ ምሰሶ እንኳን አስተካክሎ መትከል አቅቶት እኔ ነኝ ያስተካከልኩለት ብሎ ለሚስቱ ነግሯታል " አለው ቁሪት ተጠርታ ስትጠየቅ "አዎ ብሎኛል" አለች ፐለቲካ የነበረች ቁራጭ አሳ ፣ ሃይማኖት የነበረች ቁራጭ አሳ ፣ ዘር የነበረች ቁራጭ አሳ የሴት ቅናት ስትሆን ፃዲቁን ኖህ አበሳጨችው በእርግጥም ምሰሶው የተጣመመ ጊዜ ከቁራና ከኖህ በስተቀር ማንም አልነበረም ብሎ ኖህ በማመኑ በቁራ በጣም አዘነ

ቁራ ይሄን ሲሰማ ራሱን ስቶ ወደቀ!! ኖህ ደነገጠ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ከባድ አደራ እና ትእዛዝ አንድ ሁለት ተብለው በቁጥር ከተሰጡት ፍጥረታት አንድም እንዲጎድል አይፈቅድምና ቁራን አንስቶ አቀፈው ወደራሱ ምኝታም ወስዶ በጭንቀት ይንከባከበው ጀመረ

**** **** ****

ታላቁ ስብሰባ ኖህ ሁሉንም እንስሳት ስብሰባ ጠራና እንዲህ አላቸው " እንግዲህ መዳረሻችን ሳይድስም አልቀረ እግዜር በራእይ ተናግሮኛል " እልልታው እርስ በእርስ መተቃቀፉና ፌሽታው ቀለጠ ኖህ የመርከቧን መስኮት ከፈተ እንስሳቱ ብርሃኑን መቋቋም አልቻሉም ጸሃይ በባህሩ ላይ ታንፀባርቅ ነበር ምንም ፍጥረት በሌለበት ምድር ላይ ምን ተፈጥሮ ይሆን አሁንስ ያለነው የት ነው በጣም አጓጊ ነበር ስምንት ወር በአንዲት መርከብ ውስጥ ታጉረው የኖሩ እንስሳት ቀጣይ እጣ ፋንታቸውን ናፈቁ ተዘግታ በኖረች መርከብ ውስጥ መላ ምት ሲደረድሩ ከመኖር ሌላ አንድም ተጨባጭ ነገር አልነበረምና የሚታይ የሚዳሰስ ምድር ናፈቃቸው

"እንግዲህ ያለንበትን እናውቅ ዘንድ ከእኛ መካከል አንድኛችን ውጭውን መቃኘት ሊኖርብን ነው ለመሆኑ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነ ጀግና ማነው " ሲል ጠየቀ ኖህ ሁሉም ወደኋላ አፈገፈጉ ማን ሞኝ አለ አለምን ዋጥ ስልቅጥ ባደረገ መአበል የሚቀልጥ "እባብ ውጩን አይተህ ትመጣለህ? " "እንዴ ጌታየ ውሃ በተሞላ ምድር እኔ እግር የለኝ አሮጥ ክንፍ ለኝ አልበር ዋና ደግሞ አልችልም ከህፃንነቴም ውሃ አልወድም " አለ ትወረወራለህ የተባለ ይመስል እየሸሸ "አንበሳ? " አለ ኖህ "ዋና አልችልም ጌታየ ባይሆን ክንፍ ያላቸው ቢሄዱ ይሻላል "

"ንስር አንተ በመቃኘት ወደር የሌህም " ብሎ ኖህ ንግግሩን ሳይጨርስ "እንዴ እኔን ለማን ትቶ ?" አለች ቁሪት አንገቱ ላይ ተጠምጥማ ኖህ ግራ ገብቶት እንደቆመ "ጌታየ እኔ እሄዳለሁ " የሚል ድምፅ ተሰማ እንስሳቱ ሁሉ ድምፁ ወደተሰማበት ዞሩ ቁራ ነበር!! "አይሆንም አንተ በደንብ አላገገምክም አሞሃል " አለ ኖህ "ጌታየ በሚገባ ድኛለሁ እስከምድር ጥግ መብረር እችላለሁ በዛ ላይ ዋና አሳምሬ ነው የምችለው "አለ በሚገርም ድፍረትና በጠንካራ ድምፅ

ኖህ አሰብ አደረገና "መልካም እንግዲህ ባይሆን እርቀህ እንዳትሄድ አለው" ቁራ ወደመስኮቱ ተንደረደረና ቂብ ብሎ እንጨቷ ላይ አረፈ ከዛም ዞር ብሎ ቁሪትን በጥልቀት አያትና በእፎይታ ተነፈሰ ፊቱ በታላቅ ሃሴት ተጥለቀለቀ አይኖቹን ከድኑ የውጭውን አየር በረዥሙ ሳበው በጥላቻ በወገንተኝነትና በመገለል ከተሞላ መርከብ ይልቅ ምኑም ወዳልታወቀ አለም በነፃነት መብረር እንደሚሻል ያመነ ልቡ ደም ሳይሆን ሃሴት እረጨ ወደሰፊው ባህር በውሃ ወደተሞላው ምድር በረረ እያነሰ እያነሰ እያነሰ ከአድማሱ ወዲያ ማዶ እስኪሰውር ኖህ በትካዜ ተመለከተው

መሸ ቁራ አልተመለሰም ነጋ መሸ ቁራ የለም ሰባት ቀናት የውሃ ሽታ ሆነ መልእክተኛው እርግብ ወደኖህ ሄደችና "ጌታየ እኔ ወደ ባህሩ ሂጀ እንድቃኝ ይፈቀድልኝ "ስትል ጠየቀች የቁራ ቀልጦ መቅረት ስላሳዘነው ለመፍቀድ አንገራገረ ይሁንና የእርግብ ውትወታ ፋታ ስላሳጣው ሁለተኛዋ እንስሳ ወደባህሩ በረረች

*** *** ***

ወደአመሻሹ ላይ ንስር በመስኮቱ አሻግሮ እየተመለከተ “የሆነ የሚንቀሳቀስ ነገር ይታየኛል” ሲል ጮኸ በመስኮቱ ለማየት ምድረ እንስሳ ተራኮተ አንደኛ መስኮቱ ላይ የደረሰችው ግን ቁሪት ነበረች እንደውም ከአበራረሯ ፍጥነት የተነሳ መስኮቱን አልፋ ወደባህሩ ከመውደቅ ያዳናት ንስር ነበር “የታለች እርግብ መሆን አለባት መቸም “ አለ እባብ በእርግጥም እርግብ ነበረች ኖህ እጁን በመስኮቱ ዘረጋላና ተቀበላት በአፏ እርጥብ የወይራ ቅጠል ይዛ ነበር በደስታ ሲያቅፏትና ሲስሟት ፊቷን አጨፍግጋ ወደቁሪት ሄደች እና የያዘቻትን የወይራ ቅጠል እግሯስር ወረወረችላት

እርግብ ከመርከቧ እንደወጣች ወደምእራብ ተጓዘች ባህሩ በሚንሳፈፍ የሰው እና የእንስሳት አስከሬን ተሞልቷል ሂወት ያለው ፍጥረት አይታይም ግማሽ ቀን እንደበረረች ንፁህ ባህር ከስሯ ተዘረጋ ምንም ነገር አይታይበትም ነበር

ድንገት ጥቁር ነገር ነጥብ አክሎ በሃሩ ላይ ሲንሳፈፍ ታያት ቁልቁል ተወርውራ ወረደች እግሯ የውሃውን ጫፍ ሳይነካ ነበር ጥቁሩ ነገር የቁራ እሬሳ መሆኑን አወቀች ወዲያው ግን ቁራ የተንቀሳቀሰ መሰላት ወሃው ላይ እየተንቦጫረቀች ቀና አደረገችው በእርግጥም ቁራ አይኖቹን ገለጠ “ቁሪት “ አላት እርግብን “እርግብ ነኝ “ አለችው ውስጧ በሃዘን ተኮማተረ

“ቁራ ትሰማኛለህ ለምንድን ነው ያልተመለስከው ለምን ከሞቀ መርከብህ ወደዚህ ቀዝቃዛ የሞት ምድር መጣህ “ አለች እንባዋ በአይነዋ ሞልቶ ቁራ ከውሃው ውስጥ አንድ እግሩን አወጣ በጥፍሩ ርጥብ ቅጠል ይዞ ነበር “ይሄን ለቁሪት ስጫት “ አለ በደከመ ድምፅ “ለመጀመሪ ጊዜ የተገናኘነው የወይራ ዛፍ ላይ ነበር ያኔ ቁሪተ ወዳኝ ነበር ዛሬ ንስርን እንደምትወደው ” አለና ከት ብሎ ሳቀ “ በል ተጠናከርና ወደመርከባችን እንሂድ አይዞህ ደህና ነህ እኮ ቁራ “ አለች እርግብ “አልሄድም” “አብደሃል እዚህ በሮዶ ላይ በዚህ ውሽንፍር ውስጥ ወድቀህ አልሄድም ትላለህ ” አለች እርግብ በቁጣ

“ሃሃሃሃሃ ከሰው ፊት የተፈጥሮ ፊት ቢገርፈኝ ይሻላል ከወገኖቸ ክፋት ወገኔ ያልሆነ ቅዝቃዜ ቢገድለኝ ይሻላል ”“ እችን ተናግሮ አንገቱን አቀረቀረ ቁራ ለዘላለሙ አሸለበ

እርግብ የወይራዋን ቅጠል በአፏ ይዛ ወደመርከቧ ስትመለስ በርካታ ተራሮች ጫፋቸው ከውሃው በላይ ብቅ እንዳለ ተመለከተች የጥፋት ውሃ በሆነ ስምንተኛ ወር በወሩም በስምንተኛው ቀን መርከቧ በአራራት ተራራ ጫፍ ላይ አረፈች ሰወች እንስሳት በከፍታቸው ውስጥ የነበረ ክፋታቸውን ይዘው ወደዝቅታቸው ተመለሱ

እግዚያብሄርም አለ “ ክፉወች ከፍ ስላሉ ከክፋታቸው አይመለሱም ደጎችም ዝቅ ስላሉ ከደግነታቸው አይመለሱም የእኔም አይን በከፍታ ይሁን በዝቅታ አብራችሁ አለች “

## ተፈፀመ

# የቤተ ዘመዱ ይታያል ጉዱ

## ይህ ተከታታይ ወግ ሶስት ክፍሎች አሉት

## ክፍል 1

ትላንት እሁድ ወደቤተሰቦቸ ቤት የሄድኩት በየሁለት ወሩ የሚካሄደው የቤተዘመድ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ነበር እንደደረስኩ ከግቢው ጀምሮ በረንዳ ላይ ሳሎን ምኝታ ቤት ኩሽና ብቻ በየቦታው ለተቀመጠው ዘመድ አዝማድ ሁሉ እንደየቅርበቱ ሰላምታ አቀረብኩ

የሰላምታው አይነት

በቸልተኛ የግንባር ንቅናቄ ሰላም ያልኳቸው የማይመቹኝን የአጎቴን የልጅ ልጆች

በእጅ ጨበጣ የአጎትና የእህት ሚስቶችና ባሎች

ትካሻ በመግጨት በእድሜ የምንቀራረበውን የአጎትና የአክስት ልጆች

እቅፍ አድርጎ ጉንጭ በመሳም የእህቶቸን ልጆችና አክስቶቸን

ከነብስ የመነጨ አጭር መተያየት ብቻ ግን ሁሉም የአለም ቋንቋወች ውስጡ የታጨቁበት ለእናቴ

እህት ወንድም የእህት ልጅ የወንድም ልጅ አክስት የአክስት ልጅ አጎት የአጎት ልጅ የአጎት የልጅ ልጅ የልጅ ልጅ ባሎች የልጅ ልጅ ሚስቶች እጮኛወች ሁሉ የቤተዘመድ ጉባኤውን ወደሰርግነት ለመቀየር የቀረጡ ይመስል ምግብ መጠጥ በግፍ አዘጋጅተው ነው ያገኘኋቸው ከዚህ ሁሉ ሰልፍ በኋላ እናቴ በአይኗ ትጠራኝና ወደውስጥ ገብተን

"ምን ሁነሃል አሞሃል እንዴ "

"ኧረ አላመመኝም"

"ፊትህ ጭው ብሏል " ከዛ ስለፊቴ ጭውታ ብዙ እናወራለን ሁልጊዜ እናቴ ስታየኝ ወይ ፊቴ "ጭው" ይልባታል ወይ ትከሻየ "ቅልል" ይልባታል ወይም ደግሞ አይኔ " ቡዝዝ" ይልባታል ጭው ፣ ቅልል እና ቡዝዝ ላለማለት ፂሜን ተስተካክየ ዘንጬ የጨርቅ ሱሪ ለብሸ እና ቀበቶየን ጠበቅ አድርጌ ስሄድ "ምነው አንጀት እራቀህ " ትለኛለች

የቤተ ዘመድ ጉባኤው የቤተሰቡ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ነው !! ከዚህ ስብሰባ ላይ አይቀርም በፍቃድም ይሁን ካለፍቃድ አይቀርም !! መጋባት ፣ መፋታት፣ አዲስ ስራ መጀመር፣ ከበድ ያለ የቤት እቃ መግዛት ሁሉ የፈለገ ሰው የዚህን የቤተ ዘመድ ቡራኬ ማግኘት ግድ ይለዋል ጉባኤው ደረቅ ቡራኬ ብቻ አይሰጥም ከካዝናው ጠቀም ያለ ብር ይጨምርበታል ስለዚህ ጉባኤው ታላቅ ነው!!

ምሳ ቀረበ ሰሃን ተኝኳኳ ጉርሻወች ከዛ ወደዚህ ከዚህ ወደዛ ተወነጫጨፉ ተሰነዛዘሩ ስለአልጫው መጣፈጥ ፣ስለቀይ ወጡ በርበሬ ሞቅ ማለት ስለቅቅሉ ጨው ማነስ ተወራ የእህቴ ልጆች ከበውኝ ነበር የአጎቶች ሚስቶች መጎራረስ የተለየ መልእክት አለው የእናቴ የወንድም ሚስት ለአባቴ የወንድም ሚስት ቀይ ወጡ በዛ ያለ ጉርሻ ታጎርሳታለች በአይኖቻቸው ግን ልብስና ጌጣጌጦቻቸውን ይገማገማሉ በቆረጣ ይታያሉ

ወንዶቹ ፖለቲካ ያወራሉ ስለግብፅ ብጥብጥ ስለአሜሪካ ምንትስ ስለሙጋቤ ወንበሩን የሙጥኝ ማለት ዊንታ ታዲያ (የአክስቴ ልጅ ) ሰሃን በያዘ እጇ ጎሸም እያደረገችኝ በፖለቲካ ትንታኔ አቅሉን የሚስተውን አጎታችንን እያየች "እራሱስ ሙጋቤ አይደል እንዴ " በሳቅ ቡፍ ስል አባቴ ይገለምጠናል(ነብር አየኝ በል አይነት)

ይሄ አጎታችን ይልማ ይባላል የቤተዘመድ ጉባኤውን ላለፉት አስር አመታት በሊቀመንበርነት መርቷል በመፈንቅለ መንግስት የቤተ ዘመድ ጉባኤ ሊቀመንበር የሆነ አስገራሚ ሰው ድሮ ትንሽ ወንድሙ ነበር ሰብሳቢው በቤተ ዘመዱ የእቁብ ብር ላዳ ታክሲ ገዝቶ ብሩን ሳይመልስ በመቅረቱ በዚህ አጎቴ አቀናባሪነት ከስልጣኑ ተሻረ እርስ በእርስ አይዋደዱም

ትንሹ አጎቴ ከስልጣኑ ሲሻር ታሪካዊ ንግግር አደረገ

" ታሪክ ይፈርደናል ይህ ቤተሰብ እንዳይበታተን የደከምኩት ድካም በአንዲት ላዳ ታክሲ የሚተካ ነው ውለታየ ይሄ ነው ይሄ ሹም ሽር ላዳ ታክሲ በመግዛቴ ብቻ ሳይሆን ከኋላ ሌላ የፖለቲካ ምክንያት አለው የሰው ሁሉ የቤተዘመድ ጉባኤ ገልባጭ መኪና ገዝቶ ለሊቀመንበሩ ይሰጣል እናተ አንዲት ታክሲ ገዛ ብላችሁ ከስልጣን ትገለብጣላችሁ ግዴለም ታሪክና ትውልድ ይፍረደን " አለ ወደእኛ እያየ ያኔ ልጆች ስለነበርን ይፈርዳል የተባልነው "ትውልድ" እኛ ነበርን ግን እስካሁን አልፈረድንም !!

አጎቴ ቦታውን ያዘና መዝገቡን ገልጦ ስም ጠራ

በለጠ

አቤት

አለምሰገድ(አባቴ ነው)

አቤት

ዙሪያሽ

አቤት

"ዊ..ወር..ዊ ውርታ ኤዲያ "አጎቴ የዊንታ ስም አልያዝ ብሎት መዝገቡላይ ሲያሳድድ አንዷ ይዛ ሰጠችው "ዊንታ" አለች

ምን እዚህ የተወናገረ ስም እያወጡ የታለች አለ በቁጣ ዊንታ ሳቋን አፍና "አቤት አጎቴ " አለች

አብረሃም አለና በክፉ አይኑ ገላመጠኝ

አቤት

በባለፈው ስብሰባ ቀሪ ነህ

ኧረ አልቀረሁም አጎቴ

ዝም በል ይሄው ኤክሱ አለ መዝገቡን እያሳየ ስሜ ፊት ለፊት ግድንግድ ኤክስ ተቀምጧል

"ውይ ይልማየ ምነው ራስህ ወይን ግዛ ብለህ ልከኸው አልነበረም " አለች እናቴ የኔ አስተዋሽ ነገር አትረሳም በቃ

"ሃዲያ ወዲያው አታሳውቂኝም ኤክስ ሳረገው " አለና "ኤክሱን" ለመሰረዝ ሁለት ደይቃ ሙሉ በስክርቢቶው መዝገቡን ሞነጨረ (ስእል የሚስል ነበር የሚመስለው)

ከስም ጥሪው በኋላ የዛሬውን የቤተ ዘመድ አጀንዳ ዘረዘረ

"1 ኛ እምሩ ሊያገባ ስለሆነ ስለሰርጉ ጉዳይና ስለአንዳንድ ነገር እንነጋገራለን "አለ ቤተ ዘመዱ ተንጫጫ

"እንዴ ስንት ጊዜ ነው ይሄ አጀንዳ የሚያዘው " አለች ለምለም አክስቴ(እሳት ናት)

“ባለፈው ሊያገባት የነበረችው ልጅ አረብ አገር ሄዳ ነገ ዛሬ ትመጣለች ስንል የገደል ስባሪ የሚያህል አረብ አግብታ ፎቶ ላከች ደሞ እች ማናት የሃኪሙ ልጅ እሷን ሊያገባ ብሎ ሰው እንዴት “ዙረት” ያገባል ብሎ ቤተዘመዱ ሳያፀድቅለት ቀረ ” አለ አጎቴ ተስማማን

“2ኛ የሽ አረግ ፈሪጅ ልትገዛ ብር ስለጎደላት አበድሩኝ ብላለች “

“ባለስንት ሊትር ነው የሸየ “ አለች ፅጌ

“መካከለኛውን ነው ያሰብኩት “

“ ከገዛሽ ትልቁን ግዥ በግ ብታርጂ አትክልት ብትይ ዋጥ አርጎ አላየሁም የሚል በቀደም አይቻለሁ ”

“እስቲ አንዴ ዝርዝሩን በኋላ እንነጋገራለን ”

“3ኛ ቤተሰቡ ውስጥ አርባ ስልሳ ስለተመዘገቡ ልጆች ክፍያ ጉዳይ

“አሃ 40/60 አላለቀም እንዴ “

“ውጭ ያሉትስ “

አጎቴ ጫጫታውን በጭብጨባ አስቆመና ኮስተር ብሎ “ከሁሉም በፊት ግን አንገብጋቢ የሆነ አጀንዳ አለ የአብረሃም ጉዳይ “ አለ

“እኔ ምን አጎቴ አልኩ ደንግጬ”

“ልናገር እኮ ነው ምን አጣደፈህ አብረሃም ይሄ ምንድን ነው ኮምፒተር ላይ የሚጣጣፉት ነገር “

“ፌስቡክ” አለች አንዷ ቃጠሎ የአጎቴ ልጅ

“አዎ እሱ ላይ ስለሚፒፈው ነገር ቤተሰቡ ሊወያይ ይገባል በአደባባይ የቤተሰቡን ሚስጥር በአደባባይ ሲያሰጣው ዝም ልንል አይገባም “ አለ

ሁሉም ወደእኔ ዞረው አዩ

## ክፍል 2

ፈላጭ ቆራጩ አጎቴ በቀኝ እጁ መዳፍ አፉን ጠረገና (ነገር ሲፈልግ አፉን ይጠርጋል) “አንገብጋቢ” የተባለውን የእኔን አጀንዳ ጀመረ

“እንግዲህ እኛ የቤተዘመድ ጉባኤ ላይ ስንታደም ከፉ ደጋችንን በጓዳችን አወግተን ቢቸግረን ለመረዳዳት ብንደሰት ደስታችንን ለመካፈል እንጅ ገመናችን እየተለቀመ የተነፈስነው ሁሉ እየተወሰደ ለአለሙ ሁሉ እንዲሰጣ አልነበረም (በለው! አባባ ራሱን በመስማማት ነቀነቀ) ይሄ ሚስጥርን የማስፈትለክ ጉዳይ እኮ እንኳን ይሄን ቤተሰብ አገራትን የሚያሰጋ ጉዳይ ነው ! አንገብጋቢ ወንጀል ነው አሁን በቀደም በራዲዮን ሁላችም ሰምታችኋል አማሪካን አገር አስተምራ አብልታ አጠጥታ ያሳደገችው ልጇ ነው ገመናዋን ለአለም ዘርግፎ ከስንቱ ወዳጅ ጋር ያቃቃራት ማነው ይሄ ሰላዩ ኮብልሎ ቻይና የገባው ” ብሎ ስሙን እንደማሰብ ሲል

“ ሰላዩ ሩሲያ ደርሷል እኮ አጎቴ “ አለ ዳንኤል ፀጉሩን እያፍተለተለ (የአክስት ልጅ ነው )

“ዝም በል ወዲያ “ሩሲያ ደረሰ እንጦሮጦስ ደረሰ” ከማለት መጀመሪያ ይሄን ሰማይ የደረሰ ፀጉርህን ተስተካከል “ አለ አጎቴ በቁጣ ቡፍ ብለን ሳቅን

አጎቴ ወንጀሌን ማሰማቱን ቀጠለ “ አብረሃም አኮ እዚህ ቤተሰብ ላይ የሰራው ይሄንኑ ነው ! ቤተዘመዱ የጣለበትን አደራ በመብላት በራዲዮን አይነገር በቴሌቢጅን አይታይ እንጅ ያው ነው የሰራው ! ቤተሰብን በመካድ ነው የአገር ክህደት የሚጀመረው ” አለና ፊቱን ከስክሶ አየኝ

“አሃ ምንድነው የምታወራው ይልማ “ አለ አባቴ አንዴ አጎቴን አንዴ እኔን እያየ

“ስለልጅህ ነዋ እዚህ የምናወራውን ሁሉ እየወሰደ አጎቴ ይልማ እንዲህ አደረገ አባቴ በዚህ ወጣ በዛ ወረደ እያለ በራዲዮን ያወጋል ለህዝቡ ሁሉ ድፍን ጦቢያ በቤተዘመድ ጉባኤው ላይ ሲስቅ ሲሳለቅ ነው የሚውለው ጀሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው እኛ ቤት አገኘን ብለን በግድግዳ የተከበብን ሲመስለን ሜዳ ላይ ነን ለካ “ አለ በብስጭት

“በምን ራዲዮን ነው እንዲህ ያልከው አንተ” አለ አባቴ እኔ ላይ አፍጥጦ አቤት ቁጣው ሲያስፈራ

“በሬዲዮ አይደለም “በፌስቡክ ነው”“ አለች ኤልሳ የምትባለው በጣም የምጠላት የአጎቴ የልጅ ልጅ ቻፕስቲካም ከወፍ ጩኸት እስከጅብ ጩኸት ዘንጣ አዲሳባን ከመዞር ሌላ ስራ የሌላት አስቀያሚ ማስቲካ እያመነዠከች ነው በነገረኛ አይኗ እኔን እያየች የምታወራው

“አንች ደግሞ መጀመሪያ ማስቲካሽን ወዲያ ትፊ “ አላት አጎቴ (አያቷ)

“ሂሂሂሂ” አለች ዊንታ ሆነ ብላ ኤልሳን ለማበሳጨት ዊንታየ የእኔ ደጋፊ ናት

“አያስቅም “ አለች ኤልሳ በብስጭት ከአንገቷ እስከትከሻዋ እየተሰበቀች ጦር!! አቤት ስጠላት !

“ወዲያ ዝም በሉ !! ቁም ነገር አይደለም እንዴ የያዝነው “ አለ አባቴ በብስጭት

ስብሰባው ቀጠለ

“አብረሃም ይሄን ያደርጋል የሚል እምነት የለኝም “አስተዋይ የተማረ የተባረከ ልጅ ነው “ አለ ሌላኛው አጎቴ እኔን በመደገፍ ሰበብ ከስልጣን ያባረረውን አጎቴን ሊቃወም ሲያደንቁ ለጥቅማቸው ሲያዋርዱ ለጥቅማቸው እኛን ተራወቹን የቤተሰብ አባላት በአድናቆትና በማጣጣል ወንጭፍ የሚወረውሩን ጠጠሮች ሊያደርጉን ይሞክራሉ

“ ኤልሳ ኮምፒተርሽን አምጭ ወዲህ “ አለ አጎቴ

“እች የውሻ ልጅ አቃጣሪ” አለች ዊንታ ቀስ ብላ በጆሮየ ”ኧረ አይባልም “ አልኳት በሹክሹክታ እውነቱን ለመናገር ኤልሳ የውሻ ልጅም አቃጣሪም ነበረች ልክ ነው !! ብስጭት አልኩ

ኤልሳ በደስታ ላፕቶፑን ለአጎቴ አቀበለችው “አሃ ምን ላርገው ክፈችዋ “አለ በቁጣ

ቤተሰቡ በጉጉት ይጠብቅ ጀመረ “ይሄን እንደወፍጮ ቤት የሚጮህ ላፕቶፕ ይዛ ደግሞ ለነገር ትሮጣለች ” አለች ዊንታየ የኔ ቆንጆ

ውፍጮ እንኳን አይደለም የድንጋይ ወፍጮ ነው !!

በቤተዘመዱ መሃል ፌስቡክ ተከፈተ “ይሄዋ ይሄው ደህና ስራ እንደሰራ ሰው ፎቶውን ገጥግጦ ይሄው “ አለ አጎቴ ፎቶየን ሲያይ ደሙ ፈላ የደምስሩ ግንባሩ ላይ ተጋደመ

“እስቲ ወዲህ በይው ኤልሳ “ አለ አባባ ፕሮፋይሌ ላይ ያለውን ፎቶ ፊቱ ከተቀመጥኩት እኔ ጋር አስተያየ እና

“አሃ አንተ ነህ ይሄ “ አለኝ አባባ

“ እና በዘራችን ሌላ ግንባራም ማን አለ ተው እንጅ ሆድህ ሲያውቅ እኛንም አታጠራጥረን “ አለ አጎቴ አጎቴ እንደዛሬው ሲሆን አይቸው አላውቅም ኤልሳ ከትከት ብላ ሳቀች ጥርስሽ ይርገፍ !!

እስቲ አዙሪው እስቲ እስቲ ወደዚህ አስቲ ተንጫጫ ቤተዘመዱ ኤልሳ ላፐቶፑን እንደቆሎ ሰሃን በየሰው ፊት እያስጠጋች ፎቶየን በጉባኤተኛው አይን አዞገነችው እየፈራች ወደኛ ዞር ስትል ዊንታ አነር ሁና "የሆንሽ ቆሎ አዘጋኝ ነገር ኮምፒውተር መክፈት እኛ አለማምደንሽ ታቃጥሪያለሽ " አለቻት በሽኩሽኩታ

"እችን እልጅ አሳርፊያት አባየ " አለች ኤልሳ ለዊንታ እናት..ድምጧ ራሱ ሲጢጢጢ የሆነ አሮጌ የጣውላ በር ሲዘጋና ሲከፈት አይነት

"አንች ደሞ ስሩ ተሸጉጠሽ ምን ትተነኩሻለሽ ቀይጣላ ! ሰው ጋር ሲጠጉ አይተሽ " አለ አጎቴ

ዊንታ ቀስ ብላ "ሽለመጥማጥ " አለቻት ኤልሳን  ልክ ነው ኤልሳ ፊቷን አስተውሎ ላየው ሸለመጥማጥ ትመስላለች !! "ግን ሸለመጥማጥ ምንድን ነው " አልኳት ዊንታን

"እኔጃ" አለችኝ በሹክሹክታ እኔም አላውቀውም ግን ኤለሳ ሸለመጥማጥ ብትባል ዝም ብሎ ቃሉ እሷን ይመስላል

ቤተዘመዱ ፎቶየን ጥግብ እስኪል ድረስ ካየው በኋላ ከፃፍኳቸው ታሪኮች አንዳንዶቹ ን ለጉባኤው እንድታነብ ኤልሳ ታዘዘች በደስታ እየተፍነከነከች ሆነ ብላ ክፉ ክፉውን ማንበብ ጀመረች

" ይሄ አሁን የማነበው አሱ (ወደእኔ እየጠቆመች) ከወር በፊት ፖስት ያደረገው ነው

"ምን ያደረገው "

"የለጠፈው " አለችና ቀጠለች " የአጎቴ አፍንጫ እንደወፍ ማንቁርት የሾለ ነው አንዳንዴ ወሬ እንደጥሬ በአፍንጫው የሚለቅም ይመስለኛል " በማለት ከዚህ በፊት የፃፍኩትን አንድ ፅሁፍ ማንበብ ጀመረች

ቤተዘመዱ ሳቁን አፍኖ ቁጭ እንዳለ እግዜር ይስጠውና ቤቢ የእህቴ ተንሹ ልጅ (አራት አመቱ ነው ) ፈሱ አመለጠው ከዛ በኋላ ከቤቢ አንጀት አስቂኝ ጋዝ ወደቤተዘመዱ የተለቀቀ ይመስል ሳቁ እንዴት ይቁም አረጋሽ ሰራተኛችን ስትስቅ ብርጭቆውን ከጠረንጴዛው ላይ ገፋ ስላደረገችው ከሽ ሲል በሳቅ ለወትሮው እቃ ሲሰበር አረጋሽን በመሃበር የተደራጀ ስድብ የምታንርፍባት እናቴ ሳትቀር በሳቅ ፈረሰች ያንኛው አጎቴ አፉን በጋቢው ሸፈን አድርጎ ትከሻውን እያርገፈገፈ በሳቅ ውድቅ

ቀጠለች ኤልሳ "አባቴ ፖለቲካ ወሬ ሲነሳ ውዳሴ ማሪያሙን ይረሳዋል ሰማያዊ መንግስቱን ትቶ ወደምድራዊ መንግስት "

"አከከከከከከ " አለ አባባ

"እኔ የምለው አብረሃም የጣፈው አንች ኮሚቢተር ላይ ምን ወሰደው " አለች እናቴ ሚስኪን እኔን ልትከላከል መስቀለኛ ጥያቄ

"አንች ደሞ ይሄ ሲያይንስ ነው አይገባሽም  ኮሚቢተር ለኮቢተር ይሳሳባል እንኳን ያክስትና አጎት ልጅ ሁነው ቀርቶ የአለሙ ሁሉ የባዳው ኮመፒተር ይሳሳባል"" አለ ና አጎቴ "ቀጥይ " አላት ኤልሳን ቀጠለች

" የአጎቴ የልጅ ልጅ (እኔን ነው ተመልከቱ ብቻ አለች ) የ አጎቴ የልጅ ልጅ በአንድ ጊዜ አራት ቦታ የምትገኝ ሰላቢ ናት ሰው ሳይቀጥሯት ሶስት ጊዜ ሲቀጥሯት አስራ ሶስት ጊዜ የምትገኝ ብቻዋን ብዙ ሴት ናት " ዊንታ ኤልሳ እንድታያት አድርጋ እረሷን በመስማማት ነቀነቀች

"ደግሞ ይሄን ስማ ጋሽ " አለች ኤልሳ ወደአባባ እያየች

"እስቲ አንብቢው " አለ አባባ በብስጭት አየት እየደረገኝ (ነብር አየኝ በል አይነት)

" አባቴ ሁልጊዜ በረንዳ ላይ ተቀምጦ የህግ መፀሃፍ ቢያነብም በቤታችን ዙሪያ በአራቱም አቅጣጫ ከጎረቤት ጋር በተፈጠረ የድንበር ይገባኛል የፍርድ ቤት ክስ በአራቱንም ተሸንፏል በግቢው ዋና በር በኩል ሳይቀር ስለተሸነፈ በራችን ሁሉ ተወስዶ በወንዙ በኩል ነው የምንሄደው " አለች ኤልሳ

አባቴ ምንጥቅ ብሎ ተነስቶ ወደምኝታ ቤቱ ገባና ወዲያው ከዘራውን ወድሮ ተንደርድሮ ወጣ ቤቱ በአንድ እግሩ ቆመ ለመገላገል የሚተራመሰው ቤተ ዘመድ ብርጭቆውን አንካካው ሁካታ ሆነ ቤቱ ፈትለክ ብየ ስወጣ ዊንታ ከተለችኝ ከፊት እነቴ ከእኔ ቀጥላ ዊንታ ከዊንታ ቀጥሎ የአባባ ከዘራ ከዛ አባባ !! " ያዘው " እያለ በወንዙ በኩል ከግቢያችን ወጣን

# ክፍል 3

እኔና ዊንታ በአባቴ አሳዳጅነት ቁልቁል ወደወንዙ እየሮጥን እያለ " ስማ አብርሽ " አለችኝ ዊንታ እያለከለከች

"እ ?" አልኳት ዞር እያልኩ ከዘራ ይዞ የሚንደረደረውን አባባን እያየሁ

"አባባ እንደዚህ ይሮጣል እንዴ ?"

"ኧረ ሩጦ አያውቅም ዛሬ ሰይጣን አግዞት መሆን አለበት "

"ደከመኝ አብርሽ "

"እንግዲህ ምርጫው ያንቺ ነው ወይ ከዘራውን መቻል ወይ እስከቻልሽ መሮጥ እና ማምለጥ " አልኳት እያለከለክን ነው የምናወራው

"ብቆም ግን አባባ የሚመታኝ ይመስለሃል "

" ቀላል ይዠልጥሻል "

"ባክህ ይምታኝ እንጂ ከዚህ በኋላ አሮጥም " አለችና አጎንብሳ ጉልበቷን ተደግፋ ቆመች እያለከለከች ቆመች

እኔ ግን ተፈተለኩ እና ፊት ለፊቴ የተጋደመውን ወንዝ እንደእርቀት ዝላይ በአየር ላይ ተሰፈንጥሬ ተሽገርኩት እጀን ወደፊት ዘርግቸ ጫፉ ላይ ቁጢጥ ብየ በሁለት እግሬ አረፍኩና ልነሳ ስሞክር ሚዛኔ ወደኋላ አጋደለብኝ ልክ ከኋላየ ልብሴን ይዞ ወደወንዙ የሚጎትተኝ ሰው ያለ ነበር የሚመስለዋ እጀን እንደክንፍ እያራገብኩ ወደፊት ለማጋደል ሞከርኩ አንድ እግሬን አንስቸ ተንገዳገድኩ አልተሳካም ወደኋላ ወዳኋዋላ ወደ ሁኋላ ሚዛኔን ሳትኩና ቦጭረ ቅ !! በጀርባየ ወንዙ ላይ ተዘረጋሁ ውሃው እንደቀብር ተከፍቶ ሳይውጠኝ በፊት ".አብርሽ" ብላ ስጥጮኽ ዊንታን ሰማኋት ባአፍና ባአፍንጫየ አፈር አፈር የሚል ውሃ ሞላ

**** *** ****

አይኔን ስገልጥ መጀመሪያ ሰማይ ታየኝ ከዛ ዊንታ እጀን ይዛ እያለቀሰች መሆኑን አወኩ ወንዙ ዳር በጀርባየ አስተኝተውኝ ነበር ቤተዘመዱ ጎረቤቱ ሁሉ ወንዙ ዳር የተራመሳል

አምቡላንስ ይጠራ

ሆዱን ተጫኑት

አየር ስጡት

ቀበቶውን ፍቱለት

አይኖቸን ስጠርግ ዊንታ በደስታ ተጠመጠመችብኝ የኔ ቆንጆ እንባዋ ጠብ አለብኝ ጉንጨ ላይ ከዛ ሁሉ የወንስ ውሃ ከዛ ሁሉ እርጥበት የተለየች አንዲት ጠብታ ስታርፍብኝ ተሰማኝ

“በቃ ነቅቷል “ አለች ኤልሳ እች ምን ነበር ያ ስድብ ጠፋብኝ ስድቡን ሳሰላስል

“ቴንኪው ኤልሲ “ ስትል ሰማሁ ዊንታ እንዴ ዊንታ ኤልሳን “ቴንኪው ኤልሲ “ አለቻት!! ሁለቱ ከታረቁማ በቃ ሁላችንም ሙተን ሰማይ ቤት ገብተናል ማለት ነው በዚች ምድር ሁለቱ አይታረቁማ ቴንኪው ደግሞ ኤልሲ እንዴ

“አብርሽየ አብርሽ ”.ዊንታ ነበረች

“እ “ አልኳት

ተናገረ ተናገረ ተንጫጫ የከበበን ሁሉ

ቀጥ አድርገው አስቀመጡኝ ፊት ለፊት እናቴ ልብሷን ጥላ በብዙ ሰው ተይዛ ደረቷን እየመታች ታለቅሳለች አባቴ ሽምቅቅ ብሎ ግራ ገብቶት በድንጋጤ ቁሟል(ከዘራው የት ሄደ) ብቻ ሁኔታው ህልም ይመስል ነበር ከእኔ አለፍ ብሎ “እ ሽለመጥማጥ” ወገቧን ይዛ በቁንጥ ቁማለች ዊንታ እቅድ አድርጋኝ ጎኔ ተቀምጣለች”

እናቴ ተንደርድራ መጥታ ባለማመን አየችኝ

“ገደሉህ ልጄን ሞትከላቸው “ አለች

“ኸረ አለሁ ማም “ አልኩ ስናገር ትን አለኝ

“አሄ የት አለ ያለኸው ? በጣዕረ ነብስ እኮ ነው የሚያወራው የለም ወይኔ ልጄ “ አለችና ወደለቅሷ ተመለች

“ወዲያ ውሰዷት የምን ማሟረት ነው “ አለ አባቴ ራሱን አረጋግቶ

ዊንታ ደግፋ አነሳችኝ ከድንጋጤ በስተቀር ደህና ነበርኩ ዊንታየ አስር ጊዜ ታየኛለች ካሁን አሁን ተዝለፍልፎ ይወድቃል ብላ ሳትፈራ አትቀርም

ስራመድ ጆሮየ ውስጥ ድዝ ድዝ የሚል ነገር አለ ድዝ ድዝ ድዝዝዝ

“አንተ እች ሽለመጥማጥ ከተወለደች ጀምሮ ዛሬ ገና ጥሩ ስራ ሰራች “ አለችኝ

“ምናባቷ ሰራች ? “ አልኳት ብስጭት ብየ

“ሆድህ ተቆዝሮ ልትሞት ነበር እኮ ሆድህን እተጫኑች በአፍህ አየር እየሰጠች አተረፈችህ “ አለች ዊንታ ትንሽ ክብር ለኤልሳ እያሳየች

“ምን ኤልሳ በአፌ አየር ሰጠችኝ ? “

“አዎ ያውም አፍንጫህን እንቅ አድርጋ ይዛ ነዋ !!”

“ ኤጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭ ቻፕስቲካም “ ብየ በበሸበሰ ሸሚዜ እጅጌ ከንፈሬን ደጋግሜ ጠረኩት ፈተኩት !!

ዊንታ ሳቋ እየተቅጨለጨለ “ለማንኛውም እሷ ተንኮል አያጣትም ከንፈርህን እንዳልነከሰችህ አረጋግጥ “ አለችኝ

እቤት ደርሰን ዘመድ አዝማዱ ከተረጋጋ በኋላ በተፈፀረው ሁኔታ ፀፀት የገባው ቤተዘመድ የተያዙት አጀንዳዎች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለምንም ቅክችክ የይሁንታ ውሳኔ አሳለፈ አንድ ያልተያዘ አጀንዳም ላይ ውሳኔ አሳለፈ

ውሳኔዎች

1. እምሩ ሰርጉ ይደምቅ ዘንድ የሰርጉ መኪና የቬሎና የመሳሰሉት ኪራዮች በቤተዘመዱ እንዲሸፈን

2. የሽአረግ ትልቁን ፍሪጅ እንድትገዛ (እንዳትታለል ዳንኤል አብሯት መርካቶ እንዲሄድ)

እንዲሁም አብረሃም ኮምፒተሩ እየተንተፋተፈችና እየጋለች ስላስቸገረችው ከቤተዘመዱ ካዝና ወጭ ተደርጎ አዲስ ኮመፒተር እንዲገዛለት !!

ማታ ራት ቀርቦ ሲበላ "ነገሩ ነው እንጂ " አለ አጎቴ በይቅርታ መንፈስ አየት አድርጎኝ " ስንት የተመሰገኑ ጋዜጠኞችና ትልቅ ሰወች ስለቤተሰባቸው በመጣፍ ነው ትልቅ ደረጃ የደረሱት ለምሳሌ ጠሃፊ ትዛዝ ክቡር አክሊሉ ሃብተወልድን ያየን እንደሆነ  እንደዚህ እንደአብረሃም " በለው!! ሲያከብሩን ለጥቅማቸው ሲንዱን ለጥቅማቸው ቅድም አገር የከዳሁት አብረሃም አሁን ጠሃፊ ትዛዝ

አጎቴ በወዳጅነት ያወራኝ ጀመረ ያውም አጥንቱን ወደኔ ገፋ አድርጎ " ብላ እንጅ " እያለ

ኤልሳ ከንፈሯን ጠመም አደረገች በአሽሙር አልሰደብኳትም ትንሽ ውለታ ሳይሰማኝ አልቀረም

ዊንታየ ወደጆሮየ ጠጋ ብላ "በል ከዚች ሽለመጥማጥ ጋር የማይሳሳብ ኮምፒተር ግዛ " አለችኝ

"አታገዛዥኝም እንዴ ?" አልኳት

"ምን ትጋብዘኛለህ ? "

"የፈለግሽውን "

"እና ደግሞ ቪክቶሪያ ትገዛልኛለህ ? "

"ምንድን ነው ? "

"ቻብስቲክ "

" ተይው ብቻየን እገዛለሁ !!"

"በቃ እሽ ፒዛ ትጋብዘኛለህ " ድርድሩ በስምምነት ተጠናቀቀ

ባለሱቅ " ፀረ ሽለመጥማጥ" ሶፍትዌር የተጫነበት ላፕ ቶፕ አለህ  ?

የፃፍነውን ለተንኮል የሚጠቀሙበት ካሉ ተንኮልን "ሰካን " ማድረጊያ አዲስ አንቲ ቫይረስ ነው ቢልጌትስ ወዶ ነው ሳይነቲስት የሆነው ???!!

አጎቴ ጋር ሌላ ቀን ስለፌስ ቡክ ስናወራ

"ይሄ ሁሉ ወፈሰማይ ህዝብ ገዋደኛየ ነው ነው ያልከው ?"አለ

"አዎ አጎቴ"

"እችም የምትስቀው ጓደኛህ ናት "

አዎ

እችስ ራቁቷን ያለችው

ጓደኛየ ናት

ይሄስ ባለመነጠሩ

እሱም ጓደኛየ ነው

"እኔ የምልህ አብረሃም ታዲያ ይሄ ሁሉ ወዳጅ እያለህ ነው በቀደም የሁለት ሽ ብር ዋስ ጥራ ብትባል እኔ ዘንድ የመጠሃው ? " አለ በኩራት ምን ያህል እንደምወደው በዚህ አስልቶት !!

**ተፈፀመ**

# ዙሪያሽ ሳትፈልግ ፖለቲከኛ ሆነች

እቤት ስገባ እናቴ ከዙሪያሽ ጋር ስትነዛነዝ ደረስኩ (ዙሪያሽ ሰራተኛችን ናት እኛን ሁሉ ያሳደገች በቃ ቤተሰብ የሆነች) "አልበዛም ጡር አለው እንዴዴዴዴዴዴ የምን መጨማለቅ ነው " ትላለች እናቴ "ኧረ ማሚ መጨማለቅ አይደለም ተይ ክፉ አትናገሪ" አለች ዙሪያሽ እንባ እየተናነቃት(ማሚ ነው የምትላት እናቴን እንደእኛ) "እንግዲያ ምን ይሉታል አንድ ሞሰብ ሙሉ እንኩሮ ሳምንት ስታነኳኩሪው ምጣዱ ይሆናል ብየ ዝም አልኩ ትላንት ለቁርስ የቀረበልን እንኩቶ ዛሬም ይሄው የእህል ጡር የለውም ገንዘብ አይደለም የወጣበት ከመሬት ታፍሰዋል " አለች ወደሞሰቡ እየጠቆመች አንገቴን ሰገግ አድርጌ ሳይ የተነኳኮረ ዳቦ ሞሰቡን ሞልቶታል !! " እትየ የኔ ችግር አይደለም እኔን እዚህ ቤት ሲያውቁኝ የዶሮ አይን በመሰለ ጠላየ ነው አይኑ ሰም በመሰለ እንጀራየ ነው ተገምጦ በማይጠገብ ድፎየ ነው " " እና አሁን ምን መጣ ? " አለች ማዘር "ስንዴው ነዋ !! ከዚህ ከቀበሌ ያመጣነው ስንዴ ወይ ሲቦካ ውሃ አያነሳ ወይ ሲጋገር ከምጣዱ አይነሳ ምድረ የቀበሌ ጉቦኛ ጋር ስንዴውን ለማምጣት የምነታረከው አንሶ ጭራሽ በሰላም ቤቴ መቀመጫ አሳጣኝ ስንዴ መውሰድ ዲሞክራሲ መብታችን ነው ዳቦ መብላት መብታችን ነው ተሰልፈን ችግር መግዛት አለብን? ማሚ ይሄ ልክ አይደለም "ቀበሌውን ስትፈሩ" ሰራተኞቻችሁ ላይ ትጮሃላችሁ!! ያውም ለቁራሽ ዳቦ!! መንገድ እንስራ ብለው ሲያነኩሩት አትናገሩም ? ሃኪም ቤት እንስራ ብለው ሲያነኩሩት አትናገሩም? ፍትህ እንስጥ ብለው ሃቀኛውን ከውሸታሙ ደባልቀው ሲያነኩሩት አትናገሩም ? የህዝብና የመንግስትን ካዝና ሲያነኩሩት አትናገሩም ወይስ ጡር ያለው ዳቦውን ደሃ ሲያነኩረው ብቻ ነው ሰራተኛው ላይ ብቻ !! "አህያውን ፈርተው ዳውላውን አሉ" አለችና እየተቆናጠረች ወደውጭ ወጣች !! ቀስ ብየ ተከተልኳት በረንዳው ላይ ቁማ ለብቻዋ እንዲህ አለች "ምን እዚህ ሰው ሳይፈልግ ፖለቲከኛ ያደርጋሉ "

(አዲስአበባ ኢትዮጵያ) (3 ግንቦት 2005)

# ዘንዶ ቢጠመጠም በወገቤ ላይ

እሷን አሳልፌ እሰጣለሁ ወይ ሞት አይደለም ወይ

ይሄው ብትተኩስ ጥይትህ የማይደርስበት ብትፎክር የማይሰማበት አገር ላይ ሆኖ ሴትህን ቀማህ ቦልት!! ያውም እንቁልልጭህ እያለ አንተ ቤት እየቀረቀርክ መብራት እያጠፋህ አዩኝ አላዩኝ እያልክ ትንፋሽህ እንዳይሰማ ከንፈርህን ነክሰህ የነበረውን ቦልት ጀግናው አሳየሃ! አንዴ አልጋ ላይ አንዴ ገንዳ ውስጥ ( አንተ ገንዳ ውስጥ ብርድ ልብስ ነው የምታጥበው ) እናልህ ዋናው ነገር ቅናት ነው ያንገበገበህ ቅጥል ያደረገህ “ድንክ ሁሉ ቀጫጫ ሁሉ” መለሎው ፈርጣማው እንዳንተ ጫት ያልጨረሰው ያችን የመሰለች ቆንጆ አጣጣማት!! አንተ በሰአት 25 ሳንቲም ቆጠረ አልቆጠረ እያልክ ኢነተርኔት ቤት ጅስምህ ግሎ ወላ ጅንስህ ወላ ጨርቅ ሱሪህ ጠቦህ በቅናት ስትንጨረጨር ቦልት እደግመዋለሁ ቦልት(ስሙ ራሱ ደምህን ያፈላዋል አይደል) ቤቲን ብ !! ምን ትሆን

“አባቶቻችን ያወረሱን ባህል እናቶቻን አደራ ያሉን ጨዋነት እያልክ በየጫት ቤቱ ስታወራ (ጫትህ ትን እስኪልህ) ቦልት እንደገና ቤቲን ብ !! ኡኡኡኡኡ እች ልጅ አብዳለችል እስክትል ታውቃት ይሆናል መቀመጫዋ በጅንስ ተወጣጥሮ ስታልፍ ስታገድም ምራቅህን ውጠሃል አበሻ ነህና የፈለካትን ከመጠየቅ ይልቅ ስትፎግራት ስታንቋሽሻት ኑረህም ይሆናል አሳየችሃ ”ባለቤት የናቀውን አሞሌ ባለእዳ አይቀበለውም ” እያልክ የአባትህን ተረት ስትተረትር ቦልት የናከውን ጨውህን ላሰው ሞጨሞጨው “ሲጥም “ እያለ! አንተ “ “ምንሽ” ይቅር እንጅ እርግጫው ምንድን ነው” ሰትል ቦልት እርግጫውን ቻል አድርጎ ቤቲን ብ !! ገና የ 80 ሚስትህን ይቀሙሃል የቦልት አገር ልጆች”እንዳንተ ድንክና ቀጫጫ ያልሆኑ የኢትዮጲያን ካርታ እያጠኑ ነው አሉ!! ላሊበላን ሊያዩ አክሱምን ሊጎበኙ እንዳይመስልህ አንተ እኮ የዋህ ነህ “ቁልቢ ሊሳለሙ ነው” ትል ይሆናል የሚሊኒየም ምልክትህ ምን ነበር ትዝ ይልሃል አሱን ሊጎበኙ ነው የሚመጡልህ መጡልህ አለቀልህ ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ! ሚስትህ ያች ዘንቢል ይዛ ገበያ የሄደች ገራገር ሚስትህ ላጥቶጥ ይዛ “ሃኒ “ የኔ ድንክ የኔ ቀጫጫ እያለች ትመጣለሃለች እዛ ፈረሱላ በርበሬ አስቤዛ ኪሎ ጎደለ እያልክ ሚዛን ላይ ስታፈጥ ሚስትህ ሱፐር ማርኬት ውስጥ “ኤክፓየርድ ዴት” እያነበበች ነው ያውም ከቦልት አገር መለሎወች ጋር በየመደርደሪያው ስር እየተሳሳመች !! ዛሬ የቤቲን ቪዲዮ እያየች “በስመ አብ” የምትለው ሚስትህ ስትሸውድህ ነው ውስጧ በመበለጧ ተቃጥሏል ባክህ ይሄን ጉድ አላይም ያለችህ ሚስትህ እግርህ ወጣ ሲል ጠብቃ ሽ ጊዜ አይተዋለች አናቷ ላይ ያሰረችው ቅቤ በቅናት እስኪቀልጥ እዚህ ትብሰለሰላለህ ቦልት ቤቲን ያንተን ኢትዮጲያዊቷን ቤቲን እዛ ብ !! ገና ሁለት ወር አለ እዚህ ትራፊውን ይወረውርላሀል ትሻማለህ ፈረንጅ (ጥቁርም ቢሆን) የነካው ነገር ትወዳለህ !! ታያለህ “ምንም ማለት አይደለም” ብሎ አንዱ ድል ባለ ሰርግ ሲየገባት!! እና አሁን አንተ ይሄን ሁሉ ነገር እስክታነብ እዛ ቦልት ቤቲን ብ !!

(አዲስአበባ ኢትዮጵያ) (ግንቦት/11/2005)

# ዘላለም የመኖር ጥበብ (የህዝብ ተረት)

በድሮ ጊዜ በአንድ መንደር ውስጥ እጅግ የተፈራ ሽፍታ ይኖር ነበር ቢገድል ቢዘርፍ የሰው ሚስት ቢቀማ ማንም የማይናገው አፄ በጉልበቱ !! ሽፍታው ታዲያ ይሄ ተፈሪነትና ክብር ድንገት ከእጁ እንዳይወጣ ፈራ ተጨነቀ "ድንገት ብሞት ልጆቸን ማንም እኔ የበደልኩት ሊበቀላቸው አይደለም" አለና አስቦ አስቦ "ያለኝ አማራጭ አለመሞት ነው " አለ እናም የሞት መድሃኒት ለመፈለግ ወሰነ ራቅ ያለ መንደር ውስጥ ጠፈር የሚያቆም የተናገረው መሬት ጠብ የማይል ጠንቋይ አለ ሲባል መስማቱ ትዝ አለውና መላ ቢገኝ ብሎ ሽፍታው ወደዛው ገሰገሰ ጠንቋዩ ጋር እንደደረሰ "እንደምን ዋሉ ጌታየ " አለ ሽፍታው በግንባሩ ተደፍቶ

"እንደምን ዋልክ ልጅ" አለ ጠንቋዩ ያም ዛሩን ይሄም ምንሽሩን ፈርተው ተከባበሩ

"የሞት መድሃኒት ያውቃሉ ተብየ ነው አመጣጤ "

" ማነው ያለው "

"አሃ አገሩ ሁሉ የሚያወራው ስለእርሰዎ ነው"

" እ አገሩን ተወወው ወደቀ ሲሉት ተሰበረ ይላል  አንተን ይገላል ሲሉ ኖሩ ደግሞ አሁን እኔን ያድናል ሆሆ"

" እና የሞት መድሃኒት አያውቁም " ሽፍታው በብሰጭት ጠየቀ

" እኔ እንኳን የሞት መዳኒት አላውቅም ግን በሰው እጅ እንዳትሞት የሚያደርግ መዳኒት አለኝ"

"ኧረረረረረረረ ሃዲያ ዋናው የምፈልገው ምን ሆነና " አለ ሽፍታው

ጠንቋዩ የሚቀምሙትን ሁሉ ቀመሙና ድግምታቸውን ደጋግመው "ይሄንን ሳታላምጥ ዋጥ " አሉት ሽፍታው ዋጠ

"እንግዲህ ጥይት በአጠገብህ አያልፍም ስለትም ወዳንተ ሲቀርብ ውሃ ነው ትፍትፍትፍ ሂድ" አሉት ጠንቋዩ

"ልሞክረው እንዴ " አለ

"ሞክር " አሉ በኩራት

አፈሙዙን ወደራሱ አዙሮ ተኮሰ (ሽፍታ ደፋር ነው) ወይ ፍንክች ጥይቷ እሱን ሳትነካው መሬት ላይ ወደቀች መድሃኒቱ ሰርቷል

ሽፍታው በጣም ተደሰተ ግ ን አንድ ነገር አስጨነቀው

"ጌታየ ለመሆኑ ይሄን መድሃኒት የሚያከሽፈው ምንድን ነው " ሲል ጠየቀ

"መድሃኒቱን ሚያከሽፍ ምንም ነገር በምድር ላይ የለም ከእኔ በስተቀር " አሉት

አጅሬው ፈገግ አለና "ከእርሰዎ በስተቀር " ብሎ ቃሉን ደገመው

"አዎ እኔ ብቻ ነኝ የማከሽፈው "

ሽፍታው ምንሽሩን ወደጠንቋዩ አዞረና ተኮሰ ጠንቋዩ ወደቁ

ሽፍታው "አሁን ዘላለማዊ ሆንኩ " አለና ሊወጣ ሲል ጠንቋዩ ከሞት ጋር እየታገሉ ጠሩት ጠጋ ብሎ

"ምን ሆኑ ጌታየ" አለ ሊጨርሳቸው ጥይት እያጎረሰ

"መ መ መድሃኒቱ ፍቱን ነው

"እሱንማ ነገሩኝ "

" ጥይት አይነካህም "

"ኦኦኦ የጅል ዘፈን አሉ " አለ ሽፍታው

" ግን መድሃኒቱ የሚሰራው አንተ ሌላ ሰው እስካልገደልክ ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር " ብለውት ግጥም አሉ !!

(አዲስአበባ ኢትዮጵያ) (ነሐሴ/23/2005)

# ዋጋህን ሳይሆን ሻጭህን አስብ......

አጼ ቴውድሮስ ቀሳውስትን እና ዲያቆናትን ሰበሰቡና እራት ጋበዟቸው ! መብላት አይበለው! ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ እየተሳቀቁ ትንሽ ትንሽ እየጎረሱ የሚወዷትን ጠላ እንኳን ሳይጠጡ አመሹ ። ምክንያት ቴውድሮስ ቄስና ዲያቆን አይወዱም በየምክንያቱ ነገር እየፈለጉ ሲቀጧቸው ሲበዛም ሲገሏቸው ኑረዋል!! "እና ዛሬ ምን ተገኘና እራት ጋበዙን እንኩ ብሉ አፈር ብሉ ሊሉን ነው እንጅ ብለው ሲሸበሩ እራት ተበልቶ ማእድ ከፍ አለ .....

ቴውድሮስ መናገር ጀመሩ ጎርደድ ጎርድ እያሉ አቤት ቁመት አቤት ግርማ ሞገስ .... " የአገሬ አዋቂወችና ሊቃውንት(ፉገራ በምትመስል አነጋገር) እናተ መቸስ ከፈጣሪ የተቀባችሁ የሚስጥራት ፍች ሁሉ በከናፍርታችሁ የተቀመጠ የእግዜር አገልጋዮች ናችሁ...." አገልጋዮቹ አድናቆቱ ሞቅ አላደረጋቸውም የቴውድሮስ ሽጉጥ ላይ አይናቸው እየተንከራተተ ቁልጭ ቁልጭ ይላል።

" እንግዲህ የዛሬውን እራት መጋበዜ በአይምሮየ የሚንከላወስ አንድ ጥያቄ ስላለ እናተ ምላሹን እንድትሰጡኝ ነው !! መቸስ ይሄን ጥያቄ ካልመለሳችሁ ወደቤታችሁ እንደማትመለሱ ከእናንተ የተሰወረ አይደለም ....." ይሄዋ አሉ ተጋባዦቹ!!

"ጥያቄየ ....እኔ መይሳው ካሳ ብሸጥ ስንት ብር አወጣለሁ" ብለው ቀሳውስቱ እና ዲያቆናቱ ላይ አፈጠጡ...አቤት አፈጣጠጥ! ከቴድሮስ በኋላ አፈጣጠጡ የሚያምር ንጉስ ኢትዮጲያ አላገኘችም !!

አንዱ ዲያቆን ተነሳና " በስማም ይበሉ ጌታየ ...ባሪያ ንግድን ያስቆሙ እርስወ እንዴት እራስወን እንደባሪያ ብሸጥ ይላሉ"

ቴውድሮስ ተቆጡ" እንደባሪያ እልኩ....ወጣኝ....ዝም ብለህ ባሪያ በለኝ ...ስደበኝ..." አሉና ወደአሽከሮቻቸው ዙረው "ስሰደብ ቁማችሁ ታያላችሁ" አሉ እያዳፉ ወሰዱት ዳቆኑን በር ላይ ተኩስ ተሰማ ዷ!

" እኮ ንገሩኝ! ብሸጥ ስንት አወጣለሁ"

አንዱ ቄስ ሲፈራ ሲቸር " ጌታየ እርሶን የሚገዛ ምን ያቀበጠው ነው ወስዶ ምን ያስቀምጠወታል ምድር የማይበቃዎ ታላቅ ንጉስ"

"እከከከከከከ ምን ያስቀምጠወታል እኔ ቴውድሮስ ቅንብርብር ያልኩ በወንድ ልክ የተሰራሁ ጀግና ነኝ እንደሰባ በሬ ላንተ ማስቀመጫ የለም ትላለህ ....ያዘው "........ዷ!

ሌላው "እርስወን መግዣ ምን ወርቅ ምን አልማዝ ምን እንቁ ይገኛል እንደው አለምግዛቱ ይሻላል ጌታየ"

"አሃ ቁመህ ትቀራታለህ አንተን ማን ይገዛል ነው ቅኔው".......ዷ!

አንድ ብልጣብልጥ ፊት ያለው ዲያቆን በሚገርም የራስ መተማመን ቴውድሮስ ፊት ቆመና " ጌታው የእርሰዎ ዋጋ እኮ የታወቀ ነው " አለ።

" ስንት ነው...." ቴውድሮስ ተገርመው ጠየቁ!

" ሃያ ዘጠኝ ብር ነዋ!"

"ምን ....ጆሮየ ነው ወይስ ......"

"ጆሮወት አይደለም ጌታው ዋጋወ 29 ብር ነው አምስት ሳንቲም አይጨምርም!" አለ ቆፍጠን ብሎ!

ቴውድሮስ ከልእልት ማንትስ በስጦታ የተበረከተላቸውን ሽጉጥ ላጥ አደረጉ... አቀባበሉና" እንዴት ብትንቀኝ ነው በፍየል ዋጋ የሸጥከኝ ጃል..." አሉ ደማቸው ፈልቶ....

" ጌታየ ጌታችን መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ የተሸጠው ሰላሳ ብር ነው ....እርሰዎ ከፈጣሪ እኩል አይሆኑም መቸስ በአንድ ብር ዝቅ ብለው ቢሸጡ ያዋጣል ብየ ነው" አላ እና ቴውድሮስን አስቆ ያን ሁሉ ቄስና ዲያቆን አተረፈው !! ማን 29 ብር እንደሚሸጣቸው ግን ማንም በወቅቱ አላሰበም!

(አዲስአበባ ኢትዮጵያ) (ግንቦት/5/2005)

# ካካካ ካካ !!

የመኮሳተሪያ እፍኝ ወኔ ሲያጣ ጥርሱን እየፋቀ ጥርሱን እያነጣ ፍንትው ያገሬ ሰው "በቃ !! የምን መገልፈጥ ነው ከመጣፍ ከሊቅ አፍ ገልጦ ላነበበ ሂዶ ለጠየቀ ለአንዲት እንኳን ቅፅበት ጌታ መቸ ሳቀ "በቃ!! " ያዛዥ ቁጣ!! ይህንን ቢሰማ አመዱን አንጥፎ ማቅ እየለበሰ ህዝቡ ተላቀሰ ፀጉሩን እየነጨ በእንባ ተራጨ ! አንድ ወፈፌ ብቻ ከት ከት ብሎ ሳቀ በአልቃሽ ተሳለቀ በሳቁ መካከል ወፈፌው ይጮሃል " ሰው ደመ ሞቃቱ ሰው ስጋና አጥንቱ በ"አትሳቅ" ት.ዛዝ ፈገግታ ቀባሪ ሙሾ አሳማሪ እንደግኡዝ አለት በቁሙ በድኖ ያድምበት ቢያጣ በሳቅ ላይ ተቧድኖ.. እንደከረምት አለት የእንባ ምንጭ ሲያፈልቅ ካካካካካካ ካካ ሲያስቅ!! ሲያለቅስ የነበረ አልቃሻ ህዝብ ሳቀ በእንባ ርስቱ ላይ የሳቅ ዛፍ ፀደቀ በትዛዝ አልቅሶ በወፈፌ የማይስቅ ካንድ ጥግ ቁሞ እንዲህ ይናገራል "ህዝቤ እኮ ጨዋ ነው በጤነኞች ትዛዝ በወፈፌ ምክር ሲመራ ይኖራል !! እንዲህ ይናገራል

(አዲስአበባ ኢትዮጵያ) (2005)

# ኪነት

ለምን እንደሆነ እንጃ ዛሬ አመለ ትዝ አለችኝ ዛሬ እሁድ አመለ ትዝ አለችኝ አመለ አንድ ላይ ያደግን የሰፈሬ ልጅ ነበረች (ነፍሷን ይማር) ታዲያ አመለ ሁላችንንም ትሰበስበንና "ኪነት ኪነት እንጫዎት " ትለናለች ደስ ይለናል ከዛም በኪነቱ ውስጥ የስራ ድርሻችን በአመለ ይነገረናል

"ዳንኤል አንተ ከበሮ ትመታለህ" ትልና አንድ የተቀደደ ጀሪካን ትሰጠዋለች "ባዩሽና መአዛ ተወዛዋዥ ናችሁ" ሹራባቸውን አውልቀው እንደነጠላ ወገባቸው ላይ ያሸርጣሉ "አለማየሁ ኦርጋን ".. የልብስ ማጠቢያ አሮጌ ጎማ ከፊቱ ያነባብርና ኮስተር ብሎ ይቆማል "ይልማ ማሲንቆ ትይዛለህ " የግራ ክንዱን ወደጆሮው ያቆምና ቀኝ እጅን እንደማሲንቆ ደጋን ተጠቅሞ ይሞክራል "አብረሃም ጊታር " የእነዳኒን ቤት የመስኮት መቀርቀሪያ እንደ ጊታር አጋድሜ እይዛለሁ "እኔ ዘፋኝ ነኝ " ትልና የፊሊት እቃ እንደማይክ አፏ ላይ ደቅና ባንዱ ስራ ይጀምራል!

"የቤቴ ወለሉ ጣራና ግድግዳው ባንተ ሃሳብ ተሞሉ "

አመለ እየዘፈነች ዳኒ አሮጌ ጀሪካ እየወገረ ተወዛዋዦቹ እየተወራጩ ትንሽ እንደቆየን ይሰለቸናል መጀመሪያ የሚሰለቸኝ እኔ ነኝ ድምፅ የሌለው መቀርቀሪያ ይዠ የባንዱ አባል በመሆኔ ጅል የሆንኩ ስለሚመስለኝ በቃ ጥየው ወደቤቴ እሄዳለሁ ሌሎቹም እንደዛው

አመለ ታዲያ ሁላችንም ብንበተንም ዘፈኗን አታቆምም (እዚህ ላይ ትዝ ለችኝ ) ዳኒ የጣለውን ጀሪካን ታነሳና እራሷ እያንኳኳች ትዘፍናለች የእኔን "ጊታር" ታነሳና እያስመሰለች ትዘፍናለች እራሷ ልቧ ውልቅ እስኪል ትወዛወዛለች እራሷ እልልልልልል ትልና እራሷ ታጨበጭባለች ከዛም የዳኒን ከበሮ አንስታ ታ ታ ታ አድርጋ "ዲሽሽሽ" ብላ ታሳርጋለች ብድግ ብላ እጇን ወደሰማይ ትዘረጋና በሃሳብ የፈጠረችውን ህዝብ ቻው ቻው እያለች የሁለት እጆቿን ጣቶች እየሳመች ፊቷ ያልተሰበሰበው የሃሳብ ህዝብ ለሰጣት የሃሳብ አድናቆት አፀፋ ትመልሳለች ከዛም እንደማይክ የምትጠቀምበትን ባዶ የፊሊት ቆርቆሮ ታነሳና

"ክቡራንና ክቡራት በዛሬው እለት ጣፋጭ የሙዚቃ ስራወችን ያቀረቡልን የፍቅር ባንድ አባላት ነበሩ ከበሮ ይዞ ያያችሁት ዳንኤል ተፈ ራ ዳኒ ጊታር አብረሃም አሌክስ ከአውሮፓ ለዚሁ ስራ ሲል ነው ትላንት የመጣው ህዝብን ለማስደሰት ብሎ ዶላር ንቆ ሞራል ሞራል ለአሌክስ ( እኔ እቤት እናቴ የዳቦ መግዣ እንድትሰጠኝ እየተነዛነዝኩ እኮ ነው ) በመጨረሻም ይህን ባንድ በማሰባሰብ ታላቅ ስኬት እንዲቀዳጅ ያደረገችው በአገርውስጥና በውጭ አገር የምትታወቀው አመ ለ ሁነኛው!!

እማማ ዘርፌ ታዲያ ወይ ጉድ አንችው ደላቂ አንችው አድማቂ ሁነሽ እዳሽን አየሽ ይሉና አስር ሳንቲም ይሰጧታል

(አዲስአበባ ኢትዮጵያ) (ነሐሴ/23/2005)

# ከወየውልሽ ወደ ወየውልሽ

## ይህ ተከታታይ ወግ ሶስት ክፍሎች አሉት

## ክፍል 1

ለወትሮው ብራቅ የሆነ ድምፄን ለስለስ አድርጌ “አሴ” እላታለሁ (እናቴ አሰለፈች ነው ስሟ ) “ወይየ” ያጠበችውን ልብስ እየጨመቀች ነው  “ለስፖርት የማዋጣው 25 ሳንቲም ስጭኝ “ “አንተ ደሞ የዛሬ ሳምንት የስፖርት ብለህ አምሳ ሳንቲም አልወሰድክም እንዴ “ “ያማ ቡድኑ ውስጥ ለመመዝገብ ነው አሁን ግን ለኳስ መግዣ ነው ” “ያንተ ለብቻው ነው እንዴ ልጁ ሁሉ በነፃ ይጫዎታል አንተ ጧት ማታ ሳንቲም እቁብ ነው የገበሃው

ኧረ አሴ.. ማሪያምን መድሃኒያለምን ሁሉንም ጠይቂያቸው አዋጥተዋል ካላመንሽ ቆይ ታምሩን ጠይቂው ብየ ለዚሁ ተዘጋጅቶ በር ላይ የቆመውን ጓደኛየን “ታሜ “ ብየ እጠረዋለሁ አቤት ከማለቱ በፊት አጠገባችን እየሮጠ ደርሷል ነፋስ!! “ኤዲያ አቧራውን እርጥቡ ልብስ ላይ ሞጀርክብኝ ቀዥቃዣ “ ትለዋለች  ታምሩ ሩጦ መጥቶ ድንገት ለመቆም በሚያደርገው ጥረት ሸራ ጫማው መሬቱ ጋር ተፋትጎ ያስነሳውን አቧራ በእጇ እያራገበች እየው እንግዲህ ምስክሬን ገና ከመምጣቱ ስትለክፊው ምስክር ማሰማቴን እቀጥላለሁ “ ታሜ ሁሉም አዋጥተው የለ እኔ ብቻ አይደለሁ የቀረሁት” (መሪ ጥያቄ ) “አዎ ” ይላል ንፍጡን በእጅጌው እየጠረገ! ” ኤሊያስ እናቱ ከፍላለት የለ

ኢስማኤል አባቱ ከፍሎለት የለ

ዳንኤል አጎቱ ከፍሎለት የለ አጎቱ ሳይሆን አክስቱ ናት የከፈለችለት “አየሽ አይደል “ ብየ ወደእናቴ በኩራት ስዞር ምስክርነቱን ከነአካቴው የሰማችውም አትመስልም ገመድ ላይ ያሰጣችውን ልብስ በመቆንጠጫ እያስያዘች ታንጎራጉራለች እህህ አህህህ እያለች ብስጭት ብየ “ሰማሽው አይደል አሴ “ እላታለሁ “የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ አሉ አታድርቁኝ ወደዛ ሂዱ !! “ ጉዳዩ ሲፈፀም በቦታው እስከነበረ ድረስ ምስክር ድንቢጥ ይሁን ቁጫጭ ይናቃል ? ወይስ በቦታው ከነበረች ድንቢጥ በቦታው ያልነበረ አንበሳ ቢመሰክር ይሻላል ነው?? “ውሸታም አንበሶች” የበዙት ለዛ ሳይሆን አይቀርም !! የቡድናችን “10” ቁጠር አጥቂ ታሜ ሲመሰክርላት ያላመነች ማን መጥቶ ይመስክርላት እንዴዴዴዴ ( ለኔ ሊመሰክር በተሰደበ እኔው የእናቴን ተረት ለጓደኞቻችን አውርቸ ለጉድ ሳቅንበት ! ምን ይሄ ብቻ የታምሩ ቅፅል ስም <ድንቢጥ> ሆኖ ቀረ እኔን ለምን አይጥ እንዳላሉኝ አሁን ሳስበው ይገርመኛል ለእውነት የመሰከሩ ላይ ቅፅል ስም እየለደፍን ቀንድ እናጨራ እየቀጠልን ምስክር ብናጣ ይገርማል?) አንጀቷን ለመብላት እንባየ እንዲመጣልኝ እየታገልኩ “ በቃ ከቡድን ያባርሩኛል “ እላታለሁ የለኝም አባትህ ሲመጣ ጠይቀው (የማዘን ምልክት ያየሁባት መሰለኝ) ያጠበችውን ልብስ ስታራግፈው ርጋፊውን የውሃ ብናኝ ያዘለ ርጥብ ንፋስ ፊቴን ፀጉሬን ከጉርድ ቲሸርቴ የወጣ ክንዴን ያለብሰኛል የውሃ ብናኝ.. አቤት ቅዝቃዜው (የ 25 ሳንቲም ጥያቄ ከአመፅ ተቆጥራ በውሃ መባረራችን ነው ?) እና አትሰጭኝም? (በማስጠንቀቂያ ) አልሰጥህም (.ምን ታመጣለህ ) እኔ ልጅሽ አይደለሁም አይደለህም ( በአቧራ የበከተ የእኔን ጨርቅ ሱሪ ባለ በሌለ ሃይሏ እየጠመዘዘች) ታዲያ ሱሪየን ለምን ታጥቢያለሽ ዝም ትላለች ሳቋ ግን መጥቶባታል  አትሰጭኝም? ሁለት (ወይኔ ከአንድ ነበር መጀመር

አልሰጥህም አልኩ አታድርቀኝ አትሰጭኝም ? ሶስት !!!! (የሆነ ኒውክሌር ቦምብ ነገር ላፈነዳ የተዘጋጀሁ ነው የሚመስለው) ኦኦኦኦ ሂድልኝ ከዚህ ስራየን ልስራበት ምን ያደርቀኛል እስከመቶ ሊቆጥርብኝ ነው እንዴ ተይዋ ከእማማ ሩቅያ እቀበላለሁ!!! (ቆንደፍ ቆንደፍ እያልኩ እሩጫ ይሁን ርምጃ ባለየለት እንቅስቃሴ ወደእማማ ሩቅያ ቤት እሄዳለሁ እማማ ሩቅያ በሚነጫነጭ ድምጽ ለበይክ (አቤት ሲሉ እንደዚህ ነው) እች አሴ የስፖርት 25 ሳንቲም ስጭኝ ብላት እንቢ አለችኝ ከቡድን ልታስባርረኝ ነው “እኔ እናትህ እያለሁ ማን ነው የሚያባርርህ ?! ሳሎን ግባና ቡፌው ላይ መሃረሜ አለልህ የሚበቃህን ውሰድ !! ደስ ብሎኝ እፈነጥዛለሁ ሳሎናቸው ምንጣፉ ያስፈራኛል ሲረግጡት ትርቡሽ ይላል !! ምንጣፉ የተሰራባቸው እና እጅብ ብለው የቆሙ በጣም ብዙ የክር ፀጉሮች

ሲረግጧቸው በአንድ ላይ ለሽ ይሉና ረገጣው ሲነሳ ቀ ስ እያሉ ተነስተው ወደቦታቸው ይመለሳሉ (የታለ አንድነት ሃይል የሆነው) ጫማየን ለማውለቅ ስታገል ብዙ እቆያለሁ በጣም ትልቅ ጥቁር ሰማያዊ ጨርቅ ላይ የተሳለ የመካ ስእል ሳሎኑ ግድግዳው ላይ ተሰቅሏል በወርቃማ ቀለም በአረብኛ የማላውቀው ነገር የተፃፈባቸው በርካታ ጥቁር ጨርቆችም ዙሪያውን ግድግዳው ላይ አሉ (እንደኛ ቤት ግድግዳ ላይ ጥቅሶች “ ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዲባቱ ምናምን የሚሉ አይደሉም) እስካሁን ጠረኑ ከአይምሮየ ያልጠፋ ደስ የሚል የብርጉድ ሽታ ሳንባየን ይሞላዋል ጀነት ሲባል የእማማ ሩቅያ ሳሎን ነው ወደአይምሮየ ቀድሞ የሚመጣው ደግሞ ዙሪያውን ፍራሽ አለ ፍራሹ ጥግ ጥግ.. ግድግዳውን የተደገፉ ትራሶች ! አቤ ት የትራሶቹ አበዛዝ!! ቆይ ልቁጠራቸው እልና 1 2 3 4 5 6 7 (ስምንተኛዋ ትንሽየ ትራስ ናት ልቁጠራት አልቁጠራት ያው ቆጥሬ በኋላ እቀነሳታለሁ ) እ ያቆምኩበት ይጠፋኛል 1.2 3 4 “ኢብሩ ጠፋብህ እንዴ “ ይላሉ እማማ ሩቅያ ቁሜ ትራስ ስቆጥር የረሳሁትን ስሙኒ መቁጠሬን አቋርጨ ወደቡፌው ማሃረማቸው ለወት ሽብ ተደርጎ ቡፌው ከፈፍ ላይ እንደዋዛ ጣል ተደርጓል ውስጡ የተቋጠሩት ብርና ሳንቲሞች ቅርፃቸው ይታያል መሃረማቸውን ፈትቸ ሁልጊዜ ከመሃረማቸው የማትጠፋውን አስገራሚ የኩል መያዣ እቃ እያገላበጥኩ አያታለሁ..” እንዴት ይሆን የምትከፈተው “ ተመራምሬ ምርምሬ ዋጋ ቢስ ሲሆንብኝ ከብዙ ብሮችና ሳንቲሞች መሃል ስሙኒየን አንስቶ ወደኳስ ሜዳ ብርርርርርር ትዝ ሲለኝ ሳንቲሙን ወስጃለሁ እንኳን አላልኳቸውም “ስመለስ እነግራቸዋለሁ” እልና እረሳዋለሁ ሌላ ቀን ለሌላ ጉዳይ መሃረማቸውን መንብኘቴ አይቀርም

እናቴ ጋር ታዲያ ይጣላሉ “ልጁን “ባለጌ” ሊያደርጉት ነው እንዴ ምን ማለተዎት ነው ሩቁ ? “ ትላለች እኔን በብስጭት እያየች “ባለጌ” የምተለውን ቃል ለብቻዋ በአይኗ ወደኔ ትወረውራታለች አቤት ስትችልበት “ ታዲያ ከልጆቹ ይለይ እንዴ የቲም ልጅ ይመስል?! እንዴት ያለ ፍርድ ነው “ ይላሉ ከእናቴ የበለጠ ተቆጥተው (አንዳንዴ የእናቴ እናት ይመስሉኛል ግን ጎረቤታችን ናቸው) እናቴ ጋር ይኮራረፋሉ ተጣልተው የሚቀሩ እየመሰለኝ ትንሽ ልቤ ሲጨነቅ ልክ ምሳ ሰአት ላይ እናቴ ኮስተር ብላ ወደማማ ሩቅያ ቤት እያየች “ሩ ቁ ” ትላለች

“ ኑ ቡናው ደርሷል “ “ መርሃባ ሶላቴን ሰግጀ መጣሁ “ ይላሉ ረጋ ባለ ድምፅ!! እፎይይይይ!! ታረቁ!! ይመጣሉ !! አጭር እና ወፍራም ናቸው.. ቀይ አይኖቻቸው ትንንሽና ኩል የማይለያቸው ባለአበባ ከሽከሽ ስፍ ቀሚስ የሚያዘወትሩ ፀጉራቸው ላይ ጉፍታ ጣል የሚያደርጉ የሚያምሩ ባልቴት በእጃቸው ባቁላ ባቁላ የሚያህሉ ጨሌወች የተሰኩበት መቁጠሪያቸውን እያቅጨለጨሉ ይመጣሉ (አንዳንድ ቀን ቡና ጠጥተው ሲሄዱ መቁጠሪያቸውን የተቀመጡበት ፍራሽ ላይ ረስተውት ይሄዳሉ እናቴ ሂድ አድርስላቸው ትለኛለች ) የራሳቸው ቦታ አለቻቸው “የእማማ ሩቅያ ፍራሽ “ የምንላት ቡና ሊጠጡ ሲመጡ እሷ ላይ ነው የሚቀመጡት ተነስተው ሲሄዱ ያች ፍራሽ ሳሎናቸውን ሳሎናቸውን ትሸታለች ቡናው ሊቀዳ ሲል እናቴን ይመርቋታል በረካ ሁኝ በረካ ሁኝ አላህ አገራችንን ሰላም ያርገው ልጆቻችንን በያሉበት ከክፉ ይከልላቸው የታመሙት ይሻሩ የሞተባቸውን አላህ ይራህማቸው አሰላሙአሊኩም ቅጅው ! እናቴ እጃቸውን ትስማለች እኔም እጃቸውን ብስማቸው ደስ ይለኛል ቡናው እየተጠጣ ስለጎረቤቱ ያወራሉ “እከሊት እኮ ልታገባ ነው ” ማሻ አላህ እሰይ እሰይ ባል ጥሩ ነው እከሊት ልጁ ታሞ ሆስፒታል ገባባት የአላህ ምን አገኘባት (የእውነት አዝነው ) እከሊት ወለደች እሰይ እሰይ እዛም ድረስ ችየ አልሄድም እንች እችን ይዘሽ ሂጅና “እንኳን ማሪያም ማረችሽ ብላሻለች ሩቅያ በይልኝ “ ይላሉ ከመሃረማቸው አስር ብር አውጥተው ለእናቴ እያቀበሏት !! እማማ ሩቅያ “እንኳን ማሪያም ማረችሽ

ያወራሉ ስለዝናብ መዝነብ አለመዝነብ ጅዳ ስላሉት ልጆቻቸው አንዳንዴም ስለሞቱት ባላቸው( ሽህ ሲራጅ) እናቴ ጋር ያወራሉ !! የማውቀው ሰው ሙቶ ስለማያውቅ ሞት ያለ አይመስለኝም ነበር ! ሽህ ሲራጅ ሲሞቱ ግን “አይገርምም ሞት አለ ለካ “ ብየ ተገረምኩ! እንደውም የመጀመሪያው የማውቃቸው ሚች ስለሆኑ ነው መሰል ሞት የተጀመረው በሽህ ሲራጅ ይመስለኝ ነበር!! ስለሳንቲሟ አይነሳም!! ስለኔ ስሙኒ አይነሳም !! በየሳምንቱ 25 ሳንቲም እናዋጣ ስንባባል አንደኛ “በጣም አሪፍ “ ያልኩት እኔ ነኝ ቅዳሜ የማይደርስ መስሎኝ የእማማ ሩቅያን መሃረም አይዋለሁ ሁልጊዜ አይጎድልም

# ክፍል 2

በደቡብ በኩል የማሪያም ቤተ ክርስቲያን በሰሜን የጊወርጊስ ጉልላት (ፈረሰኛውና ጦረኛው ጊወርጊስ)

በምስራቅ የሼህ አብደልቃድር እድሜ ጠገብ መስጊድ (<እሳቸው መጀን> እማማሩቅያ እንደሚሉት)

በምእራብ ዛፉ ሙዚቃ ቤት መሃል ላይ የእኛ ሰፈር አለ

እዚህ ሰፈር ያደግን ህፃናት በሙሉ ቅዳሴውንም የመስጊዱንም አዛን በቃላችን ሸምድደነዋል እንደውም የሶላት ሰአት ደርሶ የመስጊዱ ኢማም ገና “አላኋክበር ” ማለት ሲጀምሩ የመንደሩ ህፃናት ከኢማሙ እኩል አዛኑን ቃል በቃል እንወጣው ነበር፡፡ በኋላ እማማ እሩቅያ የመንደሩን ልጅ ሰብስበው ሻይ አፈሉልንና ደስ ብሎን እየጠጣን ያንድኛችን ብርጭቆ ከሌላችን ይበልጣል አየበልጥም እያልን ልናወዳድር ስናጠጋጋ ሻዩ ተንቦራጭቆ ልብሳችን ላይ እየተረጨ እማማ ሩቅያ ቀስ ብለው መከሩን ”አትጣሉ ማንቆርቆሪያ ሙሉ ሻይ መቸ ተነካና ” ሲሉን ወደማንቆርቆሪያው አይናችን ትክል !! ቶሎ ጨርሰን ለመጨመር ደግሞ ጥድፊያ ከፋቱ የሻዩ ትኩስነት ከንፈሬን አሞጥሙጨ በረዥሙ ሳብ ሳደርገው ምላሴን አንገረገበኝ ምላሴን ለመታደግ ላንቃየን ከፍቸ ስውጠው ከጉሮሮየ ጀምሮ ቁልቀል ሆድ እቃየን የእሳት ጎርፍ የጎረፈበት እስኪመስለኝ እያንገበገበኝ ወረደ እንባየ በአይኔ ሙልት ማንቆርቆሪያው ብዥ ብሎ ታየኝ ከግብግባው በኋላ እማማ ሩቅያ እንዲህ አሉን “ አዛን ሲባል አይጮኽም እሽ?” አሉን( በቃ እችኑ ብቻ ነው ያሉን) “እሽ !” አልን ባንድ ላይ ከዛ በኋላ አዛን ሲደረግ አብረን መጮኻችንን አቆምን !!

እንግዲህ እሁድ እሁድ ማሪያም ቤተክርስቲያን እንሄዳለን እዛም መዋጮ አለው ያውም በሳምንት አምሳ ሳንቲም !! ደግነቱ የእናቴ መሃረም ካለንዝንዝ የሚፈታው ለማሪያም ብቻ ነው !! ነጫጭ ነጠላ ያለብሱንና ውሉን ማጅራታችን ላይ ያስሩልናል፡፡ ቁንዲላውን ያሰሩት ነጭ ሸንኩርት ነው የምንመስለው!! ስንዘምር ውለን ወደሰፈራችን ስንመለስ ቁልቁለቱን በሩጫ እየተሽቀዳደምን ነው ነጠላችን እንደክንፍ እየተውለበለበ ያሁሉ ማቲ ወደታች ሲንደረደር ላየ እግዜር “ለዚች ኮሳሳ መንደርማ ለአቅመ መለአክ የደረሰ መለአክ አልክም “ ብሎ በህፃን መለአክ መንደሩን ያስወረረው ነው የሚመስለው !!

እነኡስማን እነመሃመድ እነኢስማኤል እነፉአድ..ደግሞ በዛው ሰአት ከመስጊድ የጣውላ ገበታ (የአሊፍ ባታ ፊደሎች የተቀረፁበት ) በጉያቸው ሸጉጠው ከቁርአን ቤት ወደሰፈር ሩጫ ነው እኛም ነጠላችንን ጥለን እነኡስማንም የአሊፋ ባ ታ ገበታቸውን አስቀምጠው ወደኳስ ሜዳ ሩጫ! ነይ ነይ እምየ ማሪያም ቤዛ ነሽ አሉ ላለም !! እያልን የመጣነው ህፃናት ወደኳስ ሜደሰ ስንሮጥ መዝሙራችን በጭፈራ ይተካል

አንበሳ ሆ አንበሳ ሆ አንበሳ ነን በጨዋታ ድል አለን !! አቧራው ይነሳል እናቶች ስጣቸው እና አጥበው ያሰጡት ልብስ ላይ ላይ አቧራ ስናቦልባቸው በመጥረጊያ ያሯሩጡናል ማሯሯጣቸው ውስጥ ፍቅር ነበር ወዳልሮጥንበት አቅጣጫ መጥረጊያውን ወርውረው ትመለሳታለህ በዚህ ይላሉ አንዱን ብንቆምም አይመቱንም የመሃበረሰብ ህግ ነውና ብትር ሲነሳ ካሮጥን ንቀት ነው !! እሩጡ እናሯሩጣችሁ !!

***** ***** ******

እየው ሎሌው ሲያገሳ ጥምቀት ሲሆን በበራችን የማሪያምና የጊዮርጊስ ታቦታት ያልፋሉ ፡፡ ሁለቱም ታቦታት ጋሽ በለጠ በረንዳ ላይ ከየቤቱ የወጣ መንጣፍ ይነጠፍና (እኛ ቤት ለዚሁ ተብሎ የተገዛ ከባድ ምንጣፍ ነበር ቁም ሳጥኑ ላይ ተጣጥፎ የሚቀመጥ) ይቆሙና ከዛ ነው ወደየደብራቸው የሚገቡት የወለዱ እናቶች የታመሙ ብቻ ታቦታቱ ወደሚያድሩበት መሄድ ያልቻሉ ከቤት ይወጡና በየበራቸው ቁመው እልልልልልልልልል እያሉ እየተሳለሙና እየተሳሉ ይሸኛሉ አንድ ቀን ታዲያ ልክ ታቦታቱ ተለያይተው የጊዮርጊስ ታቦት እንደሁልጊዜው በእኛ ቤት አልፎ ሲሄድ እናቶች እየዘመሩ ነበር እየው ሎሌው ሲያገሳ ሎሌው ሲያገሳ የጊዮርጊስ አንበሳ ሎሌው ሲያገሳ (የፍስሃ ባሪያው እናት ናቸው የሚያወራርዱት መንደርተኛው ይቀበላቸዋል) ሎሌው ሲያገሳ (መንደርተኛው )

ሎሌው ሲያገሳ ድንገት ዞር ስል የመጨረሻዋን "ሲያገሳ" እማማ እሩቅያ እናቴ ጎን ቁመው ሲቀበሉ አየኋቸው "ሲያገሳ" አመንኳቸው!! አንበሳው ሲያገሳ ባላየውም እማማ ሩቅያን አመንኳቸው አንበሳ ግቢ ካሉት አንበሶች ለጥምቀት ተብሎ የጊዮርጊስን ታቦት እየተከተለ የሚያገሳ አንበሳ ያለ መሰለኝ ሰው ጋርዶኝ ነው እንጅ መኖር አለበት !!

***** ****** ********

አንድ ቀን እሁድ ወደሶስት ሰአት ግድም በደቡብ በኩል ከማሪያም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያልተለመደ ድምፅ መንደርተኛው ሰማ ! የመንደሩ ህፃናት ያልሸመደድነው መዝሙር !! እናም ከልጅነት እስከእውቀት የእግዜር ቁጣ (እናቴ ናት ያአችው) ተሰምቶ የማያውቅ ጉድ "ሸላላባሳ ወገኖቸ ጌታ ጌታ ነው አሜ ን!!(በህብረት)የገደል ማሚቱ ጊዮርጊስ ላይ ነጥሮ ይመለሳል!! ሃሌ ሉ ያ አሜን!

የሙዚቃ መሳሪያው ድምፅ እና የሚስረቀረቅ የህብረት መዝሙር (የሴቶች ድምፅ ጎልቶ የሚሰማበት) የማሪያምን ቅዳሴ ዋጠው !! ወዲያው ዘሩ የሚባለው ልጅ "ከማሪያም ቤተ ክርስቲያን ዝቅ ብሎ የሚገኘውን ድሮ የወተት መሸጫ የነበረና ታሽጎ የቆየ አዳራሽ ጴንጤወች ገዝተው ቤተ ክርስቲያን አደረጉት " ብሎ ለእናቴ ነገራት !! ወደእኔ ዞር አለችና በብስጭት "ሂድ ወደዛ ምን ጆሮህን አቁመህ የትልቅ ሰው ወግ ትሰማለህ አንተ ና እንሂድ ቢሉህም ትሄዳለህ " አለች በጣም ተበሳጭታ ነበር !!(መጥራት ጀምረዋል እንዴ)

የዛን ሰሞን የመንደሩ ህፃናት ከባድ ማስጠንቀቂያ ተሰጠን አሴማ ቋሚ ስራዋ አድርጋ ያዘችው አብርሃም !(ሙሉ ስሜን የምትጠራኝ መረረር ያለ ጉዳይ ሲኖር ነው ! በሰላሙ ቀን አብቹ አብርየ ነው የምትለኝ) አቤት አሴ (በሰላም ቢሆን በሰላም ባይሆን ለእኔ ግን አሴ አሴ ናት!) "ትምህርት ቤት የምትሄደው በየት ነው " "በወተት ቤቱ ነዋ ታውቂው የለ" "ለሞላ ምልክት ምን ዘሎ ወተት ቤቱን አስጠራህ እየው (አመልካች ጣቷን አይኔ ላይ ቀስራእየነቀነቀች ) ከአሁን በኋላ ትምህርት ቤት ስትሄድ ስትሄድ በጋሽ አሰፋ ቤት አድርገህ በታች በወንዙ በኩል ሂድ በዛች በወተት ቤት በኩል ተሳስተህ ብታልፍ ስጋህን ነው የምዘለዝለው እመቤቴ አትለመነኝ !!" ትለኛለች "እንዴ አሴ! በወንዙ ስሄድ ስንት ቀን ገርፈሽኝ የለ እንዴ ደግሞ "ወንዙ ሰይጣን አለው በዛ የሚያልፉትን ስቦ ይበላቸዋል" አላልሽም እራስሽ " እላታለሁ። በወንዙ በኩል እንዳንሄድ ከባድ ማስጠንቀቂያ ይሰጠን ነበር በፊት!! "እሱማ አዎ ምን እዳ ነው በዛ በዚህ ሰይጣን " ብላ ግራ በተጋባ ሁኔታ ፀጉሯን መንጨር መንጨር ታደርጋለች (ወንዙ ብሱ ሰው ወስዷል ) ከዛም ሻሻን አጥብቃ ታስር እና " እሽ ማለፉን እለፍ ግን እዛ ስትደርስ ወደውስጥ እንዳታይ ቶሎ እልፍ አንድ ነገር ብላ ቢሉህ ኳስ እንስጥህ ቢሉህ ማሙሽ ጎበዝ ይጣፍጣል ከረሜላ ምናምን እንካ ቅመሰው ቢሉህ እንዳትነካ! ወዲያው ተቀይረህ እንቁራሪት ነው የምትሆነው " "ከረሜላ ይሰጣሉ እንዴ " እላታለሁ ካለችው ሁሉ እችን ነው የሰማሁት

"ማን ይሰጣሉ አለህ አልኩ ወጣኝ ኧረ ተው ተው አብርሽ ከልብህ ሁን ወቸ ጉድ!! እንዴት ያለ አጣብቂኝ ውስጥ ገባሁ ዘንድሮ " ትላለች በምሬት እንባ ሁሉ እየተናነቃት አሴ ከምር ተጨንቃ ነበር  ግን እነዚህ የሚዘምሩ ከረሜላ የሚሰጡ ደግሞ አሴን የሚያስጨንቁ ጴንጤዎች ምንድናቸው " ለማየት ፈለኩ !! በጣም ጓጓሁ !! ግን አሴ እንዳለችው ወደእንቁራሪት ቢቀይሩኝስ

የሰፈር ልጆች ጋር ስናወራ ዳንኤል "ኧረ ወደንቁራሪት አይደለም ወደውሻ ነው የሚቀይሩት " አለ ታምሩ ወደእባብ ነው ቶሎሳ ወደ ጅብ ነው እናቴ ነግራኛለች አለ ይሄ ሁሉ ልጅ ወደእንቁራሪት ወደ ውሻ እና እባብነት ሲቀየር ታየኝ ቢሆንም ግን ወተት ቤቱን ለማየት ሁላችንም ፈልገን ነበር  "ለምን ቀስ ብለን በአጥሩ ተንጠላጥለን አናያቸውም ? " አለ አሸናፊ (የቡድናችን በረኛ ነው) እርስ በእርስ ተያየን አንዱ ለቤተሰቦቻችን እንዳይናገርና ጉድ እንዳይፈላ ፈርተን !! ተያየን ተያየንና ከት ብለን ሳቅን " ግን አንድ ሰው ለማንም እንዳይናገር " አልኩ እኔ በማስጠንቀቅ እኔ አልናገርም እኔም እኔም እሽ እንማማል እጃችንን አነባብረን " ማሪያምን ላልናገር " "አንተ ዳኒ በደንብ አላልክም ጭክ ብለህ ማሪያምን በል " ይምላል ዳኒ ላንቃው እስኪሰነጠቅ ጩሆ!! "ደግሞ አንተ ኡስማን ማሪያምን ትላለህ መሸወድህ ነው ወላሂ በል ወላሂ አልናገርም!! "ግን ሰይጣኑስ " አልኩ እየፈራሁ "ባክህ ወንዛ

እየተደበቅን ስንሄድ መቸ ይዞን ያውቃል በስማም ብለን እንሄዳለን ኡስማን “ቆይ ጠብቁኝ ብሎ “ ወደቤቱ ሩጦ ትንሽ ከመዳፍ የምታንስ ቁርአን ደብቆ አመጣ “በቃ ይሄ ሾይጣን ይከላከላል ” “ የቡድናችን አምበል ይያዘው “ እንላለን “ ኡዱ ያላደረገ ሰው አይነካውም እራሴ እይዘዋለሁ “ ይላል ኡስማን ተስማምተን ማንም ሳያየን ወደወተት ቤቱ ጉዞ ጀመርን

ሃሌ ሉ ያ! ድምፃቸው እያስፈራን ቀረብን ፀጥ ብለው ቆይተው በህብረት “አሜ ን!” ብለው ሲጮሁ ወደኋላ ተበታትነን ድንጋጤያችን ሲለቀን እንደገና እንመለሳለን ! ከዛም ቀስ ብለን እንጠጋለን ጣ ጋ ጣ ጋ ” “አሜ ን እልልልልልልል ብትንትንትትትን ቀስ ብለን እንደገና ቀስ ቀ ስ ቀ ስ “ኮሽ” ድንግጥ!! ኤጭ ! ድመት ናት አልፋን ሄደች ጠ ጋ

# ክፍል 3

“ሩቂ “ አለች እናቴ “ለባይከ” አጃክሱን ሁሉ ምን በላው ? “እኔ ምን አውቃለሁ ጓዳውን የከረምሽበት አንቸው “ አሉና ሁለቱም ተሳሳቁ! እኔም ባይገባኝም ሳኩ ባይገባኝስ እማማ ሩቅያ ከሳቁ እስቃለሁ!! እናቴ የራሷ እጅ እንዳይነካት ተጠንቅቃ አጃክስ ፍለጋዋን ቀጠለች እማማ እሩቅያ ጓዳ ውስጥ!! ረመዳን ከገባ ሁለት ሳምንት ሁኖት ነበር ። ሰራተኛቸው "አባትሽ በጠና ታሟል" ተብላ ገጠር ስለሄደች የእማማ ሩቅያን ማፍጠሪያ የምትሰራላቸው እናቴ ነበረች ከስር ከስሯ እየተከተልኩ አያታለሁ “ሂድ እስቲ ወደዛ እንደ ሴት ጓዳ ለጓዳ ” ትለኛለች የትም አልሄድም እሷም እንድሄድ አትፈልግም ማን ይላላካታል ? ከሽን ያለ የበግ ቀይ ወጥ አጥንቶቹ ብቅ ጥልቅ ሲሉ ምራቄ በአፌ ይሞላል አሴ አንዴ እንኳን ተሳስታ አለመቅመሷ ይገርመኛል ዱለት እና አልጫ ከድንች ጋር ደግሞ በረዶ የመሰለ ሩዝ “የእስላም ስጋ “ ስለሆነ ልብሷን እንዳይነካባት ከእማማ ሩቅያ ቢጃማ አንዱን በልብሷ ላይ ደርባ ነበር የምትሰራው ኩሽናው ግን በወጡ ጠረን ታፍኗል አጃክሱን ፈልጋ ስላጣችው “አቡቹ “ ትለኛለች ድንገት “እ” እላታለሁ አይኔን ከስጋ ወጡ ላይ ሳልነቅል አንድ ትልቅ ቅልጥም እረጋ ብሎ ቀይ ባህሩን ሰንጥቆ ወደላይ ወጣና መልሶ ገባ አ አፈፍ ማድረግ ነበር !

“እ ማለት ምንድን ነው አቤት አትልም በስርአት “ “እህ አልኩሽ አይደል እንዴ “ ጭቅጭቋ ይሰለቸኛል (የጎድን አጥንት ተንሳፈፈ)

“ግዴለም እሱን በኋላ እንነጋገራለን አሁን ለንቦጭህን መጣሉን ተወውና እቤት ሂደህ መስኮቱ ላይ በውጭ በኩል ቁራጭ አጃክስ አለችልህ አምጣልኝ “ ወደቤት ሮጣለሁ “የእስላም ስጋ ግን ምን ምን ይላል ? ሽታው ግን ይጣፍጣል ” እያልኩ ! አጃክሱን አላገኘውም "ለምንድነው ስጋ እና ሩዝ በአንድ ላይ የሚሰሩት ?" “አ ሴ” ጮክ ብየ እጠራታለሁ “ወ ይ” “የለም አጣሁት ”

“ኤጭ ድሮም አንተን እቃ ፈልግ ማለት ደንባራ “ ትልና እራሷ ልትፈልግ ትመጣለች..ምንም ሳትፈልግ ወዲያው ታገኘዋለች ፊት ለፊቴ (እንዴት አላየሁትም)

“ይሄ ምንድን ነው? ቀልበ ቢስ! በዚህ ቀልብህ መስኮቱም ይጠፋሃል አንተ “ ትለኝና ወደማማ ሩቅያ ቤት ስትሄድ መምሬ ይፍሩ ጋር ግጥምጥም!! ጉድ ፈላ! የንስሃ አባቷ ናቸው

“ ወለተ ማሪያም ደሞ ዛሬ ምን ለበሰሻል ? “ ይላሉ አሴ የለበሰችውን ቢጃማ እያዩ ነጠላ ስትለብስ ብቻ ነው ፊታቸው ፈገግ የሚለው

ዝም ብላ አንገቷን ለመሳለም ታሰጋለች ሁለት እጆቿን ወደኋላ ታደርግና (እጆቿ ከመምሬ የተደበቁ እስላሞች ) እንግዲህ ሮብ ነው መመሬ ሊያሳልሙ ጠጋ ሲሏት ስጋ ስጋ ትሸታቸዋለች ከነቅመሙ ከሽን ያለ ቀይ ወጥ “ምነው ወለተ ምን ሰይጣን ቤትሽ ገባ ያውም በሮቡ “ “ኧረ ” ትላለች ምን ትበላቸው “አ ይ ይሄ እግዜርን በንጨት መውጋት ነው ለዚህ አንድ ፍሬ ልጅ ምን ታስተምሪዋለሽ ” ወደኔ በብረት መስቀላቸው እየጠቆሙ

እኔን ሊያሳልሙ ጠጋ ሲሉ ማተቤ አንገቴ ላይ የለም በየሳምንቱ ቢያስሩልኝም በየሳምንቱ ይበጠስብኛል ከኪሳቸው በስርአት የተጠቀለለ ኩል የመሰለ( ከርቤ ከርቤ የሚሸት) ክር ያወጡና በልኬ ተርትረው አንገቴ ላይ ሊያስሩልኝ ጎንበስ ሲሉ የእኔም ጠረን ስጋ ስጋ እኔም ክሽን ያለ ቀይ ወጥ !! መምሬ ራሳቸውን በማዘን እየነቀነቁ ያስሩልኝና የሚደግሙትን ነገር ይደግማሉ!! አሴ ከፊት እኔ በመጠኑ ከኋላ የመምሬን ቡራኬ እየተቀበልን እንዳቀረቀርን ቀስ ብየ አያታለሁ አዲሷ ማተቤ ጋር እየተጫወትኩ በቀኝ እጁ የአጃክስ ቁራጭ እንደያዘች ልቧ ላይ የታተመውን ፍቅር በዘላለማዊ ጉርብትና አፅንታ ከእጇ ላይ ስለፍቅር መተላለፏን ልታጥብ እማማ ሩቅያስ ለፋሲካ የእኛን ዶሮ ሲገነጥሉ አምሽተው ይሄንኑ አልነበር የሚያደርጉት !

***** ***** *****

የመንደራችን ደብሮች ሁሉ ጴንጤወች መጡ ከተባለ በኋላ የጌታን ምሳሌ የድንግል ማሪያምን ገድል ማስተማር እየቀነሱ ስብከታቸው ጠንከር እያለ መጣ መናፍቅ የምትለው ቃል ከዛ ከዚህ መወርወር ጀመረች ቄጥሮች በረከቱ ይኋንስ ወንጌል ምራፍ ቁጥር ወየውልሽ ቃሉን የምትቀንሽ የምትጨምሪ ወዮልሽ ተአምር አይተሽ የምትከተይ እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ ቡችሎች እግር ስር የከበረ እንቁ አታስቀምጡ (አቤት መፀሀፉን እናድንበት ካሉ ሲጠበቡበት እንሳደብበት ካሉም ሲጠቡብት ቀበቶ! በሂሊናቸው ወገብ ልክ አስተካክለው ሽብ ያደርጉታል ምን ችግር ሽ ሽንቁር አለው ) በመጨረሻው ዘመን "እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ መናፍቅ እናቱን የናቀ ልጇን ናቀ ወዘተ ኦርቶዶክስ ልክ እንደአሴ ስለልጇቿ ተጨነቀች! ወንዙ ሰይጣን ወተት ቤቱ ሰይጣን ልትል ምንም አልቀራት!! መምሬ ይፍሩ በፊት በወር ብቅ የማይሉት ንስሃ አባት በቀን ሁለት ጊዜ ሁሉ ይጎበኙን ጀመር(እንደሳቸው አባባል መንጋውን ከተኩላ ለማዳን) ታዲያ እናቴ ጋር የሚያወሩት ስለጴንጤወቹ ክፋት ፣መናፍቅነትና ከሃዲነት ነው አንድ ቀን እኔ ቁጭ ያልኩበት " ወለተ ማሪያም ራቁታቸውን መሬት ላይ እየተንፈራፈሩ ሲያለቅሱ እኮ ነው የሚውሉት " አሉ "በስ ማም " አለች አሴ እያማተበች "ኧረ አንድ አይነት ቀይ ቀሚስ ለብሰው ተሰልፈው ነው የሚዘምሩት " ካልኩ በኋላ አፌን በእጆቸ ጥርቅም አድርጌ ወደእማማ ሩቅያ ቤት በረርኩ አሴ ባንዴ ፊቷ ወረቀት መሰለ እማማ ሩቅያ ጥገኝነት ጥያቄየን ባለመቀበል አሳልፈው የሰጡብኝ ብቸኛ ቀን ያ ቀን ሆነ !! ግን ለአሴ አልነበረም ለመምሬ ይፍሩ!!

እጀን ታስሬ ሰባት ቀን ትምህርት ቤት ሳልሄድ ተጠመኩ ጎረቤቱ ሁሉ እንደሃዘን እናቴን እየመጣ ይጠይቃት ጀመር ! ሚስጥራችንን ባላወጣም በጥርጣሬ የመንደሩ ልጅ ሲወገር ከረመ ወተት ቤቱ ሂደን በአጥር ተንጠላጥለን ያየናትን ሁሉ ቀስ በቀስ ተናገርን ወደአጥሩ ቀርበን ተንጠላጠልን ቀይ ዘርፋፋ ቀሚስ የለበሱ ዘማሪወች ተሰልፈው ኦርጋኑ ድምፅ ጋር እኩል እየተንቀሳቀሱ ይዘምራሉ በየመሃሉ ሙሉ ልብስ የለበሰ መላጣ ሰውየ የመዝሙሩን የመጀመሪያ ቃል ጮክ ብሎ ይናገራል ይከተሉታል ህዝቡ በመደዳ በተሰደሩ ወንበሮች ተቀምጦ እጁን ወደላይ ከፍ እያረገ እልል ይላል መዝሙሩ አልቆ ሰባኪው መናገር ሲጀምር እንዲህ አለ

" ህፃናትን ወደእኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው ህፃናትን ወደዚህ እጠራለሁ ኑ ኑ ኑ ይፀለይላችሁ የእግዚያብሄር ስጦታወች ናችሁ እግዚአብሄር እነዚህን ህፃናት ስለሰጠኸን እናመሰግናለን ህፃናት ኑ ወደዚህ አገልጋዮች ህፃናትን አምጧቸው ኑ ኑ ኑ "

እኛን መስሎን ከአጥሩ ላይ እየዘለልን ወደሰፈራችን ተፈተለክን "እውነትም ሰይጣን አላቸው እንዴት አዩን ".(ሃሃሃሃሃሃሃሃ አስባለን ስናድግ) በኋላ ስንሰማ በየሳምንቱ ስብከት ከመጀመሩ በፊት የራሳቸውን ልጆች ወደመድረኩ ጠርተው ይፀልዩላቸው ነበር አሉ!! የመንደሩ ልጅ ሁሉ ይሄን በማየቱ ተጠመቀ

ቀስ በቀስ ግን አዛኑም የማሪያም መዝሙራችንም ለጴንጤወቹ መዝሙር ቦታቸውን እየለቀቁ ከልጅነት ልባችን ውስጥ ይደበዝዙ ጀመር በተለይ " ጳውሎስና ሲላስ " የሚለውን መዝሙር ከአፋችን ላይ የሚያጠፋ ሃይል ጠፋ አንዳንዴማ አሴ ፊት ሳይቀረ ያመልጠኛል

"ምንድነው የምታጉረመርመው አንተ "

"ምንም !! " አንድ ደይቃ እንፋጠጣለን

*** *** **** ****

እሽክም እሽክም እሽክም

አንድ ቀን እማማ ሩቅያ እና አሴ ቡና እየጠጡ እኔ የሌለሁ መስሏቸው ሲያወሩ መስኮቱ ስር ሁኘ ሰማኋቸው

እማ ሩቅያ እየሳቁ አንዲህ አሉ " አሰለፍየ እንደው እነዚህ ሚንጤወች እሽክም እሽክም እሽክም ሲሉ ይሄ ታምቡሩና ምናምኑን ሲያስጎሩት እንኳን ለልጆቹ አዋቂም ይነሽጣል ወላሂ ሁሁሁሁሁሁ ወደው አይስቁ አሉ " አብረው በሳቅ ፍርስስስስ አሉና አሴ "ሰይጣኑ እኮ ነው" አለች

አንድ እሁድ ቀን ጧት አሴ በረንዳ ላይ ተቀምጣ ድንች እየላጠች ነበር ከጴንጤወቹ "ቸርች" "ገናናው የእኛ ኢየሱስ " የሚለው ሞቅ ያለ መዝሙር ሲዘመር ሪትሙን ተከትላ በእግሯ መሬቱን ተም ተም ተም ስታደርግ አየኋት እሽክም እሽክም እሽክም ሴጣኑ አስየን እናቴን ነሸጣት !!

ምስክር 1

ጥቁር መፀሃፍ ይዘው በመንደራችን የሚወጡትና የሚወርዱት ጴንጤወች እየተሳሳቁና እያወሩ አንድ አረፍተ ነገር በተናገሩ ቁጥር "ጌታ ምስክሬ ነው" እየተባባሉ ሲያልፉ እማማ ሩቅያ ሰሙና "እዚህ ላይ የተከፈተው የሜንጤ መስጊድ ነው ወይስ ፍርድ ቤት" ብለው ጠየቁ "ሃዲያ ሲገቡ ሲወጡ ምስክር የሚቆጥሩት ምንድን ነው" ቃል በቃል ሩቁ እንዲህ አሉ !!

ምስክር 2

ኳስ ስንጫወት በረኛችን "ፎራ" ነው ብሎ ታምሩ ያስገባው ግብ ላይ አፈረ ግብ ነው አይደለም ስንባባል በረኛችን ድንገት "ጌታ ምስክሬ ነው ግብ አይደለም " አለ!! ተገርመን ደንግጠንም አየነው ግብ ሳይሆን ቀረ!!

ማንነቱን ያላወቅነው ምስክር ጋር መሳፈጥ ፈርተን!! ግብ ይሁን አልን!! (ዛሬ በረኛችን አሹ ፓስተር አሸናፊ ሁኖ ምስክርነቱ በሲዲና ዲቪዲ ሳይቀር ተሰራጭቷል ኳስ ማጥመዳችሁን ተውና ተከተሉኝ ሰው ማጥመድን አስተምራችኋለሁ ይላል ስለኳስ የሚያወሩትን ወጣቶች ሲሰብክ )

አንድ ቀን አሴ "ዛፉ ሙዚቃ ቤት ሂድና ቆንጆ የባህል ዘፈን ካሴት ገዝተህ ና "የማይረባ ከሆነ ትመልሳታለህ" ብላ ድፍን አስር ብር ሰጠችኝ እንደነገ አዲስ አመት ሊገባ ነበር ወደዛፉ ሙዚቃ ቤት ታምሩ ጋር ሁነን ሄድን ዛፉ ከመደርደሪያው ኋላ ተቀምጦ መፅኃፍ ቅዱስ ያነባል የጴንጤ መዝሙር ድምፁ ዝቅ ተደርጎ ተከፍቷል "ከዚህም የሚበልጥ የጌታ ሃይል ሲገለጥ " የሚል መዝሙር በጊታር የታጀበ "የባህል ዘፈን አለህ ዛፍሻ ?" አልኩት እረጋ ብሎ "ዘፈን መሸጥ አቁሚያለሁ " አለ እና ወደንባቡ ተመለሰ ጎንበስ ሲል መሃል አናቱ ላይ ሸበት የቀላቀለበት ፀጉሩ ላይ አይኔ አረፈ መደርደሪያው ላይ ግማሹ ከተለጠፈበት የለቀቀ የባህሩ ቃኘ የቆየ ምስል ተንጠልጥሏል ትዝ አለኝ የባህሩ ዘፈን ስናልፍ ሰናገድም እንሰማው የነበረው እዚሁ ሙዚቃ ቤት

ታከመው ይሉኛል እንግዲህ ምኑን እንደተወጋሁት የቀረሁትን

አደግን

ውጭ አገር ቆይቶ ከብዙ ጊዜ በኋላ ስመለስ ትንሽ እህቴ ሮዛ ቀንደኛ የጴንጤ ሰባኪ ሁና ላላፊ አግዳሚው የቃል መንጠቆዋን እየወረወረች ጠበቀችኝ ዘመን እናቴ አሴን አለዝቧት ዝምታን መርጣለች

የእማማ ሩቅያ የልጅ ልጅ ዘይንያ ከላይ እስከታች ጥቁር ሂጃብ ለብሳ "ዝንፍ የማትል" ሃይማኖተኛ ሁናለች አይ ዘይኒ እቃቃ ስንጫወት ሚስቴ ነበረች ላፕቶፔን ይዤ አንድ ጥግ ቁጭ ብያለሁ እማማ ሩቅያ ዘመን የማይሽራት የፍራሽ ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠዋል ከነመቁጠሪያቸው!!

አሴ ከጀበናው ኋላ እጣኑ ቡልቅ እያለ እህቴ ሮዛ ጆሯ ላይ በሰካችው ማዳመጫ መዝሙር እያዳመጠች አይኗን ታስለመልማለች ዘይንያ ሶፋው ላይ ተቀምጣ አልፎ አልፎ አይናችን እየተጋጨ ቁጭ ብላለች ዝም ብየ ሳስበው ምኔም ከአሜሪካ የመጣ ሰው አይመስልም!!

እማማ ሩቅያ የፊታቸው ቆዳ ሰብሰብ ብሏል አሴ የሚበዛው ፀጉሯ ነጭ ለብሷል በቅርብ የሰራናትን ሰረቢስ ቤት የተከራየ አየለ የሚባል የቀበሌ ካድሬ ሲለው ሃይማኖት ውስጥ ዘሎ የሚዘፈቅ ማቶ.. ቡናው ላይ ታድሟል የፍቅር ድግሳችን ላይ ጉብ ብሏል አብሮንታችን ውስጥ ተሰንቅሯል እህቴ ሮዛ የእጣኑ ጭስ አልተመቻትም የከፉ አሰራር በእጣን ጭስ ውስጥ መኖር ይመቻዋል ባይ ናት (ከፉ ከፉውን የሚያሳይ ነገር ተጠናውቷታል) እማማ ሩቅያ መረቁ ልጆቻችንን ሰብስቦ በሰላም ለመተየየት ያበቃን አላህ ቀሪወቹንም ለአገራቸው ያብቃልን አሜን ! እንጨጭ እህቴ "አገራችን በሰማይ ነው" ብላ አጉረመረመች "

ሰበብ ፈልጋ መንጠቆዋን ልትወረውር ዳር ዳር እያለች እንዳቆበቆበችው ሃሳቤ ወደምሰራው ስራ ሄደት ብሎ ባልሰማሁት መነሻ የቀለጠ የሃይማኖት ክርክር ተነሳ ተከራዩ አየለ ኦርቶዶክስን ወከልኩ ብሎ ደም ስሩ እስኪገታተር እህቴ ጋር በቃል ይናረቱ ጀመር

ዘይንያ አልፎ አልፎ ጣል የምታደርገው ሃሳብ ነዳጅ ሁኖ የፍቅር ቡናችን  የግልብ ወጣቶች መነታረኪያ ማእድ አስርጎት ቁጭ አለ መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የተሰጠን መአበል ዝም ያስባለ ሙታንን ከነከፈኑ ያስነሳ ክርስቶስ (ፉከራ በሚመስል ድምፅ) እማማ ሩቅያ "እሳቸው መጀን አሰለፈች አጭሽበት እስቲ እኒህ ልጆች እንደው የሚጠሩት ነብዩ ኢሳን እኮ ነው " ይላሉ ከልባቸው አሴ እጣኑን ቡን ታደርገዋለች እህቴ ብስጭት !! አየለ ይቀጥላል ከእመቤቴ ቅድስት ብፅእት ድንግል ማሪያም ስጋ ነስቶ ሲሰቀል እናቴ አቻትልህ ያለው ለይኋንስ ብቻ አይደለም ለአለም ነው ያለሷ አማላጅነት አለም አይድንም ኧረ እንዴት ሁኖ " አሰለፈች አጭሽበት እናታችን መሬምን እኮ ነው እንዲህ ቅልል አድርገው የሚጠሯት አጭሽበት " ይላሉ መቁጠሪያቸውን እያንኳኩ አሴ ታቦናዋለች " አ ማ ጋድ ማሚ ምን እየሰራሽ ነው ይሄን ጭሳጭስሽን ወደዛ በይ ባክሽ " እህቴ አሴን እያመናጨቀች ትቀጥላለች ክርስቶስ ይመጣል ያኔ እንክርዳድና ፍሬውን በእሳት መንሽ ይለያል ቻፕስቲክ የተለደፈበት አፏ ሲያሞጠሙጥ መንሽ ይመስላል

እነዚህ ልጆች ስለሃይማኖት እየተከራከሩ ስለመሆኑ እስኪገርመኝ እልህና ፅንፍ የሌለው ጥላቻ ፊታቸው ላይ ይንቀለቀላል ቢመቻቸው መፅሃፍ ቅዱሳቸውን ወርውረው ክላሽ ከመማዘዝ የማይመለሱ የጨለማ ልጆች እልቂት በሚያውጅ የጥላቻ ፊታቸው ስለመዳን ይደሰኩራሉ

እማማ ሩቅያና አሴ አንቀፅ ሳይጠቀሱ ምእራፍ ሳያነበንቡ ለዘመናት በስራ ይዘውት የኖሩት ፍቅር አብሮ መኖር አፍ ላይ ተሸምንሙኖ ቃል ብቻ ሲሆን ተመልከቱ እነዚህ ግልብ የቃል ቀበኞች ባልተፈወሰ አንደበት ስለፈውስ እየተንኳኩ ነው አንቀፃቸው ውስጥ ራስ ወዳድነታቸውን እየቀበሩ ነው እርስ በእርስ ለመስማማት እንኳን ቁራጭ ትእግስት የሌላቸው ወንጌል ስለመስማት ያወራሉ

ሰለቹኝ አቅለሸለሹኝ አፋቸው ኤርታሌ የጥላቻ እሳት የሚንተከተክበት ጥልቅ ነው ሂሊናቸው ሃይማኖተኝነት የገዘፈበት ፍቅር በአብሮነት ጠኔ በመከባበር እርሃብ በመደማመጥ ውሃ ጥም የሞተበት ጨለማ መቃብር !! በሌላ የሃይማኖት መም የሚሮጠውን ወደራሳቸው መም ጎትቶ ማስገባት እንጅ በራሳቸው መም ስር ስለወደቁ ሚስኪኖች ቁራጭ ርህራሄ የላቸውም አቦል እስኪጠጣ እንኳን ፍቅራቸው አይቆይም ወደስድድብና መናናቅ ለመግባት አፍታ አልቆዩም ኤጭጭጭጭ!!

አጭሽበት አሴ የኔ የፍቅር ቆሌ አሜን በሉ እማማ ሩቅያ የኔ የመቻቻል አድባር

ክርስቶስ በወንዙ በኩል ወደሰፈራችን ይመጣል !! ወንዙ ውስጥ ያለውን ሰይጣን እዛው ደፍቆት ሌጌዎንን በመደዳ አስር አስር ዝልጦ ይመጣል ክርስቶስ ሽቅብ ወደኛ ቤት የደሃ ልብስ ለብሶ ተራ ሰው መስሎ ይመጣል ማንም ቤት አይገባም ሁልጊዜ እየመጡ እንደሚመፀወቱት የኔ ቢጤዎች አሴና እማማ ሩቅያ ቡና ሊጠጡ ሲዘጋጁ ከተፍ ይላል

ግባ ይሉታል አሴና እማማ ሩቅያ ትራፊ አይሰጡትም ሞሰባቸውን ከፍተው ንፁህ እንጀራ በሰሃን ወጥ ባይኖራቸው በርበሬ ነስንሰው ይሰጡታል ግባ ተቀመጥ ቡና ጠጣ ይሉታል ለሁሉም ይሄው ናቸው

ይገባል ክርስቶስ እማማ ሩቅያ አገር አማን ይሁን ሲሉ ይሁን ይላል አብሮ ልጆቻችን ሰላም ይሁኑ ሲሉ ይሁን ይላል አብሮ የታመሙት ይዳኑ ሲሉ ይሁን ይላል አብሮ ይሁን ያለው ሁሉ ወዲያው እየሆነ እንደሆነ አሴና እማማ ሩቅያ አያውቁም አቦል ላይ ደረስከ "ሆድህ ንፁህ ነው" ይሉታል እማማ ሩቁ ክርስቶስ ሆዳቸውን እያየ የራሳችሁን ባያችሁት ይላል በሆዱ አቦሉን ያቀብሉታል ክርስቶስ ደስ ብሎት ይቀበላቸዋል አንዴ ፉት ብሎ " ግሩም ቡና ናት ትንሽ ስኳር አንሷል" ይላታል አሴን ብድግ ብላ ስኳር ትጨምርለታለች

ክርስቶስ ግን ስለማጀቷ አውርቷልና ማጀቷ ሙሉ ይሆን ዘንድ በዛች ሰአት መለአክቱን አዟል ስለአገር አውርቷልና የስኳር እጥረቱን በአሴና በእማማ እሩቅያ ደግነት ከአገር ነቅሎታል በምድር እንዲደላቸው ለእማማ ሩቅያና ለአሴ አምሳ አምሳ አመት መርቆላቸው ጥግ ጋር ወደተቀመጥኩት እኔ ያያል ላፕቶፔን ቫይረስ አጨናንቋት ስማረር ፈገግ ብሎ ይሁን ይላል በምድር ላይ ለዘላለም ቫይረስ የማያጠቃት ላፕ ቶፕ ያለኝ ብቸኛ ሰው እኔ ብቻ እሆናለሁ ክርስቶስየ እህቴ ቤዛ እሱ ጎኗ ተቀምጦ ፍሊጋ ስትባዝን አይቶ ይገረምባታል

በካድሬው አየለ የዋህነት ያዝናል(አየለ ሞኙ ሰው አማኙ አትቀላቅል እንደማለት ) የእማማ ሩቅያ የሶላት ሰአት ሳይደርስ በፊት አመስግኖ ይወጣል ከለበሰው ድሪቶ ብርሃን ይፈነጥቃል ግርማ ሞገሱ እዚች ምድር ላይ ታዳጊ ክንዱ ስራ ላይ እንደሆነች ሹክ ይላል ህዝቤ ሃብቴ ነው ታዳጊው እኔ ነኝ የሚል አንዳች መልእክት ከእርምጃው

"ሩቁ ይሄ ሰው አዲስ አልሆነብኝም እንደው የት እንደማውቀው ጠፍቶብኝ ነው እንጅ ትላለች አሴ " "ወላሂ ልናገር ስል ከአፌ ቀለብሽኝ እኔም አውቀዋለሁ " ይሉና ወደአሴ በግርምት እየተመለከቱ " አሃ ነይ እስቲ ወዲህ አይኔ ነው ወይስ ፀጉርሽን ጥቁር ቀለም ተቀብተሻል? " ይላሉ አሴ መስተዋት ታነሳለች አንዲትም ሽበት የለባትም ሃያ አመት ቀንሶላት ሂዷል እማማ ሩቅያ ቀስ ብለው ክንብንባቸውን ይገልጣሉ ሽበት የለም ለግልጡም በግልጥ ለሽፍኑም በሽፍንፍኑ የበጎነት ዋጋው አይቀር መከፈሉ!! እሽክም እሽክም እየው ሲነሽጠን የሂወት ዜማ ወየውልሽን የጎሪጥ እያየን ጥራ!! የመንደራችንን ታወቂ አዝማሪ ጣሴን !! አሴ ነጭ ልብሷን እማማ ሩቅያ ሽንሽን ቀሚሳቸውን ለብሰው ጎረቤቱ ተሰብስቦ

የመጣውም መጣ የሄደውም ሄደ የምን መናቆር ነው እድሜ እየነጎደ

ድሮማ በፍቅር ይጠጣ ነበረ ድሮማ ባንድ ላይ ይበላ ነበር ከፊለቴር ተቀድቶ ፉት ይባል ነበረ ከጠጁም ተቀድቶ ፉት የባል ነበር ዛሬስ መበተኛው ነገር ሁኖ ቀረ

ተቀበል ይሉታል እማማ ሩቅያ ፀሃይ ወጣ ሲሉት ደሞ ያዘቀዝቃል እድሜም ካንዱ ሲሸሽ አንዱ ቤት ይዘልቃል አብሮ መብላት እንጅ ቀባሪን ማን ያውቃል (ድገመው) ቀባሪን ማን ያውቃል ቀባሪን ማን ያውቃል ቀባሪን ማን ያውቃል

አጭሽበት አሴ የኔ የፍቅር ቆሌ ይመርቁን አማማ ሩቁ የአብሮነት አድባር የመቻቻል ነብይ አጭሽበት ቡ ልቅልቅ ልቅልቅ ጫፉ የግዜርን እግር የሚነካ ጭስ ከፍንጃሉ ወላ ከተወጋ ሚስኪን ልብ

"ወየውልሽ ዘፋኝ " ትላለች እህቴ ዜማ ያለው ብሶት ዘፈን የሚመስላት እንጩጭ!! ወየውልሽ የስንቱን ወዮልሽ ያየ ሚስኪን ህዝብ ወዮሉሽ ይፈራ መስሏት ወዮሉሽ

ተቀበል ኧረ እንዴት ነሽ ዛቻ እንዴት ነሽ ወዮልሽ እኛስ እንደምንም እግዜር የሰጠውን ሰው አልችል አይልም እማማ ሩቁ ቀይ ጉንጮች ላይ እንባ አየሁ እንዴ ?

## ተፈፀመ

# ከነፈሰው ጋር

ከአአ ወደ ሰሜን ስትሄዱ ደብረ ሲና የምትባል አገር ላይ ቆሎ የሚሸጡ በርካታ ልጆች አሉ ቆሎውን በትልቅ ቁና ይሞሉና በተለያዩ መስፈሪያወች ለመንገደኛው ይሸጣሉ እነዚህ ልጆች ቋሚ ቦታ የላቸውም አንዱ አውቶብስ ውስጥ ገብተው ለተሳፋሪው ቆሎ እየቸረቸሩ አውቶብሱም እየሄደ ቀጥሎ ያለችው ከተማ ድረስ ይሄዳሉ ከዛ ደግሞ ሌላ የሚመለስ አውቶብስ ውስጥ ውስጥ ይገቡና ቆሏቸውን እየቸረቸሩ ይመለሳሉ በቃ ሲመላለሱ ይውላሉ መድረሻ መነሻ የላቸውም እንደተሳፋሪ አውቶብስ ላይ ይወጣሉ አላማቸው ግን ቆሎ መቸርቸር ብቻ ነው ተሳፋሪው ሰርገኛ ይሁን ሃዘንተኛ ተማሪ ይሁን የሰላም ተጓዥ ግድ አይሰጣቸውም አላማቸው ቆሎ መቸርቸር ነው በቃ!!

አንዳንድ ብሎገሮችና የፌስቡክ ፀሃፍት እንደዛ ይመስሉኛል !! የራሳቸው ሃሳብ የላቸውም መነሻ መድረሻም የላቸውም ለማለት ያህል ብለው የሚሉትን ይላ ሉ አንዱ ያነሳው የሃሳብ አውቶብስ ላይ ተንጠላጥለው ጥቂት ቀናት ስለዛ ጉዳይ ይደሰኩሩና ሌላ ሃሳብ ሲነሳ ተንጠላጥለው ይመለሳሉ ብዙወች የተሳፈሩበት ሃሳብ ላይ ተንጠላጥለው ብዙ ህዝብ ጋር ስለተከራከሩ ስለዘለፉና ሌሎች ሃሳብ ላይ ሃሳብ ያሉትን ትርኪ ሚረኪ ስለደፉ ብዙ ተከታይ ያላቸው ይመስላቸዋል የሃሳብ ቆሎ ቸርቻሪወች በሳቁላቸው ልክ የሚሰፍሩ ከንቱወች !!

እነዚህ ብሎገሮች (ብሎግ እነዚህ ሰወች ላይ ሲደርስ ብልግና ባለገ ብልግልግ አለ የሚል ፍች ያለው ይመስለኛል ) የሚፅፉትን ነገር ሳይ እገረማለሁ! ሰው ከመስከረም አንድ እስኮጳግሜ አምስት ሳይፎርሽ መዋሸትና መባለግ እንዴት ነው የሚችለው አደይ አበባ መስከረም ላይ የፈነዳው በእኛ ምክንያት ነው ሊሉ የሚዳዳቸው ሳይመከሩ መምከር የተጠናወታቸው ደግሞ ፈሪወችና ስጋት የተጠናወታቸው እንኳን አደረሳችሁ ብትሏቸው ምን ማለት ነው ብለው ሙሉ ቀን ጠንጋራ ፍች ሲፈልጉ የሚውሉ አይነት ሰወች ናቸው በፌስ ቡክ ከተማ ከነፈሰው ጋር የሚነፍሱ "የፌስ ቡክ አደገኛ ቦዘኔወች" ፌስቡክን የሰጠአምላክ ከጓደኝነት ማባረሪያውንም ባይሰጠን ምን ይውጠን ነበር !! ሰምታችኋል !!

# ከሚቀበሉ ይልቅ የሚሰጡ ብፁአን ናቸው

“ከሚቀበሉ ይልቅ የሚሰጡ ብፁአን ናቸው” ይላል መፀሃፉ

(እየው እንግዲህ ስብከት መስሎህ ፊትህን ስትጥለው)

(አሌክስ አብርሃም ታክሲ ጥበቃ ተሰልፎ የፃፈው)

ታክሲ ከመጠበቅ በላይ የሰለቸኝ ነገር ታክሲ መስታወት ላይ የሚፃፉ የባለቤትነት ማረጋገጫወችን ማንበብ ነው !! በተለይ ይሄ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚባል “ንብረት ምዝገባ እጀምራለሁ የተመዘገበው ንብረት ምንጩ ከየት እንደሆነም አብጠርጥሬ እመረምራለሁ” ካለ በኋላ ታክሲው ሁሉ የባለስልጣኖች ብቻ የሆነ ይመስል ምንጩ መስታወቱ ላይ በጉልህ እየተፃፈ (ያለበት ሁኔታ ነው ያለው) !! ይሄ የጃፓን ስጦታ “ዶኔትድ ባይ ማንትስ” ከሚሉት መኪኖች በተጨሪ የሃብት ምንጭ !! መንገድ ዳር ላይ ተሰልፋችኋል እንበል (ተረጋጉ የምን መበርገግ ነው ሰልፉ ታክሲ ለመጠበቅ ነው) እና ከታክሲወቹ የኋላ መስተዋት ላይ ምን ታያላችሁ ?

የኪዳነ ምህረት ስጦታ

የድንግልየ ስጦታ

የመድህኑ ስጦታ

የገብርኤል ስጦታ

የሚኪየ ስጦታ (ሚካኤልን ሲሞዳሞዱ)

የጉስቋም ስጦታ

የልደትየ ስጦታ

የአርሴማ ስጦታ

የህፃኑ ቂርቆስ ስጦታ ሁሉ የሚል ታያላችሁ የዚህ አገር ታክሲወች ከጻድቃን ሰማእታት እና ከታቦታት ከሆነ የሚበረከቱት ምናለ መንገድና ትራንስፖርት ለየታቦታቱ በህዝብ ስም በርከት ያሉ ታክሲወችንና አውቶብሶችን ጠይቆ ሰልፉን በቃችሁ ቢለን! እንደው ይሄ ህዝብ መቀበል ስለሚወድ “ስጦታ” እያለ ይለድፍባቸዋል እንጅ እነሱ ታክሲ ሲያድሉ የሚውሉ አይመስለኝም !!እስኪ አሁን ማን ይሙት አለምን የሚያድን ልጅ ያህል ትሰጥ ዘንድ የተመረጠች ቅድስት ብጽእት ድንግል ማሪያም ወንበሩ እንደአነዳንድ የከተማችን ነዋሪ ሴቶች ጥርስ በሽቦ የታሰረ አንድ ትርፍ ሰው ሲጭን ከትራፊክ ፖሊስ ቀድሞ ራሱን የሚያቆም ቸርቸር ጎዳናን ሲወጣ ፒያሳ ከደረስኩ ለጊወርጊስ ጧፍ አስገባለሁ ብሎ ከሞተሩ(ከልቡ ማለቴ ነው) የሚሳል ከርካሳ ሚኒባስ ትሰጣለች ? ስም ማጥፋት ነው (ኧረ መናፍቅነትም ነው ሂሂሂሂ)

አንዳንዱ ደግሞ ከውጭ “የዛሬዋን ቀን ለጨመረልን እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ምናመን “ ብሎ ስትገቡ “ደግሞ ነጋልሽ” የሚል ፅሁፍ ፊት ለፊት ለጥፎ ታገኙታላችሁ የመድህኑ ስጦታ ውስጥ ይሄ ይለጠፋል ?

ቅዱስ ጊወርጊስ አንዲት ብሩክታዊት የተባለች ልጅ ከዘንዶ ያውም ከሚበር አደገኛ ዘንዶ በጦር ወላ በጎራዴ ተፋልሞ ሲያድናት የሚያሳይ “የአዲካን የኮንሰርት ማስታወቀያ ፖስተር” የሚያክል ስእል አገር እንዲያየው የኋላ መስተዋቱ ላይ የለጠፈ ሚኒባስ በብሩክታዊት አምሳል የተፈጠረችውን እህቱን “ጢጋ አልልም” በማለቷ ብቻ በፀያፍ ስድብ ሲያበሻቅጣት ያየ ሰው “እረዳቱ የሚያመልከው ጊዮረጊስን ነው ዘንዶውን” ቢል ይፈረድበታል? !! አንዳንዴማ ይሄ ጉድ ሲፈፀም ጊወርጊስ ጦሩን እንደአይነስውራን ነጭ ብትር አጣትፎ በልብሱ ስር ደብቆ እንደተራ ተሳፋሪ ኋላ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ቢያይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በሃሳብ ትስሉታላችሁ

" አንተ ለምን በስርአት አታናግራትም " ይለዋል ወያላውን

" አንተ ምን አገባህ ያናገርኳት እሷን" ይላል ወያላ አሟሟቴን አሳምረው ማለት አሁን ነው

"አላናገርካትም ሰደብካት እንጅ ደግሞ የግዜር ፍጥረት ናት እናት ናት እህት ናት ማክበር አለብህ"

"ኧረ ሰላም ስጠን ሰውየ ይሄ እኮ ታክሲ ነው ቤ/ክርስቲያን አደረከው ?..ቆይ ጊወርጊስ ስንደርስ እናወርደሃለን እዛው ትሰብካለህ ! ተረጋጋ " ሲያመልጠው

ጊወርጊስ በሳቅ ፍርስስስስ

"ስቀህ ሙተሃል " አይጥ ደላላ የድመት አፍንጫ ሲያሸት

"ወራጅ "ይላል ጊዮርጊስ

"እዚህ አይቆምም " ሹፌር በብስጭት !

" እንኳን ታክሲ ሂወትህ የትና መቸ እንደምትቆም እናውቃለን"

" ንገረና የት እንደምናቆም " ሹፌሩ በስፖኪዩ ጫት ያበለዘው ጥርሱን እያሳየ

" ታክሲህማ ፣የትም አትቆምም አንተ ግን ከነ እረዳትህ " ብሎ ረዳቱ እያየ በጣራው ሹልክ እንደጭስ.. ተሳፋሪው በድንጋጤ እስኪደነዝዝ!! ሙሉ የተባለው ታክሲ ውስጥ ጊዮርጊስና የተሰደበችው ልጅ ቦታ ባዶ!! ሹፌር ደንግጦ ፍሬን ቢይዝ ወይ መቆም ጭራሽ ታክሲዋ ወደፊት ተወረወረች ተመነጠቀች!! ጓ ከሽ ከሽሽሽሽሽሽሽሽ ፋጭጭጭጭጭጭጭ

ጥዋት ሳጅን አሰፋ መዝገቡ "ለኤሌክትሪክ ምሰሶ ቅድሚያ ባለመስጠት አንዲት ሚኒባስ ታክሲ ምሰሶው ጋር ተላትማ ሹፌርና እረዳቱ ወዲያው ሲሞቱ በሚገርም ሁኔታ ሌሎች ተሳፋሪወች ምንም ሳይሆኑ ተርፈዋል"

( ትፍ ትፍ ይቅር ይበለኝ!! )

እና ዋናው ነገር ይሄ የቅዱስ እከሌ ስጦታ የሚባለው ነገር ለአንዳንድ "ፀረ ሰላም ሴቶች" መደበቂያ ሊሆን ሁሉ ይችላል (ሂሂሂ) ለምሳሌ አንዳንድ ሴቶች "ከሹገር ዳዲ" የተሰጠቻቸው አቶዝ ላይ "የሊቀ መለአክቱ ሚካኤል ስጦታ" ብለው ሲለጥፉበት የሰሩትን ስራ እንዳላየን ስናልፍ ጭራሽ የእንጨት ሸበት ባለጌ ቅሌታም ሽማግሌ "ሊቀ መለአከት" ብለው ማስታወቂያ ሲለጥፉለት አይደብርም?

"አቶዛዊ ሃረካት" አያሰራም? እንደውም ሳጅን አሰፋ መዝገቡ የሃይማኖት ሰወች የተካተቱበት ኮሚቴ አሁኑ ያቋቁሙና በከተማችን የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ እንደገና ያስጠኑልን !! አሃ ሰርቆም አመንዝሮም መኪና የገዛው ሁሉ በስማቸው ሲቀልድ ቅዱሳኑ ተቆጥተው ቢሆንስ ይሄ ሁሉ እልቂት "ለእግረኛ ቅድሚያ ባለመስጠት ሳይሆን ለቅዱሳኑ ክብር ባለመስጠት የደረሰ አደጋ "የሚል ሪፖርት ከሳጅን አሴ ከሆነስ ሆነና ይሄ የሚሰራው ባቡር የማን ስጦታ ይሆን

# እዛው የለመድክበት !!

የአንደኛ ክፍል ትምህርት የጀመርኩት በአምስት አመቴ ነበር ክፉቱ ደግሞ ደቃቃ መሆኔ ረእሰ መምህሩ “ብላችሁ ብላችሁ አራስ ልጅ አስተምሩ ልትሉን ነው እንዴ “ ብሎ መልሶኝ ነበር “ግዴለም ሶስት ቀን ብቻ ይዩት” ተብለው ተለምነው አስገቡኝ !! ታዲያ “ እሳት የላስኩ “ ተማሪ ስለነበርኩ በዛ እድሜ ፊደሎችን ወላ አማርኛ ወላ እንግሊዝኛ “ጠጣኋት”

እንደውም እማማ ሸጊቱ የሳምሶን የእናቱ እናት አያቱ ማለት ነው “ ተማር ያለው እናቱ ሆድ ይማራል እንዳሰለፈች ልጅ) ይላሉ አሰለፈች እናቴ ናት “አሰለፈች “ ስላት ከነቅድም አያቷ የጠራኋት ስለሚመስለኝ “አሴ” እያልኩ ላውራችሁ

በወር ሁለት ብር እየተከፈለልኝ እዛው መንደራችን የሚገኝ የቄስ ትምህርት ቤት ውስጥ ፊደል መቁጠር በጀመርኩ በአስራ አምስት ቀኔ “ወላጅ ጥራ “ ተባልኩ (ያኔ ተማሪ ወላጅ የሚጠራው የሆነ ነገር ካጠፋ ነበር እናም ወላጅ ሲጠራ “ ልጅህ ባለጌ ስለሆነ ናና እንዴት እንዳሳደከው አስረዳ “ አይነት መልክት ነበረው)

አባቴን ይዤው ሄድኩ አባባ ገና ምኑንም ሳይሰማ መንገድ ላይ ይወርድብኝ ጀመረ ” ገና ሁለት ሳምንት ሳይሆንህ ወላጅ እንደው ምነ ይሻለሃል ” እጀን ይዞ ቶሎ ቶሎ በቁጣ ሲራመድ እርምጃየን ከአባቴ እኩል ለማስተካከል ሱክ ሱክ እላለሁ

“ምንድን ነው ያጠፋሃው ”

“ምንም”

“ዝም በል ! መች አጣሁት ያንተን ክልፍልፍነት “ (ካላጣው ለምን ይጠይቀኛል )

“ልጅ ጋር ተጣልተህ ነው”

“ኧረ አልተጣላሁም “

“ዝም በል! ስንደርስ እንሰማው የለ ምን አቅለበለበህ “ ጠይቆኝ ዝም በል ሆሆ!

ስንደርስ የኔታ የሉም ” ኩታ የቋጨሁላት ሴት ቤት ብር ልቀበል ስለምሄድ ትምህርት የለም” ብለው መሄዳቸውን ሰማን

(የኩታ ቁጭት ሂሳብ ማወራረጃ ቀንን ምክንያት በማድረግ ትምህርት የለም ሂሂሂ) ስንመለስም አባባ በግምት ሲቆጣኝ እና ሲገስፀኝ እቤት ደረስን ደርሶ መልስ ማራቶን ግሳፄ!!

“የሰው ፊደል ቀደህ ነው”

“ኧረ አልቀደድኩም”

“ዝም በል” ዝም እላለሁ አባባ ግን ይቀጥላል

መንገድ ላይ “አቶ አለሙ ሰላም አደርክ “ ይለዋል አንዱ

“እግዚሃር ይመስገን ምን ይሄ ልጅ ወላጅ ተብሎ ሂጀ መምጣቱ ነው “ (ስለእኔ ሳይጠይቁት)

“ምነው ምን ሆነ ” ልክ ታምሜ ሆስፒታል መሄዴ የተነገራቸው ነበር የሚመስሉት አጠያየቃቸው

**** **** **** ****

በቀጣዩ ቀን የኔታ ለአባቴ እንዲህ ሲሉ መልክት ላኩ “ እዚህ ድረስ እንዳትንከራተት እናተው አካባቢ የታመመ ሰው ልጠይቅ ብቅ ስለምል እኔው እግረመንገዴን እዘልቃለሁ”

ወደረፋዱ ላይ መጡና ምሳ ተጋበዙ ካሁን አሁን የመጡበትን ያወራሉ እያልኩ ብቁለጨለጭ የሚያወሩት ሁሉ ሌላ ሌላ ነው እረስተውት ይሆናል ብየ እንዲያስታውሱ አሳልኩ

አባቴ ዞሮ አየኝና "ይሄን አቧራ እያቦነነ ይውላል በቃ ማሳል ነው " አለ ከዛ ደግሞ ስለጉንፋን ስለግንቦቱ ፀሃይ የማያልቅ ወግ ጀመሩ አቤት ትልቅ ሰወች ሲያበሳጩ ቶሎ ቶሎ አያወሩም ሊያልቅ ሲል እንደገና ይቀጥላሉ ስለአንድ ነገር ይሄን ሁሉ ሰአት ሲያወሩ አይሰለቻቸውም ኤጭ!

በመጨረሻ አባ ልክ እንደምርቃት ወላጅ ያስጠሩብኝን ጉዳይ አነሷት

"አሰለፈች"

"አቤት አባ "

"እንደው ይሄን ልጅ የወለድሽው በምን ቀን ነው "

" አስመረረዎት አይደለም ይሄው ነው ቤትም ውስጥ ረብሻው "

"ኧረ በስማም በይ እሱ ኩሽም አይል እግዜር የባረከው ልጅ ነው " አሉና ኩም አደረጉልኝ አባ

"አሄ ሄ ሄ ነው ብለው ነው " አለች አፏን ወደጎን በአሽሙር ሸርመም አድርጋ (ግድ ረባሽ ይሁን ነው እንዴ)

" የለም የለም ወዲህ ነው ጉዳዩ እንግዲህ አንድ ልጅ ፊደል ለመለየት ሁለትም ሶስትም ወር ይወስድበታል ደንዘዝ ያለም ከሆነ ሾጥ እየተደረገ መንፈቅ ይሄ ያንች ልጅ ግን እግዜር ተመሃጠንሽ አስተምሮ ነው የፈጠረው " አሉ እንደፉከራ በሚቃጣው ድምፅ

"አባባ ተቋጥሮ የነበረው ፊቱ በኩራት ቷ ብሎ በራ ወንበሩ ላይ በደስታ ተንቆራጠጠ ሲጢጢጥ ይላል ወንበሩ ወንበሩም የሳቀ መሰለኝ

"ያስጠራሁህም " አሉ ወዳባቴ እያዩ " ሰው አፍ የገባ ነገር ደግ አይደለም በሚስጥር እንጨዋወት ብየ ነው "

"እሱስ ልክ ነዎት አባ የሰው አፍ " አለች አሴ በጭንቀት እያየችኝ

"አዎ ክፉ አይይብሽ እንጅ እሱስ እሳት ነው ናስቲ ወዲህ አብረሃም " አሉኝ ሂጀ አጠገባቸው ቆምኩ "

"ጉልበታቸውን ሳም እንጅ አንተ " አለ አባባ እንደወትሮው ባልመረረ ግሳፄ ቀሚስ ካፖርት ስለሚለብሱ አባ ጉልበት ያላቸው አይመስለኝም ዝም ብየ በግምት ጎንበስ ብየ ልስም ስል ግንባርን ለስላሳ መዳፋቸው ላይ አሳርፈው ቀጥ አደረጉኝ

የኔታ ፀጉሬን እያሻሹ እንዲህ አሉ "አሁን እንግዲህ በቄስ ትምህርት እድሜውን አንፍጀው አስኮላ ጨምሩት " አሉ!!

የዛኑ ቀን ከሰአት አባባ ይዞኝ ወጣና ሶሏ እንደበረዶ የነጣ ሰማያዊ ሸራ ጫማ ገዛልኝ ኮካኮላም ጋበዘኝ ጫማየ አቧራ በነካ ቁጥር በመዳፌ ልጠርግ ሳጎነብስ የኮካኮላው ትንታ አፍንጫየ እየመጣና አይኔ በእንባ እየተሞላ ስቸገር ዋልኩ !! አይ አባባ ሲሳደብም ሲያስደስትም አይሳሳምኮ!!

በቀጣዩ አመት አስኮላ ተመዘገብኩ አሴ ነበረች እጀን ይዛ የምትወስደኝ አዲስ ጫማ ስለተጫማሁ አካሄዱ ሁሉ ግራ ሆነብኝ አሴ ከአረማመድ እስከአበላል ትመክረኛለች

"ስትራመድ እንደባላገር ጫማህን ጧ ጧ አታድርግ ቀስ ብለህ " ትለኛለች መንገድ ላይ ጫማየ እንዳይጮህ አስፋልቱ ላይ ቻማየ እንዳይጋጭና ጧ እንዳይል እግሬን በጣም እያነሳሁና ቀስ አድርጌ እያሳረፍኩ ስራመድ የማደባ እመስላለሁ

"ምን ታደባለህ " ትላለች አሴ ጧ ጧ ጫማውን ስላመደው አረማመዴ ተስተካከለ

ቀጣዩ ምክር የአበላል ነው “ስትበላ ትልቅ ትልቅ አትጉረስ ደግሞ በሁለት ጉንጭህ ሞልተህ አታላምጥ ”

“እ ሽ” እላታለሁ ጉንጨኝ በምግብ ሞልቶ

“ምግብ በአፍህ ይዘህ አታውራ “ በቁጣ ትናገራለች ራሴን ከፍ ዝቅ አድርጌ መስማማቴን በምልክት እገልፃለሁ

“ደግሞ ስታላምጥ ከንፈርህን አታጩህ ከንፈርን ገጥመህ ”

“እ ” እረስቸው ልናገር እጀምርና የጎረስኳትን እስከምውጥ ዝም እላለሁ

“ጎበዝ” ትለኛለች በደስታ እፍነከነካለሁ

ትምህርት ቤት ከእኔ ከፍ የሚሉ ልጆች “እናቱ ናት የምታመጣው” እያሉ ሲስቁብኝ አሴን ከግቢው በር እንድትመለስ ማስገደድ ጀመርኩ ከዛ ከትምህርት ቤቱ ራቅ ካለ ቦታ ተመለሽ አልኩ በመጨረሻ ከሸኘሽኝ አልሄድም አልኩ መሸኘቷን አቆመች ብቻየን በኩራት መሄድ ጀመርኩ አቤት የሚሰማኝ ኩራት ! ( ካደኩ በኋላ የነገረችኝ ነገር ግን አሳቀኝ ለካስ ለረዥም ጊዜ ሳላያት እስከትምህርት ቤቱ ከኋላየ ትከተለኝ ነበር አንድ የአነምስተኛ ክፍል የሰፈራቸን ልጅ ጋር አብረን መሄድ እስከጀመርን ድረስ )

በዚህ ሁኔታ እያለሁ ነበር አስቂኙ የሂወት ገጠመኝ በቤተሰባችን ላይ የተከሰተው

አማርኛ 100

እንግሊዝኛ 100

ሂሳብ 100

ሳይንስ 100 (አይ ምነው ከመቶ በላይ በተሰጠ ኖሮ እያሉ)

ስፖርት 100

ሙዚቃ 99

የክፍል ሃላፊው አስተያየት ----በቀይ እስክርቢቶ “ በ23 አመት የመምህርነት ቆይታየ ካየኋቸው ተማሪወች ሁሉ አብረሃም የተለየ የትምህርት”ተሰጥኦ” ያለው ተማሪ ነው ። የወላጅ ክትትልና እንክብካቤ ካልተለየው ለት/ቤታችን ፣ ለቀበሊያችን ፣ ለወረዳችን ለከተማችን ፣ ለአገራችን፣ለአህጉራችን ብሎም ለአለማችን ታላቅ ነገርን እንደሚያበረክት ጥርጥር የለኝም!! ኢትዮጲያ ትቅደም!! ደምሰው ዘበነ አበባው ፊርማ!!

አሴ ይሄንን ሳነብላት “ እልልልልልልልልል እሰይ የኔ አንበሳ የኔ ነብር እንደው ምን ላድርግህ” ብላ ሳመችኝ ከዛም የተጣላቻቸው ጎረቤቶች እንዲሰሙ ጮኸ ብላ ላልተጣላቻቸው ጎረቤቶቻችን እየተጣራች የምስራቹን ተናገረች

መጀመሪያ እማማ ሩቁ ”ሩቁ ”

“ለበይከ”

“አብርሽ ከትምርት ቤት አንደኛ ሆነ”

“ማሻ አላህ አንተ ጀሯም ለእኔ ሳታሰየኝ ወደናትህ ትሮጣለህ ? በል ና ሳመኝ ” አሉ ደስ ብሏቸው

“አንተ ለሩቁ ሳታሳይ ነው እንዴ ወደኔ የሮጥከው ?” አለች አሴ (እንዳላወቀ ሰው)

“የሰው አፍ ጥሩ አይደለም አላልሽም ? ”

“ እመቤቴ ማሪያም ! እና ሩቁ ሰው ናቸው ? “ አለችና ተሳሳቁ

አባቴ ከዋለበት ሲመጣ እኔም አሴም ለመናገር አቆበቆብን

“ምን ሁናችኋል ? “ አለ ፊታችንን ሲያይ ግራ ገብቶት

“ አብርሽ ከተማሪ ቤቱ ልጅ ሁሉ አንደኛ ሆነ” አለች አሴ ሳልቀድማት በፊት ፍንክንክ ብላ

“ኧረግ ኧረግ የኔ አንበሳ ና ሳመኝ ነይ አንችም ሳሚኝ ” አሴንም እንደልጅ ጉንጭና ጉንጯን ሳማት

“እስቲ ካርድህን ይዘህ ና “ አለና ሊያወልቅ የነበረውን ኮቱን ሳያወልቅ ጥግ ላይ ያለች የልብስ ሳጥን ላይ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ!! ለወትሮው ቢሆን የራሱ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ነበር ፈልሰስ ብሎ የሚቀመጠው እንዲህ ነው አባት ለልጁ ደስታ ዙፋኑን ትቶ የልብስ ሳጥን ላይ ኩርምት የሚል ገና ለገና ዙፋኔን ይነጥቀኛል ብሎ የሚያንከላፍት አባት ስለሌለኝ ኮራሁ!!

ካርዴን ስሰጠው “አንብብልኛ እኔማ ምኑን አውቄው” አለኝ ከአባባ የበለጠ አዋቂ የሆንኩ ስለመሰለኝ ልቤ አበጠች ልትፈነዳ

አማርኛ 100

እንግሊዝኛ 100

ሙዚቃ 99

“ ለትንሽ አንድ ኤክስ ገባችብህ ግዴለም ለሚቀጥለው ትደፍናታለህ “ አለ ሳቄ መጣብኝ

የክፍል ሃላፊውን አስተያየት ሳነብለት “አሃጉር ምንድን ነው” አለኝ ግር ብሎት

“እኔጃ “ አልኩ እኔም አላውቀውም ነበር

“እች ናት ማለት ነው ኤክስህ አየህ የተሳሳትካትን ነው እንድታርማት የጣፉት “

ከሰአት እማማ ሩቅያ ቡና አፍልተው ምሳም ሰርተው እኔን፣ አሴንና አባባን ጋበዙን ። በጣም ደስ ብሏቸው ስለነበር በየመሃሉ

“አልሃምዱሊላሂ ” ይላሉ ደግሞ በእኔ ግብዣ እነአሴ የራሳቸውን ረዣዥም ወሬ ያወራሉ ! በመጨረሻ እማማ ሩቅያ መረቁኝ

“ትምርቷን ሁሉ እንደቁርአን ሃፍዛት “ አሉኝ (በቃልህ ሸምድዳት እንደማለት) ምርቃታቸው ሰራች መሰል “ሃፈዝኳት” በሁለተኛው “ሴሚስተር” ሁሉንም መቶ!! “ደብል” አለፍኩ

እዚህ ላይ ፉከራ ግድ ይላል አሴ በሳቅ እንበዋ ጠብ እስኪል የአባባን ዣንጥላ እንደጠመንጃ ወድሬ ፎከርኩላት

ለመስከረም ሁለት አባቴ ጋር መስቀል አደባባይ ሂጀ የሰማኋትን ለራሴ አድርጌያት

እንቢ እንቢ

የአስየ ልጅ ይሄ ትንሹ

50 ነው ሲሉት መቶን አሳሹ

ሶስተኛ ክፍል ድንገት ደራሹ እትትትትትትት

በምርቃና መከፈቻውን ተጫንኩት መሰል ድንገት እጀ ላይ “ቷ” ብሎ የተዘረጋው የአባቴ ዣንጥላ የተጣደውን ቡና ከከሰል ምድጃው ላይ ከነበለው ደንግጬ ቁሜ ቀረሁ

“ አለሙ ድረስ “ብላ አሴ ከወዲያ በሚገርም ፍጥነት ተወረወረችና ጀበናው መሬት ሳይነካ የፈላውም ቡና እግሬ ላይ ሳይከነበልብኝ በአየር ላይ አፈፍ አደረገችው እጇን ቢያቃጥላትም እኔ ተረፍኩ ። ፎክሬ ያመጣሁትን

ጣጣ አሴ ተጋፍጣ አዳነችው ፎከረው ችግር የሚያመጡ ሌሎች የሚጋፈጡ ሌሎች  የአባቴ ዣንጥላ አተላለቁ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቡም ጭምር ይበቃል !!

ወደቀደመው ነገር ስመለስ እቤታችን አስቂኝ አጋጣሚ ተፈጠረ ብየ ነበር

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ አሴና አባባ ፍራሹን ከአልጋው ላይ አንስተው የአልጋውን ስር ያፀዳሉ አባቴ ቤት ሲጠርግ አይቸው ስለማላውቅ ተገረምኩ በየመሃሉ “ይበቃል አይበቃም” እያሉ ይከራከራሉ በኋላ እንደተረዳሁት የአልውን ስር ለመደበቂያነ እያዘጋጁት ነበር

የሚደበቁት ለመሰረተ ትምህርት በየቤቱ ቅስቀሳ ከሚያደርጉ የቀበሌ ካድሬወች ነበር ”ወደትምህርት ውጡ” እያሉ ሲመጡ አባባ ልክ እንደሰርከስ ባለሙያ ረዥም ቁመቱን እጥፍጥፍ አድርጎ አልጋው ስር ይደበቃል እናቴ ትከተላለች ፍራሹ ትንሽ ወደላይ ከፍ ይላል ( ስትጫኑኝ ከርማችሁ እስቲ ዛሬ እንኳን ልጫናችሁ ብሎ ደረቱን የሚነፋ አይነት) እኔ በሩ ላይ እቆምና “የሉም “ እላለሁ ሰበብ እየደረደርኩ

አንድ ቀን ግን ሁለቱም ተያዙ አባባ የቤታችን ጣራ አፍስሶ ሊጠግን መሰላል ላይ ቁሟል አሴ እንዳይወቅ መሰላሉን ደግፋ ይዛለች በዚህ ሁኔታ የቀበሌወቹ ሰወች ከተፍ አሉ!!

“ሂጅ አንች ተደበቂ እኔን አይተውኛል “ አለ አላት አባባ

“ኧረ ሙት ብየ ነው መሰላሉን ለቅቄ የምሄደው ? “ አለችው ሲነዛነዙ ተያዙ!! አንዴ ከተመዘገቡ በኋላ መቅረት የማይታሰብ ስለበር በቃ እየዘነጡ ወደትምህርት ቤት ሆነ !! የአባባንና የአሴን ደብተሮች ማታ ማታ አያቸዋለሁ የእጅ ፅሁፎቻቸውን አወዳድራለሁ

ለምሳሌ የአባባ “ሸ” ቆቧ በጣም ከመርዘሙ ብዛት ኢሊኮፕተር ትመስል ነበር የአሴ ፊደሎች ትንንሾች ሁነው ወደግራ ያዘነብላሉ ለምን እንደሆነ እንጃ “ጳ” የተባለችው ፊደል አሴን እራሷን ትመስለኛለች !

ከመንደራችን መሰረተ ትምህርት የማይማሩት እማማ ሩቅያ ብቻ ነበሩ ከቀበሌ እንደሚያማቸው ተመስክሮላቸው !! አስመስክረው ሲመጡ “አላህ አይቁጠርብኝ “ አሉና ከት ብለው ሳቁ እየተርገፈገፉ የባሰ ድርቀት ጠበቃቸው የሰፈሩ ሰው በሙሉ ህፃን ልጆቹን እማማ ሩቅያ ቤት አስቀምጦ ነው ትምርት የሚሄደው !!

የመሰረተ ትምህርት ፈተና ደረሰ አሴ በጣም ተጨናነቀች!! ብቻዋን ማውራት ሁሉ ጀመረች “አንዱንም ሳላውቀው ፈተና ሆሆ.. መሳቂያ ሊያረጉኝ “ ትላለች ጓዳ ጉድ ጉድ እያለች አባባ ግን ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ያጠናል የከበደውን እኔን ይጠይቃል ሲጠይቀኝ በጉልበት ነው “ና አንተ እች ምንድናት ?” ይላል ኮስተር ብሎ !

አንድ ቀን ዝም ብሎ ተቀምጦ ፂሙን ሲያሻሽ “አታጠናም እንዴ? “ ብየው ከዛ በፊትም ከዛ በኋላም ሰቆት የማያውቀውን ረዥም ሳቅ ሳቀ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ ምን እንዳሳቀው ግን አልገባኝም እሱ ሁልጊዜ “አታጠናም እንዴ አንተ” ሲለኝ አልስቅም !!

አሴ የፈተናው ቀን ማታ አስገራሚ ሃሳብ መጣላት የቀበሌ ሊቀመንበሯ ቤት ቀጥ ብላ ሄደችና “ልጀን ስላመመው ነገ ፈተና አልመጣም” አለቻት

ሴትዮዋ ብዙ ዲስኩር አሰማችና በመጨረሻ “ ልጁን ይዘሽም ቢሆን ተፈተኝ “ አለቻት በዚች ቅፅበት አሴ እየሳቀች ወደቤት ተመለሰችና “አብርሽ ና “ አለችኝ አንድ ትልቅ ጋቢ ለሁለት እያጠፈች ከዛም ዞር አለችና ከፊቴ ተቀምጣ “ና ጀርባየ ላይ ውጣ “ አለችኝ

እየሳኩ ጀርባዋ ላይ ወጣሁና አንገቷን በሁለት እጀ አቀፍኳት አዘለችኝና ጋቢውን አልብሳ ወደመስተዋቱ ቀረብ አለች ልክ ልብስ የምትለካ ነበር የምትመስለው አስተዛዘሏን እየተዟዟረች ስታይ

“እንደው የሆንክ ላባ ነገር አስረንህ የምንበላ ይመስል እንዲህ መቅለል አራስ አሉ ያ ሰውየ እውነትም አራስ “ አለች በሰውነቴ መቅለል እና ጀርባዋ ላይ ልጥፍ ስል ያ ትምህርቱን ሁሉ መቶ ያጋጨሁት “ጀግና “ ልጅ ሳልሆን የአመት ጨቅላ ማከሌ ገርሟት ። ለዛሬ ግን መቅለሌ አላስከፋትም

“በል ውረድ “ አለችኝ ጋቢውን ወደፊቷ ገፋ

አንገቷን እንቅ አድርጌ አቅፌ እየተንከተከትኩ “አልወርድም” አልኩ ሙልቅቅ

“እፀድቅ ብየ ባቅፋት ተንጠልጥላ ቀረች አሉ “ ውረድ ብላ ታፋየን ሳታሳምም ቆነጠጠችኝ ይሄን ሁሉ ስታደርግ ጋቢዋን እያጣጠፈች ወደዛ ወደዚህ እያለች ነበር ምንም አልከበድኳትም

በቀጣዩ ቀን አዝላኝ ፈተና ገባች የፈተና ወረቀቱን በትከሻዋ ላይ ተንጠራርቸ ማየት እንድችል እኔን ከፍ አድርጋ አዝላኝ እሷ ዝቅ ብላ ተቀመጠች ተጀመረ!!

ጥያቄ አንድ ፣. የሹካውን ሰ ዝርያወች ፃፉ

“ሶስት እግር ነው ያለው “ አልኳት በጆሮዋ ፃፈችው

“ አሴ እሱማ “ጠ” ነው እግሩን ወደላይ አድርጊው “ሠ”“

“ታዲያ ጣት አትልም እንዴ እግር ወደላይ የሆነው በየት አገር ነው “ አለች ቆጣ ብላ ደግሞ እያስኮረጅኳት ትቆጣለች እንዴ

2ኛ ጥያቄ አበበ በሶ በላ በሚለው አረፍተ ነገር ማሰሪያ ግሱ የቱ ነው ሀ. አበበ ለ. በሶ ሐ. በላ መ. ግስ የለውም

“ግሳንግሳሞች” አለች አሴ በብስጭት

“ ሐ በላ የሚለው “ አልኳት በሹክሹክታ

“ አይ አበበ ነው እንጅ “ አለችና አበሳጨችኝ

“አበበማ ባለቤት ነው “

“አሃ ታዲያ ባለቤቱ የራሱን በሶ ማሰርም መፍታትም አይችልም ? አንተ ደሞ ታበዘዋለህ “

“ማሪያምን አሴ “በላ” ነው መልሱ “

“ታሳስተኝና ውርድ ከራሴ”

“ግድ የለሽም “

ፈተናው አለቀ!! ያውም ማንም ሳይነቃብን እኔና አሴ ተዛዝለን ፈተናውን ጨረስነው ሂሂሂ

ውጤት የተሰጠ ቀን አባቴ ከአስሩ አራት አግኝቶ ወደቀ!

አሴ የእኔ ጎበዝ ድፍን አደረገችው !! ካስሩ አስር!! የጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ፎቶ ያለበት ደብተር ከሁለት እርሳስ ጋር ተሸለመች

ታዲያ አንድ ምሽት ጓድ ሊቀመንበር በቴሌቭዥን ንግግር ሲያደርጉ “ ስንቱን ፀረ አቢዮተኛ አዝለን እንኖራለን ? ወዳጅ መስለው በጀሯችን ሹክ እያሉ ገደል አስገቡን በቃ ካሁን በኋላ ከጀርባችን ላይ እያወረድን እናፈርጣቸዋለን እንፈጠፍጣቸዋለን መቀመቅ ውስጥ ነው የምናስገባቸው የኢምቴሪያሊዝም አንቀልባ የሆንክ ሁሉ አዛይም ታዛይም "እዛው የለመድክበት" “ አሉ ታዛይን ቀጥፈው ሚስኪን አዛይን ሊያመክኑ

ወደአሴ ጆሮ ጠጋ ብየ

“አሴ ካሁን በኋላ ሁለተኛ ክፍል ስትሆኝ አልታዘልም” አልኳት

“እኔም ፀረ አቢወተኛ አላዝልም” ብላ በሳቅ ፍርስስ አለች የተሸለመችውን እርሳስ እየቀረፀች እንደጦር እያሾለች

እችን መተዛዘል ጓድ ሊቀመንበር ሁሉ ድረስ የተሰማች መተዛዘል አባባን ጨምሮ ማንም አያውቃትም ነበር እማማ ሩቅያ ግን ከፈተና ስንመለስ አሴ ጋር እየተንሾካሾኩ ሰውነታቸው እስኪርገፈገፍ ሲስቁ ስለነበር አሴ ሳትነግራቸው አትቀርም

ቅርብ ጊዜ አባባ ሊጠይቀኝ እቤቴ መጣና የሆነውን ሁሉ ባለቤቴ እየሳቀች ነገረቸው (እንዳትናገሪ ብየ አስምየ ነበር የነገርኳት አባባ ጋር ይዋደዳሉ እናም መሃላዋን ጥሳ አቀራቀረች )

“ ሌባ ሁሉ ! ሃቃችንን የኖርን ንፁሃኑ ስንወድቅ የሰረቃችሁት ተሾማችሁ ተሸለማችሁ “ ብሎ እርጅና በተጫጫናቸው አይኖቹ በፍቅር እያየኝ ፈገግ አለ!!

# አጥፍተው እንዳትጠፉ ይሉናል

አበራ “ አጥፍተው እንዳትጠፉ ይሉናል “ አለ ፡፡

ወደእኛ ሰፈር የምትወስደው ፒስታ መንገድ ከዋናው አስፓልት ጋር የምትገናኝበት ልክ መጋጠሚዋ ላይ በግራ በኩል የአበራ ድንጋይ አለች !! የአበራ መቀመጫ ናት (ውድድር የሌለባት ወንበር ይላታል አበራ ራሱ ) ከሷ ላይ አይጠፋም !!

አበራ ታዋቂ የሰፈራችን የኔ ቢጤ ነው (በርግጥም የኔ ቢጤ ነው) አንድ እግር የለውም ፡፡ ታዲያ ለአበራ ሳንቲም ሳይሰጡ ማለፍ ከባድ ነው!! የመብራትና የውሃ ወርሃዊ ክፍያ ሲመጣ ድንኳን አስጥለው ሃዘን ሊቀመጡ የሚቃጣቸው አባባ ዳምጠው እንኳን አበራ አጠገብ ሲደርሱ ስድስት ኪሳቸውን ፈትሸው (ሁለት የሱሪ ኪስ፣ ሁለት የኮታቸውን የውጭ ኪስ ፣አንድ የውስጥ ኪስ እና አንድ የደረት ኪሳቸውን) ሰባተኛዋ ሰደርያቸው ኪስ ውስጥ የሚያገኟትን አስርም አምስትም ሳይሰጡት አያልፉም ይሄንን የአላፊ አግዳሚ ፍቅር (ከሳንቲም ጋር) ያገኘው በሚለምንባቸው አስገራሚ የልመና ግጥሞቹና ለመፅዋቾች በሚያበረከረተው ምርቃት ነው ፡፡ የአበራ ምርቃት እንደደረሰኝ ይቆጠራል !! ማንም ሳንቲም ወርውሮ ሊሄድ ቢል “ጋሸየ ደረሰኝ እረስተሃል” ብሎ እየተከተለ ሁሉ ይመርቃል!!

በልመና ግጥሞች ላይ የመመረቂያ ፅሁፉን የሰራው የሰፈራችን ምሁር ተመስገን (የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሽዮሎጂ ምሩቅ እና በአሁኑ ሰአት የኮልኮሌ ሆቴል ገንዘብ ተቀባይ ሁኖ እየሰራ ያለ) የአበራን የልመና ግጥሞች በሶስት ይከፍላቸዋል

ኢኮኖሚያዊ

ማህበራዊ እና

ፖለቲካዊ በማለት

ኢኮኖሚያዊ ግጥም ካላቸው አንዱ እንደሚከተለው ነው

ባንክ ቤት ቢያኖሩት

ብሩም እንደሳልቫጅ

ዋጋው ይቀንሳል

ለደሃ ቢሰጡት በሰማይ ያነግሳል

መሃበራዊ

ይደኸያል እንጅ ይለብሳል ድሪቶ

ሰው ባለበት አገር ሰው በራብ አይሞትም

የሰው ፍቅር አጥቶ

ፖለቲካዊ

እኩል ነህ ይሉኛል አለም እየሰማ

ተንሻፎ እያየሁት የእኩልነት ጫማ

እንግዲህ አበራ ለድፍን 20 አመት እዚቹ ቦታ ላይ በልመና ቆይቷል (በቀደም ሃያኛ አመቱን ምክንያት በማድረግ20 ቁጥር ሻማ አብርቶ በልዩ ሁኔታ ሲለምን ነበር) አንድ ቀን ታዲያ ዝነኛው ዘፋኝ “ተውረግረጊ የኔ

ቆንጆ “ ለሚለውን ዘፈኑ ክሊፕ ሊሰራ ወደመንደራችን መጣና የአበራን ግጥም በተመስጦ ቁሞ አዳመጠ ከሱ ዘፈን የተሸሉ ግጥሞችን በመስማቱ ተደምሞ ለአበራ አስር ብር በመመፅወት እንዲህ ሲል መከረው

“ እየውልህ የኔ ወንድም የግጥም መክሊት ውስጥህ ይታየኛል  አደራ እንዳታባክነው!! አጭርና ዜማቸው ከመልእክታቸው የተሰናሰለ ግጥሞች ውስጥህ አ ይመረታሉ ማለት ይቻላል ዋናው ነገር አ ጭብጨባ እንዳያጠፋህ ተጠንቀቅ ጭብጨባን በ ጣም ተጠንቀቅ “ ብሎት ሄደ

አበራ አስር ብሯን ወደኪሱ እያስገባ ብቻውን ያወራ ጀመር “ጭብጨባ እንዳያጠፋህ ? አጨብጭበው ወታደር ቤት ላኩኝ አጨብጭበው ጠላት ጋር አፋለሙኝ አጨብጭበው ፈንጅ አስረገጡኝ አጨብጭበው እግሬን አሳጡኝ አጨብጭበው ጡረታ አስወጡኝ ሃሃሃሃሃሃሃሃ ከዚህ ሁሉ የጭብጨባ የጥፋት ውሃ በኋላ ሰላማዊ ጭብጨባ እንጀራየ በሆነ ጭብጨባ እንዳያጠፋህ ይሉኛል አጥፍተው እንዳትጠፉ ይላሉ ” ብሎ የተቆረጠ እግሩን እየተመለከተ ድንጋው ላይ እንደተቀመጠ በሃሳብ ጭልጥ አለ

ከእሩቅ ያለች ሙዚቃ ቤት “ተውረግረጊ የኔ ቆንጆ”የሚለው ዘፈን ይሰማል

“ቾብ ቾብ አርጉላት ዳሌዋ ይውረግረግ

ጭብጨባ አይደለም ወይ የሴት ሁሉ ማረግ ላላላላ አሄሄሄሄ ( እየው ሲያጠፏት )

አይታየንም ቢታየንም ብዥዥዥ

“ፍሬንድ የእነሃና ቤት የቱ ጋ ነው ” አልኩት አንዱን ጎረምሳ

“ሃና ሃና አላወኳትም ” ጎረምሳው ሁሉ ሴት ማየት አቆመ እንዴ ?

ሃና ፍቅርኛየ ናት ዛሬ ቤተሰቦቿ ጋር ልታስተዋውቀኝ ቀጥራኝ ሰፈራቸው ደርሻለሁ እዚህ አካባቢ እጠብቀሃለሁ ብላኝ ነበር የለችም ”ኔትወርኩም ኤጭ

“ይቅርታ የእኔ እህት የነሃና ቤት የቱ ጋ ነው ” አልኳት መንገዱ ዳር ላይ ዘንጣ የቆመች ቆንጆ ልጅ

“ ሃና የሆነች ቆንጅየ  ልጅ ? በ ዛጋ ውሻው በቆመበት ስትታጠፍ ” አለችኝ

“የትኛው ውሻ ”

“እንዴ ስንት ውሻ ነው ያለው እዛ የሆነ ጥቁር ነገር ከለበሰው ልጅ ጎን ጥቁር ውሻ አይታይህም “ አለች ፈገግ ብላ

““አኬ” ሁለቱም ጥቁር ሲሆኑብኝ ተመሳስለውብኝ ነው ይቅርታ” ብየ መንገዴን ቀጠልኩ

“ተው እንጅ ሞዛዛ ” ብላ ቀይ ፊቷ ተቀያየረ ጥቁር የለበሰው “ልጅ” ባጠገቤ አለፈ ዞር ብየ ሳይ ልጅቱ ጋር ከንፈር ለከንፈር ተሳስመው መንገዳቸውን ቀጠሉ  እሱን ነበር የምትጠብቀው ለካ እሷ ያለችው ጥቁሩ ውሻ ጋር ስደርስ ውሻ አልነበረም የእኔዋ ሃና ጥቁር ቱታ ለብሳ የሆነ በረንዳ ነገር ስር ተቀምጣ አገኘኋት..ዞር ብየ “ሞዛዛ “ አልኩ!

የእኛ ያልሆነ ሰው ሁሉ ውሻ መስሎ የሚታየን እስከመቸ ነው ?!

አብርሃም የት አምሽተህ ነው

“ አብርሃም የት አምሽተህ ነው ሰው ይሰጋል አይባልም እንደው ምናይነት አንጀት ነው የሰጠህ” እናቴ ! ገና 1፡25 ሰዓት ላይ

“ አብርሃም በጧቱ ወዴት ነው እስኪ ቁርስ እንኳን አፍህ ላይ አድርግ መጋኛ እንዳይጠረቅምህ” አሁንም እናቴ !

" አብርሃም ማነው አሁን የደወለልህ በሰላም ነው..."

"ጓደኛዬ ነው ማም" 'ጓደኛዬ ናት' አልል ነገር ችግር ነው።

"ምነው በሰላም..."

(ምን ሰላም አለ) "አዎ ሰላም ነው" ኡኡኡኡኡአ እ ናቴ!!

" አብርሃም ስትገባ ደህና ዋላችሁ እንኳን አይባልም" አባቴ ሙሉ ቀን አላፊ አግዳሚው ሰላም ሲለው ነው የሚውለው። ኮፍያውን እያነሳ መልሶ አናቱ ላይ እያስቀመጠ እንደገና እያነሳ ከዚህ ሁሉ ኮፍያ ባያደርግስ እስከምል ድረስ አገር መንደሩ ሰላምታ ያጠገበው አባቴ የኔ ሰላምታ ምን ያደርግለታል

" አብርሃም ጎረቤታችን ጋሽ ታምሩ አክስታቸውን ተረድተዋል ለቅሶ ድረስ ሆሆ አሳድገው አሳድገው" አባቴ !

"...አብርሽ ሆሞርክ ስራልኝ ከበደኝ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ከ መጀመሪያው ጀምሮ እስከ ኦባማ ስማቸውን እ የሰሩትን ዋና ዋና ስራ እና የሚስቶቻቸውን ስም እና ደ,ሞ ስንት ልጅ እንደወለዱ ንገረኝ...ለነገ ከአስሩ የሚያዝ የቤት ስራ ነው " ትንሽ እህቴ (ሁለተኛ ክፍል ናት) እስኪ አሁን ይሄ ምን ይሰራላታል። እንዴት ነው ታዲያ እች ልጅ ስታድግ ዲቪ የማትሞላው የሶስት ሺ ዓመት የታሪክ ቤት እያፈረሱ ለትውልዱ የቤት ስራ ይሰጣሉ፤ የት ሆነው ይስሩት

" አብርሽዬ ልክ ስፈልግህ መጣህ እስኪ ስለ 'አልዛይመር ብራውዝ' አድርግልኝ ነርሲንግ የምትማረው እህቴ ! እግሯን ጠረጴዛ ላይ ሰቅላ የጥፍር ቀለም እየቀባች እኔ የሷን አሳይመንት ስጎረጉር እሷ እግሯን እያሸሞነሞነች የአስቴርን ትዘፍናለች (እህቴ እግሯን ለማሳመር የምታጠፋውን ጊዜ ቻይናዎች ቢያገኙት ከአባ ታምሩ ቤት እስከኛ ቤት የሚደርስ የእግር መንገድ ይሰሩበታል !! ይሄ ሎሚ መስሎ በየመንገዱ የምታየው የሴት እግር ስንት ጉድ ድካም "ኢንቨስት" ተደርጎበታል መሰለህ።)

"ሱ ፍ ገበርዲን ለብሰህ ናልኝ አልልህም፣

የዘመኑን ካፖርት ደርብ አልልህም

ያገሬን የወንዜን እጀ ጠባቡን "ያበደ ወንድ ካልሆነ ማን አንቺ ጋር ይመጣል" እላታለሁ ነገር ሲያምረኝ ጉራዋን ልትንድብኝ ነው እንግዲህ 1 2 3 ተ ና ደ "ማ ን ጋ ? እኔ ልጅት ጋር ? ደግሞ ላዲሳባ ወንድ አስር ሺውን ነው የማሰልፈው " በንቀት ከግር እስከራሴ እያየችኝ

"ተይ ባክሽ ይሄ ሚስኪን ወንድ ለስንቱ ይሰለፍ ለታክሲ ለስኳር ለሰላማዊ ሰልፍ ደግሞ ላንቺ ያውም ሽሮ ሜዳ ሂዶ እጀ ጠባብ ገዝቶ ወላ ተከራይቶ ሂሂሂ " የሶፋውን ትራስ ትወረውረዋለች ነገር ከጀመርኩ አላቆምም "ታየኝ እኮ ከላይ እስከታች ነጭ እጀ ጠባብ የለበሰ ጎረምሳ የጅፕሰም ሐውልት መስሎ በራችን ላይ ሲቆም ሂሂሂሂ"

"በሰባራ ፎሌ ውሃ አይጠለቅም " ስልኳ ይጠራል። "ሃኒ ደህና አመሸህ አነሳሁት አይደል ባክህ ያ ጀዝባ ቲቸር የአገር አሳይመንት ሰጥቶኝ 'ብሮውዝ' እያደረኩ ነው (ኡኡቴ...) የእሪች 'በርዝደይ' ወይኔ ጉዴ ረስቼው አሁን የት ናችሁ መጣሁ በቃ መጣሁ" ቦርሳዋን ካንዱ ቦታ ጫማዋን ከሆነ ቦታ ለቃቅማ በሩጫ ለብሳ በሩጫ ተቆነጃጅታ ከቤት ትወጣለች (ነርስ ልትሆን መንገድ የጀመረች እህቴ ለድንገተኛ አደጋ ለበሽተኛው በነፍሱ ድረሽ የተባለች እኮ ነው የምትመስለው።) እንግዲህ ይሄ ሁሉ ጉዳይ የሰለቸው ለአቅመ ቤት መከራየት የደረሰ የ25 አመት ወጣት ቤት ቢከራይ ይፈረድበታል ?

ቤት ተከራየሁ !! ግልግል ብዬ ሳልጨርስ አከራዬ የቤተሰቦቼን ዱላ ተቀብለው በነፃነቴ 'ትራክ' ላይ ሩጫቸውን ቀጠሉ "አብርሃም አታምሽ ልጄ ሰፈሩ ክፉ ነው ቁመትህ ቅዥልል ብሎ እችን ቦርሳ (ላፕቶፔን) ተሸክመህ ስትንከላወስ ኪስህ ሙሉ መስሏቸው ማጅራትህን ብለው ይገሉሃል ሌባ እንደሆነ አንተን ሲያጠና አይውል የቤት

ኪራይህን እንኳን አስር ቀን አሳልፈህ በስንት ፆም ፀለት የምትከፍል ያጣህ የነጣህ መልከመልካም ደሃ መሆንህን ሌቦቹ መች ያውቃሉ" ይሉኛል ! እየው እንግዲህ ራሳቸው በነገር ካራቴ ማጅራት ሲመቱ !!

"አብርሃም"

"አቤት ማዘር"

" እች በቀደም የመጣችው ቀይ ልጅ እንደው ፊቷ ጤነኛም አይመስል ቆዳዋ እንደታጠበ አንሶላ ወዙን ነስቶታል...ጨርሳ ከራማዋ የተገፈፈ ነገር ናት...ምነው ሴት ጠፋ እንዴ ባገሩ ኤዲያ አስር ጊዜ ከንፈሯን ይሄ ምንድነው. ቻብስቲክ መለቅለቅ ነው...ከንፈሯ እሳት ላይ እንደተጣደ ባዶ መጥበሻ ቶሎ የሚደርቅ ሴት ጤናም አትመስለኝ...እግዜር ያደረቀውን ቻፕስቲክ አያወዛው ልጄ...ትቅርብህ ልጄ ባይሆን ያች አንድ ቀን የመጣችው ምነው እንኳን የሻወሩ በር አልከፈት ብሏት የከፈትኩላት እሷ ባይሆን ትሻላለች ዛላዋም ያምራል ሞላ ሞንደል ያለች ናት።

አብርሃም (ምናባትዎት ፈለጉ ማለት እያማረኝ 'አቤት ማዘር' እላለሁ) ውይ ንዝንዝ...ቤተሰቦቼስ ከፍለውኝ ነበር የሚነተርኩኝ...ከፍዬ ሰላሜን ልጣ....

"ምነው እህቴ ታማ ሳትጠይቃት 'እግዜር ይግደልሽ' ማንን ገደለ "

(ኧረ እግዜር ይግደላችሁ ማዘርዬ ብዬ ቢወጣልኝ ደስታዬ) ግን ምን ያደርጋ "ኧረ ምን አገኛቸው" እላለሁ ለመደንገጥ እየሞከርኩ...

"ምን.  የዛሬ አስር ዓመት ፋብሪካ ስትሰራ ካርቶን እግሯ ላይ ወድቆ..." የአስር ዓመት ታሪክ ድፍን የአዲስ አበባ ሆስፒታሎችን ያካለለ የህክምና ዙረት.  የኢትዮጵያ ገዳማትን አድባራትን እምነትና ፀበል ያስሞከረ በሽታ ገድል ቁጭ ብዬ ማድመጤን እቀጥላለሁ

# አስቴር አወቀ እና “ቲቸር” መልከአ

የትምህርት ቤታችን የመምህራን “ካፍቴሪያ ውስጥ

እሮብ በሶስተኛው ፔሬድ “ጆግራፊ ቲቸር” ከመአት ጥያቄና ማማሳያ ከምትመስል ልምጫቸው ጋር

“ መስፍን የናይጀሪያ ዋና ከተማ ማን ነው

“አቡጃ ” ጎበዝ !! መስፍን ታድሎ ቢያንስ ዛሬን አለፋት ለነገ እግዜ ያውቃል

“ዳግማዊት (የክፍላችን አንደኛ ጎበዝ ተማሪ ናት ) የጣሊያን ዋና ከተማን ንገሪኝ እስቲ ” ምናለ በሉኝ ትመልሰዋለች

“ ሮም” አላልኳችሁም

ጎበዝ አጨብቡላት( ለአፍሪካ ከተሞች አይጨበጨብም እንዴ  እያልኩ አስባለሁ)

“ናትናኤል የፈረንሳይ ዋና ከተማ ”

“ ዋሽንግ ተን “ ወይኔ ጉዱ  አስር ተገረፈ ብትሩ በአየር ለይ ዝዝዝ ብሎ እጁ ላይ ጧ ማሪያም ገብርኤል ጊዮርጊስ የዛሬን አውጡኝ በናታችሁ

“ጋሻው አንተ ሁልጊዜ ሰው ጋር መጣላትና መደባደብ ነው ስራህ እስቲ እ ” ታፋቸውን በብትሯ እየተመተሙ ለጋሻው የምትሆን ከተማ ሲያስቡ ቆዩና

“የሱማሊያ ዋና ከተማ ማናት ” “ ሱማሊያ ዋና ከተማ አላት እንዴ “ እያልኩ አስባለሁ

“ሱማሊያ ሱማሊያ ሞቃዲሾ ” ደንግጦ መሆን አለበት የመለሰው !! ጎበዝ ! ቲቸር ደስ አላቸው ጋሻው በዚህ አመት እችን ብቻ ነው የመለሰው ትምህርት ቤት ሊዘጋ እኮ ሁለት ወር ነው የቀረው ሁላችንም ገርሞናል አይ ጋሻው ባለፈው የኤርትራን ዋና ከተማ ተሳስቷል መሳሳት ብቻ  “አዲስ አበባ” ብሎ ቁጭ አለ እንጅ ! ቲቸር ሆድ ባሳቸው ስለመገንጠል ምናምን አወሩ ማንም አልገባው ” ትውልዱ አይምሮ ውስጥ አለመገንጠሏም አንድ ነገር ነው  ” ብለው ጋሻውን ሳይገርፉት አለፉ ! እንዴት አልተገረፈም ገርሞናል!!

“አብርሃም !!” በስማም ወልድ ድንገት ጠርተው አስደነገጡኝ  እመቤቴ ማሪያም ህፃኑ ቂርቆስ የሱዳንን ዋና ከተማ እንዲጠይቁኝ አሳስቡልኝ የሱዳንን ዋና ከተማ ጥሎብኝ አረሳትም!

“የአንጎላ ዋና ከተማ ማነው “ ይሄ ሰውየ ከኔ ጋር ችግር አለባቸው አንጎላ ደግሞ ማናት ዝም ብለው አይጋረፉም የሌለ ከተማ እየጠሩ ሰበብ ከሚፈልጉ

“ አንት እኮ ነው ” ዝም ከማለት ብየ አፌ ላይ የመጣልኝን ተናገርኩ

”ካርቱም “ አልኩ ዳግማዊት ሳቀች ጥርሳም !

ቲቸር ብስጭት ብለው “እሽ የኬንያ ዋና ከተማስ ” አሉኝ መገረፌ ካልቀረ

“ፕሪቶሪያ ” በራስ መተማመኔ ሲታይ ፕሪቶሪያ ለኬንያ ዋና ከተማነት የተሰጠች ሁሉ ያስመስላል

“ እዚህ አፍንጫህ ስር ያለች አገር የጠፋችህ አንተ ምን ፍጥረት ነህ ዘርጋ ” አስር ተገረፍኩ (ለጭብጨባው ጊዜ ከጣሊያን እናንሳለን ለመገረፍ ግን ከፈረንሳይ ጋር እኩል አስር )

“አባይ ከየት ይነሳል ? “ እንሳሳታለን

“ አገርን አለማወቅ አገርን ለመካድ ግማሽ መንገድ ነው ቁራጭ መሬት ለምን አትሆንም ጠብታ ውሃ ለምን አትሆንም ልቅም አድርጋችሁ ማወቅ ነገ ሌሎች ድንበር እንሸረፍ ውሃ እንጭለፍ ሲሉ አይሆንም የሚል ትውልድ የሚፈጠረው ከእናንተ ነው እንደቀልድ ነው ቦታ የሚጣረሰው ታሪክ የሚንሻፈፈው ” ይፈላሰፋሉ ቲቸር ከዛ በመደዳ አስር አስረ እንቀጠቀጣለን !”ነገ የተዛባ ታሪክ እንዳይከትቡ እነዚህ እጆች ዛሬ ሂሳባቸውን ይቀበሉ” ይሉናል!!

“መቅደላ የት ይገኛል ? ካርታ ፊታችን ዘርግተው “ እንሳሳታለን 10

“ የአማራ ክልል የትኛው ነው ? ” እንሳሳታለን 10

“የትግራይ ክልል የትኛው ነው ? “ ለተብርሃን ከደቡብ ወሎ ጀምሮ ያለውን ትጠቁማለች ቲቸር በብስጭት

“ ይሄም አማራችሁ “ ብለው 11 ይገርፏታል። “ለተ የተገረፈችው 10 ነው 11 ነው እንከራከራለን ብዙው በልማዳዊው 10 አይምሮውን የተሸበበ ስለሆነ 15 ብትገረፍም 10 ነው ብሎ ይከራከራል ። ቁጥሩ ላይ ካልተግባባን ምክንያቱ ላይ አንግባባም ምክንያቱ ካልገባን ነገም ካርታው ላይ እጃችንን እስከ አዲስ አበባ እንዘረጋለን !!

አንድ ቀን ታዲያ ቲቸር መልከአ የተማሪወችን ደብተር ሰብስበን የመምህራን ካፌ ድረስ እንድንወስድላቸው አዘዙንና እኔና ኡስማን ተሸክመን ወሰድንላቸው አርመው እስኪጨርሱ ቁጭ እንድንል ፈቅደውልን አስተማሪወች ጋር እኩል በመቀመጣችን ደስ ብሎን ስንጠብቃቸው የገረመኝ ነገር ተፈጠረ የአስቴር ዘፈን ተከፍቷል ቲቸር የሙዚቃውን ሪትም ተከትለው የስሚንቶውን ወለል ታ ታ ታ እያደረጉ አስቴር ጋር አብረው ይዘፍናሉ ደብተሮቻችን ላይ “ራይት” እና “ኤክስ” እያሰፈሩ ልክ እንደዚህ

አስቴር በስማም በስማም አልኩኝ ሴጣኑን ፈርቼ ስትል አንዱ ደብተር ላይ “ራይት”

አስቴር የወረኢሉ አገር ስሙ ነው አምባሰል

እህል እየበሉ ሰው ወዶ መሰልሰል” ቲቸር ጭራሽ አብረው እየዘፈኑ ደብተሩ ላይ “ኤክስ “ ኤክሱ እኔ ደብተር ላይ ነው የብራዚልን ዋና ከተማ ተሳስቸ አስቴር የወረኢሉን አገር አምባሰል ስትል አብረው የሚዘፍኑ ቲቸር ስለብራዚል የተሳሳትኩ እኔ ደብተር ላይ “ታሪካዊ ኤክስ” ያስቀምጣሉ ዛሬ ላይ አስቴርን ቲቸር ዝም ካሏት ነገ

“የአባይ ውሃ ወርዶ ይገባል መረብ

እኔና አንተ ሁነን ፈረስ እንጋልብ “ ብትል ቲቸር አብረው መዝፈናቸው አይቀርም ለወንዙ ባያዝኑ ለፈረሱ አይቆረቆሩም !! ወይስ ጥበብ እስከፈለገችው የመስፋት እስከፈለገችው የመጥበብ መብት አላት ግን ቲቸር ያላሳሰባቸውን ምናገባን ብለን እኛም የአስቴርን ዘፈን በቀስታ አብረን መዝፈን ጀመርን

“የወረሂሉ አገር ስሙ ነው አምባሰል

ካፌ እየቀለዱ ክላስ ጀግና መምሰል በስማም በስማም አልኩኝ ሰይጣኑን ፈርቼ ቀጥ ስል “ሂስትሪ ቲቸርም ትኩስ ሻይ እየጠጡ አብረው ይዘፍናሉ

# ትንቢተ ቃሊቲ

አንች ቃሊቲ ሆይ እንባሽ ወደእኔ ከፍ ከፍ ብላለች በፊቴም ሞገስን አግኝታለችና ከእንግዲህ የሞባይል ነጣቂ የተራ ሌቦችና የደርግ ባለስልጣናት መታጎሪያ ብቻ አትሆኝም! ፊቴን ወዳንች አዙሪያለሁ በሮችሽ ይከፈቱ ቃፊሮችሽ እልል ይበሉ አለቆችና ሙሰኞች ነጋዴወችና ባለፀጋወች ሁሉ "ቃሊቲ ማረፊያችን" ይሉሻል አየኖች ሁሉ ወዳንች ይመለከታሉ!

አህዛብ በገናቸውን አንስተው ስለክብርሽ እንዲህ ይዘምራሉ

አንች ቃሊቴ ሆይ ከተራራው ስር ያለሽ አለት

ስንቶች ከላይ ወርደው ተፈጠፈጡብሽ

ስንቶች ካባቸውን ተገፈው ማቅ ለበሱ

ደጆችሽ እንደገሃነም ደጆች ሰፉ

ጭፍሮችሽ ሰራዊትሽን ሰበሰቡ ወደጥልቅሽ የተወረወሩ ከአህዛብ መካከልም በንስር አይን የተለቀሙ የማህፀንሽ ፍሬወች ተበራከቱ

እናንተ ቀራጮጨችና አስመሳዮች አይናችሁን ከፈቱ ማረፊያችሁንም ተመልከቱ አንች ቃሊቲ ሆይ ደምፅሽ እንደተራበ አንበሳ ግልገሎቿን እንደነጠቃጥ አራስ ነብርም ነው አንች እንደአበሻ ቁና ነሽ የሰፈሩብሽን ትሰፍሪያቸዋለሽና የገቡብሽ ቀለጡ ዋስም አልተገኘም ስለምን ዋናወቹን ትታችሁ ገለባ ደፋችሁብኝ ብለሻል እውነት እውነት እልሻለሁ የመኳንንትና የመሳፍንት የነገስታትና የጦር መሪወች መናሃሪያ ልትሆኝ አምላክሽ ፊቱን አዙሯል ! ማጀትሽን አስፊ ቁኝጫሽን ጥረጊ አጥሮችሽንም አጠንክሪ ትውልድ ሁሉ

የፍትህ ክንድ በዚህ አለ ይበል ! የንፁሃን እጆችም ላይ ከእንግዲህ የእጅ ብረት አይግባ

# ባቢሎን ድብልቅልቅ

## ይህ ተከታታይ ወግ አምስት ክፍሎች አሉት

### ክፍል 1

ከቤታችን ፊት ለፊት ያለው አቧራ መንገድ ላይ እየተንከባለልኩ እየተንፈራፈርኩ ሪሪሪሪሪሪሪ ብየ ጮኽኩ ከቤቴ ተንደርድሬ በመጣሁበት ፍጥነት ነበረ እንደበረኛ ተወርውሬ በመውደቅ ኡኡታየን ያቀለጥኩት ዋይይይይይይይይይ !!! እንባ አልነበረኝም ግን ጉሮሮየ ላይ አንዳች ነገር እልህ ፣ብስጭት፣ ንዴት ተወትፎብኛል እንደዛ አይነት ብራቅ ድምፅ ከምኔ ውስጥ እንደወጣልኝም እንጃ

እንደአንዳች ክንፍ እንዳለው ነገር የጮህኩበትን ቧሬ አፌን ሳልዘጋ ማን አጠገቤ ደረሰ ? የእኔ መለአክ እማማ ሩቂያ ! !

"ምንድን ነው ምን አደረጋችሁት ኧረ ምንድነው ጉዱ አኡዙቢላሂ " እያሉ አቧራው ላይ ተንበረከኩና ብብቴ ስር ገብተው ሊያነሱኝ ሲሞክሩ ቲሸርቴ ተሰብስቦና እንብርቴ እና ሁዴ አካባቢ ተራቁቸ እግሬን እያንዘፋዘፍኩ ተፈራገጥኩ

እሳቸውን ሳይማ ባሰብኝ የደረቀው እንባየ ተዘረገፈ እናቴ አሴ የቤታችንን መቀርቀሪያ ይዛ ወደእኔ እየተንደረደረች ነበር ጩኸቴ አስደነብሮት የወጣ ጎረቤት ሁሉ ከላይ ከታች ከኋላ ከፊት ተብትቦ ያዛት "ልቀቁኝ ዛሬ ጨፍልቄው እጀን ለመንግስት እሰጣለሁ ኡኡኡኡኡኡ እንዳታሳብዱኝ ልቀቁኝ " አቤት ስታስፈራ ደግሞ ሃይሏ ያ ሁሉ ሰው እንዴት ይቻላት ድንጋይ ፈላጩ ግርማ ባይኖር ኖሮ አሴን ማንም አያቆማትም ነበር

እማማ ሩቅያን ሳያቸው ገረመኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ፀጉራቸው ተገልጦ አየሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ! ወደእኔ ሲንደረደሩ ጉፍታቸውን የቁርቁሮው በር ጫፉን ይዞ ስለገፈፋቸው ነበር ማንም አይቶት የማያውቀውን ፀጉራቸውን ጎረቤቱ ሁሉ ያየው ደግሞ ቢሞቱ መሬት በባዶ እግራቸው የማይረገጡት ሴትየ በባዶ እግራቸው ነበሩ ሩቂ የእኔ እናት መንደርተኛው በሙሉ አሴን ከቦ ይዟል እኔን ግን እማማ ሩቂ ብቻ ይበቁኛል !! የእኛ መንደር ቤተክርስቲያን ቢሆን ጉልላቱ እማማ ሩቅያ ናቸው መንደራችን መስጊድ ቢሆን እማማ ሩቂ ሚናራ እዛ አሴን የከበበው ሁሉ ሚናራ የሌለው መስጊድ ጉልላት የሌለው ቤተክርስቲያን ነው ለእኔ

አሴ "ቀበጠች" ማሪያምን አሴ ከበጠች !! እኔ እንኳን ንዴቴ በርዶልኝ (በእርግጥ ደንግጬ ነው ) ዝም ስል እሷ እስካሁን ትለመናለች ያውም ምን የሚያክል መቀርቀሪያ ይዛ ጎረቤቶቻችን እንደምንም ገፋፍተው አሴን ወደቤት አስገቧት እማማ ሩቂም እኔን አንስተው "እኔ ደሞ ኤሌትሪክ ያዘህ ብየ ነበር እንጅ " እያሉ አቧራውን ከልብሴ ላይ እያራገፉልኝ እያለ አሴ በጓሮ በር በኩል ወጥታ ወደኔ ተንደረደረች ጎረቤቱ እንደገና ተንጫጫ ተሯሯጠ "ያዛት ያዛት "አሴን አየኋት በስማም በወልድ  ጠፋብኝ አዎ በመንፈስ ቅዱስ ሚካኤልየ ገብርኤልየ ማሪያምየ አሴ በእጇ መፍለጫ ይዛ እኮ ነው ወደኔ የሮጠችው ዛሬ በቃ አልቆልኝ ነበር !! እጀን ከእማማ ሩቅያ እጅ ነጥቄ ልሸሽ ስል እንቅ አድርገው ይዘው አሴን ወደያዟት ጎረቤቶቻችን ጮኹ "ልቀቋት አንድ ሰው እንዳይዛት " አሉ ጎረቤቱ በእማማ ሩቂ ጩኸት ደነገጠ "እንዴ ሩቂ በደም ፍላት ትግደለው እንዴ " "ልቀቁ እሷን ሴት ብያለሁ ልቀቁ " እማማ ሩቅያ በብስጭት ጮኹ አሴ ራሷ ደነገጠች ጎረቤቱ እየፈራ ለቀቃት አሴ መፍለጫዋን ይዛ ተንደረደረች የለቀቃት ጎረቤት ንደገና ሊይዛት ከኋላዋ ተከተለ  በእማማ ሩቂ ቀሚስ ስር ሽጉጥ ስል ወደፊታቸው እጀን ጎትተው አጠገባችን በደም ፍላት ለቆመችው አሴ እንዲህ አሏት "ይሄውልሽ ግደይው በያ ፍልጥልጥ አድርጊው ይሄው "ብለው እፊቷ አቆሙኝ አቤት ቅፅበቱ አረዛዘሙ የአሴ መፍለጫ ጫፉ ስለቱ ያብረቀርቃል በቀደም ለበአል እኔ እራሴ ነኝ አባ ሰይድ ቤት አስየው የመጣሁት ለስጋ መከትከቻ ተብሎ በቃ ራሴ ልከተከትበት

ነው!! እያልኩ ሳስብ አሴ በመሃላችን የቀሩትን አንድ ሶስት እርምጃወች መፍለጫዋን ይዛ ወደኔ ተንደረደረችና የመጨረሻዋ እርምጃ ላይ ስትደርስ መፍለጫውን ወደመሬት ጥላ ታፋየ ስር በቁንጥጫ ለመዘገችኝ "እኔ ባንተ ምክንያት ብን ብየ ልጥ ፋ ወይ ?" ል ም ዝ ግ !! "ልሙት? ታንቄ ልሙትልህ ? " ል ም ዝ ግ ዝ ግ ዝ ግ እማማ ሩቂ አሴ እልኳ ሲወጣላት "በይ በቃሽ ወዲያ " ብለው እጇን ነጠቋትና በአሴ ፉከራና ስድብ ታጅበን ወደቤታቸው ወሰዱኝ አይገርምም? ለካስ ጩኸቴን ሲሰሙ ሶላታቸውን አቋርጠው ነበር የሮጡት እማማ ሩቂ የፍቅር ልክ

እኔና አሴን እንዲህ ዱላ ያማዘዘን ፀብ ምን ነበር በእርግጥ ከባድ ጉዳይ ነበር ለአሴ

## ክፍል 2

አሴ ጋር ያጋጨን ጉዳይ ተራ የእናትና ልጅ ግጭት አልነበረም በጭራሽ !! ይልቅ መንደራችንን ሰላም የነሳ..... እድሩን የበጠበጠ ጎረቤቱን ሁሉ ሲያምስ የሰነበተ ጉዳይ ነው እኛም ጓዳ ድረስ ገብቶ ለዚህ ሁሉ ግብ ግብ ያበቃን .......

"ሮዛ ልታገባ ነው"ሲባል ማንም ጎረቤት "የአብረሃም የሳራ" ጋብቻ አላለም ይልቅ የተመካከረ ይመስል ጎረቤቱ በአንድ አፍ "ቱ ይድፋሽ " ነው ያላት!! ሮዛ ሳትደፋ የሰርጓ ቀን ደረሰ !! እንደውም አንዳንዱ ሰው እርግማን ይስማማዋል መሰል አማረባት !ለነገሩ ድሮም ቆንጆ ናት...

እንግዲህ ታፍሮ እናተከብሮ የኖረ መንደራችን.... በቤተክርስቲያን ቅዳሴ በመስጊድ አዛን ሲባረክ የኖረ ሰፈራችን ....."ጴንጤ" የሚባሉ ..."ሰይጣን ጋር እንዲህ እንደጓደኛ ቁጭ ብለው የሚያወሩ ...የተነፈሱበት ላይ ሁሉ ጽንጥጥናቸውን እንደጉፋን የሚያጋቡ "ጉዶች" ገቡበት" ተብሎ ለጉድ ተወራ ..."ልጆቻችሁን ያዙ ነጭ ሸንኩርት የማይመልሳቸው ቡዳወች ናቸው " ተባለ ...."እንደውም እዛታች ሰፈር በቀደም የሞተው... የሻምበል ቶሎሳ ልጅ እነሱ በልተውት ነው ...እንዲቹ እንቃዣ እና እንደቀዣበረ አንድ ፍሬው ልጅ በአጭር ቀረ ...ነብሱን ይማረውና ሴት ይወድ ነበር ...አንዷን ሴት ጴንጤ ተከትሎ ሱክ ሱክ ሲል እሷው ናት ቅርጭም አድርጋ የገላገለችው ..." ተባለ

ብቻ ያልተባለ ነገር ያልተነዛ ፍርሃት የለም ! በዚህ ሁኔታ እያለን "የእማማ አይናለም ልጅ ሮዛ የጴንጤወቹ አዳራሽ ስትገባ ታየች" ተባለ .... "አይ ስትወጣ ነው የታየችው" አሉ ሌሎች ... "ካልገባች አትወጣም ያው ነው " በሚል ሃሳብ ጎረቤቱ ተስማማና ሮዛ አስደፈረችን ብሎ ሲሸልል ሲፎክር ከረመ ጎረቤቱ ቀኝ አዝማቿ ማን ናት....አሴ!!። ሮዛ ይግረማችሁ ብላ እሁድ ጧት ጥቁር መፅሃፍ ቅዱስ (ሰይጣን ስለሆኑ ነው ጥቁር መፅሃፍ የሚይዙት ይባላል) ይዛ ወደጴንጤወቹ ግቢ ስትገባ ታየች ....

ያን ጊዜ ድፍን ጎረቤቱ ጉብታዋ ላይ ተሰብስቦ ልክ ጉድጓዷ ውስጥ እንደምትገባ የጎልፍ ኳስ ትንፋሹን ውጦ ሮዛን ከመነሻዋ እስከመድረሻዋ ተከታተላ "ሄደች ... ተጠጋች ...ቀረበች" እና የግቢውን በር እግሯ እልፍ ከማቱ ሁሉም ባንድ ላይ ተንጫጫ... "ወይ ድፍረት ...ወይ መለከፍ ....አስደግመውባት ነው ..." አሴ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ....ሮዛን እንደነብሷ ነበር የምትወዳት

የመንደራችን እድር ይሄን ጉዳይ እንደቀልድ አላየውም መጀመሪያ እማማ አይናለምን ልጃቸውን እንዲመክሩ አስጠነቀቃቸው እማማ አይናለም ግን እያለቀሱ "እኔ እንዳሻት ትሁን አንድ ልጅ ተበሳጪታ ወዳንዱ አገር ብትሄድብኝ ምን ይውጠኛል " አሉ

መንደሩ ቀስ በቀስ እችን ባልቴት አገለላቸው... ፀበል ቤት ሲሄዱ ጎረቤቱ ሁሉ እሳቸው አጠገብ ላለመቀመጥ ሲያፈገፍግ የቀረበላቸውን ጠበል ፃዲቅ ሳይቀምሱ ተሸማቀው ወደቤታቸው ይመለሳሉ ....

አንድ ቀን የሸወርቅ የምትባለው ሴትዮ(የሰንሰል አጥር ነው ከእኛ ቤት ጋር የሚለያየን አሴ ጋር በዶሮውም በምኑም ይጣላሉ) እና የዚች ሴትዮ እህቷ ሙታ (ትልቅ ሰው እህት የሚኖረው አይመስለኝም ነበር) እማማ

አይናለም ሊያስተዛዝኑ ሻይና ዳቦ ይዘው እቤቷ ሄዱ.... ለወትሮው ቢሆን የእዝን ሲመጣ ጎረቤት ይጠራና የመጣው ነገር እየተበላ እየተጠጣ ሃዘንተኛው ይፅናናል ...

ወዲያው የጎረቤታችን ሰራተኛ በሩ ላይ ቁማ "እትየ አሰለፍ ኑ ቡና ....እትየ ዘሙ ...እማማ ሩቅያ ...አስቴር ..." እያለች ሁሉንም ጠራች አሴ ወዲያው ድምጽዋን ቀንሳ ጠራችኝ "አቡቹ" "እ" "ማነው የእዝን ይዞ የገባው " "እማማ አይናለም ናቸው (ምራቋን ዋጥኩና) ሻይና ትልቅ ድፎ ዳቦ...." ብየ ሳልጨርስ "ዝም በል! ማን ያመጡትን ጠየቀህ" አለችና ወደውስጥ ገባች። አሴ ሳትሄድ ቀረች !ጎረቤቱ ሁሉ ሳይሄድ ቀረ እማማ ሩቅያ እራሳቸው ሳይሄዱ ቀሩ ግን እሳቸው አመፁ ውስጥ ተሳትፈው አይመስለኝም ትልልቅ ባለጥምጣም ሰወች እቤታቸው መጥተው "ዱአ" እያደረጉ ነበረ።

ትንሽ ቆይቶ እማማ አይናለም አንገታቸውን ደፍተው እጆቻቸውን ወደኋላ በማድረግ ወደቤታቸው ሲያዘግሙ አየኋቸው ...ስላረጁ ወገባቸው ጎብጧል ከድሮ ጀምሮ ባል የላቸውም ሮዛ ብቻ ናት ልጃቸው ጎረቤቱ ሁሉ የሚያከብራቸው ንፁህ ደሃ ነበሩ !!

የጎረቤታችን ውሻ ሲያጉረመርም ሰማሁና በሰንሰል ቅጠል ወደተከለለው አጥር ጠጋ ብየ ሳይ ትልቅ ድፎ ዳቦ የታሰረበት ላይ ተጥሎለት እየተስገበገበ ይቦተርፈዋል አቤት የዳቦው ንጣት ውስጡ የተባዘተ ጥጥ ይመስላል ... ከውሻው ቤት አለፍ ብሎ አጥሩ ጥግ ያለ ቆሻሻ ውሃ መድፊያ ላይ ሰራተኛዋ እንፋሎቱ ለጉድ የሚጉተለተል ሻይ ትደፋለች.......

ወደቤት እሩጨ ገበሁና " አሴ ...አሴ...እማማ አይናለም ያመጡትን ...ዳቦ ሰራተኛዋ ለቦቢ ሰጠችው ...ሻዩን ደሞ...." አሴ ሳወራ የማወናጭፈውን እጄን በማማሰያ ቀለጠመችኝ... አቤት እንዴት እንዳመመኝ እንቅ አድርጋ ታፋየ ላይ አንዴ ከጨመረችልኝ በኋላ "ሁለተኛ እችን አይነት ወሬ ለሰው ታወራለህ " አለችኝ ልትመታኝ እየቃጣች "አላወራም አሴዋ..ማሪያምን አላወራም " "አይተሃል" "አላየሁም" "ሂድ ወዲያ..." ብላ ወደበሩ ገፋችኝና አውቃ በማማሳያው ሳተችኝ .....ከዛ በኋላ ለአንድ ሰው አላወራሁም !! አንዲት ነገር.... እንኳን ድፎ ያ የተረገመ ውሻ የአሴን ጫጬት ቀም አድርጎ ሲበላት ያየሁ ቀን አልነገርኳትም ዝም!!

ሌላ ቀን ደግሞ አባ መልኩ (የመንደሩ ሁሉ ነብስ አባት) እማማ አይናለም እንዲያሳልሟቸው ወደሳቸው ሲሄዱ ያላዩዋቸው መስለው ሲያልፏቸው እማማ አየናለም "እውነት የለህማ" ብለው ሁለት እጃቸውን ወደሰማይ ዘርግተው አለቀሱ ገርሞኝ አየኋቸው ...

ይሄ ሁሉ ሲሆን መንደርተኛው እማማ አይናለምን በአደባባይ አልዘጋቸውም እንደድሮው ሰላም ይላቸዋል "ተሻለዎት" ይላቸዋል... እያለ ግን ያሳምማቸዋል አቤት ጎረቤቱ ሰላምታ እያሞቀ ሰላም መንሳት ሲችልበት ...እየሳቁ ማኩረፍን እንዴት ነው የተካኑበት ...

ሮዛ በጣም ቆንጆ ልጅ ናት ባዛ ላይ ጨዋ "እግዜር አሚልቶ የሰጣት" ይላት ነበር ጎረቤቱ እንደዛሬው "አሚልቶ የቀማት" ተደርጋ ሳትታሰብ በፊት ! የመንደሩ ጎረምሳ ሁሉ ሮዚ ነው የሚላት በሌለችበት ይሰድቧትና ..."መናፍቅ የሰይጣን ግልገል " ይሏትና ስትመጣ ተጠምጥመው ይስሟታል እውነቱን ለመናገር ሮዛ እንደእናቷ አልተገለለችም .....

አሴ አንድ ቀን ሌሎች ጎረቤቶች ጋር ተሰብስባ ስለሮዛ ስታወራ (ሲያሙ) "አላየንም ጨዋ እቴ የምትስለመለመው ላካ ሰይጣን ሰፍሮባት ነው " አለች ጎረቤቱ ተስማማ "ሮዛ የምትስለመለመው

ሰይጣን ሰፍሮባት ነው" !! ይሄን ሰማሁና የሮዛን አይን አየሁት ትልልቅ ሁኖ እንባ የኳተረ ይመስላል የሆነ ልታለቅስ ትንሽ የቀራት "ጭፍን ብታደርገው እኮ ይፈሳል" እላለሁ እናም የራሴን አይን እጨፍነዋለሁ ... ሰይጣን ማለት ፈሳሽ ነገር መሰለኝ አይኗ ውስጥ እንባ መስሎ የተኳተረ ወይ አይጠፋ ወይ አይፈስ .....የራሴን አይን በመስተዋት ሳየው "ሰይጣን" የለኝም ....

እሮዛ ከዛሬ ነገ “ሰይጣኗ” ይለቃታል ሲባል ጭራሽ አስማማው የሚባለውን የሰፈራችንን ዱርየ ወደጴንጤወቹ ቤት ወሰደችው እሷ “ቸርች” ነው የምትለው ...ጎረቤቱ አሁን ለየለት ....የነአሴ እድር ዋናው ሰውየ ጋሽ ታደሰ እሁድ ቀን እነኤሊያስ ሰፈር እንጀሪው ዛፍ ስር ስብሰባ ጠራና እማማ አይናለምን ከፍ ዝቅ አድርጎ እንደህፃን ልጅ ተቆጣቸው ....

“የራስዎ ልጅ ለራሷ መባለጓ ሳያንስ ጭራሽ ልጆቻችንን እያታለለች ወደመናፍቅ ቤት ትወስድ ጀመረ ...እርሰወ ጠላታችንን እያበሉ እያጠጡ ... እንዴት ነው እኛ ጋር መሃበር የሚጠጡ ...ከቤተዎ ወዲያ ያባሩና ለኛም ሰላም ስጡን ብንል አልሰማ አሉ ......ነውር አይደለም እንዴ ...የናት ያባቶቻችንን ማተብ በርሰወ ልጅ ምህኛት ካንገታችን ሲበጠስ ... እንዴት እንዴት ነው ነገሩ ዝም ማለተዎ ....” አለ እየተንቀጠቀጠ

እማማ አይናለም አንገታቸውን ደፍተው ዝም አሉ

“ይናገሩ እንጅወ/ሮ አይናለም እንግዲህ እኛ አብረን ኑረናል..አብረን አርጅተናል ብለን እስካሁን ቻልን ... ከዚህ ወዲያ እንግዲህ እርሰወ ጋር መጎራበቱም አያሻን ...ሳትሰብከዎት አልቀረችም ...እቤተዎ የገባው ሰይጣን ቀላልም አይደል እንዲህ ያፈዘዘዎት...ሃዲያ ምን ቢሆን ነው ...” ሰውየው ጥያቄው ከምክሩ ምክሩ ካስተያየቱ አይለያይም ....

“እኔ እንግዲህ ያረጋችሁትን አርጉ እንጅ ልጀን አባርሬ ላሞራ አልሰጥም ...ለየትኛው እድሜ ...” ብለው አለቀሱ ...ጎረቤቱ ተበሳጨ “ኤዲያ ያዘ እንባ” አላቸው አሴም ብላለች ....

የእድሩ ሊቀመንበር በብስጭት እንዲህ አለ “እችን ሴትዮ ዘመድ ወዳጅ የሆናችሁ ምከሩ! በእኛ በኩል ኮሚቴው ተማክሮ አንድ ውሳኔ ያሳልፋል “ አለና አንድ አምስት ሽማግሌወች ሰብሰብ ብለው ያንሾካሹኩ ጀመረ(ኮሚቴው ነው ) ....ጎረቤቱ እማማ አይናለምን መከረ ዘከረ “ሮዛን ለጊዜው ወደዘመድ ይላኳት እራቅ ስትል ትረሳዋለች “ አሏቸው “ምን ዘመድ አለኝና ወዴት ልላካት.... አልደረሰችባችሁ ምናለ እንዳሻት ብትኖር” አሉ የከበባቸውን ጎረቤት በምሬት እያዩ ........

ኮሚቴው ወሰነ!!

“እንግዲህ መክረናል ዘክረናል በእድራችን ተሰምቶም ታይቶም የማያውቅ ነገር ነው ይሄ...ለሌላውም መማማሪያ እንዲሆን ወሮ አይናለም ላይ “ደንጎራ ይዘናል” (ቢሞቱ ወይም ዘመድ ቢሞትባቸው አንቀብርም ) የሚቃወም ካለ ይናገር “ አለ ሊቀመንበሩ ሁሉም መስማማቱን በዝምታው ገለፀ ....ምድር ጥግ ድረስ የሚሰማን ጩኸት በዝምታ የሚገልፅ ጎረቤት !! የእማማ አይናለም ሳግ ብቻ ነበር የሚሰማው ...የዱርየው አስማማው አባት “ልክ ነው እንደውም ዘግይተናል” አሉ የልጃቸው ጉዳይ ሆድ ሆዳቸውን ሲበላው ኖሮ!

ሊቀመንበሩ “እንግዲህ ስብሰባችንን በዚሁ.....” ብሎ ሳይጨርስ..... የመለአክ ድምፅ ...የፍቅር ድምፅ ... የሰላም እና የአንድነት ልሳን ከእድርተኛው መሃል ተሰማ ከነግርማ ሞገሱ.......እማማ ሩቅያ.....

“ያላችሁትን ሁሉ ሰማሁ ... እንግዲህ ወላሂ ብያለሁ ... እኔም ብሞት አንድ ሰው በሬ እንዳይደርስ .....እናተም አላህ አያምጣባችሁ በራችሁ አልደርስም” አሉና ወንበራቸው ላይ ተመቻችተው ቀጠሉ “....እናተ በአላህ ቦታ ናችሁ...... ማን ይቅደም ማን ይከተል የሚያውቀው አንድየ ነው (ወደሰማይ እያዩ) ቀባሪም ከአላህ ዘንድ ነው ...እንኳን አብራን የኖረች በክፉ በደጉ ብዙ ያየን መልካም ጎረቤታችን .... ይሄ እድር ስንቱን እግር የጣለው ሚች አንስቶ አልቀበረም ... አልቀበረም ወይ ... ማን ባቀናው እድር ማን አፈር ይከለከላል ....እንደው እንዴት ያለው ዘመን ላይ አደረሰን .....” አሉ በቁጣ እየተንቀጠቀጡ ማን ይናገር ጭጭ!!

አሴ ቀስ ብላ “ሩቁ ኸረ ሰው እብድ ይለዎታል ይተው “ አለቻቸው “ዝም በይ ...እኔ ሩቅያ አላህን አምኘ ነው የምኖረው ሰው አሁን ታይቶ አሁን የሚጠፋ ያለውን ቢል ምናሻኝ ....እንግዲህ ጨረስኩ! ካሁን በኋላ ማንም እቤቴ እንዳይደርስ እኔም አንድ ሰው ቤት አልሄድም ... ወላሂ ብያለሁ ...ክፉዎች! ...እኔ ሰው ጋር ተጎራበትኩ ብየ

ነበር እንጅ አውሬ ሁሉ !! ብለው አሴን ተደግፈው ተነሱና ወደቤታቸው መንገድ ሲጀምሩ እድርተኛው እየተኝጫጫ እየተውካካ ተከትሏቸው ተመመ....

ላበሳጫችሁ ፈልጌ ሳይሆን ...በቃ

# ክፍል 3

ትልቅ ትንሽ ሳይል የመንደሩ ሰው በእማማ ሩቅያ ቁጣ ደነገጠ የማንንም ልመናና ሽምግልና ከመጤፍ ሳይቆጥሩ እቤታቸው ገቡና እድርተኛው ላይ የግቢውን በር ጠረቀሙት አዘጋጋቸውን ላየ ለዘላለሙ የሚከፍቱ አይመስልም ነበር ሰው ላይ ሳይሆን እብድ ውሻ ላይ የዘጉ ነው የሚመስለው ሊነክስ እብደቱን ሊያጋባ የሚሮጥ እብድ ውሻ ላይ ጥርቅም በሩን! የሚለያዩ የሚከፋፈሉ "እኛን ካልመሰላችሁ" ብለው የእግዜር አፈር የሚከለክሉ ላይ ጥርቅም የሩቂ በር!! የመለያየት ቆሻሻችሁን የአድሎና የወገንተኝነት እድፋችሁን ይዛችሁ የፍቅር ግቢየን መርገጥ የለም እዛው የለመድሽበት እያንዳንድሽ !! ባማረ ቃል ብትሸፍኑት ባነጋገር ብታሳምሩት በእድር ህግ ህጋዊ ልታደርጉት ብትሞክሩም ክፉት ያው ክፉት ነው ጥርቅም !!

ጅራታችሁን ሸጉባችሁ ክፋታችሁን የምታዝረበርቡ እብድ ውሾች የነከሳችሁት ሁሉ ያው እብድ ነው እነውሾ.. እነ ሊቀመንበር እነፃሃፊ እነ ተራ አባል አሽቃባጭ አሽሟጣጭ እነወሬ አቀባይ ሁሉ ጥርቅም በሩን !! በራሴ በር ክፊች የሚል ወንድ ማነው ወንድ ውሻ ማነው ወንድ ያበደ ውሻ ማነው ተከትሏቸው ሲግተለተል የነበረው አጀብ ሁሉ ግቢያቸው በር ላይ ቁሞ ይታመስ ጀመረ እየተንጠራራ በጥፍሩ እየቆመ በአጥሩ ፋካ ወደውስጥ ሊያይ የከፉ አይን ቡዳ ነው ሩቂ ቤታቸው ውስጥ ገብተው የቤቱንም በር ዘጉ ጎረቤት ታመሰ እድርተኛ ታመሰ መታመስ ይነሰው ? ሲቸገር በችግሩ ደራሽ፣ ሲራብ አጉራሹ ነበሩ ለመንደርተኛው ማነው የእማማ ሩቁን እጅ ያልቀመሰ ? እድሩ ራሱ እንደዛሬው ሰሃን ሳይገዛ የውሃ ኩባያ ሳይኖረው "እማማ ሩቂ ውለው ይግቡልን" እያለ በእርሳቸው እቃ ነበር የሚጠቀመው ሁልጊዜ ከተበላና ከተጠጣ በኋላ ለማማ ሩቂ ይጨበጨብላቸው ነበር "ወይ እናት ለሚሰበር ሰሃን " ብለው ፈገግ ሩቂ የደግነት ጥግ

( ሰሃኑን ሳነሳ የኔ ቢጤው ትዝ አለኝ ቆይ እችን ልንገራችሁ ) እድሩ ልክ እንደራሱ ሰሃን እማማ እሩቂ ነጫጭ ሰሃኖች ላይ ከኋላ በኩል በ ቀይ ቀለም " ምግብ ማስተረፍ ብር ተስሙኒ ያስቀጣል " ብሎ ፃፈበት አርባ ሁለት ሰሃን ላይ! ባለቤቷን ሳያስፈቅድ!! እማማ ሩቂ ራሳቸው ፅሁፉን አላዩትም ቆይቶ እቤታቸው ለመጣ አንድ የኔ ቢጤ ግማሽ እንጀራ በዚሁ ሰሃን ሰጡትና እዛው በረንዳው ላይ ተቀምጦ በሶስት ጉርሻ ጨርሷት በሳቅ ፍርስስስ አለ "ምነው?" አሉት ሩቂ "ነካ" ያደረገው ሰው መስሏቸው ፈራ ተባ እያሉ " ኧረ እኔስ ጡህፌቱ አስቆኝ ነው እናቴ" አለ ባዶውን ሰሃን ገልብጦ እያሳያቸው "አሃ የምን ጥሁፍ ነው ማነው የጣፈው ?" አሉ ሩቂ ግራ ተጋብተው " ጠሃፊውን ምን አውቄ ብለው ከዚች ግማሽ እንጀራ ምን ይተርፋል ብሎ ይሄን ሁሉ ጣፈ ብየ ገረመኝ እንጅ " ብሎ የምሬት ሳቁን ቀጠለ " ምግብ ማስተረፍ ብር ተስሙኒ ያስቀጣል ሃሃሃሃሃ ወቸ ጉድ " !!

የኔ ቢጤው ሳቁን ቆም አደረገና እንዲህ አለ "ቴሌቪዥኑም "ከምግብ በፊት እና በኋላ እጃችሁን ታጠቡ" ይለናል በቀደም የነፃ አስወጥቸ ልታከም ጤና ጣቢያ ብሄድ አንዲት ሴት "ላስተምራችሁ" ብላ "ምግብ በመጠኑ ስሩ በተቻለ መጠን አታስተርፉ ሲተርፍባችሁ ግን ከድናችሁአስቀምጡ ያስ ቀመጣችሁትን ስትበሉ አሙቁ " እያለች ለፈለፈችብን እኔ ደሞ ሃኪሙ ጋ ስንገባ "እህል ሊሰጡን ይሆን እንዴ?" እያልኩ በአፌ ምራቅ እየሞላ ትምርቱን ሰማሁ !! ግ ን ሃኪሙ በጥያቄ ሲያናዝዘኝ እና ሲመረምረኝ ውሎ " ህመምህ የምግብ እጥረት ነው" አለኝ "ይሄንማ መች አጣሁት ዶክተር?" ብለው ተቆጣና መዳኒት እንድገዛ ጥፎልኝ "ይሄን ግዛና ከምግብ በፊት እና ከምግብ በኋላ ዋጠው " አለኝ አሁን ደሞ እርሰዎ "ማስተረፍ ክልክል ነው " ሃሃሃሃሃ ኧረ ለመሆኑ እንኳን የሚተርፈው የሚያጠግበው እህል ወዴት ነው ? "ቀድሞ ሙችና ሰደቃሽ ይውጣ " አሉ " ብሎ ብቻውን እየለፈለፈ ሄደ ከዛን ቀን በኋላ እማማ ሩቂ ለኔ ቢጤ ሙሉ እንጀራ መስጠት ጀመሩ

***

ሩቁ ተቀየሙ ማሪያምን ተቀይመዋል!! ከማንም በላይ እኔ ነኝ የማውቃቸው ተቀይመዋል ! ሲቆጡ ጉፍታቸውን አስር ጊዜ ያስተካክላሉ ዛሬም ከስብሰባው ቦታ ቤታቸው እስኪደርሱ አምሳ ጊዜ ይሆናል ያስተካከሉት መንደርተኛውም እድሩም በራቸው ላይ ቁሞ ሲንሾካሾክ ቆየና መበታተን ጀመረ ሁሉም ተበታትኖ ሲሄድ እማማ ሩቁ በር ላይ ማን ብቻውን ቆመ ? እኔ!! ቆይ ግን እኔ የዚህ ሰፈር ሰው አይደለሁም? እና ተመካክረው ሲበታተኑ እንሂድ አይሉኝም? ወይስ እኔ የማላውቀው ቋንቋ አላቸው የመበታተን የመለያየት ቋንቋ ? ሾካካ ሁሉ !! ወይ ከተበታተኑት አልሆንኩ ወይ አኩርፈው ቤታቸውን ከዘጉት ብቻየን እንደቆምኩ አንድ ውሻ እማማ ሩቁ አጥር ላይ ሽንቱን ሲሸና አየሁ ድንጋይ አንስቸ ባለ በሌለ ሃይሌ ዥውውው ሳደርገው መሃል አናቱ ላይ ቆራሁት አላዝኖ ተፈተለከ “ነጃሳ!” ብየ ሰደብኩት !! “የገበያ ግር ግር ለነጃሳ ያመቻል”

ቀስ እያልኩ ወደቤቴ አዘገምኩ ዞር እያልኩ ወደማማ ሩቁ ቤት እያየሁ አልተከፈተም!!

እቤት ስደርስ አሴ የለችም ቆይታ ቆይታ መጣች ነጠላዋን አልጋው ላይ ጣል አድርጋ ቆም ብላ እንደማሰብ ካለች በኋላ “ አቡቹ ና ቡና ገዝተህ ና ከበድሩ እንዳትገዛ ይሄ ቆንቋና “ ብላ መሃረሟን ፈታችና ሳንቲሞች ሰጠችኝ

ቡናውን ስትወቅጥ ከወትሮው የተለየ አስጮኸችው ጓ..ጓ ጓ ደግሞ ሁለት ጊዜ የሙቀጫውን ጉድጓድ ስታ እጇን ልትቀረጥፈው ለትንሽ ሳተችው አሴ ነገር ይዛለች በሆዷ ቡናውን ወቅጣ እና ጀበናው ውስጥ አስገብታ እንደጨረሰች ካለወትሮዋ ነገረኛዋ ጎረቤታችን ጋር በአጥር እየተንሾካሾኩ ያወሩ ጀመር “አሴ አልባሌ ቦታ ዋለች”!! አልኩ ለራሴ የነገረኛዋ ውሻ የታሰረበትን ሰንሰለት እየታገለ አሴ ላይ ይጮሃል እኔም ውሻ ብሆን ኑሮ አሴ ላይ እጮህ ነበር እንዴት እማማ ሩቁ የሚባሉ መለአክ ጋር ስታወራ የኖረች አሴ ተምዘግዝጋ ጭቃ ላይ ትወድቃለች

ቡናውን አቀራርባ ስትጨርስ ወደእማማ ሩቅያ ቤት ፊቷን አዙራ ለመጣራት ተዘጋጀችና ድንገት ሃሳቧን ቀይራ “አብረሃም “ አለችኝ (ነገር አለ ማለት ነው ሙሉ ስሜን ጠራችኝ “ “እ” “እ አቤት አትልም?” ብላ ተቆጣች (ቅድመ ማስፈራሪያ ናት እች ነቅቻለሁ) ሂድ እማማ ሩቅያን ቡና ጥራ” (ሩቁ አላለችም) “እምቢ” አልኳት ትካሻየን ንጨ አሴ ፈገግ ያለች መሰለኝ ወዲያው ልክ እንደዘፋኝ ጉሮሮዋን “እእህ እህህህ ” ብላ አፀዳዳችና “ሩ ቁ “ አለች..ከዛም ጀሯን አቁማ መልሳቸውን በጉጉት ጠበቀች “ለበይክ” አሉ ከወትሮው ባልተለየ ድምፅ ገረመኝ ይዘጓታል ብየ ነበር

“ቡናው ወርዷል “ አለች አቤት ማለታቸው ስላደፋፈራት ሁለተኛው ድምፅ ከመጀመሪያው ጠንከር ያለ ነበር “አልመጣም እዛው ጠጭ!! “ አሉ!!

እማማ ሩቁ በታሪክ ቡና ሲጠሩ “መርሃባ” ከምትለው ቃል ውጭ ተናግረው አያውቁም ነበር በቃ ሳይመጡ ቀሩ ነገ ሲባል ዛሬ ሲባል ድፍን ሳምንት ቡና ሳይመጡ ከቤታቸውም ሳይወጡ ቀሩ ሽማግሌ ተመርጦ ወደቤታቸው ቢላክም በኩርፊያቸው እንደፀኑ ቆዩ !! እኔንም አያናግሩኝም ለነገሩ የት ተገናኝተን እቤታቸው እንዳልሄድ ፈራሁ !

***** ***** *****

እማማ ሩቁ “ኢብሩ “ አሉኝ አንድ ቀን ቅዳሜ ጧት (እንኳን እማማ ሩቁ ተጨምረውበት እንዲያውም ቅዳሜ ነፍሴ ነች ) እንዴት ልመን ? አሴም ደንግጣለች እንኳን እኔ “አ..ቤ ት “ አለች አሴ ( በሰበቡ ልትታረቅ ሂሂሂ) “አንችን አልጠራሁም ኢብሩ ነሽ አንች ? “ አሉ አሴ እየሳቀች ገባችና “ሩቁ ይጠሩሃል” አለችኝ ( አይ አሴ አብረን እኮ ነው የሰማናቸው ) እየበረርኩ ወደቤታቸው ከመቸኮሌ ብዛት በረንዳቸው ላይ ቁመው ሳላያቸው አልፌያቸው ልገባ ነበር “ቀስ ይሄ ቆርቆሮ እንዳይቀድህ ” አሉና ከሩቅ አገር እንደመጣ ሰው አገላብጠው ከሳሙኝ በኋላ “አንተ ጀሯም ከጀመአው ጋር አብረህ ማኩረፍህ ነው “ አሉ “ኧረ እኔ ማሪያምን ያንቱ ጋራ ነኝ !!” አልኳቸው ከልቤ ነበር ሰውነታቸው እየተርገፈገፈ እንባቸው ጠብ እስኪል ሳቁና “በል ሂድ ጫማህን አርግና ና የምንሄድበት ቦታ አለ” አሉኝ ሌላ ጊዜ ቢሆን እማማ ሩቅያ ጋር የትም መሄድ አልወድም ነበር ምክንያቱም በየመንገዱ ሰላም የሚላቸው

እያቆመ ብዙ ሰአት የሚያወራቸው ሰው ስለሚበዛ ይሰለቸኛል ዛሬ ግን ወደቤቴ ሮጥኩ አሴ በጉጉት ታየኛለች ጫማየን አንድ እግሩን ካልጋው ስር አንዱን በስንት ፍለጋ ከባለመደገፊያው የቀርቀሃ ወንበሩ ስር አግኝቸ አጠለኩትና ወደ እሩቁ!!

የሄድነው ባንክ ቤት ነበር ብዙ ብር አወጡ መቶ መቶ ደግሞ አምሳ አምሳ ሲቆጥሩ ሲቆጥሩ እኔ ልክ እንደቱሪስት ባንክ ቤቱን ቃኘሁት  እንዴት ደስ እንደሚል ሳድግ ባንክ ቤት ነው የምሰራው አንዷት ሴትዩ የተቆለለ ብር በሁለት እጇቿ አቅፋ ወደዛ አለፈች ጫማዋ ግን ከወደተረከዙ ጠመም ያለ ነበር "ይሄ ሁሉ ብር እያላት እንዴት ጠማማ ጫማ ታደርጋለች?? ስስታም መሆን አለባት"  ግን በዚህ ሁሉ ብር ምን ልትገዛ ይሆን ? ለካ እነ አሴ "ብር አጣን" እያሉ የሚነጫነጩት ብሩን ሁሉ እዚህ ደብቀውባቸው ነው እና ሌላም ብዙ ነገር አሰብኩ !!

ስንመለስ ሩቁ ከሆነ ኬክ ቤት በአረንጓዴ ለስላሳ ወረቀት የተጠቀለለ ኬክ ገዙልኝ ክሬሙ የተጠቀለለበተን ወረቀት አልፎ እጀላይ ስለፈሰሰ መንገድ ላይ ቀልጦ እንዳያልቅብኝ ፈራሁ "በቃ ወረቀቱን ስከፍተው ባዶ ቢሆንስ ? በስማአብ! " ኬኩን የያዝኩበትን እጀን ባቀያየርኩት ቁጥር ነፃ የሆነውንና በክሬም የወዛውን የእጀን መዳፍ ከታች እስከላይ በስስት እልሰዋለሁ እሩቁ ይቆጡኛል "እንዲህ አይደረግም መንገድ ላይ ኢብሩ " "እሸ" እላቸውና ወዲያው እረሳዋለሁ ላ ስ.. ሲጣፍጥ!!

*** *** ***

ሁልጊዜ የምትሸከመኝን ድንጋይ ዛሬ ተሸከምኳት

ወደእኛ ቤትና ወደ እማማ ሩቁቅያ ቤት መለያያዋ ላይ ስንደርስ ኬኳን ለመብላት ተጣድፌ እሩቁን ቻው እንኳን ሳልላቸው ወደቤቴ ሮጥኩ እቤቴ ዘው ስል የአገር ሰው ቤቱን ሞልቶታል ኤጭጭጭጭ ሰው ከገዛ ቤቱ የት ሂዶ ኬክ ይብላላቸው !! የእድር ዳኛው ፣የእድር ፀሃፊው ባጠቃላይ ኮሚቴው ብቻ የቀረ ሰው የለም አሴ ገና ከመግባቴ "እሰይ መጣህ ?" አለችኝ  " ጎረምሳው መጣህ ?" "መጣህ?" ምን ጉድ ነው  ተንጫጩብኝ እድሩ ከዚህ በፊት የቀበረው ሰው ተመልሶ የመጣ እንጅ እኔ የመጣሁ አይመስልም እኮ አሴ ኬኩን ከእጀ ተቀብላ (ቀምታ ነው እንጅ ደሞ "ተቀብላ " ብየ አሳምርላታለሁ እንዴ) ወደ ውስጥ አስቀምጣ ከተመለሰች በኋላ እድርተኛው ሲመካከር የዋለውን ነገረችኝ

ምክክሩ ሊያስቀኝ ነበር ጨዋታ ነው የሚመስለው እማማ ሩቁ "የእኔ ነገር ስለማይሆንላቸው" (እንደአሴ አባባል ) የእድር ኮሚቴውን "እኔ" እየመራሁ ወደቤታቸው "ቀጥ ብለን" እንገባለን ሰአቱ ደግሞ ከሶላት ሰአት በፊት መሆን አለበት  ታዲያ ባዷችንን አይደለም "ድንጋይ ተሸክመን!!" ወላ ሊቀመንበር ወላ ፀሃፊ ወላ ገንዘብ ያዥ ወላ አባል ሁሉም ድንጋይ ተሸክሞ በ"አብርሽ" መሪነት ወደማማ ሩቁ ቤት ሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂሂ ድንጋይ ራስ ኮሚቴ ድንጋይን ተሸከማት ! " ስቶን መሸከም ምን ነበር በእንግሊዝኛ ?" ሂሂሂ !

አሴ ጋር በድንጋይ ምርጫ ተጣላን ኮሚቴው የየራሱን ድንጋይ ከየአጥሩ ስር መርጦ እየሞከረ አሴ እኔ የመረጥኩልህን ካልተሸከምክ ብላ ክችች አትልም ? "እንዴ አሴ እኔ እሱን አልችለውም " እያልኩ ተነጫነጭኩ "ዝም በል! እች ታቅተሃለች? ዳንኤል ወይ ኡስማን ቢሆኑ ኖሮ እስካሁን ያንከበክቧት ነበር " ስትለኝ እልህ ያዘኝ (ዳንኤልም ኡስማንም ጓደኞቸ ናቸው) እናም ሁሌም እግሬን ስታጠብ ውጭ ጋር የምቀመጥባትን ጥቁር ድንጋይ ፈንቅየ ተሸከምኳት..አቧራው በአንገቴ ገብቶ ኮሰኮሰኝ "እ ከበደህ ? " አለችኝ አሴ አንጀቷ አልችል ብሎ በሁለት እጇቿ ትካሻየ ላይ ያረፈውን ድንጋይ ይዛልኝ "ልቀቂው "አልኳት በእልህ ስትለቀው ክብደቱ ጨምሮ ገድገድ አልኩና በአሴ ድጋፍ ሚዛኔን ጠብቄ ቆምኩ የእድሩ ሊቀመንበር "መከበዱ ጥሩ ነው አሰለፍ ጥሩ ነው ካላቅሙ ይሄን ተሸክሞ እየተሸመደመደ ፊታቸው ሲቆም አዝነው ቶሎ እሸ ይሉናል" አለ ምናይነቱ ነው ራሱ ባመጣው ጣጣ እኔ ላይ "ሙድ ይይዛል" እንዴ

መንገድ ጀመርን ድንጋይ የተሸከመ ሰለልፈኛ "በለፈለፉ ድንጋይ ይዘው ይሰለፉ"ሃሃሃሃ ከእኛ ቤት ወደእማማ ሩቅያ ቤት የሚወስደው መንገድ በዋናው በር በኩል አቀበት ናት እናም ስንሄድ ሰንበት ትምህርት ቤት የምንዘምረው መዝሙር ትዝ አለኝ " መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ "

የግቢውን በር በትካሻየ ገፍቸው ከነአጀቤ ወደውስጥ ስገባ ሩቂ በኡዱ እቃቸው (ጡሌ ነው የሚት አንገተ ረዥም ቅል) ከቧንቧ ውሃ እየቀዱ ነበር ዞር ብለው እንዳዩን በግማሽ ሞልቶ የነበረው የኡዱ እቃ ከእጃቸው አምልጦ መሬት ላይ ዘጭ አለ እማማ ሩቂ ደነገጡ በጣም ደነገጡ

አጠገባቸው ደርሰን እንደቆምን አሴ ያስጠናችኝን ተናገርኩ "እማማ ሩቂ በማሪያም አፉ በሉን " ድንጋዩ ከብዶኝ ስለነበር እያቃሰትኩ ነበር የምናገረው ተንደርድረው መጥተው ድንጋዩን ከትካሻየ ላይ ሊያወርዱት ሲሉ "እምቢ ካልታረኩን አላወርድም" አልኩ ተከታዮቸም ይሄንኑ እየተቀባበሉ ተንጫጩ "ኧረ ላላህ ብላችሁ አውርዱልኝ መአት አታምጡብኝ አላህ ነው የሚለመነው ሰው አይለመንም አስታፉረላህ " "እሽ በሉን " "እሽ እሽ እሽ ይሄው እሽ አልኩ አውርዱ " "ወላሂ ታርቂያቸኋለሁ በሉ እስኪ"አልኳቸው ይሄን ማንም በል አላለኝም ግን ሸውደውን እንደገና ድንጋይ እንዳያሸከሙኝ ፈርቸ ነው

"ወላሂ ይሄው ሶስት ጊዜ ወላሂ " ብለው ድንጋዩን አወረዱልኝ እፎፎፎፎይ (አቦ የምትወዱት አላህ አዛውን ሁሉ ያውርድልሁ ብያቸዋለሁ በሆዴ) ሌሎቹ የተሸከሙትን ድንጋይ ራሳቸው አወረዱ ከዛ መወቃቀሱ መለቃቀሱ መመካከሩ ተከተለ

ሩቂ የአንድነት አድባር ሰው የመሆን ልክ ወደቤት ካስገቡን በኋላ እኔን ልከው ሮዛን ከነእናቷ አስጠሩና ኮሚቴውን ይቅርታ አስጠየቁት ሮዛና እናቷ አለቀሱ

ሩቂ ኮሚቴውን እንደልጅ ቁጭ አድርገው መከሩት " ምን ቀርጦን እንናቆራለን ? ነገ አገር ምድሩ ክርስቲያን ቢሆን የኔን ልጆች አንቀብርም ልትሉ ነው? ነገ ሙስሊም ምድሩን ቢሞላው የክርስቲያን እሬሳ ለጅብ ሊጣል ነው ? የሚገል አላህ የሚያኖር አላህ እኛ ምን ቤት ነን?

ክርስቲያን ልጆቻችን አረብ አገር አይደለም ያሉት ? ሙስሊሞቹስ ክርስቲያን አገር አይደለም ለእንጀራ የሚንከራተቱት ? አንዷት ያሳደግናት ልጅ ሚንጢ ሆነች ብሎ እንዲህ ይጨከናል ? አስተምረው ከወሰዷት አስተምሮ መመለስ የምን አድማ የምን ማግለል ነው አኮ የምን መ " የጀመሯትን ቃል ሳይጨርሷት " ዋዋዋይ " ብየ ምንጣፉ ላይ መንፈራፈር ጀመርኩ ተሸክሜው የነበረው ድንጋይ ስር ሰፍሮ የነበረ የጉንዳን ሰራዊት መላ ሰውነቴን ወሮ እንደእሳት የሚያቃጥል ንክሻውን እኩል ጀምሮት ኑሯል

ቤቱ ተተረማመሰ ኮሚቴው ልብሴን አወላልቆ የወረረኝን ጉንዳን ማራገፍ ጀመረ እማማ ሩቂ አቶ ወልደ ሚካኤል ሮዛ የሮዛ እናት እስላም..ኦርቶዶክስ ጴንጤ ሳይባባል ከትውልድ ሰውነት ላይ ተናካሽ ጉንዳንን ለማራገፍ ተረባረበ ባንድ አፍታ ነፃ ሆንኩ ቆዳየ በርበሬ መስሎ ቢቀላም

ስንረጋጋ እማማ ሩቂ እንዲህ አሉ "አያችሁ አይደለም ብቻየን ይሄን ጉድ ጉዳን ስለቅም ብውል ይሄ ምንም የማያውቅ ልጅ በማያውቀው ነገር ሲሰቃይ ማምሸቱ ነበር ሳንለያይ ሳንከፋፈል በየእጃችን እንዳቅማችን አራግፈን እፎይ አስባልነው " ሃቅ ነው "እፎይ" ብያለሁ !!

ጉንዳኑ ቢራገፍም እቤቴ ስገባ የጓጓሁላትን ኬክ "ገንባው" የሚባለው የመንደራችን ዱርየ ድመት ጥርግ አድርጎ በልቶ በመጠቅለያ ወረቀቱ ሲጫወት ነበር የደረስኩት !! ከሰአት እማማ ሩቂ ጎረቤቱን ሁሉ ጠርተው ምን የመሰለ የእርቅ አነባብሮ ( ቅቤና በርበሬ የተለቀለቀ ) ቢጋብዙንም የኬኳ ነገር ከሆዴ አልወጣችም ነበር(የእግር እሳት) ግን እማማ ሩቂ የጎረቤቱን የፍቅር እና የመቻቻል ቆሌ ሻንጣውን ሸክፎ ከተሰደደበት የመለሱ የእኔን ኬክ መልሰው መግዛት ያቅታቸዋል?

# ክፍል 4

ሁሉም ሰው ቦታ አለው ቤታችን ውስጥ እንኳን የምንመርጠው ጥግ አውቀንም ይሁን በደመነፍስ የምናዘወትረው ቦታ አለ ሶፋ አለ፣ ዱካ አለ፣ የቀርቀሃ ወንበር አለ ፍራሽ አለ እኔም ቦታ አለኝ ግን እቤት አይደለም

ቦታየ ከጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ጀርባ ትንሽ ጫካ አለች ጫካዋን ገባ እንዳሉ የሰይጣን ወንዝ በቃ ወንዟ አጠገብ ያለችው ለምለም ሜዳ አቤት ስወዳት ዳኒ ነው ያሳየኝ ብዙ ጊዜ አብረን ነበር የምንሄደው ሲቆይ ግን ብቻየን መሄድ ጀመርኩ ማንም ሰው እዛ ድርሽ አይልም!! ሰይጣን አለ ስለሚባል እየፈሩ ነው የማይሄዱት

እኔም ታዲያ ሰፈሬ ስሆን ጫካው ውስጥ ሰይጣን ያለ ይመስለኛል ጫካዋ ውስጥ ስሆን ግን ሰፈሬ ውስጥ ነው ሰይጣን ያለ የሚመስለኝ ልክ መንገድ ላይ ሰይጣኑ ጋር ተገናኝተን "አብርሽ ሰላም ነሽ በይ ጫካየን ጠብቂ እኔ ሰፈርሽን እጠብቃለሁ"ተባብለን የተላለፍን ነገር

እዛች ሜዳ ላይ ሁልጊዜ ስሄድ አክሮባት ነው የምለማመደው ወደፊት መገልበጥ ችየበታለሁ ወደኋላ ስገለበጥ ግን እንቅስቃሴየ ይዛነፍና ወደጎን ዘጭ እላለሁ እዛው ላይ በጀርባየ ተንጋልየ ሰፊውን ሰማይ እያየሁ ብቻየን በራሴ አወዳደቅ ፍርፍር ብየ እስቃለሁ ጫካዋን በፍቅር ነው የምወዳት

ወደጫካዋ ለመድረስ አካሄዱ "ሲስተም" አለው ዝም ብሎ ወደጫካው አቅጣጫ መሰጥሰጥ አይደለም መጀመሪያ ወደጊወርጊስ ቤተ ክርስቲያን በእርጋታ መራመድ ልክ ፆምና ስግደት እንዳደከመው ምእመን ረጋ ብሎ በግራና በቀኝ የበሩን ምሰሶ ከተሳለምኩ በኋላ ወደውስጡ በቀስታ እገባና በጓሮው በር ወጥቸ ወደጫካው እየፈነጠዝኩ መብረር ነው የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ቄስ አፈወርቅ ቢጠየቁ ማለት "አብርሽ የት ነው ?" ቢባሉ "እዚሁ ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ነው የተባረከ ልጅ ዛሬ በሱ እድሜ ማን ቤተክርስቲያን ሳያሰልስ ይሳለማል " እንደሚሉ ጥርጥር የለኝም !! በበር እየገቡ በጓሮ መሹለክ አይታያቸውም

አንድ ቀን ታዲያ አሳቻ ሰአት መርጨ (አሴ መሃበር ስትሄድ) ወደቅድስቲቷ ጫካ ተፈተለኩ ስደርስ ግን ያየሁትን ነገር ማመን አልቻልኩም ልክ አክሮባት የምሰራባት ቦታ ላይ ፊቷን ወደወንዙ አዙራ ሮዛ ተቀምጣለች ዘንፋላ ፀጉሯ ጀርባዋ ላይ ተንዝናዞ ራሷ መሬት ወደተመረኮዘችበት ቀኝ እጇ ዘንበል ብሎ ነጠላ ጫማዋን አውልቃ ከጎኗ አስቀምጣ እግሮቿን አነባብራ ዘርግታቸዋለች ሮዛ ጫካየ ውስጥ፣ ሮዛ ሜዳየ ላይ ጫካየን ሜዳየንና ሰይጣኔን ተጋርታኝ ሮዛ ወደሷ ሄድኩ ደንገጥ ብላ ዘረችና በግርምት አየችኝ "አቡቹ ደግሞ እዚህ ምን ትሰራለህ ? " አለችኝ ተገርማ "ምንም " "አሴ ታውቃለች መምጣትህን ?" "ተደብቄ ነው የምመጣው " የእግሮቿ ጣቶች ሲያማምሩ "የምመጣው? ሌላም ቀን ትመጣለህ እንዴ? " "አዎ" ከንፈሯ የልብ ቅርፅ ነው "ብቻህን ?" "አይ ጓደኞቸ ጋር " ዋሸኋት አይኗ አተላለቁ "መምጣት የለብህም ወንዙ መጥፎ ነው በዛ ላይ በቃ መምጣት የለብህም " "አንች ለምን መጣሽ ?" አልኳት የእጇም ጣቶች ያማምራሉ እኔማ ላነብ ፀጥ ያለ ቦታ ስለሆነ ደስ ይላል በዛ ላይ እኔ ትልቅ ነኝ" አጠገቧ ተንበርክኬ ተረከዜ ላይ ተቀመጥኩ እና ወግ ጀመርን ሮዛ በጣም ቆንጆ ናት እንኳን ጎረምሳ ያልሆንኩ በዛ ላይ ወሬዋ ደስ ይላል አጠገቧ ተከፍቶ የተቀመጠውን ጥቁር መፅሃፍ "ልየው ?" አልኳት ሰጠችኝ "ምንድን ነው? " የሰይጣን መፀሃፍ ነው እየተባለ ሲታማ እንዳልሰማ ሰው ጠየኳት "መፀሃፍ ቅዱስ ነዋ " ደንግጬ ላኖረው ነበር እቤታችን "መፀሃፍ ቅዱስ" አለ እንኳን እንዲህ አገላብጦ ማየት ከነካሁት አሴ ታብዳለች እራሷም አትነካውም አንዳንዴ በስርአት ወልውላው እንደመስቀል ትሳለመውና ወደቦታው ትመልሰዋለች "ይሄ መፅሃፍ ቅዱስ ነው? እኛም ቤት እኮ አለ ግን እንደዚህ አይነት አይደለም ታዲያ ለምን ታነቢዋለሽ ? " "እንዴ የእግዚአብሄር ቃል ስለሆነ ነዋ እግዚአብሄር ምን እንደሚወድ ምን እንደሚጠላ እዚህ ውስጥ ፅፎ ሰጠን " "ለነማን ? ላንች ነው የሰጠሽ ?" ከምር እግዚያብሄር ለሮዛ የሰጣት መስሎኝ ነበረ "ለኔም ለአሴም ለሁሉም ሰው ላንተም" "እአአአአ ለኔ አልሰጠኝም ኧረ " "ሰጥቶሃል በእጅህ ሳይሆን መልእክቱን እኔ እንድነግርህ " አመንኳት ሮዛ ጨዋ ልጅ ስለሆነች አትዋሽም "ምን አለሽ? " ብየ ጠጋ አልኳት በጉጉት "አሴ ከምትወድህ የበለጠ እማማ ሩቅያ ከሚወዱህ የበለጠ እወድሃለሁ " ብሎሃል "ማን እግዚአብሄር ነው እንዲህ ያለሽ? " "አዎ እራሱ " ገርሞኝ ልሞት "የት ነው ያለው

እግዚአብሄር? “ “እዚህ ውስጥ” አለችኝ ልቧን እየነካች ጡቶቿ ሸሚዞቿን ወጥረውታል እግዚአብሔር ሸሚዟን የወጠረው መሰለኝ አንገቴን አስግጌ በተከፈተው ቁልፍ ልመለከት ስል ወደኋላዋ ሸሸት አለችና በሳቅ ፍርስስ ብላ “አይ አቡቹ ልቤ ውስጥ እኮ ነው ውስጥ ” አለችኝ

“እግዚአብሄር ሰማይ ላይ አይደል እንዴ ያለው ?” ድንገት ትዝ ብሎኝ “አዎ ሁሉም ቦታ አለ እኔ ልብ ውስጥ.. ሰማይ ላይ ምድር ላይ አሴ ልብ ውስጥ አንተም ልብ ውስጥ ” ልቤ ከበደኝ ማታ እቤቴ ስገባ ሁሉ ልቤ ውስጥ የሆነ ነገር የሚፈራገጥ እየመሰለኝ ነበር ።

ሮዛን ጠየኳት ለምንድነው ያንች መፅሃፍ ቅዱስ ጥቁር የሆነው “ “ ሽፋኑ ነው እንጅ ሁሉም መፅሃፍ ቅዱስ አንድ አይነት መልክት ነው ያለው ለምሳሌ የአንተ ሂሳብ ደብተር ሽፋኑ ምን አይነት ነው? “ “ሰሚያዊ ሁኖ መስመር መስመር ያለው “ “የዳንኤል ሂሳብ ደብተርስ “ “የሱማ አልተሸፈነም ራሱ የደብተሩ ልባድ ቢጫ ነው” “አየህ አቡቹ ሽፋኑ ቢለያይም ውስጡ ግን አንድ አይነት ነው አይደል?” “ኧረ አይደለም “ “የሁለታችሁም ሂሳብ ደብተር አይደለም ?” “ቢሆንም የኔ ውስጡ ልክ በልክ ሲሆን የዳኒ ኤክስ በኤክስ ነው” ሮዛ የትና የት በሚሰማ ድምፅ ጮሃ ሳቀች ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ (ጠርሶቿ ያምራሉ) “ካላመንሽ አሳይሻለሁ ዳኒ ስልሳ ስድስት “ራይት” ብቻ ነው ያለው እኔ ሰማኒያ አንድ “ ሳቋ ከመጀመሪያው ባሰ

ሮዛን ወደድኳት በቃ ውድድድድድ እሷም ሳትወደኝ አትቀርም (ኧረ ወዳኛለች) ሁልጊዜ ቅዳሜ ቅዳሜ በዚቹ ሰአት እዚህ እንደምትመጣ ነገረችኝ አንዳንዴ እመጣለሁ ማለት “ና” እንደማለትም ይሆናል ” ና “ ሳትል ቀጠረችኝ “እመጣለሁ” ሳልላት ቀጠሯችንን አክብሬ ተገኘሁ እኔና ሮዛ ሁልጊዜ ተጠቃቅሰን ወንዝ መውረድ የጀመርነው ከዛን ቀን ጀምሮ ነበር እሷ መፀሃፍ ቅዱስ ታነባለች እኔ አክርባት እለማመዳለሁ ምርጥ ጓደኞች ሆንን ቅዳሜ እስከሚደርስ ትናፍቀኛለች ባለፈው ቅዳሜ ታዲያ “አይንህኝ ጨፍን “ አለችኝ ጨፈንኩ “ግለጥ! “ ገለጥኩ አረንጓዴ ሽፋን ያለው መፅሃፍ በሚያማምሩ ስእሎች የተሞላ ሰጠችኝ ልቤ በደስታ ሊሰነጠቅ ደረሰ ትንፋሽ አጠረኝ “የልጆች መፅሃፍ ቅዱስ ከስእላዊ መግለጫ ጋር” ይላል በምኗ ይዛው ነበረ አላየሁትም ! ደስታየ አስደሰታት “ካሁን በኋላ ቅዳሜ ቅዳሜ ቁጭ ብለህ ታነባለህ ከጨረስክ ሌላ አመጣለሃለሁ እና ደግሞ እቤትህ መውሰድ አትችልም አንብበህ ወደቤት ስንሄድ ለእኔ “ አለችና አንድ ሶስት ገፅ ልክ እንደተረት ተረከችልኝ ከዛን ቀን ጀምሮ ሁልጊዜ ቅዳሜ አንድ ምእራፍ ታነብልኛለች ስትተርክ ፊቷ እየተኮሳተረ እየፈገገ ስለነበር አብሪያት ፊቴን እቀያይር ነበር ደግሞ ልቤን እንዴት እንደምትሰቅለው “ ከዛ መአበሉ ተናወጠ ጀልባዋ ብዲ ግ ትልና ውሃው ላይ ቦጭረ ቅ ደቀመዛሙርቱ ተጨነቁ ኢየስ ግን ተኝቶ ነበር በቃ አሳ ነባሪወች ደግሞ ከነሚያስፈራ ጥርሳቸው በጀልባዋ ዙሪያ ብቅ ጥልቅ ይላሉ አቤ ት ሲያስፈሩ ” ትላለች ሮዛ “ከዛስ “ እላታለሁ ጓጉቶ እየተቁነጠነጥኩ ”አሁን መሽቷል ቅዳሜ እንቀጥላለን ብላ ብስጭት ታደርገኛለች “በማሪያም እችን ብቻ ጨርሻት አሴ አሁን አትመጣም ተይ ሮዚ ተይ ” ላለቅስ እደርሳለሁ ልብሷን እያረጋገፈች መንገድ ትጀምራለች መሄጃችን ይለያያል እሷ በታች በኩል እኔ በቤተክርስቲያኑ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ስብከት ይኖራል ማታ ቤተ-ክርስቲያን በዋናው በር በኩል “ተመለሱ” ትላለች በጓሮ ልጆቿ ጭልጥ ብለው እየሄዱ ከምእመኑ ጋር ተደባልቄ እወጣለሁ

በቀጣዩ ቅዳሜ ደግሞ ስለጎሊያድ እና ዳዊት ትተርክልኛለች ” ግድንግድ ሰው ነው በቃ ምን እንደሚያክል “ ብላ አይኗን ፍጥጥ ታደርገዋለች (እንኳን አፍጥጣው እንደውም ) “ጎሊያድ ፍስሃን ያክላል ?” እላታለሁ ፍሰሃ የሰፈራችን ታዋቂ ስፖርተኛ ነው ብቻውን ጭቃ ውስጥ የገባች መኪና ጎትቶ ያወጣ “ፍስሃን እማ ጎሊያድ ቢያገኘው በዚች ነው የሚያሽቀነጥረው “ ትላለች ሮዛ ትንሽ ጣቷን እያሳየችኝ “አሽ ጎሊያድ ሬንቦን ያክላል” ሬንቦን ፊልም ላይ ሽ ገሎ ሶስት ሽ ሲያቆስል አይቸዋለሁ “ሬንቦ ምን አለው ቀጫጫ በለው” ትላለች ሮዚ በቃ ጎሊያድን አግዝፋ አግዝፋ ከአይምሮየ በላይ ታደርገውና ከመግዘፉ ብዛት “ግዝፈት” እራሱ ጎሊያድ ይመስለኛል ገዝፎ ገዝፎ አለሙን ሁሉ ይጋርድብኛል ትቀጥላለች ሮዛ “ ከዛ አንድ ቀጫጫ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ የሚያክል በቃ ልክ አንተን የሚያክል ልጅ ይሄን ጎሊያድን ሊገጥመው ፊት ለፊቱ ቆመ ዳዊት ነው ስሙ ” በሳቅ ፍርስስስ እላለሁ ዳዊት እንደቡድናችን በረኛ እንደ አሹ ባሪያው ትእቢተኛ መሆን አለበት

“ ከዛ ጎሊያድ ጎራዴውን መኸረጥ አደረገና ወደዳዊት ተንደረደረ ጎራዴው ስለቱ እንደፀሃይ ያበራል እንከዋን ሰው ይሄን ዛፍ ቢያገኘው እንደሸንኩርት ነው የሚከታትፈው ተንደረደረ የጎሊያድ እግር በሬቱን ሲደቃው ዳዊት እንደሰፌድ ላይ ቆሎ ይንቀረቀባል የመሬቱ ንዝረት ዳዊትን ያንቀጠቅጠዋል ሮጠ ጎሊያድ ዳዊት ላይ ሊደርስ አስር እርምጃ ከዚህ እንደዛ ዛፍ የሚሆን ሲቀረው ” ስቅቅ ብሎኝ ጉልበቴን አጥብቄ አቅፈዋለሁ ሮዛ ዝም ትላለች “ከዛስ ጨፈለቀው ? ከታተፈው ?” እጠይቃታለሁ በጉጉት “ሳምንት ከዚህ እንቀጥላለን ” ትለኛለች ኤጭጭጭጭ ! አቤት ቅዳሜ እስኪደርስ ጭንቀቴ ደግሞ መፀሃፉን አትሰጠኝም የዳዊትን መጨረሻ ለመስማት ደግሞ ቅዳሜ ራቀብኝ እሁድ ሰኞ..ሰኞ ከሰአት ሰኞ ማታ ሰኞ ሌሊት የሆነ ሃሳብ መጣልኝ “የአሴ መፅሃፍ ቅዱስ ላይ ስለዳዊት እና ጎሊያድ አለ ወይስ የለም? “ የሚል ሃሳብ ላየው ወሰንኩ አሴ ገበያ ስትሄድ ጠበኩና እየፈራሁ ገለጥኩት “ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ” የሚል ፅሁፍ አለበት ሮዛ የነገረችኝ ታሪክ ውስጥ ይሄ የለም ! ገለጥኩት ብዙ ገፆችን ባንዴ ገለጥኩ “ ሙሴ ባህሩን ሲረገጠው ባህሩ ተገመሰ ” ገለጥኩ “ ሙሴ ሞተ መቃብሩም አልታወቀም ” ዳዊት ዳዊተ ዳዊት የት ነው የጠፋብኝ ገለጥኩ “ የዳዊት መዝሙር ነፍሴ በእግዚአብሄር ሃሴት ታደርጋለች በመድሃኒቴ አምላክ ” በቃ ዳዊት እና ጎሊያድ አሴ መፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የሉም !! ሲያበሳጭ በመጨረሻ ስፈራ ስቸር ወሰንኩ (ታሪካዊ ውሳኔ ወሰንኩ) ቀስ እያልኩ ግራና ቀኝ እያየሁ ወደእነሮዛ ቤት ሄድኩ ማንም ሰው የለም አሴ ገበያ ሂዳለች ሮዛ ሁልጊዜ ጧት እቤት እንደማትኖር አውቃለሁ ተረጋግቸ የማንንም ትኩረት ሳልስብ እያቆራረጥኩ እነሮዛ ቤት በር ላይ ደረስኩና ወደበሩ ተጠግቸ አንኳኳሁ ልቤ ልታፈተልክ ደርሳለች የጎሊያድን ግቢ ያንኳኳሁ ነው የመሰለኝ ግቢውን ብርግድ አድርጎ “ምናባትህንስ ፈለክ አንተ?” የሚለኝ አይነት በሩ ተከፈተ ደነገጥኩ ልሮጥ ነበር የሮዛ እናት ነበሩ እጃቸው በሊጥ ተሸፍኗል “ውይ አቡቹየ ከየት ተገኘህ ና እስቲ ግባ ና አይዞህ ” አሉኝ ተገርመው ገባሁ ወደዋናው ቤት ሳሎን ስንደርስ በድፍረት “ሮዛ ጧት ስትሄድ ልካኝ ነው አረንጓዴውን የህፃናት መፅሃፍ ቅዱስ የሚለውን መፅሃፍ ከቤት ተቀበልና “ቸርቹ” ጋር ያለችው መዝሙር ቤት ስጥልኝ ብላኝ “ “ና ግባ እኔ ምኑን አውቄው እስቲ እዛ ጋ ካሉት መሃል ይሆን “ አሉኝ ወደተደረደሩት መፅሃፎች እያሳዩኝ ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ አየሁት!!!!! አፈፍ አድርጌ አቀፍኩት “አገኘሽው ? “ “አዎ እማማ ” ስማቸው ጠፋብኝ “በል ደበቅ አድርገህ ውሰድና ስጥላት ምን እዚህ ራሷ አትወስድም ልጀን ሰው አፍ ውስጥ ልታስገባህ ” አሉና ለእኔ በማዘን ተነጫነጩ

በቲሸርቴ ውስጥ ደብቄ ወደቤቴ በረርኩ ዳዊት ጎሊያድ እግሬ አልፈጥን አለኝ የህልም ሩጫ ሆነብኝ ቤቴ እንዲህ ሩቅ ነው እንዴ ? ልክ አንድ እግሬ የቤታችንን በር አልፎ እንደገባ ነበር ቀዝቃዛ መዳፍ ማጅራቴን የጨመደደኝ በሩ ጥርቅም ተደርጎ ተዘጋና አሴ ወርውራ ከመሬት ደባለቀችኝ አይታኛለች እነሮዛ ቤት ስገባ አሴ አይታኛለች እዛ ዙሪያሽ የሚባሉት ሁልጊዜ በራቸው ላይ ጌሾ የሚያሰጡት ሴትዮ ቤት ቁማ እንደሌባ ግራና ቀኝ እየገላመጥኩ ስሄድ አይታ ተከትላ አይታኛለች ከገበያዋ ቀርታ በአለም ላይ ካሉ ግርፋቶች ሁሉ የትኛው አንጀቷን አንደሚያርሰው እያሰበች ነበር የጠበቀችኝ ይሄው እጇ ላይ ወደኩ!!

ወዲያው እንደእሳት የሚለበልብ የተጎነጎነ የኤሌክትሪክ ገመድ ጀርባየ ላይ ሲያርፍ ነፍሴን እስክስት ጮኽኩ ደገመችኝ ከታፋየ እስከግራ ኩላሊቴ ሰንበሩ እንማሪያም መቀነት ለሶስት ቀን የተጋደመ ምት ሰለሰችኝ ጉልበቴንና ታፋየን አሽከረከረችው ገመዱን ፊው ፊውፊውፊው አፏጨ (ሰይጣን እየሳቀ መሰለኝ እችን ሊያዘጋጅ ነው ለካ መንገድ ላይ አልፎኝ የመጣው )

ልከላከል እጀን ሳነሳ መፀሃፉ ዱብ አለ አሴ አነር አራስ ነብር ሆነች ቀጥ ስል መስኮቱ በሰፊው ተከፍቷል መፀሃፉን አንስታ ልትቀድ ስትታገል ብርርር እንደወፍ የቀርቀሃ ወንበሩን መደገፊያ ተረግጬ በመስኮት ተፈተለኩ ከመዝለሌ በፊት ጀርባየ ላይ በጨለፍታ አግኝታኛለች ሙሉ በሙሉ ቢያርፍብኝ ይሻል ነበር ጫፉ እንደመርፌ ነው የሚወጋው

ግርፋቱ እንደእሳት ፈጀኝ በድንጋጤ ያፈንኩት ጩኸት ከውስጤ ተስፈንጥሮ ወጣ ከቤታችን ፊት ለፊት ያለው አቧራ መንገድ ላይ እየተንከባለልኩ እየተንፈራፈርኩ ሪሪሪሪሪሪሪ ብየ ጮኽኩ ከቤቴ ተንደርድሬ በመጣሁበት ፍጥነት ነበረ እንደበረኛ ተወርውሬ በመውደቅ ኡኡታየን ያቀለጥኩት ዋይይይይይይይይይ !!!

እንባ አልነበረኝም ግን ጉሮሮየ ላይ አንዳች ነገር እልህ ፣ብስጭት፣ ንዴት ተወትፎብኛል እንደዛ አይነት ብራቅ ድምፅ ከምኔ ውስጥ እንደወጣልኝም እንጃ እንደአንዳች ከንፍ እንዳለው ነገር የጮህኩበትን ቧሬ አፌን ሳልዘጋ ማን አጠገቤ ደረሰ ? የእኔ መለአክ እማማ ሩቂያ ! ! አሴ መፍለጫ ይዛ ሳያት ኀሊያድን መሰለችኝ !!

ሮዛ ጋር ከዛ በኋላ ሳንገኛኝ ብዙ ቆየንና (ሳያት እየተደበኳት) ድንገት "ልታገባ ነው " ሲባል "ባሏ ታድሎ ሁልጊዜ ቅዳሜ ሁልጊዜ ማታ ማታ መፀሃፍ ታነብለታለች አልኩ"

## ክፍል 5

ሃሙስ ከሰአት እቤታችን ውስጥ ስብሰባ ነበር ። ተሰብሳቢወቹ እግር ጥሏቸው ይምጡ ወይም ተጠራርተው አላወኩም ! ብቻ ከሰፈራችን የቀረ ትልቅ ሰው አልነበረም ማለት ይቻላል የስብሰባው አጀንዳ ደግሞ የሮዛ ሰርግ ነበር (ስሟ አፌ ላይ እንዴት ይጣፍጠኛል ሮዛ ሮዛ እኔ ስብሰባ ያስጠላኛል ስለሮዛ ጉዳይ በመሆኑ ግን ጆሮየን ቀስሬ ማዳመጥ ጀመርኩ)

ከአስራ አምስት ቀን በፊት ነበር ለመንደሩ ሰው ሁሉ "የሮዛ ሰርግ የጥሪ ወረቀት" የታደለው በቃ ከዛን ቀን ጀምሮ ወሬው ሁሉ "ሮዛ" እና "ሰርግ" ሆነ የልጅ አዋቂው ሁሉ ወሬ ሮዛ ሆነ የጥሪ ካርዱ ላይ ካሉት ስርአተ ነጥቦች ጀምሮ እስከ ማስጌጫ መስመሮቹ ድረስ በመንደርተኛው ከፍ ያለ ምርምር ተደርጎበታል በመጥሪያው ካርድ ዙሪያ የተሳሉት ሃረግ መሰል ቅጥልጥል ጌጦች ውስብስብ ምልክቶች ስለነበሩ ውዝግብ ተነሳ

(ቦፅፅፅፅፅፅፅፅፅፅፅፅ የሰርግ መጥያው ላይ ዙሪያውን ለጌጥ የተቀመጡት ምልክቶች) " ይሄማ ስድስት ስልሳ ስድስት ነው ጅራታቸው ለማሳሳት የተጨመረ ስድስቶች ናቸው " ይላል አንዱ ስነ-መለኮትን ጫት እየቃመ ያጠና ይመስል

"ምንድን ነው ስድስት ስልሳ ስድስት " ይጠይቃል ሌላው "ሰይጣን በሰው ልጆች ነብስ ሲጫወት የሚለብሰው ማሊያ ቁጥር ነው " "እግዚኦኦኦኦኦኦ ይጫወቱብን ግዴለም " "ኧረ ይሄ ነገር ጅራቱ ሲጠፋ ቢ ነው የሚሆነው " ይላል አንዱ ደገሞ ተመራምሮ " "እና "ቢ" ቢሆን ያው "ቢ" ማለት "ባይብል" ማለት ነው የጴንጤ መፅሃፍ ቅዱስ ማለት ነው ከምልክቱ ላይ o ለብቻ በትነጠል ምን ይቀራል ኤል ኤል ማለት ሉሲፈር የሚባለው ቀንዳም ሰይጣን የመጀመሪያ ፊደል ነው " አለና ሳምሶን የሚባለው የመንደራችን መለስተኛ ሙህር ትንታኔ ሰጠ "ወይ መማር " ተባለ !!

በዚህ ሁኔታ ተከረመና ይሄው ሰርጉ ሳምንት ቀረው ሰርጉ "ቸርች" ውስጥ ነበር ጎረቤቱ ግራ ተጋባ ከሰርጉ እንዳይቀር እማማ ሩቅያን ፈራ እንዳይሄድ "ሰይጣኑን" ፈራ ግራ ሰርጉ ሶስት ቀን ቀረው ስብሰባ እኛ ቤት !! አጀንዳ ወደሰርጉ ቦታ እንዴትና ምን ይዘን እንሂድ ውሳኔ "መቸስ ምንም ቢሆን ያሳደግናት ልጅ ናት ብታዋርደንም አሳድገናታል! ስለዚህ ወደሰርጉ ቦታ አበባ መስለን ዘንጠን እንሄዳለን ግን ሁላችሁም በኪሳችሁ ውዳሴ ማሪያም መያዝ እንዳትረሱ " አንድ ሁለት ራስ ነጭ ሽንኩርትም ብንይዝ ጥሩ ነው ሰይጣን ያባርራል " "ደህና " አለና መንደርተኛው ተስማማ ማሳሰቢያ ምንም ነገር የሚበላ ነገር ቢቀርም አንቀምስም !! ስብሰባው አለቀ!!

ሮዛ ሰርግ ላይ ለመገኘት ፈለጌያለሁ ግን እንዴት አሴን "የሮዛን ሰርግ እንዳይ "የጴንጤ ቸርች" ልሂድ" ብላት በዘነዘና ድራሽን ነው የምታጠፋው እንዳልተወው የሮዛ ሰርግ ነው የሰፈር ልጆች ተደብቀን ለመሄድ ብንመካከርም እኔ ፈራሁ ሆሆ ያ የኤሌክትሪክ ገመድ

እማማ ሩቅያ ቤት ሄድኩና አጠገባቸው ቁጭ አልኩ ብዙ ትራስ ከምረው ተራ በተራ የትራሶቹን ልብሶች እየቀየሩ ነበር ትራሱን በአገጫቸውና በደረታቸው መሃል አጣብቀው ይይዙና ልብሱን ከታች ወደላይ ያጠልቁታል አብሪያቸው መስራት ጀመርኩ ትራሱን እኔ ከፍ አድርጌ እይዝና እርሳቸው በሁለት እጆቻቸው በያዙት ልብስ ውስጥ እቆጥረዋለሁ ብዙ ትራስ አልብሰን እንደጨረስን "ኢብሩ " አሉኝ "እ" " አሞሃል እንዴ " በለስላሳ እጃቸው

ፊቴን እየደባበሱ ጠየቁኝ ቀለበታቸው ትቧጨራለች “ ኧረ አላመመኝም” “ምነው ታዲያ ካለወትሮህ አደብ ገዛህ(ፀባይተኛ ሆንክ እንደማለት )” ለካስ ይሄን ሁሉ ስራ ስሰራ አንዲት ቃል አልተነፈስኩም ነበር “ማማ ሩቂ” አልኳቸው ድምፄን ልስልስ አድርጌ “ለበይክ” “ሮዛ ሰርግ አንቱ ጋር ልሂድ አርፌ አጠገብሁ እቀመጣለሁ አረብሸም “

“ ኦኦኦኦኦኦ ኢብሩ አሁን እህል ውሃህ ማከተሚያው ደረሰ ይሄን ወሬ ብትሰማ እናትህ እንደቡጡ ልብሷን ጥላ ታብድብናለች (ቡጡ ራቁቷን መንደራችን የምትውል የአይምሮ ህመምተኛ ናት) እኔንም ነው አሁንስ የምትጨርሰኝ “ አሉና ፈገግ አሉ ቀጥለውም “ ምን ያረግለሃል ያው እንደሁሉም ሰርግ እኮ ነው እንደውም የሚንጢ ሰርግ ጨዋታ የለው ዘፈን የለው ይቅርብህ አሁን ነጃትን ስድር ሻማ ያዥ ነው የማደርግህ” አሉ ነጃት ውጭ የምትኖር ልጃቸው ናት ዝም ብየ ሳዳምጣቸው ቆየሁና ተነስቸ ወደቤቴ አዘገምኩ በጣም ከፍቶኝ ነበር በጣም

ሰርጉ አንድ ቀን ቀረው ወደዘጠኝ ሰአት እማማ ሩቅያ እኛ ቤት መጡ ቡና ካልተጠሩ ወይም ከበድ ያለ ጉዳይ ካልገጠማቸው እኛ ቤት ስለማይመጡ የውጭ እንግዳ እንደመጣ ሰው ነበር አቀባበሉ “መልሰን መጣን “ አሉና እልፍ ብለው የራሳቸው መቀመጫ የሆነችው ፍራሽ ላይ ተቀመጡ “እንችማ ይሄን አፍይው የቅድሙ ቡናሽ ቀጠን ብሎ ሱሴን አልቆረጠልኝም “ አሉ ከጉፍታቸው ስር ግማሽ ኪሎ ቡና አውጥተው ለአሴ እያዘረጉላት “ሩቂ ደሞ ታበዙታለሁ አሁን እስቲ ይሄን ሁሉ ምን አሸከመሁ ዝም ብለሁ አትመጡም ” ብላ ተነጫነጨች ከምሯ ነበር እሩቂ የአሴ ቡና “ቀጣጠነ” ማለታቸው ገርሞኛል ከሰፈራችን አንደኛ ቡና የአሴ ነው!! ማሪያምን እናቴ ስለሆነች አይደለም ሁሉም ሰው ነው የሚለው እማማ መላክነሽ እንኳ “የራሴን አቦል ቡና ከምጠጣ የአሰለፈችን ሶስተኛ ቡና መጠጣት ይሻለኛል” ብለዋል !! ለሙያማ እንዲህ የተመሰከረላት እናት ናት ያለችኝ ትንሽ ፀባይዋ ነው እንጅ አሁን ሮዛ ሰርግ ላይ ብሄድ ምን አለበት

ቡናው ተፈልቶ አቦሉ ተጠጣና እሩቂ እንዲህ አሉ “እንደው የነገው ሰርግ ነገር ጨንቆኛል ይሄን አቀበት እንዴት እንደምወጣው ግራ እግሬን ስብስብ አድርጎ ይዞኛል አሁን እንኳን ወዲህ ስመጣ በመከራ ነው “

“ምነው ቅድም ደህና አልነበሩ “ አለች አሴ ተጨንቃ “እንዳላሰጋሽ ብየ ነው አሞኛል” “ወይ ሩቂ እንግዲህ ቻል አድርገሁ መሄድ ነው መንደሩን ቀስቅሰው እርሰዎ ቢቀሩ ሌላ ነገር ይመስላል “ አለች “ እውነትሽን ነው እሱስ ኢብሩ “ ድንገት ጠሩኝ ትንሽ አኩርፈያቸው ነበር አሴ በትንሽ ሲኒ የሰጠችኝኝ ቡና ጠጥቸ ሲኒው ስር የረጋውን ስኳር በመላስ ስራ ተጠምጀ ነበር “አቤት “ “ነገ ደግፈህ ሰርጉ ቤት አታደርሰኝም “ ማመን አልቻልኩም “አይ እኔ እደግፈኋለሁ” አለች አሴ ቀደም ብላ ወይ አሴ ደስታየን ነጅሰችው “ኤዲያ ገንፎ ለገንፎ አሉ አንች ብሎ ደጋፊ ግዴለም ኢብሩ ድግፍ አርጎ ይወስደኛል የኔ ምርኩዝ ልጆቸ ሲለዩኝ አላህ እሱን ባይሰጠኝ ምን ይውጠኝ ነበር ” አሉና የማይገፉ ማህበራዊ ግንብ አሴ ፊት ገተሩባት “ልጆቸ ባይኖሩም ልጅሽ ልጀ ነው!! ልጆቸ ቢኖሩ ይደግፉኝ ነበር ” እንደማለት !! እና ምን ትበል አሴ ዝም ጭጭ!! ወይኔኔኔኔ ሩቂ እንዴት አይነት አስማተኛ ናቸው ሩቂ ነፍስ ነገር የመጡት ቡናው ቀጥኖባቸው አልነበረም ለዚቹ ነበር እዚህ ግባ የማይባል አንድ ጨቅላ ጉዳይ አሳስቧቸው ቀጥ ስል በሁለት አይናቸው ጠቀሱኝ እጓዳ ገብቸ አፌን አፍኘ በሳቅ ልፈነዳ

*** **** *****

የሰርጉ ቀን የሮዛ የሰርግ ቀን

አሴ አበባ አስመስላ አዘነጠችኝ ባለፈው ለዘመን መለወጫ የተገዛልኝን ሙሉ ልብስ ለብሸ ያውም ከነከረባቱ ትልቅ ሰው መሰልኩ በደረት ኪሴ ውዳሴ ማሪያም በሱሪየ ኪስ ደግሞ ነጭ ሽንኩርት በወረቀት ጠቅልላ አስቀመጠችልኝ ሰይጣን እኔን የመሰልኩ “ቆንጆ ልጅ” ሊበላ ቢፈልግ ሲያምረው ይቅር !! ጓደኞቸ አመድ አመድ መስለው ወደኳስ ሜዳ ሲሄዱ በመስኮት አየኋቸው ሲያስጠሉ !

አሴ ወደጓዳ ውስጥ ገብታ አስር ጊዜ በመጋረጃው አንገቷን ብቅ እያደረገች ”አቡቹ ጫማውን አቀብለኝ ይሄን አይደለም ያንኛውን ቡና አይነቱን አቡቹ ማበጠሪያ አቡቹ ሳጥኑ ውስጥ ከላይ የታጠፈ ልብስ አለ ቀስ ብለህ

እንዳትመነቅር " ስትለኝ ከቆየች በኋላ ዝንጥጥጥጥ ብላ ከጓዳ ብቅ ስትል ሌላ ሰው መሰለችኝ! ወይኔ አስየ የኔ እናት ስታምር ደግሞ በጣም ወጣት ሆነች እናቴ ወደጓዳ ገብታ ቆየች ቆየችና ስትወጣ እህቴ መስላ ወጣች

"ወይኔ አሴ ስታምሪ " ስላት አፈረች እና "እንሂድ እረፈደ አለችኝ " ልክ አድናቆቴን እንዳልሰማች ወጣን ስንወጣ ደግሞ አሴ የባሰ አማረች ፀጉሯ ፀሃይ ላይ አብረቀረቀ እማማ ሩቅያም ዝንጥ ብለው ነበር ልክ እኔና አሴን ሲያዩ "ማሻ አላህ ትፍፍትፍትፍ " አሉና እንደየአቅሙ የዘነጠው መንደርተኛ ጋር ወደድሮው ወትት ቤት ወደአሁኑ "ቸርች" ተመምን መንደርተኛው ለአይኑ ወደሚጠላው አንዴ "ለእሳት" አንዴ "ለሙብረቅ ያድርገው" እያለ ሲረግመው ወደኖረው "ቸርች" ዘንጠ ተመመ

እንደገባን በጌጣጌጥ ያበደ አዳራሽ ተቀበለን መድረኩ በተለይ በተለያዩ ፊኛወች፣ በሚያብረቀርቁ እና ንፋስ በሚያውለበልባቸው ወረቀቶች ተጊጧል አቀማመጣችን ያስቅ ነበር በቀኝ በኩል ወደኋላ መደዳ ወደመውጫው በር ጠጋ ብሎ(የሚመጣው አይታወቅም ሂሂሂ) የእኛ ሰፈር ሰው ድንበር ለጥቶ ተኮፍሷል ወደፊት ደግሞ "ጴንጤወቹ" መጀመሪው ረደረፍ ላይ ተቀምጠው የነበሩት ሙሉ ሰሚያዊ ሁኖ ደረቱ ላይ ነጭ መስቀል ያለው ሰፋፊ ቀሚስ የለበሱት ዘማሪያን ወደመድረኩ ወጡና ጎን ለጎን ተጠጋግተው ተደረደሩ የሙዚቃው መሳሪያ አንዴ ሲጮህ አሴ ደነገጠች "እነህ ሰይጣኖች" እያለች አጉረመረመች ከዛማ መዝሙሩ ቀለጠ ጭብጨባው እልልታው ሃሌ ሉያውና ሌላውም ጩኸት ተዳምሮ አዳራሹ በአንድ እግሩ ቆመ የእኛ ሰፈር ሰው ዝም !!

*ሙሽሮቹ ከኋላችን ባለው በር ገቡ ሮዚ አረፋ የመሰለ ቬሎ ለብሳ አበባ ታቅፋ ባሏ እጇን አልያዛትም መዝሙሩን ተከትሎ እያጨበጨበ ነበር ባሏ በእድሜ ትንሽ ገፋ ያለና ቦርጫም ነው ሚዜወቻቸው ቀያያይ ቀሚስ ለብሰው አበባ እየበተኑና እየዘመሩ ሲገቡ እልልታው ቀለጠ መዝሙሩ ከፍ አለ የእኛ መደዳ ብቻ ሙሽራ ለመቀበል ቢቆምም ከባድ ዝምታ ዝም ብሎ ነበር እማማ ሩቂ "እልልልልልልልልልልልልል እሰይ የኔ ልጅ እሰይ " ብለው ጮኹ ሮዚ ዞር ስትል እጇን እያወዛወዝኩ ቻው ቻው ስላት ፈገግ አለችለኝ አሴ ማንም እንዳያይት አድርጋ በቁንጥጫ ለመዘገችኝ*

*ሙሽሮቹ መድረኩ ላይ ወጥተው ቀሚስ የለበሰ ሰውየ የሚለውን ነገር እየተከተሉ ማለት ጀመሩ መጀመሪያ ባሏ ነበር ቃል የገባው "በክፉ ቢሆን በደግ በደስታ ይሁን በሃዘን ላልለያት ቃል እገባለሁ " ሲል አሴ ተበሳጨች "ኡኡቴ እመቤቴንም ስትለያት አልፈራህ እንኳን ሮዛን " አለች በሹክሹክታ እኔ ብቻ ነኝ የሰማኋት ቃል የመግባት ስርአቱ አልቆ ቀሚስ የለበሰው ሰውየ ስብከት ጀመረ አነጋገሩ እና የሰውነቱ እንቅስቃሴ ድራማ ነበር የሚመስለው " ወገኖች አንዳንዶች መልክ አይተው ይከተላሉ አንዳንዶች ስምና ዝና ያሸንፋቸዋል ሊሎች ሃብት ተከትለው ይጎርፋሉ መልካም ባል መልካም ሚስት የተባረከ ትዳር ግን ከእግዚብሄር ብቻ ነው ከፈጣሪያችን ብቻ ነው አሜን አሜን " "አሜን" አለ ህዝቡ "ሃቅ ነው አንድየ ካልሰጠ ምን ዋጋ አለው" አሉ ሩቂ ጮክ ብለው አጠገባችን የነበሩት ሳቁ "ጌታ ይባርክዎት እማማ" አለ ሰባኪው ሩቂን እያየ በፈገግታ "አንተም በረካሁን አየዋ" ሲሉት አዳራሹ በሳቅ ተሞላ ሮዛ ሳትቀር ፍርፍር ብላ ስቃለች አሴ ብቻ ናት ያልሳቀችው እኔም እንዳልስቅ አሴን ፈርቸ ዝም አልል ነገር ሳቁ አስቆኝ መሃል መንገድ ፊቴን ከጅል የተረፈ ገንፎ አስመስየ ቁሚያለሁ*

ከአዳራሹ *ሙሽሮችን ተከትለን ስንወጣ እንደአሴ አባባል "ጴንጤዎቹ ወበሩ" በሙሽሮቹ ዙሪያ እየተሸከረከሩ መዝሙሩን አቀለጡት "ምህረቱ " ትላለች አወራራጇ "ገነነ በላየ " ይላሉ ተቀባዮቹ እያጨበጨቡ ስጦታው ገነነ በላየ ማዳኑ ገነነ በላየ "ይሄ የነሱ የሰርግ ዘፈን መሆኑ ነው " ተንሾካሾኩ እነአሴ*

አባ ግርማ የሰፈራችን ታዋቂ ዛፍ ቆራጭ "*ጎበዝ እንዲህ አፋችን ተለጉሞ ባሳደግናት ልጅ ሰርግ ላይ ጴንጤ ይፈንጭበት እንዴ " አሉና ጎረቤቱ ሁሉ መስማማቱን ሲያዩ ያዝ እንግዲህ አሉና ማወራረድ ጀመሩ "ያ ሆ " "ያ ሆ ጎረቤቶቻችን በእልህ ተቀበሉ ዘማሪወቹ ደነገጡ*

*ሃይሎጋ ሆ ሃይሎጋ ሆ "ይበላሃል እርገጥ ይበላሃል ጅቦ*

ዘማሪወቹ ከጭፈራው በማይተናነስ ድምፅ “ጠላቴ ሊበላኝ ዻጉቶ ጌታየ አዳነኝ መሃል ገብቶ አሰይ እሰይ ይበላሃል ይጎረድመሃል ይበለሃል ምታ ይበለሃል ጅቦ ሴቶቹ ዘማሪወች ጌታ በታምራቱ እስራቴን ፈታ ባደባባይ አቆመኝ ከፃድቃኑ ተርታ

እነአሴ ” ታሰረች አሉ በሰንሰለት እንግዲህ ሙሽር ወደማጀት እልልልልልልልል (አንድነታችን እልልታችን ) እንግዲህ ቀረ መፈንጠዝ ሙሽር ሚስትህን አጥብቀህ ያዝ ዘፈን

እንደዋላ እንቦሳ እፈነጥዛለሁ በከንዶቹ ጥላ ስር አድራለሁ መዝሙር

ድብልቅልቅ መዝሙሩ ከዘፈኑ ሽብሽባው ከእስክታው የፍቅር ባቢሎን አልፈራረሰም እንደውም ትልቁ የፍቅርና የመቻቻል ግንብ ሰፈራችን ውስጥ በዚች ቀን ቆመ እማማ ሩቅያ የሚባሉ ጉልላቱን እንደተራራ ላይ ሙብራት ጫፉ ላይ እያንቦገቦገ

እነሮዛ ቤት የሰርጉ ኬክ ሲቆረስ ወደእማማ ሩቅያ ጆሮ ጠጋ ብየ “ ባንክ ቤት ስንሄድ የገዛሁልኝን ኬክ እኮ ገንባው በላብኝ “ አልኳቸው “እኔ እናትህ ደህና ነገ ምን የመሰለ ኬክ እገዛለሃለሁ “ አሉኝ አሁን መጨፈር ወላ መዘመር አማረኝ ገንባው ኬኬን ቢሰርቀኝም ሩቁ አያሳፍሩኝም ሃሌ ሉ ያ !!

ወገኖቸ ኬክ ተበላብን ብላችሁ ተስፋ አትቁረጡ ድሙቶች ላይ ቂም አትያዙ የምርጥ እናታችን የፍቅር ቆሊያችን የእማማ ሩቅያ የማይነጥፍ መሃረም ለዘላለም እንዲኖር ትጉና ፀልዩ አሜን ነዋ

# ምርጫ በአንዲት አፈሪካዊት መንደር

ምርጫ በአንዲት አፈሪካዊት መንደር (ተመራጮች ለህዝብ ስትሉ ሱሪያችሁን አውልቁ) (አሌክስ አብርሃም) (የምታፍሩ ወንዶች ይሄን ፅሁፍ እንዳታነቡ እመክራለሁ!! ሴቶች እንኳን አታድረጉ የተባሉትን ማድረጋቸው ስለማይቀር መምከሩ ዋጋ የለውም ) በውጭ አገር በሚገኝ አንድ ታዋቂ ዩኒቨርስቲ ምናምኖሎጂ የሚባል ስለህዝቦች አኗኗርና ባህል የሚያጠና ትምህርት የተማረ ጓደኛየ የመመረቂያ ፅሁፉን ሊሰራ ወደአንዲት አፍሪካዊት መንደር ሂዶ ያየውን ነው የምነግራችሁ ልክ እሱን ሁኘ ላውራችሁ

**** ****** ****** ******

በአጋጣሚ ወደሰፈሩ የደረስኩት ልዩ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት በመሆኑ መንደሩ በአል በአል ይሸታል ሴት ወንዱ ሃፍረተ ስጋቸው ላይ ጣል ካደረጓት ሌጦ ሌላ ምናምኒት ልብስ የላቸውም ሰውነታቸው ቀይ ዋርካ ይመስላል ወንዶቹ ፈርጣማ ሴቶቹም ሸንቅጥ የሉና ጡታቸው የተቀሰሩ “ምንድነው ወከባው “ብየ አስተርጓሚየን ጠየኩት “በሁለት አመት አንድ ጊዜ በመንደሯ መሪ ይመረጣል አሁን የምርጫው ጊዜ አንድ ሳምንት ቀርቶታል ትልቅ በአል ነው ፋሲካ በለው !” አለኝ እንግዲህ የዚህን መንደር ምርጫ ከሌላው አለም ልዩ የሚያደርገው የመወዳደሪያ ምልክቱ የሁሉም ተወዳዳሪወች አንድ አይነት መሆኑ ነው “የወንድ ብልት!!” መስፈርት የለውም ወንድ ነኝ ያለ ሁሉ መወዳደር ይችላል!! !! ሃፍረተ ስጋቸው ላይ ቁራጭ ቆዳ ጣል ካደረጉት ወንዶች መካከል መለመላቸውን “ነገርየውን” ለመንደርተኛው እያሳዩ የሚንጎማለሉ ጎረምሶች ካያችሁ እነሱ የምርጫ ቅስቀሳ ላይ እንደሆኑ እወቁ !! የመንደሩ መሪ ለመሆን ከሁሉም የመንደሩ ወንዶች ዘለግ ያለ ብልት ባለቤት መሆን ያስፈልጋል እዚህ ሰፈር መንገድ እሰራለሁ ውሃ እተክላለሁ ሂወት የሚቀጥል ሆስፒታል እገነባለሁ ምናምን ብትል ሰሚ የለህም ! መንገድም ሂወትም ዘለግ ያለ ብልት ብቻ ነው!!አለቀ ! ኦባማ እራሱ እዚህ መጥቶ “ቸንጅ ፎር ዋርድ “ ቢል አትጨህብን ወደዛ ወንድ ከሆንክ ከነሴናተሮቸህ ሱሪህን አውልቅ ይባላል !! እንግዲህ የምርጫ ምልክቱ ተረጋግቶ አንገቱን ደፍቶ በተቀመጠበትም ይሁን “እምቢ” ብሎ በደም ፍላት በተወደረበት ርዝመቱ ወይ መሪ ያደርገዋል አልያም ተመሪ!! በመንደሩ ያሉ ቆነጃጅት ሰብሰብ ብለው ሲያወሩ ወጋቸው ሁሉ ስለወዳጃቸው ብልት ርዝመትና ሃያልነት ነው አንዷ “የኔ ጀግና ይሄን ያክላል እንትኑ” ትላለች ክንዷን እያሳየች በኩራት ሌላኛዋ “ምን አላት እሷ የኔ ባል ይሄን ያክል የለ ” ግራ እግሯን እስከመጨረሻው ዘርግታ “ ሂሂሂሂ አትንጫጩ ባካችሁ!! “ቹቹ ባኦን ታራ ገሪሪ ባራራ “ ብላ ትተርታለች በአማርኛ ሲተረጎም “አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል” እንደማለት ነው!! ከዛም” እዛ ጋ ያለው ይታያችኋል የኔ ጓደኛ ብልቱ ያንን ነው የሚያህለው” ትላለች ፊት ለፊታቸው የቆመውን ዛፍ እያሳየቻቸው የምርጫው ቀን መንደርተኛው ፊቱን ሰውነቱን በሸክላ አፈር ተውቦ በተለይ ሴቶች ፀጉራቸውን ተሰርተው እና አማላይ ሁነው የምርጫው ቦታ ላይ ቀደም ብለው በመገኘት ዘፈንና ጭፈራውን ያስነኩታል ትልቅ ሜዳ ላይ ነው ምርጫው ከዘፈኖቹ ግጥሞች አንዳንዶቹ ውሃ ልቅዳ ብየ አልፌ በበርህ እቃህ ዘንዶ መስሎኝ ገንቦ ሰበርኩልህ !! ጭብጨባ እልልታ ዳንስ እንዲህ እየተባለ የአገር ሽማልሌወች ጦራቸውን ይዘው በኩራት ወደተዘጋጀላቸው መቀመጫ ይሄዳሉ ከዛም ተፎካካሪወች እየፎከሩ እየሸለሉ በህዝቡና በሽማግሌወቹ ፊት ያልፋሉ እልልታው ይደምቃል ዘራፍ ትንታጉ ዘራፍ ሳተናው የአንበሳ አለቃ የነብር አለቃ አንጄ ካቆምኩት ለሽ እሚበቃ !! እልልልልል ይላሉ ከሸወቹ አንዷን ለመሆን የቋመጡ የመንደሩ ቆነጃጅት! ተወዳዳሪወች ተደርድረው ሽማግሌወቹ ፊት ይቆማሉ ፡፡ ሽማግሌወች በምርቃት ፕሮግራሙን ይከፍታሉ አገራችን አማን ይሁን (..አሜ ን ይላል ህዝቡ !) ዝናብ ምድራችንን ያረስርሰው የሴቶቻችን መሃፀን ይለምልም ጫፉ ቁርጭምጭምታቸውን አልፎ አፈር ነክቶ የሚመለስ ብልት ያላቸው ልጆች ቃያችንን ይሙሉት አሜን የልጆቻችን ብልት ሲበርድ እንደተኛ ዘንዶ ሲቆም እንደተወረወረ ጦር ይሁን አሜን!! ምርጫው ይጀመራል!! ተወዳዳሪወች እንደሚሳኤል ወደፊት የተወደረ ብልታቸውን ለህዝብና ለሽማግሌወች እንዲታይ አድርገው ይደረደራሉ (እንዴት ይቆምላቸዋል ብየ ጠይቄ ነበር “ምርጫ ሲቃረብ የማይቆም ምን ነገር አለ” የሚል መልስ ተሰጠኝ) ሴቶች እየተጋፉ እና እየተንጠራሩ በጉጉት “የእንትናን አየሸው “ ”ፓ የእንትናየ እንዲህ ረጅም ነበር እንዴ “ እየተባባሉ ያያሉ በመንደሩ ታዋቂ አናፂ የሆነ

አንድ ሰው ከከተማ በገዛት ሜትር የተወዳዳሪወቹን ብልት ይለካል ይመዘገባል ይለካል ይመዘገባል ውጤት ተደምሮ ተቀንሶ እስኪነገር ዝምታ ሹክሹክታ ከዛም የሽማግሌወቹ መሪ ውጠቱን ይናገራሉ " መልካም ነው! እንግዲህ የሁላችሁም ብልት ጎሳችን የሚያስመሰግንና የሚያኮራ ነው ቢሆንም ከጣት ጣት የበልጣል እንዲሉ በዚህ ምርጫ ግሩም የሆነ ረዥም ብልት ያለው "እከሌ ሁኗል" እልልልልልልልልለ ጭፈራው ፉከራው አቧራ ይጨሳል ግብዣው በገፍ ነው ይበላል ይጠጣል በመጨረሻም አምስት ቆንጆ ሴቶች ተመርጠው ለአሸናፊው ይሰጡታል አዲስ ቤት የሰጠዋል በቃ የመንደሩ መሪ ሆነ!! እንግዲህ መሪው በስልጣን ዘመኑ ከሚጣልበት ሃላፊነቶቸ ውስጥ አንዱ በጎሳው ውስጥ ባሏ ጋር በወሲብ ያልተስማማች ሴት ካለች በሱ በኩል የጎደለባትን መሙላት ነው ! መሪ የህዝብ ነው!! ባሏ ጋር ኮከብ አልገጥም ያላት ሴት ወደመሪው ቤት አውራ ዶሮ ይዛ ትሄዳለች ትርጉሙም "ባሌ ጋር ኮከባችን አልገጠመም የልቤን አላደረሰልኝም እንደአውራ ዶሮ ዘሎ ይወጣና ዘሎ ይወርዳል " ማለት ነው ዶሮውን ተቀብሎ ያስገባትና ከባሏ ያጣችውን እነሆ በረከት ብሎ አንጀቷን ያርሰዋል !! እንዲህ ነው እንጅ ወንድ እስከትል!! ብሎ ጓደኛየ ታሪኩን ጨረሰ "እንዴ አንድ ወንድ ሚስቱ ባታስደስተውስ ለማን አቤት ይላል " አልኩት "ለመሪው የተሰጡጥ አምስት ቆነጃጅት ስራቸው ምን ሆነና!! በሚስቱ ያልተደሰተው ወንድ የግንድ ቁራጭ ተሸክሞ ወደመሪው ቤት ይሄዳል በሩ ላይ ሲደርስ ግንዱን ያስቀምጥና ግንዱ ላይ ይተኛል ትርጉሙም ሚስቴ እንደግንድ ከስሬ ተጋድማ የማደርገውን እንደቱሪስት ከማየት በስተቀር ምንም አትላወስም " ማለት ነው !! ቆነጃጅቶቹ አስገብተው ጧት እንደተቀቀለ ፓስታ እየተሽመደመደ ወደቤቱ!!መንገድ ላይ ምነው በሰላም ነው ካሉት ግብድ ወድቀብኝ እያለ ለማኘኛውም ምርጫው ሰላማዊ ፍትሃዊ ዲሞክራሲያዊ ነበር !ጓደኛየ እንደታዘበው !!

# መቀስ ሸርጥ ቦለቲካ

አባቴ ፀጉሩንም ሆነ ፂሙን በተስተካከለ ቁጥር እናቴ ጋር ይኮራረፋሉ ይነታረካሉ ይሄን መኮራረፍ እየፈራ ነው መሰል ፂሙ ሲያድግ ሽቅብ ወደኮርኒሱ አንጋጦ አገጩን በመዳፉ በማሻሸት "ኤዲያ ደግሞ ይሄ ፂም አደገ " እያለ ይበሳካል!! እንግዲህ የኩርፊያው መነሻ ፍቅር መሆኑ የገባኝ ቆይቶ ነው !!

የመንደራችን ፀጉር አስተካካዩ ግዛቸው "ትንሽ ወፈፍ" ያደርገዋል እየተባለ ይወራል ! ታዲያ አባቴ በአንገቱ ገመድ ቢገባ ከግዛቸው ሌላ ማንም ጋር ፀጉሩን አይስተካከልም ከኩርፊያቸው በኋላ እናቴ አባባን በለሰለሰ ድምፅ ትመክረዋለች

" ኸረ ተው አለሙ ተው ለኔ ባታስብ ለልጆችህ እዘን እስቲ በዛ በጨርቅ ተጠቅልለህ ከስሩ ቁጭ እንዳልክ ቢነሳበት ምን ይውጣሃል ይሄ ሰው ያመዋል አንዴ ከተነሳበት ጆሮህም አፍንጫህም አንገትህም ፀጉር ነው የሚመስለው በያዘው መቀስ ከታትፎ ቁጭ ቢያደርግህ የማን ያለህ ይባላል ?" ትላለች በእራሷ ንግግር እራሷ እያማተበች !!

አባቴ ከት ብሎ ይስቅና " አይ አንች አብደሽ የምታውቂ እኮ ነው የምትመስይው " ይላታል አዲስ የተስተካከለውን ፂሙን እያሰሻሸ ትበሳጫለች ከአጠገቡ ተነስታ በቁጣ ፊት ለፊቱ ትቀመጥና " ለእኔ ባታስብ ለልጆችህ አታስብም ? የራስህ ጉዳይ! <እሬሳችሁን ውሰዱ> ሲሉን ከፀጉር ቤት ለቃቅመን በደግ ቀን የገባነው እድር አለ "ቅበሩልን" ማለት ነው !! ከዛ ወዲያ እኛም እግዜር እንዳለልን እንሆናለን !! " ጩኸቷ ጣራውን ሊበሳው ይደርሳል በተናገረች ቁጥር ራሷ ላይ ሸብ ያደረገችውን ሻሽ ታስተካክላለች

"ኸረ ተይ ሰንየ እንዲህማ አትናደጅብኝ በቃ ሁለተኛ አልሄድም " ይላታል "ሁልጊዜ ትምላለህ ትገዘታለህ ያው ነህ ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭ " ትላለች በምሬት ቀጠል አድርጋ "እንደው መጥፊያህ ቢሆን እንጅ ስንት ጎበዝ ጠጉር አስተካካይ ሞልቶ እንዲህ እንደበግ ሸልቶ የሚልክህ ሰው ጋር መጣበቅ " "ሰኒየ መቸ ጠጉር አስተካካይ

ጠፉ አልኩ ስለአገር ጉዳይ ለማውጋት እኮ ነው ግዛቸው ቤት የምሄድ ደግሞስ እኔ ብቻ አይደለሁ የመንደሩ ሰው ሁሉ እዛው ነው ፀጉን የሚቆረጥ ቦለቲካ እናወራለን እንወያያለን “ ይላል እውነቱን ነው ፀጉር ቤቱ ሁልጊዜም ስለወቅታዊ ጉዳዮች የሚወራበት የመወያያ መድረካቸው ነበር ለመንደሩ አባቶች ሁሉ !!

“ አላየንም ውይይት እቴ! በእጁ አንዳች የሚካል መቀስ ጨብጦ ከበላይህ የቆመ ሰው ጋር ጋር ቦለቲካ መወያየት ሁሁሁ ወደው አይስቁ አሉ ” “ምናለበት አሱ መቀስ መያዝ ስራው ነው እንግዲህ እሱ መቀስ ይዟልና ለመወያየት እኔም መቀስ ይዠ አልሄድ ሆሆ “ ይላል አባባ “ግዴለህም አለሙየ ውይይት ካማረህ እሱም መቀሱን አስቀምጦ አንተም ከታሰርክበት ሽርጥ ተፈተህ ገብሬ ቤት (ግሮሰሪ ነው) ገጥ ለገጥ ቁጭ ብላችሁ ተወያዩ በዛውም አንድ ሁለት ስትሉ ወጉ ይደምቃል “

“አይ ሰኒ እዛ ያለውን ጨዋታና ደስታ በምን አባቴ ባሳየሁሽ” ይላል አባቴ “ጨዋታ “ሲል ልቤ ተሰቀለ እናቴ ብስጭት ትላለች

“ አባባ ተነስቶ አጠገቧ ይቀመጣል እጇን ትከሻዋ ላይ ጣል ያደርግባትና በሌላኛው እጁ የእጇን መዳፍ እየመታ እንደማይሄድ ይምልላታል ታምነዋለች የአባቴ እጆች የሆነ አስማት አላቸው እናቴን ከነኳት ያበርዷታል ፂሙ እስከሚያድግ ሰላም ይወርዳል

አንድ ቀን ታዲያ እናቴ “ ፀጉርህን ተቆረጥ” ብላ ሁለት ብር ሰጠችኝና መንገድ እንደጀመርኩ የግዛቸው ፀጉር ቤት ጋር ደረስኩ ምን ሰይጣን እንዳሳሳተኝ እንጃ ዞር ዞር ብየ አየሁና ዘው ብየ ገባሁ ብቻውን ነበረ ወንበሩ ላይ ትራስ ጨምሮ ከፍ አድርጎ አስቀመጠኝ ኩራትና ክብር ተሰማኝ

ከዛም አንገቴን ግጥም አድርጎ በሽርጡ ሲያስረኝ ትንፋሽ አጠረኝ በጣቴ ቀስ አድርጌ አላላሁት በመስተዋት ውስጥ ግዛቸውን ሳየው ብቻውን ይስቃል ፈራሁ ደግሞ ብቻውን ያወራል አሁንም ፈራሁ ትልቅ መቀስ አነሳና በግራ እጁ ይዞ (በመስተዋት ውስጥ ስለማየው ነው መሰል ግራኝ የመሰለኝ ) ጆሮየ አካባቢ ለሙከራ ሲያስፏጨው የእናቴ ምክር ተግተለተለብኝ

“ በዛ በጨርቅ ተጠቅልለህ ከስሩ ቁጭ እንዳልክ ቢነሳበት ምን ይውጣሃል ይሄ ሰው ያመዋል አንዴ ከተነሳበት ጆሮህም አፍንጫህም አንገትህም ፀጉር ነው የሚመስለው በያዘው መቀስ ከታትፎ ቁጭ ቢያደርግህ የማን ያለህ ይባላል “ ልቤ በፍርሃት ልትፈጠረቅ ሆነ ጆሮየ ተበጥሶ ሽርጡ ላይ ዶብ ሲል ታየኝ ግዛቸው በለሆሳስ ሲያጉተመትም ቆይቶ “መሆን አለበት “ አለና ጮክ ብሎ ተናገረ ብቻውን እኮ ነው የሚያወራው ወይኔ ውሳኔ መሰለኝ!!

ማበጠሪያ ሊያነሳ ራቅ ሲልልኝ አመቻችቶ ካስቀመጠብኝ ወንበር ቱርርር ብየ የወለሉ ምንጣፍ ላስቲክ አንሸራቶኝ ነበር ለትንሽ ነው የተረፍኩት በሩን አንዴ ዘልየ ከነ ሽርጤ ፈትለክ ወደቤቴ “አንተ ኧረ ሽርጡን ” እያለ ከኋላየ ይጮኻል ግዛቸው ጅልህን ፈልግ ሽርጡን እንደክንፍ እያውለበለብኩ ብርርርርርርርር ታስሮ በክብር ወንበር ላይ ከመቀመጥ ከነእስራት እስከቻሉት መሮጥ ይሻላል

ሌሊት ነው ሰው ሁሉ ለጥ ብሏል

ሌሊት ነው ሰው ሁሉ ለጥ ብሏል (አንተን እኔንና አንችን ጨምሮ) በረዶ የቀላቀለ የዝናብ ድምፅ የጣራውን ቆርቆሮ ሲያንኳኳው መቶ ሽ ፈረሶች ጣራው ላይ የሚጋልቡ ይመስላል በዚህ ዶፍ የሚሰማው የነጎድጓድ ድምፅ ልብ ያርዳል ንፋሱ የመንደሩን ቆርቆሮ ቤቶች ጣራ ያንኳኳል ዛፎች ውሽንፍር በቀላቀለው ንፋስ ንጉስ ፊት እንደቀረበ ተራ አሽከር ጎንበስ ቀና ይላሉ ከነቅጠል ቅርንጫፋቸው !!( ከዛ መሃል አንዱ ቅጠል “ላለፈው ንፋስ ሁሉ አልሰግድም” ማለት አትችልም ግንዱ ከሰገደ ቅጠሉ

ሰማዩን እንደወረቀት መሃል ለመሃል እየበሸከት አገር ምድሩን በአስፈሪ ቅፅበታዊ ወጋገን የሚያጥለቀልቀው ሙብረቅ ሰላሳ ጊዜ ያስማትባል ቀን ሲፎክር እና ሲሸልል የነበረው ሁሉ እቤቱ ከቤቱም አልጋው ውስጥ ተደብቆ ጓ ባለ ቁጥር ሰውነቱ አልጋው ላይ ይነዝራል ጓጓታው በስሙ የተላከ

በዚህ ጨለማ አንበሳ እራሱ “ውጭ ጋር የተረሳ እቃ” አስገባ ተብሎ ቢላክ በፍርሃት ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል !! ጅብ ምን የመሰለች ጠብደል አህያ ሙታላሃለች ሂድና ብላ ቢባል “ ጅብ በአህያ ብቻ አይኖርም” ብሎ ከጉድጓዱ ንቅንቅ አይልም!! ይሄን ዶፍ ይሄን ውሽንፍር ይሄን ጨለማ የናቀች አንዲት ሴት ውሽንፍርና ጨለማውን እየሰነጣጠቀች ትገሰግሳለች በድፍረት!! “ሚስኪን የምተበላው የምትጠጣው ያጣች የጎዳና ተዳዳሪ ትሆን ? “ ወይስ “ ልጁ የጠፋባት ሚስኪን እናት ?” ሁለቱንም አይደለችም ማን እንደሆነች ገምቱ አላወቃችኋትም!! ጅጅ ናት!! እጅጋየሁ ሽባባው !! “እኮ ጅጅ እች የእኛ ጅጅ ?” አዎ የእኛ ጅጅ !! በቃ ሴት ልጅ ከምር ስታፈቅር ማየት ከፈለጋችሁ የጅጅን ሙዚቃ አዳምጡት ፍቅር ላይ “ሙድ” እንያዝ የምትሉ “ዘፋኞች “ እራሳችሁ ጅጅ እግር ስር ቁጭ ብላችሁ ፍቅርን ተማሩ ! የሃኪም ትዛዝ ነው!! (ቧት አንድ ማታ አንድ ከምግብ በፊት ) ወደ ሙዚቃው ከላይ ባልነው አስፈሪ ሌሊት ጅጅ “ያፈቀርኩትን ሰው አይኑን ሳላይ አላድርም “ አለችና ከሞቀ ከደመቀ ቤቷ ተነሳች የመጀመሪያው መካሪ ልቧነው ”ምን ነካሽ በዚህ ጉድ ነገ ምናምን ታይዋለሽ አርፈሽ ተኚ ጅቡ አሳዝነሽው ቢምርሽ ብርዱ ይገልሻል “ አላት ጅጅ ጫማዋን አሰረች “ሰምተሸኛል “ አለ የጅጅ ልብ ችላ ስትለው

ጠልና አንዛቡ ብርዱ እሳትና “ውኢይ” ዝናብና ዶፉ ጎረፉ ውርጭና አመዳይ ከንቱ ላያግደኝ አትፍራ አትጨነቅ ልቤ ሳላየው አላድርም ያንን ናርዶስ ያንን ከርቤ!! “እ” አለ ልቧ አበደች እንዴ እች ልጅ አይነት ሃሳብ

“ሰምተሃል” ብላው በሩን ከፈተች ልቧ እንደፈረደበት ተከተላት እያወራት መንገድ ጀመሩ “በለጭጭጭጭጭጭ “ እግዜር የተተረተረ የብረት ሰማይ የሚበይድ ነው የሚመስለው ለአ ፍቃሪዋ ጅጅ የፍቅር ርችት ፈሪህን እዛ ሂድ

“ ለመሆኑ ማነው እንዲህ ክንፍ እብድ አድርጎ በዚህ ጉድ የሚያንቀዠቅዠሽ ” አለ ልቧ ጅጅ እንዳታመልጠው ከጎኗ ኩስ ኩስ እያለ ያፈቀረ ሰው እንኳን ተጠይቆ እንደውም አውራ አውራ ይለዋል ጅጅ ስለውዷ ልቧ እስኪገርመው ሙገሳውን

“ እንግዲህ የኔ ውድ የኔ ፍቅር የኔ ጌታ የኔ በቃ የኔ ኡኡኡኡኡአ በቃ የኔ ሁሉ ነገር ” በዝናቡ እጆቿን ዘርግታ ወደሰማይ በእርካታ በደስታ

“ተይዛለች እች ልጅ “ አለ ልቧ በልቡ

.” የኔ ጀግና ግርማው እንደአንበሳ ነው እንደማንም ኮሳሳ ላንጌሳ እንዳይመስልህ ” “ ውድሽ ስፖርተኛ ነው እንዴ ጅጅየ ” አለ ልቧ

“ ባክህ ሰውን የሚያገዝፈው ስፖርት አይደለም ፍቅር ነው ሞገስ የሚሆነው ፍቅር! ክብር የሚሆነው ፍቅር ነው ጡንቻህን አፈርጥመህ ካለፍቅር ብትንጎራደድ ጥላ ቢስ ነህ! ወለፈንዲ !! ፍቅር ነው ከፍ የሚያደርግህ ፍቅር ነው ከሰማይ የሚወርድ መናህ ፍቅር ነው መጠጊያ መሸሸጊያህ ፍቅር ነው ንብረትህ ፍቅር ነው ወዳጀ ልቤ !! የእኔ ጀግና የፍቅር ከራማ የሰፈረበት አንበሳ ነው ጎፈሩ ፍቅር ጡንቻው ፍቅር ሃብት ንብረቱ ፍቅር !! ብወደው

ኮሳሳ ልቧ ፍቅር “ጠብ” አለበትና “ሲገዝፍ” ተሰማው ፍርሃቱ ለቀቀው ጅጅ የደፈረችውን ሲደፍር ጭራሽ ከሷ ቀድሞ በዶፉ ውስጥ በጨለማው ውስጥ ተፈተለከ !! ወደወደደችው ውዷ ወደፊት ወደፊት በፍቅር ወደኋላ የለም በፍቅር ያለፈ በደልን መቁጠር የለም ፈትለክ መቅደም በፍቅር ነው በአፍሽ የቀደምሽ ብልጣ ብልጥ መሳይ ደነዝ ሁሉ በኮተትሽ መረብ ፍቅርን ያጠመድሽ የመሰልሽ ከንቱ ቁማርተኛ ሁሉ መቅደም በፍቅር ነው ተከተይኝ ተከተለኝ (ልብህን ተከተል ያመነን ልብ ማንም አይመልሰው ) ፈትለክ ከሩቁ በጨለማው ውስጥ መንገድ ላይ የተኳተረውን ውሃ እያንቦጫረቀው

ዶፍ ዝናብ ሳይፈራ ወንዙ ሙላት ሳያግደው የሃምሌ ነሃሴ ቆፉ ብርዱ ሳይመልሰው ፍልቅልቅ ብራቁን ድምፁን ሽብሩን ሳይፈራ ልቤ ገሰገሰ "ዛሬ" ሊኖር ከአንተ ጋራ !! ዛሬ!!(NOW) ጀምበር ሳትወጣ ውዳችን በር ላይ ከች!! ኳኳኳ መጥተናል !! ፍቅራችን ብቻ ይዘን እዛ ውስጥ ሀሉም አለ!! ሳንቀጠር ሳይደወልልን ሳንለመን ሳንደለል( ክፈት በለው በሩን የጌታየን) ሳንቅደረደር ሴትነት ቪያ ገደል ይግባ ከፍቅር አይበልጥም "ወንድነት" ስለፍቅር ትእቢቱ ይንኮታኮት ዘራፍ ለፍቅር ብቻ!! "ወንድን ልጅ መለመን ያስንቃል" የምትሉ የንቀት ርዝራዦች እንናቅ!!!! ወንበር ስቦ ማስቀመጥ የመከበር ጥግ መስሏችሁ ወንበር ሳቢ የተሳበ ወንበር አነፍናፊ ሁሉ ክብር ወዲህ ነው ሂሳቡ ኑ ጀምበር ሳትወጣ

ስለፍቅር እንናቅ!!!!! አዳሜ ስለገንዘብ እንደቁጤማ የትም እየተጎዘጎዝክ ስለፍቅር መናቅን ስለምን ትፈላሰፍባታለህ ባዶ ልብህ ዝቅ ማለትን ተፀየፊች ".ፍቅር ሰጥቶ መቀበል ነው." ሁሁሁሁ የከሰሩ ባዶ ልቦች ጨኸት ፍቅር መስጠት ነው መሰጠትም ነው መልስ አንፈልግም ስናፈቅር አድርገን አድርገን ያለንን ሰጥተን ሰጥተን ምንም ያልሰጠን ሲመስለን ያኔ ነው የፍቅር ልኩ !! አድንቀህ አድንቀህ ሽ ቃላት ሚሊየን ድርጊት ጋር ተቀይጦ ሲያንስህ መቀበልን ብቻ የሚያልሙ ለማኝ ልብን ተሸክመዋል የውሻሸት ቁስሉን በፍቅር ፋሻ ጠምጥሞ የፍቅር ጎዳና ላይ ተኝቶ የሚለምን ውሸታም ለማኝ!! ለማኝ አይመርጥም የተወረወረላችሁን ተቀበሉ ! የአላፊ አግዳሚ አድናቆት ያደለበውን ደነዝ ሂሊና ውጭ ያደረ የፀበል እቃ ነው አትበሉ !! ጅጅ መንገዷን ቀጠለች ውዷን እያሞገሰች ዝናቡ ፍቅር ነው በፍቅር የሚያጠምቅ በየእርምጃው ወደውዷ በቀረበች ቁጥር ከጥላቻ

በካህን ሽብሻቦ በሊቅ በዲያቆኖች ዜማ ቢወደስ "ቢመለክ" በታላቅ ጉባይ ቢሰማ ሽ ቃላት የሚያንሰው የወንድ የቆንጆወች አውራ የታተምከው ፈሳሽ በልቤ ገነት አዝመራ የአፍቃሪ ልቧ በጥላቻ ሃሩር በመለየት ድርቀት ተሰነጣጥቆ የፍቅር አዝመራዋ እንደጠወለገ ውዷ እንደሃምሌ ዝናብ ዘነበ ጨሰ የደረቀው መሬት ትንፋጉ የፍቅር መስዋት ሽታ ነው ናርዶስ ደግሞም ከርቤ !! ረሰረሰ አበበች ፈኩ ውዷ የሂወት ውሃ አጥግቧት ጎረፈ አዋሽ ሆነ አባይ ሌላ ብርሃን

ግርማው እንደአንበሳ ውበቱ እንደፀሃይ የአይኖቹ ማረፊያ የልቤ ሲሳይ ትለዋለች

እንዳለችው ውዷ በር ላይ ደረሰች ሊነጋጋ ሲል ውስጥ አንበሳዋ አለ ናርዶስ እና ከርቤ የአይኗ ማረፊያ ሲሳይዋ ውስጥ አለ ብርዱ አንጀቷ ውስጥ ገብቶ እያንዘፈዘፋት በሩ ላይ ቁማለች ፀጉሯ ላይ በሹርባዋ መካፈያ የበረዶ ብናኝ ሽበት መስሎ ሰፍሮባታል ጠል እውስጥ እሳት

አለች በራሴ ጠል ሰፍሯል ውዴ በሹርባየ አንዛብ ደረስኩ ንጋት አለ ክፈትልኝ የኔ ሰበብ ፀሃይ ብልጭ አለ ጠራ ፈካ ገመገሙ ክፈት አይንህን ልይ ውዴ የአገር ልጅ ድማሙ ፀሃይ ብልጭ አለ ጠራ ፈካ ገመገሙ ቀድሞ የደረሰ ልቧን ይዞ

# አንዲት ቃል!

## ይህ ተከታታይ ወግ ሁለት ክፍሎች አሉት

## ክፍል 1

ለጠየቁኝ ሰዎች ሁሉ ሊያን ያፈቀርኩበትን ምክንያት ስነግራቸው የምቀልድ ይመስላቸዋል! እኔ ግን ከልቤ ነው! ለምንድነው ሰው ሁሉ ራሱ በተያዘበት ወጥመድ ሌላ ሰው ካልገባ በስተቀር ከእርሱ ውጭ ሌላው የተጠመደ የማይመስለው!? ሊያን አፈቅራታለሁ ያውም ሁለት አመት ሙሉ የገባችበት ገብቾ ነው ያፈቀርኳት! እርሷም ታፈቅረኛለች (እና ባታፈቅረኝ ) ብቻ ብዙ ነገሯን አሳልፋ ሰጥታኛለች ተቀብያለሁ!

የግቢው ተማሪ ሁሉ ሊያን ያፈቀርኳት የሃብታም ልጅ ስለሆነች ይመስላቸዋል .... በእርግጥ የሃብታም ልጅ ናት ቤተሰቦቿ ((ከተማ)) አላቸው (ምን ልበል ታዲያ) ነዳጅ ማደያ ጋራዥ ሆቴል ካፍቴሪያ የቆዳ ጫማ ፋብሪካ ወርቅ ቤት ሱፐርማርኬት ግሮሰሪ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመኪና ማከራያ ይሄ ሁሉ አላቸው .....እኔስ ምን አለኝ ...እግዜሩ ብቻ ! ላአከአምላክ የሚባል ዲያቆን ወዳጄ ይሄን ብነግረው " ብቻ አይባልም ወዳጄ አብርሃም .....እነሱ ከተማ አላቸው አንተ ደግሞ የአለም ጌታ አለህ በቃ ሁሉ አለህ ...." አለኝ !ተፅናናሁ !

ጓደኞቾ ሁሉ "አብርሃም ባንክ ጠበሰ " እያሉ ያሙኛል ....ኧረ ፊት ለፊትም እንደዛ ነው የሚሉኝ ...ቸሩ መዳኒያለም ያውቀዋል ሊያ ከተዋወቅንበት ቀን ጀምሮ ሰባራ ሳንቲም አውጥታ አታውቅም ! እግዜር ይባርካት የፈለገ ትልቅ ሆቴል ብትገባ ከቡናና ከሽሮ ውጭ አታዝም ! ቢሆንም ሊያየ የኔ " ንግድ ባንክ " ብር አታስወጣኝም ! ታውቀዋለች ጎኔን ! ደግሞም የምር ሃብታሞች ብር አይደንቃቸውም ! ሰው ነው ረሃባቸው ! እናም እኔን ጥግብ እስክትለኝ እንዳሻት እንድታደርገኝ ፈቀድኩላት እነዳሻትም አ,ረገችኝ

ድፍን የዩኒቨርስቲው ተማሪስ እኔና ሊያ በመፋቀራችን ምን አስገረመው ብለን ብንጠይቅ ..."የሊያ ሰውነት" የሚል መልስ ነው የምናገኘው ሊያ "ትንሽ ደልደል" ያለች ናት...እኔ ብቻ ነኝ" ደልደል ያለች" የምላት ...ሌላው ሰው አገር ናት ይላታል ....ዝግባ ነው የምታክለው ይላታል .....እንደአብርሃም አይነት ሰባት ሚስኪኖች እንደችቦ ባንድ ላይ ታስረው ታክላለች ይሏታል ....የኛ ሰው ስም ለመለጠፍ ማን ብሎት ! ዋናውን ስም አጣርቶ ሳያውቀው እኮ ነው ቅፅል ለመቀጠል የሚሮጠው !

እና እንደነገርኳችሁ ሊያየ ደልደል ያለች ልጅ ነች ...ሰማኒያ ሰባት ኪሎ ብቻ ! ግን ሰማኒያ ሰባት ብቻ መሆኗ ይገርመኛል ... እኔ መጀመሪያ "አብርሃም ባንክ ጠበሰ" ሲሉ በገንዘቧ ሳይሆን በሰውነቷ ቅርፅ መስሎኝ ነበር ክብ ናት

ልክ እዚህ ሰንጋ ተራ እንዳለው ወርቃማው ባንክ ቤት! በእርግጥ ማጋነን ይመስላል ግን በሁለት እጆቾ ሳቅፋት እጆን ከኋላዋ ማነካካት አልችልም (እጅ ያጥረኛል ) እንደምንም እጆቸን ለማገናኘት ስሞክር በጭንቀት እየተነፈሰች "አንተ ጨመከኝ " ትለኛለች ! የኔ ቆንጆ ! እኔን ይጭመቀኝ ብየ እጆን ትከሻዋ ላይ ብቻ ጣል አደርገዋለሁ ! የማይናወጥ ተራራ የተደገፍኩ ይመስለኛል ለስላሳ ተራራ ከወደአናቱ የፍቅር ምንጭ የሚንፎለፎልበት

የሊያ ውፍረት በህመም ወይም በሌላ ምክንያት አይደለም መረሳት ነው ! በቃ ቤተሰቦቿ ቢዝነስ ሲያሯሩጡ ረሷት ያገኘችውን ስትበላ "ኧረ ቀስ "የሚል ዘመድ ጠፋ ....እንደውም ወንድሞቿ ባዶ እጃቸውን እቤት አይገቡም አንዱ ቸኮሌት አንዱ የታሸገ ምግብ ነገር ሌላው ሌላ ሊያየ የኔ ውድ ሪሞቷን ይዛ ሶፋዋ ላይ ቁጭ ትልና ፊቷ የተከመረውን የምግብ ተራራ ታወድመዋለች ! "አንበጣ ነበርኩ " ትለኛለች ስታወራኝ ...ጥሩው ነገር ማንም ምንም ይበል መንገደኛው ሁሉ አንገቱን እየቀለመመ በግርምት ሲመለከታት ሊያ ሲበዛ በራሷ የምትተማመን ውፍረቷ የማያሳቅቃት ልጅ ነበረች !

ሊያን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወኳት ለአጎቴ ነበር "ዛላዋ ከበድ ያለች ጓደኛ መያዝህ ጥሩ ነው …ብቻህን ውልብ ውልብ ከማለት እንዲህ ጥላዋ ሲያርፍብህ አንተም ከበድ ትላለህ " ብሎ መረቀልኝ ! ቀጥየ ለእናቴ አስተዋወኳት እናቴ በጣም ወደደቻት ! ምክንያቱን ግን አልነገረችኝም ! ሊያም እናቴን ከልቧ ነበር የወደደቻት " ምናልባት የእናቴ ቡናና ሽሮ ከአፍሪካ አንደኛ ከአለምም አንደኛ ስለሆነ ይሆናል ! " ስላት ሊያየ "ጉረኛ " ትለኛለች !

ሊያን እንዴት ለፍቅረኝነት እንደጠየኳት ነገርኳችሁ እንዴ ? ያው ቅኔ ተዘራርፈን ነው ….ጓደኞች ነበርን እኔ ግን ፍቅር ጀማምሮኛል ሲመስለኝ እርሷም ገብቷታል …ታዲያ አንድ ቀን ካፌ ውስጥ ተቀምጠን ቡና ስንጠጣ….ዝናብ እየዘነበ ነበር …እኔ ደግሞ በቲሸርት ብቻ ብርድ እያጫወለኝ ኩርምት ብየ ቡናየን ቶሎ ቶሎ እጠጣለሁ

" በረደህ አይደል " አለችን ድምጿ ውስጥ ርህራሄ ነበር

" በጣም "

" እንደኛ ደልደል ብትል ኖሮ ብርድ አይደፍርህም ነበር ሃሃሃሃ" ተሳሳቅን …ስትናገር ትከሻዋን ከፍ አድርጋ በቀልድ ጉራ ነበር

" እኔ የምልህ አብርሽ አንድ ሰባት ኪሎ ስጋ ላውስህ እንዴ ለብርዱ " አለች ክንዷ ላይ ያለውን ትርፍ ስጋ ቆንጥጣ አንድ እጇን እንደቢላዋ እየመተረች ( እየው እንግዲህ ኢላማውን የመታ ተኩስ የሆነ ምላሸን )

((((("አይ ሊያየ ስጋ ማንም ይሰጣል ነፍስ የሚያበድረን ነው ያጣነው …")))) ፓፓፓፓፓፓፓፓፓ አንዳንዴ የራሴ ንግግር ይጥመኛል ! በቃ ባለቅኔስ ከዚህ በላይ ምን ሊናገር ይችላል ….አሪፍ ቅኔ ማለት ሰው ሊለው የሚፈልገውን በየትኛውም መንገድ በትክክለኛው ሰአት ማለት መቻሉ አይደል ! መፅሃፉም ይላል "በወቅቱ የተወረወረች ቃል ምንኛ መልካም ናት "

ሊያ ፊት ላይ ሃፍረት አይሉት ደስታ አይሉት ፍርሃት አይሉት አንጃበበ " በስርአት ማስቀመጥ ከቻልክ " ብላኝ እርፍ !ከዛ ዝምታ ቡናዋን ስታነሳ እጇ ትንሽ የተንቀጠቀጠ መሰለኝ በቃ ይሄው ነው ….ሌላ ቀን ቅኔ ሳይዘረፍ የዙሪያ ሳይኬድ እንደው ተጠጋግተን እንደተቀመጥን …የእኔ የራሴ ከንፈር ጠፍቶብኝ "አሁን እዚህ አልነበር እንዴ የት ሄደ " ብየ ስፈልግ ከንፈሬ ሊያ ከንፈር ላይ ተገኘ !!

ስንሳሳም በሃፍረት እየሳቀች (ሳቋ ራሱ ደልደል ያለ ነው ) እንዲህ አለችኝ " አንተ እንደ ውሃ ተነንኩ መሰል ሰውነቴ ቀለለኝ " ሃሃሃሃሃ የኔ ሊያ እኔ ግን ሰውነቴ ከበደኝ አጎቴ እንዳለው ጥላዋ አረፈብኝ መሰል ….

"አይዞሽ የኔ ቆንጆ ገና ሽንቅጥቅጥ እስከምትይ ነው የምናተነው "

ግን ሊያን ከመሳሜ …ከመጠየቄ …ከመቅረቤ በፊት …ለምን የወደድኳት ይመስላችኋል ….አይኗ ….አፍንጫዋ … ጥረሷ…..ሁሉም አይደለም " ቃሏ "…አንድ ቃል ብቻ አለች ሊያ ላይ ብቻ የምታምር እንግሊዝኛ ቃል ….ለነገሩ ይች ቃል አማርኛ ከመሰለችኝ ቆይታለች ….እና በዛች ቃል ምክንያት ሊያን ማየት ሱስ ሆነብን …አልቀለድኩም !!

## ክፍል 2

ከአሜሪካ ፡- ጆርጅ ቡሽ ልጃቸውም ትንሹ ቡሽ ፣ ክሊንተን ፣ ኦባማ ፣ሚሸል ኦባማ ፣ ቢዮንሴ ፣ሪሃና ፣ ማይክል ጃክሰን (ነብሱን ይማር) ኦፕራ ወዘተ …ከአውሮፓ ሁሉም የእግር ኳስ ተጨዋቾችና አሰልጣኞች እንዲሁም ደጋፊወች …..ከአፍሪካ ደግሞ ፡ - ሙጋቤ ፣ ማንዴላ (ነብሳቸውን ማርርርርርር ያድርጋቸው ) እእእ ማነው ደግሞ ይሄ ትላንትና በወታደራዊ እርምጃ ተንደርድሮ ፕሬዝዳንታዊ ወንበር ላይ ጉብ ያለው የግብፁ ሰውየ …አዎ እሱ !

እና የአፍሪካ ህብረት የወቅቱ ሊቀመንበር ኧረ ብዙ መሪወች ...ከኢትዮጲያ ደግሞ ፡ - ስማቸውን የማላውቃቸው ብዙ ሰወች ተሰልፈው ታክሲ እየጠበቁ ሲያወሩ ... ካፌ እና ሆቴሎች ውስጥ ተቀምጠው ሻይ ቡና ሲጠጡ ...

ይሄ ሁሉ ቱባ ቱባ ባለስልጣን አርቲስትና ህዝብ ((አንዲት ቃል)) ሲናገር በተለያየ ጊዜ ሰምቻለሁ ! ግን ሁሉም ቃሉ አፋቸው ላይ አያምርባቸውም! በዚች አለም ቃሉ እጅጅጅጅጅጅግ በጣም የሚያምርባት (ምነው ሌላ ቃል ባልተፈጠረ እስከል ድረስ )አንዲት ሴት ብቻ ናት የእኔ ፍቅረኛ ሊያ !! እውነቴን እኮ ነው ሊያ ያንን ቃል ስትናገረው .....በስማም !!

ሊያ አልፎ አልፎ የምትናገራት ግን የእኔ የሁልጊዜ ትዝታ የሆነች ያች አንዲት ቃል ሊያን አፍቅሬ እንድቀር አድርጋኛለች ! ውይ ያች ቃል ሊያ ላይ እንዴት እንደምታምር ....አቤት ያች ቃል ሊያ ከንፈር ላይ እንዴት ስእል እንደምትሆን ....ሙዚቃ እንደምትሆን ጃዝ ዶክተር ሙላቱ አስታጥቀቁ አቀናብሮ ሊያየ ከንፈር ላይ ያስቀመጠልኝ ነው የሚመስለኝ ! ይሄው ሃያ ሰባት አመት ሞላኝ እንደሊያ ያች ቃል የምታምርበት ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም !! ወይኔ ያች ቃል !!

በነገራችን ላይ ሊያ ያችን ቃል ለሌላ ወንድ እንዳትናገራት አስምያት ነበር ! ቀልድ እንዳይመስላችሁ በምትወደው ታናሽ ወድሟ ስም ነው የማለችልኝ ...

“ቤቢየ ይሙት ለማንም ይችን ቃል አልናገርም “

“አይ የምን ቤቢየ ነው በስሙ ማይልኝ “

“ ብሩክየ ይሙት አሌካ ...ለማንም ያችን ቃል አልናገራትም የግድ እንኳን ቢያስፈልገኝ ሌላ አማራጭ ምናምን እጠቀማለሁ “ ከምር ! ልክ እንደዚህ ምላልኝ ቃሉ የእኔ ብቻ ሆነ ! እስቲ ፍቅረኛችሁ ለእናተ ብቻ የሚናገረው ቃል አለ ? ሁልጊዜ ወደስጦታ መሸጫ ሱቅ ከመሮጥ እንዲህ ቃል የምትሰጥ ፍቅረኛ ማግኘት መታደል ነው ! እና ልክ እንደጋብቻ ቀለበት ከሊያ ለእኔ ብቻ የሚነገር ቃል አለኝ ! ...ደግሞ ማስማሌ ልክ ነበር እኔን ጉድ የሰራኝ ቃል ሌላውንስ ምን እንደሚያደርገው ምን አውቃለሁ ... ? መጠንቀቅ ጥሩ ነው ! በእርግጥ ጓደኛየ መስፍን “ያው እንደማንኛውም ሰው ተራ ንግግር ነው “ ብሎ ቃሉን ቢያናንቀውም ቆይቶ የገባኝ ነገር መስፍን የሊያን እንቁ የሆነ ቃል የሰማው በጆሮው ሲሆን እኔ ግን ሊያን የምሰማት በአይኔ ነበር ! አንድ ቀን ታዲያ መስፍንን “እስቲ ግዴለህም ስትናገር እያት” አልኩት አያት

“እሽ ምን ታየህ “ አልኩት በኩራት

“ ያው ከኋላዋ ያለውን አለም በግዝፈቷ የከለለች ልጅ ናታ “ ብሎኝ በስልክ ወደሚጫወተው “ጌም “ አቀረቀረ ! ድሮውንስ ጌም ያደነዘዘው ሰው ምን ይታየዋል ! ተበሳጨሁ ! እና ለዚህ ሁሉ ፍቅር ያበቃኝን ጦሰኛ ቃል ከላይ ነገርኳችሁ አይደል ? አ ል ነ ገ ር ከ ን ም ? .....እንዴዴዴዴዴዴደዴ ! እና እስካሁን ቃሉን ሳልነግራችሁ ነው ይሄን ሁሉ የማወራው ...? (አቤት የሰው ልጅ ትእግስት ከምር አሳዘናችሁኝ ! ይሄን ሁሉ ነገር ሳወራ ካሁን አሁን ቃሉን ተናገረ ብላችሁ ላፕቶፓችሁ እና ስልካችሁ ላይ ቁልጭ ቁልጭ ስትሉ ታየኝ ? ለነገሩ ምን ላድርግ እኔም እኮ ሊያየ ስታወራ ካሁን ካሁን ያንን ቃል ተናገረችው እያልኩ እንዲህ እንደናተ ነበር አፍ አፏን እያየሁ የማፈጠው )

ለነገሩ ቃል አይደለም ቃላት ናቸው ያው ግን ከመኖር ብዛት አንድ ቃል ሁነዋል ...ምን መሰላችሁ ቃሉ ...” አ, ራ ይ ት “ በቃ ይሄን ሁሉ አመት ከሊያ አፍ እንደጫጨት ስለቅመው የነበረው ቃል ...የፍቅሯ እስረኛ ያደረገኝ ቃል አ ራ ይ ት ነው ! አራይት የኔ ሙዚቃ... የኔ ትዝታ ባቲ ....አንችሆየ መዲና ዘለሰኛ ....አራይት የእኔ ስእል ... አራይት የእኔ ፊደል የለበሰ ፍቅር..... አራይት የኔ የኔ ሊያ ቃል !

አ ራ ይ ት .... ብትንትኔን እንዳወጣው በታትኝ እነግራችኋለሁ ( እናተ ናችሁ ያላችሁኝ ለሌላ ለማን እናገራለሁ ታዲያ ) የምናፈቅረው ሰው የምንወደው ሰው እኮ ውስጣችን የሚተዋቸው ብዙ ጭረቶች ብዙ መስመሮች አሉ

...ለእኛ ብቻ የሚገቡን ተቀላቅለው ትልቅ ምስል የሚከስቱ ግን በየትኛውም ቋንቋ ለሌሎች ልናስረዳቸው የማንችላቸው የእኛ የግላችን የውስጣችን ህመሞች ሁነው የሚቀሩ ስንት ጉድ ትዝታወች አሉ ...የወደድነውን ልጅ “በደፈናው ጥሩ ልጅ ነበር” እንላለን ...ለእኛ ግን በአይምሯችን ውስጥ ጥሩነቱን የገነቡብን አነጋገሩ ፣ድምፁ ውስጥ ያለው ዜማ ከአይኖቹ የሚፈናጠቁት የደግነት ብርሃኖች ሁሉ ይታዩናል ....ለሰው ግን ምን ተብሎ ይወራል ....

“ አፈቅራታለሁ “ ስንል የምናፈቅራት ልጅ ጠረን ውስጣችን አለ ...የእጇ ልስላሴ ይሰማናል ...ተቀጣትረን ከዛጋ ስትመጣ እኛ ጋ እስክተደርስ ያለው ስሜት አረማመዷ ስታየን የፊቷ ገፅ ላይ የሚታየን ስሜት ደርሳ ስንሳሳም እቅፍ ስናደርጋት ሰውነታችን የሚሰማው ንዝርት ደስታ እረፍት ... ውስጣችን አለ..... ስሜቱ ስታቅፏት ከፀጉር ቤት መጥታ ይሆናል የሆነ የእርሷ ብቻ የፀጉር ሽታ አለ ...ጋውያ ነካክቶ ያገነነው ! የፀጉሯን ቁጥር ሁሉ ታውቁታላችሁ ...አዎ አንድ ሁለት ብላችሁ ቆጥራችሁት ሳይሆን ደመነፍሳችሁ የሰፈረው ስፍር የለካው ልኬት አለ !

ነፍስ ሲናበብ የፍቅረኛችሁ ትንፋሽ ይለካል በፍቅር ስርቅርቅ ስትሉ ያፈቀራችሁት ሰው... ነፍሱ ሳይቀር ስንት ግራም እንደሆነ ሹክ የሚላችሁ መንፈስ አለ ! የስልጣኔ ትልቁ ቁሸት ይህን የእኔነት ስሜት ይቀማናል የምናቅፋት ሴት የብዙ ...እኛም የእልፍ ሴቶች ንብረት የመሆን ስሜት ውስጥእንገባለን ! መንገደኞች ከሆንን ውስጣችን ስም ያላት ምስል ያላት ጠረን ያላት ሴት ሳትሆን ማንም ትሁን ማን “ሴት “ ብቻ ትቀራለች ! ጠረኗ ዲዮድራን እና ሽቶ የሆነ ...ያንን የተጠቀመችውን ዲዮድራን ት የተጠቀሙ ሴቶች ሁሉ የሚጋሩት ጠረን ... ስለዚህ ተመሳሳይ ጠረን ያላቸው ሴቶች ከአንድ ሱቅ ተመሳሳይ ሽቶ ስለገዙ ብቻ አንድ ይሆኑብናል ...”ሴት ያው ሴት ነው” ይላል አይምሮህ ! አንድ አይነት ወሬ ያላቸው ወንዶች አንድ ዩኒቨርስቲ ጠፍጥፎ የሰራቸው አንድ ሚዲያ አንድ አይነት ዜና አንድ አይነት ድምፅ ያስቀመጠባቸው ... “ወንድ ያው ወንድ ነው “ ይላል አይምሮ ...ማንም ቢያቅፈን ግድ አይሰጠንም ... መነካካቱ አደንዝዞን መተሻሸቱ አደንዞን ቃላችን ኳኳታ አብሮነታችን ድካም ሁኖብናል ! አንድ እይታ በስሜት የሚንጠን እኛ ...ደንዝዘን ስንቱ ትዳር አፈር ድቤ በላ ! ጭረት የለሽ ስእል ልሙጥ ነፍስ አሸክሞን ከተሜነቱ ! ስልጣኔ ....ያለችንን እኛነት እንደብቅል ዘቅዝቆ አራግፎን !

እነዚህ የስሜት ጭረቶች የነፍስ መስመሮች ካልተገጣጠሙና ውስጣችን ካልተጠራቀሙ ደግሞ ውበት እና የወሲብ ስሜት እንጅ ፍቅር አይገነቡም ! ሰዓሊ ጓደኛየ እያሱ እንደነገረኝ “ማንም ሰአሊ ስእል አይደለም የሚሰው ... ጭረት ነው ሸራው ላይ የሚያስቀምጠው መስመር ነው የሚዘራው እይታውን እንደዝናብ እያጠጣ በምናቡ እንደመስኖ እያረሰረሰ ጭረትና መስመሮቹን ሲያሳድጋቸው ራሳቸው የሆነ ምስል ይከስታሉ ....ሰውም ይሁን ቁሳቁስ የሚሊየን ጭረቶች ውጤት ነው !” እውነቱን ነው ! መልክ ከመልክ የሚለየው በጥቃቅን ጭረቶቻችን ነው ! ...ስሜትም ጭረቶች የገነቡት መስመር... መስመሮች ያዋቀሩት ምስል ነው ! የድምፅ ጭረት አለ የምስል ጭረት አለ የጠረን ጭረት አለ የመንፈስ ጭረት አለ .... ይሄ አይምሯችን ይሄን ሁሉ ጉድ እንዴት ባንድ ላይ እንደሚመዘግበው የፈጠረው ይወቅ ! ቃል ደካማ ነው ምን ይገልፃል ....

እ......ና ይሄውላችሁ እቤቴ ስትመጡ ግድግዳየ ላይ አራት ትንንሽ የፎቶ ፍሬሞች ተሰቅለዋል... ፍሬሞቹ ውስጥ አራት አፎች አሉ ...ሊያን እያንዳንዱን ፊደል እያስባልኩ ፎቶ አንስቻት እኮ ነው ! ኦ...ራ...ይ...ት ይሆናል ይሄ የፊደል ጭረት ተደማምሮ መስር ሲሆን ....

ኦ

“ኦ” ኦራይት የሚለው ቃል የመጀመሪያ ድምፅ ነው ! ሊያየ “ኦ “ ስትል ቀይና ወፈር ያለ ከንፈሯ ሰብሰብ... ሞጥሞጥ ይልና እንዴት እንዳመሳሰልኩት እንጃ እንጅ ...የወዳጅ ጉርሻ መስሎ ፊቴ ይደቀናል ! ስትር ያለ በደንብ የተጠቀለለ ቀይ የዶሮ ፍትፍት ጉርሻ ይ መ ስ ላ ል ! “ኦ” ሰትል የግንባሯ ቆዳ ወደላይ ሰብሰብ ይልና አይኖቿ ፈጠጥ ይላሉ ...እና ድምፁ ደግሞ ትንሽ ጎተት ይላል ...የሊያ ከንፈር ከሌሎች ከንፈሮች የሚለየው “ኦ” ን በመጥራት የተለየ ቅርፅ ስለሚይዝ ነው የ ተ ለ የ!

ብዙ ሰወች "የአንጀሊና ጆሊ ከንፈር ያምራል " ይላሉ ...አንጀሊና ብዙ ፊልሞቿ ላይ " ኦራይት " ስትል "ኦ" ላይ በሪሞት ኮንትሮል እያቆምኩ ከንፈሯን ከተለያየ አቅጣጫ አጥንቸዋለሁ .....ምን ያደርጋል የሊያ ከንፈር ላይ እግሩ ስር አይደርስም !! (ከንፈር እግር አለው እንዴ ...ያው እግር እስኪቀጥን ያንከራትታል እንጅ እሱማ እግር የለውም ) ሊያየ "ኦ" ን በጠራች ቁጥር ኦ ላይ በከንፈሬ አቋርጣታለሁ ...ከዛ ከንፈሯን በመዳፏ ጠርጋና ወደኋላ ገፋ አድርጋኝ " ራይት " የሚሉትን ፊደላት ትጨርሳቸዋለች (ይሄ ትትትትትንሽ ግነት አለበት ሂሂ) በርግጥ ቤታችን ከሆንን እንኳን "ኦ" "..ጨ " ብትልም ኦ ያለች ነው የሚመስለኝ !

ራ

ሊያ ከ "ኦ" ወደ "ራ" ስትሻገር ድንገት ሰብሰብ ያለው ከንፈሯ እንደርችት ይበተንና ከንፈሮቿ ግራና ቀኝ ሸሽት ብለው አፏ በመጠኑ ከፈት ይላል ...የታችኛው ከንፈሯ ጠልጠል ብሎ የላይኛው ከንፈሯ የሚያምር የግማሽ ክብ ቅርፅ ይይዛል ! የምላሷጫፍ የታችኛው ጥርሷን ነካ አድረጎ ይቆማል "ራ" ደምፅ አለው ከአ ድምፅ እንደ ማስቲካ የሚለጠጥ ...ኦርርርርርርራ....አቤት ከንፈሮቿ ከፈት ብለው ጥርሶቿ በመጠኑ ሲታዩ ሊያ ፊት መቀመጥ ፈተና ነው .....ያው ራ ላይም አቋርጣታለሁ !!

ይ

ይ ስትል ከንፈሮቿ ወደግራና ቀኝ ልጥጥ ይላለ የላይኛው ጥርሷ በደንብ ይታያል .....ከንፈሮቿ ሲለጠጡ ስስ ይመስላሉ ቅድም ኦ ላይ ሙጥሙጥ ያለ ጉርሻ የሰራው ከንፈር አይመስልም ! ይ ስትል የበለጠ የሚያምረው የታችኛው ከንፈሯ ነው ! በጣም ይቀላል ! ደም የቋጠረ ይመስላል !

ት

ግርም የሚለኝ የሊያ "ት" ነው ! በምኗ እንደምትጠራው እግዜር ይወቅ ! ብዙ ቀን በትኩረት አፏን አየሁት ከንፈሯን አጠናሁ ፎቶም አነሳኋት ...ግን "ት"ን በከንፈሯ ትጥራው በጥርሷ ትበለው በምላሷ ታዚመው አላውቅም ...እኔ "ት" ስል ምላሴና የላይኛው ትናጋየ ተጋጭቶ ነው ፊደሉ የሚፈጠረው ሊያ ግን እንጃ !

አንድ ቀን

"ሊያየ " አልኳት

"ወይየ "

"ት" ን የምትፈጥሪያት የት ነው

"ኦራይት ስል "ት" ኦሚት ስለምትሆንብኝ ነው " አለችኝ ! "ኦሚት" ስትል አሁንም "ት" አመለጠችኝ ...ላጣራ በጣም ተጠግቻት "ት ት ት ት ት ት " ሳስብላት ሳላስበው በጣም ተጠግቻት ነው መሰል ሁሉን ነገር "ት"ተነው ወደጉዳያችን !!! ድሮስ በዚህ ርቀት በዚህ ቅርርብ ያውም የሚከጃጀሉ ልጆች መሃል ......አማርኛ ይጠናል ? ግን እንኳንም አጠናን !! ተሳስመን ተሳስመን ተሳስመን ከንፈሯን ነከስኳት መሰል ..." ሶሪ ነከስኩሽ " አልኳት

" እም ኦ ራ ይ ት " አለችኝ ሙትት ባለ ድምፅ !!

አማርኛ ለዘላለም ትኑር በተለይ "ት " !! ጥርስ ላይ ትፈጠር ትናጋ ላይ ከፈለገች ለምን የእግር አውራ ጣት ላይ አትፈጠርም .....የትስ ብትፈጠር ምናገባኝ ! ! አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋነቋና ስነ ምንትስ የትምህርት ክፍል ምን ሰርቶ ይብላ !?

ይቀጥላል

# የቀን ጅቦች ነን!

አገራችን ኢትዮጲያ ደሃ አገር ናት !! ድህነታችን ደግሞ ይሄ የሚበላ የሚጠጣ ማጣት ብቻ አይደለም እሱማ ዓለም ነው አባቴ፣ የእርዳታ ድርጅት አንዴውኑ አውቆት ሰንዴና ዘይት እየመጸወተ እንዳትሞት እንዳትሸር አድርጎ ያሰነብተሃል ! አሰቃቂ አሳቃቂ አፋችንን ሞልተን ከሰው እኩል እንዳናወራ የሚያደርግ ድህነት ነው እንደመንፈስ የተጠናወተን!! ድህነቱ ከእግር ጥፍራችን ጀምሮ እስከራስ ጸጉራችን ቅርጥፍ አድርጎ በልቶን ምላሳችንን ብቻ ነው የተወልን !! መለፍለፍ ብቻ !አንድ ሲናገሩን አስር መመለስ ብቻ ! ጣት መጠቋቆም ብቻ ! የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ አገሪቱ ራሷ ደስተዋም ተሰፋዋም እንደጫት ቃሚ በምርቃና የሚመራ መሆኑ ነው!!

የሆነ ሰዓት ላይ በምርቃና ተሰፋ ፣በደሰታ፣ ዘመቻ በዘመቻ ሰልፍ በሰለፍ መፎከር በመፎከር ትሆንና ምርቃናዋ ሲበርድ ውሃ ውስጥ እንደነከሯት ድመት የዘር ጸጉሯ ተንጨባሮ፣ የጥላቻ ፣የድህነት ጽጉሯ ቁሞ በተሰፋ ያቀፏት ዜጎቿን እንደጃርት እሾኋን ትሰካባቸዋለች ! ይሰደዳሉ ይሞታሉ ወይም ቅስማቸው ተሰበሮ ከለፍላፊው ግሩፕ ተቀላቅለው ከሩቅ ይጮሃሉ !! ጥፋቱን ያላከካሉ ! የሆነው ሁሉ ሆኖ አሁን የምነመኘው ዴሞክራሲ ምናምን ልክ እንዳደጉት አገራት ቢሟላልን እንኳን እንደመርግ ከተጫነንን ድህነት ለመውጣት አምሳ አመታት ላይበቁን ይችላሉ !! ያውም አፋን ዘግቶ ቀን ከሌት ሳይታክት ይሚሰራ ብርቱ ዜጋ ማሰለፍ ከቻልን ነው!!

ከዚህ በተረፈ በየድራፍት ቤቱ በረንዳ ላይ ተዘፍዝፈን ፖለቲካ ሰናወራ ከአገራችን የነገ ተሰፋ ላይ ጊዜ የምንበላ የቀን ጀቦች ነን !! ጫት ቤት ተዘፍዘፈን የምርቃና እንቶፈነቶ ሰናወራ ቀናችንን የምንበላ የቀን ጀቦች ነን !!ተምረው ነገ ሰው ይሆናሉ የተባሉ ተማሪዎች ኮልኮሌ የዘርና ምናምን ፖለቲካ ተራ ሱስና ጥራዝ ነጠቅ እውቀት ሽምዳጅ ከሆኑ በመጨረሻ ለምንም የማይጠቅም ድግሪ ያለው የቀን ጅብ ነው የሚሆኑት !! አገራችን ትልቅ እና ደሃ አገር ናት ጥቂቶች ብቻ በልተው የሚጨርሷት ጥቂቶች ብቻ አስበውና ሰርትው የሚገነቧት አገር አይደለችም! በትልቁ የሚገምጥ መኖሩ ባይካድም ሁላችንም ግን ለእድገትና ለአንድነት ለመሰራት ባልሞከርን መጠን በሚታይም በማይታይም ሁኔታ የድርሻችንን የቦጨቅን

የ ቀ ን ጅ ቦ ች ነን !!

# የአደዋ ጦርነት ገና አላለቀም

(አንቀፅ 17 እኛም መስኮታችንን አንከፍትም እናንተም ሚስቶቻችንን አትዩ)

ጣሊያን ኢትዮጲያን ወራ አምስት አመት ፍዳዋን በልታ ፍዳችንን ስታበላን አያቴ እሳት የላሰ የውስጥና የውጭ አርበኛ ነበር በጦር ሜዳ ብትሉ አንድ ባታሊዮን ጦር ጭጭ ምጭጭ ያደርግና <ጀግና> ሲሉት "ኤዲያ ምን አላት እች" ይላል!! በከተማ ብትሉ ሲሰልል ጀምስቦንድ በሉት !! ለአገር በሰራው ታላቅ ጀብዱ አሁን የጣሊያን ኤምባሲ የሚባለውን ቦታ ጃንሆይ በሽልማት ሰጡት! ትንሽ ጎጆ ቀልሶ የተረፈው ሜዳ ላይ በቆሎ ዘርቶ ሲኖር.. አንድ ቀን የመንግስት ሰወች እቤቱ ድረስ ሂደው "እዚህ በቆሎ የዘራህበት ቦታ ላይ "የምባሲዮን" ሊሰራበት ነውና መድረሻህን ፈልግ ብለውሃል ጃንሆይ " አሉት !

"ኧረ ውሰዱት ደሞ ለሞላ ቦታ " አላቸው ትንሽ ቆይቶ

" ግ ን ይሄ "የምባሲዮን "ያላችሁት ነገር መንገድ ነው?" ሲል ጠየቀ

አይደለም!

የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ነው?

አይደለም!

አሃ ትምርት ቤት መሆን አለበት!

አይደለም !!

ሃዲያ ምንድን ነው ቤተ ክተስኪያን ይሆን እንዴ ?

"ኤምባሲዮን ማለት ንጉሱ የፈቀዱላቸው የውጭ አገር መኳንንት እና መሳፍንት የሚቀመጡበት ማረፊያ ነው" አሉት ከመልከተኞቹ አንዱ!

በቃ?

በቃ!

" እኮ ፈረንጆች ይሄን ሁሉ ቦታ አጥረው ቁጭ ሊሉ ነው" አለ በግርምት

"አዎ! ይሄ የምባሲዮን የወከላቸው አገር የማይደፈር ግዛት ነው"

" ሃዲያ ድንበራችን ላይ ያባረርነውን ጠላት መናገሻችን ላይ "አርደንለት ጋርደንለት" ልናስቀምጠው ነው በሉኛ"

"እንደሱ አይደለም "

"አሃ ሃዲያ እንደጃርት እኔ በቆሎ እርሻ ውስጥ ምን ይሰራሉ ወደከተማው አይሰፍሩም " አለ ጥሎበት ፈረንጅ አይወድም !! አያቴ ላይ ሳቁበት። ስለኤምባሲም ለድፍን ሁለት ሰአት አወሩ ተግባብተው ሊለያዩ ሲሉ ግን ነገር ፈነዳ አገር ተሸበረ "የምባሲው የ"ጥሊያን ኤምባሲ" መሆኑ ሲነገረው አያቴ ሰይጣኑ ተነሳ ተንደርድሮ ገብቶ ምንሽሩን አወጣና "ባንዳ ሁሉ" ብሎ የጃንሆይን መልክተኞች ማሳደድ ጀመረ ! ጥሎብን መከተል እንወዳለን መንገድ ላይ ድንገት አባቴን ያዩ ሁሉ ምንሽራቸውን አፈፍ አድርገው "ያዘው " እያሉ እየፎከሩ ማሳደዱን ተቀላቀሉ ቢያዝ ላይጠቅማቸው!! ቤተ መንግስት ሲደርሱ አያቴን የተከተሉት ሰወች 19 ባለምንሽር 9 ባለ አልቤን 2 አውቶማቲክ መሳሪያ የያዙ 43 ባለጎራዴና 22 ባለ ዱላ ! ከጣሊያን ኤምባሲ እስከቤተ መንግስት ይሄ ሁሉ ሰው ተከታይ!! የሚገርመው ምንም መሳሪያ ያሊያዙ በሙቶ የሚቆጠሩ ሰወችም ተከትለው ነበር።" ምን ሆናችሁ "

ቢላቸው አያቴ “ አይ.. እሩጫው ወደቤተመንግስት መሆኑን ስንሰማ ነው የተከተልናችሁ” አሉ !! አያቴ የተከታዩን ብዛት አየና በዛው ሽፈተ ! ስሙ በጣም የገነነ ሽፍታ ሆነ ! ሜክሲኮ ቁሞ ዞር ብላችሁ ዞር ስትሉ መገናኛ ነው ንፋስ የሱ ስም ከተጠራ ጣሊያኖች ንስሃ ይገባሉ ! ጭራሽ የኤምባሲው ግንባታ ሲጀመር በወርም በሳምንትም በል ሲለው በየ ሶስት ቀኑ ብቅ እያለ ይሄን ጣሊያን ሁሉ ይፈጀው ጀመረ!! የወቅቱ የጣሊያን ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ለግንባታ እየመጡ “አለቁ” የሚባሉትን ጣሊያናዊያን መሃንዲሶችና ግንበኞች ጉዳይ አስመርሮት ለፕሬዝዳንቱ እንዲህ የሚል ሪፖርት አቀረበ “ ክቡር ፕሬዝዳንት ለግንባታው የሚያስፈልጉ እቃወችና ጣሊያናዊያን ሰራተኞቻችን እኩል ነው የሚያልቁት” ፕሬዝዳንቱ በደም ፍላት ጮኹ “ ይሄ ኤምባሲ የሚገነባው ኢትዮጲያ ውስጥ ነው ቤርሙዳ ትሪአንግል ውስጥ”

“ጌታየ በአድዋ ጦርነት እንዳገኘነው ልምድ ከሆነ ሁለቱም ለጣሊያን ህዝብ ያው ናቸው እዛም ገብቶ መጥፋት እዚህም ገብቶ መቅለጥ” አለ በምሬት።

ጃንሆይ በበኩላቸው አያቴን “በዲፕሎማሲ” ማሳመን መርጠው መልክት ላኩበት ! በድፍረት ፊታቸው ቀርቦ “ ጃንሆይ ትላንት ጥሊያንን “እንኳን አባረርከው” ብለው የሸለሙኝን ቦታ ዛሬ ከኔ ነጥቀው ላባረርኩት ሰላቶ በመስጠተዎ ተቀይሜወታለሁ!!እዴት እንዴት ነው ነገሩ  እዚች አገር አባራሪው ከተባራሪው ተደባለቀባት እኮ” አለ ። ጃንሆይ እዛው ኤምባሲው ጎን ሰፊ ቦታ ሰጡት እና እርቅ ወረደ ! ጃንሆይ ብልጥ ናቸው አንዳንዴ አያቴን ይጠሩትና “ጎረቤቶችህ ሰላም ናቸው?” ብለው ይጠይቁታል “ ሰላይ አደረጉት!! የአያቴ ጎጆ እና የጣሊያን ኤምባሲ በአጥር ብቻ ነበር የሚለያዩት ! አያቴ ጣሊያኖቹን ባያቸው ቁጥር ደሙ እየፈላ “ወይ ነዶ” እያለ በብስጭት ሲግል ሚስቱ ወ/ሮ ቤልጅጌ መኮነን (የፊታውራሪ መኮነን ታምሩ ልጅ) እንደልጅ እያባበለች ወደምኝታ ቤታቸው ትወስደውና ከብስጭቱ አብርዳ በሌላ ጉዳይ ትለኩሰዋለች ከነገር እሳት ወደፍቅር እሳት ! አቤት ማባበል ስታውቅበት ! ገና ስትታይ ነገር ታብርዳለች እሳት ፈገግታዋ እሳት ያጠፋል !! ለመስቀል ደመራ ሲቃጠል ቀሳውስቱ ለአያቴ ቀድመው መልክት ይልኩበታል “ሚስትዎ ወደደመራው አይምጡ እሳቱ ይጠፋብናል “ ብለው (ሲካበድ)!! እና አያቴን ሲበሳጭ ስታባብለው ሲበሳጭ ስታባብለው አምስት ሴትና ስድስት ወንድ ልጆች ወለዱ አንዱ የእኔ አባት ነው!! የልጆቹ ስም በረዱ ጥሞና ሰከኑ ርጋታ ርጎየ ወዘተ !!

አያቴ ለልጆቹ የጣሊያንን ጭካኔ የፋሽስትን አረመኔነት እየተረከ አሳደጋቸው “ እነህ ጥሊያኖች ጠላቶቻችሁ ናቸው በታንክ ኢትዮጲያዊያንን እየጨፈለቁ “ እያለ ሲተርክ ልጆቹ ግን ወደኤምባሲው የሚገቡ ዘመናዊ አውቶ ሞቢሎች ላይ አይናቸው እየተንከራተተ አይሰሙትም ነበር በተለይ ሴቶቹ !! ጭራሽ ሁሉም ልጆቹ (ከአባቴ በስተቀር) ጣሊያናዊያንን አግበተው አረፋት !!

በዚሁ ብስጭት አያቴ ደም ግፊቱ ጨምሮ ሞተ!! አያቴ መሞቱን ለማረጋገጥ ከጣሊያን ኤምባሲ ወደአያቴ ግቢ በሌሊት ዘለው የገቡ ሰላዮች ነበሩ ግን አልተመለሱም! የአባቴ ጓደኛ ፊታውራሪ ውቃው እንደወፍ በአየር ላይ ቀለቧቸው!! አባቴ ያገባት ሴት(እናቴ) እጅግ በጣም ውብ ናት “ ሙሉ” ይባላል ስሟ እንዳትረሱት !! አያቴ ቦታ ላይ ቤት ሰርተው መኖር ጀመሩ !! በእናቴ ምክንያት ጣሊያን ኤምባሲ ጋር ትልቅ ፀብ ተፈጠረ!! !! ስትገባ ስትወጣ ማፍጠጣቸው ሳያንስ ”ለደህንነት” በሚል ሰበብ ፊታቸውን ወደኛ ቤት ያዞሩ አራት ካሜራወች ተከሉ እናቴ ግቢ ውስጥ በተንቀሳቀሰች ቁጥር አራቱም ካሜራወች ወደሄደችበት ተከትለዋት ይዞራሉ ሌላ ሰው ሲንቀሳቀስ ግን ግኡዝ ናቸው !! ጭራሽ የጣሊያንና ኢትዮጲያ አንድነት በኣል ሲከበር ያሳተሙት መፅሄት ላይ እናቴ አጎንበሳ ልብስ ስታጥብ ከኋላዋ (ያውም አጭር የውስጥ ልብስ ብቻ ለብሳ ) የሚያሳይ ባለቀለም ፎቶ ተካቶ ነበር ቀይ ባቷ ሎሚ ተረከዟ የፎቶ አንሸው እጅ ይባረክ ያስብላል ! ከእናቴ ፎቶ ጎን አንዲት ጥላ ቢስ ሽርጥ ያሸረጠች ጣልያናዊት ኮረዳ (ውብቷ እናቴ እግር ላይ የማይደርስ) ዘመናዊ የልብስ ማጠቢያ ማሽን ደገፍ ብላ የሚያሳይ ፎቶ አለ ! ከስር “ኢትዮጲያ ከጣሊያን ስድስት ዘመናዊ የልብስ ማጠቢያ ማሽኖች በእርዳታ አገኘች ይህም የኢትዮጲያዊያንን ሴቶች ድካም በመቀነስ ጊዜያቸውን ለሌላ ጉዳይ እንዲያውሉት ይረዳል “ የሚል ፅሁፍ ጋር ”ሌላው ጉዳይ” ምን ይሆን

አባቴ በቀጥታ ወደኤምባሲው ዋና በር ሄደና እንደግለሰብ ቤት አንኳኳ ዘበኛው ባለማመን እያየው “ምን ፈለክ ?;” አለው እርዳታ የፈለገ ኢትዮጲያዊ ይሆናል ብሎ ” ጌታህን ጥራው ባልቻ በር ላይ ይፈልገሃል በለው “ ዘበኛው ግራ ተጋባና “ማንን ነው የጥበቃ አለቃውን ነው ?” አለ

“ እሱ ምን ያረግልኛል? አምባሳደሩን ነው ያልኩህ ”

“አ ሃሃሃሃሀሃሃሃ በል ሂድ ወደዛ ደፋር ! “ ብሎት እርፍ አባቴን!! በዛቹ ቅፅበት በአለማችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የኤምባሲ ዘበኛን የዘረረ ብርቱ ጥፊ ከአባቴ ተሰነዘረ! ጥፊው ጣሊያን ድረስ በመሰማቱ ታላቅ ዲፕሎማሲያዊ ንትርክ ተፈጠረ!! ምክንያቱን እንዲያጣራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጥፋቱ የጣሊያን ኤምባሲ ሁኖ በመገኘቱ ጣሊያን ባምባሳደሯ በኩል የኢትዮጲያን ህዝብና መንግስት ይቅርታ ጠየቀች! (በጣሊያን ኤምባሲ በኩል ስታልፉ ዘበኞቹ የጥፊ መከላከያ አድርገው የሚታዩት በዚህ ታሪካዊ ጥፊ መነሻ ነው)

በኋላ አባቴ “ልጆቸ ስለበረከቱ ፎቅ ቤት እሰራለሁ” ብሎ ተነሳ! ባለ ሁለት ፎቅ ቪላ ማንንም ሳያስፈቅድ ጀመረ!! ጣሊያኖች ከሰሱ ኤምባሲ ጎን ፎቅ መስራት ክልክል ነው ተብሎ ታገደ !

“አገሬ ላይ እስከጨረቃስ ፎቅ ብሰራ ምናገባችሁ “

“ለወዳጃችን የጣሊያን ምንግስት ስጋት ስለሚፈጥር ለደህንነታቸውም ስለሚያሰጋ አይፈቀድልህም “

“አሄሄ እነሱን ለመግደል ፎቅ ማን ይሰራል ውቤ በርሃ ሲያውደለድሉ አይደለም የሚውሉት”

“ስርአት ጌታው” ጉዳዩ በጣም ተጋነነና በአባቴና በጣሊያኑ አምባሳደር መካከል የሁለትዮሽ ድርድር ቢካሄድ የተሸለ ነው በማለት ድርድር ተካሄደ ይህ ድርድር በታሪክ “ አንቀፅ 17 እኛም መስኮታችንን አንከፍትም እናንተም ሚስቶቻችንን አትዩ” በመባል ይታወቃል!

የ ውሉ ዋና ዋና ነጥቦች !

1. አቶ ባልቻ ደመቀ ኤምባሲያችን ጎን የሚሰሩት ፎቅ መስኮቱ ወደጣሊያን ኤምባሲ ላይዞር !!

2. ጣሊያኖች ሲገቡ ሲወጡ አሁን ያሉትንም ሆነ ወደፊት የሚወለዱትን የአቶ ባልቻን ሴት ልጆች በቃልም ሆነ በድርጊት. ላያማልሉ በመኪናም ሆነ በእግር በር ላይ ላየንንማለሉ

❈ ❈ ❈ ❈

. 17 ወደአቶ ባልቻ ቤት የዞሩት የኤምባሲው ካሜራወች “ ሙሉ በሙሉ ሊነሱ “ የዚህ ውል 17 ኛው አንቀፅ ጣሊያነኛ ትርጉም ግን እንዲህ ይል ነበረ

“ የኤምባሲያችን ካሜራወች “ የወይዘሮ ሙሉን እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ ፎቶ ሊያነሱ” ፈቃድ አላቸው” ታሪክ እራሱን ይደግማል !!

እናቴ ታዲያ ከንፈሯን ሽርመም አድርጋ የተንኮል ፈገግታ ፈገግ አለች ማንም አላያት ከሰይጣን በስተቀር ትንሽ ወንድሜ አባቴን አለመምሰሉ እንደውም ፈረንጅ መምሰሉ አስቋት ይሆን ?

# የሚያስጠልሉ ብፁአን ናቸው .... ዝናቡ ይቆማልና!

“ይቅርታ እዛች ድረስ ልጠለል “ አልኳት ከፊቴ ዣንጥላ ይዛ በችኮላ የምትራመደውን ቆንጆ ወጣት ሴት ... “እዚህ ጋ ነኝ “ አለችኝ በአገጯ ወደፊት እየጠቆመችኝ .... ከፊቷ ምልክት የሚሆን ምንም ነገር አልነበረም ... የቱ ጋ ማለቷ እንደሆነ እግዜር ይወቅ! ከፊታችን ያለው ለባቡሩ ስራ የተቆፈረ ጉድጓድ ነው ...ዘላ ልትገባ ይሆን እንዴ ...(ሂሂሂ) በዛ ላይ ፊቷን ስላጨፈገገችው ጥያቄን መቀበል እንዳልፈለገች ታስታውቃለች ....ኧረ እንደውም እኔ በግራዋ በኩል ስለነበርኩ ዣንጥላዋን ወደቀኝ እጇ አዘዋወረችው (አሸሸችው ማለት ይሻላል) ይታያችሁ በአካባቢው መጠለያ የለም ....ድንገት ከሰማይ የተዘረገፈው ዝናብ ለጉድ ይንዠቀዠቃል .... ደግሞ ዝናቡ ይለያል የሁነ የውሃ ኮረት ነገር ነው ዱብ ዱብ ዱብ

....የለበስኩት ቲሸርት ሰውነቴ ላይ በስብሶ ደረቴ ላይ ልጥፍ ብሏል ...በዛ ላይ መንገዱን ሞልቶ እስከ ቁርጭምጭሚቴ እየተነከርኩ የተሽገርኩት ውሃ ጫማየ ውስጥ ገብቶ በተራመድኩ ቁጥር ቦጭረቅ ቦጭረቅ ይላል ! ልጅቷ ደግሞ “ድንገት አስር ሰዓት ላይ ሜክሲኮ አካባቢ ዝናብ

ይጥላል” ብሎ ሹክ ያላት ዘመድ ያለ ይመስል ቡትስ ጫማዋን እስከጉልበቷ ገጥግጣ ካፖርት ደርባለች ኮፍያም አድርጋለች ( ፈረሱ የጠፋበት ጋላቢ ነው የምመስለው) በካፖርትና በቡትሷ መሃል ቀይ ታፋዋ ይታያል (ቀሚስ አለበሰችም እንዴ?) አይኗ ደግሞ ሲገርም ...አይኗ ዙሪያ በርከት አድርጋ የተኳለችው ኩል

ዣንጥላውን አልፎ ባገኛት ዝናብ ታጥቦ በእንባ ምትክ ቡና የሚያስለቅስ ሃዘን ያገኛት እንግዳ ፍጡር አስመስሏታል ! እና አማራጭ ስላልነበረኝ ቢያንስ መጠለያ ያለበት አካባቢ እስከምደርስ ዣንጥላ የያዘችን ብቸኛ ልጅ መጠጋት ምን ክፋት አለበት ? ደግሞ አበሻ ናት ...እንዲህ ያለው ቦታ ላይ መረዳዳት

ማንን ገደለ ...? ይች ክረምት ፊት ግን በ “ፕላስቲክ ሰርጀሪ” ጠይም ቆዳ የለበሰች መናጢ ፈረንጅ ናት መሰል ፊቷን ኮስኩሳ ከእግር እስከራሴ ገረመመችኝ ! “አይ ይች መገላመጥ ምነው በቦታዋ በሆነች” ብየ እንድታስጠልለኝ በመጠየቄ አፍሬ ትቻት አለፍኩ ....በእርግጥ ካለፍኩኝ በኋላ ስለልጅቱ አሰብኩ “ምን ሁና ይሆን ...በዝናብ ሰዓት የሚታወሳት መጥፎ ትዝታ ይኖር ይሆን ...ምናልባት የከዳት ፍቅረኛዋ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቃት በዝናብ ቀን አስጠልይኝ ብሎ ይሆን እንዴ ....ደግሞ ብዙ ሴቶች

“አብርሽ የድሮ ቦይፍሬንዴን ትመስላለህ “ ስለሚሉኝ (የድሮ ቦይ ፍሬንዶቻቸውን የተዋቸው እኔን በመምሰላቸው ይሆናል ) ምናልባት የሷንም ከሃዲ ቦይ ፍሬንድ መስያት ቢሆንስ ...” እያልኩ ይቅርታ ላደርግላት አሰብኩ ...ደግሞ እንጅ ፊቷን ማጨፍገጓ ...እኔ ሴት ልጅ ሁለት ጊዜ ትሞታለች የሚል እምነት አለኝ ...አንድ ፈገግታዋ ፊቷ ላይ ሲሞት ነው ! ሴት ልጅ ካለፈገግታ በጅምር የቀረ ሃሳብ ነው የምትመስለኝ .... ታዘቡኝማ ብዙወቹ የከተማችን ሴቶች እኮ ፈገግታቸው ፊታቸው ላይ ሙቷል....የሆነ እቤታቸው ሳቃቸውን ጭርስስሰስ አድርገው ጣሙጋ ፊታቸውን ይዘው የሚወጡ እኮ ነው የሚመስሉት...ቻፕስቲክ ብትሉት ሊፕስቲክ ፌር ብትሉት ምንተስ ሎሽን ቅቤ ብትሉት ኮኮስ ቅባት ምን ዋጋ አለው

.....ሴት ልጅ በሚያስቀው ፍንትው በሚያስኮርፈውም ቡጥጥ ...በሚያኮራው ኮራ በሚያዝናናው ዘና በሚያስለቅሰው ንፍርቅ ስትል ነው ፊቷ የሚያምረው የሃቅ ስሜቷ እንደተፈጠረ ፊቷ ላይ ሲፃፍ !! አሁን ግን ...የሆነ መከራ ፊት በዝቷል ! መንገድ ላይ ካሜራ የተደቀነባቸው ይመስል እያስመሰሉ የሚኖሩ ድራማ ፊት ሴቶች ! ከሃያ ሁለት ሜክሲኮ ድረስ በረዥዥዥሙ ሊኮሳተሩ ሁሉ ይችላሉ ... ሰው ለሰው ፊት !

አለ አይደል “ምናይነት ለኔ የማይመጥን አገር ነው “ አይነት ፊትን ማጨፍገግ ...ጉረኛ ጭፍግግ ፊት ! እንዲህ አይነት ሴቶች ሳር ቅጠሉን እየገለመጡ ሲሄዱ የቁም ተስካራቸውን ሊያወጡ ድግሱ ወደተዘጋጀበት የእድር ድንኳን የሚጣደፉ ሚስኪኖች ነው የሚመስሉኝ ! አለመሳቅም አለመኮሳተርም ይቻላል እኮ ...በነገራችን ላይ ከመሬት ተነስቶ መኮሳተር ከመሬት ተነስቶ ከመሳቅ የበለጠ ትኩረትን እንደሚስብ ገብቷቸዋል ! (በእርግጥ ልጅቱ

ስላላስጠለለችኝም ተበሳጭቻለሁ ቢሆንም የምለው እውነት ነው ) ሁለተኛው ሞት ያው እድሩ የሚያውቀው ሞት ነው ! ድፍት !ጡጡጡ ባለዣንጥላዋ እከሊት ባደረባቸው

የቆንቋናነት ህመም ምክንያት በሃኪም ሲረዱ ቆይተው ....በቃ ! ወዲያው አስር እርምጃ ሳርቅ እንደኔው በዝናቡ ውስጥ የሚራወጡ ሰወች " እኔን ..." ብለው ሰወች ሲጮሁ ወደኋላየ ዞርኩ ....ልጅቱ ዣንጥላዋ እዛ ቦርሳዋ እዚህ አሷ ወዲያ ...ብትንትኗ ወጥቶ ወድቃለች ....ጭቃው አንሸራቷት ...ልክ ከሜክሲኮ ወደቄራ መታጠፊያው ጋ ! ከምር አወዳደቋን ሳየው እቃዋ ብቻ ሳይሆን የሰውነት ግፍሷ ሁሉ የተበታተነ መስሎኝ ነበር ...እንደውም ወደኔ አቅጣጫ የተወረወረ አንድ እቃ አፍንጫዋ መስሎኝ ጠጋ ብየ ሳየው የጥፍር ቀለም እቃ ነው (ሂሂሂሂ ሳጋንነው ነው ) እና እኔ እንደሷ አይነት መጥፎ ልጅ ስላልሆንኩ ረጋ ብየ "እኔን " ሳልል ሂጀ እቅፍ ድግፍ አድርጌ አነሳኋት (እግዚኦ ክብደቷ ኪሷ ውስጥ ቤተሰቧን ይዛ ነው እንዴ የወጣችው ...) የዛሬ ልጆች ሲያዩዋቸው መለሎ ሸንቃጣ ይመስላሉ ክብደታቸው ግን አይጣል ነው .... አንስቸ ካቆምኳት በኋላ የኮራችበትን ዣንጥላ አንስቸ ሰጠኋት ...."ቴንኪው " ብላ ፈገግ ለማለት ሞከረች ....( እንዲህ ሲፈርጡ ፈገግ ሊሉ ....) ልታስጠልለኝ ፈልጋ ነበር እኔ ግን ትቻት ሄድኩ ....ቆንቋና ከፈረጡ በኋላማ እንኳን አንዲት ሴት መንግስታትም ደግ ይሆናሉ ! ቆንቋናዋን ትቻት በብስጭት ቁልቁል ስሮጥ ቢጫ የባህል ቀሚስ የለበሰች ሹርባ የተሰራች ሴት ከወደጠማማው ህንፃ ብቅ አለች ..."ፓራሹት " የሚያህል ዣንጥላ ዘርግታ ላልፋት ስል " ና ተጠለል ምነው እንዲህ እስክትበሰብስ " አለችኝ ... ጠጋ አልኳት ሰማይ የሚያህል ዣንጥለዋ ስር ተጠለልኩ ልጅቱ እንዴት ደስ እንደምትል ....ቁመቷ የትየለሌ ነው እኔ ደረቷ አካባቢ ቀረሁ ....በዛ ላይ ከታች እስከላይ ሙልት ያለ ሰውነት .....ከሁሉም በላይ ግን በተራመደች ቁጥር ግራና ቀኝ የሚራወጡት ትልልልልልልልልልልልልልልቅ ጡቶቿ ገርመውኝ ልሞት ! በጣም ትልልቅ ናቸው አለ አይደል በህፃንነታችን " ከአፍሪካ አንደኛ ከአለም ሁለተኛ " የምንለው አይነት...እና ጎን ለጎን ስንራመድ የቀኝ ጡቷ ከግራ በኩል ተወርውሮ ይመጣና ጉንጨን ነክቶኝ ይመለሳል ....አንዳንዴም ጠንከር ያለ ጉሽማ ይሆናል ...ለስላሳ የቦክስ ጓንት ያጠለቀ ቦክሰኛ ጋርየምጋጠም እስኪመስለኝ ...ጓ ....ገጭ ....! ላስጠልልህ ብሎ ሰው መደብደብ አለ እንዴ (ሂሂ ለብርዱ አሪፍ ነው አለ ያ የተረገመ ጓደኛየ ማታ ስናወራ ) በነገራችን ላይ ከድሮ ጀምሮ ትልልቅ ጡት ያላቸው ሴቶች ደግ ይመስሉኛል ... የሰፈሩን ልጆች ሁሉ እያጠቡ የሚያሳድጉ አይነት ! ጡቶቻቸው የማያልቅ ወተት የተሞላባቸው .....ልጅቱ ጋር ገነት ሆቴል አካባቢ ተለያየን ....ወደቄራ የሚሄድ ታክሲ አግኝቸ ገባሁ ... አንዲት ሴትና አንድ ሰውየ ከኋላየ እያወሩ ነው ....ልጅቱ እንዲህ ትላለች " ምናለ እንዲህ ዝናብ ሲሆን እንኳን ሊፍት ቢሰጡ ስንት ሰው ለመንኩ አንድ እንኳን ባለመኪና አያቆምም ኦ ማይ ጋድ ምናይነት ጨካኝ ጊዜ ነው አበሻ መቸ እንደሚሰለጥን እኔጃ ...ሴትን ልጅ ማክበር ..." ቀስ ብየ ዞሬ አየኋት ......ቆንቋናዋ ልጅ ነች ! እውነትም .....ኦ ማይ ጋድ !

# እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ

ጋሽ አዳሙ የሰፈራችን ታዋቂ ሰካራም ከሰሞኑ ለአስራ አምስት ቀናት ጠፍቶ ሰንብቶ ንፍ.....ቅ ብሎን ነበር ....ድንገት ታዲያ ትላንት ማታ ልክ ከምሽቱ አራት ሰአት ላይ እየፎከረ እየሸለለ “

እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ “ እያለ ሲመጣ በጨለማው ውስጥ ድምፁን ሰማንና ተሯሩጠን ቲቪ ነሽ ሬዲዮ ነሽ ዘጋግተን ጆሯችንን አቆምን ..... ጨለማው ውስጥ ቁሞ ብቻውን በስካር በተኮላተፈ ድምፁ ያወራል ......ጎርናና ድምፁ በነፍሳት ሲርሲርታና በመንደሩ ውሾች ጩኸት ታጅቦ ሲሰማ በሙሉ ባንድ የታጀበ ቆየት ያለ ሙዚቃ ነው የሚመስለው ....

“ ወደን ነው እንዴ የምንሰክረው ...... እዚህ ሰፈር ኳ ኳ ኳ ....አላችሁ ......? መልሱልኝ አላችሁ ወይ ? ...... ሃሃሃሃሃ አሁንማ አለን ለማለትም ፈራችሁ ! ሃሃ ፍርሃታችን አስራ አንድ ነጥብ ምናምን በመቶ ጨመረች ......የራሳችሁ ጉዳይ! እኔ ደሆንኩ አለሁ ! ሃሃሃ ... በደንብ አድርጌ አለሁ ! ገና እኖራለሁ ! በመኖሬ ደስተኛ ነኝ መኖሬ የሚያስከፋው ካለ

“ በሊማሊሞ ገደል “ ....ብለዋል የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር ..... ገደል የሚጠቁም መሪ አያሳጣን ...... ሃሃሃሃሃ ደሞ እሳቸው የጀመሩትን ብላችሁ ገደል እንዳታስገቡን ...... !! እና አላችሁ ወይ ስል ምነው ሰፈሩ ዝዝዝዝም አለ ? እኔኮ ግርም የሚለኝ “አላችሁ ወይ “ ስትባሉ ጭጭ ትሉና ሌላ ሰው

“አለሁ “ ሲል “ከማናባቱ በልጦ ነው የሚኖረው “ ብላችሁ እምቧ ከረዩ የምትሉት ነገር ሃሃሃ ኑር ሌሎች እንዲኖሩ አድርግ ይላል ሞፈክሩ ... ሚስኪን መፎክር ፀሃፊ ልባችንን ባያውቃት ! እናተ የላችሁም መሰል ..... ቆይ ታዲያ እዚህ ሰፈር ያለው ምንድን ነው ......ይመስገነው ... እዚህ ሰፈር ምንም የለ !! ሂሂ ኢቦላ የለ .... ውሃ የለ ....መብራት የለ ...... ሰው የለ .... ተቀዋሚወች ደሞ “ፍትህ የለ” ...ይላሉ ...መንግስት ደሞ “ተቀዋሚ የለ” ይላል ....እሽ ማነው ያለው ? ምንግስት እኮ ግራ ቢገባው ነው “ አለ በጅምላ “ ብሎ ሱቅ ያስከፈተው .....ሃሃሃሃ ..... አዳሙ ብቻ አንድ አገር ይዞ ብቻውን ይኑር ? ? ይችን በምታክል “የሶስት ትሪሊየን” አመት ታሪክ ባላት አገር ብቻየን ልኑር አላሳዝናችሁም ? “ ወደው አይደለምኮ አለቃ ገብረሃና የተናገሩት ......እንደኔ ግራ ቢገባቸው ነው ...... አፈር ስሆን ስሙኝ ! አመት አላወራ ...ስሙኝ

....ለነገሩ ደርግም “አመት አላወራ” ብሎ የመናገሪያ ሰገነቷ ላይ ከወጣ በኋላ ነው አስራ ሰባት አመት ያወራው ! አሁንም

“አመት አናዋራ እስከዚችኛዋ ምርጫ የማሪያም መንገድ” ... እያሉ ነው ሃያ ሶስት አመት ያወሩብን ..... ቢሆንም ግዴለም ስሙኝ ተረቱን ........እና .....አለቃ ገብረሃና ነበሩ (መቸም “ነበሩ” እንወዳለን እራሳችን አንኖርም እንጅ ) እና ሲኖሩ ሲኖሩ በአገሩ ረሃብ ገባና ህዝቡ ቅጠል መብላት ጀመረ አሉ ....ሰንሰል ነሽ ...ጉሎ ነሽ ...ግራዋ ነሽ ፅድ ነሽ ሙጃ ነሽ ሳር ነሽ ... እንክት አድርጎ በላው ህዝቡ !! ...የራበው ህዝብ አንበጣ ነው የማይበላው ነገር የለም ....መሪውን ሁሉ ይበላል ይላሉ “ተቀዋሚወች” ሃሃሃሃሃሃ

....( አዳሜ ክትፎ ጥብስ የምትይው አባቶችሽ ቅጠል በልተው ...መሪም በልተው ባቀኑት አገር ነው )

እና ....ያ የችጋር ቀን አለፈና የጥጋብ ቀን መጣ ...አለቃና ጎረቤቶቻቸው ተሰብስበው እየተበላ እየተጠጣ ሲያወሩ ሁሉም ትላንትን ረስቶ ጉራውን ይቸረችረው ገባ

“እኔ በዛ ችግር ወቅት ህዝብ ሲራብ ጎተራየ አበባ በመሰለ ጤፍ ሞልቶ ነበር “ ይላል አንዱ ጉረኛ ...ሃሃሃ ሌላው “ ጎተራየ ገብስ በሸበሸ ነበር” ይላል ...” እኔስ ብትል ባቄላ ሞልቶኝ መጣያ አጥቸ “ እያለ ይወሸክተዋል ጉራውን .....አለቃ ታዲያ ግርርርርርርም ብሏቸው ጮክ ብለው ጓዳ ለምትንጎዳጎድ ሚስታቸውን እንዲህ አሉ አሉ....

" እንች አልጣሽ....በዛ ክፉ ቀን የድፍን አገሩን ቅጠል እና ሙጃ እኔና አንች ብቻ ነበርን ለካ በልተን የጨረስነው " ሃሃሃሃሃ የሰፈሩ ሰዎች ሳቃችንን አፍነን በጉጉት ጋሽ አዳሙን እናዳምጣለን .....

"እስቲ አሁን ማን ይሙት እግር እስኪቀጥን በአዲስ አበባ ቢዞሩ.... በክልል ቢዞሩ ....በአፍሪካ ቢዞሩ (አ.....ይ አፍሪካ እንኳን ራሷ ዙሮባት ምን ታዞራለች ሃሃሃሃ) እና በአለም ቢዞሩ

....በሌላ ፕላኔት ቢዞሩ እንደዚህ እንደኛ ሰፈር ውብ ሰፈር አለ ? በ.........ጭራሽ !! ይሄ ሰፈር ማለት እኮ እትብቴ የተቀበረበት ... አየሩ ብትሉ ....ውሃው ብትሉ .... ኔትዎርኩ ብትሉ .....የፈለጋችሁትን ብትሉ .... ሲያምያራችሁ የሚቀርበት ሰፈር እኮ ነው ...... !

ምን ዋጋ አለው እነ አረጋሽ ለልማት ይፈርሳል እያሉ ያስፈራሩናል .....ለነገሩ ይፍረስ ...ድሮስ መቸ ኖርን ! ይችን ሶስት ከተማ ወደሁለት እናምጣት ነው ያሉት ሰውየው ... ባይሉትም ኑሮው ራሱ እንኳን መንደሩን ሰውን ራሱን ሁለት እያደረገው ነው እውነቴን ነው ሰው ሁለት ሁኗል እዚህ በጆሯችሁ ሌላ ነገር አውርቶ እዛንኛው ሰፈር ሌላ ...አስር ጓደኛ ካላችሁ ሃያ ብላችሁ ያዙት ሰው ሁለት ሁኗላ !

ለነገሩ አይፈረድበትም አንዱን ሰው ብትሰሙት የሁለት ሰው ምሬት ነው የሚማረረው ... ባንዱ ለሁለት ጉዳይ የሚሰለፍ ትውልድ ነውኮ .......ይሄ ነገር በዚሁ ከቀጠለ ከጀርባው የገዥው ፓርቲ ምስል ከፊት የተቀዋሚ አርማ ያለበት ቲሸርት የለበሰ ሰላማዊ ሰልፈኛ መስቀል አደባባይ ማየታችን አይቀርም !

"ይላሉ የፖለቲካ ተንታኞች " ሀሃሀሃሀሃ ቀድሞ ሙችና ሰደቃሽ ይውጣ አሉ ....መጀመሪያ የሚተነተን ፖለቲካ ሲኖር አይደል ሃሃሃሃሃ አንዱ ሰውየ ....እዚህ ታክሲ ተሰልፎ እየጠበቀ እያያችሁት እዚሁ ኔትወርክ ተሰልፎ ይጠብቃል ....ይሄ እኮ ነው ሁለት መሆን ...... ሃሃሃሃሃ ቡፍ እያልን እንስቃለን ! በየቤታችን !

ሰልፉ በግል ነው ጎበዝ ... ተበተን ብትባልም ወዴት ትበተናለህ.... ሰላማዊ ሰልፍ የለም ትላለህ እንጅ አዳሜ ግንባሩ ላይ የብሶት መፎክሩን በመከፋት ቀለም ፅፎ ብቻውን ሰልፍ ወጥቷል ! ስራፈላጊው በእጁ አንከርፍፎ የሚዞረው ፋይል መፎክር እኮ ነው "ስራ ለሰሪው " የሚል ...." ጋሽ አዳሙ ዝምምም ብሎ ይቆያል በቃ ወደቤቱ ሄደ ብለን ወሬ ስንጀምር

"እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ " ብሎ በጩኸት ያንባርቃል! በሳቅ እናውካካለን ...ጋሽ አዳሙ ሃሳቡም ንግግሩም እዚህና እዚያ እየረገጠ ይቀጥላል .....

" ይች አገር ወዴት እየሄደች ነው " አለች አሉ አንዲት አርቲስት

በቀደም የምታሳየው ፊልም ታግዶባት ሃሃሃሃ ...የት ትሄዳለች ... ኗሪውን እያሳቀቀች ታባርር እንጅ ! እውነቴን ነው ... አንዳንዴ ኑሮን ለማሻሻል ሳይሆን ዜናም ለመስማት ስደት እስክንመኝ ድረስ ዜናው ስልችትትትትትትት ይለናል ! ባስራ አራት ኢንች ቴሌቪዥን አስራ አንድ ነጥብ ምናምን ፐርሰንት እድገት.. እድገቱ በዚሁ ከቀጠለ የቴሌቪዥናችን ኢንች ሳያድግ እድገቱ እስክሪኑን ሞልቶ ሊፈስ ነው .... ኧረ እድገታችን ቴሌቪዥናችን ጠበበው እስቲ ቴሌቪዥናችን ጋር የተመጣጠነ እድገት እንደግ ለነገሩ መንግስታችን ብልህ ነው ...በየመንገዱ ዳር ባለትልልቅ ሶኒክስክሪን አስቀምጦልናል ...

"አለ በጅምላ በዜና መልክ" መሆኑ ነው ሃሃሃ.... ችግር ነው በታዳጊ አገር መኖር ....አሁን ማን ይሙት አዳሙ አሜሪካ ሂዶ " የአገሬ ዜና መረረኝ ዜናችሁን ልሰማ መጥቻለሁ የዜና ጥገኝነት ስጡኝ " ቢል ማን ይሰመዋል .....እና ይሄ ሁሉ በየጣራው ላይ የቆመ ዲሽ ምን መሰለሽ ህዝቡ የዜና ጥገኝነት ጠይቆ እየተሰደደ እኮ ነው ሃሃሃሃ አባማ እንደሆነ ማጣፊያው አጥሮታል ....ጥቁር ፕሬዝዳንት ብለው ያሞካሹት ሁሉ ፊታቸውን አጥቁረውበታል ! ዜናው ከማሰልቸት ሲመለስ አሳቃቂ ....የትውልዱን ቁልቁል እድገት እኮ ነው የሚያሳየን ...ድሮሮሮ ንጉሱ ብቻቸውን ዙፋን ላይ ቁጭ አሉና "አንድየ አንድየውኑ ሹሞናል " ብለው ... እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ ሲሉን ....የትውልዱን የዘመን እሳቤ እግዜር ጋር አስተሳስረው አሳዩን .....ይሁና ብለን ሰገድን ! ጎንበስ ብለን ቀና ስንል ንጉሱ ዙፋናቸው ላይ የሉም ....

ደርጉ ሰብሰብ ብሎ መከረና ንጉሱን በወታደራዊ ጫማ ከነዙፋናቸው በካልቾ ብሎ ሲያበቃ ተሰብሳቢውንም አንድ በአንድ ፈጅቶ እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ ሲለን መድፍ ቀረሽ ሰላምታ ሰጥተን ተረግጠን ተገዛን ... እምቢ ያሉትን እንደቢንቢ በጥይት ፊሊት አረገፋቸው .......ኢሃዴግ መጣና "አምስት ሁነን ጫካ ገብተን ፋሽቱን የደርግን ጨካኝ አገዛዝ ገረሰስን በደማችን ነፃነትን ዋጀን እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ " ሲለን "የማያልፉት የለም " እያልን ተቀበልን .......አረረም

መረረም ...ከፋም ለማም ... ሁሉም አንድም ሁነው ነገሱ ደርግም ሁነው ተነካከሱ ወላ አምስትም ሁነው አገዛዝ ገረሰሱ ያው የትውልዱ ውጤቶች ናቸው....ነበሩ !! ዛሬስ ........ይሄ በጫት የነበዘ በመጠጥ የደነዘዘ አይኑን እያጉረጠረጠ የወሲብ ፊልም ላይ አፍጥጦ የሚውል አሸን ከትውልዱ መሃል እንደአረም እያቆጠቆጠ እራሱንም ለመሃበረሰብ ጠንቅ መሃበረሰቡንም ጆሮ ጭው የሚያደርግ ዜና እንዲሰማ አደረገው ... ከዩኒቨርስቲ ወጥተን አምስት ሁነን ጫካ ገብተን ጨካኙን አገዛዝ ገረሰስነው ....የሚል ታሪክ ለአንድ ሚሊየነኛ ጊዜ ልንሰማ ዜና ስንከፍት " አምስት ሁነው ወደሽሻ ቤት የሽፈቱ ጎረምሶች አንዲት ፍሬ ልጅ ደፍረው ለሞት እንዳበቋት ነግሮን ቁጭ .... የዘመናችን ስፍር ነዋ ! ከትውልድ የሚመዘዙ በጎ ሰሪዎች "የኛው" እንደሆኑ ሁሉ ትውልዱን ያሸማቀቀ ድርጊት አድራጊወቹም " ከኛው " ናቸው ! ሴት ልጅ ሚስት ናት... እናት ላይ እያልሽ እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ ቃል ለመቀመር ትሮጫለሽ .....ትላንት

"ምናለበት" እያልሽ ያናናቅሽው ሽሻ ይሄው እንዲህ አይነት ትውልድ ያመርታል .....ትላንት ምናለበት እያልሽ "የገባኝ አሪፍ " ነኝ ለማለት ያናናቅሽው አደንዛዥ እፅ ይሄው ዛሬ እንዲህ ራሳቸውን እንኳን መከላከል የማይችሉ ህፃናት ላይ ክንዱን ሲያሳርፍ ! ልጅቱን ማን ደፈራት ??...አምስት ጎረምሶች ብቻ መሰሉሽ ? አሄሄ ግዴለሹ ህዝብ በሙሉ !! ቤቱን አከራይቶ ሽሻ ቤት ያደረገው .....ዩኒፎርም የለበሱ ታዳጊወች በየመጠጥና ጫት ቤቱ ሲኮለኮሉለት እየገለፈጠ "ምናገባኝ ያለው " በየአጥርሽ ስር እድሚያቸው ያልደረሰ እንቦቀቅሎች ዩኒፎርማቸውን ለብሰው አጉል ነገር ሲያደረጉ እያማተብሽ ያለፍሽ ሁሉ ...... ትላንት ስለሱስ ሲወራ

"አካበዳችሁ " ያለው በሙሉ ! " አራዊቱ " ሚሊየን ነው .... ጫካው ፊቱ ሲመነጠር ተኝቶ ከርሞ ታዳጊዋ ችግኝ መቀጠፏን በዜና ሲሰማ ኡኡታውን ያቀልጠዋል .... አራዊቶቹ የሚወለዱት ያው ከአራዊት ነው " ጋሽ አዳሙ ምርር ያለ ድምፁ እየራቀ እየራቀ ...ሄደና በመጨረሻ ከሩቅ በሚሰማ ድምፅ እንዲህ አለ .........እ ያ ን ዳ ን ድ ሽ እጅሽ ላይ ደም አለ !!

# ፍቅር አኬልዳማ

ያለፈው ቅዳሜ ረፋድ ሰአት ላይ ተቀጣጥረን ነበር ምሳ እንድንበላ አብረን "ፊልም" እንድናይ

ባለመገኘቴ የቀጠርኩሽ ቦታ ልኬብሽ ነበረ የፀፀት ይቅርታ ዛሬም አኩርፈሻል ...አልበረደም ቁጣሽ ስልክም አታነሽ መልክት ልኬብሽ ከእቤቴም አልመጣሽ ! አፈር ስሆንልሽ የቀረሁበትን ጉዳዩን ልንገርሽ .....አንድ ጊዜ

ስሚኝ ........ያው እንደሁልጊዜው እንቡጥ ፅጌሬዳ ይዠልሽ ልመጣ አበባ መሸጫ ....ሱቅ ጎራ ብያለሁ

ያዘዝኩት አበባ እስኪታሰርልኝ ፊት ለፊቴ ባለች አንዲት ቴሌቪዥን .... ጦርነት አያለሁ የጋዛ ጎረምሳ ህዝብ መሃል ደፍጦ አዳፍኔ ይተኩሳል የስራኤል ጎረምሳ ዲሞፍተር አንስቶ ህፃን ይጨርሳል በጎረምሶች መሃል ......በቦንብ ተጠምቀው የሸንፈት ሃይማኖት አማኝ እንዲሆኑ ኢስራኤል "ጠማቂው" ኢስራኤል "ካህኑ"

አምላኩን ቸንክሮ ሞት ለሰው ያቀርባል በበደል ሰሃኑ ! ያውም ለህፃናት ያውም ለባልቴቶች ያውም ለ እ ና ቶ ች ያውም ........ (ራስ መከላለከል ኡኡቴ) ልሙትልሽ ውዴ አበባሽን ይዠ ልክ ልወጣ ስል ሌላ ትይንት መጣ ....ልቤ አድማስ አለፈ እግሬ ቁሞ ቀረ የነብሴ የደም ስር በሃዘን ነዘረ በፈራረሰ አገር አንዱ ጎረምሳ

በሚጋልበው ታንክ አቧራ እያስነሳ

"በላቸው " ሲል ሰማሁ ትጥቁን አሳምሮ ወዲህ ያገሬው ህዝብ ሲያወጣ ይታያል የህፃን ሬሳ ፍርስራሽ

ቆፍሮ ብጭቅ እንደራፊ.... የአንዲት ህፃን ቀኝ እጅ ከፍርስራሹ ስር ሊያወጡ ሲስቧት የልጇን እጅ አቅፋ የምታለቅስ እናት ግራ የገባው አባት ፍርስራሽ ላይ ቁሞ ልጁን ካላደነ ሚስቱን ካልጠበቀ ከሞት በፊት ቀድሞ ወንድ ልጅ ከፊቱ ላገር ካልወደቀ ምንድነው ባልነት ምንስ ነው ወንድነት የሚል ይመስለኛል አበባሽን ይዠ በተገተርኩበት ይሄ ግፍ ያመኛል ! ልሙትልሽ ውዴ ....ልሰጥሽ የያዝኩት ፅጌሬዳ አበባ

ይመስለኝ ጀመረ በግፍ የበቀለ በንፁህ ህፃን ደም በእናቶች እንባ ደግሞ ከታንኩ ፊት እርሳስ ለመጨበጥ እጃቸው ያልጠና ህፃናት በምሬት ጠጠር እየጣሉ እየወረወሩ የግፈኞቹን ታንክ ካ,ኬልዳማ ምድር በልህ ሊያባርሩ ይውተረተራሉ እናቶች ከኋላ " አድነን " ይላሉ በእንባ መአበል በምሬት እሪታ አለም በሚሰማው የሰቆቃ ዋይታ ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ ልሙትልሽ ውዴ....... ይህ ዜና ሲያበቃ አበባሽን ይዠ ለመሮጥ ስዘጋጅ ሌላ የድሎት ዜና በቴሌቪዥኑ ጠባብ መስኮት ሲዋጅ ተመልሽ ቆምኩኝ ....የ,ንግሊዟ ልእልት ህፃናት ሰብስባ በቤተመንግስቷ በጣፋጭ ያበደ ሲያዩት የሚያስጎመዥ ኬክ ደግሞ ከፊቷ ህፃናቱ ጠግበው ሲጨማለቁበት ጣፋጩ ተርፏቸው በደስታ ተራውጠው " ክሬም " ተለቅልቆ እጅና ፊታቸው ሳ...............ያ............ቸ............ው መላ አካላታቸው በነጭ የደም ዥረት የተጥለቀለቀ የጋዛ ህፃናት መስለው እየታዩኝ ሰውነቴ አለቀ ይሄውና እንግዲህ አለም አባይ ሚዛን ልጆቿን የካደች አንዱን በደም ባህር ሌላውን በክሬም ታጨማልቃለች !

" ኧረ ያለም ህፃናት በግፈኞች በትር በጭካኔ አለቁ " ብለው ለጠየቁ

"ይሄው ያለም ህፃን አይስክሬም ሲልስ በደስታ ሲቦርቅ እንዲህ ያለ መርዶ ባክህ ወደዛ አርቅ "

ይለዋል ለህዝቡ ! እያበጠ ዜናው ወጉም እየበዛ ከድሎት ጋር እኩል ይደነቅረዋል ሞትን እንደዋዛ !.ሰቆቃውን እዚህ ጋ .....እልልታውን እዛ ! እኔ የምልሽ ውዴ ...የኔና አንች ፍቅር ነገ ትዳር ቢሆን ብንወልድ ልጆች ለአይን የሚያሳሱ ገና ሳንጠግባቸው በግፈኞች ጥይት እንደከንቱ ሸክላ እየተገመሱ ፊታችን ቢወድቁ አይንሽና አይኔ ስር በሳት ቢታመሱ የያዝኩት አበባ ጠረኑ ይሸትሻል ? የምንበላው ምሳ አንጀትሽ ይደርሳል?

አየሽ ፍቅሬ ሲመከን ...የፍቅር አበባየን ምን ላምጣልሽ አልኳት ወደምድር ውረድ ወደሰማይ ውጣ ብቻ በዚች አለም ደም ያልፈሰሰበት እፍኝ አፈር አምጣ ለካ በዚች አለም.......አበባ አንከርፍፎ ሴት አሳዳጅ እንጅ

አበባ ሲቀጠፍ ሀይ የሚል ወንድ የለም!! ለባለ ክንድ ጥጋብ የአለም ክንድ ሲላሽ በሰቆቃው ጬኸት በህፃናቱ እልቂት ተቀብሮ ነው መሰል

ጠፋብኝ ትዝታሽ

ጠፋብኝ ፈገግታሽ

ጠፋብኝ ከንፈርሽ

ጠፋብኝ አይኖችሽ ......

ጠፋብኝ ቀጠሮው

ጠፋብኝ ሰአቱ

ጠፋብኝ ዘመኑ

ጠፋብን ወራቱ ! የገዛሁልሽን አበባ ወርውሬ ወዳልቀጠርሽብኝ መጓዝ ጀመርኩ በግሬ ልሙትልሽ ፍቅሬ!!

# የሰርግ ቀን ስድቦች

በጣም የተገረምኩበት ቀን እህቴ ትእግስት ስታገባ !! .....አሸኗትም ወይ መሄዷ አይደለም ወይ ....ሲባል በቃ ሆድ ባሰኝ ...ከምር ከነገ ወዲያ ምላሽ ብለው የሚመለሱ አይመስሉም እኮ ! ሙሽራው ደረቱን ነፍቶ ወደእኔ እየተመለከተ ህዝቡን ቻው ቻው ሲል ብስጭት አልኩ ....ሰርጉን ተቃውሜ ስለነበር "ተቃጠል ፈንጅ ብላ " የሚለኝ ነበር የሚመስለው ! አዳራሹ ቀውጢ ሆኖ የእህቴ ጓደኞች እንኳን ሰበብ አግኝተው አንደውም ጨፍሩ ጨፍሩ ይላቸዋል ያቀውጡታል በተለይ ሰናይት የምትባለው ልጅ አስራ አንድ ነጥብ አንድ ክንድ ምላሷን ለእልልታ ስትዘረጋው ይሄ የኪራይ አዳራሽ ብትንትኑ የሚወጣ ነበር የሚመስለው ! ኢትዮጲያ ድንበር ላይ ቁማ እልል ብትል አስመራ የተደገሰ ሰርግ ታደምቃለች ! አጠገቤ ከነበረው ጠረንጴዛ ላይ የሆነ የሚጠጣ ነገር አንስቸ እያቀበልኳት

"ሰኒ እየጠጣሽ " አልኳት

"ታ.....ኒኪው አቡቹየ " ብላኝ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረገችውና ምን ብትል ጥሩ ነው ....እልልልልልልልልልልልል ልልልልልልልል በዚህ አጋጣሚ ግርም ያለኝ ነገር የሰርግ ዘፈን ግጥሞች

.....ቆይ ግን እነዚህ ፌሚንስት ነን ምናምን የሚሉ ሴቶች ሰርግ ቤት ያንን ወገባቸውን ይዘው የሚከራከሩለትን "የሴቶች መብት እኩልነት ምናምን " በሩ ላይ አስቀምጠውት ነው እንዴ የሚገቡት ...እና ምን ልበል ...እንደአገራችን የሰርግ ዘፈኖች ተሳዳቢ አለ እንዴ ....እስኪወጣላቸው እኮ ነው ሴት እህቶቻችንን እናቶቻችንን የሚያሞልጯቸው ... ቆይ ሴቶች በአገራቸው ላይ የወደዱትን እና ያልወደዱትን ወንድ የማግባት መብታቸው ለምን በሰርግ ዘፋኞች ይገፋል .....ልክ አይደለም !! ከዛን ቀን ጀምሮ

የሰርግ ዘፈኖችን ሆነ ብየ ማድመጥ ጀመርኩ ! ይታያችሁ የእህቴ ሰርግ ላይ

"እሰይ አበጀሽ የኛ ሎጋ ባሳር ተገኘሽ በፍለጋ " ብሎ ዘፋኙ አሸሞረ (መቸም ዘፈነ አይባልም ) .... ቆይ ይሄ ዘፈን በትክክል የሚገባው ለኔ ነበር ወይስ ለባሏ ....እንዴት ማለት ጥሩ ...ስንትና ስንት ቀን ነው እዚህ ላንጌሳ ባሏ ጋር እያመሸች አባባ "ይችን ልጅ ሂድና ፈልግ ምን ሁና ነው ያመሸችው " እያለኝ ፍለጋ የተንከራተትኩት ...እኔ ነኝ አሳሬን የበላሁት ... እኔ ነበርኩ ባሳር ፈልጌ የማገኛት .....(ኧረ እኔ እጀ አመድ አፋሽ ነው ) ባሏ መቸ ነው እርሷን ፍለጋ አሳር የበላው ...ኧረ ዘፈናችን ፍትሃዊ ይሁን ተው .....ሌሊት

ሚስኮል ሲያደርግ አይደል እንዴ ባፍጢሟ እስክትደፋ በሌሊት ልብሷ በመስኮት ዘላ ወደእርሱ ቤት የምትከንፈው ....ኡኡቴ ደግሞ አለ ባሳር ተገኘሽ ! እሽ ይሄስ ይቅር "አትሸኟትም ወይ ብሎ ዘፈን ምን ይሉታል ...እድሜ ልኬን ሸኘሁ ትምህርት ቤት ስትሄድ ሸኘሁ ...ሱቅ ስትሄድ ሸኘሁ ...በሄደችበት ሁሉ ለአቅመ ምንትስ ከደረሰች ጀምሮ (መቸም ቆንጆ ናት) ወንዶች እንዳይተናኮሏት ብየ ስሸኝ ኖርኩ

....ዛሬ ደግሞ ሊያሳርፈኝ ነው ስል ጭራሽ ከነባሏ ሸኝ ይሉኛል ...እና ባሏ ምን ሰርቶ ይብላ አይገርማችሁም አልሸኝም !! በቃ! እንደውም እዘፍናለሁ " የኛ ሙሽራ ትእግስት ባል አግብታለች ይሸኛት " ሂሂሂሂ ለራሴ ሆድ ብሶኛል ከምር እህቴ ግን እንዴት ታምራለች ...በቃ የሰርጓ ቀን ሳያት እያማረች ታሳዝናለች .....እስኪ አሁን ይሄን ሰውየ የት አውቃው ነው ተከትላ የምትሄደው ...ተያዥ የለው ምን የለው ...እንደው

የእርሷስ ይሁን የሰርገኛው እምነት .... ከምር ግን አምኖ ልጁን ለሆነ ሰው መስጠት አይከብድም ? እስቲ ስታገቡ ሙሽራውን የት ታውቁታላችሁ ከፍቅር በላይ ታያዥ የለም ብላችሁ አምናችሁ ስትከተሉ .....ሆሆ ...ወንዱስ ቢሆን የማያውቃትን ልጅ አስከትሎ ሲሄድ ምን ይባላል ...ሌሊት ድንገት ወደሰው ጅብነት ብትቀየርስ... እንደው ሼሎ ስለለበሰችና ስላማረባት ብቻ ጎኗ በኩራት መኮፈስ ተገቢ ነው .....(መጠርጠር አይከፋም ሂሂ እኔ እፈራለሁ ) ዘፋኙ ሊያቆም መሰላችሁ "አባቷ አንበሳ ገዳይ ...." እኔ አባባን ሳውቀው ፊታውራሪ ደጀኔ አንደኛ ደረጃ የሁለተኛ ክፍል ሳይንስ አስተማሪ ነው ....ትምህርት ቤቱ በስማቸው የተሰየመላቸውም ፊታውራሪ አንበሳ መግደላቸው

በታሪክ አልተፃፈም ! አባባ ደግሞ እውነት መስሎት ነው መሰል በኩራት ኮቱን እያስተካከለ ፈገግ ይላል (ወይስ ለበአል የሚያርደው በግ አንበሳ መስሎት

ነው )...በአባቴ ተበሳጭቻለሁ ለምን እህቴ እንድትዳር ፈቀደ ወይኔ ! እና ዲጀው የከፈተው ዘፈን ደግሞ ገርሞኝ ልሞት ሲሄዱም አንድ ላይ ሲመጡም አንድ ላይ ሲበሉም አንድ ላይ ሲተኙም አንድ ላይ ሲያስሉም አንድ ላይ ሲስቆም አንድ ላይ ሲጮሁም አንድ ላይ ሲያኮርፉም አንድ ላይ ሂሂሂሂሂሂ ...ቆይ ይሄ

ዘፋኝ ተጣብቀው ለተወለዱ ህፃናት ህክምና ገቢ ማሰባሰቢያ ይሆን እንዴ ይሄን ዘፈን የዘፈነው ?

ከሁሉም ግን የገረመኝ ሰርገኛው " ልጃችንን ለሙሽራው አደራ ያለበት መንገድ ነበር " ስንት አደራ የሚባል ነገር እያለ እስቲ "ልጃችን የሆዷ ነገር አይሆንላትምና አደራ እንዳታስርባት " እያሉ ይዘፍናሉ ከምር ....ካላመናችሁ ግጥሙን ልንገራችሁ " እኛ ያሳደግናት በማር በወተት እንዳታስለምዳት የሽሮ ፍትፍት " አሁን ይሄ ቁም ነገር ሁኖ አደራ ይባላል በእግዚአብሔር ... እስኪ እኛ እስከዲፕሎማ በምግብ ዝግጅት አስተምረናታል አንተ ደግሞ ድግሪዋን አስቀጥላት ምናምን ቢሉ ምለበት ....ይሄ በግልፅ ሴት ልጅ ካገባች በኋላ በሆዷ ብቻ መገዛት አለባት እንደማለት ነው ....ለዛ እኮ ነው ሴቶች ሲያገቡ ክብደታቸው

የሚከብዳቸው ........ምን ይሄ ብቻ ሴቶች የራሳቸውን ሂወት ሳይሆን የሌሎች ሴቶችን ሂወት በቅናት ማየት የሚወዱ ይመስል " አይበልሽ ከፋ ሁሉም ያገባል በየወረፋ " ቆይ ስለሌሎች ወረፋ ምናገባት ከምር ምናገባት ....የመጨረሻ የተበሳጨሁት ግን የዚችኛይቱ ሲገርመኝ ዘፋኙ ለሰርጉ በአለም ላይ ያለውን ሜካፕ ሁሉ የተጠቀሙ ወደሚመስሉት አራት እህቶቸ እየተመለከተ " አለ ገና አለ ገና ....." ደግሞ አያፍሩም ለወረፋው የቸኮሉ ይመስል በመደዳ ተሰልፈው እልልልልልልልልልል ለማትሪክ ውጤትም እንዲህ

እልል አላሉ ......ደግሞ " አቡቹ ዛሬ የእህትህ አለም እኮ ነው ምነው ፊዘዝክ " ትለኛለች እናቴ ....አለም በዚህ ሳምንት አለ ያ ዜና አንባቢ እንዲህ ዝብርቅርቅ ቢልበት እኮ ነው ...

# የተንጨባረረ ሂወት በፍቅር ሚዶ ሲበጠር

“የኔ ጌታ !” አለች ሚስት ባሏን በሚያማምሩ አይኖቿ እያየችው “ወይየ የኔ ማር” አላት ድምፁ ውስጥ ቃል የለበሰ ፍቅር አለ ! “ቆንጆ ባለማያዣ ማበጠሪያ ብትገዛልኝ ደስ ይለኝ ነበረ ፀጉሬ ተንጫጨብኝኮ አየኸው ? “ አለች ለምትወደው ባሏ ሳይበጠር እንኳን ወርዶ ጀርባዋ ላይ የተነሰነሰ ውብ ፀጉሯን እያሳየችው ...እውነትም ቅባት ነገር ሽው ተደርጎ በጠር በጠር መደረግ አምሮታል ፀጉሯ ...ተንሳቁሏል ! ይሁንና ማበጠሪያም ከባድ እቃ ሁኖ በቤታቸው አልነበረም ! ባልና ሚስት ናቸው ! አገር ምድሩ ፍቅራቸውን ያውቃል ....ገና ከድሮ ከልጅነታቸው ጀምሮ “ውይ የነሱ ፍቅር ካይን ያውጣቸው” የሚባሉ አይነት ! የፍቅር ማማወች ! እርሷ ያያት የሚመኛት ውብ ነች ከኋላዋ ሽ ከፊቷ መቶ ወንድ የሚሰግድላት አይነት ! “ከምን ፈጠራት” ይላታል አገሬው ! እርሱም ቢሆን ይሄ ቀረህ የማይባል ወጣት ነው ! እንግዲህ አገጣጠማቸውና አገር ምድሩን ጉድ ባስባለ ፍቅር ወደቁ ....ተጋቡም !! ታዲያ ምንዋጋ አለው ፍቅራቸውን የሚከል ግዙፍ ድህነት ቤታቸው ውስጥ እንደትልቅ ቋጥኝ ተደላድሎ ቁጭ አለ !ቢገፉት የማይገፋ ጥቁር ቋጥኝ ባለፉ ባገደሙ ቁጥር ስሜትን የሚገጭ አብሮነትን ሊያደቅ ቢወድቁበት ቢወድቅባቸው እጣ ፋንታቸውን መድቀቅ ሊያደርግ ድህነት ይሉት ድንጋይ በቤታቸው ተጎለተ ! በልተው ከሚያድሩበት ቀን ፆማቸውን የሚያድሩበት ይበዛል ! ያጡ የነጡ ድሆች ...ቆንጆ ድሆች ! ፍቅር ብቻ ሳይሆን ድህነትም ያፈቀራቸው ድሆች ! ይታያችሁ ማበጠሪያ እንኳን መግዣ ያጡ ደሆች ! “እንደነሱ አይነት ፍቅር የትም የለም “ የሚለው ጎረቤት በተጨማሪ እንዲህ ይላል “ እንደነሱ አይነት ድህነት የትም የለም “ እና ሚስት “ማበጠሪያ ግዛልኝ” አለችው ባሏን !”ላይንና ለወዳጅ ትንሽ ይበቀዋል” ባል በሚስቱ ጥያቄ ከፋው “ እንዴት ኪሴ ባዶ መሆኑን እያወቅሽ እንዲህ ትይኛለሽ ...እስቲ የእጅን ሰአት ተመልከችው መስተዋቱ ተሰንጥቆ ሰው ፊት እንኳን ሰዓት ማየት እያፈርኩ ቢኖረኝ ይችን መስተዋት አላስቀይርም ...” ሲል

ተንጫነጨ ሰአቱ በጣም የሚወዳት እናቱ ስጦታ ነበር ሚስት በበኩሏ “ ከእኔ ፀጉር የእጅ ሰዓትህ በልጦብህ እንዲህ ትናገረኛለህ ... ? እኔ ላንተ እንዲህ ነበርኩ ? “ ብላ እንባዋ ቀደማት ....ባል በብስጭት ጥሏት ከቤት ወጣ ! ትዳሬን ብሎ እንጅ እዚህና እዚያ እንደጓደኞቹ ቢዛለል “ጌታየ” ብለው ወርቅ የሚያለብሱት በፍቅሩ እንግብግብ የሚሉለት ሃብታም ቆንጆ ሴቶች ሞልተዋል !! ሚስትም ብዙ አልቆየችም ተነስታ ወጣች ! ትዳሬን ብላ እንጅ ወጣ ብትል እንኳን ማበጠሪያ “እመቤቴ” ብለው ...እግሯን ስመው ሙሉ ፀጉር ቤት የሚከፍቱላት ወንዶች በከተማው እየተርመሰመሱ ሞልተዋል ! ወደአመሻሹ ላይ ባል ወደቤቱ እየተጣደፈ ሲመለስ ግን በቀኑ ብስጭት አልነበረም እንደውም ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ በጉጉት ነበር እንጅ .... የእናቱን ውድ ስጡታ የሆነችውን ሰባራ ሰዓቱን ሽጦ ለሚወዳት ሚስቱ የገዛውን ማበጠሪያ በኪሱ ይዞ ነበር ...እቤት ሲገባ ግን ባየው ነገር ደነገጠ ....ማመን አልቻለም

....ሚስት ያንን ጥቁር ፏፏቴ የመሰለ ውብ ፀጉሯን ሙሉ ለሙሉ ተቆረጣ ወንድ መስላ ተቀምጣለች .... በእጇ ግን ውድ የሆነ ባለወርቅ ማሰሪያ የወንድ ሰአት ይዛ በጉጉት ባሏን እየጠበቀችው ነበር ...ፀጉሯን ሽጣ ለምትወደው ባሏ የገዛችው ነው ! ሁለቱም በዝምታ እንባቸው በጉንጮቻቸው ላይ ፈሰሰ

....አዲሱ ሰአት... ቲክ ቲክ ቲክ ቲክ ይላል  ይህም መራር እውነት እንደሚያልፍ ሊነግራቸው የፈለገ ይመስላል !! የእኔ አይደለችም ተርጉሚያት ነው !!

# ሴትነት ድንበሩ የት ነው?

የመንደራችን ታዋቂ ሰካራም ጋሽ አዳሙ ልክ አራት ሰአት ሲሆን እየዘፈነ እና ብቻውን እያወራ ሰፈራችን ደረሰ ... መንደርተኛው የቴሌቪዥኑን ድምፅ ቀንሶ ሬዲዮውን ዘግቶ የእርስ በርስ ጨዋታውን አቁሞ ጆሮውን ቀሰረ .....ለመሳቅ እየተዘጋጀ ...ቴሌቪዥን ዜናውን መድገሙ አይቀርም ሬዲዮውም ቢሆን

“አንድ ሙዚቃ ሰምተን እንመለስ “ ብሎ መመለሱ አይቀር..... ጋሽ አዳሙ የመንደራችን እውቅ ሰካራም አጭር ዲስኩር ግን ካለፈ አለፈ ነው!! ...ነገ ጧት እንኳን ለኛ ሊደግመው ጋሽ አዳሙ ራሱ ምን እንዳለ አያስታውሰውም ! እናም ያው የመንደሩ ሰው እንደሚያውቀው ጋሽ አዳሙ ወቅታዊ ጉዳዮችን እያነሳ በሞቅታው ታጅቦ በጨለማው ውስጥ ብቻውን ማውራት ጀመረ ....ብቻውን እንኳን አይደለም ሁሉም በየቤቱ ጆሮውን ቀስሮ ይሰመዋል ....ሰማነው አልሰማነው ጋሽ አዳሙ እንደሆነ የመሰለውን ከመናገር ወደኋላ አይል ...ስካሩ ውሎ ይግባለት መጠጥ አቅራቢ ኮማሪት ነገ ዞራ ሳካራም ብትለውም ቅሉ አዳሙ ምን እዳው )

“ እያንዳንድሽ ....ተኝተሽል እ ? እኔኮ ግርርርርርርርርርርርርርርም የሚለኝ የዚህ ሰፈር እንቅልፍ .... ነው ....ለሽሽሽ ! ወይኔ አዳሙ ! አንድ መንደር ህዝብ በተኛበት እንደህልም ብቻየን ስንከላወስ አልገርምም ? መቸ ነው ይሄ እንቅልፋም ሰፈር የሚነቃው ... አሁን የዛሬ አስራ ምናምን አመት ቢላደን ያሜሪካ

ህንፃ ሲያፈነዳው ሁልሽም ተኝተሽ ነበር እኔም ይሄ ሽብር ፍንጣሪው እዚህ እኛ መንደር ይደርሳል እያልኩ እዚቹ ቦታ ቁሜ ተናገርኩ ...በየቤትሽ በየብርድ ልብስሽ ተጠቅልለሽ በእንቅልፍ ልብሽ ስትስቂ “ ፍንጣሪ ካሜሪካ እዚህ ድረስ ሊመጣ አይ ሰካር” ስትይ ይሄው ፍንጣሪው ህግ ሁኖ መጣና ወላ ፀሃፊ ወላ ጋዜጠኛ ወላ ሃይማኖተኛ ወላ ፖለቲከኛ ወላ ወንድ ወላ ሴት ል ቅ ም ቅ ም ! የሩቁን ተውት አሁን በቀደም “አውሮፕላን ጠፋ አለም እንኳን አንድ ልትሆን ቀርቶ አንድ አውሮፕላን ሽ ሁና ማግኘት ግራ ገባት” ስል “ያ ገ ኙ ታ ል “ እያልሽ ስታላግጭ ይሄው አሁን ከትላንት በስቲያ ክፍለ ከተማ የምታህል ነዳጅ ጫኝ መርከብ ምጥ ትግባ ስምጥ እልም !! ሁልሽም ዝም ብለሻል ....ኧረ መርከብ ጠፋ ባህሩ እንደሆነ የኛም መርከቦች ያልፉበታል እግዚኦ በሉ ....ሁልሽም አውሮፕላን ሲጠፋ ጭጭ መርከብን ያህል ነገር ሲጠፋ ጭጭ !! እሽ ከዚህ በላይ ምን ይጥፋ ? ...ሰማዩ ተጠቅልሎ ይጥፋ ? ወይስ ባህሩ ይጥፋ ? ........ትንፍሽ

የለም እ ? በየቤትሽ ለሽሽሽ! እኔማ ዜናውን ጠጅ ቤት ስሰማ “ ኧረ የኔ መንደር ሰወች ዝም አይሉም....እንኳን መርከብ ጠፍቶ ይቅርና ከአገራችን መርከብ ላይ የተፃፈች አንዲት “ቐ” ቆቧ ሲጠፋባት አገር ያናወጡ የመንደሬ ሰወች ፍሊጋ ይዘምታሉ “ ብየ ፎክሬ ነበር ...እዚህ ስደርስ እያንዳንድሽ ለሽሽሽ! መቸ ነው የአለም ህዝብ የምንሆነው ....የኛ ፊደል ከሌላው መርከብ ይመዝንብናል

....ኤዲያ ትርጉሙን ተውት ማን ትርጉም አወራችሁ አሁን የፊደሉን ያህል ስጋ ለለበሰው ቃል ቦታ ስጡ ነው ያልኩት ምንድነው ሳይሰሙ መጮኽ “ ጋሽ አዳሙ ማንም ሳይመልስለት ከመሬት ተነስቶ ይጮህና ዝም ብሎ ይቆያል ....... ድንገት ደግሞ ይጮሃል ! “ ቦኮሃራምም ሃያ ልጃገረድ ጨምሮ ወሰደ አሉ ...እነዛን

እሽጣለሁ ብሎ እንደፎከረው አጣርቶ ጨረሰ መሰል .... “ አፋችንን አፍነን በጋሽ አዳሙ አባባል በየቤታችን እንስቃለን

“ እኔ የምለው .....ለመሆኑ እኛ አገር ያለው የሴቶች ጉዳይ መስሪያ ቤት ለናይጀሪያ እናቶች የሃዘን መግለጫ ወይ ከጎናችሁ ነን አይዟችሁ የሚል መልክት ላከ ወይስ ሴትነትም ከድንበር ወዲህ ብቻ ነው የሚያሳዝነን ? እኮ የአገራችን ሴቶች ጉዳይ በዚህ የአፍሪካ እንቦቀቅሎች ጉዳይ ምን አለ ? .... አመት እየጠበቁ “ ዘጠኝ ሴቶች ተደፈሩ ተደፋሪወቹ ላይ ዘጠኝ ዘጠኝ አመት እስር ተደፈረ .... ሃያ ዘጠኝ ከባሎቻቸው ጋር ተፋተው አስራሁለቱ በእኛ ትግል እቃቸውን ተካፈሉ “ የሚል ሪፖርት ብቻ ነው ? ....

“እኛ የአፍሪካ መዲና እናቶች የአፍሪካ ሴቶች ሁሉ እናቶች ነን ...ያገባናል “ ካላላችሁ ምንድነው ለሴት መቆርቆር ...እኮ ሴትነትም ድንበር አለው ? ንገሩና እንስማው ...የሴትነት ድንበሩ የት ድረስ ነው ....አንዲት እናት ናይጀሪያዊም ትሁን ኢትዮጲያዊ የልጇ መጠለፍ ያው የማትችለው ስቃይ ነው መቸስ ! ያም ይሄም የእናት አንጀት !! ከኛ ጠቆር ስለሚሉ አንጀታቸው ደንዳና መስሎን እንዳይሆን ፈረንጆቹ እኛን እንደሚሉን! ለአለም ሴቶች ካላገባን በአለም ለምንትስ ጊዜ የሚከበረው የሴቶች ቀን ላይ መሸለል እናቁማ ! ! ከአለም ሴቶች የበዓል ቀን መካፈል ብቻ ሳይሆን የትም ያሉ ሴቶች ጎን ቁመን ከፉ ቀንንም መካፈል ነው

“የሴቶች ጉዳይ” ማለት እንዲያ ነው ... መቸስ ዜግነት ለሰው እንጅ ተነጥሎ ለፆታ አይሰጥም ...ናይጀሪያዊ ፆታ የለም ናይጀሪያዊት ሴት እንጅ ! ጋሽ አዳሙ ዝም ብሎ ይቆያል ሰፈሩ ረጭ ከማለቱ ብዛት የነፍሳት ሲርሲርታ ብቻ ነው የሚሰማው ድንገት ግን የጋሽ አዳሙ ድምፅ ዝምታውን እየሰነጠቀ በሰፈሩ ይናኛል.......

“...ለምሳሌ አሁን ጎረቤታችን አያልነሽ ....የክፍለ ከተማችን የሴቶችና ህፃናት ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ሃላፊ ነሽ ... የሴቶች ጉዳይ ምንትስ የምትይው ...ምርጫ ሲደርስ ሴቶችን ሰልፍ ለመጥራት ብቻ መሆን የለበትም ! ከአፍሪካውያን እናቶች ጎን ተሰልፈሽ ለአፍሪካዊያን እንቦቀቅሎችም ጩኺ እስቲ .... .....ይሄ ዛፍ ቆራጩ ተክሌ “ምን ሴት ቢያውቅ በወንድ ያልቅ” ብሎ ቢተርት “የዚህ ሰፈር ወንዶች በኮሌራ ወይ በሆነ ነገር ካላለቁ እኛ ሴቶች እኩል አንሆንም “ ብለሽ ስብሰባ ላይ ስትጮኺ ነበር.... ሁሉም ካለቁ ከነማን ጋር እኩል እንደምትሆኚ እግዜር ይወቅ ! ምን ይሄ ብቻ ባለግሮሰሪው አቶ ዘነበ “ እንኳን ዘንቦብሽ እንደውም ጤዛ ነሽ “ ብሎ ቢተርት “ሴቶችን ጤዛ ብሎ ተሳደበ “ ብለሽ ለፍርድ ሸንጎ አቅርበሽ ስትጮኺ ነበር ምናለ ታዲያ የአፍሪካ እንቦቀቅሎች እንደጤዛ ጧት ከታዩበት ትምህርት ቤት ረፋድ ላይ ሲጠፉ ብትጮሂ ......ኢትዮጲያዊያን ሴቶች ቦኮሃራም ለጠለፋቸው ህፃናት አዲስ አበባ ላይ ሰልፍ ወጡ “ የሚል ዜና አለምን ሞልቶ ገፅታችንን ቢገነባ ምናለ ....ሁሌ በጥሬ ስጋና በጠጅ ብቻ ገፅታ አይገነባም እኮ ....ሁሌ የአበሻ ሴቶች “ቆንጆ” እየተባለ መልከጥፉ ሴቶቻችንን ለገፅታ ግንባታ ሲባል ስንደብቅ መኖር የለብንም ! ግዴለም ቆንጆውም መልከጥፉውም ባንድ ላይ ሰበአዊ ጩኸት ይጩህ ! ሰላም አስከባሪ እንደምንልከው ሩህሩህነታችንን ልከን ከአፍሪካዊያን ሴቶች ጎን እንቁም .....አይዞሽ አያልነሽ ... በአማርኛም ቢሆን ጩኺ በደል ድንበር የለውም የሰቆቃ ቋንቋ እንግሊዝኛ ሳይሆን ስቃይ ራሱ ነው ! ....ቋንቋቸውን ሳይሆን ስቃያቸውን እንካፈል ! ሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃሃ በብርድ ልብስሽ ተከልለሽ “እኛም ቤት ጠለፋ አለ ለራሳችን በጮህን “ እያልሽ ይሆናል ሃሃሃሃሃ ....ወይስ

“ለሰልፉ የውሎ አበል አለው ወይ ?” ..........ሃሃሃሃ ሴትነት ድንበሩ የት ይሆን ? ....አንጀቴ ጩኸት ..... የቀበሊያችን ሴቶች ብቻ ናቸው ሴት የሚመስሉን ?.....እያንዳንድሽ አውሮፕላን ጠፋ ዝም ! መርከብ ጠፋ ጭጭ ...አንድ ፍሬ ልጆች ጠፉ ለሸሸሸ “ሴት” ሲባል “ስማችን ጠፉ” እያሉ በየግድግዳው

ጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭጭ... ጩጩጩጩጩጩጩጩጩጩጩጩጩጩጩ ጩጩጩ !!

ጋሽ አዳሙ ወደቤቱ መንገድ ይጀምራል ....

..... የኔ ውድ ሚስት ግን አሁን በተጠንቀቅ እየጠበቀችኝ ነው

.....የኔ ሴት ! ሴትነት ስልጣን ሳይሆን ፍቅር መሆኑ የገባት የኔ ውድ....ሴትነት የፆታ ፖለቲካ ሁኖ ያሰከራት የለቃቀመቻትን የቃል ጡሩምባ ወድራ የምትጮኽ ለፋፊ ሳትሆን ሴትነቷ ከቃል ገዝፎ በእምነት ዙፋኗ ላይ ያነገሳት ልእልት ...ሚ ስ ቴ ......ችት እያንዳንድሽ ..... ሴትነት የማንም የትግል ውጤት ሳይሆን

የተፈጥሮ ስጦታ መሆኑን ጠንቅቃ ያወቀች ሚ ስ ቴ .......የኔ ውድ የማንም ፍሬ አይደለችም የራሴ ጎን አጥንት ብቻ ! .....በየአደባባዩ አፍ መካፈት ሳይሆን ልብን ለሰብአዊነት ለክብርና ለፍቅር መክፈት የተሰጣት የኔ ነጭ ርግብ .....ጋሽ አዳሙ ወሬው ሲቀላቀልብን አንዱን ከአንዱ ለማያያዝ እየሞከርን የመንደሩ ሰዎች እንሰመዋለን ያው ሰካራም ቢያቀላቅልስ ማን ቀላቀልክ ይለዋል ....

“ ....እዚህ ሴት መሆን ሲከብዳቸው የሚንገዳገድ “አርቲፊሻል” ሴትነታቸውን በሰላሳ የመፎክር ምርኩዝ እያስደገፉ ጠንካራ ሰብእና ያስመስሉብናል ! በደፈናው መፎክሮች በደፈናው ዘለፋወች ....ሴት እናት ናት ...ሴት እህት ናት ...ሴት ሚስት ናት ....ሴት ካልሲ ታጥባለች ....ሴት ሊጥ ታቦካለች ..... ኤዲያ .....በስልጣኔ ስም ለዛው ተሟጦ ቅስሙ የተሰበረ ሴትነት እንደሆነ ..... እንኳን በመፎክር እንደዛር በየአደባባዩ ቢያጎሩለትም አይመለስ ... የከሸፈ ሴትነት አለች ያች የመንደራችን ልጅ ! መፎክር ወንዱም ሞልቶታል በደፈናው መፎክሮች “ ወንድ አባት ነው ...ወንድ ወንድም ነው ...ወንድ ባል ነው ...ወንድ እንጨት

ይፈልጣል ....ወንድ ጭቃ ያቦካል ..... ወንድ ሰካራም ነው ሂሂሂሂ እና የሴትነት ድንበሩ መፎክር መስሎሽ ነገር እየለቀምሽ ጨጨጨጨጨ ... በጫጨት ማንነት የነገር ጥሬ እየለቃቀመ ለሽሽ ! ደግሞ እኮ ርቆ ላይርቅ ያው ሴቱም ከወንዱ ክንፍ ስር ወንዱም ከሴቱ ክንፍ ስር ... አዳሜ ተሰልችቶ ከክንፍ ወጥቶ ሲወረወር እንደሸንኮራ ተመጦ ሲተፋ አንዱ ደጋፊ አንዱ ነቃፊ ሁኖ የፆታ ተከራካሪ ሊሆን ይዳዳዋል ! ንቃቱ ከዚች መንደር አያልፍ እንቅልፉ ከዚች መንደር አያልፍ ...የፈረደበት መንደር !! ገና ከተቆረቆረ አስር አመቱ የስንት ሽ አመት የዘፍጥረት የቤት ስራ ሊሰራ ይውተረተራል ! እንቢልታ እየነፉ አታሞ እየጎሰሙ ግድ ሴትነታችንን አውጁ ይሉናል .... በማፍቀር አውጀናል ! በማግባት መህተም አትመነዋል !...በየሬስቶራንቱ የራት ቀሚስ እየንተቱ ሰላሳ ጊዜ አበባ መቶ ጊዜ የፍቅር ዲስኩር ከሙቶ ወንድ ካልሰሙ ሴትነታቸውን የሚጠራጠሩ ችግራቸው የሴትነት ሳይሆን ሴትነትን የሚተረጉሙበት አይምሮ ነውና አናታቸው ላይ ከሚጎዘጉዙት ፀጉር ይልቅ አናታቸው ውስጥ የሚያስቀምጡትን ሰበአዊ እውነት ያበጥሩ ! የተንጨባረረ እውነት ግራ የተጋባ ስነልቦና የተሸከመ ነፍስ እንደማይተማመን ጓደኛ በየስርጡ ከራሱ ጋር ይማማላል “ እናቴ ትሙት ሴት ነኝ” እንደማለት ! እና አለም ሁሉ ካልማለላቸው ባለጌ ይመስላቸዋል ! “የኔ ማር አይንሽ

..ጥርስሽ ...ቅንድብሽ ....ምንሽ ...ምናምንሽ ....በቃ ከልብሽ ሴት እኮ ነሽ “ እልልልልልልልል! ጋሽ አዳሙ ድምፁ እየቀነሰ እየቀነሰ እየቀነሰ ...በሩ ላይ ሲደርስ ዝም ይላል ..... የሚያሰክረው የራሱ ብሶት የሚያስጮኸው የነብሱ ቁጣ ቢኖርም ሚስቱ ጋ ሲደርስ ግን ቃል አይተነፍስም ! የትኛውም ጩኸት ከሚያከብሩት ነፍስ ስር በጥሞና ይኖራልና ...ቢሆንም ሁሉም ሰው የራሱ የነፍስ ጩኸት አለው ...አንዳንዱ ጨዋ ለመባል የሚያለሳልሰው ሌላው በጎ ቃልን እንደጉቦ ሰጥቶ ከተቀባዩ ምናምንቴውን በውለታ ሊቀበል ... ኤዲያ ! ለሚያከብሩት ሰው ታላቁ ክብር ባለጌ ከሆኑ ባለጌ ነኝ ብሎ

ሃቂቃውን መናገር ነው.... ጨዋ ከሆኑም ጨዋነቴን እወቁልኝ አዋጅ ለማስነገር “ባለጌወችን “ ለመዘለፍ በየአደባባዩ እንደቁራ መጮኽ ከንቱ ! እና አዳሙ ባለጌ ነው ጨዋ  ስካሩን ግዴለም እያሉ የሰካራሙን ቃል የሚሰነጥቁ ራሳቸው ባ ለ ጌ ! ከሰካራምም አፍ “የአድናቆት ቃልን” ይሻሉና “ በነፍሳቸው ውስጥ ለሁሉ ነገር ምስክር ለቀናቸው መሃላ የሚያስጠራ ነፍሳቸው ያለፉት ሂወት ጭንቀትና ጥላቻ የሞላው

ከራሳቸው የሚጋጭ የትዝታ መዶሻ ያለበት ጥቁር ካባ የለበሰ የሃሰት ፈራጅ የተኮፈሰበት በመዋቢያ ያበደ ጥቁር ነብስ ....ትንፋሻቸው ሁሉ ጥቁር ነው ...እናም ይጮሃሉ ....ወንዙን ምን ያስጮህሃል ቢሉት “ በውስጤ ያለው ድንጋይ” ብሎ የለ .....ዘላለማዊ ክብር ድንበር አልባ ንፁህ ነፍስ ላላቸው (((. ))) ጓ ! ያደርጋል ዳኛ ! (በአማርኛ ይተርጎምና ወደመዝገብ ቤት ) በመንደራችን በሰፈነው ዝምታ እኛም ለጥ ...ነገ ፀሃይ ወጥቶ የተረኛው ስካር መንደሩን ቃጤ እስኪያደርገው !

# የመዝጊያ ንግግር

ሳሙኤል የሚባለው የስራ ባልደረባየ ጠፈርተኛ የሚያስመስለውን ጃኬት <ሌዘር> እስከአገጩ ቆልፎ በጨርቅ ሱሪና በነጭ ስኒከር ለብሷል በቃ ሲዘንጥ እንዲህ ነው

ሃይሉ (የመስሪያ ቤታችን ገባየ ጥናት ባለሙያ ነው ) ቡኒ ሱሪና ቀይ ድምቅ ያለ ሸሚዝ ለብሷል የሸሚዙ ቅላት ሲጨንቅ ! በደም የተነከረ የሆነ ሸሚዙን ለማቅለም ሲባል ብዙ ሰወች ደማቸው የፈሰሰ አይነት

አምሳሉ (የህዝብ ግኑኝነት ባለሙያ ነው እውነቱን ለመናገር ) ከሁላችንም የበለጠ ሽክ ብሎ ነበር ኦሞ የመሰለ ጅንስ ሱሪ በጥቁር ሹራብ ለብሶ ሲዘንጥ የሚያስራትን ነጭ ማሰሪያ ያላት ሰአት ሸብ አድረጓታል እችን ሰአት ሲያደርግ እግዜር የቀኑን ሰአት ከ 24 ወደ 48 የሚያሳድገው ይመስል አምሳሉ አወራሩም አረማመዱም በእጥፍ ረጋ ይላል !

ጋሽ ጀምበሩ ( አንድ ለናቷ የሆነችው የድርጅታችን መኪና ሹፌር ናቸው )ቀለሙን የማላውቀው ኮትና ሱሪ በሚያብረቀርቅ ቡኒ ቆዳ ጫማ ለብሰዋል ሴቶቻችንን መግለፅ ይከብዳል ከሁሉአገርሽ በስተቀር (የሃገር ባህል ልብስ ነው የለበሰችው ) ከቁምጣ እስከ ታይት ከመራቆት እስከመንኳተት ያልተለበሰ ልብስ የለም

ድርጅታችን በየአመቱ ለሰራተኞች በሚያካሂደው ግብዣ ላይ ለመገኘት ወደደብረ ዘይት ለመሄድ ነበር እንዲህ አይነት ዝግጅቶች ተወዳጅና በየአመቱ የሚናፈቁ ናቸው ! እኔ በበኩሌ የመዝናኛ ፕሮግራም በመስሪያ ቤት በኩል ስካፈል የመጀመሪያ ስለነበር ጓጉቸ ነበር

ደብረዘይት ከጧት ሃይቆቹን ስንጎበኝ ዋልን ቢሾፍቱ " ይሄ ጃንሆይ ቅንድቡ የገጠመ ልጅ ይገብሩበት የነበረው ሃይቅ ነው ይባላል" አለኝ ሃይሉ ወደጆሮየ ጠጋ ብሎ ሃይሉን ስመለከተው ቅንድቡ የገጠመ ነው

" በል አቶ መላኩ እንዳይገብሩህ " አልኩት ተሳሳቅን አቶ መላኩ የድርጅታችን ስራ አስኪያጅ ናቸው ድርጅታችን ትንሽ አገር አቶ መላኩም ትንሽ ንጉስ ነው !

ደብረ ዘይት እች የበሬ ግንባር የምታክል ከተማ ይሄን ሁሉ ሃይቅ መሰብሰቧ ገረመኝ ምናለ አንዱን አዲስ አበባ ላይ ቢፈጥረው ብየም ተመኘሁ ሃሜቱ እውነት ከሆነ ንጉሱም እዚህ ድረስ የማንንም ቅንድባም እያንዘፋዘፉ ባልደከሙ ነበር ! እዛው አዲስ ላይ ሽክ !! ሂሂሂ ቅንድቤን በእጀ ዳሰስኩት አልገጠመም ! ያው በየትኛውም ዘመን በየትኛውም አገዛዝ ፊዳ የሚሆን ህዝብ አይጠፋም በዚህ ዘመን እንኳን ቅንድብህ በመግጠሙ ሳይሆን ሃሳብህ ባለጊዜው ጋር ባለመግጠሙ ነው የምትገበረው !

የጉብኝት ፕሮግራማችን ሳንጠግበው ተጠናቀቀ! ቀጥሎ ሙዚቃ ተከፍቶ ጠረንጼዛወቹ በውብ ልብሶች ተሸሞንሙነው በተዘጋጀ በአንድ ሆቴል ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ሰራተኛው ሁሉ ቦታ ቦታውን ይዞ ምሳ እስኪቀርብ በጉጉት ይጠብቅ ጀመረ!

ሁሉም ፊት ላይ ከልብ የሆነ ደስታ ይነበብ ነበር ካሸሪዋ እትየ አረጋሽ እንኳን ካለወትሮዋ ፈታ ብላ እየተሳሳቀች ከፋይናስ ሰራተኞች ጋር እወራች ነበር መቸም እንዲህ ያሳቃቸው ለፕሮግራሙ "ስፖንሰር" ተገኝቶ መሆን አለበት እንጅ የድርጅቱ ብር ሲወጣ በታሪክ ስቀው አያውቁም !

እርቦን ነበር ብዙወቻችን ቁርስም አልበላንም በተለይ እኔ በባዶ አንጀቴ ማስቲካ ሳላምጥ መዋሌ ርሃብ ከነዘር ማንዘሩ ሰፍሮብኝ ነበር ፊት ለፊታችን በተቀመጠው ረዥም ጠረንጼዛ ላይ ቁጥር ስፍር የሌለው ምግብ ተሰድሯል አቤት ብዛቱ አልጫው ጥብሱ ቁርጥ ሁሉ አለ አንድ በሬ የሚያክል የበሬ ስጋ ከጠረንጼዛው በቀኝ በኩል እንደ ትልቅ ካቦርት ተሰቅሏል ስለቱ የሚያበራ ቢለዋ አጠገቡ ይታያል ( መጣሁልህ ዛሬ እንለዋለን በአይናችን )

አናቱ ላይ የአክሱም ሃውልትን የሚያህል ነጭ ቆብ የደፋ አስተናጋጅ እስክንበላለት ቁሞ ይጠብቀናል የፍም ጥብሱ ደግሞ ይንጨፈጨፋል ጭጭጭ ጭ ጭ ጭ እያለ ሸክላው ላይ ሽታውም አፍንጫችንን ያውደናል የብዙው ሰራተኛ ጉሮሮ ከፍ ዝቅ ይላል ርሃብ የሚባል ኦኬስትራ እንደሚመራ “ኮንዳክተር” ጉሮሯችን ከፍ ዝቅ

ስራ አስኪያጃችን ወደመድረኩ ሲወጡ አጨበጨብንላቸው ! ፈገግ አሉና ንግግራቸውን ቀጠሉ

“ አመሰግናለሁ ንግግሬን ከመጀመሬ በፊት እስኪ የድርጅታችን ሰራተኛ ለነበሩት አቶ መብራቱ ገዛሃኝ የአንድ ደይቃ የሂሊና ፆለት እናድርግ “ አሉን አቶ መብራቱ ማለት በእኔ ቦታ ይሰራ የነበረ ሰራተኛ ነበር አሁን እኔ የምሰራበት ቢሮ ውስጥ እራሱን አንቆ ነው አሉ የሞተው አንዳንዴ ቢሮ ውስጥ ብቻየን ስሆን ያቃዠኛል ሁላችንም ከወንበራችን ተነስተን ቆምን (አንድ ደይቃ ነው ያሉት አንድ ሰአት ረዘመብኝ )

“ አመሰግናለሁ ተቀመጡ እንግዲህ ፕሮግራማችን በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ለመሆኑ ፊታችሁ ላይ ከሚታየው ፈገግታ መገንዘብ ችያለሁ ” ሳቅንላቸው “ አሁን እንግዲህ እንደምታዩት ለአይን ያማረ ገበታ ተዘጋጅቷል የወደድነውን እየበላን እየጠጣን እንድንዝናና እጋብዛለሁ “ ተነስቸ ወደቡፌው ልሮጥ ስል ቀጠሉ “ ከዛ በፊት ግን የድርጅታችን የሰው ሃይል አስተዳደር ሃላፊ አቶ በድሉ በለጠ አጭር የመክፈቻ ንግግር ያደርጉልናል “ አጨበጭብን አቶ በድሉ ንግግራቸው ረዥም ስለሆነ ብስጭት ብለን ነበር

“ክቡራን እህቶቸ ወንድሞቸ ልጆቸ ሃላፊወቸ ክቡራን ጥበቃወች ፅዳቶች ሹፌሮች ተላላኪወች ክቡራን ፀሃፊወች አካውንታቶች ዲፕሎማወች ድግሪወች ማስተርሶች በልምድ የተቀጠራችሁ በሹመት የመጣችሁ ሁሉ ለዚች ቀን እንኳን አደረሰን አደረሳችሁ “ ቿቿቿቿቿ

“ እንዲህ ባማረ ሁኔታ ተሰናድቶ የምናየው ምግብ (ወደምግቡ እያመለከቱ ምራቃችንን ዋጥን ) የሰላም ፍሬ ነው አገራችን ስሟ በእርሃብ ሲነሳና መሳቂያ መሳለቂያ ስንሆን መኖራችን የአደባባይ ሚስጥር ነበር አሁን ግን ያ ነገር ተረት ሁኗል “ አሉ ፉከራ በሚመስል ድምፅ አጨበጨብን !

“ ድህነት መሮንና ቆጭቶን እንዳንሰራ ጨቋኝ አገዛዝ ጫንቃችን ላይ ተቀምጦ አላላውስ ብሎን ተሰቃይተን ነበር እልህ አስጨራሽና መራር ትግል አድርገን ያንን አስከፊ ስርአት ገርስሰነዋል መቸም ዛሬ ላይ ሲናገሩት ቀልድ ይመስላል እንጅ ወገኖቸ የተከፈለው መስዋትነት እንዲህ ቀላል አልነበረም ” ግማሽ ደይቃ የሚሆን ተከዙ

“ አያችሁ ብዙወች ሂወታቸውን ከፍለዋል አገር ቀላል ነገር አይደለም ብዙወች አካላችንን ከፍለናል ነፃነት እንዲሁ አይመጣም ዛሬም ድረስ የማይሽር ቁስል ያምይድን ጠባሳ አትርፈን ነው ለዚህ ጥጋብና ሰላም የበቃነው “ ለዚህ ጥጋብ ሲሉ ወደምግቡ ጠቆሙን ምራቃችንን ዋጥን ደግሞ አንዲት ቀይ አስተናጋጅ በፒራሚድ ቅርፅ ትሪ ላይ የተቆለለ እንጀራ ቁርጠ አምጥታ ጠረንጴዛው ላይ አስቀመጠችው ስንት ቁርጥ እበላ ይሆን ሶስት አራት ለነገሩ ዳቦም ስላለ ሁለት ይበቃል ወይም እንጀራውን ቀንሸ ቁርጡን

ተናጋሪው ቀጠሉ “ ወገኖቸ እኔ ራሴ ዛሬ ላይ ህዝቤ ሲደሰት ሲዝናና ሳይ ደስ ይለኛል እንጅ ጦር ሜዳ በቦንብ የቆሰለ ሰውነቴ እስካሁን እያመረቀዘ ያሰቃየኛል አሁን ባለፈው አስራ አምስት ቀናት ሆስፒታል ነው የከረምኩት ያው ብዙወቻችሁ ደውላችሁ እግዜር ይማርህ ብላችሁኛል እግዜር ይስጥልኝ ምን መሰላችሁ ” ሸሚዛቸውን ከቀበቷቸው መዘዙና ፊታቸውን አዙረው ጀርባቸው ላይ አሰቃቂ እና በቦንብ የተቦደሰ ቁስል አሳዩን ደም ያረገዘ መሃሉ ደርቆ ዳር ዳሩ ያመረቀዘ አሰቃቂ ቁስል

“ እንዲቹ ስንት አመት ሲያሰቃየኝ ኑሮ ሁለት የእጅ ማስታጠቢያ መግል የቀላቀለ ደም ነው ቀድተው እፎይ ያስባሉኝ መቸስ እንደሃኪም ቤት ያለ ትልቅ ልማት የለም ይሄም የሰላም ውጤት ነው እንደው ደስታችሁን ለማደፍረስ ሳይሆን የዛሬው ነፃነትና ደስታ እንዲሁ አልመጣም ለማለት ያህል ነው አመሰግናለሁ “ ብለው ወደቦታቸው ተመለሱ አጨበጨብን

ከዛ በኋላ ግን የምሳው ነገር ከምሳው በፊት በተፈጠረው የ"መዝጊያ" ንግግር እና ትእይንት የቀዘቀዘ ነበር በበኩሌ የዛ አይነት ትልቅ ቁስል በሂወቴ አይቸ ስለማላውቅ እንኳን ምግብ መመገብ መተንፈስም አቅቶኝ ወደአዲስ አበባ እስክመለስ አንዲት ነገር አልቀመስኩም ነበር !!

# የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት

የአንድ ደይቃ የሂሊና ፆለት አድርገን እንደተቀመጥን ፕሮግራሙ ቶሎ እንዲያበቃ ሌላ የሂሊና ፆለት ጀመርኩ

አለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ለማክበር የክፍለ ከተማው የሴቶች ሊግ ባዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ተገኝቻለሁ ሲጉ በመስሪያ ቤታችን በኩል ግዳጅ የተቀላቀለበት ጥሪ አቅርቦልን አለቃየ "ሂድ! " ስላለኝ የቀበሌው አዳራሽ ውስጥ ተገኝቻለሁ ያውም ቅዳሜን በሚያክል ቀን ከሰአት!! ሰምታችሁኛል? ቅዳሜ ከሰአት ቀበሌ አዳራሽ ውስጥ (ሰኔና ሰኞ ገጥሞብኝ)

" አሁን ደግሞ የክፍለ ከተማችን የህፃናትና ሴቶች ፑል ምክትል ሃላፊ ወ/ሮ ደርባቤ በላቸው "እንስራውን ሰብሮ ወሰዳት ልጅቱን " የሚል ምርጥ ግጥም ያቀርቡልናል " አለ ጉጉት የመሰለው መድረክ አስተዋዋቂ  አፉ ላይ የደቀነውን ማይክሮፎን ድምፅ ማጉላቱን የተጠራጠረ ይመስል በጣም እየጮኸ ነው የሚናገረው!

ቀጠለ " ወሮ ደርባቤ ለክፍለ ከተማችን ብሎም ለከተማችን ብሎም ለኢትዮጲያ ሴቶች ብሎም ለአፍሪካ ሴቶች ታላቅ ምሳሌ የሚሆኑ የዘርፈ ብዙ ሙያወች ተሰጥኦወች ትምርቶች ስልጣኖች ባለቤት ናቸው" አለና " እስቲ ወ/ሮ ደርባቤን ወደመድረክ "

 ቿ ቿ ቿ ጥልፍ ቀሚስ የለበሱትና አንዳንድ ልማታዊ ዝግጅቶች ላይ ልማታዊ ግጥም በማቅረብ የሚታወቁት ወ/ሮ ደርባቤ መድረክ ላይ ቁመው በፈገግታ ለህዝቡ ጎንበስ ቀና እያሉ ምስጋና ይሁን ሰላምታ ያለየለት ግማሽ ስግደት አቀረቡ

ግጥሙን ሊያቀርቡ ነው ብለን ፀጥ ስንል አስተዋዋቂው ማዋደዱን ቀጠለ " ብታምኑም ባታምኑም ወ/ሮ ደርባቤ ይሄን ዝግጅት አስመልክቶ ግጥም እንድትፅፍልን የነገርናት (አንች አላት) ትላንት ዘጠኝ ሰአት ነው ይገርማችኋል ሌሊቱን ስትፅፍ አድራ ጧት ስደውልላት በስልክ ግጥሙን አነበበችልኝ "ወይ መባረክ" ነው ያልኩት (በህዝብ ስልክ አራት ገፅ ግጥም እያነበቡ አላየንም ባርኮት)

" የግጥሙን ጥልቀት እና ውበት እራሳችሁ ታዘቡት እስቲ ለዚች ብርቱ ሴት ሞቅ ያለ ጭብጨባ " ብሎ ጭብጨባውን እራሱ ጀመረው ማይኩን በሌላኛው እጁ ሲጠፈጥፈው አዳራሹ ጓ ጓ ጓ በሚል ለጆሮ የሚቀፍ አስቀያሚ ድምፅ ተሞላ ከታዳሚው የተንቦጫረቀ ደካማ ጭብጨባ ጋር ተዳምሮ በጭብጨባ የታጀበ ተኩስ ነበር የሚመስለው

ብዙው ታዳሚ በየእጁ ፈንድሻ እና ለስላሳ ይዞ ስለነበረ ማጨብጨብ አልቻለም (እንጅ ለጭብጨባማ የእኛን ክፍለ ከተማ የሴቶች ሊግ ፅ/ቤት ሰራተኞች ማን ብሏቸው በተለይ እጃቸው ባዶ ሲሆን የሚያጨበጭቡት ጭብጨባ ቢሾፍቱ ይሰማል እጃቸው ባዶ ሲሆን ለዜና ያጨበጭባሉ  ለሪፖርት ያጨበጭባሉ የቀበሌው ሊቀመንበር ሲያስነጥሱ ሁሉ ያጨበጭባሉ እጃቸው ሞላ ካለች ግን ጠቅላይ ሚንስትራችን ቢዘፍኑም አያጨበጭቡ )

ቀጠለ አስተዋዋቂው (ወ ይ ዛሬ) “ ወ/ሮ ደርባቤ ገጣሚ ብቻ አይደሉም የታሪክ ተመራማሪም ናቸው (ወ/ሮ ደርባቤ በፈገግታ ቁመው በቁማቸው ገድላቸው ሲለፈፍ ይሰማሉ) ከፍተኛ አድናቆት ያተረፈውን

“የክፍለ ከተማችን የእድገት ማራቶን ሩጫ ከዘመነ ደርግ ውድቀት በኋላ”

የሚለውን መፅሃፍ ጨምሮ አራት የግጥም መፀሃፍትን አሳትመዋል ይሄን ያህል ካልኩ እንዳላሰለቻችሁ ወደ ወ/ሮ ደርባቤ ልምራችሁ ” ብሎ ማይኩን በአክብሮት ለሴትየዋ አቀበላት (እፎይ” አንድ አዛ ለቀቀ “ ይላሉ እማማ ሩቅያ ሲተርቱ)

ማይኩን ተቀብላ ጓ ጓ አደረገችና (የፈረደበት ማይክ) እ እኔ እንኳን የተባለውን ያህል ነኝ ብየ አላምንም ምክንያቱም እንደእኔ እድሉን ቢያገኙ እንኳን ኢትዮጲያን አለምን “ጉ ድ” የሚያስብሉ ሴቶች ከእናንተ መሃል አሉ ብየ ስለማምን ነው ” አለች በፈገግታ ጭብጨባ !!ቿቿቿቿቿቿቿቿ (ፈንድሻው አለቀ እንዴ ጭብጨባው ደመቀ)

ከጎኔ የተቀመጠች ሴት “እውነት ነው “ ብላ ጮኸች (አለምን “ጉድ” ከሚያስብሉት ሴቶች መሃል አንዷ ሳትሆን አትቀርም ብየ) ዞር ብየ ሳያት በግራ እጇ “ሞባይ”ስልኳን በቀኟ መዳፏ እስኪወጣጠር የዘገነችውን ፈንድሻ ይዛ በስሜት ወደመድረኩ እያየች ቁጭ ብድግ ትላለች ከፈንድሻው ኮርሸም አደረገች

ሴትዮዋ ግጥሟን ከማቅረቧ በፊት ሰላሳ ደይቃ አወራች እንዴት የወንዶችን ተፅእኖ ተቋቁማ “ታላቅ ገጣሚ” ለመሆን እንደበቃች ሴቶች የእርሷን ፈለግ ይዘው እንዲከተሏት (ብትወዱስ እኔን ምሰሉ ዳር ዳርታ) ይሄን ሁሉ አወራችና “እንዳላሰለቻችሁ” በማለት ወደግጥሟ ተሸጋገረች!!

ወደመድረክ ስትወጣ መነፅሯን ቦታዋ ላይ ረስታው ስለነበር “ አቀብሉኝ” ስትላቸው የእጅ ቦርሳዋን አራት ካድሬወች ግራና ቀኝ ይዘው (ማሸርገዳቸው ስላበሳጨኝ የጨመርኩት) አቀበሏት ቦርሳዋ ውስጥ አስር ደይቃ ፈልጋ መነፅሯን እቤቷ መርሳቷን አረጋገጠች እናም ወደብርሃኑ ቀርባ ግጥሟን ማንበብ ጀመረች

እንስራውን ሰብሮ ወሰዳት ልጅቱን(ርእስ)

ኧረ አያ ደገፋው አንተ ትልቅ ሰው

አንዲት ፍሬዋን ልጅ ማስቸገርህን ተው

ውሃ ልትቀዳ ወንዝ ስትሄድ

ቁመሽ አውሪኝ አልካት በግድ

ይሄ አልበቃ ብሎህ ሰው ጭር ሲልልህ

ህፃኗን ደፈርካት እግዜር ይይልህ!! (ውይ ወንዶች አለች ከጎኔ ያለችዋ ባለ ፈንድሻ)

ደሟን እያዘራች እቤቷ ስትደርስ

እንስራ ሰበርሽ ብለው ገረፏት አያድርስ

ደሞ በሌላ ቀን እንደገና አድብተህ

አሁንም ደፈርካት አንተ ግን ምን አይነት ሰው ነህ (በስማም ጭካኔ ሌላዋ ሴት) አዳራሹ ፀጥ ብሎ “ግጥሙን” እያዳመጥን ድንገት ጎኔ ያለችው ሴት ጎርደምደምደም ከሸሸሸ ስታደርግ ደንግጨ ዞሬ አየኋት ተመስገን ፈንድሻ እየበላች ነው እኔማ በግጥሙ ተመስጣ በስህተት ሞባይሏን የጎረደመችው መስሎኝ ነበር

ግጥሙ ለድፍን ሀያ ሰባት ደይቃ ተነበበ የግጥሙ የመጨረሻ ስንኞች

ፊስቱላ ተይዛ ስትንከራተት

ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ አገኘታት

አዲሳባ በመኪና አመጣቻት

መንግስታችን በሰራው ዘመናዊ አፓልት አመሰግናለሁ ቿቿቿቿቿቿቿቿቿቿቿቿ (ታዳሚው ፈንድሻውን ጨርሶ ነበር)

ለመውጣት ሳቆበቁብ አስተዋዋቂው እንዲህ አለ "ለሴቶች ቀን ያልሆነ ግጥም ለመቸ ይሆናል በማለት ወሪት ዘቢደር የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ለግንቦት ሃያ አንብባው የተደነቀላትን "ታታሪዋ ስራ ፈጣሪ " የሚለውን ግጥሜን ላቅርብ ብላለችና እስቲ ወደመድረክ" ቿቿቿቿቿ

ተነስቸ ወጣሁ ወደቤቴ ከኋላየ የአስተዋዋቂው ድምፅ ይሰማኛል ወጣት ዘቢደር "የእንስቷ ጣጣ የሚል የግጥም መድብሏ ከፍተኛ እውቅና ያተረፈች  ይሄ ቀበሌ ሳንሰማ ማተሚያ ቤት ከፈተ እንዴ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY